በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት**
**የወንጀል ሕግ ትርጉም ውሳኔዎች ስብስብ**

**(በየጉዳዮች የተደራጀ ልዩ እትም)**

የካቲት 2018 ዓ.ም
ኢትዮጵያ፤ አዲስ አበባ

©ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመጀመሪያ እትም
የካቲት 2018 ዓ.ም ታተመ

አሳታሚ እና አከፋፋይ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ከአውሮፓ ሕብረት በተገኘ ገንዘብ ድጋፍ ታተመ

*<u>አዘጋጆች</u>*

1. *ምስጋና ዴቢሳ ዶዮ (LLB,LLM)*
2. *ገናናው ጎበና ደርቤ (LLB)*
3. *ጥሩነህ እንደሻው አበበ ((LLB,LLM in Legislative Drafting, and LLM in Constitutional and Public Law)*
4. *ተስፋሁን ወርቁ ኃ/ማሪያም (LLB,LLM,BA in Economics)*

*ማውጫ*

# ይዘት


....... xi

የክቡር ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት ....... xi

I. የአህፅሮተ-ቃል ትርጉም ....... xiii

II. መግቢያ ....... 1

III. የመፅሐፉ የአጠቃቀም መምሪያ ....... 2

ምዕራፍ አንድ ....... 4

I. የወንጀል ሕግ የጠቅላላ ድንጋጌ ክፍል የሰበር ሕግ ትርጉም ውሳኔዎች ....... 4

መግቢያ ....... 4

ክፍል አንድ ....... 4

1. የወንጀል ሕግ መርሆዎች እና የፍርድ ቤቶች ስልጣን ....... 4

1.1 በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስ ወይም ቅጣት ክልክል ስለመሆኑ ....... 4

1.2 የሕጋዊነት መርህ ....... 9

1.3 በወንጀል ጉዳዮች የፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን ....... 12

ክፍል ሁለት ....... 22

2. የወንጀል ድርጊትን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ....... 22

2.1 ሕጋዊ ፍሬነገር እና የአሳብ ክፍል ....... 22

2.2 በሕብረት የተፈፀመ ወንጀል ....... 26

2.3 ወንጀልን የሚያቋቁሙ ፍሬነገሮች (ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር) 37

ክፍል ሶስት ....... 39

3. የወንጀል አፈፃፀም ደረጃ ....... 39

3.1.የሙከራ ወንጀል ....... 39

ክፍል አራት ....... 41

4.በወንጀል አፈፃፀም ላይ ተካፋይ መሆን ....... 41

4.1 በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ መሆን ....................................................41
ክፍል አምስት ....................................................47
5.የወንጀል ኃላፊነት ....................................................47
5.1 በልዩ አዋቂ ስለሚረጋገጥ ኃላፊነት ....................................................47
ክፍል ስድስት ....................................................55
6.በወንጀል ጥፋተኛ መሆን ....................................................55
6.1 አሳብ፣ ቸልተኝነት እና ድንገተኛ ነገር ....................................................55
6.2 በቸልተኝነት ጥፋተኛ መሆን ....................................................59
ክፍል ሰባት ....................................................62
7.በተደራራቢ ወይም በደጋጋሚነት የወንጀል ጥፋተኛ መሆን ....................................................62
7.1 ተደራራቢ ወንጀሎች ....................................................62
7.2 ተደራራቢ ወንጀሎችን ላይ የተያዙ አቋሞችን የሚያሳዩ የሰበር ውሳኔዎች ........69
7.3 ቼክን የተመለከቱ ተደራራቢ ወንጀሎች ....................................................76
ክፍል ስምንት ....................................................83
8.በሕግ የተፈቀዱ ድርጊቶች፣ የማያስቀጡ እና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች ................83
8.1 ሕጋዊ መከላከል ....................................................83
ክፍል ዘጠኝ ....................................................86
9.ቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎች እና መመሪያ ....................................................86
9.1 የእሥራት ቅጣት አወሳሰን፣ የሞት ቅጣት እና የገንዘብ መቀጮ ........................86
9.2 የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ....................................................95
9.3 በወንጀል ጉዳይ ንብረት መውረስ ....................................................97
ክፍል አስር ....................................................102
10.ቅጣትን መገደብ ....................................................102
10.1 የገደብ ጥያቄን በዝምታ ማለፍ ....................................................102
10.2 ቅጣትን ለመገደብ መመዘኛዎች - የወንጀል ክሱን አምኖ ወይም ክዶ የመከራከር ውጤት (የተለያዩ አቋም የተያዘበት ውሳኔዎች) ....................................................108
10.3 የወንጀል ክስን ክዶ መከራከር ቅጣት እንዲገደብ በቅድመ ሁኔታነት የማይታይ፤ ....................................................111

10.4 ንግድ ምልክት መጠቀም ወንጀል ቅጣት ለመገደብ፤ ..... 113
ክፍል አሥራ አንድ ..... 122
11. የፍ/ብሄር እና የወንጀል ጉዳይ ተጣምሮ የሚታይበት አግባብ ..... 122
ክፍል አስራ ሁለት ..... 126
12. የወንጀል ይርጋ ፣ ይቅርታ እና መሰየም ..... 126
ክፍል አስራ ሶስት ..... 130
13. ወጣት ጥፋተኛን በተመለከተ ..... 130
I. የተጠቀሱ የሰበር መዝገቦች ዝርዝር ..... 135
ምዕራፍ -ሁለት ..... 138
II.የወንጀል ሕግ የልዩ ክፍል የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች ..... 138
መግቢያ ..... 138
ክፍል አንድ ..... 138
1. በመንግስት፣ በአገር እና በአለምአቀፍ ጥቅሞች ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች ..... 138
1.1 የከበሩ ማዕድናትን በሕገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወር ..... 138
ክፍል ሁለት ..... 146
2.በመንግስት ስራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ..... 146
2.1 የሥራ ኃላፊነትን አለመወጣት ..... 146
ክፍል ሶስት ..... 152
3.የፍትህ አስተዳደር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ..... 152
3.1ሀሰተኛ ምስክርነት ..... 152
3.2 ፍርድ ቤትን መድፈር ..... 156
ክፍል አራት ..... 158
4.በሕዝብ ደህንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ..... 158
4.1 ሕግወጥ ጦር መሳሪያን በተመለከተ ..... 158
ክፍል አምስት ..... 165
5.በሰው ሕይወት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ..... 165
5.1 የሰው ግድያ (በቸልተኝነት) ..... 165
5.2 ተራ የሆነ የሰው ግድያ ..... 174

5.3 የሰው ግድያ ወንጀል -ሕጋዊ መከላከል ....178
ክፍል ስድስት ....182
6.በሰው አካል እና ጤና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ....182
6.1 ከባድ አካል ጉዳት ....182
6.2 ቀላል የአካል ጉዳት ....185
ክፍል ሰባት ....188
7.በሰው ነፃነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ....188
7.1 በሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክ ....188
ክፍል ስምንት ....192
8. በሩካቤ ስጋ ነፃነት እና ንፅህና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ....192
8.1 የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ- የወንጀሉ ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር ....192
ክፍል ዘጠኝ ....195
9.በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ....195
9.1 የስርቆት ወንጀል- (ሙከራ ወንጀል) ....195
9.3 እምነት ማጉደል ፣ የማታለለ ወንጀል እና ሥራን ያለአግባብ መምራት ወንጀል ....202
9.4 በቂ ስንቅ የለሌው ቼክ ማውጣት ....207
9.5 በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ ማውጣት የአሳብ ክፍል ....216
ክፍል አሥር ....220
10. የሕሊናን ወይም የሰው ችግር መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ....220
10.1 የአራጣ ወንጀል ....220
I.የተጠቀሱ የሰበር መዝገቦች ዝርዝር ....223
II.የምዕራፍ አንድ እና ሁለት የሕግ ማጣቀሻዎች ....225
ምዕራፍ ሶስት ....228
III. በልዩ ልዩ አዋጆች ላይ የተሰጡ አስገዳጅ የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች ....228
መግቢያ ....228
ክፍል አንድ ....229
1.የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጡ አዋጆች ....229

1.1 የሽብር ድርጊት ለመፈፀም መሰናዳት የወንጀል ተጠያቂነት ....229
ክፍል ሁለት ....235
2.ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ድንበር ማሻገር ....235
2.1 (አዋጅ ቁጥር 909/2007) ....235
2.2 (አዋጅ 1178/2012) ....241
ክፍል ሦስት ....245
3.የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ....245
3.1 የተከሳሽን የአሳብ ክፍል የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ የሚዛወርበት ....245
ክፍል አራት ....259
4.የቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ ....260
ክፍል አምስት ....263
5.የታክስ አስተዳደር አዋጅ ....263
5.1 የሕግ ሰውነት ያላቸው የንግድ ድርጅቶች የወንጀል ተካፋይነት እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግ ....263
5.2 የግብር ደረሰኝ ሐሰተኛነት የወንጀል ተጠያቂነት ....279
ክፍል ስድስት ....285
6.የጉምሩክ አዋጅ ....285
6.1 የጉምሩክ ህጎችን መተላለፍ የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነት ....285
6.2 የጉምሩክ አዋጅ ሲሻሻል ለተከሳሽ የተሻለው ተፈጻሚ የሚሆንበት ሁኔታ ....290
6.3 የተሽከርካሪ መለያ መረጃዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ መቀየር የወንጀል ተጠያቂነት ....294
ክፍል ሰባት ....298
7. የባንክ ስራ አዋጅ ....298
7.1 የተጠበቁ መረጃዎችና የፍርድ ቤት የምርመራ ትዕዛዝ ....298
ክፍል ስምንት ....301
8.የመከላከያ ሚኒስቴር አዋጅ ....301
8.1 የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂነት ....301

8.2 በወንጀል የተከሰሱ የመከላከያ አባላት በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍ የማግኘት መብት ....304

ክፍል ዘጠኝ....307

9.የሊዝ አዋጅ ....307

9.1 ሕገ-ወጥ የከተማ ቦታ ወረራ ማስለቀቅ ሂደት እና የወንጀል ተጠያቂነት ....307

ክፍል አስር ....310

10.የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ አዋጅ....310

10.1 የኮንትሮባንድ ወንጀል እና ያልታደሰ ንግድ ፈቃድ ወንጀል ሀላፊነት ....310

10.2 የንግድ ዕቃዎችን ከመስመር ውጭ ማጓጓዝ ....319

ክፍል አስራ አንድ....323

11.የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ....323

11.1 ተጠርጣሪ በመረጠው የግል ሕክምና ተቋም የመታከም መብት....323

ክፍል አስራ ሁለት ....327

12.የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ....327

12.1 የምዝገባ ጊዜ ሳይጠናቀቅ የጦር መሳሪያ መያዝ የወንጀል ተጠያቂነት ....327

ክፍል አስራ ሶስት....336

13.ሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ....336

13.1 የግል ተበዳይ ባለመቅረበበት የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎችን ብቁነት ....336

ክፍል አስራ አራት....339

14.የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ....339

14.1 በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ከቅጣት በተጨማሪ መሳሪያ እንዲወረስ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት....339

II.የሕግ ማጣቀሻዎች ....343

ምዕራፍ አራት ....345

IV. በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ላይ የተሰጡ የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች....345

መግቢያ ....345

ክፍል አንድ....346

1.የፖሊስ ምርመራ....346

1.1 ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል....346
1.2 ኢግዚቢት- ኢግዚቢት አመመላለስ ....349
1.3 ብርበራ- የብርበራ ሕጋዊነት ....353
ክፍል ሁለት....362
2.የዋስትና መብት....362
2.1 ዋስትና በሕግ የሚፈቀድበት እና የሚከለከልበት አግባብ....362
2.2 ዋስትና በሁኔታ የሚፈቀድበት እና የሚከለከልበት አግባብ....365
2.3 የሙስና ወንጀል የዋስትና ሁኔታ ፣ ንብረት እግድ እና ቅድመ ክስ ....380
2.4 ዋስትና በድጋሚ የሚታይበት አግባብ እና ይግባኝ ....393
2.5 በምርመራ ወይም በወንጀል ክርክር ሂደት የግለሰቦች መብት እና ነፃነት....398
ክፍል ሶስት....403
3.ክስ ስለመሰማት....403
3.1 የወንጀል ክስ አዘገጃጀት ....403
3.2 የወንጀል ክስ ማሻሻል....407
3.3 የወንጀል ክስ ወደሌላ ስፍራ ማዛወር ....412
3.4 የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ....419
3.5 የእምነት ክህደት ቃል ....429
3.6 የወንጀል ድንጋጌን ፍርድ ቤት የሚለውጥበት አግባብ ....433
ክፍል አራት....438
የወንጀል ክስ ማስረጃ አቀራረብ እና ምዘና ....438
4.1 የሰበር ችሎቱ ማስረጃ የመዘነበት መዛግብት ....447
ክፍል አምስት ....458
5.ክስ ማንሳት ....458
ክፍል ስድስት....459
6.በግል አቤቱታ ስለሚቀርብ የወንጀል ክስ ....459
ክፍል ሰባት ....461
7.ተከሳሽ በሌለበት ክርክር ስለመቀጠል እና መጥሪያ አደራረስ....461
7.1 ከእምነት ክህደት ቃል እና መከላከያ ማስረጃ በኂላ የተከሳሽ አለመቅረብ....461

7.2 ተራ የሆነ የሰው ግዲያ ሙከራ ወንጀል ተከሳሽ በሌለበት የማይታይ...............463
ክፍል ስምንት ...............474
8. የይግባኝ ሥነ ሥርዓት እና የሰበር አቤቱታ...............474
8.1 የይግባኝ ሥነ ሥርዓት ...............474
8.2 የሰበር አቤቱታ ...............478
I.የሰበር ውሳኔዎች ማጣቀሻዎች ...............485
II.የሕግ ማጣቀሻዎች ...............488
III.የመፈለጊያ ቃላቶች**Error! Bookmark not defined.**...............504



<u>የክቡር ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎችን ሪፖርት ማድረግ ለረጅም ጊዜ ሲሰራበት የቆየ ሲሆን የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም ወጥ ባልሆነ ድግግሞሽ፣ ትኩረት እና ስፋት ቢሆንም ለረጅም ጊዜ ልምድ ሆኖ የቆየ ነው፡፡ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጡ ውሳኔዎች አስገዳጅ ሲደረጉ እነዚህን ውሳኔዎች አሳትሞ በማሰራጨት ለህዝብ ማድረስ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ላይ የተጣለ ኃላፊነት ሆኖዋል፡፡ አስገዳጅ ውሳኔዎች መታተማቸው የፍርዶችን ይፋዊ ይዘት ለመረዳት፣ ውሳኔ ተደራሽ ለማድረግ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡ ውሳኔዎች ተደራሽ መሆናቸው በመላ አገሪቱ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር፣ክርክሮች በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ወጪ እንዲቋጩ፣ክስ ከመመስረቱ በፊት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተሰጡ ውሳኔዎችን በመመርመር ተገቢ እና ብልህ ውሳኔ ለመወሰን እንዲቻል፣ የሕግ ትምህርትና ምርምር ለማዳበር እና ሕጎች በመሬት ላይ በሰው ሕይወትና በዕለት ተዕለት ኑሮ እያስከተሉ ያለውን ውጤት ለማየት፣ ለመመርምር እና ለመፈተሽ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ሕግ ሕይወት የሚዘራው ሲተገበርና በትርጉም ሲዳብር በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚሰራው ስራ ተደራጅቶ መገኘቱ ለሥነ ሕግ እድገት፣ ለእውቀት መስፋፋት፣ ለውይይት መዳበር ብሎም ለቀጣይ ለውጥ አስፈላጊ ስለሆነ በፍርድ ቤቶች በሚሰጡ ውሳኔዎች የተካተቱ የሕግ ትርጉም እና ትንታኔ ተደራጅቶ ተደራሽ መደረጉ አስፈላጊ ነው፡፡

የሰበር ስርዓት ከተዋወቀ በኋላ ከተደረገው ለውጥ አምስት ዳኞች ባላነሱ የሚሰየሙበት ችሎት የሚሰጣቸው ውሳኔዎች አስገዳጅ መደረጉ ጎልቶ የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህ መፍትሔ የጉዳዩችን ተገማችነት፣ ውሳኔዎችን ጸንቶ መቆየት የፍርድ ቤቶችን የስራ ጫና መቀነስ ወዘተ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን እነዚህ ጥቅሞችን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ስራ ላይ እንዲውል መደረጉ የሕግ ስርዓቱን ውጤታማነት፣ ተአማኒነት እና መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አለው፡፡ ይህ ውጤታማ የሚሆነው የውሳኔዎች ጥራት፣ መናበብ፣ መሰናሰል እና ጸንቶ መቆየት እንዲሁም ውሳኔዎች ተደራሽ ሆነው፤

በበቂ ሁኔታ ዜጎች ተረድተው የሚተገብሩት ሲሆን ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ውሳኔዎችን ተደራሽ ለማድረግ በተደረገው ጥረት እስከ አሁን 28 ቅጾቸን ለእትመት ማብቃት የተቻለ ከመሆኑም በላይ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎችና ሴቶችን ሕጻናትን የተመለከቱ ውሳኔዎች በሚል በልዩ እትም ተደራሽ ለማድረግ ተሞክሮዋል፡፡ አሁን ደግሞ በወንጀል ጉዳዩች ላይ የተሰጡ ውሳኔዎች ተደራጅተው እንዲገኙ ለማድረግ ይህ እትም ተዘጋጅቶዋል፡፡

በአውሮፓ ሕብረት ድጋፍ የወንጀል ፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ተነድፎ ወደ ስራ ከተገባ ጀምሮ በፕሮጀክቱ አስቀድመው የተለዩ ስራዎች ክንውን ሲካሄድ የቆየ ሲሆን ይህ ስራም የዚሁ ፕሮጀክት አካል ሆኖ የተሳካ ነው፡፡ ምንም እንኳ በፕሮጀክት ሰነዱ ይህ ሐሳብ ከመነሻው ያልነበረ ቢሆንም የውሳኔዎች ተደራሽነት ብቻ ሳይሆን በተደራጀ መንገድ መቅረባቸው ለወንጀል ፍትህ ስርዓቱ የሚኖረውን ፋይዳ በመረዳት ተጨማሪ ተግባር ተደርጎ በማካተት ይህ ስራ የተከናወነ መሆኑ ለፕሮጀክቱ ዓላማ መሳካት የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ስራ ውሳኔዎች ሰብሰቦ ከማሳተም ባለፈ በወንጀሉ ዓይነት እንዲደራጁና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተሰጡ ውሳኔዎችን በአንድ ላይ ማሰናዳት መቻሉ እና ተዛማጅ ውሳኔዎች በማጣቀሻ እንዲመላከቱ መደረጉ ከዚህ በፊት ከተደረጉት ጥረቶች በተለይ እሴት የተጨመረበት ስራ ነው፡፡ ይህም ለዳኞች፣ ለዐቃያነ ሕግ፣ ለጠበቆች፣ ለተመራማሪዎች እና ፍላጎት ላላቸው ዜጎች በተለየ ርዕስ ላይ የተሰጡ አስገዳጅ ውሳኔዎች በቀላሉ ለማግኘት፤ ተመሳሳይ ውሳኔዎች ያላቸውን ግንኙነት ለመገንዘብ፣ ለማጥናት እና ለመረዳት የሚያግዝ በመሆኑ ተጠቃሚን የበለጠ የሚረዳ እንደሚሆን ታምኖበታል፡፡

በወንጀል ፍትህ አስተዳደር በርካታ አካላት የሚሳተፉ ሲሆን የሂደቱ የመጨረሻ እልባት የሚገኘው በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች ባላቸው የሕግ ተርጓሚነት ኃላፊነት ሕጉን በክሱ ለተመለከቱት ፍሬ ነገሮች ተፈጻሚ በማድረግ የተከሳሹን ንጹህ ወይም ጥፋተኛ መሆን በመለየት ጥፋተኛ ሆነው በተገኙት ላይ ቅጣት የመወሰን ድርሻ አለው፡፡ ይህ የሚከናወነው በሚሰጠው ውሳኔ ሲሆን ይህ ውሳኔ የተሰጠው በሰበር ሰሚ ችሎት ከሆነ አስቀድሞ የተሰጠ ትርጉም በቀጣይ በሚነሱ ተመሳሳይ ጉዳዩች ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች ከሌሎች ጉዳዩች ጋር ተዳብለው በየጊዜው ሲታተሙ የቆዩ ቢሆንም በአንድ ተሰብስበውም ሆነ በመካከላቸው ያለውን መስተጋብርና ተመሳሳይነት በሚያሳይ እና በተደራጀ መልክ ታትመው የማይገኝ ስለነበረ ፈልጎ ለማግኘትም ሆነ ከሌሎች ውሳኔዎች ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ለመረዳት፣ በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጡ ውሳኔዎች ተመሳሳይነት፣ ልዩነት ወይም ግንኙነት ለመገንዘብ የሚቻልበት ዕድል ውስን ወይም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይህ እትመት ይህን ችግር የሚቀርፍ ከመሆኑም በላይ የአስገዳጅ ውሳኔዎችን ተደራሽ በማድረግ የሕጋዊነት መርህ መፈጸምን ምክንያታዊ የሚያደርግ ነው፡፡ ስራው ብዙ የተደከመበት የሆነውን ያህል ለተጠቃሚዎች በሚሰጠው አገልግሎት የሚያስገኘው ጥቅም የላቀ ከመሆኑም በላይ ተደራሽነትን ውጤታማ የሚያደርግ በመሆኑ ለወንጀል ፍትህ አስተዳደር አዎንታዊ አበርክቶ ያለው መሆኑ እሙን ነው፡፡

የዚህን ስራ ሐሳብ ከመደገፍ ጀምሮ ለፍሬ በማብቃት የተጉትን አዘጋጆች፣ ለእትመት እንዲበቃ በሁሉም ረገድ የተሳተፉትን እና በገንዘብ ድጋፍ ያደረገውን የአውሮፓ ህብረትን ማመስገን ተገቢ ስለሆነ በዚህ አጋጣሚ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስም ምስጋና ይድረሳችሁ፡፡

መልካም ንባብ!

**ቴዎድሮስ ምህረት ከበደ**

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት**

## I. የአህፅሮተ-ቃል ትርጉም

- ፍ/ቤት ............... ...... ፍርድ ቤት
- ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ...............ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት
- ፌ/ከ/ፍ/ቤት ............. ... ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
- ፌ/ጠ/ፍ/ቤት .......... ... ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
- ፌ/ዐ/ህግ ............. ...... ፌዴራል ዐቃቤ ህግ
- ሰ/መ/ቁ ............. ...... ሰበር መዝገብ ቁጥር
- ኮ/መ/ቁ ............ ...... ኮምፒውተር መዝገብ ቁጥር
- ወ/ህ ..................... ወንጀል ህግ
- ወ/መ/ስ/ስ/ህ ............ ወንጀል መቅጫ ስነ ስርአት ህግ
- ፍ/ብ/ህ .......... ...... ፍትህ ብሄር ህግ
- ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ ...... ...... ፍትህ ብሄር ስነ ስርአት ህግ
- የወ/ቅ/አ/መ...................የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ
- ፍ/ሚ ...... ...... ...... ፍትህ ሚኒስቴር

## II. መግቢያ

የአገራችን ወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ሦስቱንም የመንግስት አካላት ሕግ አውጭውን ፣ ሕግ አስፈፃሚውን እና ሕግ ተርጓሚውን እንደየስልጣናቸው አንዱ በሌላኛው ጣልቃ ሳይገባ በአንድነት የሚያሳትፍ ሥርዓት ነው፡፡ ሦስቱም በጋራ እና በተናጠል በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ፣ ይህንን የሚደርገው ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከማድረግ እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ሌሎች ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱ መንግስት ሕዝቦቹን፣ ነዋሪዎቹን ፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብት እና ጥቅም የማስጠበቅ እና የማረጋገጥ ዓላማ እና ግብ የማሳካት ሚና አላቸው፡፡

ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ እና በሌሎች ሕጎች እንዲሁም በአለምአቀፍ ስምምነቶች የተሰጣቸው የዳኝነት ሚና በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የመጨረሻው እና ወሳኙ ነው፡፡ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሕገመንግስቱ ከተሰጠው ከዳኝነት ሥልጣን ውስጥ አንዱ እና ከፍተኛው በአንቀፅ 80(3ሀ) መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የማረም ሥልጣን ነው፡፡ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም ሥርዓት እንዲኖር የማስቻል ሚና ያለው ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013ዓ.ም አንቀፅ 10 መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ጉዩች በሰበር የማየት ስልጣን እንዲኖረው ተደንግጓል፡፡

በዚህ አግባብ ከአምስት ባለነሱ ዳኞች የሚሰጥ የህግ ትርጉም ውሳኔዎች ከተሰጡበት ቀን ጀምሮ በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ የክልልም ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶችን አስገዳጅ እንዲሆን እና ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የህግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ወይም በሕትመት በተቻለ ፍጥነት ማሰራጨት እንደሚገባው በህጉ ተመላክቷል፡፡

ይህንን የሕገ-መንግስታዊ እና የአዋጁን ግዴታ ለመወጣት ባለፉት ዓመታት ውሳኔዎቹ በቅፅ መልክ እየታተሙ በኤሌክትኒክስ ሚዲያም ሆነ በሕትመት እንዲሰራጩ ሲያደረግ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ይህንን በተሻለ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ፍርድ ቤቱ ከያዘው ዳኝነት ሥርዓት ማሻሻያ ጋር በተናበበ መልኩ ግብዓት እንዲሆን ለማስቻል ይረዳ ዘንድ የሰበር ውሳኔዎች የቅፅ ሕትመት ሳይቋራረጥ በተከታታይ እንዲታተሙ እና ሁሉም ውሳኔዎች በፍርድ ቤቱ ድህረ ገፅ ላይ እንዲጫኑ እና መፈለጊያ ተሰርቶለት በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ፍርድ ቤቱ የሰበር ውሳኔዎች ሕትመት እና ስርጭትን ተደራሽ እና ተገማች ለማድረግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ ስለቶችን ተግባራዊ እያደረገ ቢሆንም የተጠናከረ አሰራር መዘርጋት የሚያስፈልግ መሆኑ ታምኖበት ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ክቡር ፕሬዚዳንት በተሰጠው ሥራ አቅጣጫ መሰረት በየጊዜው የሚወሰኑትን የሰበር ውሳኔዎች በድህረ ገፅ በመልቀቅ እንዲሁም በበቂ ሁኔታ ጊዜያቸውን ጠብቆ እንዲታተሙ ከማስቻል ባሻገር ያለውን ውስን ሀብት እና የሰው ሀይል በማስተባበር ውሳኔዎችን በተገቢ ሁኔታ በማደራጀት ግብዓት በመጨመር በልዩ እትም ማሳተምን እንደ አንድ ስልት ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል በማድረግ ይህ ልዩ እትም በባለሙያዎች ቡድን ተደራጅቶ እንዲዘጋጀ ተደርጓል፡፡

ይህ ልዩ እትም በአራት ምዕራፎች እና አርባ አምስት (45) ክፍሎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን የወንጀል ጉዳዮች እስከ አሁን የታተሙ ቅጾች ላይ ታትመው የወጡትን ውሳኔዎች አንድ እንዶቹ ደግሞ ያልታተሙትን አንድ ላይ በማሰባሰብ እንደየዘርፉ የወንጀል ህጉን ፍሰት በመከተል ተደራጅቶ ለተጠቃሚው ቀላል እና ምቹ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡

የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች በባሕሪያቸው ከተተረጎሙት አንቀፆች አንፃር የሚመሳሰሉ ወይም የሚቀራረቡ እና ተያያዥ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የተለመደ ባይሆንም አልፎ አልፎ በተመሳሳይ

ጉዳይ ላይ የተለያየ አቋም የተያዘበት የህግ ትርጉም ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ስለሆነም ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ ወይም ተቀራራቢ ውሳኔዎች አንድ ላይ በማደራጀት እንዲሁም በአቋም የተለዩ ያጋጠሙ እንደሆነም በዚያው በማመላከት የውሳኔዎች ጥራት እና ወጥነት እንዲጨምር ለማገዝ ነው፡፡

በዚህ ልዩ እትም የባለሰባት የሰበር ዳኞች የሰጡትንም ውሳኔዎች በመጨመር በውስጡ 86 (ሰማኒያ ስድስት) ውሳኔዎችን ከነሙሉ ይዘታቸው ተመርጦ ታትሟል፡፡ ለሕትመት የተመረጡት ስለጉዳዩ ገላጭ የሆኑት ሲሆኑ ሌሎች ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ የሆኑትን ውሳኔዎች ደግሞ ገላጭ በሆነ መልኩ በግርጌ ማስታወሻ በማደራጀት የተሰራ ነው፡፡ በባለሰባት የሰበር ችሎት ዳኞች እስካልተለወጠ ድረስ ለሕትመት የተመረጠውም ሆነ በግርጌ ማስታወሻ የተመለከቱት ውሳኔዎች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ሲሆን ለሕትመት የተመረጡት ለአዘገጃጀት እና ለማደራጀት ምቹ እንዲሆን ብቻ ነው፡፡ ተያይዘውም የሚደጋገፉ ብቻ ሳይሆኑ በአቋም በተወሰነ መልኩ የተለያዩትን የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች በሚኖሩበት ጊዜ ለማስተያየት ይረዳ ዘንድ ተመርጦ በዚህ ልዩ እትም የታተመ ሲሆን ከዚህም ጋር የሚያያዝ ሌላ ውሳኔ በግርጌ ማስታወሻ እንዲጠቀስ ተደርጓል፡፡ ይህንን ልዩ እትም በቀላሉ ለመጠቀም ቀጥሎ ያለውን የአጠቃቀም መመሪያ ማየት ይችላሉ፡፡

## III. <u>*የመፅሐፉ የአጠቃቀም መምሪያ*</u>

ይህ ልዩ እትም በአራት በምዕራፎች እና በ45 ክፍሎች እንዲሁም በንዑስ ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ ምዕራፎቹ እና ክፍሎቹ የተመረጡት የሕጎችን አፈጣጠር እና ፍሰት በመከተል ነው፡፡ አንድ አንድ ክፍሎች ራሳቸውን ችለው የተዋቀሩ ሲሆን በንዑስ ክፍል የተከፋፈሉትንም በማካተት ተዋቅሯል፡፡ የክፍሉ ርዕስ እና ከንዑስ ርዕስ ቀጥሎ ለህትመት የተመረጡ ውሳኔዎች ጭብጥ ይገኛል፡፡ በክፍሉ ወይም ንዑስ ክፍሉ ላይ ከጭብጡ በፊት የግርጌ ማስታወሻው ለሕትመት የተመረጡ ውሳኔዎች ማሳያ ነው፡፡

በልዩ ሁኔታ ካልተመላከተ በስተቀር በጭብጡ መጨረሻ ላይ የተመላከተው የግርጌ ማስታወሻ ከሰበር ውሳኔው ወይም ጭብጡ ጋር ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ የሆኑ ሌሎች የሰበር ውሳኔዎች ዝርዝር ማመላከቻ ነው፡፡ በግርጌ ማስታወሻው የገቡት የሰበር ውሳኔዎቹ ዝርዝር በተቻለ መጠን ይህ ልዩ እትም እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ያሉትን ተያያዥ ውሳኔዎች ሁሉንም ለማካተት የተሞከረ ቢሆንም ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ያልተካተተም ሊኖር ስለሚችል አንባቢው በዝርዝሮቹ ብቻ እንዳይገደብ እናሳስባለን፡፡

በዝርዝር በግርጌ ማስታወሻ ላይ የገቡት ውሳኔዎች ከተመረጡት ውሳኔዎች እና ጭብጦች ጋር ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ በመሆናቸው ነው፡፡ አንባቢው ከጉዳዩ ጋር በተገናኘ የተሰጡ የሰበር የህግ ትርጉም ውሳኔዎችን ከታተሙት ቅፆች እና/ወይም ከፍርድ ቤቱ ድህረገፅ በቀላሉ አውጥቶ መጠቀም እንዲችል እንደጥቆማ እንዲያገለግሉ የተዘረዘሩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ለህትመት የተመረጡት ውሳኔዎች በተቻለ መጠን ስለጉዳዩ ሁሉን አቀፍ እና በሀተታው ምሳሌ ሊሆን የሚችል ወይም ቀደምትነት ያለው እንዲሆን ታስቦ ስለሆነ በርዕሱ ስር የታተመውን ውሳኔ መጠቀም ይቻላል፡፡ አንድ አንድ ክፍሎች ላይ ተጨማሪ አጠር ያለ መረጃ የሚሰጥ ፅሁፍ በጉዳዩ ላይ በሰበር የተለያየ አቋም የተያዘ ስለመሆኑ ለማሳያነት ተካቷል፡፡ ለምሳሌ ስለተደራራቢ ወንጀሎች፣ ስለቅጣት መገደብ እና ሌሎችም ላይ ውሳኔዎቹ የተጠቀሱ እና በዝርዝር የተመለካቱ ሲሆን አቋሞቹ የተለያዩ ስለመሆናቸው የዚህ ልዩ እትም አዘጋጆች ሀሳብ ስለመሆኑ እናሳውቃለን፡፡

አንባቢዎች ከዋናው ማውጫ በተጨማሪ በዚህ እትም መጨረሻ ክፍል ላይ ባለው የቃላት መፈለጊያዎች እንደ ጠቋሚ በመጠቀም በቀላሉ ስለተፈለገው ጉዳይ የተፃፈበትን ቦታ ማወቅ ይችላሉ፡፡የሰበር ውሳኔዎች ዝርዝር በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ በየክፍሉ የተደራጀ ሲሆን ከክፍሉ ጋር ተያይዞ ያሉትን ውሳኔዎች ለማወቅ ያግዛል፡፡ በመጨረሻም ስለጠቅላላ ወንጀል ሕግ

ክፍል ከምዕራፍ አንድ፣ ስለ ወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ከምዕራፍ ሁለት፣ በልዩ ልዩ አዋጆች የተደነገጉትን ወንጀሎች ከምዕራፍ ሶስት እና ስለ ወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥርዓት ሕግ የተሰጡ የሕግ ትርጉሞችን ከምዕራፍ አራት ማግኘት ይችላሉ፡፡

መልካም ንባብ!

## ምዕራፍ አንድ

## I. የወንጀል ሕግ የጠቅላላ ድንጋጌ ክፍል የሰበር ሕግ ትርጉም ውሳኔዎች

### መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ከአራቱ ምዕራፎች የመጀመሪያው ሲሆን በወንጀል ሕጉ የጠቅላላ ድንጋጌ ክፍል የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎችን በ13 (አሥራ ሦስት) ክፍሎች በማደራጀት የያዘ ነው፡፡ ክፍሎቹ የተዋቀሩት በተቻለ መጠን የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ሂደትን በመከተል ሲሆን ዋና ዋና ጉዳዮችን እና አካታች ሊሆን የሚችሉትን እንደ አርዕስት በመምረጥ ገላጭ የሆነውን የሰበር ውሳኔ በመጠቀም ሌሎችን ተመሳሳይ እና ተያያዥ የሆኑትን በግርጌ ማስታዋሻ በማካተት የተደራጀ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የወንጀል ሕግ መርሆች እና የፍርድ ቤቶች ስልጣን፣ የወንጀል ድርጊትን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች፣ የወንጀል አፈፃፀም ደረጃዎች፣ የወንጀል ኃላፊነት( ከፊል ኃላፊነት ፍፁም ኃላፊነት)፤ በወንጀል ጥፋተኛ መሆን፣ በተደራራቢ ወንጀል ጥፋተኛ መሆን፣ በሕጉ የተፈቀዱ የማያስቀጡ እና ይቅርታ የሚያሰጡ፣ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎችና መመሪያ፣ ንብረት መውረስ፣ የፍ/ብሄርና የወንጀል ጉዳዮች ተጣምረው መታየት፣ ቅጣት መገደብ፣ የይርጋ ድንጋጌዎች እና ወጣት ጥፋተኛ በሚሉ ዋና ዋና ክፍሎች በመከፋፈልና በነዚህ ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸውን 24 (ሃያ አራት) አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎችን በሙሉ ይዘታቸው በማስገባት ቀሪዎቹን ውሳኔዎች በማጣቀሻነት በመጠቀም በዚህ ምዕራፍ ስር ተካቶ ቀርቧል፡፡

### ክፍል አንድ

### 1. የወንጀል ሕግ መርሆዎች እና የፍርድ ቤቶች ስልጣን

#### 1.1 በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስ ወይም ቅጣት ክልክል ስለመሆኑ[1]

- በድጋሚ ያለመከሰስና ያለመቀጣት መብቱን የሚጥስ ነው ብሎ ለመከራከርና የህገ መንግስቱም ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዲሆንለት ለመጠየቅ ሁለት መሠረታዊ መስፈርቶች ሊሟሉ ይገባል፡፡ የመጀመሪያው ተከሣሹ በተመሣሣይ የወንጀል ድርጊት በወንጀል ህግና ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት የተከሰሰ የነበረ መሆኑ ማረጋገጥ ነው፡፡ ሁለተኛው ተከሣሹ ከዚህ በፊት በተከሰሰበት ወንጀል ድርጊት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡
- በአስተዳደራዊ ውሳኔ መቀጣት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስቀር የሚችል ካለመሆኑም በላይ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከልን ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡[2]

---

[1]የሰ/መ/ቁ 72304 (ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13

[2]በሰ/መ/ቁ 60217(ጥቅምት 15 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ/ 85237 (መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ 237423 (መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ/ም) ቅፅ 27፣ በሰ/መ/ቁ 103775 (ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 223134 (ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 151034 (ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23

የሰ/መ/ቁጥር - 72304

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የትግራይ ክልል አጽቢ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ

ተጠሪ፡- ተማሪ ሐጎስ ወልደሚካኤል በሌለበት ታይቷል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 42048 በግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአጽቢ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ በአንድ የወንጀል ድርጊት ሁለት ጊዜ የመከሰስና የመቀጣት ሕጋዊነትን አስመልክቶ በቀረበ ክርክር ላይ የተሰጠውን የሕግ ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለአጽቢ ወረዳ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 8.00 ሰዓት በማለት በም/እምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት የገደለ በመሆኑ ሆነ ብሎ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ በወንጀል ክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሟችን ድንጋይ ወርውሬ መትቻለሁ፡፡ ነገር ግን ሟች ድኖ ሌላ ጊዜ የሞተ በመሆኑ ለሟች መሞት በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰው ምስክርና የፅሑፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ሟች በድንጋይ ከተመታ በኋላ ሕክምና ተደርጐለት ድኖ የመስኖ እርሻ ሥራ ሲሰራ የነበረ መሆኑን ያውቁልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት የገደለ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው በማለት ተጠሪ በአሥር ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውቅሮ ምድብ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ከመረመረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ነጥብ የለም በማለት የተጠሪን ይግባኝ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ተጠሪ አመልካች ከዚህ በፊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ በመተላለፍ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀነ 8.00 ሰዓት በም/እምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ በመምታት በግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ለወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርቦብኝ ጥፋተኛ ተብዬ በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም ተቀጥቻለሁ፡፡ አመልካች ተጠሪ በተቀጣሁበት ድርጊት በማንሣት በድጋሚ በወንጀል መከሰሱና የበታች ፍርድ ቤቶችም እኔን ጥፋተኛ ብለው ቅጣት መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይህንን ነጥብ

መጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አድርጐ ያላቀረበ ስለሆነ የሰበር መከራከሪያ ሊያደርገው አይገባም፡፡ ተጠሪ ከዚህ በፊት የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ነው አሁን የተከሰሰው በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል ተብሎ ስለሆነ የቀረበው ክስ በፊት ከተከሰሰበት ጋር በአንድ ጉዳይ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23ና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 በመተርጐም የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ በመሆኑ በድጋሚ በዚያው ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔን በመሻር ተጠሪን አሰናብቶታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ለዚህ የሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትና በድርድር ጥፋተኝነቱን አምኖ ጥፋተኛ ተብሎ ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የተቀጣው የተሳሳተ ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አቶ ግደይ ገብረየሱስ የካቲት 21 ቀን 2002 በተጠሪ ድንጋይ ተመትተው መጋቢት 30 ቀን 2002 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ የሟች አቶ ግደይ ገብረየሱስ ህይወት ለሕልፈት የበቃው ተጠሪ በድንጋይ ጭንቅላታቸው ላይ ባደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት መሆኑ በሚኒሊክ ሆስፒታል ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ትክክለኛውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል በማለት ያቀረብነውን ክስ ተቀብለው የወረዳው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 የሚጥስ ነው በማለት በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በአድራሻው ተፈልጎ ያልተገኘ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ያቀረበው የሰበር ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ በወንጀል አንቀጽ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች አቶ ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል በማለት በድጋሚ መክሰሱንና ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤትና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 5 የሚጥስ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ ስምንት ስዓት በም/እምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ የግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስን የመታቸው መሆኑን ያልካደ ሲሆን ይህ ፍሬ ጉዳይ በዓቃቤ ሕግ ማስረጃም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ይህንን ድርጊት በፈጸመ በሁለተኛው ቀን ማለትም የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም አመልካች ለወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ በግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦበት ተጠሪ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የተቀጣ መሆኑን አመልካች ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርና ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በግልጽ በማመን አቅርቦታል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በይዘቱ መጀመሪያ ለወንበርታ

ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ወንጀል ክስ፣ በዓቃቤ ሕግ የቀረበው የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ የሞት አደጋ ማድረሱ ከመታወቁ በፊት ነው፡፡ አሁን ግን የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ ሞት አደጋ ማድረሱ በመታወቁ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሆነ ብሎ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ተጠሪን በድጋሚ መክሰሳችን ሕጋዊና ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት መሠረታዊ የወንጀል ሕግ መርህ አድርጎ ከደነገጋቸው ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች አንደኛው አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ በተቀጣበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና መከሰስና መቀጣት የለበትም የሚለው ነው፡፡ ይህ የወንጀል ሕግ መርህ በሕገ መንግስቱ ብቻ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 ተደንግጓል፡፡ ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 23 "ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነሥርዓት መሰረት ተከስሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም" በማለት ደንግጓል፡፡ የወንጀል ህግ መርሁ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ሲሆን አገራችን ባጸደቀችው በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 7 "No one shall be liable to be tried or punished again for an offence for which he has already been finally convicted or acquitted in accordance with the law and penal procedure of the country " በሚል መንገድ ደንግጎል፡፡ ሆኖም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት አተረጓጐም በዕለት ከዕለት የወንጀል ክስ አቀራረብ በሚታዩ ስህተቶች የሚፈጠሩ ችግሮችን ዓቃቤ ሕግ በድጋሚ የወንጀል ክስ በማቅረብ ለማረም በሚፈቅድ ሁኔታ የተቀረጸ ነው ወይስ አይደለም፤ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ድንጋጌ እንዴት መተርጎምና ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል የሚለው ነጥብ አከራካሪ መሆኑን አመልካች ተጠሪ የግል ተበዳይን በድንጋይ ወርውሮ የመታው በግል ተበዳይ ላይ ቀላል የአካል በደል ለማድረስ አስቦ በድርጊቱ ቀላል የአካል ማጉደል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈፅሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦ ተጠሪ በአመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ተከራክሮ ከተቀጣ በኃላ አመልካች ከዚህ በፊት በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ ሳቀርብ የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ያስከተለውን ወይም ሊያስክትል የሚችለውን ውጤት በማገናዘብም ሆነ አግባብነት ያለውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመምረጥና በመጥቀስ የተሳሳትኩ ስለሆነ ተጠሪን ሆነ ብሎ ተራ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት በድጋሚ ክስ እንዳላቀርብ የሚከለክለኝ ሕግ የለም በማለት በዚህ መዝገብ ያቀረበውን ክርክር በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት የሚቻለው አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በድጋሚ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በአንድ ጉዳይ በድጋሚ ያለመከሰስና ያለመቀጣት መብቴን የሚጥስ ነው ብሎ ለመከራከርና የህገ መንግስቱም ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዲሆንለት ለመጠየቅ ሁለት መሠረታዊ መስፈርቶች ሊሟሉ ይገባል፡፡ የመጀመሪያው ተከሣሹ በተመሣሣይ የወንጀል ድርጊት በወንጀል ህግና ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት የተከሰሰ የነበረ መሆኑ ማረጋገጥ ነው፡፡ ሁለተኛው ተከሣሹ ከዚህ በፊት በተከሰሰበት ወንጀል ድርጊት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በአንድ ተከሣሽ ላይ የወንጀል ክስ ለማቅረብ ወይም ላለመቅረብ የሚሰጠው ውሣኔና የወንጀል ክስ ለማቅረብ ከወሰነ በኂላ ተከሣሹ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልበትን የወንጀል ድርጊትና የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በወንጀል የፍትህ ሥርዓቱና በወንጀል የፍርድ ሂደት ውስጥ እጅግ ወሣኝና የመጀመሪያውና መሠረታዊ ውሣኔና ክንውን ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ በአንድ ተከሣሽ ላይ የወንጀል ክስ ከማቅረቡ በፊት ተከሣሹ አንድ ወንጀል በመፈጸም ሃሣብ የሰራው አንድ የወንጀል ድርጊት ያስከተላቸውን ወይም ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ውጤቶች ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ በማገናዘብና አግባብነት ያላቸውን ህግ ድንጋጌዎች በመለየትና በመጠቀስ የወንጀል ክሱን በጥንቃቄ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት፣ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 1፣ ከወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 41፣ አንቀጽ 111 እና አንቀጽ 112 ና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ በህግ የተጣለበትን ግዴታ

ሣይወጣ ተከሣሹን በቀላል ወንጀል ኃላፊና ተጠያቂ የሚያደርግ የወንጀል ድንጋጌ ጠቅሶ ክስ አቅርቦ ተከሣሹም፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የእምነት ክህደት ቃልን ከሰጠና ተከራክሮ በቀረበበት የወንጀል ክስ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ ከተቀጣ ወይም በነፃ ከተለቀቀ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ከዚህ በፊት በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ ያስከተለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በማገናዘብም ሆነ አግባብነት ያለውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመምረጥና በመጥቀስ ተሳሳቻለሁ በሚል በተከሣሹ ላይ በድጋሚ የወንጀል ክስ ቢያቀርብ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 በምን መንገድ መተርጐምና ተፈጻሚ መሆን አለባቸው የሚለውን ነጥብ እንድንመረምር ያስገድደናል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች ያቀረበው የዚህ አይነት ክርክር ሲያጋጥም ከሁሉም በፊት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌው ሊያሳካው የሚፈልገውን ግብና ዓላማ መሠረት በማድረግ ክርክሩን በመመርመር መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 23 ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን አስመልክቶ የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች በህገ መንግስቱ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነቶች በተለይም ከዓለም ዓቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 7 ይዘት፣ ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን ጋር ማገናዘብ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የዚህ ዓለምአቀፍ የወንጀል ህግ መርህ መሠረታዊ ዓላማ የአንዲት አገር መንግስት ህግ አስከባሪ አንድ ጊዜ የወንጀል ክስ አቅርቦበትና ተከራክሮ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት: በሌላ ጊዜ ተከሳሹን በድጋሚ ለመክሰስና ለማስቀጣት የማይችል መሆኑን በመደንገግ ሰዎችን በአንድ ወንጀል ድርጊት በተደጋጋሚ በሚቀርብ የወንጀል ክስ ስጋት ውስጥ እንዳይወድቁ በመከልከል ለሰዎች የተረጋጋና ሰላማዊ ኑሮ ዋስትና እና ጥበቃ መስጠት ነው፡፡ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 በአቀራረጹና በይዘቱ በአንድ በኩል ዓቃቤ ህግ ለአንድ የወንጀል ድርጊት በተለያየ ጊዜ የተለያየ የወንጀል ርዕስና የህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ወይም ተመሳሳይ የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ተከሳሽ ተከስሶ በፍ/ቤት በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ነፃ ከወጣ ወይም ከተቀጣ በኋላ በድጋሚ በወንጀል እንዳይከሰስና እንዳይጠየቅ የሚከለክል በሌላ አነጋገር የመንግስት የወንጀል ክስ የማቅረብ ሥልጣንን የሚገድብ መሰረታዊ ድንጋጌ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድንጋጌው አንድ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል ተብሎ ከወንጀል ክሱ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት ጉዳይ ሌላ የወንጀል ክስና ተጠያቂነት ይመጣብኛል ከሚል ጭንቀት ሥጋት እንዳይሸማቀቅ ህገ መንግስታዊ ዋስትናና ጥበቃ በመስጠት ተከሳሹ በወንጀል ተከስሶ በመጨረሻ ፍርድ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት የወንጀል ድርጊት በድጋሚ የማይከሰስና የማይፈረድበት ስለመሆኑ ህገ መንግስታዊ ዋስትና ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የተረጋጋ ህይወት እንዲኖር የማድረግ ዓላማና ግብ ያለው ነው፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ህግና በወንጀል ስነ ስርዓት ተከስሶ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ ተቀጥቷል ወይም በነፃ ተለቋል የሚለው መከራከሪያ በመጀመሪያ የወንጀል ክስ የክስ መቃወሚያ ሆኖ መቅረብ ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 የተደነገገ ሲሆን ፍ/ቤቱ ያቀረበው የክስ መቃወሚያና ማስረጃ በመመርመር ውሳኔ መስጠት ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 131 ተደንግጓል፡፡

ሆኖም አንድ ተከሳሽ በወንጀል ተከስሶ በመጨረሻ ፍርድ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት የወንጀል ድርጊት በድጋሚ ያለመከሰስ ያለመጠየቅ መብት መሰረታዊና ህገ መንግስታዊ መብት በመሆኑ ክርክሩ በሚካሄድበት በማናቸውም ደረጃ ሊነሳ የሚችልና በማስረጃ ተረጋግጦ በተገኘ ጊዜ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ብይን የሚሰጡበት የመከራከሪያ ነጥብ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ይህን ነጥብ በወረዳው ፍ/ቤት ሣይነሳ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪን ክርክር ተቀብሎ መወሰኑ የህግ መሰረት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ አመልካች ያቀረበውን ሁለተኛ ክስ በመቀበልና በማከራከር የሰጡትን የጥፋተኝነትና

የቅጣት ውሳኔ መሻሩ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረታዊ ይዘት፣ ዓላማና የተፈፃሚነት ወሰን ያገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 42048 በግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>1.2 የሕጋዊነት መርህ[3]</u>

- በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሳል በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደ ወንጀል ሊቆጥሩት እንደማይችሉ በወንጀል ህግ በአንቀጽ 2 ስር የተደነገገ በመሆኑ ወንጀልነቱ በግልጽ ባልተደነገገ ድርጊት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፍ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡
- የወንጀል ሕግ ስለልዩ ልዩ ወንጀሎችና በወንጀል አድራጊዎች ላይ ስለሚፈፀሙት ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች በዝርዝር እንደሚደነግግ እና ፍ/ቤቶች በሕግ ከተደነገጉት በቀር ሌሎች ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን እንደማይችሉ በወ.ሕ.አ. 2(1)እና (2) ተመልክተዋል፡፡
- ንብረት ወይም ሀብት ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግን ጨምሮ ፍ/ቤቶች በወንጀል ረገድ የሚሰጡት ማናቸውም ውሳኔ በወ/ሕ/አ 2 የተደነገገውን የሕጋዊነት መርህ መሰረት ያደረገ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡[4]

የሰ/መ/ቁ. 81178

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ረታ ቶሎሳ
ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ከበደ ተሰራ
2. አቶ ሌንጫ ዘገየ

አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ቁጥሩ 81178 በሆነው በዚህ መዝገብ፣ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ደግሞ ቁጥሩ 81179 በሆነው መዝገብ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ ተጣምሮና ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

[3]የሰ/መ/ቁ. 81178 (መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 18
[4]በሰ/መ/ቁ 75387 (ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 14

## ፍርድ

አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ተጠሪዎቹ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በተናጠል በተለያየ መዝገብ ተከሰው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠባቸው የወንጀል ክሶች መካከል ሁለቱንም ተጠሪዎች በ1ኛ ክስ ከተመለከተው ወንጀል በነፃ በማሰናበት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አመልካች በተጠሪዎቹ ላይ በተለያዩ መዝገቦች ያቀረባቸውን የተለያዩ የወንጀል ክሶች የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ፤ በ1ኛ ተጠሪ ላይ በአምስት ክሶች የጥፋተኝነት እና በድምሩ የሃያ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ከብር 165,000 መቀጮ ጋር፤ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በአምስት ክሶች የጥፋተኝነት እና በድምሩ የአስራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ከብር 100,000 መቀጮ ጋር፤ ውሳኔ መስጠቱን፣በውሳኔው ቅር በመሰኘት ሁለቱ ወገኖች ያቀረቡለትን ይግባኝ

የመረመረው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን ይግባኝ በተመለከተ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁለቱንም ተጠሪዎች ከ1ኛ የወንጀል ክስ በአብላጫ በነጻ በማሰናበት እና በሌሎች የወንጀል ክሶች ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን ቅሬታ በሙሉ ድምጽ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱን፤አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ በተመለከተም የተጠሪዎቹ የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ በተደረገባቸው የወንጀል ክሶች በተጠሪዎቹ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተጥሎ የነበረውን የቅጣት መጠን ከፍ በማድረግ በ1ኛ ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት በአምስት የወንጀል ክሶች ተጥሎ በነበረው የሃያ አመት ጽኑ እስራት ምትክ በይግባኝ ደረጃ የጥፋተኝነት ውሳኔው በጸናባቸው አራት የወንጀል ክሶች የ25 ዓመት ጽኑ እስራት፤በ2ኛው ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት በአምስት የወንጀል ክሶች ተጥሎ በነበረው የ13 ዓመት ጽኑ እስራት ምትክ በይግባኝ ደረጃ የጥፋተኝነት ውሳኔው በጸናባቸው አራት የወንጀል ክሶች የ20 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት በመጣል ውሳኔ መስጠቱን፤በ2ኛ ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተጣለው የመቀጮ መጠን በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያልተለወጠ ሲሆን በ1ኛ ተጠሪ ላይ ተጥሎ የነበረው የብር 165,000 መቀጮ ወደ ብር 300,000 ከፍ መደረጉንና እና በንብረት ውርስ ረገድም አንዳንድ ማሻሻያዎች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መካተታቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ከላይ እንደተገለጸው በተጠሪዎቹ ላይ በ1ኛ ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመሰረዝ ተጠሪዎቹ በእነዚህ የወንጀል ክሶች ረገድ በነጻ እንዲሰናበቱ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አመልካች በሶስት መዝገቦች ያቀረበው አቤቱታ ቁጥሩ 81117 በሆነው መዝገብ ተጣምሮ ከታየ በኃላ ተጠሪዎቹ ብድርን እንደመደበኛ ስራቸው በማድረግ በተደጋጋሚ ጊዜ ቼኮችን፣የቦታ ካርታን፣የንግድ ፍቃድን እና የመኪና ሊብሬን መያዣ በማድረግ ለተለያዩ ሰዎች በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በብድር ይሰጡ እንደነበር ከፍተኛ ፍ/ቤት በማስረጃ አረጋግጦ የጥፋተኝነት ውሳኔ በሰጠበት ሁኔታ ተጠሪዎቹ ብድር መስጠትን እንደመደበኛ ስራ በማድረግ ተደጋጋሚ ብድር መስጠታቸውም ሆነ ብድሩን የሰጡት በተደጋጋሚና በከፍተኛ መጠን መሆኑ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አነጋገር አንፃር የባንኮችንና የሌሎች የገንዘብ ተቋማትን ስራ ያለ ፍቃድ ሰርተዋል ለማለት የማይቻል በመሆኑ ድርጊቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 61 መሰረት በአራጣ ወንጀል ክስ ስር ተጠቃሎ የሚታይ ነው በማለት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የመሰረዙን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለመመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎቹ በተያዘላቸው ቀጠሮ መልስ ባለማቅረባቸው መብታቸው ከታለፈ በኃላ 1ኛ ተጠሪ በተያዘላቸው ቀጠሮ መልስ ያላቀረቡበትን ምክንያት ገልጸው በተፈቀደላቸው መሰረት በጠበቆቻቸው የተዘጋጀና የተፈረመ መልስ በማያያዝ የክርክሩ ተካፋይ ሆነዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የተጠሪዎቹን ይግባኝ በከፊል

በመቀበል በፌ/ከ/ፍ/ቤት ከተሰጠው ውሳኔ ውስጥ በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ ተጠሪዎቹ ከእነዚህ ክሶች በነጻ እንዲሰናበቱ በድምጽ ብልጫ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በተጠሪዎቹ ላይ ቀርቦ የነበረው 1ኛ ክስ ተመሳሳይ ድንጋጌ የተጠቀሰበት ሆኖ ይዘቱ በጥቅል ሲታይ ተጠሪዎቹ በገንዘብና በባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሽ) እና 2 (ሀ)ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የብድር ስራ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ከብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፍቃድ ሳይኖራቸው ለተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ በብድር በመስጠትና ለብድሮቹም ቼኮችንና የተለያዩ ሰነዶችን በመያዣነት በመቀበል ለባንኮችና ለመሰል ፋይናንስና አክሲዮን ማህበራት የተፈቀደውን የባንክ ስራ በህገወጥ መንገድ እንደንግድ ስራ በተደጋጋሚ የመስራት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን ወንጀሉን ፈጽመዋል የተባሉትም 1ኛ ተጠሪ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ አምስት ጊዜ ለአንድ ድርጅት በድምሩ ብር 12,090,000 ፤2ኛ ተጠሪ በአስር ዓመታት ውስጥ በ25 የውል ሰነዶች ለ11 ተበዳሪዎች በድምሩ ብር 3,711,111 በብድር በመስጠት መሆኑን የክሶቹ ዝርዝር ያመለክታል፡፡ሁለቱ ተጠሪዎች በየቀረበባቸው 1ኛ ክስ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን፣በየክሶቹ በተመለከተው የጊዜ ወሰን፣የድግግሞሽ መጠን እና ሁኔታ በየክሶቹ ለተጠቀሱት ግለሰቦችና ድርጅቶች በብድር መስጠታቸውን ክሱ የቀረበለት ፌ/ከ/ፍ/ቤት በማስረጃ አጣርቶ ያረጋገጠ ሲሆን በክሶቹ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠባቸውም ተጠሪዎቹ ከሳሽ ወገን ያስረዳባቸውን ፍሬ ነገሮች በመከላከያቸው አላስተባበሉም በማለት ነው፡፡ በክሶቹ የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር በተጠሪዎቹ መፈጸሙ በማስረጃ ተጣርቶ ተረጋግጦአል መባሉ በመሰረቱ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔውን በሰጠው አብላጫ ድምጽም ቢሆን አልተነቀፈም፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ግዙፋዊ ፍሬነገሩ ተረጋግጦአል መባሉን ተቀብሎ ነገር ግን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔውን በአብላጫ ድምጽ ለመሰረዝ የሰጠው ዓይነተኛ ምክንያት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በቀረበው 1ኛ ክስ ማንኛውም ሰው "…በማናቸውም ሌላ አኳኃን የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ ወንጀል የተሰራበት እንደሆነ ወንጀል የተሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀለኛ ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡" የሚል አነጋገር እና "ወንጀሉ የተፈጸመው ሥልጣንን መከታ በማድረግ ወይም በመንግስት ስራ አጋጣሚ ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትን ለማካበት ወይም በተደጋጋሚ ሲሆን ወንጀል የተሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 20,000 የማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡" የሚል አነጋገር ያዘሉት የአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሽ) እና (2)(ሀ) ድንጋጌዎች በተደጋጋሚ፣ለንግድ መጠን እና ለበርካታ ተበዳሪዎችም ቢሆን በግለሰብ ደረጃ ብድር የመስጠት ስራ የተከለከለ ወይም የሚያስቀጣ የወንጀል ተግባር መሆኑንና እና ብድር የመስጠት ስራ ሊከናወን የሚችለው በባንክ ብቻ መሆኑን በግልጽ እንደማይደነግጉ፣ ፍ/ቤቶች ሕግን ከመተርጎም የማይታገዱ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገወጥነቱ በሕግ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደ ወንጀል ሊቆጥሩትና ቅጣት ሊወስኑበት እንደማይችሉ፣በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሳል በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደ ወንጀል ሊቆጥሩት እንደማይችሉ በወንጀል ህግ በአንቀጽ 2 ስር የተደነገገ በመሆኑ ወንጀልነቱ በግልጽ ባልተደነገገ ድርጊት በተጠሪዎቹ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መተላለፉ መሰረታዊ የሆነውን የህጋዊነት መርህ የሚጻረር ነው የሚል መሆኑን የውሳኔው አጠቃላይ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

እንደተባለው በከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለቱ ተጠሪዎች በ1ኛ ክስ ጥፋተኛ ተብለውበት የነበረው የገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሽ) እና (2)(ሀ) ድንጋጌዎች ይዘቱ ቀደም ሲል የተገለጸውንና በተጠሪዎቹ መፈጸሙ የተረጋገጠውን ግዙፋዊ ፍሬነገር በወንጀልነት የሚፈርጁ ወይም የሚደነግጉ አለመሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት አብላጫ

ድምጽ የሰጠውን ሰፊ ትችት እና የደረሰበትን ድምዳሜ በበኩላችን ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የወንጀል ሕግ በተወሰኑ ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ ህጉ ደንግጎ ሲገኝ ግምት የሚወስድባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በመሰረታዊነት ግን የአንድ ድርጊት ወይም ግድፈት ወንጀልነት በሕጉ በግልጽ ተደንግጎ መገኘት የሚገባው መሆኑ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 በተመሳሳይ ሁኔታ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለድርጊቱ እና ስላአፈጻጸሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 112 የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ የድርጊቱ ወይም የግድፈቱ ወንጀልነት በሕጉ በግልጽ ያልተደነገገ በሆነ ጊዜ ወንጀልን ለማቋቋም ከሚያስፈልጉት ፍሬ ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው ሕጋዊ ፍሬ ነገር የተጓደለ ስለሚሆን ከወ.ሕ.አ. 23(2) መሰረታዊ ድንጋጌ አንጻር ወንጀል ተፈጽሞአል ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የወንጀል ሕግን መሰረታዊ መርሆዎች መሰረት በማድረግ በተጠሪዎቹ በቀረበለት ይግባኝ መነሻ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ በዚህ ረገድ ተጠሪዎችን በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪን አስመልክቶ በመ.ቁ. 59831 በ03/08/2004 ዓ.ም.፣2ኛ ተጠሪን አስመልክቶ በመ.ቁ. 55859 በ01/08/2004 ዓ.ም. ከሰጠው ውሳኔ ውስጥ በተጠሪዎቹ ይግባኝ መነሻ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በመ.ቁ. 82321 በ09/09/2002 ዓ.ም.፤በ2ኛ ተጠሪ ላይ ደግሞ በመ.ቁ. 82644 በ16/06/2002 ዓ.ም. በአንደኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ በዚህ ረገድ ተጠሪዎቹን በማሰናበት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቶአል፡፡
2. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ክርክሩ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ከተወሰነው መ.ቁ. 81179 ጋር እንዲያያዝ ይደረግ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡
   የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>1.3 በወንጀል ጉዳዮች የፍርድ ቤቶች  የስረ-ነገር ስልጣን[5]</u>

- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በወንጀል ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ስረነገር ስልጣን የሚኖረዉ ወንጀሉ የፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን ነዉ ተብሎ ከተዘረዘሩት ወንጀሎች ዉስጥ የተካተተ እንደሆነ እና በጉዳዩ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ስልጣን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡
- በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12(1) እና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ በግልጽ ያልተሸፈነ ጉዳይ ሲያጋጥም ወይም የአዋጁ ድንጋጌ አሻሚ

[5] የሰ/መ/ቁ 248494 (ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም)

ሲሆን በስራ ላይ ያሉትን ሌሎች የስነ ስርዓት ህጎች ተከትሎ እልባት መስጠት ሕጋዊ መሰረት አለው፡፡[6]

- የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 3(1) በመተላለፍ ያለ ፈቃድ የባንክ ስራ ሰርቷል ተብሎ የሚቀርብ ወንጀል ክስ የስረነገር የዳኝነት ስልጣኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ ወይስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ነዉ የሚለዉን ጥያቄ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12(1) እና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 ሰንጠረዥ በጣምራ ስንመለከት የስረነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አለመሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የሰበር/መ/ቁ 248494

ጥቅምት 6 ቀን 2017ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች - ዳንኤል መኮንን አደሙ

ተጠሪ - በፍትህ ሚኒስቴር ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ስህተት የለዉም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 011774 ላይ በቀን 21/09/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በሰበር ችሎት እንዲታረም ሲል አመልካች በቀን 02/10/2015 ዓ.ም ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በ19/01/2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ አመልካች የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 3(1) እና 58(1) በመተላለፍ የባንክ ስራን ለመስራት ፈቃድ ሳይኖረው በሳውድ አረቢያ የምትኖር ዘሀራ መሃመድ ከተባለች የአጎቱ ልጅ ጋር በሳውዲ የሚኖሩ ግለሰቦች ለቤተሰቦቻቸው ወደ ኢትዮጵያ የሚልኩትን ገንዘብ በመቀበል እንዲላክላቸው የተባሉትን ሰዎች ስም፤አድራሻ እና የገንዘብ መጠኑን በምታደርገው ገለፃ መሰረት በተከፈው የሂሳብ ቁጥር 220501001183/1000029636463 እና 100126393095 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፖፑላሬ ቅርንጫፍ ከአዲስ አበባ ውጭ ለሚገኙት ገንዘብ ተቀባዮች ከ30/4/2004ዓ.ም እስከ 19/01/2008 ዓ.ም ድረስ አራት መቶ የሐዋላ መልዕክት በመላክ በአጠቃላይ 2,990,526.30 በማስተላለፍ ይህ ገንዘብ በህጋዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ተልኮ ቢሆን ኖሮ ሀገሪቱ ታገኝ የነበረውን 156,408.28 የአሜሪካ ዶላር

---

[6] በሰ/መ/ቁ 248286 (ታህሳስ 28 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ ሰ/መ/ቁ/ 243034 (ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 265085 (ጥር 27 ቀን 2017 ዓ/ም)፣ በሰ/መ/ቁ 155773 (ጥቅምት 23 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ/ 99883 (ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 228813 (መጋቢት 27 ቀን 2015)

እንድታጣ ያደረገ በመሆኑ ያለብሄራዊ ባንክ ፈቃድ የባንክ ስራ መስራት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነዉ፡፡

አመልካችም በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ የተከራከረ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የአቃቤ ህግ ምስክሮች ቀረበዉ በሰጡት ምስክርነት አመልካችን በአካል የሚያውቁና ስልክ እየደወለ ብር መላኩን ነግሯቸው በኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በከፈቱት ሂሳብ ቁጥር እንደሚያስገባላቸው የሚልኩትም ዘመዶቻቸው መሆናቸውን መመስከራቸዉንና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኦዲተሮችም ተጠሪ ከ30/04/2004ዓ.ም እስከ 19/01/2008ዓ.ም አራት መቶ ጊዜ የሐዋላ መልዕክት በመላክ ብር 2,990,526.30 በማስተላለፍ ሀገሪቱ ታገኝ የነበረውን 156,408.28 የአሜሪካ ዶላር እንድታጣ ያደረገ መሆኑን በኦዲት ሪፖርት ተመላክቷል በሚል አመልካች እንዲከላከል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቶ 3 የመከላከያ ምስክሮችን ያሰማ ሲሆን ምስክሮቹ ስለ አመልካች ባህሪና የስራ ሁኔታ ማስረዳታቸዉን እና ፍርድ ቤቱም ማስረጃዉን መርመሮ መከላከያ ምስክሮች ቃል ግምት እንጂ የተጠቀሰውን ድርጊት ስላለመፈፀሙ አላስረዱም ሲል የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 3/1 እና 58/1 እና በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/149(1) ጠቅሶ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተሰኘበት አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 3(1) እና 58(1) የጥፋት ድርጊቱ በ3 ዓመት ከ7 ወር ፅኑ አስራት እና በ100,00 ብር እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ የሚያስቀርብ በቂ ምክንያት የለም ሲል በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/195 መሰረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች በቀን ሰኔ 2 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ ጥፋተኛ የተባልኩበት ድንጋጌ የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 58(1) ሲሆን ይህ ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ አስራት ነው፤ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ-ስርዓት የመጀመሪያ ሰንጠረዥን ለማሻሻል የወጣው ማስታወቂያ ቁጥር 17/1967 በሌሎች ህጎች ስለተወሰኑ ቅጣቶች በሚለው እርእስት ስር ከአስር ዓመት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ ጉዳዮችን በተመለከተ አይቶ ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን በግልፅ ስለሚያስቀምጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህን ተላልፎ ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2/4/ረ መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረው የሰጠው ፍርድ ነው በማለት ውሳኔውን መሻር ሲገባው ይግባኙን መሰረዙ የህግ ስህተት ነው፤ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር ሲል አመልክቷል፡፡

የሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በሀምሌ 25 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ላይ የቀረበው የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 3(1) እና 58(1) ከሚያስቀጣው የቅጣት መጠን አንፃር ጉዳዩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየቱ ከወንጀል ስነ-ስርዓት ማሻሻያ ህግ ቁጥር 17/1967 አንፃር ፍርድ ቤቱ ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ ለማጣራት በሚል ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ አዟል፡፡

ተጠሪ በ18/12/2015ዓ.ም በሰጠው መልስ የወንጀል ስነስርዓት ማሻሻያ ህግ ቁጥር 17/1967 በቁጥር ደረጃ ወይም በደፈናው ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጡ የወንጀል ድርጊቶች ተፈፅመው ሲገኙ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሚቀርቡ የደነገገ ሲሆን ይህን ያሻሻለ በሚመስል መልኩ በ1985 ዓ.ም የወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1985 በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶችን በተመለከተ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ሰጥቷል፤ የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው ከ30/4/2004 እስከ 19/01/2008ዓ.ም በነበረው ጊዜ ውስጥ ሲሆን ይህም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከመውጣቱ በፊት ነው፤አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 4 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮችን የሚለይ እንጂ ለመጀመሪያ ደረጃ እና ለከፍተኛ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከመለየት አንፃር ግልፅነት የሚጎድለው ሲሆን በአንቀፅ 15(1) ስር የፌዴራል

መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወንጀል ስልጣንን ሲደነግግ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 3 እና 4 ስር የተመለከቱና አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የማይቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች በማለት ተደንግጎ ይገኛል፤ አንዳንድ ልዩ ህጎች የወንጀል ድንጋጌ ሲኖራቸዉ ክሱ ለየትኛው ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት የሚያመለክት ድንጋጌ አካተዉ ስለሚይዙ አዋጁ ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ያስገነዝባል፤አዋጁ ቁጥር 1234/2013 በአንቀፅ 11 ስር በፌዴራል መንግስቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን መሆኑን እንጂ በየትኛው የፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን እንደሚታይ የለየ ካለመሆኑ አንፃር ክሱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መቅረቡ የአመልካችን የይግባኝ መብት የሚያሰፋ እንጂ መብቱን የሚያጣብብ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ሲል ተከራክሯል ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤ ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉ የዚህ ሰበር ችሎት ዉሳኔ የሚሻዉ ጭብጥ በዚህ ጉዳይ ላይ ቀጥታ ክስ ተቀብሎ ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሰረቱ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን(judicial jurisdiction)፣ የስረነገር የዳኝነት ስልጣን (material jurisdiction) እና የግዛት ወይም ከባቢያዊ ዳኝነት ስልጣን(local or territorial jurisdiction) በሚል የተከፋፈለ ነዉ፡፡ ከዚህም ባሻገር የመንግስት አወቃቀር ስርዓት ተከትሎም የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል ሊደረግ ይችላል፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ አከራካሪ የሆነዉ የባንክ ስራ አዋጅ በመተላለፍ የተፈጸመ ወንጀል ላይ ከፌዴራል ፍርድ ቤት አደረጃጀት አኳያ የስረ ነገር ስልጣን ያለዉ ማነዉ? የሚለዉ ነዉ፡፡ወንጀል ጉዳይ ሲሆን ደግሞ በወንጀሉ ክብደት/ዓይነት ወይም በቅጣት መጠን ለይቶ መዘርዘር የተለመደ አስራር ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ በ1949ዓ.ም የወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አባሪ አንደኛ ሰንጠረዥ ከነማሻሻያዉ እንደተመለከተዉ የወንጀል ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ እና የይግባኝ ስረነገር የዳኝነት ስልጣን የሚወሰነዉ በአብዛኛዉ የወንጀሉን ዓይነት እና በወንጀሉ ክብደት ወይም የቅጣት መጠን ላይ በመመስረት እንዲሁም እንደወንጀሉ ዓይነት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 11 እስከ 22 የተደነገገዉን በመከተል ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ክስ የቀረበዉ የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 3(1) እና 58(1) መሰረት ተደርጎ ነዉ፡፡ይህ አዋጅ የባንክ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ እና የቁጥጥር ስርዓት በመዘረጋት የባንክ ስራ በተገቢዉ ስርዓት እንዲመራ ለማስቻል የወጣ አዋጅ ስለመሆኑ ከአዋጁ መግቢያ መገንዘብ ይቻላል፡፡አዋጁ የባንክ ስራ ጋር በተያያዘ የተከለከሉ ድርጊቶችን እና የወንጀል ቅጣቱንም ደንግጓል፡፡(የአዋጁን አንቀጽ 58 ይመለከታል)፡፡ ይሁንና ከዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ልዩ ህጎች በተለመደዉ ዓይነት የባንክ ስራ ፈቃድ አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለማየት የስረነገር የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ የፌዴራል ፍርድ ቤት ማን እንደሆነ አዋጁ በግልጽ ለይቶ አላስቀመጠም፡፡ ከዚህም የተነሳ የስረነገር ዳኝነት ስልጣን ለመለየት ሌሎች ተዛማጅ ህጎችን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የፌደራል መንግስት የገንዘብ ጥቅሞች ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ሲሰራበት የነበረዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን ዉስጥ ተካቶ እናገኛለን፡፡ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ (4) ይመለከቷል፡፡በርግጥ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 ላይ የባንክ ስራ አዋጅ በሚል ቃል በቃል ባይገለጽም በፌዴራል መንግስቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎች፤ በጠቅላላዉ ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ለማየት የስረነገር የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ከአዋጅ አንቀጽ(4) እና 15(1)ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 እስከተተካበት ጊዜ ድረስ የባንክ ስራ አዋጅ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የስረነገር

የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደሆነና በተግባርም ሲሰራበት እንደነበር ይታወቃል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ከ30/04/2004ዓ.ም እስከ 19/01/2008ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ዉስጥ እንደሆነ በአቃቤ ህግ ክስ ላይ የተገለጸ ሲሆን ክሱ የቀረበዉ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ በቀን 19/01/2014ዓ.ም ስለሆነ የዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘ ምላሽ የምናገኘዉ በዚሁ አዋጅ በተደነገገዉ አግባብ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ይዞ ከመጣዉ አዲስ ነገር አንዱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረነገር የዳኝነት ስልጣን ላይ በርካታ ለዉጦች ማድረጉ ነዉ፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ ከቀደመዉ አዋጅ ቁጥር 25/88 ጋር ሲነጻጸር በርካታ አዳዲስ ጉዳዮች የተጨመሩ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 ይዘት በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መካከል የስረነገር የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል የተደረገበት አግባብ ሲታይ እንደቀደመዉ (አዋጅ ቁ/25/88 ይመለከታል) በጉዳዮቹ ዓይነት በዝርዝር ከማስቀመጥ ይልቅ በጥቅል አገላለጽ ማስቀመጡን ያሳያል፡፡አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 12 እና 15 ን ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12 እና 15 ድንጋጌ በንጽጽር ማየት ይቻላል፡፡

አሁን በእጃችን ባለዉ ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን የማነዉ የሚለዉን ጥያቄ አስመልክቶ ግራቀኙ ያቀረቧቸዉ ክርክሮችም ሲታዩ አቃቤ ህግ አጠናክሮ የተከራከረዉ ህጉ ግልጽ ባይሆንም የቀደመዉ አዋጅ ቁ/25/88 እና የተለመደዉ አሰራር እንዲቀጥል ማድረግ ለተከሳሹ የይግባኝ እድል ያሰፋለታል እንጂ የሚጎዳዉ አይደለም የሚል ሲሆን በአመልካች ጠበቃ በኩል የቀረበዉ ክርክር ደግሞ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ወደ ቀደሞ ስነስርዓት ህግ የሚያመላክት ስለሆነ ስልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ ተብሎ መተርጎም አለበት የሚል ነዉ፡፡ይህም አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12(1) እና 15(1) አቀራረጽ ግልጽነት የጎደለዉ እና ክርክር የሚጋብዝ መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለሆነም አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12 እና 15 ድንጋጌ አቀራረጽ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 ጋር ሲነጻጸር የኋላኛዉ አዋጅ ጉዳዮችን በዝርዝር እና/ወይም በዓይነት ባለመለየቱ ነገሩን ለመረዳት ሌሎች የስነስርዓት ህጎችን መመርመር የሚያስገድድ ነዉ፡፡ በዚህ ልክ ህጉ ግልጽነት የጎደለዉ ነዉ ካልን የህጉ አቀራረጽና እና ሃይለቃል በመመርመር መፍትሔ መስጠት ተገቢ ነዉ፡፡ ለዚህ ዓላማ ሲባል የድንጋጌዎችን ይዘት ቃል በቃል መጥቀስ አስፈላጊ ነዉ፡፡ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12 እና 15 ሃይለቃል እንደሚከተለዉ ይነባበል፡፡

አንቀጽ 12(1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል የዳኝነት ስልጣን የሚደነግግ ሲሆን ንኡስ አንቀጽ አንድ ሲነበብ "በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 4 ላይ የተመለከቱና አግባብነት ባላቸዉ ህጎች መሰረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡ የፌደራል ወንጀል ጉዳዮች" ይላል፡፡

የዚህን ድንጋጌ ይዘት ለመገንዘብ ቢያንስ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን ለያይቶ ማየት ያስፈልጋል፡፡አንደኛዉ በአዋጁ አንቀጽ 3 እና 4 መሰረት ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች ምንድናቸዉ የሚለዉን የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛዉ ከእነዚህ ወንጀሎች ዉስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ስረነገር ስልጣን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሆነዉን መለየት ይጠይቃል፡፡ በዚህ አግባብ ሁለቱን መስፈርት ያሟላ መሆኑ የተረጋገጠ ወንጀል ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ ስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ ተብሎ ይወሰዳል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወንጀል የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ በአዋጁ ላይ የተደነገገበትን አግባብ ማየት ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፡፡የአዋጁን አንቀጽ 15 ድንጋጌ ይዘት ስንመለከት፤ "በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል" ካለ በኋላ በንኡስ አንቀጽ አንድ ስር "በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 4 ስር የተመለከቱና አግባብነት ባላቸዉ ህጎች መሰረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የማይቀርቡ የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች" ን ይመለከታል ይላል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በወንጀል ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ስረነገር ስልጣን የሚኖረዉ ወንጀሉ የፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን ነዉ ተብሎ ከተዘረዘሩት ወንጀሎች ዉስጥ የተካተተ እንደሆነ እና በጉዳዩ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ስልጣን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ በሌላ አገላለጽ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል በተመለከተ በሌላ ህግ በግልጽ ተለይቶ ካልተደነገገ በስተቀር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን የሚኖረዉ ወንጀሉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስረነገር ስልጣን ስር የማይወድቅ መሆኑ ከተረጋገጠ ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር የቀረበዉን ጉዳይ ስንመለከት ወንጀሉ የብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳይኖረዉ ገንዘብ በማስተላለፍ ሀገር ታገኝ የነበረዉን ብር 156,408.28 ዶላር በማሳጣት ጉዳት አድርሷል ተብሎ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 3(1) እና 58(1) ተጠቀሶ የቀረበ ነዉ፡፡ተጠቃሹ አዋጅ የፌዴራል መንግስት አዋጅ በመሆኑ እና ድርጊቱም በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል ተብሎ የሚወሰድ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3 እና 4(4) መሰረት ወንጀሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በመቀጠል በዚህ ጉዳይ ከሁለቱ ፍርድ ቤቶች ዉስጥ የመጀመሪያ ደረጃ የስረነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ ማነዉ? የሚለዉን እንመለከታለን፡፡ከላይ እንደተገለጸዉ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጠን በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12 (1) ስር የተገለጸዉ ሁለተኛዉ መመዘኛ ሲሆን ይኸዉም አግባብነት ባላቸዉ ህጎች መሰረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ…" መሆን አለመሆኑን በመለየት ነዉ፡፡ (ሰረዝ የተጨመረበት)፡፡

እንደሚታወቀዉ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ከጸደቀበት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ሀገሪቱ በፌዴራል ስርዐተ መንግስት የምትተዳደር ከመሆኑ አኳያ በአሃዳዊዉ ስርዓት ወጥተዉ ስራ ላይ የነበሩ መሰረታዊ ህጎች ዙሪያ ማሻሻያ ተድርጎበታል፡፡እንዲሁም ዋናዎቹ የስነስርዓት ህጎች ተብለዉ የሚታወቁት የ1958"ቱ የፍትሐብሔር ስነስርዓት ህግ እና የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ህግ ላይ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ማሻሻያዎች የተደረጉ ቢሆንም መሰረታዊ የሚባል ለዉጥ ሳይደረግ እየተሰራበት ነዉ፡፡ከዚህ አንጻር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88"ም ሆነ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በተመሳሳይ አንቀጽና አገላለፅ በስራ ላይ ያሉ የወንጀል እና የፍትሓብሔር ስነስርዓት ህጎች ከአዋጁ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በአዋጁ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንዳላቸዉ መደንገጉ ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡(አዋጅ ቁጥር 25/88 እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 7 ይመለከታል)፡፡

ስለዚህም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ በግልጽ ያልተሸፈነ ጉዳይ ሲያጋጥም ወይም የአዋጁ ድንጋጌ አሻሚ ሲሆን በስራ ላይ ያሉትን ሌሎች የስነ ስርዓት ህጎች ተከትሎ እልባት መስጠት የሚያስችል የህግ መሰረት መኖሩን ያሣያል፡፡ይህንኑ መሰረት አድርገን ስራ ላይ ባለዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት (አዋጅ ቁጥር 1/1954 ይመለከታል) ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ የወንጀል የስረነገር የዳኝነት ስልጣን ስንመለከት በስነስርዓት ህጉ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል የተደረገዉ በጉዳዩ ዓነይነት ወይም በቅጣት መጠን መሆኑን የስነስርዓት ህጉ አባሪ አንደኛ ሰንጠረዥ ይዘት ያሣያል፡፡ይህ ሰንጠረዥ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 የተሻሻለ ሲሆን በተሻሻለዉ ሰንጠረዥ እንደተመለከተዉ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ የተደነገጉት ወንጀሎች ላይ የፍርድ ቤቶች ስልጣን ክፍፍል የተደረገዉ በወንጀሎቹ አይነት ሲሆን በሌሎች ህጎች ያሉ ወንጀሎች ግን የቅጣቱን መጠን መሰረት በማድረግ የሚለይ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ሰንጠረዡ ላይ እንደተገለጸዉ ቅጣቱ ከአስር ዓመት የሚበልጥ ከሆነ ስረነገር የዳኝነት ስልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በዚህ ጉዳይ ክስ የቀረበበት የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 3(1) በመተላለፍ ያለ ፈቃድ የባንክ ስራ ሰርቷል ተብሎ ነዉ፡፡ድንጋጌዉ እንደሚያመለክተዉ በብሔራዊ ባንክ የተሰጠ የባንክ ስራ ፈቃድ ካልተያዘ በስተቀር የባንክ ስራ ማካሄድ ክልክል መሆኑን እና ቅጣቱም መቀጮ እና ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደረስ ጽኑ እስራት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ስለሆነም ቅጣቱ

ከአስር ዓመት በላይ እንደመሆኑ ከቅጣቱ መጠን አንጻር ሲታይ የስረነገር የዳኝነት ስልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ይህ ከሆነ የስረነገር የዳኝነት ስልጣኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ ወይስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ነዉ የሚለዉን ጥያቄ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12(1) እና የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 ሰንጠረዥ በጣምራ ስንመለከት የስረነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አለመሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረነገር ስልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩ ላይ አከራካሮ የተሰጠዉ ዉሳኔ ከስልጣኑ ዉጪ ስለሆነ ሊታም የሚገባ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1ኛ በዚህ ጉዳይ የስረነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/296508 ላይ በቀን 05/2015ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 011774 ላይ በቀን 21/09/2015ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ9(1) መሰረት በአብላጫ ተሽሯል፡፡

2ኛ/በዚህ ጉዳይ የስረነገር ዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ ብለናል፡፡

3ኛ/በዚህ ጉዳይ አቃቤ ህግ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ መብቱን ይህ ዉሳኔ አያግድም ብለናል፡፡ይጻፍ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>የልዩነት ሀሳብ</u>

በተራ ቁጥር 4 ላይ የተሰየምኩት ዳኛ በአብላጫ ድምጽ በአመልካች ላይ የቀረበዉን የወንጀል ክስ የመዳኘነት ሥልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ ተብሎ በመወሰኑ ስላልተስማማሁ የሚከተሉትን ምክንያቶች መሰረት በማድረግ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬያለሁ፡፡

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና ይህንን አዋጅ በተካዉ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 ላይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ የወንጀል ጉዳዮች ተዘርዝረዉ ተደንግገዋል፡፡ አመልካች የተከሰሰዉ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 3/1 እና 58/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ የባንክ ሥራን ለመሥራት ፈቃድ ሳይኖረው በሳውድ አረቢያ የሚኖሩ ግለሰቦች ለቤተሰቦቻቸው ወደ ኢትዮጵያ የሚልኩትን ገንዘብ በመቀበል በክሱ ላይ በዝርዝር በተገለጸዉ መሠረት አራት መቶ የሐዋላ መልዕክት በመላክ በአጠቃላይ 2,990,526.30 በማስተላለፍ ይህ ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ተልኮ ቢሆን ኖሮ ሀገሪቱ ታገኝ የነበረውን 156,408.28 የአሜሪካ ዶላር እንድታጣ ያደረገ በመሆኑ ያለብሄራዊ ባንክ ፈቃድ የባንክ ሥራ መሥራት ወንጀል ፈጽሟል በሚል ነዉ፡፡ እንዲህ አይነት ወንጀል በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ እንደተፈጸመ ወንጀል የሚቆጠር መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ይህንን ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን በቀድሞዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4/4 እና ይህንን አዋጅ በተካዉ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4/11 ስር እንደተመለከተዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነዉ፡፡አከራካሪዉ ጉዳይ በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብና የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ እንደተፈጸመ የሚቆጠረዉን አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እንዲዳኝ ሥልጣን የተሰጠዉ ለየትኛዉ የፌዴራል ፍርድ ቤት ነዉ የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ ለፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በተለይም የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የሚሠጠዉ በሕግ ነዉ፡፡ስለሆነም ለአከራካሪዉ ጭብጥ ተገቢዉን ዉሳኔ መስጠት ይቻል ዘንድ ተፈጻሚ እየሆኑ

ያሉትንና ቀደምት ሕግጋትን በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል፡፡በቀድሞዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4/4 እና አንቀጽ 15/1 ስር በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህ አዋጅ በመጀመሪያ በአዋጅ ቁጥር 138/1991 ቀጥሎም በአዋጅ ቁጥር 321/1995 ተሻሽሏል፡፡ ነገር ግን በእነዚህ የማሻሻያ አዋጆች በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 15/1 ላይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል እንዲዳኝ የተሰጠዉ የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ጸንቶ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 321/1995 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 12 እና 15 ስር የተደነገገዉን አጣምረን ስናነብ በሥራ ላይ ባለዉ የወንጀለኛ መቀጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አባሪ አንደኛ ሰንጠረዥ እና ይህንን ሰንጠረዥ ለማሻሻል በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 ላይ ከዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ጋር በተያያዘ የተደነገገዉ ቢኖርም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 4/4 ላይ የተመለከተዉን በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል እንዲዳኝ ሥልጣን አልተሰጠዉም፡፡በሌላ አገላለጽ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4/4 ስር በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል በሚል የተመለከተዉ የሚያስቀጣዉ ቅጣት ምንም ይሁን ምን የወንጀለኛ መቀጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አባሪ አንደኛ ሰንጠረዥ እና ይህንን ሰንጠረዥ ለማሻሻል በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 በተደነገገዉ የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ሳይወሰን ወይም ደግሞ ይህ ወንጀል በሚያስቀጣዉ የእስራት ቅጣት መጠን ሳይገደብ ወንጀሉን እንዲዳኝ ሥልጣን የተሰጠዉ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡(የአዋጅ ቁጥር 25/1988(በአዋጅ ቁጥር 321/1995 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 15/1 ይመለከቷል፡፡)

በወንጀለኛ መቀጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አባሪ በሆነዉ አንደኛ ሰንጠረዥ ላይ የተመለከተዉን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ለማሻሻል በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 ላይ ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጣ ወንጀል ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ነዉ፡፡ ነገር ግን ከደንብ ቁጥር 17/1967 በኋላ በወጣዉ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 321/1995 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 4/4 እና አንቀጽ 15/1 ስር በተደነገገዉ መሠረት በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጣ ቢሆን እንኳን ይህንን ወንጀል የመዳኘት ሥልጣኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ በደንብ ቁጥር 17/1967 ላይ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ በመንግሥት የገንዘብና ኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የተፈጸመ ወንጀል በሚመለከት የሚቀርብ ክስ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ይዳኛል በሚል የተመለከተዉ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 321/1995 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 4/4 እና አንቀጽ 15/1 ላይ በተደነገገዉ መሠረት በስዉር ተሽሯል (implicitly repealed) ብዬ አምናለሁ፡፡በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 25/1988 (ከእነማሻሻያዎቹ) ተፈጻሚ ሲሆን በነበረበት ጊዜ በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እንዲዳኝ በግልጽ ሥልጣን የተሰጠዉ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡

የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን በአብዛኛዉ የሚወሰነዉ በሥነ ሥርዓት ሕግ በመሆኑ አንድን የወንጀል ክስ ለመዳኘት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ያለዉ ፍርድ ቤት የትኛዉ ነዉ የሚለዉ በመርህ ደረጃ ሊወሰን የሚገባዉ ክሱ ወደ ፍርድ ቤት በቀረበበት ጊዜ በሥራ ላይ በሚገኝ የሥነ ሥርዓት ሕግ እና/ወይም ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌ በያዘ የፍርድ ቤቶች አዋጅ እና በሌላ ልዩ ሕግ ነዉ፡፡ አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ተፈጸመ የተባለዉ ከቀን 30/04/2004ዓ.ም እስከ ቀን 19/01/2008ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ቢሆንም ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ የመሠረተዉን ክስ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በቀን 19/01/2014 ዓ.ም

ነዉ፡፡በመሆኑም ክሱ በቀረበበት ጊዜ ተፈጻሚ መሆን ያለበት አዋጅ ቁጥር 1234/2013 እንደሆነ ከዚሁ አዋጅ አንቀጽ 58 መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ክሱን እንዲዳኝ ሥልጣን የተሰጠዉ ለትኛዉ ፍርድ ቤት ነዉ የሚለዉ ሲወሰን ከላይ ስለአዋጅ ቁጥር 25/1988 (ማሻሻያ አዋጆችን ጨምሮ) የተገለጸዉ ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ (ማሻሻየውን ጨምሮ) ስለዳኝነት ሥልጣን የተደነገገዉን እና በወንጀል ሕግ የተያዘዉ ወንጀል ስለሚያስቀጣዉ ቅጣት መጠን የተደነገገዉን ከግምት በገባ አኳኋን ሊመረመር ይገባል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 321/1995 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 4/4 እና አንቀጽ 15/1 ስር የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅም ላይ ስለሚፈጸም ወንጀል የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን በግልጽ ስለተደነገገ የድንጋጌዎቹን ይዘት እዚህ ላይ ማስፈር አስፈላጊ አይደለም፡፡ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12/1 እና 15/1 ስር ስለ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ የመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የተደነገገዉን መመልከት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12/1 ስር ፡- “ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡- 1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 4 ላይ የተመለከቱና አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡ በፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፤” በሚል ተደንግጓል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 15/1 ላይ ደግሞ ፡-

“ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡- 1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 4 ላይ የተመለከቱና አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የማይቀርቡ በፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች፤“ በሚል ተደንግጓል፡፡

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 ላይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ የወንጀል ጉዳዮች ተዘርዝረዉ ከመደንገጋቸዉ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የሚዳኛቸዉ የወንጀል ጉዳዮች ተዝርዝሮ አልተደነገገም፡፡ እንዲሁም በእነዚህ አዋጆች አንቀጽ 3 እና 4 ስር ስለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወል ዳኝነት ሥልጣን ከመደንገጉ በስተቀር በተለይ ስለፌዴራል ከፍተኛም ሆነ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የተደነገገ ነገር የለም፡፡በዚህ መልኩ በአንቀጽ 3 እና 4 ላይ የሁለቱም ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃም ሆነ የይግባኝ የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ተለይቶ ካልተደነገገ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12/1 እና 15/1 ስር *“...በአንቀጽ 3 እና 4 ላይ የተመለከቱ...”* የሚለዉ አገላለጽ እነዚህ ፍርድ ቤቶች የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ናቸዉ ተብለዉ በተለዩ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሥልጣን እንዳላቸዉ ለማመላከት የገባ አገላለጽ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ይህ ሐረግ በእነዚሁ አናቅጽ *“...አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጡ...”* ከሚለዉ ሐረግ ጋር በአንድነት ሊታይ ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት ሲታይ *“አግባብነት ያላቸዉ ሌሎች ሕጎች”* በሚል ከተገለጹ ሕግጋት ማዕቀፍ ዉስጥ ሊታቀፍ የሚችለዉ ደግሞ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1/1954 እና በዚህ አዋጅ አባሪ የሆነዉን አንደኛ ሠንጠረዥ ለማሻሻል የወጣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 እና ሌሎች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የሚሰጡ ልዩ ልዩ ሕግጋት እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 364(1/መ) እና ከፍ ያለ ግምት ባለዉ ገንዘብ ላይ የተፈጸመ ወንጀል በሆነ ጊዜ አንቀጽ 365 ስር እንደተደነገገዉ የባንክ ሥራ ደንብና ትዕዛዝ በመተላለፍ ወንጀል ሲፈጸም በልዩ ሕግ ከፍ ያለ ቅጣት ከተደነገገ በልዩ ሕግ የተደነገገዉ ተፈጻሚ መሆኑ እንደተጠበቀ

ሆኖ በቀላል እስራት ወይም እስከ አምስት አመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ የዳኝነት ሥልጣን በወ/መ/ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንደኛ አባሪ ሠንጠረዥ መሠረት ለአዉራጅ ፍርድ ቤት የተሰጠ ነዉ። እንዲሁም አሁን ሥራ ላይ ባለዉ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1/ረ) ስር በተመሳሳይ የባንክ አሠራርና ቁጥጥር አስመልክቶ የወጡ ድንጋጌዎችን አስቦ መጣስ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ የሚያስቀጣ ሲሆን ነገሩን የሚያከብዱ ሁኔታዎች ለአብነት ከፍ ያለግምት ባለዉ ገንዘብ ላይ የተፈጸመ ወንጀል ሲሆን ወይም ደግሞ ወንጀለኛዉ ...ያለተገባ ትርፍ ለማግኘት... የማስተላለፍና በሕግ የተከለከለ ነገር መሥራትን የዘወትር የሞያ ሥራዉ በማድረግ የተፈጸመ እንደሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 354/1 መሠረት በመቀጮ እና ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ያስቀጣል፡፡በዚህ መሠረት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 353(1/ረ) ላይ የተደነገገዉ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አባሪ ሠንጠረዥ አንድ መሠረት በአዉራጃ ፍርድ ቤት የሚታይ ሲሆን ይህም የፌደራል ሥርዓቱን ተከትሎ በተፈጠረዉ የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን ይሆናል፡፡ በወንጀለኛ ሕግ አንቀጽ 354/1 የተደነገገዉ ወንጀል ደግሞ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 መሠረት በከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚዳኝ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም አመልካች የተከሰሰበት ስለባንክ ሥራ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 58/1 በድንጋጌዉ ላይ በተመለከተዉ የገንዘብ መቀጮ እና ከ19 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጸኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 አንጻር ብቻ ከታየ (ሠረዝ የተጨመረበት) በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የመዳኘት ስረ ነገር ሥልጣን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡

በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12/1 እና 15/1 ስር የተደነገገዉ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 ጋር በአንድነት ሲታይ አመልካች በተከሰሰበት አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 58/1 ስር የተደነገገዉ ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ይህንን ወንጀል አስምልክቶ የቀረበዉን ክስ የመዳኘት ሥልጣን በማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል ወደሚል ድምዳሜ መድረስ ይቻላል፡፡ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸዉ አዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 321/1995 እንደተሻሻለዉ) ተግባራዊ ሲሆን በነበረበት ጊዜ ይህንን ወንጀል የሚመለከት ክስ በአዋጁ አንቀጽ 4/4 እና 15/1 መሠረት ሲዳኝ የነበረዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በሌላ በኩል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 364(1/መ)ም ሆነ በአንቀጽ 365፤በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 353(1/ረ) እና አንቀጽ 354/1 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 58/1 ስር የተደነገገዉ ወንጀል በፌዴራል መንግሥቱ የገንዘብና የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ እንደተፈጸመ የሚቆጠር ወንጀል እንደመሆኑ የመዳኘት ስረ ነገር ሥልጣን በወ/መ/ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ እና በማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 አንጻር ሲታይ ለአዉራጃ ፍርድ ቤት እና ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ቢሆንም ከእነዚህ የሥነ ሥርዓት ሕግጋት በኋላ የወጣዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 321/1995 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 15/1 ላይ በተጠቃሾቹ የሥነ ሥርዓት ሕግጋት ላይ የተደነገገዉን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል በመተዉ ወይም ደግሞ በተጠቃሾቹ የሥነ ሥርዓት ሕግጋት ላይ ይህ ወንጀል የሚያስቀጣዉን የእስራት ቅጣት መጠን መሠረት ተደርጎ በተሰጠዉ የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ሳይገደብ ወንጀሉን የመዳኘት ሥልጣን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲሆን ደንግጓል፡፡በዚህ መልኩ በመንግሥት የገንዘብና የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የሚፈጸም ወንጀል አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ የመዳኘት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 321/1995 እንደተሻሻለዉ) ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሰጥ በተጠቃሾቹ ነባር የሥነ ሥርዓት ሕግጋት ላይ ከዚህ ጋር ወንጀል ጋር በተያያዘ የተደነገገዉ ተሽሯል ብዬ አምናለሁ፡፡

በአሁን ጊዜ ሥራ ላይ ባለዉ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 57/1 ላይ እንደተመለከተዉ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ከነማሻሻያዎቹ መሻሩ በግልጽ ተመልክቷል፡፡በዚህ መልኩ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ከእነማሻሻዎቹ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሻሩ በተለየ አኳኋን በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 25/1988 በተለይም ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉን የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደተሰጠ በመቁጠር ለሕጉ ትርጓሜ መስጠት አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ሲወጣ ታሳቢ የተደረጉትን የፖሊሲ ምክንያቶች እና የሕጉን ዓላማዎች ከግምት አለማስገባት ይሆናል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ለማሳካት ከሚፈለጉ ዓላማዎች መካከል አንዱ የዳኝነት አገልግሎት አሠጣጡን ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ሲሆን ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከተወሰዱ እርምጃዎች ዉስጥ አንዱ ቀደም ሲል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ሲዳኙ ከነበሩ ጉዳዮች ቀንሶ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲዳኙ በሚያደርግ አኳኋን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ማድረግ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ያለዉ የአደረጃጀት ተደራሽነትም ሲታይ ከክልሎች የዉክልና ሥልጣን አንጻር ጭምር ሲታይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአንጻራዊነት ለሕብረተሰቡ የበለጠ ቅርብ በሆነ ስፍራ የሚገኝ ነዉ፡፡እንዲሁም በመንግሥት የገንዘብና የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የሚፈጸም ወንጀል ለመዳኘት የሚችል ብቃት ያላቸዉን ዳኞች ከመያዝ አንጻር ሲታይም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 321/1995 ሥራ ላይ ሲዉል በነበረበት ጊዜ ከነበረዉ አሁን እጅግ በጣም የተሻለ የትምህርትና የሥራ ልምድ ዝግጅት ያላቸዉ ዳኞች እንዳሉት ከዳኝነት አስተዉሎት መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶችና ከሕጉ ዓላማ አንጻር ሲታይ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉ የስረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ተቀንሶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሰጥ የሚያደርግ አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ ላይ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 12(1) እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 ሰንጠረዥ ላይ የተደነገገዉን ብቻ በማየት ክሱን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ ሲል የተደረሰበት ድምዳሜ በመንግሥት የገንዘብና የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የሚፈጸም ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን በተመለከተ በደንብ ቁጥር 17/1967 ሰንጠረዥ ላይ የተደነገገዉ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 321/1995 ተሸሮ ያደረ መሆኑን እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ለማሳካት ያለመዉን ዓላማ እና ከሥልጣን ክፍፍል አንጻር ይህ አዋጅ የያዘዉን አቋም ያላገናዘበ ነዉ ብዬ አምናለሁ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትን ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን የለዉም ተብሎ የቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ክፍል ዉድቅ መደረግ ነበረበት በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## 2. የወንጀል ድርጊትን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች

### 2.1 ሕጋዊ ፍሬነገር እና የአሳብ ክፍል[7]

- ሕጋዊ ፍሬነገር የሚባለዉ አንድን ድርጊት ሕገ-ወጥነትና አስቀጭነት ወንጀል ስለመሆኑ በህግ በግልጽ ተደንግጎ መገኘት ያለበት ስለመሆኑ፣ግዙፋዊ የሚባለዉ በህጉ የተደነገገዉ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ድርጊት ማለት በህግ የተከለከለዉን ማድረግ ወይም በህግ የታዘዘዉን አለማድረግ /አል-ድርጊት/ ፍሬነገሮች መፈጸማቸዉና የተፈጸሙትም በተከሳሹ ስለመሆኑ

[7]የሰ/መ/ቁጥር 181206 (መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25

መረጋገጥ እና የሞራል /ሀሳብ/ ክፍል የሚባለዉ ተከሳሹ ድርጊቱን አስቦ ወይም በቸልተኛነት የፈጸመ መሆኑ የማረጋገጥ ጉዳይ የሚመለከት ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 2፣ 23/1/ እና 57/1/ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሥገነዝቡን ጉዳይ ነዉ፡፡

- የወንጀል ሕጋችንም በአንቀፅ 27(1) “ማንም ሰው አስቦ…” የሚለውን ሃረግ በማካተት መቀረፁ ድርጊቱ በአውቆ አጥፊነት የተጀመረ መሆኑ መረጋገጡ መሰረታዊ መስፈርት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች የተከሰሱበት ድርጊት በቸልተኝነት የተፈፀመ የሙከራ ድርጊት መሆኑ ከተረጋገጠ በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መስጠት መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡[8]

የሰ/መ/ቁጥር 181206

መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መሳከ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ሐይሉ(አብይ) ሲሳይ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሀምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች የመግደል ሙከራ ሳልፈፅም እንደፈፀምኩ ተደርጎ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

አመልካች በስር የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስም ተከሳሽ የወንጀል ህግ አንቀፅ 27(1) እና 540 በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ በሰንዳፋ በኬ 02 ቀበሌ ውስጥ አለማየሁ ሙላቱ የተባለውን የግል ተበዳይ በሽጉጥ ተኩሶበት ሆዱ ላይ በመምታት ጉዳት አድርሶበት ህክምና በማግኘቱ ምክንያት ህይወቱ ሊተርፍ ችሏል በዚህም የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈፅሟል በማለት ከሷል፡፡ አመልካች ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ስለተከራከሩ የአቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው የተሰሙ ሲሆን 1ኛ ምስክር አመልካች ወደ ሱቃቸው መጥተው ሲጋራ እንዲሸጡላቸው አዘዋቸው ዞር ሲሉ ሽጉጥ ያልያዙ ቢሆንም ሲጋራውን ይዘው ዞር ሲሉ የተኩስ ድምፅ የሰሙ መሆኑን ሆዳቸውን በግራ በኩል ተመትተው ሲወድቁ አመልካች

---

[8]በሰ/መ/ቁ. 235233 (ጥቅምት 26 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 226641 (የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ 267231 (ጥር 30 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣267230 (ጥር 30 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 91535 (የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ 203746 (መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅፅ 26 ፣ በሰ/መ/ቁ 212243 (ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 251700 (ጥር 26 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 46382 (ነሃሴ 28/2001ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ የሰ/መ/ቁ. 23855 (ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7 ፣ የሰ/መ/ቁ 22069 (ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7፣ የሰ/መ/ቁ 22452 (ሐምሌ 30 ቀን 2000ዓ.ም) ቅፅ 7

መታሁክ ብለው ጥለዋቸው የሄዱ መሆኑን ያስረዱ ሲሆን 2ኛ ምስክርም ድምጽ ሰምተው ጎሚስታ ቤታቸው ፊት ለፊት ስላለ የጎማ ድምፅ መስሏቸው ሲወጡ አመልካች ሲሮጡ የተመለከቱ መሆኑን የግል ተበዳይ ውጪ ወጥተው የነበሩ ቢሆንም መሮጥ ያልቻሉ መሆኑን ምን ሆንክ ሲሉት አመልካች በሽጉጥ መታኝ ብለው የሆዳቸውን ግራ ጎን አሳይተዋቸው መቆም አቅቷቸው የወደቁ መሆኑን ስላስረዱ አመልካች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቷል፡፡

አመልካች በሰጡት የተከሳሽነት ቃልም ከግል ተበዳይ ጋር ፀብ የሌላቸው መሆኑን በተለመደ ሁኔታ ወደ ሱቃቸው በመሄድ ሲጋራ፤ውሃ የመሳሰሉትን ገዝተው የሚያልፉና የግል ተበዳይም የሚሸጧቸው መሆኑን በእለቱም በተመሳሳይ ሊገዙ ሄደው ሽጉጣቸው በካፖርት የውጭ ኪሳቸው ስለነበረ አውጥተው ወደ ግራ ጎናቸው ሊያዛውሩ ሲሉ መሳሪያው ባርቆባቸው የግል ተበዳይን የመታ መሆኑን ተመታህ ብለው ሆዱን ይዘውልት የነበሩ ቢሆንም ቤተሰቦቹ ስለነበሩ ይገሉኛል ብለው በመፍራት ሸሽተው የሄዱ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የአመልካች ምስክርም በእለቱ ውሃ ለመግዛት ሄደው ከአመልካች ጎን ቆመው የነበረ መሆኑን አመልካች ሽጉጡን ከካፖርቱ ቀኝ ኪስ ወደ ግራ ኪስ ለማዛወር ሲል መሳሪያው ተተኩሶ ጥይቱ በኮንቴነር ውስጥ አልፎ የግል ተበዳይን የመታው መሆኑን በዚህ ጊዜ አመልካች" መታሁክ " ያሉ መሆኑን ነገር ግን ወደ ውስጥ ገብተው የግል ተበዳይን ያልያዙ መሆኑን አመልካች የግል ተበዳይን አስበውበት ያልመቱ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ከዚህ በኂላ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔም አቃቤ ህግ በምስክሩ አመልካች የግል ተበዳይን በሽጉጥ ሆዳቸውን የመቱ መሆኑን ያስረዳ መሆኑን የህክምና ማስረጃውም የግል ተበዳይ በተተኮሰባቸው ጥይት በደረሰባቸው ጉዳት ትንሹ አንጀት የተለያየ ቦታ ተበሳስቶ ፤ትልቁ አንጀት የላይኛው ክፍል ትንሹን አንጀት ሸፍኖ የሚገኘው በሆዱና በጉበት ሽፋን ላይ ሰንበር መኖሩን የሚገልፅ ሆኖ ነገር ግን አመልካችና የመከላከያ ምስክራቸው ያስመዘገቡት ሽጉጡን ያዛወሩበትን ቦታ እና ከድርጊቱ በኂላ አመልካች የግል ተበዳይን መያዝ አለመያዛቸውን አስመልክቶ እርስ በእርሱ የሚጋጭ የምስክርነት ቃል ስለሰጡ አመልካች በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ በስድስት አመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝ ተው ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልገው ይግባኙን የሰረዘው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት የሰበር አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ከግል ተበዳይ ጋር ከትውውቅ የዘለለ ፀብ ወይም ጥላቻ ሳይኖረኝ ምስክሮቹም በክሱ አግባብ ሳያስረዱ የግል ተበዳይን ልገድል የምሞክርበት ምክንያት ሳይኖር አቃቤ ህግ የወ/ህ/ቁ.540ን ጠቅሶ ከፈፀምኩት ድርጊት ጋር የማይመሳሰል ክስ ማቅረቡ አላግባብ ነው፤እንደ ድርጊቱ እና እንደ ማስረጃው ቅርበት በአንዝላልነት ወይም በግዴለሽነት ጥፋተኛ ተብዬ ልቀጣ ሲገባ በመግደል ሙከራ መቀጣቴ የወንጀል ህጉን አላማ የሳተ ነው፤የአመልካች ሽጉጥ ወንጀል የተፈፀመበት ስለሆነ ለመንግስት ገቢ ይሁን ተብሎ የታዘዘውም አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በአንዝላልነት ወይም በግዴለሽነት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ይሰጥልኝ እንዲሁም ሽጉጡ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የተሠጠው ትዕዛዝ ተነስቶ ሽጉጤ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፤

በአመልካች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከድርጊቱ አፈፃፀምና ከወንጀል ህግ አንቀፅ 23(2) አንፃር ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኂላ ተጠሪ በሰጠው መልስም የአቃቤ ህግ የሰውና የሰነድ ማስረጃ የግል ተበዳይ ሆዱ ላይ ተመትቶ ጉዳት የደረሰበት በአመልካች ሽጉጥ መሆኑን ያረጋገጡ በመሆናቸውና ይህ ፍሬ ነገር በአመልካች ያልተካደ በመሆኑ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በዚሁ አግባብ የተሰጠ በመሆኑ ሊፀና ይገባል፤አመልካች

ሽጉጡን አቀባብሎት ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር እንደነበረ በአመልካች ያልተካደ ፍሬ ጉዳይ በመሆኑ የተቀባበለ ሽጉጥ ጉዳት ቢያደርስ ውጤቱን እቀበለዋለሁ በማለት ሲንቀሳቀስ ወንጀሉ በግል ተበዳይ ላይ ስለተፈፀመ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 58(2)(ለ) በዚህ አይነት የሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ሆነ ተብሎ እንደተፈፀመ የሚደነግግ በመሆኑ የመከላከያ ምስክሩም ወንጀሉ በእንዝላልነት መፈፀሙን በማስረዳት የአቃቤ ህግን ማስረጃ ያላስተባበሉ በመሆኑ ወንጀሉ የተፈፀመበት ሽጉጥ ይመለስልኝ ማለቱ አግባብነት የሌለው በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፤ከተገቢው ህግና፤ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡አንድ የወንጀል ድርጊት ተፈፀመ የሚባለው ህጋዊ ፤ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ መሆኑ በወ/ህ/አንቀፅ 23(2) የተመለከተ በመሆኑና አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው የወ/ህ/አ.540ን ተላልፈው የመግደል ሙከራ ወንጀል መፈፀማቸውን መሰረት በማድረግ በመሆኑ ከአመልካች በተተኮሰ ጥይት የግል ተበዳይ በግራ ጎን ሆዳቸው ላይ መመታታቸውን ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ በመሆኑ ይህም የህጉ መሰረታዊ ነጥብ ማለትም ግዙፋዊ ፍሬ ነገር የተሟላ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ በአመልካች ላይ በአንቀፅ 27(1) እና 540 መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው አመልካች ድርጊቱን አስበው የፈፀሙ መሆናቸው በአቃቤ ህግ ማስረጃ ሲረጋገጥ ሊሆን ይገባል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ከላይ በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም አመልካች የወንጀል ሙከራ ድርጊቱን የፈፀሙት አስበው መሆኑን ያረጋገጠበትን የህግ አግባብ በውሳኔው ላይ አላመለከተም፡፡ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው ምላሽ ሲሰጥ የተቀባበለ ሽጉጥ ይዘው መንቀሳቀሳቸው የተቀባበለው ሽጉጥ ጉዳት ቢያደርስ ውጤቱን ተቀብለው መንቀሳቀሳቸውን ስለሚያሳይ የሃሳብ ክፍሉ በወ/ህ/አ.58(2) አግባብ የተሟላ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ አንድ የወንጀል ድርጊት ቀጥተኛ ባልሆነ አውቆ አጥፊነት ተፈፀመ የሚባለው ድርጊቱ ህገ ወጥና የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ የሆነው ይሁን ብሎ ውጤቱን በመቀበል ድርጊቱን ያከናወነ መሆኑ ሲረጋገጥ ለመሆኑ በወ/ህ/አ.58(1)(ለ) ተመልክቷል፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ አቃቤ ህግ በመልሱ ላይ አመልካች ሽጉጡ መቀባበሉን የሚያውቁ መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ቢሆንም የአመልካች ሽጉጥ ተቀባብሎ የተቀመጠው አመልካች መቀባበሉን አውቀው ይሁን በእንዝላልነት አቀባብለው በመርሳታቸው መሆኑን ለይቶ ሊያስረዳ የሚገባ ቢሆንም ይህንን ስለማድረጉ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

ሽጉጡን ከአንድ ጎናቸው ወደ ሌላው ሲያዛውሩ ሽጉጡ የተቀባበለ መሆኑን ያውቁ የነበረ መሆኑንም አላስረዳም፡፡አመልካች ሽጉጡ መቀባበሉን እያወቁ እንዳይቀባበል በማድረግ ሊያዘዋውሩ ሲገባ ተቀባብሎ እያለ በጥንቃቄ ቢዘዋወር ጉዳት አያስከትልም ቢያስከትለም የመጣው ይምጣ በማለት ውጤቱን በመቀበል ሽጉጡን ሲያንቀሳቅሱ በግል ተበዳይ ላይ ጉዳቱን ያደረሱ መሆኑን አቃቤ ህግ ባላስረዳበት ወይም ወደዚህ አይነት መደምደሚያ የሚወስድ የምስክርነት ቃል ባልተሰጠበት ከመነሻውም አመልካች ወደ ግል ተበዳይ ሱቅ ሲሄዱ የተቀባበለ ሽጉጥ የታጠቁ መሆኑን ያውቁ የነበረ መሆኑን ባላስረዳበት ድርጊቱን ቀጥተኛ ባልሆነ አውቆ አጥፊነት እንደተፈፀመ ተደርጎ በአመልካች ላይ በወ/ህ/አ.27(1) እና 540 መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(2) እና 58(1)(ለ) ን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ከዚህ ይልቅ አመልካች ሽጉጡን ከአንድ ጎናቸው ወደ ሌላው ሲያዛውሩ መቀባበል አለመቀባበሉን በማረጋገጥ ሊያዘዋውሩ ሲገባ ይህንን ሳያደርጉ ሽጉጡን ሲያንቀሳቅሱ በግል ተበዳይ ላይ ጉዳቱን

ማድረሳቸው ጉዳት ያደረሰውን ድርጊት አስመልክቶ ምንም ጥንቃቄ ወይም በቂ ጥንቃቄ አለማድረጋቸው አመልካች ድርጊቱን በቸልተኝነት የፈፀሙ መሆኑን ያሳያል፡፤

አመልካች የግል ተበዳይን በሽጉጥ የመቱት በቸልተኝነት ከሆነ ደግሞ የአመልካች ድርጊት ሞትን ያላስከተለ በሙከራ ደረጃ የቀረ በመሆኑ የግራ ቀኙ ክርክር ከወ/ህ/አንቀፅ 27(1) ሊታይና ሊመረመር ይገባል፡፡በቸልተኝነት የሚፈፀሙ ድርጊቶች እንደ ሙከራ ሊቆጠሩ ይችላሉ የሚል አስተያየት ቢኖርም አንድን የወንጀል ድርጊት ሙከራ ነው ለማለት ድርጊቱ በእውቀትና በፍላጎት የተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ መሰረታዊ መስፈርት መሆኑ በተለያዩ ሀገራት ህጎች ውስጥ መካተቱ በቸልተኝነት የሚፈፀሙ ድርጊቶችን እንደ ሙከራ መቁጠሩ በአሁኑ ጊዜ ብዙም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያሳያል

የወንጀል ህጋችንም በአንቀፅ 27(1) “ማንም ሰው አስቦ…” የሚለውን ሃረግ በማካተት መቀረፁ ድርጊቱ በአውቆ አጥፊነት የተጀመረ መሆኑ መረጋገጡ መሰረታዊ መስፈርት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች የተከሰሱበት ድርጊት በቸልተኝነት የተፈፀመ የሙከራ ድርጊት መሆኑ ከላይ በተመለከተው አግባብ የተረጋገጠ ሆኖ እያለ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መስጠቱ እና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች ይህንን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊያርሙ ሲገባ ሳያርሙ መቅረታቸው አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር አመልካች ከቀረበባቸው የመግደል ሙከራ የወንጀል ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች የወንጀል ሙከራ ድርጊቱን የፈፀሙበትን ሽጉጥ እንዲወረስ የወሰነበትን የህግ አግባብ በውሳኔው ላይ ያላመለከተ በመሆኑና ተጠሪም የወንጀል ሙከራ ድርጊቱ የተፈፀመበት መሳርያ የሚወረስበትን አሳማኝና ህጋዊ ምክንያት ያላቀረበ በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1.በፊንፊኔ ዙርያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.18862 ግንቦት 06 እና 08 ቀን 2011 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.315181 በ04/10/2011 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.311856 በ28/10/2011 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት እንዲሁም የሽጉጥ ውርስ ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.195 (2)(ለ)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2.አመልካች ከቀረበባቸው ክስ በነፃ የተሰናበቱ ስለሆነ ከእስር ሊለቀቁ ይገባል ብለናል፡፡ለማረሚያ ቤቱ የመፈቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡

3.መለያ ቁጥሩ EP1291212 የሆነው የቱርክ ሽጉጥ ለአመልካች እንዲመለስላቸው በአብላጫ ድምፅ ታዟል፡፡መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

## <u>2.2 በሕብረት የተፈፀመ ወንጀል[9]</u>

- በክሱ ላይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 35 አለመጠቀሱ ስህተት ቢሆንም ተጠሪ ድርጊቱን በሕብረት ከፈጸሙ ሰዎች መካከል መገኘታቸዉን ዐቃቤ ሕግ ካስረዳ ተጠሪ በቦታዉ አለመገኘቱን ወይም ወንጀሉን ለመፈጸም አስቦ በቦታዉ አለመገኘቱን እና የወንጀል ድርጊቱን አለመፈጸሙን በማስረዳት የማስተባበል ኃላፊነት የተጠሪ ኃላፊነት ይሆናል፡፡

[9] ሰ/መ/ቁ 235233 (ጥቅምት 26 ቀን 2016ዓ.ም)

ሰ/መ/ቁ 235233

ጥቅምት 26 ቀን 2016ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች ፡-** የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ - ጌታቸው አሰፋ - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** መገርሳ ካሳዬ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተጠሪ ከቀረበባቸው የወንጀል ክሶች በነጻ እንዲሰናበቱ በመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል በአመልካች የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ እና በዚህ ሰበር አቤቱታ ባልተካተቱ ሌሎች ስር ተከሳሾች ላይ ከመሰረተው በርካታ የወንጀል ክሶች መካከል በአሁን ተጠሪ(የስር 30ኛተከሳሽ የነበሩ) ላይ 1ኛ እና 2ኛ ክሶችን መስርቷል፡፡ የመጀመሪያዉ ክስ እነዚህ ተጠሪ 29ኛ፣31ኛ፣32ኛ ከነበሩ ስር ተከሳሾች ጋር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣35፣38 እና 240/3 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በተደራጀ እና በተነሳሳዉ እንቅስቃሴ ዉስጥ በራሱ ፍቃድ ተካፋይ ለመሆን በማሰብ በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ የቡራዩ ከተማ ወረዳ 01፣ ወረዳ 02 እና ወረዳ 03 ዉስጥ ከቀን 02-06/01/2011 ዓ/ም ባሉት ቀናቶች በቀን 05/01/2011 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ በመስቀል አደባባይ ወደ ሀገር ቤት ለሚመለሱት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦ.ነ.ግ.) ከፍተኛ አመራሮች ለሚደረገዉ አቀባበል ሥነ ሥርዓት ላይ ለመካፈል እና ለዝግጅቱ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ከሚገቡ የሥነ ሥርዓቱ ተካፋይ የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች ወደ አዲስ አበባ እንዳንገባ፣ ባንዲራችን እንዳንሰቅል፣የአርማችንን ቀለም እንዳንቀባ ተከልክለናል፣ እንዳንገባ የከለከሉን የዶርዜ ተወላጆች ናቸዉ፣ የኦሮሞ ሴቶችን ጡት እየቆረጡ የኦሮሞ ህፃን ገለዉ በኦ.ነ.ግ ባንዲራ ጠቅልለዉ ጥለዋል በሚል ባልተረጋገጠ ወሬ በመነሳሳት በተፈጠረ ግጭት ምክንያት ክላሽ ፣ ገጀራ፣ሽጉጥ ጩቤ፣ፌሮ፣ዱላ እና ድንጋይ የመሳሰሉትን ገዳይ መሳሪያዎች በመያዝ ከላይ በተገለፀዉ ቀንና ቦታ በተፈፀመ ወንጀል የ37 ሰዉ ህይወት እንዲያልፍ በርካታ ግለሰቦች ላይ ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት እንዲደርስ፣ብዛታቸዉ 4506 በላይ የሆኑ የአካባቢ ነዋሪዎች ከመኖሪያ ቤታቸዉ እንዲፈናቀሉ በማድረጋቸዉ በአጠቃላይ በመዝረፍ በመሰባበር እና በማቃጠል ብር 17,538,744 የሚገመት ንብረት ሲወድም ተጠሪ በራሱ ፍቃድ በድርጊቱ ተካፋይ በመሆን፡- ተጠሪ በቀን 04/01/2011 ዓ.ም በግምቱ ከ4፡00 ሰዓት አካባቢ በኦሮሚያ ክልል በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ ወረዳ 01 ለኩ ከታ ቀበሌ እየተባለ በሚጠራዉ ስፍራ ተጠሪዎች በዋናነት ገጀራ፣ ቢላ፣ ጩቤ፣ድንጋይና ሽጉጥ በመያዝ ብዛት ያላቸዉን ያልተያዙ ግብረአበሮቻቸዉን በማስተባበር የስር 28ኛ ተከሳሽ የሆነው ግርማ በቀለ ወደ አዲስ አበባ ወጣቶች ሽጉጥ እየተኮሰ ሲያጋጭ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ድንጋይ በመወርወር ወደ ኦሮሚያ ድንበር ከመለሷቸዉ በኋላ ከላይ በተገለፀዉ ቦታ ላይ የግል ተበዳይ ታምራት ጠርዞ ዋልኬ የተባለዉን የጋሞ ብሄር ተወላጅ በዱላ ደብድበዉ ሞቷል ብለዉ ጥለዉት የሄዱ ሲሆን በቀን 03/01/2011 ዓ/ም ንብረትነቱ የአቶ ግዛቸዉ አሰፋ እና የወ/ሮ ዙሪያሽ ወርቅ ደገፋ የሆነዉን ፊኔት ግሮሰሪ እንዲወድም በማድረጋቸዉ፤ እንዲሁም በቀን 05/01/2011 ዓ/ም በ28ኛ ተከሳሽ አስተባባሪነት ብሔር እየለዩ ንብረትነቱ የአቶ ቸርነት እሸቱን እና የሌሎችንም የጋሞ ብሔረሰብ ተወላጆች ንብረት እንዲወድም በማድረግ የተሳተፉ በመሆኑ፤ በአጠቃላይ ተጠሪ ከስር ተከሳሾች ጋር አንዱ ወገን

በሌላዉ ወገን ላይ የጦር መሳሪያ እንዲያነሳ እና የእርስ በርስ ጦርነት እንዲነሳ በማሰብ በተፈጠረዉ እንቅስቃሴ ዉስጥ የጦር መሳሪያ እና ሌሎች ገዳይ መሳሪያዎችን በመጠቀም በሰዉ ህይወት እና አካል ላይ ጉዳት በማድረስ እንዲሁም ሰዎችን በማፈናቀል እና በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ ተግባር ላይ የተሳተፉ በመሆኑ በፈፀሙት በተደራጀ ወይም በተነሳሳ እንቅስቃሴ ዉስጥ በራሳቸዉ ፍቃድ ተሳታፊ በመሆን ወንጀል ተከሰዋል የሚል ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

በተጠሪ ላይ የቀረበው ሁለተኛ ክስም ተጠሪ እና የስር 28ኛ፣39ኛ፣31ኛ፣32ኛእና 33ኛ ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1፣ 32(1/ሀ)፣ 240/4 እና 539(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተጠቀሰው ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም ላይ የግል ተበዳይ ታምራት ጠርዞ ዋልኬ የተባለዉን የጋሞ ብሄር ተወላጅ በዱላ ደብድበዉ ሞቷል ብለዉ ጥለዉት የሄዱ በመሆኑ፤ በግብረአበርነት በፈፀሙት ከባድ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነዉ ፡፡

ተጠሪ ክሱ ደርሶት ሁለቱንም ክስ ክዶ የተከራከረ በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ከቆጠራቸዉ ምስክሮች ዉስጥ 72 ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ዐቃቤ ሕግ አቅርቦ ካሰማቸዉ ምስክሮች መካከል ከቀረበባቸዉ ክስ አንጻር ከተጠሪ ጋር በተያያዘ የምስክርነት ቃል የሰጡ የዐ/ህግ 42ኛ ምስክር ሆነው የመሰከሩት በአጭሩ- ወ/ሮ ዙሪያሽ ወርቅ የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሲመሰክሩ- በቡራዩ ከታ ልዩ ስሙ ሙገር በሚባል አካባቢ በቀን 03 እና 04/01/2011ዓ/ም በ4፡00 ሰዓት ቁጥራቸዉ በግምት ከ500 በላይ የሆኑ ሰዎች ገጀራና ዱላ ይዘዉ መጥተዉ ምክንያት ሳናዉቅ አዲስ አበባ ድንበር ወደአሉት ወጣቶች ድንጋይ ይወረውሩ ነበር፡፡ ድንጋይ የሚወረዉሩት የማላዉቃቸዉ ቄሮዎች የሚባሉ ሰዎች ናቸዉ፡፡መጨረሻ ላይ ቶሎሳ ግርማ በቀለ መሳሪያ ወደ አዲስ አበባ ወጣቶች እየተኮሰ ወጣቶችን ወደ አዲስ አበባ ይዟቸዉ ገባ፡፡ እያስተባበሩ የነበሩት ግርማ በቀለ፣ረታና ቶሎሳ ነበሩ፡፡ ከታ ሙገር ሰፈር ላይ ኪኔት ባር እና ሬስቶራንት አለኝ፡፡ መስከረም 3 ቀን የተወሰነ ነገር ሰባብረዉ ሄዱ፣መስከረም 4 ግን አጠቃላይ ንብረቴን አወደሙት፡፡ ወንዝ አካባቢ ሽራ ከልሎ የሚቀመጥ ታምራት የሚባል ሰዉ ጎትተዉ አዉጥተዉ እኔ በር ፊት ለፊት ሲገፉና ልዩ ኃይል የሚለብሰዉን ልብስ ለብሰዉ የነበሩ ፖሊሶች ረግጠዉት ሲያስሙቱት ነበር፡፡ አገላብጠዉ አይተዉ ሞተዋል ብለዉ ጥለዉት ሄዱ፡፡ ተጠሪም ቆሞ ረታ ከተባለው ስር ተከሳሽ ጋር አብሮ እያስተባበረ ወጣቶቹን በግሩፕ በግሩፕ ሆነው በዚህ ሂዱ በዚህ ሂዱ በማለት እያሰማሯቸው ነበር በማለት መስክረዋል፡፡

በተጨማሪም የዐ/ህግ 45ኛ ምስክር ሆነው የመሰከሩት የግል ተበዳይ ታምራት ጠርዞ በሰጡት ምስክርነት ቃል ማንነታቸዉን የማላዉቀቸዉ ቄሮዎች የምኖርበትን ሽራ ቤት አንዱ በገጀራ ቆርጦ ገብቶ ለሌሎች በሩን ከፍቶላቸዉ ሌሎች ገብተዉ ሚስቴን ዶርዜ ካለ እንድትጠቁሚ ነዉ የመጣነዉ አዉጪ ስላት እሷም እዚህ ዶርዜ የለም ስትላቸዉ እሷን መተዋት ስትወድቅ እኔ የተደበቅሁበትን አልጋ ገልብጠዉ ባትሪ አብርተዉ አግኝተዉኝ እዚያዉ በመጥረቢያ እንጨት አናቴን ጭንቅላቴን መቱኝ ሰዎችን ማየት ስላልቻልኩ ድንጋጩም ስለነበር ጎትተዉ ወደ ግቢ አዉጥተዉ ሰዉነቴን በሙሉ መተዉኝ ዥንጉርጉር ለለበሱ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ፖሊሶች አሳልፈዉ ሰጡኝ፡፡ እነሱም ብር፣ሽጉጥ መሳሪያ ያለበትን አሳይ ምራ ጠቁም ስሉኝ እኔ አላዉቅም ስላቸዉ ልቤን መቱኝ ወደኩ ድብደባ ሲጀመሩ እኔ እራሴን አላዉቅም በማለት መስክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 229262 ክሶቹንና የዐቃቤ ሕግን ማስረጃዎች መርምሮ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ተጠሪና ሌሎቹ ስር ተከሰሾቹን በችሎት ለይተዉ አሳይተዉ በቀን 03 እና 04/01/2011ዓ/ም ግርግር የነበረና ከ500 በላይ የሆኑ ሰዎች ገጀራና ዱላ ይዘዉ ወደ አዲስ አበባ ለመግባት ድንጋይ እየተወረወረ መሆኑን፣ የአዲስ አበባ ወጣቶች ከድልድይ በታች ሆነዉ ተጠሪ ከስር 31ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ረብሻውን ሲያስተባብር የነበረ መሆኑንና በረብሻው ምክንያት የአቶ ግዛቸውና የወ/ሮ ዙርያሽ የሆነ 500000 የሚገመት ንብረት ያወደሙና ሽራ ከልሎ የሚኖርን ታምራት ጠርዞ የሚባል ሰዉ ደብድበዉት ሞቷል ብለዉ ጥለዉት የሄዱ መሆኑ ተመስክሮባቸዋል፡፡

ነገር ግን ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾች ላይ ክስ የመሰረተዉ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣35፣38 እና 240/3 በመጥቀስ ቢሆንም ለአንቀጽ 240/3 መነሻ የሆነዉ አንቀፅ 240/1 ሲሆን የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ሀ)በመንግስት በተቋቋሙ አካላት ወይም ባለስልጣናት ላይ ሕዝብ፣ ወታደሮች ወይም ሽፍቶች የትጥቅ አመፅ እንዲያነሱ ያደራጀ ወይም የመራ እንደሆነ የሚል ሆኖ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ለ) ዜጎች ወይም በሀገር የሚኖሩ ዜጎችን በማስታወቅ ወይም አንዱ ወገን በሌላዉ ላይ የጦር መሳሪያ እንዲያነሳ በማነሳሳት የእርስ በእርስ ጦርነት እንዲነሳ ያደረገ እንደሆነ የሚል ነዉ፡፡ በመጀመሪያ ንዑስ አንቀፅ ላይ የተቀመጠዉ በሕገ መንግስት በተቋቋመ ባለስልጣናት ላይ የሚፈፀም ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ክስ የተፈፀመዉ ወንጀል በሕገ መንግስት በተቋቋመ ባለስልጣናት ላይ ባለመሆኑ፤ እንዲሁም በአንቀፅ 240(1/ለ) የተቀመጠዉን ሃሳብ ዜጎችን ያስታጠቀ አካላት መኖሩን የሚያስቀምጥ በመሆኑ በዚህ ክስ ምስክሮቹ እንዳስረዱት የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመዉ በአዲስ አበባ ላይ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ ጉዳት ደርሷል በማለት በጊዜዉ በተነሳ ግጭት ምክንያት ተነስቶ የተፈፀመ እንደሆነ ያስረዱ በመሆኑ በቀረበዉ የሰዉ ማስረጃ መሰረት ተጠሪዎች ስለመፈጸማቸዉ የተመሰከረዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 240/3 ስር የሚሸፈን አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ስለመፈጸማቸዉ የተመሰከረባቸዉ የአምቧጓሮ ወንጀል ስለሆነና በሰዉ አካል ላይ ጉዳት ያደረሱና የግድያ ሙከራ ወንጀል የፈጸሙ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ የተጠቀሰባቸዉ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 240/3 በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/1 መሰረት ወደ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1/ሀ)፣35፣38 እና 577/3 ተለዉጦ ሊከላከሉ ይገባል በማለት ብይን ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በክስ 2 ተጠሪ በዋና ወንጀል ፈፃሚነት ተካፋይ በመሆን ሰዉ ለመግደል በማሰብ ... የግል ተበዳይ ታምራት ጠርዞ ዋልኬ የተባለዉን የጋሞ ብሄር ተወላጅ በዱላ ደብድበዉ ሞቷል ብለዉ ጥለዉት የሄዱ በመሆኑ በግብረአብርነት በፈፀሙት ከባድ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል በተከሰሱት መሰረት በክስ አንድ ላይ በተገለጸዉ መሰረት የወንጀል ድርጊቱን የፈፀሙት በቂም በቀል በመሆኑ ክሳቸዉ ከተቋረጠላቸዉ 28ኛ እና 33ኛ ተከሳሾች ወጪ ያሉ ተከሳሾች ማለትም የአሁን ተጠሪ ጨምሮ በተከሰሱበት የሰዉ መግደል ሙከራ ወንጀል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 27/1፣32(1/ሀ)፣ 577/4 እና 539 (1/ሀ) ስር ይከላከሉ በማለት ብይን ተሰጥቷል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ አንድ መከላከያ ምስክር አቅርቦ ያሰማ ሲሆን እንደሚከተለዉ አሰምተዋል፡፡ መከላከያ ምስክሩ አቶ ተመስገን ሰርቤሳ የተባለ ሲመሰክር ከመስከረም 1 አዲስ አመት በአል ስለነበር ጎረቤታሞች በመሆናቸው አብረው የነበሩ መሆኑን በዋዜማውም የወንድሙ ግሮሰሪ አብረው እንደዋሉ መስከረም 3 ቀን ተጠሪ ሽሮ ሰርቶ እንደጠራውና አብረው እንደበሉ መስከረም 4 ይሁን መስከረም 3 ሽሮ አብረው የበሉበት ቀን ቀኑ ስለራቀ መርሳታቸውን መስከረም 5 ቀን ኦነግ ይገባል የተባለበት ቀን በመሆኑ ከተጠሪ ጋር የወንድሙ ግሮሰሪ ውስጥ አብረው እንደዋሉ ውጪ ላይ ረብሻ ድንጋይ መወርመር ስለነበረ የተጠሪ ወንድም ከግሮሰሪው እንዳንወጣ በሩን መዝጋቱን፤ ግሮሰሪ ውስጥ በመሆን ኦነግ ሲገባ በቴሌቭዥን ሲከታተሉ የነበረ መሆኑን በግምት ከስምንት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ቆይቶ ወደ ቤቱ መሄዱን መስክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 229262 ላይ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምሮ በቀን 14/08/2013ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ ተጠሪ ባሰማው አንድ መከላከያ ምስክር መከላከል አለመከላከሉን ሲመረመር መከላከያ ምስክሩ ከተጠሪ ጋር ከመስከረም 1 ቀን እስከ መስከረም 5 ቀን አብረው የነበሩ መሆኑን ሲመሰክር ቀኑን ከመጥቀስ ውጭ የትኛው ዓመተምህረት እንደሆነ አይገልጽም እንዲሁም የምስክሩ ቃል አሰጣጥ ሲታይ ተጠንቶ የቀረበ በሚመስል መልኩና አጠራጣሪ ሆኖ ስላገኘነው ተዓማኒነት ያለዉ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ እንዲከላከል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የቀረበበትን ክስና ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ስላልተከላከለ በክስ 1 በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 577/3 ስር በክስ 2 ደግሞ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1፣32(1/ሀ)፣577/4 እና 539(1/ሀ) ስር ጥፋተኛ ነው ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የግራ

ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ በቀን 16/09/2013 በሰጠዉ የቅጣት ዉሳኔ ተጠሪ በ15 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት መሆኑን ተመልክተናል፡፡

ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅረበዉ ችሎቱም በመ/ቁጥር 213064 ላይ የስር ፍርድ ቤት ባስተላለፈዉ የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ ስህተት አለ ወይስ የለም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 4/11/2014 ዓ/ም ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ክሱን ለማስረዳት የቀረቡት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ውስጥ ከተጠሪ ጋር በተያያዘ የመሰከሩት አንድ ምስክር ወ/ሮ ዙርያሽወርቅ ደገፉ አቲሴ የተባሉ ሲሆኑ ምስክርነታቸውም ተጠሪ ረታ ከተባለው የስር ተከሳሽ ጋር ሲያስተባብር ነበር ከማለት ውጭ በክሱ በተጠቀሰው አግባብ የወደመውን ንብረት እና የተፈናቀሉ ሰዎች እንዲፈናቀሉ አድርጓል ለማለት የሚያስችል በቂ ማስረጃ አለመቅረቡን እንዲሁም በተጠሪ ላይ የቀረበው 2ኛ ክስም ተጠሪ የግል ተበዳይ ታምራት ጠርዞን አስደብድበዋል በማለት በከባድ ሰው መግደል ሙከራ ወንጀል የተከሰሱ ሲሆን ወ/ሮ ዙሪያሽ ወርቅ የተባሉ የዐ/ህግ ምስክር ተጠሪ ቆመው ታምራት ጠርዞ የተባለዉን የግል ተበዳይን በፖሊሶች ሲያስደበድቡት ነበር በማለት ያስረዱ ሲሆን በሌላ በኩል የግል ተበዳዩ የደበደቡኝ ዥንጉርጉር ልብስ የለበሱ ፖሊሶች ናቸው በማለት ተጠሪ በቦታው ይኑር አይኑር እንደማያውቁ ከመሰከሩት አንጻር ሲታይ የዐ/ህግ ምስክርዋ የሰጡት ቃል ተአማኒነት ያሳጣ መሆኑን እንዲሁም በተጨማሪም ተጠሪ የግል ተበዳይን በፖሊሶች እንዲመቱ ለማድረግ ስልጣን ያላቸዉ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ተጠሪ የግል ተበዳይ ታምራት ጠርዞ ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈፅመዋል ሊያስብል የሚችል ሆኖ አላገኘነዉም በማለት የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ያስተላለፈዉን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195(2/ሀ) መሰረት በመሻር ተጠሪ በነጻ እንዲለቀቁ ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 30/01/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ- ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተጠሪ የከባድ ግድያ ሙከራ ወንጀል ስለመፈጸማቸዉ አልተረጋገጠም ማለቱ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተደረገን ክርክር እና ማስረጃን መሰረት ያላደረገ ነዉ፡፡ምስክሮቻችን ተጠሪ ወጣቶቹን(ቄሮዎችን) ሲመሩ እና ሲያስተባብሩ የነበሩ መሆኑን፣በእነርሱ ምሪት ቄሮዎች የጋሞ ብሔር ተወላጆችን ለይተዉ ሲደበድቡ እና ሲገድሉ ሲያስገድሉ የነበሩ መሆኑን፣ ንብረታቸዉን ሲያወድሙ እና ሲያስወድሙ የነበረ መሆኑን ከእነዚህ ዉስጥ ታምራት ጠርዞ የተባለዉን የግል ተበዳይ በተጠሪ ሲመራው የነበረው ወጣቶች ምሪት በቤቱ በመግባት እየደበደቡ ካስወጡ በኋላ ለኦሮሚያ ፖሊስ ያስረከቡ መሆኑን፣የኦሮሚያ ፖሊሶችም መሳሪያዉን እና ብሩን የት ነዉ ያስቀመጥከዉ አምጣ በማለት ደብድበው ሞቷል ብለው ትተው የሄዱ መሆኑን መስክረዋል፡፡ ከዚህ ባለፈም የቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ በግል ተበዳይ ላይ ጉዳት መድረሱን የሚያረጋግጥ ሲሆን ሰነዱም የምስክሮቻችን ቃል የሚደግፍ እና የሚያጠናክር ነዉ፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም ሆኑ የግል ተበዳይን የደበደቡት ዥንጉርጉር የለበሱ የኦሮሚያ ፖሊሶች ብቻ ሳይሆኑ በተጠሪ የሚመራ ወጣቶች መሆናቸዉ ተመስክሮ እያለ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተጠሪ ላይ አልተመሰከረም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በአግባቡ ማስረጃ አለመመዘኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ተጠሪ የግል ተበዳይን በፖሊስ ለማስደብደብ ሥልጣን ያላቸዉ ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ አልቀርብም በሚል ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የሰጠዉ ምክንያት ሲጀምር ሰዉን መደብደብ ወንጀል ስለሆነ ሰዉን ለመደብደብ ሆነ ለማስደብደብ ማስረጃ መቅረብ ነበረበት ተብሎ በነጻ እንዲሰናበቱ መወሰን ስህተት ነዉ፡፡ይህም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ጉዳዩን በአግባቡ እንዳልተመለከተ እና በማስረጃ ምዘና ረገድ መሰረታዊ ስህተት የፈጸመ መሆኑን የሚያመላክት ነዉ፡፡በመሆኑም ተጠሪዎች ከተከሰሱበት ድንጋጌ አንጻር አሊያም ድርጊቱን ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 37/1 አንጻር በመመልከት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ማጽናት ሲገባዉ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ እና የማስረጃ ምዘና ስህተት ነዉ፡፡

እንዲሁም ተጠሪ በቦታዉ ተገኝተዉ ሲያበረታቱ የነበሩ መሆኑ ተመስክሮባቸዋል፡፡ በተጠሪዎች ላይ ክሱ የቀረበዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ እና ለ) 35፣38 እና 240/3 ተላልፈዋል በሚል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 መሰረት ከዐቃቤ ሕግ የሚጠበቀዉ የማስረዳት ሸክም ተጠሪ ድርጊቱ በተፈጸመዉ ቦታ ስለመገኘቱ ብቻ ሲሆን ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ምስክሮቻችን ተጠሪ በቦታዉ የነበረ እና ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን መስክረዋል፡፡ ከዚህ ባለፈ የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተጠሪ የሚተላለፍ ሲሆን ተጠሪ በመከላከያ ምስክሩ አላስተባበለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተጠሪ ከተከሰሰበት ድንጋጌዎች አንጻር ማለትም ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 አንጻር ተመልከቶ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አለማጽናቱ ስህተት ነዉ፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ምስክሮቻችን ግልጽ በሆነ ሁኔታ መስክረዉ ሳለ እንዲሁም በተጠሪ በኩል ያሰማው አንድ መከላከያ ምስክር የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ጥርጣሬ ዉስጥ በሚከት አኳኋን ሳይመሰክር የዐቃቤ ሕግን ማስረጃዉ ከሙሉ ይዘቱ አንድ ላይ መመዘን ሲገባዉ እንዳልተመሰከረ አድርጎ ከምስክሮቹ ምስክርነት ቃል አዉድ እና ይዘት ዉጭ እንዲሁም የምስክሮቻችን ቃል ነጣጥሎ በማየት እና በመመዘን ዐቃቤ ሕግ ከጥርጣሬ በጸዳ መልኩ አላስረዳም ማለቱ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ እና ሕግን ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ በሰ/መ/ቁጥር 64813፣35697 እና 89676 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የሰበሪ አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያስተላለፈዉን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ሽሮ ተጠሪ ከቀረበበት ክስ በነፃ እንዲሰናበት የወሰነበትን አግባብነት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 35697፤64813፤89676 በሆኑ መዝገቦች በመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆች ላይ ከሰጠው የሕግ ትርጉም አኳያ ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል ከተባለ በኃላ ተጠሪ ተገቢው የመጥሪያ አሰጣጥ ቅደም ተከተል ተከትሎ ነሀሴ 22 ቀን 2015ዓ.ም እትም በሆነው በአዲስዘመን ጋዜጣ ተጠርተው ስላልቀረቡ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በስር ፍርድ ቤቶች የነበረው የግራ ቀኙን ክርክርና የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተጠሪ በነጻ ሊለቀቁ ይገባል ሲል የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሮ በመወሰኑ በሰበር ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም የስር ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረተባቸዉን ክሶች ተጠሪ በመከላከያ ማስረጃዉ አላስተባበለም በሚል በክስ 1 አምባጓሮ ወንጀል ዉስጥ ተካፋይ በመሆን ቂም በመያዝ ማሳሪያዎችን፣ድንጋዮችንና ሌሎች ማቁሰል የሚችሉ ነገሮችን ከያዙ ወጣቶች ጋር በመሆን በመሳተፉና በዚህም በሰዉ ላይ የመግደል ሙከራ መፈጸሙ ተረጋግጧል በሚል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 577/3 ስር ጥፋተኛ ያለዉ ሲሆን በክስ 2 ደግሞ ተጠሪ በተሳተፈበት አምባጓሮ በአንድ ሰዉ ላይ የግድያ ሙከራ መፈጸሙን ምክንያት በማድረግ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1፣32(1/ሀ)፣577/4 እና 539(1/ሀ) ስር ተጠሪ ጥፋተኛ በማድረግ ፍርድ ሰጥቶ ቅጣት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ደግሞ ተጠሪ በሁለቱ ክሶች የተመለከተዉን ወንጀል በመሳተፍ የተከሰሰበት ወንጀል ሊያቋቁም የሚችል ድርጊት ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ አላስረዳም በሚል የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር በነጻ እንዲሰናበት የተወሰነ ሲሆን ከላይ በዝርዝር በተመለከተዉ መሰረት አመልካች የሰበር አቤቱታዉንም ያቀረበዉ በዚህ መልኩ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነዉ፡፡ ከላይ ለተመለከተዉ ዋና ጭብጥ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ሊመረመሩ የሚገባቸዉና ምላሽ የሚሹ ጭብጦች ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተጠሪ በነጻ እንዲሰናበት የወሰነዉ በክሶቹ ከተጠቀሱት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች አንጻር የዐቃቤ ሕግን እና የተጠሪን የማስረዳት ሸክም መሰረት ባደረገ መልኩ ነዉ ወይ? ከሕግና ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አኳያስ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን የሚመለከት ነዉ፡፡

በአገራችን በተዘረጋዉ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መሰረት ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙ ወይም ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በተሟላ መልኩ መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ አግባብ መቀጣት ይገባዋል፡፡ በዚህ መልኩ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለዉ በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተከሳሹ ድርጊቱን/አል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በሚያሳይ አግባብ በማስረጃ ሲያስረዳ ነዉ(የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ይመለከቷል)፡፡ በአንጻሩ የወንጀል ክስ የቀረበበት ሰዉ የወንጀል ድርጊት/አል ድርጊት አለመፈጸሙ ወይም የወንጀል ሕጉ የወንጀል ተጠያቂነትን በሚያስከትለዉ ተካፋይነት ደረጃ በወንጀል አፈጻጸሙ ተካፋይ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ከቀረበበት የወንጀል ክስ በነጻ የሚሰናበትበትን አግባብ በአገራችን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ፍርድ ቤቶችም ክርክር ሲሰሙ፣ማስረጃ ሲመረምሩና ሲመዝኑ እንዲሁም ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጡ ከማንኛዉም ተጽዕኖ ነጻ በመሆን ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሳይመሩ የወንጀል ሕጉን ግብ፣ ዓላማዎችና መርሆዎች ባከበረ እንዲሁም የተጎጂዉን እና የከሳሹን መብቶች ማዕከል ባደረገ አኳኋን የቀረበላቸዉን ክስ፣ክርክርና ማስረጃ በአግባቡ አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበዉ በመመርመር በገለልተኛነት እና በሙሉ ነጻነት የዳኝነት ተግባራቸዉን የማከናወን ግዴታ እና ኃላፊነት እንዳለባቸዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1፣2፣ እና 4)፣13፣20 37፣79(2 እና 3)፣ ከዋናው የወንጀል ሕጉ ክፍል እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች በተለይም ክስ 1 ላይ ተጠሪ በክሱ በተጠቀሰዉ የወንጀል ድርጊት ስላለዉ ተካፋይነት ለመግለጽ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32(1/ሀ)፣35 እና 38 ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉን በመጥቀስ ክስ መስርቶበታል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች አንድ ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል አፈጻጸም ላይ ተካፋይ ሊሆን የሚችልባቸዉን የተካፋይነት አይነትና ደረጃ(degree) የሚደነግጉ ናቸዉ፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 እና ተከታዮቹ ላይ ከተመለከተዉ መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ የወንጀል ድርጊት በአንድ ሰዉ ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ(ብዙ) ሰዎች ተሳትፈዉበት ሊፈጸም ይችላል፡፡ በብዙ ሰዎች የተፈጸመ ወንጀል በሆነ ጊዜ የወንጀል ፈጻሚዎቹ ተሳትፎ ደረጃ አንድ አይነት ወይም የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ በወንጀሉ አፈጻጸም ያላቸዉ ተካፋይነት አንድ አይነት ነዉ ወይስ የተለያየ የሚለዉን ለመለየት የተከፋይነታቸዉን አይነት፣ ደረጃ እና በወንጀሉ አፈጻጸም የነበራቸዉን ሚና (the degree of involvement and the role played by such persons in the commission of the crime) መለየት ይገባል፡፡

የወንጀል ተካፋይነት (Participation) በተለያዩ የሕግ ስርዓቶች በተለያዩ መገለጫዎች በሰፊዉ ወይም በጠባቡ ይገለጻል፡፡ አንዳንድ አገራት የወንጀል ተካፋይ መሆንን በጠባቡ በማየት በወንጀል ድርጊቱ በአካል (physically or personally) የተሳተፈዉን ወይም ድርጊቱን የፈጸመዉን (material offender)ብቻ ተጠያቂ የሚያደርጉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ የወንጀል ድርጊቱን በቀጥታ በመፈጸም የተካፈለዉን ብቻ ሳይሆን በወንጀል ድርጊቱ አፈጻጸም በተዘዋዋሪ ወይም የወንጀል ድርጊቱን የራሱ በማድረግ በሀሳብ ተካፋይ የሆነዉን ሰዉ ሁሉ (take part in the commission of the offence either morally or indirectly) እንደተካፋይ በመቁጠር ተጠያቂ ያደርጋሉ፡፡ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 እና ተከታዮቹ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አገራችን ለወንጀል ተካፋይነት ሰፊ ትርጓሜ የሚሰጥ የሕግ ሥርዓት የምትከተል ናት፡፡በዚህ መሰረት የወንጀል ድርጊቱን በቀጥታ(በራሱ) የፈጸመም (Material Criminal) ሆነ በራሱ ድርጊቱን ባይፈጽምም የወንጀል ድርጊቱንና የሚያስከትለዉን ዉጤት የራሱ በማድረግ በሀሳብ ወይም በሌላ ሁኔታ ተካፋይ የሆነ ሰዉ( Moral Criminal) በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ እንደሆነ ይቆጠራል(የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1 ይመለከቷል)፡፡ ማንም ሰዉ በአንቀጽ 32/1 ስር ከተደነገጉት ሁኔታዎች በአንዱ ዘዴ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን አድርጎ እንደሆነ ወይም ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ደርጊትና

በሚሰጠዉ ዉጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ እንደሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት(A principal criminal in the first degree)ተካፋይ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡በሌላ በኩል ማንኛዉም ሰዉ በሁለተኛ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት(A principal criminal in the second degree) ተካፋይ ሆኗል ሊባል የሚችለዉ በቀጥታ ወንጀል ድርጊቱን በራሱ ባይፈጽምም በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ወንጀሉን የሚፈጽመዉን ሰዉ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ወይም ወንጀሉ በሚፈጸምበት ሂደትና ጊዜ በመጎትጎት ፣ወሬ በማቀበል፣በመምክር፣ ወንጀል የሚደረግበትን ዘዴ ወይም ገንዘብ፣ መሳሪያ ወይም ግዙፋዊ እርዳታ ወይም ስጦታ በመስጠት ወይም ለወንጀሉ አፈጻጸም በሚጠቅም በማናቸዉም ሌላ አይነት መንገድ ወይም ዜዴ አንድ ወንጀል እንዲደረግ በማግባባት ወይም በማበረታታት የተሳተፈ እንደሆነ ነዉ(የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 36 እና 37 ይመለከቷል)፡፡

እንዲሁም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል ተካፋይነት ወይም በሁለተኛ ደረጃ ዋና ወንጀል ተካፋይነት ወንጀል ሲያደርግ ተጠያቂ ስለሚሆንበት አግባብ የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 35 ስር በሕብረት ወንጀል በመፈጸም ተካፋይ ስለመሆን (Collective Crimes) በሚል ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 41 የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት ግላዊ ነዉ የሚለዉን የወንጀል ሕግ ጠቅላላ መርህ (General Principle of Individual Criminal Responsibility) ባገናዘበ መልኩ ተግባራዊ መሆን የሚገባዉ ነዉ፡፡በዚህ መሰረት ቁጥራቸዉ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች በሕብረት አንድ የወንጀል ድርጊት በተፈጸመ ጊዜ የወንጀሉ ተካፋይ መሆኑ ያልተረጋገጠበት ሰዉ በወንጀል አይቀጣም(የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 የመጀመሪያዉ ፓራግራፍ ይመለከቷል)፡፡እያንዳንዱ በሕብረቱ ዉስጥ ተካፋይ የሆነ ሰዉ በተካፋይነቱ ደረጃ፣በጥፋቱ መጠን፣ራሱና ድርጊቱ ሊያስከትለዉ በሚችለዉ የአደጋ ከባድነት መጠን እራሱ በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል ተካፋይነት ወይም በሁለተኛ ደረጃ ዋና ወንጀል ተካፋይነት ባደረገዉ ወንጀል ብቻ ይቀጣል፡፡ ከዚህ የምንገነዘበዉ ወንጀሉ በሕብረት የተፈጸመ ወንጀል ቢሆንም የወንጀል ተጠያቂነትም ሆነ የወንጀል ቅጣት በተሳትፎዉ ልክ የተገደበ ወይም ግላዊ እንደሆነ ነዉ፡፡

ከላይ የተመለከተዉ አጠቃላይ መርህ እንደተጠበቀ ሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 በሁለተኛዉ ፓራግራፍ ላይ ልዩ ሁኔታ ተመላክቷል፡፡ ይኸዉም በሕብረት የተፈጸሙ ወንጀሎች እንደ አድማ፣ሕገ-ወጥ ሰልፍ፣ ግርግር ፣ አምባጓሮ እና የመሳሰሉ ወንጀሎች የሆኑ እንደሆነ በሕብረቱ ዉስጥ መገኘቱ የተረጋገጠበት ሰዉ የማይቀጣዉ፣በወንጀሉ ተከፋይ አለመሆኑን ሲያስረዳ ነዉ፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 የመጀመሪያ ፓራግራፍ መሰረት ሰዎች በሕብረት የግድያ፣የዘረፋ ወይም ማናቸዉንም ሌላ መሰል ወንጀል የፈጸሙ እንደሆነ በሕብረቱ ዉስጥ ባሉት በእያንዳንዳቸዉ ወንጀል ፈጻሚዎች የተፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ማስረጃ አቅርቦ ጥፋተኛነታቸዉን የማስረዳት እና የማስቀጣት ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ ነዉ፡፡በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 ሁለተኛዉ ፓራግራፍ የተጠቀሱት ወንጀሎች ሲፈጸሙ የዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት የሚሆነዉ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ እና ጊዜ እያንዳንዱ ሰዉ በሕብረቱ ዉስጥ መገኘቱን የማስረዳት ሸክም ብቻ ነዉ፡፡ከዚህ ዉጭ በሕብረቱ ዉስጥ ያሉ ሰዎች ምን ምን እንዳደረጉ የማስረዳቱ ሸክም የዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት አይደለም፡፡በእነዚህ ወንጀሎች የወንጀል ድርጊቱን ለመፈጸም አስቦ በሕብረቱ ዉስጥ አለመገኘቱን ወይም አስቦ የወንጀሉ ተካፋይ አለመሆኑን በማስረጃ ማስረዳት በሕብረቱ ዉስጥ ተገኝቷል የተባለዉ ሰዉ ኃላፊነት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ በሰ/መ/ቁ 228017 ላይ ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር እንደተመለከተዉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉሥልጣን ማናቸዉንምመሠረታዊየሕግስህተትየተፈጸመበትንየመጨረሻዉሳኔበሕግ በዝርዝር በሚወሰነዉ አግባብ መርምሮ እንዲያርም ነዉ፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመመዘን ጉዳይ ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩን

ወይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ፈጽሟል ወይስ አልፈጸመም የሚለዉን በማረጋገጥ ዉሳኔ መስጠት መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደማረም የሚቆጠር ባለመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ አይደለም፡፡

ሆኖም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች (Principles of Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence) አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standards of proof orweight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲረጋገጥ፤ በተጨማሪም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን ወይም በምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን በአግባቡ ያላገናዘበ እና ዉሳኔ የሚሻዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ለሆነ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ ሳይሰጡ ዉሳኔ መስጠት እንዲሁም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰን ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ተገብቷል የሚያስብል ሳይሆን እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 45595፣64813 (በቅጽ 12 የታተሙ)፣ 225975(ያልታተመ) እና በሌሎች መዛግብት ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች በአሁን ተጠሪ እና በሌሎች ስር ተከሳሾች ላይ በመሰረተዉ ክስ 1 ላይ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣35፣38 እና 240/3 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በተደራጀ እና በተነሳሳዉ እንቅስቃሴ ዉስጥ በራሳቸዉ ፍቃድ ተካፋይ በመሆን የጦር መሳሪያ ይዘዉ በማመጽ፣ወይም የእርስ በርስ ጦርነት እንዲነሳ አድርገዋል በማለት ከሷቸዋል፡፡ ይህ ወንጀል በሕብረት ሊፈጸም የሚችል አይነት ወንጀል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 በሁለተኛ ፓራግራፍ መሰረት በተጠሪና በስር ተከሳሾች ላይ ክስ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪና የስር ተከሳሾች ስለመፈጸማቸዉ ይበልጥ በምስክሮች የተመሰከረባቸዉ የአምባጓሮ ወንጀል ስለመፈጸማቸዉ ነዉ በሚል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/1ን በመጥቀስ የተከሰሱበትን ድንጋጌ በመለወጥ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 577/3 ስር ክሱን እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ባቀረበው መከላከያ ምስክር በማስተባበል መከላከል እንዳልቻለ በመግለጽ በዚሁ ድንጋጌ ስር በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 577/3 ስር ጥፋተኛ ነው ሲል የወሰነ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን በአግባቡ እንዳልመዘነ በመግለጽ ተጠሪ በወንጀል ድርጊቱ ተካፋይ በመሆን በክሱ የተጠቀሰዉን የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ አላስረዳም፤እንዲሁም ተጠሪ ክሱን እንዲከላከል ከተነገረዉ በኋላም የተከሰሰበትን ወንጀል አለመፈጸሙን በማስረዳት ተከላክለዋል በማለት ማስረጃዎችን በድጋሚ መዝኖ በነጻ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ በዚህ መልኩ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተጠሪ የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ አላስረዳም የሚል ድምዳሜ ላይ ሲደርስ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 ሁለተኛዉ ፓራግራፍ ላይ በተደነገገዉ መሰረት ዐቃቤ ሕግ ያለበትን የማስረዳት ሸክም በአግባቡ እንዳልመረመረ ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት ተጠሪ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ እና ጊዜ በሕብረቱ ዉስጥ ወይም ወንጀሉን ፈጻሙ ከተባሉ ሰዎች መካከል የተገኙ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ብቻ ነዉ፡፡ ዐቃቤ ሕግ ይህንን ያህል ካስረዳ የወንጀል ድርጊቱን ለመፈጸም በማሰብ በሕብረቱ ዉስጥ አለመገኘታቸዉን ወይም በወንጀሉ አፈጻጸም ተካፋይ አለመሆናቸዉን በማስረጃ የማስረዳት ሸክም የተጠሪዎች ነዉ፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ተጠሪ ወደ ሀገር ቤት ለሚመለሱት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦ.ነ.ግ.) ከፍተኛ አመራሮች በአዲስ አበባ ከተማ በመስቀል አደባባይ ላይ ለሚደረገዉ አቀባበል ሥነ ሥርዓት ላይ ለመካፈል እና ለዝግጅቱ ወደ አዲስ አበባ ከተማ የሚገቡ የሥነ ሥርዓቱ ተካፋይ የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች ወደ አዲስ አበባ እንዳንገባ ፤ባንዲራችንን እንዳንሰቀል እንዲሁም አርማችንን ቀለም እንዳንቀባ ተከልክለናል

በሚል በተፈጠረ ግጭት ምክንያት እንዳንገባ የከለከሉን የጋሞ(የዶርዜ) ብሄር ተወላጆች ናቸዉ፣ የኦሮሞ ሴቶችን ጡት እየቆረጡ የኦሮሞ ህፃን ገለዉ በኦ.ነ.ግ ባንዲራ ጠቅልለዉ ጥለዋል በሚል ደረሰብን ያሉትን ጥቃት ለመመለስ ክላሽ፣ ገጀራ፣ሽጉጥ ጩቤ፣ ፌሮ ፣ዱላ እና ድንጋይ የመሳሰሉትን ገዳይ መሳሪያዎች በመያዝ ከቀን 03-05/01/2011ዓ/ም በተነሳሱ ወጣቶች (ቄሮዎች) እንቅስቃሴ በሰዉ ሕይወት፣አካል እና በንብረት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ባደረገዉ ሕብረት ዉስጥ ተጠሪ እንደተገኘ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ማስረዳታቸዉን የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ አረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ጉዳዩን ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 35 ሁለተኛ ፓራግራፍ አንጻር ስላልመረመረዉ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በዚህ ልክ አላስረዱም የሚል ድምዳሜ ላይ አልደረሰም፡፡ ዐቃቤ ሕግ ይህንን ያህል ካስረዳ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 35 ሁለተኛዉ ፓራግራፍ መሰረት ሕጉ የሚጠብቅበትን የማስረዳት ሸክም ተወጥቷል ማለት ነዉ፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበትን ድንጋጌ ለዉጦ ክሱን እንዲከላከል ብይን መስጠቱ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 35 ሁለተኛ ፓራግራፍ የተከተለ ነዉ ብለናል፡፡ በመቀጠል ሊመረመር የሚገባዉ የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተጠሪ ስለሚተላለፍ ተጠሪ በሕብረት ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ እና ጊዜ አለመገኘታቸዉን ወይም የወንጀሉ ተካፋይ አለመሆናቸዉን በማስረጃ በማስረዳት ተከላክለዋል ወይስ አልተከላከሉም የሚለዉ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በአግባቡ ማስረጃ ተመዝኖ መረጋገጥ አለመረጋገጡን የሚመለከት ነዉ፡፡ በክሱ በተጠቀሰዉ ጊዜ ከነበረዉ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ወደ ሀገር ቤት ለሚመለሱት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦ.ነ.ግ.) ከፍተኛ አመራሮች በአዲስ አበባ ከተማ በመስቀል አደባባይ ላይ በሚደረገዉ የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ላይ ለመካፈል በርካታ የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች እና ደጋፊዎች ወደ አዲስ አበባ ሲገቡ የነበረ መሆኑ ዐቃቤ ሕግ በክሱ በፍሬ ነገር ደረጃ ከገለጸዉ እና በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ተገንዝበናል፡፡ የአምባጓሮ ወንጀል የተፈጸመዉም በዚህ መልኩ ሥነ ሥርዓቱን ለመካፈል በወጡ ወጣቶች፣የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በሆኑ ወጣቶች እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት አካባቢ ነዋሪ በሆኑ የጋሞ ብሄር ተወላጆች መካከል እንደመሆኑ በተጠቀሰዉ ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘት ጎዳና ላይ ወይም አደባባይ ላይ የወጣ ሰዉ ሁሉ በአምባጓሮ ወንጀል ተሳትፏል ማለት አይቻልም፡፡በመሆኑም ተጠሪ ሥነ ሥርዓቱን ለመካፈል በወጡበት ጊዜ አምባጓሮ በፈጸሙ ሰዎች መካከል መገኘቱን ዐቃቤ ሕግ ያስረዳ ቢሆንም እንኳን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 577(1 እና 3) ስር እንደተመለከተዉ ተጠሪ በሰዉ ሕይወት ፣አካል፣ ጤንነት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ባስከተለዉ አምባጓሮ ወይም ጠብ ተከፋይ እንዳልነበረ በሕግ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የተሰጠዉ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ዐቃቤ ሕግ ተጠሪ ተካፋይ በሆነበት የእርስ በእርስ ግጭት በአንድ ሰዉ ላይ የግድያ ሙከራ ወንጀል ተፈጽሟል በሚል የከሰሰዉ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ይህ የግድያ ሙከራ የተፈጸመበት ሰዉና ባለቤቱ ከተጠሪ ጋር አንድ ላይ በተከሰሱ 29ኛ እና 32ኛ ተከሳሾች መከላከያ ምስክር ሆኖ በመቅረብ በሰጡት ምስክርነት ቃልም ሆነ ፣ሌሎች ንብረታቸዉ የወደመባቸዉ የግል ተበዳዮች አስቀድሞ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆነዉ በመቅረብ በሰጡት ምስክርነት ቃል ተጠሪም ሆነ ከሱ ጋር አንድ ላይ ወጣቶቹን ሲያስተባብሩ ነበሩ የተባሉት 29ኛ እና 32ኛ ተከሳሾች በጠቡ ተካፋይ የነበሩ ስለመሆኑ ካለማስረዳታቸዉም በተጨማሪ ተጠሪ የግድያ ሙከራ ወንጀሉን ፈጸሙ ከተባሉ ወጣቶች ጋር በሕብረት መፈጸሙን ወይም ድርጊቱን በሌሎች ሰዎች ማስፈጸሙን አለማስረዳታቸዉን ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ አረጋግጧል፡፡ በዚህ መልኩ ማስረጃዎችን ሲመዝን የማስረጃ ምዘና መርሆዎችን በአግባቡ ተግባራዊ ሳያደርገም የሚያስብል መሰረታዊ ስህተት አልተገኘም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ማስረጃዎችን መዝኖ የደረሰበትን ድምዳሜ ይህ ችሎት የሚቀበለዉ በመሆኑ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታና ጊዜ ተጠሪ በሕብረቱ ዉስጥ የነበረ መሆኑ ቢረጋገጥም የጋሞ ብሄር ተወላጅ በሆኑት የግል ተበዳይ ታምራት ጠርዞ ዋልኬ ላይ የግድያ ሙከራ ሲደርስባቸዉም ሆነ ንብረትነቱ የአቶ ግዛቸዉ አሰፋ እና የወ/ሮ ዙሪያሽ ወርቅ ደገፋ

የሆነዉን ፊኔት ግሮሰሪ እንዲወድም ሲደረግ እንዲሁም የአቶ ቸርነት እሼቱን እና የሌሎችንም የጋሞ ብሔረሰብ ተወላጆች ንብረት እንዲወድም ምክንያት በሆነዉ አምባጓሮ ወይም ጠብ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል ተካፋይነት ወይም በሁለተኛ ደረጃ ዋና ወንጀል ተካፋይነት ሀሳብ በድርጊቱ ተካፋይ እንዳልሆነ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ ጭምር ማስረዳቱን ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ በማረጋገጥ ተጠሪ በነጻ እንዲሰናበት በሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት አልተፈጸመም ብለናል፡፡ በተጨማሪም በክስ 2 ላይ እንደተጠቀሰዉ የግል ተበዳይ ታምራት ጠርዞን በመደብደብ የሙከራ ወንጀል የፈጸሙት በወቅቱ በጠቡ ዉስጥ ወይም እንደዐቃቤ ሕግ ክስ ደግሞ እርስ በእርስ ግጭቱ ዉስጥ ተካፍለዉ የነበሩ ማንነታቸዉ ተለይቶ ሊታወቅ ያልቻለ ወጣቶች እና የስር ተከሳሾች እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ልዩ ኃይል ፖሊስ ዥንጉርጉር ደንብ ልብስ የለበሱ ሰዎች መሆናቸዉ ተረጋግጧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በሁለተኛ ክስ ላይ የተጠቀሰዉን ወንጀል ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 35 ስር በተደነገገዉ መሰረት በሕብረት ተካፋይ ሆነዉ የፈጸሙት ነዉ በሚል የወንጀል ሕጉን አንቀጽ ጠቅሶ አልከሰሳቸዉም፡፡ ይልቁንም የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32(1/ሀ)ን ጠቅሶ የመረመረዉ ክስ እስከሆነ ድረስ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰዉን የወንጀል ድርጊት በዋና ወንጀል አድራጊነት መፈጸማቸዉን ማስረዳት ይኖርበታል፡፡

ነገር ግን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ክሱን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 577/4 እና 539(1/ሀ) ስር ይከላከል ብሎ ብይን በመስጠቱ እና የግድያ ሙከራ ወንጀሉም የተፈጸመዉ በሕብረት በተፈጸመ የአምባጓሮ ወንጀል ወይም በክሱ ላይ እንደተገለጸዉ በተነሳሳ የእርስ በርስ ግጭት ዉስጥ በመሆኑ በክሱ ላይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 35 አለመጠቀሱ ስህተት ቢሆንም ተጠሪ ድርጊቱን በሕብረት ከፈጸሙ ሰዎች መካከል መገኘታቸዉን ዐቃቤ ሕግ ካስረዳ ተጠሪ በቦታዉ አለመገኘቱን ወይም ወንጀሉን ለመፈጸም አስቦ በቦታዉ አለመገኘቱን እና የወንጀል ድርጊቱን አለመፈጸሙን በማስረዳት የማስተባበል ኃላፊነት የተጠሪ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማስረጃዎችን መዝኖ የግል ተበዳይ በተጠሪ አለመደብደባቸዉን ወይም ተጠሪ የግል ተበዳዩን አለማስደብደቡን አረጋግጧል፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማስረጃዎችን በመመዘን በደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል ስህተት አልተገኘም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎን ጥፋተኛ ባደረገበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1፣32(1/ሀ)፣ 577/4 እና 539(1/ሀ) መሰረት ጥፋተኛ ሊሆን የሚችለው በዋና ወንጀል አድራጊነት በራሱ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር በግል ተበዳይ ላይ ከባድ የግድያ ሙከራ ወንጀል መፈጸሙ ሲታወቅ እና ይሄዉ በማስረጃ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ሆኖም ተጠሪ የተከሰሰበትን የግድያ ሙከራ ወንጀል በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር አለመፈጸሙን ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ አረጋግጦ ተጠሪ በነጻ እንዲሰናበት በመወሰኑ እና የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በመሻሩ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም ብለናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተመሳሳይ ከተጠሪ ጋር በስር ፍርድ ቤት አንድ ላይ የተከሰሱ ስር 29ኛ እና 32ኛ ተከሳሾች ለዚህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 228017 ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተወሰነውን በማጽናት በዚህ ችሎት የተወሰነ በመሆኑ በዚህ መዝገብ የቀረበው ሰበር አቤቱታ ተመሳሳይ ይዘት ያለው መሆኑን ተመልክተናል በዚሁ መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 213064 ላይ በቀን 04/11/2014 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

የዉሳኔዉ ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎትና ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## 2.3 ወንጀልን የሚያቋቁሙ ፍሬነገሮች (ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር)[10]

- ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር ድርጊት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 436/ሐ/ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችለው ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ወይም ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ በጠቅላላው የሌለውን ወይም በህጉ መሠረት ሊሰራበት የማይችለውን መብት የተጠቀመበት እንደሆነ ነው፡፡
- በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁምበት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ[11]

የሰ/መ/ቁ. 38161

የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች ፡-** እነ ጀሚላ መሐመድ ሀጉስ - ጠበቃ እሸቴ ጓንጉል ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** የፌዴራል የመ/ደ/ዓ/ቃህ - ፋሲል ገብሬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

---

[10] የሰ/መ/ቁ. 38161 (የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9

[11] የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014 ዓ.ም)፣ ሕጋዊነት መርህ እና ወንጀልን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች በሚል ርዕስ ስር የተዘረዘሩት የሰበር አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎች ከዚህ ጋር ተያያዥ መሆናቸው ይመልከቱ፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ መዝገብ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል በማለት ግንባት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው ስላቀረቡ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ የመሠረተው ክስ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ዘርፌ ጥላሁን በአቶ መሐመድ ሐጐስ ቤት በቤት ሰራተኛነት ሲሰሩ ከቆዩ በኂላ ግለሰቡ በ1990 ዓ.ም ወደ ኤርትራ ሲባረሩ ቤታቸውን በኃላፊነት እየጠበቁ እንዳለ ሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም አመልካቾች የግል ተበዳይን እቃ ከቤት አውጥተው ግቢ ውስጥ በማስቀመጥ በግብረአበርነት በፈፀሙት ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን የማስከበር ወንጀል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1ሀ/ እና 436/1/ሀ/ መሠረት ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል የሚል ሲሆን አመልካቾችም የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን ጥፋተኛ አይደለንም ሲሉ አስመዝግበዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የዓ/ህግን ማስረጃዎች ከሰማ በኂላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ሰጥቶ የአመልካቾችን የሰው እና የጽሑፍ ማስረጃዎችን በመስማት ጉዳዩን በመመርመር የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎች የዓ/ህጉን ማስረጃዎችን ለማስተባበል በቂ አይደሉም የሚል ምክንያት ይዞ አመልካቾችን በዓ/ህግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጐ እያንዳንዳቸውን በብር 800.00 /ስምንት መቶ/ የገንዘበ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኂላም አመልካቾች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ አመልካቾች ጥፋተኛ መባላቸው ባግባቡ መሆኑን በመግለጽ ድርጊታቸው የሚሸፈንበትን ድንጋጌ ብቻ በማሻሻል ቅጣቱንም በማጽናት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን የጥፋተኛነት ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሰጠበትን አንቀጽ የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦችን የሚያሟላ የወንጀል ሓላፊነትን የሚያስከትል መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታዩ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ የአመልካቾች ድርጊት ወንጀሉን የሚያቋቁም መሆኑንና ጥፋተኛ መባላቸውም ባግባቡ መሆኑን ጥቅምት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ዘርዝሮ የጥፋተኛነት ውሣኔው ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘበ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም አመልካቾች ፈፀሙ የተባለው ድርጊት የወንጀል ድርጊት ያቋቁማል ወይም አያቋቁምም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡ አመልካቾች የተከሰሱትና በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1ሀ/ እና 436/1/ ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል በሚል ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች የተሰጠውን የጥፋተኛነት ውሣኔ አንቀፁን በመለወጥ አጽንቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካቾችን ጥፋተኛ ያደረጋቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 436/ሐ/ ስር ነው፡፡ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር ድርጊት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 436/ሐ/ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችለው ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ወይም ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ በጠቅላላው የሌለውን ወይም በህጉ መሠረት ሊሰራበት የማይችለውን መብት የተጠቀመበት እንደሆነ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የግል ተበዳይ ወ/ሮ ዘርፌ ጥላሁን ቤቱን እንዲለቁ ሲያደርጉ የግል ተበዳይዋ ቤቱን የያዙት በጠባቂነት በነበራቸው ኃላፊነት ስለመሆኑ 1ኛ አመልካች ደግሞ የቤቱ ባለቤት የተባሉት ግለሰብ የአቶ መሐመድ ሐጐስ ልጅ 2ኛ አመልካች ደግሞ ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው ላይ የተገኙት ከ1ኛ አመልካች በተሰጣቸው ውክልና መሠረት ስለመሆኑ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በመሆኑም 1ኛ አመልካች በቤቱ ላይ በጠቅላላው መብት የሌላቸው ወይም በህጉ መሠረት ሊሰሩበት በማይችሉት መብት የተጠቀሙ ሳይሆን በቤቱ ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 23/2/ ስር አስቀምጧል እጃችን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካቾች ድርጊት የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የህግ ድንጋጌ የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች የተሟሉበት አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23/2/ እና 436/ሐ/ ስር የተመለከቱትን የህጉን መስፈርቶች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት መ/ቁ. 35370 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ. 64237 መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠ ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ሐ/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ፈጽመውታል የተባለው ድርጊት የወንጀል ባህርይ የለውም ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>3. የወንጀል አፈፃፀም ደረጃ</u>

### <u>3.1.የሙከራ ወንጀል[12]</u>

- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27 እንደተደነገገው ማንም ሰው አስቦ ወንጀሉን ማድረግ ጀምሮ የወንጀሉን ድርጊት እስከመጨረሻው ባይከታተልም ወይም ለመከታተል ባይቻልም የወንጀል ድርጊቱ እንዲፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትሎ አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላስገኘ ቢሆንም የሙከራ ወንጀሉን እንደፈፀመ እንደሚያስቀጥረው ተመልክቷል፡፡
- ከድርጊቱ በፊት ተከሳሾች ሁልጊዜ የዘረፋ ወንጀል በሚፈፀምበት ጫካ መግባታቸው፤ ይህን በተመለከተ በሰው ጥቆማ አማካኝነት በፀጥታ ኃይሎች በተደረገው ክትትል ተሳፍረውበት ከነበረው መኪና ከጦር መሣሪያ፣ ጩቤና ጭንብል ጋር መያዛቸው፤ እንዲሁም በእራሳቸው የእምነት ቃል እንደተረጋገጠው ለዘረፋ ወንጀል አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አጠናቀው ከዚሁ ጫካ ውስጥ ሲጠባበቁ አድረው በማግስቱ በመኪና ተሳፍረው ሲሄዱ ለዘረፋ ተግባር ሲሉ ከያዙት ቁሳቁስ ጋር መያዛቸው ሁሉ ሲታይ አመልካችና ግብረ-አበሮቹ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትለው ነገር ግን የሚዘረፍ ነገር ባለማግኘታቸው ውጤቱን ያላገኙ ቢሆንም ጥፋተኛ የሚያደርግ ስለመሆኑ፤[13]

---

[12]የሰ/መ/ቁ 66856 (መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም ) ቅፅ 13

[13]በሰ/መ/ቁ 230945 (ጥር 30 ቀን 2015 ዓ/ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 90089 (ጥቅምት 20 ቀን 2006 ዓ.ም)ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ 63727 (ሰኔ 13/2003) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014

የሰ/መ/ቁጥር -66856

መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች- ውድማ አበጀ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ዐ/ሕግ አልቀረበም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአንድ የወንጀል አፈፃፀም ተግባር በሙከራ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚባለው መቼ፤ እንዴት ነው? የሚለውን ነጥብ በዚህ የወንጀል ጉዳይ በማስረጃ ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮች ጋር በማናገዝብ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ በክልሉ የጉራጌ ዞን ዐ/ሕግ በአሁኑ አመልካችና በግብረ-አበሮቹ ላይ ሦስቱም ተከሳሾች በወ/ህ/ቁ 32/1/ /ሀ/ 27/1/ እና 671/1/ለ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በጅማ ወለኔ ቀበሌ የሚመላለሱትን ተሽከርካሪዎች ለመዝረፍ የጦር መሣሪያ፣ ጭንብል፣ የእጅ ባትሪ፣ ጩቤ በመያዝ ከመጋቢት 07 ቀን እስከ መጋቢት 08 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ተንቀሳቅሰው ጠብቀው ተሽከርካሪ በማጣታቸው ሲመለሱ በተደረገው ጥቆማ መነሻ በፀጥታ ኃይሎች ስለተያዙ በፈፀሙት ከባድ የውንብድና ሙከራ ወንጀል ተከስዋል በማለት ያቀረበው ክስ ሲሆን፤ የአሁን አመልካች በተከሳሽነቱ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡

በማስረጃነትም የሰው ማስረጃና ተከሳሾች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 27 እና 35 መሠረት በምርመራ ጊዜ ለመርማሪ ፖሊስ እና በፍ/ቤት የሰጡት ቃል ቀርቧል፡፡ በሰው ማስረጃው የተረጋገጠው መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ከአንድ የመኪና አሽከርካሪ ሽፍቶች ለመዝረፍ ተሰማርተዋል የሚል ጥቆማ አግኝቼ ወዲያውኑ ስከታተል ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ተሽከርካሪ በማስቆም በተደረገው ጥብቅ ክትትል እነዚህ ሦስት ሰዎች መታወቂያ ሲጠየቁ የላቸውም፡፡ በግንባታ ሥራ ተሰማርተን የግንባታ ቁሳቁስ እጥረት ስለአጋጠመ ወደ መኖሪያችን እየሄድን ነው አሉ፡፡ ዕቃቸው ሲፈተሽ ግን አንድ የጦር መሣሪያ፣ ጩቤ፣ ጭንብል ተገኝቶባቸዋል የሚል ነው፡፡ እንዲሁም በምርመራ ጊዜ በሰጡት የእምነት ቃልም ለዘረፋ ተስማምተው አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አድርገው ያመቸናል ብለው ወደ አሰቡበት ቦታ በመሄድ ጫካ ውስጥ ከአደሩ በኋላ ባገኙት መኪና ተሳፍረው ሲመለሱ ከያዙት የዘረፋ ቁሳቁስ ጋር በፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋላቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ የዐ/ሕግ ማስረጃ እና ተከሳሾች እንከላከላለን ሲሉ ያቀረቡትን ማስረጃ በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ እንደ ክሱ አቀራረብ ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኋላ ከሦስተኛው ተከሳሽበ በስተቀር በአሁን አመልካችና ሁለተኛ ተከሳሽ በነበረው ሌላ ግብረአበር ላይ የቀረበውን የወንጀል ጥፋተኝነት እና ቅጣት ሪከርድ መነሻ በማድረግ በአሁን አመልካች ላይ የ22 ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት ጥሏል፡፡

---

ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 60345 (ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ የሰ/መ/ቁ 119500 (ሐምሌ 22 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 20፣ የሰ/መ/ቁ 127505 (መስከረም 25 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22

ከዚህም ቀደም ብለው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተባለበት ፅኑ እስራት የ10 ዓመቱን በእስር ሊጨርስ በሚል በአመክሮ መለቀቁን መነሻ በማድረግ የተጣለ ቅጣት እንደሆነ የውሳኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ በየደረጃው ላሉ የበላይ ፍ/ቤቶች እንዲታረም ቅሬታ ቢያቀርብም ቅሬታው ውድቅ በመደረጉ ለመጨረሻ ጊዜ ጉዳዩን በዚህ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡

በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ክርክር ያደረጉበት ነጥብ ይህ አመልካች እና ሌሎች ግብረ-አበሮች የፈፀሙት ተግባር በሙከራ ወንጀል ሥር ሊወድቅ የሚችል ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ላይ ነው፡፡ እኛም በዚሁ ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ቅሬታ ከሥር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በ1997 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27 እንደተደነገገው ማንም ሰው አስቦ ወንጀሉን ማድረግ ጀምሮ የወንጀሉን ድርጊት እስከመጨረሻው ባይከታተልም ወይም ለመከታተል ባይችልም የወንጀል ድርጊቱ እንዲፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትሎ አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላስገኘ ቢሆንም የሙከራ ወንጀሉን እንደፈፀመ እንደሚያስቆጥረው ተመልክቷል፡፡

በዚህም ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው ከድርጊቱ በፊት ተከሳሾች ሁልጊዜ የዘረፋ ወንጀል በሚፈፀምበት ጫካ መግባታቸው፤ ይህን በተመለከተ በሰው ጥቆማ አማካኝነት በፀጥታ ኃይሎች በተደረገው ክትትል ተሳፍረውበት ከነበረው መኪና ከጦር መሣሪያ፣ ጩቤና ጭንብል ጋር መያዛቸው፤ እንዲሁም በእራሳቸው የእምነት ቃል እንደተረጋገጠው ለዘረፋ ወንጀል አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አጠናቀው ከዚሁ ጫካ ውስጥ ሲጠባበቁ አድረው በማግስቱ በመኪና ተሳፍረው ሲሄዱ ለዘረፋ ተግባር ሲሉ ከያዙት ቁሳቁስ ጋር መያዛቸው ሁሉ ሲታይ አመልካችና ግብረ-አበሮቹ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትለው ነገር ግን የሚዘረፍ ነገር ባለማግኘታቸው ውጤቱን ያላገኙ መሆኑን አስረጂ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በአመልካችና በግብረ- አበሮቹ በኩል የተፈፀመው ተግባር በእራሱ የዘረፋ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደ ኋላ ከማይመለሱበት ደረጃ ደርሰው የነበረ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቱ ይህንን ሁሉ በማገናዘብ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ አመልካች ተላልፎታል ተብሎ በተጠቀሰው ሕግ አነጋገር መሠረት ሆኖ የተገኘ እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 33619 በቀን 12/06/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2//ለ//2/ መሠረት ፀንቷል::
2. አመልካች ይህንኑ እንዲያውቀዉ ውጤቱ ባለበት ማ/ቤት ይገለፅለት:: መዝገቡ ተዘግቷል::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

## ክፍል አራት

## 4.በወንጀል አፈፃፀም ላይ ተካፋይ መሆን[14]

### 4.1 በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ መሆን[15]

- ማንኛዉም ሰዉ በሁለተኛ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ ሆኗል ሊባል የሚችለዉ በቀጥታ ወንጀል ድርጊቱን በራሱ ባይፈጽምም በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ወንጀሉን የሚፈጽመዉን ሰዉ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ወይም ወንጀሉ

[14]ለዚህ ህግ ትርጉም የተያያዘው ሰበር ውሳኔ ከወንጀል ተካፋይነት ደረጃ በተጨማሪ ስለማስረጃ ምዘና መርህን አስመልክቶ በቂ እና አሳማኝ የሚል የማስረዳት ሸክም እና የማስረጃ ምዘና መርህን አስቀምጧል፡፡

[15]የሰ/መ/ቁ 247535 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም)

በሚፈጸምበት ሂደትና ጊዜ በመጎትጎት ፣ወሬ በማቀበል፣ በመምክር፣ ወንጀል የሚደረግበትን ዘዴ ወይም ገንዘብ፣ መሳሪያ ወይም ግዙፋዊ እርዳታ ወይም ስጦታ በመስጠት ወይም ለወንጀሉ አፈጻጸም በሚጠቅም በማናቸዉም ሌላ አይነት መንገድ ወይም ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲደረግ በማነሳሳት፤በማግባባት ወይም በማበረታታት የተሳተፈ እንደሆነ ስለመሆኑ፤[16]

- ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነውን ፖሊስ አባል ሚች ሲሮጥ በለው በማለት በማነሳሳቱ ምክንያት ስር 2ኛ ተከሳሽ ሚችን ተኩሶ ሊገድል ችሏል በሚል የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 247535

ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- አቶ አፈንዲ መሐመድ አሊዪ ጠበቃ መታሰቢያ ኃይልዬ

ተጠሪ፡- የሐረር ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

**መዝገቡ መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 21652፤ አመልካች የግድያ ወንጀሉ እንዲፈፀም በማነሳሳት ወንጀል ተሳትፈሀል በማለት ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ጥፋተኛ በማለት፤ ሚያዝያ 17 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ይግባኝ ያለባቸው በመ.ቁ 06073፤ 06098 እና 06104 መዝገቦች በማጣመር ህዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት በመ.ቁ 00510፤ የካቲት 21 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ተጠሪ የአሁኑ አመልካች ስር 1ኛ ተከሳሽ፤ በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ አብዱልሀፊዝ ሰቡር የተባለ የፖሊስ አባል 2ኛ ተከሳሽ በማድረግ በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) (ለ)፤ 33፤ 36 እና 540 ድንጋጌን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም ከጠዋቱ 5፡00 ሰአት አከባቢ በሐረር ሕ/ክ/መንግስት ድሬ ጠያራ ወረዳ ሲጊቻ ቀ/ገ/ማህበር በልዩ ቦታው ድሬ ጠፎ እየተባለ በሚጠራው ስፈር የአሁኑ አመልካች) ስር 1ኛ ተከሳሽ ስር 2ኛ ተከሳሽ የነበረውን የፖሊስ አባል ሚች ከድር ዩንስ የተባለውን በጥይት መቶ እንዲገድለው በማነሳሳት ስር 2ኛ ተከሳሽም ሚች ከዲር ዮንስን በቀጥታ ደረቱ ላይ በመተኮስ በመግደሉ በፈጸሙት በተራ የሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል

[16]በሰ/መ/ቁ 228017 (ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 164030 (ህዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ 44031 (ነሃሴ 30 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9

ሲሆን በተጨማሪም በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ 113 መሰረት በወ/ህ/ቁ 541 መሰረት በአማራጭ ክስም ቀርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኂላ ሟቹ የኔን ባጃጅ በመሰባበር በንብረቴ ላይ ጉዳት በማድረሱ ለፖሊስ አመልካቹ ፖሊስ ተመድቦልኝ ጉዳት አድራሹን ለማሳየትና ለመያዝ ሲባል ከፖሊሶች ጋር ሄድኩኝ እንጂ ይህ ወንጀል እንዲፈፀም ያደረግኩት ተሳትፎ የሌለ በመሆኑ የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛም አደለሁም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ከሰማ በኂላ በተመሰከረባቸው ልክ በወ/ህ/ቁ 540 ስር እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የራስ ተከሳሽነት ቃላቸውና መከላከያ ምስክር አስቀርበው አሰምተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኂላ የአሁኑ አመልካች ስር 2ኛ ተከሳሽን ሟች ከድር የኑስ የተባለውን ይሔ ነው በሚል በመጠቆም ተከተለው በለው ሲለው ሟች ሲሮጥ ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነው የፖሊስ አባልም ሟችን ተከታትሎ ተኩሶ ሲመታው ሟቹ ሲወድቅ በወደቀበት ቦታ ለሁለተኛ ጊዜ በስተግራ በኩል ደረቱ ላይ በመተኮስ ሟች ከድር የኑስ የገደለው መሆኑን በተጠሪ በኩል ቀርበው በተሰሙት ቀጥተኛ የአይን ምስክሮች የተመሰከረበት ሲሆን ይህም አመልካች ስር 2ኛ ተከሳሽ ሟችን ተኩሶ እንዲገድል በለው በማለት በማነሳሳቱ ወንጀል ህግ አንቀጽ 36 መሰረት በማነሳሳት የወንጀል ተሳትፎ የነበረው መሆኑን የተመሰከረ ሲሆን የአመልካች መከላከያ ምስክሮች ተጠሪ በሆነው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ቀጥተኛ የዓይን ማስረጃ ማስተባበል የሚችል አይደለም በማለት አመልካች በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ በማለት በሰባት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘታቸው ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመ/ቁ 06073፣06098፣06104 ላይ በቀን 12/03/2015 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠው አመልካች መኪና ከሌላ ሰው ተቀበሎ ከፍ/ቤት ወይም ከፖሊስ ህጋዊ መጥሪያ ወይም የመያዣ ትዕዛዝ ሳይኖር ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነው የፖሊስ አባል ሟች በነበረበት ቦታ ወስዶ እሄ ነው በለው በማለት ድርጊቱን እንዲፈፅም ያሳመነ መሆኑን ነው ይህም አመልካች ተራ የሰው ግድያ ወንጀል እንዲፈፀም በማነሳሳት የወንጀል ተሳትፎ ማድረጉ የሚያሳይ በመሆኑ በወ/ህግ /ቁ 36(1) መሰረት አመልካች በተሰሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነው በማለት ቅጣትን በተመለከተ ሲወስን ስር 2ኛ ተከሳሽ መቀጣት የነበረባቸው በእርከን 28 ስር ሆኖ በዘጠኝ አመት ጽኑ እስራት ሆኖ እያለ ሰባት አመት ጽኑ እስራት መወሰኑ ተገቢ አይደለም በመሆኑም በዘጠኝ አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን የአሁኑ አመልካች በሚመለከት ግን ጥፋተኛ የተባለው ወንጀሉን እንዲፈጸም አነሳስተዋል በሚል የወ/ህግ/ቁ 36 መሰረት በማድረግ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም አንጻር ሲታይ ስር 2ኛ ተከሳሽ በተኮሰው ጥይት ሟች በመጀመሪያ ተመቶ ሲወድቅ ሟች በወደቀበት ቦታ ለሁለተኛ ጊዜ በደረቱ ላይ የተኮሰበት ሲሆን ለ2ኛ ጊዜ ተኩሶ ሟችን መግደሉ በአመልካች የተፈለገ ውጤት መሆኑን የሚያጠራጥር ሆኖ ስላገኘነው በወ/ህ/ቁ 36(3-4) እና 179(ሐ) መሰረት የአመልካች ቅጣት መሻሻል ያለበት በመሆኑ በዚህ መሰረት አመልካች ለወደፊት ሊያስተምር ይችላል ብለን ያሰብናውን በወ/መ/ህግ 36(3-4) እና 179(ሐ) መሰረት የ7 ዓመት እስራት ሊቀጣ ይገባል በማለት በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ቅጣት ውሳኔ ስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ የተወሰነውን ቅጣት ብቻ ከፍ በማድረግ በዚህ አግባብ ውሳኔውን በማሻሻል በመ/ቁ 06073፤06398፤06104 የሆኑ መዝገቦች በማጣመር ወስኗል፡፡

በመቀጠል አመልካች መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በሰ/መ/ቁ 00510 በቀን 21/06/2015 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀን 21/09/2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ይዘቱ ሲታይ፡- ሟቹ የኔን ባጀጅ በመሰባበር በንብረቴ ላይ ጉዳት ያደረሰብኝ በመሆኑ ምክንያት ለፖሊስ አካላት

አመልክቼ ፖሊስ ታዞልኝና የመያዣ ትዕዛዝ ይዘው ጉዳት አድርሹን ለመያዝ ወይም ለመጠቆም ሲባል ከፖሊሶች ጋር ሔድኩኝ እንጅ ይህ ወንጀል እንዲፈፀም ያደረኩት አንዳችም ማነሳሳትም ሆነ የሰጠሁትም ተስፋ የለም፡፡ በማናቸውም በድንጋጌው ላይ የተቀመጠውን ሁኔታዎች ባመላከተ ሁኔታ የፈፀምኩት ነገር የለም፡፡ በተጠሪ በኩል ቀርበው በተሰሙት ምስክሮችም አመልካች የወ/ህግ አንቀፅ 36 ስር ስለተገለጹት ሁኔታዎች ስለመፈፀሜ ባልመሰከሩበት ሁኔታ ጥፋተኛ መባሌ ተገቢ አይደለም፤አመልካች ፖሊስም አይደለሁም፡፡ የፖሊስ አዛዥም አይደለሁም፤ አመልካች ፖሊስን በለው ስላለው ነው ፖሊስ ተኩሶ የመታው መባሉ መሰረታዊ ስህተት ነው፡፡ እንዲሁም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመከላከያ ማስረጃ አቅርቤ ያስመሰከርኩና በአግባቡ የተከላከልኩ ሆኖ እያለ የዐ/ህግ ምስክሮችም ሆነ የሰነድ ማስረጃዎች ስለ አመልካች ጥፋት/ድርጊት ያሉት ነገር በሌለበት ሁኔታ ጥፋተኛ መባሌ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡ ጥፋተኛ ነህ ብባል እንኳ በወ/ህግ 540 መሰረት የፈፀምኩት ግድያ ተግባር ወይም ድርጊት በሌለበት ሁኔታ በግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ልባል አይገባም፡፡ በመሆኑም በነፃ እንድሰናበት ይወሰንልኝ፤ ጥፋተኛ ነክ የምባል ከሆነ ደግሞ ቅጣቱ ቀሎልኝ በገደብ እንዲሆንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ እና በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመመርመር አመልካች የወ/ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)፤ 33፤ 36(ሀ) እና 540 በመተላለፍ ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነውን የፖሊስ አባል የግድያ ወንጀል እንዲፈጸም አነሳስቷል በሚል ጥፋተኛ ተብሎ በሰባት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ የመወሰኑን አግባብነት የወንጀሉ አፈፃፀም፤ በአመልካች ተነሳስቶ ግድያ ወንጀል ፈፀመ የተባለው ስር 2ኛ ተከሳሽ ፖሊስ መሆኑ ካለው የስራ ኃላፊነት አንጻር የወንጀል ህጉ አንቀፅ 36 አተገባበር ረገድ የሚኖረው ውጤት እንዲሁም ወ/ህግ/ አንቀጽ 2፤ 23/2 ድንጋጌዎችና በሰ/መ/ቁ 38161፤ 91535፤75387 ከተሰጡት ውሳኔዎች አንጻር ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ሲባል በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4) (ሸ) እና 10 /1(ሐ) እንዲሁም በሰበር ሰሚ ስነ-ስርዓት መመሪያ ቁጥር 12/2015 ዓ.ም አንቀፅ 7/3 መሰረት ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት አዟል፡፡

ተጠሪም በቀን 29/-8/2016 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ በመልሱም የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃ በአግባቡ መዝኖ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለው በመሆኑ ምንም አይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም፡፡ የወንጀል አፈጻጸሙ ሲታይ ፖሊስ ካለው የስራ ሃላፊነት አንጻር ምንም ህጋዊ መጥሪያና የመያዣ ትዕዛዝ በሌለበት በአንድ ተራ ሰው ያዝልኝ ምታልኝ ትዕዛዝ ወይም ስምምነት ድርጊቱን ፈጽሞ እያለ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ በማስረጃ ያላስደገፈ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶቹ በየደረጃው የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያለው ነው፡፡ በሌላ በኩል የዐ/ህግ ክስ የወ/ህግ አንቀጽ 23 ስር የተዘረዘረውን የሚያሟላና ግልፅ የሆነ ዐ/ህግ ክሱን በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ አግባብ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም በቀን 09/09/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀውን የሚመስል ሲሆን በዚህ ጉዳይ አንድ ግለሰብ ለፖሊስ ሟቹን በለው ሲለው ፖሊሱ ሟቹን ቢገድለው ግለሰቡ የፖሊስ አባሉ የግድያ ወንጀል እንዲፈጽም አነሳስተዋል ለማለት ይቻላል ወይ የሚለው ፖሊስ ካለው የስራ ሀላፊነት አንጻር የአመልካቹ ድርጊት የወንጀል ህጉ አንቀፅ 36 የተመለከተውን የማነሳሳት ተግባር ሊያሟላ የሚችል ነው ሊባል የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ህጉ አንቀፅ 23(2) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ህጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ህጋዊ ፍሬነገር የሚባለዉ አንድን ድርጊት ህገወጥነትና አስቀጭነት ወንጀል ስለመሆኑ በህግ በግልጽ ተደንግጎ መገኘት ያለበት ስለመሆኑ፣ግዙፋዊ የሚባለዉ በህጉ የተደነገዉ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ድርጊት ማለት በህግ

የተከለከለዉን ማድረግ ወይም በህግ የታዘዘዉን አለማድረግ /አል-ድርጊት/ ፍሬነገሮች መፈጸማቸዉና የተፈጸሙትም በተከሳሹ ስለመሆኑ መረጋገጥ እና የሞራል /ሀሳብ/ ክፍል የሚባለዉ ተከሳሹ ድርጊቱን አስቦ ወይም በቸልተኛነት የፈጸመ መሆኑ የማረጋገጥ ጉዳይ የሚመለከት ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 2፣ 23/1/ እና 57/1/ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሥገነዝቡን ጉዳይ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል በአንድ የወንጀል ድርጊት ላይ ከአንድ በላይ ተከሳሾች ተካፋይ የሆኑ እንደሆነ የእያንዳንዱ ተከሳሽ ተሳትፎ/የተካፋይነት/ ደረጃ ተለይቶ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 32 እስከ 41 ያሉት ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ተጠሪ አመልካች በክሱ በተጠቀሰዉ የወንጀል ድርጊት ስላለዉ ተካፋይነት ለመግለጽ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32(1/ሀ)፣ 33 እና 36(ለ) ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉን በመጥቀስ ክስ መስርቶበታል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች አንድ ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል አፈጻጸም ላይ ተካፋይ ሊሆን የሚችልባቸዉን የተካፋይነት አይነትና ደረጃ የሚደነግጉ ናቸዉ፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 እና ተከታዮቹ ላይ ከተመለከተዉ መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ የወንጀል ድርጊት በአንድ ሰዉ ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ(ብዙ) ሰዎች ተሳትፈዉበት ሊፈጸም ይችላል፡፡ በብዙ ሰዎች የተፈጸመ ወንጀል በሆነ ጊዜ የወንጀል ፈጻሚዎቹ ተሳትፎ ደረጃ አንድ አይነት ወይም የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ በወንጀሉ አፈጻጸም ያላቸዉ ተካፋይነት አንድ አይነት ነዉ ወይስ የተለያየ የሚለዉን ለመለየት የተከፋይነታቸዉን አይነት፣ ደረጃ እና በወንጀሉ አፈጻጸም የነበራቸዉን ሚና መለየት ይገባል፡፡ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 እና ተከታዮቹ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የወንጀል ድርጊቱን በቀጥታ(በራሱ) የፈጸመም ሆነ በራሱ ድርጊቱን ባይፈጽምም የወንጀል ድርጊቱንና የሚያስከትለዉን ዉጤት የራሱ በማድረግ በሀሳብ ወይም በሌላ ሁኔታ ተካፋይ የሆነ ሰዉ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ እንደሆነ እንደሚቆጠር በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል ፡፡

ማንም ሰዉ በአንቀጽ 32/1 ስር ከተደነገጉት ሁኔታዎች በአንዱ ዘዴ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን አድርጎ እንደሆነ ወይም ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ደርጊትና በሚሰጠዉ ዉጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ እንደሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ እንደሆነ እንደሚቆጠር በሌላ በኩል ማንኛዉም ሰዉ በሁለተኛ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ ሆኗል ሊባል የሚችለዉ በቀጥታ ወንጀል ድርጊቱን በራሱ ባይፈጽምም በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ወንጀሉን የሚፈጽመዉን ሰዉ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ወይም ወንጀሉ በሚፈጸምበት ሂደትና ጊዜ በመጎትጎት ፣ወሬ በማቀበል፣ በመምክር፣ ወንጀል የሚደረግበትን ዘዴ ወይም ገንዘብ፣ መሳሪያ ወይም ግዙፋዊ እርዳታ ወይም ስጦታ በመስጠት ወይም ለወንጀሉ አፈጻጸም በሚጠቅም በማናቸዉም ሌላ አይነት መንገድ ወይም ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲደረግ በማነሳሳት፤በማግባባት ወይም በማበረታታት የተሳተፈ እንደሆነ መሆኑን (የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 36 እና 37 ይመለከቷል) ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 228017 ላይ በዚህ አግባብ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥ ውሳኔ በተከሳሹ ነጻነት ወይም ሕይወት ላይ የሚሰጥ ውሳኔ በመሆኑ በአንድ የወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ በቂና አሣማኝ በሆነ ሁኔታ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙንና የወንጀል ድርጊቱን ፈፃሚ ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት ያለበት ስለመሆኑ እና ከሳሽ የሆነው አቃቤ ሕጉም ይህንኑ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ያለበት ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን ሊሰጥ የሚችለውም ዓቃቤ ሕግ ባቀረባቸው ማሥረጃዎች ተከሳሹ ወንጀል መፈፀሙን ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ያረጋገጡ ሆነው ባገኛቸው ጊዜ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) እና (4)፤ 57፤ 58(1) እና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዓቃቤ ሕግ ወንጀሉ በተከሳሽ የተፈጸመ ለመሆኑ ለማሥረዳት ባቀረበው በቂ እና አሣማኝ ማስረጃ እንደክሱ ያስረዳ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተከሳሽ ክሱን እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ባቀረባቸው

ማሥረጃዎች ክሱን ያላስተባበለ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149 መሠረት በተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እንደሚሰጥ በግልጽ በስነ ስርአት ህጉ ላይ ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተከሰሰበት የተራ ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የቻለው ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነውን ፖሊስ አባል ሚች ሲሮጥ በለው በማለት በማነሳሳቱ ምክንያት ስር 2ኛ ተከሳሽ ሚችን ተኩሶ ሊገድል ችሏል በሚል ነው፡፡

ማንም ሰው ወንጀል እንዲደረግ አነሳሳ የሚባለው አስቦ ሌላውን ሰው በመጎትጎት ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ፣ በስጦታ፣ በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲያደርግ ያግባባ እንደሆነ መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 36(1) የሚደነግግ ሲሆን ዋና ወንጀል አድራጊው ያደረገው ወንጀል፣ አነሳሹ ከፈለገው በላይ በሆነ ጊዜ አነሳሹ የሚቀጣው እርሱ በፈለገው ወይም ይሆናል ብሎ ሊገምተው በሚችለው ወንጀል ብቻ መሆኑን በወንጀል ህግ አንቀጽ 58(3)፤ ይህም የሚሆንበት ጊዜ ዋና ወንጀል አድራጊው ላደረገው ከባድ ወንጀል እርሱ ብቻ ሀላፊ ሆኖ ይቀጣል በማለት በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 4 ስር ተመልክቷል፡፡

አመልካች ሚች በንብረቴ ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነው የፖሊስ አባል ጋር በመሆን ሚችን ሲያፈላልጉ ሚችን ሲያገኘው የፖሊስ አባሉን ይሄውና በንብረቴ ላይ ጉዳት ያደረሰው ሰው በሚል በመጠቆም ሚችን ሊይዙት ሲሉ በመሮጡ አመልካች የፖሊስ አባል የሆነውን ስር 2ኛ ተከሳሽን ሚችን በለው ሲለው ሁለቴ በጥይት ተኩሶ ሚቹን ሊገድለው መቻሉን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ እዚህ ላይ አከራካሪው ነጥብ አመልካች ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነው ፖሊስ አባል ሚችን በለው ሲለው ፖሊስ አባሉ ሚችን ሁለቴ ተኩሶ መግደሉ አመልካች ለፖሊስ አባሉ ሚችን በለው ማለቱ እንደሚታወቀው ፖሊስ የዜጎችን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር ዘብ የቆመ፤ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው እንዴት በቁጥጥር ስር ማድረግ እንዳለበት ያውቃል ተብሎ የሚገመት ሰው፤ አመልካች ሚችን በለው በማለቱ የፖሊስ አባሉ ሚችን እንዲገድለው አነሳስቷል  ለማለት የማይቻልና አመልካች ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ቢያደርግ ወይም በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ ሐሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን ወንጀሉን የራሱ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የፖሊስ አባሉ ካለው የስራ ሀላፊነትና ህግን የማስከበር ትልቅ ሀላፊነት አንጻር አመልካች በለው ስላለ አንድን ሰው ተኩሶ ይገድላል ተብሎ የሚታሰብ ባለመሆኑ፤ ስር ተከሳሾቹ በአድራጎታቸው እና አድራጎታቸው በሚያመጣው ውጤት ላይ በተከሳሾች መካከል የሐሳብ መስማማት /meeting of minds/ የነበረ ስለመሆኑ አያሳይም ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች ተግባር በወንጀል ህጉ አንቀጽ 36 ስር በተደነገገው መሰረት ሚችን ለመግደል የማነሳሳት ተግባር ፈጽሟል ለማለት አይቻልም፡፡ እንዲሁም አመልካች አስቀድሞ ሚቹን ለመግደል በመላ ሐሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን የግድያ ወንጀሉን እንዲፈፀም በማነሳሳት ወንጀሉን የራሱ ያደረገ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ተራ የግድያ ወንጀል እንዲፈፀም አነሳስቷል በማለት በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባሉ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 36 አተገባበር አንጻር እንዲሁም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 2፤23/2፣57 እና 58 (3) ድንጋጌዎች የሚጥስና በመሆኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 2(4) እና 10/1(ሐ)እና(መ) ላይ ከተቀመጡት መመዘኛዎች አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ ያስተላለፉትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር አመልካች በነጻ እንዲሰናበት በማለት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1. በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 21652፣ ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም አመልካችን ጥፋተኛ በማለት፣ ሚያዝያ 17 ቀን 2014ዓ.ም በአመልካች ላይ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 06073፣ 06098 እና 06104 የሆኑ መዝገቦች በማጣመር አመልካችን በሚመለከት ህዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት አመልካችን በሚመለከት በመ.ቁ 00510፣ የካቲት 21 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል ክስ በነጻ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካች በነጻ የተሰናበተ መሆኑን አውቆ ከእስር እንዲፈታው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፣
- የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## 5.የወንጀል ኃላፊነት

### 5.1 በልዩ አዋቂ ስለሚረጋገጥ ኃላፊነት[17]

- ፍርድ ቤቱም የተከሳሹን ኃላፊነት በሚመለከት ተከሳሹን ፍጹም ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ የሚያደርገዉ ሁኔታ እንዳለ በክርክሩ ሂደት ጥርጣሬ ሲያድርበት ይህንን ሳያጣራ የጸና ፍርድ መስጠት ስለሚያዳግተዉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 130/3 በተደነገገዉ መንፈስ መሰረት በራሱ አነሳሽነት ተከሳሹን ፍጹም ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ ሊያደርገዉ የሚችል ሁኔታ መኖር አለመኖሩ እንዲመረመር ተገቢዉን ትእዛዝ ሰጥቶ ማጣራት ይኖርበታል፡፡
- በተከሳሹ ኃላፊነትን የሚመለከት ክርክር ሲቀርብ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ተከሳሹ በተከሰሰበት ጉዳይ ፍጹም ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ጥርጣሬ ሲያድርበት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 51/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት ልዩ ዕዉቀት ያለዉን የአዋቂ ሀሳብ መጠየቅ አለበት፡፡
- በተለይ ተከሳሹ የአእምሮ በሽታ ያለበት ለመሆኑ የሚያመላክቱ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ ልዩ ዕዉቀት ያለዉን የአዋቂ ሰዉ አሳብ መጠየቅ እንዳለበት በፍርድ ቤቱ ላይ በሕጉ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡
- የምርመራ ዉጤቱ በትክክል ሳይጠና የቀረበ ከሆነም በድጋሚ እንዲጠና ትእዛዝ ተሰጥቶ በትክክል ተጠንቶ እንዲቀርብ ይደረጋል እንጂ የምርመራ ዉጤቱ የተደረሰበትን ድምዳሜ ወደ ጎን በመተዉ በህክምና ሳይንስ ረገድ ድምዳሜ

---

[17]የሰ/መ/ቁ 225975 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)

ሊደረስበት በሚገባ ፍሬ ነገር ላይ በዘርፉ ባለሙያ ያልሆኑ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ቃል ጋር በማገናዘብ ለህክምና ምርመራ ዉጤቱ ተገቢዉ ዋጋ ሳይሰጥ በፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ዉሳኔ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 51/3 ስር የተደነገገዉን ጠቅላላ መርህ የሚጥስ ስለመሆኑ፤

የሰ/መ/ቁ 225975

የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች ፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች ፡- በፍትሕ ሚኒስቴር - የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ- ዐ/ህግ ማርሻ ቢያንስ

ተጠሪ፡- ምንተስኖት ዘለቀ ደፋሩ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ኃላፊነት የሚመለከተዉን የወንጀል ሕጉን ድንጋጌ አፈጻጸም የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ የወንጀል ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በቀን 20/08/2010ዓ/ም በግምት 4፡00 ሰዓት ሲሆን አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ፒያሳ ሼል ጀርባ ልዩ ቦታዉ አሃዱ ባር ዉስጥ ይዝናና የነበረዉን ኤርሚያስ ሰይፉን ያለምንም ምክንያት በሽንኩርት ቢላዋ ደረቱ ላይ በመዉጋት ከቦታዉ የተሰወረ ሲሆን ሟች ብዙ ደም ፈሶት ደረቱ ላይ በደረሰበት መወጋት የተነሳ ህይወቱ በማለፉ ተከሳሽ ተራ በሆነ የሰዉ ግድያ ወንጀል ተከሷል የሚል ክስ መስርቶበታል፡፡

ተጠሪ በክሱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ ፍርድ ቤቱን ዉድቅ አድርጎ ከወሰነ በኋላ የእምነት ክህደት ቃሉን ተጠይቆ ድርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡በመቀጠል ዐቃቤ ሕግ ምስክሮቹን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ምስክሮቹም፡- 1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተጠሪ ሟች ኤርሚያስ ዘዉዱን ደረቱ ላይ አንድ ጊዜ ወግቶት የሮጠ መሆኑን ሟች በጊዜዉ ምስክሩ ፊት ለፊት ተቀምጦ የነበረ መሆኑን እና ደንግጠዉ እንደነበረ ተጠሪን ለመያዝ ተከትሎ የነበረ መሆኑን፤ቤተልሄም ወይኔ ኤርሚያስ ብላ ስትጮህ ተመልሶ ሆስፒታል የወሰዱት መሆኑን ሆስፒታል ሲደርሱ መሞቱ እንደተነገራቸዉ አስረድተዋል፡፡ 2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ የነበሩ መሆኑን ገልጸዉ ጩኸት ሲጮህ እና ተጠሪ ሮጦ ወደ ዶሮ ማነቂያ መሄዱን ማየቱን፤ቤተልሄም ስትጮህ መዞሩን ሲዞርም ምንተስኖት ሲሮጥ እና ሟች ደም ሲፈሰዉ ያየ መሆኑን አስረድቷል፡፡3ኛ ምስክር ተከሳሽ ቀደም ብሎ ብርጭቆ ይሰብር እንደነበር ለምን ትሰብራለህ ብሎ ተናግሮት እንደወጣ እና ሌላ ቦታ እንደሄደ ሲመለስም ጓደኛዉ ብርጭቆ ሲሰብር የነበረዉ ልጅ ኤርሚያስ እንደወጋዉ እንደነገረዉ በኋላም ተጠሪ የወንጀል አፈጻጸሙን ቪዲዮ እየተቀረጸ ሲያሳይ በታዛቢነት ማየቱን አስረድቷል፡፡4ኛ ምስክርም የወንጀል ድርጊቱ በተፈጸመበት እለት አሀዱ ባር ዉስጥ በስራ ላይ የነበሩ መሆኑን ገልጸዉ የሆነ ሰዉ ሮጦ ገብቶ ወግቶት ንቅል አድርጎ ሲሮጥ ማየታቸዉን ይህን ያደረገዉ ማን መሆኑን እንደማያውቁ ነገር ግን ግራጫ ሹራብ ለብሶ የነበረ መሆኑን በኋላም በቀን 29/09/2010ዓ/ም ለቀረጻ

ተጠሪ መጥቶ የድርጊቱን አፈጻጸም ሲያሳይ የተመለከቱ መሆኑን አስርድተዋል፡፡ 5ኛ ምስክርም ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ አህዱ ባር ዉስጥ እንደነበሩ መጠጥ ወደሚቀዳበት ዞረዉ ሲመለሱ አብይ ምን ተፈጠረ ብሎ ሲጠይቃቸዉ ኤርሚያስ ሽርተት ብሎ እንደወደቀባቸዉ፤ ተጠሪም እጁን መንትፎ ሲያወጣ ማየታቸዉን፤ኤርሚያስ ተንሸራቶ ሲወድቅባቸዉ በጣም ደምቶ የነበረ መሆኑንና ሆስፒታል መወሰዱን ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም ግራጫ ልብስ ለብሶ የነበረ መሆኑን በኂላም ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ከሰዎች መሀል የመረጡት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ተጠሪ ድርጊቱን ከመፈጸሙ በፊት እዛዉ ከጎናቸዉ ተቀምጦ አይተዉት እንደነበረ እና ጃኬቱን እንዳለበሰ ጨለማም ቢሆን ፊቱን ያዩት መሆኑንም ጨምረዉ ያስረዱ በመሆኑ ተጠሪ የቀረበበትን ክስ ሊከላከል ይገባል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ የመከላከያ ምስክሮቹን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ምስክሮቹም ተጠሪ የአእምሮ ህመም ያለበት መሆኑን፣ ህመሙ ሲነሳበት ምን እንደሚያደርግ እንደማያዉቅ፣ ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜም ህመሙ ተነስቶበት ጠፍቶ እንደነበር ጓደኞቹ ሲፈልጉት እንደነበር እና በጊዜዉ ሲነሳበት ህክምና ይከታተል እንደነበር ማስረዳታቸዉን በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡

እንዲሁም ተጠሪ ባቀረበዉ የክርክር ማቆሚያ ንግግር ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 48 እና 49 መሰረት ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ ነዉ በማለት በነጻ እንዲያሰናብተዉ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ተጠሪ ይጨንቀኛል ከሚል ዉጭ የአእምሮ ህመም እንደሌለበት በሐኪም ማስረጃ መረጋገጡንና ባቀረባቸዉ ምስክሮችም ክሱን እንዳልተከራከረ ገልጾ መከራከሩን በዉሳኔዉ ተመልክቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም ከፍ ሲል በተገለጸዉ መሰረት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃዎችን በመመርመር ዐቃቤ ሕግ እንደክሱ አቀራረብ ተጠሪ ኤርሚያስ ዘዉዱ የተባለዉን ሰዉ ወግቶ ህይወቱ እንዲያልፍ ያደረገ መሆኑን በማስረዳቱ ተጠሪ ክሱን እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ተጠሪ ባቀረባቸዉ የመከላከያ ማስረጃዎች ድርጊቱን አለመፈጸሙን አላስረዳም፡፡ ከዚህ ባሻገር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 48 እና 49 መሰረት ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ ልባል በማለት ያቀረበዉም ክርክር ቢሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የወንጀል ኃላፊነት በተመለከተ የተደነገገዉ ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ የነበረን የአእምሮ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡ ከአማኑኤል አጠቃላይ ሆስፒታል የቀረበዉ የህክምና ምርመራ ዉጤት ማስረጃ የሚያሳየዉ ተጠሪ ድርጊቱን በሚፈጽምበት ወቅት የድርጊቱን ዉጤት ለመረዳት በሚችልበት የአእምሮ ጤንነት ሁኔታ ላይ ይገኝ የነበረ መሆኑን የተረጋገጠበት በመሆኑ ተጠሪ ለፈጸመዉ ድርጊት ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ ሊባል አይገባም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ሟች ኤርሚያስ ዘዉዱን በሸንኩርት መክተፊያ ቢላ በስተግራ በኩል ደረቱ ላይ ወግቶ ህይወቱ እንዲያልፍ ያደረገ መሆኑ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠዉን ተጠሪ በመከላከያ ማስረጃዎቹ ያልተከላከለ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ስር ተራ በሆነ የሰዉ ግድያ ወንጀል በመ/ቁጥር 005651 ላይ በቀን 18/10/2013ዓ/ም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 149 መሰረት የጥፋተኝነት ዉሳኔ አስተላልፎበታል፡፡ በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ በቀን 21/11/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 212357 ላይ አከራክሮ በቀን 04/06/2014ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ አቅርቦ ባሰማቸዉ መከላከያ ምስክሮች የተረጋገጠዉ ተጠሪ ወንጀሉን ፈጸመ በተባለበት ጊዜ ከቤቱ ጠፍቶ ቤተሰቦቹ ሲፈልጉት እንደነበር ነዉ፡፡ በተጨማሪም ከአማኑኤል ሆስፒታል የቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪ ከ13 ዓመቱ ጀምሮ በአእምሮ በሽታ ምክንያት መድኃኒት ሲወስድ እንደነበር፣አንዳንዴ ሲነሳበት የሰራዉን ነገር እንደማያዉቅና በኂላ ቆይቶ የሚረዳ መሆኑን እንዲሁም የተጠየቀዉን ጥያቄ በአግባቡ የማይመልስ መሆኑን ሀኪሞች በካርዱ ላይ ያሰፈሩት ያረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ እንዲህ አይነቱ ችግር ያለበትማ አንዴ ደህና ሆኖ ሲነሳበት እንዲህ አይነት ችግር ያለበት ለሚፈጽማቸዉ የወንጀል ድርጊቶች ሙሉ በሙሉ ኃላፊ ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 49/1 መሰረት ከፊል ኃላፊነት ሊሆን የሚገባ

ነዉ፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195(2/ለ) መሰረት አሻሽሎ ተጠሪ ከፊል ኃላፊነት አለበት በማለት በ5 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 12/08/2014ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ አጭር ይዘትም፡- ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ለፈጸመዉ ወንጀል ሙሉ ኃላፊነት እንዳለበት አመልካች ባቀረበዉ የሰዉ፣ የሠነድ ፣የሙያ ምስክርነት እና ገላጭ ማስረጃዎች በአግባቡ አስረድቷል፡፡ማስረጃ ሲመዘን የአዋቂ ምስክርነቶች በወንጀል ሕጉ መሰረት ተገቢዉ ዋጋ ተሰጥቶት ሊመዘን ይገባል፡፡ የአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆሲፒታል ተጠሪን መርምሮ በሰጠዉ ማስረጃ ላይ ተጠሪ በቀን 24/03/2000ዓ/ም እና በቀን 30/03/2000ዓ/ም ታክሞ እንደሚያዉቅ የጭንቀት ህመም ያለበት እና ከባድ የአእምሮ ህመም የሌለበት መሆኑን፣ አሁንም በመመላለስ በተለያዩ ቀናት በተደረገለት ምርመራ ምንም የአእምሮ ህመም የሌለበት እና በተከሰሰበት ወንጀል እንደማንኛዉም ግለሰብ መስተናገድ የሚችል መሆኑን በምርመራ አረጋግጦ የደረሰበትን ድምዳሜ ለሚያሳይ ማስረጃ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተገቢወን ዋጋ ሳይሰጥ የማስረጃ ምዘና መርህን ባለተከተለ ሁኔታ ተጠሪ ለቀረበበት ክስ ከፊል ኃላፊነት አለበት ሲል የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን የቅጣት ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ የጣሰ ከመሆኑም በተጨማሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 51 እና 54 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ተብሎ የይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ዉሳኔ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ የተጠሪ የአእምሮ ሁኔታ በሚመለከት ከሆስፒታል የቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪ አንዳንዴ ይጨንቀኛል ከማለት ዉጭ ከባድ የአእምሮ በሽታ የሌለበት መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ይህንን በማለፍ ተጠሪ ከፊል ኃላፊነት አለበት በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከወንጀሉ አፈጻጸም ሁኔታ አንጻር ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 04/02/ 2015ዓ/ም የተጻፈ መልሱን አቅርቧል፡፡የመልሱም አጭር ይዘት፡- የአእምሮ በሽታ ሲነሳብኝ ቤተሰብ ፈልጎ ካለሁበት በማምጣት መዉሰድ ያለብኝን መድሐኒት እንድወስድ ያደርገኛል፡፡እንዲሁም በእምነቴ ከጸበል ተለይቼ አላዉቅም፡፡ከ13 ዓመቴ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በቤተሰብ ጥረትና ክትትል በሕክምና እገዛ እየተደረገልኝ ይገኛል፡፡በአማኑኤል ሆስፒታል የህክምና ክትትል እያደረኩ የምገኘዉ የአእምሮ ሕመም ስላለብኝ ነዉ፡፡ ሲዝናና በሽንኩርት ቢላዋ ቀዶ ሰዉ ገድሏል የተባለዉን በጊዜዉ ሰዉ መግደሌን አላስታዉስም፡፡ ቢላዉንም ከየት እንዳመጣሁ አላዉቅም፡፡ከዛም በኋላ ወዴት እንደሄድኩ አላዉቅም፡፡ይህንኑ በምስክሮቼ አስረድቻለሁ፡፡የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም ከዚህ የተለየ ምስክርነት አልሰጡም፡፡ይህ በተረጋገጠበት በትክክለኛ አእምሮ ነበር በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ስለሆነም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተጠሪ ከፊል ኃላፊ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ለፈጸመዉ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ወንጀል ከፊል ኃላፊ ሊሆን ይገባል በማለት የተወሰነበትን የቅጣት ዉሳኔ በማሻሻል በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉ አንድ ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን የወንጀል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት ባሟላ መልኩ መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ አግባብ መቀጣት ይገባዋል፡፡በዚህ መልኩ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለዉ በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተከሳሹ ድርጊቱን ወይም አል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ

ነገሮችን በሚያሳይ አግባብ በማስረጃ ሲያስረዳ ነዉ፡፡ እንዲሁም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 48/1 ስር እንደተደነገገዉ በወንጀል ክስ የተከሰሰ ሰዉ በወንጀል ሕግ መደበኛ ድንጋጌዎች መሰረት የሚቀጣዉ ላደረገዉ ድርጊት ኃላፊ መሆኑ የተረጋገጠበት ወንጀል አድራጊ መሆኑ ሲረጋገጥበት ብቻ ነዉ፡፡ ይህኛዉ የወንጀል ኃላፊነት በቀጥታ ከወንጀል ፈጻሚዉ የሞራል(የሀሳብ) ፍሬ ነገር(mens rea or criminal intent) ጋር የተያያዘ ቢሆንም ተቃራኒ ክርክር በተከሳሹ እስከሚቀርብ ድረስ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ የቀረበበት ሰዉ ለፈጸመዉ ድርጊት ኃላፊ (responsible) እንደሆነ ግምት ይወስዳል፡፡

ተከሳሽ በክሱ ፈጸመ ተብሎ ለተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ኃላፊ አይደለሁም የሚል ከሆነ በተቻለ መጠን ይህንኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 130(2/ሰ) መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አድርጎ በማንሳት መከራከር ይገባዋል፡፡እንዲህ አይነት መከራከሪያ የጸና ፍርድ ከመስጠት የሚያግድ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ ተከሳሹ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ማንሳት ካልቻለ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 130/3 ስር በተደነገገዉ መሰረት በሌላ ጊዜ ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ አንስቶ መከራከር ይችላል፡፡ እንዲሁም ተከሳሹ ባለበት ኃላፊነትን በሚያስቀር ችግር ወይም ሌላ ሁኔታ ምክንያት የወንጀል ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ የድርጊቱን አይነት ወይም ዉጤት ለመገንዘብ ወይም በዚህ ግንዛቤ መሰረት ራሱን ለመቆጣጠር ያልቻለ መሆኑን በማስረጃ ማስረዳት ይገባዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱም የተከሳሹን ኃላፊነት በሚመለከት ተከሳሹን ፍጹም ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ የሚያደርገዉ ሁኔታ እንዳለ በክርክሩ ሂደት ጥርጣሬ ሲያድርበት ይህንን ሳያጣራ የጸና ፍርድ መስጠት ስለሚያዳግተዉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 130/3 በተደነገገዉ መንፈስ መሰረት በራሱ አነሳሽነት ተከሳሹን ፍጹም ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ ሊያደርገዉ የሚችል ሁኔታ መኖር አለመኖሩ እንዲመረመር ተገቢዉን ትእዛዝ ሰጥቶ ማጣራት ይኖርበታል፡፡

የወንጀል ሕጉ የወንጀል ፍጹም ኢ-ኃላፊነት እና ከፊል ኃላፊት የሚቋቋምበትን አግባብ ለአዋቂ ሰዉ (ዕድሜዉ 9 ዓመት የሞላዉን ሰዉ/adult) እና ለህጻን (ዕድሜዉ 9 ዓመት ያልሞላዉን ሰዉ/Infant) በሚል በሁለት ዘርፎች ለይቶ ይመድባቸዋል (የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 48፣49 እና 52 ስር ይመለከቷል)፡፡ የመጀመሪያዉ 9 ዓመትና ከዚያ በላይ እድሜ ያለዉ ሰዉ በወንጀል ጉዳይ በሙሉ ወይም በከፊል ኃላፊ የማይሆንበት አንደኛዉ ሁኔታ ሲሆን ይሄዉም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 48 እና 49 ስር በተደነገገዉ መሰረት  በዕድሜ፣ በሕመም፣ ባልተለመደ የዕድገት መዘግየት፣ወይም ጥልቅ በሆነ የአእምሮ የመገንዘብ ወይም የማመዛዘን ችሎታ መቃወስ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በማናቸዉም ሌላ ተመሳሳይ ስነ-ህይወታዊ ምክንያት *የወንጀል ድርጊት በሚፈጽምበት ጊዜ የድርጊቱን አይነት ወይም ዉጤት ለመገንዘብ ወይም በዚህ ግንዛቤ መሰረት ራሱን ለመቆጣጠር በፍጹም ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ፍጹም ኢ-ኃላፊ* የሚሆንበት ነዉ፡፡ በእነዚሁ ምክንያቶች የተነሳ *የወንጀል ደርጊት በሚፈጽምበት ጊዜ የተግባሩን አይነት ወይም ዉጤት ለመገንዘብ ወይም በዚህ ግንዛቤ መሰረት ራሱን ለመቆጣጠር ያለዉ ችሎታ ከፊል እንዲሆን* ላደረገዉ ወንጀል ከተደነገገዉ ቅጣት ዉስጥ ከፊሉ ተፈጻሚ እንዲሆን የሚደረግበት *ከፊል ኃላፊነት* በሚል የሚታወቅ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ በዚህ ዘርፍ ያለዉ ሁኔታ ደግሞ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 50 ስር በተደነገገዉ መሰረት በስካር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የሚፈጠር ኢ-ኃላፊነት የሚመለከት ነዉ፡፡

ሁለተኛዉ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስቀር ዘርፍ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 52 ስር የተደነገገዉ ሲሆን ይኸዉም በወንጀል ሕግ አይን ዘጠኝ ዓመት ያልሞላዉ ሰዉ ገና ሕጻን በመሆኑ/ኗ የሚፈጽመዉ/የምትፈጽመዉ ድርጊት ወንጀል መሆኑንና ዉጤቱን ለማወቅ ያልበሰለ/ች ስለሆነ/ነች (due to his/her immaturity) በወንጀል ሕግ ኃላፊ የማይሆንበትን/የማትሆንበትን የሚመለከት ነዉ፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሰረት ኃላፊነትን የሚመለከት ክርክር በማንና መቼ መቅረብ ይችላል በሚል ከሥነ ሥርዓት ሕጉ አኳያ የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተከሳሹ ኃላፊነትን የሚመለከት ክርክር ሲቀርብ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ተከሳሹ በተከሰሰበት ጉዳይ ፍጹም ኢ-ኃላፊ ወይም ከፊል ኃላፊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ጥርጣሬ ሲያድርበት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 51/1 ስር በተደነገገዉ

መሰረት ልዩ ዕዉቀት ያለዉን የአዋቂ ሀሳብ መጠየቅ አለበት፡፡ በተለይ ተከሳሹ የአእምሮ በሽታ ያለበት ለመሆኑ የሚያመላክቱ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ ልዩ ዕዉቀት ያለዉን የአዋቂ ሰዉ አሳብ መጠየቅ እንዳለበት በፍርድ ቤቱ ላይ በሕጉ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ በጉዳዩ ላይ ልዩ ዕዉቀት ያለዉ ሰዉ ጉዳዩን መርምሮ ለፍርድ ቤቱ መግለጫ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት መሰረት አድርጎ መያዝ የሚገባዉ ልዩ አዋቂዉ በሕግ ረገድ የሚያቀርብለትን አሳብ ሳይሆን በሳይንስ ረገድ በትክክል ተጠንቶ የሚቀርብለትን በአስረጂዉ ዉጤት መሰረት ላይ የተገኘዉን እንደሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 51/3 ስር ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 130(2/ሰ) መሰረት የአእምሮ ህመም እንዳለበት በመግለጽ ክስ በቀረበበት ወንጀል ፍጹም ኢ-ኃላፊ መሆኑን ገልጾ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሳት መከራከሩን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ተመልክተናል፡፡ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 005651 ላይ በቀን 25/11/2010ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ የተጠሪ የአእምሮ ሁኔታ ተምርምሮ ዉጤቱ እንዲገለጽለት ለአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ትእዛዝ ሰጥቶ ሆስፒታሉ በቁጥር አማ/82/1/40 በቀን 11/07/2012 ዓ/ም የተጻፈ የምርመራ ዉጤት ለፍርድ ቤቱ መላኩን ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ላይ ተመልክተናል፡፡የምርመራ ዉጤቱም እንደሚከተለዉ ይነበባል፡-

> "… ምንተስኖት ዘለቀ በአማኑኤል ሆስፒታል ለ2 ቀናት ያህል ብቻ በቀን 24/03/2000ዓ/ም እና በቀን 30/03/2000ዓ/ም በህክምና ካርድ ቁጥር 41740 ለህክምና በተመላላሽ ታይቶ ያዉቃል፡፡በእነዚህ ቀናት የተገኘበት የአእምሮ ህመም የጭንቀት ህመም መሆኑን እንገልጻለን፡፡ከባድ የአእምሮ ህመም የለበትም፡፡
>
> አሁንም በተመላላሽ በተለያዩ ቀናት በተደረገለት ምርመራ ምንም ከባድ የአእምሮ ህመም የለበትም፡፡በመሆኑም በተከሰሰበት ወንጀል እንደማንኛዉም ግለሰብ መስተናገድ ይችላል የሚል ሙያዊ አስተያየታችንን እንሰጣለን፡፡" የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

የስር ፍርድ ቤት ከላይ የተገለጸዉን የተጠሪ የአእምሮ ጤና ሁኔታ በተመለከተ በሀክምና ምርመራ ተደርጎ የቀረበለትን ማስረጃ እና በግራ ቀኙ የቀረቡትን ሌሎች ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ ተጠሪ ድርጊቱን በፈጸመበት ወቅት የድርጊቱን ዉጤት ለመረዳት በሚችልበት የአእምሮ ጤንነት ሁኔታ ላይ ይገኝ የነበረ መሆኑ ስለተረጋገጠ ተጠሪ ፍጹም ኢ-ኃላፊ ነዉ ወይም ከፊል ኃላፊነት አለበት የማይባል አይደለም፤ እንዲሁም በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጠበትን ክሱንም ባቀረባቸዉ ማስረጃዎች አለመከላከሉን ገልጾ ጥፋተኛ ነዉ ሲል በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ በመከላከያ ምስክሮች የተረጋገጠዉ ተጠሪ ወንጀሉን ፈጸመ በተባለበት ጊዜ ከቤቱ ጠፍቶ ቤተሰቦቹ ሲፈልጉት እንደነበር ተመስክሯል፡፡በተጨማሪም ከአማኑኤል አእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪ ከ13 ዓመቱ ጀምሮ በአእምሮ በሽታ ምክንያት መድሀኒት ሲወስድ እንደነበር እና ሀኪሞቹ በካርድ ላይ ባሰፈሩት መሰረት አንዳንዴ ሲነሳበት የሥራዉን ነገር እንደማያዉቅ በኋላ ቆይቶ የሚረዳ መሆኑን እና የተጠየቀዉን ጥያቄ በአግባቡ የማይመልስ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለሆነ ተጠሪ በፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት ከፊል ኃላፊነት አለበት የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በዉሳኔዉ ላይ ተጠሪ ከ13 ዓመቱ ጀምሮ በአእምሮ በሽታ ምክንያት መድሀኒት ሲወስድ ነበር በሚል የገለጸ ቢሆንም ከላይ ይዘቱ በተገለጸዉ የሀኪም ምርመራ ዉጤት ላይ በዚህ መልኩ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ በምርመራ ዉጤቱ ላይ የተገለጸዉ "…ለ2 ቀናት ያህል ብቻ በቀን 24/03/2000ዓ/ም እና በቀን 30/03/2000ዓ/ም በህክምና ካርድ ቁጥር 41740 ለህክምና በተመላላሽ ታይቶ ያዉቃል፡፡" የሚል ሲሆን ይህ ደግሞ ከ13 ዓመቱ ጀምሮ በአእምሮ በሽታ ምክንያት መድሀኒት

ሲወስድ ነበር ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት "…አንዳንዴ ሲነሳበት የሥራዉን ነገር እንደማያዉቅ በኋላ ቆይቶ የሚረዳ መሆኑን እና የተጠየቀዉን ጥያቄ በአግባቡ የማይመልስ መሆኑን የሚያረጋገጥ…" በሚል በዉሳኔዉ ላይ በገለጸዉ ልክ ምርመራዉን ያደረጉ ሀኪሞች ከላይ ይዘቱ በተገለጸዉ የምርመራ ዉጤት ላይ ድምዳሜ አልደረሱም፡፡

በእርግጥ በስር ፍርድ ቤት መዝገብ ዉስጥ ያለዉ የተጠሪ የህክምና ካርድ ግልባጭ ላይ እንደተመዘገበዉ ተጠሪ በቀን 03/07/2012ዓ/ም በሀኪም ተጠይቆ ሲመልስ - በነፍስ በማጥፋት ወንጀል መከሰሱን፣ የታሰረበትን ጊዜ ማስታወስ አለመቻሉን ገለጸ ተብሎ መመዝገቡን፤ እንዲሁም በሌላ ጊዜ በቀን 08/07/2012ዓ/ም በሀኪም ሲጠየቅ - ህክምና ለማግኘት መጥቻለሁ፣ እንቅልፍ የለኝም፣ይጨንቀኛል፣…ምን ማድረግ እንዳለብኝ ሳላዉቅ የማደርገዉ ነገር አለ፤ ምንም አላስታዉስም ማለቱን እንዲሁም አጠቃላይ የግንዛቤ ጥያቄዎች ተጠይቆ በአሁኑ ጊዜ ህመም ይሰማኛል፣ተኝቼ እዉላለሁ፣የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ማነዉ?-ኃይለስላሴ ናቸዉ፣ ፕሬዝዳንት? ቲራምፒ፣ የት ተወለደህ አደግህ? አላዉቅም፣ይህ ቦታ የት ነዉ? ትምህርት ቤት በማለት መመለሱን በካርዱ ላይ የሰፈረዉ ያሳያል፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 51/1 ስር ተከሳሹ የአእምሮ በሽታ ያለበት… ለመሆኑ የሚያመላክቱ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ ልዩ ዕዉቀት ያለዉን የአዋቂ ሰዉ አሳብ መጠየቅ አለበት በሚል በፍርድ ቤቱ ላይ ግዴታ የተጣለበት ምክንያት ዳኞች ባላቸዉ የሕግ ሙያ እንዲህ አይነት ጉዳዮች ላይ የመወሰን የሙያ ብቃት እንደሌላቸዉ ስለሚታወቅ ነዉ፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በካርዱ ላይ የሰፈረዉ ተጠሪ በሀኪሙ ተጠይቆ የመለሰዉ መልስ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡አከራከሪዉ ነጥብ እንዲህ አይነት መልስ ለጥያቄዎቹ መስጠት የአእምሮ ሕመምተኛ ያስብላል? አያስብሉም የሚለዉ ነዉ፡፡ ተጠሪ በተጠቀሰዉ መሰረት ተጠይቆ የሰጠዉ መልስ የአእምሮ ህመምተኛ ነዉ የሚል እና የህምም ደረጃዉም ይህንን ያህል ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚችለዉ ፍርድ ቤት ሳይሆን በሕክምና ሳይንስ በአእምሮ ህመም ዘርፍ ልዩ እዉቀት ያለዉ ሀኪም ነዉ ፡፡ ምክንያቱም በተገለጸዉ መሰረት በህክምና ካርዱ ላይ የተገለጸዉ ተጠሪ ከሀኪሙ ጋር ያደረገዉ ቃለ ምልልስ ተጠሪ የወንጀል ክስ ከቀረበበት በኋላ የተደረገ መሆኑና ተጠሪ ለጥያቄዎቹ የሰጠዉ ምላሽ ይዘት በእርግጥም የአእምሮ የጤና ህመም እንዳለበት የሚያሳዩ ናቸዉ ወይስ የወንጀል ኃላፊነት የለበትም ተብሎ እንዲወሰን በማቀድ የሰጠዉ መልስ ነዉ የሚለዉ ከሌሎች ሀኪሙ ከግምት ዉስጥ ከሚያስገባቸዉ ነገሮች ጋር ተደምሮ ታይቶ ሙያዊ ትንታኔ ተሰጥቶበት በህክምና ሳይንሱ መሰረት ድምዳሜ ላይ የሚደረሰበት እንጂ በፍርድ ቤት የሚወሰን ባለመሆኑ ነዉ፡፡

ከዚህ አኳያ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት "ተጠሪ …አንዳንዴ ሲነሳበት የሠራዉን ነገር እንደማያዉቅ በኋላ ቆይቶ የሚረዳ መሆኑን እና የተጠየቀዉን ጥያቄ በአግባቡ የማይመልስ መሆኑ…" በሚል በዉሳኔዉ የገለጸዉ ብቻዉን ተጠሪ እንደማንኛዉም ጤነኛ አእምሮ እንዳለዉ ሰዉ ሊታይ እንደማይገባዉ እና የአእምሮ ህመም እንዳለበት የሚያሳይ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ነዉ በሚል በህክምና ምርመራ ዉጤት ላይ አልተገለጸም፡፡ ይልቁንም በሀኪም የተደረሰዉ ድምዳሜ ተጠሪ ያለበት ህመም የጭንቀት ህመም በሚል የሚገለጽ ህመም እንደሆነና በከባድ የአእምሮ ህመም የሚገለጽ ምንም ህመም እንደሌለበት እና በተከሰሰበት ወንጀል እንደማንኛዉም ግለሰብ መስተናገድ እንደሚችል ሙያዊ አስተያየት ጭምር የተሰጠበት እንደሆነ ማስረጃዉ ያሳያል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 51/3 ስር እንደተደነገገዉ ፍርድ ቤቶች ልዩ አዋቂዉ በሳይንስ ረገድ በትክክል በማጥናት የሚቀርብላቸዉን የምርመራ ዉጤት ተገቢዉን ዋጋ ሰጥተዉ መመዘን ይኖርባቸዋል፡፡ የህክምና ምርመራ ዉጤቱ ልዩ አዋቂ በሆኑ ሀኪሞች ሳይንሱ በሚፈቅደዉ መሰረት ተመርምሮ የሚቀርብ ነዉ፡፡ የምርመራ ዉጤቱ በትክክል ሳይጠና የቀረበ ከሆነም በድጋሚ እንዲጠና ትእዛዝ ተሰጥቶ በትክክል ተጠንቶ እንዲቀርብ ይደረጋል እንጂ የምርመራ ዉጤቱ የተደረሰበትን ድምዳሜ

ወደ ጎን በመተዉ በህክምና ሳይንስ ረገድ ድምዳሜ ሊደረስበት በሚገባ ፍሬ ነገር ላይ በዘርፉ ባለሙያ ያልሆኑ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ቃል ጋር በማገናዘብ ለህክምና ምርመራ ዉጤቱ ተገቢዉ ዋጋ ሳይሰጥ በፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ዉሳኔ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 51/3 ስር የተደነገገዉን ጠቅላላ መርህ የሚጥስ ስለሆነ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር እንደተመለከተዉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ሥልጣን ማናቸዉንም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ በሕግ በዝርዝር በሚወሰነዉ አግባብ መርምሮ እንዲያርም ነዉ፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመመዘን ጉዳይ ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን በማረጋገጥ ዉሳኔ መስጠት መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደማረም የሚቆጠር ባለመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ አይደለም፡፡

ሆኖም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች (Principles of Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence) አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standards of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲረጋገጥ፤ እንዲሁም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን በአግባቡ ያላገናዘበ እና ዉሳኔ የሚሻዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ለሆነ ማስረጃዉ ተገቢዉን ዋጋ ሳይሰጡ ዉሳኔ መስጠት እንዲሁም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰን ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ተገብቷል የሚያስብል ሳይሆን እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ከላይ ይዘቱ በተገለጸዉ መሰረት የተጠሪ የአእምሮ ጤና ሁኔታ በልዩ አዋቂ ተመርምሮ ለመጣዉ ዉጤት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 51/3 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተገቢዉን ዋጋ ሰጥቶ አለመመዘኑ ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አኳያ ሲታይም የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ጉድለት ያለበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ ሰዉ የመግደል ድርጊት በፈጸመበት ጊዜ ስለፈጸመዉ ድርጊት አይነት ወይም ዉጤት ለመገንዘብ ወይም በዚህ ግንዛቤ መሰረት ራሱን ተቆጣጥሮ ለመስራት በሚያስችል የአእምሮ ጤና ሁኔታ እንዳልነበረዉ ባቀረባቸዉ ማስረጃዎች እንዳላስረዳ የስር ፍርድ ቤት የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ እንዲሁም የተጠሪን የጤና ሁኔታ በልዩ አዋቂ ሐኪም አስመርምሮ የመጣለትን የምርምራ ዉጤት ጭምር መዝኖ የሰጠዉ የቅጣትና የጥፋተኝነት ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ብለናል፡፡በአንጻሩ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በልዩ አዋቂ ሀኪም የተጠሪ የአእምሮ ጤና ሁኔታ ተመርምሮ ለመጣዉ የምርመራ ዉጤት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 51/3 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተገቢዉን ዋጋ ሰጥቶ ሳይመዝን እንዲሁም ተጠሪ የግድያ ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ከፊል ኃላፊ የሚያደርገዉ የአእምሮ ህመም ያለበት ስለመሆኑ በማስረዳት በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጠዉን ምክንያታዊ ጥርጣሬ ዉስጥ በመክተት አስተባብሏል የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ማስረጃ ባልቀረበበት ተጠሪ ከፊል ኃላፊ ነዉ ሲል ቅጣቱን በግማሽ ቀንሶ የሰጠዉ ዉሳኔ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 49 እና 51ን የሚቃረን ከመሆኑም በተጨማሪ የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ጉድለት ያለበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 212357 ላይ በቀን 04/06/2014 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 005651 ላይ በቀን 18/10/2013ዓ/ም የሰጠዉ የጥፋተኝነት ፍርድ እና ተጠሪ በአስር አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በቀን 21/11/2013ዓ/ም የሰጠዉ የቅጣት ዉሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195(2/ለ/2) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ አስቀድሞ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የተወሰነበትን የ5 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ጨርሶ ከማረሚያ ቤት መዉጣቱን በችሎት ስለገለጸ በዛሬዉ እለት በተሰጠ ዉሳኔ በከፍተኛ ፍርድ ቤት በተወሰነዉ መሰረት በ10 ዓመት ጽኑ እስራት መቀጣት ስላለበት ቀሪዉን 5 (አምስት) ዓመት ጽኑ እስራት ከዛሬ ጀምሮ በሚታሰብ እስራት ታስሮ እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የፌደራል ማረሚያ ቤት ከላይ በተራ ቁጥር 3 ስር በተወሰነዉ መሰረት እስራቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ታዟል ፡፡ይጻፍ
2. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ክፍል ስድስት

## 6.በወንጀል ጥፋተኛ መሆን

### 6.1 አሳብ፣ ቸልተኝነት እና ድንገተኛ ነገር[18]

- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57 በግልፅ እንደሰፈረው "ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም በአንፃሩ አንድ ሰው "የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57(2) ይደነግጋል፡፡
- ከዚህ የሕጉ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ህግ ድርጊቱ የተፈፀመው ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት ስለ መሆኑ፤
- ድርጊቱ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሳሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከሕጉ መንፈስ ውጪ ስለመሆኑ፤
- ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ

[18]የሰ/መ/ቁ. 93741 (ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ የሰ/መ/ቁ 42703 (ሐምሌ 22 ቀን 2001ዓ.ም) ቅፅ 9፣ የሰ/መ/ቁ 134549 (መስከረም 23 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ/መ/ቁ 132266 (ታህሳስ 26 ቀን 2009ዓ.ም) ቅፅ 21

ነው። ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው እድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀጽ 59(1) ይደነግጋል።

የሰ/መ/ቁ. 93741

ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አብነት ዋቆ ብሩ - ጠበቆች መሃመድ አሚን እና ጫንያለው እሸቱ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በጂማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው። የክሱ ይዘትም፡- አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) ስር የተመለከተውን በተመላለፍ በሾፌርነቱ ሙያቸው የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ/ም ከጠዋቱ 12፡30 ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-28157 ኦሮ የሆነውን ሚኒባስ መኪና እያሽከረከረ ከጅማ ከተማ ወደ አጋሮ ከተማ ሕዝብ ጭኖ በማሽከርከር ላይ እያሉ መንገዱን ለቅቆ ከእንጨት ጋር አጋጭቶ በመገልበጥ የተሽከርካሪው ረዳት የሆነው አብዲ ዋቆ የገደላቸው በመሆኑ በፈፀሙት በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው። የአሁኑ አመልካችም የክስ ማመልከቻው ደርሷቸው ክሱን እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ዳኛ በመሆናቸው ያለመከሰስ መብት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው በክሱ ላይ ተቃውሞ እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አቃቤ ሕጉ አመልካቹ ድርጊቱን እንደፈፀሙ ወዲያውኑ የተያዙ መሆናቸውን ገልፀው ያለመከሰስ መብታቸው ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡትን አስተያየት በመቀበል የክስ ተቃውሞውን ያለፈው ሲሆን የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን የክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል። አቃቤ ህግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል። ከዚህም በኋላ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸውና ሟች በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ሕይወታቸው ያለፈ መሆኑን አቃቤ ህግ በማስረጃዎቹ ያስረዳባቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ታምኖበት ይህንኑ እንዲያስተባብሉ እድል ተሰጥቶ አመልካች አደጋው የደረሰው በድንገተኛ አደጋ አጋጣሚ መሆኑን የሚያሳይ ጭብጥ አስይዘው የመከላከያ ማስረጃ ያሰሙ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎቹ የዐቃቤ ህግ ማስረጃዎቹን ያላስተባበሉ መሆኑን በመጥቀስ አመልካችን በአቃቤ ህግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጓቸዋል። ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት በመቀበልና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ በአንድ አመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት እና በብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን የሰበር አቤቱታቸውን እንደየቅደም ተከተላቸው ለክልሉ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም ቅሬታቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ቁጥር 195(1) መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 16 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የአመልካች ያለመክሰስ መብት የታለፈው ያላግባብ መሆኑን፣ አመልካች ድርጊቱን የፈፀሙት በወንድማቸው ላይ ሆኖ ከአቅም በላይ በሆነ የአደጋ አጋጣሚ ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤቶች መታለፉ ያላግባብ መሆኑን፣ የቅጣት ውሳኔም ተገቢነት የሌለው መሆኑና የእስራት ቅጣቱ መገደብ ሲገባው መታለፉም ያለግባብ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ጥፋተኛ መባላቸው ከሰ/መ/ቁጥር 42703 አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልጽ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደምተከተከላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በምክንያትነትና በውጤት መካከል ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 24 በተመለከተው አግባብ ግንኙነት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ሲያሽከረክሩት የነበረው ተሽከርካሪ ተገልብጦ ሟችን ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ/ም መግደላቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች የሚከራከሩበት ነጥብ ሟች የሞቱት በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለውን የባለሙያ የምስክርነት አስተያየት፣ በአደጋው ቦታ የተነሳውን ፕላንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል መዝኖ አመልካች ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ቀርተው አደጋው መድረሱን ማረጋገጡን ደምድሟል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ማስረጃ ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ከመሆኑም በላይ ታአማኒነቱ ሲታይ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 በተመለከተው የማስረጃ ምዘና አግባብ ጉዳዩን ለማስረዳት በቂና አሳማኝ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ይህን ማስረጃ ክብደት ሊሰጠው አይገባውም ነበር ለማለት የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች አደጋው በድንገተኛ አጋጣሚ የተከሰተ ነው በማለት የሚያቀርቡት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር በዚህ ችሎት ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57 በግልፅ እንደሰፈረው "ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆነም በአንፃሩ አንድ ሰው "የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል

ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57(2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የሕጉ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ህግ ድርጊቱ የተፈፀመው ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ ድርጊቱ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሳሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከሕጉ መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ቸልተኛ ነበር? ወይስ አልነበረም? የሚለው ጥያቄ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው በመሆኑም የሕጉን ይዘት እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው፡፡ ይኸውም፡- ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አደርጓል የሚባለው፡-

(ሀ) ድርጊቱ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን፣ ወይም

(ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያሰቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡”

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው እድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀጽ 59(1) ይደነግጋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በሙያቸው አሽከርካሪ ሆነው እያለና በአሽከርካሪነት ሙያው ደግሞ የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-28157 ኦሮ የሆነውን ሚኒባስ መኪና እያሽከረከረ ከጅማ ከተማ ወደ አጋሮ ከተማ እያሽከረከሩ ተገቢውን ጥንቃቄ ከማድረግ ጉድለት መኪናው ተገልብጦ ሟች የሞቱ በመሆኑ አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ስር የማይጠየቁበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡

ስለሆነም አመልካች የጥፋተኝነት ውሳኔውን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ክርክር ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23፣24፣57፣57 እና 543(2) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) መሰረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሊቀጣ የሚገባው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ነው፣ ቅጣት ደግሞ ሊጣል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ነጥቦች በማመዛዘን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ ቅጣት ሲጥል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር እና በወንጀል ሕጉ ከተመለከቱት የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ጋር በማገናዘብ ቅጣቱን መወሰኑን የገለፀ ቢሆንም ሟቹ የአመልካች ወንድም በመሆናቸው ምክንያት ቅጣቱን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1) መሰረት ማክበዱ የሕግ መሰረት ያለውና የወንጀል

ሕጉን መሰረታዊ አላማ የሚያሳካ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ይሄው ምክንያት ሊያዝ የማይገባው ከሆነ አመልካችን ሊያርማቸው፣ ሌላውን ደግሞ ሊያስጠነቅቅ የሚችለው የቅጣት መጠን አንድ አመት ቀላል እስራት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም የቅጣት ውሳኔ ክፍል ግን በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 26643 ነሐሴ 03 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 167016 ነሐሴ 12 ቀን 2005 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 123422 ነሐሴ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(2)) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኛ ናቸው መባላቸው በአግባቡ ሲሆን ቅጣቱ ግን ተገቢ ያልሆነ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተይዞ እንዲከብድ የተደረገ በመሆኑ ምክንያቱን ውድቅ በማድረግ አመልካች ሊቀጡ የሚገባው የቅጣት መጠን በአንድ አመት ቀላል እስራት ነው ብለናል፣ የገንዘብ መቀጮው ብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) እንዲቀጡ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ይገለጽለት ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>6.2 በቸልተኝነት ጥፋተኛ መሆን</u>[19]

- ወቅቱ ሌሊት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የግል ተበዳይን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ሰው ከቤት ሊኖር እንደሚቻል ማወቅ ሲገባው ወይም እያወቀ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 የተደነገገውን ቸልተኝነት የሚያሟላ ነው፡፡
- በአጠቃላይ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ ከግል ተበዳዩ ጋር በነበረው ጠብ በቂም በቀል ተነሳስቶ የግል ተበዳይን ቤት በእሳት ያቃጠለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ በለኮሰው እሳት ተቃጥለው ሰዎች ሞተዋል፡፡ ተጠሪ ቤቱን የማቀጠል እንጂ ሚኞቹን የመግደል ሀሣብ አልነበረውም ቢባል እንኳን በቸልተኝነት ሚኞችን በመግደሉ ተጠያቂ የማይሆንበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም፡፡

[19]የሰ/መ/ቁ. 35697 (ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9

የሰ/መ/ቁ. 35697

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ - ዓቃቤ ሕግ አውግቸው መኮንን ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ከበደ ወርቅነህ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13840 ኅዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ታህሣሥ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የምዕራብ ጎጃም ዞን ዓቃቤ ሕግ ተከሣሽነት ተጠሪ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ የዞኑ ዓቃቤ ሕግ በተጠሪ ላይ መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም. ከምሽቱ በግምት አራት ሰዓት ሲሆን የግል ተበዳይ የመኩሪያው ተጋፋውን ቤት በማቃጠል በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተኝተው የነበሩትን ይታይሽ አለማየሁ አለባቸው መኩሪያውና ፋሲካ መኩሪያው በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ ያደረገ በመሆኑና ድርጊቱን የፈፀመው በእሳት ቃጠሎ ምክንያት በውስጥ ያሉ ሰዎች ሊሞቱ እንደሚችሉ እያወቀ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ 539/1/ሀ/ በመተላለፍ የሆነው ይሁን በሚል ተነሳስቶ በመሆኑ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል፣ ይህ የሚታለፍ ቢሆን በአማራጭ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል፡፡

እንደዚሁም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 494 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ግምቱ ከ20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ በላይ የሆነ ንብረት ሙሉ በሙሉ እንዲወድም አድርጓል የሚሉ ክሶችን አቅርቦበታል፡፡ ተጠሪ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ የገለፃቸውን የወንጀል ድርጊቶች አልፈፀምኩም በማለት ክዶ በመከራከሩ ዓቃቤ ሕግ ሁለት ምስክሮች አሰምቷል፡፡ ተጠሪ ለወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት የሰጠውን የዕምነት ቃል በሰነድ ማስረጃነት አቅርቧል፡፡ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቤቱ ከውጭ እንደተቆለፈ በእሳት የተቀጣጠለ መሆኑንና በክሱ ስማቸው የተገለፀ ሰዎች በእሳት ተቃጥለው መሞታቸውን እውነት በሌለው ሁኔታ የመሰከሩ መሆኑንና ሁለተኛው የዓቃቤ ሕግ ምስክር በእሳት ተቃጥላ የሞተችው ሴት ተከሣሽ መኩሪያው ተጋፋውን ከእነ ቤተሰቦቹ ቆልፌ በእሳት አቃጥላለሁ እያለ ይዝት እንደነበር ከዚያ ቀን በፊት ቀን ነግራኛለች በማለት የመሰከረ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል፡፡ ሌላው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ በወንጀለኛ መቀጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት የሰጠው የዕምነት ቃል ሲሆን መጋቢት 29 ቀን 1998 ሌሊት 4 ሰዓት ሲሆን የመኩሪያው ተጋፋውን ቤት አቃጥያዋለሁ ያቃጠልኩት የመጋቢት መባቻ በዱላ ስለመታኝ ነው፡፡ ቤቱ ከውጭ ተቆልፎ የነበረ በመሆኑና የቤቱ ባለቤት ወደ ማኀበር ሲሄድ ስላየሁት ቤተሰቦቹም ሄደዋል ብዬ ነው ያቃጠልኩት ቤቱም ከውጪ ተቆልፎ ነበር የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ በወቅቱ በአካባቢው ያልነበረ መሆኑን ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/3/ የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት ሶስት ሰዎችን የገደለ ጥፋተኛ ነው፡፡ እንደዚሁም በወንጀል

ሕጉ 691 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተ ለመጀመሪያው ጥፋት በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር መቀጮ በሁለተኛው ጥፋት በሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና በአምስት መቶ ብር መቀጮ በጥቅሉ በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራትና በሁለት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በእሳት ተቃጥለው የሞቱት ሰዎችን በተመለከተ ተጠሪ ሊያደርገው የሚችለው ጥንቃቄ አልነበረም፡፡ የሀሣብ ሁኔታው አልተሟላም በማለት ሙሉ በሙሉ በነፃ እንዲለቀቅ የወሰነ ሲሆን የሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና አምስት መቶ ብር ቅጣት በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ ቤቱን በማቃጠል የግል ተበዳይ የደረሰበትን ጉዳት ለመበቀል አስቦ ያደረገው መሆኑ በሰው ምስክርም ሆነ በጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ከምሽቱ አራት ሰዓት በመሄድ ቤት ያቃጠለው ንብረት ለማውደም ብቻ ሣይሆን ሰዎች የሚተኙበት የእንቅልፍ ሰዓት በመሆኑ የግል ተበዳይን ከነቤተሰቡ በእሳት ለማቃጠል በነበረው ሀሣብ እንደሆነ በማስረጃ አስረድተናል ሆኖም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአማራጭ የቀረበውን የቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ተጠሪን ጥፋተኛ ሲል ዓቃቤ ሕግ ይግባኝ ያልጠየቀ በመሆኑ በከባድ ሰው መግደል ተጠሪ መጠየቅ አለበት ብለን ለመከራከር የሥነ ሥርዓት ገደብ ቢኖርብንም ከዚህ አልፎ የጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት የለም በማለት መወሰኑ ለወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 እና 543/3/ የተዛባ ትርጉም የሰጠና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሰራ መሆኑን ስለሚያሣይ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች አቤቱታ መልስ ይዞ እንዲቀርብ መጥሪያ የደረሰው ሲሆን መልሱን ይዞ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ቤቱን ከምሽቱ አራት ሰዓት ያቃጠለው የግል ተበዳይ መኩሪያው ተጋፋው ጋር ከዚያ በፊት ተጣልተው የግል ተበዳይ በዱላ ስለደበደበው መሆኑን የዓቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የግል ተበዳይን ቤት ከውጭ ቆልፎ ከነቤተሰቡ ነው የማቃጥለው በማለት ይዝት እንደነበር አንደኛዋ ሟች ነግራኛለች በማለት አስረድቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ መመዘን አለበት በማለት የሰጠው ትችት ተቀባይነት ያለው የማስረጃ አመዛዘን መርህ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ሆኖም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ከነ ሙሉ ይዘቱና መልዕክቱ የመዘነ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ዓቃቤ ሕግ የጽሁፍ ማስረጃ አድርጎ ባቀረበው የተጠሪ ዕምነት ቃል የግል ተበዳይ ወደ ማኅበር ስሄድ ስላየሁት ቤተሰቦቹም ሄደዋል ብዬ በማሰብ ቤቱን አቃጠልኩት የሚል ፍሬ ጉዳይ አለ፡፡ ከዚህም የምንረዳው ተጠሪ በእሳት ቃጠሎ ሕይወታቸው ያለፈው የግል ተበዳይ ቤተሰቦች ወደ ማኅበር ሲሄዱ ያላያቸው መሆኑን ነው ተጠሪ ሟቾች ወደ ማኅበር ስለመሄዳቸው እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ ማኅበር ሄደዋል ብሎ ስለገመተ ብቻ ቸልተኝነት የለበትም ለማለት አይቻልም፡፡ ወቅቱ ሌሊት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የግል ተበዳይን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ሰው ከቤት ሊኖር እንደሚቻል ማወቅ ሲገባው ወይም እያወቀ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 የተደነገገውን ቸልተኝነት የሚያሟላ ነው፡፡ የሟቾች ከቤታቸው ውስጥ ተኝተው መገኘት ከተጠሪው አቅም በላይ የሆነ ኃይል ወይም የድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሰለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ ከግል ተበዳዩ ጋር በነበረው ጠብ በቂም በቀል ተነሳስቶ የግል ተበዳይን ቤት በእሳት ያቃጠለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ በለኮሰው እሳት ተቃጥለው ሰዎች ሞተዋል፡፡ ተጠሪ ቤቱን የማቀጠል እንጂ ሟቾቹን የመግደል ሀሣብ

አልነበረውም ቢባል እንኳን በቸልተኝነት ሚቾችን በመግደሉ ተጠያቂ የማይሆንበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ አልነበረም በቸልተኝነት በሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ መባል የለበትም በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13840 ኀዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/3/ በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ሊጠየቅ አይገባውም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14498 ሀምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገውን በመተላለፍ ሚች ይታይሽ አለማየሁ አለባቸው መኩሪያውና ፋሲካ መኩሪያውን በቸልተኝነት የገደለ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡ ለዚህ ጥፋቱም ከፍተኛው ፍርድ ቤት በወሰነው መሠረት በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር መቀጮ ይቀጣል ብለናል፡፡ ይህንን ቅጣት ተከትሎ እንዲያስፈጽሙ ለክልሉ ፖሊስ ኮሚሽንና ለክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ክርክር ያወጣውን ወጪ አመልካች በራሱ ይቻል ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## 7.በተደራራቢ ወይም በደጋጋሚነት የወንጀል ጥፋተኛ መሆን

### 7.1 ተደራራቢ ወንጀሎች[20]

- ግዙፍ ተደራራቢ ወንጀሎችን በተመለከተ የድርጊት መደጋገም መኖሩ እስከተረጋገጠ ድረስ የተፈፀሙት ወንጀሎች አንድ መሆን አለመሆናቸው መሰረታዊ ለውጥ የማያመጣ ሲሆን በሃሳባዊ መደራረብ ጊዜ ግን የድርጊቱ አንድ ነጠላ መሆን መሰረታዊ መስፈርት በመሆኑ ይህ አንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ መሆኑ መረጋገጡ አንቀፅ 60(ለ) ን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምሮ ተገቢውን እልባት ለመስጠት መሰረታዊ መስፈርት መሆኑን ያሳያል፡፡
- የተፈፀመው አንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ ግዙፍ ውጤቶችን ማስከተል አለማስከተሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጊቱ ከአንድ በላይ የሆኑ ግዙፍ ውጤቶችን ባያስከትልም ድርጊቱ ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን መጣሱ መረጋገጡ ግለሰቡ ሀሳባዊ የተደራረቡ ወንጀሎችን ፈፅሟል ለማለት በቂ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ነው፡፡
- ሐሳባዊ(ጣምራዊ) መደራረብ ወንጀሎች በዋነኝነት እልባት ሊሰጣቸው የሚገባው ከወ/ህ/አ.61(1) አንፃር ሲሆን በዚህ አግባብም ጥፋተኛው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ ቅጣቶች የማይቀጣው ድርጊቱ የተፈፀመው በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ

[20]የሰ/መ/ቁ 123046 (የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21

ወይም ቸልተኝነት መፈፀሙ ከመረጋገጡ ባሻገር ድርጊቶቹ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ መሆናቸው ሲረጋገጥ ለመሆኑ ከድንጋጌው አጠቃላይ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የወ/ህ/አ.61(3) ከዋናው ድርጊት በኋላ ተከታትለው ስለተፈፀሙ ድርጊቶች የሚደነግግ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተጠቃሚ ለመሆኑ ከዋናው የወንጀል ድርጊት በኋላ ተከታትለው የተፈፀሙ ድርጊቶች ለመኖራቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡[21]

የሰ/መ/ቁጥር - 123046

የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

አይሸሽም መለስ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ አዲሱ ገመቹ ተከታታይ ዘመድ ቀረቡ

ተጠሪ- የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዐ/ሕግ ሞገስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበዉ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በቸልተኝነት ሲያሽከረክር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559 ንኡስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ ገንዘብ አስከፍሎ አሳፍሯቸዉ በነበሩት በሰባት ሰዎች ላይ ሰባት በቸልተኝነት በሰዉ አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀሎችን የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉም የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ጭብጥ በሰበር አይቶ ለመወሰን ነዉ፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየዉ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ መስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ ሆነዉ ተከራክረዋል፡፡

ለክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ነዉ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሥምንት የወንጀል ክሶችን አቅርቦበታል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበዉ የመጀመሪያዉ ወንጀል ክስ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ በመተላለፍ የሰዉን ሕይወትና ጤንነት የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ እያለበት ሆኖ እያለ ይህንን ግዴታዉን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመወጣት ነሐሴ 15 ቀን 2006 ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት 1:00 ሰዓት ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-29507 ኦ.ሮ የሆነ የሕዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ እያሽከረከረ ይዞ ከሰንበ ወደ ሽኖ አቅጣጫ ሲጓዝ ሕግ እንዲጭን ከተፈቀደለት አስራ ሁለት ስዎች በላይ ሥድስት ሰዎችን በትርፍነት በመጫን በአንለላና ጠራ ወረዳ ፊጦናአላመስኖ ቀበሌ ጨለቅለቃ ከተባለዉ ልዩ ሥፍራ ሲደርስ ከአስፓልት መንገድ 11 ሜትር 40 ሳንቲሜትር ወጥቶ መኪናዉ በመገልበጡ በአደጋዉ ሟች መሰረት በደኑና ሟች ሳህለ ማርያም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዉ፣ በሕክምና ሲረዱ ቆይተዉ ሀምሌ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ሕይወታቸዉ ያለፈ በመሆኑ በከባድ ቸልተኝነት የስዉ መግደል ወንጀል ፈጽሟል፡፡

---

[21]የሰ/መ/ቁጥር 119159 (ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ የሰ/መ/ቁጥር 153690 (መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23 ፣ የሰ/መ/ቁ 226130 (ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ. 96078 (መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ በሰ/መ/ቁ 228597 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 65325 (ሕዳር 22 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13

እንደዚሁም ተጠሪ ከላይ በተገለጸዉ ሥፍራና ጊዜ በመኪናዉ ዉስጥ ተሳፋሪ የነበሩት 1ኛ ሞገስ መገርሳ 2ኛ ደሉ ወልዴ 3ኛ በሻህ ጌታነህ 4ኛ ቤዛ ሞገስ 5ኛ እሸቱ ሉቤን 6ኛ ዘዉድነሽ አለሙና እና 7ኛ አለነሽ ጋሸን በተለያየ የሰዉነት ክፍላቸዉ ላይ ጉዳት የደረሰባቸዉ በመሆኑ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ በመተላለፍ ሰባት በሰዉ አካል በቸልተኝት ጉዳት የማድረስ ወንጀሎችን ፈጽሟል በማለት በእያንዳንዱ ተጎጅ ሥም አንድ ወንጀል ክስ በጥቅል ሰባት ወንጀል ክሶችን አቅርቧል፡፡

ተከሳሽ በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት ከተረዳ በኃላ በሰጠዉ የእምነት ክህደት ቃል የወንጀል ድርጊት የፈጸመ ቢሆንም እንደ ክሱ አይደለም የሞት አደጋም ሆነ የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉ ግለሰቦች ጉዳት የደረሰባቸዉ በድንገት የኃላ ጎማ በመፈንዳቱና ሚዛኑ ወደ አንድ በኩል በማጋደሉ ነዉ፡፡ አደጋ የደረሰዉ በድንገት በመኪናዉ ላይ በደረስ ችግር ስለሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በወቅቱ መኪናዉ ዉስጥ በነበሩ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፤ ትራፊክ አደጋ ፕላን መግለጫ ሰነድና ፕላኑን ያነሳዉን ባለሙያ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሥር ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለዉ መሆኑን በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ተደራራቢ ወንጀል ክስና ማስረጃ ከመረመረ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543/3/ የተመለከተዉን በመተላለፍ በከባድ ቸልተኝት ስዉ መግደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ፡፡ እንደዚሁም አመልካች የወንጀል ሕግ ቁጥር 559/2/ በመተላለፍ ከሳሽ ባቀረባቸዉ ሰባት የወንጀል ክሶች የተገለጹትን ሰባት በቸልተኝት አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ በማለት የጥፋተኝነት ዉሳኔ ስጥቷል፡፡

የቅጣት ዉሳኔዉን በተመለከተ የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543/3/ በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘበት አንደኛዉ ክስ የእስራት ቅጣቱ እርከን ሃያ አምስት የገንዘብ መቀጮ እርከን ሰባት ላይ ይወድቃል፡፡ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 559/2/ በመተላለፍ ጥፋተኛ ለተባለባቸዉ ሰባት ወንጀል ክሶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 22 መሰረት ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ሁለት እርከን ለሰባት ወንጀሎች አስራ አራት በእርከን ሃያ አምስት ላይ ሲጨመር እርከን 39 ላይ ያርፋል፡፡ ሆኖም በወንጀል ሕግ ቁጥር 187(ለ)(2) እና በወንጀል ሕግ ቁጥር 66 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) ቅጣቱ በሕግ ልዩ ክፍል ከተደነገገዉ በላይ መብለጥ የሌለበት በመሆኑ የእስራት ቅጣቱ እርከን 32 የገንዘብ መቀጮ አርከን ሰባት ሥር ለመመደብ በህግ ተገድደናል፡፡ ተከሳሽ መልካም ፀባይ የነበረዉ መሆኑ ለጎጆዎች ካሳ መክፈሉና ቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆኑ ሶስት ማቅለያ በመያዝ በእርከን 29 ከተቀመጠዉ ቅጣት በአስር ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 5000(አምስት ሺ ብር) ገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ በማጽናት ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ያልተማረ መሀይም መሆኑ አንድ የቅጣት ማቅለያ ሆኖ ሊያዝለት ይገባል በማለት ግን የቅጣት አወሳሰን መመሪያን መሰረት አድርጎ በማስላት ተከሳሽ ከዚህ ቀደም የታሰረዉ ታስቦ በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ አመልካች ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች በድንገት በመኪናዉ ላይ በደረሰ የቴክኒክ ብልሽት አደጋዉ የደረሰ መሆኑን ገልጸዉ እያለ ጥፋተኛ መባሌ የህግ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች መጠየቅ አለበት ከተባለ እንኳን በሰባት አካል ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ መባል የለብኝም በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በ 30/04/2008ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡

የመልሱም ይዘት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድና ዉሳኔ በማስረጃ ምዘና መርህ እና በሕግ አተረጓጎም ረገድ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ የሕግ ድጋፍ ስለሌለዉ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍርድና ዉሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸውን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአሁን አመልካች በዐ/ህግ ክስ ላይ በተመለከተው  ጊዜ እና ቦታ የሰሌዳ ቁጥሩ የተጠቀሰውን ሚኒባስ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ እያሽከርከረ እያለ፤ መኪናዋ ለመጫን ከተፈቀደላት በላይ ትርፍ ሰው በመጫን አደጋው የደረስና ከመንገድ ወጥታ በመገልበጧ በሁለት ሰዎች ላይ የሞት እና በሌሎች ሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት አደጋ እንደደረሰባቸው የዐ/ህግ ማስረጃ ያረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያመለክታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህን የዐ/ህግ ምስክሮች ቃል እና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን የአሁን አመልካች ባለው የማሽከርከር ሙያ ተሳፋሪዎች በተሽከርካሪውን አሳፍሯቸው ሲጓዝ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ደንብ በመጣስ፣ ከአቅም በላይ ሰው በማሳፈር የሙያውን ግዴታ እና የስራ ልምድ በሚጠይቀው መጠን ሳሳፈራቸው የሰዎቹን ህይወት፣ ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ በአግባቡ ባለመወጣቱ አደጋው የደረሰ መሆኑ ፍሬ ጉዳይና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርደ ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ይህን ተከትሎ ፍ/ቤቱ አመልካች የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በሰጠው ትዕዛዝ የመከላከያ ምስክሮች የሌለው መሆኑን በመግልጽ ያልተከላከለ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን መዝኖ የመወሰን ስልጣኑን መሰረት በማድረግ የአሁን ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በበቂ ማስረጃ፣ አመልካች ሙያዊ ግዴታውን ባለመወጣት እና በቸልተኛነት በፈጸመው ድርጊት የሁለት ሰዎችን ህይወት እንዳጠፋ እና በሰባት ሰዎች አካል ላይ ጉዳት እንዳደረሰ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) እና 559(2) ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱን ከውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህ ችሎት ደግሞ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ሲታይ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ በህጉ አግባብ የተሰጠ ነው በማለት ከሚቀበል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የማይቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

“በእኛ በኩል በዚህ ሰበር ችሎት መታየት ያለበት አመልካች ጥፋተኛ ነው የተባለባቸው ሰባት በቸልተኝነት በሰው የአካል ላይ ጉዳት የማድረስ የወንጀል ድርጊቶቸ በወንጀል ህጉ ከተመለከተው በአንድ የወንጀል ሀሳብና በአንድ የወንጀል ድርጊት በተለያዩ ሰዎች ላይ ከደረስ ጉዳትና ተደራራቢ ወንጀሎች ተከሳሽ ተጠያቂ ከሚሆንባቸው ሌሎች ሁኔታዎች አንጻር እንዴት ይታያል? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎችን በተመለከተ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60 እና ተከታዮች ድንጋጌዎች ተመለክቶ እናገኛለን፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ሐ) እንደሚያመለክተው “ማንም ሰው ተደራራቢ ወንጀሎችን አድርጓል የሚባለው በአንድ የወንጀል የማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት ያደረገው ወንጀል አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው” በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጅ "In the case of criminal act which, though flowing from the same criminal intention or negligence and violating the same criminal provision, causes the same harm against the rights or interests of more than one person." በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው የተደራራቢ ወንጀሎች መርህ ከላይ በተገለጸው መንገድ የተቀረጸ መሆኑ

የህጉን ድንጋጌ ከሌሎች የህግ ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ በማድረግና በመተግበር በኩል ግልጽና ከችግር የጸዳ የሚያደርገው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በተለየም ከላይ የተገለጸው የድንጋጌው ይዘትና ተግባራዊ ተፈጻሚነት በወንጀል ህግ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መርህን ከሚደነግገው የወንጀል ህግ አንቀጽ 61 ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በጭብጥነት ከተያዘው ነጥብ አንጻር አንድ ሰው በቸልተኝነት በሚፈጸመው አንድ ድርጊት፣ በአጋጣሚ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ተጎጅዎች ሆነው ቢገኙ፣ ተከሳሹ መክሰስና መቀጣት ያለበት በእያንዳንዱ ተጎጅ ላይ አንድ ራሱን የቻለ የወንጀል ድርጊት እንደፈጸመ ተቆጥሮና ጥፋተኛ ተብሎ ነው ወይስ አንድ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ ነው የሚለው ነጥብ የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው፡፡ ከላይ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ በተለይም በአንድ የቸልተኝነት ወንጀል ድርጊት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ተጎጅ ቢሆኑ ውጤቱ ምንድንነው የሚለውን ለመተርጎምና ለመረዳት ህግ አውጭው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የተደራራቢ ወንጀሎችና ቅጣት መርህ ተፈጻሚ መደረጉ ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ከሚያራምዳቸው ሃሳቦች ጋር የሚሄድና የሕጉን አላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘነውም፡፡የተቀረፀበትን አግባብና የድንጋጌውን አውደንባብና መሰረታዊ ዓላማ ማገናዘብ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረቱ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው መሰረት በተከሳሹ ቸልተኝነት የሰው ሕይዎት ሕልፈት የተዳረገ መሆኑ ነው፡፡ በተከሳሹ ቸልተኝነት የሰው ሕይወት ለሕልፈት የተዳረገ መሆኑ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት ማቋቋሚያ አንዱ መሰረታዊ ሁኔታ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 የማክበጃ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ አንድ አሽከርካሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት አለበት የሚባለው ጥፋተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ እንደሆነ መሆኑን በግልፅ ተደንግጓል፡፡ “ጥፋተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ስዎችን የገደለ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ግልፅ የሆነ ደንብ ወይም መመሪያ ተላላፎ ቅጣቱ ከአምስት እስከ አስራ አምስት አመት ፅኑ እስራት እስከ አስራ አምስት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል” ከሚለው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 አቀራረፅ፣ ይዘትና አውደ ንባብ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ አሽከርካሪ በአንድ የቸልተኝነት ተግባር ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑትን ሰዎች በሕይወት የመኖር መብት በመጣስ በቸልተኝነት በመግደሉ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ በደነገገው መሰረት እያንዳንዱ ሟች ለመገደል አንድ ራሱን የቻለ በቸልተኝነት ስው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ተደራራቢ የወንጀል ክስና ቅጣት ማይወስንበት መሆኑና በአንፃሩ አንድ ከባድ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመተላለፉ ጥፋተኛ ተብሎ እንደሚቀጣ ከሚለው ድንጋጌው አውደ ንባብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጥፋተኛው በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት አንፃር የሚጠየቅ ባይሆንም ጥፋተኛው ሁለት እና ከዛ በላይ ሰዎችን መግደሉ ሊወሰንበት የሚገባውን ቅጣት ከፍ እንደሚያደርግበት የማያመለክት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ አግባብ በቸልተኝነት ሰውን መግደል ምንም እንኳን የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ላይ የሞት አደጋ ያስከተለ ቢሆንም ቅጣቱን ከፍ ከሚያደርግበት በስተቀር፤ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ በሚደነግገው መሰረት እያንዳንዱ ሟች ለመገደል አንድ ራሱን የቻለ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ የሚያሰኘውና የሚያስቀጣው ሳይሆን በድንጋጌው በተመለከተው ልዩ ማክበጃ ሁኔታ ባለበት አንድ ከባድ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ጥፋተኛ የሚባልና ቅጣት የሚወሰንበት መሆኑን ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመደንገግ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አሽከርካሪው በፈፀመው በአንድ ቸልተኝነት ተግባር በዚህ መዝገብ አከራካሪ ጭብጥ በሆነው መንገድ ሰባት ሰዎች የአካል ጉዳት ቢደርስባቸው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ ስር በተመለከተው መሰረት ሰባት በቸልተኝነት በሰው አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደፈፀመ ተቆጥሮ ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ይገባዋል ወይስ አንድ ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጠሮ ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ይገባዋል? የሚለው ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው በተሽከርካሪ በቸልተኝነት ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ ጥፋተኛ ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 ቅጣቱን ከፍ የሚያደርግበት በስተቀር፣ ተደራራቢ, በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀሎችን ፈፅሟል ተብሎ ተደራራቢ ወንጀል ክሶች እንደማይቀርቡበትና በተደራራቢ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ እንደማይቀጣ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

ይህ ከሆነ አሽከርካሪው በአንድ ቸልተኝነት ተግባር በተለያዩ ሰዎች አካል ላይ ጉዳት ሲያደርስ በቸልተኝነት ተደራራቢ አካል ማጉደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ተደራራቢ ወንጀል ክስ ሊቀርብበትና በተደራራቢ ወንጀል በመፈፀም ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ይገባዋል የሚለው የተጠሪ ክርክርና በታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ሰባት በቸልተኝነት በሰው አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል የፈፀመ ነው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መርህን ከሚደነግገው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 61 መሰረታዊ መርህ ጋር የሚጣረስና የሕጉን ድንጋጌዎች ከፍትሐዊ፣ ወጥነት እና ተገማች የሆነ የሕግ ትርጉም ከመስጠት አንፃር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የአሁኑ አመልካች ምንም እንኳን በክሱ እንደተመለከተው የሰውን አካል ደህንነት ለመጠበቅ ያለበት ግዴታ ወደ ጎን በመተው ከመኪናዋ አቅም በላይ ትርፍ ሰዎች በመጫን መኪናዋ መገልበጥ አደጋ እንዲደርስበት በማድረግ በሰባት ስዎች ላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ቢሆንም፣ በቸልተኝነት በፈፀመው አንድ ተግባር ሰባት ሰዎች አካል ደህንነት መብት በመጣሱ ብቻ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ የተመለከተው የተደራራቢ የወንጀሎችና ቅጣት መርህ ተፈጻሚ መደረጉን ህግ አዉጭዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 61 እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚያራምዳቸዉን አሳቦች ጋር የሚሄድና የህጉን አላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡ የአሁን አመልካች ምንም እንኳን በሰባት ሰዎች ላይ በተሽከርካሪው የአካል ጉዳት ያደረሰ ቢሆንም እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት እንደፈጸመ እንጅ በአንድ ቸልተኝነት ተግባር ምክንያት በደረሰው መኪና መገልበጥ በአደጋ በአጋጣሚ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ቁጥር ሰባት በመሆናቸው ሰባት ተደራራቢ በቸልተኝነት አካል ጉዳት የማድረስ ወንጀሎች እንደተፈጸሙ ተደርጎ የወንጀል ክስ ሊቀርብበትም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት አይገባም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በሰባት ስዎች ላይ የአካል ጉዳት በማድረሱ በአንድ ሰው ላይ አካል ማጉደል ካደረሰው አሽከርካሪ ጋር ወንጀሉ ክብደት በእኩል አይን የሚያየው የወንጀሉን ደረጃ በእኩል የሚሳየው አይሆንም፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን ስራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በተከሳሹ የቸልተኝነት ተግባር የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ቁጥር መሰረት በማድረግ ወንጀሉን ደረጃ እና እርከን የሚደነግግ አለመሆኑ በመመሪያው መሰረት ቅጣት በመወሰን ሂደት በግልጽ የሚታይ ክፍተት ያለበት በመሆኑ መመሪያው ሊሻሻል በተከሳሹ የቸልተኝነት ተግባር የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ቁጥር መሰረት በማድረግ ወንጀሉን ደረጃ እና እርከን ከፍ ሊያደርግ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይህ ማለት በተሽከርካሪ በቸልተኝነት ድርጊት በአንድ ሰው አካል ላይ ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ እና በሁለት እና ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች የአካል ላይ ጉዳት ያደረስ አሽከርካሪ እኩል ሊቀጡ ይገባል ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች በሚያሽከረክረው ተሽከርካሪ በቸልተኛነት በሶስቱ ሰዎች ላይ ላደረስባቸው የአካል ጉዳት እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት ተወስዶ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ ስር ጥፋተኛነት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ብለናል፡፡ በዚህ አግባብ የቅጣት ስሌቱ ሲታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ

ችሎት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረት በማደረግ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ስር በደረጃ 1 እርከን 25 ስር ስምንት አመት መነሻ ቅጣት ተወስዷል፡፡

በቸልተኛነት በሰባት ሰዎች አካል ላይ ጉዳት ማድረስን በተመለከተ እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት በመውሰድ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ ስር ጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ አመልካች በሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ያደረሰ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ይህ ድንጋጌ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 7 ድረስ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ መሰረት ደረጃ 1 ሲታይ ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት አድራሹ የሌላ ሰውን አካል ወይም ጤንነት የመጠበቅ ሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ህክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው እንደሆነም የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 7 የገንዘብ ቅጣት እርከን 1 ስር እንደሚያስቀጣ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ከደረጃ 2 እስከ ደረጃ 7 ባሉት ስር በሁለት ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰባቸው እንደሆነ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ በተዘረዘሩት ደረጃዎች የሚሸፈን ሆኖ አይገኝም፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 27/1/ መሰረት ከዚህ ቅጣት መመሪያ ወጥቶ ተገቢ ቅጣት ሊወሰን ይገባል፡፡

በዚህ አግባብ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/ቁ. 559/2/ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እስራትና አንድ ሺህ ብር የማያንስ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች እንደ አንድ አሽከርካሪ ያለበትን ግዴታ መወጣት ሲገባው የሆነው ይሁን በማለት የሚያሽከረክረውን ተሽከርካሪውን ተሽከርካሪ ጥሎ በመውረድ በሰባት ሰዎች ላይ ቀላል የአካል ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ስር አመልካች ሊቀጣ ይገባል በማለት ችሎት ያመነበት ሁለት /2/ አመት ቀላል እስራት ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ወደ ጽኑ እስራት ሲቀየር 1 ዓመት /አንድ አመት/ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከላይ የወ/ሕ/ቁ. 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር ከተያዘው መነሻ ቅጣት ጋር ተደምሮ 8 ዓመት ጽኑ እስራት ጋር ተደምሮ ዘጠኝ ዓመት እንደቅጣት መነሻ የሚወሰድ ሲሆን ይህ ደግሞ እርከን 26 ስር የሚወድቅ ይሆናል፡፡ በስር ፍ/ቤት ሶስት የቅጣት ማቅለያ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንድ ማቅለያ በድምሩ አራት ማቅለያዎች ይዘውለታል፡፡ ይህም ችሎት እነዚህን ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመውሰድ ቅጣቱ ከእርከን 26 ወደ እርከን 22 ዝቅ እንደሚል ተገንዝቧል፡፡ እርከን 22 ስር ከአምስት ዓመት ከስድስት ወር እስከ ስድስት አመት ከሰባት ወር የሚያስቀጣ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ችሎት አመልካችን ያስተምራል፣ ሌሎችን ያስጠነቅቃል በማለት ያመነበት ቅጣት አመልካች በዚህ ጉዳይ ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በስድስት ዓመት ከሥድስት ወር ጽኑ እስራት በብር 5000(አምስት ሺ ብር ሊቀጣ) ይገባል ብለናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.0235878 የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንን ዉሳኔ በማሻሻል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 02-15930 በ 10/09/2007ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.50596 ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ከሚታስብ በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራትና በብር 5000(አምስት ሺብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡ የክልሉ ማረሚያ ቤት በዚህ ዉሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች እና. ለአመልካች ይድረስ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 7.2 ተደራራቢ ወንጀሎችን ላይ የተያዙ አቋሞችን የሚያሳዩ የሰበር ውሳኔዎች

### 7.2.1 ማታለል እና ሀሰተኛ ሰነድ መገለገል ወንጀል

- ከላይ ከተዘረዘሩት ስለተደራራቢ ወንጀል ሕግ ትርጉም ውሳኔዎች በተጨማሪ ቀጥሎ ባሉት በሰበር ሰሚ ውሳኔዎች ስለተደራራቢ ወንጀሎች የተለየ አቋም ተይዟል፡፡
- የማታለልና እና ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰ/መ/ቁ 104715 (መጋቢት 2 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ በሰ/መ/ቁ 76773 (ጥቅምት 1 ቀን 2005 ዓ.ም) እና የሰ/መ/ቁ. 85237 (መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15 በሰጠው ሕግ ትርጉም አንድ ወንጀል ከመስራት የሚመነጩ የተለያዩ ድርጊቶች አንድ ወንጀል ከመስራት የመነጩ ናቸው በማለት ተጠቃልለው ሊታዩ እንደማይገባ በመግለፅ "...... ማንኛውም ሰው ሀሰተኛ ሰነድ ላሰራልህ በማለት የገንዘብ ጥቅምን ተቀብሎ ሌላ ሰውን ያታለለ እንደሆነ በኢፌድሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 699 መሰረት በሀሰተኛ ሰነድ መገልገልና በማታለል ወንጀል ሊጠየቅ እንደሚችል...." አቋም ተይዟል፡፡
- በሌላ በኩል በሰ/መ/ቁ 232750 (ጥር 25 ቀን 2015 ዓ.ም) እና በሌሎችም[22] ላይ ከላይ ከተጠቀሰው አቋም በተለየ መልኩ "..... ማንኛውም ሰው የማታለል ወንጀልን ለመፈፀም ሲል የሀሰት ሰነድ የተገለገለ እንደሆነ የመጨረሻ ግቡን የማታለል ወንጀል ለመፈፀም ሲል የሀሰት ሰነዱን በመገልገሉ በተደራራቢ ወንጀል ሊጠየቅ አይችልም...." በማለት ቀደም ሲል ከተሰጠው ውሳኔ የሚለይ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ለማሳያ ይረዳ ዘንድ ውሳኔዎቹ ከዚህ በታች ተያይዟል፡፡

### 7.2.2 የማታለል ወንጀል እና ሀሰተኛ ሰነድ መጠቀምን ሁለቱም ድርጊቶች በአንድ ድንጋጌ አይጠቃለሉም፤[23]

- አንድ ድርጊት አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ መሆኑ በሕጉ አገላለጽ የተረጋገጠ ከሆነ በአንድ ድንጋጌ ሥር ጉዳይ የሚታይ ስለመሆኑ ከወ/ሕ/ቁ 61 መሰረታዊ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ተደራራቢ ወንጀሎች መፈጸማቸው ሲረጋገጥ ደግሞ ሁለት እና ከሁለት በላይ ለሆኑ ድንጋጌዎች አጥፊው በሕጉ አግባብ የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ፤
- በአንደኛው ክስ የማታለል ወንጀል በ2ኛ ክስ ደግሞ ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት ለግል ተበዳዮች መስጠቱን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በማታለል ድርጊቱ መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሁኖ በ2ኛ ክስም በተደራቢነት ሊጠይቅ እንደሚገባ በወ/ሕ/ቁ 699 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም አመልካች ሁለቱም ድርጊቶች በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚጠቃለሉ ናቸው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡[24]

---

[22]በተመሳሳይ መልኩ በሰ/መ/ቁ 104637 (ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21 ፣ በሰ/መ/ቁ 234082 (ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም) እና 107195 (ሰኔ 4 ቀን 2007ዓ.ም) አቋም ተይዟል፡፡

[23]የሰ/መ/ቁ. 104715 (መጋቢት 02 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17

[24]በዚህ ሰበር ውሳኔ የተያዘው አቋም በሌሎች ሰበር መዝገብ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ከላይ በተገለፀው መሰረት ከሌሎች ጋር ግን ተመሳሳይ አይደለም፡፡ ቀጥሎ ያሉትን ውሳኔዎች ይመልከቱ

የሰ/መ/ቁ. 104715

መጋቢት 02 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- እንደሻው ይልማ ዳዲ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ አቶ ያሬድ አየለ - ቀረቡ መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሁለት ክሶች አቅርበዋል፡፡ አንደኛው ክስ አመልካች የወ/ሕ/ቁ 692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጉዳይ ፈፃሚ ነኝ የፍቺ የምስክር ወረቀት ላሰራልህ በማለት የግል ተበዳይ ወንድወሰን አራጋው እህት ለሆነችው ፍቅርተ አራጋው እና ባለቤቷ በማታለል በሁለት ጊዜ ክፍያ አርባ ሺህ ብር ከወሰደ በኃላ ከልደታ ክፍለ ከተማ ውልና ጋብቻ መዝገብ የተሰጠ በማስመሰል ሀሰተኛ የፍቺ የምስክር ወረቀት የሰጠመሆኑን፤ 2ኛ ክስ ደግሞ የወ/ሕ/ቁ 385(1)(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ በሀሰት የተዘጋጀ የፍቺ ምስክር ወረቀት በማዘጋጀት ለግል ተበዳይ የሰጠ በመሆኑ፤በምስክር ወረቀቶች ላይ በሚደረግ ወንጀል መከሰሱን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካችን የእምነት ክህደት ቃል በሕጉ አግባብ ከመዘገበ በኃላ አመልካች ክዶ በመከራከሩ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አዳምጧል፡፡ አመልካች በቀረቡ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን በመግለጽ በመመስከራቸው ምክንያት እንዲከላከል ታዞ የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ሰምቷል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡት ምስክሮች የአሁኑ አመልካች 40 ሺህ ብር ተቀብሎ በሀሰት የተዘጋጀ የፍቺ ምስክር ወረቀት መስጠቱን የቀረቡት የሰው ምስክሮች እንዲሁም አመልካች ለፖሊስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27(2) በሰጠው ቃል ጭምር እንዳመነ፤በአመልካች በኩል የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ አላስተባበሉም በማለት በተከሰሰባቸው ሁለቱም የህግ ድንጋጌዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149(1) መሰረት ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ቅጣትን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከመዘገበ በኃላ አንደኛው ክስ የወ/ሕ/ቁ 692(1) የወንጀል ደረጃ፣ መነሻ የእስራት ቅጣት እና መቀጮ እርከን የወጣለት በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ 5 ተጓዳኝ የእስራት ቅጣት እርከን 14 መቀጮ ደግሞ 3 በመሆኑ ፍርድ ቤቱም መነሻ ቅጣቱ 2 ዓመት ከ 9 ወር እና 2,500.00 ብር መቀጮ እንዲሆን ወስኗል፡፡ 2ኛ ክስ የወንጀል ደረጃ እና የእስራት ቅጣት መነሻ እርንከን ያልተዘጋጀለት በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ ደረጃ በመመደብ አንድ ዓመት ቀላል እስራት በመነሻነት ይዟል፡፡ ሁለቱም መነሻ ቅጣቶችን በመደመር በእርከን 17 ሥር በመክተት ፍቅድ ሥልጣኑ 3 ዓመት ከ 3 ወር እስከ 3 ዓመት ከ 11 ወር ፅኑ እስራት እና 3000,00 ብር መሆኑን በመግለጽ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አልቀረበም፡፡ በአመልካች በኩል

ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመቀበል በእርከን 14 ሥር 2 ዓመት ከ 9 ወር እና ብር 600.00 እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል የተባለ በመሆኑ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን አመልካች በሰበር ቅሬታው የጠቀሰው መሠረታዊ ነጥብ የወንጀል ድርጊት በሁለት የህግ አንቀጾች የሚያስጠይቅ አይደለም፤ የቅጣት አወሳሰን ሥርዓቱም ቀላል እስራት ወደ ጽኑ እስራት ሳይለወጥ የተደመረ በመሆኑ የወ/ሕ/ቁ 184(1)(ለ) ያገናዘበ አይደለም የሚል ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በሰጠው መልስ የማታለል እና የሀሰት ምስክር ወረቀት ማዘጋጀት ሁለቱም ድንጋጌዎች እራሳቸው የቻሉ እና አንደኛው ሌላኛውን የላካተተ በመሆኑ በሁለቱም የህግ አንቀጾች ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው፡፡ ቅጣት በተመለከተ የጽኑ እና ቀላል እስራት በወ/ሕ/ቁ 184(1)(ለ) መሰረት ያልተሰራ በመሆኑ በህጉ አግባብ ተስተካክሎ በእርከን 12 ሥር ተሰልቶ ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌለው አመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት መታየት ያለባቸው መሰረታዊ ጭብጦች፡- አንደኛ አመልካች ተጠሪ በቀረበው ክስ የተጠቀሱ የህግ ድንጋጌዎች ሥር በሁለቱም ጥፋተኛ መባሉ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?ሁለተኛ የጥፋተኝነት ውሳኔው በአግባቡ ከሆነ የቅጣት አወሳሰን ሥርዓቱስ የወ/ህ/ቁ 184(1)(ለ) እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2005 ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመርያው ጭብጥ በተመለከተ፡- በመሰረቱ አንድ ድርጊት አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ መሆኑ በሕጉ አገላለጽ የተረጋገጠ ከሆነ በአንድ ድንጋጌ ሥር ጉዳይ የሚታይ ስለመሆኑ ከወ/ሕ/ቁ 61 መሰረታዊ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ተደራራቢ ወንጀሎች መፈጸማቸው ሲረጋገጥ ደግሞ ለሁለት እና ከሁለት በላይ ለሆኑ ድንጋጌዎች አጥፊው በሕጉ አግባብ የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ በወ/ሕ/ቁ 60፣63 ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የሚመነጩ ድርጊቶች ሕግ አውጪው ራሳቸው ችለው ወንጀል እንደሚያቋቁሙ ለወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የደነገገ ከሆነም ወንጀል ፈፃሚው በሁለቱም የሕግ አንቀጾች እንደሚቀጣ ግልጽ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች በአንደኛው ክስ የማታለል ወንጀል በ2ኛ ክስ ደግሞ ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት ለግል ተበዳዮች መስጠቱን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በማታለል ድርጊቱ መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሁኖ በ2ኛ ክስም በተደራቢነት ሊጠይቅ እንደሚገባ በወ/ሕ/ቁ 699 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም አመልካች ሁለቱም ድርጊቶች በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚጠቃለሉ ናቸው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች በሁለት የህግ ድንጋጌዎች ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ የሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለመጀመሪያው ክስ የጽኑ እስራት አማራጭ የተወሰደ ሲሆን ለሁለተኛ ክስ ደግሞ የአንድ ዓመት ቀላል እስራት ወስደዋል፡፡ በጽኑ እስራት እና ቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው ሲገኙ የቀላል እስራት ወደ ጽኑ እስራት እንደሚለወጥ ፤ ስሌቱም የሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚቆጠር በወ/ህ/ቁ 184(1)(ለ) ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሁለተኛው ክስ (ወ/ሕ/ቁ 385) የአንድ ዓመት ቀላል እስራት የወሰነ ቢሆንም ወደ ጽኑ እስራት ሳይለወጥ የሁለቱም ድንጋጌዎች መነሻ ቅጣት በመደመር መወሰኑ የወንጀል ሕጉ እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ያላገናዘበ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመው የሕጉን አተገባበር ስህተት ሳያርም ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእነዚህ

ሁለቱ ምክንያቶች በሥር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመው የሕግ አተገባበር ስህተት በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሊታረም ይገባል። በመሆኑም ከላይ በተመለከተው የህግ ድንጋጌ መሰረት የሁለቱም ድንጋጌዎች መነሻ ቅጣት ሲደመር 3 ዓመት ከ 3 ወር ጽኑ እስራት እንደሚሆን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው የቅጣት ስሌት የምንረዳው ነው። በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 26(3) መሰረት መነሻ ቅጣቱ በመወሰንና በመደመር በቅጣት እርከኑ ሠንጠረዥ የሚያርፍበት የቅጣት እርከን መለየት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ መሰረት መነሻ ቅጣቱ በእርከን 15 የሚካተት ሲሆን በአመልካች በኩል በሥር ፍ/ቤት ተቀባይነት ያገኙ ሦስት የቅጣት ማቅለያዎች መኖራቸው ተረጋግጧል። በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 23(1)መሰረት በእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት እርከን አንድ ወደታች ይቀንሳል። እንዲህ በመሆኑም ቅጣቱ በእርከን 12 ከተመለከተው ከ2 ዓመት እስከ 2 ዓመት ከ 6 ወር ባለው ፍቅድ ሥልጣን ፍርድ ቤት የመወሰን ሥልጣን አለው።

ቅጣቱ ሲወሰን የወንጀል ሕጉ ዓላማ ግብ በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል ፈፃሚው ግላዊ ሁኔታዎች፤ የወንጀል አፈፃፀም ሁኔታ እና ተዛማጅ ጉዳዮች ግምት ውስጥ ይገባሉ። በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ላይ የሚወሰነው ቅጣት የሚያስጠነቅቀው፤ የሚያስተምረው፤ሌላ ወንጀል እንዳይፈፅም የሚያደርገው መሆን አለበት። በሌላ በኩል ማሕበረሰቡም በቂ ትምህርት በመውሰድ ከወንጀል ድርጊት እንዲርቅ የሚያደርገው መሆን አለበት። ስለሆነም ከላይ የገለጽነው አጠቃላይ የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች መሰረት በማድረግ አመልካች በዚህ ጉዳይ ከአሁን በፊት የታሰረበት ካለ በቅጣቱ የሚካተት ሆኖ በ 2 ዓመት ጽኑ እስራት እና 600.00 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ወስነናል።

<u>ው ሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 143927 በ5/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 102208 በ 30-10-2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195(2)(ለ)(2) ተሻሽሏል። ይፃፍ።

2. አመልካች በተከሰሰባቸው ሁለቱም ድንጋጌዎች ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል። በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የውሳኔ ክፍል ጸንቷል።

3. የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የወሰኑት እስራት ቅጣት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 195(2)(ለ)(2) በማሻሻል በሁለት ዓመት ጽኑ እስራት እና 600.00 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ወስነናል። የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤትም በዚህ ችሎት በተሻሻለው ቅጣት መሰረት ተቆጣጥሮ እስራቱን እንዲያስፈጽም ታዟል። ይፃፍ።

4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ።

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።**

### <u>7.2.3 ተደራራቢ ወንጀሎች- ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት እና የማታለል ወንጀል መፈፀም ሁለት ድርጊት በተደራቢነት የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ</u>[25]

- አመልካች ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ያልወጡትን ሰነዶችን ከመንግስት መስሪያ ቤቶች እንደወጡ በማስመሰል፤በሐሰተኛ መንገድ በማዘጋጀት የግል ተበዳይን ቤት የሸጡ መሆናቸው በአንቀፅ 696(ሐ) ስር የተመለከተውን መተላለፋቸውን የሚያሳይ ሲሆን ይህንኑ ቤቱን ለመሸጥ አድራጎት ጥቅም የዋለው ሐሰተኛ ሰነድ መሆኑ ደግሞ ይኼው አድራጎት በተገቢው ድንጋጌ በተደራቢነት የሚያስጠይቃቸው መሆኑን ከወንጀል ሕጉ

[25]የሰ/መ/ቁ. 85237 (መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15

አንቀጽ 699 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም አመልካች በአንቀጽ 696(ሐ) እና 375 ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ መባላቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2)፣58 እና ከወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር ሲታይ ተገቢ ስለመሆኑ፤[26]

የሰ/መ/ቁ. 85237

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዘካሪያስ ገ/ጻዲቅ አለማየሁ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ጉዳይ በድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይገባም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረተው ክስም በሁለት ምድብ የተከፈለ ነው፡፡አንደኛው ክስ አመልካች ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት አስቦ በቦሌ ክፍለ ክተማ ቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኘውን ንብረትነቱ የአቶ ታደሰ ሙለታ መኖሪያ ቤት የሆነውን ከተከራየ በኋላ ካርታ ላሳድስላችሁ ብሎ በውክልና ከወሰደ በኋላ ቤቱን ለመሸጥ ሲል በመታወቁ የተሠጠው ውክልና ተነስቶ ክስ ቀርቦበት ይህ ቤት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት, አግድ ተሰጥቶ እያለ ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ/ም ሐሰተኛ ሰነድ የእግድ ትእዛዝ አዘጋጅቶ እግድ እንዲነሳ ከአደረገ በኋላ የግል ተበዳይ ታደሰ ሙለታ ውክልና የተሰጠው በማስመሰል በሐሰተኛ ውክልና በመገልገል ቤቱን በብር 1,030,000.00(አንድ ሚሊዩን ሰላሳ ሺህ ብር) ለወ/ሮ ሰናይት ብርሃኑ ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ሸጦ ለግል ጥቅም በማዋል በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 696(ሐ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ ማታለል ፈፅሟል የሚል ሲሆን ሁለተኛ ክስ ደግሞ በሐሰተኛ ሰነዶች በመገልገል የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 378 ድንጋጌን ተላልፏል የሚል ነው፡፡የአሁኑ አመልካችም ክሱን ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ስድስት የሰው ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ ክሱን ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ ከተገነዘበ በኋላ የአመልካችን የመከላከል መብት በመጠበቅ የመከላከያ ማስረጃዎችን ሰምቷል፡፡ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በክሱ መሰማት ጊዜ ቀድሞ በጉዳዩ ላይ ተከሰው በነፃ የወጡ መሆኑን የገለጹ መሆኑን የተረዳ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የመከራከሪያ ነጥብ ቀድሞ አመልካች ተከሰው ነጻ

---

[26]የዚህ ሰበር መዝብ አቋም በሰ/መ/ቁ. 104715 (መጋቢት 02 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17 ላይ ሀሰተኛ ሰነድ በመጠቀም የማታለል ተግባር መፈፀም በተደራራቢ ወንጀል የሚያስጠይቅ እና ቅጣቶቹም ለየብቻ መሆን እንዳለበት ከተሰጠው ውሳኔ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በሌሎች ሰበር ውሳኔ ጋር ግን ተመሳሳይ አይደለም፡፡

የወጡበት ጉዳይ በኋላ ከቀረበባቸው ክስ ጋር ልዩነት ያለው ነው በማለት በሚል ምክንያት ውድቅ ያደረገው ሲሆን ዋናውን ጉዳይ በተመለከተም አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎች የአቃቤህግን ማስረጃዎችን ያላስተባበለ መሆኑን በመግለጽ የመከላከያ ማስረጃዎችን ውድቅ በማድረግ አመልካችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሰው በቀረቡት ሁለቱም ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ አድርጎታል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመልከቱን በመግለፅ ለሁለቱም ክሶች በድምሩ በ17(አስራ ሰባት)አመት ፅኑ እና በብር 40,000.00(አርባ ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ላይ ቀድሞ ክስ ቀርቦበት በነፃ ተለቀው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የነፃ መለቀቁ ውሳኔ ጸንቶ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ አልፈው አመልካችን በድጋሚ ክስ ቀርቦ በመቀበል ተጠያቂ በማድረግ መወሰናቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ስር የተመለከተውን የሚጥስ ነው በማለት መከራከሩንና በዚህ ምክንያት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ቀድሞ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ;ጥር 64230 ክስ ቀርቦበት በነጻ ተሰናብቶ ይኼው ውሳኔ በመ/ቁጥር 109368 በይግባኝ ቀርቦ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጸንቶ ባለበት ሁኔታ በድጋሚ ክሰ ቀርቦበት በወንጀል ተጠያቂ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለአሁኑ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በአመልካች ላይ የተሰጠው በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 696(ሐ) እና 378 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊቶቹን መፈፃማቸው ተረጋግጧል ተብሎ መሆኑን፣አመልካች በነፃ ተሰናብቼአለሁ በማለት የሚከራከሩበት ጉዳይ ደግሞ አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል ተብሎ ክስ ቀርቦባቸው የነበረ መሆኑን፣በሁለቱም ክሶች የቤቱ ባለንብረት የተባሉትና ለክርክሩ ምክንያት የተባለው የቤት ሕጋዊ ባለንብረት የሆኑት ግለሰብ አቶ ታደሰ ሙለታ የተባሉት መሆናቸውን፣አመልካች በነጻ ወጡ የተባለበት የወንጀል ድርጊት ዝርዝር ይዘቱ ሲታይም አመልካቹ ያላግባብ ለመበልፀግ ሳይሆን የንብረቱን ባለቤት በንብረቱ እንዳጠይቀምበት ለማድረግ በማሰብ ታህሳስ 30 ቀን 2002 ዓ/ም በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 ልዩ ቦታው የቦሌ ክፍለ ከተማ መስተዳደር ግቢ ውስጥ የግል ተበዳይ አቶ አጋ ሙሉታ በሰጡት ህጋዊ ውክልና ተጠቅሞ የቤት ቁጥሩ 52716 የሆነውን ኦርጂናል የቤት ካርታ ወስዶ ባለመመለሱ የግል ተበዳይ ንብረትነቱ የአቶ ታደሰ ሙሉታ የሆነውን በውክልና የሚያስተዳድሩበትን ኦርጅናል የቤት ካርታና ፕላን ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ/ም ከወሰደ በኋላ የግል ተበዳይ መልስልኝ ሲሉት ባለመመለሱ በሌላ ሰው ሃብት ያላግባብ መገለገል ወንጀል ፈጽሟል የሚል መሆኑን፣የአሁኑ ክስ ግን በሐሰተኛ ሰነድ የአቶ ታደሰ ሙሉታን ንብረት በመሸጡ ከባድ የማታላል ወንጀል ፈጽሟል፣በሐሰተኛ ሰነድም ተገልግሏል የሚል ሁኖ ድርጊቶቹ የተፀሙበት ጊዜና ሁኔታ ቀድሞ ቀርቦ ከነበረው ክስ ጋር የተለያዩ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪብሊክ ሕገ መንግስት የወንጀል መርህ ተደርገው ከተደነገጉት መብቶች አንዱ አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነት ተረግጋግቶ በተቀጣበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና መከሰስና መቀጣት የሌለበት መሆኑን የሚደነግገው አንቀጽ 23 ይገኝበታል፡፡ይህ መርህ በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ውስጥም በአንቀጽ 2(5) ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(4) መሰረት የአገሪቱ

የህግ አካል በተደረጉ አለምአቀፍ ስምምነቶች የሲቭልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 14 ስር ያስቀመጠው ድንጋጌ ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም ይህ መብት በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መሆኑ ግልጽ ሲሆን መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ በሕጉ የተቀመጡት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡አንድ ሰው በድጋሚ ልከሰስ አይገባም ብሎ ለመከራከር በሕጉ ይዘትና መንፈስ መሰረት መሟላት ያለባቸው ሕጋዊ መስፈርቶች ተከሳሹ በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ መሰረት ተከሶ የነበረ መሆኑና ቀድሞ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆን በሚገባ መረጋገጥ ስለመሆናቸው ከመርሁ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡የዚህ መርህ ዓይነተኛ አላማም ዜጎች በአንድ የወንጀል ድርጊት በተደጋጋሚ በሚቀርብ ክስ ስጋት ውስጥ ከመኖር ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡በሌላ በኩል መርሁ ተግባራዊ ሲደረግ በሕጉ የተቀመጡት መመዘኛዎችን በጥንቃቄ በማየት የተከሳሹን መብት ተገቢ በሆነ ሁኔታ ለማስከበር ከማስቻሉም በላይ አጥፊዎች ከወንጀል ድርጊት ነጻ እንዳይወጡና ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግና የወንጀል ሕጉን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ተግባራዊ መደረግ ያለበት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ የተመለከቱትን ሕጋዊ መመዘኛዎችንና ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መመልከቱና ዳኝነት መስጠቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የአመልካችን ጉዳይ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በቀድሞው ክስ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥትቶ አመልካች በነፃ የተሰናበቱ መሆኑን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥ 64230ና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 109368 የሚያረጋግጡት ሀቅ ሲሆን በእነዚህ መዛግብት የታዬው ጉዳይ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በሌላ ሰው ሃብት ያላግባብ መገልገል ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው የተከሰሱትና በኋላም ፍርድ ቤቶቹ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተጠሪን ነፃ ያደረጉበት ምክንያት አመልካች የወሰዳቸው የቤት ካርታዎች በሽያጭና በብድር ውል መያዣነት መሆኑን ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡ይህም የሆነው በክሱ ላይ የተጠቀሳን የባለቤትነት ደብተር ካርታና ፕላን እንዲያወጡ እንዲረከቡ ውክልና ሰጪው ለአመልካች ውክልና መስጠታቸው በመረጋገጡ፣የቤቱ ባለቤት ከባለቤታቸው ጋር በመሆኑን ቤቱን ለአመልካች በመሸጣቸውና በአሁኑ አመልካችና በአቶ ታደሰ ሙለታ የገንዘብ ብድር ውል ተደርጎና በፍርድ ቤት አመልካቸ አቶ ታደሰ ሙለታን በመክሰስ በመ/ቁጥር 88655 የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ለአሁኑ አመልካች የተፈረደላቸው መሆኑን በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት ፍርድ ቤቶቹ ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው ምክንያት ነው፡፡ባሁኑ ጉዳይ አመልካች የተከሰሱት የግል ተበዳይ ቤት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 165253 እግድ ተሰጥቶ እያለ ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ/ም በሐሰተኛ ሰነድ የእግድ ትዕዛዝ በማዘጋጀት እግዱ እንዲነሳ ከአደረገ በኋላ የግል ተበዳይ የአቶ ታደሰ ሙለታ ውክልና የተሰጠው በማስመሰል በሐሰተኛ ውክልና በመገልገል ቤቱን ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ሸጠዋል በሚል ነው፡፡ስለሆነም አመልካች ቀድመው በግል ተበዳይ ላይ የፍትሓ ብሔር ክስ አቅርበው የነበሩ መሆኑ ቢረጋገጥም በፍርድ ቤት የተሰጠውን እግድ ግን ለውጠዋል፣እግድ የተነሳ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃም ሐሰተኛ ነው በማለት አቃቤ ክስ መመሰረቱን በግልጽ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡አመልካች ከግል ተበዳይ ወሰዱ የተባሉትና ስለመኖሩ በመ/ቁጥር 64230 በቀረበው የወንጀል ክስ ተረጋግጧል የተባለው የውክልና ሰነድም በጥር ወር 2002 ዓ/ም ውስጥ መሻሩ አሁን እያከራከረ ባለው የወንጀል ጉዳይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል ተብሎ በአቃቤ ሕግ በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበባቸውም የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ስለመሆኑ በፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 64230 ጋር ተያይዞ ካለው የክስ ማመልከቻ ተመልክተናል፡፡እንግዲህ የግል ተበዳይ ቤት የተሸጠው በሐሰተኛ የፍርድ ቤት እግድ ማንሻ ትዕዛዝና የውክልና ስልጣን ስለመሆኑ በሰው ምስክርነትም ሆነ በፎረንሲክ ምርምራ ውጤት ማስረጃዎች በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ በቀደመው ክስ አመልካች የግል ተበዳይን በቤቱ

እንዳይገለገል አድርጓል የተባለው የቤቱን ካርታ ሊመለስ አልቻለም ተብሎ ሲሆን በሁለተኛው ክስ ግን ሐሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት የግል ተበዳይን ቤት ሸጧል በሚል ነው፡፡ በግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ወይም በፊት አመልካች የግል ተበዳይን ቤት በሕጋዊ መንገድ የገዙት ስለመሆኑም አልተረጋገጠም፡፡በመሆኑም አመልካች አሁን የቀረበበት ክስ ዝርዝር ይዘቱ፣የድርጊቱ አፈጻጸም እና ጥሰት ተደርጎበታል የተባለው የግል ተበዳይ የመብት አድማስ ቀድሞ ክስ ከቀረበበት ጉዳይ ዝርዝር ይዘት ጋር የማይገናኝ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት በአንደ ጉዳይ በድጋሚ በወንጀል የተከሰሱ መሆናቸውን ገልጸው ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አላገኘንም፡፡

የወንጀል ድርጊቶችን አፈጻጸም በተመለከተ አመልካች ግልጽ የሆነ የሰበር ቅሬታ ያላቀረበቡት ቢሆንም ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርደ ቤቶች በሚገባ ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑና ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ሲታይም የተለዬ ድምዳሜ የሚያዝበት ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ያልወጡትን ሰነዶችን ከመንግስት መስሪያ ቤቶች እንደወጡ በማስመሰል፤በሐሰተኛ መንገድ በማዘጋጀት የግል ተበዳይን ቤት የሸጡ መሆናቸው በአንቀፅ 696(ሐ) ስር የተመለከተውን መተላለፋቸውን የሚያሳይ ሲሆን ይህንኑ ቤቱን ለመሸጥ አድራጎት ጥቅም የዋሉት ሐሰተኛ ሰነድ መሆኑ ደግሞ ይኼው አድራጎት በተገቢው ድንጋጌ በተደራቢነት የሚያስጠይቃቸው መሆኑን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 699 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም አመልካች በአንቀጽ 696(ሐ) እና 375 ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ መባላቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2)፣58 እና ከወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር ሲታይ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው ድንጋጌዎች ከሚያስቀጡት የቅጣት መጠንና ከቅጣት አጣጣል መርሆዎች እንዲሁም ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 101193 ሕዳር 21፣ታህሳስ 02 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79603 መስከረም 30 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ሐ)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ለማረሚያ ቤቱ ይፃፍ፡፡

አመልካች በአንድ የወንጀል ድርጊት ድጋሚ አልተከሰሱም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>7.3 ቼክን የተመለከቱ ተደራራቢ ወንጀሎች</u>

- በተከታታይ በቂ ስንቅ የሌለውን ቼክ ለተመሳሳይ ሰው ማውጣት በተደራራቢ ወንጀል የማያስጠይቅ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ[27]
    - የወንጀል ድርጊቱ ተደጋግሞ /ተከታትሎ እና በአንድ የግል ተበዳይ መፈጸሙ ሲታይ እና አዲስ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ በመነጨ ድርጊቱን መፈጸሙን ሳይረጋገጥ አራቱም ድርጊቶች ተነጣጥለው እንደተደራራቢ ወንጀል የሚያስጠይቁ ሳይሆን በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ድርጊቶች ናቸው ነው፡፡

[27]የሰ/መ/ቁ/ 107195 (ሰኔ 04 ቀን 2007 ዓ.ም)

➢ የሥር ፍርድ ቤቶች የወንጀል ድርጊቱ ዓይነት ባህርይ በአግባቡ ሳያገናዝቡ በቼኩ ለክፍያ ቀርቦ ስንቅ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ አዲስ ቼክ ሳያወጣ አራት ክሶች እንደተደራራቢ ወንጀል መውሰዳቸው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/2/ መሠታዊ ይዘት ዓላማና መንፈስ የሚቃረን ነው፡፡

➢ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች የፈጸመባቸው አራት ድርጊቶች አዲስ ወንጀል ከመሥራት ያልመነጩ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሁነው ሳለ እንደተደራራቢ ወንጀል መቆጠራቸው አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፤[28]

የሰ/መ/ቁ/ 107195

ሰኔ 04 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አልማው ወሌ

2. ዓሊ መሀመድ

3. ሱልጣን አባተማም

4. ሙስጠፋ አህመድ

5. ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ ህሩይ ወርቁ ሽዋንግዛው - ጠበቃ ትዕግስት ታፈሰ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል አቃቤ ሕግ አጋፔ ሙሉ ወርቅ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት ነው፡፡ አመልካች የኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ፈጽሙት በተባለው ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በየደረጃው ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድና ቅጣት መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ዓቃቤ ሕግ/ተጠሪ/ በአመልካች /ተከሳሽ/ ላይ አራት ክሶች አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው ክሶች አጭር ይዘት፡- 1ኛ ክስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካች ቼኩ በሚወጣበት ወይም በባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ በ10/03/2006 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ሲሆን በቂ/ክ/ከ ቀበሌ 15/16 ክልል ልዩ ቦታው ጊዮን ሆቴል አካባቢ ለግል ተበዳይ ያሬድ ገዛኸኝ በ18/04/2006 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ ከሂሣብ ቁጥር 0171893247400 የሚመነዘር ብር 50,000/ሀምሳ ሺ.ህ/ በቼክ ቁጥር CD 6714512 እና የገንዘብ መጠኑ 20,000 ብር /ሃያ ሺ.ህ ብር/ የሆነ ቼክ ቁጥር CD 6714514 ፅፎና ፈርሞ ሰጥቶት ስለቼኮቹ በ11/07/2006 ለክፍያ ለባንክ ሲቀርብ ሂሣቡ ውስጥ በቂ ስንቅ እንደሌላቸው በመረጋገጡ በፈፀመው የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል መከሰሱ፤

---

[28]ነገር ግን በሰ/መ/ቁ. 95438 (ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ለተለያዩ ሰዎች የተሰጠ ቼክ ሲሆን በተደራራቢ ወንጀል የሚያስጠይቅ እና ለእያንዳንዱ ተደራቢ ወንጀል ቅጣት ለብቻው ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

2ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካች ቼክ በሚያወጣበት ወይም ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ በ11/03/2006 ዓ.ም ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት ሲሆን ከላይ በ1ኛ ክስ ላይ በተጠቀሰው ቦታ ለግል ተበዳይ ያሬድ ገዛከኝ በ21/06/2006 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ ከሂሣብ ቁጥር 017189324700 የሚመነዘር ብር 295,950 በቼክ ቁጥር CD 6714483 ጽፎና ፎርም ሰጥቶት ሳለ ቼኩ በ11/07/2006 ዓ.ም ለክፍያ ሲቀርብ ባንኩ በቂ ስንቅ /ገንዘብ/ በሂሣቡ ውስጥ እንሌለው በማረጋገጡ በፈጸመው የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል መከሰሱ፤ 3ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ.693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካች ቼኩ በሚወጣበት ወይም በባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ በ13/03/2006 ዓ.ም ከቀኑ 4:00 ሰዓት ሲሆን በ1ኛ ክስ ላይ በተጠቀሰው ቦታ በ1ኛ ክስ ለተጠቀሰው የግል ተበዳይ በ17/04/2006 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ ከሂሣብ ቁጥር 0171893247400 የሚመነዘር 161,000 በቼክ ቁጥር CD 6714513 ጽፎና ፎርሞ ሰጥቶ ሳለ ቼኩ በ11/07/2006 ዓ.ም ለክፍያ ሲቀርብ በሂሣቡ ውስጥ በቂ ገንዘብ እንደሌለው በመረጋገጡ በፈጸመው የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል መከሰሱ፤ 4ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ.693/1/ የተመለከተው በመተላለፍ አመልካች ቼክ በሚያወጣበት ወይም ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ በ13/06/2006 ዓ.ም ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት ሲሆን ከላይ በ1ኛው ክስ ላይ በተጠቀሰው ቦታ በ1ኛ ክስ ለተጠቀሰው የግል ተበዳይ በ24/06/2006 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ ከሂሣብ ቁጥር 017189324700 የሚመነዘር ብር 251,160 ቁጥሩ 6714538 በሆነ ቼክ ጽፎና ፎርሞ ሰጥቶት ሳለ ቼኩ በ11/07/2006 ለክፍያ ሲቀርብ ባንኩ በቂ ገንዘብ በሂሣቡ ውስጥ እንደሌለው በማረጋገጡ በፈጸመው የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል መከሰሱን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች የዓቃቤ ሕግ ክስ እንዲደርሰው ተደርጎ በጠበቃው እየታገዘ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፡፡ ድርጊቱን በተመለከተ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ቼኩ ለዋስትና እንደሰጠው እንደ ዓቃቤ ሕግ ክስ አቀራረብ ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ተሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓ.ም የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመከላከያ ምስክሮች ይዞ እንዲቀርብ ሚያዝያ 03 ቀን 2006 ዓ.ም በተያዘው ቀጠሮ የእምነት ክህደት ቃሉን እንዲያሻሽል የጠየቁ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የፈቀደለት ሲሆን አመልካች ቼኩ በወጣበት ጊዜ ወይም ለክፍያ በቀረበበት ቀን በሂሣብ ቁጥሩ በቂ ገንዘብ ሳይኖረው የሰጠው በመሆኑ በክሱ መሠረት ጥፋተኛ ነኝ በማለት የእምነት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም አመልካች በሰጠው የእምነት ቃል መሠረት ጥፋተኛ ነው በማለት በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.149/1/ መሠረት ፍርድ መስጠቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የጥፋተኝነት ውሳኔ ተከትሎ የግራቀኙ የቅጣት አስተያየት ከመዘገበ በኋላ መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ ቅጣት ወስኗል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተሰኘበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693/1/ የወንጀል ደረጃ እና የእስራት መነሻ ቅጣት የተዘጋጀለት በመሆኑ ፍርድ ቤቱም 1ኛ ክስ ደረጃ 3 የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 9 መቀጮ እርከን 1 በማድረግ 1 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት እና ብር 300 መቀጮ፤ 2ኛ ክስ ደረጃ 7 እርከን 17 3 ዓመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እና ብር 6,000 3ኛ ክስ ደረጃ 6 እርከን 15 2 ዓመት ከ9 ወር እና ብር 4,000 4ኛ ክስ ደረጃ 7 እርከን 17 3 ዓመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እና ብር 6 መቀጫ መነሻ ቅጣት ከወሰነ በኋላ በእርከን 29 የሚያርፍ ሲሆን በፍቅድ ስልጣኑ ከ10 ዓመት እስከ 12 ዓመት መቀጮው 20 ሺህ ብር መሆኑን ፍርድ ቤቱ በውሳኔው አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ቀጥሎ የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች የተመለከተ ሲሆን በዓ/ሕግ በኩል የቀረበው የማክበጃ ምክንያት ወንጀሉ ተደራራቢ ነው የሚል ሲሆን ተቀባይነት በማግኘቱ ቅጣቱ ወደ እርከን 30 ከፍ ያለ ሲሆን፣ በአመልካች /ተከሳሽ/ በኩል ከቀረቡ የቅጣት ማቅለያዎች፡- 1) ድርጊቱን አምኖ መከራከሩ (2) የዘውትር ፀባዩ መልካም

መሆኑ (3) የቤተሰብ አስተዳዳሪ (4) በሽተኛ መሆኑ (5) እና መጸጸቱና ከግል ተበዳይ መታረቁ መሠረት በማድረግ አምስት ማቅለያዎች ይዘውለት በእርከን 25 ሥር በ7 ዓመት ጽኑ እስራት እና ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በተደራራቢ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር የጥፋተኝነት ውሳኔው በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.134/1/ መሠረት የተሰጠ ስለሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 185/1/ መሠረት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም፡፡ የቅጣት ማክበጃ አያያዝ በተመለከተ በአራቱም ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣቱ ተደምሮ የተወሰነ በመሆኑ የወንጀል ድርጊቱ ተደራራቢ ነው የሚለው እንደ አንድ ማክበጃ ሊወሰድ አይገባም፡፡ በመሆኑም አንድ የቅጣት ማክበጃ በመቀነስ በእርከን 24 ሥር በ6 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በቅጣት ረገድ ብቻ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ አሻሽሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓአል፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- የወንጀል ድርጊቱ በአንድ ክስ መሸፈን ሲገባው 4 ክሶች መሆናቸው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/2/ ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- የወንጀል ድርጊቱ በወ/ሕ/ቁ 60/ሀ/ ሥር የሚካተት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ተደራራቢ የወንጀል ድርጊት ነው በማለት መወሰናቸው በአግባቡ ነው በማለት መከራከሩን ተመልክተናል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስም ድርጊቱ አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈን ነው በማለት አቤቱታው በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚያስፈልገው ዓብይ ጭብጥ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሰሰባቸው ድርጊቶች በአራት ክሶች ሥር ጥፋተኛ መባሉ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለግል ተበዳይ አቶ ያሬድ ገዛኸኝ አራት ቼኮች መስጠቱን፤ ቼኩ ለክፍያ በቀረበበት ጊዜም በሂሣብ ቁጥሩ በቂ ገንዘብ እንዳልነበረ በማመን ቃል መስጠቱን ተመልክተናል፡፡ አመልካች ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው ድርጊቶቹ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ናቸው በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የፈጸመው ድርጊት ተደራራቢ ወንጀል ነው በአራቱም ድርጊቶች ጥፋተኛ መባሉ በአግባብ ነው የሚል ስለመሆኑ ከቀረበው መልስ መገንዘብ ተችሎዋል፡፡ አመልካች በዓቃቤ ሕግ የቀረበበት ክስ ሙሉ በሙሉ አምኖ መከራከሩ እና ፍርድ ቤቱም በእምነቱ መሠረት ቅጣት መወሰኑ መዝገቡ ያሳያል፡፡ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ድርጊቱ በተደራራቢ ወንጀል የሚያስቀጣ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ጥፋተኛ በተባለት ድርጊት ድጋሚ ይግባኝ ማለት እንደማይችል በመግለጽ ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወ.ሕ.ሥ.ሥ.አ 185/1/ የተረጎመበት አግባብ እንደተመለከትነው በወንጀል ጥፋተኛ መሆኑን ያመነ ተከሳሽ ወንጀሉ ተደራራቢ አይደለም በማለት ከመከራከር የሚከለክለው ስለመሆኑ የድንጋጌው መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ አያሳይም፡፡ አመልካች ጥፋተኛ አይደለሁም የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡ አመልካች እየተከራከረ ያለው ጥፋተኛ ቢሆንም ድርጊቱ እንደተደራራቢ ወንጀል የሚወሰድ አይደለም በሚል ነው፡፡ የወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 185/1/ ድንጋጌ ሙሉ ይዘት "የተፈረደበት ሰው የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበትና በቅጣቱ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ ነገር ግን ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ያመነ ሆኖ በእምነቱ መሠረት ጥፋተኝነቱ ከተወሰነ በኋላ ስለ ቅጣቱ ልክ ወይም ቅጣቱ ሕጋዊ ላለመሆኑ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ እንጂ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት ላይ ይግባኝ ማለት አይችልም" በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና

መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው በእምነቱ መሠረት ጥፋተኛ የተባለው ግለሰብ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ይሁንና የጥፋተኝነት ውሳኔው ተቀብሎ የወንጀል ድርጊቱ እንደተደራራቢ ወንጀል የሚወሰዱ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ከቅጣት ውሳኔ ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ የሕጉ አጠቃላይ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ጥፋተኝነቱን በማመን ወንጀሉ ተደራራቢ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ነጥብ ክርክር ማንሳቱ በሕጉ የተደገፈ ነው ብለናል፡፡

አመልካች ጥፋተኝነቱ በማመን የወንጀል ድርጊቱ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈን እና አንድ ክስ ብቻ መሆን ይገባው ነበር ተብሎ የተነሳው ቅሬታ መርምረናል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ እንደተረጋገጠው ቼኮቹ የወጡባቸው ቀናት ህዳር 10፣ 11፣ 13/2006 እና የካቲት 18 ቀን 2006 መሆናቸው፤ ቼኮቹ ለክፍያ የሚቀርቡት ታህሳስ 17 እና 18፣ ህዳር 21 እና የካቲት 24/2006 ዓ.ም ስለመሆኑ፤ አመልካች በሂሣብ ቁጥሩ ውስጥ በቂ ገንዘብ እንደሌለው የተረጋገጠው አራቱም ቼኮች ለክፍያ መጋቢት 11/2006 ዓ.ም ቀርበው ባንኩ ማረጋገጫ በመስጠቱ ስለመሆኑ የዓቃቤ ሕግ ክስ ያስረዳል፡፡ አመልካች የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣቱ ወንጀል መፈጸሙን አምኖ የተሰጠው ቃል ከላይ የተመለከቱት ፍሬ ነገሮች መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ቼኮቹ በቂ ስንቅ የላቸውም ተብሎ በኋላ ለአዲስ ቼክ ማውጣቱን መዝገቡ አያሳይም፡፡ በአንድ የወንጀል ድርጊት አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈን መሆን ያለመሆኑ ለመወሰን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 60 እና 61 ድንጋጌዎች አቀራረጽ እና ይዘት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 60 መሠረት አንድ ሰው ተደራራቢ ወንጀሎች አድርጓል የሚባለው፡-

“ /ሀ/ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ማናቸውም ዓይነት ግዙፍ ወንጀሎች አከታትሎ ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

/ለ/ በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎች በመጣስ ወይም በአንድ ድርጊት ልዩ ልዩ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎች በመፈጸም ጣምራ ወንጀሎች ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

/ሐ/ በአንድ ወንጀል የማድረግ ሐሳብ ወይም ቸልተኝነት ያደረገው ወንጀል አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው በማለት ደንግጓል፡፡

ከላይ በተመለከተው ድንጋጌ አንድ ጉዳይ ተደራራቢ የወንጀል ድርጊት ነው ወይስ አይደለም? ለማለት እንደመስፈርት የተወሰዱ ነጥቦች፡- በመጀመሪያው ንኡስ አንቀጽ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ግዙፍ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ፤ በአንድ መብት /ጥቅም/ ላይ የተፈጸመ ሳይሆን ሁለት አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ወንጀሎች በሁለት ወይም በላይ በመሆኑ መብት /ጥቅም/ ላይ የሚፈጸም ድርጊት የሚመለከት ስለመሆኑ ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ በሁለተኛው ንኡስ አንቀጽ የተመለከተው ድርጊት አንድ ቢሆንም በሁለት የሕግ ድንጋጌዎች የሚያስቀጣ ተግባር ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት ያስረዳል፡፡ ሦስተኛው ንኡስ አንቀጽ ድርጊቱ አንድ ቢሆንም በተለያዩ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ያስከተለው ጉዳት መሠረት በማድረግ ከአንድ በላይ በሆነ ድንጋጌ የሚያስቀጣ ስለመሆኑ እና እንደ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የተደራራቢ ወንጀሎች ዋነኛ መለያ ባህሪ በተፈጸመው ድርጊት በመብት ወይም ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ቁጥር ከበላይ መሆን ያለመሆኑን፤ ወንጀሉ አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ መሆን ያለመሆኑን፤ ድርጊቱ በራሱ በርካታ ድንጋጌዎች ለመጣስ ምክንያት ከሆነ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች /material currence/ እንደሆነ ወይም በአንድ የወንጀል ድርጊት /ተግባር/

ልዩ ልዩ የሕግ ድንጋጌዎች መጣስ /National concurrence/ መሆኑን ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 60 ንኡስ አንቀጾች ጥምር ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ለማለት የሚቻለው ድርጊቱ በተለያዩ የወንጀል ሕግ አንቀጾች ሥር የሚያስቀጡ፤ ልዩ ልዩ የወንጀል ድርጊቶች መፈጸማቸው ሲረጋገጥ፤ ወይም ድርጊቶቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት መቆጠራቸውና በአንድ ድንጋጌ ሥር ማስቀጣታቸው ቀርቶ እያንዳንዱ ተመሳሳይ ድርጊት እንደ አንድ ወንጀል ተቆጥሮ በአንድ አንቀጽ በተደራራቢነት የሚያስከስስና የሚያስቀጣ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መሆኑን በግልጽ ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ አንድ የወንጀል ድርጊቱ በአንድ መብት ጥቅም የተፈጸመ ከሆነ፣ የወንጀል ድርጊቱ አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ ከሆነ፤ ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈን ከሆነ አድራጊው ተመሳሳይ ባህርይ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ድንጋጌዎች እንደማይቀጣ ተመልክቷል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/2/ ይዘት "በሕግ በተጠበቀ በዚያው በአንድ መብት ተደጋግሞ ወይም ተከታትለው የተደረጉ የወንጀል ተግባሮች በአንድ ወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኝነት በተደረጉ ጊዜ እንደ አንድ ወንጀል ይቆጠራል፡፡ ወንጀል አድራጊው ለዚሁ እንደ አንድ ወንጀል ለተቆጠረው እንጂ ተደጋግሞ ወይም ተከታትሎ ለተፈፀመው ለእያንዳንዱ ድርጊት አይቀጣም፡፡" በማለት የደነገገ ሲሆን የዚህ ንኡስ አንቀጽ የእንግሊዝኛ ትርጉም Article 61/2/"successive or repeated acts against the same legally ptotected right flowing from the same initial criminal intention or negnigence constitute one crime; the criminal shall be furnished for the said crime and not for each of the successive act which constitute it. የሚል ይዘት አለው፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ እንደተመለከትነው ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት /unity of quilty and penalty/ የሚለው መርህ ተግባራዊ ለማድረግ እንደ መሠረታዊ መመዘኛ የሚወሰዱ ነጥቦች /1/ አድራጊው ድርጊቶቹ ደጋግሞ ወይም አከታትሎ መፈጸሙ /2/ የወንጀል ድርጊቱ በአንድ መብት /ጥቅም ላይ መፈጸሙ /3/ ድርጊቱ አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ መሆኑ /flowing from the same criminal intention or act of negligence /4/ እና ድርጊቱ አንድ ዓላማ ለማሳካት መፈጸሙ ሲረጋገጥ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ያወጣቸው ቼኮች አራት ስለመሆናቸው ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው ቼኮቹ ከህዳር 10 እስከ የካቲት 18/2006 በተከታታይ የወጡ ሲሆኑ በተለይም በ1ኛ፣ በ2ኛ እና 3ኛ ክስ የተጠቀሱ ቼኮች በአንድ እና ሁለት ቀን ልዩነት የወጡ ስለመሆናቸው የዓቃቤ ሕግ ክስ አረጋጋጭ ነው፡፡ ለክሱ መነሻ የሆኑ ቼኮች ለክፍያ ቀርበው ገንዘብ የለም በማለት ባንኩ የመለሳቸው መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ.ም ነው፡፡ ከክርክር ሂደቱ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ቼክ የማውጣት ድርጊቱ ደጋግሞ ወይም አከታትሎ የፈጸመው ስለመሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ቼኩ የተሰጠው በክሱ ለተጠቀሰው አንድ የግል ተበዳይ አቶ ያሬድ ገዛኸኝ ነው፡፡ አመልካች ቼክ በወጣበት ወይም ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ እንደሌለው ግልጽ ቢሆንም በአመልካች እና የግል ተበዳይ ግንኙነት ስለመኖሩ የሚያመለክቱ ክርክሮች በሥር ፍርድ ቤት ቀርበዋል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የወንጀል ድርጊቱ የፈጸመበት ሁኔታ ስንመለከተው ተጠሪ እንደሚከራከረው ተደራራቢ ወንጀል ሳይሆን ድርጊቱ ተከታትሎ /ተደጋግሞ የተፈጸመ፤ የወንጀል ድርጊቱም በአንድ የግል ተበዳይ ብቻ የተፈጸመ አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ መሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ ተደጋግሞ /ተከታትሎ እና በአንድ የግል ተበዳይ መፈጸሙ ሲታይ እና አዲስ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ በመነጨ ድርጊቱን መፈጸሙን ሳይረጋገጥ አራቱም ድርጊቶች ተነጣጥለው እንደተደራራቢ ወንጀል የሚያስጠይቁ ሳይሆን በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ድርጊቶች ናቸው ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የወንጀል ድርጊቱ ዓይነት ባህርይ በአግባቡ ሳያገናዝቡ በቼኩ ለክፍያ ቀርቦ ስንቅ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ አዲስ ቼክ ሳያወጣ

አራት ክሶች እንደተደራራቢ ወንጀል መውሰዳቸው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/2/ መሠታዊ ይዘት ዓላማና መንፈስ የሚቃረን ነው ብለናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች የፈጸመባቸው አራት ድርጊቶች አዲስ ወንጀል ከመሥራት ያልመነጩ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሁነው ሳለ እንደተደራራቢ ወንጀል መቆጠራቸው የሥር ፍርድ ቤቶች መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽመዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች በተለያዩ ቀናት በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ በማውጣቱ ወይም ለክፍያ ሲቀርብ በቂ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ በፈጸመው ድርጊት በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693/1/ ሥር ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 693/1/ ሥር በአንድ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ መባሉ ከተረጋገጠ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ ቅጣት ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተሰኘበት የህግ አንቀጽ የወንጀል ደረጃ እና መነሻ የቅጣት እርከን የወጣለት ነው፡፡ አመልካች በአራቱም ቼኮች በአጠቃላይ በገንዘብ የተገኘው ጥቅም /የደረሰው ጉዳት 778,110 / ሰባት መቶ ሰባ ስምንት ሺህ አንድ መቶ አስር/ ነው፡፡ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 2/2006 ነው፡፡ በዚህ መሠረት የወንጀሉ ደረጃ 8 ሲሆን የእስራት ቅጣት መነሻ እርከኑ 19 ነው፡፡ የእርከን 19 ፍቅድ ሥልጣን ከ4 ዓመት እስከ 4 ዓመት ከ10 ወር ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የእስራት መነሻ ቅጣት 4 ዓመት ከ5 ወር ጽኑ እስራት እንዲሆን ወስኗል፡፡ መቀጮን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር የያዘ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበ ክርክር የሌለ በመሆኑ ይህ ችሎትም እንዳለ ወስዶታል፡፡ መነሻ ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ቀጥሎ መታየት ያለበት የግራ ቀኙ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በዓቃቤ ሕግ በኩል በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረው የቅጣት ማክበጃ በሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ተደርጓል፡፡ ዓቃቤ ሕግ በዚህ ረገድ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ካለመኖሩ በተጨማሪ ወንጀሉ ተደራራቢ ወንጀል አይደለም በመባሉ ምክንያት የቀረበ ማክበጃ ምክንያት የለም፡፡ በተጠሪ በኩል በሥር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኙ አምስት የቅጣት ማቅለያዎች ቀርበዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ካቀረባቸው የቅጣት ማቅለያዎች ሌላ ስለማቅረቡ ወይም መታለፉ ያቀረበው ክርክር የሌለ በመሆኑ አምስት የቅጣት ማቅለያዎቹ እንዳሉ ተይዘዋል፡፡ እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ አንድ እርከን የማስቀነስ ዋጋ ያለው ስለመሆኑ ከቅጣት መመሪያው አንቀጽ 23/4/ መረዳት ይቻላል፡፡ ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ በአንድ በኩል፤ የአጥፊው ግላዊ ሁኔታዎች በሌላ በኩል መታየት አለባቸው፡፡ በዚህ መሠረት የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ የሚያሳካ እንዲሁም አመልካች ያርማል ያስተምራል ሌሎችን አጥፊዎች ያስጠነቅቃል ብለን ያመንበት በእርከን 14 ከተደነገገው ቅጣት ጣሪያውን በመውሰድ በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 2500 መቀጮ እንዲቀጣ የሥር ፍ/ቤቶች የፈጸሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት በማረም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 149105 በ03/08/2006 የሰጠው ፍርድና ቅጣት፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.101041 በ28/02/2007 የሰጠው ፍርድ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የፈጸመው የወንጀል ድርጊት በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈን ነው ብለናል፡፡ አመልካች በወ/ሕ/ቁ. 693/1/ ሥር ጥፋተኛ ነው ብለን ወስነናል፡፡
3. አመልካች በዚህ ጉዳይ የታሰረበት ካለ በቅጣቱ የሚካተት ሆኖ እጅ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በሦስት ዓመት ጽኑ እንዲቀጣ ወስነናል፡፡ የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤትም በተሻሻለው የእስራት ቅጣት መሠረት ተቆጣጥሮ እንዲያስፈጽም የዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡ የገንዘብ መቀጮ የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ክፍል ስምንት

## 8.በሕግ የተፈቀዱ ድርጊቶች፣ የማያስቀጡ እና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች

### 8.1 ሕጋዊ መከላከል[29]

- ሕጋዊ መከላከል በወንጀል የሚያስቀጣው የራስን ወይም የሌላውን ሰው መብት ህገ ወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈጸመ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፤

- ሕጋዊ መከላከል የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትለው ተመጣጣኝ የሆነ ዘዴ ወይም መሳሪያ በመጠቀም በቅርብ መድረሱ የማይቀረውን ህገ ወጥ የሆነ ጥቃት ለመከላከል አስፈላጊ የሆነ ድርጊት መፈፀም ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፤[30]

- አመልካች በሕይወታቸው ጥቃት እንዳይደርስ ሌላ አማረጭ ያልተጠቀሙ መሆኑን ሟቹ ከያዘው መሳሪያ ተመጣጣኝነት የሌለውን መሳሪያ መጠቀማቸው በሚገባ የተረጋጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ድርጊቱ የተፈፀመው በህጋዊ መከላከል ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

የሰ/መ/ቁ. 86570

ሚያዝያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ጌታቸው ገላዬ ፈረደ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የደቡብ ክልል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ሰው የመግደል ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ባሁኑ አመልካች እና አቶ ሰይፈ ገ/ሚካኤል በተባሉት ግለሰብ ላይ በሐዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተከሳሾቹ በዋና ወንጀል አድራጊነትና ተካፋይነት ሰኔ 02 ቀን 2004 ዓ/ም በሀዋሳ ከተማ ባህል አዳራሽ ክፍለ ከተማ በአደሬ ቀበሌ ፋሚሊ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው ቤት ሟች

---

[29]የሰ/መ/ቁ. 86570 (ሚያዝያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15

[30]በሰ/መ/ቁ.226650 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 43501 (መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10

ቡቹ ወይም ብስራት ተፈሪ የተባለውን የአሁኑ አመልካች በያዘው ሽጉጥ ተኩሶ ግራ ብብቱን መትቶ እንደገደለውና የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ ደግሞ የውሲኪ ጠርሙስ ይዞ ሟች እንዳይንቀሳቀስ ያደረገውና ሟች የተመታበት ሽጉጥ ቀላህ በመሰወር የአሁኑን አመልካች የረዳ መሆኑን ዘርዝሮ ተከሳሾቹ ሆነ ብለው በፈፀሙት ከባድ የግድያ ወንጀል በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 32(1(ሀ) እና 539(1ሀ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም እንደክሱ ድርጊቱን ያለመፈፀማቸውን ጠቅሰው ጥፋተኛ ያለመሆናቸውን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም ድርጊቱን ራሱን ለመከላከል ሲሉ የፈፀሙት መሆኑን የሚያሳይ ጭብጥ አስይዘው የመከላከያ ማሰረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአመልካች ድርጊት በሕጋዊ መከላከል ስር የማይወድቅ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ጠቅሶ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ  በማድረግ የወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሰ ሲሆን ድርጊቱ የሚሸፍነው ደግሞ በአቃቤ ክስ በተመለከተው ድንጋጌ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 540 ስር ነው በማለት አመልካችን በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ያላቸው ሲሆን ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን ጋር አዛምዶ መመልከቱን ገልፆ አመልካችን በ15 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ መባላቸውን በተመለከተ ያፀናው ሲሆን ቅጣቱን በተመለከተ ግን አሻሽሎ ስምንት ዓመት ሊሆን ይገባል ሲል ምክንያቱን ጠቅሶ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበል የቀረ ሲሆን የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች  የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ድርጊቱን በሕጋዊ መከላከል ስር የሚሸፍን ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካችን በወንጀል ተጠያቂ ማድረጋቸው ከህጉ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ የአመልካች አድራጎት በሕጋዊ መከላከል ስር የማይሸፈን ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ጠቅሶ  በጉዳዩ ላይ  የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በወንጀል ድርጊት ተጠያቂ መደረጋቸው ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሟችን መግደላቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ድርጊት ሕጋዊ መከላከል ነው፡፡ በወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም በማለት መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን በወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው በማለት ውሳኔ ሊሰጡ የቻሉት አመልካች ከሟች ጋር ተጣልተው በሰዎች ከተገላገሉ በኃላ ሟች ወደ አመልካቹ በመሄድ ላይ እያለ አመልካች ሌሎች አማራጮችን ሳይጠቀሙ የጦር መሳሪያ ያልያዘውን ሟች ወደ አመልካቹ ሳይጠጋ ተኩሰው መምታታቸው በሕጋዊ መከላከል ስር የሚሸፈን አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካቹ ሟች በሕይወቴ ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል ሳንጃ ይዞ በመምጣት ጥቃት ሊሰነዝርብኝ ሲል ድርጊቱን መፈፀሜ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን ውድቅ ማድረጋቸው ያላግባብ ነው በማለት አድራጎታቸው በሕጋዊ መከላከል ስር እንዲወድቅ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ ባግባቡ

ያልታዩላቸው መሆኑን በመግለጽ የሚከራከሩ መሆኑንም ተረድተናል፡፡ ሆኖም አመልካቹና ሟቹ ተጣልተው ቆይተው ሰዎች ከገላገሏቸው በኃላ ሟቹ ወደ አመልካች የሥራ ቦታ ተመልሶ በመሄድ ላይ እያለ በሽጉጥ ጥይት ተመትቶ ስለመሞቱ ከመረጋገጡ ውጪ አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ ሟቹ በህይወት አትኖራትም ብሎ ዝቶ ከሄደ በኃላ ሳንጃ ይዞ በመመለስ ሌላ አማራጭ በሌለበት ሁኔታ ጥቃት ሊያደርስ ሲል ነው ድርጊቱ የተፈፀመው በማለት የሚያነሷቸው ፍሬ ነገሮች ፍሬነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያላረጋገጧቸው በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረት ከተሰጠው ስልጣን አንፃር በዚህ የሰበር ደረጃ ተቀባይነት የሚሰጣቸው ነጥቦች አይደለም፡፡ ይህ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተትን ከማረም ውጪ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በሕግ አልተሰጠውምና፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጧቸው ነጥቦች አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ ከሚያነሷቸው ጋር የማይጣጣሙ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረቡትን የአመልካችን ቅሬታዎችን የምንቀበላቸው ሁነው አልተገኘም በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እንዳለ ይዘን ጉዳዩ በህጋዊ መከላከል ስር የሚወድቅ መሆን ያለመሆኑን ተመልክተናል፡፡ በመሰረቱ ህጋዊ መከላከል በወንጀል የሚያስቀጣው የራስን ወይም የሌላውን ሰው መብት ህገ ወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈጸመ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪብሊክ የወንጅል ሕግ አንቀጽ 78 ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ሕጋዊ መከላከል የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትለው ተመጣጣኝ የሆነ ዘዴ ወይም መሳሪያ በመጠቀም በቅርብ መድረሱ የማይቀረውን ህገ ወጥ የሆነ ጥቃት ለመከላከል አስፈላጊ የሆነ ድርጊት መፈፀም ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 78 እና 79 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ በግልጽ ያሳያል፡፡ አመልካች በሕይወታቸው ጥቃት እንዳይደርስ ሌላ አማራጭ ያልተጠቀሙ መሆኑን ሟቹ ከያዘው መሳሪያ ተመጣጣኝነት የሌለውን መሳሪያ መጠቀማቸው በሚገባ የተረጋጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ድርጊቱ የተፈፀመው በህጋዊ መከላከል ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 541 ስር በተመለከተው አኳኋን ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን ያለፈ አድራጎት ነው እንዳይባልም ድርጊቱ የተፈፀመው አመልካቹና ሟቹ ጠብ አስነስተው በሰዎች ተገላግለው ከተለያዩ በኃላ በመሆኑ ቅጣትን የሚያቀሉ ምክንያቶች ሰውን የመግደል ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጡት ነጥቦች ስንነሳ የአመልካች አድራጎት በህጋዊ መከላከል ስር የሚሸፈን ሁኖ ስላላገኘነው በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡ ሌላው አመልካች በቅጣት አወሳሰን ጊዜ የበታች ፍርድ ቤቶች የወንጀሉን ደረጃ ከባድ ነው በማለት መመደባቸው ተገቢ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ውሳኔ ሲሰጥ የያዘው ድምዳሜ መሰረት ያደረገ እንጂ ይሕ የሥር ፍርድ ቤት ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተለውጦ ወንጀሉ መካከለኛ ደረጃ ተብሎ የተመደበ መሆኑን መሰረት ያላደረገ የክርክሩን ሂደት የማያሳይ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም አመልካች በወንጀል ተጠያቂ ናቸው ተብሎ በተራ ቁጥር የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላላገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12474 ጥቅምት 14 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58175 ታህሳስ 04 ቀን 2005 ዓ.ም ቅጣቱ ብቻ ተሻሽሎ የፀናው እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር58330 ታህሳስ 18 ቀን 2005 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡

2. የአመልካች ድርጊት በሕጋዊ መከላከል የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
3. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

## ክፍል ዘጠኝ

## 9.ቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎች እና መመሪያ[31]

## 9.1 የእሥራት ቅጣት አወሳሰን[32]፣ የሞት ቅጣት[33] እና የገንዘብ መቀጮ[34]

- የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን ስለ መሆኑ[35]፣ አንቀጽ 179 የቅነሣውን ገደብ የሚያሳይ ሲሆን ከዚህ መደበኛ ቅነሣ በተጨማሪ ልዩ ቅነሣ ለማድረግ እንደሚቻልም ህጉ በአንቀጽ 180 ስር አስቀምጧል፡፡ በህጉ አንቀጽ 86 ቅጣትን በማቅለልም ሆነ በማክበድ ረገድ ከህጉ አንቀጽ 179፣ 182 ውጪ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥማቸው ዳኞች ምክንያታቸውን በመግለፅ ቅጣቶችን ለመቀነስ ወይም ለማክበድ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡
- ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን እንዲተገብሩ በሚደነግገው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍና የቅጣቱ ድምር ውጤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ሃያ አምስት አመት ጽኑ እስራት ሊበልጥ እንደማይችል አስገዳጅ ገደብ በሚጥለው በወንጀል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ መካከል በይዘትም ሆነ በተግባራዊ አፈጻጸማቸው ክፍተትና አለመጣጣም ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡[36]

---

[31] ይህ የሰበር ውሳኔ ቀደም ሲል የነበረውን የወ/ቅ/አ/መ ቁጥር 1/2002 ወይም 2/2006 መሰረት ያደረገ እንጂ መመሪያ ቁጥር 3/2017 የሚመለከት አይደለም፡፡
[32] የሰ/መ/ቁ.92296 (ህዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17
[33] የሰ/መ/ቁ 47831 (ሰኔ 3 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12
[34] የሰ/መ/ቁ 88542 (ሐምሌ 17 ቀን 2005ዓ.ም) ቅፅ 20
[35] በሰ/መ/ቁ123046 (የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21
[36] የሰ/መ/ቁ119159 (ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 20፣ የሰ/መ/ቁ 226508 (መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ. 239931 (ጥቅምት 07 ቀን 2016 ዓ/ም) ፣ በሰ/መ/ቁ. 96503 (ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ 62332 (ግንቦት 29 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 186919 (ታሕሳስ 27 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣ የሰ/መ/ቁ 122766 (ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21 ፣ የሰ/መ/ቁ 95438 (ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16፣ የሰ/መ/ቁ 21411 (ጥቅምት 5/2000) ቅፅ 7 ፣ የሰ/መ/ቁ 48956 (መጋቢት 10 ቀን 2002ዓ.ም) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ 95440 (ሰኔ 4 ቀን 2006ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 103448 (የካቲት 16 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 105289 (መጋቢት 15 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ የሰ/መ/ቁ 107219 (ሐምሌ 1 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ የሰ/መ/ቁ 111006 (ሐምሌ 17 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ የሰ/መ/ቁ 135787 (መስከረም 24 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22

የሰ/መ/ቁ.92296

ህዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1. አንዱዓለም አራጌ

2. ናትናኤል መኮንን ጠበቆች አቶ ደርበው ተመስገንና አቶ አበበ ጉታ ቀረቡ

3. ክንፈሚካኤል ደበበ

ተጠሪ፡- የፌደራል ዓቃቤ ህግ አቶ ወንድምአገኝ ብርሃኑ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በየግላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 112546 የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔና፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 83593 ጉዳዩን በይግባኝ ካየ በኋላ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ሥለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ተጠሪ አመልካቾች የሽብርተኝነትና ከፍ ያለ የመክዳት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ያቀረበውን የወንጀል ክስና ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው የወንጀል መዝገብ ቁጥር 112546 ተጠሪ ከሳሽ፣ አንደኛው አመልካች አንደኛ ከሳሽ፣ሁለተኛው አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ እና ሶስተኛው አመልካች አምስተኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. ከሥር የክርክሩን አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተረዳነው፣ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾችና ሌሎች ተከሳሾች በአራት ወንጀል ክሶች የጠቀሳቸውን የወንጀል ሕግና የአዋጅ ቁጥር 652/2001 ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካቾችና በሌሎች ተከሳሾች ላይ ካቀረባቸው አራት ክሶች ውስጥ፣ አመልካቾች በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑት ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/፣ አንቀጽ 38 እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 252 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ በመተላለፍ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ሚስጥሮችን በመሰብሰብ ለኤርትራ መንግስት አሳልፈው በመሰጠት የስለላ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በአምስተኛው ተራ ቁጥር ያቀረበውን የወንጀል ክስ የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ባለማቅረቡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾችና ሌሎቹ ተከሳሾች በነጻ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ክስና ማስረጃ፣ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት፣በመመርመርና በመመዘን በአመልካቾች ላይ ጥፋተኛኝነትና የቅጣት ውሳኔ የሰጠው ተጠሪ ባቀረበባቸው በሶስት የወንጀል ክሶች የተገለጹትን የወንጀል ድርጊቶች መፈጸማቸው በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል በማለት ነው፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት

የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 4፣ የተመለከተውን በመተላለፍ፣የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣የተመለከተውን በመተላለፍና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ክሱ የዘረዘራቸውን የወንጀል ድርጊቶች ዋና ወንጀል አድራጊና ተካፋይ በመሆን የፈጸሙ መሆናቸው በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል በማለት የጥፋኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002ን መሰረት በማድረግ አንደኛው አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፣

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት፣

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ ሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና፤

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248 (ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት፣በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ሲደመር ሰላሳ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚሆን በቅጣት ውሳኔው አመላክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የጽኑ እስራት ቅጣት ከሃያ አምስት የማይበልጥ መሆኑን በመግለጽ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2005 ከፍተኛው ጣሪያ ሃያ አምስት ዓመት እርከን 37 ላይ ይወድቃል፡፡ አንደኛ አመልካች ከዚህ በፊት በጽኑ እስራት ተቀጥቶ የነበረ በመሆኑ አንድ እርከን ከፍ ብሎ እርከን 38 ላይ እንደሚወድቅ በውሳኔው አስፍሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላቀረበ በመሆኑ በእርከን 38 ከተቀመጠው ቅጣት በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በውሳኔ ሰጥቷል፡፡

4. ሁለተኛው አመልካች በተመለከተ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፤

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት፣

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘውን ቅጣት ስምንት ዓመት ፅኑ እስራትና፣

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት፣ መሆኑን በቅጣት ውሳኔው አመላክቷል፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(1) መሰረት ሲደመር አርባ ዓመት እንደሆነ ነገር ግን የጽኑ እስራት ከሃያ አምስት የማይበልጥ መሆኑን በመግለጽ፤የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 እርከን 37 ላይ የሚወድቅ መሆኑን፣ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ያልቀረበ መሆኑንና፤ሁለተኛ አመልካች ወንጀል ፈጽሞ የማያውቅ በመሆኑ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያለው መሆኑን ገልጾ ሶስት እርከን ተቀንሶለት እርከን 34 ላይ ይወድቃል፡፡ በዚህ እርከን የተመለከተው የቅጣት ሬንጅ ከ

15 ዓመት እስከ 18 ዓመት የሚደርስ መሆኑን አስፍሮ ሁለተኛ አመልካች 18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. ሶስተኛው አመልካች በተመለከተ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፣

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ ሃያ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት፣

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ ሥምንት ዓመት ጽኑ እስራትና፣

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት መሆኑንና፣በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ሲደመር አርባ ዘጠኝ ዓመት መሆኑን ቅጣት ውሳኔው አመላክቷል፡፡ ነገር ግን የጽኑ እስራት ከሃያ አምስት ስለማይበልጥ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 እርከን 37 ላይ ይወድቃል፡፡ ሶስተኛ አመልካች በችሎት መድፈር ስምንት ወር በመቀጣቱ የዘወትር ጸባዩ መልካም ነው ብሎ ለመያዝ የማይቻል መሆኑን ገልጾ በእርከን 37 የተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ከሃያ ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ነው፡፡ ሶስተኛ አመልካች የፈጸማቸው የወንጀል ክብደቶችና ግላዊ ሁኔታ በማየት በሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6. አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑት ሌሎች ይግባኝ ባዮች ጋር በማጣመር አይቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ስህተት ያለበት ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔውን ሽሮ አመልካቾች በነጻ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

7. ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንደኛ፣ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበራቸው ተሳትፎ መካከለኛ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ሀ) አንደኛ አመልካች በሁለቱ ወንጀሎች መካከለኛ ደረጃ ላይ ተመድቦ በሥር ፍርድ ቤት የተወሰነበት 32 ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት በወንጀል ሕጉ ከተመለከተው ከሃያ አምስት ዓመት በላይ በመሆኑ ቅጣቱ ከእርከን 37 እንደሚሆንና አንደኛ አመልካች ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማቅለያ ያላቀረበና አንድ የቅጣት ማክበጃ ያለበት በመሆኑ በእርከን 38 መነሻ ተደርጎ ቅጣቱ ሲሰላ የሥር ፍርድ ቤት በአንደኛው አመልካች ላይ የሰጠውን የእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለ) ሁለተኛ አመልካችን በተመለከተም የሥር ፍርድ ቤት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ደረጃ እንደሆነና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ደረጃ ነው በማለት ያስቀመጠውን የቅጣት መነሻ እንዳለ በመቀበል፣ በሁለቱ ወንጀሎች የስር ፍርድ ቤት የወሰነው መነሻ ቅጣት ሲደመር ሰላሳ ሁለት ዓመት በወንጀል ሕጉ ከተደነገገው 25 ዓመት በላይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱ እርከን 37 መነሻ በማድረግ ሁለተኛው አመልካች ያቀረበውን አንድ ቅጣት ማቅለያ በመቀበል በእርከን 34 ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ በ18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የስር ፍርድ ቤት የወሰነውን የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

ሐ) ሶስተኛ አመልካች በተመለከተ በችሎት መድፈር መቀጣቱ አመልካች የወንጀል ሪከርድ የሌለበት በመሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝለት እንደሚገባ ያቀረበውን ጥያቄ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛው አመልካች በችሎት መድፈር ወንጀል ተቀጥቷል በማለት በቅጣት ማቅለያነት አለመያዙ ስህተት መሆኑን ገልጾ ይህ ማቅለያ ሲያዝ ደረጃው ከእርከን 37 ወደ እርከን 34 የሚቀንስ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የወሰነውና ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ተገቢ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ተሻሽሎ ሶስተኛው አመልካች በአሥራ ስድስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሌላ አነጋገር ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አጽንቶ፣ በሶስተኛው አመልካች ላይ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡

8. አመልካቾች ሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ዝርዝር ይዘት ከላይ የተገለጸው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡ አመልካቾች በጋራ ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ጥፋተኛ ተብለን የተቀጣነው የግዙፍ ተግባር፣ ሃሳብና የህግ ሁኔታዎች ባልተሟሉበትና በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ነው፡፡

ወንጀሎቹን ለመፈጸማችን ከሳሽ በበቂ ማስረጃ ባላስረዳበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ሊሻር ይገባዋል፡፡አመልካቾች በይግባኝ ሰሚው ችሎት ጥፋተኛ የተባልንባቸው ሁለት የህግ ድንጋጌዎች በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሃሳብ የተፈጸሙ መሆኑን የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ የሚያሳይ በመሆኑ በሁለት ወንጀል ጥፋተኛ መባላችን የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ መርህና ይህ ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሻረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካችዎች በስር ፍርድ ቤት በሶስት ወንጀሎች ጥፋተኛ ናቸው ተብለን የተወሰነብን የቅጣት ውሳኔ፣በይግባኝ ሰሚው ችሎት በአንደኛው ወንጀል ነጻ ተብለን በሁለት ወንጀሎች ብቻ ጥፋተኛ በተባልንበት ሁኔታ ሳይሻሻል እንዳለ የሚጸናበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

9. ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች ላቀረቡት የሰበር አቤቱታ የካቲት 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን

አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የግዙፍ ተግባር፣ ሀሳብና የህግ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ጥፋተኛ ተብለናል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ አመልካቾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 የፈጸሙት ወንጀል፣ አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ከፈጸሙት ከፍ ያለ የክዳት ወንጀል የተለያዩ ናቸው፡፡ ሁለቱም ወንጀሎች ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ወንጀሎች በመሆናቸው አመልካቾች በአንደኛው ወንጀል ብቻ ጥፋተኛ ልንባል ይገባል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት የለውም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች ለፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ ጥፋተኛ መባል የለባቸውም በማለት ቢወስንም፣ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካቾች ላይ ባጸናቸው ሁለት የወንጀል ድርጊቶች በአንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም፡፡ ሶስተኛውን አመልካች በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎታል፡፡ ስለዚህ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች መጋቢት 11 ቀን 2006 በተጻፈ የመልስ መልስ በሰበር አቤቱታቸው ያነሷቸውን ነጥቦች በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

10. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት፣የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ላይ ካስተላለፋቸው ሶስት የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ውስጥ ለፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1፣ በመተላለፍ ወንጀል የፈጸሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ሽሮ፤ አመልካቾች ጥፋተኛ መባል የሚገባቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ የተመለከተውን በመተላለፍ በማሴር፣ በማነሳሳት፣በማቀድና በማዘጋጀት ወንጀልና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀፅ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ከፍ ያለ የክዳት ወንጀል ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሶስተኛው አመልካች የሰጠውን ቅጣት ከማሻሻልና ከማስተካከል ውጭ በአመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ሳያደርግ መወሰኑ ሕጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

11. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት በተፈረጀውና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ የጦርነት፣የአመጽና ሌሎች የወንጀል ተግባራትን የሚፈጽመው የግንቦት 7 አሸባሪ ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ በአገር ውስጥ ካሉት የድርጅቱ አመራሮች ጋር በሕቡዕ በመገናኘት፣ የሽብር ተልዕኮ በመቀበል ፣ለዚሁ የሽብር ተግባር አጋዥ የሚሆኑ ሰዎችን በመመልመል፣ ወደ ኤርትራ ለወታደራዊና ፖለቲካዊ ሥልጠና በመላክ እንደዚሁም ስለ ግንቦት 7 የፖለቲካ ዓላማ፣ ጉዞ መመሪያና ወታደራዊ አደረጃጀት ለአባላት ገለጻ በመስጠት፣ የታቀደውን የሽብር ተግባር በቀጥታ በመምራት፣ በህቡዕ የሚተላለፈውን ገንዘብ ተቀብሎ የሽብር ወንጀል ፈጻሚዎች ያስተላለፉና የሽብር ዓላማ ያላቸውን ስብሰባዎችን በመጥራት፣ በመምራትና በተለያዩ የሽብር ተግባሮች ላይ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ዋና ወንጀል አድራጊና ሙሉ ተካፋይ በመሆን፣ በማሴር፣ በማነሳሳት፣ በማቀድና በማዘጋጀት ወንጀል የፈጸሙ ስለመሆናቸው ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጦባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾች ወሩና ቀኑ ተለይቶ ከማይታወቅበት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ

የጦርነት፣ የአመጽና ሌሎች የወንጀል ተግባራትን የሚፈጽመው የግንቦት 7 አሸባሪ ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ ኢትዮጵያ ጋር በሰላማዊ ሁኔታ ሳይሆን በጦርነት ሁኔታ ከሚኖረውና በጠላትነት በመሰለፍ በማናቸውም መንገድ ኢትዮጲያን የማተራመስ አጀንዳ ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በህቡዕ በመገናኘት፣ ለኤርትራ መንግስት የሚጠቅሙ የተለያዩ ተግባራትን ይፈጽሙ እንደነበር ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጦባቸዋል፡፡

12. እኛም አመልካቾች ከላይ የተገለጹትን ሁለት ወንጀል ድርጊቶች የፈጸሙ ስለመሆናቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የደረሱበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ሙሉ በሙሉ እውነት ናቸው በማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት በመቀበል እነዚህ አመልካቾች የፈጸሟቸው ሁለት ድርጊቶች ጥፋተኛ የሚያስብሉት በአንድ ወንጀል ነው ወይስ በሁለት ወንጀል የሚለውን ነጥብ መርምረናል፡፡ አመልካቾች በአሸባሪነት የተፈረጀው የግንቦት 7 ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ በአገር ውስጥ ካሉት የድርጅቱ አመራሮች ጋር በሕቡዕ በመገናኘት፣የሽብር ተልዕኮ በመቀበል፣ለዚሁ የሽብር ተግባር አጋዥ የሚሆኑ ሰዎችን በመመልመል፣ ወደ ኤርትራ ለወታደራዊና ፖለቲካዊ ሥልጠና በመላክ እንደዚሁም ስለ ግንቦት 7 የፖለቲካ ኣላማ፣ ጉዞ መመሪያና ወታደራዊ አደረጃጀት ለአባላት ገለጻ በመስጠት ፣ የታቀደውን የሽብር ተግባር በቀጥታ በመምራት፣ በህቡዕ የሚተላለፈውን ገንዘብ ተቀብሎ የሽብር ወንጀል ፈጻሚዎች ያስተላለፉና የሽብር ዓላማ ያላቸውን ስብሰባዎች በመጥራትና በመምራት በተለያዩ የሽብር ተግባሮች ውሳኔ በማሳለፍ የፈጸሙት የማሴር፣ የማነሳሳት፣የማቀድና የማዘጋጀት ድርጊት ራሱን የቻለ ወንጀል ድርጊት እንደሆነና ከአሥራ አምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት፣ በእድሜልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 4፣ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

13. አመልካቾች ኢትዮጵያ ጋር በሰላማዊ ሁኔታ ሳይሆን በጦርነት ሁኔታ ከሚኖረውና በጠላትነት በመሰለፍ በማናቸውም መንገድ ኢትዮጵያን የማተራመስ አጀንዳ ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በህቡዕ በመገናኘት፣ ለኤርትራ መንግስት የሚጠቅሙ የተለያዩ ተግባራትን መፈጸማቸው ራሱን የቻለ የወንጀል ድርጊትና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) መሰረት ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት፣ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ አመልካችዎች ሁለቱም የወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሃሳብ ማለትም ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል የመናድ ኃሳብ በመሆኑ በሁለቱ ወንጀሎች ጥፋተኛ መባላችንና የቅጣት ውሳኔ መስጠቱ ሕጋዊ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካችዎች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙባቸው ተደራራቢ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የመጣስ አድራጎት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(ሀ) የተደነገገው መሰረታዊ መርህ ተፈጻሚ የሚሆንበት ሁኔታ የለም፡፡ በአንጻሩ ወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187(1) መሰረት እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 65 በግልጽ ይደነግጋል፡፡

14. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187(1) ወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ (አንቀጽ 65 ) ፍርድ ቤቱ የአካባቢ ሁኔታዎችን ሲመረምር በተለይም ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ሕግ መጣሱን ወይም ግልጽ የሆነ መጥፎ ጸባይ ማሳየቱን ባመነ ጊዜ በአንቀጽ 184 መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ለመወሰን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ድንጋጌ ይዘት ስንመለከተው ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነጻነትን የሚያሳጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ እያንዳንዱ ተደራቢ ወንጀል ቅጣት ተወስኖ፣ ቅጣቱ እንደሚደመርና የቅጣቱ አይነት በሕጉ ከተመለከተው ከፍተኛ ቅጣት ሊበልጥ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካቾች የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(ሀ) በመጥቀስ

ያቀረቡት ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 65፣ አንቀጽ 187(1) እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተደነገገውን የቅጣት አወሳሰን መርሆች ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

15. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ህጋዊነት በተመለከተም አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉበት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ ሕጉ መነሻ ቅጣት አድርጎ በደነገገው አሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራትና በሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መካከል ያለው ልዩነት አስር ዓመት ነው፡፡ ይህም በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወራት፣ በመካከለኛ ደራጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወራት፣ እስከ ሃያ አንድ አመት ከስምንት ወር፣ በከፍተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ሃያ አንድ አመት ከስምንት ወር፣ እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ካወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ለመረዳት ይቻላል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሶስቱም አመልካቾች በዚህ ወንጀል ያላቸው ተሳትፎ በመመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ መሆኑን በውሳኔው አስፍሯል፡፡

16. አመልካቾች ጥፋተኛ ሆነው በተገኙበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የቅጣት ዝቅተኛው መነሻ ሆኖ በተደነገገው አምስት ዓመት ጽኑ እስራትና እና ከፍተኛ በሆነው ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መካከል ያለው ልዩነት ሃያ ዓመት ነው፡፡ይህም በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አንድ ዓመት ከሥምንት ወራት፣ በመካከለኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ አንድ ዓመት ከስምንት ወራት እስከ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወር፣ በከፍተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወር፣ እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት በማድረግ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሶስቱም አመልካቾች በዚህ ወንጀል ያላቸው ተሳትፎ በመመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ መሆኑን በውሳኔው አስፍሯል፡፡

17. የጽኑ እስራት ቅጣት ከሃያ አምስት አመት ሊበልጥ እንደማይችል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጨረሻው ፓራግራፍ እና ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ በመሆኑ የሶስቱም አመልካቾች ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያ 25 ዓመት ጽኑ እስራት ሲሆን ይህም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት እርከን 37 ላይ የሚወድቅ ይሆናል፡፡ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ መሰረት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላቸው መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አንደኛ አመልካች የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የሌለው መሆኑንና አንድ የቅጣት ማክበጃ የቀረበበት በመሆኑ በእርከን 38 ላይ የሚወድቅ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተስማምተዋል፡፡ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን የሚቀንስ መሆኑን፣የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በውሳኔያቸው አስፍረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ሶስት እርከን ተቀንሶላቸው እርከን 34 ላይ በማሳረፍ ፈቃደ ሥልጣናቸውን ተጠቅመዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የተሰጣቸውን ፈቃደ ሥልጣንና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 88(2) የተደነገገውን መሰረት በማድረግ አንደኛ አመልካች በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣና ሁለተኛው አመልካች በአስራ ሥምንት ዓመት ጽኑ እስራት ያስተላለፉት የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤት በሶስተኛ አመልካች ላይ ያስተላለፈውን የሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 2(ለ)2

መሰረት በማሻሻል በአስራ ስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

18. የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን ተፈጻሚ ማድረግ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይህም አንድ ሰው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎችን ከፈጸመና ወንጀሎቹ ነጻነትን በሚያሳጣ ቅጣት የሚያስቀጡ ከሆነ ለእያንዳንዱ ወንጀል ሊቀጣ የሚገባውን ቅጣት በመወሰንና ቅጣቱን በመደመር በወንጀለኛውላይ የሚወሰነውን ቅጣት ለማስላት የሚያስችል ቅጣት አወሳሰን መርህ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድንጋጌው ድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህ የሚገድብና ውጤት አልባ የሚያደርግ ደንብ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በያዝነው ጉዳይ በጽኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሁለት ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመዋል፡፡ እንደዚህ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ለሁለቱ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰኑት ቅጣት የድምር ውጤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፍተኛ የጽኑ እስራት ቅጣት ሆኖ ከተደነገገው ሃያ አምስት አመት ጽኑ እሰራት ሊበልጥ እንደማይችል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ ገደብ ያስቀምጣል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ የተቀመጠው ገደብ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ፣በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍ መሰረት በጥፋተኛው ላይ ሊወሰን የሚገባው ድምር የቅጣት ውጤት ከሃያ አምስት ዓመት በላይ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የቅጣት ድምር ውጤቱን ወደ ሃያ አምስት ዓመት ዝቅ በማድረግ እንዲወስኑ የሚያስገድድና ሕግ አውጭው በአዲስ መልክ በወንጀል ሕጉ ያስገባውን የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን ውጤት አልባ የሚያደርግ ገደብ ነው፡፡

19. ይህም ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን እንዲተገብሩ በሚደነግገው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍና የቅጣቱ ድምር ውጤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ሃያ አምስት አመት ጽኑ እስራት ሊበልጥ እንደማይችል አስገዳጅ ገደብ በሚጥለው በወንጀል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ መካከል በይዘትም ሆነ በተግባራዊ አፈጻጸማቸው ክፍተትና አለመጣጣም ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሆኖም ህጉ ባለው ክፍተትና አለመጣጣም አመልካቾች ተጠቃሚ እንጅ ተጎጅ አይደሉም፡፡ ስለሆነም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በመጀመሪው ፓራግራፍ የደነገገውን የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህ ዋጋ በማያሳጣ ሁኔታ ለተደራራቢ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ የሚወስነው ድምር የቅጣት ውጤት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ሃያ አምስት ዓመት መብለጥ የለበትም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ የጣለውን አስገዳጅ ገደብ ማሻሻል ለህግ አውጭው የስራ ኃላፊነትና ተግባር ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ካላይ በገለጽናቸው ወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች የሚታየው ክፍተት አመልካቾችን መብት የሚያጣብብ ሳይሆን እነርሱን በሚጠቅም መልኩ የተተረጎመና ሥራ ላይ የዋለ በመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ላይ የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ማጽናቱና በሶስተኛው አመልካች ላይ የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት ጸንቷል፡፡

2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 83593 በአመልካቾች ላይ የወሰነው የቅጣት ውሳኔ የጸና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 9.2 የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ[37]

- በወ/መ/ሕግ ቁ. 107 እንደተደነገገው ጽኑ እስራት የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ 25 /ሃያ አምስት/ ዓመት ቢሆንም፤ በሕጉ ልዩ ክፍል የቅጣቱ መነሻ ከአንድ ዓመት በላይ ከፍ ብሎ ከተወሰነ ግን በሕጉ አግባብ ያላቸው የማቅለያ ምክንያት ካልተገኙ በቀር እንደመነሻ የሚያዘው ይኸው በልዩ ክፍል የተመለከተው ነው፡፡
- በያዝነው ጉዳይም ቅጣቱ መወሰን ያለበት በዚህ መሠረት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የጠ/ፍ/ቤቱ ከግምት ውስጥ ያስገባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጠሪ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከአንድ /1/ ዓመት በታች ሊወርድ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡[38]

የሰ/መ/ቁ. 34521

ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች፡-** የአማራ ብ/ክ/መ/ ፍትሕ ቢሮ

**ተጠሪ፡-** ስንታየሁ ተፈራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተጠሪ በሰው ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል የቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክሱን የሰማው የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ በቅድሚያ የተጠሪን የእምነት ክህደት ቃል ከተቀበለ በኋላ ተጠሪ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለቱ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን ምስክሮች ሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ እንዲከላከል ብይን በመስጠት

---

[37]የሰ/መ/ቁ. 34521 (ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7፣

[38]የሰ/መ/ቁ 53612 (ሚያዚያ 25 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10፣ የሰ/መ/ቁ 59356 (ሰኔ 3 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 47831 (ሰኔ 3 ቀን 2003ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 82572 (ጥር 1 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 14፣ የሰ/መ/ቁ 100736 (ሰኔ 23 ቀን 2009ዓ.ም) ቅፅ 21፣ የሰ/መ/ቁ 131705 (ሚያዚያ 16 ቀን 2009ዓ.ም) ቅፅ 21፣ የሰ/መ/ቁ 161791 (የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 24፣የሰ/መ/ቁ 171943 (ሕዳር 26 ቀን 2012ዓ.ም) ቅፅ 24

የመከላከያ ምስክሮችን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ተጠሪ ወንጀሉን ላለመፈጸሙ በመከላከያው አስረድቶአል በማለት በነፃ አሰናብቶታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዓቃቤ ሕጉ ውሣኔውን በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ከዚህ በኋላም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ነው ብሏል፡፡ ለጥፋቱ ይመጥናል ብሎ ባመነው መሠረትም ተጠሪ በስድስት /6/ ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በወ/መ/ሕግ ቁ. 27/1/ እና 523 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል ጥፋተኛ የተባለውን ተጠሪ በስድስት /6/ ወር እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎአል፡፡ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/መ/ሕግ ቁ. 523ም የሚያስቀጣው ከአምስት /5/ ዓመት በማያንስ ከሃያ /20/ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ነው፡፡ በእርግጥ ጥፋተኛ በተባለ ተከሣሽ ላይ ቅጣት ሲወሰን የተለያዩ የማክበጃም ሆነ የማቅለያ ምክንያቶች /ሕጉን መሠረት ያደረጉ/ ከግምት ውስጥ በማግባት በመሆኑ እንደ ሁኔታው ቅጣቱ ሊቀልም ሊከብድም የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የቅጣቱ መነሻ በሕጉ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ የወሰነው ቅጣት ግን ከመነሻው ወርዶ /ዝቅ ብሎ/ ስድስት ወር ሆኖአል፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቀረበውም ፍ/ቤቱ ይህን ያሕል ዝቅ ብሎ ለመውረድ የሚያስችለው የሕግ ምክንያት ነበረው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ለማቅለል ይችል ዘንድ በዋቢነት የጠቀሰው የወ/መ/ሕግ ቁ. 184/መ/ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ቁ.184 ቅጣትን ለማቅለል የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር የያዘ ሲሆን፣ ይህም ከፍተኛው ቅጣት ማለትም ከሞት ቅጣት ነው የሚጀምረው፡፡ የሞት ፍርድን ከሃያ /20/ ዓመት እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣ የእድሜ ልክ እስራትን ከአስር /10/ ዓመት እስከ ሃያ /20/ በሆነ ጽኑ እስራት ማቃለል እንደሚቻል በንኡስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ የተመለከተ ሲሆን፣ የእስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በተለይ የታዘዘ ከሆነ ደግሞ ቅጣቱ ዝቅ ማድረግ የሚቻለው ከአንድ /1/ ዓመት ጀምሮ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ /ሐ/ ተመልክቶአል፡፡ በወ/መ/ሕግ ቁ. 107 እንደተደነገገው ጽኑ እስራት የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ 25 /ሃያ አምስት/ ዓመት ቢሆንም፤ በሕጉ ልዩ ክፍል የቅጣቱ መነሻ ከአንድ ዓመት በላይ ከፍ ብሎ ከተወሰነ ግን በሕጉ አግባብ ያላቸው የማቅለያ ምክንያት ካልተገኙ በቀር እንደመነሻ የሚያዘው ይኸው በልዩ ክፍል የተመለከተው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም ቅጣቱ መወሰን ያለበት በዚህ መሠረት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የጠ/ፍ/ቤቱ ከግምት ውስጥ ያስገባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጠሪ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከአንድ /1/ ዓመት በታች ሊወርድ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ውሣኔ በሰጠበት ጊዜ ሥራ ላይ በነበረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179/ሐ/ እንደተመለከተውም የጽኑ እስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ በዚህ ቅጣት ምትክ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል መነሻ ሆኖ ከተደነገገው ከአንድ ዓመት ጀምሮ የጽኑ እስራት ቅጣት ሊወሰን እንደሚቻል ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 103/98 ኀዳር 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕግ ስ/ስ/ቁ. 195/2/መ/ መሠረት ተሻሎአል፡፡

   2. ተጠሪ በአንድ /1/ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡ የኸው ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

### 9.3 በወንጀል ጉዳይ ንብረት መውረስ[39]

- በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ የሚቻልባቸዉ ሁኔታዎች፤ ቅጣቱ ንብረት መዉረስን እንደሚያካትት በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በግልጽ የተደነገገ ሲሆን፤ የጥፋተኛነት ዉሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ ወንጀለኛዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘዉ ንብረት ሲኖር፤ አንድ ሰዉ ለወንጀል ስራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳዉ ወይም ወንጀሉን ለፈጸመበት ዋጋ እንዲሆነዉ የተሰጠዉ ወይም ሊሰጠዉ የታቀደዉ ንብረት ሲኖር፣ ወንጀልን ለመፈጸም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም ለወንጀል ተግባር ያገለገሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ አደገኛ የሆኑ ነገሮች ሲሆኑ ስለመሆኑ፤
- ንብረት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀለኛዉ ላይ ሊጣሉ ከሚችሉ ቅጣቶች አንዱ በመሆኑ፣ ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔን ተከትሎ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን መወሰን የሚችሉት እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አቃቤ ህግ ሊወረሱ የሚገባቸዉን ንብረቶች ዝርዝር በወንጀል ክሱ ካመለከተ፣ ንብረቶቹም ከፍ ሲል በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ የተገኙ ስለመሆናቸው በወንጀል ፍርድ ሂደት ከተረጋገጠ እና በወንጀል መዝገቡ ላይ አቃቤ ህግ ንብረቶቹ እንዲወረሱ ካመለከተ ስለመሆኑ፡፡[40]

የሰ/መ/ቁጥር - 137908

ቀን - 21/05/2010 ዓ.ም

ዳኞች - ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ አስፋ ከጠበቃ ደመነ ቱንኤ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

---

[39]የሰ/መ/ቁ 137908 (21/05/2010 ዓ.ም) ቅፅ 24

[40]በሰ/መ/ቁጥር 66943 (ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣የሰ/መ/ቁ 228813 (መጋቢት 27 ቀን 2015) ፣ የሰ/መ/ቁ 229403 (መጋቢት 29 ቀን 2015ዓ.ም)

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ስበብ ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅት በተገኘዉ ገንዘብ ያፈሩት ሀብት እና ንብረት እንዲመልሱ እንዲሁም በሕፃናት ላይ ለደረሰዉ የሞራል ካሳ ገንዘብ እንዲከፍሉ የቀረበዉን ክስ መሠረት በማድረግ የተሰጠዉን ፍርድ በመቃወም የቀረበ የሰበር አቤቱታን የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረዉ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ ተጠሪ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ፊቃድ ሳይኖራቸዉ ያላቸዉ በማስመሰል ፀሐይ አሰፋ የሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከል በሚል ስያሜ ከ1983 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ቁጥራቸዉ 282 የሚሆኑ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ለሌላ ድርጅት አሳልፈዉ የሰጡ መሆናቸዉን፤ በዚህ ምክንያት ከአርባ ምንጭ ከተማ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ወስደዉ. 800,000.00 ብር የሚገመት ቤት መገንባታቸዉን፣ ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገንዘብ በማግኘት የተለያዩ ንብረቶችን በህገ ወጥ መንገድ ማፍራታቸዉን፤ በዚህም ምክንያት በወንጀል ተከስሰዉ ጥፋተኛ ተብለዉ የተቀጡ በመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 100(1) መሠረት በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩትን ንብረት ለመንግስት ገቢ ማድረግ ያለባቸዉ በመሆኑ የተለያዩ ንብረቶች ዋጋ ብር 1,916,300.00፣ በ282 ሕፃናት ላይ ለደረሰ የሞራል ጉዳት ካሳ ብር 282,000.00 እንዲከፍሉ እና በአርባ ምንጭ ከተማ በ1000 ካ/ሜትር ላይ ያረፈዉን ቤት እና ቦታዉን ለመንግስት እንዲያስረክቡ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ፡፡

ተጠሪ ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ናቸዉ የሚሏቸዉን ነጥቦች ካነሱ በኋላ፣ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ/ንብረት ለመንግስት ገቢ ማድረግ የሚቻለዉ በወንጀሉ ማቋቋሚያ ድንጋጌ ላይ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን በመሆኑ እና ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 433 ድንጋጌ ንብረት የሚወረስ ስለመሆኑ የማይደነግግ መሆኑን፣ ተጠሪ ካላቸዉ የሰብአዊነት እና የእናትነት ፍቅር በመነሳሳት ወላጆቻቸዉን በሞት ያጡ እና በችግር ላይ ያሉትን ሕፃናት በሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ተጣርቶ በሚቀርብላቸዉ መሠረት ተቀብለዉ ወደ ሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ከማስተላለፍ በስተቀር በስማቸዉ የሚታወቅ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት የሌላቸዉ መሆኑን፣ ተጠሪ እ.ኤ.አ ጥር 10/2007 እስከ እ.ኤ.አ ነሐሴ 05/2011 ዓ.ም ድረስ ከኤስ ኦ ኤስ ኢንፋንትስ ኢትዮጵያ ጋር የስራ ዉል በመፈጸም የድርጅቱ የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ኃላፊና ተጠሪ በመሆን ሲሰሩ መቆየታቸዉን፤ ድርጅቱ የተጠሪን የመኖሪያ ቤት ተከራይቶ ሲሰራ መቆየቱን እና አመልካች በክሱ የጠቀሳቸዉ 282 ሕፃናትም ድርጅቱ በስሙ የተረከባቸዉ እንጂ በግል ያልተረከቡ መሆኑን፤ ችግረኛ ሕፃናትን ተቀብለዉ በግል ገንዘባቸዉ በራሳቸዉ መኖሪያ ቤት የሚያሳድጉ መሆኑን ተገንዝቦ የአርባ ምንጭ ከተማ ማዘጋጃ ቤት 1000 ካ/ሜ ቦታ የሰጣቸዉ ሲሆን በቦታዉ ላይ የተሰራ ቤት በግላቸዉ የሰሩት መኖሪያ ቤት እንጂ የሕፃናት ማሳደጊያ ቤት አለመሆኑን፤ በ25 ሕፃናት ስም በየወሩ ሲላክ የነበረጠ. 120.00 ብር በኢ/ንግድ ባንክ አ/ምንጭ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 1033 ገቢ ሲደረግ የነበረዉም በድርጅቱ ባለሙያ ህጋዊነቱ ተጣርቶ ሂሳቡ የተዘጋ መሆኑን፣ ተጠሪ ለስራ ሲጠቀሙበት የነበረዉ እና አመልካች በክሱ የጠቀሰዉ መኪናም የልጃቸዉ መሆኑን፤ አመልካች በክሱ የዘረዘራቸዉ ሌሎች የተለያዩ ቁሳቁሶችም የተጠሪ የግል ንብረቶች መሆናቸዉን፤ ለ282 ሕፃናት የተጠየቀ የሞራል ካሳም የህግ መሠረት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ የቀረበባቸዉ ክስ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ግራ ቀኝ ያቀረቡትን ክርክር እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን እንዲሁም የሰዉ ምስክሮችን አቅርቦ ከሰማ እና ከመረመረ በኋላ፤ በአርባ ምንጭ ከተማ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ለተጠሪ ሊሰጥ የቻለዉ ለወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያነት መሆኑ ስለተረጋገጠ ተጠሪ ይህን ቦታ ሊመልሱ እንደሚገባ፣ በቦታዉ ላይ የተገነባ ቤት በህገ ወጥ መንገድ በተገኘ ገንዘብ ስለመሆኑ አመልካች በማስረጃዎቹ ያላስረዳ መሆኑን እና ተጠሪ ቤቱን የሠራዉ ያለማንም ተቃዉሞ መሆኑ ስለተረጋገጠ የግንባታዉ ወጪ ተገምቶ ሲቀርብ አመልካች

እንዲከፍል በማለት የወሰነ ሲሆን! ሌሎች የተለያዩ ንብረቶችን ተጠሪ በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩ መሆኑን አመልካች ያላስረዳ መሆኑን በመግለጽ በዚህ ረገድ የቀረበዉን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበዉ አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በቀን 10/06/09 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፥ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ስም በአርባ ምንጭ ከተማ በተሰጣቸዉ ቦታ ላይ የሰሩት በሕፃናት ስም ከተለያዩ ድርጅቶች በተገኘ ገንዘብ መሆኑ እየታወቀ ቤቱን በተመለከተ መንግስት ካሳ ከፍሎ መሬቱን እንዲወስድ መወሰኑ፣ መኪናዉን እና ለሕፃናት ማሳደጊያ የሚሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶች ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት በተቋቋመ ኮሚቴ ታሽጎ እያለ ተጠሪ ገንጥለዉ መዉሰዳቸዉ ተረጋግጦ እያለ አመልካች እንደ ክሱ አላስረዳም በሚል ምክንያት ዉድቅ መደረጉ እንዲሁም ተጠሪ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆናቸዉ እና በወንጀል ፍሬ የተገኘ ሀብት ደግሞ ሊወረስ እንደሚገባ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ዉሳኔ ሰጥቶ እያለ ተጠሪ ኃላፊነት የለባቸዉም ሲል በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቶ የተወሰነ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አቤቱታዉ ተመርምሮም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ከወንጀል ዉሳኔዉ ጋር ተገናዝበዉ የታዩ መሆን አለመሆናቸዉን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበዉ እንዲከራከሩ ጥሪ የተደረገላቸዉ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት በቀን 24/09/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት በጽሑፍ በቀረበ መልስ፤ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ፀንቶ እንዲወሰንላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘታቸዉ ብቻ ከ1000 ካ/ሜትሩ የከተማ መሬት ዉጪ ያሉትን እና አመልካች በክሱ ያመለከታቸዉ ንብረቶችን ወይም የንብረቶቹን ዋጋ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ ለመጠየቅ የሚያስችለዉ መብት አለዉ ወይስ የለዉም? መብት አለዉ የሚባል ከሆነ በክሱ የተዘረዘሩትን ንብረቶች ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩ መሆን አለመሆኑ ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በስር ፍርድ ቤት በአግባቡ ተጣርቷል ወይ? የሚሉ ጭብጦች የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

በመግቢያዉ እንደተመለከተዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ላቀረበዉ ክስ መሠረት ያደረገዉ 1ኛ ተጠሪ ፈቃድ ሳይኖራቸዉ ፈቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት በስማቸዉ በማድረግ ሕፃናትን በመዉሰድ ለሌላ ድርጅት ሲሰጡ የነበረ በመሆኑ በወንጀል ተከሰዉ ጥፋተኛ መባላቸዉን፣ ይህን ህገ ወጥ ድርጊት በመፈጸም ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ የተለያዩ ንብረቶችን በማፍራታቸዉ እና የከተማ ቦታ በመዉሰዳቸዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 100(1) መሠረት ንብረቱ ለመንግስት ገቢ መደረግ የሚገባዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግም ተጠሪ ለመንግስት ገቢ ሊያደርጉ ይገባል የሚላቸዉን ንብረቶች ዝርዝር በማቅረብ ግምቱን እንዲከፍል፣ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም የተሰጣቸዉን 1000 ካ/ሜትር ይዞታም እንዲመልሱ የጠየቀ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀል ህጉ ከተመለከቱት የቅጣት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱ ስለመሆኑ ንብረት

ስለሚወረስበት ሁኔታን የሚመለከቱ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ከሚገኙበት የህጉ ሁለተኛ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች አጠቃላይ አወቃቀር እና ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ የሚቻልባቸዉ ሁኔታዎች፤ ቅጣቱ ንብረት መዉረስን እንደሚያካትት በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በግልጽ የተደነገገ ሲሆን፤ የጥፋተኛነት ዉሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ ወንጀለኛዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘዉ ንብረት ሲኖር፤ አንድ ሰዉ ለወንጀል ስራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳዉ ወይም ወንጀሉን ለፈጸመበት ዋጋ እንዲሆነዉ የተሰጠዉ ወይም ሊሰጠዉ የታቀደዉ ንብረት ሲኖር፣ ወንጀልን ለመፈጸም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም ለወንጀል ተግባር ያገለገሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ አደገኛ የሆኑ ነገሮች ሲሆኑ ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 98፤ 100(1) እና 140 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ንብረት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀለኛዉ ላይ ሊጣሉ ከሚችሉ ቅጣቶች አንዱ በመሆኑም፣ ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔን ተከትሎ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን መወሰን የሚችሉት እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አቃቤ ህግ ሊወረሱ የሚገባቸዉን ንብረቶች ዝርዝር በወንጀል ክሱ ካመለከተ፣ ንብረቶቹም ከፍ ሲል በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ የተገኙ ስለመሆኑ በወንጀል ፍርድ ሂደት ከተረጋገጠ እና በወንጀል መዝገቡ ላይ አቃቤ ህግ ንብረቶቹ እንዲወረሱ ካመለከተ ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች እንዲሁም በወንጀል ሥ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 211 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ አመልካች በተጠሪ ላይ ላቀረበዉ ክስ መሠረት ያደረገዉ 1ኛ ተጠሪ ፊቃድ ሳይኖራቸዉ ፊቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት በስማቸዉ በማድረግ ሕፃናትን በመዉሰድ ለሌላ ድርጅት ሲሰጡ የነበረ በመሆኑ በወንጀል ተከሰዉ ጥፋተኛ መሆናቸዉን ነዉ፡፡ በርግጥ ተጠሪ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 433 ስር ጥፋተኛ ተብለዉ የተወሰነባቸዉ ስለመሆኑ ግራ ቀኝ አልተካካዱም፡፡ ይሁንና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 433 መሠረት ጥፋተኛ በሆነ ሰው ላይ የሚጣል ቅጣት ንብረት መውረስን ወይም ለመንግስት ገቢ ማድረግን እንደሚያካትት በድንጋጌው አልተመለከተም፡፡ ተጠሪ ፍቃድ ሳይኖራቸው ህጻናትን በማሳደግ ስራ ላይ በመስማራት በፈጸሙት የወንጀል ተግባር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኙት ንብረት ካለ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 98(2) መሠረት ሊወረስ የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም፣ ይህ የሚሆነው፣ ከላይ በተገለጸው ምክንያት፣ አቃቤ ህግ የወንጀል ክሱን ሲያቀርብ ተጠሪ ጥፋተኛ በተባሉበት ድርጊት ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ያፈሩት ንብረት ስለመኖሩ ገልፆ በዚህ መልኩ ተጠሪ ያፈሩት ንብረትም በወንጀል መዝገቡ ላይ ተረጋግጦ ንብረቱ እንዲወረስም በወንጀል መዝገቡ ላይ አቃቤ ህጉ በሚያቀርበው የቅጣት አስተያየት መሰረት ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው፡፡

ከዚህ ዉጪ፣ በወንጀል መዝገብ ላይ ቀርቦ ክርክር ተደርጎበት ተረጋግጦ በቅጣት መልክ ንብረት እንዲወረስ የወንጀል መዝገቡን በያዘው ፍርድ ቤት ባልታዘዘበት ሁኔታ፣ ቀደም ሲል በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረት በማድረግ በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ተጠሪ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ በፍትሐብሔር መዝገብ ዳኝነት የጠየቀበት አግባብ የወንጀል ድርጊትን መነሻ በማድረግ ንብረት ሊወረስ የሚችልበትን አላማ መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት በመንግስት ላይ ያደረሱት ፍትሐብሔራዊ ጉዳት ካለ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2035 እና 2162 መሠረት ኃላፊነት የሚኖርባቸዉ በመሆኑ አመልካች የደረሰዉን ጉዳት ጠቅሶ በተጠሪ ላይ ክስ እንዳያቀርብ የሚከለክለዉ የለም፡፡ ይሁንና ይህ ጉዳት የሚመራዉ በመደበኛዉ የፍትሐብሔር የሙግት ስርዓት በመሆኑ፤ ክርክሩ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡ በህጉ ከተመለከቱት ደንቦች ዉስጥም ከሳሽ ለክሱ መነሻ በሆነዉ ነገር ወይም ክሱ

በተመሰረተበት ሀብት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆኑን የማሳየት ግዴታ አንዱ እና ዋነኛዉ ነዉ፡፡ የዚህ መርህ ጠቀሜታ ጉዳት ከደረሰበት ሰዉ በቀር አንድ ሌላ ሰዉ ስለ እርሱ ሆኖ ወይም እርሱን ተክቶ ክስ እንዳይመሰርት ለማድረግ በመሆነ ክሱ የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም ክሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት (የፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 33/2/ እና 231/1-ሀ/ ድንጋጌዎች ይመለከታሉ)፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ በክሱ ከጠቀሳቸዉ ንብረቶች ዉስጥ አንዱ በአርባ ምንጭ ከተማ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም ለተጠሪ ያላግባብ የተሰጠ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ሲሆን፣ ተጠሪ በፈጸሙት ህገ ወጥ ድርጊት መሬቱ በእጃቸው የገባ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች መንግስትን ወክሎ መሬቱ እንዲመለስ ለማስወሰን ክስ ለማቅረብ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣን ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 106/99 መሠረት ስልጣን ያለዉ ከመሆኑም በላይ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተሰጠዉን ውሳኔ በመቃወም ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ ባለመኖሩ ይህን በተመለከተ የተሰጠዉን ውሳኔ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይሁንና ከመሬቱ ዉጪ ያሉትን ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተ አመልካች ለክሱ መሠረት ያደረገዉ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም ከተለያዩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ ተጠሪ በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ማፍራታቸዉን ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ክስ ሲያቀርብ ተጠሪ ከሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ ንብረቶቹን ማፍራታቸዉ የአመልካችን መብት እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል ያልገለጸ ከመሆኑም በላይ፣ ተጠሪ ሕፃናትን የማሳደግ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸዉ ፈቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የፈጸሙት ድርጊት እዉነት መስሎአቸዉ እርዳታዉን ሊያደርጉ የነበሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ስም በክሱ አላመለከተም፡፡ አመልካች እነዚህን በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ጭምር ወክሎ መከራከር የሚችል ስለመሆኑም አልገለጸም፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ወደ ዋናዉ ክርክር ከመግባቱ በፊት አመልካች በክሱ ካመለከታቸዉ ንብረቶች ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ነበረበት፡፡

የፍሬ ነገር ክርክሩን በተመለከተ አመልካች በክሱ ባመለከተዉ እና ለመንግስት እንዲመለስ በተወሰነዉ 1000 ካ/ሜ ቦታ ላይ ለሕፃናት ማሳደጊያ የሚሆኑ የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ቤት መሰራቱን፣ ለዚሁ ዓላማ የሚዉሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች መኖራቸዉ፣ የስሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-20744 የሆነ መኪና በተጠሪ ስም ተገዝቶ በእጃቸዉ የሚገኝ እና ለስራዉ የሚጠቀሙበት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ ተጠሪ እነዚህን ንብረቶች ሊያፈሩ የሚችሉበት ሌላ የተለየ ገቢ ያላቸዉ መሆን አለመሆኑ በተጨማሪ ማስረጃ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባዉ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ከወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ ንብረት የሚወረሰዉ ወይም ለመንግስት ገቢ የሚደረገዉ በወንጀል ህጉ እና በወንጀል ስ/ስ/ህጉ መሠረት በቅጣት መልክ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ንብረቱ የሚወረስ መሆን አለመሆኑ ዉሳኔ ማግኘት ያለበት በወንጀል መዝገብ እንጂ በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ብቻ መነሻ በማድረግ በአዲስ መልክ በሚቀርብ የፍትሐብሔር ክርክር ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት ያፈሯቸዉ ንብረቶች የአመልካችን ጥቅም ወይም መብት የሚነካ ከሆነ ክሱ የሚቀርበዉ እና ሙግቱም የሚመራዉ መደበኛዉን የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት በተከተለ መንገድ በመሆኑ፣ አመልካች መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆኑን በክሱ በግልጽ ሳያሳይ እና ፍርድ ቤቱም ይህን በቅድሚያ ማረጋገጥ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ከከተማ ቦታ ዉጪ ያሉትን ንብረቶች በተመለከተ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር ገብቶ አከራክሮ ያዉም በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ለማፍራት የሚያስችላቸዉ ተጠሪ የተለየ ገቢ ያላቸዉ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ሳይረጋገጥ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11871 በቀን 21/04/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/11000 ላይ እንዲሁም የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/26888 የሰጧቸዉን ዉሳኔዎች በማጽናት፣ የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአርባ ምንጭ ከተማ የተሰጣቸዉን 1000 ካ/ሜትር ቦታ ተጠሪ እንዲመልስ በሚል የተሰጠዉን የዉሳኔ ክፍል በማጽናት፤ ቀሪዉን የዉሳኔ ክፍል በመሻር ወስነናል፡፡
3. የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚል የገለፃቸዉ ድርጅቶች እነ ማን ናቸዉ? አመልካች ከ1000 ካ/ሜትር ቦታ ዉጪ ቀሪዎቹን ንብረቶችን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለዉ ከህግ የመነጨ መብት አለዉ ወይስ የለዉም? አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት ያለዉ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር የሚገባ ከሆነ በ1000 ካ/ሜትር ቦታ ላይ የተገነቡትን ቤቶች ጨምሮ ሌሎች በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ለማፍራት የሚያስችላቸዉ ተጠሪ የተለየ የገቢ ምንጭ አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? በሚሉት ጭብጦች ላይ የግራ ቀኝ · ክርክር እና ተጨማሪ ማስረጃዎችን በመስማት እንዲሁም የፍ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደዉ መሠረት ጭብጦቹን በአግባቡ አጣርቶ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉን ተገቢዉን ሁሉ በማድረግ ጉዳዩን አጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አስር

## 10.ቅጣትን መገደብ

### 10.1 የገደብ ጥያቄን በዝምታ ማለፍ[41]

- ፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ሲመረጥ ምክንያቱን በውሳኔው ማካተት እንዳለበት የተከሳሹ የቀደመ ታሪክ፤ የጠበዩና የዓመሉ አካሄድ ሲመዘን ጊዜ መስጠቱ መልካም ውጤት የሚያስገኝ መስሎ ካልታየው የማገጃ ትዕዛዝ እንደማይሰጥ፤ ከምንም በላይ ጉዳዩን ያየዉ ፍ/ቤት የአጥፊዉን ጠባይና የዓመሉን ሁኔታ ሲመዝን ቅጣትን ማገድ መልካም ዉጤት የሚያስገኝ መሆኑን ካላመነ ወይም ካልገመተ በቀር የተወሰኑ መስፈርቶች ስለተሟሉ ብቻ ቅጣት ማገድ ነበረበት ሊባል አይችልም፡፡
- የስር ፍ/ቤት በዝምታ ማለፉ ወይም ምክንያት አለመስጠቱ ተገቢ ባይሆንም ይህ ችሎት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም፡፡[42]

---

[41]የሰ/መ/ቁ 169726 (ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 24

[42]በሰ/መ/ቁ 262248 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ. 185700 (የካቲት 30/2013 ዓ.ም) ቅፅ 25 ፣ በሰ/መ/ቁ 218957 (መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም)ቅፅ 26 ፣ በሰ/መ/ቁ 263173 (ሰኔ 20 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 225686 (ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ. 85596 (መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ. 94404 (መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ

የሰ/መ/ቁጥር 169726

ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፦ ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- አቶ ፍቅሩ ደሌሳ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተስጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ አለመስጠት ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሙሉ አርጋዉ፣ ሰርግነሽ በዛ እና በአሁኑ አመልካች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡

አመልካች ላይ የቀረበዉ 2ኛ ክስ ሲሆን ይዘቱ፡- በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር የተመለከተዉን በመተላለፍ የስር 1ኛ ተከሳሽን የንግድ ሥራ እንዲቆጣጠር፣ እንዲያስተዳድር፣ ሙሉ ዉክልና ወስዶ በንግድ ቤቱ ደረሰኝ መስጠቱን መቆጣጠር ሲገባዉ ይህንን ሳያደርግ የቀረ በመሆኑ በፈጸመዉ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ዉጪ ግብይት እንዲከናወን የመርዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ጥፋተኝነቱ በራሱ በማረጋገጡ ፍርድ ቤቱ አመልካችን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) መሠረት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08/አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር ጥፋተኛ በማድረግ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበለዉ ቀርቷል፡፡ አመልካች የገደብ ጥያቄዉ በስር ፍ/ቤት በመታለፉ ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንኑ የዉሳኔ ክፍል በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡ የአመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት: ድርጊቱ የተፈጸመዉ አመልካች ዕቃ ለመግዛት በወጣሁበት ወቅት በስር 2ኛ ተከሳሽ መሆኑን፤ ነገር ግን በዉክልናዉ መሰረት ስራዉን ስከታተል የነበርኩት እኔ ስለሆንኩ መቆጣጠር ስለነበረብኝ ይህንን ባለማድረጌ ጥፋተኛ ነኝ ብያለሁ፡፡ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪከርድ የሌለብኝ፣ ድርጊቱን በማመን መጸጸቴን በተግባር ማሳየቴን፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪነቴን እንዲሁም በልማት በመሳተፍ መልካም ሰዉ መሆኔን በማስረጃ አረጋግጫለሁ፡፡ ይህ በወ/ሕግ አንቀጽ 192 መሰረት ቅጣቱን በገደብ በማድረግ የአመልካችን ፀባይ ቢፈተን አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ በቂ ነዉ

---

16 ፣ በሰ/መ/ቁ 255633 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 34280 ቅፅ 7 (ግንቦት 14/2000) ፣ የሰ/መ/ቁ. 46382 ( ሐምሌ 28 ቀን /2001 ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ የሰ/መ/ቁ. 34280 (ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7፣ በሰ/መ/ቁ 210020 (ሕዳር 8 ቀን 2014ዓ.ም)

የሚያስብል በቂ ምክንያት ቢኖርም የስር ፍ/ቤት በምን ምክንያት ሊቀበለዉ እንዳልቻለ እንኳን ሳይገልጽ ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 46382 በሰጠዉ ትርጉም መሠረት ቅጣቱ ቢገደብልኝ እና አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ጸባዬ ቢፈተን ዳግመኛ ወንጀል እንደማልፈጽም የሚያሳዩ በቂ ምክንያቶች እያሉኝ የገደብ ጥያቄ መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይኸዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሮ ቅጣቱ ይገደብልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት የተከሰሱበትን ወንጀል አምነዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ከተሰጠ በኃላ ቅጣቱ እንዲገደብላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች በዝምታ ያለፉበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 128፣ 131(1/ለ)፣ ከወ/ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አንጻር ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ያቀረበዉ መልስ፡- የስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረባቸዉን የቅጣት ማቅለያዎችን ተቀብሎ ቅጣት በማቅለል የወሰነ ሲሆን ቅጣቱ እንዲገደብ ትዕዛዝ አለመስጠቱ ብቻ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል አያስብልም፡፡ የወ/ሕ/አንቀጽ 192 ፍ/ቤቱ የነገሮችን ሁኔታ ዓይቶ ጥፋተኛዉ በጽኑ ማስጠንቀቂያ ቢታለፍ ይሻላል ብሎ ሲያምን የሚወስነዉ እንጂ አመልካች እንዳቀረቡት እንደመብት ሊጠየቅ የሚገባዉ አይደለም፡፡ አመልካች ባጠፋዉ ጥፋት በግሉ መታረሙን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን ሌሎች የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲቆጠቡ በማስተማር የሕዝብና የመንግስትን ጥቅም ማስጠበቅን ታሳቢ አድርጎ ቅጣት ሊጣል እንደሚገባ የሚታመን በመሆኑ የቅጣት ዉሳኔ አለመገደቡ ከወንጀል ሕጉ አላማ ጋር የተጣጣመ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 46382 የተሰጠዉ ዉሳኔ ከዚህ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለዉም፡፡ ስለሆነም ዉሳኔዉ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔን አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ የስር 1ኛ ተከሳሽን የንግድ ሥራ እንዲቆጣጠር ሙሉ ዉክልና ወስዶ በንግድ ደርጅቱ ደረሰኝ መስጠቱን መቆጣጠር ሲገባዉ ይህንን ሳያደርግ በመቅረቱና ግብይቱ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ዉጪ መከናወኑ በአመልካች የእምነት ቃል ተረጋግጦ በተጠቀሰዉ የሕግ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ መባሉም ሆነ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት መቀጣቱ ላይ አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የለም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉም ሆነ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ከወ/ሕ/አንቀጽ 192 ድንጋጌ አንጻር አመልካች ቅጣት እንዲገደብለት ያቀረበዉን ጥያቄ የስር ፍ/ቤት በዝምታ ሳይቀበለዉ መቅረቱ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

የወንጀል ቅጣት በገደብ ለማቆየት በሕጉ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ እንደሚገባ በወ/ሕ/አ/197(1) እና(2) ተመልክቷል፡፡ አንድ ተከሳሽ ቅጣቱ ሊገደብለት የሚችለው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ ግዴታ የሚቀበል መሆኑ መረጋገጥ እንዳለበት፤ በጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት እና የፍ/ቤት ወጪ ለመክፈል ማረጋገጫ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፤ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈፃፀም አንደ መተማመኛ መስጠት እንዳለበት ሕጉ አስገደጅ መስፈርት አስቀምጧል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ከዚህን ቀደም በሰ/መ/ቁ 94404 በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንድ ጥፋተኛ በተወሰነ ገደብ ከእስር ለመፍታት በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማረጋገጥ ያለበት ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ሆኖም በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች ተሟልተዉ መገኘት አንድ አጥፊ የተወሰነበት እስራት የግድ ይገደብለታል ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ቅጣትን በገደብ ለማቆሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ

190 የተመለከተው መሰረታዊ መርህ ከወ/ሕ/አንቀጽ 192 እና 196 ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባል፡፡

በመርህ ደረጃ የወንጀል ቅጣት የሚገደበው የወንጀለኛው ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ ሊሆን የሚችል መሆኑን ፍ/ቤቱ ማረጋገጥና ማመን ሲችል መሆኑን የወ/ሕ/አንቀጽ 190 ድንጋጌ ያስገናዝበናል፡፡ እንዲሁም በአንድ ወንጀል ፈፃሚ ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይፈጸም የሚታገደው ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለ ጠበዩም ማሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ በቂ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምን መሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 192 ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቅጣትን እንዳይፈጽም ለማገድ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 196 የተዘረዘሩት የወል ድንጋጌዎች በአግባቡ ሊታዩ እንደሚገባ ከድንጋጌው መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ሲመረጥ ምክንያቱን በውሳኔው ማካተት እንዳለበት የተከሳሹ የቀደመ ታሪክ፤ የጠበዩና የዓመሉ አካሄድ ሲመዘን ጊዜ መስጠቱ መልካም ውጤት የሚያስገኝ መስሎ ካልታየው የማገጃ ትዕዛዝ እንደማይሰጥ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ከምንም በላይ ጉዳዩን ያየዉ ፍ/ቤት የአጥፊዉን ጠባይና የዓመሉን ሁኔታ ሲመዝን ቅጣትን ማገድ መልካም ዉጤት የሚያስገኝ መሆኑን ካላመነ ወይም ካልገመተ በቀር የተወሰኑ መስፈርቶች ስለተሟሉ ብቻ ቅጣት ማገድ ነበረበት ሊባል አይችልም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪከርድ ያልቀረበበት፣ ጥፋቱን አምኖ ተፀፅቶና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ሲታይ በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በአብዛኛው ያሟላ ቢሆንም በወ/ሕ/አንቀጽ 190 እና 192 ድንጋጌዎች መሠረት በአመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት ሳይፈጸም ቢገደብ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠበዩም ማሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ በቂ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ባለማመኑ የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት በዝምታ ማለፉ ወይም ምክንያት አለመስጠቱ ተገቢ ባይሆንም ይህ ችሎት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ዉድቅ ሲያደርግ ምክንያት ስላልሰጠ ብቻ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት መመለሱ የተለየ ዉጤት የሚያመጣ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት አመልካች የወሰነዉን የአንድ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ዉሳኔ ሳይገደብ መቅረቱ ከወ/ሕ/አንቀጽ 190፣ 192 እና 197 ድንጋጌዎች አንጻር የሚነቀፍ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ በአብላጫ ድምፅ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 262072 ጥቅምት 14 እና 15 ቀን 2011 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 225003 ታሕሳስ 09 ቀን 2011 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ) መሠረት ጽንቷል፡፡
2. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኝ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተ.ቁ 5 ላይ የተገለጸው ዳኛ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የቅጣት ገደብ ጥያቄ በዝምታ በማለፍ በሰጠው ውሳኔ ላይ አብላጫው ድምጽ በደረሰበት መደምደሚያ በሀሳብ ስለተለየሁ የሀሳብ ልዩነቴን እንደሚከተለው አስፍሬአለሁ፡፡

አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ጥፋተኝነቱ በራሱ በማረጋገጡ ፍርድ ቤቱ አመልካችን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) መሠረት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08/አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር ጥፋተኛ በማድረግ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበለዉ አልፎታል፡፡

አመልካች ድርጊቱን ማመኑ እና በፈጸመው ድርጊት ምክንያት የተጸጸተ መሆኑ፤ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪኮርድ የሌለበት መሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ሲሆን አብላጫው ድምጽም አመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያልቀረበበት፣ ጥፋቱን አምኖ የተፀጸተና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ሲታይ በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በከፊል ያሟላ መሆኑን በመግለጽ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ አብላጫው ድምጽ የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ያልተቀበለው የስር ፍ/ቤት በዝምታ ማለፉ ወይም ምክንያት አለመስጠቱ ተገቢ ባይሆንም ይህ ችሎት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ሕጉ ዓላማ ወንጀል እንዳይፈጸም ማድረግ ሲሆን ይህንንም የሚያደርገው ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ወንጀል ፈጻሚዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቅጣት ሲገደብ የፍርዱ ውሳኔ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ከሌላው ውጤት ጋር ነዋሪ የሚሆን በመሆኑ ቅጣትን መገደብ በወንጀለኛው ላይ ቅጣት እንዳይፈጸም የማድረግ ውጤት ብቻ ያለው ሳይሆን ወንጀለኛው ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲታቀብ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ቅጣትን መገደብ የወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ ከሚሳካባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡

ቅጣት ሊገደብ የሚችለውም ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው፤ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፤ ጥፋቱ በመቀጮ፤ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻ እስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን 'ያመነበት' እንደሆነ፤ እንዲሁም ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ

እንዲቆይ ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን፤ እነኚህም ሁኔታዎች ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የጽኑ እሥራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ እና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወስንበት እንደሆነ ወይም ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት አመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነው በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በሕጉ ከተመለከቱት ከእነኚህ ሁኔታዎች ውጪ ጥፋተኛው ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት በመንግስት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ እንዲገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ተብሎ በሕጉ ላይ አልተገለጸም፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 የወንጀሉ ከባድነት / the gravity of the crime /፤ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለው እምነት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት የሚባለው ፍ/ቤቱ ቅጣቱ እንዲገደብ አቋም ከያዘ በኋላ ቅጣቱ ተገድቦ የሚቆይበትን የፈተና ጊዜ ለመወሰን / ..... to fix the probation period ..... / እንጂ ቅጣቱን ለመገደብ ሊሟላ ይገባል ተብሎ የተቀመጠ ቅድመ-ሁኔታ አይደለም፡፡

በመሠረቱ ከባድ ወንጀሎች ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194/1/0 ድንጋጌም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ጥፋተኛው አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ቅጣትን ማገድ አይቻልም በማለት በግልጽ መደንገጉ ከመነሻውም ቢሆን ከባድ ወንጀል የፈጸመ ወንጀለኛ በሚጣልበት ከፍተኛ የቅጣት መጠን ምክንያት ቅጣት ሊገደብለት የማይችል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 ላይ የተገለጸው 'የወንጀሉ ክብደት' የሚለው ቃል ለፈተናው ጊዜ አወሳሰን ታሳቢ የሚደረግ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ቅጣቱን ለመገደብ በመመዘኛነት የተቀመጠ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 የተመለከቱት ቅድመ-ሁኔታዎች ፈተና የሚስጥባቸውን ሁኔታዎች እንደሆኑ ከድንጋጌው ርዕስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን እነኚህ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸው ሊረጋገጥ የሚችለው ፍ/ቤቱ ከተከሳሹ የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ በመነሳት ቅጣቱን መገደብ እንዳለበት ሲያምን እና ጥፋተኛው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንደሚያሟላ ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192፤196/1 እና 197 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጥፋተኛው በድንጋጌው የተመለከቱትን ቅድመ- ሁኔታዎች ማሟላት አለሟሟላቱን ማረጋገጥ የሚቻለውም ጥፋተኛው ራሱ በራሱ ተነሳሽነት በሕጉ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች ያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ጥፋተኛው በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲያሟላ እድል በሰጠው ጊዜ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ በጥፋተኛው ላይ የሚጣለውን ቅጣት ለጊዜው ማገድ ለወደፊቱ ጥፋቱን ለማረም እንደሚችል ሊያምን ወይም ላያምን የሚችለው የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ አስመልክቶ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቶች በሕግ እና በተገቢ ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው በመሆኑ አመልካች ቅጣቱን ለማስገደብ ያቀረባቸው ምክንያቶች ፍ/ቤቱን የሚያሳምኑ ናቸው ወይም አይደለም ለማለት ሕግን መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ምክንያት በመስጠት ሊሆን ይገባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ድርጊቱን ማመኑ እና በፈጸመው ድርጊት ምክንያት የተጸጸተ መሆኑ፤ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪከርድ የሌለበት መሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ እነኚህ ሁኔታዎች የተከሳሹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ

ለመመዘን የሚያስችሉ እና ቅጣቱ ቢገደብ የአመልካችን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚያስችሉ አሳማኝ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ከማለፉ በቀር የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ለማስከልከል የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለ ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ አብላጫው ድምጽ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ቢሆንም ይህ ምክንያት በሕጉ ቅጣትን እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ተብሎ ያልተገለጸ ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤት ቅጣቱ እንዳይገደብ የሚያደርጉ ሕጋዊ ምክንያቶች ያሉ መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ሊመለስለት ይገባ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በመሆኑም የእነኚህን ሁኔታዎች የአመልካቹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ አሳማኝ እና በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሆነው ሳለ አመልካች በራሱ ተነሳሽነት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ከሆነ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ወይም እንዲያሟላ በማድረግ ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ከተፈጸመው ወንጀል ጋር ሲታይ ቅጣቱን ለመገደብ አላመንኩበትም በማለት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መታረም ይገባው ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡.

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

## 10.2 ቅጣትን ለመገደብ መመዘኛዎች - የወንጀል ክሱን አምኖ ወይም ክዶ የመከራከር ውጤት (የተለያዩ አቋም የተያዘበት ውሳኔዎች)

- የወንል ክሱን አምኖ መከራከር አስፈልጊ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ በሰ/መ/ቁ/131741 (ታህሳስ 11 ቀን 2010 ዓ.ም) አቋም የተያዘ ቢሆንም  በሰበር መ/ቁ 185700 (የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25 በተሰጠው ውሳኔ ደግሞ አምኖ መከራከር መመዘኛ መሆን እንደማያስገድድ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ እንደቀደም ተከተላቸው ጭብጥ እና ውሳኔው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡
- ተጠሪዉ ከፈጸመዉ ድርጊት ከባድነት እና ጥፋቱንም አምኖ አለመቀበሉ እንዲሁም ተበዳይ ላይ የደረሰዉን ጉዳት ለመካስ ወይም ገንዘቡን ለመክፈል ፈቃደኛ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱን መገደብ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፤[43]

የሰበር መ/ቁ/131741

ታህሳስ 11 ቀን 2010 ዓ.ም

[43]የሰ/መ/ቁ 131741 (ታህሳስ 11 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 94404 (መጋቢት 9 ቀን 2006ዓ.ም) ቅፅ 16

ዳኞች ፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡ የፌዴራል ጠ/ዓቃቤ ህግ - ያልምታሪክ ሽመልስ ቀረቡ

ተጠሪ፡ ሃይላይ ገ/መድህን ገ/ማሪያም - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርመምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል ፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ የጉዳይ በተጠሪ ላይ የተወሰነዉ የእስራት ቅጣት አፈጻጸም በገደብ እንዲቆይ በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ አግባብነት የሚመለከት ነዉ ፡፡የክርክሩ አመጣጥ ሲታይ ተጠሪ የወ/ህግ አንቀጽ 676/2/ሀ ተላልፎ ከግል ተበዳይ ጸጋ ኪዳኑ የተሰጠዉን ዉክልና መሰረት በማድረግ በቂ/ክ/ከ/ወረዳ 3 ቀበሌ 02/03 የሚገኝ ቤት ቁ/1058 የሆነ መኖሪያ ቤት በብር 450,000 በዉልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በተደረገ የሽያጭ ዉል ለወ/ሮ ሰንበቱ ተ/መድህን አስተላልፎ ገንዘቡን የግል ተበዳይ ሲጠይቁት ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑና ለግል ጥቅሙ በማዋሉ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል አመልካች ክስ ያቀረበበት ሲሆን ተጠሪ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ በመከራከሩ ግራቀኙ ማስረጃ ተሰምቶ ተጠሪ ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ በ1ዓመት ከስምንት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ወስኖ የቅጣት አፈጻጸም በ2 ኣመት የፈተና ጊዜ በገደብ እንዲቆይ የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነ ሲሆን ዓቃቤ ህግ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ቀርቧል ፡፡

የዓቃቤ ህግ የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ላይ በስር ፍ/ቤት የተወሰነዉ የ1ዓመት ከ8 ወር እስራት ቅጣት በገደብ እንዲቆይ የመደረጉን አግባብነት ከወ/ህግ አንቀጽ 197/1/እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/94404 ከሰጠዉ ፍርድ ጋር ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተያዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዟል ፡፤ተጠሪ በአድራሻዉ ባለመገኘቱ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለትም ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል ፡፡በዚሁ እኛም መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለዉ ተጠሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 676/1/ሀ ተላልፎ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል መፈጸሙ ተረጋግጦ የጥፋተኝነትና የ1ዓመት ከ8ወር እስራት ቅጣት በስር ፍ/ቤቶች ተወስኖበታል ፡፡የእስራት ቅጣት አፈጻጸም አስመልክቶ በ2 ዓመት ገደብ እንዲቆይ መደረጉ ከተፈጸመዉ ወንጀልና ከደረሰዉ ጉዳት እንዲሁም ይህ ሰበር ችሎት ስለቅጣት አፈጻጸም ገደብ በተመለከተ ከሰጠዉ ትርጉም ጋር ተገቢነቱን ማየት የሚያስፈልግ ነዉ ፡፡በዚህ ረገድ ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን የፍርዱ ሃተታ ሲታይ እንደተመለከተዉ ስለቅጣት ገደብ ሁኔታ እና አተገባበር በወ/ህጉ አንቀጽ 190 እና ተከታዩቹን ድንጋጌዎች የሚመለከት ነዉ ፡፡የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 196 ስር እንደአስቀመጠው ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው የሚሰጠውን የፈተና ጊዜ የሚወሰነው የወንጀሉን ከባድነት፣ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳትና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለውን እምነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ የተከሳሹን የገደብ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ ከመቀበሉ በፊትም ተከሳሹ ቀድሞ የነበረውን ጠባይ ፣ የአኗኗርና የስራውን ሁኔታ ምን አይነት እንደነበር ፍርድ ቤቱ መረጃ መሰብሰብ እንደሚችልም ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197/1/ ሲታይም ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ እንዳይፈፀም ለማድረግ በቅድሚያ ሊሟሉ የሚችሉትን ሁኔታዎች አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ እነዚህም ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ

ካመነ፣ ጥፋተኛው እንዲፈፀም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ካረጋገጠ ፣ ጥፋተኛው በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ከሰጠ በኋላ ስለመሆናቸው ሕጉ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈፃፀም መተማመኛ ዋስትና እንዲያቀርብ እንደሚያደርግ ተጠቃሹ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር አስፍሮ ይገኛል፡፡

እንግዲህ ህግ አውጭው አንድ ሰው በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ቅጣት ሳይጣል ጥፋተኛ ነህ በማለት ብቻ ሊታለፍ የሚችልበትን እንዲሁም ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ቅጣቱ ከተጣለ በኋላ ደግሞ የእስራት ቅጣቱ ሳይፈፀም ተገድቦ የሚቆይበትን አግባብ በግልፅ የዘረጋ መሆኑን ከአንቀፅ 190 እስከ 200 ድረስ ያሉትን የወንጀል ህግ ድንጋጌዎችን በማየት የምንረዳው ጉዳይ መሆኑን ያስገነዝባል ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሰር ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ የጣለውን የአንድ አመት ከስምንት ወር እሰራት ቅጣት በሁለት አመት የገደበው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን መርምሮ ስለመሆኑ የውሣኔው ግልባጭ አያሣይም፡፡ ይልቁንም ፍርድ ቤቱ አጽንኦት የሰጠው የተጠሪን በሽተኛ መሆንና የቤተሰብ አስተዳዳሪነት እንጂ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰ ጉዳት ስለመካሱ ወይም ገንዘቡን ለመክፈል እንኳን ፈቃደኛ ስለመሆኑ አላረጋገጠም ፡፡ ይልቁንም ፍርድ ቤቱ ተጠሪ መልካም ጠባይ እንደሚመራ ስለማመኑ፣ ተጠሪ እንዲፈጽም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ማረጋገጡን፣ ተጠሪ በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍልና ባልተረጋገጠበትና ከጅምሩም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ ክዶ እየተከራከረ ቅጣቱ ቢገደብለት ከጥፋቱ ለመማር ዝግጁ ነዉ የሚያስብል ሁኔታ የለም ፡፡በሌላ በኩል ቅጣቱን ለመገደብ ፍ/ቤቱ የተጠቀመበት ምክንያት የቤተሰብ አስተዳዳሪነትና በሽተኛ መሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ተወስዶለታል ፡፡ስለሆነም ተጠሪዉ ከፈጸመዉ ድርጊት ከባድነት እና ጥፋቱንም አምኖ አለመቀበሉ እንዲሁም ተበዳይ ላይ የደረሰዉን ጉዳት ለመካስ ወይም ገንዘቡን ለመክፈል ፈቃደኛ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱን ለመገደብ ለመልካም ጸባይ 2000 ብር ለፍ/ቤት ወጪ 1500 ብር እንዲከፍል በማድረግ ብቻ ቅጣት ዉሳኔዉን አፈጻጸም በገደብ እንዲሆን የስር ፍ./ቤት የሰጠዉ ትእዛዝ ሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ/94404 እና ሌሎች ተመሳሳይ መዝገቦች ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ ዉሳኔ እና የወ/ህጉን አንቀፅ 190፣192፣196 እና 197 እንዲሁም አዋጅ ቁ/454/97 አንቀጽ 2/1/ መሰረት አስገዳጅ የሰበር ችሎቱን ዉሳኔዎች ያላገናዘበ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል ፡፡

**ውሳኔ**

1ኛ/የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 11693 በ07/04/07 ዓ.ም በተጠሪ ላይ የወሰነዉ የጥፋተኛነትና የአንድ ዓመት ከስምንት ወር ቀላል እስራት ቅጣት ጸንቷል ፡፡

2ኛ /የቅጣት አፈጻጸም አስመልክቶ በ2 ዓመት የፈተና ጊዜ ተገድቦ እንዲቆይ ፍ/ቤቱ በተጠቃሹ መዝገብ የሰጠዉ ትእዛዝ እና ይህንኑ በማጽናት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/163881 የሰጠዉ ፍርድ በወ/መ/ስ/ስ/ህገ ቁ/195 2/ለ/2 መሰረት ተሽሯል ፡፡

3ኛ/ ተጠሪ ላይ የተወሰነዉ 1ዓመት ከ8ወር ቀላል እስራት በማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲፈጽም ብለናል ፡፡ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ትእዛዝ መሰረት ለፍ/ቤት ወጪና ለመልካም ፀባይ ያስያዘዉ ገንዘብ ካለ በደረሰኙ መሰረት ይመለስለት ብለናል ፡፡ይጻፍ ፡፡

4ኛ /የአ/አ/ፖሊስ ተጠሪን ካለበት ይዞ ለአ/አ/ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ ማረሚያ ቤቱም ተቀብሎ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/163881 ተጠሪ ላይ የተወሰነዉን እስራት ቅጣት ተቆጣጥሮ እንዲያስፈጽም ብለናል ፡፤ይጻፍ ፡፤

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## 10.3 የወንጀል ክስን ክዶ መከራከር ቅጣት እንዲገደብ በቅድመ ሁኔታነት የማይታይ፤[44]

- ከመነሻውም ቢሆን የወንጀል ክስን ክዶ መከራከር በራስ ላይ ማስረጃ ካለመሆን እና የወንጀል ጥፋተኝነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ ንፁህ ሆኖ ከመገመት ህገ መንግስታዊ መብት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የወንጀል ክስ ያላመነ ሰው የቅጣት ውሳኔ ሊገደብለት አይገባም በሚል ትርጉም ሊሰጥበት የሚቻል ጉዳይም አይደለም፡፡
- የወንጀል ክስን ማመን፣ ከተበዳዩ ጋር ታርቆ በእውነት መፀፀትን ማሳየት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የወንጀል ቅጣት ውሳኔን ለመገደብ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ መመዘኛዎች ሳይሆኑ የወንጀል አጥፊው በመልካም ጠባይ የሚመራ ለመሆኑ እንዲያቀርብ የሚጠየቅ የዋስትና ማረጋገጫ በመሆኑ በህግ በግልፅ ያልተቀመጠ ክልከላ መሰረት ተደርጎ ቅጣቱ ሊገደብ አይገባም የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፡፡

የሰ.መ/ቁ. 185700

የካቲት 30/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- አቶ ቢዝነስ ለማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው የወንጀል ቅጣት ሊገደብ ስለሚቻልበት ሁኔታ በወንጀል ህጉ ውስጥ ስለ ወንጀል ቅጣት አገዳደብ ከተቀመጠው መመዘኛ እና በዚሁ ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ/17211 ላይ ከተሰጠው የህግ ትርጉም አኳያ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪን ጨምሮ በሁለት ተከሳሾች ላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና 670 ድንጋጌን ጠቅሶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ የቀረበበትን ክስ ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ክዶ በመከራከሩ የግራ ቀኙ ምስክሮች ተሰምተው ተጠሪ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በ1(አንድ) ዓመት ከ6(ስድስት) ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኖ የቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም በ2(ሁለት) ዓመት የፈተና ጊዜ እንዲቆይ ታዟል፡፡ አመልካች የቅጣት ውሳኔው ሊገደብ አይገባም በማለት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ህዳር 08/2012 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የቀረበበትን ክስ ክዶ በተከራከረበት፣ ከተበዳይ ጋር ታርቆ ባልካሰበት እና የፍርድ ቤቱን ወጪ ለመክፈል ማረጋገጫ ባላቀረበበት የቅጣት ውሳኔው መገደቡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 192 እና 197 መመዘኛን ያላማከለ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

[44]የሰ/መ/ቁ 185700 (የካቲት 30/2013 ዓ.ም) ቅፅ 25

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ከላይ በመግቢያው ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ ግራ ቀኙ በተገኙበት ለማጣራት ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ጭብጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንግዲህ የወንጀል ቅጣት ዋና ዓላማው አጥፊውን ማስተማር ነው፡፡ በወንጀል ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለማስተማር ደግሞ ሁሌም ወደ ማረሚያ ቤት መላክ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ ይልቁንም ለጥፋተኛው አንድ የፈተና ጊዜ ከፅኑ ማስጠንቀቂያ ጋር ሰጥቶ አመሉ ቢፈተሽ መልካም ይሆናል ተብሎ ሲታመን የእስራት ቅጣቱን አፈፃፀም ለጊዜው አግዶ ማቆየት እንደሚቻል ከወንጀል ህጉ አንቀፅ 192 እና ተከታዮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤት በአንድ የወንጀል ተከሣሽ ላይ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የተወሰነው የእሥራት ቅጣት ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችልበት መሰረታዊ መርሆዎችም በወንጀል ህጉ አንቀፅ 192 ስር ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ሊገደብ የማይቻልባቸው ልዩ ሁኔታዎች ደግሞ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 ስር በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር ቅጣት እንዳይገደብ የተቀመጠው ክልከላ 1ኛ/ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የፅኑ እስራት ቅጣት ወይም ከ3(ሶስት) ዓመት በሚበልጥ ቀላል እስራት ቅጣት ተፈርዶበት ከሆነ እና አሁን ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀልም ከእነዚሁ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት ከሆነ፤ 2ኛ/ ከዚህ በፊት ያልተቀጣ ሆኖ አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ ፅኑ እስራት የሚፈረድበት ከሆነ፤ 3ኛ/ የቅጣት አፈፃፀሙ ከመታገዱ በፊት ጥፋተኛው በተራ ቁጥር 1 እና 2 ስር ከተመለከቱት ቅጣቶች ውስጥ በአንዱ ሊያስቀጣው የሚችል ሌላ ወንጀል ስለመፈፀሙ የተደረሰበት ከሆነ፤ 4ኛ/ ወንጀለኛው ቅጣቱ ታግዶለት ለፈተና በተለቀቀበት ጊዜ ውስጥ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 200 ስር በተመለከተው አኳኋን አስቦ አንድን ወንጀል የፈፀመ ከሆነ ወይም 5ኛ/ የቅጣት አፈፃፀሙ በታገደለት ጉዳይ የተሰጠው የፈተና ጊዜ መልካም ፍሬ የሚያስገኝ አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲረዳው የሚሉት ናቸው፡፡ እናም ፍርድ ቤት አንድን የወንጀል ቅጣት ከመገደቡ በፊት የቅጣት ውሳኔው እንዳይገደብ ከእነዚህ መመዘኛዎች ውስጥ በአንዱ ክልከላ ያልተደረገበት መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ አሁን በቀረበው ጉዳይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ተገቢ ነው ያለውን የወንጀል ቅጣት ከወሰነ በኋላ የቅጣት ውሳኔን አፈፃፀም በፈተና ጊዜ እንዲቆይ አዟል፡፡ በተጠሪ ላይ የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ እንዳይገደብ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 ስር የተቀመጠ ክልከላ የለም፡፡ አመልካችም የቅጣት ውሳኔው ሊገደብ አይገባም የሚለው በወንጀል ህግ አንቀፅ 194 ክልከላ ተደርጎበታል በሚል ሳይሆን ተጠሪ ክሱን ክዶ ከመከራከሩም በላይ ከተበዳይ ጋር ታርቆ ለመካስ እና የፍርድ ቤቱን ወጪ ለመሸፈን የሰጠው ማረጋገጫ የለም በሚል ነው፡፡ በመሰረቱ እነዚህ መመዘኛዎች በወንጀል ህጉ አንቀፅ 197 መሰረት ጥፋተኛው በተሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ በመልካም ጠባይ እንዲመራ እና የፈተና ጊዜው ተገቢውን ፍሬ እንዲያፈራ በሚል ለመልካም ጠባይ አመራር ዋስትና የሚሰጡ ትዕዛዛት እንጂ ቅጣትን ለመገደብ ቅድመ ሁኔታዎች አይደሉም፡፡ በሰ/መ/ቁ/172111 ላይ የተሰጠው ውሳኔም በመዝገቡ ላይ በወንጀል ጥፋተኛ ከተባሉት ግለሰብ የግል ሁኔታ አንፃር የፈተና ጊዜ ቢሰጣቸው በመልካም ጠባይ የሚመሩ ለመሆኑ አሳይተዋል የሚያስብል ነገር አልተገኘም በሚል አቋም የተያዘበት ጉዳይ እንጂ ሁሌም ቢሆን የወንጀል ክስ ክዶ የተከራከረ ወይም ከተበዳዩ ጋር ታርቆ ተገቢውን ካሳ ላልከፈለ የወንጀል አጥፊ ቅጣት ሊገደብ አይገባም የሚል ግልፅ ትርጉም አይደለም፡፡ ከመነሻውም ቢሆን የወንጀል ክስን ክዶ መከራከር በራስ ላይ ማስረጃ ካለመሆን እና የወንጀል ጥፋተኝነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ ንፁህ ሆኖ ከመገመት ህገ መንግስታዊ መብት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የወንጀል ክስ ያላመነ ሰው የቅጣት ውሳኔ ሊገደብለት አይገባም በሚል ትርጉም ሊሰጥበት የሚቻል ጉዳይም አይደለም፡፡ ከላይ እንደተመለከው የወንጀል ክስን ማመን፤ ከተበዳዩ ጋር ታርቆ በእውነት መፀፀትን ማሳየት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የወንጀል ቅጣት ውሳኔን ለመገደብ በቅድመ

ሁኔታነት የተቀመጡ መመዘኛዎች ሳይሆኑ የወንጀል አጥፊው በመልካም ጠባይ የሚመራ ለመሆኑ እንዲያቀርብ የሚጠየቅ የዋስትና ማረጋገጫ በመሆኑ በህግ በግልፅ ያልተቀመጠ ክልከላ መሰረት ተደርጎ ቅጣቱ ሊገደብ አይገባም የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ላይ የወሰነውን የቅጣት ውሳኔ ማገዱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ በመቀበሉ የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁ/181393 ላይ ጥቅምት 26/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፀናበት ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## 10.4 ንግድ ምልክት መጠቀም ወንጀል ቅጣት ለመገደብ፤[45]

- የወ/ሕግ አንቀጽ 194(1) የተወሰነዉን የቅጣት ክብደት መነሻ በማድረግ ለመጀመሪያ አጥፊ ከ5 ዓመት የበለጠ ጽኑ እስራት ለተቀጣ አጥፊ ቅጣቱ እንዳይገደብለት ክልከላ አደረገ እንጂ የሌላን ሰዉ የንግድ ምልክት ያለአግባብ መጠቀም በአገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ ወንጀል መሆኑን የለየና ቅጣቱም ሊገደብ እንደማይገባ ክልከላ ያደረገ አይደለም፡፡
- በዚህ አግባብም ለተጠቀሰዉ ወንጀል የተወሰነ ቅጣት እንዳይገደብ በልዩ ሁኔታ ክልከላ ያደረገ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የለም፡፡
- በአገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈፀመ ወንጀል በመሆኑ ቅጣቱ ሊገደብ አይገባም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ አይደለም፡፡[46]

የሰ/መ/ቁጥር 262248

ቀን- ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች**:- ወ/ሮ መነን መላኩ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐ/ሕግ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

---

[45]የሰ/መ/ቁ 262248 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም)

[46]በሰ/መ/ቁ 171403(ህዳር 22 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24፣በሰ/መ/ቁ 177216 (ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም )ቅፅ 24

## ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ ተጠሪ በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች እና በአቶ ቴዎድሮስ ንጉሴ ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 76549 ጥር 03 ቀን 2016 ዓ.ም እና ጥር 07 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጡ ትዕዛዞች የጸናዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት አቶ ቴዎድሮስ ንጉሴ ላይ ያቀረበዉ ክስ ይዘት፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ እና ለ) እና የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 4 እና 41(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት አስበዉ ሚያዚያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት 10፡00 ሰዓት ሲሆን በሸገር ከተማ አስተዳደር መልካ ኖኖ ክ/ከተማ መልካ ገፈርሳ ወረዳ ልዩ ስሙ ወይብላ ማርያም ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የንግድ ምልክትነቱ አርማ የዜኒት የፀጉር ቅባት ሆኖ ንብረትነቱ የዜኒት ገብስ እሸት ኢትዮጵያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሆነ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ "ዜኒኒ" ተብሎ በቁጥር LTM/413/2006 ሚያዚያ 03 ቀን 2005 ዓ.ም የተመዘገበ ቅባቶችን፣ የፀጉር እና የሰዉነት ኮስሞቲክስ እንዲሁም የተለያዩ የንጽህናና የዉበት መጠበቂያ ምርቶችን በማምረት ለረጅም ዓመታት ሲጠቀምበት የቆየዉን የንግድ ምልክት መብቱን በግልጽ በመጣስ ዜኒት የሚል ጽሑፈት በላዩ ላይ የተቀረጸ እና የተለጠፈበት ጠርሙስ ዜኒት ገብስ እሸት ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሚል አርማ በመጠቀም ተመሳስሎ የተሠራ ፈሳሽ የፀጉር ቅባት ስሙ ኦክሊቫ የሚባለዉን ወደዚህ የግል ማህበር ጠርሙስ በመጨመር በወይብላ ማሪያም አካባቢ በጋራ በማምረት 2ኛ የዜኒት ምርት በማለት ለገበያ አቅርበዉ ተገኝተዋል፡፡ ተከሳሾች የባለቤትነት መብት ሳይኖራቸዉ በሕገ-ወጥ መንገድ በሌላ ሰዉ የንግድ ምልክት በመጠቀም የማታለል እና የማምታታት ወንጀል በመፈጸም የዜኒት ገብስ እሸት ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበርን መልካም ስም እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በመጉዳት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት በሚያስገኘዉ ከፍተኛ የግብር ገቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረሳቸዉ፤ በተለይም 2ኛ ተከሳሽ በተመሳሳይ የፀጉር ቅባት ምርት ላይ በራሱ ስም የንግድ ፍቃድ ባይኖረዉም በአመልካች ላይ በመደገፍ በሀሳቡና በድርጊቱ ሁሉ የወንጀል ድርጊቱን እና በሚያስገኘዉ ጥቅም ተካፋይ በመሆን በጋራ በፈጸሙት በሌላ ሰዉ የንግድ ምልክት የመጠቀም ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነዉ፡፡

ሁለቱም የስር ተከሳሾች የእምነት ክህደት ቃላቸዉን ሲጠየቁ በክሱ የተገለጸዉን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸዉን ገልጸዉ በመካዳቸዉ የስር ፍ/ቤት የዐ/ሕግ ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ በመቀጠለም የተከሳሾችን የመከላከያ ምስክሮችን ከሰማ በኃላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች መርምሮ ተከሳሾችን በተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ ስር የተመለከተዉን በመተላለፋቸዉ ጥፋተኛ በማድረግ አመልካችን በ4(አራት) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሁም የስር 2ኛ ተከሳሽን ደግሞ በ5(አምስት) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ተከሳሾቹ በዚህ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ በየደረጃዉ ላሉት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በዚህ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ እንዲሁም ቅጣት እንዲገደብ ያቀረቡት የገደብ ጥያቄ ተቀባይነት ባጣበት ዉሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

ተከሳሾቹ መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ በጋራ ያቀረቡ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ የነበረዉ ቴዎድሮስ ንጉሴ ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ሙሉ በሙሉ እና አመልካች በጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔዉ ላይ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ ግንቦት 22 ቀን 2016 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ለሰበር አያስቀርብም ተብሎ ዉድቅ የተደረገ በመሆኑ በዚህ ፍርድ አልተካተተም፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል የተባለዉ በአመልካች ላይ የተወሰነዉ የጽኑ

እስራት ቅጣት ሳይገደብ የታለፈበትን አግባብ ለማጣራት ሲሆን በዚህ ረገድ የቀረበዉ ቅሬታ ይዘት በአጭሩ፡- በስር ፍ/ቤት አመልካች ቅጣቱ በፈተና ጊዜ እንዲገደብላቸዉ መጠየቃቸዉን፤ ምክንያታቸዉም አመልካች የካንሰር ታማሚ ሆነዉ በመጨረሻ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ፤ ለአቅመ አዳምና ሔዋን ያልደረሱ 3 ልጆችን የሚያሳድጉ መሆናቸዉን ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት ወንጀሉ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ በመሆኑ ቅጣቱ መገደብ የለበትም በማለት የገደብ ጥያቄያቸዉን ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 171403 እና 177216 ቅጣትን ከመገደብ ጋር ተያይዞ ከሰጠዉ ገዥ ትርጉም ጋር የሚቃረን ዉሳኔ ነዉ፡፡ በወ/ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣትን ላለመገደብ የተቀመጡ ግልጽ ክልከላዎች ያሉ ሲሆን ወንጀሉ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ አይደለም እንጂ ተፈጽሟል ቢባል እንኳ በክልከላ ምክንያትነት አልተቀመጠም፡፡ ተከሳሾች የ3 ሕጻናት አባትና እናት ሆነዉ ሁለቱም እስር ላይ በመገኘታቸዉ ከልጆች መብትና ጥቅም አንጻር ሲታይ የሁለቱም ወላጆቻቸዉ እስር ላይ መቆየት ልጆችን ሜዳ ላይ የሚበትንና መልካም ዜጋ ሆነዉ ለማደግ የወላጆቻቸዉ ቁሳዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ የሚፈልጉ ከመሆናቸዉ አንጻር መብታቸዉን እጅጉን የሚጎዳ ነዉ፡፡ ስለሆነም የአመልካች የገደብ ጥያቄ ዉድቅ መደረጉ በሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 171403 እና 177216 የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ በገደብ እንዲለቀቁ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ታማሚ መሆኗንና የሦስት ህጻናት እናት ከመሆኗ አኳያ ያቀረበችዉ የገደብ ጥያቄ መታለፉ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ሰበር ችሎት በሰ/መቁ 171403 እና 177216 ላይ ከሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

ተጠሪ ሰኔ 07 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- አመልካች በወ/ሕ/አንቀጽ 192 እና 194 በገደብ ለመለቀቅ የሚያስችላቸዉን መስፈርቶችን አሟልተዉ አልተገኙም፡፡ ምክንያቱም አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል የሌላ ሰዉ የንግድ ድርጅት ላይ ጉዳት አድርሰዋል የሚል ሲሆን ለተጎጂዉ አካል የሚገባዉን ካሳ ስላልከፈሉ እና የፈጸሙትን ወንጀል ስላላመኑ በሕግ የተቀመጠዉን መስፈርት ስላላሟሉ የቅጣታቸዉ አፈጻጸም እንዲታገድ አለመደረጉ ተገቢ በመሆኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል የተባለዉ አመልካች ታማሚ መሆኗንና የሦስት ህጻናት እናት ከመሆኗ አኳያ ያቀረበችዉ የገደብ ጥያቄ መታለፉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ሰበር ችሎት በሰ/መቁ 171403 እና 177216 ላይ ከሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ አንጻር ለመመርመር ነዉ፡፡ አመልካች በገደብ ለመፈታት ላቀረበችዉ ጥያቄ በምክንያትነት የጠቀሰችዉ አመልካች ታማሚ እና የ3 ሕጻናት ልጆች እናት መሆኗን ሲሆን የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ዉድቅ ያደረገዉ ወንጀሉ የንግድ ምልክትን ያላግባብ በመጠቀም የተፈጸመ እና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ በመሆኑ አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብ ያቀረበችዉ ምክንያት የወ/ሕግ አንቀጽ 192 እስከ 197 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የማያሟላ ነዉ በሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ ቅጣት ሊገደብ የሚችለው ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በተለይ ቅጣቱ ከመፈጸሙ በፊት ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ በፍ/ቤቱ ሲታመንበት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ

በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ሲባል የሚደረግ ስለመሆኑ ከወ/ሕግ አንቀጽ 192 እና የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት ሌሎች የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። የቅጣት አፈጻጸምን መገደብ የማይቻለዉ ጥፋተኛዉ ከዚህ በፊት የጽኑ እስራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ የቀላል እስራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም፤ ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ የጽኑ እስራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነዉ በማለት የወ/ሕግ አንቀጽ 194(1) ደንግጓል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ በተለይ ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ጥፋተኛ በተከሰሰበት ወንጀል ከ5 ዓመት የበለጠ ጽኑ እስራት እስካልተቀጣ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197(1) ስር የተመለከቱትን ጥፋተኛዉ በመልካም ጠባይ እንደሚመራ፣ እንዲፈጽም የተሰጠዉን ግዴታ እንደሚቀበል ፍርድ ቤቱ እስካመነበት ድረስ ፍ/ቤት የወሰነዉን ቅጣት አፈጻጸም መገደብ የሚችል መሆኑን ነዉ።

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ ጥፋተኛዉ ቅጣቱ እንዲገደብለት ያቀረባቸው ምክንያቶች የጥፋተኛዉን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ አሳማኝ እና በጥፋተኛዉ ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሆነው ሳለ ፍ/ቤት ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ የአመልካች የቅጣት ገደብ ጥያቄ ከአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት የገደብ ጥያቄዉን ዉድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 171403 ገዥ ትርጉም ሰጥተበታል። በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ከዚህ ቀደም በሌላ ወንጀል የተቀጡበት ወንጀል ስለመኖሩ በተጠሪ በኩል ያልቀረበ በመሆኑና በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ እንዲቀጡ የተወሰነባቸዉ 4 ዓመት በመሆኑ በወ/ሕግ አንቀጽ 194(1/ለ) መሰረት ቅጣቱን ለመገደብ የሚከለክል የሕግ ክልከላ የለም። የስር ፍ/ቤት የተፈጸመዉ ወንጀል የሌላን ሰዉ የንግድ ምልክት ያለአግባብ መጠቀም በመሆኑ በሀገራዊ ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ ስለሆነ የአመልካች የገደብ ጥያቄ በወ/ሕግ አንቀጽ 192 እስከ 197 የተዘረዘረዉን መስፈርት አያሟላም በሚል ነዉ። ሆኖም የወ/ሕግ አንቀጽ 194(1) የተወሰነዉን የቅጣት ክብደት መነሻ በማድረግ ለመጀመሪያ አጥፊ ከ5 ዓመት የበለጠ ጽኑ እስራት ለተቀጣ አጥፊ ቅጣቱ እንዳይገደብለት ክልከላ አደረገ እንጂ የሌላን ሰዉ የንግድ ምልክት ያለአግባብ መጠቀም በአገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ ወንጀል መሆኑን የለየና ቅጣቱም ሊገደብ እንደማይገባ ክልከላ ያደረገ አይደለም። በዚህ አግባብም ለተጠቀሰዉ ወንጀል የተወሰነ ቅጣት እንዳይገደብ በልዩ ሁኔታ ክልከላ ያደረገ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የለም። ስለሆነም የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ዉድቅ ለማድረግ የሰጠዉ ምክንያት የወ/ሕግ አንቀጽ 194 እና 197 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 171403 የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ።

በሌላ በኩል አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብላቸዉ ያቀረቡት ምክንያት ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በነበራቸዉ ጋብቻ ዉስጥ ያፈሯቸዉ የሚስተዳድሯቸዉ 3 ልጆች ያሏቸዉ መሆኑ ሕጻናቶቹ ከአባታቸዉ በተጨማሪ እናታቸዉ በመታሰራቸዉ ምክንያት ሕጻናት ልጆች ለዕድገታቸዉ የሚሆን ቁሳዊም ሆነ ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ የሚያጡ ከመሆናቸዉም በተጨማሪ አመልካች መጨረሻ ደረጃ የደረሰ የጡት ካንሰር ታማሚ በመሆናቸዉ ቅጣቱ ሊገደብ ይገባል የሚል ነዉ። እነዚህ ሁለት ምክንያቶች በስር ፍ/ቤት በማስረጃ ተረጋግጠዉ በቅጣት ማቅለያነት ለአመልካች የተያዙ ናቸዉ። በተለይ አመልካች የተወሰነባቸዉን የእስራት ቅጣት በማረሚያ ቤት ሆነዉ እንዲፈጽሙ ቢደረግ ሕጻናት ልጆቻቸዉ የሁለቱን ወላጆቻቸዉን ድጋፍ የሚያሳጣቸዉ በመሆኑ በሕጻናቱ ላይ ቁሳዊም ሆነ ህሊናዊ ጫና የሚደርስባቸዉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም። እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ፍ/ቤቶች የሕጻናትን ደህንነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ ያለባቸዉ በመሆኑ በወንጀል ሕጉ ቅጣት ለመገደብ

የተቀመጡ ሁኔታዎች መሟላታቸዉን በማረጋገጥ ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ እንደሚገባ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 177216 በሰጠዉ ገዥ ትርጉም መሠረት አመልካች የተወሰነዉ የእስራት ቅጣት በስር ፍ/ቤቶች አለመገደቡ ስህተት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የተወሰነባት የአራት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት እንዲገደብላት ያቀረበቻቸዉ ምክንያቶች በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲትቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሚያሟሉ ከመሆናቸዉም በላይ አመልካች የእስር ቅጣቱን በሙሉ እንድትፈጽም ቢደረግ በሕጻናት ልጆቿ ላይ የሚደርሰዉን ቁሳዊና ስነ-ልቦናዊ ጫና ከግምት በማስገባት ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ የአመልካች የቅጣት ገደብ ጥያቄ ወንጀሉ በንግድ ምልክት ላይ የተፈጸመ ነዉ በሚል ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ሕጉ ቅጣት ስለሚገደብባቸው የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰ/መ/ቁ 171403 እና 177216 የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና አንቀጽ 10(1) መሠረት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1.በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 76549 ጥር 07 ቀን 2016 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 356664 የካቲት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 452708 መጋቢት 16 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) እና በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2.በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ከተወሰነዉ የአራት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ዉስጥ ያልፈጸመችዉ ቀሪ የጽኑ እስራት ጊዜ በአራት ዓመት የፈተና ጊዜ ሳይፈጸም ተገድቦ እንዲቆይ ተወስኗል፡፡

3.በወ/ሕግ አንቀጽ 197 መሰረት አመልካች ለገባችዉ የገደብ ግዴታ አፈጻጸም መተማመኛ ዋስትና ይሁን ዘንድ ብር 20,000(ሃያ ሺህ ብር) የሚበቃ ዋስ ታቅርብ ወይም ገንዘቡን እንድታሲዝ ታዟል፡፡ አመልካች የገደብ አፈጻጸም ዋስትና ግዴታ ስትገባ ግንቦት 22 ቀን 2016 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ያስያዘችዉ ገንዘብ እንዲለቀቅ ታዟል፡፡

4.የስር ፍ/ቤት አመልካችን ሆነ የስር 2ኛ ተከሳሽን አስመልክቶ የሰጠዉ ጥፋተኝነትና የቅጣት መጠን የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>**10.5 ከሕፃናት መብት ጋር በተያያዘ የገደብ ጥያቄ**</u>

- ፍ/ቤቶችም የሕጻናት ደሕንነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕገመንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ[47]
- በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት በመገደብ ህፃናቱ ተገቢውን የወላጅ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችል ዘንድ በአመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት ሊገደብ ሲገባው የተወሰነውን ቅጣት እንዳይፈጸም ለማገድ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ

[47] ሰ/መ/ቁ 262910 (ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ.ም)

የሚያስችሉ ሁኔታዎች ባልቀረቡበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ በወንጀል ሕጉ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው፡፡[48]

ሰ/መ/ቁ፡- 262910

ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- በሱ ፈቃድ መኮንን

ተጠሪ፡- ፍትህ ሚኒስቴር ስር ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ

መዝገቡ በክረምት ስራ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 97113፤ የካቲት 14 ቀን 2016 ዓ.ም የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ባለመቀበል የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 013671፤ ሚያዝያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ የቀረበን የገደብ ጥያቄ አስመልክቶ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/2 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ህዳር 30 ቀን 2016 ዓ.ም በግምት ከረፋዱ 4፡10 ሰዓት ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-26109 አ.አ የሆነ ዶስክ መኪና እያሽከረከረ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ክልል ልዩ ቦታው 3ኛ ሻለቃ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሲደርስ ከመንገድ የቀኝ ጠርዝ ይዛ ስትጓዝ የነበረችውን የግል ተበዳይ ወ/ሮ አሪፍ አይኔ ዳኘውን በመግጨት በግል ተበዳይ የግራ እግሯ የታችኛው ቅልጥምና ትልቁ የታችኛው ክፍል እንዲደቅ ያደረገ እና በቁርጭምጭሚቷ በዳርኛው በኩል ወጣ ብሎ ባለው አጥንት ክፍል ስብራት እንዲደርስባት ያደረገ በመሆኑ በቸልተኝነት በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ክሱ ለአመልካች ተነቦላቸው መቃወሚያ የሌላቸው መሆኑን ከገለጹ በኋላ የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁ የድርጊቱን መፈጸም አምነው ባመኑት መሰረት ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማስላት በዓቃቤሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፤ ተጠሪ በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝላቸው ካቀረባቸው ምክንያቶች ውስጥ የተጠሪ የቀድሞ ባሕርይ መልካም የነበረ መሆኑን፤ ቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑን እና ከግልተበዳይ ጋር

[48]በሰ/መ/ቁ 177216 (ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24 ፣ የሰ/መ/ቁ 262248 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም) ገደብ ጋር ተያይዘው የህፃናት መብትን በተወሰነ መልኩ እንደምክንያት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ወስኗል፡፡

የታረቁ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ሶስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ደረጃ ሶስት እርከን ዘጠኝ ስር ተይዞ የነበረው መነሻ ቅጣት ሶስት እርከን በመቀነስ እርከን 6 ስር ያርፋል በማለት ቅጣት ሲወስን አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ባለመቀበል በስምንት ወር ቀላል እስራት እና በብር 3000(ሶስት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

አመልካች የስር ፍ/ቤት የገደብ ጥያቄውን ባለመቀበል በእስራት እንዲቀጡ መወሰኑን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ይግባኝ ቅሬታውን መርምሮ ቅጣት አወሳሰኑንና የገደብ ጥያቄው ውድቅ መደረጉን አግባብነት ለመመርመር በሚል ያስቀርባል ካለ በኃላ በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ በአመልካች ያቀረባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ውስጥ በስር ፍርድ ቤት ከተያዙት ሶስት ማቅለያ ምክንያቶች በተጨማሪ አመልካች ወንጀሉን መፈፀማቸው ሙሉ በሙሉ ማመናቸው እና ማህበራዊ ተሳትፎ ስለማድረጋቸው በማስረጃ የተረጋገጠው ሁለት ማቅለያ ምክንያት መያዝ ሲገባ አለመያዙ ተገቢ ባለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ከተያዙላቸው ሶስት ማቅለያ ምክንያቶች በተጨማሪ ሁለት ማቅለያ ምክንያቶች ተይዞላቸው አጠቃላይ አምስት ማቅለያ ምክንያቶች ሲያዝላቸው ከእርከን 9 ወደ 4 ዝቅ ብሎ ሊቀጡ የሚገባው በ8 ወር ቀላል እስራት ሳይሆን በ 4 ወር ቀላል እስራት ሊሆን ይገባል በማለት የእስራት ቅጣት በማሻሻል ሲወስን ቅጣቱ ቢገደብ መልካም ፍሬ ያስገኛል ብሎ ችሎቱ አላመነም በሚል የገደብ ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ 013671፤ ሚያዝያ 10 ቀን 2016ዓ.ም በሥር የተወሰነው የእስራት ቅጣት በማሻሻል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም የስር ፍ/ቤት አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኔ የሁለት ህጻናት ልጆች አባት በመሆኔ አንዱ ልጄ ከፍተኛ የሆነ የልብ ህመም ስላለበት እና ወደ ውጭ ሀገር ወስጄ ለማሳከም እየሞከርኩ ባለሁበት የታሰርኩ በመሆኑ ከነማስረጃው አቅርቤ እያለ፤ ከግል ተበዳይ ጋር መታረቄንና ወንጀሉን መፈፀሜን ሙሉ በሙሉ ያመንኩ መሆኑ ሲታይ በተለይ ህጻናት ልጆቼ ላይ ከሚደርሰው ቁሳዊም ሆነ ህሊናዊ ጫና ለማስቀረት ሲባል ህጻናት የወላጆቻቸውን ድጋፍና እንክብካቤ አግኝተው እንዲያድጉ ሲባል ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 177216 ከዚህ ጋር በተያያዘ ገዢ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶ እያለ፤ የግል ተበዳይን በመካስ እርቅ መፈፀሜ እና ወንጀሉ ስለመፈፀሜ ሙሉ በሙሉ አምኜ እያለ የስር ፍ/ቤት የቅጣት ገደብን አስመልክቶ የሰጣቸውን የሕግ ትርጉሞች ባለመከተል ቅጣቱን ሳይገድብ መቅረቱ ተገቢ አይደለም፤ ከአጠቃላይ የወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ አንጻር ቅጣቱ መገደብ ሲገባው አመልካች ቅጣት እንዲገደብ ያቀረብኩትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት አመልካች የግል ተበዳይን በመካስ በእርቅ ስለጨረስንና በልብ ህመም የሚታመም ልጅ ስላለኝ ወደ ውጭ ሄዶ መታከም ስላለበት የተወሰነብኝ የእስራት ቅጣት እንዲገደብልኝ በማለት ያቀረበውን የገደብ ጥያቄ ውድቅ ያደረገበትን አግባብነት ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 177216(ቅጽ 24) ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ለተጠሪ ሰኔ 18 ቀን 2016ዓ.ም ጽፎ የሰጠው መልስ በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት ሳይፈፅም በገደብ ቢቆይለት ተቃውሞ የለኝም የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፤ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ይህ በሰበር ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ሙሉ በሙሉ ማመኑ፤ ከዚህ በፊት የወንጀል ድርጊት ፈጽሞ የማያውቅ እና የዘወትር ባሕርይው መልካም መሆኑ፤ ከግል ተበዳይ ጋር እርቅ መፈፀሙን፤ የቤተሰብ

አስተዳዳሪ ባለትዳር እና የሁለት ህጻናት ልጆች አባት እና አንዱ ልጁ በከፍተኛ የልብ ሕመም የሚታመምና ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ መታከም ስላለበት ለማሳከም በሂደት ላይ ያለ መሆኑን፣ እንዲሁም በተለያየ ማሕበራዊ ጉዳዮች በመሳተፍ እና ገንዘብ በማዋጣት ማሕበረሰቡን የሚያገለግል እና ይህም የመልካም ዜጋ ተግባር መሆኑን በመግለጽ በስር ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ ጉዳዩ ታይቶ አምስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የተያዙለት መሆኑን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ከቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ መገንዘብ ችለናል፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ሕጉ ዓላማ ወንጀል እንዳይፈጸም ማድረግ ሲሆን ይህንንም የሚያደርገው ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ወንጀል ፈጻሚዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ቅጣት ሲገደብ የፍርዱ ውሳኔ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ከሌላው ውጤት ጋር ነዋሪ የሚሆን በመሆኑ ቅጣትን መገደብ በወንጀለኛው ላይ ቅጣት እንዳይፈጸም የማድረግ ውጤት ብቻ ያለው ሳይሆን ወንጀለኛው ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲታቀብ የማድረግ ውጤት ስላለው ቅጣትን መገደብ የወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ ከሚሳካባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡

ቅጣት ሊገደብ የሚችለውም ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው፣ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፣ጥፋቱ በመቀጮ፣ በግዴታ ስራ ወይም ከአምስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻ እስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን 'ያመነበት' እንደሆነ፣ እንዲሁም ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሳይፈጸም በገደብ ለማቆየትም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197/1/ እንደተመለከተው በቅድሚያ ሊሟሉ የሚችሉትን ሁኔታዎች አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ እነዚህም ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ ማመን፣ጥፋተኛው እንዲፈፀም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ማረጋገጥ፣ ጥፋተኛው በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ መስጠት ስለመሆናቸው ሕጉ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈጻፀም መተማመኛ ዋስትና እንዲያቀርብ እንደሚያደርግ ተጠቃሹ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር አስፍሮ ይገኛል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የተጣለውን የአራት ወር ቀላል እስራት ቅጣት እንዲገደብ የቀረበውን አቤቱታ ከዚህ በላይ የተመለከቱን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን መርምሮ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ሲቀርብለት አመልካች በቅጣት

ማቅለያነት ያቀረበውንና ፍርድ ቤቱ በማቅለያነት የተቀበላቸውን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን በማሻሻል የወሰነ ሲሆን አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተ ግን ከወንጀሉ ልዩ ባህሪ፤ ህጉ ሊያሳካ ከሚፈልገው ዓላማና ግብ አንጻር ቅጣቱ ቢገደብ መልካም ፍሬ ያስገኛል ተብሎ አይታመንም በሚል ጠቅለል ባለ አነጋገር ሳይቀበለው መቅረቱን ውሳኔው ያሳያል፡፡ ፍ/ቤቱ ቅጣት ለጊዜው ለማገድ መነሻ የሚሆነው በጥፋተኛው ለወደፊቱ ጥፋቱን ለማረም እንደሚችል ሊያምን ወይም ላያምን የሚችለው የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ አስመልክቶ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቶች በሕግ እና በተገቢ ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ከመሆኑ አኳያ አመልካች ቅጣቱን እንዲገደብለት ያቀረባቸው ምክንያቶች ፍ/ቤቱን የሚያሳምኑ ናቸው ወይም አይደሉም ለማለት ሕግን መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ምክንያት በመስጠት እንጂ በደፈናው ቅጣቱን መገደብ መልካም ፍሬ ያስገኛል ብሎ ፍርድ ቤቱ አላመነበትም በማለት ሊሆን አይገባም፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የቀረበበትን ክስ ሙሉ በሙሉ በማመን የእምነት ክሕደት ቃሉን ሰጥቶ ፍ/ቤቱም አመልካች ባመነው መሠረት በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ያለው መሆኑን፤ አመልካች ከዚህ በፊት የወንጀል ድርጊት ፈጽሞ የማያውቅ እና የዘወትር ባሕርይው መልካም መሆኑ፤ ከግል ተበዳይ ጋር እርቅ መፈፀሙን፤ በተለያየ ማሕበራዊ ጉዳዮች በመሳተፍ ማሕበረሰቡን የሚያገለግል መሆኑን እንዲሁም ባለትዳር እና የሁለት ህጻናት ልጆች አባት መሆኑ እና በከፍተኛ ሕመም ላይ ያሉትን እናቱን የሚንከባከብ መሆኑን፤በተለይ አንዱ ልጁ በከፍተኛ የልብ ህመም ታማሚ በመሆኑ ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ መታከም ያለበት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ እውነታዎች ናቸው፡፡ እነኚህ ሁኔታዎች የተከሳሹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ እና ቅጣቱ ቢገደብ የአመልካችን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚያስችሉ አሳማኝ ሁኔታዎች ሲሆኑ በተለይ ደግሞ አመልካች የሁለት ህጻናት ልጆች አባት መሆኑና አንዱ ልጁ የልብ ህመም ታማሚ በመሆኑ ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ለመታከም ህጻናቱ የወላጆቻቸው ጥበቃ፤እንክብካቤና ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው እሙን ነው፡፡ የህጻናት ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት ረገድ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 36(2) እና ኢትዮጵያ የሕጋችን አካል እንዲሆኑ ተቀብላ ካፀደቀችው የሕጻናት መብት የቃልኪዳን ሰነድ ስምምነት አንቀጽ 3 ድንጋጌ ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤ በፍርድ ቤቶች፤ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕጻናት ደሕንነት በቀደምትነት መታሰብ ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በሰ/መ/ቁ 177216(ቅጽ 24 የታተመ) ገዢ የሆነ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች በእስር ቢቆዩ በሕፃናት ልጆቻቸው ላይ ሊደርስ ከሚችለው ቁሳዊም ሆነ ኅሊናዊ ጉዳት ከግምት በማስገባት ይህን ለማስቀረት ሲባል እንደሁም የአንዱ ህጻን ልጅ ያለበት ከፍተኛ የጤና ሁኔታ የወላጅ እንክብካቤ እና ድጋፍ የሚስፈልገው ከመሆኑ አንጻር፤ ፍ/ቤቶችም የሕጻናት ደሕንነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕገመንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት በመገደብ ህፃናቱ ተገቢውን የወላጅ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችል ዘንድ በአመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት ሊገደብ ሲገባው የተወሰነውን ቅጣት እንዳይፈጸም ለማገድ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ባልቀረቡበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ በወንጀል ሕጉ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የአራት ወር የእስራት ቅጣት በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ እንዲገደብ በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና 197/1 መሠረት ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 97113፤ የካቲት 13 ቀን 2016 ዓ.ም የአመልካች የገደብ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ክፍል እንዲሁም የገደብ ጥያቄ ውድቅ መደረጉን በማጽናት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 013671፤ ሚያዝያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት በአመልካች ላይ የተላለፈው የአራት ወራት እስራት ቅጣት ቀሪው እስራት ሳይፈጸም ለሁለት ዓመት እንዲገደብ በማለት ወስነናል፡፡

ትዕዛዝ

- አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 መሠረት የብር 1000 /አንድ ሺህ /መተማመኛ ዋስትና እንዲያስይዝ ታዟል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ

### 11. የፍ/ብሄር እና የወንጀል ጉዳይ ተጣምሮ የሚታይበት አግባብ

- የፍታብሔር ክርክር ከወንጀል ክርክር ጋር ሊጣመር የሚችልበት መሠረታዊ ሁኔታ በወንጀል ህግ አንቀጽ 101 የተደነገገ ሲሆን የፍታብሔር ክርክሩ የወንጀል ስለባ የሆነ ሰው የሚያቀርበው የካሣ ጥያቄ በሆነ ጊዜ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ ሊወሰን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡
- በወንጀል የሚደረገው ክርክርና በፍታብሔር በሚደረገው ክርክር የሚያዘው ጭብጥና የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደዚሁ የማስረጃ አመዛዘን ሥርዓቱ የተለያየ ነው፡፡[49]

የሰ/መ/ቁጥር - 59045

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የስልጤ ዞን ምርመራና ክስ ዐቃቤ ህግ ቃሲም ባጼ

[49]የሰ/መ/ቁ 59045 (ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ በዚህ ሰበር መዝገብ የተሰጠው የህግ ትርጉም የፍታብሔር ክርክር በወንጀሉ ጉዳት ደርሶብናል የሚሉ ሰዎች ካሣ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ እንዳልሆነ፣ በወንጀል የሚደረገው ክርክርና በፍታብሔር በሚደረገው ክርክር ጭብጥና የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደዚሁ የማስረጃ አመዛዘን ሥርዓቱ የተለያየ ስለመሆኑ እና በወንጀል መዝገብና በፍታብሔሩ መዝገብ ተከራካሪ የሆኑት ሰዎች የተለያዩ ስለመሆናቸው በመዘርዘር ተመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ጌታቸው አስራት - ቀረቡ

2. አቶ አመነ ድሪባ - ቀረቡ

3. አቶ ሰንበቶ ጃራ - አልቀረቡም

4. አቶ ፋንታሁን ዘውዴ - አልቀረቡም

5. አቶ አድነው ያዕቆብ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ለወረዳው ፍ/ቤት የወረዳው መርማሪ ከሣሽ ዐቃቤ ህግ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 686 ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ በዳሎቻ ከተማ 01 ቀበሌ ልዩ ስሙ ሰሊም ሰፈር ከሚባለው አንደኛ ተከሣሽ ለመኖሪያ ቤት የተፈቀደለትንና የሰራውን ቤት አላግባብ ለመሰረተ ክርስቶስ አማኞች በመጸለያነት እንዲጠቀሙበት በመስጠቱ በርካታ የእምነት ተከታዩች ተሰባስበው ከግንቦት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ ሁለት ስዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ከፍተኛ ጩኸት በማሰማትና በድምጽ ማጉሊያ መሣሪያ በመጠቀም የሁከት ማድረስ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች ክሱን ክደው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ዐቃቤ ህግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ዐቃቤ ህግ በክሱ የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 113 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት በመለወጥ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 815 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የደንብ መተላለፍ ጥፋት የፈጸሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው በብር 80 /ስማኒያ ብር/ መቀጫ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ተጠሪዎቹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ መርማሪ ከሣሽ የሰጠው አስተያየትና የቀረበውን ክርክር ተቀብሎ ከመዘነ በኋላ የክልሉ መርማሪ ከሣሽ የተጠሪዎችን የሰበር አቤቱታ በመደገፍ የተከራከረ መሆኑን በውሣኔው በገጽ 9 ካሰፈረ በኋላ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በወረዳው ፍ/ቤት በትዕዛዝ የተዘጋው የጸሎት ቤት እንዲከፈት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት የወረዳው መርማሪ ከሣሽ ያቀረበው የወንጀል ክስ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 ቀርቦና ክርክር ተደርጐበት ፍ/ቤቱ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በተጠሪዎች ላይ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የወንጀል ይግባኝ የስልጤ ዞን በመዝገብ ቁጥር 05761 በማየት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ ተጠሪዎች የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት የወንጀል ሰበር አቤቱታ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ሲታይና ክርክርና አስተያየት የተደረገበት እንደሆነ በየደረጃው የተከፈቱትን መዛግብትና አመልካች ያቀረበውን ክርክር ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከአንደኛው ተጠሪና ከአምስተኛው ተጠሪ ጋር የከተማዋን ፕላን መከበር ማዕከል ያደረገ ክስ የፍታብሔር ክርክር ለዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ጉዳዩ ከወረዳው ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 02428 ክርክር ከተደረገበት በኋላ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የመኖሪያ ቤት እንዲገነቡ በተሰጣቸውና በሰሩት ቤት ከመኖሪያነት ውጭ ለሆነ አገልግሎት ማዋል የሌለባቸዉ መሆኑ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የፍታብሔር ይግባኝ ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአንደኛና የአምስተኛ ተጠሪን የፍታብሔር ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 05607 በማየት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የህግም ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሌለ መሆኑን ገልጾ ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የወረዳው ፍ/ቤት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 የሰጠውን ወሣኔ የዞኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 05607 ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ራሱን የቻለ የሰበር አቤቱታ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ሲመረምር ከቆየ በኋላ የፍታብሔሩን ጉዳይ የወንጀሉ ጉዳይ ከሚታይበት የሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከህግ ውጭ ሁለቱን መዛግብት በማጣመርና አግባብነት የሌላቸዉን የህግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በወንጀሉ መዝገብም ሆነ በፍታብሔር መዝገብ የሚነሣው ክርክርና የሚያዘው ጭብጥ ተመሣሣይ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ሁለቱን መዛግብት በማጣመር መርምሮ ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም:: አመልካች የመኖሪያ ቤት በመስራት እንድትገለገሉበት በተፈቀደ ቦታ ላይ ለአምልኮ አገልግሎት አውለዋል በማለት ያቀረበው ክስ በህገመንግስቱ የተረጋገጠልንን የሀይማኖትና የእምነት ነጻነት የሚጋፋ ነው፡፡ አገሪቱ ኋላ ቀር አገር በመሆኑ የመኖሪያ ሰፈር የኢንዱስትሪ ሰፈር የሚባል የሌላት ሲሆን ቤተክርስቲያንና መስጊዶችን በመኖሪያ ቤት ውስጥ ማግኘት የተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ በመኖሪያ ሰፈር ለጸሎትና የአምልኮት ማከናወን አይቻልም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልስ መልሱ ከተማዋ እድገቷን የምትመራበት ፕላን አለ፡፡ በከተማዋ ፕላን መሠረት መስጊዶች፣ ቤተክርስቲያንና የጸሎት ቤቶች መገንባት ሲያስፈልግ የሚገነቡበት ቦታ ተለይቷል፡፡ በፕላኑ መሠረትም የጸሎት ቤት መገንቢያ ቦታ ተሰጥቷቸው እያለ የመኖሪያ ቤታችን ተቀይሮ የጸሎት ቤት ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 እና የፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 35808 ጋር በማጣመር ተጠሪዎች የፈጸሙት የሁከት ተግባር የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው በወረዳው ፍ/ቤት በወንጀል ተከሣሽ የነበሩት ሶስቱም ተጠሪዎች የነበሩ መሆኑንና ተጠሪዎች በወረዳው ፍ/ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 በዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁ. 05761 ይግባኝ ባይ በመሆን የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ በመሆኑና የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከላይ ቁጥራቸው በተገለጸው ሁለት መዛግብት የሰጡትን የወንጀል ፍርድ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ ስለዚህ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡትን የወንጀል ፍርድ በመቃወም በክርክሩ ተሣታፊ የሆኑት አምስቱም ተጠሪዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የመኖሪያ ቤት ለመስራት የተፈቀደላቸውን ቦታና ለመኖሪያነት የሰሩትን ቤት ለአምልኮት አገልግሎት ለዘላቂነት እንዲውሉ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት የፍታብሔር ክስ የመሠረተው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነው፡፡ የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ክስ ያቀረበው በአምስቱ ተጠሪዎች ላይ ሣይሆን በአንደኛ ተጠሪና በአምስተኛው ተጠሪ ላይ ብቻ ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት በማዘጋጃ ቤቱ የቀረበውን የፍታብሔር ክርክር በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 በማየት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 05607 በማየት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪዎች የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር አቤቱታቸው በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ሲመለከት የቆየ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የፍታብሔር ክርክር ከወንጀል ክርክር ጋር ሊጣመር የሚችልበት መሠረታዊ ሁኔታ በወንጀል ህግ አንቀጽ 101 የተደነገገ ሲሆን የፍታብሔር ክርክሩ የወንጀል ስለባ የሆነ ሰው የሚያቀርበው የካሣ ጥያቄ በሆነ ጊዜ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ እንዲወሰንለት ማመልከት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፍታብሔር ክርክር በወንጀሉ ጉዳት ደርሶብናል የሚሉ ሰዎች ካሣ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል የሚደረገው ክርክርና በፍታብሔር በሚደረገው ክርክር የሚያዘው ጭብጥና የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደዚሁ  የማስረጃ አመዛዘን ሥርዓቱ የተለያየ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል መዝገብና በፍታብሔሩ መዝገብ ተከራካሪ የሆኑት ሰዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ በፍታብሔር መዝገብ ተከራካሪ የሆነው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሲሆን አመልካች የሚከራከረው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በመወከል ነው፡፡ የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሚከራከረው ከአምስቱ ተጠሪዎች ጋር ሣይሆን ከአንደኛውና ከአምስተኛው ተጠሪ ጋር ብቻ ነው፡፡ በወንጀሉ መዝገብ ከስር ጀምሮ የመርማሪ ከሣሽና በአምስቱ ተጠሪዎች ተከራካሪ መሆናቸውን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ በፍታብሔር የሚከራከሩበትን የሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 አመልካችና ተጠሪዎች ከሚከራከሩበት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር ማየቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 101 መሠረታዊ የህግ ድንጋጌ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ተጠሪዎች ከግንቦት 22 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ጸሎት እንዲደረግ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የድምጽ ሁከት የመፍጠር የደንብ መተላለፍ ጥፋት ፈጽመዋል በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልጾ አመልካች አስተያየትና ክርክር ያቀረበ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 በሰጠው ውሣኔ በግልጽ አስፍሯል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የደንብ መተላለፍ ጥፋት እንዳልፈጸሙ የክልሉ ሰበር ችሎት በሰጠው አስተያየትና ባቀረበው ክርክር የተከራከረ በመሆኑ ተጠሪዎች በወንጀሉ ጥፋተኛ ተብለው የተወሰነባቸውን ቅጣት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሻረው አግባብ ነው በማለት የቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሻረው የአመልካችን ክርክርና አስተያየት መሠረት በማድረግ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የወንጀሉን ጉዳይ በተመለከተ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር የሰጠውን ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 ንኡስ አንቀጽ 2/ለ/1 መሠረት አጽንተናል፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ክርክር የያዘውን የሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ከወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር አይቶ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የወንጀሉን ጉዳይ በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በዳሎቻ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔና የስልጤ ዞን በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 05761 የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪዎች ከቀረበባቸው የወንጀል ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አንደኛ ተጠሪና አምስተኛ ተጠሪ የዳሎቻ ወረዳ ፍርድ ቤት ከዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ጋር የነበራቸውን የፍታብሔር ክርክር በማየት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 የሰጠው ውሣኔ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 05607 ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ያቀረቡትን ክርክር የወንጀሉ ጉዳይ ከሚታይበት የሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 አጣምሮ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡
3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪና አምስተኛ ተጠሪ በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አመልካች የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በመወከል ያቀረበውን ክርክር የወረዳ ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍታብሔሩን ጉዳይ በተመለከተ የሰጡትን ውሣኔና ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጓቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 391/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ በዚህ ፍርድ የወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አስራ ሁለት</u>

### <u>12. የወንጀል ይርጋ[50] ፣ ይቅርታ[51] እና መሰየም[52]</u>

- በሕጉ በተለየ ሁኔታ በግልጽ ካልተደነገገ በቀር ቀላል እስራት ከአስር ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 106(1) ተመልክቷል፡፡በሌላ በኩል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ ከአንድ ዓመት በላይ በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል የክስ ማቅረቢያው የይርጋ ጊዜ አምስት ዓመት ስለመሆኑ፤
- የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመርህ ደረጃ ጥፋተኛው ወንጀሉን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ እና ይሁን እንጂ የወንጀሉ ድርጊት እየተደጋገመ ተፈጽሞ እንደሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የወንጀል ድርጊት ከተፈጸመበት

[50]የሰ/መ/ቁ 105406 (መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18
[51]የሰ/መ/ቁ 41248 (ሰኔ 23 ቀን 2002ዓ.ም) ቅፅ 10
[52]የሰ/መ/ቁ 161791 (የካቲት 25 ቀን 2011ዓ.ም) ቅፅ 24፣የሰ/መ/ቁ 61221(መስከረም 22 ቀን 2005ዓ.ም)ቅፅ 14

ቀን አንስቶ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም የወንጀሉ ድርጊት ለረጅም ጊዜ ሲፈጸም የቆየ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የወንጀሉ ድርጊት ካቆመበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ፤[53]

የሰ.መ.ቁ 105406

መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ኃይሉ ወልዴ መኮንን - ጠበቃ ጳውሎስ ተሰማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን ለእርሳቸው አገልግሎት ባልታሰበ ወይም እርሳቸውን በማይመለከት ሰነድ የመገልገል የወንጀል ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት በማሰብ ትክክለኛ ስማቸው ኃይሉ ወልዴ ሆኖ እያለ ሰይፉ ወልዴ እንደሆነ አድርገው በመግለጽ ለእርሳቸው አገልግሎት ያልታሰበውን ወይም እርሳቸውን የማይመለከተውን እና የወንድማቸው ስይፉ ወልዴ የሆነውን ከመድኃኒዓለም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሰጠ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ የምስክር ወረቀት (ትራንስክሪፕት) እና ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መልቀቂያ የምስክር ወረቀት በማቅረብ በየካቲት ወር 1977 ዓ.ም. በኢትዮጵያ አየር መንገድ የተቀጠሩ በመሆኑ፣ ከተቀጠሩ በኃላ ወንጀሉን ለመደበቅ በማሰብ ህዳር 30 ቀን 1979 ዓ.ም ፍርድ ቤት ቀርበው ሰይፉ ወልዴ እና ኃይሉ ወልዴ በሚሉ ሁለት ስሞች ሲጠሩ እንደነበረ እና አሁን ግን ኃይሉ ወልዴ በሚለው ስም ብቻ ለመጠራት እንደሚፈልጉ በመግለጽ በፍርድ ቤት በማስወሰን ይህንን የፍርድ ቤት ውሳኔ ለተቀጠሩበት መስሪያ ቤት አቅርበው ከማህደራቸው ጋር እንዲያያዝ በማድረግ እስከ ህዳር 19 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በበረራ አስተናጋጅነት እና በመሪ በበረራ አስተናጋጅነት ሲሰሩ የቆዩ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 385(1)(ለ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ሀሰተኛ በምስክር ወረቀት የመገልገል ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው በክሱ የተመለከተውን ወንጀል አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ያቀረባቸውን ሶስት ምስክሮች ምስክርነት ከሰማ እና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ አመልካች መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ

---

[53]በሰ/መ/ቁ 45572 (የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10 ፣ የሰ/መ/ቁ. 79389 (መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ የሰ/መ/ቁ. 77097 (ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 14 ፣ የሰ/መ/ቁ 95875 (ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16

መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች የሰው መከላከያ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ መግለጫው ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 ዘርዝሮ በማስረጃነት ካቀረባቸው ሰነዶች መካከል ሶስቱን በመከላከያነት ጭምር የጠቀሱ ከመሆኑም በላይ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ኃይሉ ወልዴ በሚል ስም የተሰጠው የምስክር ወረቀቶችን፣የስራ እድገት ደብዳቤን እና በዚሁ ስም የተሞላ የጡረታ ቅጽ በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ በተጠሪ የቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ አስተባብለዋል ሊባሉ የሚችሉት በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች ለስራ ቅጥር ስላለመገልገላቸው ወይም የትምህርት ማስረጃዎቹ የሌላ ሰው ሳይሆኑ የራሳቸው ስለመሆናቸው በማስረዳት መሆኑን እና ይሁን እንጂ አመልካች ያቀረቧቸው የመከላከያ ሰነዶች ከላይ ከተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች አንዱንም የማያስረዱ መሆኑን ገልጾ አመልካች ባቀረቡት የሰነድ መከላከያ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን፣ ድንጋጌው የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ መሆኑን፣ አመልካች ሰነዱን በመገልገል ከሃያ ዓመት ላላነሰ ረጅም ጊዜ ያልተቋረጠ ጥቅም ያገኙ እና ፍርድ ቤትን ሳይቀር አሳስተው የመጀመሪያውን ወንጀል ለመሸፈን ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸው በድርጊቱ አለመፀፀታቸውን የሚያሳይ ነው በማለት የእስራት ቅጣቱን አማራጭ በመውሰድ እና ወንጀሉንም በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በከባድ ደረጃ በመመደብ፣በድንጋጌው ስር በከባድ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ከተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ የሁለት ዓመት እስራት መነሻ አድርጎ በመያዝ፣ይህ የቅጣት መጠን በመመሪያው አባሪ አንድ በእርከን 10 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አለመኖሩን፣ የአመልካቹ የዘወትር ጠባይ መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው በሁለት የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዙ ፍቅድ ስልጣኑን ከእርከን 10 ወደ እርክን 8 ዝቅ የሚል መሆኑን በዝርዝር ገልጾ በመጨረሻ አመልካች በእርከን 8 በተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን መሰረት በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ወንጀሉን ፈጽመዋል ከተባለበት ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት አመልካች ላቀረቡት መቃወሚያ የስር ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ድርጊቱ ከቆመበት ህዳር ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ እንጂ ድርጊቱ መፈጸም ከጀመረበት ከ1977 ዓ.ም. ጀምሮ አይደለም በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 219(2) ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ በአብላጫ ድምጽ በተሰጠ ትዕዛዝ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ፡-

1. በአመልካች የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
2. በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች የተከሰሱበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ሲሆን በሕጉ በተለየ ሁኔታ በግልጽ ካልተደነገገ በቀር ቀላል እስራት ከአስር ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 106(1) ተመልክቷል፡፡በሌላ በኩል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ ከአንድ ዓመት በላይ በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል የክስ ማቅረቢያው የይርጋ ጊዜ አምስት ዓመት ስለመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 217(1)(ሠ) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመርህ ደረጃ ጥፋተኛው ወንጀሉን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ እና ይሁን እንጂ የወንጀሉ ድርጊት እየተደጋገመ ተፈጽሞ እንደሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የወንጀል ድርጊት ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም የወንጀሉ ድርጊት ለረጅም ጊዜ ሲፈጸም የቆየ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የወንጀሉ ድርጊት ካቆመበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 219(2) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

አመልካች በአየር መንገዱ የተቀጠሩት በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም የተሰጠውን የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ እና እስከ ህዳር ወር 2005 ዓ.ም. ድረስ በአየር መንገዱ ውስጥ በስራ ላይ ሊቆዩ የቻሉትም በእነዚሁ የትምህርት ማስረጃዎች አማካይነት እና መነሻ በተፈጠረ የስራ ቅጥር ግንኙነት ወይም የስራ ውል መሰረት መሆኑ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ የይርጋ ጊዜው መቆጠር መጀመር የሚገባው ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ነው በማለት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት አመልካች ለወንድማቸው ለአቶ ሰይፉ ወልዴ የተሰጠውን የትምህርት ማስረጃ በ1977 ዓ.ም ለኢትዮጵያ አየር መንገድ አቅርበው የተመዘገቡ ቢሆንም የተቀጠሩት ግን ፈተናውን አመልካች ራሳቸው ተፈትነው በመሆኑ እና የተቀጠሩበትን ስራ ለረጅም ጊዜ ሲሰሩ የነበረውም አየር መንገዱ በሰጣቸው ስልጠና ባገኙት ዕውቀት እንጂ በምዝገባ ጊዜ ባቀረቡት የትምህርት ማስረጃ ባለመሆኑ ስልጠናውን አጠናቀው ስራ ከጀመሩ እና በተለይ ደግሞ ኃይሉ ወልዴ በሚለው ስም ብቻ እንዲጠሩ በፍርድ ቤት ካስወሰኑበት ከ1979 ዓ.ም. ጀምሮ በሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጠው የትምህርት ማስረጃ ተገልግለዋል ወይም ጥቅምን ወይም መሻሻልን አግኝተዋል ሊባሉ አይገባም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ለስራው የተመዘገቡትም ሆነ ፈተናውን ወስደው ለስልጠና እና ለስራ ቅጥር የበቁት የእርሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች በመገልገል በመሆኑ አመልካች ስልጠናውን ካጠናቀቁበት ቀንም ሆነ ስራ ላይ ከተሰማሩበት ቀን ጀምሮ የትምህርት ማስረጃዎቹ አገልግሎት ተቋርጧል ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ለስራው የተቀጠሩት የራሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች በመገልገል መሆኑን ስልጠናውን ባጠናቀቁበት ቀን ወይም ስራ ላይ በተሰማሩበት ቀን ለአየር መንገዱ አስታውቀው የነበረ ስለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት የእርሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች የመገልገላቸው ሁኔታ እንዲያበቃ ወይም እንዲቋረጥ የተደረገ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ለረጅም ጊዜ ሲፈጸሙ የቆዩትን ወንጀሎች የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 79389 በ12/07/2005 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች ወንጀሉን አላደረግኩም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የራሳቸው ያልሆኑትን እና ሰይፉ ወልዴ ለተባሉ ወንድማቸው የተሰጡትን የትምህርት ማስረጃዎች የራሳቸውን ፎቶግራፍ በመለጠፍ የራሳቸው እንደሆኑ አስመስለው ለኢትዮጵያ አየር መንገድ በማቅረብ በ1977 ዓ.ም ለስራ ቅጥር የተገለገሉበት መሆኑ እና በዚህ ሁኔታ በተቋቋመ የስራ ውል መሰረት እስከ ህዳር ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ጥቅም ሲያገኙበት የነበረ መሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና አመልካች በቤተሰብ ውስጥ ሰይፉ በሚል ሌላ ስም ተጠርተው የማያውቁ፣ ይልቁንም ሰይፉ ወልዴ ከኢትዮጵያ ውጭ

በመኖር ላይ የሚገኙ የአመልካች ታላቅ ወንድም ስለመሆናቸው የአመልካች ወንድም መሆናቸውን በገለጹት 2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጭምር የተመሰከረ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡ አመልካች ያቀረቧቸው የሰነድ ማስረጃዎች ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች ለስራ ቅጥር ስላለመገልገላቸው ወይም የትምህርት ማስረጃዎቹ የሌላ ሰው ሳይሆኑ የራሳቸው ስለመሆናቸው የማያስረዱ መሆኑንም መዝገቡ ያመለክታል ወንጀሉን ስለመፈጸሜ በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም ወይም የተጠሪን ማስረጃ በመከላከያዬ አስተባብያለሁ በማለት አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በግልጽ ያቀረቡት ክርክርም የለም፡፡ የቅጣት ውሳኔውም ቢሆን ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የወንጀሉን አፈጻጸም ሁኔታዎች፣ሕጉን እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት በማድረግ በአግባቡ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 114900 በ16/10/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152347 በ13/12/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች እንዲሁም አመልካች ለሚገኙበት ማረሚያ ተቋም ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አስራ ሶስት

## 13. ወጣት ጥፋተኛን በተመለከተ[54]

- ✓ በወንጀል ለተከሰሱ ህፃናት ምቹ የሆነ የክርክር መሰማት ሥርዓትን ማስጠበቅና ማስከበር በዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣ በአፍሪካ የህፃናት ሙብቶች ቻርተር፣ በኢፌዴሪ ህግ መንግሥት፣በወንጀል ህግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት በተደነገገው መሠረት የፍርድ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡[55]

የሰ/መ/ቁጥር - 118130

ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች - ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

[54]የሰ/መ/ቁ 118130 (ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20

[55]የሰ/መ/ቁ 136262 (መስከረም 24 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22

አመልካች፡- ህፃን አድማሱ አገዘ--ከወልዲያ ማረሚያ ቤት ጉዳይ የምትከታተል እህቱ እየሩሳሌም አገዘ ቀርባለች

ተጠሪ፡-የአማራ ክልል ዓቃቤ ህግ አቶ ታራቀኝ አረጋ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተከሰሰበት የግብረ ሥጋ ድፍረት ወንጀል በመፈጸም ጥፋተኛ ተደርጎ በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት የተወሰነበትን የሰሜን ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማጽናቱ እንዲሁም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ5 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ቅጣቱን አሻሽሎ የወሰነበትን በመቃወም አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች እድሜው 11 (አስራ አንድ) ዓመት ሲሆን በጉባላፍቱ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0200915 እድሜዋ 13 ዓመት ያልሞላትን የአራት ዓመት ህፃን ልጅ አፀደ ምስጌን አስገድዶ ክብረ ንጽህናዋን የደፈራት በመሆኑ በፈጸመው የህፃናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል ወንጀል ተከሷል በማለት በወንጀል ህግ ቁጥር 627(1) መሠረት ክስ ቀርቦበት በዚሁ ጥፋተኛ ተብሎ በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት የተወሰነበትን በመቃወም ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ያሰናበተው በመሆኑ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ሰበር ሰሚ ችሎቱም ጥፋተኝነቱን በማጽናት አልፎ ቅጣቱ በምን መልክ ይፈጸም የሚለውን በአብላጫ ድምፅ ወደ 5(አምስት) ዓመት ጽኑ አስራት ዝቅ በማድረግ አሻሽሎ እንዲቀጣ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

የአሁኑ አመልካች እድሜው የ11 (አስራ አንድ) አመት ህፃን መሆኑን ጠቅሶ ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ማስረጃ እንዳልቀረበበት እና ጥፋተኛ ሊባል እንደማይገባው እንዲሁም ጥፋተኛ ቢባል እንኳን ቅጣቱን በማረሚያ ቤት ከሌሎች አዋቂ ታራሚዎች ጋር መታሠር እንደሌለበትና በቤተሰቦቹ ሥር ሆኖ ክትትል ሊደረግበት እንደሚገባ ገልጾ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች እድሜ 11 ዓመት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ቁጥር 157 እስከ 168 ባሉት ድንጋጌዎች ለምን መፈጸም እንደሌለበት የሥር ፍርድ ቤቶች ሳይገልጹ በመደበኛ የቅጣት ድንጋጌዎች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት የክልሉ ዓቃቤ ህግ መልስ እንዲሰጥበት ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪም አመልካች ቅጣቱን ከአዋቂ ታራሚዎች ጋር ይፈጸም ቢባል በአመልካች ላይ ለያስከትል ከሚችለው ጉዳት አንጻር ዕድሜውን መሠረት ያደረገ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ ተፈጻሚ ቢሆን እንደማይቃወም ገልጾ በቁጥር ወየሃ-424/08 በቀን 9/05/2008 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ ሃደት አጠር ባለመልኩ ከላይ እንደተመዘገበው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክር፣ አጣሪው ከያዘው ጭብጥ እንዲሁም አግባብነት ካለው ህግ አንጻር መርምረናል፡፡ አካለ መጠን ያላደረሱ ወጣቶች ወንጀል ፈጽመው በተገኙ ጊዜ የሚደረገው የክስ ሥነ ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 171 እና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የምርመራውም ሆነ የክስ ሥነ ሥርዓት የሚመራው በፍርድ ቤት ክትትልና ቁጥጥር ነው፡፡ የቀረበው ክስ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ አቃቤ ህግ የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሚሰጥ በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 172(3) ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም አካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል በተከሰሰ ጊዜ ፍርድ ቤቱ አካለ መጠን ያልደረሰውን ወጣት የሚረዳው ጠበቃ ያዝለታል በማለት በዚሁ የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 174(ለ) ላይ ተደንግጓል፡፡

አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት የተከሰሰበትን የሚሰማው ችሎት በሌላ ነገር ተሰይሞ ከሚያነጋግረው አኳኋንና ሁኔታ የተለየ እንደሆነ የሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 176(2) ደንግጓል። እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት በተከሰሰ ጊዜ የወጣቱን እድሜ ባገናዘበ መልኩ ያለውን የአእምሮ ብስለት፤ስለ ጉዳዩ ያለውን አረዳድ፣የሞራል ሁኔታ፣ስለተከሰሰው ህፃን ደህንነት ህግ አውጪው ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ አሟጋች ፍርድ ቤት ስለ ጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት ክርክሩን እንዲመራ ለማድረግ ታስቦ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሳል። ይህም ስለ ህፃናት መብት ከተደነገገው ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 36(2) ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወስዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤ በፍርድ ቤቶች፤ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደኅንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት በማለት ከተደነገገው ድንጋጌ ጋር የሚጣጣም እንደሆነ ለመመልከት ይቻላል። በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1) ላይ የሰፈረው ይህ መርህ የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት በሚወስዷቸው እርምጃዎች ለህጻናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው መሆኑን ያሳስባል። የአፍሪካ የህፃናት መብቶች ደህንነት ቻርተር በአንቀጽ 4(1) ላይ በተመሳሳይ መልኩ ደንግጓል። ወንጀል ፈጽሞ የተከሰሰ ህፃን ደህንነት የሚጠበቀው የህፃኑን ሥነ ልቦና በመጠበቅ፣ በክርክር ሂደት የሚደርስበትን መሸማቀቅ በመከላከል፤ እንዳይጨናነቅ በማድረግ፣ አዋቂዎችን በሚያስችሉበት ችሎት አብሮ እንዳይሆን በማድረግ፣ የሚረዳው ጠበቃ እንዲኖር በማድረግ ነው።

በዚህ መሠረት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህጉም ሆነ የወንጀል ህጉ ለህፃናት ወንጀል ፈጻሚዎች ከአዋቂዎች የተለየ የምርመራ፣ የክስ፤ የፍርድ እና የቅጣት ሁኔታን ማስቀመጥ ያስፈለገው ህገ መንግሥቱ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ላይ ከተደነገጉ የህፃናት መብቶች በእጅጉ ለማያያዝ ታስቦ ነው። የዚህም አስፈላጊነት መደበኛ የክርክር ሥርዓት ለመዘርጋት ያለመ ሳይሆን በህፃናት ላይ ለጥፋተኝነት የሚወሰን ቅጣት ማስተማርና ማረም እንጂ መበቀል እንዳይሆን ታሳቢ አድርጎ ህፃናት በአከባቢያቸው አብሮዋቸው የሚውለው፣ የሚያዩት፤ የሚማሩበት በተለይም በምርመራ፣ ክስ፣ ፍርድ እና የቅጣት አፈጻጸም ላይ ጥንቃቄ ካልተደረገ እነርሱን ከመጉዳት አልፎ የመጡበትን ማኅበረሰብ፣አካባቢና ሀገር የሚጎዳ ማንነት እንዳይከሰት ነው።በተጨማሪም ህፃናት እራሳቸውን የሚጠብቁና የሚቆጣጠሩ ባለመሆናቸው ያጠፉት ጥፋት ቢኖር እንኳ እኩል ከአዋቂዎች ዓይነት የቅጣት አፈጻጸም ከመከተል ይልቅ ስለወደፊት መልካም አስተዳደግ እና ደኅንነታቸው ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ ነው።

ይህን ዓላማ ለማሳካትም ሲባል ከህገ መንግሥት አንቀጽ 36(2) እና (3)፣ ከአህጉሩና ዓለም አቀፍ ስምምነት ሰነዶች በተጨማሪ በዝርዝር የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 157 እስከ 168 እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ 171 እስከ 180 ላይ ዝርዝር የምርመራ፣ የክስ፣ የፍርድ እና የቅጣት አፈጻጸም ድንጋጌዎችም ሥራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ የተጣለው በፍርድ ቤት ላይ ነው። በሌላ አነጋገር በወንጀል ለተከሰሱ ህፃናት ምቹ የሆነ የክርክር መሰማት ሥርዓትን ማስጠበቅና ማስከበር በዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣ በአፍሪካ የህፃናት መብቶች ቻርተር፣ በኢፌዴሪ ህግ መንግሥት፤በወንጀል ህግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት በተደነገገው መሠረት የፍርድ ቤት ኃላፊነት ነው። የተያዘውን ጉዳይ የተመለከተው የጉባላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚያመለክተው ከላይ የተገለጹትን ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች ተከትሎ የተደረገ ክርክር አይደለም። ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የሥነ ሥርዓት ግድፈት እንደፈጸመ መገንዘብ ተችሏል።

የጥፋተኝነት ውሳኔን በተመለከተ አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑ በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋገጦ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም።

ቅጣትን በተመለከተ እድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ዓመት የሞላቸው ወንጀል ያደረጉ ወጣቶች የሚወስንባቸው ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ከአንቀጽ 157 እስከ 168 የተደነገጉ ብቻ

ናቸው፡፡ ለአዋቂ ጥፋተኞች የተደነገጉት መደበኛ ቅጣቶች ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፤ ከአዋቂዎችም ጋር አይታሰሩም በማለት የወንጀል ህግ አንቀጽ 53(1) ይደነግጋል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 168(2) ወጣቱ የፈጸመውን ወንጀል ከባድነትና ጥፋቱንም በፈጸመበት ጊዜ የነበረውን የዕድሜ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ታስሮ የሚቆይበትን የጊዜ ልክ ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡ ጊዜውም ከአንድ ዓመት ሳያንስ እስከ አስር ዓመት ሊደርስ ይችላል በማለት ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚወሰነው ቅጣት ከአንድ ዓመት እስከ አስር ዓመት ሲሆን የሥር አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን የቅጣት ውሳኔን በማሻሻል አመልካች በአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ ቅጣቱንም የወልዳያ ማረሚያ ቤት እንዲያስፈጽም በአብላጫ ድምፅ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አነስተኛው ድምፅ የአመልካችን አቆያየት በተመለከተ የወንጀል ህግ ቁጥር 168(1)ሀ) ላይ ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር ወንጀለኛው ወደ ፀባይ ማረሚያ ተቋም ሊላክ እንደሚችል ቢገልጽም ይህ ዓይነት የማረሚያ ተቋም በአሁኑ ጊዜ የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የወንጀል ህግ ቁጥር 53(1) ደግሞ በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ወንጀለኞች ከአዋቂዎች ጋር አይታሠሩም በማለት ግልጽ የሆነ ክልከላ አስቀምጧል፡፡ ይህ ከመሆኑ አንጻር አመልካች ወደ ማኅበረሰቡ እንዲቀላቀል ተደርጎ ፀባዩ በፖሊስ ክትትል ሊደረግበት ሲገባ ግልጽ የሆነውን የህግ ክልከላ በመተላለፍ አብላጫው ደምፅ አመልካች ከአዋቂዎች ጋር እንዲታሠር መወሠኑ ተገቢነት የለውም በማለት ከአብላጫው ድምፅ ተለይቷል፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጣሪ አቤቱታውን ሲያስቀርብ የአመልካች እድሜ 11 ዓመት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ቁጥር 157 እስክ 168 ባሉት ድንጋጌዎች ለምን መፈጸም እንደሌለበት የሥር ፍርድ ቤቶች ሳይገልጹ በመደበኛ የቅጣት ድንጋጌዎች የመወሰኑን አግባብነት መመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ጭብጥ የያዘውም የአነስተኛውን ድምፅ ልዩነት ሀሳብ ህጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን ተመልክቶ ነው ወደ ሚል ድምዳሜ ያደርስናል፡፡

እኛም የስር ፍርድ ቤት ሁለት ዳኞች በልዩነት ያነሱትን እንዲሁም አጣሪው የያዘውን ጭብጥ የምንስማማበት ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ይህ ችሎት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ህፃናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተገቢውን ባለሙያ በመመደብ ስለ አመልካቹ ህፃን ጠባይ፣ ስለአስተዳደጉ፣ ስለኑሮውና ስለሀይወቱ እንዲሁም የአካልና የአእምሮ ሁኔታውን አስጠንቶ ውጤቱን እንዲያቀርብ ሚያዝያ 6 ቀን 2008 ዓ/ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ መሠረት የህፃናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ በመመደብ በወልዲያ ማረሚያ ቤት ስለሚገኘው ህፃን አድማሱ አገዘ ሁኔታ ያጠናውን ጥናት በቁጥር ሃ/4-9-3/17920 ሐምሌ 19 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ መሸኛ ደብዳቤ ልኳል፡፡ ጥናቱም ከአመልካቹ፣ ከቤተሰቦቹ፤ከጓደኛው፣ ከጎራቤቶቹ እና ከማረሚያ ቤቱ ሙያተኞች የተገኘ መረጃ እንደሆነ ሲገልጽ የሚከተሉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች ለመውሰድ የሚረዱ ሃሳቦች ለማግኘት አንዳስቻለ ያመለክታል፡፡ እነዚህም፡-

አመልካች ወንጀሉን መፈጸሙን ባያምንም ከዚህ በኃላ ፀባዩን ለማሻሻልና ትምህርቱ ላይ ብቻ ሙሉ ትኩረቱን ለማድረግ ማቀዱ፤ 2 ህፃኑ ከቤተሰቡ እና ከጓደኞቹ ተለይቶ ማረሚያ ቤት መግባቱ ከባድ እንደሆነ በመረዳቱ እና ለወደፊት ከወንጀል ነክ ነገሮች ለመራቅ ማቀዱ፣ ህፃኑ- ወደ ወላጅ እናቱ ጋር ለመኖር ከተመለሰባቸው ምክንያቶች አንዱ በሥራ ጫና ምክንያት ትምህርቱን ላለማቋረጥ ባደረገው ትግል ከወላጅ አባቱ እና ከእንጀራ እናቱ ጋር አለመስማማት ተፈጥሮ መሆኑ፤ ከማረሚያ ቤቱ ሙያተኞች ለመረዳት እንደተቻለው ህፃን አድማሱ/አመልካቹ/ ታዛዥ እና ምክርም የሚሰማ መሆኑ፤ ከቤተሰቦቹ ከጓደኛው እና ከመኖሪያ አካባቢው የተገኘውም መረጃ አመልካች በባህሪይው ጨዋ እና ምስጉን እንደሆነ እና ከዚህ በፊት በወንጀል ድርጊት ተከሶም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ እንደማያውቅ የሚያሳይ በመሆኑ፣ የአመልካች ወላጅ እናትም ህጻኑ ወደ ወንጀል ድርጊት ሊገባ የቻለው በተለያየ ቦታ በማደጉ ከአስተዳደግ ክፍተት እና ከቤተሰብ ክትትል እና ቁጥጥር ማነስ ሊሆን እንደሚችል

በማመን ወደፊት ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዳቀዱ የገለጹ መሆኑ እና የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ቤተሰቡ ተበዳይን ለመካስ ጥረት ማድረጋቸው በጥናቱ የተካተቱ ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ የጥናት ውጤቶች በአመልካች ላይ ሊወሰድ የሚገባው ቅጣት ምን ሊሆን እንደሚገባ ግንዛቤ የሚሰጡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡የወንጀል ህግ ቁጥር 157 አስከ 168 ላይ የተመለከቱት የቅጣት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች ተፈጻሚ ሲሆኑም የወጣቱን ፀባይ እና የቀድሞ ባህሪው ምን እንደሚመስል መገንዘብ እንደሚያስፈልግ የደነገገ ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 177(2) ድንጋጌም ይህንን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች የፈጸመው የወንጀል ድርጊት ከእሱ ዕድሜ በታች ላይ የምትገኘው ህፃን ልጅ ላይ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸሙ ወንጀሉ ከባድ የሚባል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት እርምጃ መወሰዱ ተገቢነት ቢኖረውም የቅጣት አፈጻጸም ሲታይ በምን መልኩ ተፈጻሚ መሆን አለበት የሚለው ጉዳይ ከአመልካቹ እድሜ እና ስለ ነበረው ባህሪ እና መልካም ፀባይ በመነሳት ከወንጀል ህግ ቁጥር 157 እስከ 168 አኳያ የተለያዩ እርምጃዎች ተፈጻሚ መሆን እንደሚገባቸው ህጉ ያስቀመጠ በመሆኑ የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት ከአዋቂ የህግ ታራሚዎች ጋር ይፈጽም ቢባል ወደፊት በአመልካች ላይ ሊያስከትልበት ከሚችለው የሞራል እና የተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች አኳያ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የክስና የክርክር ሂደት የመሩበት አካሄድ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት፣ የወንጀል ህጉን መሠረታዊ ድንጋጌዎች እና በህገ መንግሥቱ ስለህፃናት የተቀመጡ መርሆችን የተከተለ ካለመሆኑም ባሻገር ፍርድ ቤቶቹ ቅጣቱን ሲወስኑ እንዲሁም ቅጣቱ ከአዋቂ ታራሚዎች ጋር እንዲፈጸም ትዕዛዝ መስጠታቸው ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0200915 በቀን 04/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0205865 በቀን 10/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቁጥር 03-10537 ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የወንጀል ህግ ቁጥር 168/1/ሀ/ ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር አካለ መጠን ያልደረሰ ወንጀል አድራጊ ወደ ፀባይ ማረሚያ ተቋም ሊላክ እንደሚችል ቢደነግግም ይህ ዓይነት ማረሚያ ተቋም በአሁኑ ጊዜ ያልተሟላ ሲሆን የወንጀል ህግ ቁጥር 53/1/ ደግሞ በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ወንጀል አድራጊዎች ከአዋቂዎች ጋር አይታሰሩም በማለት ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር አመልካች ወደ ማኅበረሰቡ እንዲቀላቀል ተደርጎ በፖሊስ ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡ በመሆኑም በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ህግ ቁጥር 171 እና 192 መሠረት ታግዶ እንዲቆይ ተወስኗል፡፡
3. ስለ አመልካቹ መልካም አስተዳደግና ባህርይ ክትትል እንዲያደርጉ ለአመልካቹ እናትና አባት እንዲገለጽ ታዟል፣ ይጻፍ፡፡ አመልካች ከማረሚያ ቤት ወጥቶ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ ለፈተና በተሰጠው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚያሳየውን ባህርይ እንደከታተል ለሚገኝበት ወረዳ ፖሊስ በጽሁፍ እንዲገለጽ ታዟል፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለወልድያ ማረሚያ ቤት በመሸኛ እንዲደርሰውና አመልካቹንም እንዲፈታው የመፍቻ ዋራንት እንዲጻፍ ታዟል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## I. <u>የተጠቀሱ የሰበር መዝገቦች ዝርዝር</u>

### *(case index)*

### *ምዕራፍ -1*

### *ክፍል -1*

*የሰ/መ/ቁ 72304 (ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 60217(ጥቅምት 15 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ/ 85237 (መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ 237423 (መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ/ም) ቅፅ 27፣ በሰ/መ/ቁ 103775 (ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 223134 (ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 151034 (ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23፣ የሰ/መ/ቁ. 81178 (መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 75387 (ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 14፣ የሰ/መ/ቁ 248494 (ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 248286 (ታህሳስ 28 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ ሰ/መ/ቁ/ 243034 (ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 265085 (ጥር 27 ቀን 2017 ዓ/ም)፣ በሰ/መ/ቁ 155773 (ጥቅምት 23 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ/ 99883 (ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 228813 (መጋቢት 27 ቀን 2015)*

### *ክፍል- 2*

*የሰ/መ/ቁ 181206 (መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣ በሰ/መ/ቁ. 235233 (ጥቅምት 26 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 226641 (የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ 267231 (ጥር 30 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣267230 (ጥር 30 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 91535 (የካቲት 12 ቀን 2006 ዓም) ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ 203746 (መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅፅ 26 ፣ በሰ/መ/ቁ 212243 (ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 251700 (ጥር 26 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 46382 (ነሃሴ 28/2001ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ የሰ/መ/ቁ. 23855 (ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7፣ ሰ/መ/ቁ 235233 (ጥቅምት 26 ቀን 2016ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ. 38161 (የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9፣ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 22069 (ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7፣ የሰ/መ/ቁ 22452 (ሐምሌ 30 ቀን 2000ዓ.ም) ቅፅ 7*

### *ክፍል- 3*

*የሰ/መ/ቁ 66856 (መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም ) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 230945 (ጥር 30 ቀን 2015 ዓ/ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 90089 (ጥቅምት 20 ቀን 2006 ዓ.ም)ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ 63727 (ሰኔ 13/2003) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 60345 (ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፡፡ የሰ/መ/ቁ 119500 (ሐምሌ 22 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 20፣ የሰ/መ/ቁ 127505 (መስከረም 25 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22*

### *ክፍል- 4*

*የሰ/መ/ቁ 247535 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 228017 (ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 164030 (ህዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ 44031 (ነሃሴ 30 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9*

### *ክፍል- 5*

*የሰ/መ/ቁ 225975 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)*

## *ክፍል- 6*

*የሰ/መ/ቁ. 93741 (ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ የሰ/መ/ቁ. 35697 (ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9፣* የሰ/መ/ቁ 134549 (መስከረም 23 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ/መ/ቁ 132266 (ታህሳስ 26 ቀን 2009ዓ.ም) ቅፅ 21

## *ክፍል- 7*

*የሰ/መ/ቁ 123046 (የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21፣ የሰ/መ/ቁጥር 119159 (ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ የሰ/መ/ቁጥር 153690 (መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23 ፣ የሰ/መ/ቁ 226130 (ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ. 96078 (መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ በሰ/መ/ቁ 228597 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 104637 (ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21 ፣ 234082 (ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም) እና 107195 (ሰኔ 4 ቀን 2007ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ. 104715 (መጋቢት 02 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ. 85237 (መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ. 104715 (መጋቢት 02 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ.መ.ቁ. 107195 (ሰኔ 04 ቀን 2007 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ. 95438 (ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16፣*የሰ/መ/ቁ 42703 (ሐምሌ 22 ቀን 2001ዓ.ም) ቅፅ 9፣ የሰ/መ/ቁ 65325 (ሕዳር 22 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13

## *ክፍል- 8*

*የሰ/መ/ቁ. 86570 (ሚያዝያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ.226650 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 43501 (መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10*

## *ክፍል- 9*

*የሰ/መ/ቁ.92296 (ህዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 47831 (ሰኔ 3 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ123046 (የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21፣ የሰ/መ/ቁ119159 (ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 20፣ የሰ/መ/ቁ 226508 (መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ. 239931 (ጥቅምት 07 ቀን 2016 ዓ/ም) ፣ በሰ/መ/ቁ. 96503 (ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ 62332 (ግንቦት 29 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 186919 (ታሕሳስ 27 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣ የሰ/መ/ቁ 122766 (ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21 ፣ የሰ/መ/ቁ 95438 (ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16፣ የሰ/መ/ቁ 21411 (ጥቅምት 5/2000) ቅፅ 7 ፣የሰ/መ/ቁ 95440 (ሰኔ 4 ቀን 2006ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 103448 (የካቲት 16 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 105289 (መጋቢት 15 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ የሰ/መ/ቁ 107219 (ሐምሌ 1 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ የሰ/መ/ቁ 111006 (ሐምሌ 17 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ የሰ/መ/ቁ 135787 (መስከረም 24 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ/መ/ቁ 88542 (ሐምሌ 17 ቀን 2005ዓ.ም) ቅፅ 20 የሰ/መ/ቁ. 34521 (ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7፣ የሰ/መ/ቁ 137908 (21/05/2010 ዓ.ም) ቅፅ 24፣ በሰ/መ/ቁጥር 66943 (ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 228813 (መጋቢት 27 ቀን 2015) ፣የሰ/መ/ቁ 100736 (ሰኔ 23 ቀን 2009ዓ.ም) ቅፅ 21፣ የሰ/መ/ቁ 131705 (ሚያዚያ 16 ቀን 2009ዓ.ም) ቅፅ 21፣ የሰ/መ/ቁ 161791 (የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 24፣የሰ/መ/ቁ 229403 (መጋቢት 29 ቀን 2015ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 53612 (ሚያዚያ 25 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10፣የሰ/መ/ቁ 59356 (ሰኔ 3 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 171943 (ሕዳር 26 ቀን 2012ዓ.ም) ቅፅ 24፣ የሰ/መ/ቁ 47831 (ሰኔ 3 ቀን 2003 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 48956 (መጋቢት 10 ቀን 2002ዓ.ም) ቅፅ 12፣የሰ/መ/ቁ 82572 (ጥር 1 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 14*

## *ክፍል-10*

*የሰ/መ/ቁ 169726 (ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 24፣ በሰ/መ/ቁ 262248 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ. 185700 (የካቲት 30/2013 ዓ.ም) ቅፅ 25 ፣ በሰ/መ/ቁ 218957 (መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም)ቅፅ 26 ፣ በሰ/መ/ቁ 263173 (ሰኔ 20 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 225686 (ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ. 85596 (መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ. 94404 (መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ በሰ/መ/ቁ 255633 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 34280 ቅፅ 7 (ግንቦት 14/2000) ፣ የሰ/መ/ቁ. 46382 ( ሐምሌ 28 ቀን /2001 ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ የሰ/መ/ቁ. 34280 (ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7 ፣ በሰ/መ/ቁ 210020 (ሕዳር 8 ቀን 2014ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 131741 (ታህሳስ 11 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 94404 (መጋቢት 9 ቀን 2006ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ የሰ/መ/ቁ 185700 (የካቲት 30/2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣ የሰ/መ/ቁ 262248 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 171403 (ህዳር 22 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 177216 (ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም ) ቅፅ 24 ፣ሰ/መ/ቁ 262910 (ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 177216 (ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24 ፣ የሰ/መ/ቁ 262248 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም)*

## *ክፍል- 11*

*የሰ/መ/ቁ 59045 (ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12*

## *ክፍል-12*

*የሰ/መ/ቁ 105406 (መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 45572 (የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10 ፣* የሰ/መ/ቁ 41248 (ሰኔ 23 ቀን 2002ዓ.ም) ቅፅ 10፣ የሰ/መ/ቁ 161791 (የካቲት 25 ቀን 2011ዓ.ም) ቅፅ 24፣ የሰ/መ/ቁ 61221 (መስከረም 22 ቀን 2005ዓ.ም) ቅፅ 14*የሰ/መ/ቁ. 79389 (መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ የሰ/መ/ቁ. 77097 (ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 14 ፣ የሰ/መ/ቁ 95875 (ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16*

## *ክፍል- 13*

*የሰ/መ/ቁ 118130 (ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20*፣የሰ/መ/ቁ 136262 (መስከረም 24 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22

## ምዕራፍ -ሁለት

## II.የወንጀል ሕግ የልዩ ክፍል የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች

### መግቢያ

በመፅሐፉ መግቢያ እንደተጠቀሰው ይህ ልዩ እትም የወንጀል ህጉን አደረጃጀት በመከተል የተደራጀ ሲሆን የዚህ ምዕራፍ ይዘት ከወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍልን መሰረት በማድረግ የተሰጡ የሰበር የህግ ትርጉም ውሳኔዎች ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሁለት አደረጃጀት ውስጥ በመንግስት ኢኮኖሚ እና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ፣ በመንግስት ስራ ላይ የሚፈፀሙ፣ የፍትህ አስተዳደር ላይ የሚፈፀሙ፣ በህዝብ ደህንነት ላይ የሚፈፀሙ፣ በሰው ህይወት ላይ የሚፈፀሙ፣ በሰው አካል እና ጤና ላይ የሚፈፀሙ፣ በሰው ነፃነት ላይ የሚፈፀሙ፤ በሩካቤ ስጋ እና ንፅህና ላይ የሚፈፀሙ፣ በንብረት ላይ የሚፈፀሙ እና የህሊና ወይም የሰው ችግርን መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የሚሉትን በየክፍሉ በመከፋፈል በነዚህ ክፍሎች ስር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸውን 18 (አሥራ ስምንት) አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎች በሙሉ ይዘታቸው በማስገባት ቀሪዎቹን ውሳኔዎች በግርጌ ማስታወሻ በማጣቀሻነት በማካተት ተደራጅቶ የተዘጋጀ ነው፡፡

### ክፍል አንድ

### 1. በመንግስት፣ በአገር እና በአለምአቀፍ ጥቅሞች ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

#### 1.1 የከበሩ ማዕድናትን በሕገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወር [56]

- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 ስር የወንጀል ተጠያቂነት ሊከተል የሚችለው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 346 በተመለከተው አኳኋን ማንም ሰው ሕገወጥ በሆነ መንገድ የከበሩ ማእድናት እንደወርቅ፣ ፕላቲኒም፣ ዩራኒየም እና ሌሎችንም እነዚህን የመሳሰሉ ማእድናት እንዲሁም የከበሩ ድንጋዮችን ለመጠበቅ ወይም ሕገ ወጥ ዝውውሩን ለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ በመጣስ ወንጀል የተሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡
- ወርቁን በሕገ ወጥ መንገድ ለማዘዋወር በማስብ ወንጀሉን በማድረግ፣ የወንጀሉን ድርጊት እስከ መጨረሻው ያልተከታተሉት ወይም ለመከታተል ያልቻሉት ወይም የወንጀሉን ድርጊት እንዲፈፀም እስከ መጨረሻው ተከታትለው አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላገኙ ቢሆንም ተጠሪዎች ወንጀሉን ለመፈፀም ከማይመለሱበት ደረጃ /Point of no return/ ደርሰው የነበረ መሆኑ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ወርቅን በሕገ ወጥ መንገድ መሸጥ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 27(1)፣32(1(ሀ))((ለ)) እና 346 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ድርጊት ስለመሆኑ፤[57]

የሰ/መ/ቁጥር 60345

ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም

[56]የሰ/መ/ቁ 60345 (ህዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13

[57]በሰ/መ/ቁ. 101618 (ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ- ገ/እግዚአብሔር ሙናቸው

ተጠሪዎች፡- 1. ገዳ ፎጫ

2. ነቢ ሲምሮ ኤጎ

3. ወሌና ወርቅና ታንታለም ማዕድናት አምራች እና ግብይት ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመሠረተው የወንጀል ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የ3ኛ ተጠሪ ድርጅት እንደቅደም ተከተላቸው ዋና እና ምክትል ስራ አስኪያጆች ሲሆኑ፣ አራት ክሶች ቀርበውባቸዋል፡፡

የመጀመሪያው ክስ፡- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1)፣ በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 53(1)፣(5) እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 26(4) በተመለከተው መሰረት ለስራ ተፈጻሚነት ባላቸው ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ማካሄድ ሲገባቸው በተጠቃሹ የማዕድን አዋጅ አንቀጽ 29(2) የተመለከተውን መረጃ የማኖር ወይም የመያዝ ግዴታን በመተላለፍ እንዲሁም በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 አንቀፅ 30(1ሀ(3))፣ ((ለ)) እና ((4(ሐ)) ስር እንደተመለከተው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ የተመረቱትን፣የተከማቹትን፣የተዘጋጁትን ወይም ለሽያጭ የቀረቡትን ማእድናትን አስመልክቶ መረጃ መያዝ እንዳለበት የተቀመጠውን ግዴታ በመጣስ እንዲሁም በተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 38 እና 39 ላይ እንደተመለከተው የተሟሉና ትክክለኛ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርቶችን፣ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ካልሰጡ ጥፋት ነው ተብሎ የተደነገገውን በመተላለፍ ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም መጠኑ 15863.18 ግራም ፣ዋጋው ብር 5,065,005.12(አምስት ሚሊዮን ስልሳ አምስት ሺህ አምስት ብር ከአስራ ሁለት ሳንቲም) የሆነውን የሐገር ውስጥ ጥፍጥፍ ወርቅ ትክክለኛና ሕጋዊ መረጃ ሳይኖራቸው ወይም ወቅታዊ ሁኔታዎችን የሚገልፅ ሰነድ ሳይዙ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-39968 አ.አ በሆነ ቪታራ መኪና በሮቹን በመፍታት መደበቂያ አዘጋጅተው ምንም አይነት ፈቃድ ሳይዙ በህገወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋዉሩ የተያዙ በመሆኑ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው ክስ ደግሞ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም የወ/ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ መጠኑ በ1ኛው ክስ የተገለጸውን ወርቅ ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ሕጋዊ ወደአልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲሉ ተይዘዋል የሚል ነው፡፡

ሶስተኛው ክስም በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ) እንዲሁም በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና

አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀሰት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ ተጠቅመዋል የሚል ነው፡፡

የመጨረሻው ክስ በ3ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም፡- በወርቅና ታንታለም ማእድናት ማምረት የግብይት ስራ መስክ የሕግ ሰውነት ተሰጥቶት ሲንቀሳቀስ የወርቅ ምርትን ከማንንዝና ለግብይት ከማቅረብ ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ሕጋዊ ሰነድ መያዝ እና ማህበሩ ስላለው፣ ስላመረተው፣ ስላንንዘው እና ለግብይትም ስላቀረበው ወርቅ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ማቅረብ እንዳለበት የማእድን ሃብትን ለማስፋፋት በወጣው አዋጅ ቁጥር 52/85 እና በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በመጣስ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣የማእድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ስርቬይ በወርቅ ግዥና አቀራረብ ሃደት ስለሚከተሉት የጋራ አሰራር የወጣውን መመሪያ ቁጥር 01/2000 በመተላለፍ ያለምንም ሕጋዊ ፈቃድ መጠኑ 15863.18 ግራም የሆነ ወርቅ ሕጋዊ ላልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲንቀሳቀስ ተይዟል ተብሎ በ1997 ዓ/ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንደሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፏል በሚል ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአቃቤ ሕግ ክስ ለተጠሪዎች እንዲደርስ አድርጎና በግልፅ ችሎትም ተነቦላቸው እንዲረዱት ካደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠይቅ ተጠሪዎች በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው፣ የድርጊቱን አፈጻጸም ግን ክደው ተከራክረዋል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰነድና የሠው ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ የዓቃቤ ህግን ማስረጃዎች ሰምቶ ተጠሪዎች የወንጀል ድርጊቶችን መፈጸማቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ መረጋገጡን በማመን የተጠሪዎችን የመከላከያ ማስረጃዎችን የማስማት መብት ጠብቆላቸው መከላከያ ማስረጃዎቻቸውን ሰምቷል፡፡ ቀጥሎም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃዎች ይዘት በአቃቤ ማስረጃዎች ይዘት ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ የፈጠረ ሆኖ ተገኝቷል የሚል ምክንያት በመስጠትና ተጠሪዎች የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎች ማስተባበላቸውን በመግለጽ ተጠሪዎችን ከክሱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡በስር 3ኛ ተከሳሽ የሆነውን ግለሰብ ግን በወ/መ/ሕ/ቁጥር 375(1(ሀ))እና ((መ)) ስር ሐስተኛ ሰነድ የመስጠት ወንጀል መፈፀማቸው ተረጋግጧል በማለት ጥፋተኛ አድርጎ ተገቢ ነው ያለውን ቅጣት አስተላልፎበታል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችን ከክሱ ነፃ ከማድረግ በተጨማሪም በኤግዚቢትነት የተያዘው የሀገር ውስጥ ወርቅም በጊዜው ባለው የወርቅ ተመን መሠረት የወርቁን ዋጋ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች የወርቅ ግብይቱን ለሚመለከተው አካል የተከሰሱት ሕጋዊ ፈቃድ የላቸውም በሚል ሳይሆን ሳያቀርቡ በሕገ ወጥ መንገድ ለሌላ አካል ለመሸጥ ሲሉ ሲንቀሳቀሱ ተይዘዋል፤1ኛ ተጠሪም ማስረጃው በጥቅም አሰርቶ ያመጣው ከመሆኑም በላይ ስለራሱና ለ2ኛ ተጠሪ ጥቅም ላይ ሊያውል ሲል መያዙ ተረጋግጧል የሚል ሆኖ እያለ ሕጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸው ስለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አረጋግጠዋል በማለት በነጻ የተሰናበቱት ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት እንዲጣል እና ኢግዚቢትነት የተያዘው ወርቅ ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪዎች ከክሱ በነጻ የተነሰናበቱት ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የተጠሪዎች ጠበቃ ባቀረቡት የፅሑፍ መልስ ተጠሪዎች በነፃ የተሰናበቱት ባግባቡ ተከላክለው በመገኘታቸው በመሆኑና አድራጎታቸውም የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትል መሆኑ በመረጋገጡ በመሆኑ የበታች ፍርድ

ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪዎች ከክሱ በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም በስር ፍርድ ቤት በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እንዲሁም የተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃዎች ያስረዱትን ፍሬ ነገር ይዘት ባጭሩ በሚከተለው መልኩ አይተነዋል፡፡

በአቃቤ ሕግ በኩል በ1ኛ ምስክርነት የተጠቀሱት ግለሰብ እውነት ለመመስከር ምለው በሰጡት የምስክርነት ቃል፡-ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም ከጥዋቱ 2፡30 አከባቢ 1ኛ ተጠሪ ደውለውላቸው ወርቅ አምጣልኝ፣ከአዋሳ 2ኛ ተጠሪ ይጠብቅሃል ሲሏቸው ወደ 2ኛ ተጠሪ ደውለው 1ኛ ተጠሪ አዝዞኛል ሲሏቸው 2ኛ ተጠሪ "ና!" ብሏቸው ከቀኑ 11፡30 አከባቢ አዋሳ ገብርኤል አካባቢ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተገናኝተው በጥቁር ሻንጣ ወርቁን እንዳመጣላቸው፣ከመንገድ ወጣ ብለው በመኪናው ሻግ ውስጥ በማድረግ ስድስቱን እሽግ ወርቅ በመደበቅ በእለቱ አዲስ አበባ መንቀሳቀስ እንደጀመሩ፣ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ሳሉም ከምሽቱ 4፡00 አከባቢ ወደ አቃቂ ቃሊቲ የጉምሩክ ፍተሻ አከባቢ ሲደርሱ በጉምሩክ ኦፊሰሮችና በጸጥታ ኃይሎች መያዛቸውንና ወዲያውኑ ወደ ጉምሩክ ጣቢያ እንዲገቡ መደረጋቸውን፣በጉዞ ወቅት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አፍሪካ ወርቅ ድርጅት ከተባለው ጋር በስልክ ይነጋገሩ እንደነበር፣በበነጋው ወርቁን የት እንዳስቀመጡት ሲጠየቁም ሻጉን ከፍተው እንደሳዩ፣ወርቁን በተመለከተ ቀኑ 30/08/2001 ዓ/ም የሚል ተሰርቶ ማስረጃ እየመጣላቸው መሆኑን 2ኛ ተጠሪ ሲነግራቸው እንደነበር፣በወቅቱም ምስክር አትሁን ሲሏቸው እንደነበር፣ከዚያ በፊትም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ወርቅ ሲያመጡ እንደነበር፣ በሻግ ውስጥ የሚያስቀምጡትም የይለፍ ወረቀት ስለማይዙና በወቅቱም ያለመያዛቸውን፣ወርቁ ወደ ጅቡቲ እንደሚወጣም በስልክ 2ኛ ተጠሪ ሲናገር መስማታቸውን ዘርዝረው መስክረዋል፡፡

ሁለተኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ደግሞ የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር የሆኑት ግለሰብ በእለቱ ከምሽቱ 5፡00 አካበቢ ሲሆን ጉምሩክ ታስሬአለሁ ጠዋት "ና!" እንደአሏቸውና ጥዋት 1፡00 አከባቢ ጉምሩክ ሲደርሱም የታሰሩበት ምክንያት ወርቅ ጭነው እንደሆነ የተነገራቸው መሆኑን፣2ኛ ተጠሪ አብሮት እንደነበር፣ይኸው ተጠሪ ወዲያውኑ ስገኛ ተጠሪ ደውልለት ብሏቸው ለምስክሩ ሲነግሩትም ምስክሩ ለ1ኛ መሆኑን፣ከዚያም ቀን ላይ 1ኛ ተጠሪ መልሶ ደውለውለት እመጣለሁ ጠብቀኝ እንዳሉት፣ ከቀኑ ተጠሪ ደውለውለት 2ኛ ተጠሪና ወርቁ መያዙን የነገሩት 8፡00 አከባቢም 1ኛ ተጠሪ ወረቀትም አስርቼ እያመጣሁ ነው ብለው ሲሏቸው ከኢትዮጵያ ሆቴል አከባቢ ሲገናኙ 1ኛ ተጠሪ ወርቁን ለማስለቀቅ ቀኑ በ30/08/2001 ዓ/ም ተብሎ ወደኋላ ተደርጎ የተጻፈ ወረቀት መያዛቸውን ለምስክሩ ገልፀው ወረቀቱን ለ2ኛ ተጠሪ ምስክሩ እንዲሰጥላቸው ነግሯዋቸው ምስክሩ "እኔ አልሰጥም፤ራስህ ስጥ ሲሉት 1ኛ ተጠሪ ወረቀቱን ለመስጠት በሄዱበት መያዛቸውን እንደሚያውቁ መስክረዋል፡፡

3ኛ እና 5ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በበኩላቸው 2ኛ ተከሳሽን በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ሰዓት ወርቅ ጭነው ሲመጡ በደረሳቸው መረጃ መሰረት ሃና ማሪያም ቀለበት መንገድ አከባቢ መያዛቸውን፣ወርቁም በመኪናዋ በሮች መደበቂያ ተሰርቶለት በአንድ በኩል ሶስት፣በሌላ በኩል ሶስት እሽግ ሆኖ ሲጓዝ እንደነበርና በወቅቱም ማስረጃ ተጠይቀው የለንም በማለት መልስ የሰጧቸው መሆናቸውን መስክረዋል፡፡ 4ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር ደግሞ 2ኛ ተጠሪን ወርቅ ከደቡብ ጭነው ሲመጡ ከሃና ማሪያም አከባቢ የያዟቸው መሆኑን፣ 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 04 ቀን 2001 ዓ/ም ከቀኑ 4፡00 አከባቢ የይለፍ ወረቀት አጣጥፎ ለ2ኛ ተጠሪ በአጥር ሲያቀብሉ እንደያዙት መስክረዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ አቃቤ ሕግ 3ኛ ተጠሪ የወርቅና የታንታለም ማእድናት አምራችና ግብይት ኃ.የተ.የግል

ማህበር ስለመሆኑ ከክልሉ የማዕድን ቢሮ ፈቃድ አግኝቶ ማዕድን በማምረት ስራ ላይ የተሰማራ መሆኑን፤1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የዚሁ ማህበር አመራሮች መሆናቸውን፤በአዶ ሻኪሶ የሚገኘው የገቢዎች ጽ/ቤትም 3ኛ ተጠሪ የመረጃ አያያዙ ችግር ያለበት መሆኑን የገለፀበት መግለጫ፣2ኛ ተጠሪ ከአፍሪካ ወርቅ ቤት ጋር በስልክ ሲገናኙ የነበሩ መሆኑን የሚያሳዩ ከቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የተገኘና ሌሎች የወርቁን ዋጋና 2ኛ ተጠሪ ወርቁ ከተደበቀበት የመኪና ክፍል መርተው ሲያስወጡ የተነሱትን ፎቶ ግራፍ በሠነድ ማስረጃነት ማቅረቡን የሥር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ያሳያል፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃነት ያቀረቡ ሲሆን የሰነድ ማስረጃዎቻቸው ይዘትም ከአንድ አመት በፊት ማዕድን ለማምረት ተደራጅተው ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የማእድንና ኢነርጂ ልማት ጽ/ቤት ፈቃድ ማግኘታቸውን፣ፈቃዱም የታደሰ መሆኑን፤ከብሔራዊ ባንክ ጋር ወርቅ የማቅረብ ግንኙነት እንዳላቸው፣ሮያሊቲ ታክስም እንደሚከፍሉ ከተደራጁበት ጊዜ ጀምሮ የከፈሉትን የሮያሊቲ መጠን፣ለብሔራዊ ባንክ ከአስራ ሁለት ጊዜ በላይ ወርቅ አቅርበው የሸጡ መሆኑን የሚያሳዩ መሆናቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

እንግዲህ በግራ ቀኙ ማስረጃዎች የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ከላይ የተገለጹት ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎችን ከክሱ ነፃ ያደረጋቸው ተጠሪዎች ሕጋዊ የወርቅ ማምረት ፍቃድ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፣ በአዋጅ ቁጥር 52/865 አንቀጽ 2 መሰረት ማምረት ማለት መሸጥን እንደሚጨምር መደንገጉን፣ማዕድኑ ሲሸጥ ለማን እንደሚሸጥ ይህ ድንጋጌ በግልጽ ያላመለከተ መሆኑና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 182/86 ደግሞ ማእድንን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ማህበር ያመረተውን ማእድን በተመለከተ ያመረተውን፣ ያጓጓዘውን፣ ያከማቸውን እንዲሁም የሸጠውን መዝግቦ መያዝ እንዳለበት፣ሲጠይቅም ማሳየት እንዳለበት ከሚደነግግ ውጪ ማዕድኑን ለዚህ አካል መሸጥ ወይም ማስረከብ አለበት ብሎ የደነገገው ድንጋጌ ያለመኖሩን፣የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ማዕድን ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ስርቬይ በጋራ ባወጡት መመሪያ ላይም ማንኛውም ሕጋዊ ወርቅ አምራች ያመረተውን ወርቅ ለባንኩ ማቅረብ ይችላል ከሚል በስተቀር የማቅረብ ግዴታ እንዳለበትና ከባንኩ ውጪ ለሌላ ሲያቀርብ 39 ስር ቢገኝ በዚህ ሕግ መሰረት ይቀጣል ተብሎ ያለመደንገጉን፤ በደንብ ቁጥር 182/86 አንቀጽ 38 እና የተቀመጡት ድርጊቶች ሪኮርድ ያለመያዝ፣ስለአመረቱት ጥፋት ተብለው ፣ስለአጓጓዙት፤ስለአከማቹት እና ስለሚሸጡት ማእድን ተገቢውንና ወቅታዊውን መረጃ ባለመያዛቸው የሚወሰድባቸው ቅጣት አስተዳደራዊ እንጂ የወንጀል ቅጣት ያለመሆኑን የደንቡ አንቀጽ 40 ድንጋጌ የሚያሳይ መሆኑን በምክንያትነት በመያዝ ነው፡ ተጠሪዎች እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚከራከሩትም ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው መሆኑና በተለያዩ ጊዜያት ለብሔራዊ ባንክ ወርቁን በማቅረብ ሲሸጡ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ ሲሆን አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ደግሞ ተጠሪዎች ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ሳይክድ የወርቅ ሽያጩን በሕገ ወጥ መንገድ ለመፈፀም ሲሯሯጡ ተይዘዋል፣ተገቢውን መረጃም በወቅቱ አልያዙም በማለት ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ሕጎች በማገናዘብ ተመልክተነዋል፡፡

በመሰረቱ የወርቅ ማዕድን ዝውውርን ለመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው ብሔራዊ ባንክ መሆኑን ብሔራዊ ባንክን ከአቋቋሙት ሕጎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 591/2000 ሲሆን ይህ አዋጅ በአንቀፅ 27(2) እና በአንቀጽ 5 ድንጋጌዎች ስር ብሔራዊ ባንክ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካትና አዋጁን በሚገባ ስራ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት የሚያስችል ስልጣን ሰጥቶታል፡፡ይኸው አዋጅ በአንቀጽ 28 ስር ደግሞ አዋጁን የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ደንብ ወይም መመሪያ በአዋጁ ውስጥ የተመለከቱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት እንደማይኖረው ይገልፃል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ይዘት መገንዘብ የሚቻለውም አዋጁን የማይቃረን ሕግ፣ደንብ እና መመሪያ በአዋጁ ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ነው፡፡በአዋጁ አንቀጽ 27/2/ እና አንቀፅ 5(9) ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለይ ሲታዩም ስለወርቅና ስለውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ባንኩ መመሪያ

የማውጣት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ድንጋጌ እና ከአዋጁ አጠቃላይ መንፈስ መረዳት የሚቻለው የገንዘብ እና የወርቅ ሥራ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት በመመልከት በተለየ ሁኔታ ሥርዓት እንዲበጅለት እና ቁጥጥር እንዲደረግበት ማድረጉ የሕግ አውጪው ፍላጎት መሆኑን ነው፡፡ይህንንም በእውን ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ደግሞ በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ባንኩ በዝርዝር መመሪያ መሰረት ጉዳዮችን ለማስተዳደር እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን አዋጁ ያስረዳል፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች የተከሰሱበት ድርጊት ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው መመሪያው ቁጥር ወን/001/1997 በአንቀጽ 1 እና 2 ስለወርቅ ንግድና ዝውውር፣መያዝ ወይም ማኖር የባንኩን ፈቃድ አስፈላጊነትና የመጠኑም ገደብ አስመልክቶ ድንጋጌ ይዟል፡፡ይህ መመሪያ ከአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 27(2) እና 5(9) እንዲሁም አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ሲታይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሲሆን አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(1) ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ አዋጁን ወይም አዋጁን ተከትሎ የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የተላለፈ ሰው የሚቀጣበትን አግባብ አስቀምጧል፡፡ስለሆነም የወንጀል ተጠያቂነትን አስመልክቶ የተደነገገው በአዋጁ መሠረት መሆኑን እንረዳለን፡፡ በአዋጅ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የሚወጣ መመሪያ ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 43781 ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በመሆኑም ባንኩ በግልጽ በአዋጁ ስለወርቅ መመሪያ ማውጣት ስልጣን አለው ተብሎ ስልጣን በሕግ አግባብ ከተሰጠው መመሪያው ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል፡፡ከዚህ አንጻር በመመሪያው የተመለከተውን ገደብ በመተላለፍ ለተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት በአዋጁ እና በወንጀል ሕጉ በተመለከተው አግባብ የሚፈፀም በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ላይም መመሪያው ተጸሚነት አለው ብለናል መመሪያ ቁጥር 10/2/001/1997 በተው # 1997 ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ ያለ ሲሆን በዚህ መመሪያ መሰረት የወርቅ አሻሻጥ ስርዓትን በብቸነት የመቆጣጠር ስልጣን ያለው አካል ብሔራዊ ባንኩ ነው፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ወርቅ የሚሸጥ ግለሰብ ወይም ሰው በቅድሚያ መሸጥ ያለበት ለባንኩ በማቅረብ ነው መመሪያው ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው ግለሰቦች ከባንክ ብቻ በሕጋዊ መንገድ ጥፍጥፍ ወርቅ መግዛት እንደሚችሉ ይደነግጋል:: የመመሪያው አጠቃላይ ይዘት ሲታይም የወርቅ ግዥና ሽያጭ የሚከናወነው በብሔራዊ ባንክ ብቻ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ በመመሪያው መሰረት ጥፍጥፍ ወርቅ የማምረት ፍቃድ ካላቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በቀጥታ የመግዛት ስልጣን ያለው ብቸኛ አካል ብሔራዊ ባንኩ ነዉ፡፡ባንኩ ጥፍጥፍ ወርቁን ለመግዛት የሚችለው ደግሞ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ወርቁን ለባንኩ በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ገቢ ሲያደርጉ ነው:: በዚህ በመመሪያው መሰረት በተዘረጋው የወርቅ ግብይት ስርዓት መሰረት የማይከናወን ማንኛውም የወርቅ ግብይት ሕገ ወጥ ድርጊት ነው ተብሎ የሚፈረጅ መሆኑን የመመሪያው አጠቃላይ ይዘት፣መንፈስና ዓላማ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 346 ድንጋጌዎች ይዘት ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ያስረዳል::

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪዎች የወርቅ ማምረት ፍቃድ አለን በማለት ያቀረቡትን ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች እንዳለ ሲቀበሉ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠውንና ሕገ ወጥ ነው የተባለውን ድርጊት ሳይለዩ አልፈዋል፡፡ይኸውም አቃቤ ሕግ ለክሱ መሰረት ያደረገው የተጠሪዎችን ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው መሆን ያለመሆኑን ሳይሆን የወርቅ ግብይቱን በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ለመሸጥ ሲንቀሳቀሱ ተይዘዋል በሚል ነው፡፡ለጉዳዩ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ደግሞ ወርቁ ለብሔራዊ ባንክ ሳይሆን ለአፍሪካ ወርቅ ቤት ቀርቦ ወደ ጅቡቲ በመላክ ለመሸጥ በማሰብ ወርቁ ሲጓጓዝ የነበረ፣በወቅቱም መያዝ የሚገባቸው መረጃዎች ሁሉ በተገቢው ሁኔታ ያልተያዙ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ለጉዳዩ ቀጥተኛ ምስክር የነበረው የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክርና ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ይህንኑ የሚያስረዱ መሆናቸውን የሥር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደሕጉ ስንመጣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በአቃቤ ሕግ የተጠቀሰው 1ኛው ክስ በዋናነት መሰረት ያደረገው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1)፣ በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 53(1)፣(5) ፣26(4) ፣29 እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንደዚሁም በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 አንቀፅ 30(1ሀ(3))፣ ((ለ)) እና((4(ሐ)) ስር እንደተመለከተው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ በሚቆይበት የተመረቱትን፣የተከማቹትን፣የተዘጋጁትን ወይም ለሽያጭ የቀረቡትን ማእድናትን አስመልክቶ መረጃ መያዝ እንዳለበት የተቀመጠውን ግዴታ በመጣስ እንዲሁም በተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 38 እና 39 ላይ እንደተመለከተው የተሟሉና ትክክለኛ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርቶችን፣ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ያለማቅረባቸው የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል በማለት ነው፡፡ይህ ችሎትም ጉዳዩን በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጡት ነጥቦች አንፃር ሲመለከት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 ስር የወንጀል ተጠያቂነት ሊከተል የሚችለው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 346 በተመለከተው አኳኋን ማንም ሰው ሕገወጥ በሆነ መንገድ የከበሩ ማእድናት እንደወርቅ፣ፕላቲኒየም፣ዩራኒየም እና ሌሎችንም እነዚህን የመሳሰሉ ማእድናት እንዲሁም የከበሩ ድንጋዮችን ለመጠበቅ ወይም ሕገ ወጥ ዝውውሩን ለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ በመጣስ ወንጀል የተሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን ቅጣቱም ወንጀሉን የፈፀመበት ከሀምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን ሕጉ ያሳያል። በደንብ ቁጥር 182/1986 ሀብት የመውረስ ደንብ የሚጸናበት መሆኑ ሳይቀር ከአስር አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና ሪፖርቶችን፣ ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ባለማቅረባቸው የአስተዳደራዊ ጥፋቶች ሊባሉ እንደሚችሉ በደንቡ የተመለከተ ሲሆን የጥፋቱን የሚችልበት አግባብ የደንቡ አንቀፅ 39 እና 40 ድንጋጌዎች በግልፅ ያሳያሉ።

ደንቡ የወንጀል ደረጃና ተደጋጋሚነት መሰረት በማድረግም የሚመለከተው አካል አስተዳደራዊ ቅጣት ሊጥል ተጠያቂነትን ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈፀመውን ተግባር ስለመሆኑ በአንቀጽ 40(5) ስር በግልጽ አስቀምጧል በመሆኑም በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በአቃቤ ሕግ በኩል የተጠቀሰባቸው የደንብ ቁጥር 38 እና 39 ድንጋጌዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 347 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትሉ የማይችሉ መሆኑን ከደንቡ አንቀፅ 40(5) ስለተገነዘብን 1ኛ ክስን በተመለከተ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ኃላፊ የሚሆኑበትን አግባብ ስላላገኘን በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም።

ሌላው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የተጠቀሰባቸው የወ/ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ መጠኑ በ1ኛው ክስ የተገለጸውን ወርቅ ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ሕጋዊ ወደአልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲሉ ተይዘዋል የሚል ነው፡ከላይ በፍሬ ነገር ደረጃ እንደተገለጸው 1ኛ ተጠሪ የአቃቤ ሕጉን 1ኛ ምስክር ክ2ኛ ተጠሪ ጋር ተገናኝቶ ወርቁን ወደአዲስ አበባ እንዲያጓጉዝ ማድረጉ፣ 2ኛ ተጠሪ ወርቁን ሲያጓጉዙ ወደ ብሔራዊ ባንክ ሳይሆን አፍሪካ ወርቅ ቤት ለተባለው የንግድ ድርጅት በማቅረብ ወደ ጅቡቲ በመላክ ለመሸጥ በማቀድ ወርቁ ሲጓጓዝ በጉምሩክ አፊሰሮችና በጸጥታ ኃይሎች አማካኝነት በመንገድ ላይ የተያዘ መሆኑ በሚገባ በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ወርቁ በሕጉ አግባብ ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ ለገበያ ሊቀርብ ሲል የተያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ይህም ተጠሪዎች ወርቁን በሕገ ወጥ መንገድ ለማዘዋወር በማሰብ ወንጀሉን በማድረግ፣ የወንጀሉን ድርጊት እስከ መጨረሻው ያልተከታተሉት ወይም ለመከታተል ያልቻሉት ወይም የወንጀሉን ድርጊት እንዲፈፀም እስከ መጨረሻው ተከታትለው አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላገኙ ቢሆንም ተጠሪዎች ወንጀሉን ለመፈፀም ከማይመለስበት ደረጃ /Point of no return/ ደርሰው የነበረ

መሆኑ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ወርቅን በሕገ ወጥ መንገድ መሸጥ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 27(1) 132(1(ሀ))((ለ)) እና 346 መሰረት ወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ድርጊት መፈፀማቸውን የሚያስገነዝብ ሆኖ አግኝተነዋል። ተጠሪዎች ያቀረቡት የመከላከያ ሰነድም ተጠሪዎች ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ለክሱ መሰረት የሆነው ድርጊት ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ ወርቁን ለብሔራዊ ባንክ ሊያቀርቡ የነበረ መሆኑን የማያሳይ በመሆኑ ክብደት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም።በመሆኑም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ2ኛው ክስ ነፃ ሊባሉ የሚችሉበት ማንኛውም አግባብ ስለሌለና ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው ደግሞ በአቃቤ ሕግ ክስ በተመለከተው መልኩ ሳይሆን ወርቁን በሕገ ወጥ መንገድ ለመሸጥ በመሞከር የወንጀል ድርጊት በመሆኑ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 27(1) 32(1(ሀ))((ለ)) እና 346 ስር በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ሆኖ አግኝተናል።ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የአቃቤ ሕግ ክስ ይዘትን ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ጋር በማዛመድ ጉዳዩን መመልከት ሲገባቸው ለክሱ መሰረት ያልሆነውን የተጠሪዎች ሕጋዊ ነጋዴ የመሆን ጉዳይ በምክንያትነት በመያዝ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪን ከ2ኛው ክስ ሙሉ በሙሉ ነፃ በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት

የተፈጸመበት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን የነፃ መልቀቅ ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2((ሀ)) መሰረት በመሻር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወ/ህግ አንቀጽ 27(1)፣32(1(ሀ))(ለ)) እና 346 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው ብለናል።

ሌላው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ የተከሰሱበት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ) እንዲሁም በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀስት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ ተጠቅመዋል የሚል ነው።ተጠሪዎች ማስረጃውን በጥቅም ላይ አውለው የተገኙ መሆኑ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ሐሰተኛ ማስረጃውን ያዘጋጀው የስር 3ኛ ተከሳሽም በበታች ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ ተብሎ ተገቢው ቅጣት የተወሰነበት መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል። 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችም ሕጋዊ የወርቅ አምራችና አቅራቢ ድርጅት የስራ ኃላፊ ከመሆናቸው ውጪ ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም ሲያንገዙትና በሕገ ወጥ መንገድ ሊሸጡት ለነበረው ወርቅ ቀድመው ትክክለኛውን ማስረጃ የያዙ መሆኑን ሊያረጋገጥላቸው የሚችል የመከላከያ ማስረጃ አላቀረቡም።ይልቁንም ተገቢውን ማስረጃ የያዙ ለማስመሰል ቀኑ ወደኋላ ሆኖ የተጻፈ ሐሰተኛ ሰነድ ለተገቢው አካል አቅርበው ለማዋል ሲሉ ተይዘዋል።በመሆኑም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ3ኛ ክስም ነፃ የሚወጡበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2((ሀ)) መሰረት በመሻር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና (ለ))) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የተላለፉ : ጥፋተኞች ናቸው ተብለው ሊቀጡ የሚገባ ሆነው ተገኝተዋል።በመጨረሻም 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ ተገቢነት ተመልክተናል።ይህ ተጠሪ ሕጋዊ ሰውነት የተሠጠው አካል ሲሆን የተከሰሰውም በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፏል በሚል ነው።ከላይ እንደተለገፀው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የ3ኛ ተጠሪ ድርጅት የስራ ኃላፊዎች ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ በሕገ ወጥ መንገድ ወርቁን ለመሸጥ ሲሞክሩ በመገኘታቸው ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባ ሆነው ተገኝተዋል።እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወ/ሕ/አንቀጽ 34 እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት በወንጀል ሊጠየቅ የሚገባ ሆኖ አግኝተናል። በዚህም መሰረት 3ኛ ተጠሪ ነጻ የተባለበትን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ሀ)) መሰረት

በመሻር በ 1997 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1)፣ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ሊባል የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎችን ሙሉ በሙሉ ነጻ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ሕጋዊ ባለመሆኑ ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ2ኛው ክስ የወ/ሕግ አንቀጽ 27(1)፣32(1)(ሀ)(ለ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ በሕገ ወጥ መንገድ ወርቅ ለመሸጥ ሲሞክሩ የተገኙ ጥፋተኞች ናቸው፣እንደሁም ሁለቱም ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀሰት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ የተጠቀሙ ጥፋተኞች ናቸው፡፡ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ያለምንም ሕጋዊ ፈቃድ መጠኑ 15863.18 ግራም የሆነ ወርቅ ሕጋዊ ላልሆነ ገበያ ለማቅረብ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አማካኝነት ሲንቀሳቀስ የተገኘ በመሆኑ በ1997 ዓ/ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34፣27(1)፣ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## 2.በመንግስት ስራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 2.1 የሥራ ኃላፊነትን አለመወጣት(ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም)[58]

- አመልካች የሥራ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ያቀረቡት የስነድ ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ንብረት እንዲገዛ የጠየቀው 1ኛ ተከሳሽ ሆኖ ሳለ 2ኛ ተከሳሽ በስሙ ግዥ መጠየቁ የቀረቡ ሰነዶች አግባብነትና አስፈላጊ ፎርማልቲዎች ያሟሉ መሆን ያለመሆናቸው የተለመደው አሠራር ተከትለው ባለማጣራታቸው ምክንያት የሥራ ኃላፊነትን ያለመወጠት ወንጀል የፈፀሙ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀጽ 407(1)(ሀ) ሳይሆን በወ/ህ/ቁ. 420/1/ ሥር ስለመሆኑ፤[59]

---

[58]የሰ/መ/ቁጥር 97291 (ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18

[59]ሰ/መ/ቁ 43049 (ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ በሰ/መ/ቁ 58514 (ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 55047 (መጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 67411 (ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ. 64612 (የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 73953 (መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 78793 (ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 86845 (መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ የሰ/መ/ቁ 98647 (ሰኔ 02 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ የሰ/መ/ቁ. 98283 (መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17 ፣ የሰ/መ/ቁ. 92826 (ጥር 05 ቀን 2007 ዓ/ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ. 137672 (ሕዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ.መ.ቁ 202508 (ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅፅ 26 ፣ የሰ.መ.ቁ 224040 (ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ. 242958 (ሐምሌ 24 ቀን 2016 ዓ/ም) ፣ የሰ/መ/ቁ. 33075 (ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ የሰ/መ/ቁ 24278 (ሕዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7፣የሰ/መ/ቁ 60518 (ጥር 15 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13፣የሰ/መ/ቁ 60542 (የካቲት 27 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13

የሰ/መ/ቁጥር - 97291

ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ጎሹ ዮሐንስ ገብሩ ጠበቃ ወንድ ይፍራው አረፈ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በስልጣን አለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት ነው፡፡

በሥር ፍርድ ቤት በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ ያልሆኑትን ጨምሮ በሦስት ግለሰቦች ላይ የቀረበው ክስ 1ኛ ተከሳሽ አደም ኑር ፣2ኛ ተከሳሽ አዳነ ይርዳው 3ኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች በመሆን ነው:: የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች እና በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ ያልሆኑ ግለሰቦች ሁለት ክስ ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ክስ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በነበሩት አደም ኑር ገበያው እና አዳነ ይርዳው የቀረበ ነው፡፡ የክሱ አጭር ይዘትም:- በ 1997ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 379(1)(ሀ) እና (ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ እና ለራሳቸው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ 1ኛ ተከሳሽ በግብርና ምርት ላኪነት የተሰማራ ባለሀብት /ኢንቨስተር /2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ወኪል መስለው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ለመቅረብ እና ከድርጅቱ በርካታ ኩንታል ማዳበሪዎች ለመውስድ ያመቻቸው ዘንድ በሀሰት የተዘጋጀ በአማራ ክልል በምሥራቅ ጎጃም ዞን በሰሊሽን ወረዳ መሬት ለማልማት የተደረገ የመሬት ኪራይ ውልና ተዛማጅ ደብዳቤ 'በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንደተሰጠ ተደረገው ተመሳስለው የተሠሩ የንግድ ፈቃዶች በአማራ ክልል መንግስት እንደተሰጠ ተደርጎ ተመሳስሎ የተሠራ የኢንቨስትመንት ፈቃድና የውክልና ማስረጃ እንዲሁም ትክክለኛው ከባንክ ገቢ የተደረገው የገንዘብ መጠን 914.55 ሆኖ እያለ ብር 914,355.00 ያክል ገንዘብ እንዳለው የሚገልጽ ሀስተኛ የባንክ ሲ.ፒ.ኦ.እና ሌሎች ሰነዶች በመያዝ ሰኔ 23 ቀን 2001 እና በተከታዮች ቀናት በግብርና ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በመቅረብ ገቢ በማድረግ አላግባብ የተጠቀሙና በ2ኛ ክስ የተመለከተውን የመንግስት ንብረት ሐምሌ 03 ቀን 2001 ዓ.ም በመወሰዳቸው ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈጸሙት በሀሰተኛ ሰነድም መገልገል የሙስና ወንጀል እንደተከሰሱ፤

ሁለተኛው ክስ በሁሉም ተከሳሾች የቀረበ ሲሆን ዋና ይዘቱ - በ1997 ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ)፣ 33 እና 407(1)(ሀ)(ለ) እና (2) የተመለከተውን ድንጋጌ

በመተላለፍ 3ኛ ተከሳሽ(የአሁኑ አመልካች) በ1ኛ ክስ በተመለከቱት ቀናት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የድርጅቱ የሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል ኃላፊ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ለራሱ እና ለሌሎች ተከሳሾች የማይገባ ጥቅም ለማግኘት እንዲሁም ለማስገኘት እና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፡-

ሀ. 2ኛ ተከሳሹ ከ1ኛ ተከሳሽ የሚገለገልበትን በርካታ ሰነዶች ይዞ በማዳበሪያ ግዥ ሲጠየቅ በመመሪያ መሠረት 3ኛ ተከሳሽ እንደ ኃላፊነታቸው ከዋናው ጋር ማመሣከር ሲገባቸው ይህንኑ ባለማድረጋቸው የማዳበሪያ ግዥ ጥያቄውን በስሙ በቀጥታ ያቀረበው 2ኛ ተከሳሽ ሆኖ እያለ ይኸው ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ የፈጠራ ድርጅት /አደም ኑር ገበያው ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ንብረት መስለው የቀረቡትን በ1ኛ ክስ የተመለከቱትን ሐሰተኛ ሰነዶች ይዞ ሲቀርብ 3ኛ ተከሳሽ የዋጋ ማሣወቂያ ከመፍቀዳቸው በፊት የራሱ ሰነዶች መሆናቸውን ሳያረጋግጡ ላላመለከተ (ግዥ ላልጠየቀ) አካል ከመመሪያው ውጭ መፍቀዳቸው፡- 2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ወኪል ናቸው ቢባል እንኳ የተያዘው የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ ያልተሟላና ለዚህ በቂ አለመሆኑ እየታወቀ እንዲታረምና በመመሪያው መሠረት የውክልና ደብዳቤ እንዲቀርብና የግዥ መጠየቂያ ማመልከቻው እንዲስተካከል አለማድረጋቸው እንዲሁም በቀን 02/11/2000 ዓ.ም በቁጥር 89/008-12/00 ከዋናው መሥርያ ቤት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአድራሻ እና ለንግድ መመሪያ በግልባጭ የተፃፈው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ለሰፋፊ የግል እርሻዎች የሚፈቀደው የማዳበሪያ የሽያጭ መጠን ለአንድ ሄክታር መሬት አንድ ኩንታል ዳፕና አንድ ኩንታል ዩሪያ በጠቅላላው ከ 500 ኩንታል ሣይበልጥ የሚሸጥ መሆኑ እየገለጹ ተከሳሽ ከመመሪያው ውጭ 3,000 ኩንታል ማዳበሪያ በመፍቀዱ፤

ለ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾችም በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው የወንጀል ሐሳብ በመነሳት ከ 3ኛ ተከሳሽ በመመሣጠርና በመንግስትና በህዝብ ሐብት ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው የመንግስት የልማት ድርጅት የሽያጭ ህጋዊ አሠራሮችና መመሪያዎች እንዲጣሱ በማድረግ ባለሀብትና ወኪል በመምሰል በ1ኛ ክስ የተገለጹትን ሐሰተኛ ሰነዶች ይዘው በመቅረብ ግምቱ ብር 913,440.45 የሆነ ማዳበሪያ ከተጠቃሹ የመንግስት የልማት ድርጅት ላይ ወስደዋል:: በመሆኑም ተከሳሾቹ የሽያጭና የአሠራር መመሪያዎች በአግባብ ከማከናውን በመታቀብ እና እርስ በርስ የጥቅም ተከፋይ ለመሆን በመመሳጠር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተሳታፊ በመሆን ድርጊቱን በመፈፀማቸው በስልጣን ያለ አግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ተከስዋል የሚል ነው፡፡

በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (አመልካች) ቀርበው በጉዳዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በተሰጠው ብይን እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሁለቱም ክሶች ተነጣጥለው እንዲታዩ ትዕዛዝ ተሰጥቷል ፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ታዟል:: 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (አመልካች) ክሱን ክደው በመከራከራቸው የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ተሰምቷል:: 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችም የበኩላቸው የመከላከያ ማስረጃ አቅርበዋል:: የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 2ኛ ተከሳሽ የነበረው በተመለከተ የዓቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃ በሁለቱም ክሶች የተጠቀሱትን ፍሬ ነገሮች የፈፀመ ስለመሆኑ መስክሯል:: የ2ኛ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ያስረዱት ፍሬ ነገር ተከሳሹ የድለላ ሥራ የሚሠራ ስለመሆኑ እንጂ ለተከሰሰበት ጉዳይ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት ድርጊት ያልፈጸመ ስለመሆኑ የመሰከሩት ነገር የለም:: 2ኛ ተከሳሽ በሰነድ ማስረጃነት የቆጠረው በአንደኛ ተከሳሽ ለ2ኛ ተከሳሽ ተሰጠ የተባለውን የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ስለመሆኑ ለግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የፃፈው ማመልከቻም በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጉዳዩ ለማስፈጸም የተዋዋለበት ሰነድ የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ የሚያጠናክሩ ናቸው ከሚያሰብል በስተቀር የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ተከላክሏል የሚያስብሉ አይደለም፡፡ ስለሆነም በቀረበበት 1ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 379(1)(ሀ) በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 32(1)(ሀ)(ለ)፣ 33 እና 407(1)(ሀ)(2) በወ/መ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 113(2) መሰረት አንቀፁን

በመቀየር በወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 407(1)(ሀ) በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.149(1)መሠረት ጥፋተኛ ነው ተብሏል፡፡

የአሁኑ አመልካች (3ኛ ተከሳሽ) በተመለከተም የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ እንዲከለከሉ በተሰጠው ብይን መሠረት በድርጅቱ የሚወጡ የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ወሰን በተመለከተ በዓቃቤ ሕግ ክስ የተጠቀሰው መመሪያ ተፈፃሚነት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንጂ ለዋናው መ/ቤት ተከሳሽ ለሚሰሩበት ለሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል አለመሆኑን በዝርዝር ያስረዱና በክሱ የተጠቀሰው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ በአድራሻ የተፃፈው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመሆኑ 3ኛ ተከሳሽ በኃላፊነት ተመድበው ለሚሰሩበት የሽያጭና የገበያ ጥናት ዋና ክፍል በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ የተጠቀሰውና በድርጅቱ ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተላለፈ የተባለው መመሪያ ከወጣ በኃላ ሚያዝያ 19 ቀን 2001 ዓ.ም ተከሳሹ በኃላፊነት ተመድበው ለሚሰሩበት ለሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል በአድራሻ የተላለፈው የማዳበሪያ ሽያጭ መመሪያ በተሰጣቸው ስልጣን መጠን እስከ 10,000 ኩንታል የሚደርስ የማዳበሪያ ሽያጭ ለግል ስፋፊ የእርሻ ልማት ባለሃብት መፍቀድ እንደሚችሉ ሥልጣን የተሰጣቸው ለመሆኑ የሚያረጋግጥ የመከላከያ የሰነድ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ይህም ተከሳሽ በዓቃቤ ሕግ ከመመሪያ ውጭ የማዳበሪያ ግዥ ፈቅደዋል በሚል የተጠቀሰባቸው የክስ ፍሬ ነገር በተመለከተ በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው ተከላክለዋል የሚያስብል ሆኖ ተገኝቷል:: 3ኛ ተከሳሽ በዓቃቤ ሕግ ከተጠቀሰባቸው የክስ ፍሬ ነገሮች ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ ከ1ኛው ተከሳሽ ጋር የሚገለገሉባቸው ሐሰተኛ ሰነዶች ይዞ የማዳበሪያው ግዥ በቀጥታ የጠየቀው 2ኛ ተከሳሽ ሆኖ የማዳበሪያው ግዥ ከመፍቀዳቸው በፊት 2ኛ ተከሳሽ ግዥው እየጠየቀ ያለው የራሱን ሰነዶች ይዞ እንደሆነ ሣያረጋግጡ ግዥው ላልጠየቀ አካል ፈቅደዋል:: 2ኛው ተከሳሽ የ1ኛው ተከሳሽ ወኪል ነው ቢባል እንኳ ተያይዞ የቀረበው የውክልና ሰነድ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው መሆኑን እያወቁ የማዳበሪያው ግዥ እንዲፈጸም ፈቅዷል በሚል ሲሆን በዓቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች 2ኛ ተከሳሽ ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የማዳበሪያ ግዥ በራሱ ስም የጠየቀና የቀረቡት ሰነዶች አደም ኑር ገበያው ኃ/የተ/የግ ማህበር የሚል ሆኖ እያለና የቀረበው የውክልና ሰነድ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ስለሆነ በግልጽ በቀላሉ ችግሩን መለየትና ማጣራት የሚያስችል ሆኖ እያለ ይህንን ሳይፈጽሙ ከድርጅቱ ማዳበሪያ ግዢ እንዲፈፅም መፍቀዳቸው የተመሰከረባቸው በመከላከያ ማስረጃዎች የተከለከሉ ሆነው አልተገኘም፡፡

በዚህም መሠረት በ3ኛ ተከሳሽ (አመልካች) ላይ ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 33 እና 407(1)(ሀ)(ለ)(2) ተላልፏል በማለት የቀረበው ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 113(2) መሠረት አንቀጹን በመቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 33 እና 407(1)(ሀ) ሥር በወ/መ/ሥ/ሥ/ህቁ 149(1) መሠረት ጥፋተኛ ነው በማለት ተወስኗል፡፡

ቅጣት በተመለከተም 1ኛ ተከሳሽ በሌለበት የታየ በመሆኑ የቅጣት ማቅለያዎች ግምት ውስጥ ሳይገባ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በተመለከተም በግራ ቀኙ የቀረቡት የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በማገናዘብ 1ኛ ተከሳሽ በ 13 ዓመት ጽኑ እስራት እና 6,000 ብር መቀጮ 2ኛ ተከሳሽ በ 8 ዓመት ጽኑ እስራት 5000 ብር መቀጮ 3ኛ ተከሳሽ (አመልካች) ደግሞ በ 4 ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራትና ብር 2500.00 እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና ቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታው ወደ ጉዳዩ ለመግባት የሚያስችል በቂ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ ተደርጓል :: የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርገዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት:- የዋጋ ማሳወቂያ መስጠት መደበኛ ሥራቸው እንደሆነ ፤የቀረበላቸው የሐሰት የሰነድ ማስረጃ የተባለው ሐስተኛ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚችሉበት አግባብ እንዳልነበረ ሽያጭ የፈቀደው የሌላ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ነው፡፡ የዋጋ ማሳወቂያ የተሰጠው ለ 5 ቀን የሚያገለግል ስለመሆኑ ፤የዋጋ ማሳወቂያ መስጠት ለመሸጥ ሐሳብ ማቅረብ እንጂ ሽያጭ መፈጸም አይደለም ::

እቃ ለመሸጥ አሳብ መቅረብ የወንጀል ድርጊት አይደለም :: በሲ.ፒ.ኦ ደረሰ የተባለው ጉዳት በቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ትዕዛዝ የተከናወነ እንጂ አመልካች ተሳትፎ እንዳልነበራቸው በድርጊቱ ምክንያት እና ውጤት ግንኙነት የለውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል የሚል ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በአመልካች በኩል መጣራት የገባቸው የነበሩ ነገሮች ባለ መጣራታቸው ከመመሪያው ውጭ ሽያጭ ተከናውነዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾች በነበሩ ግለሰቦች የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ሳያጣራ በማሳለፍ ምክንያት ድርጊቱ የወንጀል ውጤት ያስገኘ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና መጠየቁን ተመልክተናል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታው በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ፣ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ፍርድ አግባብነት ካላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች በማዛመድ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው በአመልካች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ የወ/ሕ/ቁ 32(1)(ሀ)(ለ)፣ 33 እና 407(1)(ሀ)(ለ) እና (2) የተመለከተውን በመተላለፍ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በነበሩ የቀረቡ ሐሰተኛ ሰነዶች የዋጋ ማሳወቂያ ከመፍቀዳቸው በፊት የ2ኛ ተከሳሽ የራሱ ሰነዶች መሆናቸው አላረጋገጡም፡፡ ግዥ ላልጠየቀ ግለሰብ ከመመሪያው ውጭ ፈቅደዋል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በአንደኛ ተከሳሽ ወኪል ነው ቢባል እንኳ የተያዘው የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የለም፡፡ ከዋናው መሥሪያ ቤት የተፃፈው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ለሰፊራ አርሻዎች የሚፈቀደው የማዳበሪያ ሽያጭ መጠን በሄክታር አንድ ኩንታል ዳፕና አንድ ኩንታል ዩሪያ በጠቅላላው ከ 500 ኩንታል እንደማይበልጥ የሚሸጥ መሆኑ እየታወቀ 3000 ኩንታል መዳበሪያ እንዲሸጥ ፈቅደዋል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ፣የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣኑ የደረሰበት ድምዳሜ አመልካች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት መጠኑ እስከ 10,000 ኩንታል ማዳበሪያ መሸጥ እንደሚችሉ ይሁንና 2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ተወካይ እነደሆነና የቀረቡ የግዥ ሰነዶች አደም ኑር ገበያው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት የሚል ሆኖ ሳለ 2ኛ ተከሳሽ በራሱ ስም ግዥ መጠየቁ የቀረበው የውክልና ሰነድም የወካይ ስምና ፊርማ የሌላው እንደሆነ ፣ይህም በቀላሉ ችግሩን መለየትና ማጣራት የሚቻል እንደነበር ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥልጣኑ ያለአግባብ የተገለገለ ከሆነ በወ/ሕ/ቁ.407 ሥር ተጠያቂ እንደሚሆን ግልጽ ነው:: የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ የተፈጸመው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ እንደሆነ ፣የድርጊቱ አፈፃፀምም የተሰጠው ሹመት ወይም ሥልጣን በግልጽ ተግባር ወይም ግድፈት ከተሰጠው ስልጣን አልፎ በመሥራት ወይም ሥልጣኑ በማይፈቅደለት በተለይም ሥልጣን ሳይኖረው ወይም ከሥራ ከታገደ ከተዛወረ ፣ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱ ከተወ በኃላ የተፈጸመ ከሆነ የወንጀል ድርጊቱ ለማቋቋም በአማራጭ የተዘረዘሩ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ እንደ ወንጀሉ ክብደትም ከወንጀል ፈፃሚው ኃላፊነት፣የደረሰው ጉዳት ወይም የተገኘው ጥቅም ወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓላማ መሠረት በማድረግ ወንጀሉ እንደሚከብድ የወ/ሕ/ቁ. 407(2) እና (3) ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት ዓላማና መንፈስ መረዳት ይቻላል:: የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ክስ በማሻሻል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) (ለ) እና 407(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ያላቸው ስለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ሙሉ ይዘት የተሰጠው ሹመት ወይም ሥልጣን በግልጽ ተግባር ወይም ግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ "የሚል ነው:: በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ለማለት እንደመነሻ የወሰደው ግዥው የተጠየቀው ለአደም ኑር ሆኖ እያለ 2ኛ ተከሳሽ በራሱ ስም የራሱ ሰነዶች ይዞ እየጠየቀ መሆን ያለመሆኑን አላጣሩም ፣2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ተወካይ ነው ቢባል እንኳ የውክልና ሰነዱ የወካይ ስምና ፊርማ ያለው

ነው በቀላሉ መለየት ይቻል ነበር በሚል ነው:: አመልካች የዋጋ ማሳወቂያ ሰነድ የሰጡ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ በዋጋ ማሳወቂያው መሠረት ሽያጭ መፍቀድና ማከናወን ደግሞ በሌላ የሥራ ክፍል የሚደረግ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በኃላፊነት እንዲጠየቁ በመሠረታዊነት የተያዘው ምክንያት የውክልና ሰነዱ የተሟላ ባለመሆኑ ችግሩን በቀላሉ መለየትና ማጣራት ይቻል ነበር በሚል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት መሠረታዊ ነጥብ አመልካች በውክልና ሰነዱ ላይ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለ መሆኑ እየታየ የዋጋ ማሳወቂያ ሰነድ መስጠታቸው በወ/ሕ/ቁ 407(1) (ሀ) ሥር ጥፋተኛ ሊያሰኛቸው ይችላልን? የሚል ነው፡፡ ከክርክር ሂደቱ መረዳት እንደተቻለው አመልካች የቀረቡ ሰነዶች በጥንቃቄ ለይተው ማጣራት የማይችሉበት ሁኔታ እንደነበር በግልጽ የቀረበ ክርክር ባይኖርም በወ/ሕ/ቁ.407(1)(ሀ) እንደተመለከተው ግን የተሰጣቸው ኃላፊነት ያለአግባብ የተገለገሉ ስለመሆናቸው የወንጀል ሕጉ እንደ መሠረታዊ ማቋቋሚያ የዘረዘረው ፍሬ ነገር ስለመረጋገጡ ከሳሽ ወገን የማስረዳት ሸክሙ ስለመወጣቱ የሚያሳይ ነገር በሥር ፍርድ ቤት አልቀረበም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በአመልካች የተፈጸመው ድርጊት ስልጣን አላግባብ መገልገል ሳይሆን የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈጸም ወንጀል መሆኑን መረዳት ይቻላል:: አመልካች የሥራ ግዴታቸው ሲወጡ ከእሳቸው የሚጠበቀውን ግብይት ለማካሄድ እንደቅድመ ሁኔታ የሚወሰዱ የቀረቡ ሰነዶች በተገቢው መንገድ ተፈረመው የቀረቡ መሆን ያለመሆናቸው ፤የውክልና ሰጪ ስምና ፊርማ መኖር ያለመኖር የድርጅቱን አሠራር በሚፈቅደው አግባብ በጥንቃቄ ባለማጣራታቸው በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በቀረቡት ሐሰተኛ ሰነድ ተጠቅመው ከግብርና ምርት ማሳደጊያ አቅራቢ ድርጅት ማዳበሪያ ወስደዋል፡፡ በዚህም በድርጅቱ የገንዘብ ጥቅም ላይ ጉዳት ደርሰዋል:: በመሆኑም አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በወ/ሕ/ቁ 407(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ማለቱ የወንጀል ድርጊቱ ይዘትና ባሕሪ ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ሊሆኑ የሚገባው ከፈጸሙት የወንጀል ድርጊት በተጣጣመ መልኩ መሆን ይገባዋል ፡፡ በዚህም አመልካች የሥራ ኃላፊነታቸው ሲወጡ ተገቢው ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ያቀረቡት የስነድ ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው:: ንብረት እንዲገዛ የጠየቀው 1ኛ ተከሳሽ ሆኖ ሳለ 2ኛ ተከሳሽ በስሙ ግዥ መጠየቁ የቀረቡ ሰነዶች አግባብነትና አስፈላጊ ፎርማልቲዎች የሚሉ መሆን ያለመሆናቸው የተለመደው አሠራር ተከትለው ባለማጣራታቸው ምክንያት የሥራ ኃላፊነትን ያለመወጠት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ ስለሆነም የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/ሕ/ቁ/32(1)(ሀ)(ለ)፤33እና 407(1) (ሀ) ሥር ጥፋተኛ ማለቱ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ በአግባቡ ባለመሆኑ አመልካች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው አግባብነት ባለው የወንጀል ድንጋጌ በመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113(2) በሚያዘው መሠረት ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 407(1)(ሀ) ወደ ወ/ህ/ቁ. 420/1/ ሥር በመለወጥ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል ፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ በመለወጡ በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው ቅጣት ተገቢነት መርምረናል፡፡ የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2002 ወይም ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተሰኙበት የሕግ አንቀጽ የወንጀል ደረጃ እና መነሻ የእስራት ወይም መቀጮ እርከን የወጣለት አይደለም:: አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 420(1) ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል:: የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው በ2001 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት መመሪያ 1/2002 ነው:: የወንጀል ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ በአንድ በኩል የወንጀል ፈፃሚው ግላዊ ሁኔታዎች በሌላ በኩል ግምት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ከወ/ሕ/ቁ 1 እና 88 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ የምንረዳ ነው:: በተያዘው ጉዳይ ፍርድ ቤቱ የእስራት አማራጭ ወስዷል:: አመልካች የፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ክብደትና ባህሪ መሠረት በማድረግ የስድስት ወር ቀላል እስራት መነሻ ይዘናል፡፡ መቀጮ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በ 2500 ብር እንዲቀጡ የወሰነ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ የቀላል እስራት

አማራጭ ብቻ የተወሰደ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የጣለው መቀጮ የሕግ መሠረት የሌለው ስለሆነ ሊነሳ የሚገባው ነው በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች ሊያርምና ሊያስተምር ይችላል፤ መሰል አጥፊዎችን ያስጠነቅቃል ብለን ያመነበት አመልካች በስድስት ወር ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካች የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ዓይነት በአግባቡ ሳያገናዝቡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና (ለ) 407(1)(ሀ)ሥር ጥፋተኛ ማለታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በማረም በወ/ሕ/ቁ.32(1)(ሀ)(ለ)፣33 እና 420(1) ሥር ጥፋተኛ ናቸው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.94053 በ 2/09/2005ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና ቅጣት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ.92016 በ 29/02/2006ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195(2)(ለ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በሥልጣን ያለአግባብ በመገልገል የወ/ህ/ቁ 407(1)(ሀ)ሥር ሳይሆን የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት ወንጀል የወ/ህ/ቁ.420(1) ሥር ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ለፈጸሙት ወንጀል በስድስት ወር ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት የተወሰነባቸው ብር 25000/ሁለት ሺህ አምስት መቶ/ መቀጮ ለመንግስት ገቢ አድርገውት ከሆነ ወጪ ሆኖ እንዲከፈላቸው ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>3.የፍትህ አስተዳደር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

### <u>3.1ሀሰተኛ ምስክርነት</u>[60]

- በወንጀል ምርመራ ወቅት ምስክሩ ለፖሊስ የሚሰጠዉ ቃል ልክ እንደመደበኛዉ የዳኝነት አካል ወይም የዳኝነት ነክነት ወይም መሰል ተቋም ቃለ መሃላ ፈጽሞ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ካለመሆኑም በተጨማሪ ምስክሩ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል እና በፍርድ ቤት የሰጠዉ የምስክርነት ቃል መካከል ልዩነት በተፈጠረ ጊዜ በፖሊስ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል እዉነት ነዉ ነገር ግን በፍርድ ቤት የሰጠዉ የምስክርነት ቃል ሀሰት ነዉ ለማለት የምስክሩ ቃል መለያየት ብቻዉን በቂ ማስረጃ ነዉ ብሎ ለመዉሰድ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፤[61]

የሰበር መ/ቁ/153228
መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

*ዳኞች:* ብርሃኑ አመነዉ
በዕዉቀት በላይ
እንደሻዉ አዳነ
ሃይሉ ነጋሽነ
እትመት አሰፋ

[60]የሰ/መ/ቁ 153228 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23

[61]የሰ/መ/ቁ 67777 (ታህሳስ 04 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ በሰ/መ/ቁ/158613 (ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 23

*አመልካች፤ የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ*

*ተጠሪዎች፡ 1ኛ/ፈንቴ ንጉሰ*

*2ኛ/ታድሎ ጥላሁን*

*3ኛ/ምናለ ዳኛዉ*

*መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡*

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ተጠሪዎች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ ተላልፈዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል ተብሎ ከቀረበባቸዉ ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ፍርድ አግባብነት ለመመርመር የቀረበ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ እነ ቂስ ወርቂ ገላየ/9 ሰዎች/በተጠረጠሩበት የደን እንጨት መቁረጥ ወንጀል የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፎገራ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ላይ በምስክርነት ቀርበዉ ተጠርጣሪዎቹ ጥር 24 ቀን 2008 ዓ.ም ከቀኑ 6፡30 ላይ ፍገራ ወረዳ ምንጡራ ቀበሌ ሸንበቆ ጎጥ ከተባለዉ ቦታ የማህበራት የተፈጥሮ ደን የሆነዉን ሁሉም ተከሳሾች መጥረቢያ በመያዝ ደኑን ሲጨፈጭፉ አይተናል በማለት ቃል ከሰጡ በኋላ የአቃቤ ህግ ምስክር ሆነዉ በፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃላቸዉን በ07/10/08 ዓ.ም ሲሰጡ ሁሉም ተከሳሾች መጥረቢያ ይዘዉ ሲቆርጡ አላየንም በማለታቸዉ ደን ቆርጠዋል ተብለዉ ክስ የቀረበባቸዉ ተከሳሾቹ በ21/10/08 ዓ.ም በተሰጠ ፍርድ በነጻ እንዲሰናበቱ ስለተወሰነ ተጠሪዎች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 453/2/ ተላልፈዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ሰጥተዋል በሚል ክስ የቀረበባቸዉ ሲሆን ተጠሪዎች ክሱን ክደዉ ስለተከራከሩ ክሱን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ ተጠሪዎች የተመሰከረባቸዉን በመከላከያ ማስረጃ አላስተባበሉም በማለት በተከሰሱበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት እያንዳንዳቸዉ በ6ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸዉ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ የተጠሪዎች ድርጊት ጥፋት መሆኑን ለማስረዳት በአቃቤ ህግ በኩል የቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡት የምስክርነት ቃል እና ከዚህ ጋር ማነጻጸሪያ ሆኖ የቀረበዉ ተጠሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበዉ ቃለ መሃላ ፈጽመዉ የሰጡት ምስክርነት ቃል ብቻ ስለመሆኑ ገልጾ በፖሊስ የምርመራ ወቅት የሚሰጠዉ ምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት ከተሰጠ ምስክርነት ቃል ጋር ተነጻጽሮ የትኛዉ ትክክለኛ ነዉ የሚለዉን ለመለየት ተጨማሪ ማስረጃ እንደሚያስፈልግ ከዚህም ባሻገር ከጅምሩም ቢሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 453 የሚሸፍነዉ ዳኝነት ወይም ዳኝነት ነክነት ባለዉ ሂደት ላይ የሚሰጥ ምስክርነትን ቃል የሚመለከት ስለመሆኑና ፖሊስ ስልጣንና ተግባር እንዲሁም የወንጀል ምርመራ ሂደት ዳኝነት ነክነት ያለዉ ተግባር ነዉ ተብሎ በዚህ አንቀጽ ስር ሊሸፈን እንደማይገባ በማተት የስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ያስተላለፈዉን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በመሻር ተጠሪዎች በነጻ እንዲሰናበቱ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የፖሊስ ተቋም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ተቋም አይደለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ትርጉም የፖሊስ ተቋም በወንጀል ጉዳይ የመጀመሪያ የምስክርነት ቃል የሚሰጥበትና አቃቤ ህግም ይህንኑ መሰረት አድረጎ ክስ የማቅረብ ወይም ያለማቅረብ ጉዳይ ዉሳኔ የሚሰጥበት ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት የፖሊስ ተቋም የዳኝነት ነክነት ተግባር የሚፈጸሚበት አይደለም ተብሎ የተሰጠዉ ትርጉም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪዎች እነ ቂስ ወርቂ ገላየ 9 ሰዎች በተከሰሱበት የደን መቁረጥ ወንጀል ምርመራ በፎገራ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ቀርበዉ ወንጀሉ ሲፈጸም

የተመለከቱ  መሆኑን መስክረዉ በፍ/ቤት ደግሞ የአቃቤ ህግ ምስክር ሆነዉ ቀርበዉ በፖሊስ የሰጡትን ቃል በመለወጣቸዉ ከቀረበባቸዉ ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ የተሰጠዉ ዉሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 453/2/ አያሟላም ተብሎ ዉድቅ መደረጉ አግባብነት ከመሰረታዊ ማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በቀበሌዉ ዉስጥ በህዝብ ተመራጭነት በተሰጣቸዉ ሃላፊነት ድርጊቱ በፖሊስ እንዲጣራ ከመጠየቅ ዉጪ የድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት እንደማያዉቁ ለፖሊስ ገልጸዉ እያለ ፖሊስ በማስፈራራትና በማንገራገር እነሱ ያላሉትን ቃል በመመዝገብ ሳያነብላቸዉ እንዳስፈረማቸዉ ጠቅሰዉ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ትክክለኛዉን እዉነታ የምስክርነት ቃል የሰጡ ስለመሆኑና የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መሰረት አድርጎ በነጻ ማሰናበቱ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ትርጉም ስህተት ተፈጽሟል ወይ? የሚለዉን አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለዉ ተጠሪዎች ላይ የቀረበዉ ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ ተላልፈዉ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት ቀርበዉ በመለወጣቸዉ ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል በመስጠት ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ነዉ፡፡የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ ተከሳሾች ደን ሲቆርጡ አይተናል ብለዉ መስክረዉ ፍርድ ቤት ቀርበዉ አላየንም በማለታቸዉ ሁለቱን የምስክርነት ቃል በማነጻጸር ልዩነት መኖሩን አረጋግጦ ፍርድ ቤት ቀርበዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል በሚል በተከሰሱበት አንቀጽ ስር የጥፋተኛነት ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን ዉሳኔ የሻረዉ በዋናነት የማስረጃ ምዘና መሰረት አድርጎ ሳይሆን የፖሊስ ተቋም የወንጀል ምርመራ ስራ በወንጀል ህግ አንቀጽ 453 ድንጋጌ መሰረት የዳኝነት ነክነት  በሚለዉ ትርጉም የሚሸፈን መሆን አለመሆኑን በመመርመር ስለመሆኑ ከዉሳኔዉ ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም በዚህ ችሎት ሊመረመር የሚገባዉ ነገር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት  የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ስራ የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት በሚለዉ ሐረግ የሚሸፈን አይደለም በማለት የሰጠዉ ትርጉም አግባብነት ላይ ነዉ፡፡እንደሚታወቀዉ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስራ ዉስጥ የፖሊስ ተቋም በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ እንደሆነ እሙን ነዉ፡፡ከፖሊስ ተቋም ዋነኛ ተግባር ዉስጥ ወንጀልን መከላከል እንዲሁም ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ተገቢዉን ምርመራ ማድረግና ወንጀለኛዉን አድኖ ለህግ በማቅረብ ብሎም ፍርድ ማሰጠት እንዲሁም ፍርዱን ማስፈጸም ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ተግባርና ሃላፊነት ስለመሆኑ የፖሊስ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጆችና የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነዉ፡፡ስለሆነም በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዓት ዉስጥ የፖሊስ ተቋም ሚና ከፍተኛ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን ከቀረበዉ ክርክር አንጻር ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ የሰጡትን የምስክርነት ቃል በፍርድ ቤት ቀርበዉ ለዉጠዋል በሚል ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል የሚለዉ የአቃቤ ህግ ክስ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 453 ስር የሚሸፈን መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲረዳን የድንጋጌዉ የተቀረጸበትን ሃይለቃል ማየት ይገባል፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/1/ ላይ የተደነገገዉ ‹‹የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሰዉ ማንኛዉንም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሀሰተኛ ምስክርነት ወይም ልዩ አዋቅነት አስተያት የሰጠ እንደሆነ ወይም እዉነቱን የደበቀ እንደሆነ ሀሳቡ ከግቡ ባይደርስም ...›› በዚህ ደንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብሎ እንደሚቀጣ እንዲሁም የተፈለገዉ ዉጤት የተገኘ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ ሁለት ስር በተደነገገዉ አግባብ የሚቀጣ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡የእንግሊዝኛዉ ቅጂም እንዲህ ይነበባል፡፡‹‹453/1/ whoever being a witness in judicial or quasi-judicial proceeding knowingly makes or gives a false statement or expert opinion or hides the truth whether to the advantage or the prejudice of any party thereto…>>.በሚል ይገልፃል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ዉስጥ ከተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ መሰረታዊ ፍሬነገሮች ዉስጥ አከራካሪ ሆኖ

የቀረበዉ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት የሚለዉ ሃይለቃል የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ስራን ያካትታል ወይ የሚለዉ ነዉ፡፡ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ‹‹ዳኝነት›› እና ‹‹ዳኝነት ነክነት›› ለሚለዉ ቃል ትርጉም መፈለግ ግድ ይላል፡፡የእነዚህ ቃላት ትርጉም በሀገራችን የህግ ኮዶች ወይም መዝገበ ቃላት ላይ በቀጥታ ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ተመሳሳዩን የእንግሊዘኛ ትርጉም መመልከት ተመራጭ ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህ ረገድ ታዋቂዉ የህግ መዝገብ ቃል Blacks law dictionary ላይ እንደተተረጎመዉ፤ ‹‹JUDICIARY-the branch of government invested with judicial power›› በማለት ትርጉም የሰጠ ሲሆን ‹‹QUASI-JUDICIAL ..hold hearings, weigh evidence; and draw conclusions from them, as basis for their official action, and to exercise discretion of judicial nature>>.በሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የመጀመሪያዉ የዳኝነት ስራ የሚያከናዉን የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አንደኛዉ የመንግስት አካል ወይም መደበኛዉን ፍርድ ቤት የሚያመለክት ሲሆን የዳኝነት ነክነት ስራ የሚካሄድበት ደግሞ በዳኝነት መልክ ወይም መሰል ሁኔታ ክርክር የሚሰማበት፣የቀረበለት ማስረጃ ተመዝኖ ከድምዳሜ የሚደረስበትና የበኩሉን ዉሳኔ የሚሰጥበት ሂደት የሚከናወንበት ተቋም የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ ረገድ ተጠቃሽ የሆኑት ተቋማት እንደግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፣የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ቦርድ፣ የግለግል ተቋማትና ሌሎችም መሰል ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸዉ አስተዳደራዊ ተቋማት ስለመሆናቸዉ ሀገራችንን ጨምሮ የተለያዩ ሀገሮች ልምድ ያመላክታል፡፡ ይህ በዘርፉ በተደረጉ ጥናቶችና በርካታ ጽሁፎች ላይም የሚጠቀስ ነዉ፡፡ ከዚህም ባሻገር የተሻሻለዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሀተታ ዘምክንያት ላይ እንደተመለከተዉ ቀደም ሲል ስራ ላይ የነበረዉ የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 447 ስር ሀሰተኛ ምስክርነትን አስመልክቶ የተደነገገዉ ያስተዳደር ፍትሐ ብሔር፣ የወንጀል ወይም የሽምግልና ዳኝነት፣ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስነስርዓት የሚፈጸምበት በሚል የተዘረዘረዉ የተንዛዛ በመሆኑ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት በሚል በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453 ስር ተሻሽሎ የቀረበ ስለመሆኑ ተገልፆል፡፡ ከዚህም አንጻር ሲታይ የወንጀል ምርመራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ስር እንዲሸፈን ያልተደረገ ስለመሆኑ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት የሚለዉ ሀረግ ጥቅል ትርጉም ዳኝነት መሰል ተግባር የሚከናወንበት ሂደት የሚያመላክት ሲሆን በህጉ የተለየ ሁኔታ ካልደነገገ በስተቀር በስነስርዓት ህጉ በተደነገገዉ አግባብ ክርክር የሚመራበትና ምስክርም ሲሰማ እዉነትን ለመመስከር ቃለመሃላ ፈጽሞ ቃሉን የሚሰጥበት አካሄድ የሚከተል መሆኑን መገንዘብ አዳጋች አይደለም ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ በፖሊስ በወንጀል ምርመራ ወቅት ምስክሩ የሚሰጠዉ ቃል ልክ እንደመደበኛዉ የዳኝነት አካል ወይም የዳኝነት ነክነት ወይም መሰል ተቋም ቃለ መሃላ ፈጽሞ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ካለመሆኑም በተጨማሪ ምስክሩ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል እና በፍርድ ቤት የሰጠዉ የምስክርነት ቃል መካከል ልዩነት በተፈጠረ ጊዜ በፖሊስ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል እዉነት ነዉ ነገር ግን በፍርድ ቤት የሰጠዉ የምስክርነት ቃል ሀሰት ነዉ ለማለት የምስክሩ ቃል መለያየት ብቻዉን በቂ ማስረጃ ነዉ ብሎ ለመዉሰድ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፡፡በእርግጥ አንድ ምስክር ለፖሊስ የሰጠዉን ቃል ፍ/ቤት ሲቀርብ ከቀየረ ከሁለቱ አንዱ የሀሰት ቃል መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ሆኖም አመልካች ክስ ከመመስረቱ በፊት ከሁለቱ ቃሎች መካከል የሀሰት ቃል የትኛዉ እንደሆነ በትክክል በሌላ ማስረጃ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ መዝገብ በተያዘዉም ጉዳይ ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡት የምስክርነት ቃል እዉነተኛ የሆነዉን ለዉጠዉ በፍርድ ቤት ቀርበዉ የሀሰት የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል በማለት አቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ መሰረት በማደረግ ያቀረበዉን ክስ ለማስረዳት ያቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪዎች በፖሊስ ምርመራ ላይ የሰጡት ቃል እና በፍርድ ቤት የሰጡትን ቃል በማነጻጸር እንደመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረዉ አማራ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድንጋጌዉ በፖሊስ የወንጀል ምርመራ ሂደት የተሰጠን

የምስክርነት ቃል በቀጥታ ከፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል በማነጻጸር የኋላኛዉ የሀሰት ቃል ነዉ ለማለት በፖሊስ የተሰጠ ቃል የዳኝነት ነክነት ከሚለዉ የሚያጠቃለል አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ላይ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚሁአግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ዉሳኔ**

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/17096 በ05/10/09 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/70512 ላይ በ26/03/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህገ ቁ/195/2/ለ/2 መሰረት ጸንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 3.2 ፍርድ ቤትን መድፈር[62]

- ፍርድ ቤቱ ፍርድ በሚያነብበት ጊዜ ስነ ስርዓት እንዲይዙ የተነገራቸውን ትዕዛዝ ያለማክበራቸውንና "ፍርድ ቤቱን በስነ ስርዓት ያናግረን" በሚል ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸው የፍርድ ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱን ማወካቸውን የሚያሳይ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 አግባብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 449(1(ሀ)) ድንጋጌ ስር ተጠያቂነት የሚያስከትል ተግባር ስለመሆኑ፤[63]

የሰ/መ/ቁ/ 92459

ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ/ም

ዳኞች፡- 1.ተገኔ ጌታነህ
2.አልማው ወሌ
3.ዓሊ መሀመድ
4.ረታ ቶሎሳ
5.አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፍጽም ብርሃን ገ/ክርስቶስ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው አመልካች ፍርድ ቤትን የመድፈር የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል ተብሎ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 አግባብ የጥፋተኝነትና የአምስት ቀን ቀላል እስራት መወሰኑም ሆነ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይኼው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መፅናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተተ ያለበት ነው በማለት አመልካች ስለአመለከቱ ነው፡፡

---

[62]የሰ/መ/ቁ/ 92459 (ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ/ም) ቅፅ 15

[63]ሰ/መ/ቁ 67777 (ታህሳስ 04 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13፣ የሰ/መ/ቁ 166294 (ግንቦት 7 ቀን 2011ዓ.ም)

አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2005 ዓ/ም በዓፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ የነበረውን ሂደትና ጉዳዩ በችሎት መድፈር የማያስጠይቃቸው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶቸ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ እንዲሻርላቸው ወይም የእስራት ቅጣቱ በገንዘብ መቀጮ እንዲቀየርላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡እኛም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተተ ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችን በፍርድ ቤት መድፈር የወንጀል ድርጊት እንዲቀጡ ትዕዛዝ ሊሰጥ የቻለው ፍርድ እየተነበበ ባለበት ሰዓት ትዕዛዙ በተሰጠበት መዝገብ ቁጥር 72908 ተከሳሽ የሆነው ድርጅት ካሌብ ሆቴል ጠበቃ የሆኑት የአሁኑ አመልካች ስልክ በማስጮህ እንደሁም ከሳሽ ከሆኑት ግለሰብ ከአቶ ሀብታሙ በላይ ጋር ያልተገባ ክርክር በመፍጠር ፍርድ ቤቱ ስነ ስርዓት እንዲይዙ ቢያሳውቃቸውም ስነ ስርኣት ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው፣እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በስነ ስርዓት ያናግረን በሚል ያልተገባ ባህርይ ማሳያታቸውን፣ከዚህም በተጨማሪ በችሎት ውስጥ ስልክ ማስጮህ እንደማይቻል ተገቢው ማስታወቂያ ተለጥፎ እያለና አመልካችም የሕግ ባለሙያ ሁነው እያለ የችሎቱን ስርዓት ያወኩ መሆኑን በመግለፅ ሲሆን እነዚህ የፍሬ ነገር ነጥቦች መኖራቸውን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ ተቀብሎአቸዋል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በችሎት መድፈር ወንጀል ሊቀጡ የቻሉት ስልክ በማስጮሃቸው ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ ስነ ስርዓት እንዲይዙ አሳውቆአቸው ስነ ስርዓት ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረትና ፍርድ ቤቱ በስነ ስርዓት ያናግረን በሚል ያልተገባ ባህርይ ሁሉ ለችሎቱ በማሳየታቸው መሆኑን ጭምር ነው፡፡ትዕዛዙን የሰጡት ዳኛም በጊዜው በፍርድ ማንበብ ስራ ላይ እንደነበሩ በመዝገቡ ላይ የሰፈረ ጉዳይ ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ችሎት በኢ.ፌ..ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ጉዳይ ያለመሆኑ የሚታወቅ በመሆኑ ከላይ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮችን እንዳሉ የምንቀባላቸው ይሆናል፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ደግሞ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ አመልካች በችሎት ውስጥ ሞባይል ስልክ አስጩኸዋል ተብለው በዚህ ድርጊት መነሻነት ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን ጋር በተደረገ የቃላት ልውውጥ መነሻነት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 449(1(ሀ)) እንዲቀጡ መደረጉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ የተያዘው ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከችሎቱ ዳኛ ስነ ስርዓት እንዲይዙ የተነገራቸውን ትዕዛዝ ሳያከብሩ መቅረታቸውን እንዲሁም ችሎቱንም በስነ ስርዓት ያናግረን በማለት ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸውን የስር ፍርድ ቤት የመዘገበውን ፍሬ ነገር ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች ፍርድ ቤቱ ፍርድ በሚያነብበት ጊዜ ስነ ስርዓት እንዲይዙ የተነገራቸውን ትዕዛዝ ያለማክበራቸውንና "ፍርድ ቤቱን በስነ ስርዓት ያናግረን" በሚል ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸው የፍርድ ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱን ማወካቸውን የሚያሳይ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 አግባብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 449(1(ሀ)) ድንጋጌ ስር ተጠያቂነት የሚያስከትል ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡በመሆኑም የአመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘትና የሰበር አጣሪ ችሎት ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አሰጣጥ መነሻ የሆኑትን ፍሬ ነገሮችን ሙሉ በሙሉ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተገቢነት የሌለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም አመልካች በገንዘብ መቀጮ እንዲቀየርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የመሰረታዊ ሕግ መመዘኛን የሚያሟላ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ፍርድ እየተነበበ ባለበት ጊዜ የችሎቱን ስነ ስርዓት ባለማክበርና ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸው ተረጋግጦ ፍርድ ቤቱን በመድፈር የተቀጡ በመሆኑ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበበ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ክፍል አራት

## 4.በሕዝብ ደህንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 4.1 ሕግወጥ ጦር መሳሪያን በተመለከተ[64]

- ማንኛዉም ሰዉ የጸና ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማንኛዉንም የጦር መሣሪያ ከንግድ ሥራ ዓላማ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 256 ስር ከተደነገገዉ ማዕቀፍ ዉጭ በሆነ በሌላ ሀሳብ ወይም ዓላማ ወደ ሀገር ዉስጥ ያስገባ፣ከሀገር ያስወጣ፣ የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ የተቀበለ፣ ያከማቸ፣ የተገለገለ፣ ያሳየ፣ የደበቀ፣ለሽያጭ ያቀረበ ፣ የደለለ፣ የሸጠ፣ የገዛ፣ ያስተላለፈ፣ ያከፋፈለ፣ ያዘዋወረ፣ ያጓጓዘ፣ የሠራ ወይም ያመረተ፣ ያሰለጠነ፣ የጠገነ ወይም ያስወገደ እንደሆነ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚገባዉ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22 ስር በተመለከቱት አግባብነት ባላቸዉ ንዑሳን ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፤[65]

የሰ/መ/ቁጥር 247351

ጥቅምት 05 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነው
በዕዉቀት በላይ
ቀነዓ ቂጣታ
ብርሃኑ መንግሥቱ
ማርታ ተካ

አመልካች፡- አቶ ተመስገን መኮንን - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ - ዐ/ህግ ሞሮዳ ጉሉማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ በጦር መሣሪያ ቁጥጥር እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4/1 እና 22/3 እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 418(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን አተገባበር የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ሲሆን የቀረበውም ክስ አጭር ይዘት - አመልካች የጦር መሣሪያ ቁጥጥር እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4/1 እና 22/3ን በመተላለፍ በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 03 የጨለለቂ መካነ ኢየሱስ ቤተ-ክርስቲያን በሚባል አካባቢ በቀን 28/01/2015 ዓ/ም ከቀኑ 6፡00 አካባቢ በፀጥታ

[64]የሰ/መ/ቁ 247351 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም)
[65]የሰ/መ/ቁ 93173 (ታህሳስ 17 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15

አካላት በተደረገ ብርበራ አንድ ባለ ሰደፍ ክላሽ የመለያ ቁጥሩ TN9199/B68094 የሆነ ከተቆረጠ አንድ ካርታ ጋር፣ሪታይፋለኮን ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ RFLA/ 190308109 ከካርታው ጋር፣ ሪታይፋለኮን ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ RFLA/190321308 ከካርው ጋር፣ 3 ቤልጅግ ሽጉጥ የመለያ ቁጥር የሌለው፣ ሰባራ የሆነ የቱርክ ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ EP171042/54 ከካርታው ጋር፣3 ቤልጅግ ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ 601805 ከካርታው ጋር፣ አስር የካሪቫይን ጥይት እና እስታር ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ HN841993 የሆነ የስር 2ኛ ተከሳሽ ፍቃድ አውጥቶበት ያለው ከመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተገኝቷል የሚል ክስ መስርቶበታል፡፡

የክስ ማመልከቻዉ ለአመልካች እንዲደርሰዉ ተደርጎ ተነቦለት በሰጠዉ ቃል አርሶ አደር ሁኜ ቤቴ እና የሰብል ማሳዬ ስለተቃጠለብኝ የምተዳደረበት አጥቼ ይህንን መሣሪያ ለመነገድ ወይም ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት ገዝቼ ለመሸጥ ብዬ እጄ ላይ ተያዘብኝ እንጂ ለማከማቸት አስቤ አይደለም፡፡እንደ አቃቤ ሕግ ክስ ጥፋት አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ በመቀጠል ሁለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቀርበው የተሰሙ ሲሆን ምስክሮቹ በሰጡት ቃል - በቀን 28/01/2015ዓ/ም ከጧቱ 4፡00 ላይ አዛዦችን የአመልካችን ቤት እንድንበረብር ትዕዛዝ ሰጥቶን ነቀምቴ ከተማ 03 ቀበሌ ሄደን የአመልካችን ቤት በርብረን ስድስት ሽጉጥ አንድ ክላሽ አስራ አራት ጥይት አግኝተን ከአመልካች ጋር ይዘን ፖሊስ ጣቢያ ወስደነዋል፡፡አመልካች አንድ ሽጉጥ ሰው ነው እኔ ጋር ያስቀመጠው ብሎ ነበር፡፡ ማን እንደሆነ አልነገረንም፡፡በሌላ በኩል የዐቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር አመልካች እነዚህን የጦር መሣሪያ ነግጄ እተዳደርበታለሁ ብሎ አመልካች ሲናገር እንደሰማ ሲያስረዱ 2ኛ ምስክር ደግሞ እነግዳለሁ ብሎ ሲናገር አልሰማሁም በማለት መስክረዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት አስረድቷል በማለት ፍርድ ቤቱ አመልካች ክሱን እንዲከላከል አዝዟል፡፡

በመቀጠል አመልካች አቅርቦ ባሰማቸዉ ሁለት መከላከያ ምስክሮቹ - አመልካች በፊት የእርሻ ሥራ የነበረው እና አርሶ አደር ሲሆን የእርሻ ሥራው ስለተቋረጠበት ልጆቹን የሚያስተዳድርበትን እና የሚያስተምርበትን ለማግኘት ብሎ እነዚህን የጦር መሣሪያ ጠግኖ ይሸጣል፡፡ለሚ ታደሰ ለሚባል ሰው ሊሸጥለት ተስማምተው በነጋታው ለሚ ፖሊስ አምጥቶ አስያዘው፡፡አመልካች መሣሪያውን ከየት እንዳመጣው አላውቅም፡፡ የንግድ ፍቃድ የለውም ሲሉ መስክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 58936 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 17/05/2015 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች ያቀረባቸው መከላከያ ምስክሮች አመልካች መሣሪያዎቹን ገዝቶ የሚሸጥ መሆኑን በማረጋገጥ ስላልመሰከሩለት አልተከላከለለትም በማለት አመልካች በተከሰሱበት አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22/3 ስር ጥፋተኛ ነዉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡በመቀጠል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ ባስተላለፈዉ የቅጣት ዉሳኔ አመልካች በ5 ዓመት ከ6 ወር ፅኑ አስራት እና በብር 10,000.00 (አስር ሺሕ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 425224 ላይ በቀን 30/05/2015ዓ/ም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት በሰጠዉ ትእዛዝ ተጠሪን ሳያስቀርብ ሠርዞበታል፡፡ በመቀጠልም አመልካች የሰበር አቤቱታዉን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ በመ/ቁጥር 422150 ላይ በቀን 24/06/ 2015 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ሠርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 11/08/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ አጭር ይዘት፡- አመልካች የእምነት ክህደት ቃሌን ስሰጥ ለክሱ ምክንያት የሆነው የጦር መሣሪያ በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ መያዙን ሳልክድ ነገር ግን መሣሪያው ቤቴ ውስጥ ሊያዝ የቻለው መሣሪያውን በማከማቸት ዓላማ ሳይሆን መሣሪያ ለመነገድ ዓላማ መሆኑን ገልጬ ነበር፡፡የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም በወቅቱ መሣሪያውን ለንግድ ዓላማ እንደያዘ ነግሮን ነበር ብለዋል፡፡ያቀረብኳቸው የመከላከያ ምስክሮችም

እነዚህን መሣሪያዎች ለመነገድ ዓላማ እንደያዝኳቸውና 1ኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር በመጀመሪያ ቀን ማስረጃዎቹን ለመግዛት ተነጋግሮ በሁለተኛው ቀን ፖሊሶችን ይዞ መጥቶ እንዳስያዘኝ ተናግሯል፡፡ በመሆኑም መሣሪያዎቹ በእጄ የተገኙት በመነገድ ዓላማ ስለመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22/1 በጦር መሣሪያ መነገድ ወንጀል በሚመለከት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 481 የተጠበቀ ስለመሆኑ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ከዚህ የሕግ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ሰው የጦር መሣሪያ ያለ ሕጋዊ ፍቃድ ይዞ ቢገኝ የሚጠየቅበት የሕግ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22/3 ስር ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 481 ስር መሆን የሚገባው እንደሆነ ነው፡፡ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብዬ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ሊወሰንብኝ ሲገባ ከተፈፀመው ድርጊት ጋር አግባብነት በሌለው በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22/3 ስር የጥፋኝነት ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ ይታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡ ችሎቱ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22/1 ስር በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 481 ስር በጦር መሣሪያ ስለመነገድ የሚደነግገው ድንጋጌ እንዳልተሸረ ተደንግጓል፡፡በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 481(1/ሀ) ስር በሕጉ አንቀፅ 256 ስር ከተደነገገው አግባብ ውጪ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማናቸውም አይነት የጦር መሣሪያዎች ፈንጆች ወይም ጥይቶች በመነገድ ዓላማ የገዛ ያስቀመጠ ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ በድንጋጌው ላይ በተመለከተው መሰረት እንደሚቀጣ ደንግጓል፡፡አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4/1 እና 22/3 እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 418/1/ሀ ተደንግጓል፡፡ በድንጋጌዎቹ የተጠቀሱትን የጦር መሣሪያዎች መግዛት መሸጥ የወንጀል ተጠያቂነትን አስከትሎ የሚያስቀጣበትን አግባብ እና የሁለቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ አፈፃፀም ለመለየት እንዲሁም አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባው በየትኛው ድንጋጌ ነው የሚለውን ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ተጠሪ መልሱን እንዲሰጥ አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 22/12/2015ዓ/ም በተጻፈ መልሱ - አመልካች በክሱ ውስጥ የተጠቀሱ የጦር መሣሪያዎችን በሕግ ፊት የፀና ፍቃድ ሳይኖረው አከማችቶ የተገኘ መሆኑን አቃቤ ሕግ በማስረጃ አረጋግጧል፡፡አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 35 መሰረት ስለ ወንጀሉ አፈፃፀም ቃል ሲሰጥ የተጠቀሰውን ብዛት ያለው የጦር መሣሪያ በቤቱ ውስጥ መገኘቱን አምኗል፡፡የቀረቡት የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በአመልካች ቤት የተገኘው የጦር መሣሪያዎች አመልካች በሕግ ፊት የፀና ፍቃድ ሳይኖው አከማችቶ የተገኘ መሆኑን እንጂ ለንግድ አላማ የጦር መሳርያ እንዳልያዘ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካችን በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23/3 ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ቅጣት በመወሰናቸዉ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች እና የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን እኛም ከፍ ሲል የተያዙትን ጭብጦች መሠረት በማድረግ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም በክሱ የተጠቀሱትን የጦር መሣሪያዎች አመልካች በቤቱ ዉስጥ ይዞ የነበረ መሆኑ በአመልካች የታመነና በማስረጃም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉ እና የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሹ ነጥቦች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 እና የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23/3 አንድነትና ልዩነት ምንድን ናቸዉ? የእነዚህ ድንጋጌዎች ተግባራዊ አፈጻጸም ምንድን ነዉ? እንዲሁም አመልካች በፈጸመዉ ድርጊት ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ በየትኛዉ ድንጋጌ ነዉ? የሚሉ ናቸዉ፡፡

በመጀመሪያም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 እና በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23/3 አንድነትና ልዩነት ምንድን ናቸዉ? እንዲሁም የእነዚህ ድንጋጌዎች ተግባራዊ አፈጻጸም ምንድን ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ ይህንን ነጥብ የክርክር ጭብጥ ማድረግ ያስፈለገዉ ከጦር መሣሪያ ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን ወንጀል አድርገዉ የሚደነግጉ ሁለት ሕጋት በመኖራቸዉ ምክንያት ነዉ፡፡የመጀመሪያዉ

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 ስር ስለጦር መሣሪያ መነገድ የተደነገገዉ ሲሆን ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር የተያያዘዉ ንዑስ አንቀጽ ይዘት የሚከተለዉ ነዉ፡፡

<u>አንቀጽ 481 በጦር መሣሪያ መነገድ</u>

ንዑስ አንቀጽ (1/ሀ) — "*ማንም ሰዉ መንግሥትን አደጋ ላይ ስለመጣል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 256 ስር ከተደነገገዉ አግባብ ዉጭ ፡- ሀ/ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማናቸዉንም አይነት የጦር መሣሪያዎች፣ፈንጂዎች፣ወይም ጥይቶች በመነገድ ዓላማ የሠራ፣ከዉጭ አገር ያስመጣ፣ወደ ዉጭ አገር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ የገዛ፣ የተቀበለ፣ ያስቀመጠ፣ ያከማቸ፣የደበቀ፣ለሽያጭ ያቀረበ ወይም እንዲዘዋወር ያደረገ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ ፤...የተባሉት ዕቃዎች መወረሳቸዉ ሳይቀር በመቀጮና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ወይም ሁኔታዉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል* " የሚል ነዉ፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ፈቃድ ሳይኖር ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ በመነገድ ዓላማ ማናቸዉንም አይነት የጦር መሣሪያዎች፣ፈንጂዎች ወይም ጥይቶች የሠራ፣ከዉጭ አገር ያስመጣ፣ወደ ዉጭ አገር የላከ...ያስቀመጠ፣ ያከማቸ፣የደበቀ፣ለሽያጭ ያቀረበ... እና በደንጋጌዉ የተጠቀሱትን ሌሎች ተግባራትን መፈጸሙ የተረጋገጠበት ሰዉ በድንጋጌዉ የተመለከተዉ ቅጣት ይፈጸምበታል፡፡ስለሆነም ማንኛዉም ሰዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግነ ተቃራኒ በሆነ አኳኋን በመነገድ ዓላማ ማናቸዉንም አይነት የጦር መሣሪያ በቤቱ ወይም በይዞታዉ ስር በማድረግ ያስቀመጠ፣ያከማቸ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ ሊከሰስና ድርጊቱን መፈጸሙ ሲረጋገጥበት ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችለዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481 መሠረት ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

በሌላ በኩል የጦር መሣሪያ አስተዳደር ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4 እና 22 ስር ከጦር መሣሪያና አጠቃቀም ጋር የተከለከሉና በወንጀል የሚያስጠይቁ ድርጊቶች ተደንግገዋል፡፡ በአመልካች ላይ በተመሰረተዉ የወንጀል ክስ ላይ የተጠቀሱት እና ተያያዥ ድንጋጌዎች በሚከተለዉ መሠረት የተደነገጉ ናቸዉ፡፡

የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 <u>አንቀጽ 4 የተከለከሉ ተግባራት</u>

ንዑስ አንቀጽ 4/1 - "በዚህ አዋጅ መሠረት ከተፈቀደዉ ሰዉ ዉጭ ማንኛዉም ሰዉ - የፀና ፈቃድ ሳይኖረዉ የጦር መሣሪያ ፣የጦር ሜዳ መነጽር፣በጦር መሣሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማንኛዉንም አይነት መነጽር ወይም የጦር መሣሪያ ሲተኮስ ድምጽ ለማስወገድ የሚያገለግል መሣሪያ ወደ ሀገር ማስገባት፣ከሀገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ መገልገል፣ ማሳየት፣ መደለል፣ መሸጥ፣ መግዛት፣ ማስተላለፍ፣ ማዘዋወር፣ ማጓጓዝ፣ ማምረት፣ ማሰልጠን፣ መጠገን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነዉ፡፡"

የአዋጁ <u>አንቀጽ 22 የወንጀል ተጠያቂነት</u>

ንዑስ አንቀጽ 1) "በጦር መሣሪያ መነገድ ወንጀል በሚመለከት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 የተጠበቀ ነዉ፡፡"

ንዑስ አንቀጽ 2) "ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ የተመለከተዉን ክልከላ እና ግዴታ በመተላለፍ የጸና ፈቃድ ሳይኖረዉ የጦር መሣሪያ፣የጦር ሜዳ መነጽር፣በጦር መሣሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማንኛዉም አይነት መነጽር ወይም የጦር መሣሪያ ሲተኮስ ድምጽ ለማስወገድ የሚያገለግል መሣሪያ ወደ ሀገር ያስገባ፣ከሀገር ያስወጣ፣ያስቀመጠ፣ የተገለገለ፣ ያሳየ፣ የደለለ፣ የሸጠ፣ የገዛ፣

*ያጓጓዘ፣ያመረተ፣ያስለጠነ፣የጠገነ ወይም ያስወገደ፣በማናቸዉም መንገድ ያስተላለፈ ወይም የያዘ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ እስከ አስር ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡”*

ንዑስ አንቀጽ 3) “በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተፈጸመዉ ወንጀል ብዛት ባለዉ የጦር *መሣሪያ ሲሆን ቅጣቱ ከስምንት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት* እና ከመቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡”

በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 *መግቢያ* ላይ ይህ አዋጅ ከወጣበት ዓላማዎች ዉስጥ አንዱ በ*ሥራ* ላይ ባሉ ሕጎችና አሠራሮች ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ሕግ መደንገግ እና ወጥነት ያለዉን ሥርዓት መፍጠር እንደሆነ ተመልክቷል፡፡በዚህ መሠረት አስቀድሞ በወንጀል ሕግ ከተሸፈኑ ወንጀሎች መካከል አንዱ ከላይ ይዘቱ የተገለጸዉና በጦር *መሣሪያ* ስለመነገድ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481 የተደነገገዉ ነዉ፡፡በአዋጁ አንቀጽ 22/1 ስር በግልጽ እንደተመለከተዉ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481 የተደነገገዉ በዚህ አዋጅ አልተሻረም፤ ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 22 እንዲተካ አልተደረገም፡፡ይልቁንም ሕግ አዉጪዉ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481 ጸንቶ እንዲቀጥል እና አዋጁ በጦር *መሣሪያ* ከመነገድ ዉጭ የሆኑ ድርጊቶችን ብቻ የወንጀል ተጠያቂነትን እንዲያስከትል መደንገጉን በአዋጁ አንቀጽ 22/1 ስር በግልጽ አቋሙን ገልጿል፡፡

*በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ የጸና ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማንኛዉንም የጦር መሣሪያ ከንግድ ሥራ ዓላማ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 256 ስር ከተደነገገዉ ማዕቀፍ ዉጭ በሆነ በሌላ* ሀሳብ ወይም ዓላማ ወደ ሀገር ዉስጥ ያስገባ፣ከሀገር ያስወጣ፣ የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ የተቀበለ፣ ያከማቸ፣ የተገለገለ፣ ያሳየ፣ *የደበቀ፣ለሽያጭ ያቀረበ ፣* የደለለ፣ የሸጠ፣ የገዛ፣ ያስተላለፈ፣ *ያከፋፈለ፣* ያዘዋወረ፣ ያጓጓዘ፣ የሠራ ወይም ያመረተ፣ ያሰለጠነ፣ የጠገነ ወይም ያስወገደ *እንደሆነ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚገባዉ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22 ስር በተመለከቱት አግባብነት ባላቸዉ ንዑሳን ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡*

ከእነዚህ ድንጋጌዎች አፈጻጸም *ጋ*ር በተያያዘ ሌላዉ ግልጽ መሆን ያለበት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር “በመነገድ ዓላማ” በሚል የተገለጸዉ ሀረግ እንዴት መታየት አለበት የሚለዉ ነዉ፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ለመሆን በመነገድ ዓላማ በድንጋጌዉ ላይ የተጠቀሱት ተግባራት መፈጸም ያለባቸዉ *የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይኖር ወይም ሕግን ተቃራኒ* በሆነ አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡ የንግድ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ አግባብ *ለመነገድ ዓላማ* በድንጋጌዉ የተመለከተዉን ግዙፋዊ ፍሬ ነገር ተፈጽሟል ሊባል የሚቻለዉ ደግሞ *ማንኛዉም ሰዉ ጥቅም ለማግኘት ወይም ትርፍ ለማግኘት ብሎ የሞያ ሥራዉ አድርጎ የጦር መሣሪያ የመሸጥ፣የመግዛት፣የመለወጥ ፣ የማስተላለፍ፣ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ሲፈጽም እና ለዚሁ ተግባር የጦር መሣሪያ የመጠገን፣ የማስቀመጥ እና የማከማቸት ተግባር ሲፈጽም ነዉ፡፡* ከዚህ አግባብ ዉጭ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481(1/ለ) ስር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ሰዉ የመነገድ ዓላማ ሳይኖረዉ ያለፈቃድ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ አግባብ በእጁ የሚገኘዉን ማንኛዉንም የጦር መሣሪያ የሸጠ፣ለሽያጭ ያቀረበ፣ ያስቀመጠ፣ያከማቸ፣የጠገነ እና ሌሎች በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4 ስር የተከለከሉ ተግባራትን የፈጸመ እንደሆነ ተጠያቂ ሊሆን የሚገባዉ ከላይ እንደተገለጸዉ *በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22 ስር በተመለከቱት አግባብነት ባላቸዉ ንዑሳን ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡*

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በክሱ የተጠቀሱትን የጦር መሣሪያዎች በቤቱ ያስቀመጠዉ ወይም ያከማቸዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አመልካች ይህንን ድርጊት የፈጸመዉ በአርሶ አደርነት ሲተዳደር ቤቱ እና የሰብል ማሳዉ ስለተቃጠለበት የሚተዳደርበትን በማጣቱ የጦር መሣሪያ በመነገድ ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት በማሰብ ገዝቶ ለመሸጥ በማሰብ እንደሆነ በመግለጽ በክሱ ላይ

የተገለጸዉን ወንጀል ለመፈጸም አስቦ እንዳላከማቸ በመግለጽ ክዶ ተከራክሯል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ቃል የሚያሳየዉ በክሱ የተጠቀሱት የጦር መሣሪያዎች በአመልካች ቤት ዉስጥ ተቀምጠዉ መገኘታቸዉን ሲሆን ይህም በአመልካች የተካደ አይደለም፡፡ይልቁንም የዐቃቤ ሕግ አንድ ምስክር አመልካች መሣሪያዎቹን በቤቱ ያስቀመጠዉ ለመነገድ ዓላማ እንደሆነ ከአመልካቹ መስማቱን መመስከሩ እና አመልካች ክሱን እንዲከላከል ከታዘዘ በኋላ አቅርቦ ባሰማቸዉ ምስክሮች አመልካች በፊት የእርሻ ሥራ የነበረው እና አርሶ አደር ሲሆን የእርሻ ሥራው ስለተቋረጠበት ልጆቹን የሚያስተዳድርበትን እና የሚያስተምርበትን ለማግኘት ብሎ እነዚህን የጦር መሣሪያ ጠግኖ እንደሚሸጥ ፤ለሚ ታደሰ ለሚባል ሰው ሊሸጥለት ተስማምተው በነጋታው ይህ ለሚ የተባለዉ ሰዉ ለፖሊስ ጠቁሞ እንደአስያዘዉ መስክረዋል፡፡ ይህ ምስክርነት ቃል በድምሩ ሲታይ አመልካች በቋምነት የሚተዳደርበትን የአርሶ አደርነት ሥራዉን በመተዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ለሕግ ተቃራኒ በሆነ አግባብ ጥቅም ወይም ትርፍ ለማግኘት በማሰብ ተጠቃሾቹን የጦር መሣሪያዎች እየገዛ እና እየጠገነ ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ወስጥ መግባቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካች የተከሰሰበትን ድርጊት የፈጸመዉ የሙያ ሥራዉ አድርጎ በተጠቀሱት የጦር መሣሪያዎች የመነገድ ድርጊት መፈጸሙን የሚያሳይ ነዉ፡፡

በመሰረቱ በአገራችን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መሰረት ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን በማድረግ የሚፈጸም የወንጀል ድርጊት ወይም አል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በሚያሟላ አኳኋን መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ እና አግባብነት ባለዉ ሌላ ሕግ የተደነገገዉን ቅጣት መቀጣት ይገባዋል፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ደርጊት ተጠያቂ የሚሆነው የተከሰሰበትን ድርጊት ወንጀል አድርጎ በሚደነግገዉ ሕግ ላይ በተመለከተዉ መሠረት ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት መፈጸሙ በማስረጃ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 58 እና 59 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ መልኩ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለዉ በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በሚያሳይ አኳኋን በማስረጃ ሲያስረዳ ነዉ(የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ይመለከቷል)፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች (Principles of Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence) አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standards of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲረጋገጥ፤ በተጨማሪም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን ወይም በምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር በአግባቡ ያላገናዘበ ዉሳኔ ሲሰጡ እና ዉሳኔ የሚሻዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ለሆነ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ ሳይሰጡ ዉሳኔ መስጠት እንዲሁም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰን ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ተገብቷል የሚያስብል ሳይሆን እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 45595፣64813(ቅጽ 12)፣ 225975 ፣228017 (ያልታተሙ) እና በሌሎች መዛግብት ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸዉ አመልካች በክሱ የተጠቀሰዉን ድርጊት የእምነት ክህደት ቃሉን በሠጠበት አግባብ ለመነገድ ዓላማ ሲል እንደፈፈጸመ ባቀረባቸዉ መከላከያ ምስክሮች ከማስረዳቱም በተጨማሪ የዐቃቤ ሕግ አንደኛዉ ምስክርም ይህንኑ በሚያጠናክር አኳኋን መስክረዋል፡፡በአመልካች ስለመፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠዉ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ(የሀሳብ ክፍል)

ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት አመልካች በክሱ የተጠቀሰዉን ድርጊት የፈጸመዉ በጦር መሣሪያ ለመነገድ ዓላማ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ድርጊቱን የፈጸመዉ ለመነገድ ዓላማ ስለመሆኑ በማስተባበል አልተከላከለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ በማስረጃ የተረጋገጠዉን የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 481(1/ሀ) ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን ያላገናዘበ በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 የተደነገገዉን መርህ እና የማስረጃ ምዘና መሠረታዊ መርህ አተገባበር የሚቃረን እንደሆነ አረጋግጠናል፡፡

ሲጠቃለል የንግድ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ አግባብ ማንኛዉም ሰዉ ጥቅም ለማግኘት ወይም ትርፍ ለማግኘት በማሰብ የሞያ ሥራዉ አድርጎ የጦር መሣሪያ የመሸጥ፣ የመግዛት፣ የመለወጥ ፣ የማስተላለፍ፣ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ሲፈጽም እና ለዚሁ ተግባር የጦር መሣሪያ የመጠገን፣ የማስቀመጥ እና የማከማቸት ተግባር መፈጸሙ ሲረጋገጥ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚገባዉ በጦር መሣሪያ ስለመነገድ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር በተደነገገዉ መሠረት ነዉ ብለናል፡፡ አንድ የወንጀል ደርጊት በሕዝቡና በመንግሥት ላይ የሚያደርሰዉን ጉዳት መጠን በማመዛዘን ወንጀሉ የሚያስቀጣዉን ቅጣት በሕግ መደንገግ ሕግ አዉጪ የሆነዉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ፡፡የፍርድ ቤት ተግባርና ኃላፊነት ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት የሕግ ድንጋጌ ላይ የተደነገገዉ ቅጣት መነሻ በማድረግ በወንጀል ሕጉና በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ ላይ የተደነገገዉን የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችንና ደንቦችን በመከተል የቅጣት ዉሳኔ ማስተላለፍ ነዉ፡፡ አመልካች በቋምነት የሚተዳደርበትን የአርሶ አደርነት ሥራዉን በመተዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ለሕግ ተቃራኒ በሆነ አግባብ ጥቅም ወይም ትርፍ ለማግኘት በማሰብ ተጠቃሾቹን የጦር መሣሪያዎች እየገዛ እና እየጠገነ ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ወስጥ መግባቱን ስለተረጋገጠ የፈጸመዉ ድርጊት የሙያ ሥራዉ አድርጎ በተጠቀሱት የጦር መሣሪያዎች የመነገድ ድርጊት መፈጸሙን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር ጥፋተኛ ነዉ ብሎ ቅጣት መወሰን ሲገባዉ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22/3 ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ቅጣት መወሰኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስህተቱን ማረም ሲገባዉ ዉሳኔዉን በትእዛዝ ማጽናቱ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች እንደፈጸመ የተረጋገጠዉ የወንጀል ድርጊት በጦር መሣሪያ መነገድ ወንጀል በመሆኑ በክሱ የተጠቀሰዉን የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4/1 እና 22/3 ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 መሰረት ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 481(1/ሀ) በመለወጥ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 481(1/ሀ) ስር ጥፋተኝ ነዉ ሲል ችሎቱ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ቅጣትን በተመለከተም የወንጀል ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰነዉ በወንጀል ሕጉ ታላቅ ክፍል ስለወንጀል ቅጣት አወሳሰን የተደነገጉ መርሆዎችንና ሁኔታዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣ ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ሕግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተመለከቱትን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን በወንጀል ሕጉ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ ላይ የተመለከተዉ የቅጣት አወሳሳን ደንብ ያሳያል (የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82-88 ይመለከቷል)፡፡በዚህ መሠረት በአመልካች እጅ የተገኙትን የጦር መሣሪያዎች ብዛት ያላቸዉ መሆኑን ከግምት በማስገባት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር ከተደነገጉት አማራጭ ቅጣቶች መካከል ከአስር ዓመት ጽኑ

እስራት የማይበልጥ የሚለዉን የቅጣት አማራጭ ይዘናል፡፡ በመቀጠል ወንጀሉ ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ለቅጣቱ ደረጃ በማዉጣት ደረጃዉን መካከለኛ ደረጃ ላይ በመመደብ መነሻ ቅጣት 5 ዓመት ጽኑ እስራት ይዘናል፡፡ይህም በእርከን 20 ላይ የሚያርፍ ነዉ፡፡ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የቅጣት ማክበጃ እንዳላቀረበ በመገለጹ የስር ፍርድ ቤት ለአመልካች የያዘለትን ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ቅጣቱን ከእርከን 20 ወደ እርከን 17 ዝቅ በማድረግ ችሎቱ በእርከኑ የተመለከተዉን ፍቅድ ሥልጣን ከግምት በማስገባት አመልካችን ያርማል፤ መሰል ወንጀለኞችን ያስጠነቅቃል ብለን ባመንበት በ3 (ሦስት) ዓመት ከ11(አስራ አንድ )ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማሻሻል ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58936 ላይ በቀን 17/05/2015 ዓ/ም የሰጠዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ ፣የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምዕራብ ቋሚ ችሎት በመ/ቁጥር 425224 ላይ በቀን 30/05/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 422150 ላይ በቀን 24/06/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች በጦር መሣሪያ የመነገድ ወንጀል በመፈጸሙ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር ጥፋተኛ ነዉ ብለናል፡፡በዚህ መሠረት አመልካች ከዚህ ወንጀል ጋር በተያያዘ የታሰረበት ካለ የሚታሰብለት ሆኖ በ3 (በሦስት) ዓመት ከ11(አስራ አንድ )ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
3. ከአመልካች የተያዙ የጦር መሣሪያዎች እንዲወረሱ የተሰጠዉ ዉሳኔ አልተነካም፡፡

**ትዕዛዝ**

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ እንዲያዉቁት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡እንዲሁም ማረሚያ ቤቱ በዚህ ዉሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም አመልካች ታስሮ ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት የዉሳኔዉ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡ ሲጠይቁ ግልባጩ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## 5.በሰው ሕይወት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 5.1 የሰው ግድያ[66] (በቸልተኝነት)[67]

- የሰው ግድያ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በአንቀጽ 84 ወይም 86 ስር የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ ተጠቃሹ

[66]የሰ/መ/ቁ 45595 (ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12

[67] በሰ/መ/ቁ 52075 ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም (ቅፅ 12)፣በሰ/መ/ቁ 44235 (መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 12

ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፤ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች በየራሳቸው መቆም የሚችሉ ነጥቦች መሆናቸውን ነው፤[68]

የሰ/መ/ቁጥር - 45595

ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ- አቶ ደሳላኝ ደንገላ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. ኢዮሲያስ አበራ ገ/ሚካኤል-አልቀረበም፡፡-የሁሉም ጠበቃ አቶ ጎበና እጅጉ ቀረቡ

2. ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል ቀረቡ፡፡

3. ወ/ሮ ትርንጎ ወ/ሚካኤል ቀረቡ፡፡

4. አብያለው አበራ ገ/ሚካኤል ቀረቡ፡፡

5. መላኩ ግዛው ማሩ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 54215 ከሆነው ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የሰው ግድያ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ የመሰረተው ክስ ይዘት ሲታይም በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ፣ለ)) እና 539(1(ሀ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ሟች አቶ የማነ መስፍንና ሟች የትናየት ጌቱ ጥር 12 ቀን 1999 ዓ/ም በነገሌ ወረዳ ላንጋኖ በቀለ ሞላ ሆቴል ልዩ መዝናኛ ስፍራ ውስጥ እያሉ 1ኛ ተጠሪ ሟች የትናየት ጌቱ እጮኛዬ ሆና እያለች ከሟች የማነ መስፍን ጋር ወደ መዝናኛ ሥፍራው ሄዳለች በማለት ከሌሊቱ ወደ 6፡00 አከባቢ ሲሆን ከአዲስ አበባ እስከ መዝናኛ ቦታው በመሄድ በዚያው ሆቴል አልጋ በመያዝ ሟቾችን አይቷቸው ከለያቸው በኂላ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር ስማቸው ለተጠቀሱት ተጠሪዎች ደውሎ ሟቾችን መግደል እንደሚፈልግ ነግሯቸው፣እነዚህ ተጠሪዎች በእለቱ ከሌለቱ 8፡00 አከባቢ ላይ

---

[68] በሰ/መ/ቁ 22069 (ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅጽ 7 ፣ በሰ/መ/ቁ 45927 (ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10 ፣በሰ/መ/ቁ 55649 (መጋቢት 06 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ በሰ/መ/ቁ 57446 (ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ በሰ/መ/ቁጥር 90089 (ጥቅምት 20 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ 97203 (መስከረም 30 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 17 ፣ የሰ/መ/ቁ 97203 (መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ. 115419 (ሚያዝያ 24 ቀን 2009 ዓ/ም)፣ በሰ/መ/ቁ 156420 (ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23 ፣ በሰ/መ/ቁ 164030 (ህዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 225558 (ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 219707 (ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 231521 (ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ/ም)፣ የሰ/መ/ቁጥር 245431 (ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 243136 (ሰኔ 26 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ/ 254742 (ሐምሌ 22 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 255633 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም)

ተሰባስበው በመወያየት ሲጓዙ አድረው፣ ጥር 13 ቀን 1999 ዓ/ም ከጥዋቱ 12:30 ሲሆን ወደ ሆቴሉ ሲደርሱ አቶ አበራ ወ/ሚካኤል ፈቃድ ያወጡበትንና ቁጥሩ 678309 የሆነ ኮልት ሽጉጥ ባልታወቀ ሁኔታ ወደ ሆቴሉ በድብቅ ካስገቡና ከ1ኛ ተጠሪ ጋራ ከተመካከሩ በሁዋላ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 1:30 ሲሆን 1ኛ ተጠሪ(ኢዩሲያስ አበራ) ሟቾች ያሉበትን የሆቴሉ አልጋ ቁጥር 9 በአልጋ በኩል ያለውን መስኮት በመስበር በመግባት፣2ኛ ተጠሪ(ለአለም አበራ) ደግሞ በበር ገብቶ 1ኛ ተጠሪ በክሱ በተጠቀሰው ሽጉጥ ተኩሶ ሟቾችን የተለያየ አካላቸውን በመምታት ሲገድላቸው 2ኛ ተጠሪ አብሮ ገብቶ በሃሳብ ሲረዳው የነበረ ሲሆን ከ3ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ደግሞ ወንጀሉ በሚፈጸምበት ወቅት በጋራ እነሱን ልኳቸው የወንጀሉን ውጤት በሆቴሉ ቁጥር 9 እና 8 መካከል ቆመው ሲጠባበቁ የነበሩ ከመሆኑም በላይ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ከሕግ ተጠያቂነት ራሳቸውንም ሆነ 1ኛ ተጠሪን ለማስመለጥ አስበው ወንጀሉ የተፈፀመበትን ሽጉጥ 2ኛ ተጠሪ በሆቴሉ አልጋ ቁጥር 9 ክፍል ውስጥ በጃኬት ጠቅልሎ ይዞ ለ4ኛ ተጠሪ ሲሰጥ ይኸው ተጠሪም ለ3ኛ ተጠሪ በማቀበል በመጡበት መኪና ውስጥ እንዲቀመጥ የደበቁ መሆኑን ዘርዝሮ በአጠቃላይ ተጠሪዎች አስበው፣ተባብረው፤ተረዳድተውና የወንጀሉን ውጤት በመቀበል በቅናት ተነሳስተው ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ሁለት ሰዎችን በግፍ ገድለዋል የሚል ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ሕጉን 808(ሀ) ድንጋጌን በመጣስ የተከሰሰ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ተጠሪዎች ክሱ ደርሿቸው በግልጽ ችሎት ከተነበበላቸውና እንዲረዱት ከተደረገ በሁዋላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ 1ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ መብቱን ጠብቆ የተከራከረ ሲሆን ሌሎች ተጠሪዎች ግን የድርጊቱን አፈጻጸም ክደው ተከራክረዋል፡፡ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎችም ድርጊቱን እንደአቃቤ ሕግ የክስ አመሰራረት ስለመፈፀማቸው በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተረጋግጦባቸዋል ተብሎ እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎችን አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክስ መሰረት የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቶ 1ኛውን ተጠሪ በ18(አስራ ስምንት አመት)፣3ኛዋን ተጠሪ(ትርንጎ ወ/ሚካኤልኝ) ደግሞ በ 15 (አስራ አምስት አመት) ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲወሰን 2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎችን ግን ክሱን ተከላክለዋል በማለት በነፃ አስተናብቷቸዋል፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች በ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ በተሠጠው የቅጣት ውሳኔ፣በሌሎች ተጠሪዎች ላይ የተሠጠው የነፃ መለቀቅ ውሳኔ ላይ እንዲሁም የአሁኑ 1ኛና 3ኛ ተጠሪዎች በጥፋተኝነት ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በተለያዩ መዛግብት አቅርበው ጉዳዩ ከታየ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች እና የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ይግባኝ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ሲሆን የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ይግባኝ ግን ተቀባይነት አግኝቶ ክርክር ከተደረገበት በሁዋላ 3ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀማቸው በሚገባ አልተረጋገጠባቸውም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በነጻ እንዲሰናበቱ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካችና የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው የአሁኑ አመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ የ1ኛ ተጠሪ አቤቱታ ግን ተቀባይነት አግኝቶ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ 1ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙ የተረጋገጠበት ቢሆንም ድርጊቱ ሊሸፈን የሚገባው በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ሳይሆን ተራ የሰው ግድያ ወንጀል በሚያስጠይቅበት ድንጋጌ ነው ተብሎ ድንጋጌው ዝቅ ተደርጎለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በሁዋላ ቅጣቱም 16(አስራ ስድስት አመት) እንዲሆን ተድርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 45595 በሆነው የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው በ1ኛ ተጠሪ ላይ በስር ፍርድ ቤት የተጣለው ቅጣት ተገቢነት የለውም፣ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎችም ከክሱ በነጻ መሰናበታቸው ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 54215 የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘትም

ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድርጊቱ በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 540 የሚሸፈን ነው ተብሎ የተገኘ የፍርድ ቤት ትርጉም ያላግባብ ነው በሚል ነው:: በሁለቱም መዛግብት የቀረቡት የአቃቤ ሕግ የሰበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦች ተመርምረውም በሰበር ችሎት ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው ተብሎ በመታመኑ በተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጠበቃቸው አማካኝነት የተጻፈ የጽሑፍ መልስ አቅርበዋል የመልሳቸው መሰረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሲቀርብ በሁለቱም መዛግብት የተያዙትን ጭብጦች በሚከተለው መልኩ መርምሯቸዋል።

1ኛ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ ድንጋጌና በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የቅጣት መጠን ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ፡-

1ኛ ተጠሪ የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ለ)፣(ሀ)) እና 539(1ሀ) የስር የተመለከተውን በመተላለፍ የትናየት ጌቱ እና የማነ መስፍን የተባሉትን ሰዎች በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ በግፍ ገድሏል በሚል ሲሆን ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ ኃላፊነት የለብኝም፣ ኃላፊነት አለብህ ከተባለም ቅጣትን ሊያቀልሉ የሚችሉ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ የሰው መግደል ወንጀል ሊያስጠይቅ በሚችለው ድንጋጌ መሰረት ነው በማለት መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል። አቃቤ ሕግ በበኩሉ የድርጊቱ አፈፃፀም በቅናት እና በጨካኝነት የተፈፀመ ስለመሆኑ ያሳያሉ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል።1ኛ ተጠሪ ራሱ በሰጠው ቃልም ሆነ በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በፍሬ ነገር የተረጋገጠው ነጥብ የሚያሳየው ሚች የትናየት ጌቱና ተጠሪ ትዳር ሊመሰርቱ ስምምነት ተድርጎ ጋብቻው ሊፈፀም ሶስት ወራት ያህል በቀሩበት ጊዜ ውስጥ ጥር 12 ቀን 1999 ዓ/ም ከሚች የማነ መስፍን ጋር ወደ ላንጋኖ መዝናኛ በመሄድ በመዝናናት ላይ የነበሩ መሆኑን ተጠሪ ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ ሌሊቱን ሄዶ መኖራቸውን አረጋግጦና አጠቃላይ ሁኔታውን ከተመለከተ በሁዋላ በበነጋው ላይ ግን ተጠሪዎችን ከአገኘ በሁዋላ ሚቾች ወደ ተኙበት አልጋ በመስኮት በመግባት ሚቾችን በወቅቱ በያዘው ሽጉጥ ተኩሶ መግደሉ ነው።ተጠሪ ድርጊቱ የተፈፀመው በንዴትና በብሥጭት ነው፣ራሴን ለመከላከል ነው በማለት ያቀረበውን መከራከሪያ ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች ያልተቀበሉት ጉዳይ ሲሆን የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የ1ኛ ተጠሪ ድርጊት በግፍ ሰው የመግደል ወንጀል ሊያቋቁም የሚችል አይደለም ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ ከሚች የትናየት ጌቱ ጋር እጮኛ ሁኖ ጋብቻ ሊመሰርት ሶስት ወር በቀረው ጊዜ ውስጥ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሟ መረጋገጡና ተጠሪ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ላንጋኖ እስኪደርስ ድረስ ሰው ለመግደል ሀሳብ ያለው ስለመሆነ በዐቃቤ ሕግም ሆነ በፈፀመው ድርጊት የተረጋገጠ አይደለም በሚል ምክንያት ነው።

በመሰረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በአንቀጽ 84 ወይም 86 ስር የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች በየራሳቸው መቆም የሚችሉ ነጥቦች ስለመሆናቸው ነው።

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ሚቾችን የገደለው ሚች የትናየት ጌቱ ፍቅረኛው ሁና ለጋብቻ ዝግጅት እየተደረገ ባለበት ጊዜ ከሚች የማነ መስፍን ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ስትፈፅም አረጋግጬአለሁ በማለት ሲሆን ድርጊቱን የፈፀመው ከአዲስ አበባ ወደ ስንጋኖ ሂዶ ሲሆን ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ ሲሄድም የሌላ ሰው መሣሪያ ይዞ መሆኑ፤ላንጋኖ መዝናኛ ሲደርስም ሚቿ ከሌላ ሰው ጋር መሆኗን

ከአዲስ አበባ በሄደበት እለት አረጋግጦ እዚያው ላንጋኖ መዝናኛ አድሮ ጥዋት ላይ የአሁኑ ተጠሪዎች ከቦታው አደረሱለት በሁዋላ ሟቾች ወደ ተኙበት አልጋ በመስኮት ገብቶ ነው፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ ቀድሞውኑም ከአዲስ አበባ ሲነሳና እስከ ላንጋኖ ሌሊቱን በመንዝ ሲደርስ ሰውን ለመግደል ሀሳብና ቅድመ ዝግጅት ያለው ስለመሆኑ በራሱ አረጋጋጭ ሲሆን ይህ ቅድመ ዝግጅቱን አያረጋግጥም ቢባል እንኳ ተጠሪ እዚያው አድሮ ሌሎች ሰዎች ወደ ቦታው ከደረሱ በሁዋላ ድርጊቱን መፈጸሙ ከላንጋኖ መዝናኛ ከደረሰ በሁዋላ ሁኔታውን አይቶና ተገንዝቦ፣አጠቃላይ ሁኔታዉን አውጥቶና አውርዶ ከአሰበና ሊከተል የሚችለውን ውጤት ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ዝግጁ ከሆነ በሁዋላ ሲሆን በቅፅበት ደም ሊያፈላ የሚችል ሁኔታ ሲያልፍና መንፈሱ ሲረጋጋ የፈፀመው ድርጊት መሆኑን የሚያስገነግዝ ነው፡፡እነዚህ ፍሬ ነገሮች 1ኛ ተጠሪ የግድያ ወንጀሉን አስቦበትና ቀድሞ ተዘጋጅቶበት በጭካኔ ወይም በአደገኛነት በተለይም በማንአለብኝነት የፈፀመው ስለመሆኑ ያሳያሉ ከሚባሉ በስተቀር በአለታዊ ፀብ እና አለመግባባት ምክንያት የፈፀመው ድርጊት ነው ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡አንድ ሰው እጮኛው የሆነችውና ጋብቻ ለመፈፀም በዝግጅት ላይ ያለች ሴት ጋብቻው ከመፈፀሙ በፊት ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅማለች ብሎ ከሴቷ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈፀም ነበር ከተባለው ሰው ጋር ይገኙበታል እስከተባለው ቦታ ድረስ ሌሊቱን ረዥም ጉዞ በመንዝ ከደረሰና ሁኔታውን ከተመለከተ በሁዋላ ቀላል የማይባል ሰዓት አሳልፎ ሕግና ሥርዓት ባለበት አገር ሁለት ስዎችን በአንድ ላይ አከታትሎ መግደሉ በማንአለብኝነት፣በቂምና በቅናት መንፈስ ክቡሩን የሰው ሕይወት አጥፍቷል ከሚባል በስተቀር በማናቸውም መመዘኛ ግድያውን ተራ የሰው ግድያ ወንጀል ሊያደርግ የሚችል አይደለም፡፡በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአቃቤ ሕጉ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ማገናዘብ ሲገባው ያለሕጋዊና በቂ ምክንያት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በአቃቤ በኩል ተጠቅሶ የቀረበውን ድንጋጌ መቀየሩ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት 1ኛ ተጠሪ ለፈፀመው የሰው ግድያ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539(1(ሀ)) ስር እንጂ በአንቀጽ 540 ስር ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በ1ኛ ተጠሪ ላይ በወ/ሕ/ቁጥር 539(1ሀ) ስር የሠጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀየረው ያላግባብ ሁኖ ስላገኘነው በ1ኛ ተጠሪ (ኢዮስያስ አበራ) ላይ በወ/ሕ/ቁጥር 540 ስር የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ለውጠን ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539(1ሀ) ስር ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

2ኛ. በሌሎች ተጠሪዎች (ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ በተጠቀሱት) ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ፡-

ሁለተኛ ተጠሪ (ለአለም አበራ) በስር ፍርድ ቤት በነፃ የተሰናበተ ሲሆን ለውሳኔው የስር ፍርድ ቤት መሰረት ያደረገው ምክንያትም ተጠሪው የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ አልተረጋገጠም፣በመከላከያ ምስክርም ወደ ቦታው የሄደበትን ምክንያት አስረድቷል በሚል ምክንያት ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ በአቃቤ ሕግ የተከሰሰው ለ1ኛ ተጠሪ ግብረ አበር በመሆን በድርጊት አፈጻጸሙ ተሳትፏል በሚል ምክንያት ሲሆን በድርጊት አፈፃጸሙ የነበረው ተሳትፎን በተመለከተም ሟቾች ወደ ተኙበት አልጋ 1ኛ ተጠሪ በመስኮት ሲገባ 2ኛ ተጠሪ በአልጋው በር በኩል ገብቷል፣ድርጊቱ ከተፈጸመ በሁዋላም በበር በኩል ወጥቷል በማለት በክሱ ላይ ገልጿል ይህንኑ የተጠሪን የወንጀል ድርጊት ተሳትፎ ለማረጋገጠም የሰው ምስክሮችን ያቀረበ ሲሆን  የአቃቤ ምስክር በወቅቱ በቦታው ላይ የነበረ መሆኑን ገልፆ ሁለት ሰዎች ሲሯሯጡ እንደነበርና አንዱ ሟቾች ወደ ተኙበት አልጋ በበር ሲገባ ሌላው በመስኮት መግባቱን መመልከቱን በአከባቢ ማስረጃነት የመስከረ ሲሆን 3ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር 2ኛ ተጠሪ ሟቾች ከተኙበት አልጋ ውስጥ ጥይት ከተተኮሰ በሁዋላ በበር በኩል ጃኬቱን ይዞ መውጣቱን መስክሯል ሌሎች የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በሰጡት ቃልም 2ኛ ተጠሪ ድርጊቱ በተፈፀመበት ቦታ የነበረ መሆኑንና 1ኛ ተጠሪን ሌሎች ሰዎች ለመያዝ ሲሞክሩም እንዳይያዝና ጉዳት እንዳይደርስበት ጥረት ሲያደርግ የነበረ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ እንግዲህ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነጥብ ሲታይ 2ኛ ተጠሪ

ሚቾች በተገደሉበት ጊዜና ቦታ በመገኘት 1ኛ ተጠሪ በመስኮት ሲገባ እሱ ደግሞ በቤርጎው በር በመግባት ጥይት ከተተኮሰ በሁዋላ እንደገና በቤርጎው በር ሩጦ የወጣና ጃኬትም ለሌላ ሰው ያቀበለ መሆኑ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪን በቦታው የነበሩት ሌሎች ሰዎች ከተኩሱ በሁዋላ ቁም ሲሉትም ይህንኑ ይከላከል የነበረ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ሲታዩ ደግሞ 2ኛ ተጠሪ ሚቾችን ራሱ በቀጥታ ተኩሶ መግደሉ ባይረጋገጥም ሚቾችን ለህልፈት የዳረገውን የተኩስ ተግባር 1ኛ ተጠሪ ሲፈፅም ከዚሁ ተጠሪ ጋር ተባብሮ ሚቾች ወደ ተኙበት አልጋ በበር በኩል መግባቱም ሆነ ከተኩሱ በሁዋላ በበር ሩጦ መውጣቱ በመላ ሀሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሠጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑን የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪን ነጻ ያደረገበት ምክንያት ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አልተረጋገጠም፣በመከላከያም አስረድቷል በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በአግባቡ ባለመያዝ በደፈናው የ2ኛ ተጠሪ የድርጊቱ ተሳትፎ አልተረጋገጠም በማለት ነው፡፡ አንድ ፍርድ ቤት በሕግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎችን ውድቅ ሊያደርግ የሚገባው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነገር ሙሉ በሙሉ በመመዘን እንጂ ከማስረጃዎቹ ውስጥ የተወሰነውን ፍሬ ነገር ብቻ በመያዝ ሊሆን እንደማይገባው ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ ፅንስ ሀሳቦች የሚያስገነዝበን ሐቅ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በ2ኛ ተጠሪ ላይ የድርጊቱን ተሳትፎ አላረጋገጡም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ እንዲከላከል ትዕዛዝ ከሰጠ በሁዋላ ሁሉም የአቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል አንድ ባንድ ባለማየት ነው፡ ተጠሪው በመከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አስተባብሏል የሚለው ድምዳሜም ተጠሪው ወንድሙ የሆነው 1ኛ ተጠሪ ያለበትን ሁኔታ ለማየት ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ መሄዱ ተመስክሯል በሚል ምክንያት ነው፡፡ሆኖም የ2ኛ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ ያረጋገጠው ይኸው ፍሬ ነገር ተጠሪው ላንጋኖ ከደረሰ በሁዋላ የነበረውን የድርጊት ተሳትፎን የሚያስተባብል አይደለም፡፡በመሆነም ሁለተኛ ተጠሪ(ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል) የወንጀል ድርጊቱን በመላ አሳቡና አድራጎቱ የወንጀሉ ድርጊት የሚሰጠውን ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑ በአቃቤ ሕግ የአከባቢና የአይን ምስክሮች ተረጋገጦበት እያለ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው ተጠሪውን የስር ፍርድ ቤት በነጻ ማሰናበቱም ሆነ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች አለመታረሙ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው 2ኛ ተጠሪ ላይ የተሰጠውን የነጻ መለቀቅ ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ለውጠን 2ኛ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ለ)) እና 539(1(ሀ)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

ሌላው በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው የስበር ቅሬታ በ3ኛ ተጠሪ(ትርንጎ ወ/ሚካኤል) ላይ ድንጋጌ ጥፋተኛ በማድረግ በአስራ አምስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ጉዳዩን በይግባኝ የተሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት ነው፡፡የስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ በተከሰሱበት የሕግ የተመለከተው ፍርድ ቤት ደግሞ ተጠሪ በግድያው ወንጀል የነበራቸው ተሳትፎ አልተረጋገጠም በማለት ሙሉ በሙሉ በነጻ እንዲሰናበቱ አድርጓል ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከተው ማስረጃን የመመዘንና ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአቃቤ ሕግን ማስረጃ ዝርዝር ይዘት በመመልከት 3ኛ ተጠሪ በግድያው ወንጀል የነበራቸው ተሳትፎ አልተረጋገጠም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሷል፡፡አቃቤ ሕግ ደግሞ የተጠሪ የወንጀል ተሳትፎ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡ ይሁን እንጂ አቃቤ ሕግ ክሱን ሲመሰርት 1ኛ ተጠሪ ሚቾችን እንደሚገድል ለ3ኛ ተጠሪ ስልክ ደውሎላቸው ይህንኑ ሰምተው ሌሊቱን በመኪና ሲጓዙ አድረው ድርጊቱ ወደተፈጸመበት ቦታ በመድረስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከተመካከሩ በሁዋላ ድርጊቱ መፈፀሙን፣ድርጊቱ ሲፈፀምም በቦታው ላይ 3ኛ ተጠሪ ቁመው ውጤቱን ሲጠባበቁ የነበሩ መሆኑን የጠቀሰ ቢሆንም ይህ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ አለማረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የሚያስገነዝብ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም 3ኛ ተጠሪ ወደላንጋኖ

የሄዱበትን ምክንያትና ከሄዱ በሁዋላ ስለግድያው የነበራቸውን ተሳትፎ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በግድያ ወንጀሉ 3ኛ ተጠሪ ተሳትፎ የነበራቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሷል፡፡ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድምዳሜ የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም አቃቤ ሕግ 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ በከባድ የግድያ ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል በማለት ያቀረበው ቅሬታ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የሚያሟላ ሁኖ ባለማግኘታችን አልፈነዋል፡፡ ሆኖም 3ኛ ተጠሪ ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ የነበሩ፣ተኩስ ከተሰማ በሁዋላም የወንጀል ድርጊቱ ከተፈፀመበት ቤርጎ ውስጥ በሌላ ሰው ወጥቶ የተሰጣቸውን ጃኬት ተቀብለው መኪና ውስጥ በማስገባት ቆልፈው በኋላ መኪናው ተከፍቶ ጃኬቱ ሲታይ ሽጉጥ መገኘቱ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ ሲታይ 3ኛ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ? ወይስ በተረጋገጠባቸው መጠን አግባብነት ባለው የሕግ ድንጋጌ ሊጠየቁ ይገባቸዋል? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡በመሰረቱ አንድ ሰው በአቃቤ ሕግ በኩል የተመሰረተበት ክስ እንደክሱ አመሰራረት ሳይረጋገጥ ቢቀርም የቀረበው ማስረጃ ከቀረበው ክስ ያነሰ የወንጀል ድርጊት በተከሳሽ መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ በተመሰከረበት የወንጀል ድርጊት የማይጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 3ኛ ተጠሪ የግድያ ወንጀል ከተፈጸመ በኂላ ሽጉጡ የተጠቀለለበትንና የተሰጣቸውን የግድያ ወንጀል ከተፈጸመበት ቤርጎ የወጣውን ጃኬት ተቀብለው ከመኪና ውስጥ መደበቃቸው የተረጋገጠ ሲሆን ይህም ወንጀል ከተደረገ በሁዋላ ሆነ ብለው ወንጀል አድራጊው ከመከሰስና ከመቀጣት እንዲያመልጥ የረዱት መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን አድራጎቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 መሰረት በአንቀጽ 445 ስር ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው፡፡በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 3ኛ ተጠሪን በግድያ ወንጀል ሊጠየቁ አይገባም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰበት መንገድ የማስረጃ ምዘና ሁኖ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችል ባይሆንም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ስለመፈፀማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠውንና ወንጅሉ ከተደረገ በኂላ ወንጀል አድራጊውን መርዳትን በተመለከተ የተደነገገውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ 3ኛ ተጠሪን ጥፋተኛ ያለማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል ስለሆነም 3ኛ ተጠሪ በአቃቤ ህግ በኩል ተጠቅሶ የቀረበባቸውን ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113(2)መሰረት በመለወጥ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 ስር የተመለከተውን የተላለፉ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

ሌላው በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ቅሬታ በስር 4ኛ ተከሳሽ(አብያለው አበራ) ላይ የተሰጠውን የነጻ መለቀቅ ውሳኔ የሚመለከት ነው፡፡አቃቤ ሕግ ይህ ተጠሪም በግድያው ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባ መሆኑን ጠቅሶ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት ይህንኑ ተጠሪ ከግድያ ወንጅሉ ያሰናበቱት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመዘን ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደተጠቀሰው ይህ ችሎት በሕግ ከተሠጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በዚህ ረገድ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ይሁን እንጂ 4ኛ ተጠሪ በግድያ ወንጅሉ የነበረው የተሳትፎ ሁኔታ አልተረጋገጠም የተባለው ማስረጃ ተመዝኖ ቢሆንም ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝቶ ድርጊቱ ከተፈጸመበት የቤርጎ ቁጥር ከድርጊቱ በሁዋላ ወዲያውኑ የወጣውንና ድርጊቱ የተፈጸመበት ሽጉጥ መጠቅለሉ የተረጋገጠበትን ጃኬት ድርጊቱ ከተፈጸመበት ቤርጎ ከወጣው ሰው ተቀብሎ ለ3ኛ ተጠሪ መስጠቱ በአቃቤ ሕግ የአይንና የአካባቢ ማስረጃ የተረጋገጠበት ሲሆን ይህንኑ ፍሬ ነገር ላለመቀበል የሚያስችል ምክንያት የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ስለሆነም 4ኛ ተጠሪ( አብያለው አበራ)

ወንጀል ከተደረገ በሁዋላ ወንጀል አድራጊውን በመርዳት ወንጀል መጠየቅ ሲገባው ከዚሁ የወንጀል አድራጎቱ ሁሉ ነፃ መደረጉ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን 4ኛ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 መሰረት ጥፋተኛ ሊሆን የሚገባው ነው ብለናል፡፡

5ኛ ተጠሪን (መላኩ ግዛው ማሩን) በተመለከተ የቀረበውን የአቃቤ ሕግን ቅሬታ ስንመለከተው ደግሞ ይህ ተጠሪ ከድርጊቱ ሙሉ በሙሉ ነፃ የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ከግድያው ባነሰ የወንጀል ድርጊት ሊያስጠይቀው የሚችል የወንጀል ተሳትፎ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት የማያረጋግጥ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

3. ቅጣትን በተመለከተ

1ኛውን ተጠሪ በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ያሉት የበታች ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት የቅጣት መጠን አስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት ነው፡፡አቃቤ ሕግ ይህ ቅጣት ተገቢ ያለመሆኑን በመጥቀስ ለበላይ ፍርድ ቤቶች ይግባኙን ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ሁለት ሰው በግፍ መግደሉ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ)) ስር ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እድሜ ልኩን በፅኑ እስራት ወይም በሞት ነው፡፡ በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ "የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ከታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዝርዝር ያሉ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሳን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2)፡ስር፡የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህን ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤አመዛዝኗልም፡ተጠሪ ሪኮርድ ያልቀረበበት መሆኑም ያለፈ የሕይወት ታሪኩ መልካም የነበረ መሆኑን እንደሚሳይ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82(1(ሀ)) መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሲሆን ከዚህ ውጪ 1ኛ ተጠሪ የተለየና ልዩ የሆነ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የለውም፡፡ የቅጣት መጠኑንም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 179(ሀ) መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪን ተጠያቂ ያደረጉበት ድንጋጌ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገና በምክንያትም የተደገፈ ቢሆንም በቅጣት ረገድ ግን ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሊያስቀጣ

ከሚችለው የቅጣት መጠንና ከቅጣት ዓይነተኛ ዓላማ አንፃር ሲታይ ተገቢ ባለመሆኑ በተጠሪ ላይ የተጣለው የአስራ ስምንት ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችንና የቅጣትን ዓላማ ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ አድራጎት በከባድ የሰው መግደል ወንጀል የሚሸፈንና የቅጣት መጠኑም ከእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሊወርድ የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

3ኛ ተጠሪን በተመለከተ ይህ ችሎት ጥፋተኛ ያደረጋቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 ስር ሲሆን ቅጣቱ ሊተላለፍ የሚገባውም በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሊቀጣ የሚችለው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ነው፡፡ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በማመዛዘን ሲሆን ይህ ችሎትም 3ኛና 4ኛ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ያስመዘገቡትን የቅጣት አስተያየት ከድርጊቱ አፈጻጸም ጋር አገናዝቦ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት 3ኛ ተጠሪ በጉዳዩ የታሰሩት ማንኛውም ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በሶስት አመት ቀላል እስራት ሊቀጡ የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14431 ሚያዚያ 01 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠ ውሳኔ ፣ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 65733 ጳጉሜ 04 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ፣ በዚሁ ችሎት በመ/ቁጥር 64223 ህዳር 02 ቀን 2001 ዓ/ም የተሠጠው ውሳኔ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 31426 የካቲት 18 ቀን 2001 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም በዚሁ ችሎት በመ/ቁጥር 74006 ታህሳስ 19 ቀን 2002 ዓ/ም የተሠጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ (ኢዮስያስ አበራ) ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539(1(ሀ)) ሲሆን ቅጣቱም እድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲሆን ተወስኗል፣3ኛ ተጠሪ የፈጸሙት ድርጊት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 445 ስር የሚሸፈን ሁኖ ቅጣቱን በተመለከተ በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በሶስት አመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስነናል፡፡
3. 5ኛ ተጠሪ (መላኩ ግዛው)ን በተመለከተ በነፃ መሰናበቱ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ቅጣቱ ተሻሽሎ የተወሰነ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
   ከተባለ በኋላ በ2ኛ እና በ4ኛ ተጠሪዎች ላይ ቅጣት ለመወሰን ይቻል ዘንድ የግራ ቀኙኝ የቅጣት አስተያየት በመጠየቅ ግራ ቀኙ ያቀረቡት የቅጣት አስተያየት በመቅረጸ ደምፅ ተቀርጿል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. ግራ ቀኙ ያቀረቡት የቅጣት አስተያየት ከመቅረፀ- ደምጽ ወደ ፅሑፍ ተቀይሮ ከመዝገቡ ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡
2. የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን ለሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ተቀጥሯል፡፡
3. 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችን የአራዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አቀይቶ ለሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ችሎት እንዲያቀርባቸው ታዝዟል፡፡ ማሰሪያ ዋራንት ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 5.2 ተራ የሆነ የሰው ግድያ[69]

- ድርጊቱ አስቀድሞ ያልታቀደ እና መነሻውም የሟች ስድብ መሆኑ የወንጀል ድርጊት አፈጻጸሙም በተመለከተ ጨካኝ ወይም ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ የተፈጸመ ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ድንጋጌ መሠረት እንጂ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539/1(ሀ) ስላለመሆኑ፤

የሰ/መ/ቁ - 235944

ሰኔ 29 ቀን 2015 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዓቃቤሕግ - ዓቃቤሕግ እጸገነት ሀይሉ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አልፊያ አመድ ኡስማን - ጠበቃ ፍቃዱ ዘነበ ቀረቡ

2. ቱርኪ ሰይፌ በከር - ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ የሰበር አቤቱታው ተቋርጧል

3. መርዋን ቱርኪ ሰይፌ- ጠበቃ ፍቃዱ ዘነበ ቀረቡ

4. ነስረዲን ቱርኪ ሰይፌ - 4ኛ ተጠሪን በሚመለከት የሰበር አቤቱታው ተሰርዟል

5. ሳዳም ሻሜ አመድ - በሌለበት

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 06038 ሠኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00370 መስከረም 26 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

አመልካች በአሁን ተጠሪዎች ላይ በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪዎች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) እና 539/1(ሀ) ድንጋጌን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን ቂም በመያዝ በሐረሪ ክልል ድሬ ጠያራ ወረዳ ሐሰንጌይ ቀበሌ ገበሬ ማሕበር ውስጥ ልዩ ስሙ አስበለ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ ጥር 20 ቀን 2012 ዓ.ም ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ 1ኛ ተጠሪ ሟች ዱጉምሳ አመድ ን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ተጠሪዎች እንዲገድሉት ጥሪ በማድረግ እና ታፋው ላይ በቢላዋ በመውጋት በቦታው ላይ እንዲሰባሰቡ በማድረግ እና በማነሳሳት፤ ሁለተኛ ተጠሪ ሟችን በሜንጫ በማባረር እና ጭንቅላቱን በመምታት፤ ሶስተኛ ተጠሪ ሟችን የግራ ጎኑን በመውጋት፤ 4ኛ ተጠሪ ሟችን ሆዱን በሜንጫ በመውጋት፤ 5ኛ ተጠሪ

[69]የሰ/መ/ቁ 235944 (ሰኔ 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ ከላይ በሰው ግዲያ አርስት ስር በግርጌ ማስታወሻ የተዘረዘሩት መዛግብት ይመለቱታል፡፡

ሟችን ግራ ትከሻ በሜንጫ በመውጋት ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ሙሉ ሰውነቱ ላይ ጉዳት አድርሰው የሆድ ዕቃው ተዘርግፎ እንዲሞት በማድረጋቸው በፈጸሙት ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ 4ኛ ተጠሪ ጉዳዩ በሌለበት የታየ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበልን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡

1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ በተመሰከረባቸው ልክ እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎችም መከላከያ ምስክሮቻቸውን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመር በኋላ የተጠሪዎች ምስክሮች መርዋን ቱርኪ ሟችን በሜንጫ ሆዱን ወግቶ ገድሎታል ቀሪ ተጠረዎች በቦታው አልነበሩም በማለት የመሰከሩ ቢሆንም ተጠሪዎችን ነጻ ለማውጣት ሲባል የተሰጠ የምስክርነት ቃል እንጂ በዓቃቤሕግ በኩል የቀረበባቸውን ቀጥተኛ የዓይን ማስረጃ ማስተባበል የሚችል አይደለም በማለት በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ብሎ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው በአስራ ሰባት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋለ 1ኛ ተጠሪ ሟችን ታፋው ላይ ወጋችው ተብሎ የተመሰከረ ቢሆንም በሕክምና ማስረጃው ላይ ያልተገለጸ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ መካለከል ሳያስፈልጋት በነጻ ልትሰናበት ይገባል፣ በ2ኛ ተጠሪ ምክንያት በሟች ላይ የደረሰው ጉዳት 1 ሲ.ሜ በ 1 ሴ.ሜ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2 ድንጋጌ መሠረት ነው፣ 2ኛ ተጠሪ ከቢቂ በላይ የታሰረ በመሆኑ እስራቱን ጨርሷል፣ 3ኛ ተጠሪ በሜንጫ የሟችን ሆድ በመምታት የሆድ ዕቃውን እንዲወጣ በማድርግ ደም እንዲፈሰው ያደረገ ቢሆንም ለጸቡ መነሻ የሆነው የሟች ስድብ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ድንጋጌ ነው በማለት በስድስት ዓመት ከሰባት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ፣ 5ኛ ተጠሪን በሚመለከት በሜንጫ ደፍካ እንጨት የሟችን የግራ እጁን በመምታ ድርጊቱን የፈጸመ እና ያደረሰውም ጉዳት 2 ሴ.ሜ በ 2 ሴ.ሜ ቁስለት መሆኑ በሕክምና የተረጋገጠ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2 ነው የታሰረው በቂ ነው በማለት ወሰኗል፡፡

አመልካች በበኩሉ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታውወተ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ወሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ጉዳዩ የቀረበለት ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ የ17 ዓመት ጽኑ እሥራት ያስተላለፈ ቢሆንም በውሳኔው ላይ ጉልህ የሆኑ ክፍተቶች አሉት፣ ዓቃቤሕግ ያቀረባቸው ሁለት የሰው ምስክሮች ቃል በአግባቡ ሳያሰፍር በዓቃቤየሕግ ምስክሮች ፊንታ የመከላከያ ምስክሮችን ቃል በማስፈር ዓቃቤሕግ ሁለት ምስክሮችን ያቀረበ ቢሆንም አንድ ምስክር ብቻ እንዳቀረበ በመቁጠር የዚሁ ምስክር ቃል እንኳን በአግባቡ ሳይጻፍ ውሳኔ ሰጥቷል፣ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስህተቱን አስተካክሎ ከሕክምና ማስረጃው ጋር አገናዝቦ እንዲወስን ብንጠይቅም ተመሳሳይ ስሕተት ፈጽመዋል፣ የተጠሪዎች ድርጊት ጭካኔ የተሞላበት ሆኖ ሳለ ድንጋጌው በመቀየር የተላለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ አይደለም፣ በጊዜው በተፈጠረ ጸብ የተፈጸመ ድርጊት ሳይሆን ታስቦበት የተፈጸመ የጭካኔ ሰው ግድያ ወንጀል ነው፣ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪን በነጻ በማሰናበት፣ 2ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2 ጥፋተኛ በማለት፣ 3ኛ ተጠሪን ደግሞ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ድንጋጌ ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች በአሁን ተጠሪዎች ላይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1ሀ እና 539/1/ሀ ድንጋጌን ተላልፈው ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል መፈጸማቸውን በመግለጽ ያቀረበውን ክስ የስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪን በነጻ ማሰናበቱ፤ 2ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) ጥፋተኛ ማለቱ፤ 3ኛ ተጠሪን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ጥፋተኛ በማለት የመወሰኑን አግባብነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎ በሰ.መ.ቁ 89676 የማስረጃ ምዘና መርሆዎች አስመልክቶ ከሰጠው ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ሒደት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑ ስለተገለጸ 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቋርጧል፡፡ 4ኛ ተጠሪን በሚመለከት በስር ይግበኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ስለሌለ ይህ ችሎት በ4ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ቀሪ አድርጎታል፡፡ 5ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ስላልቀረበ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቀን 11/07/2015 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ምስክሮቹን በሚመለከት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ቅሬታ የለም፤ ስለሆነም የምስከር ቃል በአግባቡ አልተመዘነልኝም በማለት ያቀረበው ክርከር ተገቢነት የለውም፤ ማስረጃ ምዘንን በሚመለከት የሚቀርብ ቅሬታን ሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀይር አይገባም፤ ዓቃቤሕግ ያቀረባቸው ምስክሮች እንደክስ አቀራረቡ አላስረዱም፤ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱን መዝገብ አስቀርቦ በሚገባ ተመልክቶ የተፈጠረውን የማስረጃ ምዘና ስሕተት በማረም መወሰኑ የሚያስተቸው አይደለም፤ ስለሆነም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለሰጡት መልስ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡ የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ 1ኛ ተጠሪን በነጻ በማሰናበት በስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት አጥብቆ የሚከራከረው 1ኛ ተጠሪ ድርጊቱን ስለመፈጸምዋ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ከሕክምና ማስረጃው ጋር በአግባቡ አልተመዘነም፤ ሁለት ምስክሮች አቅርነብ ሳለ አንድ ምስክር ብቻ እንዳቀረብን ተቆጥሯል በሚል ነው፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ የሚከረከር ቢሆንም የስር ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው 1ኛ ተጠሪ ሟችን ታፋው ላይ ወግታዋለች ተብሎ በክሱ አቤቱታው ላይ የተገለጸ እና ምስክሮችም ይህንኑ በመግለጽ የመሰከሩ ቢሆንም የቀረበው የሕክምና ማስረጃ ሟች ታፋው ላይ እንደተወጋ የማያሳይ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከቀረበባት ክስ በነጻ ልትሰናበት ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ይህም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተሰጠው ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን መሠረት ዓቃቤሕግ ያቀረባቸው የሰው ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ከሕክምና ማስረጃው ጋር በማገናዘብ መዝኖ ምስክሮቹ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ውድቅ ያደረገው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ሟችን ታፋው ላይ በቢላዋ ወግታለች በማለት የዓቃቤሕግ ምስክሮች ያስረዱ ቢሆንም የቀረበው የሕክምና ማስረጃ ይህን የማሳያሳይ መሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባለው የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተረጋገጠ

በመሆኑ ይህንኑ መሠረት በማድረግ 1ኛ ተጠሪን ከቀረበባት ክስ በነጻ በማሰናበት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በሌላ በኩል የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ድንጋጌ፣ 5ኛ ተጠሪ ደግሞ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) ድንጋጌ መሠረት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ዓቃቤሕግ በተከሳሾች ላይ በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) እና 539/1(ሀ) ድንጋጌን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን ቂም በመያዝ 1ኛ ተጠሪ ሟች ዱጉምሳ አመድ ን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ተጠሪዎች እንዲገድሉት ጥሪ በማድረግ እና ታፋው ላይ በቢላዋ በመውጋት በቦታው ላይ እንዲሰባሰቡ በማድረግ እና በማነሳሳት፣ ሁለተኛ ተጠሪ ሟችን በሜንጫ በማባረር እና ጭንቅላቱን በመምታት፣ ሶስተኛ ተጠሪ ሟችን የግራ ጎኑን በመውጋት፣ 4ኛ ተጠሪ ሟችን ሆዱን በሜንጫ በመውጋት፣ 5ኛ ተጠሪ ሟችን ግራ ትከሻ በሜንጫ በመውጋት ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ሙሉ ሰውነቱ ላይ ጉዳት አድርሰው የሆድ ዕቃው ተዘርግፎ ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርገዋል በሚል ነው፡፡

በወንጀል አፈጻጸም ላይ ተካፋይ ስለመሆን በሚመለከት በወንጀል ሕጉ ላይ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ውስጥ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ ስለመሆን አስመልክቶ የተደነገገው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1/ሀ ድንጋጌ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥቶ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር በተለይም በእንስሳት ወይም በተፈጥሮ ሀይል አማካይነት በእርግጥ ወንጀሉን አድርጎ እንደሆነ ነው፡፡

በሌላ በኩል በያዝነው ጉዳይ 3ኛ ተጠሪ በሜንጫ የሟችን ሆድ በመምታት የሆድ ዕቃውን እንዲወጣ በማድርግ ደም እንዲፈሰው ያደረገ ቢሆንም ለጸቡ መነሻ የሆነው ሟች አጸያፊ ስድብ በመሳደቡ ምክንያት መሆኑ እና ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ድርጊቱ አስቀድሞ ያልታቀደ እና መነሻውም የሟች ስድብ መሆኑ የወንጀል ድርጊት አፈጻጸሙም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539/1(ሀ) በተመለከተው ሁኔታ ጨካኝ ወይም ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ የተፈጸመ ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ በማለት በሰጠው ወሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በሌላ በኩል ዓቃቤሕግ ክስ የመሰረተው የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) በመጥቀስ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን የሟችን የተለያየ የሰውነት አካል በሜንጫ በመውጋት ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርገዋል በሚል ነው፡፡ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬነገር 5ኛ ተጠሪ የሟችን ግራ ትከሻ በሜንጫ በመውጋት በሟች ላይ 2 ሴ.ሜ በ 2 ሴ.ሜ የሆነ ጉዳት እንዳደረሰ እስከተረጋገጠ ድረስ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1(ሀ) እና 540 ድንጋጌ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 5ኛ ተጠሪ በሟች ላይ ያደረሰው ጉዳት 2 ሴ.ሜ በ 2 ሴ.ሜ ስለሆነ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 556(2) ድንጋጌ መሠረት ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በ5ኛ ተጠሪ ላይ ቅጣቱን እንደሚከተለው አስልተናል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ደረጃ እና እርከን የወጣለት ነው፣ ለወንጀል ድርጊቱ መፈጸም ሟች አጸያፊ ስድብ በመሳደቡ እና 5ኛ ተጠሪም ድርጊቱን የፈጸመው አደገኛ ሊባል በሚችል መሣሪያ / ሜንጫ / በመሆኑ የወንጀል ደረጃው ደረጃ ሶስት የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ደግሞ እርከን 25 ተይዟል፣ በስር ፍርድ ቤት የተያዘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፣ 5ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኙ ሶስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ስላሉት ቅጣቱ ሲቀል በእርከን 22 ላይ ያርፋል፣ በእርከን 22 ያለው ፍቅድ ስልጣን ከአምስት ዓመት ከስድስት ወር እስከ ስድስት ዓመት ከሰባት ወር ነው፣ ስለሆነም በዚህ እርከን ስር 5ኛ ተጠሪን

ያርማል ሌሎችንም ያስጠነቅቃል በማለት በአምስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 06038 ሠኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም 1ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪን በሚመለከት የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00370 መስከረም 26 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
- ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት 5ኛ ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 መሠረት ነው በማለት በአምስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የውሳኔ ክፍል አልተነካም

ትዕዛዝ

- የፌዴራል ፖሊስ እና የክልሉ ፖሊስ 5ኛ ተጠሪን አፈላልጎ በመያዝ ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ፣ የሚመለከተው ማረሚያ ቤትም በዚህ ውሳኔ መሠረት በ5ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ላይ የተላለፈውን ቅጣት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ በዚሁ መሠረት ማስፈጸም ይቻለው ዘንድም የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ እንዲደርሰው ታዟል፡፡
- የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ እንዲደርሳቸው ታዟል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 5.3 የሰው ግድያ ወንጀል -ሕጋዊ መከላከል[70]

- ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ አስቦ ሰውን የገደለ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 541(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው ስለመሆኑ::[71]

የሰ/መ/ቁ. 117335

የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም

**ዳኞች** - ዓሊ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀንአ ቂጣታ

አይሸሽም መለሰ

ፀሐይ መንክር

[70]የሰ/መ/ቁ 117335 (የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም)

[71]ሕጋዊ መከላከልን በሚመለከት ሰ/መ/ቁ. 86570 (ሚያዝያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ.226650 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)

**አመልካች** - አቶ ገብረሂወት ብርሃነ       የቀረበ የለም

**ተጠሪ** - የትግራይ ብ/ክ/መንግስት - ዓቃቤ ህግ  የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል ፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የወንጀል ክስን የሚመለከት ሲሆን ዓቃቤ ህግ በአመልካች እና ሌሎች ሶስት ተከሳሾች ላይ በትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ የጉዳዩ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘት ተከሳሾች በወ/ህ/ቁ 32(1)(ሀ) እና 539(1)(ሀ) ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ከምሽቱ 4፡00 እስከ 5፡00 ሰዓት ሲሆን ጨለማን ተገን በማድረግ በወረዳ ናዕዴር ዓዴት ጣብያ ላዕላ ህዱግ ቁሸት ዓድጉምቦ ጫሞ በተባለ ቦታ አመልካች ከሥር 2ኛ ተከሳሽ ታደሰ ገ/ክርስቶስ ቁጥሩ 650809 የሆነ ክላሽ ጠመንጃ ተቀብሎ አስቀድሞ ቆርቆሮ ደብድቦብኛል በሚል ቂም ተነሳስቶ ከተኮሳቸው 5(አምስት) ጥይቶች በአንድ ጥይት ቀኝ ሽንጡ ላይ በመምታት ሟች ነጋሲ ብርሃነን በመግደሉ፤ 2ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካችን በያዝከው በለው ተገናኝንተናል በማለቱ እና ሚሊሻ ሆኖ ጠመንጃውን ለአመልካች አሳልፎ በመስጠቱ፤ 3ኛ ተከሳሽ ቄ/ቀለም ታደሰ እና 4ኛ ተከሳሽ ገ/ዋህድ በየነ በለው ይህን ጨምላቃ በማለት በተግባር እና በሃሳብ ባደረጉት ተሳትፎ በአባሪነት በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው የዕምነት ክህደት ቃል ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር የጥበቃ ሥራ ተረኛ ሁነን በጥበቃ ላይ እያለሁ የምጠብቀውን የመንግስት ንብረት እና ጠመንጃየን ሊነጥቁኝ መጥተው ሟች ጠመንጃየን ከያዘው በኂላ ስንነጣጠቅ ጥይት ተተኩሶ ሟች ተመትቶ ወድቋል፤ ወንጀል አልፈፀምኩም ጥፋተኛም አይደለሁም ብሏል፡፡ ቀሪዎቹ ተከሳሾችም ክደው ተከራክረዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ህግ ምስክሮችን ቃል እና የሰነድ ማስረጃውን ፤ እንዲሁም የመከላከያ ምስክሮችን ቃልና በመከላከያነት የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ መርምሮ ከ2ኛ እስከ 4ኛ የተመለከቱት ተከሳሾች በነፃ እንዲሰናበቱ የወሰነ ሲሆን፤ አመልካችን በተመለከተ ድርጊቱን ፈፅሟል ነገር ግን የወንጀሉ አፈፃፀም ሲታይ ጥበቃ ሆነው በሚጠብቁበት ድርጅት አካባቢ የጥበቃ ስራቸውን እያከናወኑ እያሉ የተፈፀመ ለመሆኑ ለመረዳት የተቻለ በመሆኑና ይህ ደግሞ ሆነ ብለው የግድያ ወንጀል ለመፈፀም አስቀድሞ ከነበራቸው ሃሳብ ቆርቆሮየ ተመቶብኛል ከሚል ሳይሆን በድንገት በሚጠብቁት ድርጅት ያጋጠመ መሆኑን ስለሚያሳይ የተከሰሰበት የወ/ህ/ቁ 539(1)(ሀ) በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 113(2) መሰረት ተቀይሮ በወ/ህ/ቁ 540 ሥር የተመለከተውን የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም ዓቃቤ ህግ በቅጣት ማክበጃነት የሚያቀርበው እንደሌለ የገለፀ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው ሟች ከሶስት ሰዎች ጋር በመሆን አመልካች ጥበቃ በሚያካሂዱበት የመንግስት ንብረት ወደሆነው ድርጅት በመሄድ ጠብ ፈጥረው አመልካችን በድንጋይ ሊመቱ መጋበዛቸው፤ ማንገላታታቸው፤ አመልካች ወደ ላይ በመተኮስ ሊከላከሉ ቢሞክሩም በመጨረሻ ሟች ጠመንጃውን በመያዝ ለሞቱ ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ፤ የቀደመ ሪከርድ ባለመቅረቡ፤ በብርቱ ፈተና ላይ የወደቁ በመሆኑ፤ በህይወታቸው እና በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስቀረት የፈፀሙት ተግባር በመሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ እና በትግል ወቅት በደረሰባቸው ጉዳት የህክምና ክትትል በማድረግ ላይ ስለሆናቸው በማቅለያነት እንዲያዙላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በቅጣት ረገድ የቀረበውን ክርክር መርምሮ የወንጀል አፈፃፀሙን በማየት በማንዋሉ በደረጃ 6 እርከን 33 ላይ መነሻ ቅጣቱ ያርፋል፤ በማቅለያነት ያለፈ ፀባያቸው ጥሩ መሆኑ ብቻ በወ/ህ/ቁ 82(1)(ሀ) እንደ አንድ ማቅለያ ሊያዝ ይገባል፤ አመልካች ያቀረባቸውን ሌሎች ማቅለያዎች ግን ችሎቱ አልተቀበላቸውም በማለት አንድ እርከን ዝቅ ብሎ በእርከን 32 ከተመለከተው ፍቅድ ስልጣን በ14 (አስራ አራት) ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ሚችና የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ከለሊቱ 5:00 ሰዓት በምጠብቀው ድርጅት በጥበቃ ሥራ ላይ እያለሁ መጥተው በድንጋይ ሊመቱኝ በተለይም ሚች ጠመንጃየን ሊነጥቁኝ በመሞከሩ ስርዓት አድርጉ እያልኩ ወደኃላ እየሄድኩ አራት ጊዜ ወደ ሰማይ ብተኩስም ሚችና ምስክሮቹ ያዘው እንዳትለቀው እያሉ ስለተከተሉኝ በእኔ እና በምጠብቀው ድርጅት ጉዳት እንዳያደርሱ ያደረኩት ህጋዊ መከላከል በመሆኑ፤ ከመጠኑ አልፏል የሚባል ቢሆን እንኳን ጥፋተኛ ልሆን የሚገባኝ በወ/ህ/ቁ 541 ነው ተብሎ ውሳኔው ይታረምልኝ፤ ይህም ቢታለፍ ጠብ አንሻዎቹ ሚች እና የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ስለሆኑ መነሻ ቅጣቱ በደረጃ 6 እርከን 33 ይወድቃል መባሉ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ቅሬታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቢያቀርብም ቅሬታው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ሃምሌ 27/2007 ዓ.ም የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በሥራ ላይ ባለበት በተከሰተው የወንጀል ተግባር ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወ/ህ/ቁ 540 ነው ወይስ 541 የሚለውንና ይህ ቢታለፍ አመልካች ያቀረበው ቅጣት ማቅለያ ሃሳብ የወንጀል ህጉን እና የቅጣት ማንዋሉን ተከትሎ በአግባቡ መሰላቱን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ሀምሌ 12/2008 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በወ/ህ/ቁ 540 ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ መሆኑን፤ በቅጣት ረገድም የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ውሳኔው እንዲፀና ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ቀዳሚ ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ የሥር ፍርድ ቤቶች ካሳለፉት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ስልጣኑ ከተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መረዳት እንደሚቻለው ምንም እንኳን ተጠሪ ባቀረበው ክስ አመልካች ከሥር 2ኛ ተከሳሽ ታደሰ ገ/ክርስቶስ ቁጥሩ 650809 የሆነ ክላሽ ጠመንጃ ተቀብሎ አስቀድሞ በማሰብ ቆርቆሮ ደብድቦብኛል በሚል ቂም ተነሳስቶ ከተኮሳቸው 5(አምስት) ጥይቶች በአንድ ጥይት ቀኝ ሽንጡ ላይ በመምታት ሚች ነጋሲ ብርሃነን በመግደሉ በወ/ህ/ቁ/539(1)(ሀ) የተመለከተውን ተላልፏ የሚል ክስ ቢያቀርብም በክሱ የተገለፁት ፍሬ ነገሮች በማስረጃ አለመረጋገጣቸው፤ ይልቁንም ድርጊቱ በተፈጸመ ጊዜ አመልካች በጥበቃ ስራ ላይ ሆኖ በሚጠብቀው ድርጅት እንደነበር፤ የወንጀሉ አፈፃፀም ሲታይ ሆነ ብሎ የግድያ ወንጀል ለመፈፀም አስቀድሞ ከነበረው ቆርቆሮዬ ተመቶብኛል የሚል መነሻ አለመሆኑንና በድንገት በሚጠብቀው ድርጅት በሥራ ላይ ያጋጠመ መሆኑን፤ ድርጊቱም በምሽት የተፈፀመ መሆኑን፤ አመልካችም ወንጀል የተፈፀመበት መሆኑን በመግለፅ በቅድሚያ ለፖሊስ አመልክቶ እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በህጉ ረገድ የሚኖረውን ውጤት መርምረናል ፡፡

በወንጀል ህጉ አንቀፅ 78 ሥር እንደተደነገገው የራሱን ወይም የሌላውን ሰው መብት ህገወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገ ወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈፀመ ድርጊት አያስቀጣም፡፡ በሌላም በኩል ህጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ከቅጣት ነፃ የማያደርግ ስለመሆኑ ነገር ግን ጥፋተኛነቱንና ቅጣቱን በመወሰን ረገድ ግምት ውስጥ እንደሚገባ ከወ/ህ/ቁ 79/1/ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ተከሳሹ ከቅጣት ነፃ የሚሆነው ህገወጥ ጥቃት በራሱ ወይም በሌላው ሰው መብት ላይ የተሰነዘረ ወይም በእርግጠኛነት ሊደርስ የሚችል ጥቃት ስለመኖሩ ይህንንም ለማስወገድ ወይም ለመከላከል ሌላ አማራጭ የሌለው ስለመሆኑ እና የመከላከሉ እርምጃ ከተሰነዘረው ጥቃት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማስረዳት ሲቻል ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ማስረጃውን የመዘነው የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ እንዳረጋገጠው ከምሽቱ 5:00 ሰዓት አካባቢ ሚች ከዓቃቤ ህግ ምስክሮች ጋር በመሆን አመልካች ይጠብቀው በነበረው

ድርጅት በመሄድ ፀብ መነሳቱን፣ አመልካችም የስር 2ኛ ተከሳሽን መሣሪያ በወቅቱ ይዞ በጥበቃ ላይ የነበረ ስለመሆኑ፣ ለመከላከል ባደረገው ጥረት ወደ ሰማይ በተደጋጋሚ ጥይት ተኩሶ እንደነበር፣ ሟች ጥቃት ሰንዝሮበት የነበረ ስለመሆኑ እና በዚህ ጊዜ አመልካች ጥይት ተኩሶ በተኩሱ ሟች ተመትቶ በዚሁ ምክንያት ለህልፈት መብቃቱ ተመልክቷል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር አመልካች በራሱም ሆነ በሚጠብቀው የድርጅቱ ንብረት ላይ የተቃጣ ህገወጥ ተግባር ስለመኖሩ እና ጥቃቱን ለማስወገድ አመልካች በያዘው መሳሪያ ተኩሶ ሟችን በመምታት ለህልፈት ማብቃቱን ያረጋግጣል፡፡ ነገር ግን አመልካች የተሰነዘረውን ጥቃት ለማስወገድ ሌላ አመራጭ ያልነበረው ስለመሆኑና የወሰደት ርምጃም ተመጣጣኝ ስለመሆኑ ባቀረበው ማስረጃ ስለማስረዳቱ የስር ፍርድ ቤቶች አላረጋገጡም፡፡ ስለሆነም ድርጊቱ የተፈፀመው ህገወጥ ጥቃትን ለማስወገድ ነው ቢባልም በጥይት መትቶ ለህልፈት ማብቃቱ በህጉ ለመከላከል ከተፈቀደው መጠን በማሳለፍ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የአመልካች ድርጊት ህጋዊ መከላከልን ከመጠን ማሳለፍ መሆኑን መሠረት በማድረግ በወ/ህጉ ልዩ ክፍል በዚህ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነውን ድንጋጌ ተመልክተናል፡፡ ህጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ አስቦ ሌላ ሰውን የገደለ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 541(ሀ) ሥር ጥፋተኛ እንደሚባል ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች የፈፀመው የወንጀል ድርጊት የወ/ህጉን አንቀጽ 540 የሚያቋቁም ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፊተኛነት ውሳኔ እና ይህን ተከትሎ ያሳለፉት ቅጣት የድርጊቱን አፈፃፀም በአግባቡ ባለማገናዘብ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ስለሆነም አመልካች በወ/ህ/ቁ 540 ሥር ጥፋተኛ መባሉ አግባብ ሆኖ ስላላገኘው ይህንኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበትን ድንጋጌ ለውጠን አመልካች በወ/ህ/ቁ 541/ሀ/ ሥር የተመለከተውን የተላለፉ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ህ/ቁ 541/ሀ/ አስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡ የወ/ህ/ቁ 541/ሀ/ ስር የተመለከተው ጥፋት በሚያጋጥምበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን በመሰለው ሊያቀል እንደሚችል ህግ አውጭው የደነገገ ሲሆን በዚህ ምክንያት ድንጋጌው በቅጣት አወሳሰን ማንዋሉ እንደማይሸፈንም በቅጣት አወሳሰን በመመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀፅ 12(8) ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የድርጊቱን አፈፃፀም እና ሥለቅጣት አወሳሰን በሥር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያደረጉትን ክርክር ከህጉ ጋር በማያያዝ መርምረን በአመልካች ላይ ሊፈፀም የሚገባውን ቅጣት እንደሚከተለው ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

- የትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 19926 የካቲት 24 እና 30 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ፣ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 74374 ሚያዝያ 19 ቀን 2007 ዓ.ም እና የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 76261 ሰኔ 24/2007 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
- አመልካች በወ/ህ/ቁ 541/ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ሆነ ብሎ ሰውን በመግደሉ ጥፊተኛ ነው በማለት ወስነናል፡፡
- አመልካች በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በ 5 (አመስት) ዓመት እስራት እንዲቀጣ ብለናል፡፡
- የአክሱም ማረሚያ ማዕከል በተሻሻለው ቅጣት መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## 6.በሰው አካል እና ጤና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 6.1 ከባድ አካል ጉዳት[72]

- በሰዉ አካል ላይ የደረሰዉ ጉዳት ለተጎጂዉ ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም ጉዳቱ በሰዉነቱም ሆነ በአእምሮዉ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ከሆነ ወይም ከአካሉ ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ሲጎድል፤በጉዳቱ ምክንያት አስፈላጊዉ ብልት አገልግሎት እንዳይሰጥ ሲሆን ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂዉ መልክ ሲበላሽ ወይም በማናቸዉም ሌላ መንገድ ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን የሚያስከትል ጉዳት ሲደርስበት ከባድ የአካል ጉዳት ስለመሆኑ፡፡[73]

የሰበር መ/ቁ 246648

ግንቦት 29 ቀን 2016ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ቀንዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካቾች-** 1.አቶ ማሙዬ ገ/ማሪያም ቸሬ ቀረቡ

2. አቶ ደረጄ ሁንዴ አያኖ ቀረቡ ከጠበቃ ታምራት አበበ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ-** የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ አቃቤ ህግ ተስፋዬ ያደሳ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

### ፍርድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሰጠዉን ፍርድ በማጽናት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ትእዛዝ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል በሰበር ችሎት እንዲታረም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

ጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ በአመልካቾች እና በግል ተበዳዮች መካከል በመሬት ይገባኛል በተነሳ ጸብ አመልካቾች የግል ተበዳዮችን በመደብደብ የአካል ጉዳት አድርሰዋል በሚል የቀረበ ክስ የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት የግል ተበዳይ ሲራጅ በሽር የሚባለዉን 1ኛ አመልካች በድንጋይ የተጎጅን ዓይን በቀኝ በኩል በመምታት

[72]የሰ/መ/ቁ 246648 (ግንቦት 29 ቀን 2016ዓ.ም)

[73]የሰ/መ/ቁ 57446 (ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 141978 (መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22 ፣ የሰ/መ/ቁ 168166 (ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 210020 (ሕዳር 8 ቀን 2014ዓ.ም)

የአይንን ከለላ አጥንቱ እንዲሰበር ማድረጉን 2ኛ አመልካች ደግሞ በዱላ አፍንጫውንና የግራ አይኑን በመምታት የአፍንጫ አጥንት በመስበር ከባድ የአካል ጉዳት ስላደረሱ በወ/ህ/ቁ/32(1(ሀ) እና 555(ለ) ስር፤ 2ኛ አመልካች በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት ጅላሎ ተማም የሚባል የግል ተበዳይን አናቱ ላይ እና ደረቱ ላይ በተደጋጋሚ በመምታት ቀላል የአካል ጉዳት ስላደረሰበት በወ/ህ/ቁ/556(2)(ለ) ስር ጥፋተኞች ናቸው በማለት በ1ኛ ክስ አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉት በእርከን 16 ስር ፅኑ እስራት መነሻ 3 ዓመት ለእያንዳንዳቸው ይዞ በ2ኛው ክስ ለ2ኛ አመልካች ደረጃ 1እርከን 5 ተይዞ በወ//ቁ/184(1) መሰረት የ1ዓመት ቀላል እስራት ወደ 6 ወር ዝቅ ተደርጎ የሁለቱም ወንጀሎች የቅጣት መነሻ እርከን 16 በመያዝ ወንጀሉ በቡድን የተፈፀመ በመሆኑ ወደ እርከን 17 ከፍ ብሎ 3 ማቅለያ ተይዞላቸው ወደ እርከን 14 ዝቅ ተደርጎ በ2 ዓመት ከ6 ወር እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በውሳኔው ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በ1ኛ ክስ የተገለፀው አጥንት ስብራት የዳነ መሆኑ በባለሙያ በመረጋገጡ የወ/ህ/አ/555(ለ) መስፈርት የማያሟል በመሆኑ በወ/ህ/ቁ/113(2) መሰረት የወ/ህ/አ/ቁ 556(2) ስር በመቀየር በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በወ/ህ/አ/195(2)(ለ)(2) መሰረት በማሻሻል እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ 1ኛ አመልካች በ8 ወር ቀላል እስራት 2ኛ አመልካች ደግሞ በአንድ ዓመት ቀላል አስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ተጠሪ በበኩሉ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ፍርድ ቤቱም አስቀርቦ ክርክራቸዉን ከሰማ በኋላ የወንጀል ድርጊት የፈፀመው ሰው የሚቀጣው ወንጀሉ በተፈፀመ ጊዜ እንደሆነ ገልጾ የወንጀል ህግ አንቀፅ 555(ለ) አላማ ስር የተደነገገ ሲሆን ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ከአካል ክፍል አንዱን ማጉደል በቂ ሆኖ እያለ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ክስ የቀረበበትን አንቀፅ በመቀየር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል መወሰኑ ስህተት ነው ሲል ውሳኔውን በወ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀፅ 195(2)(ለ)(2) መሰረት በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡አመልካቾች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካቾች በግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት ከተሰሙት ምስክሮች እንዳስረዱት ጉዳቱ ተጠሪ እንዳለው ሳይሆን በወንጀል ህጉ 556(2) ስር የሚወድቅ ነው፤የጫንጮ ሆስፒታል በተበዳዮች ላይ የደረሰው ጉዳት ሙሉ በሙሉ የዳነ መሆኑን ማረጋገጫ የሰጠ ሲሆን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳቱ እስከደረሰ ድረስ መዳን አለመዳኑ ከግምት ሊገባ አይገባም በማለት ጉዳቱ መድረሱ ከተረጋገጠ አንቀፅ የሚቀየርበት ምንም ምክንያት የለም በማለት አቋም ይዞ የወ/ህ/ቁ/555(ለ) ባልተጋባ መልኩ ተርጉመው የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በማሻሻል የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ አግባብነት የለውም ተብሎ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ ትክክለኛ ነዉ ተብሎ እንዲፀናልን በማለት አመልክተዋል ፡፡

ሰበር ችሎቱ አቤቱታቸዉን መርምሮ በግል ተበዳዮች ላይ የደረሰው ጉዳት መዳኑን ከሆስፒታል ማስረጃ መቀረቡ ተረጋግጦ ጥፋተኛ መባል የሚገባቸው በተከሰሱበት የወንጀል ህግ አንቀፅ 555(ለ) ስር ሳይሆን በአንቀፅ 556(2) ስር ነው በማለት ልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሻሩን አግባብነት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/156521፤ 219862 እና 244589 ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(ሐ) አንፃር ለማጣራት ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ነሃሴ 20 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን በዚህም የወ/ህ/ቁ/555(ለ) ለሰው ህይወት በሚያሰጋ ሁኔታ ወይም በአእምሮ ላይ ከባድ ጉዳት በማድረስ ወንጀሉ ከተፈፀመ ቅጣቱ ከፍ ያለ መሆን እንዳበት ተደንግጓል፤ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ማየት ያለበት የደረሰውን ጉዳት እንጂ ተጎጂዎች ከህክምና በኃላ መዳናቸውን አይደለም፤የግል ተበዳይ የአይን ማቀፊያ አጥንት እና አፍንጫው በዱላ በመምታት አጥንቱ እንድሰበር ማድረጋቸው የህክምና ማስረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን የቁስሉ መዳን ብቻውን

ሙሉ በሙሉ እንደዳነ መወሰድ የለበትም፤ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 555(ለ) ቁስሉ ከዳነ ወደ አንቀፅ 556 (2) ተቀይሮ ቅጣቱ ይወሰናል የሚል እንድምታ የለውም፤በመሆኑም የስር ሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቶ እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በነሃሴ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈዉ አቅርበዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ ከግራቀኙ ክርክር፤በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ አቃቤ ህግ ሁለት ክሶችን ያቀረበ ሲሆን በ1ኛ ክስ ላይ የግል ተበዳይ የሆነዉ አቶ ሲራጅ በሽር “ን” 1ኛ አመልካች በድንጋይ የተጎጅን ዓይን በቀኝ በኩል በመምታት የአይንን ከለላ አጥንቱ እንዲሰበር ማድረጉን 2ኛ አመልካች ደግሞ በዱላ አፍንጫውንና የግራ አይኑን በመምታት የአፍንጫ አጥንት እንዲሰበር አድርገዋል በሚል የወ/ህ/ቁ/32(1(ሀ) እና 555(ለ) ተላለፎ ከባድ የአካል ጉዳት አድርሰዋል በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ በአንድ የወንጀል ድርጊት የደረሰዉ የአካል ጉዳት ከባድ ነዉ ወይስ ቀላል ነዉ የሚለዉን መለየት የሚቻለዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 555 ስር የተደነገገዉን መመዘኛ መሰረት በማድረግ እንደሆነ እሙን ነዉ፡፡በዚህ ድንጋጌ ስር እንደዘረዘረዉ በድርጊቱ ምክንያት በሰዉ አካል ላይ የደረሰዉ ጉዳት ለተጎጂዉ ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም ጉዳቱ በሰዉነቱም ሆነ በአእምሮዉ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ከሆነ ወይም ከአካሉ ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ሲጎድል፤በጉዳቱ ምክንያት አስፈላጊዉ ብልት አገልግሎት እንዳይሰጥ ሲሆን ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂዉ መልክ ሲበላሽ ወይም በማናቸዉም ሌላ መንገድ ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን የሚያስከትል ጉዳት ሲደርስበት ከባድ የአካል ጉዳት እንደሆነ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡(የወንጀል ህጉ አንቀጽ 555 ይመለከቷል)፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ለክሱ ምክንያት የሆነዉ የወንጀል ድርጊት የተፈጸመዉ በ15/11/2014ዓ.ም ሆኖ ክሱ የቀረበዉ በ21/02/2015ዓ.ም ሲሆን ተጎጂ ላይ የደረሰዉ ጉዳት የአይን ከለላ አጥንት እና የአፍንጫ አጥንት ስብራት እንደሆነ በክሱ የተጠቀሰ ሲሆን ወረዳ ፍርድ ቤት በአንቀጽ 555 (ለ) ስር የጥፋተኛነት ዉሳኔ የሰጠዉ ከቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል በቀን 09/12/2014ዓ.ም የተጻፈዉን የህክምና ማስረጃ መሰረት አድርጎ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ በሰዉነቱ ላይ ደርሶ የነበረዉ ጉዳት ስለመዳኑ ሆስፒታሉ በቀን 19/12/2014ዓ.ም በሰጠዉ ማስረጃ መሰረት ጉዳቱ መዳኑ በባለሙያ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ወደ አንቀጽ 556(2) በመቀየር ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ጉዳዩ መታየት የሚገባዉ ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ እንጂ በሂደት መዳኑ አይደለም በሚል የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሻሩን ያመለክታል፡፡ከላይ እንደተገለጸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ለዉሳኔ መሰረት ያደረጉት በተለያዩ ቀናት የተጻፉት ሁለት የህክምና ማስረጃዎች ሲሆኑ እነዚህ ማስረጃዎች የተዘጋጁት አቃቤ ህግ ክስ ከማቅረቡ በፊት የተጻፉ መሆኑን እና ሁለተኛዉ ማስረጃ ማለትም በቀን 19/12/2014ዓ.ም የተሰጠዉ ማስረጃ ሲታይ ክስ በቀረበበት ጊዜ ጉዳቱ የዳነ መሆኑን ያሳያል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጎጂ ላይ ደርሷል የተባለዉ የአጥንት ስብራት በሂደት በህክምና መዳኑ ቢረጋገጥ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ በቀላል የአካል ጉዳት ነዉ ወይስ በከባድ የአካል ጉዳት ነዉ የሚለዉን መመልከት ተገቢ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ ከባድ አካል ጉዳት ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚገባዉ የደረሰዉ ጉዳት ሊድን ወይም ሊጠገን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ በመግለጽ ሰበር ችሎቱ ገዥ ህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ሰበር መ/ቁ/ 156521፤ 219862 እና ሌሎችመዝገቦችን ይመለከታል፡፡

በዚህ ጉዳይ በ1ኛ ክስ ላይ የተጠቀሰዉ የግል ተበዳይ ላይ የደረሰዉ የአፍንጫ እና የአይን ቆብ የአጥንት ስብራት በሂደት ይልቁንም አቃቤ ህግ ክስ ከማቅረቡ በፊት የዳነ መሆኑ በህክምና ማስረጃ መረጋገጡን ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጠዉ ፍሬነገር ነዉ፡፡ከዚህ አኳያ ይግባኝ ሰሚ

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድርጊቱ በአንቀጽ 555(ለ) ስር ሳይሆን አንቀጽ 556(2) ስር የሚሸፈን ነዉ በማለት የሰጠዉ ፍርድ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር፣ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ገዥ ዉሳኔ እና ህጉን ያገናዘበ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ለመሻር የሰጠዉ ምክንያት በክርክር ሂደት የተረጋገጠዉን ፍሬነገር እና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉን ገዥ ዉሳኔ የሚቃረን ነዉ፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ሳያርም አልፎም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ዉሳኔ ማጽናቱ ስህተት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል በ1ኛ ክስ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰዉ አካል ጉዳት የዳነ መሆኑ በማረጋገጥ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 556(2) ስር በቀላል የአካል ጉዳት የሰጠዉ የጥፋተኛነትና ቅጣት ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩም ሆነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ማጽናቱ በክርክር ሂደት የተረጋገጠዉን ፍሬነገር እና ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ገዥ ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(ሐ) መሰረት መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ዉሳኔ**

1ኛ/ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 354786 ላይ በቀን 30/06/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 422785 ላይ በቀን 26/07/2015ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(/ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/75437 ላይ በቀን 26/04/2015ዓ.ም የሰጠዉ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ዉሳኔ ጸንቷል፡፡

3ኛ/ የቅጣት አፈጻጸም በተመለከተ አመልካቾ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ የታሰሩት ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ አቃቤ ህግ አጣርቶ እንዲያቀርብ ተብሎ መዝገቡ በአዳሪ ተቀጠረ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 6.2 ቀላል የአካል ጉዳት[74]

- አንድ ሰው በፈፀመው በአካል ላይ ጉዳት ወንጀል የተጎጅው አጥንት መሰበሩ የተረጋገጠ ቢሆንም ስብራቱ መዳኑ በባለሙያ ከተረጋጠና በስብራቱ ምክንያት ጉዳቱ በደረሰበት ሰው በሰውነቱም ሆነ በአእምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ስለመሆኑ ወይም ከአካሉ ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብሶቶች መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ መጉደሉ፣ በጉዳቱ ምክንያት አስፈላጊው ብልት አገልግሎት አለመስጠቱ ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጅው መልክ መበላሸቱ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን የሚያስከትል መሆኑ ክልተረጋገጠ በስተቀር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ተላልፎ ከባድ የአካል ጉዳት ፈፅሟል ተብሎ ሊቀጣ አይገባም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ድርጊት የሚሸፈነው የስር ፍርድ ቤቱ እንደወሰነው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2) ድንጋጌ ስር እንጅ በወንጀል ህግ አንቀጽ 555(ለ) አይደለም፡፡[75]

የሰ/መ/ቁጥር 219862

ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም

[74]የሰ/መ/ቁ 219862 (ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም)

[75]በሰ/መ/ቁ 210020 (ሕዳር 8 ቀን 2014ዓ.ም)

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ተድላ ክፍሌ ኦሻ ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ከኦሮሚያ ጠቅላይ ዐ/ሕግ ዳኘ አማረ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 391980 ጥር 4ቀን 2014ዓ/ም በዋለው ችሎት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ሲል መዝጋቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ተብሎ እንዲታረም አመልካች በመጠየቁ ስለጠየቀ ነው፡፡ ጉዳዩ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀልን በሚመለከት የቀረበ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አርሲ ዞን የዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ሐምሌ 6ቀን 2011ዓ/ም በተፃፈ ክሱ የአሁን አመልካችን አንደኛ ተከሣሽ በማድረግ እንዲሁም አቶ ደጀኔ ከበደን ሁለተኛ ተከሣሽ በማድረግ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና 555(ለ) የሚደነግገውን በመተላለፍ በጋራ ሆነው በሰው አካል ላይ ጉዳት ለማደረስ አስበው ሚያዚ 19ቀን 2013ዓ/ም ከምሽቱ 2፡00 አረቢ ቀበሌ ልዩ ቦታው ቱሉ ገሬ ከሚባለው ስፍራ የግል ተበዳይ ሐብታሙ ሙላቱን አመልካች በከዘራ የግራ ጭንቅላቱ ላይ መቶ በመፈንከት ጥድ ላይ ሲጥለው የቀኝ ዓይኑ አካባቢ አጥንት ወደ ውስጥ በመስበር ጉዳት መድረሱን ሁለተኛው ተከሣሽ በበኩሉ በወደቀበት በዱላ ቀኝ ትክሻውን በመምታት ከበድ የአካል ጉዳት መድረስ ወንጀል ፈጽሚል የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

አመልካች ክዶ የተከሣሽነት ቃል መስጠቱን ተከትሎ የተጠሪ ምስክሮችና በተበዳይ ላይ ደረሰ የተባለውን ጉዳት የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ እንዲሁም ማስረጃው ከተደመጠ በኋላ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ተመርምሮ እንዲቀርብ የሰጠውን ትዕዛዝ ተከትሎ የቀረበው የምርምራ ውጤት በመመዘን በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት የዳነ መሆኑ እና ቋሚ ጉዳት አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል አመልካቹ ተከሠሠበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555(ለ) ወደ 556(2) በመቀየር እንዲከላከል አዟል፡፡ አመልካች ሶስት መከላከያ ምስክሮች አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካችንና ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው የተጠሪን ክስና ማስረጃ አላስተባበሉም ሲል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) ጥፋተኛ ብሎ ሁለቱም እያንዳንዳቸው በስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታውን ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክሩ ከተመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤት በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአጥንት ስብራት ድኗል በሚል አንቀፁን መቀየሩ ተገቢ አይደለም ምክንያቱም ጉዳቱ ሊመዘን የሚገባው ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ እንጅ ከጉዳጡ በኋላ የሚመጣውን ውጤት መሰረት አድርጎ ሊሆን አይገባም ሲል ውሣኔውን አሻሽሎ አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ስር ጥፋተኛ ብሎ በሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ያቀረበ ቢሆንም ስላልተለወጠ የያዝነውን የሰበር አቤቱታ

አቅርቧል፡፡ አመልካች ጥር 16ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው አንድ ሰው በሌላ ሰው አካል ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 555፣556 እና 560 መካከል በየትኛው እንደሚከሰስ የሚወሰነው የጉዳቱን መጠን መሰረት አድርጎ እንደሆነ በመደንገጉ የወረዳው ፍርድ ቤት ይህን ታሳቢ በማድረግ አንቀፁን ከ555 ወደ 556 መቀየሩ ተገቢ ሆኖ ሣለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተገቢ ባልሆነ ምክንያት መሻሩ፣ አንቀፁ መቀየሩ ተገቢ ነው ቢባል እንኳ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአጥንት መሰበር በአመልካች ድርጊት ሣይሆን ሲወድቅ በመታው እንጨት ምክንያት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋጠበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 555(ለ) ጥፋተኛ ተብሎ በዚሁ መሰረት ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር የአርሲ ዞን የዲገሉኛ ጦጆ ወረዳ ፍርድ ቤት የግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአጥንት ስብራት የዳነ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ዐ/ህግን ክስ ድንጋጌ ወደ 556(2) ቀይሮ የጥፋተንነት ውሣኔ ከሰጠ በኂላ ጉዳዩን በይግባኝ የያው የፍርድ ቤት ወደ 555(ለ) በመመለስ ጥፋተኛ በሚል የወሰነበትን አግባብት ከወንጀል ሕ አንቀጽ 555 እና ከሰበር መዝገብ ቁጥር 156221 ከተሰጠው ትርጉም እንዲመረመር ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ግንቦት 26ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ መልሱ በጥቅሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ አንቀፁን ወደ 555 ቀይሮ አመልካችን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት መወሰኑ ተገቢ ነው የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲፀናለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል፡፡ ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ ከ556 ወደ 555 በመቀየር ቅጣት መወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በሚመለከት ውሣኔ ለመስጠት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱን ውሣኔ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ጉዳዩ አግባብት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡ እንደተመረመረው ከይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ጀምሮ በየደረጃው በሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶችና በዚህ ችሎት ጭምር አከራካሪ የሆነው ጉዳይ በግል ተበዳይ የቅንድብ የአጥንት ስብራት በመዳኑ አመልካች ጥፋተኛ መባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ነው ወይስ 556 የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሰረቱ በአንድ የወንጀል ድርጊት የደረሰው የአካል ጉዳት ከባድ ነው ወይስ ቀላል ነው ለሚለው አከራካሪ ነጥብ መልስ የሚሰጠው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ድንጋጌ ነው፡፡ በአንድ የወንጀል ድርጊት ምክንያት በሰዎች አካል ላይ ጉዳት ከደረሰና በደረሰው ጉዳት ምክንያት የተጎጅውን ሕይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም ጉዳቱ በሰውነቱም ሆነ በአእምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ከሆነ ወይም ከአካሉ ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብለቶች መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ሲጎድል፣ በጉዳቱ ምክንያት አስፈላጊው ብልት አገልግሎት እንዳሰጥ ሲሆን ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጅው መልክ ሲበላሽ፤ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን የሚያስከትል ጉዳት ሲደርሰበት እንደሆነ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ይደነግጋል፡፡ በቀረበልን ጉዳይ የግል ተበዳይ በአመልካች ድብደባ የተፈፀመበት መሆኑና በአመልካችና በሁለተኛ ተከሳሽ ድብደባ ምክንያት የግል ተበዳይ እንጨት ላይ በመውደቁ የቅንድቡ አጥንት ተሰብሮ የነበረ መሆኑም በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦ በመከላከያ ማስረጃ ያልተስተባበለ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በሌላ በኩል በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የቅንድብ አጥንት ስብራት ከጊዜ በኂላ መዳኑ በሕክምና ማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም አንድ ሰው በሌላ ሰው አካል ላይ በፈፀመው የድብደባ ድርጊት የአጥንት ስብራት መድረሱ ቢረጋገጥና ቆይቶ ስብራቱ መዳኑ ቢረጋገጥ ጉዳያ የደረሰው ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ነው ወይስ በከባድ የሚለው ጉዳይ መልስ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ነጥብ ጋር በተያያዘ ይኸው ችሎት አንድ ያአካል ጉዳት ከባድ የአካል ጉዳት ነው የሚባለው የደረሰው ጉዳት ሊድን ወይም ሊጠገን የማይችል መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ስለመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 156521 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ መሰረት በግል ተበዳይ የደረሰው ስብራት መልሶ የዳነ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይሕ ስብራት በተጎጅው ላይ ዘላለማዊ የሆነ ጠንቅ የሚያተርፍ ስለመሆኑ

ወይም የተሰበረው የአካል ክፍል አገልግሎት እንዳይሰጥ ስለማድረጉ ወይም የተሰበረውን የአካል ክፍል በሚያሰቅቅና ጉልሕ ሆኖ በሚታይ መልኩ መልኩን ያበላሸ ስለመሆኑ ክርክር አልቀረበም በማስረጃም አልተረጋገጠም፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው በፈፀመው በአካል ላይ ጉዳት ወንጀል የተጎጅው አጥንት መሰበሩ የተረጋገጠ ቢሆንም ስብራቱ መዳኑ በባለሙያ ከተረጋጠና በስብራቱ ምክንያት ጉዳቱ በደረሰበት ሰው በሰውነቱም ሆነ በአእምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ስለመሆኑ ወይም ከአካሉ ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶቹ መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ መጉደሉ፣ በጉዳቱ ምክንያት አስፈላጊው ብልት አገልግሎት አለመስጠቱ ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጅው መልክ መበላሸቱ፤ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን የሚያስከትል መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ተላልፎ ከባድ የአካል ጉዳት ፈፅሟል ተብሎ ሊቀጣ አይገባም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ድርጊት የሚሸፈነው የስር ፍርድ ቤቱ እንደወሰነው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2) ድንጋጌ ስር እንጅ በወንጀል ህግ አንቀጽ 555(ለ) ስላልሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1) የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 391980 ጥር 4ቀን 2014 ዓ/ም በመዝገብ ቁጥር 384767 ታሕሳስ 6ቀን 2014ዓ/ም የሰጧቸው ትዕዛዛት፤ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዘገብ ቁጥር 98 829 ሕዳር 17ቀን 2014ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሽሯል፡፡
2) በአርሲ ዞን የዲገሉና ጦጀ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዘገብ ቁጥር 40897 ጥቅምት 9ቀን 2014ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1) በዚህ ውሣኔ መሰረት በስር ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀጣ ከተወሰነው የእስራት ቅጣት ያልተፈፀመ ካለ የስር ወረዳ ፍርድ ቤቱ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ታዟል፤ የውሣኔው ቅጅ ይላክለት፡፡
2) መዝገቡ እልባት ያገኘ በመሆኑ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# ክፍል ሰባት

## 7.በሰው ነፃነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 7.1 በሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክ[76]

- በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጪ አገር የተላከች ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ከደረሰና ይህም ጉዳት ውጭ አገር የደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ በሕገወጥ መንገድ የላከው ሰው ራሱ በቀጥታ ጉዳዩን ባያደርሰውም በሕገወጥ መንገድ በመላኩና ጉዳቱ በውጪ አገር በመድረሱ ምክንያት ብቻ የወንጀሉ ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

[76] የሰ/መ/ቁ 71753 (ጥር 03 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ የሰ/መ/ቁ 54839 (ጥቅምት 30 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 10

- በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 598/2/ ድንጋጌ ስር አንድ ሰው ሊቀጣ የሚችለው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለስራ ወደ ውጭ የላከ እንደሆነ እና በዚህ ድርጊት ምክንያት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ፣ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፤

ሰ/መ/ቁጥር - 71753

ጥር 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ወርቅነህ ዳቲ ጉዳይ ተከታታይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ተስፋዬ አባቡ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘቱም:- አመልካች በ1996 ዓ/ም የወጣውን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወንጀል አንቀፅ 32/1/ሀ/ እና 598/2/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ወደ ውጪ ለመላክ የሚያስችል ምንም አይነት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሣሽ ከነበረው ከአቶ ሙሉጌታ ገ/ማርያም ጋር ግብረ አብር በመሆን የግል ተበዳይ ነፃነት መንግስቴ የተባለችውን ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 12:30 ሠዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል በኢትዮጵያ አየር መንገድ አማካይነት ወደ ቤሩት በመላክ ሟች በአሰሪዎቿ ከባድ ድብደባ እየደረሰባት መሆኑን ለቤተሰቦቿ ውጪ አገር ባለችው ዘመዷ አማካይነት ስትናገር ይህ ጉዳይ እየደረሰባት መሆኑን በተመለከተ ለአመልካችና ለግብረ አብሩ ተገልፆ ሟች አገሯ እንድትመለስ እንዲያድርጉ ሲነገራቸው ተከሣሾች መምጣት አትችልም፣ የሁለት አመት ከአርባ አምስት ቀናት የስራ ኮንትራት አላት በማለት መልስ ከመስጠታቸው ውጪ ወጪ በመክፈል ወደ አገር እንድትመለስ ሁኔታዎችን ጨርሳ ሟች በኢትዮጵያ አየር መንገድ መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:10 ሲሆን ስትደርስ እግሯ በጣም ያበጠና መቆም የማትችል ፣ በአውሮኘላን ሰራተኛ ድጋፍ ወርዳ ወደ ቤቷ ሄዳ መጋቢት 27 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተወስዳ ምንም እርዳታ ሳይደረግላት በደረሰባት ጉዳት ከቀኑ 5:00 ሠዓት ሲሆን ሕይወቷ ሊያልፍ መቻሉን ዘርዝሮ ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊን ወደ ውጪ አገር መላክ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች የአቃቤ ክስ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በሁዋላ አሉኝ ያላቸውን የክስ ተቃውሞ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ተገቢ ነው ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ስለድርጊቱ አፈፃፀም የአመልካችን የእምነት ክህደት ቃል በመጠየቅ አመልካች ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች በዐቃቤ ህግ ማስረጃ ወንጀሉን መፈፀሙ መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ገልፆ አመልካች እንዲከላከል መብቱን ጠብቆት አመልካችም አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን በማስቀረብ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች ማስረጃዎች የአቃቤ ህግን ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ የሚችሉ አይደሉም በማለት ቃላቸውን ውድቅ አድርጎ አመልካችን

በተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ ስርቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር በማገናዘብ በእያንዳንዱ ክስ ተገቢ ነው ያለውን የአስራት እና የገንዘብ መቀጮ ከአስቀመጠ በሁዋላ በድምሩ ደግሞ 9/ዘጠኝ አመት /ፅኑ እስራት እና በብር 3000.00/ሶስት ሺህ / የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/1/ መሠረት ተሰርዟል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለግል ተበዳይ መሞት ምክንያት አመልካች ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ አመልካች ለድርጊቱ ተጠያቂ መደረጉ ያለአግባብ መሆኑን ፣ ሚችን አመልካች ወደ ውጪ በመላክ ሂደት የተሳተፈ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ሳይረጋገጥና የመከላከያ ምስክሮች ቃልም ውድቅ የተደረገው ያለአግባብ መሆኑን ዘርዝሮ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔው እንዲታረም ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የግል ተበዳይ የሞተችው በበረታ የሳምባ ምች በተሰራጨ የቲቢ በሽታ ታማ ሊሆን እንደሚችል የሕክምና ማስረጃ ቀርቦ እያለ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/2/ ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም በሰጠው መልስ ሚች ወደ ውጪ አገር አመልካችና ግብረ አበሩ ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ልከዋት በውጪ አገር እያለች እግሯ አብጦ መምጣቷና ወደ አገሯ እንደተመለሰች ህክምና ሳታገኝ ሕይወቷ ማለፋ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የሳንባ ምች የሚባለው በሽታም ከድብደባ ጋር ተያይዞ ሊከሰት እንደሚችል ሳይንሱ የሚያረጋግጠው ሐቅ መሆኑን ዘርዝሮ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 598/2/ ተጠቅሶበት ሁኖ ይዘቱም ባጭሩ ሲታይ አመልካች ምንም ሕጋዊ የሆነ ፈቃድ ሳይኖረው የግል ተበዳይ ነፃነት መንግስቴን ወደ ውጪ በመላክ የግል ተበዳይ ከተላከችበት አገር ድብደባ ደርሷባት እግሯ አብጦ ወደ አገሯ ከተመለሰች በሁዋላ በበነጋታው ሕይወቷ አልፏል የሚል ነው፡፡ አመልካች ክሱን የካደ ሲሆን አቃቤ ሕግ አሉኝ ባላቸው የሰውና የሠነድ ማስረጃዎች አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ማስረዳቱን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

አመልካች በዚህ ሰበር ስሚ ችሎት አጠብቆ የሚከራከረውና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በጭብጥነት የተያዘው ዋናው ነጥብ የግል ነፃነት መንግስቴ የሞተችው በአመልካች ድርጊት ምክንያት መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የተጠቀሰበት ድንጋጌ ይዘትም ሆነ የክሱ ዝርዝር ይዘት አመልካች ለግል ተበዳይ ሞት ምክንያት የሆነ ድርጊት ራሱ በቀጥታ ፈፅሟል የሚል ሳይሆን ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ኢትዮጵያዊ ዜጋን ወደ ውጪ በመላክ የግል ተበዳይ ድብደባ የደረሰባት መሆኑንና ይህ ጉዳትም ከዉጪ አገር ስትመለስ የነበረ ስለመሆኑና ከውጪ አገር ከተመለሰች በሁዋላ በሁለተኛው ቀን ሕይወቷ አገሯ ውስጥ አልፏል በሚል ነው፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 598/2/ ድንጋጌ ስር አንድ ሰው ሊቀጣ የሚችለው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለስራ ወደ ውጭ የላከ እንደሆነ እና በዚህ ድርጊት ምክንያት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ፣ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት መሆኑ ከተረጋገጠ ሲሆን ቅጣቱም ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን ሕጉ ያሳያል፡፡ ይኸው ድንጋጌ በተጠቃሽ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ቀጣይ ሲሆን ዝርዝር ይዘቱ ሲታይ ቅጣትን የሚያከብዱ ምክንያቶች መቀመጣቸውን የሚያሳይ ነው:: በመሆኑም ድንጋጌው ማንም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም

በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለስራ ወደ ውጭ አገር በመላኩ ድርጊት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብት ፤ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ከደረስ የወንጀል ተጠያቂነት አለበት:: ድንጋጌው በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር የተላከች ኢትዮጵዊት ላይ በሰብአዊ መብቷ፣ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት መድረሱ መረጋገጡን እንጂ በሕገ ወጥ መንገድ የላከው ሰው ራሱ በቀጥታ በሚፈፀመው ድርጊት ወይም በሌላ ጣልቃ ገብ በሆነ ምክንያት ጉዳቱ መድረሱ መረጋገጡን በወንጀሉ ማቋቋሚነት አያስቀምጥም፡፡ በሌላ አገላለፅ በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጪ አገር የተላከች ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ከደረሰና ይህም ጉዳት ውጭ አገር የደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ በሕገወጥ መንገድ የላከው ሰው ራሱ በቀጥታ ጉዳዩን ባያደርሰውም በሕገወጥ መንገድ በመላኩና ጉዳቱ በውጪ አገር በመድረሱ ምክንያት ብቻ የወንጀሉ ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ሟችን ወደ ውጪ አገር በመላክ የግል ተበዳይዋ ውጭ አገር እያለች ድብደባ ደርሶባት እግሯ አብጦ ወደ አገሯ ከተመለሰች በሁዋላ ሕይወቷ ማለፉና በአካሏ ላይ ጉዳት መድረሱ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 598/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አመልካች ለድርጊቱ ተጠያቂ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታም ሆነ የተያዘው ጭብጥ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አላገኘንም፡፡ ቅጣቱን በተመለከተ የቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው የቅጣት መጠን ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ሲሆን

ቅጣቱ የተጣለው በግራ ቀኙ የቀረቡት የቅጣት አስተያየቶች ተመዛዝነው በወንጀል ሕጉ የተመለከቱትን የቅጣት አጣጣል መርሆችን እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሠረት ተደርጎ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአመልካች ላይ የተጣለው የዘጠኝ አመት ጽኑ እስራትና የብር ሶስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ የሚነቀፍ ሁኖ አላገኘውም፡፡ ሲጠቃለልም ጉዳዩ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ተከተዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

- በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94074 ጥር 20 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ጥፋተኝነት ውሣኔ እና በ26/05/2003 ዓ/ም የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 65555 ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሠረት ጸንቷል፡፡
- መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## 8. በሩካቤ ስጋ ነፃነት እና ንፅህና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 8.1 የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ- የወንጀሉ ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር[77]

- በወ/ሕ/ቁ. 627(1) የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር ሆኖ አልተመለከተም፤
- የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ አለመኖሩን የሕክምና ማስረጃ የሚያሳይ ቢሆንም የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ባለመሆኑ ዐቃቤ ሕግ የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ መኖሩን የማስረዳት ኃላፊነት የለበትም፣ በዚህ ረገድ በሕክምና ማስረጃ የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ አለመኖር የሚገልጸው ለክሱ አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር አይደለም፤[78]

የሰ/መ/ቁ. 222452

ሕዳር 30 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ሌሊሴ ደሳለኝ

ደጀኔ አያንሳ

ሀብታሙ እርቅይሁን

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች ፡- የኢፌዴሪ ፍትሕ ሚኒስቴር

ተጠሪ ፡- 1. አህመድ አብሪያ

2. ሙባረክ ታጁ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

#### ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻ ግራቀኙ ማስረጃቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው 1ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 627(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ሳንሱሲ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ጥር 01 ቀን 2013 ዓ/ም በግምት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን ተቃራኒ ፆታ ካላትና ዕድሜዋ 7 ዓመት ከሆናት የግል ተበዳይ ኢክረም ሬድዋን አባትሽ የእርሾ ኬሚካል እንዲገዛልኝ ንገሪው በማለት ከጠራት በኋላ አቅፎ ወደሚሰራበት የዳቦ ቤት ይዟት በመግባት የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈጸመባት በመሆኑ በሕጻናት ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፤ በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው 2ኛ ክስ ደግሞ የወ/ሕ/ቁ. 627(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለጸው ሁኔታና ቦታ የግል ተበዳይ ኢክረም ሬዴዋን ከጥቅምት እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2013 ዓ/ም ባለው ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈጸመባት በመሆኑ በፈጸመው በሕጻናት ላይ የሚፈጸም የግብረ

[77] የሰ/መ/ቁ. 222452 (ሕዳር 30 ቀን 2015 ዓ/ም)

[78] የሰ/መ/ቁ 46412 (ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ. 107166 (ጥቅምት 4/2008 ዓ.ም) ቅፅ 19 ፣ የሰ/መ/ቁ. 222452 (ሕዳር 30 ቀን 2015 ዓ/ም)

ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው 3ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 627(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ሳንሱሲ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ/ም እስከ ነሀሴ 06 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ተቃራኒ ፆታ ካላትና ዕድሜዋ 13 ዓመት ካልሞላት የግል ተበዳይ ኢክረም ሬድዋን ተቀጥሮ ወደሚሰራበት ዳቦ ቤት ይዟት በመግባት በተደጋጋሚ የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈጸመባት በመሆኑ በሕጻናት ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፤

ተጠሪዎች ክሱን የካዱ ሲሆን ዐ/ህግ ክሱን ለማስረዳት የሰውና የሠነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የግል ተበዳይ ቀርባ ተጠሪዎች ከሚሰሩበት ዳቦ ቤት በማስገባት 1ኛ ተጠሪ ሁለት ጊዜ እና 2ኛ ተጠሪ ሦስት ጊዜ የሽንት መሺኛቸውን ወደሽንት መሺኛዋ ያስገቡ ስለመሆኑና ለወላጆቿ የነገራቸቸው ስለመሆኑ አስረድታለች፤ የግል ተበዳይ ወላጆች ቀርበው ተጠሪዎች ሠራተኞቻው መሆኑን ገልጸው ልጃቸው የግል ተበዳይ መነሳት ሲያቅታት ስንጠይቃት ሁለቱም ተጠሪዎች በተለያየ ጊዜ የሽንት መሺኛቸውን ወደሽንት መሺኛዋ ያስገቡ መሆኑን ስለመናገሯ አስረድተዋል፡፡ የሕክምና ማስረጃው የግል ተበዳይ የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ እንደማያሳይ ያስረዳል፡፡ ተጠሪዎች እንዲከላከሉ ታዞም ወንጀሉን ያልፈጸሙ ስለመሆኑ ያውቃሉ የተባሉ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው የሰው ማስረጃ ተጠሪዎች ሕጻን የሆነችው የግል ተበዳይ ላይ የግብረ-ስጋ ግንኙነት የፈጸሙ ስለመሆኑ የተመሰከረ ሲሆን የሕክምና ማስረጃው ደግሞ የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ ሆነ ሌላ አካላዊ ጉዳት አለማሳየቱ በተጠሪዎች የተፈጸመው ድርጊት የግብረ-ስጋ ግንኙነት መሰል ድርጊት እንጂ የግብረ-ስጋ ድፍረት ወንጀል አይደለም፤ በመከላከያ ማስረጃም ድርጊቱ አለመፈጸሙን አላስተባበሉም፡፡ የተከሰሱበትን ክስ በወ/ሕ/ቁ. 61 መሠረት ወደ አንድ ክስ በማጠቃለልና ክሱን በመለወጥ በወ/ሕ/ቁ. 627(3) ሥር ተጠሪዎች ጥፋተኛ ናቸው በማለት እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ ማመልከቻ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የወ/ሕ/ቁ. 627(1) የክብረ-ንጽሕና መገርሰስን እንደወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር አድርጎ አላስቀመጠም፣ ሰበር ችሎትም በመዝገብ ቁጥር 107166 (በቅጽ 19 እንደታተመ) ክብረ-ንጽሕና መገርሰስ የወንጀሉ ማቋቋሚያ አለመሆኑን ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸሙን ምስክሮች አስረድተዋል፣ የግል ተበዳይ እድሜ ሰባት ስለመሆኑ ማስረጃ ስለቀረበ በተከከሱበት የወ/ሕ/ቁ. 627(1) መሠረት ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪው ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ለወ/ሕ/ቁ. 627(1) ክብረ-ንጽሕና መገርሰስ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር አለመሆኑ በሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 107166 ከተሰጠው ትርጉም አንጻር የውሳኔውን ሕጋዊነት ለመጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ተጠሪዎች ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖር አለመኖሩ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪዎች የተከሰሱት የወ/ሕ/ቁ. 627(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ሳንሱሲ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ተቃራኒ ፆታ ካላትና ዕድሜዋ 7 ዓመት ከሆናት የግል ተበዳይ ኢክረም ሬድዋን ወደሚሰሩበት ዳቦ ቤት በማስገባት በተደጋጋሚ የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈጸሙባት በመሆኑ በሕጻናት ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው፡፡ በወንጀል ሕግ ቁጥር 23(2) መሠረት ወንጀል አድራጊ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ የወንጀሉ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር፣ የሃሳብ ክፍሉ እና ሕጋዊ ፍሬ ነገሩ ተሟልተው ሲገኙ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ሊባል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወ/ሕ/ቁ. 627(1) ላይ ተቃራኒ ጾታ ካላት፣ ዕድሜዋ 13 ዓመት ካልሆናት ሕጻን ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም የወንጀሉ ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች ሆነው ተቀምጠዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ከሚሰሩበት ዳቦ ቤት በማስገባት 1ኛ ተጠሪ ሁለት ጊዜ እና 2ኛ ተጠሪ ሦስት ጊዜ የሽንት መሺኛቸውን ወደግል ተበዳይ ሽንት መሺኛዋ ያስገቡ ስለመሆኑ ስለመረጋገጡ ከሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ይዘት ያሳያል፤ ይሕም ተጠሪዎች ታቃራኒ ጾታ ካላትና ዕዴሜዋ ሰባት ዓመት ከሆናት የግል ተበዳይ ኢክራም ሬዴዋን ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት ማድረጋቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በድንጋጌው ላይ የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር ሆኖ አልተመለከተም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመዝገብ ቁጥር 107166 (በቅጽ 19 እንደታተመ) በወ/ሕ/ቁ. 627(1) ላይ ክብረ-ንጽሕና መገርሰስ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ሆኖ አለመቀመጡን አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ አለመኖሩን የሕክምና ማስረጃ የሚያሳይ ቢሆንም የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ባለመሆኑ ዐቃቤ ሕግ የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ መኖሩን የማስረዳት ኃላፊነት የለበትም፣ በዚህ ረገድ በሕክምና ማስረጃ የክብረ-ንጽሕና መገርሰስ አለመኖር የሚገልጸው ለክሱ አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ለወ/ሕ/ቁ/ 627(1) አግባብነት የሌለውን ፍሬ ነገር በመመዘን የድንጋጌው መስፈርት አልተረጋገጠም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በግል ተበዳይ ላይ የግብረ-ስጋ ግንኙነት በሚፈጸምበት የሴት ብልት ውስጥ ድርጊቱ መፈጸሙ ተረጋግጦ እያለ ድርጊቱ በወ/ሕ/ቁ. 627(3) የግብረ-ስጋ ግንኙነት መሰል ድርጊት በሚለው ሥር የሚሸፈን ነው ማለቱም ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች እድሜዋ 13 ዓመት ካልሞላት ሕጻን ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት የፈጸሙ በመሆኑ በወ/ሕ/ቁ. 627(1) መሠረት የግብረ-ስጋ ድፍረት ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ የወ/ሕ/ቁ. 627(1) ከ15-25 ዓመት ጽኑ እስራት ድረስ ያስቀጣል፤ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ወንጀሉ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ዕድሜዋ ዘጠኝ ዓመት ካልሞላት ሕጻን ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት ከፈጸመ ደረጃ 2 እርከን 35 ላይ 16 ዓመት ከ6 ወር እስከ 19 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ ዕስራት የሚያስቀጣ ነው፤ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ሪከርድ ያልቀረበባቸው መሆኑ፣ እድሜያቸው 20 እና 18 ዓመት መሆኑ ገና አፍላ ወጣት የሚገኙና የማገናዘብ ችሎታው የአነስተኛ መሆኑን በመገንዘብ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በወ/ህ/ቁ. 82(1)(ሀ) እና 86 መሰረት ሊያዝላቸው የሚገባ በመሆኑ ከዕርከን 35 ቅጣቱ ዕርከን 33 ላይ ያርፋል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት አላቀረበም፡፡ ዕርከን 33 ደግሞ ከ14 ዓመት እስከ 16 ዓመት ከ10 ወር ጽኑ ዕስራት ያስቀጣል፡፡ የወንጀሉን አፈጻጸም ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጠሪዎችን ያስተምራል ሌላውን ያስጠነቅቃል ያልነውን ከአሁን በፊት የታሰሩት ታሳቢ በሚሆን እያንዳንዳቸው በ14 (አስራ አራት) ዓመት ጽኑ ዕስራት ሊቀጡ ይገባል ብለናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 008464 ታህሳስ 14 ቀን 2014 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 118583 ጥቅምት 11 እና 17 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

2. ተጠሪዎች ከአሁን በፊት የታሰሩት ታሳቢ በሚሆን እያንዳንዳቸው በ14 (አስራ አራት) ዓመት ጽኑ ዕስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪዎች አፈላልጎ በመያዝ ለፌዴራል ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብና ማረሚያ ቤቱም ተጠሪዎች ላይ የተወሰነውን እስራት እንዲያስፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
3. የሥር መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## 9.በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 9.1 የስርቆት ወንጀል[79]- (ሙከራ ወንጀል)

- ድርጊቱ የተፈጸመው ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውል ጠባቂ የሌለው ፖልን ሲወስዱ የተያዙ ሳይሆን ንብረቱን ገና ሳይወስዱ በመጋዝ በመቆራረጥ ላይ እያሉ የተያዙ በመሆኑ ድርጊቱ ከአቅማቸው በላይ በሆነ ምክንያት የተቋረጠ እና በሙኩራ የቀረ ስለሆነ በከባድ ስርቆት ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል፤[80]

የሰ/መ/ቁ. 230945

ጥር 30 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት

አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች ፡- አቶ አስቻለው አያሌው

ተጠሪ ፡- የኢፌዴሪ ፍትሕ ሚኒስቴር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻ ግራቀኙ ማስረጃቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች እንዲሁም ቴዲ ኃይለሚካዔል እና ዮናስ ደሳለኝ በተባሉ ሰዎች ላይ ባቀረበው 1ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 669(1)(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን አካባቢ መጋቢት 15 ቀን 2013 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ሲሆን ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆነ የብረት ፖል ግምቱ ብር 8,527.00 የሚሆነውን አራት ቦታ ቆራርጠው በመውሰድ ለ2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሸጡ በመሆኑ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን፤ በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 669(1)(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ ክሰ በተገለጸው ቦታ መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ/ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ሲሆን ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆነ የብረት ፖል ግምቱ ብር 2,131.00 የሚሆነውን አመልካችን ጨምሮ ሦስቱ ተከሳሾች ቆርጠው ሲወስዱ እጅ ከፍንጅ የተያዙ በመሆኑ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክሱን አቅርቧል፡፡

---

[79]የሰ/መ/ቁ. 230945 (ጥር 30 ቀን 2015 ዓ/ም)፣

[80]የሰ/መ/ቁ 251537 (ጥቅምት 27 ቀን 2017 ዓ/ም)፣ የሰ/መ/ቁ 57988 (ጥር 10 ቀን 2003ዓ/ም)ቅፅ 12

አመልካችና የሥር 2ኛ ተከሳሽ ቴዲ ኃይለሚካኤል ክሱን የካዱ ሲሆን ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው ዮናስ ደሳለኝ ባለመቅረቡ ክርክሩ በእርሱ ላይ ተቋርጧል፡፡ ዐ/ህግ ክሱን የሰው ማስረጃ አቅርቦ አስረድቷል፡፡ እንዲከላከሉ ታዘም አመልካች የሰው ማስረጃ በማቅረብ መጋቢት 15 ቀን 2013 ዓ/ም ሌላ ቦታ የነበረ ስለመሆኑ አስረድቷል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ማስረጃ ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውል የብረት ፖል ተከሳሾች በመጀመሪያ ቀን አራት ቦታ ቆራርጠው በመውሰድ ስለመሸጣቸውና በሁለተኛው ቀን ደግሞ በመጋዝ እየቆረጡ ሳለ ምስክሮች ለፖሊስ በመጠቆም ወዲያው የተያዙ ስለመሆናቸው ያረጋገጡ ሲሆን አመልካች ባቀረበው አንድ ምስክር አብሮ ስለመዋሉ ብቻ የመሰከሩ እንጂ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ በልጦ ሊያስተባብል የሚችል ሆኖ ባለመገኘቱ በቀረበበት በሁለቱም ክስ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካችን በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሁም የሥር 2ኛ ተከሳሽ የነበረውን ቴዲ ኃይለሚካኤልን በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ ማመልከቻ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ባቀረብኩት የሰው ማስረጃ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ አስተባብያለሁ፣ ቅጣቱም የተጋነነ ነው፣ በገደብ ይደረግልኝ የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪው ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የወንጀል ድርጊቱ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ንብረት ላይ በተደጋጋሚ የሥርቆት ወንጀል በመፈጸሙ ምክንያት ብቻ በሁለት ክሶች ሥር ጥፋተኛ የተባለበት አግባብነት ከወ/ሕ/ቁ. 61(1) አንጻር ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው መልስ በተለያየ ቀን ሁለት ወንጀል ለመፈጸም በተያዘ ሃሳብ ስለሆነ በሁለት ክስ ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክሱን አስረድቷል፣ አመልካች በመከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የሚያስተባብል አይደለም፣ ቅጣቱም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት የተወሰነ ነው፣ የቅጣት ገደብ መስፈርትን የሚያሟላ ባለመሆኑ ቅጣቱ ሊገደብ አይገባም፤ ውሳኔው ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖር አለመኖሩ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው 1ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 669(1)(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን አካባቢ መጋቢት 15 ቀን 2013 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 11:00 ሰዓት ሲሆን ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆነ የብረት ፖል ግምቱ ብር 8,527.00 የሚሆነውን አራት ቦታ ቆራርጠው በመውሰድ ለ2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሸጡ በመሆኑ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን፤ በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 669(1)(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ ክሰ በተገለጸው ቦታ መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ/ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ሲሆን ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆነ የብረት ፖል ግምቱ ብር 2,131.00 የሚሆነውን አመልካችን ጨምሮ ሦስቱ ተከሳሾች ቆርጠው ሲወስዱ እጅ ከፍንጅ የተያዙ በመሆኑ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ነው፡፡ በወንጀል ሕግ ቁጥር 23(2) መሠረት ወንጀል አድራጊ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ የወንጀሉ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር፣ የሃሳብ ክፍሉ እና ሕጋዊ ፍሬ ነገሩ ተሟልተው ሲገኙ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ሊባል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) እና በፌዴራል ፍድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሠረት በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከቱ ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ አመልካች የስርቆት ወንጀል ስለመፈጸሜ አልተረጋገጠም ቢሉም በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው በ1ኛው ክስ ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን

ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆነ የብረት ፖል ግምቱ ብር 8,527.00 የሚሆነውን አራት ቦታ ቆራርጠው በመውሰድ ለ2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሸጡ ስለመሆኑ ሆነ በ2ኛው ክስ በመጋዝ እየቆረጡ ሳለ ምስክሮች ለፖሊስ በመጠቆም ወዲያው የተያዙ ስለመሆናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ለድርጊቱ ኃላፊ መባላቸው ተገቢ ነው፡፡

ነገር ግን በ2ኛው ክስ የተረጋገጠው ድርጊት ወንጀሉ ፍጻሜ ያገኘ ወይም በሙከራ የቀረ ስለመሆኑ መመርመር ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በወ/ሕ/ቁ. 669 ከባድ ስርቆት ማክበጃ ድንጋጌ ሲሆን የስርቆት ወንጀል ትርጉም በወ/ሕ/ቁ. 665 እንደተመለከተው ወንጀሉ የሚፈጸመው አንድን ዕቃ አንስቶ በመውሰድ፣ በቀጥታ የራሱ ንብረት በማድረግ ወይም በተዘዋዋሪ ከራሱ ንብረት ጋር እንዲቀላቀል በማድረግ ነው፤ ተጠሪ በክስ አቤቱታው መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ/ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ሲሆን ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆነ የብረት ፖል ግምቱ ብር 2,131.00 የሚሆነውን አመልካችን ጨምሮ ሦስቱ ተከሳሾች ቆርጠው ሲወስዱ እጅ ከፍንጅ የተያዙ በመሆኑ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ የመሰረተ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ከሰፈረው የተረዳነው የቀረቡት ማስረጃዎች አመልካች እና ግብረአበሮቹ የብረት ፖሉን በመጋዝ እየቆረጡ ሳለ ምስክሮች ለፖሊስ በመጠቆም ወዲያው የተያዙ መሆኑን ነው፡፡ ይሕም በክስ እንደተገለጸው ንብረቱን ሲወስዱ የተያዙ ሳይሆን ንብረቱን ገና ሳይወስዱ በመጋዝ በመቆራረጥ ላይ እያሉ የተያዙ መሆኑ ድርጊቱ ከአቅማቸው በላይ በሆነ ምክንያት የተቋረጠ እና በመኩራ የቀረ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡ ስለሆነም ድርጊቱ የተፈጸመው ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውል ጠባቂ በሌለው ፖል ላይ በመሆኑ 2ኛው ክስ ወደ ወ/ሕ/ቁ. 27(1) እና 669(1)(ለ) ከባድ ስርቆት ሙከራ ወንጀል በመለወጥ ጥፋተኛ ሊባል ይገባል ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አጣሪው ችሎት የያዘው ጭብጥ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ንብረት ላይ በተደጋጋሚ የሥርቆት ወንጀል በመፈጸሙ ምክንያት ብቻ በሁለት ክሶች ሥር ጥፋተኛ የተባለበት አግባብነት ከወ/ሕ/ቁ. 61(1) አንጻር ለመመርመር ነው፡፡ በወ/ሕ/ቁ. 60(ሀ-ሐ) መሠረት አንድ ሰው ተደራራቢ ወንጀሎችን አድርጓል የሚባለው ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ማናቸውንም ዓይነት ግዙፍ ወንጀሎችን አከታትሎ ያደረገ /material concurrence/ እንደሆነ ወይም አንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ወይም በአንድ ድርጊት ልዩ ልዩ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን በመፈጸም ጣምራ ወንጀሎችን ያደረገ እንደሆነ ወይም በአንድ የወንጀል ማድረግ ሃሳብ ወይም ቸልተኝነት ያደረገው ወንጀል አንድን የሕግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡ ግዙፍ የሆነ መደራረብ /material concurrence/ በሁለት ዓይነት መንገድ የሚፈጸም ነው፤ አንደኛው ተመሳሳይ ድርጊት በተለያየ ጊዜ መፈጸም ሲሆን ሁለተኛው የተለያዩ ድርጊቶችን በተመሳሳይ ጊዜ በመፈጸም ነው፡፡ አመልካች ክስ የቀረበበት ተመሳሳይ ድርጊትን በተለያዩ ጊዜያት መፈጸም በመሆኑ ጉዳዩ የሚሸፈነው በወ/ሕ/ቁ. 60(ሀ) የተመለከተው ግዙፍ የሆነ መደራረብ ወንጀል ነው፡፡ የድርጊት መደጋገም እስካለ ድረስ ተደራራቢ ክስ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ወንጀል ፈጻሚው በተደራራቢ ክስ ላይቀጣ የሚችለው በወ/ሕ/ቁ. 61 እንደተመለከተው ድርጊቱ በአንድ የወንጀል ማድረግ ሃሳብ ከተፈጸመ እና እንደ አንድ ጥፋት የሚወሰድ ከሆነ ነው፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 ስር በተደነገገዉ መሰረት የሚከተሉት ሦስት ሁኔታዎች ሲሟሉ አንድ የወንጀል ድርጊት ፈጻሚ ተመሳሳይ ባህርይ ባላቸዉ ሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ ቅጣት በሚያስከትሉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች አይከሰስም እንዲሁም አይቀጣም፡፡ይህም ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት በሚል የሚታወቅ አጠቃላይ መርህ ሆኖ ተግባራዊ የሚሆነዉ በአንድ የወንጀል ድርጊት የመፈጸም ሀሳብ ወይም ዓላማ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የወንጀል ድርጊቶች ተደራርበዉ ሲፈጸሙ ፍጹምነት የሚጎድለዉ መደራረብ ሲከሰት ነዉ፡፡ ፍጹምነት የጎደለዉ የወንጀል ድርጊቶች መደራረብ

ተፈጽመዋል በሚል ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት የሚል መርህ ተግባራዊ የሚሆነዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/1 ስር የተደነገጉት ሁኔታዎች፡- 1) አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች ሲፈጸሙ 2) ደርጊቶቹ የተፈጸሙት በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ ሲሆን እና 3)አድራጊዉ ድርጊቶቹን የፈጸመዉ በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን የሚሉ ሁኔታዎች ተሟልተዉ ሲገኙ ነዉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ በ1ኛው ክስ እንደተመለከተው አመልካች ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን አካባቢ መጋቢት 15 ቀን 2013 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ሲሆን ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆነ የብረት ፖል ግምቱ ብር 8,527.00 የሚሆነውን አራት ቦታ ቆራርጠው በመውሰድ ለ2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሸጡ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ድርጊት ስርቆት በመፈጸም ሀሳብ የተከናወነ ነው፡፡ በማግስቱ መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ/ም ሌላ የአሌክትክ ፖል በመጋዝ ሲቆርጡ መያዛቸው በሌላ ስርቆት የመፈጸም አዲስ ሃሳብ የተከናወነ ድርጊት እንጂ በ1ኛው ክስ ሥር የሚጠቃለልና እንደ አንድ ጥፋት የሚወሰድ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም በአመልካች ላይ የቀረቡት ሁለቱ ተደራራቢ ክሶች መሠረት በ1ኛው ክስ በወ/ሕ/ቁ. 669(1)ለ) ከባድ ስርቆት ወንጀል እና በ2ኛው ክስ የወ/ሕ/ቁ. 27/(1) እና 669(1)(ለ) ሥር ከባድ የሥርቆት ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ የወ/ሕ/ቁ. 669(1)(ለ) ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከ15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ያስቀጣል፤ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ወንጀሉ ደረጃ የወጣለት ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት ወንጀል የተፈጸመበት ንብረትን ግምት በመያዝ በ1ኛ ክስ ደረጃ 4 እንዲሁም በ2ኛው ክስ ደረጃ 3 በመያዝ በሁሉቱም ክሶች የ7 ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ይዟል፡፡ ይሕም እርከን 23 ላይ አርፏል፡፡ ወንጀሉ ከሌሎች ሰዎች ጋር ወንጀል በማድረግ ሥምምነት የተፈጸመ በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት የተያዘውን ቅጣት ማክበጃ ተቀብለናል፤ ቅጣቱ እርከን 24 ላይ እንዲያርፍ ያደርገዋል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ሪከርድ ያልቀረበባቸው መሆኑ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው፣ በበጎ አድራጎት መሳተፋቸው ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በወ/ህ/ቁ. 82(1)(ሀ) እና 86 መሰረት ሊያዝላቸው የሚገባ ሲሆን 2ኛው ክስ ደርጊቱ በሙኩራ የቀረ በመሆኑና በወ/ሕ/ቁ. 27(3) ሁለተኛ አንቀጽ መሠረት የነገሩ ሁኔታዎች የሚገቡ ምክንያቶችን ሲያስገኙ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ሊያቀል የሚችል መሆኑን በመደንገጉ አንድ እርከን ቀልሎ እንዲወሰን በመያዝ በድምሩ አራት እርከን ቀንሰናል፡፡ ይሕም ቅጣቱን እርከን 20 ላይ እንዲያርፍ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም የድርጊቱን አፈጻጸም ከግምት ውስጥ በማስገባት አመልካችን ያስተምራል ሌላውን ያስጠነቅቃል ያልነውን ከአሁን በፊት የታሰሩት ታሳቢ በሚሆን በ4 ዓመት ከ5 ወር (አራት ዓመት ከአምስት ወር) ጽኑ ዕስራት ሊቀጡ ይገባል ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 009457 ግንቦት 04 ቀን 2014 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 84392 ጥር 25 እና የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

2. አመልካች በ1ኛ ክስ በወ/ሕ/ቁ. 669(1)(ለ) ከባድ ስርቆት ወንጀል እና በ2ኛ ክስ የተከሰሱበትን የከባድ ሰው ስርቆት ወንጀል በመለወጥ በወ/ሕ/ቁ. 27(1) እና 669(1)(ለ) ሥር ከባድ ስርቆት ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ብለናል፡፡

3. አመልካች እስካሁን የታሰሩት ታሳቢ በሚሆን በ4 ዓመት ከ5 ወር (አራት ዓመት ከአምስት ወር) ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- የሸዋሮቢት ማረሚያ ቤት በተሻሻለው የእስራት ዘመን መሠረት እንዲያስፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## 9.2.የወንብድና ወንጀል[81]

• በተበዳይ ላይ በቋሚነት ከባድ የአካል ጉዳት ባለመድረሱ ብቻ የወ/ሕ/አንቀጽ 671,101 የተመለከተዉን ከባድ የዉንብድና ወንጀል አያቋቁምም ተብሎ አንቀጹ ቀላል ወደ ሆነዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 670 ተቀይሮ ጥፋተኛ መባላቸዉ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፤[82]

የሰ/መ/ቁጥር 153227
መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ
በዕዉቀት በላይ
እንዳሻዉ አዳነ
ኃይሉ ነጋሽ
እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዐ/ሕግ
ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አራጋዉ እዉነቱ
2ኛ. ገረመዉ አመራ
3ኛ. ጋሳ ሙሉ አድማስ
4ኛ. ጫኔ ማተቤ አማረ
5ኛ. ታከለ አንተነህ ዘዉዴ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ አመልካች በአማራ ክልል የባህር ዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ የክሱ ይዘት፡- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ለ) እና 672(1/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ተጠሪዎች ያልተገባ ብልጽግና እና ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሚያዚያ 22 ቀን 2008 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 1፡30 ሰዓት ሲሆን ሜጫ ወረዳ ለሁሉም ሰላም ቀበሌ ልዩ ቦታዉ ገርጨች እየተባለ ከሚጠራዉ ቦታ የግል ተበዳይን ጠብቀዉ መላኩን 1ኛ ተጠሪ በጠርሙስ ግንባሩን ሲመታዉ፣ 2ና ተጠሪ ጉሮሮዉን በመያዝ በጠርሙስ ግንጭሉን ሲመታዉ፣ 3ኛ ተጠሪ

---

[81] የሰ/መ/ቁጥር 153227 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም)

[82] የሰ/መ/ቁ 231850 ( ጥር 25 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣የሰ/መ/ቁ 212472 (መጋቢት 30 ቀን 2014ዓ.ም፣የሰ/መ/ቁ 66856 (መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 197432 (ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም) ፣የሰ/መ/ቁ 249641 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም) የሰ/መ/ቁ 208890(ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም) 26፤ የሰ/መ/ቁ 249641 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ/209051 (ጥር 27 ቀን 2014ዓ.ም) ቅፅ 25

ግንባሩን በጠርሙስ የመታው ሲሆን 4ኛ ተጠሪ ደግሞ ሆዱን በሽመል የመታዉ እንዲሁም 5ኛ ተጠሪ በጩቤ የግራ እግሩን የወጋዉና የግራ እግሩ እንዲሰበር እንዲሁም የተለያዩ የሰዉነት ክፍሉ ላይ ጉዳት ካደረሱበት በኃላ ልብሱን አዉልቀዉ ይዞት የነበረዉን ብር 25,000 የወሰዱበት በመሆኑ በፈጸሙት ከባድ የዉንብድና ወንጀል አድራጎት ተከሰዋል የሚል ነዉ፡፡በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ የወንጀል ድርጊቱን አለመፈጸማቸዉን ገልጸዉ ክደዉ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ማስረጃዎች ከተሰሙ በኃላ የስር ፍ/ቤት መርምሮ ተጠሪዎች በተመሠከረባቸዉ ልክ እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች የመከላከያ ማስረጃዎቻቸዉን ካሰሙ በኃላ መርምሮ የአመልካች ምስክሮች የዉንብድና ተግባር መፈጸሙን ቢመሠክሩም ከቀረበዉ የሕክምና ማስረጃና ከደረሰዉ ጉዳት አንጻር ሲታይ ተበዳዩን እንገድለሀለን ብለዉ እርግጠኛ የሞት አደጋ እንደሚደርስበት በመቃጣት ይልቁንም የጦር መሳሪያ በመያዝ ጉዳት ያደረሱ ስለመሆኑ በምስክሮችና በሰነድ ማስረጃ ዉ አልተረጋገጠም፤ የግል ተበዳይም ስብራት የደረሰበት ሰለመሆኑ ማስረጃዉ አይገልጽም በማለት ተጠሪዎች የተከሰሱበትን የወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) በወ/መ/ሕ/ሥ/ስ/ቁ 113(2) መሠረት ዝቅ በማድረግ በወ/ሕ/አንቀጽ 670 ስር በአብላጫ ድምጽ ጥፋተኛ በማድረግ እያንዳንዳቸዉ በ3 ዓመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ አመልካች በየደረጃው ላሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ተጠሪዎች የዉንብድና ተግባር የፈጸሙት የግል ተበዳይን የተለያየ የሰዉነት ክፍል አደገኛ በሆነና እስከ ሞት ድረስ ጉዳት ለማድረስ በሚችል በጠርሙስና በጩቤ በመጠቀም አንገቱን አንቀዉ የማስቃየትና በማንገላታት ደብድበዉና ወግተዉ ብር 25,000 ከነልብሱ ቀምተዉ በኃይል መዉሰዳቸዉና በአካል ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ ሲታይ በወ/ሕ/አንቀጽ 670 ላይ የተመለከተዉ ወንጀል የተፈጸመዉ አደገኛ በሆነ የመሳሪያ ዓነት በመጠቀም ስቃይ በሚያደርስ ሁኔታ በማንገላታት በመሆኑ የከባድ ዉንብድና ወንጀል ማቋቋሚያ ምክንያቶች ከሆኑት መካከል ሁለቱ መለኪያዎች የተሟሉ ከመሆናቸዉ አንጻር የተጠሪዎች አድራጎት ሊሸፈን የሚችለዉ በወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) ነዉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት በአብላጫ ድምጽ አንቀጹን ወደ የወ/ሕ/አንቀጽ 670 ተራ ሆነ የዉንብድና ወንጀል መለወጡ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተጠሪዎች የወ/ሕ/አንቀጽ 32(1/ሀ) እና 671(1/ለ) ስር ጥፋተኛ ተብለዉ ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ተሰልቶ እንዲወሰን የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪዎች የተከሰሱት በጠርሙስ፣ በሽመል እና በጩቤ የግል ተበዳይን በመምታትና በመዉጋት እንዳይከላከል አድርገዉ ልብሱን አዉልቀዉ ኪሱ ዉስጥ የነበረዉ ሞባይልና ገንዘብ ወስደዉበታል በሚል ሲሆን የስር ፍ/ቤት አንቀጹን የለወጠበት አግባብ ከወ/ሕ/አንቀጽ 671 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸዉ ያልቀረቡና መልስ ያልሰጡ በመሆናቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የአመልካች ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የግል ተበዳይን ጨምሮ የአመልካች ምስክሮች ተጠሪዎች መጠጥ ቤት ገብተዉ በር በመዝጋታቸዉ የግል ተበዳይ ለምን በሩን ተዘጋላችሁ በማለቱ 2ኛ ተጠሪ ጉሮሮዉን አንቆት በቢራ ጠርሙስ የመታዉ መሆኑን፤ 4ኛ ተጠሪ ግንባሩን በቢራ ጠርሙስ ሲመታዉ፣ 5ኛ ተጠሪ ቁርጭምጭሚቱ አካባቢ በጩቤ መዉጋቱን፣ 3ኛ ተጠሪ በጅን ጠርሙስ ግንባሩ ላይ ሲመታዉ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ጀንፎ ባለዉ ከዘራ ሆዱን መምታቱን በዚህም የግል ተበዳይ መሬት ሲወድቅ ደም ይፈሰዉ እንደነበርና በፓንት ብቻ

የነበረ መሆኑን፤ ከዚያም አንስተዉት ጤና ጣቢያ ቢወሰድም አንችልም በመባሉ ባሕርዳር ፈለገ ሕይወት ሆስፒታል ተወስዶ መታከሙንና ብር 25,000 ተወሰደበት መሆኑ ተመስክሯል፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱትም ሆነ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት አንቀጹን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 113(2) መሰረት ወደ የወ/ሕ/አንቀጽ 670 በመለወጥ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ አብላጫዉ ድምጽ አንቀጹን ለመለወጥ የሰጠዉ ምክንያት በግል ተበዳይ ላይ ከደረሰዉ ጉዳት አንጻር እርግጠኛ የሞት አደጋ እንደሚያደርስበት በመቃጣትና ይልቁንም የጦር መሳሪያ በመያዝ ጉዳት ያደረሱ ስለመሆኑ አልተመሠከረም በሚል ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት አንቀጹን መለወጡ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ለመመለስ የወ/ሕ/አንቀጽ 670 እና 671(1/ለ) ድንጋጌዎችን ይዘት መመልከቱ ተገቢ ነዉ፡፡

የወ/ሕ/አንቀጽ 670 ማንም ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት አስቦ፤ የሌላ ሰዉ ንብረት የሆነዉን ተንቀሳቃሽ ዕቃ ለመዉሰድ እንዲመቸዉ ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኃላ የገጠመዉን ተቃዉሞ ዉጤታማነት ለማስቀረት ሲል በሌላ ሰዉ ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ከባድ የሆነ የማንገላታት ተግባር ወይም ከባድ ዛቻ የፈጸመ ወይም በማናቸዉም ሌላ መንገድ ይህን ሰዉ ለመከላከል እንዳይችል ያደረገ የሚቀጣበት ሲሆን የወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) ደግሞ የዉንብድና ተግባሩ የተፈጸመዉ ተበዳዩን እገድልሀለሁ ብሎ እርግጠኛ የሞት አደጋ እንድሚያደርስበት በመቃጣት፣ ይልቁንም የጦር መሳሪያ ወይም በተለይ አደገኛ በሆነ ሌላ ዓይነት መሳሪያ በማስፈራራት ወይም ስቃይ በሚያደርስ ሁኔታ በማንገላታት ወይም ከባድ የአካል ጉዳት በማድረስ ሲሆን በከባድ ዉንብድና ጥፋተኛ ተደርጎ እንደሚቀጣ የሚደነግግ ነዉ፡፡ በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ያለዉ ልዩነት ገንዘቡን ወይም ንብረቱን ለመዉሰድ ሲባል በሚፈጸም የኃይል ተግባር ወይም የማስፈራራት ተግባር ክብደት ላይ የሚመሠረት ሲሆን በወ/ሕ/አንቀጽ 670 ከባድ የሆነ የማንገላታት ተግባር መፈጸምን ወይም ከባድ ዛቻ በመፈጸም ወይም በሌላ በማንኛዉ መንገድ እንዳይከላከል በማድረግ የዉንብድና ተግባር መፈጸምን የሚመለከት ሲሆን አንቀጽ 671(1/ለ) የተመለከተዉ ከባድ ዉንብድና ደግሞ ሞትን ሊያስከትል የሚችል መሳሪያ በመያዝ ማስፈራራትን ወይም በማንኛዉም መንገድ ከባድ የአካል ጉዳት በማድረስ የዉንብድና ተግባር መፈጸምን የሚመለከት ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪዎች በግል ተበዳይ ላይ የዉንብድና ተግባር የፈጸሙት የግል ተበዳይን በተደጋጋሚ በጠርሙን ግንባሩ ላይ በመምታትና በፈንከት፣ በሆዱ ላይ ጀንፈል ባለዉ ከዘረታ በመምታትና እግሩ ላይ በስልት በመዉጋት ጉዳት በማድረስ መሬት እንዲወድቅ በማድረግና ሱሪዉን አዉልቆ በመሄድ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች የተጠቀሟቸዉ መሳሪያዎች ሞትን ሊያስከትሉ ከመቻላቸዉም በላይ ከማስፈራራት ባለፈ በመሳሪያዎቹ ተጠቅመዉ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ የግል ተበዳይ ጤና ጣቢያ ተወስዶ ለማሳከም ጥረት ቢደረግም ከጤና ጣቢያዉ አቅም በላይ በመሆኑ ባሕርዳር ፈለገ ሕይወት ሆስፒታል ተወስዶ ታክሟል፡፡ በተበዳይ ላይ በቋሚነት ከባድ የአካል ጉዳት ባለመድረሱ ብቻ የወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) የተመለከተዉን ከባድ የዉንብድና ወንጀል አያቋቁምም ተብሎ አንቀጹ ቀላል ወደ ሆነዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 670 ተቀይሮ ጥፋተኛ መባላቸዉ ተገቢ ያልሆነና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች የግል ተበዳይን ግምባሩ ላይ በተደጋጋሚ በጠርሙስ በመምታት፣ በከዘራ ሆዱ ላይ በመምታትና እግሩን በጩቤ በመዉጋት ሱሪዉን በአዉልቀዉ በመዉሰድ በዉስጡ የነበረዉን ብር 25,000 የወሰዱና በተግባራቸዉ ጭምር እርግጠኛ ሞት ለማድረስ በሚያስችል መልኩ ከመቃጣት አልፈዉ ጉዳት ያደረሱበት በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባዉ በተከሰሱበትና አድራጎታቸዉን በሚያቋቁመዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ በመሆኑ በዚሁ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ተብለዋል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ የወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) በተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ደረጃ የወጣለት ሲሆን ድርጊቱ በቡድን መፈጸሙ፣ ማስፈራራትና የአካል ጉዳት የደረሰበት እንዲሁም የገንዘብ መጠኑ ብር 25,000 በመሆኑ በደረጃ 3 እርከን 27 ስር የሚያርፍ ነዉ፡፡ በስር ፍ/ቤት ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸዉ ሁለት የቅጣት ማቅለያ የተወሰደዉን እንዳለ በመዉሰድ ሁለት እርከን ሲቀነስ እርከን 25 ላይ ያርፋል፡፡ የዚሁ እርከን ፍቅድ ስልጣኑ ከ7 ዓመት እስከ 8 ዓመት ከ4 ወር የሚያስቀጣ በመሆኑ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸዉ የእርከኑ መነሻ በሆነዉ በ7 ዓመት ጽኑ እስራት ሊቀጡ የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

- በባህር ዳርና አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 04-03299 ግንቦት 09 ቀን 2009 ዓ.ም እና ግንቦት 11 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 17963 ሐምሌ ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 71077 ታሕሳስ ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
- በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ጥፋተኛ የተባሉበት የሕግ አንቀጽ ተለዉጦ አድራጎታቸዉን በሚሸፍነዉና በተከሰሱበት የወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኞች ናቸዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡ ቅጣትን በተመለከተም ተጠሪዎች እያንዳንዳቸዉ በ7 (ሰባት) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
- በተጠሪዎች ላይ ተሻሽሎ የተወሰነዉን የጽኑ እስራት ቅጣት እንዲያስፈጽም ለሚመለከተዉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
- መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 9.3 እምነት ማጉደል[83] ፣ የማታለል ወንጀል[84] እና ሥራን ያለአግባብ መምራት ወንጀል[85]

- ማንም ሰው በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቀው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይምለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፤[86]

---

[83]የሰ/መ/ቁ/89276(መሥከረም 23 ቀን 2006 ዓ. ም)ቅፅ 15፣የሰ/መ/ቁ 118084 (ሐምሌ 21 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 20

[84]በሰ/መ/ቁ 12025 (መጋቢት 18 ቀን 1999 ዓ.ም) ቅፅ 4 ፣ የሰ/መ/ቁ. 46189 (ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10 ፣ የሰ/መ/ቁ. 64813 (ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣የሰ/መ/ቁ 251436 (ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 104923 (መጋቢት 28 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18

[85]የሰ/መ/ቁ 77989 (ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣የሰ/መ/ቁ 236062 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)

[86]የሰ/መ/ቁ 65054 (ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ. 67408 (ጥር 01 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ የሰ/መ/ቁ 74530 (ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ ፣ የሰ/መ/ቁ 89276 (መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15

የሰ/መ/ቁ/89276

መሥከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች:-**

ተገኔ ጌታነህ

ተሸገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሙሥጠፋ አህመድ

**አመልካች** ተፈሪ ሚናሞ አልቀረቡም

**ተጠሪ** የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ዐቃቤ ሕግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሶዶ ከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09361 ህዳር6ቀን 2005 ዓ.ም፣ የሰጠው ፍርድና የወላይታ ዞን ከፍተኛፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 23731 በጥር 9ቀን 2005ዓ.ም የሰጠው ውሳኔናየደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎትመሰረታዊ የህግ ሥህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡በሥር ፍርድ ቤት አመካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ተከሳሽ (አመልካች) በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ለራሱ ብልጽግና ለማግኘት አስቦ ተካሳሹ የቅርብ ጓደኛው የሆነውን የግል ተበዳይ አቶ አሰፋ ደመቀ ሶዶ መርካቶ ክፍለከተማ ከሚገኘው የግል ድርጅቱ( ግሮሰሪ)በህዳር ወር 2003 ዓ.ም ዓ.ም በመሄድ ጨረታ አሸንፌአለሁ በማለትና በሚስቱ ሥም የተዘጋጀ ፐርፎርማ በማስያዝ ብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) ከወሰደ በኋላ ግል ተበዳዩ በሽማግሌ ሲጠይቀው ካመነ በኋላ ገንዘቡን ያልከፈለው ስለሆነ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ከስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ መጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ አመልካች ወንጀል አልፈጸምኩም፣ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡
2. ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ሥድስት የሰው ምስክሮች አቅርቧል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ የተጠሪ ምስክሮች የግል ተበዳይና አመልካች ጓደኞሞች መሆናቸውን፣ አመልካች የጋምጎፋ ዞን ደንባ ጎፋ ወረዳ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት አላቂ ዕቃ ለማቅረብ በጨረታ አሸንፌአለሁ፡፡ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) ስጠኝ በማለት በዕምነት ወስዶ አልመለሰም፡፡ ሌሎቹ ምስክሮች የግል ተበዳይንና አመልካችን ሲያሸማግሉ አመልካች ገንዘቡን የወሰደ መሆኑን

ለሽማግሌዎቹ ያመነ መሆኑን የመሰከሩ መሆኑን ጉዳዩ ያሳያል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከግል ተበዳይ በአደራ ወሰድኩት ገንዘብ ላለመኖሩ ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኃላተከሳሽ ጨረታ አሸንፌአለሁ በማለት ከግል ተበዳይ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያ የወሰደውን ብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) ያልመለሰ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ1የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከአምስት ወር እሥራት እንድቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝለ ወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡የዞኑ ከፍተኛፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ከሰማ በኂላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠውን የጥፋኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር195 ንዑስ አንቀጽ2(ለ)2 መሰረት አጽንቶታል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡

4. አመልካች ሚያዚያ 11ቀን200ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታየሥር ፍርድ ቤት፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትየሰጡትውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የግል ተበዳይ የሰጠው ምስክርነት ለአመልካች ብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) በብድር ሰጥቸው አልመለሰልኝም የሚል ነው፡፡ይህ ፍታብሔራዊ ግኑኝነትን ሚመለከት እንጂ ወንጀል አይደለም፡፡ በተጠሪ ክስም ሆነ ማስረጃ እኔ እንደፈጸምኩት የተገለጸው ተግባር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነነውን የእምነት ማጉደል ወንጀል የማቃቁምና በወንጀል ሕጉ በወንጀልነት ያልተደነገገነው፡፡ እንደዚሁም ተጠሪ ክስና ማስረጃ አመልካች በወንጀል ህጉ አንቀጽ23 መሰረት የህግ፣ የግዙፍ ተግባርና ሞራል ሁኔታ በተሟላበት ሁኔታ ወንጀል የፈጸምኩ አለመሆኑ ያላረጋገጠበት ሆኖ እያለ የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤት፣ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካችበወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከአምስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ23 የሚተላለፍና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሥለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶትና መልስ የሚያቀርብበት ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶት መልስ ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገጸው ሲሆን እኛምየሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካችበወኝጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከአምስትስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጡት ውሳኔተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥበመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለ መወሰን በመጀመሪያ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ መሰረታዊ ፍሬ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

6. ተጠሪ አመልካች የእምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ስለመሆኑ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ በይዘቱ፣ የግል ተበዳይና አመልካች ጓደኛሞች እንደሆኑ፣ አመመልካች የጋምጎፋ ዞን ደንባ ጎፋ ወረዳ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት አላቂ ዕቃ ለማቅረብ በጨረታ አሸንፌአለሁ፡፡ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) ስጠኝ በማለት የጠየቀው መሆኑንና ገንዘቡን የግል ተበዳዩ አመልካችንሰነዶችን በሚስቱ በኩል በማስፈረም በመያዥነት ይዞ ገንዘቡን ለአመልካች የሰጠው መሆኑን፣ አመልካች ገንዘቡን ለግል ተበዳይ ያልመለሰ መሆኑን እንዳስረዱ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትና ከላይ የተገለጹት ተግባራት የግል ተበዳይና በአመልካች መካከል የመሰረቱት ግኙኝነት አደራ ሰጭና የአደራ ተቀባይ ነው ወይስ አበዳሪና የተበዳሪ ግኑኝነት አመልካችና የተጠሪ ግኑኘነት አበዳሪና የተበዳሪ ግኑኙነት አላቸው ቢባልህጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው የሚሉት ጥያቄዎች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡
7. ከላይ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ፣ዝርዝር ይዘትናመሰረታዊ ዓላማ መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ በወንጀል ህጉ በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝርበት ምእራፍ ሁለት በልዩ ሁኔታ በተንቀሳቃሽ ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝረው ክፍል አንድ ሥር የተደነገገ የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሰረታዊ ባህሪ፣ ይዘትና የሚስከትለውን ኃላፊነት የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 ድንጋጌ የአማረኛ ቅጅ ቃል በቃል ሲነበብ ማንም ሰው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይምለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው የደረገ፣የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን መሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ3 የተከሳሹ ወንጀል ሃሳብ ግምት ሚደነግግ ሲሆን ይዘቱም ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ማዋል ሀሳብ እንዳለው ይቆጠራል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡
8. የእንግሊዘኛውን ቅጅ ስንመለከት- Breach of Trust የሚል ርዕሥ ያለው አንቀጽ 675 Whoever, with intent to obtain for himself or to procure for a third person an unjustifiable enrichment, appropriates, or procures for another, takes or causes to be taken, misappropriates, uses to his own benefit or that of a third person, or disposes of for any similar act, in whole or in part, a thing or a sum of money which is the property of another and which has been delivered to him in trust or for a specific purpose, is punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment, or with rigorous imprisonment not exceeding five years. በማለት በንዑስ አንቀጽ1 የሚደነግግ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ3 The intent to obtain for himself or to procure for third person an unjustifiable

enrichment shall be presumed where the criminal is unable upon call, to produce or repay the thing or sum entrusted, or at the time when he should have returned it or accounted there for. በማለት ይደነግጋል፡፡

9. አመልካች ከግል ተበዳይ ጨረታ ያሸነፍኩ ስለሆነ ለሥራ ማስኪጂያና ለቅድመ ክፍያ ብር 21000 ( ሃያ አንድ ሺ ብር) የጠየቀና የግል ተበዳይም የአመልካችን ሰነዶች በመያዥነት ይዞ የሰጠው መሆኑን በተጠሪ ማስረጃ እንደተገለጸ ተረድተናል፡፡ አንድ ሰው ለሌላወ የተበደረውን ነገር በአይነቱ ለመመለስ ተገዳጅ በማድረግ ገንዘብ ወይም በማገልገል የሚያልቅ ሌላ ነገር ለተበዳሪው ለመስጠትና ኃብትነቱን ለማስተላለፍ የሚፈጽሙት ተግባር የማያልቅ ነገር ብድር እንደሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2471 ከተሰጠው ትርጓሜ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንድን ነገር በብድር መሥጠትና አንድን ነገር በአደራ መስጠት የተለያየ ባህሪና ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ አደራ ተቀባዩ አደራ አስቀማጩ ሰጠውን ዕቃ ተቀብሎ በአደራ እንዲያስቀምጥለት የሚገባው ግደታና ተግባር መሆኑንከፍታብሔር ሕግ ቁጥር2779 ከተሰጠው ትርጓሜ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአደራ የተቀበሉትን ገንዘብ ለአደራ አስቀማጩ አለመመለስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 በመተላለፍ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ሊያስጠይቅ የማይችል የወንጀል ተግባር ነው፡፡

10. በአንጻሩ ተበዳሪ በብድር የወሰደውን ገንዘብ በወቅቱ አለመክፈሉ አግባብነት ባላቸው ህግ ድንጋጌዎች በፍታብሔር ከሚጠየቅ በሰተቀር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 ተላልፏል ተብሎ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ሊጠየቅ የማይችል መሆኑንከወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ ዝርዝር ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡.ማንም ሰው በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቀው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይምለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ፡፡ የአመልካች አድራጎትየወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ3 በሚደነግገው ወንጀል ሃሳብ ግምት የማይሸፈን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

11. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በህግ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ እንደማይችል በህገመንግስቱ አንቀጽ22 ንዑስ አንቀጥ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው የህግ ፣የግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ23 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ከላይ ዘረዘርነው የግዙፍ ድርጊት የህግ የሃሳብ ሁኔታዎች አልተሟሉም፡፡ ይህ ሁኔታ መሟላቱን ሳያረጋግጡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካችበወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድዓመት አምስት ወር እሥራት እንዲቀጣ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ፣ዝርዝር ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሰርታዊ የህግ ስህተት ያለበት በማለት ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የሶዶ ከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት ፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛፍርድ ቤትናየደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ቁጥር195 ንዑስ አንቀጽ2(ለ)1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ጨረታ አሸንፌለሁ በማለት ለሥራ ማስኬጃና ለቅድመ ክፍያ የሚሆን ብር21000(ሃያአንድሺ ብር) ከግል ተበዳዩ በብድር የወሰደውን ገንዘብ ለግል ተበዳይ አለመክፈሉ አለመመለሱ) አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቀው ባለመሆኑ በነጻ ይሰናበታል በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካች ከቀረበበት ወንጀል ክስ በነጻ ተሰናበተ በመሆኑ ከእስር እንዲለቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## 9.4 በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ ማውጣት[87]

- ቼክ ሰጥቷል ተብሎ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ከወንጀል ኃላፊነት ነፃ ሊወጣ የሚችለው ቼኩ የተሰጠው በዋስትና ወይም በመያዥያነት መሆኑን እና የዋስትናው አልያም የመያዣ ውሉም በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረዳት ሲቻል ነው፤[88]

የሰ.መ.ቁ. 161448

ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- የሺመቤት ጥላሁን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

---

[87]የሰ/መ/ቁ 161448 (ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25 እና በምዕራፍ አንድ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ርዕስ ስር ስለቼክ ማውጣት የተመለከተው እንደተጨማሪ ይመልከቱ፡፡

[88]ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ቼክ ለዋስትና (ለመያዣነት) በሚሰጥበት ጊዜ መሟላት ያለበትን መመዘኛን በተመለከተ በሰ/መ/ቁ 166392 (ሚያዚያ 26 ቀን 2012ዓ.ም ) ቅፅ 27 የሕግ ትርጉም በፍትሐብሔር ጉዳይ ላይ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የወንጀል ህጉ አንቀፅ 693(1) ተጠቅሶ በተጠሪ ላይ ባቀረበው ስድስት የወንጀል ክስ ላይ የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በአራተኛ ክስ ውስጥ ከተጠቀሰው ቼክ ውጭ ሌሎቹ የተሰጡት በተጠሪ እና ተበዳይ ተብለው በተጠቀሱት ግለሰቦች መካከል በነበረው የንግድ ግንኙነት መነሻነት ለካፒታል መዋጮ መተማመኛነት እንጂ ለምንዛሪ አለመሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት ክስ የቀረበበትን አንቀፅ ወደ አንቀፅ 693(2) በመቀየር የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ማግኘቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በሚል ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ የወንጀል ህጉን አንቀፅ 693(1) ድንጋጌን ጠቅሶ የሚያዙበት በቂ ገንዘብ ሳይኖራቸው ለተለያዩ አራት ሰዎች የተለያየ የገንዘብ መጠን የተፃፈባቸውን በጠቅላላው ስድስት ቼኮችን ሰጥተዋል በሚል ስድስት የወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ተጠሪ ቀርበው ቼኮቹ ለተበዳዮች የተሰጡት ለሚያቋቁሙት የጠጠር ማምረቻ አክሲዮን ማህበር የአባላትን ድርሻ ለማረጋገጥ ለመተማመኛ እንዲሆን እንጂ ለመመንዝር እንዳልሆነ በመግለፃቸው ፍርድ ቤቱ የተከሳሽነት ቃሉን በክህደት መዝግቦ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በመጨረሻም በአራተኛ ክስ ውስጥ ከተጠቀሰው ቼክ ውጭ ቀሪዎቹ ለካፒታል መዋጮ መተማመኛነት እንጂ ለምንዛሪ ያልተሰጡ መሆናቸውን በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጡን ጠቅሶ ከአራተኛ ክስ ውጭ ያሉትን አምስቱን ክሶች በተመለከተ ክስ የቀረበበት አንቀፅ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 113(2) መሰረት ወደ አንቀፅ 693(2) በመለወጥ አራተኛ ክስን በተመለከተ ደግሞ ክስ በቀረበበት አንቀፅ ስር ጥፋተኛ በማለት ለአራተኛ ክስ የእስራት ቅጣትን፤ ለተቀሩት ደግሞ የገንዘብ መቀጮ ቅጣትን መርጦ በጠቅላላው በ1(አንድ) ዓመት ከ8(ስምንት) ወር ፅኑ እስራት እና ብር 3,500(ሶስት ሺህ አምስት መቶ) እንዲቀጡ ከወሰነ በኋላ የእስራት ቅጣቱን አፈፃፀም በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ እንዲቆይ አዟል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ በአሁን አመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ/156522 ላይ ሚያዝያ 29/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልገው በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(1) መሰረት አቤቱታው በአብላጫ ድምፅ ሰርዟል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 18/2010 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ቃሉም ክስ የቀረበበት የወንጀል ህጉ አንቀፅ መሰረታዊ ዓላማ ቼክ አውጪው ቼክ ከማውጣቱ በፊት በባንክ ሂሳቡ ውስጥ በቂ ገንዘብ መኖሩን እንዲያረጋግጥ በማድረግ ለገንዘብ እንቅስቃሴ ጥበቃ ማድረግ ሆኖ እያለ ከድንጋጌው ዓላማ ውጭ በዋስትና የተሰጠ ነው ተብሎ ድርጊቱ ወደ ቸልተኝነት መቀየሩ ከህግ አግባብ ውጭ ነው፤ የተወሰነው ቅጣትም ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ጋር የማይመጣጠን ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ከግል ተበዳዮች ጋር ታርቀው ገንዘቡንም ባልከፈሉበት የእስራት ቅጣት ውሳኔውን አፈፃፀም መገደቡ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ከተመረመረ በኋላ የግራ ቀኙ የንግድ ግንኙነት መሰረት ተደርጎ ክስ የቀረበበት አንቀፅ ወደ አንቀፅ 693(2) የተቀየረበት እና ቅጣቱም የተገደበበት የህግ አግባብ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በአጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ ጥር 03/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ክስ ከቀረበባቸው ስድስት ቼኮች ውስጥ በአራተኛ ክስ ውስጥ ከተጠቀሰው ቼክ ውጭ ቀሪዎቹ የተሰጡት ከተበዳዮች ጋር በጋራ ላቋቋምነው ኩባንያ በተበዳዮቹ በኩል ለተደረገው የካፒታል መዋጮ ማረጋገጫነት እንጂ ለምንዛሪ አይደለም፤ ቼክን ጨምሮ የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶች በዋስትና ሊሰጡ የሚችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2863 የሚደነግግ በመሆኑ ድርጊቱ ወንጀል አይደለም፤ ለንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ ተብሎ የሚዋጣው መዋጮ የውል ግዴታን ከማቋቋም አልፎ የወንጀልም ሆነ ከውል ውጭ ኃላፊነትን የማያስከትል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2037 ላይ ተመልክቷል፤ የስር ፍርድ ቤትም ቼኮቹ በንግድ ግንኙነት ውስጥ ለካፒታል መዋጮ እንጂ ለምንዛሪ አለመሰጠታቸውን አረጋግጦ የወሰነ በመሆኑ በውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፤ ቅጣቱም ቢሆን የወንጀል ህጉን እና የቅጣት መሰረታዊ ዓላማን ያገናዘበ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር ቅሬታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ሞግቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው የግራ ቀኙ ክርክር የሚያጠነጥነው ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የሚችል መሆን አለመሆኑ እና ከወንጀል አኳያ በሚኖረው ውጤት ላይ ነው፡፡ ይህንን ነጥብ አስመልክቶ ይኸው ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ/67947 ላይ ሰኔ 15/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት "የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት በሚል በወንጀል ህጉ አንቀፅ 693(1) ውስጥ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ለማቋቋም ቼኩ ለክፍያ ባንክ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን/ያለመኖሩን/ ማረጋገጥ ብቻ በቂ ነው" የሚል የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ እናም ከወንጀል ተጠያቂነት አኳያ ቼክን ለዋስትና አልያም ከምንዛሪ ውጭ ለሆነ ሌላ ዓላማ ሰጥቻለሁ የሚለው የወንጀል ክስ መከላከያ ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡

ሆኖም ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/166392 ላይ ሚያዝያ 26/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቼክ እንደማንኛውም ሊተላለፍ እንደሚችል የንግድ ሰነድ በመያዥያነት ወይም በዋስትና ሊሰጥ የሚችል መሆኑን፤ ይህ ሲሆንም በንግድ ህጉ አንቀፅ 952 እና በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2864-2866 ላይ በተመለከቱት ጥብቅ መመዘኛዎች አግባብ መመራት እንዳለበት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በእርግጥ ይህ የህግ ትርጉም የተሰጠው በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ቢሆንም ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በማናቸውም ደረጃ ላይ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ላይ የአስገዳጅነት ባህሪ ያለው በመሆኑ በወንጀልም ሆነ በፍትሐ ብሄር ጉዳይ ላይ የሚሰጠው የህግ ትርጉም አንዱ ሌላውን እንዳያፋልስ እና ውጤትም እንዳያሳጣ ወጥነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ/67947 ላይ የተሰጠው የህግ ትርጉም ባለበት በኋላ ላይ የተሰጠው ትርጉም በወንጀል ጉዳይ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ በውጤት ደረጃም ሲታይ አንድ ቼክ አውጪ በፍትሐ ብሔር ክስ ቼኩን ለዋስትና አልያም ለመያዥያነት የሰጠ ስለመሆኑ አረጋግጦ ከክሱ ነፃ ቢባል እንኳን በወንጀል ጉዳይ በቼክ ማጭበርበር ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ይቀጣል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከወንጀል እና ፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ተፈጥሮዓዊ ባህሪ እና ከሚያስከትሉት ውጤት አኳያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

እናም ቀደም ሲል የወንጀል ህጉ አንቀፅ 693(1) አተረጓጎምን አስመልክቶ በሰ/መ/ቁጥር 67947 ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ትርጉሙ የተሰጠበትን ድንጋጌ መሰረት አድርገው የሚቀርቡትን የወንጀል ክሶችን ተግባራዊ አፈፃፀም መሰረት በማድረግ የድንጋጌው አተረጓጎም እና አተገባበር አጠቃላይ ከወንጀል ህግ መሰረተ ሀሳብ እንዲሁም በዚሁ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 166392 ላይ ከተሰጠው ትርጉም አኳያ ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ አግባብ ቀድሞ የተሰጠው የህግ ትርጉም "በወንጀል የተከሰሰ ቼክ አውጪ ቼኩን ለዋስትና ወይም ለመያዥያነት የሰጠ ለመሆኑ እና የዋስትና ወይም የመያዥያ ውሉም በንግድ ህግ ቁጥር 952 እና በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2864-2866

በተመለከተው አግባብ የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረዳት ከቻለ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ አይገባም" በሚል በተሻሻለ ትርጉም ተተክቷል፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይም ከዚሁ ከተሻሻለው የህግ ትርጉም አንፃር ተቃኝቷል፡፡ ተጠሪ አጥብቀው የሚከራከሩት ክስ ከቀረበባቸው ስድስት ቼኮች ውስጥ አምስቱ ለምንዛሪ ሳይሆን ለካፒታል መዋጮ የተሰጡ በመሆኑ በወንጀል ልጠየቅ አይገባም በሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ክስ የቀረበበትን አንቀፅ ወደ ቸልተኝነት አንቀፅ የለወጠው አምስቱ ቼኮች በተጠሪ እና የግል ተበዳዮች መካከል በነበረ የንግድ ግንኙነት ለካፒታል መዋጮ የተሰጡ ስለመሆናቸው አረጋግጫለሁ በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ ፍርድ ቤቱ በዚህ መልኩ ሲወስን ከላይ የተመለከተው የህግ ትርጉም ያልተሰጠ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለው በሰ/መ/ቁ/67947 ላይ ተሰጥቶ የነበረው ነው፡፡ በዚህ ትርጓሜ መሰረት ደግሞ ቼክን ለዋስትናም ሆነ ለሌላ ከምንዛሪ ውጭ ለሆነ ዓላማ ሰጥቻለሁ የሚለው ጉዳይ ለወንጀል ክስ መከላከያነት ሊውል የሚችል አይደለም፡፡ እናም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ምክንያት ጠቅሶ ድርጊቱን ወደ ቸልተኝነት አንቀፅ መቀየሩ ከድንጋጌው አፈፃፀም እና አተረጓጎም አኳያ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ ነው፡፡ ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ ውሳኔ ደግሞ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4(ሸ)) የሚደነግግ በመሆኑ ውሳኔው በእርግጥም ሊነቀፍ የሚገባው ነው፡፡

ሆኖም ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ ቀድሞ ከተሰጠው የህግ ትርጉም የተለየ ትርጉም የተሰጠ በመሆኑ የተጠሪ መከራከሪያ ተሻሽሎ ከተሰጠው የህግ ትርጉም አኳያ ስለሚኖረው ውጤት ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ እንግዲህ ተሻሽሎ በተሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ ሰጥቷል ተብሎ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ከወንጀል ኃላፊነት ነፃ ሊወጣ የሚችለው ቼኩ የተሰጠው በዋስትና ወይም በመያዣያነት መሆኑን እና የዋስትናው አልያም የመያዣያ ውሉም በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረዳት ከቻለ ነው፡፡ አሁን በቀረበው ጉዳይ ተጠሪ ቼኩን ለካፒታል መዋጮ ማረጋገጫነት ስለመስጠታቸው ያረጋገጡት በሰው ምስክር ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በተሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት ቼኮቹ ስለመሰጠታቸው የተረጋገጠ ነገር ባለመኖሩ የተሻሻለው ትርጉም በተጠሪ የወንጀል ኃላፊነት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/187459 ላይ ጥር 22/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና ይህንኑ ፍርድ በማፅናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/156522 ላይ ሚያዝያ 29/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ቁጥር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሻሽሎ ተጠሪ በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ እና 6ኛ ክሶች በወንጀል ህግ አንቀፅ 693(1) ስር ጥፋተኛ ናቸው ተብሏል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ የጥፋተኝነት ፍርድ ለተሰጠበት የወንጀል ህጉ ድንጋጌ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ደረጃ እና እርከን የወጣለት ነው፡፡ ተጠሪ በአምስቱ ክሶች ውስጥ በቂ ስንቅ ሳይኖራቸው ሰጥተዋል በተባሉት ቼኮች ላይ ያለው የገንዘብ መጠን እንደ ቅደም ተከተላቸው ብር 5,000,000(አምስት ሚሊዮን ብር)፣ ብር 1,000,000(አንድ ሚሊዮን ብር)፣ ብር 240,000(ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር)፣ 100,000 ዩሮ(አንድ መቶ ሺህ ዩሮ) ወይም ብር 2,205,000(ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺህ ብር) እና ብር 500,000(አምስት መቶ ሺህ ብር) ነው፡፡ በዚሁ አግባብ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት 1ኛ ክስ ደረጃ 10፣ የእስራት ቅጣት እርከን 23 እና መቀጮ እርከን 6፤ 2ኛ ክሰ ደረጃ 8 የእስራት ቅጣት እርከን 19 እና መቀጮ እርከን 6፤ 3ኛ ክስ ደረጃ 6 የእስራት ቅጣት እርከን 15 እና መቀጮ እርከን 4፤ 5ኛ ክስ ደረጃ 10 የእስራት ቅጣት እርከን 23 እና መቀጮ እርከን 6፤ 6ኛ ክስ ደረጃ 7 የእስራት ቅጣት እርከን 17 እና መቀጮ እርከን 5 ይሆናል፡፡

የእስራት ቅጣትን በተመለከተ በቅጣት እርከኖች ስር በተቀመጠው ፍቅደ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣታቸው ብቻ ተወስዶ ሲደመሩ 22 ዓመት ፅኑ እስራት ይሆናል፡፡ የገንዘበ ቅጣትን በተመለከተ እርከን 4 እስከ ብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር)፣ እርከን 5 እስከ ብር 7,000 (ሰባት ሺህ ብር) እና እርከን 6 እስከ ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የሚደርስ ነው፡፡ በእነዚህ እርከኖች ስር አማካይ ቅጣት ተወስዶ ሁሉም ሲደመሩ በጠቅላላው እስከ ብር 35,500(ሰላሳ አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይሆናል፡፡ የእስራት እና የገንዘብ አማካይ ቅጣቱ ተጠሪ በ4ኛ ክስ ስር ጥፋተኛ ከተባሉበት ጋር ሲደመር የእስራት ቅጣቱ 24 ዓመት ከ9 ወር ፅኑ እስራት እና እስከ ብር 39,500(ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ብር) የገንዘብ ቅጣት ይሆናል፡፡ ይህም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አባሪ አንድ በእስራት እርከን 37 እና መቀጮ እርከን 9 ስር የሚገኝ ነው፡፡

በሌላ በኩል በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት እና አምስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መኖራቸውን ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ይዘት ለመገንዘብ የተቻለ በመሆኑ እና በእነዚህ የቅጣት አስተያየቶች ላይ የቀረበ መከራከሪያ ባለመኖሩ ምክንያቶቹ በዚህ ችሎትም ተወስደዋል፡፡ በዚሁ አግባብ በሚደረግ ስሌት መጨረሻ ቅጣቱ የሚሰላው በእስራት እርከን 34 እና መቀጮ እርከን 6 ስር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለዚህ እርከን የተቀመጠው ቅጣት ደግሞ ከ15(አስራ አምስት) ዓመት እስከ 18 (አስራ ስምንት) ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና እስከ ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የሚደርስ መቀጮ ነው፡፡ እናም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በሚደረስ ስሌት ተጠሪ በትንሹ 15 ዓመት ፅኑ እስራት ይቀጣሉ ማለት ነው፡፡

ይሁንና ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት እንዲሁም ከድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ አኳያ የዚህ ቅጣት ተመጣጣኝነት እና አስተማሪነቱም መፈተሽ ያለበት ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንግዲህ የወንጀል ቅጣት ቀዳሚ ዓላማው ወንጀል ፈፃሚዎችን በማረም በቀሪ ህይወታቸው ከመሰል ድርጊት ታቅበው መልካም ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ የቅጣት ውሳኔ የወንጀል አጥፊዎችን ለማረም ደግሞ አጥፊው ከፈፀመው የወንጀል ድርጊት ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ አገላለፅ የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ቀላል ወይም የአጥፊውን አደገኛነት የማያሳይ ሆኖ እያለ የተጋነነ ቅጣት የሚወሰንበት ከሆነ ወይም ድርጊቱ ከባድ ሆኖ አነስተኛ ቅጣት የሚወሰን ከሆነ አጥፊውንም ሆነ ሌላውን ማህበረሰብ የማያስተምር በመሆኑ የወንጀል ቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ ዓላማን የማያሳካ ነው ማለት ነው፡፡ ሥራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያም በመርህ ደረጃ የትኛውም የወንጀል ቅጣት ውሳኔ በመመሪያው መሰረት እንዲወሰን ካዘዘ በኋላ ከመመሪያው ውጭ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበትን ሁኔታ በአንቀፅ 27 ስር ያስፈረውም በዚሁ መነሻነት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ተጠሪ የተከሰሱትም ሆነ በወንጀል ጥፋተኛ የተባሉት ስድስት የተለያየ የገንዘብ መጠን የተፃፈባቸውን ቼኮች ለአራት ግለሰቦች ሰጥተዋል በሚል ነው፡፡ በ4ኛ ክስ ውስጥ ከተጠቀሰው ቼክ ውጭ ቀሪዎቹ የተሰጡበት ሁኔታ የተጠሪን የወንጀል ኃላፊነት የሚያስቀር ባይሆንም በተጠሪ እና በቼክ ተቀባዮቹ መካከል በነበረው የጋራ የንግድ ስራ ውስጥ የተሰጡ ለመሆናቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ የዚህ ድርጊት አፈፃፀም ሁኔታ ሲታይ የተጠሪን ወንጀል የመፈፀም አደገኛነት የሚያሳይ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በንግድ ግንኙነት ውስጥ በተሰጠ ቼክ መነሻነት ተጠሪ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በተለየው የእስራት ቅጣት እንዲቀጡ መወሰኑ ከተፈፀመው ድርጊት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ቅጣቱ የወንጀል ህጉን አላማና ግብ የማያሳካ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቅጣቱ ከመመሪያው በመውጣት በወንጀል ህግ አንቀፅ 88(2) እና 179 መሰረት መወሰን እንደሚገባው ታምኗል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ድርጊት የተፈፀመበት ከባቢያዊ ሁኔታ እና የተጠሪን አደገኛነት መጠን ከግንዛቤ በማስገባት ለሁሉም የወንጀል ድርጊቶች ተጠሪ ከዚህ በፊት በዚሁ ጉዳይ የታሰሩት ካለ ታስቦበት በ5(አምስት) ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 10,000(አስር ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡ በሌላ በኩል በወንጀል ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለማስተማር ሁሌም

ወደ ማረሚያ ቤት መላክ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ ይልቁንም ለጥፋተኛው አንድ የፈተና ጊዜ ከፅኑ ማስጠንቂያ ጋር ሰጥቶ አመሉ ቢፈተሽ መልካም ይሆናል ተብሎ ሲታመን የእስራት ቅጣቱን አፈፃፀም ለጊዜው አግዶ ማቆየት እንደሚቻል ከወንጀል ህጉ አንቀፅ 192 እና ተከታዮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ሊገደብ የማይቻልባቸው ልዩ ሁኔታዎች ደግሞ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 ስር በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ በእነዚህ መመዘኛዎች መሰረት የአሁን ተጠሪ ላይ በዚህ ችሎት የተላለፈው የእስራት ቅጣት ውሳኔ እንዳይገደብ የተቀመጠ ክልከላ ባለመኖሩ የቅጣቱ አፈፃፀም በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. ከወንጀል ህግ አንቀፅ 693(1) አተረጓጎም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በዚሁ ችሎት በሰ/መ/ቁር67947 ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም በፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 26 መሰረት ተሻሽሏል፡፡ በዚሁ አግባብ "በወንጀል የተከሰሰ ቼክ አውጪ ቼኩን ለዋስትና ወይም ለመያዥያነት የሰጠ ለመሆኑ እና የዋስትና ወይም የመያዥያ ውሉም በንግድ ህጉ እና በፍትሐ ብሔር ህጉ በተመለከተው መመዘኛ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረዳት ከቻለ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ አይገባም" ተብሏል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/187459 ላይ ጥር 22/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና ይህንኑ ፍርድ በማፅናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/156522 ላይ ሚያዝያ 29/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2)) መሰረት ተሻሽሎ ተጠሪ በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ እና 6ኛ ክሶች በወንጀል ህግ አንቀፅ 693(1) ስር ጥፋተኛ ናቸው ተብሏል፡፡
3. በውሳኔ ተራ ቁጥር 2 ስር በተገለፀው አግባብ ተጠሪ ጥፋተኛ በተባሉበት ስድስቱም ክሶች በጠቅላለው በአምስት ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የመቀጮ እንዲቀጡ ተወስኖ የእስራት ቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም በ4(አራት) ዓመት የፈተና ጊዜ እንዲቆይ ተወስኗል፡፡
4. ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 197(2) መሰረት ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆን ዘንድ ብር 5,000(አምስት ሺህ) የአራት ዓመት ጊዜው እስኪጠናቀቅ ድረስ በዋስትና ያስይዙ፡፡
5. የቅጣት ውሳኔው ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ውጭ የተወሰነ መሆኑን እንዲያውቅ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፍርድ ቤቱ ለሚመለከተው የስራ ክፍል እንዲተላለፍ በመመሪያ አንቀፅ 27(3) መሰረት ታዟል፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሃሣብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 4 እና 7 ስር የተሰየምነው የችሎቱ ዳኞች ከባልደረቦቻችን /አብላጫው ድምጽ ከያዙት/ የወንጀል ቅጣትን አስመልክቶ በሰጡት የውሣኔ ሃሣብ ላይ የተለየ ሀሳብ ስላለን ለልዩነት ያበቃንን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

የቀረበው ጉዳይ በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ በማውጣት የሚፈፀም ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን አስቀድሞ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቼክ ማታለልን አስመልክቶ የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ተሰጥቶ የነበረውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተወሰኑ መመዘኛዎች እንዲጨመሩበት በማድረግ እንዲሻሻል መደረጉ ተገቢና የምናምንበት ውሳኔ ነው፡፡

ሆኖም በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት አስመልክቶ አብላጫውን ድምጽ የያዙት የዚህ ችሎት ዳኞች ቅጣቱ ሊወሰን የሚገባው ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰን *መመሪያ* ቁጥር 2/2006 ከሚደነግገው *መደበኛ* የቅጣት አወሳሰን *መ*ርህ በመውጣት እንዲወሰን የሚወሰነው ቅጣት አፈፃፀምም በፈተና ጊዜ ተገድቦ እንዲቆይ የተደረሰበት *መደምደሚያ* ላይ የምንስማማበት አይደለም፡፡

ምክንያቱም፡-

1ኛ. የቅጣት አላማው እና ግቡ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን *መንግሥት*፣ የሕዝቦቿን፣ የነዋሪዎቹን፣ሰላም፣ደህንነት፣ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም ማረጋገጥ እና ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል፣ ስለ ወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆን ወይም እንዲታረሙ ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 1 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በአንድ ሰው ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ ክርክር መርምረው ጥፋተኛ ሆነው ባገኙት ሰው ላይ ቅጣት ሲወስኑ ይህን አላማና ግብ ሊያሳካ የሚችልና በተጠቀሰው የወንጀል ህግ ተቀባይነት ያገኙትን የቅጣት አወሳሰን መርሆችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል፡፡

የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 3 የቅጣት አወሳሰን መመሪያው የወጣበት ዋና ዓላማ የዳኝነት አካሉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ውጤታማና ተገማችነት ያለው ቅጣት የሚሰጥበትን ሥርዓት መመስረት ሲሆን፣ ግቦቹም ተቀራራቢና ተገማች የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለው ቅጣት እንዲወሰን፣ እንደ ወንጀሉ ክብደትና አደገኝነትም የቅጣትን ተመጣጣኝነት ማረጋገጥ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በአጥፊዎች ላይ የሚወስኑትን ቅጣት በዚህ *መመሪያ* መሰረት ለመወሰን የማያስችል ነገር ካላገጠማቸው በስተቀር ቅጣቱ የሚወሰነው የቅጣት አወሳሰን መመሪያውንና አጥፊው ጥፋተኛ የተባለበትን ልዩ ድንጋጌ የሚያስቀምጠውን ቅጣት መሰረት በማድረግ መሆን ይገባዋል፡፡

ሆኖም የተለየ ነገር ሲያጋጥማቸው በቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* አንቀጽ 27/1 ስር በተደነገገው መሰረት ከመመሪያው ውጪ ወጥተው ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ እንደሚታወቀው በህግ አተረጓጎም የተለየ ነገር ሲባል በዋናው መርህ መሰረት ሊወሰን የማይችል በጠባቡ ሊተገበር የሚገባ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በወንጀል አጥፊዎች ላይ ቅጣት ሲወስኑ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ሲወጡ ከወዲሁ ከሌላው የተለየ በወንጀል አፈፃፀሙም ሆነ ባህሪው በዚህ *መመሪያ* ደረጃ በወጣላቸው ሊወከል የማይችል ሆኖ ባገኘው ጊዜ ወይም በዚህ *መመሪያ* በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ነው ብሎ ለማመን የሚያስችል ነገር ሲገጥማቸው ሊሆን ይገባል፡፡

በዚህ መርህ መሰረት አብላጫው ድምጽ ተጠሪ ላይ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው ከቅጣት መመሪያው ተወጥቶ ነው ሲል የደረሰበት *መደምደሚያ* አመልካች ላይ የቅጣት መነሻው ከብዶ እና በማቅለያ ምክንያት ቀልሎም ቢሆን 15 ዓመት ጽኑ እስራት ይሆናል፤ ይህ ደግሞ አስተማሪነቱ መፈተሽ አለበት በሚል እና በተጠሪ ላይ የሚጣለው ቅጣት አጥፊውን ሆነ ማህበረሰቡን አያስተምርም የሚል እሳቤን በመያዝ ነው፡፡

ነገር ግን ቼክን አስመልክቶ ህግ አውጭው ቅጣቱን ከፍ አድርጐ ያስቀመጠበት የማያወላዱ ምክንያቶች ያሉት ስለመሆኑ ልብ ሊባል የሚገባው ነው ብለን እናምናለን፡፡ ምክንያቱም በቼክ የሚገበያዩ ሰዎች ስለ ቼክ በቂ እውቀት ያላቸው፣ በአገር ኢኮኖሚ እና በባንኮች ተአማኚነት ላይ የሚያመጣውንና የሚያደርሰውን ጉዳት ጠንቅቀው የሚረዱ መሆናቸውን እንዲሁም በቼክ አውጪና በቼክ ግብይት ፈፃሚዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን መተማመን ለማስጠበቅ ታስቦ እንደሆነ ግንዛቤ የሚወሰድበት

ነው፡፡ ይሄን በመድፈር በቂ ሰንቅ የሌለው ቼክ በማውጣት ወንጀል መፈፀማቸው የተረጋገጠባቸው ሰዎች የሚወሰንባቸው ቅጣት የተለየ ነገር ካላጋጠመ በስተቀር በመመሪያው መሰረት ሊሆን እንደሚገባ የሚያከራክር አይሆንም፡፡ በያዝነው ጉዳይ አብላጫው ድምጽ ያየዙት የስራ ባልደረቦቻችን የአመልካች ቅጣት ከመመሪያው በመውጣት ቅጣቱን ለመወሰን ያበቃቸው ምክንያት ቅጣቱ ከብዷል በሚል ምክንያት እንጂ የአመልካች የወንጀል ድርጊት በቅጣት መመሪያው አንቀጽ 24/1 ስር የወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባህርይው በመመሪያው ደረጃ በወጣላቸው ሊወከል የማይችል ሆኖ ያልተገኘ ወይም መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ስለመሆኑ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሚላ ሌላ የማይታለፍ ምክንያት ስላጋጠመ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው በመውጣት ቅጣት ለመወሰን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሳይኖር ቅጣት በዝቷል በሚል ምክንያት ብቻ በሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ከመመሪያው በመውጣት ቅጣት መወሰን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የፍርድ ቤቶችን ተገማችነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው ብለን እናምናለን፡፡

2ኛ. ስለተወሰነው ቅጣት አፈፃፀም መገደብን የሚመለከት ነው፡፡ በአንድ የወንጀል ጥፋተኛ ላይ የተወሰነው ቅጣት አፈፃፀሙን ለተወሰነ የፈተና ጊዜ ተገድቦ ስለሚቆይበት ሁኔታ ወይም መስፈርቶችን በሚመለከት፡-

- ጥፋተኛ የተባለው ሰው አስቀድሞ የተፈረደበት መሆን አለመሆኑን ግምት ውስጥ ሳይገባ፣
- ቅጣቱ ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ታግዶ ቢቆይ አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ የጥፋት ድርጊት ከመፈፀም የሚቆጠብ ወይም የሚታገድ ስለመሆኑ ሲታመንበት እና፣
- ስለአመሉ መሻሻል አንድ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምንበት የወሰነው ቅጣት አፈፃፀም በገደብ ሆኖ እንዲቆይ ሊወሰን እንደሚችል የወንጀል ህግ አንቀጽ 192 ይደነግጋል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪም በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይፈፀም በመልካም ጠባይ እንደሚመራ የተጣለበትን የገደብ ግዴታ የሚቀበል በተቻለው መጠን በጥፋቱ ምክንያት ያደረሰውን ጉዳት ሁሉ እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እንዲሁም የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ሲሰጥ እንደሆነ የወንጀል ህግ አንቀጽ 197 ይደነግጋል፡፡
- እንዲሁም የቅጣት ገደብ ጥያቄ ጥፋተኛ በተባለው ሰው ስለተጠየቀ ብቻ የሚሰጥ መብት ሳይሆን የዳኞችን ፈቃድ መሰረት ያደረገ እና የሚከለክልም ሆነ የሚፈቅድ ሲሆን ክርክር የሚደረግበትና ማስረጃም የሚቀርብበት ስለመሆኑ ህጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ከመጀመሪያውም ቢሆን በአመልካች ላይ የሚወሰነው ቅጣት ከመሪያው ሊወሰን አይገባም የሚል የፀና እምነት ያለን በመሆኑ ቅጣቱ ከ 5 አመት በላይ እንደሚያስቀጣ አያከራክርም፡፡  በሌላ በኩል ተጠሪ ቼክ አውጥቷል የተባለው 6 የተለያዩ ቼኮችን በመሆኑ ምንም እንኳን 5ቱን ያወጡት ከግል ተበዳዮች ጋር ባላቸው የንግድ ግንኙነት ነው ቢባል ቀጥለውም ሌላ ቼክ ፈርመው መስጠታቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ ተደራራቢ ወንጀል የፈፀሙ መሆናቸው እንዲሁ ተረጋግጧል፡፡ ገደብ ለመከልከል የተቀመጡት መስፈርቶችን ስንመለከት ደግሞ ከ5 ዓመት በላይ የሚቀጣ ያልሆነ እንደሆነ እና ተጠሪ ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ እልባት ሳያገኝ ከታሰሩበት መጥተው ጉዳዩን ወደ ችሎት መቅረብ ያቆሙ በመሆኑ የቅጣት ገደብ ከመስጠቱ በፊት በገደቡ ላይ የተጣሉባቸውን ግዴታዎች መቀበል አለመቀበላቸው ሳይረጋገጥ የተወሰነባቸውን የእስራት ቅጣት ከሚፈጽሙ ይልቅ በውጪ ሆነው አመላቸው ቢፈተን ሌላ ወንጀል ከመፈፀም ይገደባሉ የተጣለውንም ገደብ ያከብራሉ ተብሎ እምነት ለመያዝ የሚያስችሉ ምክንያቶች ባልተረጋገጠበት ስለአመላቸው መሻሻል ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ በችሎት ተገኝተው እንኳን የዳኛ ተግሳጽን ሊቀበሉ የማይችሉበት ሁኔታ የተወሰነባቸው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም በገደብ እንዲሆን መወሰኑን የወንጀል ህግን አላማና ግብ የቅጣት መመሪያው መሰረት እና አስቀድሞ ከዚህ ሰበር ሰሚ

ችሎት በሰ/መ/ቁ. 171503 በሆነው ላይ ከተሰጠው የህግ ትርጉም ጋር የማይጣጣም ነው ብለን ስላላመን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

<u>**የማስማሚያ ሀሳብ**</u>

በንግድ ህጉ አንቀፅ 952 እና በፍታብሄር ህግ ቁጥር 2864፤2865 እና 2866 ላይ የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎች ያሟላ ቼክ በመያዥያነት ወይም በዋስትና የሰጠ ቼክ አውጪ በወ/ህ/አ.693(1) የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ በማውጣት ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት በሰ/መ/ቁ.67947 የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ በመቀየር በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ የምስማማበት ቢሆንም የስራ ባልደረቦች ወደዚህ መደምደሚያ የደረሱት ከመነሻውም የህጉ አቀራረፅ ግልፅ ያልሆነ በዚህ አግባብም ትርጉም የሚያስፈልገው መሆኑን መነሻ ሳያደርጉ ከዚህ ይልቅ የቀደመውን ውሳኔ ለመቀየር በቂ ተደርጎ የተቀመጠው በወንጀልም ሆነ በፍትሐ ብሄር ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን የህግ ትርጉም ወጥነት ከማረጋገጥ አንፃር ብቻ በመሆኑ በኔ እይታና ግንዛቤ የወ/ህ/አ.693 ለብቻው ሳይሆን በወንጀል ህጋችን ተካትቶ ከተቀመጠበት ምዕራፍ አንፃር በማየትና በመመርመር ትርጉም ሊሠጠው ይገባል የሚል እምነት ስላለኝ በዚህ አግባብ በሰ/መ/ቁ.67947 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመቀየር የሚከተለውን ምክንያት በተጨማሪነት ሊካተት ይገባል በማለት የማስማሚያ ሀሳቤን እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የወ/ህ/አ.693 በወንጀል ህጋችን በስድስተኛ መፅሀፍ በንብረት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ስር በምዕራፍ ሶስት፤ ክፍል አንድ ማታለልን ካካተቱ ወንጀሎች ጋር የተቀመጠ መሆኑ ለክፍሉ ከተሰጠው አርዕስት ስንነሳ በወ/ህ/ቁ.693 የተመለከተው የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት የወንጀል ድርጊት የማታለል ድርጊትን የሚወክል ከማታለል የወንጀል ድርጊት ጋር የሚጠቃለል የወንጀል ተግባር መሆኑን ያሳያል፡፡በወ/ህ/አ.693 የተመለከተው ድርጊት በቼክ ማውጣት የሚፈፀምን የማታለል ድርጊትን የሚወክል ከሆነ ደግሞ በወ/ህ/አ.693 አንድን በሂሳቡ ውስጥ በቂ ገንዘብ ሳይኖረው ቼክ ፅፎና ፈርሞ የሰጠን ሰው ጥፋተኛ ለማለት ቼክ በሚወጣበት ወይም ቼኩ ለክፍያ ባንክ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ቼኩን የተቀበለውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም አታልሎ የቼክ ተቀባዩን ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት መፈፀሙ በተጨማሪነት ሊረጋገጥ የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ በኔ እምነት የቼክ ተቀባዩ ቼኩን በሚቀበልበት ወቅት መታለል ወይም አለመታለልን አስመልክቶ ለማረጋገጥ ሁሉንም የማስረጃ አይነቶች መቀበል ለክርክሮች መንዛዛት፤በዚህ አግባብም ፍርድ ቤቶችን ላልተፈለገ ጫና የሚዳርግ በመሆኑ በዚህ የሕግ ትርጉም ሊጠቀም የሚገባውም ምክንያታዊ እና ጥንቁቅ ቼክ አውጪ ብቻ ሊሆን ይገባል ብዬ ሰለማምን፤ በንግድ ህጉ አንቀፅ 952 እና በፍታብሄር ህግ ቁጥር 2864፤2865 እና 2866 ላይ የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎች ያሟላ ቼክ በመያዥያነት ወይም በዋስትና የሰጠ ቼክ አውጪ ይህንኑ መስፈርት ያሟላ የመያዢያ የዋስትና ውል በማቅረብ ማስረዳት ከቻለ ፤ቼኩ የህጉን መስፈርት ያሟላ መያዥያ መሆኑን እያወቀ አምኖ የተቀበለው ቼክ ተቀባይ ተታልሏል፤ቼክ አውጪውም ቼኩን በመፃፍ ለቼክ ተቀባዩ ሲሰጥ ጀምሮ የቼክ ተቀባዩን የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት ተጠቅሟል በዚህ አግባብም አታልሎ የቼክ ተቀባዩን ወይም የሶስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት ፈፅሟል ሊባል ስለማይችል በንግድ ህጉ አንቀፅ 952 እና በፍታብሄር ህግ ቁጥር 2864፤2865 እና 2866 ላይ የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎች ያሟላ ቼክ በመያዥያነት ወይም በዋስትና መስጠቱ የተረጋገጠ ቼክ አውጪ በወ/ህ/አ.693(1) የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ በማውጣት ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት ተጨማሪ የህግ ምክንያትን በማስቀመጥ የማስማሚያ ሀሳቤን አስፍሬያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

## 9.5 በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ ማውጣት የአሳብ ክፍል[89]

- ተሰጠ በተባለው ቼክ ለማን እንደሚከፈል ከየትኛው ባንክ እንደሚከፈል እንዲሁም ተጠሪ ፊርሞ የገንዘብ መጠኑ ተገልፆ የተሰጠ እና ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ እያወቀ ቼክ የሰጠ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሹ ባላቸው የግል ግንኙነት መሰረት በማድረግ ብቻ ወንጀሉ የፈፀመው በቸልተኝነት ነው ለማለት አይቻልም፡፡[90]

የሰ/መ/ቁ 149071

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች፡-** የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ

**ተጠሪ፡-** አቶ አሰግድ አባ ቦሬ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 003731 በቀን 27/10/2009 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 145134 መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ አቅርቧል ይዘቱም፡- አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ ግንቦት 23 ቀን 2008 ዓ/ም በግምት ከጥዋቱ 4:30 ሰዓት አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ካቴድራል ት/ቤት ተብሎ ከሚጠራ አካባቢ ለግል ተበዳይ አቶ ጊቱ ተፈራ ቁጥሩ 20552352 የሆነ እና ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የሚመነዘር የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፊርሞ ከሰጠው በኋላ የግል ተበዳይ በ02/03/2009 ዓ/ም ቼኩን ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የለውም በመባሉ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶት ተቃውሞ እንደሌለው ገልፆ፣ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ደርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የአመልካች ምስክሮች

---

[89]የሰ/መ/ቁ 149071 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23

[90]የሰ/መ/ቁ 67947 (ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ 77592 (ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 149071 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23፣የሰ/መ/ቁ 152755 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23 ፣የሰ/መ/ቁ 225645 (ጥቅምት 29 ቀን 2015)፣የሰ/መ/ቁ 231232 (የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም )

እንዲሰሙ ባዘዘው መሠረት ምስክር ቀርበው በሰጡት የምስክርነት ቃል ተጠሪ በ23/09/08 ዓ/ም 4፡00 ሰዓት ላይ ካንትሪ ታወር የግል ተበዳይ ቢሮ ውስጥ 5ኛ ፎቅ መጥቶ ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የሚመነዘር የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፈርሞ ከሰጠኝ በኋላ ለመመንዘር ባንክ ስሄድ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ባንክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የሌለ መሆኑን የተለገፀላቸው መሆኑን መስክረዋል ፣ አመልካች በፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ቃል እና ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል በሰጠው ብይን ተጠሪ የመከላከል ምስክሮች አቅርቧል፡፡ ምስክሮቹም ተከሳሽ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያለቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መስክርዋል፡፡ተከሳሽ እና የግል ተበዳይ የሚያደርጉት የንግድ ግንኙነት በዱቤ ሽያጭ መሆኑ ሰነድ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው ስለሆነና ቼኩን የሰጠው በመተማመኛ መልኩ እንጂ የሚመነዘር አለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ቼኩ በቸልተኝነት የተሰጠ ነው በማለት የቀረበበት ክስ ፍርድ ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113 መሰረት በመቀየር ተከሳሽን በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(2) ስር ጥፋተኛ በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ተከሳሽን፡፡ በስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ29/02/2010 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ፡- ተጠሪ በወ/ህ/ዓንቀፅ 693(1) መሰረት ጥፋተኛ ሊባል ሲገባው በቸልተኝነት የተፈፀመ ሊያስብል በወ/ህ/ዓንቀፅ 59 መሰረት የሚያሳይ ማስረጃ ሳይኖር በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(2) ስር በመቀየር የስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተሽሮ ተጠሪ በተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቅጣት እንዲሰጥበት አመልክቷል ፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርቦ በፅሁፍ መልስ እንዲሰጥ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ መልስ በፅሁፍ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የአሁኑ ተጠሪ ቼኩን ለግል ተበዳይ የሰጡት በነበራቸው ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዲሁም የዱቤ ሽያጭ ቼክ ይሰጥ የነበረው በመተማመኛ መልኩ እንጂ የሚመነዘር አለመሆኑ ተመስክሯል ተብሎ በክሱ ላይ የተመለከተውን ወ/ህ/ዓንቀፅ 693(1) ወደ በወ/ህ/ዓንቀፅ 693(2) በመቀየር ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው በማለት የተወሰነበት አግባብነት ለመመርመር ሲሆን ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ለግል ተበዳይ ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ የሚመነዘር በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፈርሞ የሰጠ መሆኑ የግል ተበዳዩ ለመመንዘር ባንክ ስሄድ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ባንክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የሌለ መሆኑን የተለገፀላቸው መሆኑን ፣ ተጠሪ በፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ቃል እና ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡

የተጠሪ የመከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ተከሳሽ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያለቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ

ስለመሆኑ መመስከራቸው ነው፡፡ ይህንን የተረጋገጠው ፍሬነገር መነሻ በማድረግ መርምረናል፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ፍ/ቤት ማስረጃ በመመዘንና ፍሬነገር በማጣራት ሥልጣኑ በደረሰበት ደምዳሜ ተጠሪ ለግል ተበዳይ ቼክ ፈርሞ መስጠቱ ሳይክድ ለዋስትና ነው የሰጠሁት በማለቱ ፍርድቤቱ ይህ የተከሳሽ እና የግል ተበዳይ ጋር ያለው የግል ግንኙነት መነሻ በማድረግ ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው በማለት ተጠሪ የተከሰሰበትን የህግ ዓንቀፅ በመቀየር የጥፋተኛ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የተያዘው ጉዳይ አመልካች ባቀረበው ክስ ተጠሪ በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ፍርድቤቱ ተከሳሽ ተከሳሽ ፈፀመ የተባለው ወንጀል ሆነ ብሎ ሳይሆን በቸልተኝነት ነው ለማለት እንደምክንያት የወሰደው ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያለቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ ይህንን የወንጀል ድርጊት የፈጸመዉ በቸልተኝነት ነዉ ለማለት በወ.ሕ.ቁ.59 /1/ መሰረት ቸልተኝነት መኖሩን የሚያሚሉ ወይም የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች በሥር ፍ/ቤት አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ስለሆነም ተጠሪ የፈፀመው የወንጀል ተግባር በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው ወይስ ሆነ ብሎ የተፈፀመ ነው የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት የተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ የወ.መ.ህግ ቁጥር 693/1/ን በምንመለከትበት ጊዜ ርዕሱ "የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት" የሚል ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ሥር የተደነገገው ማንም ሰው ቼክ በሚያወጣበት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ / እንደሆነ በሚል ተደንግጓል፡፡

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(1) ሥር የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል ለማቋቋም እንደመስፈርት የተወሰዱት አንደኛው ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በሰጪ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቼኩ የተጠቀሰውን መጠን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቼኩ ማውጣቱ አልተካደም ቼኩ በወጣበት ጊዜ ይሁን በግል ተበዳይ ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ስለመኖሩ ያቀረበው ክርክር የለም ፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበት የህግ አንቀፅ በመቀየር ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው ለማለት የቻለው ተጠሪ ቼኩ የተሠጠው ለባንክ ቀርቦ እንዲመነዘር ሣይሆን በተከሳሽ እና ተበዳይ መካከል ባለው የብድር ግንኙነት ለዋስትና መያዣ መሰረት ተደርጎ ቼክ በገደብ የተሠጠ ነው በማለት መሆኑ ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

ይህ የሁለቱም ግንኙነት በፍትሃብሄር ክርክር ላይ ቼክ ለክፍያ ሲቀርብ (ገንዘብ ሲጠየቅ) ሊቀርቡበት ከሚችሉት መቃወሚያዎች አንዱ ቢሆንም ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ እያወቀ ቼክ የሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቼኩ የተጠቀሰውን መጠን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩ እስከተረጋገጠ ድረስ የተፈፀመው ወንጀል ሆነ ብሎ የተፈፀመ እንጂ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው የሚባል አይደለም ፡፡ ስለሆነም በቼክ አውጪው እና ተቀባዩ የሚኖረው ግላዊ ግንኙነት መሰረት በማድረግ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 67947 በሰጠው ገዥ (አሳሪ) የሕግ ትርጉም ቼክ በወንጀል ጉዳይ እንደዋስትና ተሰጥተዋል በማለት እንደመከላከያ ሊቀርብ እንደማይችል ፍርድ ሰጥተዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተሰጠ በተባለው ቼክ ለማን እንደሚከፈል ከየትኛው ባንክ እንደሚከፈል እንዲሁም ተጠሪ ፈርሞ የገንዘብ መጠኑ ተገልፆ የተሰጠ እና ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ እያወቀ ቼክ የሰጠ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሹ ባላቸው የግል ግንኙነት መሰረት በማድረግ ብቻ ወንጀሉ የፈፀመው በቸልተኝነት ነው ለማለት አይቻልም ፡፡ ምክንያቱም ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸመበት ሕጋዊ ሰነድ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ሕግ አውጭው በቼክ ላይ የሚፈፅመው ወንጀሎች ሕጋዊ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ በግልፅ ከመደንገጉ

በተጨማሪ ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈፀምበት ምንም ቅድመ ሁኔታ የማይቀመጥበት ሰነድ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል ፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን አመልካች የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ / መሆኑና ቼኩን ለክፍያ ተበዳይ ሲያቀርበውም በቂ ገንዘብ የለውም ተብሎ መመለሱን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰዉ ምስክሮች ቃል እና የሰነድ ማስረጃ በመመዘን በበቂ ሁኔታ እንደ ክሱ ያስረዱ መሆናቸዉን በማረጋገጥ ፍርድቤቱ ተጠሪ እንዲከላከል ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ባላስተባበለበት ሁኔታ የስር ፍርድቤት ተጠሪ የተከሰሰበትን የህግ አንቀፅ በመቀየር የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(2) ጥፋተኛ ማለቱ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(1) እንዲሁም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23፣59 የተመለከተውን የህግ ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በቀረበበት ክስ በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኛ ውሳኔ ሰጥተናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይየሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ የተቀየረ በመሆኑ በዚሁ አግባብ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሊስተካከል ይገባል ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለው ወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) በመሆኑ ቅጣቱ ሊሰላ የሚገባው ጥፋተኛ በተባለበት የህግ ድንጋጌ ነው ፡፡ተጠሪ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት የህግ ድንጋጌ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የወንጀል ደረጃና እርከን የወጣለት ስለሆነ የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) በመሆኑ የእስራ ቅጣት መነሻ እርከኑ 23 የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከኑ 6 ይሆናል፡፡

በከሳሽ (አመልካች) በኩል የቀረበ እና በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ማክበጃ ስለሌለ የቅጣት እርከኑ ከተያዘው መነሻ እርከን ከፍ አላለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የቀድሞ ሪከርድ የሌላቸው መሆኑ እና ቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ የተያዘላቸው በመሆኑ የእስራ ቅጣት መነሻ እርከኑ ከእርከን 23 ወደ እርከን 21 እንዲሁም የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከኑ ወደ እርከን 4 ዝቅ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም በእርከን 21 ስር ባለው ፍቅድ ስልጣን ከ5 አመት እስከ 6 አመት ስለሆነ ተጠሪ ጥፋተኛ በተባለበት የህግ ድንጋጌ ያስተምረዋል የተባለውን የአምስት አመት ፅኑ እስራት እና የአራት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል ብለናል፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ላይ የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 003731 ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሳኔ ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14134 መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም. የፀናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ክስ በቀረበበት የህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ሁሉ የሚታሰብላቸው ሁኖ በአምስት አመት ፅኑ እስራት እና በአራት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪ በሚገኙበት በመያዝ ለሚመለከተው ማርሚያ ቤት እንዲያሰረክብ ፣ ማረሚያ ቤቱም ከፌዴራል ፖሊስ ተረክቦ ተጠሪን በጉዳዩ ላይ ቀድሞ የታሰሩበት ጊዜ ካለ ታሳቢ በማድረግ የተወሰነውን የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣትን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ የገንዘብ ቅጣቱ የሚመለከተው የፋይናንስ ክፍል ያስፈፅም ብለናል ፡፡ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ክፍል አሥር

## 10. የሕሊናን ወይም የሰው ችግር መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### 10.1 የአራጣ ወንጀል[91]

- የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች በባህሪያቸው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆኑ ድንጋጌው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት ተፈፃሚነት የለውም የሚል ነው:: በእርግጥ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀመው የተበዳዩን ችግርተኝነት፣ የበታችነት፣ ወይም የገንዘብ ችግሩን ወይም መንፈስ ደካማነቱን ወይም ልምድ ወይም ችሎታ የሌለው መሆኑን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ድንጋጌ ያስገነዝባል::
- በዚህ አንቀፅ ስር የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተብለው የተጠቀሱት በአማራጭ መስፈርትነት የተቀመጡ ሲሆን አንዳንዶቹ በትክክልም የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ እንደ አግባብነታቸው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካልም የሚሰሩ ናቸው:: ለአብነት ያክል "መንፈስ ደካማነት" እና "የበታችነት" የሚለው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከት ሲሆን ችግርተኝነት ወይም የገንዘብ ችግር" የተባለው ደግሞ ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ሊፈፀም የሚችል ስመሆኑ፤[92]

የሰ/መ/ቁጥር 167805

ጥቅምት 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ኃይሉ ነጋሽ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ - የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡ 1. አቶ ታደሰ ኪዳነ ማርያም

2. አቶ ዳንኤል ኃይለ

3. አቶ ኪሮስ ፀጋይ

4. አቶ ብርሃነ ፀጋይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

#### ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የአራጣ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/100969 ላይ ጥቅምት 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ክርክሩ የተጀመረው የአሁን

---

[91]የሰ/መ/ቁ 167805 (ጥቅምት 26 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24

[92]የሰ/መ/ቁ. 80119 (የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15

አመልካች በሸረ እንዳስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪዎች ላይ የ1996 ዓ.ም የወንጀለ ህግ 712(1(ሀ)) ጠቅሶ ባቀረበው የአራጣ ወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ የአሁን ተጠሪዎች “ወልደ ገብርኤል አልጋሁን እና ጓደኞቻቸው ዕጣን ለቀማ ሕብረት ሽርክና ማህበር” ለተባለው ተበዳይ በሽረ እንዳስላሴ ከተማ ውስጥ በተለያዩ ቀናት የተለያየ መጠን ያለውን ገንዘብ በአራጣ በማበደር የአራጣ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ክሱን እንዲከላከሉ አድርጎ የመከላከያ ማስረጃቸውን ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች የተከሰሱበትን የአራጣ ወንጀል ያልፈፀሙ ለመሆኑ የዐቃቤ ህግ ማስረጃን በሚያስተባብል መልኩ አስረድተዋል በሚል ከተከሰሱበት ወንጀል በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ አሰናብቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታው በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁር 195(1) መሰረት ሰርዟል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር እና ቀን በዋለው ችሎት የአራጣ ወንጀል የሚፈፀመው የተበዳይን ችግር፣ የበታችነት፣ ወይም የገንዘብ ችግር፣ ወይም መንፈስ ደካማነት ወይም ልማድ ወይም ችሎታ ማጣትን መሰረት ተደርጎ መሆኑን፤ እነዚህ ተግባራት ሊኖሩ የሚችሉት በተፈጥሮ ሰው ላይ መሆኑን፤ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የአራጣ ወንጀል ተፈጽሟል የተባለው በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው ማህበር ላይ በመሆኑ በወንጀል ህጉ ስለ አራጣ ወንጀል ከአንቀፅ 712-715 ድረስ የተደነገጉት ለተፈጥሮ ሰው እንጂ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ተፈፃሚነት የለውም፤ በፍሬ ነገር ደረጃም በግራ ቀኙ መካከል የአራጣ ብድር ግኑኝነት ያልነበረ ለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃ በመረጋገጡ ተጠሪዎች ከክሱ በነፃ መሰናበታቸው ተገቢ ነው በማለት በውጤት ደረጃ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በአብላጫ ድምፅ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 15/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ችሎት ትርጉም ላይ ያለውን ቅሬታ በመጥቀስ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ቃሉም በወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ስር "ማንኛውም ሰው" ተብሎ የተጠቀሰው የተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል የሚያጠቃልል ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ችሎት የድንጋጌው ተፈፃሚነት ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው ብሎ መተርጎሙ አግባብ ባለመሆኑ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጣቸው ድርጅቶችም ተፈፃሚነት አለው በሚል ተተርጉሞ ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል የሚል ነው፡፡

የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ከወንጀል ህግ አንቀፅ 23(2) እና 712(1(ሀ)) ጋር ተገናዝቦ ተመርምሮ በዚህ ችሎት ትርጉም እንዲሰጥበት በዚህ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ለብቻው፤ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በጋራ ሰኔ 03/2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ዘርዘር ያለ ሲሆን አጠቃላይ ጭብጥ በሁለት ነጥብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የመጀመሪያው የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ድንጋጌዎች ስር የተቀመጡት መመዘኛዎች የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆናቸው እና የአራጣ ብድር ተሰጥቷል የተባለው ለማህበር በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት በአተረጓጎም ረገድ የፈፀመው ስህተት የለም የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው በስር ፍርድ ቤቶች በነፃ የተለቀቁት ከተበዳይ ጋር ተራ የብድር ውል ግኑኝነት እንጂ የአራጣ ብድር ያልነበረ ለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም የሚል ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 14/2011 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ ቀደም ሲል ያቀረበውን የቅሬታ ነጥብ የሚያጠናክርበትን ምክንያት በማከል በቀረበው ቅሬታ መሰረት እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል:: በመሰረቱ ተጠሪዎች በተከሰሱበት የወንጀል ህጉ አንቀፅ 712 ስር “ማንም ሰው” ተብሎ የተጠቀሰው የወንጀል ፈፃሚውን ማንነት የሚመለከት እንጂ

የተባዳዩን ማንነት የሚገልፅ አይደለም:: ሆኖም ይህ ድንጋጌ ያለበት የወንጀል ህጉ ስድስተኛ መፀሃፍ፣ ምዕራፍ ሶስት፣ ክፍል ሶስት "የንሲናን ወይም የሰውን ችግር መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎች" በሚል አርዕስት ስር በመሆኑ ዞሮ ዞሮ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀምበት ተበዳይ ሰው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

በህግ አስተምህሮ ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው እና በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማህበር/ድርጅት/ ስለመሆኑ በችሎቱ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው:: በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በልዩ ዓላማ የመብት እና ግዴታ ባለቤት እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም የሚንቀሳቀሰውም ሆነ ስራውን የሚከውነው በተፈጥሮ ሰው አማካኝነት ነው:: ድርጅቱን ለማንቀሳቀስ በህግም ይሁን በውል ስልጣን የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ ለድርጅቱ ጥቅም እና መብት እስከሰራ ድረስ በተሰራው ስራ ተጠቃሚውም ሆነ ተጎጂው ድርጅቱ ይሆናል::

ይህ በመሆኑም ነው ከድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በተለያየ የወንጀል ተሳትፎ ደረጃ ወንጀል አድርገው በተገኙ ጊዜ በእንደራሴዎቹ የተሳትፎ ደረጃ ልክ ድርጅቱ እራሱ ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣ ስለመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3) እና 34 ስር የተደነገገው:: እናም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት የመብት እና ግዴታ ባለቤት በመሆኑ በህግ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ በወንጀል ተከስሶ ሊቀጣ እንዲሁም እንደማንኛውም የተፈጥሮ ሰው የወንጀል ድርጊት ተጎጂ ሊሆን ይችላል ማለት ነው::

አሁን በቀረበው ጉዳይ በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ትርጉም የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች በባህሪያቸው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆኑ ድንጋጌው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት ተፈፃሚነት የለውም የሚል ነው:: በእርግጥ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀመው የተበዳዩን ችግርተኛነት፣ የበታችነት፣ ወይም የገንዘብ ችግሩን ወይም መንፈስ ደካማነቱን ወይም ልምድ ወይም ችሎታ የሌለው መሆኑን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ድንጋጌ ያስገነዝባል:: በዚህ አንቀፅ ስር የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተብለው የተጠቀሱት በአማራጭ መስፈርትነት የተቀመጡ ሲሆን አንዳንዶቹ በትክክልም የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ እንደ አግባብነታቸው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካልም የሚሰሩ ናቸው:: ለአብነት ያክል "መንፈስ ደካማነት" እና "የበታችነት" የሚለው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከት ሲሆን ችግርተኛነት ወይም የገንዘብ ችግር" የተባለው ደግሞ ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡

እናም የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮቹ በአማራጭነት የተቀመጡ በመሆናቸው እንደ ነገሩ ሁኔታ እና አግባብነት መመዘኛው ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ተግባራዊ ከሚደረግ በቀር ድንጋጌው ተፈፃሚነቱ ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው የሚባል አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ በቀረበበት አግባብ ተረጋግጧል አልተረጋገጠም የሚለው ቀጥሎ የሚታይ ሆኖ በድርጊቱ ተበዳይ ተብሎ የተጠቀሰው የንግድ ማህበር እንደራሴዎች በክሱ ውስጥ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከተጠሪዎች ሲበደሩ የነበረው ድርጅቱ አጋጥሞት በነበረው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ምክንያት መሆኑን ከክርክሩ አጠቃላይ አመጣጥ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የአንድ ድርጅት እንደራሴዎች ድርጅቱ ባጋጠመው የገንዘብ ችግር ምክንያት በአራጣ ገንዘብ ከተበደሩ እና ይህ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጥ ከተቻለ የንግድ ድርጅቱ በአራጣ ወንጀል ድርጊት ተበዳይነት የማይጠቀስበት ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም የትግራይ ሰበር ችሎት የወንጀል ህጉን አንቀፅ 712 የተረጎመበት መንገድ የድንጋጌውን አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል የወንጀሉን ድርጊት በተመለከተ ማስረጃና ፍሬ ነገርን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ያላቸው በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ማስረጃዎች መርምረውና መዝነው በተጠሪዎች እና በተበዳይ ድርጅት መካከል የነበረው ግንኙነት የተራ ብድር እንጂ የአራጣ ብድር አለመሆኑን ያረጋገጡ ለመሆኑ ከቀረበው የመዝገብ ግልባጭ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ከማለት ባለፈ የስር ፍርድ ቤቶች የአራጣ ወንጀል አልተፈፀመም ለማለት በተጓዙበት መንገድ እና በደረሱበት ድምዳሜ ውስጥ የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ምን እንደሆነ ለይቶ ያላመለከተ በመሆኑ ተጠሪዎችን ነፃ በመልቀቅ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/100969 ላይ ጥቅምት 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ስር የተመለከተው የአራጣ ወንጀል ተፈፃሚነት የተፈጥሮ ሰው በሆነ ተበዳይ ላይ ብቻ ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሮ የተቀረው በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 195(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በወንጀል ህግ አንቀፅ 712 ስር የተመለከተው የአራጣ ወንጀል በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ላይ ሊፈፀም ይችላል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. ውሳኔው መሻሻሉን እንዲያውቅ የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበ

**<u>I.የተጠቀሱ የሰበር መዝገቦች ዝርዝር</u>**

***<u>(case index)</u>***

***<u>ምዕራፍ -2</u>***

***<u>ክፍል -1</u>***

የሰ/መ/ቁ 60345 (ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ/ 101618 (ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19

***<u>ክፍል-2</u>***

የሰ/መ/ቁጥር 97291 (ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18 ፣ ሰ/መ/ቁ 43049 (ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ በሰ/መ/ቁ 58514 (ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 55047 (መጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 67411 (ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ. 64612 (የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 73953 (መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 78793 (ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 86845 (መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ የሰ/መ/ቁ 98647 (ሰኔ 02 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ የሰ/መ/ቁ. 98283 (መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17 ፣ የሰ/መ/ቁ. 92826 (ጥር 05 ቀን 2007 ዓ/ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ. 137672 (ሕዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ.መ.ቁ 202508 (ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅፅ 26 ፣ የሰ.መ.ቁ 224040 (ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ.

242958 (ሐምሌ 24 ቀን 2016 ዓ/ም)የሰ/መ/ቁ. 33075 (ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ የሰ/መ/ቁ 24278 (ሕዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 7፣የሰ/መ/ቁ 60518 (ጥር 15 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13፣ የሰ/መ/ቁ 60542 (የካቲት 27 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13

## ***ክፍል -3***

የሰ/መ/ቁ 153228 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23፣ የሰ/መ/ቁ 67777 (ታህሳስ 04 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ በሰ/መ/ቁ/158613 (ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 23 የሰ/መ/ቁ/ 92459 (ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ/ም) ቅፅ 15 ፣ ሰ/መ/ቁ 67777 (ታህሳስ 04 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13፣ የሰ/መ/ቁ 166294 (ግንቦት 7 ቀን 2011ዓ.ም)

## ***ክፍል -4***

የሰ/መ/ቁ 247351 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም) ፣የሰ/መ/ቁ 93173 (ታህሳስ 17 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15

## ***ክፍል-5***

የሰ/መ/ቁ 45595 (ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ 22069 (ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅጽ 7 ፣ በሰ/መ/ቁ 45927 (ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10 ፣ በሰ/መ/ቁ 52075 ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም (ቅፅ 12) ፣ በሰ/መ/ቁ 44235 (መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ በሰ/መ/ቁ 55649 (መጋቢት 06 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ በሰ/መ/ቁ 57446 (ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ በሰ/መ/ቁጥር 90089 (ጥቅምት 20 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ በሰ/መ/ቁ 97203 (መስከረም 30 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 17 ፣ የሰ/መ/ቁ 97203 (መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ. 115419 (ሚያዝያ 24 ቀን 2009 ዓ/ም)፣ በሰ/መ/ቁ 156420 (ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23 ፣ በሰ/መ/ቁ 164030 (ህዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 225558 (ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 219707 (ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 231521 (ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ/ም)፣ የሰ/መ/ቁጥር 245431 (ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 243136 (ሰኔ 26 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ/ 254742 (ሐምሌ 22 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 255633 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣የሰ/መ/ቁ 235944 (ሰኔ 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 117335 (የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም)፣ ሰ/መ/ቁ. 86570 (ሚያዝያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ.226650 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)

## ***ክፍል -6***

የሰ/መ/ቁ 246648 (ግንቦት 29 ቀን 2016ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 57446 (ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 141978 (መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22 ፣ የሰ/መ/ቁ 168166 (ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 210020 (ሕዳር 8 ቀን 2014ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 219862 (ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 210020 (ሕዳር 8 ቀን 2014ዓ.ም)

## ***ክፍል- 7***

የሰ/መ/ቁ 71753 (ጥር 03 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ የሰ/መ/ቁ 54839 (ጥቅምት 30 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 10

## ***ክፍል-8***

የሰ/መ/ቁ. 222452 (ሕዳር 30 ቀን 2015 ዓ/ም)፣ የሰ/መ/ቁ 46412 (ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ. 107166 (ጥቅምት 4/2008 ዓ.ም) ቅፅ 19 ፣ የሰ/መ/ቁ. 222452 (ሕዳር 30 ቀን 2015 ዓ/ም) ቅፅ 20

## ***ክፍል- 9***

የሰ/መ/ቁ. 230945 (ጥር 30 ቀን 2015 ዓ/ም)፣ የሰ/መ/ቁ 251537 (ጥቅምት 27 ቀን 2017 ዓ/ም)፣የሰ/መ/ቁ 57988 (ጥር 10 ቀን 2003ዓ/ም)ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁጥር153227 (መስከረም 24

ቀን 2011 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 231850 (ጥር 25 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 212472 (መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 66856 (መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13 ፣ የሰ/መ/ቁ 197432 (ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁጥር 249641 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 208890 (ታሕሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም) ቅፅ 26፣ የሰ/መ/ቁ 249641 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣የሰ/መ/ቁ/89276 (መሥከረም 23 ቀን 2006 ዓ. ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ 12025 (መጋቢት 18 ቀን 1999 ዓ.ም) ቅፅ 4 ፣ የሰ/መ/ቁ. 46189 (ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10 ፣ የሰ/መ/ቁ. 64813 (ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣ የሰ/መ/ቁ 251436 (ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 77989 (ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ የሰ/መ/ቁ 236062 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 65054 (ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ. 67408 (ጥር 01 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ የሰ/መ/ቁ 74530 (ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ ፣ የሰ/መ/ቁ 89276 (መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣የሰ/መ/ቁ 118084 (ሐምሌ 21 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ የሰ/መ/ቁ 161448 (ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣የሰ/መ/ቁ 149071 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23፣ የሰ/መ/ቁ 104923 (መጋቢት 28 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ የሰ/መ/ቁ 67947 (ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ 77592 (ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 149071 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23፣የሰ/መ/ቁ 209051 (ጥር 27 ቀን 2014ዓ.ም) ቅፅ 25 ፣የሰ/መ/ቁ 152755 (መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23 ፣የሰ/መ/ቁ 225645 (ጥቅምት 29 ቀን 2015)፣የሰ/መ/ቁ 231232 (የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም)

## ክፍል-10

የሰ/መ/ቁ 167805 (ጥቅምት 26 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ የሰ/መ/ቁ. 80119 (የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15

II.የምዕራፍ አንድ እና ሁለት የሕግ ማጣቀሻዎች

- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፣ 1987 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 11ኛ አመት፣ ቁጥር 1
- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ 2013 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ዓ.ም ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 2ኛ አመት፣ ቁጥር 13
- የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር፣ 1995 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 361/1995፣ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 9ኛ አመት፣ ቁጥር 86
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ፣ 1996 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 414/1996 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ህግ 1954 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 182/1954
- የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍትሀ ብሄር ህግ፣ 1952፣ አዋጅ ቁጥር 165፣ በነጋሪት ጋዜጣ በተለየ የወጣ፣ 19ኛ አመት፣ ቁጥር 2
- የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ድንጋጌ፣ 1958፣ ድንጋጌ ቁጥር 520፣ ነጋሪት ጋዜጣ በተለየ የወጣ፣ 25ኛ አመት፣ ቁጥር 3
- የባንክ ስራ አዋጅ፣ 2000 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 592/2000 ዓ.ም ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 14ኛ አመት፣ ቁጥር 57

- በሰው መነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፣ 2012 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ዓ.ም፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 26ኛ አመት፣ ቁጥር 31
- ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውወር እና ስደተኞችን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ 2007 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 909/2007 ዓ.ም፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 21ኛ አመት፣ ቁጥር 67
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 1994 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 285/1994፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 8 ዓመት፣ ቁጥር 33
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 2016 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ዓ.ም፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 30ኛ አመት፣ ቁጥር 61
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 2011 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1157/2011፣ 25ኛ ዓመት፣ ቁጥር 81
- የገቢ ግብር አዋጅ 1994 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 286/1994፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 34
- የጉምሩክ አዋጅ 2001 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥረ 622/2001፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ አመት፣ ቁጥር 27
- የጉምሩክ አዋጅ 2006 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 859/2006፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 20ኛ አመት፣ ቁጥር 82
- የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ 2008 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 983/2008፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 22ኛ ዓመት፣ ቁጥር 103
- የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ 2008 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 979/2008፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 30ኛ ዓመት፣ ቁጥር 61
- የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ 2004 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 721/2004፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 18ኛ አመት፣ ቁጥር 4
- የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓት የማስረጃ ህግ የወጣ አዋጅ 1997 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 434/1997፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 11ኛ ዓመት፣ ቁጥር 19
- የሙስና ወንጀሎች አዋጅ 2007 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 881/2007፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 21ኛ ዓመት፣ ቁጥር 36
- የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርአትና የማስረጃ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 2007 ዓ.ም፣ አዋጅ 882/2007፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 21ኛ ዓመት፣ ቁጥር 37
- የፌዴራል የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 2013 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 27ኛ ዓመት፣ ቁጥር 15
- የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ 2012 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1174/2012፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 26ኛ ዓመት፣ ቁጥር 14
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 2012 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1177/2012፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 26ኛ ዓመት፣ ቁጥር 28

- የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ 2002 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 686/2002፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 16ኛ ዓመት፣ ቁጥር 42
- የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ 2004 ዓ.ም፣ ዓዋጅ ቁጥር 760/2004፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 18ኛ ዓመት፣ ቁጥር 58
- ስለ ስራና ሰራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ 2002 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 632/2002፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ ዓመት፣ ቁጥር 54
- የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ 2001 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 652/2001፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 15ኛ ዓመት፣ ቁጥር 57
- በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ 2012 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 26ኛ ዓመት፣ ቁጥር 31
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መከላከያ ሰራዊት አዋጅ 2015 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1286/2015፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 29ኛ ዓመት፣ ቁጥር 36

## ምዕራፍ ሶስት

## III. በልዩ ልዩ አዋጆች ላይ የተሰጡ አስገዳጅ የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች

### መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በኢትዮጵያ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተለያዩ አዋጆች ላይ የተሰጡ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች የቀረቡበት ሲሆን ለአጠቃቅም ይመች ዘንድ በአስራ አራት ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ **በክፍል አንድ** የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጡ አዋጆችን መሰረት በማድረግ የተሰጡ አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች ውሳኔዎች የቀረቡ ሲሆን በተለይም የሽብር ድርጊት ለመፈፀም የመሰናዳት ተግባር እና የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ የሕግ ትርጉም እንዲሁም ሌሎች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች ተመላክተውበታል፡፡ **ክፍል ሁለት** በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና በሰው መነገድ ወንጀል ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በተለይም ለብዝበዛ ዓላማ የሚፈጸም ወንጀል እና የሚያስከትለው የወንጀል ኃላፊነት እንዲሁም ይህን ወንጀል የማየት የሥረ ነገር ስልጣን ያለውን ፍርድ ቤት በተመለከተ በችሎቱ የተሰጡ አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች እና ሌሎች ተያያዥ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸው ውሳኔዎች ተካተው ቀርበውበታል፡፡ **ክፍል ሶስት** በሙስና ወንጀሎች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣በተለይም በሙስና ወንጀሎች ክስ የተከሳሽን የሀሳብ ክፍል የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ የሚዛወር ስለመሆኑ ችሎቱ የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንዲሁም የሙስና ወንጀሎች አዋጅን በተመለከተ የተሰጡ ሎሎች አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎች በማጣቀሻነት ተገልፀው ቀርበውበታል፡፡ **ክፍል አራት** የቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅን በተመለከተ የተሰጠ የህግ ትርጉም የቀረበበት ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረበው ውሳኔ በቴሌኮሚኒኬሽን ሲስተም ላይ የተፈፀመ ወንጀል ተጠያቂነን በዝርዝር ያስረዳል፡፡ **ክፍል አምስት** በግብር ሕጎች ላይ የተሰጡ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎችን ያቀርባል፡፡ በተለይም፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግን መጣስ፣ ሐሰተኛ ደረሰኞችን ማቅረብ፣ እና የግብር ግዴታን አለመፈፀም ያሉ ወንጀሎችን ይመለከታል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረቡት የፍርድ ቤት ጉዳዮች የግብር ሕጎችን መጣስ እና የሚያስከትለው የወንጀል ኃላፊነት በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡ **ክፍል ስድስት** የጉምሩክ አዋጆችን መሰረት በማድረግ የተሰጡ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎችን ያቀርባል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረቡት ጉዳዮች የጉምሩክ ሕጎችን በመተላለፍ የሚያስከትለውን የወንጀል ተጠያቂነት፣ ከሕጋዊ መተላለፊያ መስመር ውጪ የሚገቡ እቃዎችን መቆጣጠር በተመለከተ የተሰጡ አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች እና ሌሎች ተያያዝ ውሳኔዎች ተገልፀው ቀርበውበታል፡፡

**ክፍል ሰባት** የባንክ ስራ አዋጅን መሰረት በማድረግ የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውሳኔ የቀረበበት ሲሆን በዋናነትም በወንጀል ምርመራ ወቅት የተጠበቁ የባንክ መረጃዎችን ለማግኘት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ አስፈላጊ እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡**በክፍል ስምንት** የመከላከያ ሚኒስቴር አዋጅን መሰረት በማድረግ የተሰጠ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔ የቀረበበት ሲሆን በዋናነትም የመከላከያ ሚኒስቴር እና የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን የተለያዩ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው በመሆኑ በፋውንዴሽኑ ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታዩ መሆኑ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡**ክፍል ዘጠኝ** የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅን መሰረት በማድረግ የተሰጡ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎችን የሚመለከት ነው፡፡ **በክፍል አስር** የንግድ ስራ ፈቃድ አዋጅን መሰረት በማድረግ የተሰጡ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎች ቀርቧል፡፡**ክፍል አስራ አንድ** የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ ላይ በዋናትም በሕግ ጥላ ስር የሚገኙ ተጠርጣሪዎች የግል ሕክምና የማግኘት መብት ላይ በማተኮር የተሰጠ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔ ቀርቦበታል፡፡**ክፍል አስራ ሁለት** በየጦር መሳሪያ አስተዳደር አዋጅ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በተለይም አዋጁ ከተፀደቀ በኋላ ለሚሰጠው የምዝገባ ጊዜ አተገባበርን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያለፈቃድ የጦር መሳሪያ ያዘ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን አይገባም በማለት የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔ ቀርቧል፡፡**ክፍል አስራ ሶስት**

በየሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በወንጀል ክስ ውስጥ የግል ተበዳይ ባለመቅረቡ ከቀረቡ ሌሎች ማስረጃዎች ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔ ቀርቦበታል፡፡በመጨረሻም **ክፍል አስራአራት** የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን በተመለከተ የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውሳኔ ቀርቦበታል፡፡በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በአጠቃላይ (20)ሀያ በየዘርፉ የተመረጡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎት የተለያዩ አዋጆች ላይ የሰጣቸው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች ሙሉ ይዘት የቀረበ ሲሆን ሌሎች ከነዚህ ውሳኔዎች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ውሳኔዎች መረጃ በግርጌ መስታወሻዎች ውስጥ ተመላክተው ቀርበዋል፡፡

## ክፍል አንድ

### 1.የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጡ አዋጆች

### 1.1 የሽብር ድርጊት ለመፈፀም መሰናዳት የወንጀል ተጠያቂነት[93]

- የመሰናዳት ተግባሮች ወንጀል አድራጊው ውጤት ለማግኘት ወይም ጉዳት ለማድረስ እንቅስቃሴ መጀመሩን የሚያመለክቱ ቢሆንም በመሠረቱ የሚያስቀጡ አይደሉም፡፡ ሆኖም ግን ለመሰናዳት የተፈጸሙ ድርጊቶች በራሳቸው ወንጀል መሆናቸው ተደንግጐ ከሆነ የድርጊቱ ፈጻሚ የሚቀጣው አንድ ወንጀል ለመፈጸም አስቦ በመሰናዳቱ ሳይሆን ለመሰናዳት የፈጸመው ድርጊት ከዚህ የተለየ የወንጀል ድርጊት በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የመሰናዳት ተግባር በራሱ የሚያስቀጣ ድርጊት የሚሆነው የሚያደርሰውን ከፍተኛ ቀውስ ከግምት በማስገባት በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ይሆናል (ሽብርተኝነትን ወንጀልን ለመከላከል የወጣው የፀረ-ሽብር አዋጅ ቁጥር 1176/2012 አንቀጽ 6/2)፡፡[94]

የሰ.መ.ቁ. 211521

ጥቅምት 01 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡-የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

ተጠሪዎች፡- 1. አሚድ በሀሙ ድጅሎ (ይትባረክ ተገኝ/ ቁረንሶ ሰባ)

2. ደበሊ (ኦብሳ) ተሬቻ አመና

3. ዶ/ር ድሪባ ዋቅጅራ ፋሪ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 20 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 328797 ሚያዝያ 19 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠውን ብይን በማጽናት፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት

---

[93]የሰ/መ/ቁ/ 211521(ጥቅምት 01 ቀን 2015 ዓ.ም)

[94]በሰ/መ/ቁ.102982 (መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20፣ በሰ/መ/ቁ 247063 እና 247065 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም)

በመ.ቁ. 207676 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪዎች እና በስር ተከሳሾች በሆኑ በሰበር ያልተጠሩ ሌሎች ሰዎች ላይ 7 ክሶችን ጠቅሶ ያቀረበ ሲሆን ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው 1ኛ ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪዎች የወንጀል ህግ ቁጥር 32(1)(ሀ)(ለ) እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን የጸረ-ሽብር አዋጅ ቁጥር 1176/2012 አንቀጽ 6(2) በመተላለፍ የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈጸም ዝግጅት በማድረግ ተጠሪዎች ከስር ተከሳሾች እና እጃቸው ካልተያዘ ሌሎች ተጠርጣሪዎች ጋር በመሆን የኦነግ ሸኔ የሽፍታ ቡድን አባላት የሆኑት አባ ቶርቤ ብለው ራሳቸውን ከሚጠሩት ጋር በመሆን የኦነግ ሸኔ ሽፍታ አመራሮች በህገመንግስቱ በተቋቋመው አካላት ወይም ባለስልጣናት ላይ ሽፍቶች የትጥቅ አመጽ እንዲያነሱ ከሚያደራጁት ወይም ከሚመሩት ተልዕኮ በመቀበል የኦሮሞ ህዝብ አሁንም ነፃ ያልወጣ ስለሆነ በኃይል ተዋግተን አሁን ያለውን መንግስት ከስልጣኑ አውርደን ራሳችንን ስልጣን ይዘን የኦሮሞን ህዝብ ነፃ እናወጣለን በማለት ይህንን የፖለቲካ አላማቸውን ወይም እቅዳቸውን በኃይል ለማሳካት ሲባል 3ኛ ተጠሪ ቀኑ ባልታወቀ ሰኔ ወር 2012 ዓ.ም ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ሾላ አካባቢ ቤት በመከራየት ካስቀመጣቸው በኋላ ሀሰተኛ የመታወቂያ ወረቀት ከአቃቂ ክፍለ ከተማ ከወረዳ 7 የወጣ በማስመሰል በ2ኛ ተጠሪ ስም የመታወቂያ ወረቀት ቁጥሩ 750/07 የሆነ 1ኛ ተጠሪ ስሙን ቱራ በዳሶ በሚል በመቀየር የመታወቂያ ወረቀት ቁጥር 620/7 የሆነውን በማዘጋጀት ከሰጠው በኋላ ቀኑ ባልታወቀ መስከረም ወር 2013 ዓ.ም ቦሌ ክፍለ ከተማ በባለስልጣናት መኖሪያ ቤት አካባቢ በመሄድ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ የነበሩ አባዱላ ገመዳ መኖሪያ ቤት፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት ሽመልስ አብዲሳ፣ የአገር መከላከለያ ሚኒስቴር የነበሩ አቶ ለማ መገርሳ፣የኦሮሚያ የብልጽግና ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ታዬ ደንደአ እና የኦነግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ኢብሳ ነገዎ የመኖሪያ ቤታቸውን በማሳየት ከለዩ በኋላ 3ኛ ተጠሪ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንቅስቃሴያቸሁ ክትትል እየተደረገበት ስለሆነ ወደ አዳማ ከተማ መሄድ አለባችሁ በማለት እስከ ቢሾፍቱ ከተማ ድረስ በራሱ መኪና በመሸኘት ወደ አዳማ ከተማ እንዲሄዱ ያደረገ ስለሆነ በሀሳቡ እና በሁለንተናው ድርጊቱ የሽብርተኝነት ወንጀል ድርጊት መፈጸም እና በሚያስገኘው ውጤት ሁሉ ሙሉ በሙሉ በመሳተፍ ድርጊቱን የራሱ ያደረገ ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ወደ አዳማ ከተማ በመሄድ የሽብርተኝነት ወንጀሉን የሚፈጽሙበትን የጦር መሳሪያ ሲያፈላልጉ ቆይተው በ22/02/2013 ዓ.ም ወደ መቂ ከተማ በመሄድ የጦር መሳሪያ ስታር ሽጉጥ ቁጥሩ 11040335 የሆነ ከ45 ጥይት ጋር ከስር 4ኛ ተከሳሽ ወስደው ከላይ ስማቸው በተጠቀሰው ባለስልጣናት ላይ የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈጸም ዝግጅት በማድረግ ላይ እያሉ ወንጀሉን ለመፈጸም ካዘጋጁት መሳሪያ ጋር በ25/02/2013 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ላይ በአዳማ ከተማ ውስጥ ስለተያዙ በግብረአበርነት ወንጀል በመፈጸም ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁም 1ኛ ተጠሪ 1ኛ ክስን በተመለከተ አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክደው በመከራከራቸው፤ 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ክስን በተመለከተ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክደው በመከራከራቸው፤ 3ኛ ተጠሪ 1ኛ ክስን በተመለከተ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም፤ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ቤት አላከራየሁም፤ ተጠሪዎቹ ለስራ ፍለጋ ወደ እኔ መጥተው ለስራ የሚያስፈልጋቸውን መስፈርት ነግሬያቸው አሰናብቻቸዋለሁ፤ እኔ የመታወቂያ ወረቀቱን አላወጣሁም አልውቅምም፤ እኔ ወደ አዳማ አልወሰድኳቸውም፤ የምሰራው ስራ የዕለት ዕለት ስራ በመሆኑ እንደዚህ አይነት እድል አይፈጥርልኝም፤ የባለስልጣናት ቤትን አላውቅም፤ ጽሁፍን ኤዲት አድርጓል የሚለው እኔ ወረቀቱን አላየሁትም፤ ለምርመራ 2 ወር በቆየሁበት ቦታ በሰውነቴ ላይ ድብደባ

ተፈጽሞብኝ ተገድጄ ቃሌን እንድሰጥ እና ብዙ ወረቀቶች እንድፈርም ተደርጓል ወረቀቶቹንም ያየሁት ፍርድ ቤት ስመጣ ነው በማለት ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱም የዓቃቤ ሕግን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን ሰምቷል፡፡

የዓቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር መሀሙድ የተባለውን ሰው በፊት የሚውቀው መሆኑን እና የሚከራይ ቤት እንዳለኝ ጠይቆኝ አለ ስለው ማታ ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ሄደው የሚከራየውን ቤት በብር 2000 ያሳየው መሆኑን እና በማግስቱ ሌላ ሰው ልከው ቤት አሳዩዋቸው ሲባል አሳይቸዋለው፤ የቤቱን ኪራይ ማን እንደከፈለ አላውቅም፤ ኮሚሽን የሰጠኝ 3ኛ ተጠሪ ነው በሚል ሲመሰክር፣ 3ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ከ3ኛ ተጠሪ ጋር በኢሊሌ ሆቴል አብረው የሚሰሩ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ የሆቴሉ ኃላፊ መሆኑን፣ ይህ ምስክር ደግሞ የሆቴል ጉዳይ አስፈጻሚ እንደሆነ በመግለጽ 3ኛ ተጠሪው ሲልከኝ የሆነ የታሸገ ፖስታ በውስጡ ምን እንዳለ አላውቅም፤ ሄጄ ቃሊቲ ገብርዔል በተባለው አካባቢ የፖሊስ ጽ/ቤት ከሚገኝበት ትንሽ ራቅ ብሎ ባለው ሄጄ አምጥቼዋለሁ፤ ተጠሪውም ደውሎ ጉዳዩ ተዘጋጀልኝ ወይ ብሎ በስልክ ሲጠየቅ ሰውዬው አዎን ሲል እኔም እዛ ስደርስ ደውሎ ከመንገዱም ዳር ቆሞ ነበር፤ ሰጥቶኝ የታሸገ ፖስታ በውስጡ ምን እንዳለ አላውቅም፤ እኔ የመታወቂያ ወረቀት መሆኑን የሰማሁት ፖሊስ ይዘውኝ ካሰሩኝ በኃላ ነው በማለት መስክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ከጥርጣሬ በላይ ያላረጋገጠ ስለሆነ ተጠሪዎች ከቀረበባቸው 1ኛ ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተሰርዟል፡፡

አመልካች ይህን በመቃወም ሐምሌ 20 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግም የምስክሮች ቃል የተያያዥነት ሁኔታ ሳይመለከት በደፈናው አሳማኝ አይደለም ማለቱ ስህተት ነው፤ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 27(2) የሰጠውን ቃል እና 1ኛ ተጠሪ የወንጀሉን ድርጊት ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር መፈጸሙን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 35 መሰረት አምኖ የሰጠውን ቃል ሳይመዝን የሰው ማስረጃን ብቻ መዝኖ በነፃ እንዲሰናበቱ የሰጠው ብይን አግባብነት የለውም፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከ1ኛ ክስ በነፃ እንዲሰናበቱ የወሰነበትን አግባብ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 23(2) እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 1176/2012 አንፃር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ በመስጠቱ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

አመልካች የፍርድ ቤቱን መጥሪያ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲያደርስ በተደጋጋሚ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ያልፈጸመ እና ያልፈጸመበትንም ምክንያት ስላልገለጸ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መቀጠል እንዳልፈለገ በመቁጠር መብቱ ታልፎበታል፡፡

3ኛ ተጠሪ መጋቢት 28 ቀን ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በ3ኛ ተጠሪ ላይ የተሰሙት የአካባቢም ሆነ የደረጃ ምስክሮች በቀረበው ክስ መሰረት አላስረዱም፤ 3ኛ ተጠሪ ከኦነግ ሸኔ ተልኮ በመቀበል የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል ከማለት ውጪ በሰውም ሆነ በሰነድ ማስረጃዎች አላስረዳም፤ 3ኛ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 27(2) መሰረት የሰጠው ቃል በፖሊስ ከፍተኛ ድብደባ ደርሶበት ተገዶ የሰጠው ቃል ነው፤ የቀረቡት የደረጃ ምስክሮች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 27(2) መሰረት ተጠሪዎች ቃላቸውን ሲሰጡ አይተናል ከማለት ውጪ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት አካባቢ ያልነበሩ ናቸው፤ 1ኛ ተጠሪ ፍርድ ቤት ቀርቦ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 35 መሰረት የሰጠው ቃል የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምንም ብለን በተከራከረው በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችል

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 17 በመ.ቁ. 96310 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል አኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል ተደርጐ ከነበረው አጠቃላይ ክርክር እና በተሰጠው ብይን እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ስር ፍ/ቤት በ3ኛ ተጠሪ ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ ከላይ እንደተመለከትነው የወንጀል ህግ ቁጥር 32(1)(ሀ)(ለ) እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን የጸረ-ሽብር አዋጅ ቁጥር 1176/2012 አንቀጽ 6(2) በመተላለፍ የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈጸም ዝግጅት በማድረግ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለሆኑት ቤት ተከራይቶ በማስቀመጥ ሀሰተኛ መታወቂያ ስማቸውን ቀይሮ እንዲዘጋጅላቸው በማድረግ፣ ቢሾፍቱ ከተማ ድረስ በራሱ መኪና በመሸኘት ወደ አዳማ ከተማ እንዲሄዱ በማድረግ በህቡ ለሚንቀሳቀስ ባለሥልጣናትን ለመግደል ለተደራጀ ቡድን በመሥራት በሀሳቡ እና በሁለንተናው ድርጊቱ የሽብርተኝነት ወንጀል ድርጊት መፈጸም እና በሚያስገኘው ውጤት ሁሉ ሙሉ በሙሉ በመሳተፍ ድርጊቱን የራሱ በማድረግ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ክስ እንዳቀረበበት ያሳያል፡፡

3ኛ ተጠሪም ድርጉቱን አልፈፀምኩም በማለት በችሎት ቀርቦ ቃሉን የሰጠ ሲሆን በጣቢያ የሰጡሁት ቃልም ተገድጄ ነው ሲል ራሱን በሚከላከል መልኩ ቃል መስጠቱን ብይኑ ያሳያል፡፡

በአጣሪው ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አኳያ 3ኛ ተጠሪ ላይ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ክስ ስለማስረዳት አለማስረዳቱ በአግባቡ ተመርምሮ የመወሰኑን አግባብነት በአጣሪው ከተያዙት ድንጋጌዎች እና ከተሰጠው ብይን አንፃር መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 23/2/ በግልጽ እንደደነገገው፡- "አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡" በሚል ነው፡፡ አንድ የወንጀል ውጥን ከሀሳባዊ ውሣኔ አልፎ ወደ ቁሣዊ ሁኔታ ሲለወጥ ወይም ወደ ተግባር ሲተረጐም ወንጀሉ በመሰናዳት የሚገለጽ ሲሆን፣ የመሰናዳት ተግባሮች በአብዛኛው መሳሪያዎችን በማሰሳሰብና ለወንጀል አፈፃፀም የሚረዱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ይገለጻል፡፡ የመሰናዳት ተግባሮች ወንጀል አድራጊው ውጤት ለማግኘት ወይም ጉዳት ለማድረስ እንቅስቃሴ መጀመሩን የሚያመለክቱ ቢሆንም በመሠረቱ የሚያስቀጡ አይደሉም፡፡ ሆናም ግን ለመሰናዳት የተፈጸሙ ድርጊቶች በራሳቸው ወንጀል መሆናቸው ተደንግጐ ከሆነ የድርጊቱ ፈጻሚ የሚቀጣው አንድ ወንጀል ለመፈጸም አስቦ በመሰናዳቱ ሳይሆን ለመሰናዳት የፈጸመው ድርጊት ከዚህ የተለየ የወንጀል ድርጊት በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የመሰናዳት ተግባር በራሱ የሚያስቀጣ ድርጊት የሚሆነው የሚያደርሰውን ከፍተኛ ቀውስ ከግምት በማስገባት በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ይሆናል፡፡ በዚህ አግባብ የተቀረፀው ሽብርተኝነትን ወንጀልን ለመከላከል የወጣው የፀረ-ሽብር አዋጅ ቁጥር 1176/2012 አንቀጽ 6/2 ስር ፡- "ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 የተመለከተውን የሽብር ድርጊት ለመፈፀም የመሰናዳት ተግባር የፈፀመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡" በሚል ደንግጐ እናገኛለን፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በ3ኛ ተጠሪ ላይ በስር ፍ/ቤት ጠቅሶ ያቀረበው ክስ የአዋጁን አንቀጽ 6/2/ ጠቅሶ መሆኑን ያሳያል፡፡ 3ኛ ተጠሪ በድርጊቱ እና በተግባሩ የሽብር ወንጀል እንዲጸፀም እቅድ የነበረውና ለወንጀሉ መፈፀም እያሰናዳ ያለው ነገር ስለመሆኑ በዝርዝር ገልጾ አቅርቧል፡፡ 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ወንጀል ለመፈፀም አልተሰናዳሁም ሰዎቹ ሥራ ፈላጊዎች ናቸው በምሰራበት ቦታ መጥተው ስለሥራ ጠይቀውኝ ነግሬአቸዋለሁ እንጂ የተባለውን ወንጀል አልፈፀምኩም በሚል ክዶ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ ራሱ 3ኛ ተጠሪ ከሰጠው ቃል የምንገነዘበው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ጭራሽ አላውቃቸውም ብሎ እየተከራከረ ባለመሆኑ በአንድ አጋጣሚ ሰዎቹን ማወቁን እና ሰዎቹን አግኝቷቸው እንደነበረ የሰጠው ቃል ያረጋግጣል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ያቀረባቸው 2 ምስክሮች በ3ኛ ተጠሪ ላይ ያስረዱትን ስንመረምር ደግሞ ቤት ለመከራየት ምሽት ላይ ከ1ኛ ምስክሩ ጋር የተገናኝ እና ኮሚሽኑን የሰጠው ይህ 3ኛ ተጠሪ መሆኑን ያስረዳ ሲሆን 3ኛ ምስክር በበኩሉ በሰጠው የምስክርነት ቃል ከ3ኛ ተጠሪ ጋር አብሮ ይሰራ የነበረ እና 3ኛ ተጠሪ የሆቴሉ ኃላፊ መሆኑን፣ ይህ ምስክር ደግሞ የሆቴል ጉዳይ አስፈጻሚ እንደሆነ በመግለጽ ተጠሪው ሲልከኝ የሆነ የታሸገ ፖስታ በውስጡ ምን እንዳለ አላውቅም፤ ሄጄ ቃሊቲ ገብርኤል በተባለው አካባቢ የፖሊስ ጽ/ቤት ከሚገኝበት ትንሽ ራቅ ብሎ ባለው ሄጄ አምጥቼዋለሁ፤ ተጠሪውም ደውሎ ጉዳዩ ተዘጋጀልኝ ወይ ብሎ በስልክ ሲጠየቅ ሰውዬው አዎን ሲል እኔም እዛ ስደርስ ደውሎ ከመንገዱም ዳር ቆሞ ነበር፤ ሰውየው የታሸገ ፖስታ ሰጥቶኝ ፖስታውን መቀበሉን እና ለ3ኛ ተጠሪ ሆቴሉ ድረስ አምጥቶ ማስረከቡን አስረድቷል፡፡

እንዲሁም አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጥብቆ እየተከራከረ ያለው 3ኛ ተጠሪ በምርመራ ጊዜ የሰጠው ቃል ሳይመረመር ውሣኔ መሰጠቱን በማንሳት ነው፡፡ በውሣኔው ላይ ለመመልከት እንደተሞከረው 3ኛ ተጠሪ በጣቢያ ስለሰጠው ቃል ተነስቶ ብይን ያረፈበት መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም፡፡ ሆኖም ግን 3ኛ ተጠሪ በጣቢያ የሰጠው ቃል በአጭሩ የሚያሳየው፡- ትክክለኛ ስሙ ሀብታሙ ዴሳ/ ጭምዲ ጭምዴሳ/ በሚል የሚታወቅ ሰው የፌስቡክ ጓደኛው መሆኑን፣ ይህ ሰው ግንቦት ወር 2012 ዓ.ም የደወለለት እና ጅሩፋ ጅሬኛ የተባለ የአገር ሰውን አናግረው ስላለኝ በቴሌግራም ወይም በፌስ ቡክ ያናገረውና በአሁኑ ሰዓትም ካናዳ የሚገኝ መሆኑን የነገረው መሆኑን፣ የአባ ቶርቤ ቡድን ተደብቀው ከተማ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ እንደሆኑ እና ተጠሪ ግን በሰዓቱ የማያውቅ መሆኑን፣ የትግል ስሙ ጢጊ የተባለውን ሰው ትክክለኛ ስሙ አዱኛ ለሜሳ እንደሚባል እና ከእሱ ጋር ተዋወቁ ያናግርሀል ተብሎ ሰኔ ወር 2012 ዓ.ም ውስጥ መገናኛ አካባቢ ሸዋሱፐር ማርኬት አጠገብ ጥጊ ከተባለው ሰው ጋር የተገናኘ መሆኑን፣ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት አቋርጦ ከጉንደር መውጣቱን የነገረው መሆኑን፣ ለረጅም ጊዜ በኦነግ ትግል ውስጥ ያለ መሆኑን፣ ሥራ እንዳስቀጥራቸው የፌስ ቡክ ስሙ ጅሩፋ ጅሬኛ የተባለው ሲነግረው የትምህርት ደረጃቸውን የጠየቀ መሆኑን፣ ፍላጐታቸውን ጠይቆ የሚነገረው መሆኑን መነጋገራቸውን፣ ጢቂ ደውሎለት ለሁለት ልጆች ክፍት ሥራ ቦታ አለህ ወይ ብሎ የጠየቀውና አለኝ ማለቱን፣ ጢቂ ቆይቶ ደውሎ ሥራ ሚፈልገው ልጅ መጥቷል ከፒያሳ ተቀበለው ብሎት በድርጅቱ መኪና ሄዶ አማድ አህሙድቱራ በዳሳ የተባለውን መቀበሉን፣ የሚከራይ ቤት የፈለገላቸው መሆኑን በካዛንቺስ አካባቢ በብር 600.00 አልጋ ተከራይቶላቸው የነበረ መሆኑን ፣ በኋላም መሀመድ አደም የተባለው የድርጅቱ ሠራተኛ የሚከራይ ቤት የጠየቀውና የደላላ ስልክ የሰጠው መሆኑን፣ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ሾላ አባባቢ በብር 2000.00 ያከራያቸውና 3ኛ ተጠሪ ኮሚሽን ብር 300.00 የከፈለ መሆኑን ፣ ከቀናት በኋላ ደበሌ የተባለ ወደ አዲስ አበባ እንደመጣና ሄዶ እንዲቀበለው ጢቂ /አዱኛ ለሜሳ/ የጠየቀውና ከጀሞ አካባቢ የተቀበለው መሆኑን፣ ጢቂ መታወቂያ ወረቀት ማውጣት እንዲችሉ ሰው የማውቅ ከሆነ በሚል ሲጠይቀው እንደማያውቅ ሲነግረው ጢቂ/አቃቂ አካባቢ የሚያውቀው ሰው እንዳለ እና ልጆቹ ፎቶግራፍ የሚነሱበት ቦታ ስላላወቁ ካዛንቺስ አካባቢ የአባ ቶርቤ አባላት ፎቶግራፍ እንዲነሱ ያሳየ መሆኑን፣ የመታወቂያ ወረቀት ከጢቂ ተቀብሎ እሱ የሚሰራበት ሆቴል ቤት ሠራተኛ የሆነው ገለታ ሮቢ፣ ዳኜ ዳንኤል ለተባለው የሰጠ መሆኑን ከማን እንደተቀበለ ያላወቀ መሆኑን፣ መታወቂያው ባዶው ወጪ ሆኖ ማህተም የተመታበትን አምጥቶ የሁለቱንም ሰዎች ፎቶ ግራፍ ራሱ መትቶ ሙሉ ስማቸውን ጽፎ እና አድራሻቸውን ቀይሮ የሞላ መሆኑን፣ ጢቂ/አዱኛ ለሜሳ የተመቸህን ነገር ሙላው ያለው በመሆኑ ትክክለኛ ስሙ ሀሚድ መሀሙድ ጅሎ የሆነውን ቱራ በዳሳ አዳ በሚለ ቀይሮ መሙላቱን የደበሌ ተሬሳ የተባለውን በትክክለኛ ስሙ የሞላና የመታወቂያ ወረቀቱን ያለፎቶግራፍ የሰጠው መሆኑን ገልጿል፡፡ በክረምት ወር 2012 ዓ.ም የኦነግ ሸኔ አባል የሆነው ጢቂ/አዱኛ ለሜሳ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናትን ቤት ላይ

ያለው መሆኑን፣ መስከረም ወር 2013 ዓ.ም ለእርምጃ ወሳጅ ቡድን እነ ቱራ በዳሶ ገሚድ ጅሎ እና ደበሌ ተሬቻ መድኃኒት ለመግዛት በሚል በሄዱበት ቤታቸውን የለየ መሆኑን፣ የእነ ለማ መገርሳ እና ኢብሳ ነገኦ ቤት አካባቢውን እና የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ያሉበትን አካባቢ ያሳያቸው መሆኑን፣ የታየ ደንደአ እና የእስክንድር ነጋ ቤት ደግሞ አንድ ቀን ለጢቂ ያሳየ የመሆኑን፣ መስከረም ወር 2013 ዓ.ም. ጢቂ ለጀግኖች ካሣ ብሎ ያዘጋጀውን ሞጁል እሱ ደግሞ ኤዲት እንዳደረገው በሶሻል ሚዲያ በኩል የላከ መሆኑን ጢቂ/ አዱኛ ለሜሳን ኤዲት ያደረገ መሆኑን፣ ጢቂ ልጆቹ የተነቃባቸው ስለሆነ ወደ አዳማ ይሂዱ ያለውና ጁሩፋ ጅሬና ሲል ጢቂ ደግሞ እኔ እንድወስዳቸው ነግሮኛል ማለቱን፣ አባላቱን ወደቢሾፍቱ ከተማ ድርጅቱ በሰጠው መኪና መስከረም ወር 2013 የአባ ቶርቤ አባላትን የወሰደ መሆኑን፣ በኋላም የከተማው ቡድን አባላት ትክክለኛ ስማቸው ሀሚድ በሀሙድ የተባለው አንዱ በፈፀመው ወንጀል አምልጦ ስሙን የቀየረለት እና ቱራ በዳቦ ብሎ ያወጣለት መሆኑን 2000.00 ብር ድጋፍ የላከ መሆኑን በመግለጽ የሰጠው ቃል ያሳያል፡፡

እንዲሁም ከወንጀል ጉዳዮች የክስ ሂደት ጋር በተገናኘ ዓቃቤ ሕግ ሊያከናውናቸው ከሚገቡ ተግባራትና ኃላፊነቶች ዋናው የተከሰሰን ሰው የወንጀል ድርጊቱን በቀረበው ክስ አይነት ስለመፈፀሙ በበቂና አሳማኝ ማስረጃ የማስረዳት ሸክሙን መወጣት ያለበት ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 141 እና 142/1/ መረዳት ይቻላል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ክስ ሊያስረዳ የሚችለው ደግሞ ከክሱ ጋር ዘርዝሮ ባቀረባቸው የሰው እና የሰነድ እንዲሁም ሌሎች የማስረጃ ዓይነቶች ሲሆን ፍ/ቤቶች በዐቃቤ ሕግ ተዘርዝረው የቀረቡ እያንዳንዱን ማስረጃ በአግባቡ በመመርመር እና አንዱ ከሌላኛው ማስረጃ ጋር የሚጣጣም ወይም የሚጣረስ መሆኑን በመመዘን ነው፡፡ ከአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት አመልካች ያቀረበውን ክስ በማስረጃ አስረድቷል አላስረዳም የሚለውን ስናየው 3ኛ ተጠሪ ክሱን እና ማስረጃውን ክዶ የተከራከረ ቢሆንም ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ግንኙነት የነበረው መሆኑን፣ ሀሰተኛ መታወቂያ በማዘጋጀት፣ ከሽብር ቡድኑ አባል ከሆነ ግለሰብ ተደውሎለት ለሽብር ሥራ እንዲዘጋጁ በማድረግ ረገድ ቤት ኪራይ ተፈልጐላቸው በተገኘላቸው ጊዜም የደላላውን ኮሚሽን 3ኛ ተጠሪ መክፈሉ በምስክር ከመረጋገጡም በላይ በፖሊስ ጣቢያ 3ኛ ተጠሪ በሰጠው ቃል በግልጽ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም በ3ኛ ምስክር የታሸገ ፖስታ እንዲያመጣ ተልኮ ተቀብሎ አምጥቶ ለ3ኛ ተጠሪ ማስረከቡን የገለፀ ሲሆን በእርግጥ ፖስታ ውስጥ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የተዘጋጀው የቀበሌ መታወቂያ መሆኑን የሚያውቅ መሆኑን ያልመሰከረ ቢሆንም አመልካች ነገርን የሚያሳይ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ በሰጠው ቃል እንዴት ሀሰተኛ መታወቂያው እንደተዘጋጀ እና በማን ትዕዛዝ እና ከማን ጋር በነበረ ቅንጅት ሥራው እንደተሰራ በዝርዝር የገለፀ በመሆኑ የምስክሩ ቃል እና የ3ኛ ተጠሪ ቃል በጥምረት ሲታይ መታወቂያው በ3ኛ ተጠሪ ድጋፍ ለሽብር ቡድኑ አባላት የተዘጋጀ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል፡፡ እንዲሁም 3ኛ ተጠሪ ለሽብር ቡድን አባላት በሚል ዐቃቤ ሕግ ለሚጠቅሳቸው ግለሰቦች የባለሥልጣናትን ቤት እንዲያሳይ በተነገረው መሠረት ያሳየ ከመሆኑም በላይ ሥራው የተደረሰበት በመሆኑ ቦታ እንዲቀይሩ በተገለፀለት መሠረት ወደ ቢሾፍቱ የወሰዳቸው መሆኑን በሰጠው ቃል ያረጋገጠ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡ 3ኛ ተጠሪ በጣቢያ የሰጠው ቃል እና የአመልካች 2 ምስክሮች የሰጡት ቃል ተዳምሮ ሲታይ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ክስ ያስረዳ መሆኑን ያሳይል፡፡

ስለሆነም በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ መመዘን የሚገባው ሙሉ ይዘቱና እርስ በእርሱ የሚጣጣም እና የሚደጋገፍ መሆኑ ተመዝኖ በሚገኝ ውጤት እንጂ አንዱን ከአንዱ ማስረጃ በመለየት የየራሳን ክብደት ብቻ በመስጠት ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ በማስረጃ አላስረዳም በማለት በ3ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጐ 3ኛ ተጠሪን ከክሱ በነፃ ማሰናበቱ መሠረታዊ የማስረጃ ምዘና ስህተት የፈፀመ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህን ስህተት ሳያርም ማለፉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት አበይት ምክንያቶች አመልካች በ3ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ በማስረጃ ያስረዳ ሆኖ በመገኘቱ

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 142 መሠረት ሊከላከል ይገባል ብለን በሙሉ ድምጽ ፍርድ ሰጥተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሣኔ**

1).የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ቁ. 207676 በ21/10/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 328797 በ19/8/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 192/2/ለ/2 መሠረት በ3ኛ ተጠሪን አስመልክቶ ተሽሯል፡፡

2).3ኛ ተጠሪ በአመልካች የቀረበበትን ክስ እና ማስረጃ ሊከላከል ይገባል ብለን በሙሉ ድምጽ ወስነናል፡፡

3).የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በ3ኛ ተጠሪ ላይ በብይን ዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ መከላከያ ማስረጃ ካለው እንደያቀርብ እና እንዲከላከል በማድረግ ተገቢ ነው ያለውን ፍርድ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡

**ትዕዛዝ**

1.የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

2.መዝገቡ ላይ ውሣኔ የተሰጠ በመሆኑ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ክፍል ሁለት

## 2.ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ድንበር ማሻገር

### 2.1 (አዋጅ ቁጥር 909/2007)[95]

### (ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል የተፈጸመ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ተጠያቂነት)[96]

- አንድ ሰው ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል በሕገ-ወጥ መንገድ ሰዎችን የማዘዋወር ወንጀል ፈፅመሃል ሊባል ስለሚችልበት አግባብ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ- ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ሀ/ አግባብ ለብዝበዛ ዓላማ ሲል ዛቻን ሀይልን ወይም ሌላ ማናቸውም ዘዴ በመጠቀም በማገት፣ በመጥለፍ ወይም በተንኮል በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት በሕገ-ወጥ መንገድ ያዘዋወራቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፤

የሰ/መ/ቁ. 167965

ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሠፋ

ጻውሎስ ኦርጂሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስተበል አንዱዓለም

---

[95]ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

[96]የሰ/መ/ቁ. 167965 (ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም)ቅፅ 24

አመልካች/ቾች፡- አሕመድ ኢብራሃም ንጉሴ - አልተጠሩም።

ተጠሪ/ዎች፡- የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ - ዐ/ህግ ምዕራፍ ወርቁ - ቀረቡ።

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው። በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 09 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል በቀረቡብት ስድስት ክሶች ተሳትፎ ውጤቱንም የወሰደ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 60/ሐ እና 184/2 ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው።

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው።የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶች ስድስት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ጉቴ በተባለ ልዩ ቦታ በቀን 30/04/10 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 5፡00 ሰዓት ማንነቱ ካልታወቀ እና ለጊዜው በቁጥጥር ስር ያልዋለ ግለሰብ የግል ተበዳይ አሲያ አባጋሮ ሱቅ ሄዳ ስትመለስ አብዱልቃድር አባጋሮ ጥሩ ስራ አግኝቶልሻል አትፈልጊም ወይ? የሚደርስሽ ጥሩ ስራ እና ጥሩ ቦታ ነው በማለት በማባበል፣ አልፋው ስትገባ በማግስቱም መጥቶ በማባበል ነገ ስለምትሄዱ በማለዳ 1ኛ ተከሳሽ ጋር አደርሳችኂለሁ በማለት፤ በማግስቱም ከቤት በማስወጣት ስሙ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር በመሄድ 1ኛ ተከሳሽ ከሌላ ሰው ጋር በመሆን ተቀብሎ አመልካች ቤት በማምጣት በመሸሸግ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ያልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር ተበዳይዋን ፎቶ በማንሳት አትፍሪ ችግር የለም ሲቸግርሽ ለእኔ ትነግሪኛለሽ ፎቶሽን ደግሞ ብትጠፊ ትፈለጊበታለሽ ከሁለት ሳምንት በኂላ ወደ ውጪ ሐገር ሄደሽ እንድትሰሪ አደርግሻለሁ በማለት ወደ ሰው ቤት አሳልፈው በመስጠት ከሰዎች ጋር በስልክ እየተግባቡ ፖሊስ ባደረገው ክትትል የተያዘ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው።

2ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለጸው ሁኔታ ስሙ እና ማንነቱ ያልታወቀ ግለሰብ የግል ተበዳይ ሩሴ አባሲመንን በቀን 03//05/10 ከቤት በማውጣት ስሙ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር ሄዳ 1ኛ ተከሳሽ ስመ ካልታወቀው ግለሰብ ተቀብሎ ነቀምቴ ከተማ በማሳድር በቀን 04/05/10 አመልካች ቤት በማሳደር ሸሽጎ በቁጥጥር ስር ካልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር በ1ኛ ክስ የተገለጸውን ድርጊት በመፈጸም ላይ ሳሉ ፖሊስ ባደረገው ክትትል ስለተያዙ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው።

3ኛ ክስ- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ነብያት መሐመድን በቀን 03/05/10 ከቀነ- በግምት 8፡00 ሰዓት 1ኛ ተከሳሽ ከበደሌ ከተማ ወደ ነቀምቴ ከተማ እየተጓዘች ሳለ ከጎንዋ በመቀመጥ ጊምቢ ከተማ ጥሩ ስራ አለ ወደዚያው አደርስሻለሁ በማለት በሌሎች ክሶች ላይ የተገለጹትን ተበዳዮች ሲሳያት በደላላ እጅ ወደ ሌላ ሰው ቤት አልገባም እንጂ ስራ እፈልጋለሁ ስትለው የደላላ እጅ አላውቅም በማለት በድጋሚ አባብሏት በነቀምቴ ከተማ አሳድሯት በቀን 04/05/2010 በግምት 3፡00 ሰዓት በአመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ከአመልካች ባለቤት ጋር በቤታቸው ሸሽገው 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎባት አመልካች እና ባለቤቱ ደግሞ ፎቶ በማንሳት

አትፍሪ ስትጠፊ ትፈለጊበታለሽ ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ውጪ ሐገር እንድትሰሪ እናደርግሻለን በማለት ወደ ሌላ ሰው ቤት አሳልፈው ለመስጠት በስልክ እየተግባቡ ሳሉ በፖሊስ ክትትል ስለተያዙ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

4ኛ ክስ- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ህ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን ወ/ት ሳቢቃ ካማል የተባለችውን የግል ተበዳይ በቀን 30/04/10 ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ተብዳይ ሱቅ ሄዳ ስትመለስ 1ኛ ተከሳሽ በመንገድ አስቁሟት አዲስ አበባ አደርስሻለሁ እዚያ ሄደሽ ጥሩ ስራ ስርተሽ ገንዘብ ታገኛለሽ እራስሽንም ቤተሰብሽንም ትረጃለሽ በማለት፣ እማራለሁ አልሄድም ስትለው ሐሙስ ቀን ድረስ ተማሪ ከዚያ በኋላ ትሄጃለሽ በማለት በቀን 03/05/10 ጠዋት እንዲሄዱ በመንገር፣ ተበዳይዋ ቤተሰቦቿን ደብቃ ከቤት ወጥታ እንድትሄድ በማድረግ በ6ኛ ክስ ላይ ከተገለጸችው የግል ተበዳይ ጋር 1ኛ ተከሳሹ በመኪና አሳፍሯቸው ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱም በአመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ለጊዜው በቁጥጥር ስራ ካልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን በራሳቸው ቤት ውስጥ በመሸሸግ፤ 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎ አመልካች እና ባለቤቱ ደግሞ ፎቶ በማንሳት ወደ ውጪ ትሄጃለሽ በማለት በማባበል ወደ ሌላ ሰው ቤት አሳልፎ ለመስጠት ከሌሎች ሰዎች ጋር በስልክ እየተግባቡ ሳሉ በፖሊስ ክትትል የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

5ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ወ/ት ለይላ አህመድ የተባለችውን 1ኛ ተከሳሽ ጓደኛዋን ሳቢቃ ከማል በሕገወጥ መንገድ ለማዘዋወር በተደጋጋሚ ሲጠይቃት ቆይቶ በቀን 02/05/10 ከቀኑ በግምት 5፡00 ሰዓት መንገድ ላይ አግኝቷት ጊምቢ ወደ ተባለ ጥሩ ሐገር አደርስሻለሁ እዚያ ገንዘብ አግኝተሽ እራስሽን ችለሽ ቤተሰብሽንም ትረጃለሽ በማለት በማባበል በማግስቱ ጉዞ ስለሆነ ተዘጋጂ በማለዳ ተነስተን እንሄዳለን እኔ ቶባ ከተማ እጠብቅሻለሁ በማለት በቀን 03/05/10 ዓ.ም ጠዋት ከቤት በማውጣት 1ኛ ተከሳሽ መኪና አሳፍሯት ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱ ወደ አመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ለጊዜው ካልተያዘችው የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን ከላይ ባሉት ክሶች በተገለጸው ሁኔታ የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

6ኛ ክስ - ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ህ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ስዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ወ/ት አይሻ አህመድ የተባለችውን በጓደኛዋ ሳቢቃ ከማል በቀን 02/05/10 ዓ.ም የሐሰት ቃል በመንገር በማታለል በማግስቱ ከቤት በማውጣት በ4ኛ ክስ ተበዳይ ከሆነችው ከሳቢቃ ከማል ጋር በመሆን 1ኛ ተከሳሽ መኪና አሳፍሮ ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱ በአመልካች መኖሪያ ቤት በማምጣት ሸሽገው 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎባት ካልተያዘቸው የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን ከላይ ባሉት ክሶች በተገለጸው ሁኔታ የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ተቀብለውታል የተባለው የገንዘብ መጠን በክሱ ውስጥ አልተገለጸም በማለት ክሱን ተቃውመው ክስ በዚህ አግባብ እንዲሻሻል የተደረገ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ አመልካች የእምነት ክሕደት ቃሉን ሲጠየቅም በዓቃቤ ሕግ ክስ መሠረት ድርጊቱ ያልተፈጸመ መሆኑን፣ በቀን 4/5/10 ዓ.ም ፖሊስ ተበዳዮችን በ2ኛ ተከሳሽ ቤት ሄዶ ሲቆጣጠር 1ኛ ተከሳሽ በ2ኛ ተከሳሽ ቤት የሚቀመጥ ልጅ ስላለው ወደ 2ኛ ተከሳሽ ቤት ሄዶ በር ሲያንኳኳ ወደ ራሱ ቤት ያስገባቸው ቀድሞውኑ 1ኛ ተከሳሽን ስለሚያውቅ እንጂ ስለተበዳዮቹ የሚያውቀው ነገር የሌለ መሆኑ እና 1ኛ ተከሳሽም ማዘዋወሩን የሚያውቀው ነገር የሌለ መሆኑን፤ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የተባለውን ወንጀል ያልፈጸመ መሆኑን፤ በአመልካች ቤት ቆይተው የሄዱት አንድ

ሰዓት ለማይበልጥ ጊዜ መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን የሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ሰምቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ከሰማ በኂላ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ 1ኛ ተከሳሾች ተበዳዮችን ጥሩ ገንዘብ ታገኛላችሁ በማለት ተስፋ ስጥቶአቸው መልምሎ በማጓጓዝ ወደ ግምቢ ከተማ ማምጣቱን 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ከሰዎች ጋር በስልክ መነጋገሩን እና ተበዳዮችን ከ1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ በድርጊቱ መሳተፉን ስላስረዳ ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የስር 1ኛ ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት ያስመዘገበ መሆኑን እና አመልካች ደግሞ ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ፍ/ቤቱም በመቀጠል የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኂላ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ከጥርጣሬ በላይ በሆነ መልኩ ተከሳሾች የተከሰሱበትን ወንጀል መፈጸማቸውን አስረድተዋል፤ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል አጠራጣሪ ነው ፤አመልካች ተመልምለው የተስፋ ቃል ተሰጥቶአቸው ተጭነው ወደ ቤቱ የመጡትን ተበዳዮችን ከ1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ በር ከፍቶ መቀበሉ ዋሳችሁ እኔ ነኝ የምትቸገሩት ነገር የለም ከ2-3 ዓመት ከስራችሁ ወደ ውጪ ሐገር እልካችኂለሁ በማለት የተስፋ ቃል መስጠቱ የተረጋገጠ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ህ መሠረት በስድስቱም ክሶች ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማስላት በ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 10000 መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- በተጠሪ ምስክሮች እንደተገለጸው የግል ተበዳይ ናቸው የተባሉት ወጣት ሴት ስራተኞች ወደ ጊምቢ ከተማ የመጡት በቤት ሰራተኝነት አገልግለው የሚገባቸውን ተመጣጣኝ ደመወዝ ለማግኘት ከመሆኑ በቀር ለብዝበዛ ዓላማ አይደለም፤ ደመወዛችን ተመጣጣኝ አይደለም ባሉም ጊዜ ሥራውን አቋርጠው የመሄድ ሙሉ መብት አላቸው፤ ይህም በማናቸውም የቤት ሰራተኛ የቅጥር ግንኙነት የተለመደ ተግባር ነው፤ በመሆኑም የወንጀሉ ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬነገር ባልተሟላበት ሁኔታ የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠጠቱ አግባብ አይደለም አመልካች የግል ተበዳዮችን ያየሁት ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ሆነው ወደ ቤቴ በመጡ ጊዜ ነው፡፡ የሰር 1ኛ ተከሳሽ ልጅ በእኔ ቤት ተቀጥራ ትሰራ የነበረ በመሆኑ ልጁን ለመጠየቅ ነው የሚል ግንዛቤ ነበረኝ፣ የልጁ ቀጣሪ ከመሆነን ውጪ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ሌላ ምንም ዓይነት ግንኙነት የለኝም አመልካች በቤቴ እንዳለሁ በቁጥጥር ስር በዋልከብት ጊዜ የሞባይል ስልኬ ወዲያው የተያዘ በመሆኑ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር አስቀድሞ የነበረ ግንኙነት ቢኖረኝ ኖሮ ተጠሪ በቴሌኮም ማስረጃ ከማስረዳት የሚያግደው ነገር አልነበረም፣ ፎቶ አንስተሀል የሚለው አውነት ቢሆን ኖሮ ተጠሪውም የፎቶግራፍ ማስረጃውን እንደማስረጃ ያቀርበው ነበር፣ ፎቶግራፍ ማንሳቱ ተረጋግጦ ቢሆን ኖሮ እንኳን ይህን ማድረጌ ብቻ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የእድሜየን ግማሽ ማረሚያ ቤት እንዳሳልፍ የሚያደርገኝ አይደለም አመልካች ስለግለሰቦቹ ከተማ መምጣት ምንም እውቀት ያልነበረኝ በመሆኑ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ ልል የምችልበት መነሻ ሁኔታ ስለሌለ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ሕገወጥ የስዎች ዝውውር ለመፈጸም ሀሳብ የነበረው ለመሆኑ እና በድርጊቱም ስለመሳተፉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ሀ መሠረት በቀረቡበት ስድስት ክሶች ጥፋተኛ የመባሉን አግባባነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ጋር

በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ፣ ለጊዜው ካልተያዘች ባለቤቱ እና ማንነቱ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር በመሆን ስራ ስርታችሁ ትለወጣላችሁ በማለት ስድስት ሴት ልጆችን መልምሎ በመኪና ወደ ነቀምት ከተማ ወስዷቸው ካሳደሯቸው በኋላ በማግስቱ ወደ ጊምቢ ከተማ አስገብቶ በማቆየት ለልጆቹ ምግብ ከሰጡ በኋላ ሥራ ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ! ከ 2 ወይም 3 ዓመት በኋላ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ በማለት ለማስታወሻ የሚሆን ፎቶ አንስቶአቸው እንደነበር እና ክብር 1000 እስከ 1500 ብር ይዛችሁ ትመጣላችሁ በማለት ስልክ ከሌላ ሰው ጋር እየተደዋወለ ሳለ ድንገት ፖሊስ ደርሶባቸው እጅ ከፍንጅ እንደተያዙ ያስረዳን በመሆኑ ለብዝበዛ ዓላማ ሊያውል እንደነበር አመላካች ነው፡፡ አመልካች በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ፍሬነገር ባቀረቡት ማስረጃ ያላስተባበለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ስጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል በማለት የተያዘው ነጥብ አመልካች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ለመፈጸም ሀሳብ የነበረው ለመሆኑ እና በድርጊቱም ስለመሳተፉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ህ መሠረት በቀረቡበት ስድስት ክሶች ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር በሚል በመሆኑ የዐቃቤሕግ ምስክሮች አመልካችን በሚመለከት በስር ፍ/ቤት የሰጡትን የምስክርነት ቃል ይዘት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተናል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ለስር ፍ/ቤት የስጡት የምስክርነት ቃል ይዘት ጠቅለል ብሎ ሲታይ ማንነቱን የማያውቁት ሰው ትሄዳላችሁ ብሎ ያባበላቸው መሆኑን እና ወደ ሌላ ከተማ ጉዞ ሲያደርጉ የጉዞ ወጪ ሲሸፍን የነበረው 1ኛ ተከስሳሽ መሆኑን፣ ካሉበት ከተማ ወደ ጊንቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ወደ ሆነችው አለውያ ቤት የገቡ መሆኑን እና ስትጠፉ ትፈለጉበታላችሁ ተስተካከሉ ብለው ፎቶ ያነሳቸው መሆኑን ሐገሪቱ ጥሩ ናት ስርታችሁ ትለወጣላችሁ ከ2 እስከ 3 ዓመት ስትሰሩ ደግሞ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ ያላቸው መሆኑን፣ 1ኛ ተከሳሽ ስልክ ሲደወልለት አንተ የምትለውን ልጆች አምጥቼልሀለሁ ያላቸው መሆኑን፡ የአመልካች ባለቤት አሲያ እና ሳቢቃ አስቀራቸዋለሁ ሌሎቹን እንደፈለግክ አድርግ ያለች መሆኑን ስልክ ደውላም ገንዘብ ይዘሽ ነይ ያለች መሆኑን እና አሲያን እና ሳቢቃን አስቀርተው ከቤት እየወጡ ሳሉ ፖሊስ የመጣባቸው መሆኑን በመግለጽ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን 6ኛ ምስክር ደግሞ በጊምቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ቤት ሲባል መረጃ ሰምተው ሄደው በቤት ውስጥ ያሉ ልጆች አምጧቸው ሲባል ሰዎቹን ያመጧቸው መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽን ሊያናግሩ ከጅማ ዞን የአመልካችን ባለቤት ላነጋግራት መጥቻለሁ ያላቸው መሆኑን፤ ፖሊስ ጽ/ቤት ልጆቹን የወሰዷቸው መሆኑን እና ፖሊስ ሲመረምራቸው 1ኛ ተከሳሽ በፈለጋችሁበት ቦታ ገንዘብ ታገኛላችሁ ብሎ አባብሎ አምጥቶናል በማለት ገልጸዋል በማለት የመስከረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.

111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቶአል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሠረት ተከሳሹ ወንጀል እሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.142 መሠረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

አመልካች የተከሰሰበት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ስደተኞችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ማንኛውም ሰው በኢትዮጲያ የግዛት ክልል ውስጥም ሆነ ከኢትዮጲያ የግዛት ክልል ውጪ ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል በአገር ውስጥ ስራ እና ስራተኛን ለማገናኘት ወይም ለስራ ወይም ለስራ ልምምድ ወደ ውጪ አገር ለስራ መላክ በሚል ሽፋን ዛቻን ሀይልን ወይም ሌላ ማናቸውም ዘዴ በመጠቀም፣ በማገት፣ በመጥለፍ ወይም በተንኮል በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት ሰዎችን የመለመለ ያጓጓዘ፤ ያዘዋወረ፣ ያስጠለለ ወይም የተቀበለ እንደሆነ እና ይህም ድርጊት በሕጻናት በሴቶች ወይም በአእምሮ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ የተፈጸመ እንደሆነ ከ 25 ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት ወይም እድሜልክ ጽኑ እስራት እና ክብር 200000-500000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተክሰስን ሰው ጥፋተኛ ለማለት ተከሳሹ በድንጋጌው በተገለጸው አግባብ ድርጊቱን የፈጸመ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥበት ይገባል፡፡

የብዝበዛ ዓላማ ማለት ደግሞ በሌሎች ሰዎች ዝሙት አዳሪነት መጠቀም ወይም ማናቸውም ዓይነት ወሲባዊ ብዝበዛን፤ የጉልበት ብዝበዛን የግዳጅ ስራን ወይም አገልጋይነት፣ ባርነት ወይም ባርነት መሰል ተግባር፣ የወሲብ አገልጋይነትን ጨምሮ ሰውን የማይገባ አገልጋይ ማድረግ፤ በመያዣነት መያዝ ወይም አሳልፎ ለሌላ መስጠት፤ የሰው ልጅን አካል ማውጣት ወይም መወስድ፣ አስገድዶ በልመና ተግባር ማሰማራት ወይም ሕጻናትን ለወታደራዊ አገልግሎት ማሰማራት እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 2/4 ላይ ከተሰጠው ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ክሱን ለማስረዳት የቀረቡት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ካሉበት ከተማ ወደ ጊንቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ወደ ሆነችው አለውያ ቤት የገቡ መሆኑን እና ስትጠፉ ትፈለጉበታላችሁ ተስተካከሉ ብለው ፎቶ ያነሳቸው መሆኑን፤ ሐገሪቱ ጥሩ ናት ስርታችሁ ትለወጣላችሁ ከ2 አስከ 3 ዓመት ስትስሩ ደግሞ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ከመመስከራቸው በቀር አመልካች በተከሰሰበት የአዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌ አግባብ አመልካች ለብዝበዛ ዓላማ ሲል ዛቻን ሀይልን ወይም ሌላ ማናቸውም ዘዴ በመጠቀም በማገት በመጥለፍ ወይም በተንኮል በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት በሕገወጥ መንገድ ያዘዋወራቸው መሆኑን በመግለጽ የሰጡት የምስክርነት ቃል የለም፡፡ አመልካች በሕጉ በተገለጸው አግባብ የግል ተበዳዮኞችን በሕገወጥ መንገድ ስለዘዋወሩ እስካልደረሰ ድረስ የተከሰሰበትን የሕግ ድንጋጌ ጥሰናል በማለት ጥፋተኛ አይደሉም፡፡ ይህንንም የማረጋገጥ ምክንያት ስለሌለ አመልካች ከቀረበበት ክስ በነጻ ሊሰናበት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በሕጉ አግባብ ድርጊቱን ስለመፈጸሙ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአመልካቹ ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1.በአሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 35700 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት

ውሳኔ፣ ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 214895 በቀን 11/08/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/1/2 መሠረት ተሽሯል፡፡

2.ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ከተከሰሰበት ክስ በነጻ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡

**ትዕዛዝ**

የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 35700 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ! ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 214895 በቀን 11/08/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በነጻ እንዲሰናበት የተወሰነ መሆኑን አውቆ አመልካችን ከእስር እንዲለቅ ታዟል፡፡ ይጻፍ

መዝገቡ ውሳኔ ስለገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 2.2 (አዋጅ 1178/2012)[97]

## (በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን)[98]

- በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 42(2)፣ አንቀጽ 3/1፣ አንቀጽ 8(3)፣ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አዋጁ በዋነኝነት ጉዳዮቹን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ለፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መስጠቱን፤
- በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሶስት ዳኞች ስለሚታዩ ጉዳዮች አስመለክቶ በተሰጠው መመሪያን የማውጣት ስልጣን መሠረት የሕገ-ወጥ ሰዎች ዝውውር እና ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ጉዳዮች ልዩነት ሳይደረግባቸው ሶስት ዳኞች በሚሰየሙበት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ማድረጉ አዋጁን መሠረት በማድረግ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በጥንቃቄ እንዲታዩ ለማድረግ የሚያስችል እና የአዋጁን ዓላማ የሚያሳካ ነው ከሚባል በቀር በሁለቱም ሕጎች መካከል የሚታይ ተቃርኖ የለም፡፡[99]

የሰ.መ.ቁ 231739

ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

[97]በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

[98]የሰ/መ/ቁ 231739 (ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም)

[99]በሰ/መ/ቁ፡ 244110(ሐምሌ 29 ቀን 2016 ዓ.ም)

አመልካች፡- የፍትሕ ሚኒስቴር ዓቃቤሕግ

ተጠሪዎች፡- 1. አብዱልሽኩር ኢማም አብዶ

2. አብዱላዚዝ ራሕመቶ ዳንዴር

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሐምሌ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 009769 ሠኔ 27 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 230369 ሐምሌ 13 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንድ ዳኛ በተሰየመበት ችሎት የአሁን ተጠሪዎች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና የአዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 3/1 ድንጋጌን በመተላለፍ በሰው መነገድ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለለት ፍርድ ቤትም ይህንኑ ክስ መሠረት በማድረግ የተጠሪዎችን የዋስትና መብት ውድቅ አድርጓል፡፡

ተጠሪዎች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች የተከሰሱት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ስደተኞችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 3/1 የተደነገገውን በመተላለፍ በፈጸሙት በሰው መነገድ ወንጀል ነው፤ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 29(4)(ለ)፤ 55(2) እና በ3 ዳኞች ስለሚሰየሙበት ችሎት የሚደነግገው መመሪያ ቁጥር 009/2013 አንቀጽ 2.2(ለ)፤ 5(ሀ) እና 7 መሠረት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀጥታ ክስ በሚታዩበት ጊዜ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ በሚታዩበት ጊዜ 3 ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ሊታይ የሚገባ መሆኑን ይደነግጋል፤ በሕጉ አግባብ ሊሟሉ የሚገባቸው ዳኞች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ እንደተሰጠ የማይቆጠር እና ሕጋዊ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ በሰ.መ.ቁ 73696 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፤ ተጠሪዎች በአዋጁ አንቀጽ 3(1) የተመለከተው ድንጋጌ ተላልፈዋል ተብሎ የተገለጸው የወንጀል ድርጊት 3 ዳኞች በተሰየሙበት የሚታይ ሆኖ ሳለ በአንድ ዳኛ ታይቶ የተሰጠው ብይን ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ የስር ፍርድ ቤት የዋስትናውን ጉዳይ 3 ዳኞች በተሰየሙበተ ችሎት በማየት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ሐምሌ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ዓቃቤሕግ ክስ የመሰረተው የአዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 3/1 ድንጋጌን በመጥቀስ ሲሆን በአዋጁ በሶስት ዳኞች ችሎት የሚታዩ ተብለው ከተመለከቱት የወንጀል ድንጋጌዎች ውስጥ የሚካተት አይደለም፤ ክሱ የቀረበበት ድንጋጌ በአንድ ዳኛ ብቻ ታይቶ ሊወሰን የሚችል ነው፤ ተጠሪዎች የተከሰሱበት ሕግ የሚያስቀጣው ከሰባት እስከ አስራአምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሶስት ዳኞች ከሚታዩ ጉዳዮች ውስጥ የሚካተት አይደለም፤ አንድ መመሪያ በልዩ አዋጅ ከተደነገገ ጉዳይ ጋር ተቃርኖ ካለው ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም፤ በልዩ ሁኔታ በመመሪያ የሚቋቋም ችሎት የአስገዳጅነት ባሕርይ የለውም፤ ችሎቶቹ ሊደራጁ የሚችሉ ቢሆንም እስካልተደራጁ ድረስ ወይም በመመሪያ እንዲደራጁ ቢወሰንም መመሪያውን መሠረት በማድረግ ተሰይመው ወደ ስራ እስካልገቡ ድረስ ጉዳዩ በአንድ ዳኛ ለተቋቋመ ችሎት ቀርቦ ሊታይ

ይችላል፤ ጉዳዩ በሶስት ዳኛ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ቢወሰን እንኳን ልዩ ሕግ የሆነው ተጠሪዎች የተከሰሱበት አዋጅ ቅድሚያ ተፈጻሚነት አለው፤ አንድ ጉዳይ በአንድ ዳኛ ሊታይ አይችልም ለማለት የሚከለክለው ሕግ ሊኖር ይገባል፤ የአደረጃጀት አማራጮችም እንደፍጹም ክልከላ ሊቆጠሩ አይገባም፤ በሰ.መ.ቁ 73696 የተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በአንድ ዳኛ የተሰጠውን ውሳኔ ለማጽናት እንጂ ውድቅ ለማድረግ ጥቅም ላይ ሊውል አይገባም፤ ይህ ውሳኔ ሕጉ እንዲሟሉ በአስገዳጅነት የሚጠይቀውን ቁጥር በተመለከተ ሊታዩ የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆን ነው፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስላልሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለክርክር መነሻ የሆነውን የዋስትና ጉዳይ በሚመለከት በሶስት ዳኞች ሊታይ ይገባል በሚል በአንድ ዳኛ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ወደ ስር ፍርድ ቤት እንዲመለስ የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 እና አዋጁን ተከትሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር 009/13 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 መካከል ትክክለኛ ተቃርኖ የለም፤ የፍርድ ቤቶች አወቃቀር እና የዳኞችን ቁጥር ለመወሰን እንደልዩ ሕግ የሚቆጠረው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 እንጂ ተጠሪዎች የተከሰስንበት ሕግ አይደለም፤ በሁለቱ ሕጎች መካከል ተቃርኖ አለ ከተባለም ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው በኋላ የወጣው አዋጅ ነው፤ የዳኛ ቁጥር ሳይሟላ የተሰጠ ውሳኔ የጸና ፍርድ ለመስጠት አያስችልም በሚል የፌዴራል ጠቅላይ ፍረድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 13 በሰ.መ.ቁ 73696 አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሶስት ዳኞች ታይቶ ሊወሰን ሲገባው አዋጁን እና መመሪያውን በተቃረነ መልኩ በአንድ ዳኛ ብቻ ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ ጸንቶ የዋስትና መብታችን ሊፈቀድ ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ዓቃቤሕግ ለዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዎች የተከሰሱበት በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ በአዋጁ ላይ በሶስት ዳኞች እንዲታዩ ከተመለከቱት ጉዳዮች ውስጥ አይደለም በሚል ነው፡፡ ይህንኑ የዓቃቤሕግ ክርክር መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደተመለከትነው የአዋጁ አንቀጽ 42(2) የዳኝነት ስልጣንን የሚመለከት ሲሆን በንዑስ አንድ ላይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአዋጁ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 4(2) እና አንቀጽ 8(3) የተመለከቱ ጉዳዮች የሚታዩት ሶስት ዳኛ በተሰየመበት ችሎት ይሆናል በማለት ይደነግጋል፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የአዋጁ አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከሀያ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ የሚያስቀጣ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 4(2) ደግሞ የአንቀጽ 3(1)(2) አክባጅ ሁኔታን የሚመለከት ድንጋጌውን ተላልፎ ወንጀል የፈጸመ ሰው ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሀያ አምስት ዓመት እና ከሀምሳ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 8(3) ድንጋጌም አክባጅ ሁኔታን የሚመለከት ሆኖ ድንጋጌውን ተላልፎ ወንጀል የፈጸመ ሰው ከአስር ዓመት እስከ 20

ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከሰላሳ ሺኅ እስከ አንድ መቶ ሀምሳ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ያስቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አዋጁ በዋነኝነት ጉዳዮቹን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ለፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መስጠቱን እና ወንጀል ፈጻሚወቹ የፈጸሙትን ወንጀል እና የሚጣልባቸውን የቅጣት መጠን መሠረት በማድረግ ደግሞ ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየት ያለባቸውን ጉዳዮች ለይቶ ያስቀመጠ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በየደረጃው ያሉ የፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ስላላቸው ስልጣን እና ስለሚያይዋቸው ጉዳዮች በዝርዝር ደንግጓል፡፡ ከዚሁም ባሻገር በአዋጁ አንቀጽ 29/4(ለ) እና 55(2) ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ የተወሰኑ ጉዳዮች በፌዴራል ከፍተኛ እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በሶስት ዳኞች እንዲታይ ሊደረግ እንደሚችል እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አዋጁን ወይም አዋጁን ተከትሎ የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ እንደሚያወጣ በግልጽ ደንግጓል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሶስት ዳኞች ስለሚታዩ ጉዳዮች ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 009/2013 ዓ.ም አውጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ይህ መመሪያም የሕገወጥ ሰዎች ዝውውር እና ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ጉዳዮች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሶስት ዳኞች የሚታዩ መሆኑ በግልጽ ደንግጓል፡፡ ዓቃቤሕግ በሁለቱም ሕጎች መካከል ተቃርኖ ስላለ ተፈጻሚ መሆን ያለበት ወንጀሉን አስመልክቶ የወጣው ልዩ ሕግ ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም በሁለቱም ሕጎች መካከል በግልጽ የሚታይ ተቃርኖ የለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ተጠሪዎች በተከሰሱበት አዋጅ ላይ አክባጅ ሁኔታዎችን እና የቅጣት መጠንን ታሳቢ በማድረግ በሶስት ዳኞች ሊታዩ ይገባቸዋል ተብለው ከተለዩት ጉዳዮች በተጨማሪ ያለውን የሰው ሀይል / የዳኛን ቁጥር / አመጣጥኖ ችሎቶችን የማደራጀት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሶስት ዳኞች ስለሚታዩ ጉዳዮች አስመለክቶ በተሰጠው መመሪያን የማውጣት ስልጣን መሠረት የሕገወጥ ሰዎች ዝውውር እና ሰዎችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ጉዳዮች ልዩነት ሳይደረግባቸው ሶስት ዳኞች በሚሰየሙበት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ማድረጉ አዋጁን መሠረት በማድረግ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በጥንቃቄ እንዲታዩ ለማድረግ የሚያስችል እና የአዋጁን ዓላማ የሚያሳካ ነው ከሚባል በቀር በሁለቱም ሕጎች መካከል የሚታይ ተቃርኖ የለም፡፡ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አልተገኘበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 009769 ሠኔ 27 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 230369 ሐምሌ 13 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## 3.የሙስና ወንጀሎች አዋጅ[100]

### 3.1 የተከሳሽን የአሳብ ክፍል የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ የሚዛወርበት[101]

➢ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ድንጋጌ እና የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 መሰረት ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 መሠረት የአንድ ተከሳሽን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን ስለመሆኑ እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብል የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ የሚዛወር ስለመሆኑ፤[102]

የሰ/መ/ቁ 162738

መጋቢት 30 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሡፋ
ጳውሎስ ኦርሺሶ
ፀሐይ መንክር
መላኩ ካሣዬ
እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡-
1. አቶ መሐመድ ያዕቆብ ከድር አልይዘአ
2. አቶ ዘውዱ ጂዳ
3. አቶ እሸቱ አበበ
4. አቶ ኡመር መሐመድ
5. አቶ ዳምጠው ለማ
6. አቶ መሐመድ አወል ጀማል ከድር
7. አቶ ሀይሌ ተሰማ አያኔ
8. አቶ ዳምጠው ጀግና
9. ወ/ሮ ገነት ሁስማን ሼካ

---

[100]አዋጅ ቁጥር 881/2007

[101]የሰ/መ/ቁ 162738(መጋቢት 30 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24

[102]በሰ/መ/ቁ 117383 (መስከረም 6 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19፣ በሰ/መ/ቁጥር 211167 (ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም )ቅፅ 26፣ በሰ.መ.ቁ 218793፤ 219208 እና 220345 (ሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ. 231681( ሕዳር 26 ቀን 2015 ዓ/ም)፣ በሰ/መ/ቁ/225709 (ህዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 230272 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁጥር 247213 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም)፣ በሰበር መ/ቁ 261944 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ/ም)፣ በሰ/መ/ቁ 261767 (ህዳር 27 ቀን 2017 ዓ.ም)

10. ወ/ሮ ሀዋ አደም
11. አቶ ዘውዴ ሽመልስ ለገሰ
12. አቶ መሐመድ ቃሲም ገርበ
13. አቶ አብዱልቃድር ከድር አሎ
14. አቶ አበራ ቶሎሳ ጋሹ
15. ወ/ሮ ቀመሪያ ገሮ ሐቤቤ

**ተጠሪ፡-** የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጸረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተክታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሲቀርብ የቻለው አመልካቾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት ነሐሴ 17 ቀን 2010 ዓ.ም ተጽፎ በቀረበ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22898 አመልካቾች ያቀረብነውን መቃወሚያ በማለፍ የሰጠው ብይን፤ በዚሁ መዝገብ በቀን 10/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በቀን 11/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፣ ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 278007 በቀን 21/09/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት በመጠየቃቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሙስና ወንጀልን በሚመለከት የቀረበ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አመልካቾችን ጨምሮ በ38 ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረበ ሲሆን የአሁን አመልካቾች እንደ ቅደም ተከተላቸው 1ኛ፤ 2ኛ ፤3ኛ፤ 4ኛ፤ 5ኛ፤ 6ኛ፤ 7ኛ፤ 8ኛ ፤9ኛ፤ 12ኛ፤ 13ኛ፤ 14ኛ፤ 16ኛ፤ 19ኛ እና 21ኛ ተከሳሾች ናቸው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች እና ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ባላቀረቡ ቀሪ ተከሳሾች ላይ በስር ተከሳሾች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶች 11 ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ስድስቱ ክሶች አመልካቾችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይዘታቸውም፡-

<u>1ኛ ክስ፡-</u> አመልካቾች እና የስር 10ኛ፤11ኛ፣15ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 ድንጋጌን በመተላለፍ የሮቤ ከተማ ማኔጅመንት፣ የሮቤ ከተማ መሬት አስተዳደር እና ማኔጅመንት ሆነው ሲሰሩ የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በመንግስት እና በሕዝብ ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው አመልካቾች እና የስር 10ኛ ፤11ኛ፤ 15ኛ ተከሳሾች በቀን 01/10/2007 ዓ.ም ቃለጉባኤ በመያዝ፣ የስር 10ኛ፣ 11ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች እንዲሁም የአሁን 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በያዙት ቃለጉባኤ መሬት የመንግስት እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሐብት እና የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑን እያወቁ፤ የገጠር መሬት ወደ ከተማ መሬት ሲካለል በፌዴራል አዋጅ 455/97 721/2004፣ በኦሮሚያ የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 ደንብ ቁጥር 155/2005 እና መመሪያ ቁጥር 9/2005 መሠረት መፈጸም እንዳለበት እያወቁ ሕግ የሚፈቅድላቸው በማስመሰል በከተማ ስር የገባውን የገጠር መራት 45% መሬት የገበሬ ነው፤ 55% መሬት ደግሞ የመንግስት ነው ተብሎ ተከፋፍሎ የቆየ እና ይህን መሬት ገበሬጡ በሽያጭ ሲያስተላልፍ የቆየ መሆኑን በያዙት ቃለጉባኤ ገልጸው እያለ ሕገወጥ ግንባታ እና የድሮ ይዞታ በማስመሰል ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ስፋቱ 247,161 እና 997 ፕሎት መሬት 76 ለሆኑ ገበሬዎች በመስጠት ለእነዚህ ገበሬዎች በሕጉ አግባብ ለእያንዳንዳቸው 500 ካ.ሜ መሬት ተስጥቷቸው ቢሆን ኖሮ ስፋቱ 894,970 እንዲሰጥ በማድረግ መንግስት ሊያገኝ የሚችለው ገቢ 199,277.70 ስላሳጡት ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

2ኛ ክስ፡- አመልካቾች እና 10ኛ፡ 11ኛ115ኛ ተከሳሾች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 በመተላለፍ በ1ኛው ክስ ውስጥ በተወሰነው ውሳኔ መሠረት ቁጥራቸው 308 ለሆኑ ሰዎች በድምሩ ስፋቱ 120,000 የሆነ መሬት እንዲሰጥ በመወስን፣ 1ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች፤ 14ኛ አመልካች እና የስር 36ኛ ተከሳሽ ደግሞ መሬት በወሰዱ እና በከተማው አስተዳደር መካከል የተደረገውን ሕገወጥ ውል በማጽደቅ፤ 27ኛ፤ 28ኛ እና 29ኛ ተከሳሾች በሕገወጥ በተላለፈው በዚህ መሬት ላይ ካርታ በማዘጋጀት የስር 10ኛ፣ 11ኛ 23ኛ እና 36ኛ ተከሳሾች እና 13ኛ እና 14ኛ አመልካቾች ደግሞ በሕገወጥ መንገድ በተሰጠ መሬት ላይ የተዘጋጀን ካርታ በማጽደቅ 16ኛ አመልካች እና 20ኛ1 24ኛ) 265 28V 30ኛ 31ኛ፡ 38ኛ ተከሳሾች ሕገወጥ የሆነን ቅጽ በመሙላት፣ በአጠቃለይ ተከሳሾች በጋራ በመሆን ሕዝብና መንግስት እኩል ሊጠቀሙበት የሚገባውን ይዞታ ሕግ እና መመሪያ በመተላለፍ ስፋቱ 65,755 የሆነ መሬት ለግለሰቦች እንዲሰጥ በማድረግ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገበ. 14,624,569.75 አሳጥተዋል የሚል ነው፡፡

3ኛ ክስ፡- 17ኛ እና 18ኛ ተከሳሾች የአዋጁን አንቀጽ 9/1/ለ ድንጋጌ በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በቀን 01/07/07 እና 03/09/07 በያዙት ቃለጉባኤ ሕገወጥ የመሬት አሰጣጡን ስራ ላይ የማዋል ድርጊት በመገምገም ሕገወጥ ስራው እንዲቀጥል አድርገዋል የሚል ነው፡፡

4ኛው ክስ፡- 1ኛ እና 8ኛ አመልካቾች እንዲሁም 10ኛ 17ኛ እና 18ኛ ተከሳሾች የኦሮሚያ ከተማ መሬቶችን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣውን ደንብ ቁጥር 155/2005 አንቀጽ 59/1 ድንጋጌን በመተላለፍ በ3ኛ ክስ የተገለጸውን ቃለጉባኤ በመያዝ ሕገወጥ የሆነውን 45/55 ተብሎ የሚታወቀውን አሰራር በስራ ላይ እንዲውል አድርገዋል የሚል ነው፡፡

5ኛ ክስ፡- 10ኛ፤ 11ኛ፤ 120ኛ ተክሳሾች፣ 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 ድንጋጌን በመተላለፍ የሮቤ ከተማ አስተዳደር እና ማኔጅመንት ኮሚቴዎች በመሆን እና 17ኛው ተከሳሽ የገቢዎች የባለስልጣን ሀላፊ በመሆን የሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 በመተላለፍ 10ኛ፤ 11ኛ፤120ኛ ተከሳሾች እና 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በቀን 14/09/2007 በያዙ-1-ቃለጉባኤ ገበሬዎች ከድርሻቸው መሬት ላይ የሸጡትን ይዞታ የድሮ ይዞታ በማስመሰል ክፍያ እንዲፈጸምበት በመወሰን ለገቢዎች ባለስልጣን በመላክ፤ 17ኛው ተከሳሽ በተለያዩ ጊዜዎች ሲይዟቸው በነበሩት ቃለ ጉባኤዎች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን እያወቀና እያየ ይህ ክፍያ እንዲፈጸም አድርጓል የሚል ነው፡፡

6ኛ ክስ፡- 1ኛ እና 15ኛ አመልካቾች 10ኛ 11ኛ እና ከ22ኛ እስከ 25ኛ ያሉ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና የሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ሐን በመተላለፍ 15ኛ አመልካች እና ክ22ኛ እስክ 25ኛ ያሉት ተከሳሾች ሕገወጥ በሆነ መንገድ የአጣሪ ኮሚቴ ሆነው በመመረጥ መመሪያው እንደሚከለክላቸው እያወቁ እንደ ሕጋዊ ኮሚቴ አራሳቸውን በመቁጠር በሮቤ ከተማ መሬት ማኔጅመንት ኤጀንሲ በሚጣራ የመኖሪያ ቤት ክምችት በቀን 11/01/07 ቁጥሩ 1076/k13/2007 በሆነ እና ለባሌ ዞን መሬት ማኔጅመንት እና ልማት ኤጀንሲ በተጻፈ ደብዳቤ 530 ሰዎች ብቻ ተጣርተው የተላኩ ሆኖ ሳለ 56 ሰዎችን በመጨመር እና ሌሎች ስዎችን በመቀነስ አጣርተው ልከዋል የሚል ነው፡፡

የአሁን 4ኛ፤15ኛ፤ 8ኛ፤ 10ኛ አመልካቾች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ ጉዳያቸው 1ኛ፤ 2ኛ፤ 3ኛ፤ 6ኛ፤ 7ኛ፤ 19ኛ ፤11ኛ፣ 12ኛ፣ 13ኛ፣ 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች ችሎት ቀርበው ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ ተደርጓል፡፡ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁም ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ፍ/ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ሰምቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የዓቃቤሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል እና ዓቃቤሕግ ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን የስነድ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ድረስ ያሉት ክሶች ተከሳሾች 45/55

የተባለን አሰራር በስራ ላይ እንዲውል መወሰናቸውን እና በስራ ላይ ከማዋላቸው ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በዚህ አሰራር መሬት ተሰጥቷቸዋል የተባሉት ሰዎች በተለያዩ ክሶች የተገለጹ ቢሆንም በተያዘው ቃለ ጉባኤ የተጣሩ ሰዎች እራሳቸው ናቸው፤ ይህም በአንድ በሕግ በተጠበቀ መብት ላይ የተፈጸመን ወንጀል ከግብ ለማድረስ ተቀላቅለው የተፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች መሆናቸውን የሚሳይ ነው፤ በሌላ በኩል ድርጊቶቹ ሲያይዋቸው የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ የተደረጉ በመሆኑ ከሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ስልጣንን አላግባብ ከመጠቀም ድንጋጌ ጋር የሚያያዝ ሳይሆን የመንግስት ስራን በማያመች መንገድ ከመስራት ጋር የሚያያዙ ናቸው፤ ስለዚህ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ክሶች በተደራራቢ ወንጀል ተከላከሉ ሊባሉ አይገባም፤ በዚህ መሠረት ከ1ኛ እስክ 5ኛ ያሉት ክሶች እንደ አንድ ክስ ታይተው አመልካቾች እና 10ኛ 11ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች የወንጀሉ ድርጊት በስራ ላይ እንዲውል የተወሰነውን ቃለ ጉባኤ በመያዛቸው እና በማጽደቅ እንዲሁም 10ኛ) 11ኛ 20ኛ ተከሳሾች እና 13ኛ እና 14ኛ አመልካቾች በስራ ላይ በማዋል ውሎችን እና የተለያዩ ሰነዶችን በማዘጋጀት እና በማጽደቅ መሳተፋቸው የተረጋገጠባቸው በመሆኑ በአዋጁ 881/2007 አንቀጽ 13/3 ስር እንዲከላከሉ በማለት ብይን የሰጠ ሲሆን፤ 6ኛ ክስን በተመለከተ ደግሞ የቀረበው ማስረጃ 15ኛ አመልካች እና ከ22ኛ እስከ 24ኛ ያሉት ተከሳሾች የቴክኒክ ኮሚቴ በመሆን ሁለት ጊዜ የማጣራት ስራ ሰርተው ለከፍተኛው ኮሚቴ ያቀረቡ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው: ይህ ኮሚቴ የመሬት ክምችትን ለማስመለስ በወጣው መመሪያ ቁጥር 12/2007 አንቀጽ 8/1 መሠረት መቋቋም ካለበት መስሪያ ቤቶች በሙሉ አልተቋቋመም፣ ይህም ይህን ኮሚቴ ያቋቋመው የቤቱ ከፍተኛ ኮሚቴ የመንግስትን ስራ አመቺ ባልሆነ መንገድ መምራቱን የሚያሳይ ስለሆነ 1ኛ አመልካች እና 10ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ 00 እንዲከላከሉ፣ ከ15ኛ አመልካች እና ከ22ኛ እስከ 24ኛ ያሉት ተከሳሾችን ደግሞ አጣርተው ለበላይ ኮሚቴ ማቅረባቸው ብቻውን እራሱን ችሎ እንደ ወንጀል ድርጊት የሚወሰድ አይደለም በማለት ዓቃቤ ሕግ ያቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ መካላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ እንዲሰናበቱ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት 1ኛ አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን ክሱን ለመከላከል ያስችለናል ያሉትን የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበዋል አስምተዋል የሰነድ ማስረጃም አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከ1ኛ እስከ 13ኛ ያሉት አመልካቾች እና 15ኛ ተከሳሽ ከ1998 እስከ 2001 ዓ.ም በስራ ላይ የነበረውን እና ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረውን 45/55 የተባለ ሕገ ወጥ አሰራር በ21/09/2007 በሮቤ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በያዙት ቃለ ጉባኤ በሕገወጥ መንገድ ለሰዎች ተላልፎ የነበረን መሬት ማስረጃ እንዲሰጥበት ማስደረጋቸው በቀረበው የሰነድ ማስረጃ በግልጽ ተረጋግጧል፣ 10ኛ 11ኛ) 20 ተከሳሾች እና 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በተመሳሳይ ቀን በ21/09/2007 በሮቤ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ጽ/ቤት በተያያዘ ቃለ ጉባኤ ይህ በሕገወጥ መንገድ የተሰጠ የመሬት ይዞታ በከንቲባው ጽ/ቤት በተያዘ ቃለ ጉባኤ አቅጣጫ በተመሳሳይ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረጋቸው ተረጋግጧል : ተከሳሾች ቀርበው የተከራከሩት ድርጊታችን ሕጋዊ ነው በማለት አንጂ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት አልተከላከሉም፣ ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓላማ 45/55 የተባለው ሙሉ በሙሉ በሕገመንግስቱ እና በሕጉ መሠረት ወደ ኋላ ተመልሶ መፍትሄ የሚስጠው ከሆነ በተለይም በመንግስት ላይ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፈተና ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፤ በከተማ አስተዳደሩ ስሕተት ምክንያት ከገበሬው መሬት የገዙ ሰዎች እና አብዛኛው ገበሬ በዚህ መሬት ላይ ከ2005 ዓ.ም በፊት ግንባታ የገነባበት እና መሬቱን ያለማው በመሆኑ ይህንን ማሕበረሰብ የመንግስት መዋቅር በፈጠረው ስሕተት ምክንያት ማፈናቀል እና የሚገባቸውን የካሳ ክፍያ መክፈል ከፍተኛ ፈተና ነው፤ በመሆኑም የአመልካቶች ድርጊት ወንጀል ቢሆንም አመልካቾች ይህን ወንጀል የፈጸሙበት ዓላማ ከፍተኛ ሊያስብለው የሚችል አይደለም፤ ከአመልካቾች ስልጣን ጋር በተያያዘም ሁሉም አመልካቾች የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ቢሆኑም ከተማዋ የዞን ከተማ ያልሆነች እና ተጠሪነቷም ለዞን የነበረ ስለሆነ ስልጣናቸው በሙስና ወንጀሎች

አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/5 ድንጋጌ መሠረት ከፍተኛ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፤ በመሆኑም ወንጀሉን ከሚያክብዱት ምክንያቶች መካከል የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ነው በማለት አመልካቾችን እና 10ኛ፡ 11ኛ 15ኛ 20ኛ ተከሳሾችን የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ በመለወጥ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/2 መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6ኛን ክስን በሚመለከት የቴክኒክ ኮሚቴው በመመሪያ ቁጥር 12/2007 መሠረት መቋቋም ካለባቸው ተቋሚት ተወካይ ተሟልቶ ያልተቋቋም መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ የቴክኒክ ኮሚቴውን ያቋቋመው አካል የመንግስትን ስራ አመቺ ባልሆነ መንገድ በመምራት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡ የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት መመረጣቸውን በቀን 10/06/2007 ዓ.ም የጻፈው 2ኛ አመልካች አልተከሰሰም 1ኛ አመልካች በሕጉ አግባብ ባልተመረጠ በዚህ ኮሚቴ የቀረበውን ቃለጉባኤ በማጽደቅ በ30/07/07 በበላይ ኮሚቴው የተያዘን ቃለ ጉባኤ የመራው እና በሸኚ ደብዳቤ ለዞን የላከው 1ኛ አመልካች መሆኑ ተረጋግጧል 10ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች ይህንን ቃለ ጉባኤ መያዛቸው እና ይህ በሕገወጥ መንገድ የተመረጠው ኮሚቴ ያቀረበው ውጤት እንዲጸድቅ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፣ የ1ኛ አመልካች መከላከያ ማስረጃዎች ይህ ኮሚቴ በሕጉ አግባብ ባለመመረጡ የተፈጠረ ችግር ስለሌለ ድርጊቱ ሕገወጥ አይደለም በማለት የመሰከሩ ቢሆንም በዚህ ማጣራት ውስጥ የአጣሪ ኮሚቴው ስላልተከሰሰ እንጂ ፕሎትን የመዝለል ችግሮች የተፈጠሩ መሆናቸው በዓቃቤ ሕግ 7ኛ ክስ እና ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ መረዳት የሚቻል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ሐ ስር ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማስላት 1ኛ አመልካች በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 20,000፤ 2ኛ፤13ኛ፤ 6ኛ፤ 17ኛ፤ 9ኛ እና ከ11ኛ-15ኛ ያሉትአመልካቾች በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 15,000 ፤ 4ኛ 15ኛ 18ኛ 10ኛ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 16,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካቾች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ያጸና ሲሆን በቅጣት ረገድ ግን ቅጣቱን አሻሽሎ 1ኛ አመልካች በአምስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 7,000 የገንዘብ መቀጮ ከ2ኛ እስከ 15ኛ ያሉት አመልካቾች ደግሞ በአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የአመልካች ድርጊት ወንጀል ነው ተብሎ በሕግ አልተደነገገም፤ አከራካሪው መሬት በመንግስት ፈቃድ በከተማ ነዋሪዎች እጅ የገባው በ1998 ዓ.ም ሲሆን ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ ግንባታ ገንብተውበታል፤ አመልካቶች በ2007 ዓ.ም በሃላፊነት ስንመደብ ይዞታው ባዶ ቦታ አልነበረም፤ መንግስት ከከተማው ነዋሪዎች ጋር በገባው ውል መሠረት ነዋሪዎ ክፍያ ከፍለው ደረሰኝ ይዘው ነበር፤ አመልካቾች በያዝነው ቃለጉባኤ የወሰነው ከ1998 ዓ.ም እስከ 2001

ዓ.ም ድረስ ለክሱ መነሻ የሆነው መሬት ባለይዞታ የሆኑ ነዋሪዎች የሊዝ አዋጅ ከመታወጁ በፊት በመሬቱ ላይ ግንባታ ፈጽመው አልምተው እየተገለገሉበት ለሚገኙት ነዋሪዎች ብቻ መንግስት በውል በገባው ግዴታ መሠረት በሕጉ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጣቸው ነው: የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት ስራው በአስቸኳይ እንዲሰራ ያዘዘ በመሆኑ ድርጊቱ እንደ ወንጀል ሊቆጠር አይገባም፤አመልካቾች ባዶ መሬት ሰጥተዋል የሚል ክስ አልቀረብንም! አመልካቾች ከ2004 ዓ.ም በኋላ በተያዘ ይዞታ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ ያስተላለፍነው ውሳኔ ሳይኖር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ስሚ ችሎት የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት መመሪያ አመልካቾችን አይመለከትም ማለቱ አግባብ አይደለም፤ የስር ፍ/ቤት 3ኛ 4ኛ 5ኛ እና 16ኛ ተከሳሾች በሕዝባዊ ድርጅት ስር

የሚመደበው የኦህዴድ ተሿሚዎች በመሆናቸው አዋጁም በእነሱም ላይ ተፈጻሚነት አለው ማለቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች ክሱን እንድትከላከሉ በማለት የተሰጠው ብይንም ሆነ ክሱን ተከላክለን ሳለ አልተከላከላችሁም በማለት የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብ አይደለም፤ በ21/09/2007 በተፈረመ ቃለ ጉባኤ የፈጸምነው ድርጊት ወንጀል ተብሎ ባልተከሰሰንበት ይህን ቃለጉባኤ መነሻ በማድረግ ጥፋተኛ መባላችን አግባብ አይደለም፡ ወንጀሉን ለማቋቋም የሚያስችሉ ፍሬነገሮች አልተሟሉም፣ በቅጣትም ረገድም የዓቃቤሕግን ማክበጃ በመቀበል እና አመልካቾች ያቀረብነውን ማቅለያዎችን ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ 45/55 በሚል ይዞታቸው ለልማት ለተወሰደባቸው ሰዎች ማካካሻነት በ1998 ዓ.ም የተሰጠ እና ሕጋዊ እንዲሆንላቸው ገበሬዎቹ መንግስትን ጠይቀው በዚህ መነሻነት መስመር ለማስያዝ አመልካቾች በስራ በሃላፊነት በቃለ-ጉባኤ የወሰኑት ውሳኔ ሕገወጥ ነው በሚል ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ከተከሰሰብት የሕግ ድንጋጌ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፦ አመልካቾች መሬት ከአርሶ አደር ሲነጠቅ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሳ መክፈል እና በሕግ አግባብ የተፈቀደለትን መሬት መስጠት ሲገባቸው ይህን አለማድረጋቸው ከአርሶ አደሩ በሕገወጥ መንገድ 3ኛ ወገኖች ከገበሬው የገዙትን መሬት ለመንግስት ገቢ ሳያደርግ ሽያጭ ማካኼዳቸው) ከአርሶ አደሩ መሬት የገዙትን ሰዎች ነባር ይዞታ ወይም የድሮ ይዞታ በማለት ማስተናገዳቸው፤ የክልሉን የመሬት ሕግ መመሪያ በመጣስ በክሱ የተመለከተውን ድርጊት መፈጸማቸው የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 መከሰሳቸው እና ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ ነው፤ በ45/55 መሬት በእጃቸው የገባው አርሶ አደሮች በድሮ ይዞታ ስር መውስድ ሲገባቸው በሊዝ ስር እንዲገባ መደረጉ፣ ከአርሶአደሮች በፊት መሬት በሕገወጥ መንገድ የገዙና በከተማው አስተዳደር እውቅና ተስጥቶአቸው ማስረጃ የተሰጣቸው በሕገወጥ ይዞታ እና ውዝፍ ስር የሚካተቱ አይደሉም፤ ከጠቅላይ ሚኒስቴር መ/ቤት የተላለፈው መመሪያ የሚመለከተው ከ2004 ዓ.ም በፊት የነበረውን ሕገወጥ ይዞታና ውዝፍ እንጂ አመልካቾች የፈጸሙትን ድርጊት የማይመለከት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚለው ነው፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በአመልካቾች ላይ የቀረቡት ክሶች የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራት ደግሞ የሙስና ወንጀል ነው፡፡ የሙስና ወንጀል በልዩ ሕግ የተደነገገ ሲሆን ሕጉ ከወጣለት ዓላማ አንጻር በአዋጁ ወንጀል ናቸው ተብለው የተደነገጉት ድንጋጌዎች ወንጀል መሆናቸውን ለማሳየት የራሱ የሆነ መስፈርት በልዩ ሕጉ የተቀመጠለት ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን መስጠታቸው አመልካቾች መካላከያ ማስረጃ ካሰሙ በኋላም በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸውን ፍሬነገሮች አላስረዱም በማለት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፋቸው ከሙስና ወንጀሎች አዋጅ፤ ከመደበኛው የወንጀል ሕግ እና ከወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕጉ እንዲሁም የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ ከተጠበቁላቸው መሠረታዊ መብቶች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ፡-

1. የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?

2. የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው ከተባለ አመልካቾች ባቀረቡት መከላከያ የቀረበባቸውን ክስ ተከላክለዋል? ወይስ አልተከላከሉም? የሚሉት ናቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

በአመልካቾች ላይ የቀረቡት ክሶች የመንግስት ስራን በማያመች አኳሃን መምራትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ዓቃቤሕግ አመልካቾች በክሱ የተገለጸውን ድርጊት ስለመፈጸማቸው ለማስረዳት የሰው ምስክሮችን እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ከመስጠታችን በፊት ከመነሻውም ቢሆን ዓቃቤሕግ አመልካቾች በክሱ የተመለከተውን ድርጊት ፈጽመዋል ለማለት ማስረዳት የሚጠበቅበት ምንድነው? የሚለው መሠረታዊ ነጥብ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 232 አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙለት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ ተከሳሹ ወንጀል ለመስራት የነበረውን የሀሳብ ክፍል የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን እና ይህን ካላስረዳ በስተቀር ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል ብይን መስጠት የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል የሙስና ወንጀሎች በፈጣን ሁኔታ የመቀያየር ባሕርይ ስላላቸው አጠቃላይ ወንጀሎችን በሚደነግገው የወንጀል ሕግ ውስጥ እንዲካተቱ ከማድረግ ይልቅ ራሱን በቻለ አዋጅ እንዲደነገጉ ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ በሐገራችን የሙስና ወንጀሎች አዋጅ በልዩ ሕግ ወጥቶ የተለያየ ማሻሻያ ሲደረግበት ቆይቷል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግም የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ወጥቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡

የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር የሙስና ወንጀሎቹ የተፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈጸመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህም የሙስና ወንጀል በሙስና ወንጀል አድራጊው እና በወንጀሉ በሚጠቀመው ሰው መካከል ስምምነት የሚፈጸም በመሆኑ ዓቃቤሕግ ወንጀሉ መፈጸሙን በበቂ ሁኔታ የማስረዳት ሸክም ከባድ የሚያደርግበት በመሆኑ ክሱ የቀረበው ያለአግባብ ነው የሚለው ወገን የዓቃቤሕግ ክስ ትክክል አለመሆኑን ያስረዳ ዘንድ የማስረዳት ሸክሙ ይዛወርበታል፡፡ ይህም ዓቃቤሕግ ክስ ሲመሰርት በሌሎች ወንጀሎች ላይ ከተጣለበት በመደበኛነት ከሚታወቀው የማስረዳት ሸክም ወጣ ያለ ልዩ ሁኔታ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 ድንጋጌ እና የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን መሆኑን፣ ይልቁንም በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ

ወደ ተከሳሹ የሚዛወር መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ዓቃቤሕግ ማስረዳት የሚጠበቅበት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን ብቻ እንጂ ተከሳሹ ወንጀል ለመፈጸም የነበረውን የሃሳብ ክፍል አለመሆኑን እና የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል አላስረዳህም ተብሎ ተከሳሹን መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ነጻ ሊያወጣው የሚችል አይደለም፡፡

ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ዒቃቤሕግ በሕጉ አግባብ የተጣለበትን አመልካቾች በተከሰሱበት ድንጋጌ ላይ የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን አስረድቷል? ወይስ አሳስረዳም? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ለመስጠት በስር ፍ/ቤት የተሰሙትን የንቃቤሕግ ማስረጃዎች ይዘት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የስጡት የምስክርነት ቃል ይዘት -

ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ጉዳዩን ያጣሩ መሆኑን፣ የሮቤ ከተማ ማስተር ፕላን የሮቤ ቡሬቻ ቀበሌ እና ሆራ ቦቃን የሚያቅፍ መሆኑን፣ በከተማው ማስተር ፕላን ስር ያለ ቢሆንም በሲናና ወረዳ እና በሮቤ ከተማ መካከል ርክክብ ያልተፈጸመ በመሆኑ የከተማው አስተዳደር በመሬቱ ላይ ማዘዝ አይችልም በማለት የመለሱ መሆኑን፡ ባክሎግ ለማስመለስ የተቋቋሙ ኮሚቴዎችን እና ቃለጉባኤ ያዩ ቢሆንም ሰው ሲፈርም ያላዩ መሆኑን፣ በቴክኒክ ኮሚቴ ውስጥ የተቋቋሙት አዋጁ የማይፈቅድላቸው መሆናቸውን፤ በአንድ ኮሚቴ የተደረገው ማጣራት 530 ሰዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ኮሚቴ ደግሞ 56 ሰዎችን ጨምሮ ያቀረበ መሆኑን፤ 45/55 የሚለው አስራር ገበሬው ካለው መሬት 45% የሚወስድ ሲሆን 55% ለመንግስት የሚገባ መሆኑን፣ በ21/09/2007 ዓ.ም የተጻፈን ቃለጉባኤ መነሻ በማድረግ የከተማ አስተዳደር በገንዘብ ሊከፈል የሚችል ክፍያ ስለሌለው እንዲፈቀድልን በማለት የኦሮሚያ መሬት ልማት እና ማኔጅመንትን እና ዞኑን በደብዳቤ የጠየቀ መሆኑን፣ ለደብዳቤዎቹ የተስጠ ምላሽ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን፤ 45/55 የሚባል አስራር በሕግ የሌለ መሆኑን) ካሳ የሚከፈልበት መንገድ በሕጉ የተቀመጠ ቢሆንም በሕጉ መሠረት ያልተከፈለ መሆኑን፣ በገበራው መሬት ላይ በከተማው አስተዳደር እና በሲናና ወረዳ መካከል ርክክብ ያልተደረገ መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አስራር በሮቤ ከተማ እና በሲናና ወረዳ መካከል ሲስፋፋ የነበረው አ1998ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም መሆኑን፣ ከሲናና ወረዳ ወደ ሮቤ ከተማ በገባ መሬት የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት የተሰሩ መሆኑን ገበሬው በ45/55 ከተሰጠው መሬት ለግለሰብ አስተላልፎ አብዛኛው እጅ ክ2007 ዓ.ም በፊት ግንባታ የተገነባበት መሆኑን፤ መንግስት በወስደው 55% መሬት ላይ ማስረጃ አለመመርመራቸውን፣ በ2004 ዓ.ም እና በ2005 ዓ.ም በገበሬው እና በከተማው አስተዳደሩ መካከል ክርክር ተነስቶ የነበረ መሆኑን፡ 45/55 የተባለው አስራር የሕዝብን ጥያቄ እንመልሳለን በሚል የተሰራ ቢሆንም መንግስት የሕዝብን ጥያቄ የሚመልስበት መመሪያ ያለው መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አስራር ሲጀመር አመልካቾች በከተማው አስተዳደር በህላፊነት ላይ ያልነበሩ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ያዘት

በአብዛኛው 1ኛ ምስክር አሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በከንቲባው የሚመራው ኮሚቴ 530 ስዎች በባክሎን መሬት ማግኘት የሚገባቸው መሆኑን ያጣራ መሆኑን፤ 2ኛው ኮሚቴ 56 ስዎችን ጨምሮ ያጣራ መሆኑን፤ 32 ስዎች መሬት ተሰጥቷቸዋል የተባለውን በሚመለከት ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን ፤በቃለ ጉባኤ 45/55 የተባለው አሰራር በተመለከተ ገበሬው 45% ድርሻውን ለግለሰቦች ማስተላለፍ ይችላል በማለት የተገለጸ ቢሆንም በምን አግባብ እንደሚያስተላልፍ የማያውቁ መሆኑን ፤እንደሚችሉ ተገልጿል፣ አመልካቾች 49/55 በስራ ላይ እንዲውል እንዲፈቀድላቸው ላቀረቡት ጥያቄ የተሰጠ መልስ ያላዩ መሆኑን 79 ለሆኑ ገበሬዎች በ45/55 መሬታቸው የተሰጣቸው መሂኑን በመግለጽ መመስከራቸውንየሚያሳይ ነው፡፡

የ3ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት፡ ከ76 ገበሬዎች ጋር በተያያዘ የቀረበው ማስረጃ በከተማው ድንበር ያሉ ገበሬዎች ቤተሰቦች መሬታቸው አገልግሎት እና ደረጃው

ምን እንደሆነ የሚገልጽ ነገር የሌለው መሆኑን ገልጿል። ቀደም ሲል 155/2005 መሰረት ከ200 ካሬ ሜትር የሚሆን መሬት ተሰጥቷል። ከዚህ በላይ 500 ካ.ሜ ለባለይዞታው ተሰጥቶ ከዚህ የቀረው የመንግስት መሬት ስለሚሆን መንግስት ከዚህ መሬት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ አስልተዋል። የሮቤ ከተማ 3ኛ ደረጃ ላይ የነበረች ሲሆን ከሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ ወደ 25 ደረጃ ተሸጋግራለች። በዞኑ ኮሚቴ በተያዘው ቃለ ጉባኤ ላይ ተመርኩዘው የሰሩ ሲሆን የሮቤ ከተማ ስታንዳርድ በ 200 ካሬ ሜትር ወስደው በደንብ ቁጥር 155/2005 መሰረት 500 ካሬ ሜትር ለገበሬው ይጸድቃል:: ከ500 ካሬ ሜትር በላይ የሆነው ይወሰድበታል:: 105 ካሬ ሜትር ተመዝግቦ ይቀመጣል። በዚህ መሰረት መንግስት ማግኘት ይገባው የነበረውን ገንዘብ አስልተው ያስቀመጡ መሆነን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው።

የ4ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት የሮቤ ከተማ መሬት ማኔጅመንት የመዝገብ ቤት አገልግሎት አቀናባሪ መሆናቸውን: በኦሮሚያ ፀረ ሙስና ኮሚሽን 311 ሰዎችን በሚመለከት እንዲያጣሩ ተጠይቀው 47 ሰዎችን ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን፤ 47 ሰዎች ሥራ በነበረበት ጊዜ ደረሰኝ ቆርጠው መዝገብ ያስፈቱቱ መሆኑን። ውል ሳይሞሉ የቀሩ ብዙ ሰዎች የነበሩመሆኑን፣ ውል ተሞልቶላቸው ባለስልጣኑ ሳይፈርምበት የቀረባቸው ሰዎችም የነበሩ መሆኑን። 47ቱ ሰዎች መሬት አላቸው ተብለው ቢሆንም በመዝገብ ውስጥ የሌሉ መሆኑን። የተለያዩ ሰዎች ለመስተናገድ ይጠይቁ የነበረ እና ስራው ይቁም ስለተባለ ልናስተናግዳቸው አንችልም እያሉ የመልስዋቸው የነበረ መሆኑን ፤ፍቃድ ያላቸው ሰዎች ብቻ ደረሰኝ የቆረጡ መሆኑን ፤ 47ቱ ሰዎች ደረሰኝ ያላቸው ከመሆን ውጪ ለይተው የማያውቋቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይነው።

ዓቃቤ ሕግ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት፡- ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት በርካታ የስነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ዋነኞቹ አመልካቾች 45/06 የተባለ አሰራር እንዲፈቀድላቸው የያዟቸው ቃለጉባኤዎች እና ቃለ ጉባኤዎችን መሠረት በማድረግ ለበላይ አካል የጻፏቸው ደብዳቤዎች, በ45/55 ከገበሬዎች ተወስዷል የተባለው መሬት የገበሬው ድረሻ ነው የተባለው 45% በውሉ መሠረት ያልተላለፈ መሆኑን፣ በሰነድ ማስረጃ መሠረት የ76ቱ በራዎች መሬት ይዞታ 919100 እንደሆነ የባክሎግ አጣሪ ኮሚቴው ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤት በሙሉ ያልተቋቋመ መሆኑን ፤ በቴክኒክ ኮሚቴው ሁለት ጊዜ የተጣራው ልዩነት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሪፖርት፤ ከከተማው መስፋፋት ጋር ተያይዞ በሮቤ ከተማ ስር የታቀፉት የገጠር ቀበሌዎች ላይ በሲናና ወረዳ እና በሮቤ ከተማ አስተዳደር መካከል ርክክብ አለመከናወኑን የሚያሳይ ደብዳቤ ለመሬት ክምችት ከተመዘገቡት 642 ሰዎች መሃከል 530 ሰዎች መሬት እንዲያገኙ መደረጉን፣ 98 ሰዎች ማግኘት የሌለባቸው መሆኑን መረጋገጡን እና በዚህ ረገድ እየተሰራ ያለው ስራ ያልተጠናቀቀ መሆኑን የሚያሳይ ቃለጉባኤ፤ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የተደረጉ ውሎች ናቸው።

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው የዓቃቤ ሕግ የሰው ምስክሮች ለፍ/ቤቱ አሰጡት የምስክርነት ቃል እና ዓቃቤሕግ ካቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ አመልካቾች በተክስሰብት የሙስና ሕግ ድንጋጌ ላይ የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን ያረጋገጠ መሆኑን ነው። ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሊያቀርብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተክሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ የሚዛወር በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ክሶች እንደ አንድ ክስ ታይተው አመልካቾች የወንጀሉ ድርጊት

በስራ ላይ እንዲውል የተወሰነውን ቃለ ጉባኤ በመያዛቸው እና በማጽደቃቸው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 ስር እንዲከላከሉ፣ 1ኛ አመልካች ደግሞ ስድስተኛውንም ክስ በተጨማሪ እንዲከላከል በማለት ብይን መስጠቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም።

## ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ በአግባቡ ነው ከተባለ አመልካቾች ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ የቀረበባቸውን ክስ ተከላክለዋል? ወይስ አልተከላከሉም? የሚለው ሁለተኛው መሠረታዊ ጭብጥ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ኣቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ አንጻር በአግባቡ ታይቶ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነው: ስለሆነም አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ይዘት በቅድሚያ መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

1ኛ አመልካች በጠ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ለፍ/ቤቱ የሰጠው ቃል ይዘት፡-

አመልካቾች የመጡት በ2007 ዓ.ም መሆኑን፣ የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ይዞታ ካሳ ለመክፈል የገንዘብ ችግር ስለነበረበት 45/55 የተባለው አሰራር ከ1998 እስከ 2000 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተጀመረ መሆኑን): 55% የገበሬውን መሬት መንግስት ወስዶ ያለማው መሆኑን፣ 45% ደግሞ ለ3ኛ ወገን የቀላለፈ መሆኑን፣ ወደኂላ ያለው 10 ዓመት ግንባታ ተገንብቶበት የለማ በመሆኑ፣ የሰብልን ካሳ ለመክፈል መሬቱ 10 ዓመት አዳሪ የነበረ በመሆኑ : የንብረት ካሳ ለመክፈል ንብረቱ በከተማ አስተዳደር ተወስዶ የራሱ መሆን የነበረበት በመሆኑን ምክንያት በአዋጅ 455/97 መሠረት ተፈጻሚ ያልተደረገ መሆኑን፣ የከተማ አስተዳደሩ እስክ ክልል መንግስት ድረስ ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፡ ክክልሉ እና ከከተማው አስተዳደር ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ሲታይ የነበረ መሆኑን ፣ መንግስት ባክሎግ የነበረበት በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 721/2007 በስራ ላይ ለማዋል የጠቅላይ ሚንስትሩን ቢሮ በመጠየቅ የጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮም ጉዳዩ ለመጨረሻ ጊዜ መልስ እንዲያገኝ በጻፈው ደብዳቤ ፍቃድ የተሰጠ መሆኑን; በቀን 18/05/2007 ከጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮ ለክልሉ ፕሬዝደንት ጽ/ቤት በቀጥታ በተጻፈ ደብዳቤ ላይ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦችን የያዘ ሲሆን እነኂህም 1ኛ ደረሰኝ ያላቸው ባክሎግ ደረሰኝ ቆርጠው መሬት ሳይገኙ የቀሩ ተስተናግደው ምላሽ እንዲሰጣቸው : 2ኛ መሬት ይዘው ቤት የሰሩት ሰዎች ሙሉ ሰነድ ሳይኖራቸው የቀሩት ለመጨረሻ ጊዜ እንዲስተናገዱ የሚል መሆኑን፣ በዚህ ደብዳቤ ላይ በመመሰረት የፕሬዝደንት ጽ/ቤት ለክልሉ ኢንደስትሪ እና ከተማ ልማት ቢሮ እና ለክልሉ መሬት ኤጀንሲ በቀን 05/06/2007 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ለማስተናገድ እንዲችሉ በማለት የጻፈ መሆኑን፤ ይህን ለማስፈጸምም ሁለቱ ቢሮዎቾ እቅድ በማውጣት በየደረጃው ላሉ ኦረንቴሽን በመስጠት ወደ ስራ እንዲገባ አቅጣጫ የተቀመጠ መሆኑን፤ የክልሉን ሕግ እና መመሪያ መሠረት በማድረግ በባክሎግ በሕገወጥ ግንባታ እና ነባር ይዞታ ላይ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ መሆኑን፣ ለገበሬው በካሳ የተሰጠው 45% ከከተማ መስተዳድሩ ጋር የፈጸሙት ውል በእጃቸው የነበረ በመሆኑ በመግለጽ ቃሉን መስጠቱን የሚያሳይ ነው።

1ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት በ1998 ዓ.ም በሮቤ ከተማ አባገዳ አዳራሽ ሰብስበው ከተማዋ ዞን ስለሆነች ልትለቁ ይገባል ያሏቸው መሆኑን፣ መሬቱን አንለቅም ሲሉ ልማትን ማደናቀፍ አትችሉም መንግስት እንዲሁም ሊወስድባችሁ ስለሚችል ካሳችሁን 45/55 እናደርግላችኂለን ያሏቸው መሆኑን፣ ካርኒ ሳይቆረጥላቸው በመቅረቱ አ2005 እስክ 2006 አቤቱታ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፡ መፍትሄ እንዲሰጣቸው በየጊዜው ለነበሩ የክልሉ ፕሬዝደንቶች በተለያየ ጊዜ አቤቱታ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፣ ሀላፊዎቹም እናንተ ጥፋት አልፈጸማችሁም ጥፋት የፈጸሙት አራሳችን እዛ ያስቀመጥናቸው ሰራተኞቾ ናቸው ከባከሎማ ጋር እንድ ላይ ተደምሮ እንዲስተካክልላችሁ እናደርጋለን ያሏቸው መሆኑን፤ በ1998 ዓ.ም ተሸንሽኖ የነበረን መሬት እና ቤት የተሰራበትን ዞረው እያሳዩ አጣርተው ለይተው ካርኒ ይቆረጥላቸው የሚል ድምጽ የተሰማ መሆኑን

ከዚህ በኂላ በአዳራሽ ሰብስበው ሊዝ የቀረጡባቸው መሆኑን ፤አመልካቾችምበ1998 ዓ.ም የተመሩትን ሰዎች ወደ 14 ተመልሰው በ2007 ዓ.ም ሊዝ ያስከፈሏቸው መሆነን ፤ ወደ ሊዝ በመለሷቸው ጊዜ 45/55 የተባለው ይዞታ ሁሉም ቤት የነበረበት መሆኑን፡ ለመንግስት የሰጡት መሬት የተለያየ ተቋማት ተስርቶበት ሙሉ ለሙሉ ለመንግስት ጥቅም የዋለ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው:

2ኛ መከላከያ ምስክር የስጡት የምስክርነት ቃል ይዘት 45.55 የተባለውን አሰራር በተመለከተ ከ1ኛ ምስክር ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በተጨማሪም አብዛኛው ስው በወቅቱ የግብርና ስራ አቁሞ ስለነበረ ቀለብ ያልነበረው መሆኑን፣ ሕዝቡ ለሰባት ስምንት ዓመታት እርሻ አቁሞ የራሱን መሬት እየገዛ የነበረ መሆኑን፤ የራሳችንን መሬት ሰጥተናችሁ መልሰን እንገዛለን ሲል የነበረ መሆኑን፣ አመልካቾች ወደ ሊዝ ስርዓት ይገባል 45/55 በሚለው ስርዓት አይፈጸምም ብለዋቸው የነበረ መሆኑን፣ በአመልካቶች የተሸነሸነ መሬት የሌለ መሆኑን፤ አመልካቾች በሊዝ ክፍያ ያስከፈለበት ዓላማ የሕዝብን ችግር ለመፍታት መሆኑን፣ መሬት ወደ ከተማ ሲመለስ የመሬት ንጥቂያ በዝቶ የነበረ እና ግለሰቦች የተለያየ ማስረጃዎች አስርተው በሰዎች ላይ ክርክር እያቀረቡ የነበረ መሆኑን፣ ዋስትናችን ምንድነው? በምን እንከላከላለን? በከተማ ድንበር ውስጥ አስገብታችሁ እንዳናገዛ ከልክላችሁናል ውል ሞልተናል ይህንን ውል ማፍረስ አንችልም የሚሉ ነጥቦችን አንስተው በእጃቸው ላይ ያለው ይዞታ እንዲጸድቅላቸው የጠየቁ መሆኑን! 45/55 ን እንደዳታ ተጠቅመው ውል የፈጸሙላቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

3ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት በአጭሩ፦

45/55 የተባለውን አሰራር በተመለከተ ከ1ኛ እና 2ኛ ምስክር ከሰጡት ቃል ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በተጨማሪም ከላይ ካሉት ጋር ተመሳሳይ በሆነ 45/55 ውል በፈረሙበት እለት ለሌላ ሰው ያስተላለፉ መሆኑን፤ በይዞታው ላይ ቤት የተገነባበት መሆነን ፤ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ካርኒ መቁረጥ ቆሟል በማለት የከለከሏቸው መሆኑን፤ መሬቱ በተወሰደባቸው ጊዜ አመልካቶች ያልነበሩ መሆኑን፣ አመልካቾች ከመምጣታቸው በፊት የፈጸሙት ውል እያለ አንፈጽምም በማለት በሊዝ ያስከፈሏቸው መሆኑን፤ በበፊቱ ውል እንዲፈጸምላቸው ሲጠየቁ መመሪያ ይከለክለናል ያሏቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

4ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፡-

በወቅቱ የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ካሳ ለመክፈል ገቢ ያልነበረው መሆኑን፤ ገበሬው የራሱን ግንባታ ሲገነባበት ሌላውን ደግሞ አሳልፎ ለሰው ሲሰጥ የነበረ መሆኑን፣ መሬት የመስጠት ጉዳይ ከቀን 16/09/2001 ዓ.ም ጀምሮ በወቅቱ በነበሩት የክልሉ ፕሬዝደንት በነበሩት የቆመ መሆኑን፤ ምስክሩ መሬት መስጠት ከቆመ ከአንድ ወር በኂላ ከንቲባ የሆኑ መሆኑን፤ ገበሬው በተለያየ ጊዜ እየቀረበ በመሬታቸው ላይ ማሕተም ተመቶበት ከንቲባ እና የማዘጋጃ ቤቱ ባለሙያ የፈረመበትን ውል ይዞ በመምጣት ካርኒ ቆርጣችሁ ባለይዞታችንን አረጋግጡልን በማለት ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ከገበሬው ላይ መሬትን በስጦታም ሆነ በሽያጭ የወሰዱትም ተመሳሳይ ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፣ ገበሬው መልስ ሊያገኝ ስላልቻለ እስከ ክልል አስተዳደር ድረስ በመሄድ ሲጠይቅ የነበረ መሆኑን፤ በ2007 ዓ.ም ምርጫ ሲቃረብ ጥያቄውን ለመመለስ መንግስት ባስተላለፈው መመሪያ በመንተራስ አመልካቾች የገበሬዎቹን ጥያቄ የመለሱ መሆኑን፤ አመልካቾች ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም በተሰራው ስራ ውስጥ ድርሻ የሌላቸው መሆኑን፣ የነባር ይዞታው ባለቤት አ2001 ዓ.ም ጀምሮ የድሮ ይዞታ የመንግስት ክፍያን ከፍሎ ባለይዞታነቱ እንዲረጋገጥ የተደረገ መሆኑን፣ ከገበሬው ላይ ተላልፎለት መሬት ያገኘ ሰው ደግሞ የሊዝ መነሻ ዋጋ ክፍያን ከፍሎ ባለይዞታነቱ እንዲረጋገጥ የተደረገ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

5ኛ ምስክር የስጡት የምስክርነት ቃል ይዘት:-

ምስክሩ የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ የነበሩ መሆኑን፤ ተንጠልጥለው የቆዩ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚፈጸሙብትን ሁኔታ ስልጠና የወሰዱ መሆኑን፤ በጠቅላይ ሚንስቴር እና በክልል ደረጃ የተጻፉ ደብዳቤዎች ስለነበሩ 45/55 በዚህ ሊስተናገድ የሚችል መሆኑን! በ1997 እና በ1998 አካባቢ, የከተማዋ ጎበ ክ 4,000,000 የማይበልጥ የነበረ በመሆኑ ለ10 ዓመት ወደ ኋላ ተመልሰው ካሳ መክፈል የማይቻል መሆኑ፡ መንግስት መሬት መስጠትን አግዶ ገበሬዎች የራሳቸውን ድርሻ መሬት ሲወስዱ የነበረ መሆኑን፤ መንግስትም የራሱን ድርሻ ወስዶ ሲያለማበት የቆየ መሆኑን፣ እስከ 500 ካ.ሜ ካርኒ ሲቆረጥበት የቆየ መሆኑን | በወቅቱ የእገሌ ቤተሰብ ነኝ በማለት ደረሰኝ ይቆረጥልኝ በማለት አቤቱታ ሲያቀርቡ ካርኒ በመቁረጥ ይስተናገዱ የነበረ መሆኑን፤ ከሚፈቀደው ስታንዳርድ በላይ የጸደቀ የሌለ መሆኑን፣ ገበሬው ወደ ከተማ አስተዳደሩ እንዲሁም ወደ ክልሉ አስተዳደር በመሄድ ሃላፊዎች ያነጋገረ መሆኑን፤ የሕዝቡ ቅሬታ በመብዛቱ በአባገዳ አዳራሽ ሰብስበው አናግረዋቸው የደንብ ስለወጣ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ ይሰጣችኋል ያሏቸው መሆኑን፤ ለአመራሩም ኦረንቴሽን የተሰጠ መሆኑን፤ አመልካቾች ሳይጠናቀቅ ተንጠልጥሎ የቆየን ነገር ሕጋዊ መስመር አስይዘው ከማጠናቀቅ ውጪ 45/55ን በአዲስ መልክ የስሩት ነገር የሌስ መሆኑን፤ 45/55 የተባለሙ አሰራር በዞንም በክልልም እንደጥሩ ምሳሌ ተወስዶ የነበረ መሆኑን፣ ገበሬው በራሱ ድርሻ ላይ ማስረጃ ያለው መሆኑን፤ ገበሬው ወደ ኋላ ተመልሶ በሊዝ እንዲከፍል ስለተደረገ የተጎዳው ገበሬው እንጂ በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት የሌለ መሆኑን፣ ከከተማ አስተዳደር ጋር ውል የሌላቸው ለዎቸ አጋዊ ያልተደረጉ መሆኑን፣ ግንባታ የፈጸሙ እና ከገበሬው ውጪ ያሉ ሰምቶ ደግሞ በሊዝ ስርዓት ባለቤትነታቸው የተረጋገጠ መሆኑን፡፡ ከገበሬው ጋር የተለያዩ ውሎች ሲደረጉ የነበረ መሆኑን፡ መንግስት 55% መብት እንዳለው ሁሉ ገበሬውም በ45% ላይ ሊያዝበት መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

6ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት-

.45/55 የተባለውን አስራር በተመለከተ ሌሎች ምስክሮች አሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር በተመሳሳይ የመሰከሩ ሲሆን በተጨማሪም መንግስት በ2007 ዓ.ም በሊዝ መሸጋገሪያ ጊዜ ተይዘው የነበሩ መሬቶች በሊዝ መመሪያ ተጠቃለው እንዲስተናገዱ፣ በድሮ ይዞታ እና በሕገወጥ ግንባታ መካከል ተንጠልጥሎ የነበረ ይዞታ መፍትሔ እንዲያገኝ አቅጣጫ ያስቀመጠ መሆኑን፣ አስቀድሞ መሬቱ የገበሬው የራሱ የእርሻ መሬት ስለሆነ ገበሬው መሬቱን መኖሪያ ቤት ለማድረግ፣ በስጦታ ለማስተላለፍ መብት አለው፡፡ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም 45/55 ን በማስቀጠል ለገበሬው ካሳ ሳይከፍሉ የወሰዱት መሬት የሌለ መሆኑን፤ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም የሰሩት ነገር መሬቱ አስቀድሞ ስለተሰጠ ማስረጃ ብቻ መስጠት እንጂ መሬት ያልሰጡ መሆኑን፣ መጀመሪያ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በተደረገ ውል በተስጠ መሬት ላይ መሟላት ያለበት መስፈርት በሙሉ መሟላቱን አረጋግጠው ሳይት ፕላን እና ማስረጃ የሰጡ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች በተጨማሪም በምስክሮቻቸው የተገለጸውን የምስክርነት ቃል የሚደግፍ የሰነድ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

እንግዲህ ከላይ በተገለጸው መሠረት አመልካቾች ደርጊቱን ለመፈጸም የቻሉበትን ምክንያት ካስረዱ አመልካቾች ባቀረቡት መከላከያ ማስረጃ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መርታችኋል በማለት እንዲከላከሉ በተሰጠው ብይን መሠረት ተከላክለዋል ወይስ አልተከላከሉም ለማለት አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው እንዲያስተባብሉት የሚጠበቀው ምንድነው? የሚለው ለጉዳዩ አወሳሰን መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡ በተያዘው መሠረታዊ ጭብጥ ላይ ምላሽ ለመስጠት ከላይ በመጀመሪያው ጭብጥ ላይ የገለጽነውን የማስረዳት ሸክም ወደ አመልካቾች የተላለፈበትን ምክንያት በድጋሚ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

አመልካቾች እንዲከላከሉ በማለት ብይን የተስጠባቸው የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 እና 13/1/ሐ ድንጋጌ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ስልጣንን ወይም ሀላፊነትን ተጠቅሞ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራት ወንጀል ነው፡፡ ዓቃቤሕግ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2

መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ ይዞራል፡፡ ይህም ማለት አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ነው በማለት አስቀድሞ ተይዞባቸው የነበረውን የሕግ ግምት ስራውን የመሩት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት አለመሆኑን እና ስራውን በሚያመች አኳኋን የመሩ መሆኑን ሊያሳይ የሚችል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በሙስና ወንጀሎች ግዙፋዊ ፍሬነገሩ መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬ ነገር መፈጸሙን የሕግ ግምት የሚያዝበት መሆኑ፤ ተከሳሹም ይህን አስቀድሞ የተያዘበትን የሕግ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ሊያስተባብለው የሚችል በመሆኑ ፍ/ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ተገቢውን ሚዛን የጠበቀ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም በአንድ በኩል የሙስና ወንጀሎች አዋጅ የሕዝብ እና የመንግስትን ጥቅም ለማስጠበቅ የወጣ በመሆኑ ወንጀሉን ፈጽመዋል ተብለው ክስ የቀረበባቸው ሰዎች ወንጀሉን የፈጸመ መሆኑ በተረጋገጠባቸው ጊዜ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለባቸው በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተከሰሱ ሰዎች የመሰማት መብታቸው ተጠብቆ በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ መሆናቸው በማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደተመለከትነው አንድ ሰው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ሲል ስራን በማያመች አኳኋን መርቷል ለማለት ስራውን በሚያመቸ አኳሃን ለመምራት የሚያስችል ሕግ እና የተዘረጋ ስርዓት መኖሩ እና ተከሳሹ ይህንኑ ሕግ እና ስርዓት ተላልፎ ስራውን በማያመች አኳኋን የመራ መሆኑ ሊረጋገጥበት ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ 45/55 የተባለው አሰራር ከ1998 እስከ 2001 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተጀመረ መሆኑን፣ አመልካቾች ወደ ሀላፊነት የመጡት በ2007 ዓ.ም መሆኑ ± የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ይዞታ ካሳ ለመክፈል የገንዘብ ችግር ስለነበረበት 45/55 የተባለው አሰራር የተጀመረ መሆኑን፣ በዚሁ መሠረት 45% ገበሬው በካሳ መልክ እንዲወስደው 55% የገበሬውን መሬት ደግሞ መንግስት እንዲወስድ የተደረገ መሆኑን፣ መንግስት በወሰደው 55% ድርሻው ላይ የተለያዩ ተቋማትን በመገንባት ያላማው መሆኑን፣ ገበሬው ደግሞ ድርሻው በሆነው 45% ከፊሉን ራሱ የወሰደ ከፊሉን ደግሞ ለ3ኛ ወገን ያስተላለፈ መሆኑን፤ ገበሬው ከከተማው አስተዳደር ጋር ውል ፈጽሞ የነበረ መሆኑን፤ ወደኋላ ያለው 10 ዓመት በመሬቱ ላይ ግንባታ ተገንብቶበት የለማ በመሆኑ፡ የሰብልን ካሳ ለመክፈል መሬቱ 10 ዓመት እጻሪ የነበረ በመሆኑ ምክንያት በአዋጅ 455/97 መሠረት ተፈጻሚ ያልተደረገ መሆኑን፤ የከተማ አስተዳደሩ እስከ ክልል መንግስት ድረስ ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ከክልሉ እና ከከተማው አስተዳደር ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ሲታይ የነበረ መሆኑን 1 መንግስት ምላሽ ያልሰጠበት ባክሎግ የነበረበት መሆኑ፤ ገበሬው ተደራጅቶ በተለያየ ጊዜ ለነበሩ የክልሉ ፕሬዝደንቶች ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፣ ሀላፊዎቹም እናንተ ጥፋት አልፈጸማችሁም ጥፋት የፈጸሙት አራሳችን እዛ ያስቀመጥናቸው ሰራተኞች ናቸው ከባክ ሎንግ ጋር አንድ ላይ ተደምሮ እንዲስተካከልላችሁ እናደርጋለን ያሏቸው መሆኑን፤ ገበሬው አስቀድሞ በነበረው አስራር መሠረት ካርኒ እንዲቀረጥለት ሲጠይት አመልካቾች ይህንኑ ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልነበሩ መሆኑን፣ የገበሬጡ ጥያቄ ገፍቶ እስኪ ጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት ድረስ የደረሰ መሆኑን፣ የጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮም ጉዳዩ ለመጨረሻ ጊዜ መልስ እንዲያገኝ በጻፈው ደብዳቤ ደረሰኝ ያላቸው ባክሎን ደረሰኝ ቆርጠው መሬት ሳያገኙ የቀሩ ተስተናግደው ምላሽ እንዲሰጣቸው፤ መሬት ይዘው ቤት የሰሩት ስዎች ሙሉ ሰነድ ሳይኖራቸው የቀሩት ለመጨረሻ ጊዜ እንዲስተናገዱ የሚል መሆኑን፣ ይህንኑ መሠረት በማድረግ የክልሉ

ፕሬዝደንት በጻፈው ደብዳቤ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ለማስተናገድ እንዲችሉ በማለት የጻፈ መሆኑን፤ አመልካቾች ሳይጠናቀቅ ተንጠልጥሎ የቆየን ነገር ሕጋዊ መስመር አስይዘው ከማጠናቀቅ ውጪ, 45/55 የተባለውን አሰራር በአዲስ መልክ ያልሰሩ መሆኑን፤ ገበሬው በራሱ ድርሻ ላይ ማስረጃ ያለው መሆኑን፣ ከከተማ አስተዳደር ጋር ውል የሌላቸው ሰዎቸ ሕጋዊ ያልተደረጉ መሆኑን፣ ግንባታ የፈጸሙ እና ከገበሬው ውጪ ያሉ ሰዎች ደግሞ በሊዝ ስርዓት ባለቤትነታቸው የተረጋገጠ መሆኑን፤ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም የሰሩት ስራ መሬቱ አስቀድሞ ስለተሰጠ ማስረጃ ብቻ መስጠት እንጂ መሬት ያልሰጡ መሆኑን መጀመሪያ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በተደረገ ውል በተሰጠ መሬት ላይ መሟላት ያለበት መስፈርት በሙሉ መሟላቱን ተረጋግጦ ማስረጃ የተሰጠ መሆኑን አመልካቾች ካቀረቡት መከላከያ ማስረጃ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ገበሬው ተገቢ የሆነ ካሳ ሳይከፈለው ከእርሻ መሬቱ ያለመፈናቀል መብት እንዳለው በሕገ መንግስቱም ሆነ በክልሉ የመሬት ሕግ የተደነገገ ቢሆንም ገበሬው ከይዞታው ላይ እንዲነሳ በተደረገ ጊዜ ከተማዋ ካሳ ለመክፈል የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያልነበራት መሆነ፤ 45/55 የተባለው አሰራር በሕግ ያልተደነገገ ቢሆንም በወቅቱ የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ሲባል በወቅቱ በነበሩ ሀላፊዎች ሲተገበር የነበረ መሆኑ፣ ይህንኑ ተከትሎ መሬቱ ከፊሉ በገበሬው እጅ ከፊሉ ደግሞ ለተለያዩ ግለሰቦች የተላለፈ መሆኑን፣ በከተማው አስተዳደር ስሕተት ምክንያት ከገበራው መሬት የገዙ ሰዎች እና አብዛኛው ገበሬ በዚህ መሬት ላይ ከ2005 ዓ.ም በፊት ግንባታ የገነባበት እና መሬቱን ያለማው በመሆኑ ሕብረተሰቡን ለማፈናቀል እና የሚገባውን የካሳ ክፍያ ለመክፈል ከፍተኛ ማሕበራዊ ቀውስ የሚፈጥር እና መንግስታዊ ኢኮኖሚውም ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያመጣ መሆኑን ክጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤትም ሆነ ከክልሉ ፕሬዝደንት ለጉዳዩ መፍትሔ እንዲሰጥ በደብዳቤ የተገለጸ በመሆኑ) አመልካቾች ውሳኔ ሳይሰጥባቸው ተከማችተው ያለ ጉዳዮችን ለመፍታት የነደፉትና የተግበራቸው አሰራሮች መሆናቸውን በግራ ቀኙ የቀረበ-ት ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ደግሞ ሆነ ብለጡ ወይም በቸልተኝነት አንዱን አካል ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ከመነጨ ሀሳብ የተፈጸመ ተግባር ስለመሆኑ አስቀድሞ ተወስዶ የነበረውን የህግ ግምት ጥያቄ ላይ የሚጥል ነው፡፡ አመልካቾች በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ መሠረት አድርገው የሠጧቸው ውሳኔያቸው ምንም ይሁን ምን የነበረውን ክፍተት በተግቢው አግባብ ለመድፈን የተፈጸመ መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ ስራውን የሰሩት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ነው የሚያስብል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካቾች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስነናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ስጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካቾችን በሚመለከት በመ.ቁ 22898 በቀን 10/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝት ውሳኔ እና በቀን 11/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 260202 በቀን 04/04/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 278007 በቀን21/09/2010 ዓ.ም የስጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2//2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካቾች ከቀረበባቸው ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

የሚመለከተው ማረሚያ ቤት የስር ፍ/ቤቶቸ በአመልካቾች ላይ አስተላልፈውት የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች በነጻ እንዲሰናበቱ የተወሰነ መሆኑን አውቆ አመልካቾችን በዛሬው እለት ከእስር እንዲፈቱ ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር የዚህን ውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት በአስቸኳይ እንዲልክ ታዟል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሃሳብ

ስማችን በአራተኛ እና አምስተኛ መስመር ላይ የተጠቀሰው ዳኞች አብላጫው ድምጽ አመልካቾችንከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ለማለት በጠቀሰው ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ የልዩነት ሀሳባችንን በሚከተለው መልኩ አስፍረናል፡፡ ከቀረበው ክስ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾች መጀመሪያ የተከሰሱት በተሰጣቸው የመንግስት የስራ ኃላፊነት ላይ ሆነው የቀረበላቸውን ጥያቄ በተመለከተ በክሱ ዝርዝር የተጠቀሱን የፌዴራል እና የክልል አዋጅ ደንብ እና መመሪያን መሰረት አድርገው ምላሽ መስጠት ሲገባቸው ይህንን ወደ ጎን በማለት የማይገባቸውን ጥቅም ለራሳቸው ለማግኘት ወይም በሌላ ሰው ለማስገኘት በማስብ የተሰጣቸውን ስልጣን ያለአግባብ በመጠቀም በህግ ያልተመለከተን እና 45% 55% የሚባል አሰራርን በመዘርጋት በህዝብ እና መንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቾች ቃለ ጉባኤ ይዘው ስራ ላይ ያዋሉት 45% 55% የተባለው አስራር የህግ መስረት የሌለው መሆኑን ማረጋገጡን ሆኖም ድርጊታቸው ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ላይሆን የህግ መሰረት የሌለውን አሰራር በመዘርጋት የመንግስት ስራ በማያመች, መንገድ መምራት ወንጀልን ነው በሚል ክስ የቀረበበትን አንቀጽ ቀይሮ እንዲከላከሉ አዟል፡፡ አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃቸው 45% 55% የተባለው አስራር እነርሱ ወደ ኃላፊነት ከመምጣታቸው በፊት የነበረ መሆኑን ከመግለጽ ባለፈ አሰራሩ የህግ ማዕቀፍ ያለው ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ከዚህ አኳያ ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡ ቀድሞ የነበረ ብልሹ አሰራር በቃለ ጉባኤ እውቅና ሰጥቶ ማስቀጠል ደግሞ የወንጀል ክስ መከላከያ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ አብላጫው ድምፅ አመልካቾችን ጥፋተኛ ከተባለበት ወንጀል በነፃ ለመልቀቅ በምክንያትነት የጠቀሰው አመልካቾች የመንግስትን ስራ በማያመች መንገድ መርተዋል በሚል ጥፋተኛ ለማለት ቀድሞ የሚያመች አስራር ሊኖር ይገባል›› የሚል ነው፡፡ ሆኖም የቀረበው ክስ በራሱ አመልካቾች የሰሩት ስራ ሊመራ እና ምላሽ ሊያገኝ ይገባ የነበረው በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱትን የፌዴራል እና የክልል ህግጋት መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በላይ ምን አይነት አሰራር እንደተፈለገ ግልጽ አይደለም፡፡ አመልካቾችም ቢሆኑ በቃለ ጉባኤ ያስቀጠሉት ብልሹ አሰራር ከእነርሱ በፊትም የነበረ መሆኑን ከመግለጽ ባለፈ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የተባሉት የህግ ማዕቀፎች መፍትሄ ለመስጠት አላስቻሉንም የሚል መከራከሪያ አላቀረቡም፡፡ ከዚህ አንፃር መከራከሪያ ቀርቦ ቢሆን እንኳን ህግ ክፍተት በህግ አግባብ ስልጣን ባለው አካል ስራን በሚያሳልጥ መልኩ እንዲታረም ክሚደረግ በቀር ህጉ አላሰራኝም›› በሚል ሽፋን ህግ በቃለ ጉባኤ ተተክቶ የሚሰራበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ ወደ ጎን ትተው የህግ መሰረት የሌለውን አሰራር ስራ ላይ በማዋል የመንግስትን ስራ በማያመች መንገድ መርተዋል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ሊሻር አይገባውም በሚል ከስራ ባልደረቦቻችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## 4.የቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ[103]

- ሕጉ በሚጠይቀው አግባብ ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጸና ፈቃድ ሳይኖረው ከቴሌኮሚኒኬሽን እውቅና እና ፈቃድ ወጭ ሶፍትዌሮችን በመገልገል በኢንተርኔት ስልኮች ማስደወል በቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13 ስር የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ፤[104]

**የሰ/መ/ቁ. 103940**

ጥር 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አልማው ወሌ

2. ዓሊ መሐመድ

3. ተኽሊት ይመስል

4. እንደሻው አዳነ

5. ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ አመለወርቅ ጌታነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

### ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የአሁኗ አመልካች ጨምሮ በ17 ተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረቡን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት 9ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኗ አመልካች ያቀረበው ክስ ባጭሩ፡- በንፋስ ስልክ ከተማ ቀበሌ 12/13 የቤት ቁጥር የማይታወቅ ንግድ ቤት ውስጥ ስልክ የማስደወል ፈቃድ ሳይኖራት ከቴሌ ኮሚንኬሽን ሲስተም በመደበቅ ስልክ ማስደወል የሚያስችል ራስ አዲስ ፒሲቶከር እና ራስ ዳሽን የተባሉ ሶፍትዌሮችና የካርድ ቁጥሮች (Accounts numbers) ከ3ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በመግዛት እንዱሁም ለጊዜው ማን እንዳስመጣው የማይታወቅ ኔት 2ፎን ዲያለር የተባለ ሶፍትዌር በመጠቀም 3ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር በስውር በመመሳጠር ባዘጋጁት ህገወጥ ተግባር በመታገዝ ወደ ወጭ አገር ስልክ በማስደወል እ.ኤ.አ ከ01/11/2004 እስከ 06/10/2010 ለ5 አመታት ከ339 ቀናት 779,040 ደቂቃዎች ወደ ተለያየ አገራት ከኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ሲስተም መደበቅ የሚያስችል ቴክኖሎጂ በመጠቀም በህገወጥ መንገድ በማስደወል ብር 7,70,400 (ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ሺህ አራት መቶ ብር) በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲዲረስ በማደርገና በህገወጥ መንገድ ብር 3895200.00 (ሶስት ሚሊዮን ዘጠና አምስት ሺህ ሁለት መቶ ብር) ተጠቃሚ በመሆኗ እንዲሁም በሽያጭ የተዘጋጁ ግምታቸው USD 17500 የሚያወጡ የካርድ ቁጥሮች በህገ ወጥ ሱቋ ውስጥ በመገኘታቸው የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)፤ 33፣ 411(1) ሐ የተመለከተው በመተላለፍ በህዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሳለች የሚል ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ የቀረበባት ክስ ክዳ በመከራከሯ የስር ፍርድ ቤት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ካደመጠ በኃላ እንድትከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ የአሁኗ አመልካች የበኩላን የመከላከያ ማስረጃ **በማስቀረብ አስምታለች፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የአሁኗ**

---

[103]አዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994

[104]የሰ/መ/ቁ. 103940 (ጥር 24 ቀን 2008 ዓ.ም)ቅፅ 19

አመልካች እና ሌሎች ተከሳሾች በክሱ በተገለጸው አግባብ ከቴሌኮሚኒኬሽን እውቅናና ፈቃድ ወጭ ሶፍትዌሮችን በመገልገል በኢንተርኔት ስልኮች በማስደወል ከፍተኛ ገንዘብ መሰብሰባቸውንና መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ የቴሌኮሙኒኬሽንን መስርያቤት ማስጣታቸውን ተረጋግጠባቸው አልተከላከሉም፡፡ በክሱ ላይ የተገለጹት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች መከላከላቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ጉዳዩ የሙስና ወንጀል መሆኑ ይቀራል ይህ በመሆኑም በ1ኛ ክስ የቀረበባቸው ዘጠኝ ተከሳሾች (3ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ፣ 7ኛ፣ 9ኛ፣ 11ኛ፣ 12ኛ እና 13ኛ ተከሳሾች) በህገወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ስልክ ለማስደወል ሶፍትዌሮች ማስደወያ ካርድ ቁጥሮችን በማከፋፈል ለአገኙት ህገወጥ ጥቅምና ለአሳጡት ጥቅም ተጠያቂና ጥፋተኛ የሚሆኑት በሙስና ወንጀል መሆኑ ቀርቶ ተከሳሾች ሊጠየቁ የሚገባቸው በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 11(4) ድንጋጌው ኢንተርኔት በመጠቀም የድምጽ መልእክትን ማስተላለፍ ወይም የማስተላለፍ አገልግሎት መስጠት ድንጋጌ ተላልፎ መገኘት በመሆኑ የተከሰሱበትን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)፣ 33፣ 411(1) (ሐ) እና (2) ድንጋጌዎች በወ/መ/ስ/ስ/ቁ. 113(2) በመለወጥ ከላይ በተጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 13 ድንጋጌ ጥፋተኛ ናቸው በማለት በአብላጫ ድምጽ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የመረመረ ሲሆን ወንጀሉ በከፍተኛ ደረጃ መድቦ ቅጣቱ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማስላት ወስኗል፡፡ ድንጋጌው ከ3 እስከ ከ4 አመት እስከ 4 አመት ከ6 ወር የሚያስቀጣ በመሆኑ በእርከን 18 የሚውድቅ ነው፡፡ በአሁኗ አመልካች የቀረበው አንድ የቅጣት ማቅለያ ተቀብሎ በእርከን 17 ስር በ3 አመት እንድትቀጣ፤ የገንዘብ መቀጮ በተመለከተ ከኢፌዴሪ የኢንፎርመሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በ11/04/2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት በአሁኗ አመልካች ተሰበሰበ የተባለው የገንዘብ መጠን 3,895,200 (ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሁለት መቶ) ያለፈቃድ በሰሩበት ጊዜ ውስጥ አግኝተውታል ተብሎ የቀረበባቸውንና በመከላከያቸው ያላስተባበሉት /ገንዘብ እጥፍ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያደረጉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች የስር ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽምበታል በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የወንጀል ድርጊቱ እንዳልፈጸሙ፤ በማስደወል አገኙት የተበለው ገንዘብም ሆነ በመንግስት ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳት አልተረጋገጠም፤ የተወሰነው የእስራት ቅጣት ይሁን የገንዘብም መቀጮ የህግ መሰረት የለውም በማለት መከራከራቸውን ያሳያል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት ያገናዘበ ስለመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርባዋል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራ ቀኝ በጽሁፍ ያደርጉት ክርክር ፣ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩን ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንዲሚከተለው መርምረናል፡፡ ጉዳዩን ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የእስራት ቅጣት በአግባቡ ሆኖ በወንጀል ስራ ምክንያት አመልካች አግኝታለች የተባለው የገንዘብ መጠን የተወሰነበት ስርዓት በህጉ አግባብ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡

ጉዳዩ እንደመረመርነውም አመልካች ፈቃድ ሳያወጡ ወይም የፀና ፈቃድ ሳይኖራቸው ስልክ በማስደወላቸው ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ባደረገው ማጣራት የአሁኗ አመልካች ምንም ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ስልክ በማስደወል ብር 3895200.00 እንደሰበሰቡ ቴሌኮሚንኬሽን ደግሞ ብር 7790400.00 ማጣቱን ከኢፌዴሪ የኢንፍርመሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ማስረጃ መቅረቡን

በውሳኔው አስፍሯል፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምኩም፣ ስልክ በማስደወል ገንዘብ አላገኘሁም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት በውሳኔው እንደገለጸው ያቀረበው ማስረጃ የሚያስተባብል ነገር አለማቅረባቸውን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ረገድ የሚደርስበት ድምዳሜ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳለ የሚቀበለው እንጂ በድጋሚ የሚያጣራበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው የአሁኗ አመልካች (የስር 9ኛ ተከሳሽ የነበሩ) ያለ ፈቃድ ስልክ በማስደወል ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሁለት መቶ ብር ጥቅም እንዳገኙ ነው፡፡ ይህ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ይዘን የአዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13 ስር የተመለከተው መቀጮ ዓይነትና ባህሪ መርምረናል፡፡

በዚህ አዋጅ ክልከላ የተደረገባቸው ድርጊቶች ፈጸሞ ጥፋተኛ የተበለው ግለሰብ በእስራትና በመቀጮ እንደሚቀጣ ተመልክቷል፡፡ የድንጋጌው የአማርኛ እንግልዝኛ ይዘት፡- "በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች አግባብ ባለቸው ህጎች መሰረት ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጸና ፈቃድ ሳይኖረው አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ በሰራበት ጊዜ ውስጥ ሊገኝ ይችላል ተብሎ የሚወሰነውን ገቢ እጥፍ የገንዘብ መቀጮና ከ3 አመት እስከ አምስት አመት በሚደረስ እስራት ይቀጣል በማለት የተደነገገ ሲሆን የእንግልዝኛው ትርጉም "any person who engages in tele communication service without having license or a valid license as per this proclamation or any other relevant laws shall be punished with fine equal to double the revenue estimated to have been earned by the person during the period of time he operated the service and with imprison mint from 3 up to 5 years" በማለት ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የመቀጮው መሰረት ወንጀል ፈጻሚው ካገኘው ጥቅም ወይም ሊያገኘው ይችላል ተብሎ የሚገመት የገንዘብ መጠን መሰረት የሚያደረግ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በህገ ወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ያገኙት የገንዘብ መጠንና መንግስት ያጣው ገቢ በሚመለከተው አካል ተጠርቶ እና ተረጋግጦ በመቅረቡን የስር ፍ/ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13 ላይ እንደተገለጸው የመቀጮው መጠን እጥፍ እንደሚሆን ነው፡፡ ደንጋጌው ተቀጪው እጥፍ እንደሚከፈል በግልጽ ካስቀመጠ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በህገ ወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ያገኙው ጥቅም እጥፍ እንዲከፍሉ መወሰናቸው ሲታይ በህጉ አተረጓጉም ረገድ የፈጸሙት ስህተት መኖሩን አያሳይም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው በአዋጅ ቁጥር 281/94 አንቀጽ 13 ድንጋጌዎች መሰረታዊ የመቀጮ አወሳሰን ስርዓት ተቀጪው ወንጀል በመስራቱ ያገኘው ጥቅም ታሳቢ ያደረጉ በመሆኑ ወንጀል በመስራቱ ብቻ ጥቅም ሲያገኝ የሚወሰንበት ስርዓት መሆኑን ተረደተናል፡፡ ከዚህ አንጻር በአመልካች ላይ የተወሰነው መቀጮ ተገኘ የተባለው ጥቅም በማስረጃ መረጋገጡን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 281/94 አንቀጽ 13 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
2. አመልካች በህገወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል አገኙት የተባለው የገንዘብ መጠን እጥፍ እንዲከፍሉ መወሰኑ በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## 5.የታክስ አስተዳደር አዋጅ

### 5.1 የሕግ ሰውነት ያላቸው የንግድ ድርጅቶች የወንጀል ተካፋይነት እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግ[105]

- አንድ የድርጅት ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው እሱ የሚመራው ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወኑ ሲረጋገጥ ይኸው ጥፋት ድርጅቱ በሚመራው ሥራ አስኪያጁ እንደ ተፈፀመ ተቆጥሮ ስራ አስኪያጁም ጭምር ተጠያቂ እንደሚሆን እንጂ ድርጅቱ ለፈፀመው ወንጀል ስራ አስኪያጁ ብቻ ተጠያቂ በማድረግ ድርጅቱ የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም ወደሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ስላለመሆኑ፤
- በፌደራል ታክስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 983/2016 አንቀጽ 120/1 ተጠቅሶ ያለደረሰኝ ግብይት በመፈፀም ወንጀል የተከሰሰ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 132/1 ድንጋጌ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ለማስቀረት የተደነገገ ድንጋጌ ባለመሆኑ እና ድርጅት የተከሰሰበት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120(1) ታክስ ከፋይ ማለቱ በህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ጭምር የወንጀል ተጠያቂ የሚያደርግ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 983/2016 ኣንቀጽ 120(1) በሆነው ያለ ደረሰኝ ግብይት መፈፀም ወንጀል መከሰሱ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 34(1) ድንጋጌ አንጻር ሲታይ የሕግ መሰረት የለውም ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ::[106]

የሰ/መ/ ቁጥር 237423

የካቲት 29 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች- ቴዎድሮስ ምህረት

አበባ እምቢአለ

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡ - የጦሳ ነጋዴዎች አጠቃላይ ንግድ ሥራ አክሲዮን ማኅበር

---

[105]የሰ/መ/ ቁጥር 237423 (የካቲት 29 ቀን 2016 ዓ/ም)

[106]በሰ/መ/ቁ 58008 (ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 11/12፣ በሰ/መ/ቁ 94913 (ሕዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19፣ በሰ/መ/ቁ 102640 (መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም) በሰ/መ/ቁ 218957 (መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅፅ 26፣ የሰ/መ/ቁጥር 74237 (ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 14 ፣ በሰ/መ/ቁ 48850 (ታህሳስ 08/2002 ዓ.ም) ቅፅ 10፣ በሰ/መ/ቁ 51090 (ታህሣሥ 12 ቀን 2003 ዓ.ም)ቅፅ 11፣ በሰ/መ/ቁ. 84623 (ሰኔ 04 ቀን 2005 ዓ.ም)ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ. 86597 (መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም)ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ. 86672 (መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ. 181958 (ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24፣ በሰ/መ/ቁ 251295 (ታህሳስ 23 ቀን 2017 ዓ.ም)

ተጠሪ፡- የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር - ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ የተቀጠረዉ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26/1 መሰረት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት መርምሮ ተገቢውን ለመወሰን በሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ስለሚሆንበት አግባብ በተመለከተ አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንዲለወጥ እንዲሻሻል በአምስት ዳኞች በተመራው መሰረት በዚህ መዝገብ ከቀረበው ከፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/1 እና 120/1 ድንጋጌዎች ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 34/1 እንዲሁም የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበት አግባብ አስመልክቶ አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳዮች የተሰጠው የሕግ ትርጉም ለመለወጥም ሆነ ለማሻሻል የሚያስገድድ ህጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም በሚለው ላይ ጉዳዩ በሰባት ዳኞች ታይቶ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ሲታይ፡- ክርክሩ የተጀመረዉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ የአሁን ተጠሪ ተወካይ የነበረዉ የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በአሁን አመልካችና የአመልካች ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኛ በሆኑት ላይ ሁለት ክሶችን መስርቷል፡፡

የመጀመርያው ክስ የመሰረተው በአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ እና የጥበቃ ሠራተኛ ላይ ሲሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ) እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ላይ የተደነገገዉን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት በማከናወናቸው ያለደረሰኝ ግብይት በመፈጸም ወንጀል ተከሰዋል የሚል ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

ሁለተኛው ክስ የመሰረተው አመልካች በሆነው ድርጅት ላይ ሲሆን የክሱ ይዘትም አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1 እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት እያወቀ በቀን 10/03/2013 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 1፡00 ሰዓት በደሴ ከተማ ሆጤ ክፍለ ከተማ መናኸሪያ አካባቢ በሚገኘዉ ጦሳ ቁጥር 1 መኝታ ቤት ደንበኛ የሆኑት ግለሰብ ለተከራዩት አልጋ ደረሰኝ ባለመስጠቱ በፈጸመዉ ያለደረሰኝ ግብይት በመፈጸም ወንጀል ተከሷል የሚሉ ናቸው፡፡

ለአመልካችና ለስር ተከሳሾች የክስ ማመልከቻዉ በጠበቃቸዉ በተወከሉበት እንዲደርሳቸዉ ተደርጎ ተነብቦላቸዉ አመልካች በጠበቃዉ አማካኝነት ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ይህ የወንጀል ክስ ከመቅረቡ በፊት የገቢዎች ሚኒስቴር ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በዚሁ ጉዳይ በአመልካች ላይ አስተዳደራዊ ክስ ስለወሰነብኝ በድጋሚ ልከሰስ አይገባም በማለት ቢቃወምም ፍርድ ቤቱም አመልካች አስተዳደራዊ ቅጣት መቀጣቱ የወንጀል ክስ እንዳይቀርብበት አያደርግም በማለት መቃወሚያዉን ዉድቅ ካደረገ በኃላ ተከሳሾች የእምነት ክህደት ቃላቸዉን እንዲሰጡ ጠይቋቸዉ ጥፋተኛ አይደለንም በማለት ክደዉ በመከራከራቸዉ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ሰምቶ ምስክሮች የሰጡት ቃል እና የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ (ተ.እ.ታ) ተመዝጋቢ መሆኑን የሰነድ ማስረጃ የሚያሳይ መሆኑን፤ የአመልካች የጥበቃ ሠራተኛ የመኝታ አገልግሎት ፈልጎ ለመጣዉ ለአመልካች ደንበኛ አልጋ በማስያዝ ብር 120.00 ተቀብሎ ደረሰኝ ሳይሰጥ ግብይት መፈጸሙ ተመስክሯል፣ ደንበኛዉም አልጋ መያዛቸዉን የሚያሳይ የእንግዶች መመዝገቢያ ፎርም የቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ዐቃቤ ሕግ እንደ ክስ አቀራረቡ ያስረዳ በመሆኑ አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች እያንዳንዳቸው ክሱን እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የተከሳሾችን መከላከያ ምስክሮች ከሰማ በኂላ የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ በመ/ቁጥር 20586 ላይ በቀን 24/06/2014 ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ የአመልካች ሥራ አስኪያጅ የነበሩት የስር 1ኛ ተከሳሽ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ በህመም ምክንያት እረፍት ላይ

መሆናቸዉን በማስረዳት ክሱን መከላከላቸዉን በመግለጽ በነጻ እንዲሰናበቱ ሲወስን የስር 2ኛ ተከሳሽ ምንም እንኳን የሥራ ድርሻቸዉ ጥበቃ ቢሆንም አልጋ በማስያዝ ገንዘብ ለመቀበል ፈቅደዉ ለሰሩት ሥራ ደረሰኝ የመስጠት ሕጋዊ ግዴታ ያልተወጡ መሆኑን በዐቃቤ ህግ የተመሰከረባቸዉን በማስተባበል ስላልተከላከሉ ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት የጥፋተኝነት ፍርድ ሲሰጥ የአሁን አመልካችን በተመለከተም በወንጀል ሕግ ቁጥር 34/1 ላይ እንደተመለከተዉ አንድ ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ የሚቆጠረዉ ከኃላፊዎቹ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ-ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም ወንጀል ሲሰራ ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ታክስ ከፋይ ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ ድርጅት በመሆን የአገልግሎት ግብይት ሲፈጽም ደረሰኝ የመስጠት ሕጋዊ ኃላፊነት እያለበት ደረሰኝ ሳይሰጥ ግብይት መፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠበትን በማስተባበል ያልተከላከለ በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 እና በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ፍርድ በመስጠት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመመርመር አመልካች በብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑን ተመልክተናል፡፡

አመልካች ይህንኑ ዉሳኔ በመቃወም ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ አቅርቦ በመ/ቁጥር 0207905 ላይ በቀን 15/07/2014 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት ሰርዞበታል፡፡ በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ አቤቱታ የቀረበበትን የመጨረሻ ዉሳኔ በሰበር ለመመርመር ሥልጣን የለኝም በማለት በመ/ቁጥር 0335004 በቀን 16/02/2015 ዓ/ም ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

አመልካች በጠበቃዉ አማካኝነት በቀን 19/03/2015 ዓ/ም የተዘጋጀ ለዚሁ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ሰበር አቤቱታ ይዘቱ አጠር ባለ መልኩ ሲታይ፡- አመልካች ከዚህ ቀደም በዚሁ ጉዳይ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ተላልፎበት በብር 15,000.00 ተቀጥቶ እያለ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 23 እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2/5 ስር የተደነገገዉን በሚቃረን አኳኋን በዚያዉ ድርጊት ለሁለተኛ ጊዜ ተከሶ መቀጣቱ ተገቢ አለመሆኑን፤ አመልካች ድርጅት ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ ግኡዝ በመሆኑ ሥራዉን የሚመራዉ፣ የሚያንቀሳቀስዉና የሚያስተዳድረዉ በቀጠራቸዉ ሠራተኞች አማካኝነት ሲሆን የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነው ስር 1ኛ ተከሳሽ ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ በቦታዉ አልነበረም ተብሎ ከወንጀሉ በነጻ ሲሰናበት አመልካች የሆነው ድርጅት ግን በማያዉቀዉና ባልፈጸመዉ ድርጊት ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽመሃል ተብሎ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ አለመሆኑ፤ አመልካች ወደ ድርጅቱ የሚመጡ እንግዶች ደረሰኝ ሳይቀበሉ ክፍያ እንዳይፈጽሙ ማስታወቂያ ግልጽ ቦታ በለጠፈበት ሁኔታ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለማይገባ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ እንዲሻር በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎቱም የአመልካችን ሰበር አቤቱታ መርምሮ፡- አመልካች ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሟል ተብሎ በአስተዳደር ብር 15,000.00 እንዲከፍል በተደረገበት ሁኔታ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ በብር 30,000.00 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የተወሰነበትን አግባብነት ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2/5 እና ጥፋተኛ ከተባለበት አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ጋር ተገናዝቦ ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በቀን 05/07/2015 ዓ/ም ጽፎ የሰጠው መልስ ይዘቱ፡- አስተዳደራዊ ቅጣትና የወንጀል ቅጣት ራሳቸዉን ችለዉ የሚቆሙ ስለሆኑ በአመልካች ላይ የወንጀል ቅጣት መወሰኑ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 2/5ን የወንጀል ክስንና ጥፋተኝነትን የሚመለከት እንጂ አስተዳደራዊ ቅጣትን የሚመለከት ባለመሆኑ ዉሳኔዉ እነዚህን ድንጋጌዎች የሚቃረን ስላልሆነ የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ጉዳዩን በሚመረመርበት ጊዜ ተጨማሪ ጭብጥ መመስረት "አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሟል በሚል የተከሰሰዉና ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 አነጋገር መሰረት ሕጋዊ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ከፈጸመ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 በግልጽ መደንገጉ ተረጋግጦ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁጥር 48850፣ 58008፣ 69899፣ 74237፣ 94913 እና በሌሎችም መዛግብት ላይ ከተሰጡ የሕግ ትርጉሞች ጋር በማገናዘብ መመርመር ይቻል ዘንድ" ለተጠሪ ደርሶት ተጨማሪ በተያዘው ጭብጥ ላይ መልሱን ሰጥተዋል ።

ተጠሪ በተጨማሪ ጭብጥ ተደርጎ በተያዘው ላይ በቀን 15/12/2015 ዓ/ም ጽፎ የሰጠው መልስ፡- በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56፣ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 102 እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132 ስር በግልጽ በተደነገገዉ መሰረት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን ስለተደነገገ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት ፍርድና ቅጣት መወሰኑ ተገቢ መሆኑን፤ አመልካች አክሲዮን ማኅበር በመሆኑ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ስላለበት ለሚፈጽመዉ ግብይት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 3(ሀ/1) እና በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2/41 መሰረት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ በመሆኑ፤ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2/26 መሰረት ሰዉ ማለት ድርጅትንም እንደሚጨምር የተደነገገ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ስር የተደነገገዉ ታክስ ከፋይ የሆነ ድርጅትን ጭምር በወንጀል ተጠያቂነት እንደሚሆን፤ የታክስ ወንጀሎች አብዛኛዉን ጊዜ በታክስ ከፋዮች የሚፈጸም በመሆኑና ድርጅቶች ታክስ ከፋይ ሆነዉ ስለሚመዘገቡ በታክስ አስተዳደር አዋጁ የድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት አልተደነገገም ማለት በአዋጁ የተመለከቱት ሁሉም ወንጀሎች በድርጅት ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን ስለሚያደርግ ከአዋጁ ዓላማና ግብ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባ መሆኑን፤ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 መሰረት የድርጅቱ ሠራተኞች ያለደረሰኝ ግብይት ሲፈጽሙ ድርጅቱ ወንጀል እንዳደረገ ስለሚቆጠር በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ በመቀጣቱ የተፈፀመ መሰረታዊ ስህተት የለም በሚል ተከራክሯል፡፡

አመልካችም በጠበቃዉ አማካኝነት በቀን 22/12/2015 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልሱን በማቅረብ የወንጀል ተጠያቂነት የለብኝም የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በአመልካች እና በስር ተከሳሾች ላይ የቀረቡትን ክሶች፣ በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎችንና ግራ ቀኙ ለዚህ ችሎት ያቀረቡትን ክርክር ባለአምስት ዳኞች ሰበር ሰሚ ችሎት መርምሮ ጉዳዩ በሰባት ዳኞች መታየት አለበት ያለበት ምክንያት እንደሚከለተው ሰፍሯል፡፡

አመልካች በቀረበበት የወንጀል ክስ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 ስር በተደነገገዉ አግባብ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ከፈጸመ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ላይ በግልጽ መደንገጉ ተረጋግጦ ነዉ ወይስ ሳይረጋገጥ የሚለው ነጥብ ላይ፡-

የሕግ ሰዉነት ከተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ ምክንያታቸውን በዝርዝር በማስፈር በአገራችን የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር አንድ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነዉ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡ ተጠያቂነቱም በተፈጥሮ ሰዉ ሊፈጸሙ በሚችሉት ሁሉም ወንጀሎች በሚመለከት ሳይሆን የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ የሚሆንባቸዉ ወንጀሎች ናቸዉ በሚል በግልጽ ሕግ በሚደነግጋቸዉ ወንጀሎች በተመለከተ ብቻ ነዉ፡፡ ከድርጅቱ ኃላፊዎቹ አንዱ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ-ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም አንድን የወንጀል ድርጊት ቢፈጽም እንኳን የተፈጸመዉ የወንጀል

ድርጊት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ የሚሆንበት ወንጀል ነዉ ተብሎ በግልጽ በሕግ ላይ ካልተደነገገ በሥራ ኃላፊዉ ወይም በሠራተኛዉ የወንጀል ድርጊት በመፈጸሙ ብቻ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፤ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994ም ሆነ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 የሕግ ሰዉነት ስለተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት በግልጽ አልተደነገገም ።

በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56/1 እና በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/1 ድንጋጌዎች የተደነገጉበት ዓላማ ምንድን ነዉ የሚለዉን ስንመረምር በእኛ እምነት በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56/1 እና በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/1 የተደነገገዉ የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ የሆነ ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 285/1994 የተደነገገዉን ወይም ከወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ ይህንን አዋጅ በተካዉ የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በድርጅቱ የተፈጸመዉን ጥፋት ራሱ እንደፈጸመ ተቆጥሮ በአዋጁ የተመለከተዉ ቅጣት በሥራ አስኪያጁ ላይ ሊወሰንበት እንደሚችል የተደነገገበት እንጂ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የተደነገገ አይደለም፡፡

ሕግ አዉጪዉ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ለሚፈጽመዉ ጥፋት በታክስ አስተዳደር አዋጁ መቀጣት የፈለገዉ በአዋጁ ምዕራፍ ሁለት ከአንቀጽ 101 እስከ 115 ድረስ በተደነገገዉ መሰረት በአስተዳደራዊ ቅጣት እንጂ በወንጀል ቅጣት መቀጣትን ስላልሆነ፤ በሰ/መ/ቁጥር 74237፤ በሰ/መ/ቁጥር 48850 እና በሌሎች ባልተጠቀሱት መዛግብት ላይ የሕግ ሰዉነት የተሰጣቸዉን ድርጅቶች በወንጀል ተጠያቂ በሚያደርግ መልኩ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል በሚል በግልጽ ባልደነገገበት የተሰጠ ትርጉም በመሆኑ ሊለወጥ ይገባል፡፡

እንዲሁም ከወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ላይ የተደነገገዉን በተካዉ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ላይ ጭምር ምንም እንኳን ሰዉ ለሚለዉ ቃል የተሰጠዉ ትርጓሜ የተፈጥሮ ሰዉን ብቻ ሳይሆን በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት ጭምር የሚያካትት ቢሆንም በሕጎቹ በማንኛዉም ሰዉ ወይም በማንኛዉም ታክስ ከፋይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚል የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 በመጀመሪያዉ ፓራግራፍ የተመለከተዉን የሕጋዊነት መስፈርት በሚያሟላ አኳኋን የተደነገጉ ስላልሆኑ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ላይ የወንጀል ተጠያቂነትን ለማስከተል ታስበዉ የተደነገጉ አይደሉም የሚል ግልጽ ትርጉም ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህንን በሚደግፍ አኳኋን በሰ/መ/ቁጥር 69899 (በቅጽ 12 እንደታተመዉ) የንግድ ምልክት ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 41/1 "ማንኛዉም ሰዉ" በሚል አገላለጽ መደንገጉ ብቻዉን የሕግ ሰዉነት ያላቸዉን ድርጅቶች በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ ታስቦ የተደነገገ እንዳልሆነ ግልጽ የሕግ ትርጉም ስለተሰጠ በተጠቃሾቹ በሰ/መ/ቁጥር 48850፣ 74237፣ በሰ/መ/ቁጥር 48850፣ 58008፣ 69899፣ 74237፣ 94913 እና በሌሎችም መዛግብት ላይ የተሰጠዉ ትርጉም ተለዉጦ ከዚህኛዉ ትርጉም ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ሊተረጎም ይገባል፡፡ እንዲሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56/1 እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/1 ላይ የተደነገገዉ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የወንጀል ተጠያቂነት የሚመለከት እንጂ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት የሚመለከት አይደለም በሚል ግልጽ ትርጉም ሊተካ ስለሚገባ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26/1 መሰረት በሰባት ዳኞች ጉዳዩ እንዲታይ መዝገቡ ተመርቷል፡፡

ጉዳዩ ለሰባት ዳኞች መመራቱን ተከትሎ በቅድሚያ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተጠያቂ ስለሚሆንበት አግባብ በተመሳሳይ ጉዳይ አስቀድሞ የተሰጡ የህግ ትርጉሞች በሰባት ዳኞች ለመለወጥ/ለማሻሻል የሚያስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ተመርምሯል፡፡ ባለአምስት ችሎቱ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል

ተጠያቂ ስለሚሆንበት አግባብ በተመለከተ ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ጉዳይ የተሰጡ የህግ ትርጉሞች ሊለወጡ/ሊሻሻሉ ይገባል ወደሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰበት ምክንያት አጠር ባለ መልኩ ሲታይ በዚህ መዝገብ 0/ህግ አመልካች ላይ የፌደራል ታክስ አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት ፈፅዋል በሚል ያቀረበው ክስ ከመነሻውም በታክስ አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/1 ድንጋጌ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት ወንጀል ፈጽሞ ሲገኝ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወንጀሉ እንደፈፀመው ተቆጥሮ ተጠያቂ እንደሚሆን እንጂ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት የወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን ስለማያመለክት ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሞ ቢገኝ አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ሊኖረው ከሚችል በስተቀር በወንጀል እንደሚጠየቅ አዋጁ አያመላክትም በአዋጁ መሰረት ድርጅቱ ወንጀል ፈጽሞ ቢገኝ የሚጠየቀው የድርጅቱ ስራአስኪያጅን እንጂ ድርጅቱን አይደለም የሚል አቋም በመያዝ ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደመረመርነው የህግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠየቂነት (corporate criminal liability) ድርጅቶች ወይም በድርጅቶቹን በሚመሩ ሀላፊዎች ወይም ሌሎች ሰራተኞች ከስራቸው ጋር በተያያዘ በሚፈጽሙት ጥፋት ድርጅቱ በወንጀል ተጠያቂ ስለሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በሕግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት ፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሊቀጣ የሚችል መሆኑን ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት በሕጉ በወንጀል እንደሚጠየቅ በልዩ ሁኔታና በግልጽ ባልደነገገባቸው ወንጀሎች የወንጀል ተጠያቂነት እንደማይኖርበት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል ፡፡ በዚሁ ንኡስ ድንጋጌ በሁለተኛው ፓራግራፍ ስር አንድ ደርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው ከሀላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ፈጽሞ ሲገኝ መሆኑን ተመልክቷል፡፡

ጉዳዩ አመልካች የሆነው ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት በመፈፀም ወንጀል የተከሰሰ ሲሆን የተከሰሰበት አዋጅ አጠቃላይ አዋጁ የወጣበት አላማ አንጻር ስንመለከት፡- ከመነሻው ታክስ ማለት መንግስት በሕግ መሰረት በማድረግ ለመንግስታዊ ተግባራትና ለልማት ስራዎች ማከናወኛ የሚያስፈልገውን ገቢ ለማግኘት የንግድ እንቅስቃሴ ከሚያከናውኑ ግለሰቦች፤ ድርጅቶች እንዲሁም ገቢ ከሚያገኙ ማናቸውም ሰዎች ገንዘብ የሚያገኝበት ስልት ነው፡፡ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 እንዲወጣ አስፈላጊ ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱም የታክስ አስተዳደሩ ይበልጥ ቀልጣፋ ውጤታማ እና ተገማችነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የአገር ውስጥ ታክሶች ሁሉ የሚመሩበት ራሱን የቻለ የታክስ አስተዳደር አዋጅ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ እንደሆነ በአዋጁ መግቢያ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

ጉዳዩ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲታይ የተመራበት ዋናው ነጥብ የአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120 ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1/ አንጻር በግልጽ የሕግ ሰውነት ያለውን አካል የወንጀል ተጠያቂነትን ስለማያመለክት ከዚህ ቀደም የተሰጠው ትርጉም መቀየር አለበት የሚል ትንታኔ በመቅረቡ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120 የሕግ ሰውነት ያለው ታክስ ከፋይን አያካትትም ለሚለው አረዳድ መነሻው የወንጀል ሕጉ አንቅጽ 34 የዚህ ኃይነት ኃላፊነት ሕጉ በግልጽ ካልደነገገ በስተቀር ሊኖር አይችልም ከሚል ነው፡፡ ሕጉ ግልጽ ነው አይደለም የሚለው ላይ የሚቀርበው ክርክር ወደፊት የሚታይ ሆኖ ሕጉ አሻሚ ነው ቢባል የሕጋዊነት መርህ ፍርድ ቤቶች የወንጀል ሕጉን እንዳይተረጉሙ ገደብ ሊሆን እንደማይችል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 4(4) በማያሻማ ሁኔታ ተመልከቶ እናገኘዋለን፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቶች የሕጉ አነጋር አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ ሕጉ ሊደርስበት ያሰበውን ግብ ለማረጋገጥ እንዲቻል ሕግ አውጪው ባቀደው ትርጉምና የህጉ መንፈስ በሚያሳካ ሁኔታ መተርጎም እንዳለበት በዚሁ ድንጋጌ ተመልከቶዋል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት አንቀጽ ግልጽ ቢሆንም አሻሚ ነው ቢባል እንኳ ፍርድ ቤቶች ትርጉም ከመስጠት

የተደረገባቸው ገደብ የለም፡፡ በዚህ አግባብ የሕጉን ይዘት፣ ዓላማና ሕግ አውጪው በታክስ ሕጉ ሊያሳካ ያሰበውን ግብ ከግምት በማስገባት ሕጉ የሕግ ሰውነት ያላቸውን ታክስ ከፋዩች በይዘትም ሆነ አጠቃላይ መንፈሱ የወንጀል ኃላፊነት እንዲኖርባቸው መወሰኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ አጠቃላይ የሕጉን ይዘት በማየት ሕጉ ታክስ ከፋዮች ላይ ግደታ በመጣል ይህ ሲጣስ አስተደደራዊ እና የወንጀል ተጠያቂነትን አስቀምጦ ስለምናገኘውና ደረሰኝ መስጠትም በሁሉም ታክስ ከፋይ ላይ የተጣለና ከዚህ ውጭ ያለው አረዳድ የሕግ ሰውነት የተሰጣቸውን ሰዎች ሽፋን በማድረግ ሕጉን ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚያደርግ ይህንን ሽፋን አድርገው የታክስ መሰብሰብን የሚያደናቅፉ ሰዎችም ከተጠያቂነት ነጻ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ከአጠቃላይ የሕጉ ይዘትና መንፈስም ሆነ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት የሚቃረን ውጤት ከመሆኑም በላይ የህግ አተረጓጎም መርህንም የሚጣረስ ይሆናል፡፡ ሆኖም በዚህ ጉዳይ ሕጉ አሻሚ ካለመሆኑም በላይ አጠቃላይ ይዘቱ የሕግ ሰውነት ያላቸውን ታክስ ከፋዩችንም ተጠያቂ ለማድረግ ያለመ በመሆኑ ለትርጉም የተጋለጠ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባለው በአዋጅ ቁጥር 983/2008 በቁጥር 120 መሰረት በመሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት ከዚህ ድንጋጌ ይዘት አንጻር ሲሆን ድንጋጌው ተጠያቂነት የሚመሰርተው በማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ነው፡፡ የታክስ ወንጀሎች የሚፈጸሙት በማንኛውም ሰው ሳይሆን በታክስ ከፋዩች ነው፡፡ ስለዚህ ሕጉ በዚህ ድንጋጌ በግልጽ የጥፋቱን ፈጻሚ አድርጎ የሚወስደው ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይን ነው፡፡ በሕጉ ውስጥ ከምናገኘው ሁለት መስፈርቶች ውስጥ የመጀመሪው ታክስ ከፋይ የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከታክስ ከፋይም ውስጥ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰውን ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የታክስ ወንጀሎች የሚፈጸሙት በታክስ ከፋይ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ ግን ይህንንም አጥብቦ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበትን ታክስ ከፋይ ብቻ የሚመለከት ነው፡፡

በሕጉ ታክስ ከፋይ ለሚለው ሐረግ የተሰጠውን ትርጉም ስናይ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(41) እንደተመለከተው ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው እንደሆነና ለተጨማሪ እሴት የተመዘገበ ወይም መመዝገብ ያለበትን ሰው እንደሚጨምር መረዳት ይቻላል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 26 ስር ደግሞ “ሰው” ማለት ግለሰብ፣ ድርጅት፣ መንግሥት፣ የመንግሥት አስተዳደር አካል ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ጭምር እንደሚያካትት የተደነገገ ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች ታክስን በተመለከተ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይም ተፈጻሚነት እንዳላቸው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ አዋጁ የህግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት አስቀርቷል የሚባል ከሆነ በሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ ባይወጣም በዚህ ልዩ የሕግ አቋሙ (status) ምክንያት ተጠያቂ የማይሆንበት ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሕግ ተፈጻሚነት ከታክስ ሕግ ዓላማ አንጻር መታየት አለበት፡፡ ታክስ ከፋይ የሆነ ሰው ታክስ በመክፈል ረገድ ያለበት ግዴታ፣ የሚከፍለው መጠን፣ የገቢ አሰባሰብና የማሳወቅ ኃላፊነት ወዘተ በሕጉ በተመለከተው አግባብ እንዲፈጽም የሚጠበቅ ሲሆን ይህን መተላለፍ የሚያስከትለው ውጤት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡ የወንጀል ተጠየቂነት ዓላማም የመንግስት መኖርን ወይም ውጤታማነትን የሚወሰነውና በአግባቡ፣ በትጋትና በጥንቃቄ መተዳደር ያለበትን ታክስ መሰብሰብ ለማረጋገጥ እንዲሁም የሕግ ተገዢነትን ለማረጋጥ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ዓላማ የሚሳካው ሕጉ ወጥ በሆነ መንገድ ሲፈጸም ነው፡፡ ሕግ አውጪው የሕግ ሰውነት ያላቸውን ታክስ ከፋዮችን ከዚህ ኃላፊነት ነጻ ለማድረግ አስቦዋል የሚለው አረዳድ በሕጉ ይዘትና ዓላማ መወሰን ያለበት ሲሆን በተቃራኒ የሚቀርበው አረዳድ የሕጉን ሙሉ በሙሉ መፈጸምን የሚያስቀር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34(1) ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት እንደአመልካች ያለ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በሕግ በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር የወንጀል ድንጋጌ ተፈጻሚ እንደማይሆንበት የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ በወንጀል ሕጉ ውስጥ ያለ ድንጋጌ ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ በሚሆነውና የሕጉን ተገዢዎች በዚህ መልኩ በሚለየው ሕግ ላይ ተፈጻሚ የሚሆንበትን አግባብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅም ሆነ የታክስ

አስተዳደር አዋጅ ሕጎች ታክስ ከፋይ ለሚለው ሐረግ የሰጡት ትርጉም አመልካችን እንደሚያካትት ግልጽ ነው፡፡ በአዋጁ ውስጥ የተካተቱን የወንጀል ድንጊቶችን ስናይ በማንኛው ሰው፣ በግብር ከፋይ፣ በሰራተኛ፣ በታክስ ወኪል ወዘተ እያለ ሕጉ ልዩነቶችን ግምት ውስጥ ያስገባ የተጠያቂነት ምድብ አካቶዋል፡፡ ከላይ ከተመለከተው ትርጉም አንጻር የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ሰዎች የተጠቀሰውን የሕግ አቋም ካሟሉ ሕጉ ለዚህ ሁኔታ ያስቀመጠው ተጠያቂነት ተፈጻሚ እንደሚሆንባቸው ግልጽ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአዋጆቹ ተፈጻሚነት በዋናነት በማናቸውም ሰው ላይ ሳይሆን ልዩ የሕግ አቋም ባላቸው ሰዎች የሚፈጸም ወንጀል አድርጎ ስለደነገገ በሕጉ የተመለከተ ወንጀል ሲፈጸም ይህ ልዩ አቋም ባለው ሰው ላይ ተፈጻሚ እንደመሚሆን ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ የወንጀል ሕጉ ከሚደነግገው በሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ታክስ ከፋዮች ታክስ ከፋይ በመሆናቸውና ይህ ልዩ የሕግ አቋም ስላላቸው በድንጋጌው በግልጽ መጠቀሳቸው አሻሚ አይደለም፡፡ ስለዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34(1) በሚያስቀምጠው ደረጃ ሕጉ ታክስ ከፋዮችን በለየበት መንገድ እና ይህ ልዩ የሕግ አቋም በአጠቃላይ የሕጉ ተፈጻሚነት መሰረት ስለሆነ የወንጀል ሕጉ በሚፈለገው መልኩ በግልጽ ተመልክቶዋል ማለት የሚቻል ነው፡፡

ሕጉ ወጠ በሆነ ሁኔታ ይህን አቋም እንደያዘ ከአጠቃላይ ይዘቱ ለመረዳት የሚቻል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይ ይህን አረዳድ ከሚያጠናክሩ ድንጋጌዎች ውስጥ የአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132 አንዱ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በሕግ ሰው የሚፈጸመውን ወንጀል ተጠያቂ ወደሆነው ድርጅት ሥራ አስኪያጁ የሚያሰፋ ድንጋጌ ነው፡፡ ሕጉ ድርጅቱን እንደታክስ ከፋይ ኃላፊ ስላደረገው በዚህ ድንጋጌ የምናገኘው መልዕክት የታክስ ሕግ በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈጸበት ወቅት ሥራ አስኪያጅ የነበረው ሰው ወንጀሉን እንደፈጸመ ይቆጠራል የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ በአንቀጽ 120 ጥፋተኛ የሚባል የሕግ ሰውነት ያገኘ ታክስ ከፋይ በሚኖርበት ጊዜ ይህ ጥፋት ድርጊቱ በተፈጸመበት ወቅት በስራ ላይ በነበረ ሥራ አስኪያጅም እንደተፈጸመ ይቆጠራል፡፡ ሕጉ የሕግ ሰውነትን ኃላፊነትን በግልጽ ከማስቀመጡም በላይ በአንቀጽ 132 ተጠያቂነቱ ወደ ሥራ አስኪያጁም እንዲደርስ አድርጎዋል፡፡ ይህን ድንጋጌ በተቃራኒው ቢወሰድ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ታክስ ከፋይም ሆነ ሥራ አስኪያጁ የሕግ ተጠያቂነት አይኖርባቸውም፡፡ የሥራ አስኪያጁ ኃላፊነት የሚመነጨው ከሕግ ሰውነቱ የወንጀል ተጠያቂነት በመሆኑና ሕጉ ይህንን ታክስ ከፋይ በሚለው ሐረግ ያካተተው በመሆኑ በድጋሚ መደንገግ ሳያስፈልገው ስራ አስኪጁን በቀጥታ ተጠያቂ አድርገንዋል፡፡ ስለዚህ የሕግ ሰውነት የተሰጠውን ግብር ከፋይ ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ የሚኬድበት አተረጓጎም አንቀጽ 120ን በሕግ ሰዎች ላይ ያለውን ተፈጻሚነት ቀሪ ከማድረግ ባለፈ የአንቀጽ 132 በሕግ ሰው ላይ የወንጀል ተጠያቂነት እንደሚኖር የሚገልጸውን ይዘት ብቻ ሳይሆን ሕግ አውጭው ይህን ተጠያቂነት ወደ ሥራ አስኪያጅ ለማስፋት የሕግ ተገዥነትን ለማረጋገጥ ያለውን ሐሳብ ዋጋ የሚያሳ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከሕጉ ወጥ አቋምና ግልጽ ይዘት የሚቃረን ከመሆኑም በላይ ሕግ አውጪው ሊደርስበት ካሰበው ግብ ውጭ ስለሚሆን ተቀባይነት ያለው አረዳድ አይሆንም፡፡

የአንቀጽ 132 ተፈጻሚነት አንድ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት በመፈጸም ወንጀል ፈጽሞ ቢገኝ አስተተዳደራዊ ቅጣት እንደሚቀጣና ሥራ አስኪያጁ ግን የወንጀል ተጠያቂነት እንዲኖርበት በማድረግ ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ክርክር ይቀርባል፡፡ ይህ በውስጡ ቅራኔ የያዘ አገላለጽ ነው፡፡ አንድ የሕግ ሰው በዋና ወንጅል አድራጊነት በአነሳሽት ወይም በአባሪነት የሚጠየቀው በሕግ በግልጽ ሲደነገገ ነው ከተባለ ከዚህ ውጭ ተጠያቂነት ሊኖር አይችልም፡፡ አንቀጽ 132 ተግባራዊ እንዲሆን በወንጀል ኃላፊ የሆነ ድርጅት መኖር አለበት፡፡ ከላይ የቀረበው ሙግት ድርጅቱ ወንጀል ፈጽሟል ነገር ግን የሚጠየቀው ሥራ አስኪያጁ ነው የሚል ተቃርኖ የያዘ ነው፡፡ የወንጀል መፈጸም ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች መሟላትን ታሳቢ የሚያደርግ ሲሆን እነዚህ ሁኔታዎች ካልተሟሉ የአንቀጹ ተፈጻሚነት ትርጉም ያጣል፡፡ ወንጀል እንዲቋቋም ከሚያስፈልጉት አላባዎች አንዱ የሕግ ሁኔታ ሲሆን በሕግ የወንጀል ተጠያቂ አይደለም ያልነው ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ ለፈጸመው ወንጀል

ተጠያቂ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ስለዚህ አዋጅ ቁጥር 983/2008 በግልጽ የድርጅቱን የወንጀል ተጠያቂነት በአንቀጽ 120ም ሆነ በአንቀጽ 132 የደነገገ በመሆኑ ድርጅቱን ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ የሚያደርግ አተረጓጎም ይህን ግልጽ የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ይሆናል፡፡

የአዋጁ ምዕራፍ ሦስት ድንጋጌዎች የታክስ ወንጀሎችን በሚመለከት የተደነገጉ ድንጋጌዎች ሲሆኑ በዚህ ምዕራፍ ሥር በአንቀጽ 116/2 የተለያዩ የታክስ ሕጎችን በመተላለፍ በምዕራፉ ስር የተመለከተ ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ እያንዳንዱን የታክስ ሕግ በመተላለፍ እንደተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ተቆጥሮ በአንቀጾቹ ላይ የተመለከቱትን ቅጣት እንደሚቀጣ ይደነግጋል፤ ከደረሰኝ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ ወንጀሎችን በተመለከተ ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከብር 25,000 /ሀያ አምስት ሺህ/ እስከ ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጫ እና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እንደሚቀጣ በዚሁ አዋጁ አንቀጽ 120/1 ስር ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2016 አንቀጽ 132 በድርጅቶች ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች በሚለው ርእስ ስር በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 1 የታክስ አስተዳደር ህጉን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈፀመበት ወቅት ሥራ አስኪያጅ የሆነው ማንኛውም ሰው ወንጀሉን እንደፈፀመ ይቆጠራል በሚል የሚደነግግ ሲሆን ወንጀሉ የተፈጸመው ሥራ አስኪያጁ ሳይፈቅድ ወይም ሳያውቅ ከሆነ እና በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያለ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብለው የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ለማድረግ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተመለከተው ተፈጻሚ እንደማይሆን በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 2 ስር ተደንግጓል፡፡

ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው በዚሁ አዋጅ ስር ባሉት ድንጌዎች ሰው በማለት የተገለፀው ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅትንም እንደሚያካትት በትርጉም ክፍል የተጠቀሰ ሲሆን በአብዛኛው በሀገራችን ታክስ ከፋይ ተብሎ የሚታወቀው በተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ወይም የመመዝገብ ግዴታ ያለባቸው ድርጅቶችንም ጭምር ያካተተ መሆኑን የምንገነዘበው ነው፡፡ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120 ከደረሰኝ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ ወንጀሎችን የሚመለከት ሲሆን በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (1) ላይ ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ በወንጀል እንደሚያስጠይቀው በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ታክስ ከፋይ ማለት ድርጅትንም ጭምር ስለሚያካትት ድርጅቱ ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሞ ቢገኝ በዚህ ድንጋጌ ስር የማይጠየቅበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ እንዲሁም የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132(1) ድንጋጌ ስራ አስኪያጁ የሚመራው ድርጅት በወንጀሉ ሃላፊ መሆኑ ከተረጋገጠ የሥራ አስኪያጁ ሃላፊነት የሕግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ የሚደነግግ ሲሆን ሥራ አስኪያጁ ከዚህ የሕግ ግምት ሃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማስረዳት ከቻለ ብቻ መሆኑን ከድንጋጌው የምንረዳው ነው፡፡ ይህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 983/2016 አንቀጽ 132 በድርጅቶች የሚፈፀመው ወንጀል የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የወንጀል ተጠያቂነት ያለበት ስለመሆኑ የሚመለከት እንጂ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት የሚመለከት አደለም በሚል ድንጋጌውን በመተርጎም ባለአምስቱ የያዘው የህግ አቋም አዋጅ ቁጥር 983/2016 አንቀጽ 132 ድንጋጌ እና እንደአጠቃላይ የታክስ አስተዳደር አዋጁ አላማ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2016 አንቀጽ 132 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያመለክተው አንድ የድርጅት ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው እሱ የሚመራው ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወኑ ሲረጋገጥ ይኸው ጥፋት ድርጅቱ በሚመራው ሥራ አስኪያጁ እንደ ተፈፀመ ተቆጥሮ ስራ አስኪያጁም ጭምር ተጠያቂ እንደሚሆን እንጂ ድርጅቱ ለፈፀመው ወንጀል ስራ አስኪያጁ ብቻ ተጠያቂ በማድረግ ድርጅቱ የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም ወደሚል

ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ሆኖ አላገኘነውም፤ አመልካች በሆነው ድርጅት ላይ በፌደራል ታክስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 983/2016 አንቀጽ 120/1 ተጠቅሶ ያለደረሰኝ ግብይት በመፈፀም ወንጀል መከሰሱ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 132/1 ድንጋጌ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ለማስቀረት የተደነገገ ድንጋጌ ባለመሆኑ እና አመልካች ድርጅት የተከሰሰበት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120(1) ታክስ ከፋይ ማለቱ በህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ጭምር የወንጀል ተጠያቂ የሚያደርግ ስለመሆኑ በቀላሉ መረዳት የሚቻል ሆኖ እያለ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 983/2016 ኣንቀጽ 120(1) በሆነው ያለ ደረሰኝ ግብይት መፈፀም ወንጀል መከሰሱ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 34(1) ድንጋጌ አንጻር ሲታይ የሕግ መሰረት የለውም ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም። በመሆኑም ከዚህ በፊት የሕግ ሰውነት በተሰጣቸው ድርጅቶች ላይ ስለሚኖራቸው የወንጀል ተጠያቂነት አስመልክቶ በተመሳሳይ ጉዳይ ሰበር ችሎቱ በበርካታ መዝገቦች የሰጠው የህግ ትርጉም ለመለወጥ/ለማሻሻል የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ስላላገኘን ጉዳዩ በሰባት ዳኞች ታይቶ የተለየ የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው አይደለም በማለት በአብላጫ ድምጽ ፍርድ ሰጥተናል በዚሁ መሰረት ተከታዩ ታዟል።

## ትዕዛዝ

ጉዳዩ በሰባት ዳኞች የተለየ የህግ ትርጉም የሚስፈልገው ሆኖ ስላላገኘነው በመደበኛው ባለአምስቱ ሰበር ችሎት ጉዳዩ ተመልሶ አመልካች ካቀረቡት ሰበር አቤቱታ አንጻር የግራቀኙን ክርክር ተመርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ተመልሷል።

## የልዩነት ሀሳብ

በተራ ቁጥር 4 እና 6 ላይ የተሰየምን ዳኞች በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 23/12/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት አምስት ዳኞች የተሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26/1 መሰረት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተለዉጦ ወይም ተሻሽሎ በፌደራል ታክስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 983/2016 አንቀጽ 120/1 ስር የተደነገገዉ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት (body corporate) የወንጀል ተጠያቂነት አይደነግግም፤ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 132/1 የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት ተጠያቂነት ሳይሆን በድርጅቱ ጥፋት (ወንጀል) ጥፋቱ በሚፈጸምበት ጊዜ የነበረ የድርጅቱ ሥራ አሥኪያጅ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበትን አግባብ የሚደነግግ ነዉ ተብሎ ግልጽና አስገዳጅ ትርጉም ሊሰጥበት እና አመልካች የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ሊሻር ይገባል ብለን ስለምናምን በአብላጫ ድምጽ በቀን 29/06/2016ዓ/ም በተሰጠዉ ዉሳኔ ባለመስማማታችን የሚከተሉትን ምክንያቶች መሰረት በማድረግ የልዩነት ሀሳባችንን አስፍረናል። አመልካች የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት መሆኑ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ተ.እ.ታ) ተመዝጋቢ መሆኑ፣ በጥበቃ ሠራተኛዉ አማካኝነት በደሴ ከተማ በሚገኘዉ ጦሳ ቁጥር 1 መኝታ ቤት ዉስጥ የመኝታ (የአልጋ) አገልግሎት ለደንበኛዉ ሰጥቶ የብር 120.00 ግብይት ሲፈጽም ለደንበኛዉ ደረሰኝ አለመስጠቱ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸዉ። እንዲሁም የስር ፍርድ አመልካችን በአዋጅ ቁጥር 983/2016 አንቀጽ 120/1 ስር በወንጀል ጥፋተኛ ነዉ በማለት በብር 30,000.00 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል። የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ የሚሻዉ ጭብጥ አመልካች በቀረበበት የወንጀል ክስ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 ስር በተደነገገዉ አግባብ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ከፈጸመ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ላይ መደንገጉ ተረጋግጦ ነዉ ወይ? የሚል ነዉ።

በአገራችን የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት (legal entity body) በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበትን አግባብ ከመመልከታችን በፊት በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት (Corporate Criminal Liability) ጋር በተያያዘ ያለዉን የሕግ ጽንሰ ሀሳቦችን አስተምህሮዎችን እና መርሆዎችን

(Theories, Doctrines and Principles) በአጭሩ መመርመሩ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በዘርፉ ከተጻፉት ድርሳነት መረዳት እንደሚቻለዉ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ምንጩ የኮመን ሎዉ ሥርዓት እንደሆነ ይነገራል፡፡ በዚህ የሕግ ሥርዓትም ቢሆን በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ግዙፋዊ ቁመና፣ የአዕምሮና የሞራል ችሎታ (physical, mental and moral capacity) የለዉም ተብሎ ይታመን ስለነበር እስከ 19ኛዉ ክፈለ ዘመን ድረስ በወንጀል ተጠያቂ ሳይሆን ቆይቷል፡፡ በዋናነት የኢንዱስትሪ አብዮት ተከትሎ በመጀመሪያ በዩናይትድ ኪንግደም (United Kingdom) በኂላም በአሜሪካ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በአገራችን በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ለመጀመሪያ ጊዜ በወንጀል ሕግ ደረጃ እዉቅና ያገኘዉ በ 1996ዓ/ም በወጣዉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ላይ ነዉ፡፡ የሕግ ሰዉነት ከተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ ሦስት አይነት አመለካከቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም፡- 1ኛ) በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖርበት አይገባም የሚል ወይም ለወንጀል ተጠያቂነት ዕዉቅና የማይሰጥ አመለካከት፤ 2ኛ) የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት በአስተዳደራዊ ቅጣት ወይም በፍትሐ ብሔር ኪሳራ በማስከፈል ኃላፊ የሚደርግበት ሲሆን እንዲሁም 3ኛው) ደግሞ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን ማድረግን እዉቅና የሚሰጥ አመለካከቶች ናቸዉ፡፡ እነዚህ አመለካከቶች በግርድፉ ግዙፍነት የሌለዉ ሆኖ የተፈጠረ (ፍክሽን) ጽንሰ ሀሳብ (Fiction Theory) እና በራሱ ድርጊትና አል-ድርጊት (commission and omission) መፈጸም የሚችል ወይም በገሃድ ያለ ድርጅት ጽንሰ ሀሳብ (Real Entity Theory) በሚሉ ጽንስ ሀሳቦች ላይ የተመሰረቱ ናቸዉ፡፡

የመጀመሪያዉ ጽንሰ ሀሳብ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ሰዉ ሠራሽ፣ ግዙፍነት የሌለዉ እና ምናባዊ በመሆኑ ሥራዉን የሚያከናዉነዉ በተፈጥሮ ሰዎች አማካኝነት ስለሆነ የራሱ የሆነ የአዕምሮ ክፍል ስለሌለዉ ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ (mens rea/ criminal intent) በራሱ ማሰብ አይችልም ብሎ ያምናል፡፡ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ወንጀል የማድረግ ሀሳብ (mens rea) ከሌለዉ ደግሞ የወንጀል ሕግ መሰረታዊ አላባ (element) ስለማይሟላ የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖርበት አይገባም የሚል መሰረት ላይ የተመረኮዘ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ በራሱ ሕጋዊያን ተግባራትን መፈጸም የሚችል ወይም በእዉን ያለ ድርጅት ጽንሰ ሀሳብ በሚል ሊገለጽ የሚችለዉ (Real Entity Theory) ደግሞ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በተግባር ያለና የራሱን ሀሳብ እና ፈቃድ ለመያዝ የሚችል መብትና ግዴታ ያለዉ ስለሆነ ለሚፈጽማቸዉ ጥፋት አስተዳደራዊ እና ፍትሐ ብሔራዊ ኃላፊነት ሊኖርበት ይገባል የሚል ጽንሰ ሀሳብ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ መሆን አለበት የሚለዉን ሦስተኛዉን አመለካከት የሚያራምዱት በእንግሊዘኛዉ (Expressive Theory of Criminal Law) በሚል የሚታወቀዉን ጽንሰ ሀሳብ በመከተል ሲሆን የጽንሰ ሀሳቡ ማጠንጠኛም የሕግ ሰዉነት የተሰጣቸዉ ድርጅቶች ጥፋት የሚፈጽሙት የተቋቋሙበትን ኢኮኖሚያዊ ትርፍ የማግኘት ዓላማ ባልተገባ መንገድ ለማሳካት በመሆኑ በዚህ ልክ ለራሳቸዉ ጥቅም ለማግኘት ብለዉ የሚፈጽሙት የወንጀል ድርጊት በራሱ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ እንዳላቸዉ ስለሚያሳይ በሕዝብ ጥቅምና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ወንጀል ከማድረግ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ሊጠቀስ የሚችለዉ ሌላዉ ጽንስ ሀሳብ በሌላ ሰዉ ጥፋት በወንጀል ተጠያቂ የመሆን ጽንስ ሀሳብ (Theory of Vicarious Liability) ነዉ፡፡ ይህ ጽንስ ሀሳብ ከዉል ዉጭ ኃላፊነት ሕግ (Tort Law) ላይ በተዉሶ የተወሰደ ሲሆን በዚህ ጽንሰ ሀሳብ መሰረት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ማንኛዉም ሠራተኛ ወይም ኦፊሰር ድርጅቱን በሥራ ኃላፊነት የሚወክል ለድርጅቱ ተቀጣሪ (ሠራተኛ በመሆን) ችሎታዉ አስቦ ለድርጅቱ ጥቅም ብሎ አንድን የወንጀል ድርጊት ከፈጸመ ድርጅቱ በወንጀል ተጠያቂ መሆን ይኖርበታል የሚል ነዉ፡፡ ሌላዉ ይህ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት በሌላ ሰዉ ጥፋት በወንጀል

ተጠያቂ የሚያደርገዉ ጽንሰ ሀሳብ (Theory of Vicarious Liability) የድርጅቶችን ተጠያቂነት ስለሚያሰፋ የድርጅቶቹ የወንጀል ተጠያቂነት በጠባቡ ሊታይ ይገባል የሚል አቋም የሚያራምደዉ ሌላ ጽንሰ ሀሳብ (The Theory of Identification) ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሚገኝ በዘርፉ የተጻፉ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ የዚህ ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኞች የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ መሆን ያለበት ድርጅቱን የመምራት እና የድርጅቱን ፖሊሲ የማዉጣት ሚና ባላቸዉ ከፍተኛ አመራሮች ለሚፈጸም ጥፋት ብቻ እንጂ የድርጅቱን ፖሊሲ በሚፈጽሙ ተራ ሠራተኞች በሚፈጸም ጥፋት ሊሆን አይገባም የሚል አመለካከት የሚያራምዱ ናቸዉ፡፡

የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርባቸዉ ድርጅቶች (Entities) የትኞቹ ናቸዉ የሚለዉን ለመወሰን አገራት ከሦስት ዓይነት ሞዴሎች ዉስጥ አንዱን ወይም በመቀየጥ እንደሚከተሉ በዘርፉ ከተጻፉት ድርሳናት መመልከት ይቻላል፡፡ አንደኛዉ ማንኛዉንም ድርጅት (organization) በሌላ አገላለጽ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉንም ሆነ ያልተሰጠዉን (both legal-status-entities and non-legal-status-entities) ያለገደብ ተጠያቂ የሚያደርግ ሞዴል ሲሆን ሁለተኛዉ ሞዴል ደግሞ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑ ድርጅት ዓይነቶችን ለይቶ የሚዘረዝር (listed legal-status-entities and non-legal-status-entities) ሞዴል ነዉ፡፡ ሦስተኛዉ ሞዴል ደግሞ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት (legal/juristic person) ብቻ በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርግ ነዉ፡፡

ሌላዉ በሕግ ሰዉነት የተሰጣቸዉ ድርጅቶች በየትኞቹ ወንጀሎች ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል የሚለዉንም በተመለከተ አገራት የተለያዩ ዘዴዎችን የሚከተሉ ሲሆን አንዳንዶች ድርጅቶች የተፈጥሮ ሰዉ ተጠያቂ በሚሆንበት ወንጀል ሁሉ እኩል ተጠያቂ መሆን አለባቸዉ የሚለዉን ሥርዓት የሚያራምዱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በድርጅቶች የሚፈጸሙ ወንጀሎችን (corporate crimes) በሕግ ለይተዉ የመዘርዘር ሥርዓት የሚከተሉ ናቸዉ፡፡ እንዲሁም የተቀሩት ደግሞ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነዉ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል በሚል አንድን ድርጊት ወንጀል አድርጎ በሚደነገግ ሕግ ላይ በግልጽ በተደነገገባቸዉ ወንጀሎች ብቻ ነዉ የሚል ሥርዓት ያራምዳሉ፡፡

ከላይ የተገለጸዉን ጽንሰ ሀሳብና አስተምርሆ ከግንዛቤ በማስገባት የአገራችንን የሕግ አቋም ስንመለከት በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለዉ የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 ነዉ፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 በመጀመሪያዉ ፓራግራፍ ላይ እንደተመለከተዉ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት በወንጀል ሊቀጣ የሚችለዉ ደርጅት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል ተብሎ በሕግ ላይ በግልጽ ተደንግጎ ሲገኝ ብቻ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ይህም ድንጋጌ ድርጅቶች በየትኞቹ ወንጀሎች ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል? ለሚለዉ ጥያቄ የሕጋዊነት መርህ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነዉ አንድን ድርጊት ወንጀል አድርጎ በሚደነገግ ሕግ በግልጽ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል በሚል (when the criminal law expressly provides criminal liability of corporation) በደነገገ ጊዜ ብቻ ነዉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአገራችን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ተቀባይነት ያገኘዉ ጽንሰ ሀሳብ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን፤ ተጠያቂ የሚሆነዉ ደግሞ አንድን በማድረግ ወይም ባለማድረግ የሚፈጸም ተግባር የወንጀል ድርጊት አድርጎ በሚደነግገዉ ሕግ ላይ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን እና ድርጅቱ ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ የሚቀጣዉ ቅጣት ጭምር በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/2 ስር በተመለከተዉ መሰረት በግልጽ ሲደነገግ ብቻ ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ በግልጽ ካልተደነገገ የወንጀል ክስ አይቀርብበትም፤ ጥፋተኛ ተብሎም ሊቀጣ አይችልም፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34(1 እና 2) ስር የተደነገገዉን በመከተል ተደንግጓል ሊባል የሚችለዉ እንዴት ነዉ የሚለዉን ማየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህንን ለመረዳት በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ያሉትን ድንጋጌዎች አቀራረጽ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የወንጀል ሕጉ በልዩ ክፍሉ ባሉ ድንጋጌዎች የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ የሚሆንባቸዉን ወንጀሎች

የደነገገ ሲሆን ከዚህ አኳያ ሊጠቀሱ የሚችሉ ድንጋጌዎች፡- በአንቀጽ 354/2 የተደነገገዉን የተመለከትን እንደሆነ የተከለከለ ዕቃ የማስተላለፍ፣ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት የተደረገ ሕገ-ወጥ ንግድ ወይም ኮንትሮባንድ… የፈጸመዉ የሕግ ሰዉነት የተሰጠ ድርጅት የሆነ እንደሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 90 የተመለከተዉ ቅጣት ተፈጻሚ ይሆናል በሚል በግልጽ ደንግጓል፡፡ በሌሎች የሕጉ ድንጋጌዎች ላይም - በሁለተኛ ታላቅ ክፍል ልዩ ክፍል ሦስተኛ መጽሐፍ ስር በሚገኝ ርዕስ አምስት ከአንቀጽ 356 እስከ 374 የተደነገጉ ወንጀሎች በሕጉ አንቀጽ 513 ስር በተመለከተዉ መሰረት ከአንቀጽ 505 እስከ 512 የተደነገጉ ወንጀሎች፣ በሕጉ አንቀጽ 524 ስር በተደነገገዉ መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 514 እስከ 523 የተደነገጉ ወንጀሎች፣ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 530 ስር በተደነገገዉ መሰረት ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 525 እስከ 529 ድረስ የተደነገጉ ወንጀሎች፣ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 609 ስር በተደነገገዉ መሰረት ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 613 እስከ 619 ድረስ የተደነገጉ ወንጀሎች፣ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 632 ስር እንደተመለከተዉ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 626 እስከ 628 እና 631 የተደነገጉ ወንጀሎች፣ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 638 ስር እንደተመለከተዉ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 634 እስከ 637 ድረስ እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 684/6 ስር በተመሳሳይ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጀት ተጠያቂ የሚሆንባቸዉ ወንጀሎችና ቅጣታቸዉ በግልጽ ተደንግገዋል፡፡

ሌሎች የወንጀል ድርጊቶችንና ቅጣትን የሚደነግጉ ልዩ ሕግጋትን (አዋጆች) የተመለከትን እንደሆነ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 34/1 የመጀመሪያዉን ፓራግራፍ በመከተል የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ የሚሆንባቸዉን ወንጀሎች በግልጽ ደንግገዋል፡፡ የተወሰኑትን ለአብነት ለመጥቀስ ያህል በቀድሞዉ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 92/2 እና 93/2 ላይ እና ይህንን አዋጅ በተካዉ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 173 ላይ በሕጋዊ ዕቃ ከለላነት የሚፈጸም የማጭበርበር ወንጀል የሕግ ስዉነት የተሰጠዉ ድርጅት የፈጸመ እንደሆነ በዚህ ወንጀል ተጣያቂ እንደሚሆንና በድንጋጌዉ የተመለከተዉን የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 5 ላይ፣ የኮምፒዩተር ወንጀል ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 958/2008 አንቀጽ 20 ላይ እና በሰዉ የመነገድ እና ሰዉን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 18 ላይ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆንና የሚቀጣዉ ቅጣት በግልጽ የተደነገጉባቸዉ ልዩ ሕግጋትና ድንጋጌዎች ናቸዉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/4 ስር ለድርጅት የተሰጠዉ ትርጓሜ ነዉ፡፡ በዚህ ትርጓሜ መሰረት በተለይም በሕጉ የእንግሊዝኛ ቅጅ ላይ "juridical person" በሚል ከተገለጸዉ በግልጽ መረዳት እንደሚቻለዉ "ድርጅት" በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን መንግሥታዊም (የመንግሥት አስተዳደር አካላትን ሳይጨምር) ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ ወይም ሕዝባዊም ሆነ ግላዊ መዋቅር ያለዉ አካል ሲሆን ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ ለፖለቲካ፣ ለሃይማኖት ወይም ለሌላ ሕጋዊ አላማ የተቋቋመንና በመንግሥት እዉቅና ያገኘዉን ማናቸዉንም ማኅበር እንደሚያጠቃልል ተደንግጓል፡፡ ይህም በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት (legal-status-entity/juristic person) ብቻ በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርግ የሕግ ሞዴል እንደምንከተል የሚያሳይ ነዉ፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 ፓራግራፍ ሁለት ስር የተደነገገዉን የተመለከትን እንደሆነ በዚህ ድንጋጌ ላይ በተመለከተዉ መሰረት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ወንጀል አድርጓል በሚል ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ የሚችለዉ ከኃላፊዎቹ አንዱ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ-ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም ተካፋይ ሲሆኑ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት መደንገጉ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነዉ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ወይም ዉሳኔ ሰጪዎችና ፖሊሲ አዉጪዎች በሚፈጽሙት ጥፋት ብቻ ሳይሆኑ የድርጅቱ ማንኛዉም ሠራተኛ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ-ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ

ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ በሚሆንበት ወንጀል ተካፋይ ሲሆኑ በመሆኑ ሕጉ በሌላ ሰዉ ጥፋት በወንጀል ተጠያቂ የመሆን ጽንሰ ሀሳብ (Theory of Vicarious Liability) መከተሉን የሚያሳይ ነዉ፡፡

በመሆኑም በአገራችን የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር አንድ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነዉ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡ ተጠያቂነቱም በተፈጥሮ ሰዉ ሊፈጸሙ በሚችሉ ሁሉም ወንጀሎች ላይ ሳይሆን የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ የሚሆንባቸዉ ወንጀሎች ናቸዉ በሚል ከእነቅጣቱ በግልጽ ሕግ በሚደነግጋቸዉ ወንጀሎች ብቻ ነዉ፡፡ ከድርጅቱ ኃላፊዎቹ አንዱ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ - ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም አንድን የወንጀል ድርጊት ቢፈጽም እንኳን የተፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ የሚሆንበት ወንጀል ነዉ ተብሎ በግልጽ በሕግ ላይ ካልተደነገገ በሥራ ኃላፊዉ ወይም በሠራተኛዉ የወንጀል ድርጊት በመፈጸሙ ብቻ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

ከላይ እንደገለጽነዉ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ስለሚሆንበት አግባብ ለመጀመሪያ ጊዜ በአገራችን የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር የተደነገገዉ ግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ በሆነዉ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 ስር በተደነገገዉ መሰረት ነዉ ብለን እናምናለን፡፡ ይህ ከሆነ የወንጀል ሕጉ ተፈጻሚ መሆን ከመጀመሩ በፊት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ዉስጥ እንዲጠቃለል በተደረገዉ በ1994 ዓ/ም በወጣዉ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56/1 ላይ የተደነገገዉ ምንድን ነዉ የሚለዉን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ አዋጅ ክፍል 12 እና በማሻሻያዉ አዋጅ ቁጥር 609/2001 ስር የተደነገጉት አብዛኞቹ የወንጀል ጥፋቶች "በማንኛዉም ሰዉ" ወይም "በታክስ ከፋይ" ወይም "በታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኞች" የሚፈጸሙ የወንጀል ጥፋቶች እንደሆኑ የድንጋጌዎቹ ይዘት ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል በአዋጁ አንቀጽ 56 ላይ በድርጅቶች ስለሚፈጸም ጥፋት ተደንግጓል፡፡ የዚህን ድንጋጌ አቋም በግልጽ መረዳት በአሁኑ ጊዜ ተፈጻሚ እየሆነ ባለዉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/1 ስር ስለተደነገገዉ በአግባቡ ለመገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56/1 እንደሚከተለዉ ይነበባል፡- "በንዑስ አንቀጽ 3 ሥራ አሥኪያጁ ስለማይቀጣባቸዉ ሁኔታዎች የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈጸመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማናቸዉም ሰዉ በድርጅቱ የተፈጸመዉን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ የተጣለዉ ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል" የሚል ነዉ፡፡ ሆኖም በአዋጁ አንቀጽ 56/1 የተደነገገዉ ድርጅት በተጨማሪ እሴት ታክስ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ስለሚቀጣበት አግባብ ሳይሆን በድርጅት ለሚፈጸም የወንጀል ጥፋት ጥፋቱ በተፈጸመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አሥኪያጅ የሆነ ማናቸዉም ሰዉ በድርጅቱ ለተፈጸመዉ ጥፋት ተጠያቂ እንደሚሆንና በሕጉ የተደነገገዉን ቅጣት እንደሚቀጣ የሚያሳይ እንጂ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን የተደነገገበት አይደለም፡፡

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/1 ላይ የተደነገገዉም አስቀድሞ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56/1 ስር ከተደነገገዉ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡ በአንቀጽ 132/1 ስር በግልጽ እንደተመለከተዉ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ሕግ በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመዉ ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወቅት ሥራ አሥኪያጅ የሆነ ማንኛዉም ሰዉ ወንጀሉን እንደፈጸመ ተቆጥሮ በድርጅት ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ሥራ አስኪያጁ ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ ይህም የሚያሳየን በአዋጁ አንቀጽ 2/5 ስር ትርጓሜ የተሰጠዉ ድርጅት የታክስ ወንጀል ለመፈጸም እንደሚችል፣ ነገር ግን ድርጅት ለፈጸመዉ ወንጀል

ተጠያቂ ሆኖ የሚቀጣዉ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ሥራ አሥኪያጅ የሆነ ሰዉ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

ሌላዉ አዋጅ ቁጥር 285/1994ትም ከወንጀል ሕጉ ቀድሞ የወጣ እንደመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34 ላይ የተደገገዉን በተከተለ አኳኋን የሕግ ሰዉነት ስለተሰጠዉ ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት እንዲደነግግ አይጠበቅም፡፡ ነገር ግን አዋጅ ቁጥር 983/2008 የወንጀል ሕጉ ተፈጻሚ ከሆነ በኋላ የወጣ ሕግ እንደመሆኑ በመርህ ደረጃ የሕግ ሰዉነት የተሰጣቸዉ ድርጅቶች ስለሚኖራቸዉ የወንጀል ተጠያቂነት ከላይ በጠቀስነናቸዉ ልዩ ሕግጋት ላይ በተደነገዉ መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34 ስር የተደነገገዉን ጠቅላላ መርህ በመከተል የሕግ ሰዉነት ያለዉ ድርጅት ስለሚኖርበት የወንጀል ተጠያቂነት መደንገግ ይኖርበታል፡፡ አዋጅ ቁጥር 983/2008 በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34 ስር የተደነገገዉን መርህ ለመከተል የማይገደደዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 3 ስር በተደነገገዉ መሰረት ለታክስ ወንጀሎች በወንጀል ሕጉ የተደነገጉ መርሆዎች ተፈጻሚ አይሆኑም በማለት ሕግ አዉጪዉ በዚሁ አዋጅ ላይ በግልጽ ሲደነግግ ብቻ ነዉ፡፡ ነገር ግን ሕግ አዉጪዉ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 ላይ የወንጀል ሕጉ መርሆዎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ የሚፈቅድ ድንጋጌ አልደነገገም፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 983/2008 በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ አድርጓል ሊባል የሚችለዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34(1 እና 2) ስር በተደነገገዉ መሰረት በአዋጁ ምዕራፍ ሦስት የታክስ ወንጀል በሚደነግጉ ዝርዝር ድንጋጌዎች ስር የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ እንደሚሆንና ስለሚቀጣዉ ቅጣት አይነትና መጠን በግልጽ ደንግጎ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡

በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ ላይ የአዋጁ አንቀጽ 120/1ም ሆነ 132/1 ትርጉም አያስፈልገዉም የሚል ድምዳሜ ላይ የተደረሰዉ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 ላይ "ሰዉ" እና "ታክስ ከፋይ" ለሚሉ ቃላት ትርጓሜ ስለተሰጠ በዚህ መልኩ የተሰጠዉ ትርጓሜ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት የሚያካትት ስለሆነ፣ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2/4 ሕጉን መተርጎም ስለሚፈቅድ አዋጁ የወጣበትን ዓላማ በሚያሳካ አኳኋን ሕጉ ተግባራዊ ሊደረግና የአዋጁ አንቀጽ 120/1 የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ በሚያደርግ መልኩ ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል በሚሉ ምክንያቶች ነዉ፡፡ ከሕጋዊነት መርህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ድርጊት ወንጀል ሆኖ አድራጊዉን እንዲያስቀጣ በወንጀል ሕግ ወይም በሌላ አንድን ድርጊት እንደወንጀል ቆጥሮ ቅጣት በሚደነግገዉ ልዩ ሕግ ላይ ድርጊቱ እንደ ወንጀል ሊቆጠርና በወንጀል አድራጊዉ ላይ ስለሚፈጸም ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ ሊደነገግ ይገባል፡፡ ፍርድ ቤት ሕግ-ወጥነቱ በሕግ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ገድፈት እንደወንጀል ሊቆጥረዉ እና ቅጣት ሊወስን እንዲሁም በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሰላል በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት እንደወንጀል ሊቆጥረዉ አይችልም፡፡ (የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2(1-3) ይመለከቷል፡፡) በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2/4 መሰረት ለፍርድ ቤት የተሰጠዉ የመተርጎም ሥልጣን ተግባራዊ መሆን ያለበት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2(1-3) ስር የተደነገገዉን መርህ በማይሸራርፍ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ መርህ የቆመለት አንዱና ዋነኛ ዓላማም በሕግ የወንጀል ድርጊት ነዉ፤ ተጠያቂነት አስከትሎ ያስቀጣል በሚል በተገቢዉ ሕግ በይፋ ሕዝብ እንዲያዉቀዉ ያልተደረገ ድርጊት በማንኛዉም ሰዉ ቢፈጸም እንደወንጀል ተቆጥሮ እንዳይከሰስ ጥፋተኛ ተብሎም እንዳይቀጣ ጥበቃ ማድረግ በመሆኑ በጥብቅ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባዉ መርህ ነዉ፡፡

በመሰረቱ ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ የሕግ ነጥብ አከራክሮ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 69899 (በቅጽ 12 እንደታተመዉ) ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ...የንግድ ምልክት ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 41/1 "ማንኛዉም ሰዉ" በሚል አገላለጽ መደንገጉ ብቻዉን የሕግ ሰዉነት ያላቸዉን ድርጅቶች በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ ታስቦ የተደነገገ አይደለም የሚል የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ በእርግጥ ታክስ በተፈጥሮ ሰዉ ብቻ ሳይሆን በሕግ ሰዉነት በተሰጠዉ ድርጅት ጭምር የሚከፈል በመሆኑ በታክስ ሕጉ ላይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34ን በተከተለ አኳኋን በተደነገገ ጊዜ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት የታክስ

ወንጀሎችን ሊፈጽም እንደሚችል እናምናለን፡፡ ሆኖም አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34(1 እና 2) በሚያዘዉ መሰረት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ በሚያደርግ አኳኋን ባለመደንገጉ በአዋጁ አንቀጽ 120/1 "ማንኛዉም ታክስ ከፋይ..." በሚል የተደነገገዉን ከአዋጁ አንቀጽ 2(26 እና 41) ትርጓሜ አንጻር በማየት በአንቀጽ 120/1 ስር የተደነገገዉ አመልካችን ወይም የሕግ ሰዉነት ያለዉን ድርጅት በወንጀል የሚያስጠይቅ ነዉ ብሎ መተርጎም አይቻልም፡፡ በዚህ መልኩ ትርጉም መስጠት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በሰ/መ/ቁጥር 69899 ላይ የተከተለዉን የአተረጓጎም ስልት አለመከተል ስለሚሆን የሰበር ዉሳኔዎች ተገማች እንዳይሆኑ በማድረግ የሕዝብ አመኔታን ይሸረሽራል፡፡

እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 120 የተመለከተዉን ወንጀል የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተላልፎ ቢገኝ ድርጅቱ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል በሚል በግልጽ ባልተደነገገበትና ድርጅቱ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ የሚቀጣዉ ቅጣት አይነትና መጠን በግልጽ በድንጋጌዉ ላይ ባልተመለከተበት ድርጅቱን በወንጀል ተጠያቂ አድርጎ መቅጣት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2/4 ስር በተመለከተዉ መሰረት ሕግ ከመተርጎም ወሰን ያለፈ እና የሕግ ሰዉነት ከተሰጠዉ ድርጅት አንጻር ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ ያልተደነገገዉን ድርጊት በትርጉም ሰበብ ጥፋተኛ አድርጎ መቅጣትን ስለሚያስከትል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2(1 እና 2) እና 23/1 ስር የተደነገጉትን መሰረታዊ የወንጀል ሕግ መርሆዎችን የሚቃረን ይሆናል፡፡ በተጨማሪም "ማንኛዉም ሰዉ" ወይም "ማንኛዉም ግብር ከፋይ" የሚለዉን የሕጉን ትርጓሜ ብቻ በመከተል የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ በማንኛዉም በታክስ አስተዳደር አዋጁ በተደነገጉ ወንጀሎች የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ተጠያቂ እንዲሆን የሚያደርግ ዉጤት ያስከትላል፡፡ ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34 ስር የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ደርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነዉ በግልጽ ተለይተዉ በተደነገጉ ወንጀሎች ብቻ ነዉ በሚል የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት የወንጀል ተጠያቂ በተመለከተ በአገራችን የተዘረጋዉ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር እንዲፋለስ ያደርጋል፡፡

በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ ላይ ድንጋጌዉ ከአዋጁ ዓላማ አንጻር መተርጎም አለበት በሚል የተገለጸዉ በመርህ ደረጃ ሕግ ሲተረጎም ሕጉ የወጣበትን ዓላማ ከግምት ማስገባት ይገባል ከሚል የሕግ አተረጓጎም ስነ ዘዴ አንጻር ሲታይ እኛም የምንስማማበት ነዉ፡፡ ነገር ግን የሚተረጎመዉ ሕግ የወንጀል ሕግ በሆነ ጊዜ ይህ የአተረጓጎም ስነ ዘዴ የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ መርሆዎች በሚሸራርፍ መልኩ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም የሚል አቋም አለን፡፡ በታክስ የሚሰበሰብ ገቢ አገራችን የወጠነችዉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ከማፋጠን አንጻር መተኪያ የሌለዉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 የወጣበት ዓላማም ከልዩ ልዩ ታክስ የሚሰበሰቡ ገቢዎችን በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ፣ የታክስ ከፋዩን አንግልት የሚቀርፍ ሥርዓት ለመዘርጋት፣ በሕጉ ታክስ ከፋይ ማድረግ አለበት ወይም የለበትም ተብለዉ የተደነገጉት ድርጊቶች ተፈጽመዉ ሲገኙ በግልጽ አስተዳደራዊ፣ ፍትሃብሔራዊ እና የወንጀል ቅጣቶችን በመደንገግ በማስጠንቀቅ ታክስ ከፋዩን ማኅበረሰብ ወደ ሕጋዊ ሥርዓት ማስገባትና በማስጠንቀቂያዉ የማይማረዉን ታክስ ከፋይ ተገቢዉን ቅጣት በመቅጣት የታክስ አስተዳደሩን ዉጤታማነት ማረጋገጥ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ አስተዳደር አዋጁ የአስተዳደር አዋጅ እንደመሆኑ ግለሰብም ሆነ ድርጅት ታክስ ከፋዮችን ወደ ሕጋዊ ሥርዓት ማስገባት የሚቻለዉ በወንጀል ተጠያቂ አድርጎ በመቅጣት ብቻ ነዉ ብሎ የሚያምን ሕግ አለመሆኑን ከአቀራረጹ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የተከሰሰበት የአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120 የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ይህንን ድንጋጌ ተላልፎ ሲገኝ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆንና ሊቀጣ የሚችለዉም ቅጣት አይነትና መጠን ይህ ነዉ ተብሎ በግልጽ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34(1 እና 2) በሚያዘዉ መሰረት የተደነገገበት አይደለም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 132/1 ስር የተደነገገዉም በአዋጁ እንደወንጀል የተቆጠረዉን ድርጊት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ሲፈጽም በወቅቱ የድርጅቱ ሥራ አሥኪያጅ በሆነ ሰዉ

እንደተፈጸመ ተቆጥሮ ሥራ አስኪያጁ እንደሚቀጣ የሚደነግግ እንጂ በአዋጁ እንደ ወንጀል የተደነገጉ ድርጊቶችን የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ሲፈጽም ድርጅቱ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል በሚል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34(1 እና 2) የተደነገገዉን መርህ ለመተካት ታስቦ የተደነገገ አይደለም፡፡ በአዋጁ ለተሸፈኑ የታክስ ወንጀሎች የወንጀል ሕግ መርሆዎች ተፈጻሚ አይሆኑም በሚል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 3 ስር በተደነገገዉ መሰረት በአዋጁ ላይ አልተደነገገም፡፡ በአዋጁ የትርጓሜ አንቀጽ ላይ "ማንኛዉም ሰዉ" ወይም "ማንኛዉም ታክስ ከፋይ" በሚል የተደነገገዉን ትርጉም በመዉሰድ በአዋጁ ላይ እንደወንጀል ተቆጥረዉ አስቀጭነታቸዉ በተደነገገባቸዉ ድርጊቶች ሁሉ የሕግ ሰዉነት የተሰጣቸዉ ድርጅቶች ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2(2-3)፣ 23/1 እና አንቀጽ 34(1 እና 2) ስር የተደነገጉትን የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ መርሆዎች የሚቃረን ይሆናል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አቀራረጽ መሰረት የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ደረሰኝ ሳይሰጥ ግብይት የፈጸመ እንዲሆን የሚቀጣዉ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 108 በተደነገገዉ መሰረት በአስተዳደራዊ ቅጣት ብቻ ነዉ፡፡ ስለሆነም ነሐሴ 23 ቀን 2015 ዓ/ም አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ መዝገብ ላይ በተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁጥር 74237፣ በሰ/መ/ቁጥር 48850፣ 102640፣ 218957 እና በዚሁ ትእዛዝ ላይ በተጠቀሱት ሌሎች መዛግብት ላይ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ስለሚሆንበት አግባብ የተሰጠዉ ትርጉም ተለዉጦ ወይም ተሻሽሎ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነዉ ወይም ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34(1 እና 2) የተደነገገዉን መርህ በሚያሟላ አኳኋን በወንጀል ሕጉ ወይም በልዩ ሕግ ላይ የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆንና ጥፋተኛ ሲሆን ስለሚቀጣበት ቅጣት አይነትና መጠን በግልጽ ሲደነገግ ብቻ ነዉ በሚል አስገዳጅ ትርጉም ሊተካ ይገባል፡፡ በአመልካች ላይ የተጠቀሰዉ የአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን ድርጅት በወንጀል የማያስከስስ ነዉ ተብሎ ዉሳኔዉ ተሽሮ አመልካች ሊሰናበት ይገባል ብለን ስለምናምን አብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ ላይ አስቀድመዉ የተሰጡ ትርጉሞች ሊለወጡ አይገባም ተብሎ በመወሰኑ ባለመስማማታችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

## 5.2 የግብር ደረሰኝ ሐሰተኛነት የወንጀል ተጠያቂነት[107]

- ከተገኘ ገቢ የሚከፈል ግብርንና የተሰበሰበን ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ደረሰኞች ሐሰተኛ መሆናቸው ብቻ አንድን ተከሳሽ ጥፋተኛ ሊያስብለው የማይችልና ሐሰተኛ ደረሰኝ ናቸው የተባለት ደረሰኞች አፈጣጠርና ለገቢ ሰብሣቢው መስሪያ ቤት አቀራረብ ሂደት ላይ የተከሳሹን ድርሻና በሕግ የተጣለበት ግዴታ ከወንጀል ህግ መሰረታዊ መርህና የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህን በተከተለ መንገድ ሊመረመር የሚገባው ስለመሆኑ፤ (ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) ፤የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 22፣49፣ 50(1))

የሰ/መ/ቁ. 181958

ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አስፋ
ጳውሎስ ኦርሺሶ
ፀሐይ መንክር
መላኩ ካሳዬ
እስቲበል አንዱዓለም

[107]የሰ/መ/ቁ. 181958 (ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም)ቅፅ 24

አመልካች፡- አቶ ገበያው ሽቴ ጠበቃቸው፡- አቶ ብናልፈው ነጋ ቀርበዋል::

ተጠሪ፡- የሰሜን ሸዋ ዞን ገቢዎች ዐ/ህግ፡- አልቀረቡም::

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ጉዳዩ ከተገኘ ገቢ የሚከፈል ግብርንና የተሰበሰበን ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን ለገቢ ሰብሣቢው ተቋም ገቢ፣ አለማድረግ እንዲሁም ሐሰተኛ ወይም አሣሣች የክፍያ ደረሰኝ ማቅረብን በሚመለከት የቀረበ የወንጀል ክስን ይመለከታል። አመልካች ልዩ ልዩ ግብይት መፈፀሜን ያረጋግጡልኛል በሚል ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ያቀረባቸው ደረሰኞች እንዲታተሙ ፍቃድ ያልተሰጠባቸው ሲሆን በቀሪውና ለከፋይ በሚሰጠው ደረሰኝ የተፃፈው የገንዘብ መጠን የተለያዬ ነው። እንዲሁም የቀንና የቁጥር ቅደም ተከተል መዛባት ምክንያት በማድረግ መከፈል የነበረበትን ግብር አለመክፈል፣ሃሰተኛ ወይም አሣሳች ደረሰኝ ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ማቅረብ እና ከልዩ ልዩ ግብይቶች የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ክፍያ በወቅቱ አሣውቆ ገቢ አለማድረግ ሶስት የወንጀል ድርጊቶችን ፈፅሟል። በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በአንድ መቶ ሺህ ብር መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ተብሎ እንዲታረም የቀረበ ክርክርን ይመለከታል።

ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም በተፃፈ ክሱ የአሁን አመልካች ደብረ ብርሃን ከተማ በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ኪራይ የንግድ ስራ የተሰማራ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆኑን በመዘርዘር፡-

- በ1ኛ ክስ በ2005ዓ.ም የግብር ዘመን 1,409,349.95 ብር ግብር የሚሰበስብበት ገቢ አግኝቶ 485,322.49 ብር ግብር በወቅቱ መክፈል ሲገባው ባለመክፈሉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀፅ 97 የሚደነግገውን ተላልፎ ግብር አለመክፈል፡-
- በ2ኛ ክስ አመልካች በ2005ዓ.ም 1,409,349.95 ብር ዋጋ ያለው ግብይት በመፈፀሙ ከl.ህ ውስጥመክፈልየነበረበትን ተጨማሪ እሴት ታክስ አንሶ እንዲከፈል በማቀድ ከአቶ ያለው አበበ፣ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ እንዲሁም ከአቶ ተፈሪ ባንቴ ጋር በገባቸው የገልባጭ መኪና ኪራይ ውሎች ገንዘብ የከፈለ እንዲሁም ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም የተሽከርካሪ ጎማ ገዝቶ ክፍያ የፈፀመ በማስመሰል በታክስ ማስታወቂያ ወቅት 19 ሀሰተኛና የተጭበረበሩ ደረሰኞች ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ በማቅረቡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 50(3)(A) የተመለከተውን በመተላለፍ ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ሃስተኛና የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ማቅረብ፡-
- በ3ኛ ክስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነው አመልካች ከልዩ ልዩ ገቢዎች የሰበሰበውን 4517.49 ብር በሐምሌ ወር 2005ዓ.ም ስገቢ ተቋሙ አሣውቆ መክፈል ሲገባው ባለመፈፀሙ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ አለማድረግ በጥቅሉ ሶስት ወንጀሎችን ፈፅሟል የሚሉ ክሶችን አቅርቦበታል።

አመልካች ክዶ በመከራከሩ የስር ፍርድ ቤት የሆነው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ካዳመጠ በኋላ አመልካች በሁስተኛው ክስ ከተዘረዘሩት 19 ደረሰኞች መካከል ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም ተሰጥቶኛል ሲል ያቀረበው አንድ ደረሰኝ እንዲሁም ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ ተሰጥቶኛል በሚል ያቀረባቸው ስባት ደረሰኞች እውነተኛ መሆናቸው ተረጋግጧል፤ ቀሪዎቹ ከአቶ ያለው አበበ የቀረቡት ደረሰኞች በበራሪው ላይ የተፃፈው የገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ አለመፃፉን፣ አቶ ያለው አበበ ደረሰኞችን እንዲያሳትም ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ያልተሰጠው መሆኑን የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል የተዛባ መሆነ፣ እንዲሁም ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ

ተሰጥቶኛል በሚል የቀረቡት አምስት ደረሰኞች በበራሪው ላይ የተፃፈው የገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ አስመፃፉን ተፈሪ ሰንደቁ ደረሰኙን እንዲያሣትም ፈቃድ አለማግኘቱን የደረሰኝ ቁጥርና የተሰጡበት የቀን ቅደም ተከተል መዛባቱ ደረሰኞች ላይ የተከናወነው የፎረንሲክ ምርምራ አረጋግጧል፡ አመልካችም ደረስኞቹን ግለሰቦች ሰጡኝ ከሚል በስተቀር ግለሰቦች እንዲያሣትሙ ፈቃድ የተስጣቸው መሆኑንና በተሰጡት ደረሰኞች ላይ የተፃፈባቸው ገንዘብ በቀሪዎቹ ላይ ስለመፃፉ ሕጋዊ ስለመሆናቸው አላስረዳም ስለሆነም ሀሰተኛ በሆኑት አስራ አንድ ደረሰኞች መክፈል የነበረበትን 192,534.43 ብር ግብር አለመክፈሉ ሀሰተኛ ደረስኝ ማቅረቡ እንዲሁም 4517.49 ብር ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ገቢ ማድረግ ሲገባው ገቢ አለማድረጉ ተረጋግጧል በሚል በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ብሎ በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅነ እስራትና በአንድ መቶ ሽህ ብር ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት በማጣቱ ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 30ቀን 2011ዓ.ም ዕፌው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታቸው አመልካች ከአቶ ያለው አበበ፣ ከአቶ ተፈሪ በንቲ; ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ ጋር የመኪና ኪራይ ውል ስለመግባቱ የውል ሰነዶችን በማቅረብ፣ ለተጠቀሱት ሰዎች ክፍያ በመፈፀም ወጪ ያወጣ ስለመሆኑ ደረሰኞችን በማቅረብ፣ ያለው አበበና ተፈሪ በንቲ፣ከአመልካች ጋር በገቡት የመኪና ኪራይ ውል መሰረት ገንዘብ ተቀብለው ደረሰኝ ስለመስጠታቸው ለገቢ፣ ሰብሣቢው መስሪያቤት አረጋግጠው ሣለ፣ አቶ ተፈሪ ሰንደቁ የኪራይ ዋጋ መቀበሉንና ደረሰኝ መስጠቱን ሣይክድ ገንዘቡን አመልካች እንደፃፈው በገልፅም በፎረንሲክ በተደረገው ምርምራ ደረሰኙን ራሱ ዕፎ ያወጣው ስለመሆኑ በተረጋገጠበት፣ አቶ ሁሴን ኢብራሂም የተገዛውን ጎማ በሚመለከት በቀረበው አንድ ደረሰኝ ግብይት አልፈፀምኩም ቢሉም እንዲሁም ከአቶ ተፈረ ሰንደቁ የተሰጡት ሰባት ደረሰኞች በፎረንሲክ ተመርምረው እውነተኛ ደረሰኞች መሆናቸው በተረጋገጠበት ጥፋተኛ መባላቸው! አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሐሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ጥፋት የሚባለው ግብር ላለመክፈል የሌለን ፍሬ ነገር እንዳለ አስመስሎ ማቅረብን በሚመለከት ሲሆን አመልካች ደረስኞችን ያቀረባቸው በወጪ እንዲያዝላቸው ሆኖ ሣለና ደረሰኞች ያለፈቃድ መታተማቸሁ በቀሪና በበራሪው ላይ የተለያዬ መጠን ያለው ገንዘብ መፃፉ የቀን ቅድም ተከተል መዛነፉ ደረሰኞችን ሃሰተኛ ሊያስብላቸው የማይችል ሆኖ ሣለ፣ በበራሪውና በቀሪው ላይ አስተካክሎ መፃፍ የአመልካች ግዴታ ሣይሆን! ይልቁንም አመልካች ባቀረበው ማስረጃ ግብይት በመፈፀም ወጪ ማውጣቱን ባረጋገጠበት፣ አመልካች ከአቶ ሁሴን ኢብራሒም ያቀረበው ደረሰኝ ትክክለኛ በመሆኑ ተጠያቂነት የለበትም ከተባለ በኂላ በ3ኛው ክስ ጥፋኛ መባሉ በቀረቡበት ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን በመዘርዘር እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎት አመልካች ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር ግብይት መፈፀሙ በተረጋገጠበት፤ በአስራ አንዱ ደረሰኞች ላይ ተረጋገጠ የተባለው የቀንና የቁጥር ቅድም ተከተል መዛባት፣ በቀሪዎች ላይ የገንዘብ መጠን አለመፃፍ፣ ከሚመለከተው ተቋም ደረሰኞች እንዲታተሙ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆን በተለይም ደረሰኞችን ከሰጡት ሰዎች ጋር የወንጀል ተሣትፎ የነበረው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት አመልካችን በሃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆን አለመሆኑና የሶስተኛው ክስ መሰረት የሆነው ደረሰኝ በፎፈረንሲክ ምርምራ ትክክለኛ መሆነ በተረጋጠበት በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት የመወሰኑን ተገቢነት ተመርምሮ እንዲወሰን ተጠሪም የመልስ ክርክር እንዲያቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ መዝገቡ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ መስከረም 30ቀን 2011 (ፍርድ ቤቱ የአፃፃፍ ስህተት እንደሆነ ግንዛቤ ወስዶበታል) በተፃፈ መልሱ ለቀረቡበት ክሶች ምክንያት የሆኑት ደረሰኞች መካከል ስምንቱ አጠራጣሪ በሆነ የፎረንሲክ ምርምራ ውጤት ሕጋዊ ናቸው መባሉ ተገቢ አለመሆኑን፤ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ, በመሆኑ ግብይትም ሊፈፅም የሚገባው ከሌሎች ቫት ተመዝጋቢዎች ሆኖ ሣለ ከሕግ

ውጪ ከተርን ኦቨር ታክስ ተመዝጋቢዎች ጋር ግብይት ፈፅሞ በወጪ እንዲያዝለት ደረሰኝ ማቅረቡ ከመነሻው ሕገ ወጥ መሆኑን፣ ደረሰኞች እንዲታተሙ ከገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ያልተሰጠባቸው መሆኑ መረጋጡን፣ የአመልካችና ደረሰኙን የሰጡት ሰዎች የወንጀል ተሣትፎ ከጅምሩ የዐ/ሕግ ክስ መሰረት አለመሆኑን፤ የሶስተኛውን ክስ በሚመለከት አመልካች በወቅቱ ገቢ አሣውቆ ስለመክፍሉ ማረጋገጫ አለማቅረቡን ያቀረበው ደረሰኝም በ2005ዓ.ም ግብይት ስለመፈፀሙ አለመረጋገጡን በጥቅሉ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት በመወሰኑ የፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት የመልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡ከፍ ሲል የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ውሣኔ እንዲሰጥበት ለለዬው ማስቀረቢያ ነጥብ መልስ ለመስጠት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ምርመረናል፡፡

እንደሚታወቀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ)ና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 እንደሚደነግጉት የክልልና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም የዳኝነት ስልጣን በሕግ የተሠጣቸው ሌሎች አካላት የቀረበላቸውን ጉዳይ አከራክረው የመጨረሻ ውሣኔ ሲሰጡ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፃማቸው በክርክር ሂደት ሲረጋገጥ የማረም ስልጣን ለዚህ ችሎት ተሠጥቶታል፡፡ በዚህ መሰረት በያዝነው ክርክር የዚህ ችሎት ስልጣን አከራካሪ የሆነ ፍሬ ነገርን በማስረጃ ማጣራት ሣይሆን የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ክርክር መርምረው ውሳኔ ሲሰጡ የፈፀሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ካለ ማረም መሆኑን ከወዲሁ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

የወንጀል ሕግ አንድ ሰው በሕግ አድርግ ወይም እንዳታደርግ ብሎ የሚደነግግ መደረግ ያለባቸውንና መደረግ የሌለባቸውን ድርጊቶች በዝርዝር የሚያመለክትና በመደረጋቸውና ባለመደረጋቸው የተነሣ የድርጊቱን ፈፃሚዎች የሚቀጣ የቅጣቱን መጠንና ዓይነት የሚወሰን ሕግ ነው፡፡ ይህም ማለት ወንጀል ድርጊት ተፈፅሟል የሚባለው በወንጀል ሕግ የተከለከሉ ድርጊቶችን መፈፀም ወይም እንዲፈፀመ የተታዘዙ ድርቶችን አለመፈፀም ነው፡፡

ከዚህ መርህ በመነሣት ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው የሶስቱም ክሶች መነሻቸው ሀሰተኛ ወይም አሣሣች ደረሰኝ ማቅረቡ እንደሆነ የስር ፍርድ ቤቱ የውሣኔ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 50(1) ለታክሱ ባለስልጣን ሰራተኛ አንድን ነጥብ በሚመለከት የሐሰት ወይም አሳሳች ማስረጃ ያቀረበ ወይም ማስረጃው አሣሣች እንዳይሆኑ መካተት የሚገባቸውን ነገሮች ቀንሶ ያስቀረ ወንጀል እንፈጸመ የሚቆጠርበት መሆኑና በዚሁ አዋጅ በአንቀፅ50(3) (ሀ)ና(ለ) ድንጋጌ መሰረት የሐሰት መግለጫው የተሰጠው እንዲካተት የሚገባው ነገር ያልተካተተው ሆነ ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ወንጀል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅጣቱ መጠን ከፍ እንደሚል ይደነግጋል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎች ተላልፏል በሚል በአመልካች ላይ የቀረቡትን ክሶች የአመልካች ድርጊት ወንጀል መሆን ያለመመሆናቸው ሊወሰን የሚገባው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(2) የተደነገጉትን የወንጀል ማቋቋሚያ መመዘኛዎችና በአንቀፅ 58(1)(ሀ) ላይ የተደነገገውን ድርጊቱ ወንጀል ነው ለማለት ታስቦ የተፈፀመ መሆን እንደሚገባው የተደነገገውን መርህ ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል፡፡

ይህ ከሆነ ተጠሪ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ክስ ማስረዳት የሚጠበቅበት አመልካች ሃሰተኛ ደረሰኙን ማቅረቡን ብቻ ሣይሆን ሃሰተኛ ደረሰኙን በማዘጋጀት ተሳትፎ ማድረጉን ወይም ራሱ በክሱ ላይ እንደጠቀሰው አመልካች ግብር ቀንሶ እንዲከፍል እና የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ላለማድረግ በማሰብ ሃስተኛ መሆኑን እያወቀ ገቢ ማድረጉን ማስረዳት ይኖርበታል፡፡

ይህ ሆኖ ሣለ የግራቀኙን ክርክር አስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ግልባጭ ጋር በማገናዘብ ስንመረምረው ዐ/ህግ በክሱ ላይ ሃስተኛ ናቸው የሚላቸውን ደረሰኞች ለአመልካች ቆርጠው የሰጡት ሰዎች በክልለ ውስጥ ሕጋዊ ነጋዴዎች ከመሆናቸውም በላይ እነዚህ ደረሰኞች ከእነሱ የወጡ ስለመሆኑ ደረሰኙን በሰጡት ሰዎች አልተካደም፡፡ ይህም ሆኖ የስር ፍርድ ቤት ደረሰኞቹ ሀሰተኛ ናቸው አመልካችም ጥፋተኛ ነው ለሚለው መደምደሚያ ያበቁት ሶስት ምክንያቶች ናቸው፡፡ እነዚህም በተለምዶ ቀሪ እና በራሪ በሚባለው ወይም ለከፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ በአንዳንዶች ላይ ለከፋዩ በተሰጠው ላይ ተፅፎ በቀሪው ላይ ያለመፃፍ፤ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ እና ደረሰኙን የሰጡት ሰዎች ከገቢ ሰብሣቢው መስሪያ ቤት ደረሰኞችን እንዲያሣትሙ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆኑ ናቸው፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው በሕግ እንዲያደርግ (እንዲፈፅም) ወይም እንዳያደርግ(እንዳይፈፅም) በሕግ ግዴታ የተጣለበትን ተላልፎ የሚያስቀጣ ድርጊት ፈፅሞ ሲገኝ ወንጀል እንፈጸመ ታምኖበት ቅጣትም እንደሚወሰንበት ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ከላይ ለቀረቡት ደረሰኞች ሐሰተኛ መሆናቸው ብቻ አመልካችን ጥፋተኛ ሊያስብለው ስለማይችል የስር ፍርድ ቤት ሐሰተኛ ደረሰኝ ናቸው በተባሉት ደረሰኞች አፈጣጠርና ለገቢ ሰብሣቢው መስሪያቤት አቀራረብ ሂደት ላይ የአመልካችን ድርሻና በሕግ የተጣለበት ግዴታ ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) መርህ አንፃር ሊመረመር ይገባል፡፡

እነዚህ ደረሰኞች ከተጠቀሱት ነጋዴዎች ለአመልካች የተሰጡበት በመካከላቸው በነበረው የአከራይና ተከራይ ግብይት ምክንያትና አመልካች ተከራይ(ገዥ) ደረሰኙን ያወጡት ሰዎች ደግሞ አከራይ(ሻጭ) እንደነበሩ የግራቀኙ ማስረጃና የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ ይህ ከሆነ ለከፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ እንዳይኖር ማድረግ፤ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ የተፃፈውን ገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ መፃፍ፤ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ እንዳይኖር መጠንቀቅ፣ ደረሰኞች እንዲታተሙ ፈቃድ የወጣባቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ የአመልካች ግዴታ ሊሆን ይገባዋልን የሚለው የግራቀኙ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ሊመረመር ይገባዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ማንም ምክንያታዊ ሰው በኑሮ ልማድ እንደሚገነዘበውና አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 22 እንደሚደነግገው ትክክለኛ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነው ሻጭ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ የምክንያታዊ ገዥ ሃላፊነት ለከፈለው ገንዘብ ደረሰኝ እንዲሰጠው ከመጠየቅ በዘለለ ደረሰኞች ፈቃድ ወቶባቸው መታተማቸውን ወይም ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ በቀሪው ላይ መፃፍ አለመፃፉን፣ የደረሰኞች ቅድም ተከተል ስለመጠበቁ ወይም አለመጠበቁ የማረጋገጥ ግዴታ የገዥ ስለመሆነ ዐ/ሕግ በክሱ ላይ የጠቀሣቸው አዋጆች አልደነገጉም፡፡በሌላ በኩል ለክስ ምክንያት የሆኑትን ደረሰኞች በማዘጋጀት ረገድ አመልካችና ደረሰኞችን ያወጡት ሰዎች ወንጀል ለመፈፀም ስምምነት ለማድረጋቸውና አመልካችም ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ ወይም ደረሰኙን በማዘጋጀት ወይም ሐሰተኛ መሆናቸው እያወቀ ግብሩን አሣንሶ ለመክፈል በማሰብ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ዐ/ህግ አላስረዳም፡፡

ተጠሪ ካቀረባቸው ማስረጃዎች መካከል የተጠሪ ምስክር በጥቅሉ ሁሉም ደረሰኞች ሃሰተኞች መሆናቸውን የመስከረ ሲሆን ሃሰተኛ ናቸው ያለበት ምክንያት ለክሱ ምክንያት ከሆኑት 19 ደረሰኞች ውስጥ አስራ አንዱ የቀን እና የቁጥር ቅደም ተከተል የተዛነፈባቸው እንዲሁም እንዲታተሙ ፈቃድ ያልተሰጠባቸውና ለአመልካች በተሰጠው ድርሻ ገንዘብ ተፅፎ በቀሪው ላይ ባለመፃፉ ቢፃፍም ተበላልጦ መፃፉን ምክንያት በማድረግ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ሆኖም አመልካች ደረሰኞች በእጁ የገቡት ደረሰኞችን ከሰጡት ሕጋዊ ነጋዴዎች ጋር በፈፀመው ግብይት ስለመሆኑ በግራ ቀኙ ማስረጃ በተረጋገጠበት፤ በአንፃሩ ተጠሪ አመልካች ያቀረባቸውን ደረሰኞች ሐሰተኛ ስለመሆናቸው እያወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ ባልተረጋገጠበት የአመልካች ግዴታ ባልሆኑ ከላይ

በተጠቀሱት መመዘኛዎች ደረሰኞች ሕጋዊ አይደሉም በሚል ብቻ አመልካችን ጥፋተኛ ሊያደርገው የሚችል ማስረጃና ክርክር ባልቀረበበት በ1ኛ እና በ2ኛ ክሶች ስለመፈፀመ በበቂ ሁኔታ ተመስክሮበታል በሚል እንዲከላከል ብይን መስጠቱና በኂላም አልተከላከለም በሚል ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሶስተኛውን ክስ በሚመለከት የተጠሪ ክስ መሰረት የሚያደርገው ከልዩ ልዩ ግብይት የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በሐምሌ ወር 2005ዓ.ም ለገቢ ተቋሙ አሣውቆ ገቢ, ማድረግ ሲገባው ባለማድረጉ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ድንጋጌን ተላለፏል የሚል ነው፡፡ አመልካች የሰበሰብኩትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለመድረጌ የተፈጠረ ችግር ሣይሆን ልዩነቱ የተከስተው ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም ጎማ ስገዛ የከፈልኩትን ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ አቅርቤ ተጠሪ ሐሰተኛ ነው በሚል ለመያዝ ፈቃደኛ አለመሆኑ ተከትሎ የመጣ ችግር እንደሆነ ይከራከራል፡፡

በተጠሪ ገቢ ያልሆነው ገንዘብ ምንጭ አመልካች አቶ ሁሴን ኢብራሒም ጋር በነበረው የጎማ ግዥ ግብይት ነው በሚለው ክርክር ላይ ግልፅ ተቃውሞ ሣያቀርብ አመልካች ከሁሴን ኢብራሒም ጋር የጎማ ግዥ የፈፀመው በ2005 ዓ.ም ሣይሆን በ2006 ዓ.ም መሆኑን ራሱ አቶ ሁሴን ኢብራሂም አረጋግጧል ይህ ደግሞ የ2006 ደረሰኝን ለ2005 ማቅረቡ ጥፋት እንደሆነ ይከራከራል፡፡ ሆኖም በአመልካች ጠያቂነት ደረሰኙ በፎረንሲክ ሲመረመር እውነተኛ ደረሰኝ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ምርመራው የተደረገው አንድ ነጠላ ፍሬነገርን ለማረጋገጥ ታስቦ ስለመሆኑ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የአንድ ደረሰኝ በፎረምሲክ ላቦራቶር ተመርምሮ እውነተኛ ነው ከተባለ የወጣበትን ቀን ጨምሮ በደረሰኙ ላይ የተፃፉትን ፍሬ ነገሮች በሞላ የሚያጠቃልል ነው:: ስለሆነም የሶስተኛው ክስ መሰረት አመልካች ከአቶ ሁሴን ኢብራሃም የተቀበለው ደረሰኝ መሆኑ ባልተካደበት፣ ይህ ደረሰኝ በተጠሪ በኩል ሃስተኛ ነው በሚል ተቀባይነት በማጣቱ ክርክር ተደርጎበት እውነተኛ መሆኑ በተረጋገጠበት የስር ፍርድ ቤትም የምርመራውን ውጤት ውድቅ ባላደረገበት የደረሰኙ እውነተኛ መሆን የአመልካች ክርክር ተገቢ መሆኑን ባረጋገጠበት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 14912) መሰረት አመልካችን በነፃ ማሰናበት ሲገባ ጥፋተኛ ማለቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን 1ኛና 2ኛ ክሶች በሚመለከት አመልካች ከሕጋዊ ነጋዴዎች ጋር ግብይት በመፈፀሙ ለከፈለው ክፍያ ከነጋዴዎች ደረሰኝ መቀበሉን ባስረዳበት የእሱ ግዴታ ባልሆኑ መመዘኛዎች ማለትም ለክፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ፣ ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ የተፃፈውን ገንዘብ መጠን በቀሪው አለመፃፍ፣ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ መኖር፣ ደረሰኞቹ እንዲታተሙ ፈቃድ የወጣባቸው አለመሆናቸው በሚሉት መመዘኛዎች ተመዝነው ሀስተኛ ናቸው የተባሉትን ደረሰኞች ለገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት አመልካች ስለቀረበ ብቻና ደረሰኞቹ ሃሰተኛ ስለመሆናቸው እውቅና ኖሮት ስለማቅረቡ ግምት የሚያስወስዱ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በተጠሪ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገንዘብ ልዩነቱ የተፈጠረው ገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ትክክለኛውን ደረሰኝ ሀሰተኛ ነው በሚል አልይዝም በማለቱ እንደሆነ በተረጋገጠበት የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት መወሰኑ የይግባኝ ክርክሩን የመረመረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህን አለማረሙ ፍርድ ቤቶች ሊተገብሩት የሚገባውን መሰረታዊ የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0239664 በሆነው ሰኔ 28ቀን 2011ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካችን በቀረቡበት ሶስት ክሶች ጥፋተኛ ብሎ በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ አስራትና በአንድ መቶ ሺህ ብር እንዲቀጣ የወሰነው ውሳኔና ይህን ተከትሎ አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ ክርክር የመረመረው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20465 በሆነው ሐምሌ 18 ቀን 2011ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(A)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች በተጠሪ ከቀረቡበት ክሶች ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በነፃ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

ትዕዛዝ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደብረ ብርሀን ማረሚያ ቤት አመልካች በሌላ ወንጀል የማይፈለግ ከሆነ ዛሬውኑ ከእስር እንዲፈታው ታዟል፡ ይፃፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይለመስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## 6.የጉምሩክ አዋጅ

### 6.1 የጉምሩክ ህጎችን መተላለፍ የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነት[108]

- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168(1) ማንኛውም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የጉምሩክ ሕጎችን በመተላለፍ ገደብ የተደረገባቸውን ወይም የንግድ መጠን ያላቸውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመባቸው ዕቃዎችን በድብቅ ወይም ከሕጋዊ መተላለፊያ መስመሩ ውጪ ወደ አገር ካስገባ ከሀገር ካስወጣ ወይም ከሀገር ለማስወጣት ወይም ለማስገባት ከሞከረ ወይም በሕጋዊ መንገድ የወጡ እቃዎችን በሕገወጥ መንገድ መልሶ ካስገባ በድንጋጌው የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡
- ተጠሪ የተከሰሰችበት የአዋጁ አንቀጽ 168(2) ድንጋጌ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 168(1) ላይ በተመለከተው ሕገ-ወጥ መንገድ የተገኙ ዕቃዎች መሆናቸውን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ዕቃዎቹን ያጓጓዘ፤ ያከማቸ፤ የያዘ፤ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ማንኛውም ሰው በድንጋጌው የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል፤[109]

የሰ/መ/ቁ 229403

መጋቢት 29 ቀን 2015ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ
ደጀኔ አያንሳ
ብርቅነሽ እሱባለው
ሐብታሙ እርቅ ይሁን
ብርሃኑ መንግስቱ

[108]የሰ/መ/ቁ 229403 (መጋቢት 29 ቀን 2015ዓ.ም)

[109]በሰ/መ/ቁጥር 48628 (ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም)ቅፅ 11፣ በሰ/መ/ቁ 58266 (ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም)ቅፅ 11፣ በሰ/መ/ቁ 64819 (ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ.ም)ቅፅ 11፣ በሰ/መ/ቁ 64115 (ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም)ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 69602 (የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም)ቅፅ 13 ፣ በሰ/መ/ቁ. 97409 (ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ በሰ/መ/ቁ. 108550 (26/11/2009 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 163069 (ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም)ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 114043 (የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም)፣በሰ/መ/ቁ 94913 (ሕዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 211028 (ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 47935 (ሕዳር 30 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12

አመልካች፡- የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ህብስት ገ/ስላሴ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሠኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 02-04297 ጥር 19 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ የተላለፈውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ከተከሰሰችበት ክስ በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 224432 ሚያዝያ 26 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈጸመበትን የውጪ አገር ገንዘብ ይዞ መገኘት ወንጀል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ እና በስር ከ2ኛ እስከ 4ኛ ባሉት ተከሳሾች ላይ ያቀረባቸው ክሶች ሁለት ሲሆኑ 2ኛው ክስ አመልካችን ስለማይመለከት መመዝገብ አላስፈለገም፡፡

የ1ኛ ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ እና የስር ከ2ኛ እስክ 4ኛ ያሉት ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168(2) ድንጋጌን በመተላለፍ ሠኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 7፡00 ሰዓት ገደብ የተደረገበትን መጠኑ 11451 የአሜሪካ ዶላር በኢትዮጲያ ሲመነዘር ብር 399,639.9 የሆነ ተጠሪ የዶላሩ ባለቤትና ሻጭ፤ 2ኛ ተከሳሽ የዶላሩ ገዢ፤ 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ደግሞ ዶላሩን ገዢ በማፈላለግ ለሽያጭ በማቅረብ ሻጭ እና ገዢን በማገናኘት ሂደት በግብይቱ ውስጥ በመሳተፍ በጎንደር ከተማ ቀበሌ 09 ከ2ኛ ተከሳሽ ሱቅ የተያዙ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኂላ ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃ ከሰማ በኂላ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተከሳሾችን የወንጀል ደርጊቱን ስለመፈጸማቸው አልተመሰከረባቸውም በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነጻ አሰናብቶአቸዋል፡፡ ተጠሪን በሚመለከት ግን የቀረበባትን ክስ እንድትከላከል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ቃልዋን የሰጠች ሲሆን መከላከያ ማስረጃም አስቀርባ አሰምታለች፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ዶላሩን ይዛ እንደተገኘች ያልካደች ሲሆን በአመልካችም ሆነ በተጠሪ ምስክሮች ጭምር ዶላሩን ሱቅ ይዛ ሔዳ የተገኘች ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ የተጠሪ ዋና መከራከሪያ የተያዝኩት ወደ ባንክ ለመመንዘር እየሄድኩ ነው የሚል ነው፤ ዶላሩ ወደ ኢትዮጲያ ሲገባ አዲስአበባ ኤርፖርት ላይ ያልተመዘገበ እና ከጉምሩክ እውቅና ውጪ የገባ ስለመሆኑ በተጠሪ እና ዶላሩን ከእስራኤል አመጣች በተባለችው ግለሰብ ጭምር ተረጋግጧል፤ የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ አገር ዶላርን በተመለከተ መግባት የሚችለውን መጠን እና በምን ያህል ጊዜ መመንዘር እንዳለበት በመመሪያ ቁጥር 4/2008 ላይ በዝርዝር አስቀምጧል፤ በመመሪያው ከተገለጸው መጠን በላይ ወደ ሐገር ውስጥ የሚገባ ዶላር ተመዝግቦ መግባት እንዳለበት መመሪያ ይደነግጋል፤ ተጠሪ ደላሩ በሕገወጥ መንገድ እንደገባ እያወቀች ወይም ማወቅ ሲገባት ይዛ የተገኘች በመሆኑ በተከሰሰችበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ናት ብሏታል፤ ቅጣቱን በተመለከተም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት አስልቶ በአንድ ዓመት ከስምንት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 5000 የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ ሲል ወስኗል ፤ የቅጣት አፈጻጸሙን በተመለከተም ቅጣቱ ቢገደብ ተጠሪን ያስተምራል ብሎ ስላመነበት በሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ገድቦታል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርባለች፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ዶላሩ የገባው በአየር መንገድ በኩል ነው፤ 1ኛ መከላከያ ምስክር ዶላሩን ይዛ መግባቷን ብቻ ሳይሆን አየር መንገድ ውስጥ የጠየቃት አለመኖሩን አስረድታለች፤ ከዚህ አንጻር ሲታይ ዶላሩ በትክክለኛ መንገድ በቦሌ በኩል የገባ መሆኑን ያሳያል፤ የተጠሪ ሀላፊነት የተላከላትን ገንዘብ መቀበል ብቻ ሲሆን ተቀብላም ለመመንዘር ስትሄድ መያዝዋ ተረጋግጧል፤ ዶላሩ በሕጋዊ መንገድ አለመግባቱን እና ተገቢው ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን ልታውቅ የምትችልበት አግባብ አይኖርም፤ ተገቢ ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን ታውቃለች ተብሎም አይገመትም፤ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2 ይዘትም ቢሆን ገንዘቡ የገባባት መንገድ በትክክለኛ መንገድ ስለሆነ ተጠሪ ገንዘቡን ከተቀበለች በኋላ ለመመንዘር ወደ ባንክ ስትንቀሳቀስ የተያዘች በመሆኑ ሀላፊነት አለባት የሚያስብል አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ የተላለፈውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሽሮ ተጠሪን ከቀረበባት ክስ በነጻ አሰናብቷል፡፡

አመልካች በበኩሉ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባን ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ሠኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡትን ጉዳዮ ወደጎን በመተው የደረሱበት ድምዳሜ አግባብ አይደለም፤ መጠኑ 1000 ዶላር የሆነ ከውጪ የሚገባ የውጪ ሐገር ገንዘብ የማሳወቅ ግዴታ በሕጉ ተጥተሎበታል፤ ተጠሪ ገንዘቡን ከተቀበለች በኋላ ወድያውኑ ለሚመለከተው የጉምሩክ መስሪያ ቤት ያሳወቀችበት ማስረጃ አላቀረበችም፤ የተያዘው ዶላር በሕገወጥ መንገድ ወደ አገር የገባ እና የጉምሩክ ሥነ ስርዓት ያልተፈጸመበት ነው፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ ተጠሪን በነጻ በማሰናበት በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ወንጀል መፈጸሟ አልተረጋጠም በሚል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን በነጻ የማሰናበቱን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንድትሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ በቀን 04/13/2014 ዓ.ም የሰጠችው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ፍሬነገር ዶላሩን የተጠሪ 1ኛ መከላከያ ምስክር ከእስራኤል ሐገር ከሚኖረው ባለቤቴ ለልጆች ማሳደጊያ እና ቀለብ የሚሆን ልኮልኝ ከእሷ ተቀብዬ ለመመንዘር ባንክ የሄድኩ ስለመሆኑ ነው፤ ዶላሩን ይዤ መገኘቴ ብቻውን ዶላሩ ሕጋዊ መስመሩን አልተከተም ወይም ማወቅ ይገባኝ ነበር ተብሎ ግምት አያስወስድም፤ ተጠሪ በድንጋጌው የተመለከተቱ ሁኔታዎች አለመሟላታቸው ላውቅ የምችልበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም፤ ተጠሪ በቀረበው ክስ ጥፋተኛ ባልተባልኩበት ሁኔታ አዋጁን መሠረት አድርጎ ዶላሩ ሊወረስ የሚችልበት ሁኔታ የለም፤ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ወሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው የመልሰ መልስ የለም፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በክስ አቤቱታው ላይ የተገለጸው መጠኑ 11451 የአሜሪካን ዶላር በኢትዮጲያ ሲመነዘር ብር 399,639.9 የሆነ ተገቢው

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሳይፈጸምበት በኢትዮጲያ አየር መንገድ በኩል የገባ መሆኑ፣ ይህ ገንዘብ የተጠሪ ባለቤት ከእሥርኤል ሐገር ለተጠሪ የላከው መሆኑ እና ገንዘቡን ከውጪ አገር ካመጣችው ግለሰብ ለተጠሪ ሰጥታ ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ ይዛ የተገኘት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ይህንኑ ሳትክድ ዶላሩን ይጊ መገኘቴ ብቻውን ዶላሩ ሕጋዊ መስመሩን አልተከተም ወይም ማወቅ ይገባኝ ነበር ተብሎ ግምት አያስወስድም በማለት የምትከራከር ነች፡፡

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168(1) ማንኛውም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የጉምሩክ ሕጎችን በመተላፍ ገደብ የተደረገባቸውን ወይም የንግድ መጠን ያላቸውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመባቸው ዕቃዎችን በድብቅ ወይም ከሕጋዊ መተላለፊያ መስመሩ ውጪ ወደ አገር ካስገባ ከሀገር ካስወጣ ወይም ከሀገር ለማስወጣት ወይም ለማስገባት ከሞከረ ወይም በሕጋዊ መንገድ የወጡ እቃዎችን በሕገወጥ መንገድ መልሶ ካስገባ በድንጋጌው የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ የተከሰሰችበት የአዋጁ አንቀጽ 168(2) ድንጋጌ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 168(1) ላይ በተመለከተው ሕገወጥ መንገድ የተገኙ ዕቃዎች መሆናቸውን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ዕቃዎቹን ያጓጓዘ፣ ያከማቸ፣ የያዘ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ማንኛውም ሰው በድንጋጌው የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በተጠሪ እጅ የተገኘው መጠኑ 11451 የአሜሪካን ዶላር ተገቢ የሆነ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈጸምበት በቦሌ አየር መንገድ የገባ ሲሆን ይህ የገንዘብ መጠን የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 4/2008 የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞበት እንዲገባ ገደብ የተደረገበት የገንዘብ መጠን ነው፡፡ ተጠሪ ተጠቃሹ የውጪ አገር የገንዘብ መጠን ሲደርሳት ገንዘቡ ተገቢው የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተፈጽሞበት የገባ መሆኑ ማወቅ ይገባት ነበር፡፡ ተጠሪ ዶላሩን ይጊ መገኘቴ ብቻውን ሕጋዊ መስመሩን አልተከተለም ወይም ማወቅ ይገባኝ ነበር ተብሎ ግምት ሊወሰድ አይገባም በማለት ከምትከራከር በቀር ተጠቃሹ ገንዘብ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈጸመበት መሆኑን በመግለጽ አልተከራከረችም ወይም ይህን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበችም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ተገቢ የሆነ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሳይፈጸምበት ወደ ሐገር ውስጥ የገባ መጠኑ 11451 የአሜሪካን ዶላር ይዛ የተገኘች በመሆኑ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168(2) መሠረት ጥፋተኛ ልትባል ይገባታል፡፡ በመሆኑም የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባቸው ዶላሩ በሕጋዊ መንገድ አለመግባቱን እና ተገቢው ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን ልታውቅ የምትችልበት አግባብ አይኖርም፣ ተገቢወ የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን ታውቃለች ተብሎም አይገመትም በማለት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ የተላለፈውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ከተከሰሰችበት ክስ በነጻ በማሰናበት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 02-04297 ጥር 19 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 224432 ሚያዝያ 26 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡

2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 02-34098 ሠኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም በተጠሪ ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሠኔ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ያስተላለፈው የቅጣት ውሳኔ ጸንቷል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የሃሳብ ልዩነት

ስሜ በተራ ቁጥር አራት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ተጠሪ የተከሰሰችው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2 የተመለከተውን በመተላለፍ ገደብ የተደረገበትን መጠኑ 11451 የሆነ የአሜሪካን ዶላር ይዛ የተገኘች ስለሆነ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽማለች በማለት ነው፡፡ በወንጀል ሕግ ቁጥር 23(2) መሠረት ወንጀል አድራጊ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ የወንጀሉ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር፣ የሃሳብ ክፍሉ ተሟልተው መገኘታቸውን ዐቃቤ ሕግ ሲያስረዳ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ሊባል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2 መሠረት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበትን ዕቃ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የያዘ ሰው በወንጀል እንደሚቀጣ ተመልክቷል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው ማስረጃ ተጠሪ የያዘችው ዶላር በሌላ ግለሰብ በአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት የገባ እና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት/ኤርፖርት ላይ ያልተመዘገበ ዶላር ስለመሆኑ፣ ገንዘቡን ይዘውት የገቡት ግለሰብ ለተጠሪ ያስተላለፉና ተጠሪ ከእነገንዘቡ ጎንደር ከተማ መያዛቸው ተረጋግጧል፡፡ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2 መሠረት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበትን ዕቃ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው /ሠረዝ የተጨመረበት/ የሚለው የወንጀል ፈጻሚው የሃሳብ ክፍል መረጋገጥ እንዳለበት ያስረዳል፡፡ የሃሳብ ክፍሉን ማስረዳት ያለበት ደግሞ ከሳሽ የሆነው አመልካች ነው፡፡ በሥር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደተመለከተው ተጠሪ ገንዘቡን ተቀብላ ልትመነዝር ስትሄድ መያዟን፣ ዶላሩ ተገቢው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን ልታውቅ የምትችልበት አግባብ ስለመኖሩ ዐቃቤ ሕግ አለማስረዳቱን እና ልታውቅ ትችላለች ተብሎ ግምት ሊወሰድ እንደማይችል አስፍሯል፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር የተጠሪ የሀሳብ ክፍል አለመረጋገጡን በመጥቀስ ከክሱ በነጻ ማሰናበቱ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 አግባብ በሰበር ችሎት ደረጃ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ የሚታረም አይደለም፡፡ በአብላጫው ውሳኔ የተመለከተው ተጠሪ ዶላሩ ተገቢው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ስለመሆኑ ማወቅ ይገባት ነበር ያለው የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት ያላደረገና እንዴት ማወቅ ትችል እንደነበርም በግልጽ ያላመላከተ፣ የሃሳብ ክፍል የማስረዳት ኃላፊነት የዐቃቤ ሕግ መሆኑን ታሳቢ ያላደረገ ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

## 6.2 የጉምሩክ አዋጅ ሲሻሻል ለተከሳሽ የተሻለው ተፈጻሚ የሚሆንበት ሁኔታ[110]

- አንድ ተከሳሽ የጉምሩክ አዋጅን በመተላለፍ በፈፀመው ድርጊት ጥፋቱ የመጨረሻ ውሳኔ እስከላገኘ ድረስ ሥራ ላይ ከነበረው የጉምሩክ አዋጅ ይልቅ አዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ለተከሳሽ ቅጣትን የሚያቀል በሚሆን ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ የተሻለው ሕግ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ፤ (የኢፌድሪ ህገመንግስት አንቀጽ 22 /2/ ፣የወ/ህ/ቁ/ 6 የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001፣ አዲሱ የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007)

የሰ/መ/ቁጥር 112032

ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጠታ

አመልካች- 1ኛ የኑስ አህመድ

2ኛ. ግዛቸው አየለ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓቃቤ ህግ ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

### ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በቤንሻንጉል ጉምዝ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት ነው፡፡ አመልካቾች ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ መሰረታዊ ይዘቱ፡- አመልካቾች ህጋዊ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር በግለሰብ መያዝም ሆነ ማዘዋወር የተከለከለ በቁጥር 903 /ዘጠኝ መቶ ሶስት / ህገ ወጥ የከሳሽ ጥፋት በሁለት ማዳበሪያዎች ቋጥረው በጉዞ ሻንጣ ውስጥ በመክተት ንብረትነቷ የ2ኛ አመልካች የሆነችው የታርጋ ቁጥር ኮድ 2-0705 ቤጉ በሆነች የሞተር ሳይክል በመጫን ከአል መሃል አቅጣጫ ወደ መንጉሻ አቅጣጫ በማጓጓዝ ላይ ሳሉ በቀን 03/11/2006 ዓ/ም ከቀኑ በ11፡30 አካባቢ ማንኩሻ

---

[110] የሰ/መ/ቁጥር 112032 (ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ/ም) ቅፅ 18

ላይ እጅ ከፍንጅ በመያዛቸው 1ኛ ተከሳሽ /አመልካች/ የህገ ወጥ ዕቃ ባለቤት 2ኛ አመልካች የሞተር ሳይክሉ አሽከርካሪ በመሆን በፈጸሙት ህገ ወጥ ዕቃ መሆኑን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት የኮንትሮባንድ ወንጀል የወ/ህ/ቁ/32/1/ሀ/ እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የተመለከተውን ወንጀል ተላልፏል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ፍርድ ቤት ቀርበው የተጠሪ ክስ እንዲደርሳቸው ተደርጎ ስለጉዳዩ እምነት ክህደት ተጠይቀው 1ኛ አመልካች እንደ ተጠሪ /ዓቃቤ ህግ/ ክስ አቀራረብ ማመኑ በማስመዝገብ ጥፋተኛ ነኝ ያለ ሲሆን 2ኛ አመልካች መካዱ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው ተሰምቷል፡፡ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው በሰጡት የምስክርነት ቃል የ1ኛ አመልካች መሆኑን የተረጋገጠው 903 ጥይት በ2ኛ አመልካችም ሞተር ሳይክል ተጭኖ ሲመጣ ኬላ ላይ መያዙን አስረድቷል፡፡ 2ኛ አመልካች እንዲከላከል ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም የመከላኪያ ማስረጃ እንደ ሌለው በመግለጽ ፍ/ቤቱ በቀረበው ማስረጃ እንዲሁም 1ኛ አመልካች ቀድሞ በሰጠው የእምነት ቃል መሰረት በማድረግ ሁለቱም አመልካቾች በተከሰሱበት የህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት መዝግበዋል፡፡ በተጠሪ /የዐቃቤ ህግ/ በኩል የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ ሆኖ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በእርከን 28 ስር ቅጣት እንዲወሰን፤ መቀጮም እንዲወሰን፤ ንብረቱ እንዲወርስ ጠይቋል፡፡ አመልካቾቹም የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች መሆናቸው ግምት ውስጥ እንዲገባ አመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የወንጀል ድርጊቱ በሀገሪቱና በህዝብ ደህንነት ላይ አደጋ የሚጥል ስለመሆኑ ድርጊቱም ሆን ተብሎ የተፈጸመ በመሆኑ በከባድ ደረጃ መድቦታል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ ሆን ተብሎ መፈጸሙ፤ አመልካቾች ድርጊቱን በስምምነት መፈጸማቸው ሁለት ማክበጃ ምክንያት እንደሆነ፤ በአመልካቾች በኩል 1ኛ የዘወትር ጸባያቸው መልካም መሆን፤ 2ኛ ድርጊቱ የፈጸሙት ከህግ እውቀት ማነስ መሆኑ 1ኛ አመልካች የወንጀል ድርጊቱ ማመኑ 3ኛ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በቅጣት ማቅለያነት ተይዞላቸዋል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙበት ወንጀል ከ7 ዓመት እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና የወንጀል ድርጊቱም በከባድ ደረጃ በመመደቡ የቅጣቱ መነሻ እና መድረሻ ለአራት እኩል ሲከፈል ከ11 ዓመት -13 ዓመት ጽኑ እስራት ባለው ፍቅድ ስልጣን በማካተት የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 29 እንደሆነ በመለየት ሁለት ማክበጃዎች በመውሰድ እርከን 31 የወደቀ ሲሆን በአመልካቾች በኩል እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ማቅለያዎች የተያዘላቸው በመሆኑ በእርከን 28 ከተደነገገው ቅጣት 1ኛ አመልካች 10 ዓመት 2ኛ አመልካች 9 ዓመት ጽኑ እስራት፤ እንዲሁም በመቀጮ ረገድ የወ/ህ/ቁ/ 90/2/ መሰረት በማድረግ እያንዳንዳቸው 6670 ብር እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በኤግዚቢትነት የተያዘው ጥይት እንዲሁም የወንጀል መፈጸሚያ የተባለው ሞተር ሳይክል ለመንግስት ውርስ ይሁን በማለት አዟል፡፡

አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ በሰበር እንዲመረመር በመቅረቡ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካቾች የስር ፍ/ቤት ወንጀሉ በከባድ ደረጃ መመደቡ እና የቅጣት ማቅለያዎች አያያዝ ላይ የፈጸመው ስህተት እንዲታረምላቸው ሲጠይቁ፤ ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት የወንጀል ድርጊት አፈፃጸም መሰረት በማድረግ በከባድ ደረጃ መድቦ ቅጣት መወሰኑ በአግባቡ ነው የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ጭብጦች 1ኛ አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ነው ወይስ በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ 2ኛ የስር ፍርድ ቤቶች የወንጀል ድርጊቱ ከባድ

በማለት መመደባቸው በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? 3ኛ በስር ፍርድ ቤት እንደ ቅጣት ማክበጃ የተወሰዱ ነጥቦች የህግ መሰረት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚሉ ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

ከስር የክርክር ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካቾች 1ኛ አመልካች ገደብ የተደረገበት /ህገ ወጥ/ ጥይት ባለቤት፤ 2ኛ አመልካች ንብረቱ የጫነችው ሞተር ሳይክል ባለቤትና ሹፌር በመሆን በ03/11/2006 ዓ/ም ከቀኑ 11:30 ሰዓት በመንኩሻ ከተማ መግቢያ እጅ ከፍንጅ እንደተያዙ፤ 1ኛ አመልካች ሙሉ በሙሉ ማመኑ፤ 2ኛ አመልካችም የዐ/ህግ ክስና ማስረጃ አለማስተባበሉን የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣኑ ከድምዳሜ ላይ የደረሰ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንደተቀበለው ነው፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ ምዘና ስርዓት እንዳለ የሚቀበለው ነው፡፡ ምክንያቱም ችሎቱ በህግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ማረም ስለመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ይዘን ከላይ የተመለከቱት ጭብጦች ከህግ አንጻር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የመጀመሪያው ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙት የኮንትሮባንድ ወንጀል በመፈጸም ነው፡፡ ይህ ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 622/ 2001 አንቀጽ 91/2/ ስር የተመለከተ ሲሆን የሚያስቀጣው በእቃዎቹ ላይ ሊከፍል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር የሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከ7 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ይህንን መሰረት በማድረግ 1ኛ አመልካች በ10 አመት 2ኛ አመልካች በ9 አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 ተሽሮ በአዋጅ ቁጥር 859/2007 ተተክቷል፡፡ የአመልካቾች የክስ ሂደት እስከ ሰበር ደረጃ ደርሶ ሳይጠናቀቅ አዲስ አዋጅ የወጣ ሲሆን በዚህ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ መስረት የኮንትሮ ባንድ ወንጀል የፈጸመው ግለሰብ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና በብር 50 ሺህ በማያንስና ከብር 100,000 የማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል፡፡ በተሻረው እና በአዲሱ አዋጅ በአመልካቾች ላይ በሚጣለው እስራት እና መቀጮ መሰረታዊ ልዩነት እንዳለው ከድንጋጌዎቹ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ወንጀሉ ሲፈጸም ስራ ላይ ከነበረው ህግ ይልቅ የኋላኛው /አዲስ/ ህግ ቅጣት የሚያቃልለት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ /አመልካቾች/ የተሻለው ህግ ተፈፃሚ እንደሚያደርግ ከወ/ህ/ቁ/ 6 እና ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 /2/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የተቀጡት በነባሩ /የቀደም/ አዋጅ ከመሆኑ አንፃር በቅጣት ረገድ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው አዋጅ ቁጥር 859/2007 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ ስር ነው ብለናል፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ፡- የስር ፍ/ቤት የግራቀኙ የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ የወንጀል ድርጊቱ ክብደትና አፈፃጸም መሰረት በማድረግ ቀላል /ዝቅተኛ/ ተብሎ እንዲመደብ ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ዓቃቤ ህግ እንዳለው በመካከለኛ ደረጃ ሊመደብ እንደሚገባ ተከራክሯል፡፡ በመሰረቱ ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎች የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት መነሻ እርከን በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 19 ስር በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት እንዲሁም ፍ/ቤቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19/5/ የተመለከቱት መመዘኛዎች ብቻ ሳይታጠር ሌሎች መስፈርቶች ተጠቅሞ የወንጀሉ ደረጃ እንደሚመደብ በአንቀጽ 19/6/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የወንጀሉ አይነትና ክብደት አፈፃጸም፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ መዝኖ ከባድ ነው ማለቱ የሚነቅፍ ሆኖ አልተገኘም ፡፡ አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

3ኛ ጭብጥ በተመለከተ ፡- የስር ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወሰን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከግራ ቀኙ የመዘገበ ሲሆን ዐ/ህግ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ እንዲሆን ከመጠየቅ ውጭ ፍ/ቤቱ እንደ ማክበጃ

የወሰዳቸው 1ኛ የወንጀል ድርጊቱ ሆነ ተብሎ መፈጸሙ፤ 2ኛ የወንጀል ድርጊቱ በህብረት ስምምነት የተፈጸመ ነው በማለት የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/1/ሀ/ እና /መ/ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካቾች ጥፋተኞች የተሰኙበት አዋጅ ቁጥር 168/2/ ስር እንደተመለከተው ድርጊቱ የተፈጸመው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው በማለት የተደነገገ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/1/ሀ/ በመጥቀስ እንደማክበጃ መውሰዱ የድንጋጌው መሰረታዊ ይዘት ያላገናዘበ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት የወንጀል ድርጊቱ በስምምነት የተፈጸመ ነው በሚል እንደ ማክበጃ የወሰደው ቢሆንም በወንጀል ህግ አንቀጽ 37/1/ እና 84/1/መ/ እንደተመለከተው ወንጀል ለመስራት አስቀድመው በመስማማት /Prior meeting of mind/ የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈጸማቸው የሚያሳይ ሳይሆን 1ኛ አመልካች የህገ ወጥ ዕቃ ባለቤት 2ኛ አመልካች ደግሞ የሞተር ሳይክል ባለቤት በመሆን የኮንትሮባንድ ዕቃው መጫኑን ከመረጋገጡ ውጭ ወንጀሉን ከመጀመሪያው አቅደው፤ ጊዜ እና ሁኔታ አመቻችተው ስለመፈጸማቸው በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ እንደ ህጉ አነጋገር ቅጣት የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሳይኖሩ ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መውሰዱ የህግ መሰረት የለውም ብለናል፡፡

በመጨረሻ መታየት ያለበት ጉዳይ ቅጣት ነው፡፡ በተጠሪ በኩል በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማክበጃ አልቀረበም፡፡ በአመልካቾች በኩል ሶስት ሶስት የቅጣት ማቅለያዎች ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙበት አዋጅ ቁጥር 859/2007/ አንቀጽ 168/2/ 3-5 ዓመት ጽኑ እስራት በገንዘብ ረገድ ደግሞ ከ50,000-100,000 ብር የሚያስቀጣ ነው፡፡ የወንጀሉ ደረጃ ከባድ የተባለ በመሆኑ የቅጣት መነሻና መድረሻ ለአራት እኩል ሲከፈል የከባድ ወንጀል ከ4 ዓመት እስከ 4 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 26/2/ሐ/ መሰረት መነሻ ቅጣት በሁለት እርከኖች ስር የሚወድቅ ከሆነ ዝቅ ብሎ ያለው የሚያዝ በመሆኑ በአንቀጽ 19/1/ በመመልከቱ በእርከን 18 ስር ይወድቃል፡፡ ፍ/ቤቱ በተሰጠው ፍቃድ ስልጣን መነሻ ቅጣቱ 4 ዓመት ጽኑ እስራት በመያዝ የቅጣት ማቅለያዎች ተመልክተናል፡፡ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅሊያ አንድ እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ ቅጣቱ በሶስት እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ በእርከን 15 ይካተታል፡፡ መቀጮ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የወ/ህ/ቁ/90/2/ መሰረት በማድረግ እያንዳንዳቸው ብር 6670 እንዲቀጡ ወስነናል፡፡ ይህ ችሎትም አዲሱ አዋጅ በዚህ ረገድ አመልካቾች የማይጠቀም በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የወሰነው መቀጮ እንዳለ ተቀብሎታል፡፡

ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ህጉ ዓላማ ግብ የሚያሳካ መሆን እንዳለበት በወንጀል ህግ አንቀጽ 1 እና 87 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካቾች የተፈጸመው ወንጀል ክብደት በህ/ሰብ/ ሊያደርስ የሚችለው አደጋ በአንድ በኩል፤ የአመልካቾች የመታረም ዕድል በሌላ በኩል ግምት ውስጥ በማስገባት አመልካቾች የሚያረምና የሚያስተምር እንዲሁም መሰል ወንጀል ፈፃሚዎች የሚያስጠነቅቅ ነው ብለን ያመንበት በእርከን 15 በተመለከተው ፍቃድ ስልጣን ስር በመሆን እያንዳንዳቸው 2 አመት ከ9 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ በመለየት እና ሁለቱ ፍርድ ቤት የቅጣት ማክበጃዎች አወሳሰድ ላይ የፈጸሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የስር መተከል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 10407 በ28/11/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድና ቅጣት፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/05758 በ06/05/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 195/2/ለ/2/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በአዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168 /2/ ስር ነው በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካቾች በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ካለ በእስራት ቅጣቱ የሚካተት ሆኖ እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ እያንዳንዳቸው በ2 አመት ከ9 ወር /ሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር/ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡ አመልካቾች የሚገኙበት ማረሚያ ቤት በተሻሻለው የእስራት ቅጣት መሰረት ያስፈጽሙ ብለናል፡፡ የእስራት ቅጣቱ መሻሻሉ አመልካቾች ባሉበት ማረሚያ ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

4. በስር ፍ/ቤት የተወሰነው መቀጮ እና የንብረት ውርስ የተመለከተ የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 6.3 የተሽከርካሪ መለያ መረጃዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ መቀየር የወንጀል ተጠያቂነት[111]

- ማንኛውም ሰው አግባብነት ካለው አካል ፍቃድ ባላገኘበት ሁኔታ የተሽከርካሪውን የሞተር፣ የሻንሲ ቁጥር እና መሠል መረጃዎችን የመቀየር ተግባር የፈጸመ ከሆነ አደራጎቱ የተከለከለና በወንጀል ህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣
- አንድ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ መግባቱ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ የጉምሩክ አዋጅ በሚደነግገዉ አግባብ መኪናዉ በመንግስት ከመወረስ ሊድን የሚችልበት ሁኔታ ስላለመኖሩ፤ (የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 104/3//ሀ/፤ ስለተሽከርካሪዎች መለያ፤መመርመሪያ እና መመዝገቢያ የወጣ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 42/5/እና 48/2//ሐ/)

የሰ/መ/ቁ 122595

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የገ/ጉ/ባለስልጣን ዓ/ህግ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ አቶ ፋሲል ጥላሁን

2ኛ አቶ ካሊድ ሳቢት

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የኮንትሮባንድ ወንጀልን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 10870 በ30/3/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት

[111] የሰ/መ/ቁ 122595 (መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም)ቅፅ 22

የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ 1ኛ ና 2ኛ ተከሳሽ ሆነው ሲከራከሩ የነበር ሲሆን፣ ከሳሽ ባቀረበዉ 1ኛ ክስ፡-በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን በመተላለፍ ተከሳሾች እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት ምንም ዓይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና በሞዴል 270 በቁጥር 876593 ተመዝግቦ ወደ መንግስት መጋዘን የገባው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-020775 ሐረር ሚኒባስ የሆነ ተሽከርካሪ ቀረጥ ተከፍሎበት የገባ መኪና ለማስመሰል የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና ሞተር ቁጥሩ 5L21455255 ከሌላ መኪና ተቆርጦ የተለጠፈውን በቀን 10/08/05 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 አከባቢ በፌዴራል ፖሊስ አካላት ክትትል በሃረር ከተማ ቀበሌ 14 በመያዙ 1ኛ ተከሳሽ የህገወጥ መኪና ባለቤት እና 2ኛ ተከሳሽ ለህገወጥ መኪናው የ1ኛ ተከሳሽ ወኪል ሆነው ህገወጥ እቃ ይዘው በመገኘታቸው ተከሷል፡፡ 2ኛ ክስ በ2ኛ ና 3ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ሲሆን የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ በመተላለፍ ተከሳሾች እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው የካቲት 30 ቀን 2005 ዓ/ም ምንም አይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና ከላይ በ1ኛ ክስ ላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ በ2ኛ ተከሳሽ ወኪልነት ለ3ኛ ተከሳሽ የሸጠለት በመሆኑ ተከሳሾች የኮንትሮባንድ እቃ የተገበያዩ በመሆናቸው በኮንትሮባንድ ወንጀል ተከሷል፣ 3ኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ የተመለከተ ሲሆን የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ ተከሳሽ በ1ኛ ክስ ለተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ ካስገባ በኋላ ተገቢዉን ቀረጥና ታክስ ለመንግስት እንዳይከፈል ለማድረግ በማሰብ በፋጢማ መሃመድ ያሲን ስም ተመዝግቦ በህጋዊ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገባውን ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 በመጠቀም በራሱ ስም ሊብሬ አውጥቶ ሲገለገልበት በቀን 10/08/05 ዓ/ም በቁጥጥር ስር በመዋሉ ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ቀርበው ክሱ ደርሷቸው ተቃውሞ እንደሌላቸው ገልፀው፣ በሰጡት የእምነት ክህደት ቃል ደርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር ተከሳሾች በቀረበባቸው ሁሉም ክሶች እንዲከላከሉ ባዘዘዉ መሰረት ተከሳሾች የፅሁፍ ማስረጃና የሰዉ መከላከያ ምስክሮችንም አቅርበው አሰምቷል፡፡ በመቀጠል ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች እና የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃዎችን በሕጉ አግባብ ከመዘነ በኂላ በሰጠዉ ዉሳኔ በክስ የተመለከተዉ ተሽከርካሪ በሕገ ወጥ መንገድ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈጸምበት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ከዉጭ አገር ወደ አገር ዉስጥ መግባቱ እና ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት እንደተከፈለ በማስመሰል ሰነድ የተዘጋጀ መሆኑም አልተረጋገጠም ተከሳሾች በሚገባ ተከላክለዋል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ18/05/2008 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ተጠሪዎች በቀረበባቸው ክስ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና የሞተር ቁጥር 5L21455255 የሆነ ተሽከርካሪ እነዚህ ቁጥሮች ለተሽከርካሪው በፋብሪካ የተሰጡት ቁጥሮች ሳይሆኑ በህጋዊ መንገድ በዲክለራሲዮን ቁጥር C-1828/2010 በፋጡማ መሃመድ ያሲን ስም ወደ ሃገር ውስጥ የገባው ህጋዊ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 ሲሆን ለሌላ መኪና ተቆርጦ የተመታ መሆኑ ለተያዘው መኪና እንደ ሻንሲ ቁጥር አገልግሏል ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ተሽከርካሪዎች ሻንሲና ሞተር ቁጥር ወደ ሃሰት ተለውጧል የሰሌዳ ቁጥር ከኮድ 3-17811 ኦሮ ወደ ሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-02075 ሐረ. ሲቀየር አካላዊ ሻንሲ ቁጥርና ሞተር ቁጥሩ ከሰነዱ ጋር አልተመሳከረም ይህ ስለመሆኑ በቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የሥር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104 /3፣ ሀ/ለ/ መኪናዉ እንዲወረስ ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸው ይህንን ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት

የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪዎች ቀርበው በፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው አመልካች የወንጀሉን ድርጊት ተጠሪዎች ፈጽሟል በሚል ያቀረበው ክስ ዋናው ድርጊት 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው ውክልናን መሠረት በማድረግ እያወቁ ወይም ማወቅ እየተገባቸው በክሱ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊች በመተባበር የፈፀሙ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዛፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2/ በግልጽ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ ማሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀጽ 24፣57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በቀረበው ክስ ላይ የተገለፀው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ በህጋዊ መንገድ በዲክለራሲዮን ቁጥር C-1828/2010 በፋጡማ መሃመድ ያሲን ስም ወደ ሃገር ውስጥ የገባው ህጋዊ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 ሲሆን ይህ አሁን በቁጥጥር ስር ከዋለው መኪና ተቆርጦ የተመታ ነው በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የባለሞያ ማስረጃ እንደተገለፀው በሰሌዳ ቁጥር 3-02075 ሐረ የሆነ ሚኒባስ ተሽከርካሪ ላይ የተገኘው መረጃ በተሽከርካሪው ጋቢና በር ስር (በተሳፋሪ በኩል ) የተገኘው የቻንሲ ቁጥር ሆን ተብሎ ለማጭበርበር ተቆርጦ በሌላ የተቀየረ መሆኑ በግልፅ ማረጋገጡ ተለጥፎ የተገኘው የቻንሲ ቁጥር LH172-1039214 መሆኑ እንዲሁም በተሽከርካሪው ሞተር ላይ የተገኘው የሞተር ቁጥር መጀመሪያ በነበረው ቁጥር ላይ በድጋሚ የተመታ መሆኑ በሞተር ላይ የተገኘው ቁጥር 5L-21455255 ስለ ተሽከርካሪው መረጃ የሚሰጥ ፕሌት (ስለ መኪናው ቀለም ፤ሞዴል፣የምርት ዘመን ፣የሞተር ጉልበት ) በሌላ መቀየሩን በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የመኪና ሞተር እና የሻንሺ ቁጥር አስመስሎ የተመታ እና መረጃ የሚሰጥ ፕሌትም የተቀየረ ሲሆን አሁን በአካል የተመረመረው ተሽከርካሪ ግን ከላይ የተገለፀው ከሌላ መኪና የተመታ መሆኑ በባለሙያ በመመርመር ተረጋግጧል የሚል በመሆኑ ተጠቃሹ አካል ከጻፋቸው ደብዳቤዎች ይዘት የመኪናው ሞተር እና ሻንሲ ቁጥር ተመሳስሎ የተሰራ እና የተመታ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለሆነም እነዚህ የሻንሲ ቁጥር መለወጥ እና የሞተር ቁጥር መምታት፤ አድራጎቶች ተጠሪዎች ሆነ ብለው ወይም ማወቅ እየተገባቸው ድርጊቱን የፈጸሙትና ውጤቱንም የራሳቸው ያደረጉ መሆኑንን የሚያስገነዝብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለተሽከርካሪዎች መለያ፤መመርመሪያ እና መመዝገቢያ የወጣው አዋጅ ቁጥር 681/2002 ቁጥር 7/1 (ለ) እና (ሐ) የተሽከርካሪን ዝርዝር መግለጫ ለመመዝገብ እና የባለንብረት መታወቂያ ለመስጠት የሞተር ቁጥሩ እና የሻንሲ ቁጥር ሊመዘገብ እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ የአዋጁ ቁጥር 42/5 እና 48/2/ሐ ማንኛውም ሰው አግባብነት ያለው አካል ሳይፈቅድ የተሽከርካሪውን የሞተር ቁጥር የሻንሲ ቁጥር እና መሰል መረጃዎች መቀየር እንደማይቻል እና በወንጀል እንደሚያስጠይቅ ይደነግጋል፡፡

በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የተሽከርካሪው ሞተር ቁጥር እና ሻንሲ ቁጥር የተመታ እና ተመሣሥሎ የተሰራ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬነገር ከመሆኑም በላይ ተጠሪ የመኪናው ሞተር ቁጥር እና ሻንሲ ቁጥር የተመታው አግባብነት ያለው አካል ፈቅዶላቸው መሆኑን መኪናው በጨረታ

ሲገዙትም አሁን ባለበት ሁኔታ የሚመለከተው አካል አውቆት ስለመሆኑ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ፈጽሟቸዋል በማለት በማስረጃ ያረጋገጣቸው ፍሬ ነገሮች ሁለቱም ተጠሪዎች የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን በመተላለፍ እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት ምንም ዓይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና በሞዴል 270 በቁጥር 876593 ተመዝግቦ ወደ መንግስት መጋዘን የገባው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-020775 ሐረር ሚኒባስ የሆነ ተሽከርካሪ ቀረጥ ተከፍሎበት የገባ መኪና ለማስመሰል የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና ሞተር ቁጥሩ 5L21455255 ከሌላ መኪና ተቆርጦ የተለጠፈውን በቀን 10/08/05 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 አከባቢ ሲገለገሉ በፌዴራል ፖሊስ አካላት ክትትል በሃረር ከተማ ቀበሌ 14 በመያዙ 1ኛ ተከሳሽ የህገወጥ መኪና ባለቤት እና 2ኛ ተከሳሽ ለህገወጥ መኪናው የ1ኛ ተከሳሽ መኪል ሆነው ህገወጥ እቃ ይዘው በመገኘታቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን የኮንትሮባንደ ወንጀል የፈፀሙ መሆኑን የተረጋገጠበት በመሆኑ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡ ሁለተኛው ክስም በተመለከተ ፣ 2ኛ ተጠሪ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ በመተላለፍ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ምንም አይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና ከላይ በ1ኛ ክስ ላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ ሚያዝያ ወር 2005 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥር ከኮድ 3-17811 ተሽከርካሪ እንዲያስተዳድር የተሰጠውን ውክልና መሰረት በማድረግ ለ3ኛ ተከሳሽ የሸጠለት በመሆኑ ተከሳሾች የኮንትሮባንድ እቃ የተገበያየ መሆኑ በኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጧል ፣እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ ተከሳሽ በ1ኛ ክስ ለተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ ካስገባ በኂላ ተገቢዉን ቀረጥና ታክስ ለመንግስት እንዳይከፈል ለማድረግ በማሰብ በፋጢማ መሃመድ ያሲን ስም ተመዝግቦ በህጋዊ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገባውን ተሸከርካሪ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 በመጠቀም በራሱ ስም ሊብሬ አውጥቶ ሲገለገልበት በቀን 10/08/05 ዓ/ም በቁጥጥር ስር በመዋሉ በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በመገንዘብ መወሰን ሲገባቸው ይህንን ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ፡፡ሌላው መታየት ያለበት በዐ/ሕግ ክስ የተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 104/3/ /ሀ/ በሚደነግገዉ አግባብ መኪናዉ በመንግስት ከመወረስ ሊድን የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ የተያዘ መኪና ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ መኪናዉ ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰዉ ሊመለስ የሚችለዉ መኪናዉ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ አጥጋቢ ማስረጃ ያልቀረበ እንደሆነ ነዉ፡፡ አሁን አከራካሪ የሆነው መኪና የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ በበቂና አጥጋቢ ማስረጃ እስከተረጋገጠ ድረስ መኪናዉ እንዲወረስ ከሚደረግ በስተቀር ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰዉ የሚመለስበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ለክርክር የሆነዉ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት መሆኑን እስከተረጋገጠ ድረስ መኪናዉ ሊወረስ ይገባል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ተሽከርካሪ የተጭበርበረ ስለመሆኑ በባለሞያ የቀረበው ማስረጃ ሳይመለከቱ ተሽከርካሪው ሕጋዊ መሆኑ ተከላክለዋል በማለት ተጠሪዎች ነፃ እንዲለቀቁ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1.የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 48692 በቀን 28/04/2007 ዓ.ም.እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10870 በቀን 30/03/2008 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2 .1ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) / ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ ፣እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) / ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ የተመለከተውን በመተላለፉ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

3 .የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈጸመበትን ከላይ የተገለጸውን በኤግዚቢትነት የተያዘው ተሽከርከሪ ሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-02075 ሐረ. በሚል የሚታወቀው ተጠሪዎች ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104/1/ መሠረት ለመንግስት እንዲወረስ ታዛል፡፡ አመልካች ተከታትሎ ያስፈጸም፡፡

4/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ የቅጣት ሀሳብ ከተቀበለና ከአከራከረ በኋላ ከሕጉ እና ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንጻር በመመርመር በተጠሪዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጥ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

## ትእዛዝ

1. የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪዎች፡-1ኛ አቶ ፋሲል ጥላሁን እና 2ኛ አቶ ካሊድ ሳቢት ከተገኙበት ቦታ ይዞ ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት እንዲያቀርበው ታዛል፡፡ ይጻፍ፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት መ/ቁ 48692 በመጣበት አካኋን በፍ/ቤቱ ሬጅስትራር አማካኝነት ተመላሽ ይሁን፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## 7. የባንክ ስራ አዋጅ[112]

### 7.1 የተጠበቁ መረጃዎችና የፍርድ ቤት የምርመራ ትዕዛዝ[113]

- ወንጀል መፈጸሙን ለማጣራትና ምርመራ ለማጠናቀቅ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎች በህግ ጥበቃ የሚደረግላቸው እና ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ለማግኘት የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች የሚቀርብላቸውን ጥያቄ በአግባቡ በማጤን ተገቢውን ትእዛዝ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ፤

የሰ/መ/ቁጥር 139107

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

---

[112]የአዋጅ ቁጥር 592/2000 እና 720/2004

[113]የሰ/መ/ቁ 139107 (ቀን መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች:- የጉለሌ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ - ኢንስፔክተር የትምወርቅ ጋሻው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ምርመራ ሂደት የተጠርጣሪን የባንክ ሂሳብ መረጃ የማግኘት ፈቃድን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠርጣሪ አቶ መኮንን በላይ ላይ ለጀመረዉ የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ምርመራ ሥራ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተጠርጣሪዉን የባንክ ሂሳብ መረጃ እንዲሰጠዉ እንዲታዘዝለት ለስር ፍ/ቤት ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ጥያቄዉን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 3(3) መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ በወንጀል ምርመራ ወቅት ባንክ ማዘዝ የሚችል ስለሆነና ስልጣኑም የጠቅላይ ዐ/ሕግ በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ በዐ/ሕግ በኩል ሊስተናገድ ስለሚችል ጥያቄዉን አልተቀበልኩም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም አመልካች ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ የአዋጅ ቁጥር 943 አንቀጽ 6(3/ሀ) ለፖሊስ የተሰጠ ወንጀል የመመርመር ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሚል ቃል ያለዉና ለፖሊስ ራሱን በቻለ አዋጅ ስልጣኑ ተለይቶ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ ተገቢ አይደለም በማለት ትዕዛዙን በመሻር ሲወስን፣ ፖሊስ እንዲሰጠዉ የጠየቀዉን ትዕዛዝ አስፈላጊነት በተመለከተ ፖሊስ ስንቅ የሌለዉ ቼክ ቀርቦለት፣ ባንኩ የቼኩ ባለቤት ቼኩ ተሰርቆብኛል በማለት ያስታወቀዉ መሆኑን በገለጸበት ሁኔታ ፖሊስ ባንክ የሚገኝ ማስረጃ የሚፈልግበት ምክንያት ግልጽ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡ አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በፌዴራል ፖሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/04 መሠረት ወንጀል የመመርመር ስልጣን ለፖሊስ የተሰጠ ሲሆን እንደሚደርሰን ጥቆማ እና የወንጀሉ ክብደት በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 እና በአዋጅ ቁጥር 592/2000 መሰረት የግለሰቦች የባንክ መረጃ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንደሚገኝ ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ማስረጃ የማግኘት ያለን መሆኑን ቢያረጋግጥም የወንጀል ምርመራዉ ተጠርጣሪዉ ለባንኩ ጠፍቶብኛል ብሎ ካስታወቀዉ ቼክ ጋር የተያያዘ በመሆኑ እየታወቀ የማስረጃዉ አስፈላጊነት ግልጽ አይደለም በማለት አቤቱታችን ዉድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለሆነም የተጀመረዉን ምርመራ ማጠናቀቅ እንዲቻል ቼኩ በወጣበትና ለባንክ ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ በተጠርጣሪዉ የባንክ ሂሳብ በቂ ስንቅ ወይም ገንዘብ መኖር አለመኖሩ እንዲረጋገጥ እንዲታዘዝልን፣ በተጠርጣሪዉ ፊርማ ላይ የፎረንሲክ ምርመራ ማድረግ በማስፈለጉ ከዚህን ቀደም ተጠርጣሪዉ የፈረመባቸዉ ከ5 እስከ 7 የሚሆኑ ቼኮች እንዲሰጡ እንዲታዝ እና ተጠርጣሪዉ ፊርማ የሌለዉ ቼክ ጠፍቶብኛል ብሎ ያመለከተበት ደብዳቤ እንዲሰጠን ትዕዛዝ ይሰጥልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማዉጣት ወንጀል ተፈጽሟል በሚል በግል ተበዳይ በኩል አቤቱታ ቀርቦ ፖሊስ ለምርመራ ይጠቁምኛል

ያላቸዉን ሰነዶች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሰጠዉ ማዘዣ ከፍ/ቤት ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት ማስረጃዉ የሚፈለግበት አግባብ ግልጽ አይደለም በሚል የአመልካች ማዘዣ ጥያቄ ዉድቅ ያደረገበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 22(2-ሠ)፣ ከአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 28(4-ሠ)፣ ከአዋጅ ቁጥር 720/04 አንቀጽ 6 እና አግባብነት ካላቸዉ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ድንጋጌዎች መሠረት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች በፌዴራል ፖሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 6 ወንጀልን የመርመር ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑና ለምርመራ የሚያስፈልገዉን የግለሰብ የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ መረጃ ማግኘት የሚችለዉ ስለባንክ ስራ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 28(4/ሠ) መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሆኑ በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ ፖሊስ ለምርመራዉ አስፈላጊ የሆነ የተጠርጣሪ የባንክ መረጃ ሲኖር ጥያቄዉን ለፍ/ቤት አቅርቦ አስፈላጊነቱ ሲታመን ፍ/ቤት ለባንክ መርጃ እንዲሰጥ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተጠርጣሪዉን የባንክ መረጃዉን የሚመለከተዉ ባንክ እንዲሰጠዉ የፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ያቀረበዉ ምክንያት በቂ አይደለም በማለት ጥያቄዉን ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ስንቅ ሳይኖር ቼክ የማዉጣት ወንጀል በተጠረጠረዉ አቶ መኮንን በላይ በጀመረዉ ምርመራ ምክንያት ምንም እንኳ ቼኩ ለባንክ ቀርቦ ክፍያ ሳይፈጸም ተመላሽ የተደረገ መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ተጠርጣሪዉ አስቀድሞ ቼኩ የተሰረቀ በመሆኑ ክፍያ እንዳይፈጸምበት ለባንኩ ማስታወቁን ባንኩ በመግለጹ ቼኩ የተሰረቀ ነዉ ወይስ በተጠርጣሪዉ ተፈርሞ የተሰጠ ነዉ የሚለዉን እዉነታ ለማጣራትና ምርመራዉን ለማጠናቀቅ የተጠርጣሪን የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ፣ ቀድሞ የፈረማቸዉን የፊርማ ናሙናዎች ማግኘቱ ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች ያለፍ/ቤት ትዕዛዝና ለተፈቀደላቸዉ ሰዎች ካልሆነ በቀር ለማንም ሰዉ ተላልፎ የማይሰጡ በሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸዉ መረጃዎች በመሆናቸዉ ፖሊስ በፍ/ቤት ትዕዛዝ መረጃዎችን ካላገኘ በስተቀር በተጠርጣሪዉ ላይ የጀመረዉን ምርመራ ሊያጠናቅቅ አይችልም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተጠርጣሪዉን የባንክ መረጃ የሚፈልግበት አግባብ ግልጽ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበል መቅረቱ የወንጀል መርመራዉን ልዩ ባህሪ፣ በአዋጅ ቁጥር 720/04 አንቀጽ 6 ለአመልካች የተሰጠዉን ወንጀል የመመርመር ስልጣንና በአዋጅ ቁጥር 592/00 አንቀጽ 28(4/ሠ) መሠረት የተጠርጣሪዉ የባንክ ሂሳብ መረጃ የሚገኝበትን አግባብ ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

ሌላዉ ይህ ሰበር ችሎት ለባንክ ትዕዛዝ ይስጥልን የሚለዉን የአመልካች ጥያቄን በተመለከተ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት ለዚህ ችሎት የተሰጠዉ ስልጣን የመጨረሻ በሆነ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ በቀጥታ ለባንክ ትዕዛዝ በመስጠትና መረጃዉ መሰጠቱን በመከታተል የሚያስፈጽምበት አግባብ ባለመኖሩ የተፈጸመዉን የሕግ ስህተት በማረም ትዕዛዙ በስር ፍ/ቤት በኩል እንዲሰጥና አፈጻጸሙን አስመልክቶ ክትትል እንዲደረግበት ለስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መመለሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 003839 የካቲት 03 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሻሽሏል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57579 የሰጠዉን ትዕዛዝ መሻሩ በአግባቡ ነዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በተጠርጣሪዉ ላይ የጀመረወን ምርመራ ለማጠናቀቅ ቼኩ በወጣበት የባንክ ሂሳብ ጋር የተያያዙና በአመልካች የተጠየቁ መረጃዎችን ማግኘት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ አመልካች መረጃዎችን ማግኘት እንዲችል በስር ፍ/ቤት ተገቢዉ ትዕዛዝ ሊሰጥበት ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ አመልካች በተጠርጣሪ ላይ እያካሄደ ላለዉ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ የማዉጣት ወንጀል ምርመራ የጠየቃቸዉን መረጃዎች ማግኘት እንዲችል ትዕዛዝ ለሚመለከተዉ ባንክ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ይመለስለት ተብሎ ተወስኗል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## 8.የመከላከያ ሚኒስቴር አዋጅ[114]

## 8.1 የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂነት[115]

- የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እና የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን የተለያየ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና የሠራዊት አባላት በፋውንዴሽኑ ንብረት ላይ የሚፈጽሟቸው ማንኛውም ወንጀሎች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ላይ እንደተፈጸሙ ተደርጎ የማይቆጠሩ ስለመሆናቸው፤
- የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት በመከላከያ ሰራዊት ፋውንዴሽን ንብረት ላይ የሚፈጽማቸው ወንጀሎችን የማየት ስልጣን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ሆኖ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን የማስተናገድ የመጀመሪያ ደረጃ የፍርድ ስልጣን የሚኖረው ስለመሆኑ፤

የሰ/መ/ቁ. 141663

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- ሻለቃ አለማየሁ ወንጀሎ ለኩ - ጠበቃ አይረሳም ሸንቁጤ

ተጠሪ፡- የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

---

[114]የአዋጅ ቁጥር.809/2006 አንቀጽ 28 እና 38 ደንብ ቁ. 179/2002

[115]የሰ/መ/ቁ. 141663 (መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16522 ጥር 18 ቀን 2008 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ብይን የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 124937 በቀን 22/02/2009 ዓ.ም በመሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ነው፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 676/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ በኢ.ፌ.ድ.ሪ የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ውስጥ ከግንቦት 8 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በአልባሳት ዋና ግምጃ ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት በማሰብ በሥራው ምክንያት ከመስሪያ ቤቱ ከተረከባቸው የ15 ዓመት የሽልማት ሜዳሊያዎች ውስጥ የሰኔ ወር ግምጃ ቤት ቆጠራ ሰኔ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ሲካሄድ 300 ሜዳሊያ የአንዱ ዋጋ ብር 2425.49 ጠቅላላ ብር 727647 ለራሱ ያደረገ/ የወሰደ/ ያስወሰደ/ የሰወረ በመሆኑ ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ የቀረበው ክስ ከደረሰው በኂላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም ፤አመልካች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ሠራዊት አባል ነኝ በአዋጅ 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ መሠረት በሠራዊቱ አባላት መካከል የሚፈፀም የግድያ የድብደባ ወንጀል ወይም የሠራዊቱ አባላት በሚንስትሩ ንብረት ላይ በሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች የማየት ሥልጣን የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው፣ ይህ ከታለፈም ጉድለቱ የተከሰተው ተቀጥሬ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ወስጥ በተደረገ ቆጠራ ነው፤ ምስክሮች ሌላ ተጠርጣሪ እንዳለ እያስረዱ ነበር ስለሆነም የሙያ ሥራን በአግባቡ አለመምራት ነው ክስ ሊቀርብብኝ የሚገባው ፡፡ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በመቃሚያው ላይ በሰጠው መልስ አመልካች የተከሰሰበት ወንጀል በቀጥታ ከውትድርና ሥራቸው ጋር የሚገናኝ ሳይሆን የህዝብና የመንግስት ንብረት አጉድሏል ተብሎ ነው ይህ የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በሌላ ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ ሌላ ተጠርጣሪ እያለ የቀረበ ነው የተባለው ወደፊት የሚነሳ እንጂ መቃወሚያ የሚሆን አይደለም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም መርምሮ በአዋጅ 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ በተመለከተው መሠረት የሠራዊቱ አባላት በሚኒስቴሩ ንብረቶች ላይ በሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎችን ስለሚል እና ከሙስና ወንጀሎች በቀር የሚል ሀረግ ስለሌለ፣ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ከወንጀል ህግ በኂላ የወጣና በቀዳሚነት ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ እና ልዩ ህግ በህጉ ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ፣ እና አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል ከመሆኑም ባሻገር ፋውንዴሽኑ ራሱን በቻለ ደንብ የተቋቋመ ቢሆንም ሠራተኞቹ ወታደሮች መሆናቸው ዓላማውም የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት ሥራ በተቀላጠፈ ማስተናገድ ተጠሪነቱም ንብረቱም /ኒሻኑም/ የመከላከያ ሚ/ር በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ አነስተኛው ድምጽ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው ብሏል፡፡

ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ራሱን የቻለ ተቋም ነው አይደለም የሚለው በቅድሚያ መርምሮ በደንብ ቁጥር 179/2002 አንቀጽ 2/3/ መሠረት በህጉ የሰውነት አካል የተሠጠው ራሱን የቻለ ተቋም መሆኑን በአንቀጽ 8 እና ተከታዮቹ በቦርድ የሚተዳደር አባላቱን ከሠራዊቱ አባላት በተጨማሪ ሌሎች ሰዎችን የሚያሳትፍ ራሱን የቻለ በራሱ በጀት የሚተዳደር ተቋም እና በራሱ መክሰስና መከሰስ የሚችል ነው፣ ተጠሪነቱ ለመከላከያ ሚኒስቴር ይሁን እንጂ በሚንስቴር በጀት የሚተዳደር ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለቀደሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ሳይሆን በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ሽሯል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ መሠረት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው፤ አመልካች በመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን አገልግሎት የምሰጠው በሠራዊት አባልነት በመመደብ በመሆኑ የተቋሙን ህጋዊ ሠውነት እና የአመልካችን ልዩ መብት ያላገናዘበ ስለሆነ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ የሚል ሲሆን አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን አግባብነት ከደንብ ቁጥር 179/2002 አንቀጽ 3፣6፣7፣13/ለ/ ጋር ለማገናዘብ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዞ በሰጠው መልሱ አመልካች ተቀጥረው የሚሰሩት በመከላከያ ፋውንዴሽን ሲሆን ይህም ራሱን ችሎ የተቋቋመ የህግ ሠውነት ያለው ተቋም ነው፤ ሠራተኞችም የፋውንዴሽኑ አንጂ የመከላከያ ሚኒስቴር አይደለም፣ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች የተቋቋሙት ወታራዊ ይዘት ያላቸው ነው ፡ አመልካች የፈፀሙት ሲቪል ጉዳይ ነው ስለሆነም ጉዳዩ ወታራዊ ይዘት ያለው ባለመሆኑ ስልጣኑ የመደበኛ ፍርድ ቤት ነው ብሏል፡፡ አልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘወ ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡ የክርክሩ ሂደት የሚያስነገዘበው አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል እና የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን የአልባሳት ዋና ግምጃ ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት በሥራው ምክንያት ፈጽሞታል ተብሎ የቀረበበትን የከባድ የእምነት ማጉደል ሙስና ወንጀል ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት የመዳኘነት ሥልጣን መኖር አለመኖርን የሚመለከት ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 79 የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው የሚለውን በዚሁ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ወሰን ከሚያመለክተው ጋር አገናዝበን ማየት እንደሚቻለው ማንኛውም ጉዳይ ያለ ገደብ በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነው፡፡ በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 የተቀመጠው የሥልጣን ክፍፍል ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል እና ጉዳዩንም አይቶ ለመወሰን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ለሌላ የዳኝነት ሠጪ አካል ያልተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህንኑ በፍርዱ ሊያልቅ የሚችለውን ጉዳይ ለማየትና ለመወሰን ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው መደበኛ ፍርድ ቤቶች መሆናቸውን ነው፡፡ ስለሆነም መደበኛ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል መሆኑ ላይ ብቻ ሳይወሰኑ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 መሠረት ይኸው ጉዳይ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ቀርቦ የሚታይ መሆን አለመሆኑን በቀጥታ የመመርመር ግዴታ አለባቸው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ክሱ በመደበኛነት የቀረበለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በወ/ህ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ130/2/ መሠረት በቀረበለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ይህንን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለ/ መሠረት ለቀዳሚ ወታራዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም የሚል መቅረቡን እና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የተለያየ ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ነው፡፡ ስለሆነም በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለ/ መሠረት ተሰጥቷል አልተሰጠም የሚለውን መርምረናል፣ የአዋጁ አንቀጽ 38 የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ሥልጣንን የሚዘረዝር ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ በሠራዊቱ አባላት መካከል በሚፈፀም የግድያ ወይም የድብደባ ወንጀል ወይም የሠራዊቱ አባላት በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ በሚፈጽማቸው ማናቸውም ወንጀሎች የዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋል በዚሁ ድንጋጌመሠረት በስር ፍ/ቤት የክርክርም ምክንያት የሆነው የሠራዊቱ አባላት በሚኒስትር ንብረት ላይ የሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች የሚለውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል ሲሆን የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሞበታል የተባለው በመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በመሆኑ በመከላከያ ሚኒስቴር ንብረት ላይ ተፈጽሟል ለማለት

የሁለቱን አካላት አንድነትና ልዩነት ካቋቋማቸው ድንጋጌዎች ተመልክተናል፡፡ የኢ.ፌ.ድ.ሪ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ.316/2008 አንቀጽ 9/1/ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የተቋቋመ እና ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የሆነ የመንግስት አስፈጻሚ አካል ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ላይ … በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ በሚፈፀሙ ማናቸውም ወንጀል ሲል በዚህ የሀገር መከላከያ ሚኒስትር ንብረት ላይ የሚፈፀም ማናቸውም ወንጀሎችን ነው፡፡ በሌላ በኩል የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በመንግስት በጀት ሊሚሉ የማይችሉት የመከላከያ ሠራዊት አባላትን ፍላጐት የሚያረኩና የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽሉ አገልግሎቶች በማቅረብ የተለያዩ ድጋፎችን የማድረግ ዓላማ ይዞ በደንብ ቁጥር 179/2002 የተቋቋመ የህግ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡ ከዓላማው አንጻር ተጠሪነቱ ለሀገር መከላከያ የሚኒስቴር መሆኑ፣ በአባልነትም ከተሰናበቱ የሠራዊቱ አባላትና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተጨማሪ የመከላከያ ሠራዊት አባላት መኖር ፋውንዴሽኑን ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ የተፈጸመ አያደርገውም፡፡ ይህም የሚያስገነዝበው የተለያዩ ህጋዊ ሠውነት ያላቸው አካላት መሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም የሠራዊቱ አባላት በፋውንዴሽኑ ንብረት ላይ የሚፈጽማቸው ማናቸውም ወንጀሎች በሚኒስቴር ላይ እንደተፈፀመ ወንጀሎች የሚገመቱ አለመሆናቸውን ነው፡፡ በሌላ በኩልም ወታደራዊ የፍትህ አካላት በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 28 መቋቋም መሠረታዊ ዓላማ ከሥራው ልዩ ባህሪ አንጻር ወታደራዊ የሆነ የወንጀል ድርጊቶችን በተለይም በቁጥር 38 የተመለከቱትን የመከላከል ፤የመመርመር ፤የመክሰስ፤ ውሳኔ የመስጠትና የማስፈፀም ነው፡፡ ስለሆነም በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ የሠራዊቱ አባል በሚኒስትሩ ንብረት ላይ የተፈፀመ ተብሎ የሚወሰዱ አይደለም፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ድርጊቱ ተፈጽሟል በተባለበት ጊዜ በሥራ ላይ በነበረው የተሻሻለው የፀረ-ሙስና የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 7/1/ መሠረት ጉዳዩን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡ በአጠቃላይ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ተጠሪ ያቀረበውን ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ክስ የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት የስር ፍ/ቤት በአብላጫ ድምጽ የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

- የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16555 ጥር 18 ቀን 2008 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ብይን በመሻር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ/ቁ 124937 በቀን 22/02/2009 ዓ.ም የሰው ፍርድ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2//ለ//2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 8.2 በወንጀል የተከሰሱ የመከላከያ አባላት በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍ የማግኘት መብት[116]

- በወንጀል የተከሰሱ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በግላቸው ጠበቃ ለማቆም የማይችሉ በሆነ ጊዜ በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍና እርዳታ ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ፣ (የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20(5) አዋጅ ቁ.27/88 አንቀፅ 35 አዋጅ ቁ.123/90)

የሰ/መ/ቁጥር - 65566

ታህሣስ 4 ቀን 2004 ዓ.ም.

[116]የሰ/መ/ቁ 65566 (ታህሣስ 4 ቀን 2004 ዓ.ም)ቅፅ 13

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች- የመከላከያ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ- ሃምሣ አለቃ ተስፋዬ ቦያለው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የመከላከያ ሠራዊት አባል በመደበኛ ፍርድ ቤት የቀረበበትን የወንጀል ክስ ለመከላከል የሚያስችለው የህግ ድጋፍ መስጠትን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የመከላከያ ሠራዊት አባል በሆኑት ሀምሣ አለቃ ቴውድሮስ ሃይለስላሴ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/11ሀ በመተላለፍ ባለ አንድ መቶ ሐሰተኛ የብር ኖት (100) ይዘው ተገኝተዋል የሚል የወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ተከሣሳሹ የተከሰሱበት የወንጀል ክስ ተገቢውን የህግ ድጋፍ እንዲያደርግና በተከላካይ ጠበቃ እንዲታገዝ የመከላከያ ሠራዊት መከላከያ ጠበቃ መድቧል፡፡ የዞኑ አቃቤ ህግ የመከላከያ ሠራዊት አባላት መከላከያ ሚኒስቴር ተከላካይ ጠበቃ የሚያቆመው በመደበኛ ፍ/ቤት በሚያስከስሱ ወንጀሎች ሣይሆን በጦር ፍ/ቤት በሚያስከስሱ ወንጀሎች ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የመከላከያ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ ተከሳሹን ወክሎ ለመከራከር አይችልም የሚል መቀወሚያ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የዞኑ አቃቤ ህግ ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል የመከላከያ ወታደራዊ ተካላካይ ጠበቃ ለተከሳሹ የህግ ድጋፍ የመስጠት በተከላካይ ጠበቃነት ቆሞ ለመከራከር አይችልም የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅረቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን አፅንቶታል፡፡ አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል የሆነውን ተከሳሽ እንድንከላከል የበታች ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 27/1988 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በወታደራዊ ተከላከይ ጠበቃ እንዲታገዙ አዋጅ ቁጥር 27/1988 የሚፈቅደው በወታደራዊ ፍርድ ቤት በሚከሰሱበት ጊዜ ብቻ ስለሆነ ለተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የህግ ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የመከላከያ ሠራዊት አባል ያሁት ሃምሣ አለቃ ቴድሮስ ሀይለስላሴ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 361 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል የሚል የወንጀል ክስ በተጠሪ በኩል ቀርቦበታል፡፡ የመከላከያ ሠራዊት አባሉ የተከሰሱበት ወንጀል ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 361 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አዋጅ ቁጥር 27/88 በአዋጅ ቁጥር 123/90 እንደተሻሻለ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው የህግ ማእቀፍ ሲሆን በዚህ መዝገብ የተያዘው ጭብጥ የአዋጅ ድንጋጌ ብቻ ሣይሆን የህገ መንግስቱን

አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 ተፈፃሚነት መመርመር የሚጠይቅ ነው፡፡ ተከላካይ “ስለማቆም” የሚል ርእስ ያለው የአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ፤ “ራሱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም ለማይችል ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰው መንግስት ተከላካይ ጠበቃ ይመደብለታል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን የእንግሊዘኛው ቅጅ “the state shall provide a defence counsel to a person charged with an offence punishable by imprisonment not less than five years and un able to retain a counsel" በሚል መንገድ የተደነገገ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ የአንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2 በዚህ “አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በተከላካይ ጠበቃነት ለማቆም የሚችለው ከሠራዊቱ አባል መካከል ይሆናል፡፡ በማለት በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከላይ የተገለፀው የህግ ድንጋጌ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በወታደራዊ ፍርድ ቤትም ሆነ በመደበኛ ፍርድ ቤት ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ክስ ሲቀረብበትና በራሱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የማይችል በሆነ ጊዜ መንግስት የህግ እውቀትና ልምድ ያለው የመከላከያ ሰራዊት አባል የሆነ ተከላካይ ጠበቃ በነፃ የማቆምና የመከላከል ግዴታ እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 27/88 አንቀጽ 35 መንግስት ለሠራዊቱ አባላት በነፃ ተከላካይ ጠበቃ በማቆም የቀረበባቸውን የወንጀል ክስ እንዲከላከል በህግ የሚገዳድበትን ዝቅተኛ መስፈርት (minimum standard) የሚደነግግ ሲሆን የአገር መከላከያ ሚኒስትር የመከላከያ ሠራዊት አባላት በግዳጅ ላይ እያሉ ፈፀመውታል ተብሎ በተከሰሱበት ከ5 አመት እስራት በታች በሚያስቀጣ ወንጀል ተከላካይ ጠበቃ በነፃ ለማቆምና ለመከላከል ከፈለገ በወታደራዊ ፍ/ቤትም ሆነ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝ መደበኛ ፍ/ቤት ተከላካይ ጠበቃ በመወከልና በነፃ የቀረበውን የወንጀል ክስ መከላከል የአዋጁ አንቀጽ 35 ድንጋጌዎችን የሚገድቡት እንዳልሆነ ከድንጋጌው አቀራረፅ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀፅ 35 ድንጋጌዎች በወንጀል የተከሰሱ የመከለከያ ሠራዊት አባላት በግላቸው ጠበቃ ለማቆም የማይችሉ በሆነ ጊዜ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍና እርዳታ የማግኘት መብት እንዳላቸው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገውን በማጣብብና በተሻሻለ ሁኔታ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ ተፈፃሚ በሚያደርግ መንገድ መተርጐምና ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከ5 አመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በወታደራዊ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ በቀረበበት ጊዜና ተከሳሹ በግሉ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የማይችል ሲሆን የመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ድጋፍ በነፃ ማግኘት በአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀጽ 35 የተደነገገ የሠራዊቱ አባል መብትና የአገር መከላከያ ሚኒስትር ህጋዊ ግዴታ ሲሆን የሠራዊቱ አባል በአምስት ዓመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በመከላከያ ፍርድ ቤት ክስ በቀረበበት ጊዜ የአገር መካከላያ ሚኒስትር በነፃ የተከላከይ ጠበቃ ድጋፍ የሠራዊት አባል ማግኘት አለበት ብሎ ካመነ የመከለከያ ወታደራዊ ጠበቃ በነፃ የህግ ድጋፍና እገዛ እንዲያደርግለት በማድረግ መከላከል የሚችል መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀጽ 35 ድንጋጌዎች ይዘትና ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻል ሆኖ እያለ የመከላከያ ሠራዊት አባል በመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ነፃ የህግ ድጋፍ የሚያገኘው በወታደራዊ ፍርድ ቤት በወንጀል ሲከሰስ ብቻ ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበውን የህግ መሠረት የሌለው መቃወሚያ በመቀበል ተከሣሹ በመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ነፃ የህግ ድጋፍ እንዳያገኝ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ብይን ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት በመደበኛ ፍርድ ቤት በወንጀል በተከሰሱበት ጉዳይ በነፃ የህግ ድጋፍና እገዛ የማድረግና የመከላከል መብት አለው በማለት ወስነናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## 9.የሊዝ አዋጅ[117]

### 9.1 ሕገ-ወጥ የከተማ ቦታ ወረራ ማስለቀቅ ሂደት እና የወንጀል ተጠያቂነት[118]

- በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 27 መሰረት አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለ ይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል" በማለት የተቀመጠው ሀሳብ በሕጋዊ መንገድ ለተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስለቀቅ የተቀመጠውን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የመስጠት እና ካሣ የመክፈል ሥርዓት ማሟላት ሳያስፈልግ በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን ማስለቀቅ የሚቻልበትን ሥርዓት የሚደነግግ እንጂ የከተማ ቦታን ወሮ ለያዘ ሰው የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስቀር ስላለመሆኑ፤

የሰ.መ.ቁ 150803

ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ
በዕዉቀት በላይ
እንዳሻዉ አዳነ
ሃይሉ ነጋሽ
እትመት አሠፋ

አመልካች፡- በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ንጉስ ሀይሉ-አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪው የአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 35/1/ለ ድንጋጌን በመተላለፍ ማንም ሳይፈቅድለት በቀን 06/07/08 ዓ.ም ከቀኑ 10፡00 ሠዓት በሐወልቲ ክፍለከተማ ቀጠና 10 ስፋቱ 11.28 ሜ2 የሆነ የመንግሥት መሬት ጨምሮ ቤት ስለሰራበት በፈጸመው የከተማ ቦታ ያለአግባብ መያዝ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐወልቲ ፍ/ቤት ተጠሪን በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኘው

[117]የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004
[118]የሰ/መ/ቁ 150803 (ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 23

ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 በማስላት በሠባት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 40,000 / አርባ ሺህ ብር / የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ የሰሩትን የድንጋይ አጥር እንዲያፈርሱ በቃል የተነገራቸው ከመሆኑ በቀር የተሰጣቸው የ7 ቀን የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ የለም፤አዋጁ የሰባት ቀን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መሰጠት እንዳለበት የሚደነግግ ሆኖ ሳለ እና ተጠሪ በቃል በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት የሰሩትን የድንጋይ አጥር አፍርሰው ሳለ የሥር ፍ/ቤት በአዋጁ የተቀመጠው ማሥጠንቀቂያ የመስጠት ቅድመሁኔታ ባልተሟላበት ሁኔታ የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን በነጻ አሰናብቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶቸ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው የቀረበላቸው ፍ/ቤቶች የሥር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አስቀድሞ የመሬት ወረራ ወንጀል ለመስራት አስቦ መሬትን የወረረ ሰው ማሥጠንቀቂያ ካልተሰጠው በቀር በወንጀል ጥፋተኛ ሊባል አይገባም የሚል ድንጋጌ በአዋጁ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው የሥር ፍ/ቤቶች ለተጠሪ ማሥጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ምክንያት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን ተጠሪ የከተማ ይዞታውን የያዘው ከሕግ ውጪ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 721/04 አንቀጽ 27 መሠረት ማሥጠንቀቂያ ባልተሠጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዋጁ አንቀጽ 26/4 እና 27/2 የተቀመጠው ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ በአዋጁ አንቀጽ 35/1/ለ የተቀመጠው ቅጣት ክብደት አኳያ ተጠሪን የመሰሉ ሰዎች ማስጠንቀቂያ በመስጠት አሥተዳደራዊ መፍትሔ ለማምጣት እና በማስጠንቀቂያ ከተግባሩ እንዲቆጠብ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ በመገንዘ ተጠሪን በነጻ ማሰናበታቸው ተገቢ ነው፤ይህ የሚታለፍ ከሆነም ተጠሪ ለጊዜው የሰራሁትን አጥር ያፈረስኩ እና የፈጸምኩት ተግባርም ቀላል ስለሆነ ጥፋተኛ ልባል የሚገበው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 686/1 ከመግሥት ፈቃድ ውጪ የመንግሥትን ቦታ መያዝ ወንጀል በሚል ሊሆን ይገባል፤ይህ የሚታለፍ ከሆነም ይዞታው ከባለቤቱ ይዞታ አጠገብ የሚገኘውን ቦታ ክረምቱ እስኪያልፍ በሚል ለማገዶ የተሰራ እንጂ ቦታውን ለማካተት ስላልሆነ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ቅጣቱም ቀሎ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ ሲባል እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ተጠሪ የአዋጁን አንቀጽ ከአዋሳኛቸው ጎን ያለውን የመንግሥት ቦታ ወደ ራሣቸው ይዞታ በመቀላቀል የድንጋይ አጥር የሰሩበት መሆኑ በወረዳው ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አነቀጽ 35/1/ለ ማንም ሰው አዋጁን ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የከተማ ቦታን አጥሮ ከያዘ ግንባታ ካካሄደበት ወይም ከአዋሳኝ ይዞታው ጋር ከቀላቀለ ከሠባት እሥከ አሥራ አምሥት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 40,000 እሥከ 200,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 26/1 አግባብ ያለው አካል ከቦታው ለሚነሳው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ የከተማ ቦታ ይዞታን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የማስለቀቅ እና የመረከብ

ሥልጣን ይኖረዋል በማለት ይነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 4 አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል በማለት ይደነግጋል፡፡

የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሰሩትን የድንጋይ አጥር እንዲያፈርሱ በቃል የተነገራቸው ከመሆኑ በቀር የተሰጣቸው የ7 ቀን የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ የለም፤በአዋጁ አንቀጽ 26/4 ላይ የተቀመጠው የሰባት ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ ባልተሟላበት ሁኔታ እና ተጠሪ በቃል በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት የሰሩትን የድንጋይ አጥር ባፈረሱበት ሁኔታ ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ 26/4 ላይ አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል በማለት የተቀመጠው ሀሳብ በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት በሕጋዊ መንገድ ለተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስለቀቅ የተቀመጠውን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የመስጠት እና ካሣ የመክፈል ሥርዓት ማሟላት ሳያስፈልግ በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን ማስለቀቅ የሚቻልበትን ሥርዓት የሚደነግግ እንጂ የከተማ ቦታን ወሮ ለያዘ ሰው የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስቀር አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የአዋጁን አንቀጽ 26/4 ድንጋጌን ያለአግባብ በመተርጎም ለተጠሪ የተሰጠው የሰባት ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1.በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመቐለ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20165 ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 88023 ግንቦት 02 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 98220 ጥቅምት 10 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡

2.ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የሐወልቲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07743 ሠኔ 01 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡

3.የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አስር

## 10.የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ አዋጅ[119]

### 10.1 የኮንትሮባንድ ወንጀል እና ያልታደሰ ንግድ ፈቃድ ወንጀል ሀላፊነት[120]

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168(1) እና (2) መሰረት፣ ማንኛውም ሰው የጉምሩክ ሕጎችን በመተላለፍ የተከለከሉ ወይም የንግድ መጠን ያላቸውን እቃዎች በድብቅ ወደ ሀገር ከማስገባት፣ ያለ ፍተሻ ከማሳለፍ ወይም እንደነዚህ ያሉ እቃዎችን የሚይዝ፣ የሚያከማች ወይም የሚያጓጉዝ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ስለመሆኑ፤
- ንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49(2) መሰረት፣ ማንኛውም ሰው ያልታደሰ የንግድ ፈቃድ በመጠቀም ንግድ ቢሰራ በወንጀል የሚጠየቅ ስለመሆኑ፤[121]

የሰ.መ.ቁ. 233458

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች:1.ብርሃኑ አመነዉ

2. በእዉቀት በላይ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ብርሃኑ መንግስቱ

5. ማርታ ተካ

አመልካች: …….. አቶ ዘዉዱ ነጋሽ -የቀረበ የለም

ተጠሪ:…………… የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ-ዐ/ሕግ ግርማ ሙሉጌታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

### ፍርድ

ይህ የሕገወጥ ንግድ ወንጀል ክርክር የተጀመረዉ በግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.404705 በ15/10/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ የክስ አቤቱታ: ተከሳሽ 1ኛ በፍቼ ከተማ አስተዳደር 04 ቀበሌ ልዩ ስሙ ኮማንዶ ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የሥጋ ቤት የንግድ ሥራ ለመስራት ፈቃድ አዉጥቶ ሲሰራ በነበረ ጊዜ የ2010 ዓ.ም የንግድ ትርፍ ግብር፣ ዋና ግብር፣ ቅጣትና ወለድ በአጠቃላይ ብር 204527.84፣ የ2011 ዓ.ም የንግድ ትርፍ ግብር፣ ዋና ግብር፣ ወለድና ቅጣት በአጠቃላይ ብር 334672.33 ተከሳሽ ይህን ግብር እንዲከፍል ማስታወቂያ የተሰጠዉ ቢሆንም ሳይከፍል የቀረ በመሆኑ የሚፈለግበትን ግብር ባለመክፈል ወንጀል ተከሷል፤ እና 2ኛ ተከሳሽ በተጠቀሰዉ ንግድ ፈቃድ የ2010 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ላለመልፈል በማሰብ ሆነ ብሎ ብር

---

[119] የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008

[120] የሰ/መ/ቁ 233458 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም)

[121] የሰ/መ/ቁ. 86388 (ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15

46643.15 እና የ2011 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 147936.70 ለመንግስት ሳይከፍል የቀረ በመሆኑ በፈጸመዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ባለመክፈል ወንጀል ተከሷል፤ እና 3ኛ ተከሳሽ አስቦበት በ1ኛ እና 2ኛ ክሶች በተጠቀሰዉ ጊዜ እና የንግድ ፈቃድ ለሥጋ ቤት ንግድ ሥራ ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን ተከሳሽ በየዓመቱ የንግድ ፈቃድ ማደስ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የንግድ ፈቃዱን ሳያድስ ሲሰራ የቆየ በመሆኑ ሕገወጥ ንግድ በመሥራት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

ተከሳሽ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያነሳቸዉ ቢሆንም ፍ/ቤቱ መቃወሚያዎቹን በብይን ዉድቅ በማድረጉ፣ ተከሳሽ በሰጠዉ የእምነት ክህደት ቃል 1ኛ ክስ በተመለከተ እኔ የንግድ ትርፍ ግብር አልከፍልም አላልኩም ግብሩ ከአቅሜ ላይ ስለሆነ መክፈል አልችልም እንዲታይልኝ በማለት ተለያየ ጊዜ ለገቢዎች ባለስልጣን ጽ/ቤት አቅርቤአለሁ፤ 2ኛ ክስ የተጨማሪ እሴት ግብር ለመክፈል እምቢ አላልኩኝም ነገር ግን ካንተ የሚፈለገዉ ይህ ብቻ አይደለም ብለዉኝ እምቢ ስላሉኝ መክፈል አልቻልኩም፤ ተከሳሽ ግብሩ በመብዛቱ ምክንያት እና የንግድ ትርፍ ግብር ስላልከፈልሉኝ የንግድ ፈቃድ ማደስ አልቻልኩም፣ ግብር ከተከፈለ እንጂ የንግድ ፈቃድ ስለማይታደስ ነዉ በማለት ሰጥቷል፡፡ በመቀጠል ዐቃቤ ሕግ የሰዉ ምስክሮችን በመስማትና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል እንደዐቃቤ ሕግ ክስ ስለመፈጸሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለተነገረበት የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ተከሳሽ የመከላከያ የሰዉ ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን ተከሳሽ የሥጋ ቤት ንግድ ፈቃድ አዉጥቶ ሲሰራ የነበረ መሆኑን፣ ከአቅሜ ላይ ግብር ተጨምሮብኛል፣ ግብርና ቫት አብዝተዉብኛል፣ ግብሩ በገብዬ ልክ ከተሰራ እከፍላለሁኝ እየለ እንደነበር መስክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘንና በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ በዐቃቤ ሕግ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ ባቀረበዉ የመከላከያ ማስረጃ ያልተካተለ በመሆኑ በተከሰሰበት በሶስቱም ክሶት በኦሮሚያ ክልል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 203/2009 አንቀጽ 125(1)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 75/1995 አንቀጽ 26 እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2) ሥር የጥፋተኝነት ዉሳኔ በመስጠት፣ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ቅጣቱ በፌዴራሉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በመመርመር ተከሳሽ በ11 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 126000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የቅጣት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ወስኗል፡፡ ተከሳሽ አሁንም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ የሚፈለግበትን የግብር እዳ አስቦበት አለመክፈሉ እና የገቢዎች ባለስልጣን ጽ/ቤት የግብር እዳዉን ለማስከፈል የተከሳሽን ንብረት ይዞበት እንዳያስከፍል ንብረቱን መደበቁና ማሸሹ ባልተረጋገጠበት በ1ኛ ክስ የኦሮሚያ ክልል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 203/2009 አንቀጽ 125 (1) እና በ2ኛ ክስ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 75/1995 አንቀጽ 26 ሥር የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በማለት በመሻር፣ 3ኛ ክስን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2) በመተላለፍ ሕገወጥ ንግድ መስራት በሚል የቀረበዉን በተመለከተ ምንም ሳይል ግን ደግሞ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ የተቀበለ በሚመስል ሁኔታ ተከሳሽ በ5 አመት ጽኑ እስራትና በብር 20000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤተታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ19/12/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች የሥጋ ቤት ንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖረዉ ሰርቷል የተባለዉ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም

ባለዉ ጊዜ ፈቃድ ሳላድስ በነበረኝ ፈቃድ መስራት የሚችልበት ሆኖ ሳለ የተሰጠዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበትና ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፤ ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበዉ 3ኛ ክስ ጊዜ ዉስጥ በነበረኝ ባልታደሰዉ የንግድ ፈቃድ የንግድ ሥራዉን የሰራሁበት ቢሆንም በዚህ ጊዜ ዉስጥ ግን በነበረኝ የንግድ ፈቃድ መስራት የሚችልበት ጊዜ ነዉ፤ በ1ኛ እና 2ኛ የዐቃቤ ሕግ ክሶች ላይ የተጠቀሰዉ የታክስ ክፍያ ከንግድ ሥራዬ ከማገኘዉ ትፍር ጋር የማይመጣጠንና በኦድት አገኘነዉ ያሉትን የገንዘብ መጠን መክፈል ባለመቻል እና የንግድ ፈቃዱ ደግሞ ሊታደስ የሚችለዉ ግብር አስከፋዩ መ/ቤት ለንግድ ቢሮ የተጠየቀዉን የግብር መጠን መክፈልን የሚያሳይ ክሊራንስ ካልተጻፈልኝ ፈቃዱን ሳያድስልኝ የቀየ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር የሚታይ ስለሆነ አመልካች በወ/ሕ/ቁ.23 ሥር በተደነገገዉ መሰረት ወንጀል ለመፈጸም ሃሳብ ኖሮኝ ድርጊቱን ያልፈጸምኩ ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች በ3ኛ ክስ ሥር የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ መወሰናቸዉ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ በነጻ እንዲሰናበት በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታዉን በማየት ፣በአመልካች ላይ የቀረበበት 3ኛ ክስ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የንግድ ፈቃድ ሳያሳድስ ነግዷል በሚል በመሆኑ በንግድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሰረት የበጀት አመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ ቀን ድረስ ያለቅጣት የሚታደስ መሆኑ ለአመልካች በተሰጠዉ  የንግድ ፈቃድ ግርጌ ላይ በተጻፈበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ፈቃድ ሳያሳድስ ሰርቷል በሚል ይህ ግምት ሳይገባ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ የሰጡበትን አግባብነት፣ መመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባ በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ በ22/5/2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 ሥር የተከሰሰዉ ጥፋተኛ የተባለዉና የተቀጣዉ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ጊዜ ዉስጥ በመስራቱ ሳይሆን ፈቃዱን ለማሳደስ በሕጉ ከተሰጠ ጊዜ በኋላም የንግድ ሥራዉን መስራቱን በሰዉ ምስክርና በሰነድ ማስረጃ እንደክሱ ያስረዳን ስለሆነ አመልካች ባቀረበዉ የመከላከያ ምስክር ማስተባበል በለመቻሉ የተሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ30/5/2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ ሰበር ችሎት በያዘዉ ተጨማሪ ጭብጥ ፣በአመልካች ላይ የቀረበዉ የ3ኛ ክስ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2)ን ተላልፏል የሚል ሆኖ አንቀጹን መተላለፍ ደግሞ እስከ 15 አመት ድረስ በሚደርስ በጽኑ እስራት ስለሚያስቀጣ ክሱ የቀረበለት ግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ለማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50 (8)፣ 52 (2) (ለ)፣ 55 (5)፣ በተሻሻለዉ የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 46/1996 አንቀጽ 49 (3)፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ አንደኛ ሰንጠረዥ በተመለከተ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ በ7/1/2016 ዓ.ም በተጻፈ የጽሑፍ ክርክር በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78 (3) መሰረት የክልል ፍ/ቤቶች የተቋቋሙ በመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 980/2008 የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚነሱ ክርክሮችን በግልጽ የክልል ፍ/ቤቶች ማየት አይችሉም የሚል ድንጋጌ ያላስቀመጠ በመሆኑ ይህ ጉዳይ በክልል የወረዳ ፍ/ቤት መታየቱ ስህተት አይደለም፤ አመልካች የንግድ ፈቃዱን ያገኘዉ ከኦሮሚያ ክልል ሲሆን የንግድ ተግባሩንም እያካሄደ ያለዉ በዚሁ ክል በመሆኑ የወረዳዉ ፍ/ቤትን ይህን ጉዳይ ማየቱ ስህተት የለዉም፤ አመልካች የዉጭ ዜጋ ባለመሆኑ ጉዳዩ በክል የወረዳ ፍ/ቤት መታየቱ ስህተት የለዉም፣ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 31 (3) እስከ 15 ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ የወንጀል ጉዳዮችን የወረዳዉ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ለማየት ስልጣን እንዳላቸዉ ተደንግጎ ስለሚገኝ፣ የክልል ወረዳ ፍ/ቤትን ይህን ጉዳይ ማየቱ ስህተት ስላልሆነ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በዚህ ጭብጥ ላይ ያቀረበዉ ክርክር ባለመኖሩ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር እና ለሰበር ቅሬታዉ መነሻ የሆኑትን የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔዎች አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥና ተጨማሪ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበዉ 3ኛ ክስ አመልካች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2) በመተላለፍ የስጋ ቤት ንግድ ሥራ ተመዝግቦ የንግድ ሥራ ሲሰራ ቆይቶ የንግድ ፈቃዱን ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ሳያሳድስ የሥጋ ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ሲሰራ የቆየ በመሆኑ ሕገወጥ የንግድ ሥራ በመፈጸሙ ተከሷል የሚል ሲሆን፣ አመልካች ፍ/ቤት ቀርቦ ወንጀል አለመፈጸሙን መብቱን ጠብቆ ክዶ መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ የሰዉና የሰነድ ማስረጃ መረዳት እንደሚቻለዉ አመልካች በተሰማረበት የንግድ ሥራ በ2009 ዓ.ም እና በ2010 ዓ.ም ዉስጥ የንግድ ፈቃዱን ሳያሳድስ ሲሰራ የቆየ መሆኑን እንዳስረዳ ያመለክታል፡፡ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ይህ ከሆነ ተጠሪ በክሱ ላይ የጠቀሰዉ ፍሬ ነገር አመልካች የንግድ ፈቃዱን ማሳደስ ይገባዉ የነበረዉ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ፣ ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ ማስረዳት የሚገባዉ ይኼንኑ ፍሬ ነገር እንጂ ከዚህ ዉጭ የሆነዉን ፍሬ ነገር ማስረዳት አይችልም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ መሰረት ያስረዳዉ መሆኑን አለመሆኑን መመርመር ሲገባቸዉ ዐቃቤ ሕግ እንደክሱ አስረድቷል በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ዉጭ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲሁም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በ1ኛ እና 2ኛ ክሶች የተጠቀሱትን የወንጀል ድርጊቶች ለመፈጸም በወ/ሕ/ቁ.23 ሥር በተደነገገዉ አግባብ የሃሳብ ክፍል የሌለዉ ስለሆነ የወንጀል ተጠያቂነት እንደሌለበት አረጋግጠዉ ባለበት፣ 3ኛ ክስም ከእነዚህ ክሶች ጋር ተያያዥነት ያለዉ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት፣ ክሶቹ ተያያዥነት የሌላቸዉና የሚነጣጠሉ መሆናቸዉን በማስረጃ ባልተረጋጠበት ሁኔታ፣ ሶስት ተያያዥነት ባላቸዉ የወንጀል ድርጊቶች መካከል በመከፋፈል አመልካች በሁለቱ ክሶች የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም ተብሎ በነጻ እንዲሰናበት መወሰን እና በአንደኛዉ ክስ ደግሞ የወንጀል ኃላፊነት አለበት ተብሎ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ዉሳኔ መስጠታቸዉ የሕግ ድጋፍ የለዉም፡፡ በመሆኑም ይህ ሰበር ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1)(ሐ) ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካች ያቀረበዉ የሰበር ቅሬታ ሲታይ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ ቅሬታዉ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ይህ ሰበር ችሎት የያዘዉ ተጨማሪ ጭብጥ እንደሚከተለዉ የሚታይ ይሆናል፡፡ ችሎቱ በያዘዉ ተጨማሪ ጭብጥ ይህ የወንጀል ድርጊት የፌዴራል ሕግ የሆነዉን አዋጅ ቁጥር 980/2008 በመተላለፍ አመልካች ሕጋዊ ንግድ ፈቃድ ሳይኖረዉ የሥጋ ቤት ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ሲሰራ የነበረና የተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ እስከ 15 አመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ፣ ከፌደራል ሕገ መንግስት፣ ከኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት፣ ከወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ እና ከኦሮሚያ ክልል የፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ አንጻር ሲታይ የክልሉ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን ነጥብ ለመመርመር መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደሚታወቀዉ ከደርግ መንግስት ዉድቀት በኂላ የ1987 የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት መጽደቅን ተከትሎ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግስት ሥርዓትን የዘረጋች መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት የሀገሪቱ ሉዓላዊ ስልጣን በፌዴራል እና በክልል መንግስታት መካከል የተከፋፈለ መሆኑን የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50 ይደነግጋል፡፡ የፌዴራሉ መንግስት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ ስልጣን ያለዉና የፌዴራል ጉዳዮች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51 ሥር የተዘረዘረ ሲሆን፣ የክልል መንግስታት ደግሞ ለፌዴራል መንግስቱ በግልጽ ያልተሰጡትን ጉዳዮች ሳይጨምር የክልል ጉዳዮች ላይ ስልጣን ያላቸዉ መሆኑን የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 52 ተመልክቶ እናገኛለን፡፡ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት

የሕግ አዉጭ፣ የአስፈጻሚ እና የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸዉ መሆኑን ማየት ይቻላል (የሕገ መንግስት አንቀጽ 50 (2))፡፡ ከዳኝነት ስልጣን አንጻር ሲታይ በፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት የዳኝነት ስልጣን ለፍ/ቤቶች ብቻ የተሰጠ መሆኑን በአንቀጽ 79(1) ሥር ተደንግጓል፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78(3) እና 80(3)(ለ) ደንጋጌዎች ሥር እንደተመለከተዉ የክልል ፍ/ቤቶች በሕገ መንግስቱ የተቋቋሙ ሲሆን፣ እነዚህ ፍ/ቤቶች የክልል የመጀመሪያ ደረጃ (ወረዳ) ፍ/ቤት፣ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲሁም በክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ስር ደግሞ የሰበር ሰሚ ችሎት መኖሩን ይደነግጋል፡፡ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት በተዘረጋዉ የፌዴራል መንግስት አወቃቀር መሰረት ሁለቱም መንግስታት ሆኑ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እና የክልል ፍ/ቤቶች በሕገ መንግስቱ ለአንዱ የተሰጠዉን የስልጣን ወሰን በማክበር ሃላፊነታቸዉን መወጣት እንደሚጠበቅባቸዉ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50(8) የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የተከሰሰበት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/200 በፌዴራሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣ ቢሆንም የኦሮሚያ ክልል ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ በክልሉ ለሚከናወነዉ የንግድ ሥራ የንግድ ፈቃድ የሚሰጥ እና የሚመዘግብ መሆኑን ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ፡፡ አሁን ለክርክር መነሻ የሆነዉና አመልካች የተሰማረበት የስጋ ቤት ንግድ ሥራ ሲያከናዉን የነበረዉ በፍቼ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ ሲሆን የንግድ ፈቃድም የሰጠዉ እና ከንግድ ፈቃድ ጋር በተያያዘ እርምጃ የሚወስዳዉ የከተማዉ ንግድ ጽ/ቤት መሆኑን እና ከዚህ የንግድ ፈቃድ ጋር በተያያዘ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞ እንደሆነ የወንጀል ኃላፊነት ለማረጋገጥ ስልጣን ያላቸዉ የክልሉ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ እና ፍ/ቤት ባጠቃላይ የክልሉ ፍትህ ተቋማት መሆናቸዉ የሚያከራክር አይደለም፡፡ እነዚህ የፍትሕ ተቋማት ይህን ተግባር የሚያከናዉኑት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ በተሰጣቸዉ የዉክልና ስልጣን ሳይሆን በክልል ስልጣናቸዉን መሰረት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑን ይህን የንግድ ፈቃድ የሚሰጠዉ የኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኝ ከተማ የሆነዉ የፍቼ ከተማ ንግድ ጽ/ቤት፣ የንግድ ሥራዉንም በሕግ አግባብ የሚቆጣጠረዉ ይኼዉ ጽ/ቤት ሲሆን፣ ከዚህ የንግድ ሥራ ጋር በተያዘዉ በሕግ አግባብ ተገቢዉን ክትትል፣ ቁጥጥርና እርምጃ የሚያደርጉት የክልሉ የመንግስት ተቋማት እንጂ የፌዴራል መንግስት ተቋማት አለመሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ይህ አዋጅ በፌዴራሉ ሕግ አዉጭ የወጣ ቢሆንም የክልል መንግስታት አዋጁን በራሳቸዉ በዘረጉት የመንግስት መዋቅር ተከትለዉ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ የሚያመለክት እንጂ እንደፌዴራል ጉዳይ ተወስዶ የክልል መንግስት በሕገ መንግስቱ በተደነገገዉ የዉክልና ስልጣን መሰረት የሚያከናዉኑ መሆናቸዉን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ከዚህ አንጻር በፌዴራሉ ሕግ አዉጭ የወጡትን የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እና የወንጀል ሕግ ማየት ይቻላል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት የኢፌዴሪ እና የክልሉን ሕገ መንግስታት ባከበረ ሁኔታ የክልሉ ፍ/ቤቶችን የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ለመወሰን ስልጣን እንዳለዉ ግልጽ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የኦሮሚ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 31(3) መሰረት የወረዳዉ ፍርድ ቤት ጣራው ከ15 ዓመት በማይበልጥ እሥራት የሚያስቀጣ የወንጀል ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለዉ ደንግጓል፡፡ በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት (ጨፌ) በዚህ አግባብ ለወረዳዉ ፍ/ቤት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን በሰጠዉ መሰረት አሁን የተያዘዉ ጉዳይ በወረዳዉ ፍ/ቤት መታየቱ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም፡፡ የክልል የወረዳ ፍ/ቤት ይህን የወንጀል ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ተቀብሎ ሰምቶ መወሰኑ እና በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች የወረዳዉ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን እንዳለዉ በመቀበል ዋናዉን ጉዳይ አይቶ ተገቢ ነዉ ያሉትን ዉሳኔ መስጠታቸዉ ከፌደራሉ ሕገ መንግስት፣ ከኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት፣ ከወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ እና ከኦሮሚያ ክልል የፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ አንጻር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ተጠሪ በበቂ ሁኔታ በማስረጃ ያስረዳ መሆኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ የማያመለክት ሆኖ ባለበት አመልካች ላይ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ዉሳኔ መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የግራር ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.40405 በ25/6/2014 ኣ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.64393 በ26/8/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.353654 በ07/10/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.404705 የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሻሽሏል፡፡
3. አመልካች የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑን በበቂ ሁኔታ በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ የሚያመለክት ስለሆነ አመልካች የወንጀል ኃላፊነት ስለሌለበት በነጻ ሊሰናበት ይገባል ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. አመልካች ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ ስለሆነ ያስያዘዉ የዋስትና ገንዘብ በደረሰኝ እንዲመለስለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**የልዩነት ሀሳብ**

በተራ ቁጥር 4 ላይ የተሰየምኩት ዳኛ በአብላጫ ድምጽ በአመልካች ላይ የቀረበዉን የወንጀል ክስ የመዳኘነት ሥልጣን የኦሮሚያ ክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ነዉ ተብሎ በመወሰኑ ስላልተስማማሁ የሚከተሉትን ምክንያቶች መሰረት በማድረግ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬያለሁ፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50 ስር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች የተዋቀረ እንደሆነ፤ የፌዴራልም ሆነ የክልሎች መንግሥታት የሕግ አዉጪነት፣የሕግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸዉ፤የክልል ምክር ቤት በክልሉ ሥልጣን ስር በሆኑ ጉዳዮች የክልሉ ሕግ አዉጪ አካል እንደሆነና ይህንን ሕገ መንግሥት መሠረት በማድረግ የክልሉን ሕገ መንግሥት የማዘጋጀት፣የማጽደቅ እና የማሻሻል ሥልጣን እንዳለዉ፤በዚህ ሕገ መንግሥት ተወስኖ የተሰጣቸዉን ሥልጣን መሠረት ባደረገ አኳኋን ለፌዴራሉ መንግሥት የተሰጠዉ ሥልጣን በክልሎች መከበር እንዳለበት ለክልሎች የተሰጠዉ ሥልጣን በተመሳሳይ በፌዴራሉ መንግሥት መከበር እንዳለበት ተደንግጓል፡፡በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/5 ስር በግልጽ እንደተመለከተዉ የወንጀል ሕግ የማዉጣት ሥልጣን ለፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠ ነዉ፡፡ የወንጀል ሕግ ከማዉጣት አንጻር ለክልሎች የተሰጠዉ ሥልጣን በፌዴራሉ መንግሥት የወንጀል ሕግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ሕግ የማዉጣት ሥልጣን ነዉ፡፡ከዚህ በተጨማሪ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/4 ስር እንደተመለከተዉ የንግድ ሕግ የማዉጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሠረት የወንጀል ሥረ ነገር ሕግ (Substantive Criminal Law) የማዉጣት ሥልጣን በግልጽ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠ ቢሆንም የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን የማን እንደሆነ በሕገ መንግሥቱ አልተገለጸም፡፡የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ

የማዉጣት ሥልጣን በአንድ በኩል በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 52/1 መሠረት ለክልል ሕግ አዉጪ የተተወ ሥልጣን ነዉ የሚል ክርክር ሲነሳ ይሰማል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ የሥነ ሥርዓት ሕግ ዋናዉን የወንጀል ሥረ ነገር ሕግ ለማስፈጸም የሚወጣ ሕግ እንደመሆኑ እንደተቀጽላ ሕግ(የዋናዉ የወንጀል ሕግ አካል) ተደርጎ ስለሚቆጠር የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን በተለይ ለፌዴራል ወይም ለክልል ሕግ አዉጪ የተሰጠ ሥልጣን ነዉ ብሎ መደንገግ ሳያስፈልግ የወንጀል ሕግ የማዉጣት ሥልጣን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሰጠቱ ይህንን ሕግ የሚያስፈጽም ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣንም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተፈጥሯዊ ሥልጣን ነዉ የሚል ክርክር ይነሳል፡፡እኔም የወንጀል ሕግ የማዉጣት ሥልጣን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠበት ምክንያት በሚገባ ይሳካ ዘንድ እና የወንጀል ሕግ የሰዉን፣ የማኅበራዊ ኑሮ ደረጃን፣ የዘርን፣ የብሔርን፣ የብሔረሰብን፣ የቀለምን፣ የጾታን የቋንቋን፣ የሃይማኖትን፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ አስተሳሰብን መሰረት በማድረግ ወይም በሌላ በማንኛዉንም አቋም ልዩነት ሳያደርግ በአገሪቱ በሁሉም ሥፍራ በእኩልነት፣ተገማች እና ወጥ በሆነ አግባብ ተፈጻሚ እንዲሆን ለማድረግ፤እንዲሁም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 4 ስር ከተደነገገዉ ልዩ ሁኔታ ዉጭ በወንጀል አድራጊዎች መሀከል ልዩነት ሳይደረግ ሕጉን ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ የወንጀል ሕግ ማስፈጸሚያ ሥነ ሥርዓት ሕጉን የማዉጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ ብዬ አምናለሁ፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሎች ምክር ቤቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/5 ስር በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሠረት በፌዴራሉ የወንጀል ሕግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የወንጀል ሕግ ሲያወጡ በዚህ ሥልጣናቸዉ የሚያወጡትን የወንጀል ሕግ ለማስፈጸም የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን አላቸዉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በጠቅላላዉ በተለይ ደግሞ የፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የሚወሰነዉ በሥነ ሥርዓት ሕግ(ኮድ)፣ በፍርድ ቤቶች አዋጆች እና አንድን ድርጊት ወንጀል አድርገዉ በሚደነግጉና ሥነ ሥርዓታዊ ባህሪይ ባላቸዉ ልዩ ልዩ ሕጋጋት ነዉ፡፡በዚህ መሠረት በነባሩና በ1954 በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1/1954 (ከዚህ በኋላ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ተብሎ የሚጠቀስ) አባሪ በሆነዉ አንደኛ ሠንጠረዥ ላይ አገራችን አሀዳዊ ሥርዓት በምትከተልበት ጊዜ የነበረዉን የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት በመከተል ለተደራጁ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ተደርጓል፡፡ በዚህ ሕግ በአባሪ ሠንጠረዥ አንድ የተመለከተዉን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ለማሻሻል በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 ላይ በሌሎች ሕጎች የተወሰነዉ የወንጀል ቅጣት ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጣ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን እንደሚኖረዉና ከአስር ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን ደግሞ የወረዳ እና የአዉራጃ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከላይ በተገለጸዉ መሠረት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል የሚያደርገዉን ነባሩን የሥነ ሥርዓት ሕግ የሚያሻሽል ሕግ ማዉጣት ያለበት የፌዴራል ሕግ አዉጪ አካል ነዉ ወይስ የክልል ሕግ አዉጪ አካል የሚለዉ ጥያቄ መነሳትና ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡ ይህንን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ይህ ነባር የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ የእንደፌዴራል ሕግ የሚቆጠር ነዉ ወይስ እንደክልል ሕግ የሚቆጠር ነዉ የሚለዉን በቅድሚያ መመርመር ያስፈልጋል፡፡በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 2/3 ስር የፌዴራሉ መንግሥት ሕጎች ማለት ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑና በሕገ መንግሥቱ ላይ የተጠቀሱትን በፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን ክልል ስር ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ነባር ሕጎችን እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡በተመሳሳይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/2 ስር የፌዴራል መንግሥት ሕጎች ማለት በፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን ክልል ስር የሚወድቁ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡ከዚህ ትርጓሜ በመነሳትና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ያወጡት የማዕከላዊ መንግሥት የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ምክር ቤቶች በመሆናቸዉ፣ እነዚህን ምክር ቤቶች በዋናነት የተካዉ ምክር

ቤት በሕገ መንግሥቱ የተመለከተዉን የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ሥልጣን ክፍፍል ከግምት ማስገባት ሳይረሳ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሆኑ ከላይ በተገለጸዉ መሠረት የወንጀል ሕጉን የሚያስፈጽም ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሆኑ ነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ የፌዴራሉ መንግሥት ሕግ ነዉ፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50/5 መሠረት የክልል ምክር ቤት ሕግ የማዘጋጀት፣የማጽደቅና የማሻሻል ሥልጣን የሚኖረዉ በክልሉ ሥልጣን ስር የሆኑ ጎዳዮችን በሚመለከት ብቻ ነዉ፡፡ከዚህ ዉጭ የክልል ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ ለፌዴራል መንግሥት የተሰጠ ጉዳይ በተመለከተ በነባር ሕጎች የተደነገገዉን የሚያሻሽል፣ የሚለዉጥ ወይም የሚሽር ሕግ ማዉጣት አይችልም፡፡ በመሆኑም የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/5 መንፈስና ዓላማ መሠረት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠ ሥልጣን በመሆኑ ነባሩና አሁን በሥራ ላይ ያለዉ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ እንደ ፌዴራል ሕግ የሚቆጠር ስለሆነ የክልል ምክር ቤት ከክልል የወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ካልሆነ በስተቀር ይህንን ሕግ የሚያሻሽል፣የሚለዉጥ ወይም የሚሽር ሕግ ማዉጣት አይችልም፡፡

ወደተያዘዉ ጉዳይ ስመለስ በአመልካች ላይ የቀረበዉ ሦስተኛ ክስ አመልካች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49(2) በመተላለፍ የተሰጠዉን ፈቃድ የስኳር ንግድ ለመነገድ የማይፈቅድ ሆኖ እያለ ለስኳር ንግድ የተሰጠዉ ፈቃድ ያለዉ በማስመሰል እየተንቀሳቀስ እያለ ስለተያዘ በፈጸመዉ የሕገወጥ ንግድ መስራት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ የንግድ ሥራ የሚመለከት ሕግ ማዉጣት የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን ነዉ፡፡ይህ አመልካች የተከሰሰበት ሕግ የወጣዉም በፌዴራሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ፡፡ነገር ግን የክልል መንግሥት ንግድ ቢሮ የኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ መመሪያ ላይ የተደነገገዉን በመከተል የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠትና በሰጠዉ የንግድ ፈቃድ መሠረት የንግድ ሥራ እየተሰራ መሆን አለመሆኑን የመቆጣጠር አስተዳደራዊ ሥራ የመሥራት ሥልጣን በሕጉ ተሰጥቶታል፡፡

በሌላ በኩል በዚህ አዋጅ ላይ ሕግ አዉጪዉ በወንጀል የሚያስቀጡ ድርጊቶችን ደንግጓል፡፡ የጸና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖር በንግድ ሥራ መሠማራት ወይም በንግድ ሥራ ፍቃዱ እንዲሰራ ከተፈቀደዉ የንግድ ሥራ ዉጭ መሥራት ወንጀል እንደሆነና የሚያስቀጣዉም ቅጣት በዚሁ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ መልኩ የተደነገገዉ በፌዴራል ሕግ ላይ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ነገር ግን በአንዳንድ በፌዴራል መንግሥት በወጡ ሕግጋት ላይ ለአብነት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 139/1 ስር የግል ሥራ ክርክር የመዳኘት ሥልጣን ለክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደተሰጠ በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 ስር የተደነገገዉን ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን የየትኛዉ ፍርድ ቤት እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 980/2008 ላይ አልተደነገገም፡፡ ሆኖም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 ስር ከተደነገጉት የወንጀል ጉዳዮች ዉስጥ ይህ ወንጀል በግልጽ ስላልተጠቀሰ በመርህ ደረጃ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከሚዳኙ የወንጀል ጉዳዮች ዉስጥ የሚካተት አይደለም፡፡ በልዩ ሁኔታ ግን ወንጀሉ የተፈጸመዉ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደር ከተሰጠ የንግድ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ወይም ፈቃድ ሳይኖር የንግድ ሥራ የተሠራዉ በእነዚህ የከተማ አስተዳደሮች ዉስጥ የሆነ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3(1/ሀ እና ሐ) እና 12/2 እንዲሁም አንቀጽ 15/2 ስር በተደነገገዉ መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይሆናል፡፡

በዚህ ጉዳይ አመልካች ወንጀል ፈጽመ የተባለዉ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት የሰጠዉ የንግድ ፈቃድ ከሚፈቅድለት ማዕቀፍ ዉጭ የንግድ ሥራ ሠርቷል በሚል በመሆኑ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ሊታይ የሚችል የወንጀል ጉዳይ ነዉ፡፡ነገር ግን የክልሉ ፍርድ ቤቶች በፌዴራል መንግሥት በወጣ ሕግ ላይ የተደነገገዉን የወንጀል ክስ ክርክር ተቀብለዉ ሲዳኙ ድርጊቱን ወንጀል አድርጎ በደነገገዉ ልዩ ሕግ ላይ ስለዳኝነት ሥልጣንና ስለሚመሩበት ሥነ ሥርዓት በግልጽ ያልተደነገገ እንደሆነ በነባሩ

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ (ማሻሻዉን ጨምሮ) ላይ የተደነገገዉን የፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል እና ስለክርክር አመራር የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት መከተል ይጠበቅባቸዋል፡፡ምክንያቱም ክልሎች በፌዴራሉ የወንጀል ሕግ የተደነገገዉን ወይም በልዩ ሕግ የተደነገገዉን የወንጀል ጉዳይ ለመዳኘት የየራሳቸዉን አዲስ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ለማዉጣትም ሆነ ነባሩን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ለማሻሻል የሚያስችል ሥልጣን ስለሌላቸዉ እና ይህንን እንዲያደርጉ መፍቀድ የፌዴራል ሕግ በአገሪቱ ግዛት በሙሉ ተገማችና ወጥ በሆነ አግባብ እንዳይተገበር ስለሚያደርግ እና በሁሉም ዜጎች ላይ በእኩልነት ተፈጻሚ እንዳይሆን ስለሚያደርግ ነዉ፡፡

እንዲሁም በአመልካች ላይ በቀረበዉ ሦስተኛ ክስ የተጠቀሰዉ የአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነዉ፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሠንጠረዥ ለማሻሻል በወጣዉ ደንብ ቁጥር 17/1997 ላይ እንደተደነገገዉ በልዩ ሕጎች የተወሰነዉ ቅጣት ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጣ ሲሆን ክሱን ተቀብሎ ለመዳኘት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ያለዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 31/3 ስር እስከ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የመዳኘት ስረ ነገር ሥልጣን ለወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን በደንብ ቁጥር 17/1997 ከተደነገገዉ፣በሕገ መንግሥቱ ከተዋቀረዉ ዳኝነታዊ ፌዴራሊዝም እና ሕግ ከማዉጣት ጋር በተያያዘ የተደረገዉን የሥልጣን ክፍፍል እንዲሁም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3፣4፣12 እና 15 ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኝ የወንጀል ጉዳዮች እንደሆነ ከተደነገገዉ ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ሕግ አዉጪ አካል(ጨፌ) በዋናነት የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ ቁጥር 216/2011ን ያወጣዉ በክልል ጉዳዮች ላይ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሚኖራቸዉን የዳኝነት ሥልጣን ለመወሰን መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 31/3 ስር እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል የሚመለከት የሚቀርብ ክስ የመዳኘት ሥልጣን የወረዳ ፍርድ ቤት ነዉ ተብሎ የተደነገገዉ በክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን እንደሆነ ተቆጥሮ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ አንቀጽ 3፣ 4፣ 12 እና 15 ላይ በተደነገገዉ መሰረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ ወንጀሎች ናቸዉ ተብሎ በግልጽ ባልተመለከተ እና ለክልል ፍርድ ቤቶች የተተተወ የወንጀል ጉዳይ በሚመለከት፤ በፌዴራል ልዩ ልዩ ሕግጋት ላይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ ወንጀሎች ናቸዉ ተብሎ በግልጽ ባልተመለከተ የወንጀል ጉዳይ እና በነባር የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ (ማሻሻዉን ጨምሮ) የተደነገገዉን የፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል በማይቃረን አግባብ ድንጋጌዉ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካች ላይ ከተመሠረቱት ሦስት ክሶች መካከል አንደኛ እና ሁለተኛ የወንጀል ክሶች እንደቅደም ተከተላቸዉ በክልሉ ምክር ቤት የታክስ አስተዳደርን ለመወሰን የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 203/2009 አንቀጽ 125/1 እና በተመሳሳይ በክልሉ ምክር ቤት የተርን ኦቨር ታክስ ለማስከፈል የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 75/1995 አንቀጽ 26 በመተላለፍ የተከሰሰበት ወንጀል በመሆኑ የክልል ወንጀል ጉዳዮችን የሚመለከቱ ስለሆኑ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 31/3 መሠረት የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት እነዚህን ሁለቱን ክሶች የመዳኘት ሥልጣን ሥላለዉ እነዚህን ክሶች ከመዳኘት አንጻር የተፈጸመ ስህተት ስለሌለ በአብላጫ ድምጽ በተደረሰበት ድምዳሜ ከዉጤት አንጻር እስማማለሁ፡፡ነገር ግን ሦስተኛዉን የወንጀል ክስ በተመለከተ አመልካች ተላልፏል የተባለዉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 በፌዴራል መንግሥቱ የወጣ ሕግ በመሆኑ፣በዚህ ሕግ ወንጀል ነዉ ተብሎ የተደነገገዉ ተፈጽሞ ሲገኝ የሚዳኝበት አግባብ በመላዉ አገሪቱ ግዛት እና በሁሉም ዜጎች ላይ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 3 እና 4 ስር በተደነገገዉ መሠረት የእኩልነትና የተገማችነት መርህን ባከበረ መልኩ በወጥነት ተፈጻሚ መሆን ስለሚገባዉ የፌዴራሉ

የሕግ አካል በሆነዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ (ማሻሻዉን ጨምሮ) የተደነገገዉን በተከተለ አኳኋን ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ቀርቦ መታየት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ፈጽሟል ተብሎ የተከሰሰበት ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ላይ እንደተመለከተዉ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሠንጠረዥ ለማሻሻል በወጣዉ ደንብ ቁጥር 17/1997 ላይ በተደነገገዉ መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ሳይሆን የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ነዉ፡፡ስለሆነም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና 10(1/ሐ) መሰረት የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎ የዳኘዉ የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ሳይኖረዉ ነዉ ተብሎ ሊሻር ይገባል ብዬ ስለማምን በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

## 10.2 የንግድ ዕቃዎችን ከመስመር ውጭ ማጓጓዝ[122]

- አንድ ተከሳሽ ማንኛውም የንግድ ዕቃን ከመበኛው የግብይት አሰራር ውጭ በማናቸውም ማጓጓዣ ከተፈቀደ የስርጭት መስመር ውጭ ሲያጓጉዝ የተያዘ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥበት፤ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆን አለመሆኑና ከመስመር ውጪ ሲጓጓዝ የነበረ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የማይገባው ስለመሆኑ፤ (የነጋዴዎች እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/)

የሰ/መ/ቁ 168067

ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
እንዳሻዉ አዳነ
ሃይሉ ነጋሽ
እትመት አሠፋ

**አመልካቾች:-** ሰይድ አሊ አበጋዝ

**ተጠሪ፡-** የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንግድ እና ሸማቾች ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

### ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 24 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0202449 ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 026018 ጥቅምት 05 ቀን 2011 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0323711 ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

---

[122]የሰ/መ/ቁ 168067 (ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 24

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶች ሁለት ሲሆኑ ይዘታቸውም 1ኛ ክስ አመልካች የንግድ ፈቃድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 01/09/2009 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 1:30 ሰዓት በባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ በሚባል ቦታ ግምቱ ብር 58500 የሆነ 9 ጥቅል ጂኦመምብሬን የሰሌዳ ቁጥሩ ኢ.አ-3-30687 በሆነ አይሱዙ መኪና በመጫን ለመሸጥ ኬላ ጥሶ ይዞ ሲሄድ በሕብረተሰቡ እገዛ መኪናውን በማስቆም እጅ ከፍንጅ ያለንግድ ፈቃድ ንግድ መፈጸም ወንጀል ተከሷል የሚል ሲሆን 2ኛ ክስ ደግሞ በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በነበሩት ላይ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና የንግድ ሕግ አንቀጽ 118/1/ እና የነጋዴዎች እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 13/09/2009 ዓ.ም በባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ በሚባል ቦታ አመልካች ባለሀብት በመሆን፤ የስር 2ኛ ተከሳሽ የሰሌዳ ቁጥሩ ኢ.አ 3-30687 የሆነው መኪና አሽከርካሪ በመሆን 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ የመኪናው ረዳት በመሆነ ጂኦመምብሬን 9 ጥቅል ግምቱ ብር 58500 የሚያወጣ የማዘዋወር ወይም የመደበቅ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

ክሱ አመልካቾች እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ አመልካች ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን ሆኖም የተያዘው ዕቃ የወንድሙ መሆኑን እና ንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የተከራከረ ሲሆን ሌሎቹ ተከሳሾችም ድርጊቱን የፈጸሙ መሆኑን ሆኖም አመልካች ንግድ ፈቃድ እንዳለው ስለገለጸላቸው ዕቃውን የጫኑ መሆኑን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች 1ኛ ክስን በተመለከተ መኪናው ጭኖ እየሄደ መያዛቸውን እንጂ እየነገደበት መሆኑን ያላስረዱ በመሆኑ አመልካች ከ1ኛ ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በነጻ ተሰናብቷል፤ 2ኛ ክስን በተመለከተ ግን ተከሳሾች ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለተረጋገጠባቸው እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ተከሳሾችም ክሱን ይከላከልልናል ያሉትን ማስረጃ አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀችን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የተያዘው ጅኦመምብሬን የአመልካች ወንድም መሆኑን እና አምጣልኝ ተብሎ የተላከ እና ይዞ ሲመለስ የተያዘ መሆኑን፤ ወንዱሙ የሚነግድበት እና ንግድ ፈቃድ ይዞ ፍ/ቤት በመሄድ ሲከራከር እንደነበር መመስከራቸው ምስክሮቹ ሀሰተኛ እና ተደራጅተው የቀረቡ መሆኑን መረዳት ይቻላል፤ አመልካች የዕቃው ባለንብረት በመሆን እና ንግድ ፈቃድ ስለሌለው የተያዘውን ዕቃ ወደ ፖሊስ እንደወሰዱት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የመሰከሩ በመሆኑ ተከሳሾች በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3 እና 43/3 መሠረት ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት በማስላት የእስር ቅጣቱን ወደ ገንዘብ ቅጣት በመለወጥ እና ከገንዘብ ቅጣቱ ጋር በመደመር አመልካች በብር 1500 የገንዘብ መቀጮ የስር ተከሳሾች ደግሞ እያንዳንዳቸው በብር 2000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ እና የተያዘው 9 ጥቅል ጂኦመምብሬን ተሸጦ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም አመልካች የተከሰስኩባቸው የአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ነጋዴ በሆነ ሰው ላይ ነው፤ አመልካች ከ1ኛው ክስ ነጻ የሆነው ነጋዴ አይደለም ወይም የንግድ ስራ አልሰራም ተብሎ ነው፤ በመሆኑም አመልካች ነጋዴ ሳይሆን ጥፋተኛ መባሉ ከሕግ ውጪ ነው፤ በአዋጁ አንቀጽ 24/4/ ድንጋጌ መሠረት ወንጀል የሆነው ተግባር እጥረት ያለበት መሆኑ በንግድ ሚኒስቴር በወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጸ የንግድ

ዕቃን ለግል ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚውል በላይ በሆነ መጠን ከተፈቀደው የስርጭት መስመር ውጪ ሚንንዝ ወይም እንዲንንዝ ማድረግ ነው፤ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ ጂኦሜምብሬን የተባለው ዕቃ የንግድ ሚኒስቴር ባወጣው ማስታወቂያ እጥረት ያለበት ስለመሆኑ መገለጹን አልጠቀሰም ይህንንም አላስተዳም፤ ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆኑ እና ከዚህ ከተፈቀደው መስመር ውጪ ሲንንዝ የነበረ መሆኑን አላረጋገጠም፤ በመሆኑም አመልካች በተገለጸው ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ ልባል አይገባም፤ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች ዕቃው የአመልካች ወንድም ንብረት መሆኑን እና ዕቃውን ወደ ወንድሙ እየወሰድኩ የነበረ መሆኑን በሚገባ አስረድተው ሳለ ፍ/ቤቱ ምስክርነቱ በሀሰት የተሰጠ ነው በማለት ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እና የንብረት ውርስ ውሳኔ በመሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት በአሁን አመልካች ላይ በቀረበው 1ኛ ክስ ጭኖ መሄዱ እንጂ እየነገደበት መሆኑን አልተረጋገጠም ተብሎ ነጻ ከተባለ በኋላ በ2ኛው ክስ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ጂኦመምብሬን የንግድ ሚኒስቴር በገበያ ላይ እጥረት አለባቸው በሚል በገለጻቸው እና ዋጋ እና የስርጭት ሁኔታቸውን በወሰናቸው የንግድ ዕቃዎች ውስጥ የተካተተ አይደለም፤ ይህ ዕቃ ምንም እንኳን በየደረጃው ያለ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል በሚል እንዲሁ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ቢሆንም በን/ው/ሽ/ጥ/አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 25 እና 26 መሠረት የንግድ ሚኒስቴር ጥናት አድርጎ ዋጋቸው እና የስርጭት ሁኔታቸው እንዲወሰን ለሚንስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ በማስፈቀድ በማስታወቂያ በገለጻቸው የንግድ ዕቃዎች ውስጥ የተካተተ ባለመሆኑ እና የአዋጁን አንቀጽ 24 በመጥቀስ የወንጀል ሀላፊነትን መወሰን የማይቻል በመሆኑ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የመሰለውን ቢወስን አንቃወምም የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፤ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር እና በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው የአመልካች አቤቱታ የቀረበው በሁለተኛው ክስ ጥፋተኛ መባሉን አስመልክቶ ሲሆን የክሱ ይዘትም አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ በመተላለፍ በቀን 13/09/2009 ዓ.ም ከባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ ከሚባል ቦታ አመልካች ባለሀብት በመሆን በሰሌዳ ቁጥሩ ኢ.አ 3-30687 በሆነ መኪና 9 ጥቅል ጂኦመምብሬን ግምቱ ብር 58500 የሚያወጣ አዘዋውሯል ወይም የመደበቅ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል በመሆኑ አመልካች የወንጀል ድርጊቱንን ፈጽመዋል ተብሎ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ በመተላለፍ ተጠያቂ መደረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በሙላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) ስር ተደንግጎአል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ፍሬ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው

ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህም ከሳሹን ወገን በወ/ሕ/አ. 23 (2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቶአል ሊባል የሚችለውም በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመለከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 በተመለተከው የማስረጃ መለኪያ መሰረት ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 142 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘት ሲታይም ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 በተመለከተው የማስረጃ መለኪያ መርህ መሰረት በበቂና አሳማኝ ሁኔታ አስረድቶ ሲገኝ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በመሰረታዊነት በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ማንኛውም የንግድ ዕቃን ከመደበኛውን የግብይት አሰራር ውጭ በማናቸውም ማጓጓዣ ከተፈቀደው የስርጭት መስመር ውጭ ሲጓጓዝ ከተገኘ እንደተከማቸ ወይም እንደተደበቀ የንግድ ዕቃ የሚቆጠር በመሆኑ ይህንን ሲያጓጓዝ የተገኘ ነጋዴ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የወንጀሉ ፍሬ ነገር የሆኑትን አመልካች ጂኦሜምብሬን የተባለው ዕቃ የንግድ ዕቃ መሆኑን አለመሆኑን፤ ከመደበኛው የግብይት አሰራር ውጭ ሲያጓጓዝ የተያዘ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት አልተረጋገጠም አመልካችና ተጠሪም በዚሁ ፍርድ ቤት ባደረጉት የጽሁፍ ክርክር የንግድ ሚኒስቴር ባወጣው ማስታወቂያ እጥረት ያለበት ስለመሆኑ አለመገለጹን፤ ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆን አለመሆኑንና ከዚህ መስመር ውጪ ሲጓጓዝ የነበረ መሆኑን አለመረጋገጡን ገልጸዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው አለመገኘታቸውን ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ይዘትና መንፈስ መሰረት የማስረዳት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ አመልካች እንዲከላከል መደረጉም ሆነ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸው ከተሰሙ በኃላም አልተከላከለም ተብሎ በወንጀሉ ጥፋተኛ ተደርገው እንዲቀጡ መወሰኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) እና በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ስር ከተመለከተው የማስረጃ ምዘና መርህ ጋር የማይሄድ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስናል፡፡

ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0202449 ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 026018 ጥቅምት 05 ቀን 2011 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0323711 ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ተላልፋል በማለት በቀረበበት 2ኛ ክስ ጥፋተኛ አይደለም ብለናል፡፡
3. በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ወሳኔ የተሻረ በመሆኑን የተወሰነበት የገንዘብ መቀጮ ብር 1500 / አንድ ሺህ አምስት መቶ/ ለመንግስት ገቢ ከሆነ ተመላሽ እንዲሆን ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

### 11.የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ[123]

### 11.1 ተጠርጣሪ በመረጠው የግል ሕክምና ተቋም የመታከም መብት[124]

- በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.184 መሠረት የትዕዛዝ ይግባኝ የሌለ ስለመሆኑ የተደነገገ ቢሆንም የተሰጠው ትዕዛዝ ወደፊት በዋናው ጉዳይ ላይ ከሚቀርበው ይግባኝ ጋር ተጠቃሎ ሊቀርብ የማይችልና ውጤቱም የሚቀለበስ ካልሆነ በጊዜያዊ ትዕዛዝ ላይ የተሰጠ ይግባኝ ነው በሚል ተቃውሞ የማይቀርብበትና በይግባኝ የሚታይ ስለመሆኑ፤
- ለእስረኞች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠው በማረሚያ ቤት ውስጥ በተዘጋጀ የጤና ተቋም ቢሆንም በሕግ ጥላ ስር የሚገኝ ተጠርጣሪ በጤና ተቋሙ ለመታከም እምነት የሌለው በመሆኑ በመረጠው የግል የሕክምና ተቋም አገልግሎት እንዲያገኝ በጠየቀ ጊዜ ይህንን ለማከናወን የፀጥታ ስጋት ቢኖርም መንግስት ጸጥታ እና ደሕንነትን በማስጠበቅ ተጠርጣሪው ህክምናውን እንዲያገኝ ሊያመቻች የሚገባ ስለመሆኑ፤

የሰ.መ.ቁ 203051

የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑሪዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ጀዋር ሲራጅ መሐመድ
2. አቶ በቀለ ገርባ ዳኮ
3. አቶ ሀምዛ አዳኔ ታዬ
4. አቶ ደጀኔ ጣፋ ገለታ

ጠበቆች መሐመድ ጀማል
ምስጋኑ ሙለታ
ቱሊ ባይሳ
ገመቹ ጉተማ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ፡- ዐ/ሕግ ምኞት ደነቀው - ቀረቡ

መዝገቡ በዛሬው ዕለት ሊቀርብ የቻለው የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ ከሰጠ በኂላ አመልካቾች የመልስ መልስ መስጠት አያስፈልገንም በቀረበው መሠረት ታይቶ ይወሰንልን በማለታቸው መዝገቡ በችሎት ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በማቅረቡ ነው፡፡ የአመልካቾች ጠበቆች በዛሬ ዕለት በችሎት ቀርበው ደንበኞቻቸው በጤና ችግር ምክንያት በሞት እና በሕይወት መካከል የሚገኙ መሆኑን ገልጸው በአስቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩ ሕክምና ከማግኘት መብት ጋር የተገናኘ እና ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ አለመሆኑን ግንዛቤ በመውሰዱ በዛሬ ዕለት መዝገቡን መርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

---

[123]የፌደራል ማረሚያ ቤት አዋጅ ቁጥር 1174/2012

[124]የሰ/መ/ቁ 203051 (የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25

<u>ፍርድ</u>

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት የካቲት 18 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 202289 በቀን 16/06/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በሕግ ጥላ ስር የሚገኝን እስረኛ ሕክምና ጉዳይ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካቾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የካቲት ባቀረቡት አቤቱታ የግል ሐኪሞቻቸው በአስቸኳይ ሆስፒታል ሄደው መታከም እንዳለባቸው ያሳወቁ ቢሆንም ማረሚያ ቤቱ አመልካቾች የግል ሐኪም ቤት ሄደው እንዳይታከሙ በመከልከሉ ምክንያት ሕክምናቸው የተቋረጠ እና ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡ መሆኑን በመግለጽ ማረሚያ ቤቱ አመልካቾች በመረጡት የግል የጤና ባለሙያ እና የሕክምና ተቋም የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ትዕዛዝ ይሰጥላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ጠበቆቻቸውን በችሎት አስቀርቦ ከጠየቀ በኋላ ማረሚያ ቤቱ የካቲት 02 ቀን 2013 ዓ.ም ባመለከተው መሠረት አመልካቾች ለመታከም ፈቃደኛ ካልሆኑ እና የሚጠቅሱት ሆስፒታል ለሕዝብ እና ለደህንነት ስጋት የሚፈጥር ከሆነ ጦር ሀይሎች ሆስፒታል እንዲያሳክማቸው ያዘዘ ሲሆን በዛሬው እለት አመልካቾች የግል ሐኪም ቤት በመግለጽ ሕክምና እንዲደረግላቸው የጠየቁ እና የሕክምና ማዕከሉ የታወቀ በመሆኑ ማረሚያ ቤቱ አመልካቾችን አዲስ አበባ ከተማ ሜክሲኮ አካባቢ በሚገኘው ላንድ ማርክ ጄነራል ሆስፒታል በአጃቢ አስፈላጊውን ጥበቃ ተደርጎ ሕክምና እንዲደረግላቸው እንዲወስዳቸው ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ኢትዮጲያ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሕገ መንግስቱን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ትችት ከሰጠ በኋላ አዋጅ ቁጥር 1174/2012 እስረኞች ወደ ግል ሆስፒታል እንዳይሄዱ ገደብ ያልጣለ እና ገደቡ ከመንግስት አቅም እና የማሟላት ግዴታ አኳያ ብቻ እንጂ ከእስረኞች የግል አቅም አኳያ የማይገደብ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ አመልካቾች በግል ሕክምና ተቋም አገልግሎት እንዳያገኙ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በሌላ በኩል ተጠሪ ከጸጥታ ችግር አኳያ የሚያቀርበው ክርክር ዝቅተኛ ግምት ሊሰጠው አይገባም፤ አመልካቾች ከተከሰሱበት የእርስ በእርስ ግጭት ማስነሳት አኳያ እና ዓቃቤ ሕግ በይግባኙ ላይ ካቀረበው ለሕብረተሰብ እና ለአመልካቾች የደህንነት እና የጸጥታ ስጋት እንዲሁም ከነባራዊው ሁኔታ አኳያ ለአመልካቾች እና ለሕብረተሰቡ ደህንነት ሲባል በላንድ ማርክ ሆስፒታል የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የተሰጠው ትዕዛዝ አማራጭ የለውም፤ የሕክምና አገልግሎት በታካሚው ዘንድ ተቀባይነት ያለው እና የሚፈለገውን ውጤት የሚያመጣ መሆን አለበት፤ በመረጡት ሐኪም ሕክምና ማግኘት የታካሚው መብት ከመሆኑ አኳያ ያለፍላጎታቸው ይልቁንም ከፍተኛ ስጋት ያላቸው በመሆኑ በመንግስት የሕክምና ተቋም አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተመራጭ አይደለም፤ ስለሆነም ከግራ ቀኙ ከተነሳው ክርክር አኳያ አመልካቾች የመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ፈቃደኝነት እና ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ የህክምና ሙያው በሚፈቅደው ደንብ መሠረት የሀኪሞች ቡድን በማደራጀት አመልካቾች ባሉበት በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ውስጥ ሙሉ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጣቸው በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ዓቃቤ ሕግ ለስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ በጊዜያዊ ትዕዛዝ ላይ የቀረበ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 መሠረት ተቀባይነት የለውም፤ ተጠሪ የመጀመሪያው ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ በ15 ቀን ውስጥ ይግባኝ እንደሚል ያላሳወቀ በመሆኑ ያቀረበው

ይግባኝ በጊዜ ገደብ የሚታገድ ነው፤ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደህንነት ችግር መኖሩን በማስረጃ ሳያረጋግጥ በላንድ ማርክ ሆስፒታል የህክምና አገልግሎት ቢሰጣቸው በአመልካቾች ላይ የጸጥታ ስጋት ይፈጠራል ማለቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች በመረጡት የግል ሐኪም የመታከም ሕገ-መንግስታዊ መብት አላቸው፤ የላንድ ማርክ ሆስፒታል ለንግድ የተቋቋመ እና በአንድ ቦታ የቆመ ድርጅት ሆኖ ሳለ ሆስፒታሉ ተነቅሎ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንዲገባ የተሰጠው ትእዛዝ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች በሚገኙበት ማረሚያ ቤት ሕክምናውን እንዲያገኙ ቢደረግ የተለያዩ የሕክምና መሳሪያዎች የሚያስፈልጉ ሲሆን እነዚህ መሳሪያዎች ደግሞ ለሕክምና በሚያመች መልኩ በሕክምና ተቋሙ ውስጥ የሚገኙ እንጂ እየተነቀሉ የሚሄዱ አይደሉም፤ ላንድ ማርክ ሆስፒታል ማረሚያ ቤት ድረስ በመሄድ ለአመልካቾች ሕክምና መስጠት እንደማይችል ያሳወቀ በመሆኑ የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ሊፈጸም የማይችል ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ሕክምና በተመለከተ የላንድ ማርክ ሆስፒታል የህኪሞች ቡድን በማደራጀት ባሉበት ማረሚያ ቤት ውስጥ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጣቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22/1 እና ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፍሬ ነገር ክርክር የሚመለከት በመሆኑ ይህ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ የአመልካቾችን የሕክምና ጉዳይ በሚመለከት የመጨረሻ ትዕዛዝ በመሆኑ በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ በሚቀርብ ጊዜ ተጠቃሎ የሚቀርብ አይደለም፤ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 21/2 የታሰሩ ሰዎች ከሀኪሞቻቸው ጋር የመገናኘት መብት ያላቸው ቢሆንም በጥቅሉ የተቀመጠ ነው፤ በፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ ቁጥር 1174/2012 አንቀጽ 37 መሠረት ለእስረኞች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠው በማረሚያ ቤት ውስጥ የተዘጋጀ የጤና ተቋም ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ላይ በማረሚያ ቤቱ የሚገኘው እስረኛ የጤና ሁኔታ በጤና ተቋሙ ከሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት አቅም በላይ የሆነ ሕክምና የሚጠይቅ ሲሆን በኮሚሽኑ በጤና ተቋሙ ባለሙያዎች በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት ወዲያውኑ ተገቢውን ጥበቃ በመመደብ እስረኛው ያስፈለገውን የሕክምና አገልግሎት ሊሰጥ ወደሚችል የመንግስት ሆስፒታል በመውሰድ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ያደርጋል ይላል፤ አመልካቾች በመንግስት ሕክምና እምነት የለንም በማለታቸው የግል ሐኪማቸው እንዲያክሚቸው ሲደረግ የቆየ ሲሆን በሕገ መንግስቱ የተሰጣቸው በግል ሐኪም የመጎብኘት መብት በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ሆነው በግል ሐኪማቸው የመታየት መብትን የሚሰጥ ነው ከሚባል በቀር ያለባቸው የጤና ችግር በተቋሙ ከሚሰጠው የሕክምና አቅም በላይ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በሌላ የሕክምና ተቋም እንዲታከሙ የሚያደርግ አይደለም፤ ሕክምናውን የሚሰጠው የላንድ ማርክ ሆስፒታል ሕክምናውን ለመስጠት የተለያዩ መሳሪያዎችን ማጓጓዝ ይጠይቃል አላለም፤ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ የአሁን ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች በመረጡት ላንድ ማርክ ሆስፒታል ሕክምና እንዲደረግላቸው በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡ በሌላ በኩል ግራ ቀኙ በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ሆነ በዚህ ችሎት ካደረጉት ክርክር ይዘት መገንዘብ የቻልነው አመልካቾች በመረጥነው የግል ሐኪም ልንታከም ይገባል በማለት የሚከራከሩት በመንግስት የሕክምና ተቋም ብንታከም ከፍተኛ የሆነ ስጋት አለን በሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች በላንድ ማርክ ሆስፒታል /በግል የሕክምና ተቋም/

እንዲታከሙ ቢደረግ የጸጥታ ስጋት አለኝ የሚል መሆኑን ነው፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደተመለከትነው በቅድሚያ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ አመልካቾች በላንድ ማርክ ሆስፒታል እንዲታከሙ ሲል የተሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ የሚባልበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ዓቃቤ ሕግ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች በላንድ ማርክ ሆስፒታል እንዲታከሙ ሲል የሰጠውን ትዕዝዝ በዋነኝነት የሚቃወመው የጸጥታ ችግር ሊፈጠር ይችላል በሚል በመሆኑ እንደ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ቢፈጸም እና ምናልባትም ዓቃቤ ሕግ ሊፈጠር ይችላል ብሎ የሰጋው የጸጥታ ችግር ቢከሰት ይህንኑ የተፈጠረውን የጸጥታ ችግር ወደፊት በዋናው ጉዳይ ላይ ከሚያቀርበው ይግባኝ ጋር አጠቃሎ ሊያቀርበው የሚችል ባለመሆኑ ውጤቱ የሚቀለበስ አይደለም፡፡ ስለሆነም ዓቃቤ ሕግ ይግባኝ የጠየቀበት ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 በተገለጸው አግባብ ይግባኝ የማይጠየቅበት ነው በማለት በአመልካቾች በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች በመረጡት ሐኪም ሕክምና ማግኘት የታካሚው መብት ከመሆኑ አኳያ ያለፍላጎታቸው ይልቁንም ከፍተኛ ስጋት ያላቸው በመሆኑ በመንግስት የሕክምና ተቋም አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተመራጭ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በኋላ ተጠሪ ከጸጥታ ችግር አኳያ የሚያቀርበው ክርክር ዝቅተኛ ግምት ሊሰጠው አይገባም በማለት አመልካቾች የመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ፈቃደኝነት እና ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ የህክምና ሙያው በሚፈቅደው ደንብ መሠረት የሀኪሞች ቡድን በማደራጀት አመልካቾች ባሉበት በቃሊት ማረሚያ ቤት ውስጥ ሙሉ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጣቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን ቀጥለን እንመልከት፡፡

የዓቃቤ ሕግ ዋነኛ ስጋት አመልካቾች በመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል እንዲታከሙ ቢደረግ የጸጥታ ስጋት አለኝ የሚል መሆኑን በተለይም በስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ የዓቃቤ ሕግ ስጋት የመነጨው አንድም ዓቃቤ ሕግ ምናልባትም ሊፈጠር ይችላል በሚለው የጸጥታ ችግር ምክንያት ተጠርጣሪዎቹ ቢያመልጡ ወይም በተጠርጣሪዎቹ ላይ አደጋ ቢደርስ በፍትሕ ስርዓቱ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ከወዲሁ በመገመት መሆኑን ይህ ችሎትም ይገነዘባል፡፡

በመሠረቱ የመንግስት ዋነኛ ሚና የሕዝቦችን ሰላም እና ደህንነት ማረጋገጥ እና ማስጠበቅ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት መንግስት በፍትሕ ስርዓቱ ውስጥ የሚያልፉ ተጠርጣሪዎች ሰላም እና ደህንነት የማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ይህ ግዴታም ተጠርጣሪዎቹ በማረሚያ ቤት በሚገኙበት ጊዜ፣ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት እና ወደ ሕክምና ተቋማት በሚሄዱበት ጊዜ ሁሉ በጥብቅ ሊተገበር የሚገባው ነው፡፡ ይህን ካልን ዘንዳ በሕግ ጥላ ስር የሚገኝ ተጠርጣሪ ሕክምና ባስፈለገው ጊዜ ሁሉ ሕክምና እንዲያገኝ መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ ማሟላት ያለበት መንግስት እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 1174/2012 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካቾች በላንድ ማርክ ሆስፒታል ሊታከሙ ይገባል በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ ዓቃቤ ሕግ ለዚህ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ የለም፡፡ ይልቁንም ዓቃቤ ሕግ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የሚከራከረው የጸጥታ ችግር ስጋት ሊኖር ይችላል በሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ባስቀመጠው አማራጭ መሠረት ሕክምናውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ የተላለፈለት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ማረሚያ ቤት ድረስ ሄጄ አመልካቾችን አላክምም ብሏል በማለት በአመልካቾች በኩል የቀረበውን ክርክር በግልጽ በመካድ ከዓቃቤ ሕግ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወሰደው አማራጭ ተፈጻሚ ሊሆን የማይችል መሆኑን ይህ ችሎት ግንዛቤ ወስዷል፡፡

በሌላ በኩል በአገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በማረሚያ ቤት የሚገኝ ተከሳሽ ወደ ሕክምና ተቋሙ ሄዶ አገልግሎቱን የሚያገኝበት አሰራር እንጂ የሕክምና ተቋሙ ራሱ በማረሚያ ቤት የሚገኝ ተከሳሽ ባለበት ማረሚያ ቤት ሕክምናውን ለመስጠት የሚያስችሉ መሣሪያዎችን ይዞ በመሄድ ተንቀሳቃሽ

ሕክምና ሊሰጥ የሚችልበት አሰራር የሌለ በመሆኑ እና በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነን አካል በአማራጭ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሕክምና ቡድኑን በመያዝ ሕክምናውን በማረሚያ ቤቱ ተቋም ሄዶ ባይሰጥ ሌላ አማራጭ ያልተቀመጠ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊፈጸም የማይችል እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም መንግስት ሊፈጠር ይችላል ያለውን የጸጥታ ስጋት ለማስወገድ ተገቢውን የጸጥታ እና ደሕንነት ማስጠበቅ ሃላፊነቱን በመወጣት አመልካቾች ቀድሞ በመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ሕክምናውን እንዲያገኙ እንዲያደርግ በማለት ወስነናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 202289 በቀን 16/06/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. መንግስት ሊፈጠር ይችላል ያለውን የጸጥታ ስጋት ለማስወገድ ተገቢውን የጸጥታ እና ደሕንነት ማስጠበቅ ሃላፊነቱን በመወጣት አመልካቾችን ቀድሞ በመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ሕክምናውን እንዲያገኙ እንዲያደርግ በማለት ተወስኗል፡፡
   መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አስራ ሁለት

## 12.የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ[125]

### 12.1 የምዝገባ ጊዜ ሳይጠናቀቅ የጦር መሳሪያ መያዝ የወንጀል ተጠያቂነት[126]

- የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ መሠረት ይህ አዋጅ ወጥቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በፊት በፈቃድም ሆነ ያለፈቃድ የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአዋጁ ለፈቃድ ማውጫ በተቀመጠው አንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ እንዲሁም በተለምድ የጦር መሳሪያ የሚያዝባቸዉ አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ እና ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የጦር መሣሪያ የያዙ ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 8(1) መሰረት እንዲያስመዘግቡ በተፈቀደዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ የአዋጁን አንቀጽ 4፣ 22(2)፤ እንዲሁም 22(3) ድንጋጌዎች በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስላለመሆኑ፤[127]
- ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 205727 እና 205827 መዝገቦች ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ተለውጧል፡፡[128]

ሐምሌ 28 2015 ዓ.ም

የሰ.መ.ቁ 239711 እና የሰ.መ.ቁ 233141

---

[125]የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012

[126]የሰ/መ/ቁ 239711 እና የሰ.መ.ቁ 233141 (ሐምሌ 28 2015 ዓ.ም) ቅፅ 26

[127]በሰ/መ/ቁ 229400( ሕዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁጥር 251113 (ጥር 30 ቀን 2017 ዓ/ም)

[128]በሰ/መ/ቁ 205727 (ጥቅምት 29/2014 ዓ.ም) ቅፅ 25 እና 205827 (ሕዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም)

ዳኞች፡- ቴዎድሮስ ምሕረት

አበባ እምቢአለ

እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

በሰ.መ.ቁ 239711 አመልካች፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር

ተጠሪ፡ አቶ ካሳሁን ግዛቸው - የቀረበ የለም

በሰ.መ.ቁ 233141 አመልካች፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር - አልቀረበም

ተጠሪ፡ አቶ ኢሳያስ መኮንን- ጠ/ አበበ መንግስቱ - ቀረቡ

በሰ.መ.ቁ 239711 እና በሰ.መ.ቁ 233141 ላይ የሰበር ትርጉም የሚሻው ጭብጥ አንድ በመሆኑ ሁለቱም መዛግብት ተጣምሮ ተመርምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የክርክሩ አመጣጥ በሰ.መ.ቁ 239771 ላይ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 268279 በ29/10/14 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 231725 በ7/2/15 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል እና በሰበር መዝገብ ቁጥር 233141 ላይ ደግሞ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 278868 በ12/7/14 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 225404 በ24/9/14 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የሰበር አቤቱታ በመቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕግጋት እና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይንም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሣሪያ የሚጠቀሙ ሰዎች ለምዝገባ በተሰጠው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችል መሆን/አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 239711 አቶ ካሳሁን ያዛቸው ላይ የመሰረተው ክስ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4(2) እና 22(3) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ በክሱ በተመለከተው ጊዜ እና ቦታ የውግ ቁጥር የሌለው አውቶማቲክ ሲ.ኤ.ኤል.ኤም 8 የሆነ መሣሪያ ከ05 (አምስት) መሰል ጥይቶች ጋር ይዞ በመገኘቱ እንዲሁም በፍርድ ቤት ብርበራ ትዕዛዝ ቤቱ ሲፈተሽ አምስት ፍሬ የሽጉጥ ጥይቶችን አስቀምጦ ተገኝቷል የሚል ሲሆን፤ በሰ.መ.ቁ 233141 በሆነው መዝገብ ደግሞ በአቶ ኢሳያስ መኮንን ቸኮል ላይ የቀረበው ክስ ከላይ የተገለጹትን የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በክሱ በተጠቀሰው ቀን፤ ጊዜ እና ቦታ መኖሪያ ቤቱ ሲፈተሽ ህጋዊ ፈቃድ ካለው ማካሮቭ ሽጉጥ የውግ ቁጥሩ ዲ 06283 የሆነ ከመሰል 8 ጥይቶች እና አንድ ካርታ ጋር ፈቃድ የሌላቸው ሌላ 31 ፍሬ የሽጉጥ ጥይቶች እና አንድ ካርታ ጋር ይዞ የተገኘ በመሆኑ በፈጸመው ብዛት ያለው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት ወንጀል ተከሷል በሚል ቀርቦባቸዋል፡፡

በሰበር መዝገብ ቁጥር 233141 ተጠሪ የሆኑት አቶ ኢሳያስ መኮንን የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከተው አንድ ዓመት የመመዝገቢያ የእፎይታ ጊዜ ከማለቁ በፊት ልከሰስ አይገባም በማለት ያቀረቡትን የክስ መቃወሚያ የመረመረው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 1177/2012 በሥራ ላይ የዋለው ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን መሳሪያው በተጠሪ እጅ የተገኘው ታህሳስ 10 ቀን 2013 ዓ.ም ነው፡፡ አዋጁ ምዝገባ ያልተደረገላቸው የጦር መሳሪያዎችን በተመለከተ

ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ የእፎይታ ጊዜ የሰጠ በመሆኑ የተሰጠው የመሸጋገሪያ ጊዜ ሳያልቅ በአዋጁ ስር ክስ መቅረብ የለበትም በማለት በወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 130(2)(ሐ) መሰረት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

በሰ.መ.ቁ 239711 አቶ ካሳሁን ግዛቸውም ክሱ ደርሷቸው የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ ዐቃቤ ሕግም ክሴን ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን በሰነድ ማስረጃነትም ተጠሪ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 27(2) እና 35 መሠረት የሰጡትን ቃል አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም ባደረገው ምርመራ፡- በክሱ ላይ በተገለፀው ጊዜ እና ቦታ ተጠሪ የተባለውን ሽጉጥ እና ጥይቶች ይዞ መገኘቱ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ፤ ተጠሪ ሽጉጡንና ጥይቶቹን ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ መያዙን የሰጠው የዕምነት ቃል ያስረዳል፡፡ በተጠሪ እጅ የተገኙት ሽጉጥ እና ጥይቶች ፈቃድ አልወጣባቸውም፡፡ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ ሳይኖራቸው መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚቋቋመው ተቆጣጣሪ ተቋም ፈቃድ መውሰድ ያለባቸው መሆኑና በተጠቀሰው ጊዜ ፈቃድ ያላገኙ ሰዎች የያዙት የጦር መሣሪያ ለተቆጣጣሪው ተቋም ማስረከብ እንዳለባቸው የሽግግር ግዜ በአዋጁ ቁጥር 23 (1), (2) እና (3) ሥር ተደንግጓል፡፡ የጊዜ ሰሌዳ የተሰጠው ለመመዝገቢያ እና ፈቃድ መውሰጃ የሽግግር ወቅት በመሆኑ የእፎይታ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንበት ዕድል አይኖርም፡፡ ተጠሪ ፈቃድ የሌለው የጦር መሣሪያ ይዟል ተብሎ ክስ የቀረበበት ሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም አዋጁ ከወጣ በአምስት ወር ግዜ ውስጥ ሆኖ የአንድ ዓመት ግዜ ሊጠናቀቅ ሰባት ወር ሲቀረው በመሆኑ የወንጀል ተጠያቅነት የለበትም፡፡ ዐቃቤ ሕግ እንደ ክስ አመሰራረቱ የተጠሪ ድርጊት ወንጀል መሆኑን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ አላስረዳም በማለት በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 141 መሠረት መከላከል አያስፈልገውም በሚል በብይን በነፃ አሰናብቶታል፡፡

አመልካችም በሁለቱም መዛግብት ላይ የተሰጠውን ብይን በመቃወም ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመሠረዙ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አስቀድሞ በሰ.መ.ቁ 205727 እና 205827 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጣረስ ፤ የአዋጁ ዓላማ ለብዙሐኑ ደህንነት ሲባል ያለፈቃድ በግለሰቦች እጅ ገብተው የሚገኙ የጦር መሣሪያዎችን መዝግቦ ህጋዊ የቁጥጥር ስርዓትን መዘርጋት ሆኖ እያለ በአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማንኛውም ግለሰብ ያለጠያቂ ህገ ወጥ የጦር መሳርያ ይዞ መንቀሳቀስ ይችላል በሚል የተሰጠው ብይንና ውሳኔ የአዋጁን አላማ ስለሚቃረን በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) (ለ) ድንጋጌ መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በሚል ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 205727 እና በመ.ቁ 205827 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔዎች አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በአዋጁ በግልጽ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳያልፍ ክስ መቅረቡ የህጋዊነት መርህን የሚጣረስ ከመሆኑም በላይ አመልካች የጠቀሳቸው አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎች ከተያዘው ጉዳይ ጋር የማይገናኙ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ሆኖ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የሰ.መ.ቁ 2331141ን በተመለከተ ተጠሪ በ24/6/15ዓ.ም በተጻፈ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26(1) መሰረት ቀድሞ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 205827 በሰ.መ.ቁ 205727 በተሰጠ አስገዳጅ ውሳኔ የተሰጠ የህግ ትርጉም እንዲሻሻል ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲታይ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት በችሎቱ ታምኖበት እንዲሁም በሰ.መ.ቁ 239711 ላይ አከራካሪው ጭብጥ በሰ.መ.ቁ 233141 ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ምክንያት ሁለቱም መዝገቦች ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ታይተው ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 በሥራ ላይ ከዋለ በኂላ ባለው የአንድ ዓመት ግዜ ውስጥ ሕጉ ከመውጣቱ በፊት የፀና ፈቃድ ሳይኖራቸው በግለሰብ ደረጃ ሊያዝ የሚችል የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘት የአዋጁን አንቀጽ 4(2) እና 22(3) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት ማስከተል አለማስከተሉን በጭብጥነት በመያዝ የሥር ፍርድ ቤቶች ብይንና ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ለማውጣት ካስፈለገበት ምክንያቶች ውስጥ ከፊሉ ግለሰቦች የታጠቋቸው የጦር መሣሪያዎች ህብረተሰቡን ሰላም እና ፀጥታ ለማስጠበቅ ተግባር የሚውሉበትን ዕድል መፍጠር መሆኑን ፤በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ሕግ በመደንገግ ወጥነት ያለው ሥርዓት መፍጠር መሆኑን፤ ሀገራችን ያፀደቀቻቸው ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ቁጥጥርን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማስፈፀምና ዓለማቀፍ ትብብር ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓትን መዘርጋት በማስፈለጉ እንደሆነ ከአዋጁ መቅድም(Preamble) መረዳት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድና በታላላቅ ሀይቆች አካባቢ ሕገ ወጥ ትናንሽና ቀላል የጦር መሣሪያዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በናይሮቢ ከተማ ሚያዝያ 13 ቀን 1996 የተፈረመውን የናይሮቢ ፕሮቶኮል ለማጽደቅ አዋጅ ቁጥር 429/1997 ወጥቶ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ የጦር መሣሪያዎችን፤ መለዋወጫዎቻቸውንና አካሎቻቸውን እንዲሁም ፈንጂዎችን በሕገ ወጥ ማምረትንና ማዘዋወርን ለመከካከል የወጣው ፕሮቶኮልም አዋጅ ቁጥር 735/2004 ሆኖ ፀድቋል፡፡፡

ማንኛውም ሰው የፀና ፈቃድ ሳይኖረው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4 ሥር የተዘረዘሩትን ተግባራት መፈፀም ክልክል ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 22(2) ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ሰው በአዋጁ የተመለከተውን ክልከላ እና ግዴታ በመተላለፍ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የጦር መሳሪያ ፤ የጦር ሜዳ መነጽር ፤ በጦር መሳሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማንኛውም አይነት መነጽር ወይም የጦር መሳሪያ ሲተኮስ ድምጽ ለማስወገድ የሚያገለግል መሳሪያ ወደ ሀገር ያስገባ ፤ ከሀገር ያስወጣ ፤ያስቀመጠ ፤ የተገለገለ ፤ ያሳየ ፤ የደለለ ፤ የሸጠ ፤ የገዛ ፤ ያጓጓዘ፤ ያመረተ ፤ ያሰለጠነ ፤ የጠገነ ወይም ያስወገደ ፤ በማናቸውም መንገድ ያስተላለፈ ወይም የያዘ እንደሆነ ከአንድ አመት እስከ ሶስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ እስከ አስር ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተፈጸመው ወንጀል ብዛት ባለው የጦር መሳሪያ ሲሆን ቅጣቱ ከስምንት አመት እስከ ሀያ አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከመቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ህጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች በአንድ አመት ግዜ ውስጥ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው የግዜ ሰሌዳ መሰረት በአካል ቀርበው ፈቃድ መጠየቅ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልተው በተቆጣጣሪ ተቋሙ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው በማለት ደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ፈቃድ ያላገኙ ሰዎች የያዙትን የጦር መሳሪያ ለተቆጣጣሪው ተቋም ማስረከብ አለባቸው በማለት ደንግጓል፡፡ አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደር፤ አጠቃቀም እና ቁጥጥር መመሪያ ከሀምሌ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ መዋሉን የመመሪያው ቁጥር 58 የሚያመለክት ሲሆን የጦር መሣሪያ ፈቃድ የሚሰጠው በአዋጁ አንቀጽ 7 እና በመመሪያው አንቀጽ 10 ሥር የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልቶ ለተገኘ ሰው ነው፡፡ ፈቃድ ሊሰጠው የሚገባው የጦር መሣሪያ ምንጩ መሣሪያ እንዲያመርት ወይንም እንዲሸጥ ፈቃድ ከተሰጠው ተቋም በግዥ የተገኘ ፤ ከመንግስት ግምጃ ቤት ፤ በዓለም ዓቀፍ ድርጅት ወይንም በውጪ ሀገር ተወካይ ወደ ሐገር ውስጥ የገባ ፤ በውርስ ፤

በሽልማት ወይንም በስጦታ የተገኘ ፤ አዋጁ ከመጽደቁ በፊት ተመዝግቦም ይሁን ሳይመዘገብ በሰው እጅ ተይዞ የነበረ፤ በተለያዩ የፀጥታ አካላት እጅ የሚገኝ እና በሕገ - ወጥ መንገድ ሲዘዋወር ወይም ተደብቆ የተገኘ ሊሆን እንደሚችል አንቀጽ 14 ያመለክታል፡፡ ለግለሰብ የሚፈቀደው የጦር መሣሪያ ዓይነት እና ብዛት በመመሪያው አንቀጽ 19 ሥር ተዘርዝሯል፡፡

የጦር መሣሪያ ለመታጠቅ ብቁ የሚያደርጉ ዝርዝር መስፈርቶችም በመመሪያው አንቀጽ 15 ሥር ተመላክቷል፡፡ በቀደሙት ሕጎች ላይ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ታስቦ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 1177/2012 በሕግ አውጪው ወጥቶ ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይገኛል፡፡ የአዋጁ ዓላማ በግለሰብ ደረጃ ሊያዝ የሚችልን የጦር መሣሪያ በፈቃድ በመያዝ የሕብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ተግባር እንዲውል ፈቃድ ሳይኖራቸው የጦር መሣሪያ የያዙ ፈቃድ ማግኘት ለሚችሉ ሰዎች ፈቃድ መስጠት ፤ ያለፈቃድ በግለሰቦች እጅ ተይዞ ከቆዩት የጦር መሣሪዎች በፈቃድ ሊያዝ የማይችለውን የጦር መሣሪያ በመሰብሰብ የነበረውን የሕግ ክፍተት በመሙላት ወጥነት ያለው የጦር መሣሪያ አያያዝ ሥርዓትን ለመዘርጋት ነው፡፡ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የጦር መሣሪያ ምንጩ በሕገ - ወጥ መንገድ የሚዘዋወር እና በሕገ - ወጥ መንገድ ተቀምጦ የተገኘ ሊሆን እንደሚችል ከአዋጁ እና መመሪያው ድንጋጌዎች ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል፡፡ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 1177/2012 ወጥቶ በሥራ ላይ የዋለው ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ቢሆንም ከላይ የተመለከቱ ተግባራት ፈጽሞ የሕጉን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ግዜ አስፈላጊ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 4 እና 22(2) ሥር የተመለከተው ክልከላ እና የወንጀል ተጠያቂነት አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎች እና አሰራሮች ሳይመዘገብ ወይንም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሣሪያ የያዙ ወይንም የሚጠቀሙ ሰዎች ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአዋጁ እና መመሪያው የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልተው ፈቃድ እንዲወስዱ የአዋጁ አንቀጽ 23(1) ደንግጓል፡፡ ስለዚህ አዋጁ ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በሥራ ላይ እንደዋለ በማግስቱ የፀና ፈቃድ ሳይኖራቸው የጦር መሣሪያ የያዙትን ሰዎች በወንጀል ተጠያቂ ከማድረግ በፈቃድ የጦር መሣሪያ ሊይዙ ለሚችሉ ሰዎች ፈቃድ ለመስጠት እና ፈቃድ ከማይሰጣቸው ሰዎች እጅ ደግሞ መሣሪያዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ግዜን ወስኖ የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር ሥርዓት ለመዘርጋት ያለመ ነው፡፡ አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ አስቀድሞ ያለፈቃድ የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎችን የአዋጁን አንቀጽ 4 እና 22(2) ድንጋጌዎች በመተላለፍ በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአዋጁ በተቀመጠው አግባብ ፈቃድ እንዳይወስዱ እንቅፋት ስለሚሆን በሕጉ የተመለከተውን የምዝገባ ሥርዓት ያሰናክላል፡፡

ከዚህ ቀደም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዐቃቤ ሕግ የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4(2)ን ጠቅሶ የመሰረተው የወንጀል ክስ በክልሉ በየደረጃው ጉዳዩን ባዩት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በመጨረሻ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በተሰጠ ውሳኔ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ የሌለውን የጦር መሳሪያ የያዙ ሰዎች መሳሪያውን አስመዝግበው ፈቃድ ለመውሰድ የሚችሉበትን የጊዜ ሰሌዳ ወስኖ ወደስራ ያልገባ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ጊዜ ውስጥ መሳሪያውን ይዞ መገኘቱ ወንጀል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ተከሳሽን በነጻ በማሰናበቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 205727 ላይ ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአዋጁን አንቀጽ 23(2)ን በመተርጎም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ *"…የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ከአዋጁ መሰረታዊ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የዚህ ድንጋጌ ዋናው ዓላማ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ መሳሪያውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የህጋዊነት ጥያቄ ለመጠበቅ እንጂ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ያለማንም ጠያቂ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመፍቀድ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው የጦር መሳሪያን አስመልክቶ ህጋዊ ፈቃድ ያለው ለመሆኑ አልያም ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ እያለ የተያዘ ስለመሆኑ እንዲሁም በመሳሪያው ላይ ፈቃድ*

*ያላወጣው ተቆጣጣሪ ተቋሙ ወደ ስራ ባለመግባቱ ነው በሚል ያቀረበው ክርክርም ሆነ ከዚህ አንጻር የተረጋገጠ ነገር በሌለበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአዋጁን ድንጋጌ ባልተገባ መንገድ ተርጉሞ ተጠሪን ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ ማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ።"* በማለት የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመሻር የስር የወረዳ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 205827 ላይ ሕዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ላይ *"...የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ከአዋጁ መሰረታዊ አላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የድንጋጌ ዋና አላማ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ መሳሪያውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የህጋዊነት ጥያቄ ለመጠበቅ እንጂ እስከ አንድ አመት ድረስ ያለማንም ጠያቂ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመፍቀድ አይደለም።"* በማለት የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመሻር የስር የወረዳው እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በተጠቀሱት መዛግብት ላይ በሰበር ችሎቱ የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2)ን አተገባበር በተመለከተ የተሰጠው ትርጉም ከአዋጁ ዓላማ እና ከሚከተሉት የወንጀል ሕግ መርሆዎች አንፃር እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የወንጀል ሕግ ዓላማ የሕዝቦችን ፤ የነዋሪዎችን ሠላም ፤ ደህንነት ፤ ሥርዓት ፤ መብት እና ጥቅም ማረጋገጥ ሆኖ ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎች እና ቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቅያ በመስጠት ፤ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ግዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ መሆኑን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 ያመለክታል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22(2) ፤ እንዲሁም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2(2) ስር ፍርድ ቤት አንድ ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይንም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ ካልተደነገገ በስተቀር ሊያስቀጣ እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ይህም የሕጋዊነት መርህ(Principle of Legality)አንደኛው መገለጫ እና የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርህ በመሆኑ በጥብቅ ተግባራዊ መደረግ የሚገባው ነው፡፡ በዚህ መሰረት ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ መመስረት የሚችለውም ሆነ ፍርድ ቤት የወንጀል ክሱን ሰምቶ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፍ የሚችለው ሕገ ወጥነቱና እና አስቀጭነቱ (ወንጀልነቱ) በሕግ የተደነገገውን ድርጊት ወይም አል ድርጊት በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሰረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ናቸው ተብሎ በሕጉ የተመለከተው ሕጋዊ ፤ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በውስጡ ያለ ሕግ ወንጀልም ሆነ ቅጣት አይኖርም የሚሉ መርሆች የያዘ ነው፡፡ የወንጀል ድርጊትን በማመሳሰል (by analogy) መፍጠርም አይቻልም፡፡ በሌላ ሕግ በተለየ መልኩ ካልተደነገገ በቀር የወንጀል ሕጉ መርሆች በሌሎች የወንጀል ድርጊት እና ቅጣት በሚደነግጉ ሕጎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 3 ያስረዳል፡፡ የወንጀል ሕግ የሰውን ማህበራዊ ኑሮ ደረጃን ፣ የዘርን ፣ የብሔርን ፣ የብሔረሰብን ፣ የቀለምን፣ የጾታን ፣ የቋንቋን ፣ሃይማኖትን ፣የፖለቲካን ወይም የሌላ አስተሳሳብን ፣ የሃብትን ፣ የትውልድን ወይም ሌላ አቋምን ልዩነት ሳያደርግ በእኩል ተፈፃሚ እንደሚሆን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 4(1) ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) ስር አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፍቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች በአንድ ዓመት ግዜ ውስጥ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በአካል ቀርበው ፈቃድ መጠየቅ እና መስፈርቱን በማሟላት ፈቃድ መውሰድ እንዳለባቸው ሲደነገግ አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ለሚኖረው ሕጉ

ከመጽናቱ በፊት ያለፈቃድ ወይንም በፈቃድ የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች አዋጁ ከፀና አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በወንጀል ተጠያቂ ሳይሆኑ ወደሕጋዊ ሥርዓት ለማስገባት ሕግ አውጪው በግልጽ አቋሙን መግለጹን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ሕጉ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አስቀድሞ ያለፈቃድ ለተያዘ የጦር መሣሪያ የወንጀል ተጠያቂነት እንዳይኖር ደንግጎ ሳለ የአንድ አመት ጊዜ ከማለቁ በፊት መሳሪያውን ለማስመዝገብ ሂደት ያልጀመሩ ሰዎች የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል በሚል ከላይ በተጠቀሱት ሁለቱም መዛግብት ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ከሕገ መንግስት አንቀጽ 22(2) ፣ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 ፣አንቀጽ 2(2) ፣ (3) ፣ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 23(1) እና (2) አንፃር እንዲሁም ሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 በተመለከተው አግባብ በሕጋዊ መንገድ መሣሪያ ለመታጠቅ ዝርዝር የአፈፃፀም ደንብ እና መመሪያ በማውጣት ወጥነት ባለው መልኩ በሥራ ላይ ለማዋል የተቀመጠው የአንድ ዓመት ግዜ ሳይጠናቀቅ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፍቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች በአንድ ዓመቱ ጊዜ ውስጥ መቼ እንደሚያስመዘግቡ ማወቅና መለየት አይቻልም፡፡ ይህንን የሚያውቀው መሳሪያውን ለማስመዝገብ የወሰነ ሰው ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሕጉ አስመዝጋቢው ላይ የጣለው ግዴታ የሌለ ከመሆኑም በላይ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ መቼ ማስመዝገብ እንዳለበት የሚወስነው መሳሪያውን ይዞ የሚገኘው ሰው ብቻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተሰጠው አንድ ዓመት ጊዜ ባሉት የመጀመሪያው ቀናት ለማስመዝገብ ሂደቱን የጀመረም ሆነ በዓመቱ መጨረሻ ወር ባሉት ቀናት መዝጋቢው አካል ያወጣውን የጊዜ ሰሌዳ ተከትሎ መሳሪያውን ለማስመዝገብ ሂደት ውስጥ የገባ ሰው ወይም አንድ አመት ጊዜ ሳያልፍ መሳሪያ ይዞ የተገኘ ሰው በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 በሕጋዊ መንገድ በፈቃድ ብቻ የጦር መሣሪያን ለመያዝ የተዘረጋውን ሕጋዊ ሥርዓት ጥሷል በሚል በአዋጁ አንቀጽ 23(2) መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖርበት አይገባም፡፡ የሕጋዊነት መርህ በውስጡ ከያዛቸው ሐሳቦች አንዱ ሰዎችን አስቀድሞ ማስጠንቀቅን ሲሆን በዚህ ሚዛን የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ሲመዘን የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ዜጎች ከአዋጁ በፊት በእጃቸው የያዙትን መሳሪያ እንዲያስመዘግቡ ማሳወቅና በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የማስመዝገብ ግዴታን መጣል ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ባይኖር ያልተመዘገበ የጦር መሳሪያ መያዝ ወይም መጠቀም የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችል የነበረ ሲሆን እንደ ግብ የተያዘው በዚህ መልክ የተያዘ የጦር መሳሪያ በሽግግር ጊዜው ውስጥ ወደ ሕጋዊ ስርዓት በማስገባት በሕጉ የታሰበውን ዓላማ ማሳካት ነው፡፡ ስለዚህ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተመዘገበ መሳሪያ መያዝ በራሱ ወንጀልን የሚያቋቁም ሳይሆን በሚወጣው የጊዜ ሰሌዳ የማስመዝገብ ግዴታን የሚጥል ነው፡፡ በተያዙት ሁለቱም ጉዳዮች የክሱ የሕግ መሰረት በሆኑት የአዋጁ አንቀጽ 4(2) እና 22(2) በግልጽ እንደተመለከተው የወንጀሉ መቋቋም የጸና ፈቃድ አለመኖርን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን በዚሁ አዋጅ ከአዋጁ መጽናት በፊት የተያዙ ነገር ግን ያልተመዘገቡትን መሳሪያዎች ለማስመዝገብ እና ፈቃድ ለማግኘት እንዲቻል የአንድ ዓመት የሽግግር ጊዜ ተሰጥቷል፡፡ ስለዚህ የጸና ፈቃድ አለመኖርን ታሳቢ የሚያደርገው አዋጅ በሽግግር ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችልበትን ሁኔታ ስላስቀመጠ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ወንጀሉ ሊቋቋም የሚችልበትን ሁኔታ አስቀርቷል፡፡ በአንድ አመት ውስጥ በነባሩ ሕግ ያልተመዘገበ መሳሪያ እንዲያስመዘግብ በሕግ ጊዜ የተሰጠው ሰው በዚህ ጊዜ ውስጥ ሕግ ተላልፎ የጦር መሳሪያ ይዘዋል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የሰበር መዛግብት ላይ በተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ መሆን የሚቻለው በምዝገባ ሂደት ውስጥ በመግባት በመሆኑ በአንድ በኩል የአንድ አመት ጊዜ ለመጠናቀቅ ገና የስድስት ወር ጊዜ ቀርቶት እያለ የምዝገባ ሂደት ያልጀመረ መሳሪያ የያዘ ሰው መሳሪያ መያዙ ከታወቀበት በወንጀል እንዲጠየቅ የሚያደርግ በሌላ በኩል መሳሪያ መያዙ ሳይታወቅበት የአንድ አመት ጊዜ ሊጠናቀቅ ጥቂት ግዜ ቀርቶት እያለ መዝጋቢው አካል ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ወደ ምዝገባ ሂደት የገባ ሰው በወንጀል ተጠያቂ እንዳይሆን የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ

ቁጥር 1177/2012 በዜጎች መካከል በእኩልነት ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚያደርግ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል ስለሚሆን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 3 እና 4 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው፡፡

ከዚህም በላይ በተጠቀሰው መዝገብ የተሰጠው ትርጉም መሳሪያ ለማስመዝገብ የሚቀርቡ ሰዎች ጭምር በወንጀል ተጠያቂ የማድረግ ውጤት ያለውና አዋጁ በመግቢያው ያሰባቸውን ግቦች የሚያከሽፍ ይሆናል፡፡ አዋጁ የጊዜ ገደብ ያስቀመጠው ከአዋጁ መውጣት በፊት በነበረው የምዝገባ ስርዓት የማይታወቁ የጦር መሳሪያዎችን ወደሕጋዊ ስርዓት ለማስገባት በመሆኑ ለዚህ ዓላማ በሚወጣው መመሪያ መሰረት በአንድ ዓመት ውስጥ በቀድሞ ሕግ ያልተሸፈኑትን መሳሪያዎች ወደ ሕጋዊ ስርዓት ለማስገባት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምዝገባውን ለማካሄድ እንዲቻል ሰዎች ከተጠያቂነት ነጻ ሆነው ማስመዝገብ እንዲችሉ ስርዓት ለመፍጠር የታሰበ ነው፡፡ ወንጀል እንዲከላከልና ተፈጽሞም ሲገኝ እንዲመረምር ስልጣን የተሰጠው አካል ከላይ በተሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ከአዋጁ በፊት የጦር መሳሪያ የያዙ ሰዎችን ሕጋዊ አድርጎ ሊመዘግብ የሚችልበት መንገድ አይኖርም፡፡ ይልቅም ለምዝገባ ዓላማ የሚቀርቡ ሰዎችን በሙሉ የወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ደግሞ በሕግ አውጪው ያልታሰበ ከመሆኑም በላይ አዋጁንም ሆነ አፈጻጸሙን ውድቅ የሚያደርግ ነው፡፡ የተጠቀሰው ድንጋጌ አሻሚ ቢሆን እንኳ መተርጎም ያለበት የሕጉን መንፈስ ጠብቆ በሕግ አውጪው የታሰበውን ግብ ለማሳካት መሆን እንዳለበት ወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2(4) ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ የሕግ አውጪውን ሐሳብ ማሳካት የሚቻለው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሰዎች ከተጠያቂነት ፍርሀት ውጪ በመሆን ስልጣን የተሰጠው አካል ዘንድ ቀርበው ቀደም ሲል በነበረው ሕግ ያልተመዘገበ የጦር መሳሪያ ማስመዝገብ ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ያለው አተረጓጎም ከላይ የቀረቡት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው አዋጁን እንዳይፈጸም የሚያደርግ በመሆኑና ሕግ መተርጎም ያለበት ሕግ አውጪው ያሰበውን ዓላማ ለማሳካትና የሕጉን መንፈስ ተከትሎ በመሆኑ ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ ይህን መስፈርት የሚያሟላ አይደለም፡፡

በተያዙት ጉዳዮች የተከሰሱ ዓይነት ሰዎችን ለመለየት የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ‹‹ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ሳይመዘገቡ ወይም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች…›› የሚል አገላለጽ ይጠቀማል፡፡ መልስ ሰጭዎች በዚህ አገላለጽ ስር የሚወድቁ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በነዚህ ሰዎች ላይ የተጣለው ግዴታ ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ቀርበው በእጃቸው የሚገኝን የጦር መሳሪያ ማስመዝገብና መስፈርቱን ካሟሉ ፈቃድ ማውጣት ነው፡፡ ከዚህ አልፎ በሽግግር ጊዜው ውስጥ በሚታዩት መዝገቦች በተለዩት ፍሬ ነገሮች መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት ሁኔታ አልተመለከተም፡፡ ግለሰቦች በአዋጁ መሰረት ለመመዝገብ እና ፈቃድ ለማግኘት ጠይቀው ካልተፈቀደላቸው ውጤቱ የሚሆነው የጦር መሳሪያውን ማስረከብ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 23(3) ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ በዚህ አገላለጽ የሚሸፈኑ ሰዎች በሙሉ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በእጃቸው የሚገኘውን የጦር መሳሪያ ማስመዝገብ፣ ፈቃድ መውሰድ ወይም ይህ ካልተሳካ የጦር መሳሪያውን የማስረከብ ግደታን ከመወጣት ባለፈ የወንጀል ተጠያቂነት ሊጣልባቸው የሚችልበት ሁኔታ በሕጉ አልተመለከተም፡፡

አንድ ሕግ የሕጉን ይዘት ከመወሰን ባለፈ የጊዜ ተፈጻሚነት ላይ በመበየን የሕጉን ውጤት ወዲያው፣ በሂደት ወይም በሁኔታዎች መሟላት ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ የአንድ ሕግ መውጣት ከሕጉ በፊት የተጀመሩ ወይም በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለውን ተፈጻሚነት የሚገዙ ድንጋጌዎችን በማካተት የሽግግሩ ሂደትን የተሳለጠ ማድረግ የተለመደ ነው፡፡ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ በቀድሞውና በአዲሱ ሕግ መካከል በድልድይነት የሚያገለግል ነው፡፡ ለተከሳሽ የሚጠቅም ካልሆነ በስተቀር የወንጀል ሕግ ተፈጻሚነት የወደፊት (prospective) በመሆኑ ጥያቄው ሊሆን የሚችለው ሽግግሩ በቀድሞ ሕግ የነበረውን ሁኔታ በአዲሱ ሕግ እንዴት እንደሚስተናገድ ማሳወቅ ነው፡፡ ስለዚህ የሽግግር ድንጋጌ ቀደም ሲል ያሉት ሁኔታዎች ወይም ድርጊቶች በአዲሱ ሕግ እንዴት እንደሚስተናገዱ በግልጽ ለማመልከት የሚያገለግል ነው፡፡ አዋጁ ከታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ

በስራ ላይ የዋለ ሲሆን ቀደም ሲል የነበረው ሕግን ስለሻረው ከዚህ በኋላ የሚቀርቡ ክሶች ይህን አዋጅ መሰረት አድርገው ነው፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ሕግ መሰረት የተከናወኑ ተግባራትም የሚበየኑት በዚሁ አዋጅ ነው፡፡ ከአዋጁ ግልጽ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የጦር መሳሪያ የያዙና ፈቃድ የሌላቸው ወይም ያላስመዘገቡ ሰዎች ላይ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆነው በሕግ በተመለከተው አግባብ የአንድ ዓመት ጊዜ ገደቡ ሲያበቃ እንደሆነ ነው፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 23 የተካተተው የሽግግር ጊዜ ድንጋጌ ዓላማ ደግሞ የአንድ ሕግ ተፈጻሚነትን ከመጀመሩ በፊት የሚኖረውን ሂደት መግዛት እና ተፈጻሚነትን ማሻሻል ሲሆን የጊዜ ገደቡ ሲያበቃ ወይም ሁኔታው ሲሟላ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ውጤቱም በሽግግር ድንጋጌ በተመለከተው ሁኔታ ጉዳዮች ላይ ሕጉ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት ያለው ሂደት የሚጀመርበት ነው፡፡ ይህም ከላይ በዝርዝር ከቀረበው የአዋጁ ዓላማ እንዲሁም ሕግ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ሲደረግ ሊያስከትል የሚችለው ችግር ከመቅረፍ አንጻር ከታየ ሕግ አውጪው የሽግግር ጊዜውን የሕጉን ተፈጻሚነት በማዘግየት ለሕጉ ዓላማ መሳካት በጥንቃቄ የወሰነ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ የአዋጁ አፈጻጸም በዚህ የጊዜ ገደብና በተጠቀሱት ሁኔታዎች በእንጥልጥል እንዲቆይ ተደርጓል፡፡ በዚህም የሽግግር ድንጋጌ ምክንያት ወንጀሉን ለማቋቋም ከሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ውስጥ የሕግ መስፈርት ስለማይሟላ የወንጀል ተጠያቂነትን መፍጠር አይቻልም፡፡ ድርጊቱ በሌላ ሁኔታ ጥፋት ቢሆንም በሽግግር ጊዜ ውስጥ የወንጀል ተጠያቂነት የላቀውንና ሕግ አውጪው ያሰበውን አጠቃላይ ዓላማ ማሳካት እንዲቻል በጊዜያዊነት ቀሪ ተደርጓል፡፡

የሕጋዊነትም ሆነ የእኩልነት መርሁ ተፈጻሚነት ከአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) ጋር ተገናዝቦ የሚታይ በመሆኑ አዋጁ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በእጁ የጦር መሳሪያ የያዘ ሰውን የሚመለከት ነው፤ አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ነጻ የጦር መሣሪያ ዝውውር የመፍቀድ ዓላማ የለውም፤ ዓላማው አስቀድሞ በእጃቸው መሣሪያ የያዙ ሰዎች በሕግ አግባብ ማስተዳደር እና ከሕግ ውጭ የጦር መሣሪያ የያዙ ሆነ የሚያዘዋውሩ ሰዎችን በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22/2 እና 22/3 መሠረት የወንጀል ክስ ሲያቀርብ የጦር መሣሪያው ተከሳሽ የሆነው ወገን ይዞ የተገኘው በአዋጁ አንቀጽ 23/2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ከሆነ መሳሪያው አዋጁ ከጸና በኋላ በተከሳሹ የተያዘ ስለመሆኑ ተጨማሪ የማስረዳት ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) በሚተገበርበት ግዜ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 481 ስለጦር መሳሪያ መነገድ ወንጀል ጸንቶ ያለና ተፈፃሚነት ያለው ህግ ከመሆኑ አኳያ የመሸጋገሪያው ግዜ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር የሚፈቅድ ሆኖ መተርጎም ተገቢነት የሌለው በመሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉሙ ሊለወጥ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም በአዋጁ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ መሠረት አዋጅ ቁጥር 1177/2012 ወጥቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ ታህሳስ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በፊት በፈቃድም ሆነ ያለፈቃድ የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች በአዋጁ ለፈቃድ ማውጫ በተቀመጠው አንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ፤እንዲሁም በተለምዶ የጦር መሳሪያ የሚያዝባቸዉ አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ እና ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የጦር መሣሪያ የያዙ ሰዎች ሲሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 8(1) መሰረት እንዲያስመዘግቡ በተፈቀደዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ የአዋጁን አንቀጽ 4 ፣ 22(2) ፤ እንዲሁም 22(3) ድንጋጌዎች በመተላለፍ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ አይገባም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሁለቱም የሰበር መዛግብት ተጠሪዎች የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4(2) እና 22(3) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ተከሰው በሰበር መዝገብ ቁጥር 233141 ተጠሪ የሆኑት አቶ ኢሳያስ መኮንን የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከተው አንድ ዓመት የመመዝገቢያ የእፎይታ ግዜ ከማለቁ በፊት ልከሰስ አይገባም በማለት ያቀረቡትን የክስ መቃወሚያ ተቀባይነት አግኝቶ አመልካች በተጠሪው ላይ ያቀረበው ክስ ውድቅ መሆኑን ፤ እንዲሁም የሰበር መዝገብ ቁጥር 239711 ተጠሪ የሆኑት አቶ ካሳሁን ግዛቸው ፈቃድ የሌለው የጦር መሣሪያ ይዟል ተብሎ ክስ የቀረበባቸው ሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም አዋጁ ከወጣ በአምስት ወር ግዜ ውስጥ ሆኖ የአንድ ዓመት ግዜው ሊጠናቀቅ ሰባት ወር ስለሚቀር

የወንጀል ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ የተሰጠው ብይንና ውሳኔ ሊነቀፍ የሚችል ባለመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የሰ.መ.ቁ 233141ን በተመለከተ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 278868 በ12/7/14 ዓ.ም እንዲሁም የሰ.መ.ቁ 239711ን በተመለከተ በመ.ቁ 268279 በ29/10/14 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የሰ.መ.ቁ 233141ን በተመለከተ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 225404 በ24/9/14 ዓ.ም እና የሰ.መ.ቁ 239711ን በተመለከተ በመ.ቁ 231725 በ7/2/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ.መ.ህ.ሥ.ሥ.ቁ 195(2) (ሀ) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 205727 እና 205827 *"…የአዋጁ አንቀጽ 23(2) ከአዋጁ መሰረታዊ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የዚህ ድንጋጌ ዋናው ዓላማ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ መሳሪያውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የህጋዊነት ጥያቄ ለመጠበቅ እንጂ እስከ አንድ አመት ድረስ ያለማንም ጠያቂ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመፍቀድ አይደለም፡፡"* በማለት ለጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ የሰጠው የህግ ትርጉም ተለውጧል፡፡
3. የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አዋጁ ከጸናበት ከ30/4/12 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አንድ አመት ይኸውም እስከ 30/4/13 ዓ.ም ባለው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በነበሩ ሕጎችና አሰራሮች ያልተመዘገበ ወይም ፈቃድ ያልተሰጠው በሰው ሊያዝ የሚችል የጦር መሣሪያን የያዘ ወይም የተጠቀመ ሰው የአዋጁን አንቀጽ 4(2) እና 22(3) ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም በማለት ለአዋጁ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ የህግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ክፍል አስራ ሶስት

## 13.ሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ[129]

### 13.1 የግል ተበዳይ ባለመቅረበበት የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎችን ብቁነት[130]

- የሥራና ሠራተኛን ማገናኘት አዋጅ ቁ.632/2002 በመተላለፍ ሊኖር ስለሚችለው የወንጀል ተጠያቂነት ከቀረበ የወንጀል ክስ ጋር በተያያዘ የግል ተበዳይ የሆነ ሰው ቀርቦ ካልመሰከረ በስተቀር ክሱን ለማስረዳት የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎች ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማለት ብቁ አይደሉም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፤ (አዋጅ ቁ.632/2002 አንቀፅ 16(1)(መ), 18(1)(ሀ), 20(2), 40(3))

የሰ/መ/ቁጥር - 71184

ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም

[129] *የሥራና ሠራተኛን ማገናኘት አዋጅ ቁጥር* 632/2002

[130] የሰ/መ/ቁጥር 71184 (ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም )ቅፅ 13

ዳኞች፡-    ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-  ዓሕመድልሃዲ ካህሳይ - ከጠበቃ ወ/ጊዮርጊስ ማሩ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡-  የፌዴራል ዓቃቤ ህግ - በሌሉበት፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 632/2002 አንቀፅ 16(1)(መ)፣ 18(1)(ሀ)፣ 20(2) እና 40(3) የተመለከቱትን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ተጠሪ በመሰረተው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የክሱም ዝርዝር ተከሳሽ (አመልካች) ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለመላክ የሚያስችል ፈቃድ አውጥቶ ገልፍ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሚል ከፍቶ በሚሰራበት ጊዜ የግል ተበዳይ ወ/ሪት ፋኢዛ ይመር ዘገየን በኤጀንሲው ፀሐፊ አማካኝነት ማሟላት የሚገባትን ቅድመ ሁኔታዎች እንድታሟላ ከተደረገች በኂላ በኤጀንሲው በኩል የአየር ቲኬት እና ቪዛ በኢሜል ተልኮላት በአዋጁ መሰረት ውሉን በሚመለከት በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ሳያዋውል ሚያዝያ 7 ቀን 2001 ዓ.ም ወደ ባህሬን አገር የላካት በመሆኑ ከተላከችም በኂላ መብቷንና ደህንነቷን መጠበቅ ሲገባው ባለመጠበቁ ተበዳይዋ ለብዙ ስቃይ እንድትጋለጥ በማድረጉ እንዲሁም ተበዳይዋን የስራ ዘመንዋ ሲያልቅ ወይም ሲቋረጥ ወደ አገሯ መመለስ ሲገባው ባለመመለሱ ወይም ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ በፈጸመው የህግ መጣስ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በክሱ የተጠቀሰውን ድርጊት አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቅድሚያ የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ከሰማ በኂላ፣ አመልካች ሊከላከል ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎች የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም አመልካች እንደክሱ አቀራረብ የወንጀል ድርጊቱ ስለመፈጸሙ በማስረጃ ተረጋግጧል የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህም አመልካች በብር 8,000 (ስምንት ሺህ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የቀረበው የግል ተበዳይ በአመልካች ኤጀንሲ በኩል መሄድዋ ሳይረጋገጥ እንዲሁም በአካል ቀርባ እንግልት እንደደረሰባት ባላስረዳችበት አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት ሊመረመር ይገባል ተብሎ ነው፡፡ በመሆኑም ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር ከተሰጠው ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው ክስ በዝርዝር እና በግልጽ ፍሬ ነገሮችን ያመለከተ ከመሆኑም በላይ፤ በአመልካች ድርጊት ተጣሱ የተባሉትን የአዋጁ ድንጋጌዎችም እንደዚሁ በዝርዝር ተጠቅሰዋል፡፡ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም እንደክሱ ያስረዳሉ ተብለው

በዓቃቤ ሕግ የተቆጠሩትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ስምቷል፡፡ በሰማው ማስረጃ ተበዳይ ወደባህሬን የተላከችው በዓቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር በተገለጸው ሁኔታ አመልካች ባመቻቸው መንገድ መሆኑን፣ የግል ተበዳይ ወደ ባህሬን ከሄደች በኂላ ችግር እንዳጋጠማት ሲነገረው እና ወደሀገርዋ እንዲያስመጣት ሲጠየቅ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን፣በመጨረሻም የግል ተበዳይ በራሷ ወጪ ተሳፍራ ወደ ሀገሯ ብትመጣም፤ ጤንነቷ ግን ደህና እንዳልሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ በዝርዝር እና በግልጽ ማመልከቱን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የግል ተበዳይ ወደውጪ ሀገር የተላከችው ከእሱ እውቀት (እውቅና) ውጪ በኤጀንሲው ፀሐፊ በኩል መሆኑን እንደሚያስረዳ በመግለፅ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት የመከላከያ ማስረጃ ማሰማቱን እና ፍ/ቤቱ ግን የተሰማው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻለም ለማለት ክብደት እንዳልሰጠው ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው አመልካች በዓቃቤ ሕግ በዝርዝር የተመለከተውን ፍሬ ነገር ክዶ በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመመስረት ማስረጃዎን ሰምቷል፡፡ በዚህ ሂደት የሰማችውን ማስረጃዎችም መዝኖ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ አመልካች ግን አሁንም የግል ተበዳይን ወደ ውጭ ሀገር ስለመላኩ በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም በማለት ነው እየተከራከረ ያለው፡፡ ጭብጥ ለማስያዝ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመርለት የጠየቀውም ይህን የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡ የግል ተበዳይ ቀርባ እስካልመሰከረችብኝ ድረስ እንግልት ደርሶባታል ተብሎ ጥፋተኛ መባል የለብኝም የሚል ክርክርም አንስቷል፡፡ እንደሚታወቀው ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራትም/የማንጠርም/ ሆነ ማስረጃውን በመመዘን ድምዳሜ ላይ የመድረስ ሥልጣን በሕጉ አልተሰጠውም፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(30(ሀ) እና በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 10 እንደተደነገገው ለሰበር ችሎቱ የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን የክርክር ሥርዓቱን ጨርሶ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ የተፈጸመውን መሠረታዊ የህግ ስህተት በማረም የተወሰነ ነው፡፡ በመሆኑም ድርጊቱን ለመፈጸሜ በማስረጃ ሳይረጋገጥ ነው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈብኝ የሚለውን መነሻ በማድረግ አመልካች ያስያዘውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የምንመረምርበት አግባብ የለም፡፡ የግል ተበዳይ የሆነ ሰው እስካልመሰከረ በሌሎች ማስረጃዎች የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ማረጋገጥ አይቻልም የሚል የህግ ፍልስፍናም ሆነ ሕግ ስለሌለም የግል ተበዳይ ቀርባ ስለደረሰባት እንግልት ሳታስረዳ ጥፋተኛ መባሌ ተገቢ አይደለም የሚለው የአመልካች መከራከሪያም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው የምንልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.95035 ሰኔ 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 59774 ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ/ሥ-ሥ-ሕ-ቁ. 195(2)(ለ) (2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## ክፍል አስራ አራት

## 14.የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ[131]

### 14.1 በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ከቅጣት በተጨማሪ መሳሪያ እንዲወረስ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት[132]

- የጸጥታ አካላት ፈቃድ ሳያገኝ የጦር መሳሪያ ይዞ በመንቀሳቀሱ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከተቀመጠዉ ቅጣት በተጨማሪ በፈቃድ የያዘዉን የጦር መሳሪያ ለመንግስት ገቢ እንዲያደረግ (እንዲወረስ) የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት መኖሩ ሳይረጋገጥ መሳሪያዉ እንዲወረስ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ፤

የሰበር መ/ቁ 243949

ግንቦት 29 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ቀንዓ ቂጣታ

ማርታ ተካ

ብርሃኑ መንግስቱ

**አመልካች-** ደፋሩ ፈቃዱ ገመዳ

**ተጠሪ-** የፍትህ ሚኒስቴር አቃቤ ህግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ያለፈቃድ የጦር መሳሪያ ይዞ መንቀሳቀስን የሚከለክል አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መተላለፍ ወንጀል የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በቀን 24/6/2014ዓ.ም ባቀረበው ክስ አመልካች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014 አንቀፅ 6/5 እና 9 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በቀን 13/05/14 ከምሽቱ 5፡00 በለሚ ኩራ ክ/ከ ወረዳ13 ፋኑዔል ቤተክርስቲያን አካባቢ የወግቁጥር ቲ07878 ማካሮቭ ሽጉጥ ይዞ መንገድ ላይ ሲንቀሳቀስ የተያዘ በመሆኑ ከፀጥታ አካላት ፈቃድ ሳይኖር ጦር መሳሪያ ይዞ መንቀሳቀስ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የከሰሰ ሲሆን አመልካች በሰጠዉ እምነት ክደት ቃል ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ ምንም ጉዳት የሌለውን ሽጉጥና ጥይት ኪሴ ውስጥ እንዳለ ይገኘ ስንቀሳቀስ ተይዣለሁ ጥፋተኛ ነኝ በማለት ቃል መስጠቱን ተከትሎ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በመ/ቁ/178880 ላይ በሰጠዉ ፍርድ አመልካች አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014 አንቀፅ 615 እና 9 ስር ፈቃድ ሳይኖር መሳሪያ ይዞ መንቀሳቀስ ወንጀል ጥፋተኛ በማለት ደረጃው በአንቀፅ 97 መሰረት ቀላል ተብሎ በወንጀል ህግ አንቀጽ 89 እንዲሁም አንቀጽ179(2) መሰረት 4 ማቅለያ ተይዞለት በእርከን 3 ስር (1000) አንድ ሺ ብር እንዲቀጣና ሽጉጡ የወንጀል ፍሬ በመሆኑ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በማለት ወስኗል፡፡

አመልካችም በውሳኔው ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይ/መ/ቁ/295564 ላይ በቀን 19/4/2015ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙ በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(1) መሰረት ሰርዟል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡አመልካች በቀን 11/07/2015ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 98 መሰረት አንድ ንብረት ከወንጀል ድርጊት ጋር በተያዘ ሊወረስ የሚችለው ጥፋተኛ የተባለው ግለሰብ ከድርጊቱ ያገኘው የወንጀል ፍሬ

---

[131]የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014

[132]የሰ/መ/ቁ 243949 (ግንቦት 29 ቀን 2016 ዓ.ም)

ሲኖር መሆኑን የደነገገ ሲሆን ንብረቱ እንዲወረስ ትዕዛዝ ከመስጠታቸው በፊት ሁለት ነገሮች ሊረጋገጡ ይገባል፤ይኸውም ንብረቱ እንዲወረስ የሚደነግግ ግልጽ የወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል መኖሩን እና ንብረቱ የተገኘው በወንጀል ድርጊት አማካኝነት ወይም ለወንጀል ድርጊት መፈፀሚያነት የዋለ ሲሆን ነው፡፡ይህ ሳይሟላ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የለውም፤ አመልካች የተከሰስኩበት እና ጥፋተኛ የተባልኩበት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014 አንቀፅ 6(5) እና አንቀፅ 9 የጦር መሳሪያ ይዞ ሲንቀሳቀስ የተያዘ ሰው በእስራት እንደሚቀጣ ከመደንገግ ውጭ ይዞ ሲንቀሳቀስ የተያዘው መሳሪያ እንደሚወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንደሚሆን አያስቀምጥም፤አመልካች መሳሪያውን ያገኘሁት በህጋዊ መንገድ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ነው፤ሽጉጡን ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 14 ዓመታት ህጋዊ ፈቃድ ተሰጥቶኝ የያዝኩት መሆኑን ማስረጃ በእጄ እያለ ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅትም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተከትሎ መንግስት ሁሉም ዜጋ ያለውን የጦር መሳሪያ እንዲያስመዘግብ በሰጠው መመሪያ መሰረት አስመዝግቤ እያለ ይህ ግምት ውስጥ ሳይገባ መሳሪያው እንዲወረስ መወሰኑ ህጉን መሰረት ያላደረገና በቅፅ 24 በሰ/መ/ቁ/137908 የተሰጠውን ውሳኔ የሚቃረን ነው፤አመልካች መሳሪያውን ይዤ ከመገኘት ውጭ መሳሪያውን በመጠቀም የፈፀምኩት ወንጀል የለም፤ይህ እየታወቀ ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት መሳሪያው ለመንግስት ገቢ እንዲሆን መወሰኑ የህግ ስህተት ነው፤በመሆኑም የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የወግ ቁጥር ቲ07878 የሆነውን ማካሮቭ ሽጉጥ ከስምንት ጥይቶች ጋር እንዲመለስልኝ ሲል አቤቱታውን አቀርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ በሀምሌ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ  ፈቃድ ያለው የጦር መሳሪያ የወንጀል ፍሬ ወይም ወንጀል የተፈፀመበት መሳሪያ ሊባል ይችላል ወይስ አይችልም?አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ህግ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014 ውርስ እንደቅጣት ማስቀመጥ አለማስቀመጡን የስር ፍርድ ቤት ሳያረጋግጥ የወንጀል ፍሬ ነው ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆን አለመሆኑ ለማጣራት ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ በነሃሴ 22 ቀን 2015 በሰጠው መልስ አመልካች ይዘው የተገኙት ጊዜያዊ ፈቃድ ያለው መሳሪያ መሆኑ ባይካድም አዋጁ ክልከላውን ያስቀመጠው ህዝብና ሀገር ላይ የሚደርስ አደጋን ለመከላከል ከመሆኑ አንፃር ቁጥጥር ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ስለሆነ በአመልካች እጅ የተያዘው የጦር መሳሪያ የወንጀል ፍሬ ከመባል ውጭ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይገባም፤የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ማመኑና የይግባኝ አቤቱታ ባለቀረቡበት ሁኔታ የወንጀል ፍሬ መሆኑ አከራካሪ ሊሆን አይገባም፤ጥፋተኛ የተባለበት አዋጅ ውርስን እንደቅጣት ባያስቀምጥም የወንጀል ፍሬ ሊሆን የሚችለው ማንኛውም ህጋዊ እና ህገ-ወጥ መሳሪያ እንደሆነ መገንዘብ ይገባል፤የአመልካች አቤቱታ አቀራረብ የአዋጁን ድንጋጌ አቀራረፅ የወንጀል ፍሬ ሊኖረው አይገባም በሚል መንፈስ የቀረበ ሲሆን የአዋጁን አስፈላጊነትና እና ዓላማ እንዲሁም ወቅታዊ አደጋ ያላገናዘበ ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቾች የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በቀን 07/01/2016 ዓ.ም አቅርበዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በመያዝ ከግራቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ አመልካች ጥፋተኛ የተባለዉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014 አንቀፅ 6(5) እና አንቀፅ 9 ተላልፎ የሚመለከተዉ አካል ፈቃድ ሳያገኝ የወግ ቁጥር ቲ07878 ማካሮቭ ሽጉጥ ይዞ ሲንቀሳቀስ በመገኘቱ ነዉ፡፡በዚህ አዋጅ መሰረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰዉ በእስራት ወይም በገንዘብ እንደሚቀጣ ከመደንገግ ባለፈ የያዘዉ የጦር መሳሪያ የሚወረስ መሆን አለመሆኑ በግልጽ አልተደነገገነም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ በአመልካቹ እጅ የተያዘዉ የጦር መሳሪያ ሊወረስ የሚችል መሆን አለመሆኑ በወንጀል ህጉ የተደነገገዉን መርህ ተከትሎ መመርመር አስፈላጊ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀል ህጉ ከተመለከቱት የቅጣት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱ ስለመሆኑ ንብረት ስለሚወረስበት ሁኔታን የሚመለከቱ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ከሚገኙበት የህጉ ሁለተኛ መጽሓፍ ምእራፍ ሁለት ድንጋጌዎች አጠቃላይ አወቃቀር እና ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ የሚቻልባቸዉ ሁኔታዎች ቅጣቱ ንብረት መዉረስን እንደሚያካትት በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በግልጽ የተደነገገ ሲሆን የጥፋተኛነት ዉሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ ወንጀለኛዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘዉ ንብረት ሲኖር፣አንድ ሰዉ ለወንጀል ስራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳዉ ወይም ወንጀሉን ለፈጸመበት ዋጋ እንዲሆነዉ የተሰጠዉ ወይም ሊሰጠዉ የታቀደዉ ንብረት ሲኖር፣ወንጀሉን ለመፈጸም ሊያገለግል የሚችል ወይም ለወንጀል ተግባር ያገለገለ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ አደገኛ የሆኑ ነገሮች ሲሆኑ ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 98፣100(1) እና 140 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ንብረት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀለኛዉ ላይ ሊጣል ከሚችል ቅጣቶች አንዱ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔን ተከትሎ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን መወሰን የሚችሉት እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አቃቤ ህግ ሊወረሱ የሚገባቸዉን ንብረቶች ዝርዝር በወንጀል ክሱ ካመለከተና ንብረቶቹም ከፍ ሲል በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ የተገኙ ስለመሆኑ በወንጀል ፍርድ ሂደት ከተረጋገጠ እና በወንጀል መዝገብ ላይ አቃቤ ህግ ንብረቶቹ እንዲወረሱ ካመለከተ ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች እንዱሁም በወንጀል ሥ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 211 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡በዚህ ረገድ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 137908 (ቅጽ 24) ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ አመልካች ጥፋተኛ የተባለዉ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌ መሰረት የሚመለከታቸዉን የጸጥታ አካላት ሳይፈቅዱ የጦር መሳሪያ ይዞ መንቀሳቀስ የህግ ክልከላ የተላለፈ በመሆኑ በእስራት ወይም በገንዘብ እንደሚቀጣ ከመደንነጉ ዉጭ መሳሪያዉ እንዲወረስ በቅጣት አይነት በግልጽ አልደነገገም፡፡በእርግጥ ድንጋጌዉ ፈቃድ ያለዉ ወይም የሌለዉ በሚል የለየ ባይሆንም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለጠቅላላ ጥቅም ሲባል ከጸጥታ አካላት ፈቃድ ሳያገኙ የጦር መሳሪያ ይዞ መንቀሳቀስን የሚከለክል ነዉ፡፡ይሁንና ፈቃድ ኖሮት ነገር ግን ደግሞ የጸጥታ አካላት ሳያስፈቅድ ይዞ የተንቀሳቀሰ ሰዉ በልዩ ህጉ ከተመለከተዉ ቅጣት በተጨማሪ መሳሪያዉ እንዲወረስ ለመወሰን የሚያስችል ሌላ ምክንያት ስለመኖሩ አቃቤ ህግ አላስረዳም፡፡ከዚህ አኳያ አመልካቹ እጅ የተያዘዉ የጦር መሳሪያ ጊዜያዊ ፈቃድ ያለዉ ስለመሆኑ በአቃቤ ህግ የታመነ ጉዳይ ከመሆኑም በተጨማሪ ለወንጀል መፈጸሚያ የዋለ ነዉ ወይም የወንጀል ፍሬ ነዉ በሚል አቃቤ ህግ እንዲወረስ ስለመጠየቁ የስር ክርክር ይዘት አያሣይም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የጸጥታ አካላት ፈቃድ ሳያገኝ የጦር መሳሪያ ይዞ በመንቀሳቀሱ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከተቀመጠዉ ቅጣት በተጨማሪ በፈቃድ የያዘዉን የጦር መሳሪያ ለመንግስት ገቢ እንዲያደረግ(እንዲወረስ) የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት መኖሩ ሳይረጋገጥ መሳሪያዉ እንዲወረስ ሲል የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የህጋዊነት መርህን የሚጻረር በመሆኑ መታረም ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ዉሳኔ**

1ኛ/አመልካቹ በተከሰሰበት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014 አንቀጽ 6(5) እና 9 ስር ጥፋተኛ ነዉ ተብሎ የተወሰነበት ቅጣት በቅደም ተከተል በመ/ቁ/ 179880 ላይ በቀን 24/06/2014ዓ.ም እና 27/10/2014ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 295564 ላይ በቀን 19/4/2015ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(/ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/በአመልካቹ እጅ የተያዘዉ ማካሮቭ ሽጉጥ ዉግ ቁጥር ቲ07878 ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሲል የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡የጥፋተኛነትና ገንዘብ መቀጮ በሚመለከት የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ጸንቷል፡፡

3ኛ/መሳሪያዉ የሚያዝበት ሌላ ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩ ተጣርቶ እንዲመለስለት ብለናል፡፡ ለሚመለከተዉ ፖሊስ ክፍል ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበ

I.የተጠቀሱ የሰበር መዝገቦች ዝርዝር

(case index)

## ምዕራፍ -3

### ክፍል -1

የሰ.መ.ቁ. 211521(ጥቅምት 01 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ.102982 (መስከረም26 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20፣ በሰ/መ/ቁ 247063 እና 247065 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም)

### ክፍል-2

የሰ/መ/ቁ. 167965 (ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም)ቅፅ 24፣የሰ/መ/ቁ 231739 (ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ፡ 244110(ሐምሌ 29 ቀን 2016 ዓ.ም)

### ክፍል-3

የሰ/መ/ቁ 162738(መጋቢት 30 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24፣ በሰመ/መ/ቁ 117383 (መስከረም 6 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19፣ በሰ/መ/ቁጥር 211167 (ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም )ቅፅ 26፣ በሰ.መ.ቁ 218793፤ 219208 እና 220345 (ሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ. 231681( ሕዳር 26 ቀን 2015 ዓ/ም)፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 225709 (ህዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 230272 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁጥር 247213 (ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም)፣ በሰበር መ/ቁ 261944 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ/ም)፣ በሰ/መ/ቁ 261767 (ህዳር 27 ቀን 2017 ዓ.ም)

### ክፍል-4

የሰ/መ/ቁ. 103940 (ጥር 24 ቀን 2008 ዓ.ም)ቅፅ 19

### ክፍል-5

የሰ/መ/ ቁጥር 237423 (የካቲት 29 ቀን 2016 ዓ/ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 58008 (ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 11/12፣ በሰ/መ/ቁ 94913 (ሕዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19፣ በሰ/መ/ቁ 102640 (መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም) በሰ/መ/ቁ 218957 (መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅፅ 26፣ የሰ/መ/ቁጥር 74237 (ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 14 ፣ በሰ/መ/ቁ 48850 (ታህሳስ 08/2002 ዓ.ም) ቅፅ 10፣ በሰ/መ/ቁ 51090 (ታህሣሥ 12 ቀን 2003 ዓ.ም)ቅፅ 11፣ በሰ/መ/ቁ. 84623 (ሰኔ 04 ቀን 2005 ዓ.ም)ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ. 86597 (መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም)ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ. 86672 (መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 15፣ በሰ/መ/ቁ. 181958 (ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24፣ በሰ/መ/ቁ 251295 (ታህሳስ 23 ቀን 2017 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ. 181958 (ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም)ቅፅ 24

### ክፍል-6

የሰ/መ/ቁ 229403 (መጋቢት 29 ቀን 2015ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁጥር 48628 (ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም)ቅፅ 11፣ በሰ/መ/ቁ 58266 (ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም)ቅፅ 11፣ በሰ/መ/ቁ 64819 (ሰኔ 30 ቀን

2003 ዓ.ም)ቅፅ 11፣ በሰ/መ/ቁ 64115 (ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም)ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 69602 (የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም)ቅፅ 13 ፣ በሰ/መ/ቁ. 97409 (ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16 ፣ በሰ/መ/ቁ. 108550 (26/11/2009 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 163069 (ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም)ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 114043 (የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም)፣በሰ/መ/ቁ 94913 (ሕዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 211028 (ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁጥር 112032 (ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ/ም) ቅፅ 18 ፣የሰ/መ/ቁ 122595 (መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም)ቅፅ 22፣ የሰ/መ/ቁ 47935 (ሕዳር 30 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12

***ክፍል-7***

የሰ/መ/ቁጥር 139107(ቀን መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22

***ክፍል-8***

የሰ/መ/ቁ. 141663 (መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22፣የሰ/መ/ቁ 65566 (ታህሣስ 4 ቀን 2004 ዓ.ም)ቅፅ 13

***ክፍል-9***

የሰ/መ/ቁ 150803 (ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 23

**ክፍል-10**

የሰ/መ/ቁ 233458 (ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ. 86388 (ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅፅ 15፣የሰ/መ/ቁ 168067 (ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 24

***ክፍል -11***

የሰ/መ/ቁ 203051 (የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25

***ክፍል -12***

የሰ/መ/ቁ 239711 እና የሰ.መ.ቁ 233141 (ሐምሌ 28 2015 ዓ.ም) ቅፅ ፣ በሰ/መ/ቁ 229400( ሕዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁጥር 251113( ጥር 30 ቀን 2017 ዓ/ም)፣ በሰ/መ/ቁ 205727 (ጥቅምት 29/2014 ዓ.ም) ቅፅ 25 እና 205827 (ሕዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም)

***ክፍል-13***

የሰ/መ/ቁ 71184 (ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም )ቅፅ 13

***ክፍል-14***

የሰ/መ/ቁ 243949 (ግንቦት 29 ቀን 2016 ዓ.ም)

## **II.የሕግ ማጣቀሻዎች**

**አዋጆች**

- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት(አንቀጽ 20(5)፣ 22(2)፣ 37፣ 50(8)፣ 52(2)(ለ)፣ 55(5)፣ 79 እና 80(3)(ሀ)
- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ (አዋጅ ቁጥር 414/1997)(አንቀጽ 1፣ 2(2)፣ 6፣ 23(1) እና (2)፣ 24፣ 32(1)(ሀ) እና (ለ)፣ 34(1) እና (2)፣ 37(1)፣ 57፣ 58(1)(ሀ)፣ 60(ሐ)፣ 84(1)(ሀ) እና (መ)፣ 87፣ 90(2)፣ 184(2) እና 676(1)
- የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ(አንቀጽ 27(2)፣ 35፣ 111፣ 112፣ 130(2)፣ 141፣ 142(1) እና (3)፣ 149(2)፣ 192(2)(ለ)(2)፣ 195(2)(ሀ) እና (ለ)(2)

- የሽብርተኝነትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አዋጅ (የፀረ-ሽብር አዋጅ) ቁጥር 1176/2012(አንቀጽ 3 እና 6(2)
- ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር አዋጅ ቁጥር 1178/2012(አንቀጽ 3(1)፣ 4(2)፣ 8(3) እና 42(2)
- ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 909/2007(አንቀጽ 2(4) እና 3(2)(ሀ)
- የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) አዋጅ ቁጥር 285/1994(አንቀጽ 22፣ 49፣ 50(1)፣ 50(3)(ሀ) እና (ለ) እና 56(1)
- የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001(አንቀጽ 22(1) እና 50(ለ)(1)
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006(አንቀጽ 168(1) እና 168(2)
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001(አንቀጽ 91(2)፣ 93(1)(መ)፣ 99 እና 104(3)(ሀ)
- የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000(አንቀጽ 28(4)(ሠ)
- የብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000(አንቀጽ 22(2)(ሠ)
- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94(አንቀጽ 97
- የኦሮሚያ ክልል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 203/2009(አንቀጽ 125(1)
- የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007(አንቀጽ 2(5)፣ 3፣ 9(1)(ለ)፣ 9(3)፣ 13(1)(ሐ)፣ 13(2) እና (3)
- የፀረ-ሙስና ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ (የተሻሻለው) ቁጥር 434/1997(አንቀጽ 7(1)
- ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/97
- የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004(አንቀጽ 26(4) እና 27
- የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99
- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988(አንቀጽ 10 እና 35
- የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ ቁጥር 1234/2013(አንቀጽ 29(4)(ለ) እና 55(2)
- የፌዴራል ፖሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/2004(አንቀጽ 6
- የተሽከርካሪዎች መለያ፤ መመርመሪያ እና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002(አንቀጽ 7(1)(ለ) እና (ሐ)፣ 42(5) እና 48(2)(ሐ)
- የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008(አንቀጽ 49(2)
- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እና የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር 809/2006(አንቀጽ 28 እና 38(1)(ለ)
- የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012(አንቀጽ 4፣ 22(2) እና 23(2) ን/አንቀጽ 3
- የቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 281/1994
- የሥራና ሠራተኛን ማገናኘት አዋጅ ቁጥር 632/2002(አንቀጽ 16(1)(መ)፣ 18(1)(ሀ)፣ 20(2) እና 40(3)
- የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ ቁጥር 1174/2012
- የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 5/2014
- የናይሮቢ ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 429/1997
- የጦር መሣሪያዎችን ሕገ ወጥ ማምረትንና ማዘዋወርን ለመከካከል የወጣ ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 735/2004

## ደንቦች

- የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ደንብ ቁጥር 179/2002(አንቀጽ 2(3)፣ 3፣ 6፣ 7 እና 13(ለ)
- የከተማ መሬቶችን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣ ደንብ ቁጥር 155/2005(አንቀጽ 59(1)

## መመሪያዎች

- የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006(አንቀጽ 19 እና 26(2)(ሐ)
- በሶስት ዳኞች ስለሚታዩ ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መመሪያ ቁጥር 009/2013(አንቀጽ 2.2(ለ)፣ 5(ሀ) እና 7
- የመሬት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2005
- የመሬት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 12/2007(አንቀጽ 8(1)

## ምዕራፍ አራት

## IV. በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ላይ የተሰጡ የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች

### መግቢያ

ይህ ክፍል የመፅሃፉ አራተኛ እና የመጨረሻው ምዕራፍ ሲሆን በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ላይ የተሰጡ የሰበር የሕግ ትርጉም ውሳኔዎች እንደ ሌሎቹ ምዕራፎች ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ በዋናነት በ1949 ዓ.ም በወጣው ወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ መሰረት የጠደረገ ሲሆን እንደወንጀል ባህሪያቸው በአዋጅ የወጡትን በተመለከተ ልዩ የወንጀል ስነ ስርዓት ህግም እንደ ሁኔታው ተካቷል፡፡[133]

የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግን መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ ክርክሮች ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ ድንጋጌዎች ላይ በርከት ያሉ ገዢ የሕግ ትርጉም ውሳኔዎችን ሲሰጥ መቆየቱ እና አሁንም እየሰጠ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የተሰጡት ገዢ የሕግ ትርጉም የሰበር ውሳኔዎች እርስ በእርስ የሚደጋገፉ በመሆናቸው ገዢነታቸው /land mark/ ከፍ ያለውን ለሕትመት በማብቃት ሌሎቹ የርዕሥ ወይም የክፍሉ ማጣቀሻነት እንደ ሌሎቹ ምዕራፎች በተመሳሳይ መልኩ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ የሰበር ውሳኔዎቹን በዚህ ምዕራፍ ስር ለማዘጋጀት የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህጉን ቅደም ተከተል መሰረት በማድረግ ነው፡፡

በአጠቃላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በወንጀል ሥነ ሥርዓት ላይ የተሰጡ ገዢ የህግ ትርጉም ህትመት በዚህ ምዕራፍ ስር ሲደራጅ በተቻለ መጠን ሁሉንም በሥነ ሥርዓት ህጉ ላይ የተሰጡ የሰበር ውሳኔዎች ለማካተት ጥረት የተደረገ ሲሆን ይህ ምዕራፍ በስምንት ክፍሎች የተደራጀ በመሆኑ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ቢያንስ አንድ የሰበር ውሳኔ እንዲታተም በማድረግ በድምሩ 24 (ሀያ አራት) የሰበር ገዢ የህግ ትርጉም ውሳኔዎች ታትመዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ክፍል አንድ የፖሊስ ምርመራን፣ ክፍል ሁለት ስለዋስትና፣ በክፍል ሶስት ውስጥ የወንጀል ክስ ስለ መስማት ክስ አዘገጃጀት እና መቃወሚያን ጨምሮ ሌሎችንም ንዑስ ክፍሎች የሚዳስሱ ገዢ የሰበር ውሳኔዎች፣ በክፍል አራት የወንጀል ክስ ማስረጃ ምዘናን፣ ክፍል አምስት እስከ ክፍል ስምንት ያሉት ደግሞ በአጠቃላይ በግል አቤቱታ ስለሚቀርቡ የወንጀል ክስ፣ ተከሳሽ በሌለበት ክርክር ስለመቀጠል እና የወንጀል ይግባኝ ሥነ ሥርዓትን እንዲሁም የሰበር አቤቱታ በተመለከተ የተሰጡ ውሳኔዎችን አካቷል፡፡

---

[133]የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997

## ክፍል አንድ

## 1.የፖሊስ ምርመራ

### 1.1 ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል[134]

- በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2/ መሠረት አንድ ተከሳሽ ለፖሊስ የሚሰጠው የእምነት ቃል ለምርመራ ዓላማ ሲባል በምርመራ ጊዜ የተገኘ ማስረጃ በመሆኑ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤት ሊመረመር እና ሊመዘን የሚገባው እንጂ ከወዲሁ ተቀባይነት አለው ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት ስላለመሆኑ፤

ሰ/መ/ቁ 152038

ህዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይለ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤህግ

ተጠሪ፡- ምንተስኖት ድሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

### ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የተሰጠን የእምነት ቃል የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 665/1 ድንጋጌን በመተላለፍ የስርቆት ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ በመከራከሩ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ በዓቃቤሕግ በኩል የቀረቡት ምስክሮች የግል ተበዳይ እና የደረጃ ምስክሮች ሲሆኑ የግል ተበዳይ ተከሳሽን አላውቀውም ድርጊቱን ሲፈጽም አላየሁም ያለ ሲሆን ሌሎቹ ሁለት ምስክሮች የፖሊስ ጣቢያው ባልደረቦች ሆነው ተከሳሽ ለፖሊስ በነጻ ፈቃዱ ቃሉን ሰጥቷል በማለት የመሰከሩ ቢሆንም ምስክሮቹ የሰጡት ቃል በሌላ ገለልተኛ አካል የተሰጠ ቃል ስላልሆነ እና በሌላ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ምስክርነታቸውን አልተቀበለውም በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት ብይን ስጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው 1ኛ ምስክር ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም አላየሁም በማለት የመሰከረ ሲሆን ሌሎቹ ምስክሮች ተጠሪ ለፖሊስ የሰጠውን ቃል ይዘት ለማስረዳት ከመቅረባቸው በቀር ድርጊቱ ሲፈጸም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ያዩ አይደሉም፤ ምስክሮቹ ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ለፖሊስ ቃል ሲሰጥ መግለጻቸው ብቻ ለፖሊስ የተሰጠው ቃል በሌላ አግባብነት ባለው ማስረጃ ተደግፏል ማለት አይቻልም፤ለፖሊስ የተሰጠ የተከሳሽነት ቃል ብቻውን በሌላ አግባብ በሆነ ማስረጃ ባልተደገፈበት

---

[134]በሰ/መ/ቁ 152038 (ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅጽ 23

ሁኔታ የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ለማሳየት በቂ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በማጽናት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ የተከራከረ በመሆኑ አመልካች ምስክሮችን እና ተጠሪው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የተሰጠውን ቃል አቅርቦ አሰምቷል፤የአመልካች ምስክሮች ተጠሪው በነጻ ፈቃዱ ወንጀሉን እንደፈጸመ በዝርዝር ቃሉን የሰጠ እና ወንጀሉ የተፈጸመበትን ቦታ መርቶ ያሳየ መሆኑን በመግለጽ በመሰከሩበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የሰጠውን ቃል የሚደግፍ ማስረጃ ዓቃቤ ሕግ አላቀረበም በማለት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ዓቃቤ ሕግ ባቀረባቸው ምስክሮች ተጠሪ ወንጀሉን መፈጸሙን ለመርማሪ ፖሊስ ቃሉን በፈቃዱ ሲሰጥ በደረጃ ማስረጃነት የነበሩ ፖሊሶች ቀርበው ከማስረዳታቸውም በላይ ወንጀሉን እንዴት እንደፈጸመ መርቶ ሲያሳይ የነበሩ መሆናቸውንም ጭምር አስረድተው ባለበት ሁኔታ ዓቃቤ ሕግ ገለልተኛ በሆነ ሁኔታ አላስረዳም ተብሎ በነጻ የመሰናበቱን አግባብነት ከመሠረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የፖሊስ ባልደረቦች ሲሆኑ ድብደባ የፈጸሙብኝ በመሆኑ በድብዳባ ለፖሊስ የሰጠሁት ቃል ማስረጃ ሊሆንብኝ አይገባም፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃል ከመስጠቴ በፊት መብት እና ግዴታዬ የተነገረኝ ስለመሆኑ ከፖሊሶች በስተቀር በሌላ ደጋፊ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ክሱን አስረድቷል ሊባል ስለማይችል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጠው የመልስ መልስ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃሉን ለፖሊስ ከመስጠቱ በፊት የሚሰጠው ቃል በፍ/ቤት በማስረጃነት እንደሚቀርብበት የተገለጸለት እና ይህንኑ ተገንዝቦ ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ በፎርማው አረጋግጧል፤ተጠሪ ለፖሊስ የሰጠሁት ቃል በተጽእኖ የተገኘ ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም በተጽእኖ ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ የሚያስረዱለት ምስክሮች አስቀርቦ ባላሰማበት ሁኔታ በደፈናው በፖሊሶች የደረጃ ምስክርነት የተሰጠ ነው ሊባል አይችልም ምስክር የሆኑት የፖሊስ አባላትም በጣቢያው በተለያየ የስራ መደብ ተመድበው የሚሰሩ እንጂ መርማሪ ፖሊሶች ባልሆኑበት ሁኔታ ገለልተኛ አይደሉም የሚል ግምት መወሰዱ ተገቢ አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሠረቱ መርማሪ ፖሊስ የተሰራውን ወንጀል በሚያውቅበት ወይም በጥርጣሬ በሚረዳበት ጊዜ ሁሉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ላይ ስለፖሊስ ምርመራ በተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብ የምርመራ ተግባሩን እንደሚፈጽም ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 22 እና 23 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ማንነቱ እና አድራሻው ከተረጋገጠ በኋላ የተጠረጠረበትን ወንጀል በሚመለከት ቃል ለመስጠት ነጻ እንደሆነ እና ፈቅዶ የሚሰጠው ማንኛውም ቃል በማስረጃነት የሚቀርብ መሆኑ ጠያቂው ፖሊስ ለተጠያቂው ሊነግረው እንደሚገባ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 ይደነግጋል፡፡ መርማሪው ፖሊስ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ከተጠሪጣሪው የሚቀበለው ቃልም ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረውን ሰው ለመመርመር ዓላማ የሚውል መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወንጀል መፈጸሙን በማወቅ ወይም በመጠርጠር ምርመራ የተጀመረ እንደሆነ ምርመራው ተጠርጣሪው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የሚሰጠውን ቃል መሠረት በማድረግ ብቻ የሚጠናቀቅ ላይሆን እንደ አስፈላጊነቱም ስለተጠርጣሪው ማንኛውንም ተገቢነት ያለውን ማስረጃ መስጠት የሚችል ምስክር በመመርመር፣የተጠርጣሪውን ቤት በመበርበር ወይም ዕቃ በመያዝ ወይም ተጠርጣሪው ቃሉን ለፍ/ቤት እንዲሰጥ በማድረግ ምርመራው የሚከናወን መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 30፣32 እና 35 ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የሚደረገው ምርመራ ዓላማም ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረውን ሰው መመርመር እና ምርመራውን በተገቢው ሁኔታ አከናውኖ ክስ ለማቅረብ ስልጣን ለተሰጠው ዓቃቤ ሕግ ራፖር መላክ እንደሆነ የፖሊስ ምርመራን አስመልክቶ ከተደነገጉት የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ዓቃቤ ሕግ በተጠርጣሪው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ ምክንያት መኖሩን ተረድቶ ክሱን ያቀረበ እንደሆነ በምርመራ ጊዜ የተገኙ ማስረጃዎች ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት ተመርምረው እና ተመዝነው የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችሉ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ተከሳሹ የሚሰጠው የእምነት ቃል ለምርመራ ዓላማ ሲባል በምርመራ ጊዜ የተገኘ ማስረጃ በመሆኑ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤቱ ሊመረመር እና ሊመዘን የሚገባው እንጂ ከወዲሁ ተቀባይነት አለው ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት አይደለም፡፡

በያዝነው ጉዳይ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች የግል ተበዳይ እና የደረጃ ምስክር የተባሉ ሌሎች ሁለት ምስክሮች ሲሆኑ የግል ተበዳይ የመኪናው ስፖኪዮ የተሰረቀበት መሆኑን በመግለጽ ከመመስከሩ በቀር ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም አይቻለሁ በማለት የስጠው የምስክርነት ቃል የለም፣ ሌሎች ሁለት ምስክሮችም ተጠሪው በነጻ ፍቃዱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃሉን ሲሰጥ አይተናል በማለት የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ቢሆንም ምስክሮቹ ያስረዱት ተጠሪ ሰጥቶታል የተባለውን ያንኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የተሰጠውን ቃል ነው፡፡ ምስክሮቹ ወንጀሉ ተፈጽሞበታል በተባለው አካባቢ ያልነበሩ እና ተጠሪ ወንጀሉን ሲፈጽም ያላዩ ከመሆናቸውም ባሻገር ተጠሪ ለፖሊስ ሰጥቶታል ከተባለው ቃል ውጪ ተጠሪ ወንጀሉን እንደፈጸመ የሚያውቁ መሆናቸውን በመግለጽ የሰጡት የምስክርነት ቃል እስከሌለ ድረስ ምስክሮቹ ተጠሪ ወንጀሉን እንደፈጸመ አስረድተዋል ሊባል አይችልም፡፡

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የሚሰጠው ቃልም እንደማንኛውም ማስረጃ ተመርምሮ እና ተመዝኖ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ ተጠሪ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ክሱን ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበውን ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 ድንጋጌ መሠረት ለፖሊስ ሰጥቶታል የተባለውን ቃል መርምሮ እና መዝኖ ክሱን ለማስረዳት በቂ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመ ስለመሆኑ የሚያስረዳ አግባብነት ያለው ሌላ ማስረጃ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ያቀረበ ስለመሆኑ መዝገቡ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የሰጠውን ቃል እንደማንኛውም ማስረጃ መርምረው እና መዝነው ማስረጃው ክሱን ለማስረዳት በቂ አይደለም በማለት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 103704 የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 177314 ጥቅምት 09 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ን

## 1.2 ኢግዚቢት- ኢግዚቢት አመመላለስ[135]

- በወንጀል ክስ ላይ ኢግዚቢት ሆነው በቀረቡ ማናቸውም ነገሮች ላይ የፍ/ቤቱ መዝገብ ሹም ቁጥር እና ምልክት በማድረግ በተጠበቀ ስፍራ የሚያስቀምጣቸው መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 97 ድንጋጌ ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ሀላፊነት በመሠረታዊነት የፍ/ቤቶች ሀላፊነት መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ የተመዘገቡት እና የተቀመጡ ኢግዚቢቶች ነገሩ በሚሰማበት ዕለት ከሳሽ በሆነው ዓቃቤሕግ ለፍ/ቤቱ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑም የዚሁ ሕግ ቁጥር 124/2 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝበናል፡፡
- ከላይ በተቀመጡት ድንጋጌዎች አግባብ ኢግዚቢት ሆኖ የቀረበው ማናቸውም ነገር በመንግስት ሊወረስ የሚገባ ስለመሆኑ ወይም ለባለንብረቱ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ በወንጀሉ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ አብሮ የሚወሰን ወይም እንደአስፈላጊነቱ በወንጀሉ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሚቀርብ አቤቱታ መነሻነት ትዕዛዝ የሚሰጥበት ነው፡፡
- ለተከሳሾች ፖሊስ መጥሪያ እንዲያደርስ በተደጋጋሚ ትዕዛዝ ተሰጥቶ መጥሪያ ሊደርሳቸው ባለመቻሉ ክርክሩ ባልቀረቡት ተከሳሾች ላይ ተቋርጦ በቀረበ ተከሳሽ ላይ ክርክሩ ቀጥሎ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤሕግ የቀረበበትን ክስ አስተባብሏል በማለት በነጻ ከተሰናበተ በኋላ በወንጀሉ ምክንያት የተያዘውን ንብረት (ኢግዚቢት) በተመለከተ ለሚቀርብ አቤቱታ ምላሽ አለመስጠት ከኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/1 ድንጋጌ ዜጎች ንብረት የማፍራት መብትን የሚጥስ በመሆኑ የአመልካች የንብረት ባለቤትነታቸው ተረጋግጦ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡[136]

የሰ.መ.ቁ 240930

ሐምሌ 25 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅ ይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

---

[135]በሰ/መ/ቁ 240930 (ሐምሌ 25 ቀን 2015 ዓ.ም)

[136]በሰ/መ/ቁ 242866 (ሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 126017 (ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 21፣ በሰ/መ/ቁ 58822 (መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 11፣ የሰ/መ/ቁ 62504 (ታህሳስ 06 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ በሰ/መ/ቁ 176890 (ግንቦት 25 ቀን 2012 ዓ.ም)

አመልካች፡- አቶ ካሣሁን ማሞ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የምስራቅ ጎጃም ዞን ፍትሕ መምሪያ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 09 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክሌላዊ መንግስት የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0227016 ግንቦት 24 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች የተያዘው ኤግዚቢት እንዲለቀቅ ያቀረቡት አቤቱታ ቀደም ሲል የመዝገቡ 3ኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ ካቀረበው አቤቱታ ያልተለየ እና ችሎቱ ምላሽ የሰጠበት በመሆኑ በይግባኝ ከማሳረም በቀር የተሰጠውን ትዕዛዝ የሚያስቀይር አይደለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ፤ ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት በየደረጃው ባለ የክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ በኤግዚቢት የተያዘን ተሽከርካሪ እንዲለቀቅ የቀረበን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ መዝገብ ተከራካሪ በሆኑ ሀይላ አበበ፤ ባሕሩ ማሞ እና ንፍታሌም ካሳሁን እንደቅደም ተከተላቸው ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተከሳሾች በነበሩ ግለሰቦች ላይ ያቀረበውን የወንጀል ክስ የተመለከተው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾችን በሚመለከት መጥሪያ ሊደርሳቸው አልቻለም በማለት ክርክሩን ያቋረጠ ሲሆን በስር 3ኛ ተከሳሽ ላይ ቀርቦ የነበረውን ክስ በሚመለከት ግን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት ክርክሩን መርቶ 3ኛ ተከሳሽ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙን አስተባብሏል በማለት በነጻ አሰናብቶታል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ መፈጸሙን ለማስረዳት በኤግዚቢት የተያዘውን ተሽከርካሪ በሚመለከት ግን 1ኛ ተከሳሽ የተከሰሰው የአዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 7(4) እና 19(7) ድንጋጌን ተላልፏል በሚል በመሆኑ እና ይህ ድንጋጌም ተሽከርካሪውን የሚመለከት ከመሆኑ አኳያ 1ኛ ተከሳሽ ላይ ያለው ክርክር ያልተቋጨ በመሆኑ በሌሎች ተከሳሾች ላይ ያለው ክርክር እስኪቋጭ ድረስ ባለበት ሊቆይ የሚገባው ነው በማለት ወስኗል፡፡

የሥር 3ኛ ተከሳሽ ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ በኤግዚቢት የተያዘው ንብረት እንዲለቀቅለት ለችሎቱ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ችልቱም ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ቀደም ሲል በተሰጠው ፍርድ ጉዳያቸው በተቋረጠ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በሚል ባለበት እንዲቆይ ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ አሁን ላይ ኤግዚቢቱ እንዲለቀቅ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁን አመልካች በበኩላቸው ይህ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኂላ ኤግዚቢቱ እንዲለቀቅ ለችሎቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች የተያዘው ኤግዚቢት እንዲለቀቅ ያቀረቡት አቤቱታ ቀደም ሲል የመዝገቡ 3ኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ ካቀረበው አቤቱታ ያልተለየ እና ችሎቱ ምላሽ የሰጠበት በመሆኑ በይግባኝ ከማሳረም በቀር የተሰጠውን ትዕዛዝ የሚያስቀይር አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባለ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጸንቷል፡፡

አመልካች ጥር 09 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- በኤግዚቢት የተያዘው የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-92627 የሆነው ተሽከርካሪ ባለቤት አመልካች ነኝ፤ በአመልካች ላይ የቀረበ ክስ የለም፤ የስር 3ኛ ተከሳሽ የሆነው ንፍታሌም ካሳሁን ወንጀል የተፈጸመበትን ተሽከርካሪ ከማከራየት ጋር በተያያዘ ከቀረበበት ክስ በነጻ ሲሰናበት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በዋስትና ወጥተው ባለመቅረባቸው በእነሱ ላይ የቀረበው ክስ ገና ውሳኔ አላገኘም፤

ስለሆነም አመልካች ተከራካሪ ባልሆንኩበት መዝገብ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በቀጥታ ይግባኝ ማቅረብ ነበረበት በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች በወንጀል ክርክሩ ተከሳሽ ባልሆኑበት በኤግዚቢት የተያዘው ተሽከርካሪ እንዲመለስ ያቀረቡት ጥያቄ ቀደም ሲል ችሎቱ ምላሽ የሰጠበት በመሆኑ በይግባኝ ከማሳረም በቀር የተሰጠውን ትዕዛዝ የሚያስቀይር አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትዕዛዝ አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶት ስላልቀረበ መልሰ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባለ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በስር ተከሳሾች ላይ የቀረቡት ክሶች አራት ሲሆኑ ፈጽመውታል የተባለው የወንጀል ተግባርም በ1ኛ ክስ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 17)3) እና 19(5) ድንጋጌን እና የመመሪያ ቁጥር 002/2012 አንቀጽ 14.1(17) ድንጋጌን በመተላለፍ የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-92627 አ.አ በሆነው የእሽግ ውሃ በሚጭን ተሽከርካሪ 33 ኬሻ ቡና በሕገወጥ መንገድ ጭነው ሲያንገዙ የተያዙ በመሆኑ ቡና ግብይት ላይ አሳሳች ድርጊት ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ 2ኛ ክስ፡- 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 17(4) እና 19(7) ድንጋጌን እና የመመሪያ ቁጥር 002/2012 አንቀጽ 14.1(18) ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለጸው ጊዜ ቦታ እና ሁኔታ 3ኛ ተከሳሽ የተሽከርካሪው ባለቤት ሆኖ በክሱ የተገለጸውን ቡና ያለፈቃድ አንገዝዋል የሚል ነው፡፡ 3ኛ ክስ፡- 3ኛ ተከሳሽ የአዋጁን አንቀጽ 17(6) እና 19(10 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ የተገለጸውን ተሽከርካሪ በውክልና የማስተዳደር ሀላፊነት ተሰጥቶት ተሽከርካሪውን በኪራይ ለ1ኛ ተከሳሽ ሲያስተላልፍ ተሽከርካሪው በሕገወጥ ድርጊት እንዳይሰማራ የመቆጣጠር ግዴታውን ሳይወጣ ሕገወጥ ቡና እንዲንንዝ ተባባሪ ሆኗል የሚል ነው፡፡ 4ኛ ክስ፡-1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የንግድ ምዝገባ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 22/1 እና 49/2 በመተላለፍ የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው በ1ኛ ክስ የተገለጸውን ድርጊት ፈጽመዋል የሚል ሲሆን አመልካች በወንጀሉ ጉዳይ ተከሳሽ አልነበሩም፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾችን በሚመለከት መጥሪያ ሊደርሳቸው አልቻለም በማለት ክርክሩን ያቋረጠ ሲሆን በስር 3ኛ ተከሳሽ ላይ ቀርቦ የነበረውን ክስ በሚመለከት ግን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት ክርክሩን መርቶ 3ኛ ተከሳሽ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙን አስተባብሏል በማለት በነጻ አሰናብቶታል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ መፈጸሙን ለማስረዳት በኤግዚቢት የተያዘውን ተሽከርካሪ በሚመለከት ግን 1ኛ ተከሳሽ የተከሰሰው የአዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 7(4) እና19(7) ድንጋጌን ተላልፏል በሚል በመሆኑ እና ይህ ድንጋጌም ተሽከርካሪውን የሚመለከት ከመሆኑ አኳያ 1ኛ ተከሳሽ ላይ ያለው ክርክር ያልተቋጨ በመሆኑ በሌሎች ተከሳሾች ላይ ያለው ክርክር እስኪቋጭ ድረሰ ባለበት ሊቆይ የሚገባው ነው በማለት ወስኗል፡፡ የሥር 3ኛ ተከሳሽ ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በኤግዚቢት የተያዘው ንብረት እንዲለቀቅለት ለችሎቱ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ቀደም ሲል በተሰጠው ፍርድ ጉዳያቸው በተቋረጠ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በሚል ባለበት እንዲቆይ ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ አሁን ላይ ኤግዚቢቱ እንዲለቀቅ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ይህ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ኤግዚቢቱ እንዲለቀቅ ለችሎቱ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ቀደም ሲል የመዝገቡ 3ኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ ካቀረበው አቤቱታ ያልተለየ እና ችሎቱ ምላሽ የሰጠበት በመሆኑ በይግባኝ ከማሳረም በቀር የተሰጠውን ትዕዛዝ የሚያስቀይር አይደለም በማለት አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡ ይህ ውሳኔም በየደረጃው ባለ የክልሉ ፍ/ቤቶች ጸንቷል፡፡

በወንጀል ክስ ላይ ኤግዚቢት ሆነው በቀረቡ ማናቸውም ነገሮች ላይ የፍ/ቤቱ መዝገብ ሹም ቁጥር እና ምልክት በማድረግ በተጠበቀ ስፍራ የሚያስቀምጣቸው መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 97 ድንጋጌ ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ሀላፊነት በመሠረታዊነት የፍ/ቤቶች ሀላፊነት መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ የተመዘገቡት እና የተቀመጡ ኤግዚቢቶች ነገሩ በሚሰማበት ዕለት ከሳሽ በሆነው ዓቃቤሕግ ለፍ/ቤቱ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑም የዚሁ ሕግ ቁጥር 124/2 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝበናል፡፡

ከላይ በተቀመጡት ድንጋጌዎች አግባብ ኤግዚቢት ሆኖ የቀረበው ማናቸውም ነገር በመንግስት ሊወረስ የሚገባ ስለመሆኑ ወይም ለባለንብረቱ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ በወንጀሉ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ አብሮ የሚወሰን ወይም እንደአስፈላጊነቱ በወንጀሉ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሚቀርብ አቤቱታ መነሻነት ትዕዛዝ የሚሰጥበት ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ለስር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ፖሊስ መጥሪያ እንዲያደርስ በተደጋጋሚ ትዕዛዝ ተሰጥቶ መጥሪያ ሊደርሳቸው ባለመቻሉ ክርክሩ በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ የተቋረጠ ሲሆን በ3ኛ ተከሳሽ ላይ ክርክሩ ቀጥሎ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤሕግ የቀረበበትን ክስ አስተባብሏል በማለት በነጻ ተሰናብቷል፡፡ ዓቃቤሕግ በዚህ ችሎት ቀርቦ የሰጠው መልስ ስለሌለ በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ ቀርቦ የነበረው ክርክር ቀጥሎ ውሳኔ የተሰጠ ስለመሆኑ ወይም 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾችን ለማቅረብ ጥረት እያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ስለሆነም በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ ተቋርጦ የነበረው ክርከር ቀጥሎ ጉዳዩ መቼ ውሳኔ እንደሚያገኝ አይታወቅም፡፡ ይህም በወንጀሉ ጉዳይ ተከሳሽ ያልሆኑት አመልካች ባለቤት ነኝ ብለው እንዲለቀቅ ጥያቄ ያቀረቡበት ተሽከርካሪ እስከመቼ ድረስ በኤግዚቢትነት ተይዞ ይቆያል? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡

በሌላ በኩል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40/1 ማናቸውም ኢትዮጲያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ የተከበረለት መሆኑ፤ ይህም መብት በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ጊዜ ድረስ ንብረት የመያዝ እና በንብረቱ የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ጊዜ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፤ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን የሚያካትት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ ቀርቦ የነበረውን ክስ በማቋረጥ የተሰጠውን ውሳኔ ተከሳሾችን አስቀርቦ እስካላስለወጠ ወይም ተከሳሾችን አፈላልጎ ለማግኘት ተገቢውን ጥረት አድርጎ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ባላደረገበት ሁኔታ በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ ያልተቋጨ በመሆኑ ኤግዚቢቱ ባለበት ይቆይ ተብሎ ቀደም ሲል ውሳኔ ያረፈበት እና አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ 3ኛ ተከሳሽ ካቀረበው አቤቱታ ያልተለየ በመሆኑ ይግባኝ ጠይቀው እንዲታረም ከሚያደርጉ በቀር ኤግዚቢቱ እንዲለቀቅ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ አመልካች የንብረቱ ባለቤት ነኝ የሚሉት ተሽከርካሪ ገደብ ለሌለው ጊዜ በሌላ አካል እጅ እንዲቆይ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም አመልካች በሕገመንግስቱ በተከበረላቸው የንብረት መብት መሠረት በንብረታቸው እንዳይገለገሉ የማድረግ ውጤት ያለው እና ይብዛም ይነስም ንብረቱ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ሊኖረው በሚገባ ድርሻ ላይ አለታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 176890 በሰጠው ውሳኔም ዓቃቤሕግ ባቀረበው የወንጀል ክስ የአሁን ተከሳሾች የነበሩ ግለሰቦች የዓቃቤሕግ ማሥረጃ ከተሰማ በኋላ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ስላልቀረቡ ፖሊስ ተከሳሾችን በሚያገኝበት ጊዜ ዓቃቤሕግ መዝገቡን

ማንቀሳቀስ ይችላል ተብሎ በተዘጋ መዝገብ በኤግዚቢት የተያዘው ተሽከርካሪ እንዲለቀቅ የቀረበን አቤቱታ በተመለከተ ተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ ደርሶ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም የምስራቅ ጎጃ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እነኚህን ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ በእርግጥም አመልካች ኤግዚቢት ሆኖ የተያዘው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-92627 አ.አ የሆነው ተሽከርካሪ ባለቤት መሆን አለመሆናቸውን አረጋግጦ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ፍትሃዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም በየደረጃው ያሉት የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባቸው አመልካች በኤግዚቢት የተያዘው ተሽከርካሪ እንዲለቀቅ ያቀረቡትን አቤቱታ በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ ያልተቋጨ በመሆኑ ኤግዚቢቱ ባለበት ይቆይ ተብሎ ቀደም ሲል ውሳኔ ያረፈበት እና አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ 3ኛ ተከሳሽ ካቀረበው አቤቱታ ያልተለየ በመሆኑ ይግባኝ ጠይቀው እንዲታረም ከሚያደርጉ በቀር ኤግዚቢቱ እንዲለቀቅ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0227016 ግንቦት 24 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 02-26639 ሐምሌ 26 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 117665 ሕዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ከላይ በፍርድ ሀተታው ላይ በተገለጸው መሠረት ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## 1.3 ብርበራ- የብርበራ ሕጋዊነት[137]

- ብርበራ የሚደረግበት የህግ ስርዓት ዝርዝር ሁኔታዎች የተመለከቱ ቢሆንም በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 32(2) የተመለከቱት ቀሪ ሁኔታዎች (Exceptions) በሌሉበት ብርበራ ያለብርበራ ትዕዛዝ ቢከናወን ወይም በብርበራ ትዕዛዙ ከተመለከተው ጊዜና ቦታ ውጪ ብርበራ ቢደረግ አሊያም በብርበራ ትዕዛዙ ላይ ከተመለከተው እቃ ውጪ በሆነ ሁኔታ ፖሊስ በብርበራ የመያዙ አግባብነት ተጨማሪ የብርበራ ትዕዛዝ ለማግኘት በቂ እና ምክንያታዊ ጊዜ ነበር የሚለው የብርበራውን ህጋዊነት ለመመዘን ከግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባ መሰረታዊ መስፈርት ተደርጎ የሚወሰድ ስለመሆኑ፣

የሰ/መ/ቁጥር 211525

መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም

[137]በሰ/መ/ቁ 211525 (መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅጽ 25

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡-1ኛ መንሱር ጁሃር መሀመድ

2ኛ ፉአድ ጁሃር መሀመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ -- ዐ/ህግ ሁመድ - ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካቾች ሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይኸው ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡

የነገሩ አመጣጥ የኮንትሮባንድ ወንጀል ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ የአሁን አመልካቾች የምግብና መድሀኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 46 እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንደተሻሻለው/አንቀጽ 168/2/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የአሁን አመልካቾች ስልጣን ባለው አካል ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ወደ ሀገር እንዳይገባ ገደብ የተደረገበት ዕቃ መሆኑ እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በቀን 19/01/2013 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 10፡30 ሰዓት ላይ በሚሆንበት ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ልዩ ቦታው በግ ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የቤት ቁጥር 668 በሆነ መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በተደረገ ፍተሻ በአጠቃላይ ታክስና ቀረጥ መጠናቸው ብር 76,982.92 የሆነ ብዛቱ በቁጥር 80 ስቴክ ሻምላ የተባለ የስሪት ሀገሩ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ እና 79 ስቴክ ብሉስ የተባለ የስሪት ሀገሩ እንግሊዝ የሆነ ሲጋራዎችን በካርቶን አስቀምጠው የተገኙ በመሆናቸው የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ከሷል፡፡

አመልካቾች ክሱ ደርሷቸው በችሎት ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምንም ጥፋተኛ አይደለንም በማለት የተከራከሩ በመሆኑ ሁለት የአቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ተደርጓል፡፡ የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክርም በህብረተሰቡ ጥቆማ መሰረት በቀን 19/01/2013 ዓ.ም ከቀኑ 10፡30 ሰዓት አካባቢ በብርበራ ትዕዛዝ እና ታዛቢዎች ባሉበት የአሁን አመልካቾች ቤት እንደተበረበረ እና የተለያዩ የውጭ ሀገር ብሮች እና ሲጋራዎች መገኘታቸውን፣ የተገኙት ሲጋራዎች የስሪት ሀገራቸው ኢንግላድ እና የአረብ ኤምሬትስ እንደነበር በሰዓቱ ደረሰኝ ተጠይቀው እንዳልነበራቸው፤ የአሁን 2ኛ አመልካች ዕቃው የእኛ ነው ብሎ እንዳላቸው ከዛም ዕቃዎቹን እና አመልካቾችን በመኪና ይዘናቸው ወደ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወስደናቸዋል በማለት መስክሯል፡፡

2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በሰጡት የምስክርነት ቃልም በተሰጠን ጥቆማ መሰረት በቀን 19/01/2013 ዓ.ም ከቀኑ 10፡30 ሰዓት አካባቢ አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 668 የሆነ አመልካቾች የሚያከራዩት አልጋ ቤት ውስጥ የብርበራ ትዕዛዝ ወጥቶ እንደተበረበረ እና በክሱ ላይ የተገለፁትን የውጭ ሲጋራዎች አግኝተናል የአሁን 2ኛ አመልካች ለ1ኛ አመልካች ደውሎለት መጣ፣ ደረሰኝ እናመጣለን ብለው የነበረ ቢሆንም አላመጡም በማለት መስክራለች፡፡ ዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎችንም ከክሱ ጋር አያይዞ አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሰረት ቀርበው የተሰሙት የአቃቤ ሕግ ምስክሮች የአሁን አመልካቾች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን ስላስረዱ የአሁን አመልካቾች ዐቃቤ ሕግ ክስ በመሰረተበት ድንጋጌዎች ስር በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.142 መሰረት እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፤ የአሁን አመልካቾች ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አሰምተዋል፡፡ 1ኛ የመ/ምስክር የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለ ቀን 10፡00 ሰዓት አካባቢ እዚያው ቤት ውስጥ እንደነበሩ በዛን ሰዓት ሰፈሩ በፖሊሶች ተከቦ እየተፈተሸ እንደነበር እና የአሁን አመልካቾች አልጋ ቤት ዶላር ይመነዘራል ብለው እንደመጡ የአሁን አመልካቾች የሉም ይመጣሉ እንዳሏቸው፤ቤት ውስጥ ትንሽ ካዝና እንዳገኙ እና ቁልፍ ሲጠይቋቸው ቁልፍ የለም ሲሉ ሰብረው እንደከፈቱት እና ውስጡ ምንም እንዳልነበር፣ከዛም በመቀጠል የተከራዮችን ቤት እንደፈተሹ እና ከአንደኛው ቤት ውስጥ ሶስት ካርቶን ሲጋራ ይዘው እንደወጡ፣ ከዛም የአሁን 2ኛ አመልካች እንደመጣ እና ደረሰኝ አለህ ወይ ብለው ሲጠይቁት ቆይ ለወንድሜ ልደውል ብሎ ለአሁን 1ኛ አመልካች እንደደወለለት እና እሱ እስኪመጣ ድረስ ብለው ዕቃውን እና የአሁን 2ኛ አመልካችን ይዘው መሄዳቸውን፤ የተገኘው ሲጋራ ቤት ሰው የሙስሊም ኮፍያ እና ሸርጥ የለበሰ ሰውዬ እንደነበር እና ሰላም ብሎት እንደሄደ መስክሯል፡፡ 2ኛ መ/ምስክር መስከረም 19/2013 ዓ.ም ቁጭ ብዬ ጫት እየቃሙ እያለ ሰፈሩ ውስጥ የጦር መሳሪያ ፍተሻ እንደነበር እና ከዚያም ወደ አሁን አመልካቾች አልጋ ቤት እንደገቡ እና ፍተሻ እንደጀመሩ ከዛም የተቆለፈ ካዝና እንዳገኙ እና ቁልፍ ብለው ሲጠይቁ የለም ጠፍቷል ሲባሉ እንደተሰበረ፣ የተከራዮች ቤት እየተፈተሸ እንደነበር እና አንደኛው ቤት ቁልፉ ተሰብሮ በሚፈተሽበት ወቅት ሁለት ካርቶን የተበታተነ ሲጋራ እንደተገኘ፣ ሲጋራው የተገኘው ቤት ሰውዬ ሰላም ብሏቸው እንደወጣ፣ የአሁን 2ኛ አመልካች እንደመጣ እና ለ1ኛ አመልካች እንደደወለለት እና ሲመጣ ፖሊሶች ይዘዋቸው እንደሄዱ መስክሯል፡፡

3ኛ መ/ምስክር በበኩላቸው ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለ ቀን ከአሁን 2ኛ አመልካች ጋር ማኪያቶ ጠጥተው እየተመለሱ እንደነበር እና ቤቱም እየተፈተሸ እንደነበር፣ አልጋ ቤቱ የእናታቸው እንደሆነ እና ፖሊሶቹ ካዝናውን እየሰበሩ እንደነበር እና ቤቶቹን እየፈተሹ እንደነበር፣ ከዛም ሲጋራው እንደተገኘ እና የአሁን 2ኛ አመልካች ለ1ኛ አመልካች እንደደወለለት እና የተከራየው ሰውዬ ደረሰኝ አለው ወይ ብሎ እንደጠየቀው እና አላየሁም እንዳለው፣ አልጋ የተከራየውንም ሰውዬ እየዞሩ እንደፈለጉት እና እንዳላገኙት እና አመልካቾችን ፖሊሶች ይዘዋቸው እንደሄዱ መስክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ይህንን ተከትሎ በሰጠው ውሳኔም በክሱ ላይ የተመለከተው የውጪ ሀገር ሲጋራ ከህብረተሰቡ በደረሳቸው ጥቆማ መሰረት ፍተሻ ተደርጎ እንደተገኘ 2ኛ አመልካችም እቃው የኛ ነው እንዳላቸው እና 1ኛ አመልካች ደረሰኝ አመጣለሁ ያለ ቢሆንም አለማምጣቱን አቃቤ ህግ በምስክሮቹ ማስረዳቱን አመልካቾች በምስክሮቻቸው ቤቱን ሌላ ግለሰብ መከራየቱን በክርክራቸው አግባብ ያላስረዱ መሆኑን፤ ቤቱን ሌላ ሰው ለመከራየቱ መታወቂያና ሌላ አግባብነት ያለው ማስረጃ አለመቅረቡን፤ የመከላከያ ምስክሮቹ አመልካቾች እቃው የኛ ነው ብለው በገለፁበት ምስክሮቹ የሌላ ሰው ነው ማለታቸው የሚያሳምን አለመሆኑን በመጥቀስ አመልካቾችን በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ በማለት አመልካቾችን ያርማል ሌላውንም ያስጠነቅቃል ባለው በአንድ ዓመት ከስምንት ወር ፅኑ እስራት እና ብር 15,000.00/አስራ አምስት ሺህ/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌ/ከ/ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 32 መግቢያ የብርበራ ስራ ስለሚከናወንበት ሂደት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ማንኛውም መርማሪ ፖሊስ ወይም የፖሊስ ሰራዊት ባልደረባ በፍርድ ቤት በተሰጠ የብርበራ ማዘዣ መሰረት ካልሆነ በቀር ቤትን መበርበር እንደማይቻል በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይህንን ተከትሎ አንቀጽ 32(2) በፍርድ ቤት የሚሰጥ የብርበራ ትዕዛዝ የሚበረበረውን ቦታና የሚያዘውን ዕቃ ማመልከት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህም ባለፈ ብርበራው የሚያከናውነው የፖሊስ ባልደረባ በመያዣው ትዕዛዝ ከተመለከተው ዕቃ ውጭ መያዝ እንደማይችል በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ምንም እንኳን አመልካቾች የብርበራውን ትዕዛዝ ይዘት ብርበራው

በተከናወነበት ወቅት በውል ባንረዳውም የተከበረው ፍ/ቤት ከመዝገቡ እንደሚረዳው በክሱም ሆነ በፍርዱ በግልጽ እንደተመለከተው ፖሊስ ከፍርድ ቤት ያወጣው የብርበራ ትዕዛዝ የቤት ቁጥር 668ን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህም ቤት ውስጥ እንዲያዝ ትዕዛዝ የተሰጠበት ዕቃ የጦር መሳሪያ እና የውጭ አገር ገንዘብ ነው፡፡

በብርበራ ትዕዛዙ የተጠቀሰው ቤትም ሆነ እንዲያዝ ትዕዛዝ የተሰጠበት ዕቃ ከአመልካቾች ምንም ግንኙነት ያለው አይደለም፤ በፍርድ ቤትም አልተረጋገጠም፤ይልቁንም በዐቃቤ ሕግ 2ኛ ምስክርና በአመልካቾች መ/ምስክር እንደተመሰከረው ዕቃዎቹ የተያዙት የተቆለፈ ክፍል ቤት በሩ ተሰብሮ ነው፡፡ ይህ የተሰበረው ቤት ደግሞ እናታችን የሚያከራዩት ቤት ስለመሆኑ የተመሰከረ ሲሆን ይህ ቤት በዐቃቤ ሕግ ክስ እንደተመለከተው የአመልካቾች መኖሪያ ቤት አይደለም፡፡ ይህ በብርበራ ትዕዛዝ የተመለከተው የቤት ቁጥር 668 ተበርብሮ እንዳበቃ እንዲሁ መደዳውን ያሉት ቤቶች ናቸው የተበረበሩት፡፡ በዚህም ሂደት የእናታችን ቤት የቤት ቁጥር 664(ለ) ሲሆን ብርበራውም የተከናወነው መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ሲጋራዎቹም የተያዙት በቤት ቁጥር 668 ሳይሆን በዚህ ቤት ቁጥር 664(ለ) ውስጥ ሲሆን ብርበራው የተከናወነው በፍርድ ቤት ከተፈቀደው ቦታ ውጭ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ከዚህ ባለፈ ፍርድ ቤት ሰጠ የተባለው የብርበራ ትዕዛዝ የውጭ ምንዛሪን እና የጦር መሳሪያ ፍለጋ ነው፡፡ በብርበራው የተያዘው ግን በብርበራ ትዕዛዙ እንዲያዝ ፈቃድ ከተሰጠበት የጦር መሳሪያ እና የውጭ ምንዛሪ ውጭ ሲጋራ ነው፡፡ ስለዚህ የተከበረው ፍርድ ቤት ፖሊስ በፍርድ ቤት ከተሰጠው ስልጣን በማለፍ ባልተፈቀደበት የቤት ቁጥር ቤቱን ሰብሮ በመግባት እንዲያዝ ከተፈቀደው ውጭ ያለን ዕቃ ነው የያዘው፡፡ በሕግ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ የሚከናውን የባለስልጣን ተግባር ደግሞ እንዳልተከናወነ የሚቆጠር እና የሕግ ውጤት የማይሰጠው መሆኑ እየታወቀ አፈፃፀሙ የሕግ ስሕተት የለበትም መባሉ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው፡፡ ስለሆነም ፖሊስ ብርበራ ያከናወነው በብርበራ ትዕዛዝ ከተጠቀሰው የቤት ቁጥር 668 ሌላ በቤት ቁጥር 664(ለ) በመሆኑ ያለስልጣኑ ነው የሰራው እንዲባልልን፤

አመልካቾች የዐቃቤ ሕግን ምስክሮች ቃል በተገቢው ሁኔታ ያስተባበልን ሆኖ ሳለና የስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ያለን የማስረጃ ምዘናን መርህ በመጣስ ሆኖ ሳለ በማስረጃ ምዘና ረገድ የተፈፀመ ስሕተት የለም መባሉ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው፤ የአመልካቾች የእስራት ቅጣት ላለመገደብ በቂ ምክንያት ስለሌለው ሊገደብ የሚገባው ሆኖ እያለ አመልካቾች የእድሜያችን ለጋነት፤አዛውንትና በሽተኛ ወላጆቻችንን የምንረዳ እና የምንደግፍ መሆናችን ከግምት ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ ሊገደብ ሲገባ መታለፉ አግባብ አይደለም፤ ብርበራው የተደረገው የቤት ቁጥር 664(ለ) በሆነው የእናታችን ቤት ላይ መሆኑን ለማስረዳት በተጨማሪ ማስረጃነት ያቀረብነውን የንግድ ፈቃድ እና የኪራይ ውል ይቀበለን ጥያቄ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ስለሆነም ክሱን በአግባቡ ተከላክለዋል ተብሎ ከክሱ በነፃ እንድንሰናበት ይወሰንልን፤ይህ የሚታለፍ ቢሆን የአመልካቾችን የእስራት ገደብ ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ በቂ ምክንያት ባለመኖሩ የእስራት ቅጣቱ እንዲገደብልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የኮንትሮባንድ ዕቃ የተያዘው አመልካቾች ባከራዩት አልቤርጎ ክፍል ውስጥ ስለመሆኑ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባስረዱበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 168/2/ ስር ጥፋተኛ የተባሉበትን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2/ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሰበር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ 25/02/2014 ዓ.ም በተፃፈ በሰጠው መልስ ሲጋራው የተገኘበት ቤት የአመልካቾች በመሆኑ እና ቤቱ ለሌላ ሰው የተከራየ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካቾች በቀረበባቸው ወንጀል ጥፋተኞች ናቸው በሚል እንዲቀጡ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው ውሳኔ የሕግም ሆነ የማስረጃ ምዘና ስሕተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾችም የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አጣሪው በማሰቀረቢያነት ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ማንኛውም ሰው የግል ህይወቱ፣ግላዊነቱ የመከበር መብት ያለው መሆኑ፣ይህ መብቱም መኖሪያ ቤቱ፣ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን እንደሚያካትት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 26(1) የተመለከተ ሲሆን ይህ መብት ያለ ገደብ የተሰጠ ሳይሆን በተወሰኑ በህጉ በተመለከቱት ሁኔታዎች ሊገደብ እንደሚችል በአንቀፅ 26(3) የተመለከተ ሲሆን በዚህ አግባብም አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሄራዊ ደህንነትን፣የህዝብን ሰላም፣ወንጀልን በመከላከል፣ጤናንና የህዝብ የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር አላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ህጎች መሰረት የመብቱ አጠቃቀም ሊገደብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

በዚህ አግባብ ሊመረመርና ተገቢው የህግ ትርጉም ሊሰጣቸው የሚገባው የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.32 እና 33 ድንጋጌዎች አንድ መርማሪ ፖሊስ ወይም የፖሊስ ሰራዊት ባልደረባ የወንጀል ድርጊት ተፈፅሟል ብሎ ሲያምንና ከወንጀል ምርምራው ሂደት ጋር በተያያዘ ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ እንዲረዳው ብርበራ በማድረግ ማስረጃዎቸን መሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በመርህ ደረጃ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(1) የብርበራ ማዘዣ ከማንኛውም ፍርድ ቤት ሊያገኝ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን ለፍትህ አላማ እንዲረዳ ምርመራውን ለማገዝ እንዲችል ይህ ሲከወንም የተጠርጣሪውን ግለሰባዊ መብት ባከበረ መልኩ መፈፀሙ አስፈላጊ መሆኑ በፍርድ ቤቱ ታምኖበት የተሰጠው የብርበራ ማዘዣ የሚበረበረውንና የሚያዘውን እቃ በግልፅ ማመልከት ያለበት መሆኑን፣ በብርበራ ትዕዛዙ ላይ ከተመለከተው እቃ ውጪ ፖሊስ ሊይዝ የማይችል መሆኑን አንቀፅ 33(2) የሚደነግግ ሲሆን፣ብርበራው የሚደረግበትን ሰአት አስመልክቶም በተለየ ሁኔታ ካልታዘዘ በስተቀር ብርበራው የሚደረገው ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰአት ጀምሮ እስከ ማታው አስራ ሁለት ሰአት ድረስ ብቻ መሆኑን በአንቀፅ 33(5) የተመለከተ መሆኑን መነሻ በማድረግ የተዘጋጀው በህጉ የተመለከተው ፎርም የብርበራው ቀንና ሰአት በግልፅ መመልከት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ዝርዝር ሁኔታዎች ብርብራ የሚደረግበትን የህግ ስርዓት በዝርዝር የሚያመለክቱ ቢሆኑም በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.32(2) የተመለከቱት ቀሪ ሁኔታዎች (Exceptions) በሌሉበት ብርበራ ያለ ብርበራ ትዕዛዝ ቢከናወን ወይም በብርበራ ትዕዛዙ ከተመለከተው ጊዜና ቦታ ውጪ ብርበራ ቢደረግ አልያም በብርበራ ትዕዛዙ ላይ ከተመለከተው እቃ ውጪ በብርበራ ቢያዝ በሂደቱ የተገኘው ማስረጃ አግባብነቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ በህጉ በግልፅ አልተመለከተም፡፡ በተለያዩ የህግ ስርዓቶች በብርበራ የተገኘ ማስረጃን አስመልክቶ ማስረጃው የተገኘበት አግባብ ህጋዊ አለመሆኑ ማስረጃውን ህገ ወጥ አያሰኘውም (Admissibility of evidence is not affected by the illegality of the means through which the party has been enabled to obtain the evidence) የሚለው በመጀመሪያ የነበረው መርህ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብትን (Right to privacy) ጥበቃ መስጠትን ግቡ በማድረግ በሂደት እየዳበረ ሄዶ የብርበራው ምክንያታዊ መሆን ከብርበራው ለተገኘው ማስረጃ ተቀባይነት የሚያስገኝለት ሆኖ ምክንያታዊ ካልሆነ በብርበራ የተገኘን ማስረጃ ዋጋ ማሳጣት እየተለመደ የመጣ ሲሆን የብርበራው ምክንያታዊ መሆንና አለመሆን የሚለካውም ብርበራው ሲካሄድ የነበሩትን አጠቃላይ (Total atmosphere of the case) ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን እንደሚገባ የተለያዩ የዘርፉ ፀሀፍት ያስረዳሉ፡፡

በዚህ አግባብም ተጨማሪ የብርበራ ትዕዛዝ ለማግኘት በቂ እና ምክንያታዊ ጊዜ ነበርን? የሚለው የብርበራውን ህጋዊነት ለመመዘን ከግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባ መሰረታዊ መስፈርት ተደርጎ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ ከሶስት አመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ክስ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ወንጀል ለማስረጃ የሚሆን ወንጀሉ የተፈፀመበት ነገር በአንድ ቦታ የተደበቀ ወይም የተቀመጠ መሆኑ ለመርማሪው ፖሊስ ወይም ለፖሊስ ሰራዊት ባልደረባ የተነገረው ከሆነና መበርበሪያ ትዕዛዝ እስኪቀበል ድረስ ወንጀል የተሰራበት ነገር ካለበት ቦታ ይወሰዳል ተብሎ በበቂ ምክንያት የታመነ ከሆነ ብርበራው

ያለብርበራ ማዘዣ ሊከናወን እንደሚችል በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 32(2)(ለ) መመልከቱ ከላይ የተመለከተው ቀሪ ሁኔታ በስነ ስርዓት ህጋችንም ተገቢው አውቅና የተሰጠው መሆኑን ያሳያል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይም በብርበራ የተገኙት ሲጋራዎች ተቀባይነትና ማስረጃዊ ፋይዳ ህገ መንግስታዊ ጥበቃ ከተሰጠው የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት አንፃር እየታየና እየተመዘነ የህግ ትርጉም ሊሰጠው ይገባል ብለን እናምናለን፡፡ አመልካቾች ብርበራው የተከናወነው ብርበራው እንዲከናወን ከተፈቀደለት ቤት ውጪ እናታቸው የንግድ ፈቃድ በማውጣት እያከራዩ በሚጠቀሙበት የቤት ቁጥር 664(ለ) ውስጥ መሆኑን በብርበራ የተገኘው እቃም የብርበራ ፈቃድ ከተሠጠበት የጦር መሳሪያና የውጪ ምንዛሪ ውጪ ሲጋራ መሆኑን በመግለፅ በብርበራው የተገኘው በውጪ ሀገር የተመረተው ሲጋራ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብባቸው እንደማይገባ ገልጸው የተከራከሩ ቢሆንም በአመልካቾች ጭምር እንደታመነው ቤቱ እናታቸው አከራይተው የሚጠቀሙበት ሆኖ እያለ የመከላከያ ምስክሮቹ እንዳስረዱትም ቤቶቹ ለአልጋ ተከራዮች የሚከራዩ ሆኖ እያለ ይህም በቤቱ ላይ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት አላቸው ሊባሉ የሚችሉት በወቅቱ የተከራዩ ግለሰቦች የነበሩ መሆኑን አመልካቾች በምስክሮቻቸው ያላስረዱ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከመረጋገጡ አንፃር የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብቱ እጅግ ቢበዛ የእናታቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

አመልካቾች የቤቱ ባለቤት ባለመሆናቸው ብርበራው ከተከናወነበት ቤት ጋር በተያያዘ ሊከበር የሚገባ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት ያላቸው መሆኑን ከመነሻውም ባላሳዩበት ብርበራው ኢ-ምክንያታዊ ሆኖ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብታችንን ጥሷል በዚህ ምክንያትም ማስረጃው አግባብነት የለውም ብለው መከራከራቸው የሚያሳምን ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በብርበራው ወቅት የነበሩትን አጠቃላይ ሁኔታዎች ስንመዝንም ለመርማሪው ተጨማሪ የብርበራ ትዕዛዝ ለማግኘት የሚያስችሉ አለመሆናቸውን ምስክሮቹ ከሰጡት የምስክርነት ቃል የምንረዳው ነው፡፡ ይህም አመልካቾች በብርበራ የተገኘው ሲጋራ ለፖሊስ ከተፈቀደለት ስልጣኑ ውጪ የተገኘ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ያቀረቡት ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችና መርህዎች መሰረት ያላደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡

አመልካቾች ከማስረጃ ምርመራና ምዘና አንጻር ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ በተመለከተ በመሰረቱ በኢፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡ በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው ውሳኔም በክሱ ላይ የተመለከተው የውጪ ሀገር ሲጋራ ከህብረተሰቡ በደረሳቸው ጥቆማ መሰረት ፍተሻ ተደርጎ እንደተገኘ 2ኛ አመልካችም እቃው የኛ ነው እንዳላቸው እና 1ኛ አመልካች ደረሰኝ አመጣለሁ ያለ ቢሆንም አለማምጣቱን አቃቤ ህግ በምስክሮቹ ማስረዳቱን አመልካቾች በምስክሮቻቸው ቤቱን ሌላ ግለሰብ መከራየቱን በክርክራቸው አግባብ ያላስረዱ መሆኑን፤ቤቱን ሌላ ሰው ለመከራየቱ መታወቂያና ሌላ አግባብነት ያለው ማስረጃ አለመቅረቡን፤የመከላከያ ምስክሮቹ አመልካቾች እቃው የኛ ነው ብለው በገለፁበት ምስክሮቹ የሌላ ሰው ነው ማለታቸው የሚያሳምን አለመሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣናቸውን ተጠቅመው የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀሙት ስህተት ከተገኘ ብቻ ሲሆን ይህ ችሎት ባደረገው ምርመራ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ያልተገኘ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠታቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ገደብን አስመልክቶም ከእስር በገደብ መለቀቅ ማለት ፍርድ ቤት አንድ ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑን አረጋግጦ ከእስር እንዲፈታ የሚደረግበት የህግ ስርዓት መሆኑን ከወ/ህ/አ.190 የምንገነዘበው ነው፡፡ የገደብ ውሳኔ በዘፈቀደ የሚሰጥ ወይም የሚከለከል ባለመሆኑ የገደብ አሰጣጥ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ ፍርድ ቤቶች በህግ የተመለከቱት ሁኔታዎች በዋነኝነትም በወ/ህ/አ.192፤194 እና 197 መሟላት አለመሟላታቸውን በጥንቃቄ ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ በዚህ አግባብ የገደብ ውሳኔ ካልተሰጠ የወንጀል ህጉን መሰረታዊ አላማ ለማሳካት የማይቻል መሆኑ ይታመናል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት የገደብ ጥያቄ አቅርበው የነበረ መሆኑን የግራ ቀኙን ክርክር ተከትሎ የተሰጠው ውሳኔ የሚያሳይ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የገደብ ጥያቄውን ውድቅ ያደረገው በደፈናው ይገደብልን በማለት ያቀረቡትን ሀሳብ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም በማለት ነው፡፡ የአመልካቾች የገደብ ጥያቄ ከወ/ህ/አ.192፤194 እና 197 መስፈርቶች አንፃር ተቀባይነት ያጣበትን ምክንያት በመዘርዘር በውሳኔው ላይ የገደብ ጥያቄውን ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት በዝርዝር አላስፈረም፡፡ ይህ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የገደብ ጥያቄን በደፈናው ውድቅ የማድረግ ሂደት ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ሊታረም ሲገባው ፍርድ ቤቱ ይህንን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሳያርም መቅረቱ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአመልካቾች የተጣለው የእስራት ቅጣት ከአምስት ዓመት ፅኑ እስራት ያልበለጠ መሆኑ በወ/ህ/አንቀጽ194(1)(ለ) የተመለከተው መሰረታዊ መስፈርት መሟላቱን የሚያሳይ ሲሆን በአመልካቾች ላይ የተያዘ የቀደም ሪከርድ አለመኖሩና የእድሜያቸውን ሁኔታ እንዲሁም ማህበራዊ ተሳትፏቸውና ለቤተሰባቸው የሚያደርጉት ድጋፍ ሲታይ አመልካቾች ከስህተታቸው እንዲማሩና በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት እንዳይሰማሩ አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ከዚህ በኋላ ባለው ህይወታቸው በመልካም ፀባይ እንዲመሩና ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲታቀቡ ይረዳል፤ያግዛል ብለን ስላመንን በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የእስራት ቅጣት በሁለት አመት የፈተና ጊዜ ሊገደብ ይገባል በማለት ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 289523 በቀን 15/10/2013 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነትና በ21/10/2013 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ (የገደብ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሳይጨምር) የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.272693 በቀን 14/11/2013 ዓ.ም ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ገደብን አስመልክቶ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 289523 በ21/10/2013 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ክፍል እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

3. በአመልካቾች ላይ የተጣለው የእስራት ቅጣት አፈፃፀሙ በሁለት አመት የፈተና ጊዜ የተገደበ ስለሆነ አመልካቾች በዚህ የፈተና ጊዜ ውስጥ በወንጀል ድርጊት ላለመሰማራት ግዴታ ገብተው ፈርመው ለገደቡ አፈፃፀም ዋስትና እየአንዳንዳቸው ብር 25,000.00(ሀያ አምስት ሺ.ህ ብር) ሲያሲዙ ወይም ተመጣጣኙን ዋስትና ሲያቀርቡ ከእስር እንዲለቀቁና በዚህ ችሎት ለዋስትና ያስያዙት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ታዟል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የልዩነት ሀሳብ

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 2 ስር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ ከሌሎች ባልደረቦቼ /አብላጫው ድምጽ/ በሀሳብ የተለየሁ ሲሆን፣ አብላጫው ድምጽ ለወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 32 እና 33 ላይ ስለብርበራ ትዕዛዝ የተደነገገውን አስመልክቶ የሰጠው ትርጉምም በከፊል የማልስማማበት በመሆኑ እና በፍሬ ጉዳዩ ላይም አመልካቾች ክሱን እና ማስረጃውን አልተከላከሉም መባሉ ተገቢ አይደለም በሚል ነው፡፡

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 32 እና 33 ጣምራ ንባብ በጥቅሉ የሚያሳዩን፡- ፖሊስ የሰውን ቤት መበርበር እና ዕቃ መያዝ የሚችል ስለመሆኑ፣ ነገር ግን የብርበራ ትዕዛዝ ከፍ/ቤት ማውጣት ያለበት ስለመሆኑ፣ እጅ ከፍንጅ የተያዘ ከሆነ ሰውነቱን መበርበር እና ወንጀል የተፈፀመበትን መሳሪያ መያዝ የሚችል ስለመሆኑ፣ የብርበራ ፈቃድ ማንኛውም ፍ/ቤት ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ፣ የሚሰጠው የብርበራ ማዘዣ ግን ለምርመራ፣ ለክስ መሰማት ወይም በሕጉ መሠረት ለሌላው የክስ ሥነ ሥርዓት የማዘዣው መሰጠት የሚጠቅም መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የሚሰጥ መሆኑን፣ የብርበራ ማዘዣው የሚበረበረውንና የሚያዘውን ዕቃ ማመልከት ያለበት ስለመሆኑ፣ በማዘዣው ውስጥ ከተመለከተው በቀር መርማሪው ፖሊስ ወይም የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ ሌላውን ዕቃ መያዝ የማይችል ስለመሆኑ፣ በብርበራ የሚገኝ ዕቃ አመዘጋገብ፣ አቀማመጥ፣ ለብርበራ የሄደው ፖሊስ ስለሚጠቀመው ሃይል፣ የመበርበሪያ ሰዓት በሚገልጽ ሁኔታ በዝርዝር ያስቀመጠ ነው፡፡

ነገር ግን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 32/2/ለ ስር ከ3 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ክስ ወይም አቤቱታ የቀረበበትን ወንጀል በማስረጃ የሚሆን ወንጀሉ የተፈፀመበት ነገር በአንድ ቦታ የተደበቀ ወይም የተቀመጠ መሆኑ ለመርማሪው ፖሊስ ወይም ለፖሊስ ሠራዊት የተነገረው በሆነ ጊዜ ተገቢ ጥርጣሬ የሚያሳድር ሲሆንና የብርበራውን ማዘዣ እስኪቀበል ድረስ ወንጀል የተሠራበት የተባለው ነገር ካለበት ቦታ ይወሰዳል ተብሎ በበቂ ምክንያት የታመነ ሲሆን ያለብርበራ ትዕዛዝ መበርበር እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 26/1/ ማንኛውም ሰው የግል ህይወቱ ግላዊነቱ የመከበር መብት ያለው ስለመሆኑ ይህ መብት ደግሞ መኖሪያ ቤቱ፣ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን እንደሚያካትት ደንግጓል፡፡

ከህገ መንግሥቱ እና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ወንጀል ተፈጽሟል በሚል ብቻ የሰውን አካል እና ቤት መበርበር እና ወንጀል የተፈፀመበት ነው በሚል ንብረት መያዝ የማይቻል መሆኑን ይህ መብት ደግሞ በህገ መንግሥቱ ጥበቃ የተደረገለት መብት መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በህጉ በዚህ መልኩ የተቀመጠ ከሆነ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካቾች ቤት እንዲፈተሽ ፍ/ቤቱ የብርበራ ፈቃድ የሰጠው ለቤ/ቁ. 668 የሆነው ቤትን የሚመለከት ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ከዚህ ቤት ተፈትሾ እንዲያዝ ፈቃድ የተሰጠበትም የጦር መሳሪያ እና የውጭ አገር ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡ ፖሊስ በተሰጠው የብርበራ ትዕዛዝ መሠረት መፈፀሙን እና ነገር ግን የብርበራ ትዕዛዝ ከወጣበት ቤት በቁጥርም ሆነ በይዘት በሚለየው የቤ/ቁ/ 664/ለ/ የሆነውን ቤት ቁልፍ በፖሊስ ተሰብሮ ፍተሻ ተደርጎ ሲጋራዎች የተገኙ መሆኑን ነው፡፡

አሁን እያከራከረ ያለው ፖሊስ ብርበራ ለማከናወን የጠየቀው የቤ/ቁ. 668 የሆነውን ሆኖ ለምን የቤ/ቁ/664/ለ/ ፈተሸ? በዚህ መልኩ የተገኘ ማስረጃስ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው ሲሆን፣ በቅድሚያ ይሄ ቤት ሲጋራ ተገኘበት የተባለው ቤት የአመልካቾች ቤት ሳይሆን የእናታቸው የኪራይ ቤት መሆኑ፣ ለብርበራ ትዕዛዝ ፖሊስ ካወጣበት ቤት ቁጥር ውጭ ማለትም ከአመልካቾች ቤት ውጭ የእናታቸው የሆነውን ቤት ለመፈተሽ ብርበራ ያላወጣበትን ቤት መፈተሽ ያስፈለገው አሁን የተያዘው ሲጋራ በዛ ቤት ውስጥ እንደሚገኝ ጥቆማ ደርሶት እና ተፈጽሟል ሊባል የሚችለው ወንጀል እንደ ህጉ አቀማመጥ ከ3 ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጣ መሆኑን አውቆ

እና የብርበራ ትዕዛዝ እስኪያወጣ ድረስ የወንጀል ፍሬው ይሸሽብኛል ብሎ ሰግቶ ስለመሆኑ ከአጠቃላይ ክርክሩ ውስጥ ማግኘት አልተቻለም፡፡

በህጉ በፍ/ቤት ከሚሰጥ ብርበራ ትዕዛዝ ውጭ አንድ ቤት ሊበረበር የሚችልበትን ምክንያት የተቀመጠ ከመሆኑ አኳያ ከዚህ ውጪ ያለብርበራ ትዕዛዝ የሚፈፀምን ብርበራ በህገ መንግሥቱ የተቀመጠውን እና የመኖሪያ ቤታቸውን ያለመበርበር መብት የሚነካ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም ፖሊስ በእለቱ የብርበራ ፈቃድ ያላወጣበትን ቤት በራሱ ፈቃድ የፈተሸ ከመሆኑም በላይ ቤቱ የተከራየ እና በሰዓቱም ተቆልፎ የነበረ በመሆኑ በዛ ቤት ውስጥ በወንጀል የሚያስጠረጥር ንብረት ተደብቋል የሚል ጥቆማ የደረሰው ቢሆን እንኳን የመበርበሪያ ፈቃድ ለማውጣት የማያስችለው ሁኔታ ላይ እንዳልነበረ እና ሰዓቱም የሥራ ሰዓት ላይ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ህጉ ለዚህ መብት ጥበቃ ማድረግ ያስፈለገውም የሰዎችን ረግቶ መኖር እና የመኖሪያ ቤታቸው ያለመደፈር መብት ከመጠበቅ ባለፈ በህግ አስከባሪው አካል የማናለብኝነት አሰራር እንዲጠበቁ ለማድረግ እና የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

ፖሊስ በዚህ ቤት ውስጥ በህጉ አግባብ በወንጀል የሚያስጠይቅ ዕቃ አለ ብሎ ስለመጠቆሙ በዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የተረጋገጠ ነገር የሌለ በመሆኑ አንድ የፖሊስ አባል የተዘጋ ቤትን ሁሉ የመበርበር መብት በህግ ያልተሰጠው ከመሆኑ አንፃር፣ በተያዘው ጉዳይ የሚበረበረው ቤት ባለቤት ሲጋራው ተያዘበት ከተባለው ሰው ባለቤትነት መብት የሚለየም ከመሆኑ አኳያ ህጉ ሊጠብቀው እና ሊከላከልለት ካሰበው የሰዎች ሰብአዊና ህገ መንግሥታዊ ሰፊ መብት አንፃር በተበረበረው ቤት ውስጥ የተገኘው ሲጋራ በህገ ወጥ መንገድ ወደ አገር የገባ በመሆኑ ብቻ ከዚህ ለሰዎች ከተሰጠው ህገ መንግሥታዊ መብት በማስበለጥ ማስረጃዎችን በህግ አግባብ እንደተገኘ በመቁጠር ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢ ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡

ሌላው አመልካቾች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ወንጀሉን መፈፀማቸው ተረጋግጧል በማለት እንዲከላከሉ በተሰጣቸው እድል እና መከላከያ ምስክሮቻቸውም የተበረበረው ቤት የተከራየ ቤት መሆኑን፣ ሲጋራው የተገኘው በዛ ቤት ውስጥ እንደሆነ፣ ለተበረበረው ቤት ንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑን፣ ቤቱ ቁልፉ ተሰብሮ የተበረበረና በቤቱ ውስጥ የነበረው ሰው ከቤቱ ሲወጣ ሰላም ብሎ የወጣ እና በቤቱ ውስጥም የሙስሊም ኮፍያ ጭምር የነበረ ስለመሆኑ የገለፁ ከመሆኑ አንፃር ቤቱ በኪራይ የሚተዳደር በሆነበት ቤቱን የተከራየው ሰው ባልተጠየቀበት ከራሳቸው ቤት ውጭ ሌላ ቤት ተበርብሮ የተገኘን ንብረት የአመልካቾች ነው ተብሎ አልተከላከላችሁም መባላቸው መሠረታዊ የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው ብዬ ስለማምን የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ አመልካቾች ነፃ ሊሰናበቱ ይገባው ነበር በሚል ከአብላጫው ድምጽ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

## ክፍል ሁለት

## 2.የዋስትና መብት

### 2.1 ዋስትና በሕግ የሚፈቀድበት እና የሚከለከልበት አግባብ[138]

- ፍ/ቤቶች ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል የዋስትናን መብት የሚያስከለክል ሆኖ ባገኙት ጊዜ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 ን መሠረት በማድረግ የተከሳሹን የዋስትና መብት ከከለከሉ / ከነፈጉ / ከመነሻውም ቢሆን የተከሳሹ የዋስትና መብት የተከለከለው በሕግ በመሆኑ ዋስትናን ሊያስከለክሉ ይችላሉ ተብለው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መመርመር እና መመዘን አይጠበቅባቸውም፡፡[139]

የሰ.መ.ቁ 199786

ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አብደላ ሽኩር መሐመድ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በጠበቃው አማካኝነት ታሕሳስ 12 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 286774 መስከረም 21 ቀን 2013 ዓ.ም አመልካች የተከሰሰበት ጉዳይ የዋስትና መብት የሚያሰጥ ስላልሆነ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተል ሲል የሰጠው ትዕዝዝ፤ ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 263195 ታህሳስ 26 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ዋስትናን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27 እና 631/1/ለ ድንጋጌን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና ጉዳይ መርምሮ አመልካች የተከሰሱበት ድንጋጌ ዋስትናን የሚያሰጥ ስላልሆነ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህን ትእዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጎጂው በሕይወት የሚገኝ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 መሠረት ዋስትና ሊከለከል የሚችል አይደለም፤ ሆኖም አመልካች

---

[138]በሰ/መ/ቁ 199786 (ሰኔ 19 ቀን 2011 ዓ.ም)

[139]ሰ/መ/ቁ 275196 (የካታት 27 ቀን 2017 ዓ.ም) በሰ/መ/ቁ 35695 (ህዳር 11 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 09 ፣ በሰ/መ/ቁ 63344 (ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12 ፣ በሰ/መ/ቁ 263872 (ሐምሌ 30 ቀን 2016 ዓ.ም) ፣፣ በሰ/መ/ቁ 34077 (መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 247563 (ሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም)

በተከሰሰበት ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊወሰንበት የሚችለውን ቅጣት በመፍራት እና በቀን ስራ የሚተዳደር ከመሆኑም አንጻር ስራውን በየትኛውም ሁኔታ እና ቦታ የማያጣው መሆኑን በማሰብ ዋስትናውን አክብሮ ሊቀርብ እንደማዩችል ፍርድ ቤቱ አምኖበታል፤ ከዚህም በላይ በዋስታና ቢለቀቅ ምስክሩን በቀላሉ በማባበል ማስረጃ ሊያጠፋ እና ተጎጂም በዕድሜ ሕጻን በመሆኑ ተከሳሽን በአካል ቢያገኘው ሌላ ድንጋጤ እና ፍራቻ ውስጥ በመግባት ጫና ሊያሳድርበት ስለሚችል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 / ሀ እና ሐ መሠረት ዋስትናው ሊከለከል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ትዕዛዝ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያላነሳውን መከራከሪያ ጉዳዩ በይግባኝ ሲታይ ማቅረቡ አግባብ አይደለም፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 194/1 የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ስልጣን በስር ፍርድ ቤት የተፈጸመውን የሕግ እና የማስረጃ ስሕተት ማረም እንጂ አዲስ ክርክር መስማት አይደለም፤ በሌላ በኩል አመልካች የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ለመቅረብ አይችልም የሚል ግምት ለመውሰድ መነሻ ምክንያት ያስፈልጋል፤ ፍርድ ቤቱ ለግምቱ መነሻ ያደረገው አመልካች በቀን ስራ ተዳዳሪ መሆኑን ነው፤ የችሎት ቀጠሮን አክብሮ መገኘት የሕግ የበላይነትን ማመን እና መቀበልን የሚጠይቅ እንጂ የቀን ሰራተኛ በመሆኑ ሕግ የማያከብር ሆኖ ሊወሰድ ስለማይገባው የስር ፍርድ ቤቶች ወሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ባቀረበው የይግባኝ አቤቱታ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ እና ሐ መሠረት ዋስትና መከልከሉ ተገቢ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በስር ፍርድ ቤት በተደረገው የዋስትና ክርክር ዓቃቤሕግ በሰጠው አስተያየት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ መሠረት ዋስትናውን የተቃወም ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ በውሳኔው ላይ ሳይገልጽ አመልካች የተከሰሰበት ድንጋጌ ዋስትናን አያስፈቅድም በሚል ብቻ ዋስትናውን ነፍግጓል፤ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ በሁኔታዎች የሚረጋገጥ እንጂ እራሱ ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ ድንጋጌ አይደለም፤ የይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ አዲስ ክርክርን መሠረት በማድረግ የተሰጠ ሳይሆን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበውን ሀሳብ እና አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ በሁኔታዎች የሚረጋገጥ መሆኑን በመረዳት በደንብ ተብራርቶ ያልቀረበውን የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማብራራት የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጠው የመልስ መልስ ፍርድ ቤቶች የግራቀኙ ተከራከሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር በአግባቡ እንደሚመዘግቡ ግምት ይወሰዳል፤ የችሎቱ ውሎ እንደሚያሳየው ክርክሩን በእጅ ጽሁፍ የመዘገበ መሆኑን ነው፤ በእጅ ሲመዘገብ ተከራካሪ ወገን የተናገረው በሙሉ ቃል በቃል ላይመዘገብ ይችላል እንጂ መሠረታዊ የክርክሩ ይዘት ሳይመዘገብ ስለማይታለፍ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ዓቃቤሕግ ያቀረበው ክርክር ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የተያዙ ሰዎች በሕገ-መንግስቱ ጥበቃ ከተደረጉላቸው መብቶች አንዱ የዋስትና መብት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6 የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሕገ-

መንግስቱ ልዩ ጥበቃ የተሰጠውን ይህን መሠረታዊ መብት አስመልክቶ የመወሰን ስልጣን እና ሃለፊነት የተሰጣቸው ፍ/ቤቶችም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው የሚያቀርበውን የዋስትና መብት ጥያቄ እና ከሣሽ የሆነው ዓቃቤሕግም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት ከሕገመንግስቱ መሠረታዊ ዓላማ እና ዋስትናን አስመልክቶ በልዩ ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ መርምረው ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ሲያደርጉም በመርህ ደረጃ የዋስትናን መብት መፍቀድ ያለባቸው ሲሆን በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ግን የዋስትናን መብት በልዩ ሁኔታ ሊነፍጉ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ምክንያቶች አንደኛው ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስትና ለመለቀቅ የሚከለክል ሲሆን በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕቁ 63 የሕግ ክልከላን መሠረት በማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስ መለቀቅን የማይከለክል ቢሆንም ተጠርጣሪው ቢለቀቅ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተገለፁትን ተግባራት ይፈጽማል ተብሎ ሲታመን ነው፡፡

ፍ/ቤቶች ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል የዋስትናን መብት የሚያስከለክል ሆኖ ባገኙት ጊዜ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 ን መሠረት በማድረግ የተከሳሹን የዋስትና መብት ከከለከሉ / ከነፈጉ / ከመነሻውም ቢሆን የተከሳሹ የዋስትና መብት የተከለከለው በሕግ በመሆኑ ዋስትናን ሊያስከለክሉ ይችላሉ ተብለው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መመርመር እና መመዘን አይጠበቅባቸውም፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል ዋስትናን የማያስከለክል ከሆነ እና ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ የተመለከተቱትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ የተከሳሹን የዋስትና መብት ጥያቄ ተቃውሞት ከሆነ ግን ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተከሳሽን የዋስትና መብት ለማስከልከል የቀረቡት ምክንያቶች ዋስትናውን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ እና ሕጋዊ ምክንያቶች መሆን አለመሆናቸውን መርምሮ እና መዝኖ ውሳኔ ሊያሳርፍበት ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቱ አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27 እና 631/1/ለ ዋስትናን የሚያሰጥ ስላልሆነ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተል በማለት የአመልካችን የዋስትና መብት ውድቅ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ ተጎጂው በሕይወት የሚገኝ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 መሠረት ዋስትና ሊከለከል አይችልም ካለ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች የአመልካች የዋስትና መብት ሊከለከል ይገባል ከሚል መደምደሚ ላይ ደርሷል፡፡ ዓቃቤሕግ ለዚህ ችሎት ባቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የአመልካች የዋስትና መብት እንዲከለከል ያቀረብኩት መከራከሪ እያለ ፍርድ ቤቱ በአግባቡ ሳይመዘግብልኝ ቀርቷል በማለት የሚከራከር ቢሆንም በስር ፍርድ ቤት ዋስትናን በሚመለከት በተደረገው ክርክር በአቃቤሕግ በኩል የቀረበው አስተያየት አመልካች የተከሰሰበት አንቀጽ ከ15 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ በመሆኑ የዋስትና መብቱ እንዲነፈግ በሚል ከመከራከሩ በቀር ዓቃቤሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የአመልካች የዋስትና መብት ሊነፈግ ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር እንዳለ የውሳኔው ይዘት አያመለክትም፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ዓቃቤሕግ በዋስትናው ጉዳይ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ በተጠየቀ ጊዜ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የአመልካች የዋስትና መብት ሊከለከል ይገባል በማለት ያቀረበው መከራከሪያ ሳይኖር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ የአመልካችን የዋስትና መብት በመንፈግ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ የይግባኝ አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ሲሆን፤ የሚቀርበውም ይግባኝ በዚሁ ወሳኔ ላይ የተመለከቱትን መከራከሪዎችን እና ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ እንጂ ይግባኝ በተጠየቀበት ውሳኔ ላይ ያልቀረበን አዲስ መከራከሪያን እና ምክንያትን መነሻ በማድረግ ሊቀርብ የማይገባ መሆኑን፤ ጉዳዩን በይግባኝ የሚመለከተው ፍርድ ቤትም ይግባኝ በተጠየቀበት ወሳኔ ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ሊያጸና፤ ሊያሻሽል ወይም ሊሽር የሚችል ስለመሆኑ፤ ከዚህ ውጪ በስር ፍርድ ቤት በተከራካሪ

ወገኖች ያልቀረቡ አዲስ መከራከሪያዎችን መሠረት በማድረግ ሊወስን የሚችልበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ ስለይግባኝ ስርዓት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ በቁጥር 181 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ዓቃቤሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የአመልካች የዋስትና መብት ሊከለከል ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር በሌለበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ የአመልካችን የዋስትና መብት በመከልከል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 263195 ታሕሳስ 06 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67(ሀ)(ሐ) መሠረት በበመከልከል የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ፈጽሞታል በተባለው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የግል ተበዳይ ሕይወት ያሳላፈ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 መሠረት የዋስትና መብቱ ሊነፈግ አይገባም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ በመሆኑ እና ዓቃቤሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች የአመልካች የዋስትና መብት ሊነፈግ ይገባል በማለት ያቀረበው መከራከሪያ የሌለ በመሆኑ አመልካች በዋስ ሆኖ ጉዳዩን ሊከታተል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

-አመልካች በስር ፍ/ቤት ቀርቦ በዋስትና መጠኑ ላይ እስኪከራከር ድረስ ለብር 10000 / አሥር ሺህ/ የሚበቃ ዋስ ሲያቀርብ ወይም ገንዘቡን በሞዴል 85 ሲያስይዝ ከእስር እንዲለቀቅ ታዟል፡፡

-የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካች በዋስትና እንዲለቀቅ የተወሰነ መሆኑን አውቆ በዚህ ችሎት እንዲያስይዝ የተወሰነውን የዋስትና ገንዘብ ማስያዙን ሲረጋገጥ በሌላ ጉዳይ የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡

-አመልካች ከሐገር እንዳይወጣ ታዟል፡፡ ይጻፍ፤ ትዕዛዙ ለሚመለከታቸው አካላት ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## <u>2.2 ዋስትና በሁኔታ የሚፈቀድበት እና የሚከለከልበት አግባብ</u>[140]

- አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወሰደው በቂና ህጋዊ ሊባለ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚገባ፤ እንዲሁም

[140]የሰ/መ/ቁ.134228 ( የካቲት 08 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20

ምክንያቶቹ በቂና ህጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህሪ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ፤[141]

የሰ/መ/ቁ.134228

የካቲት 08 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓሊ መሃመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አይሸሽም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ስማቸው ከበደ

- ጠበቆች ታምሩ ወ/አገኝ፤ ሲሳይ ለምለም ፍስሃ አለማየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ - ያለምወርቅ አስታጥቄ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ባለው የወንጀል ክስ ክርክር የቀረበን የዋስትና ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ክሱን እየተመለከተ ለሚገኘው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ከ2ኛው ክስ ነጻ ስለወጣሁና ተከላከል የተባልኩባቸው ክሶች ላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ዋስትና የማያስከለክሉ በመሆኑ የዋስትና መብት ይፈቀድልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ ተከሳሽ የተከሰሱበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ መሆኑን፤ እንዲሁም ነፃ በወጡበት ጉዳይ ይግባኝ የጠየቁበት መሆኑን በማንሳት የዋስትና መብታቸው እንዲነፈግ ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአመልካች እና 19ኛ ተከሳሽ በሆነው ድርጅታቸው ላይ የቀረቡት 37ኛ፤ 38ኛ፤ 40ኛ፤ 41ኛ፤ 42ኛ፤ 43ኛ፤ 44ኛ፤ እና 45ኛ ክሶች የግብር ዓዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 96 እና 97፤ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49፤ 50፤ 102

---

[141] በሰ/መ/ቁ 35611 (ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅጽ 07 ፣ በሰ/መ/ቁ 67874 (ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ በሰ/መ/ቁ 59304 (ህዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ 244554 (ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 262650 (ሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 262313 (ሐምሌ 30 ቀን 2016 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 112725 (ጥቅምት 22 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19 ፣ በሰ/መ/ቁ 182266 (ጥቅምት 19 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24 ፣በሰ/መ/ቁ 119391 (ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 134228 (የካቲት 08 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 132055 (ጥቅምት 08 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 23 ፣ በሰ/መ/ቁ 182050 (ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 271048 (ህዳር 23 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 273594 (ታህሳስ 21 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 131863 (ህዳር 08 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 31734 (ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 218737 (የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 225533 (ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 233903 (ጥቅምት 08 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 218080 (የካቲት 22 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 269430 (ጥቅምት 29 ቀን 2017ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 172185 (ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 198881 (የካቲት 2 ቀን 2013 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 273144 (ታህሳስ 21 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ ሰ/መ/ቁ 253740 (ሕዳር 27 ቀን 2016ዓ.ም)፣ ሰ/መ/ቁ 275196 (የካታት 27-2017 ዓ.ም) ፣ ሰ/መ/ቁ 68407 (ሐምሌ 14 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12

እና 56 መሰረት ያደረጉ እና በእነዚህ 8 (ስምንት) ክሶች በድምሩ ብር 50,374,960.00 የሚጠጋ የመንግስት የገቢ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ እዳ እንዳለባቸው የሚያሳዩ ግብር አሳውቆ ለለመክፈልን እና አሳንሶ ማሳወቅን የሚመለከቱ የወንጀል ክሶች በመሆናቸው፤ በድርጅቱ ላይ የቀረቡትም ክሶች አመልካችን የሚመለከቱ እና በተደራቢነት የሚታዩ በመሆናቸው፤ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በመርህ ደረጃ ዋስትና የሚከለክሉ ባይሆንም ተደራራቢ ቅጣትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች በመሆናቸው አመልካች ሊከተል የሚችለውን ከፍተኛ ቅጣት በመሸሸ በዋስ ቢወጡ ሊቀርቡ ይችላሉ ተብሎ መገመት አለመቻሉን፤ የክሱ የገንዘብ መጠን ከፍተኛ መሆኑና በሃገር ኢኮኖሚ የሚያሳድረው ተፅእኖ ከፍተኛነት ሲታይ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት እና የወንጀሉ ከባድነት ስለሚያስገነዝብ አመልካች በዋስትና ቢወጡ ይቀርባሉ ተብሎ ለመገመት የማያስችል በመሆኑ፤ አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የሚለውን ግምት የሚያስተባብል አሳማኝ ምክንያት ያላቀረቡ በመሆኑ፤ በአጠቃላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች አመልካች የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ የለም ብሎ ፍርድ ቤቱ ስላመነ የዋስትና ጥያቄውን አልተቀበልኩም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ብይን በመቃወም ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ብይኑን ለመለወጥ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት አልተገኘም ተብሎ የይግባኝ ማመልከቻው ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ህዳር 10 ቀን 2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የተከሰሱባቸው የወንጀል ክሶች በመርህ ደረጃ የአመልካችን የዋስትና መብት የሚያስነፍጉ ስላለመሆናቸው የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ነገር ግን ክርክሩ ከተጠናቀቀ በኋላ አመልካች ጥፋተኛ ቢባሉ ሊያስከትልባቸው ከሚችለው ቅጣት አንፃር አመልካች ከሃገር ሊሸሹ ይችላሉ የሚለውን ግምት መነሻ በማድረግ የዋስትና መብት የመከልከሉን አግባብነት፤ እንዲሁም ከሃገር ሊሸሹ ይችሉ ይሆናል የሚል ግምት ቢወሰድም እንኳ ከሀገር ለመሸሸ የማይችሉበትን ሥርዓት ማስፈፀም እየተቻለ መሰረታዊ የሆነውን የዋስትና መብት ለመንፈግ የተሰጠው ምክንያት እንደሀጉ አነጋገር በቂ ምክንያትን የተመረኮዘ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በሰበር መ/ቁ 31734 ከሰጠው ትርጉም አንፃር ማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቀረብ ተብሏል፡፡ በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት መርምረናል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(6) በግልፅ እንደተመለከተው የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት ያላቸው ሲሆን ዋስትና ሊከለከል የሚችለው በህግ በተደነገገ ልዩ ሁኔታዎች ነው፡፡ በህጉ ከተደነገጉት ልዩ ሁኔታዎች መካከል በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ) ሥር የተደነገገው ተጠቃሽ ነው፡፡ በድንጋጌው ሥር እንደተመለከተው ተከሣሹ የዋስትና ግዴታውን ሊፈጽም አይችልም ተብሎ ሲገመት ዋስትና መከልከል ይቻላል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ በዋስ ቢለቀቁ ተመልሰው ሊቀርቡ አይችሉም የሚል ግምት ለመውሰድ እና ዋስትና ለመከልከል የሚያስችል ማስረጃም ሆነ ምክንያት ሳይኖር፤ ይልቁንም ከፍተኛ ባለሃብት በመሆናቸው በቢሊዮን የሚቆጠር ሃብት የሚያንቀሳቅሱ እና አንደኛ ደረጃ ግብር ከፋይ ተብለው መሸለማቸውን፤ እንዲሁም ከፍተኛ የሥራ ዕድል መፍጠራቸውን ሁሉ ለፍርድ ቤቱ ተገልፆ በገሃድ ቀርቦ እያለ ምንም ማፍረሻ ማስረጃ ሳይቀርብ በደፈናው አይቀርቡም የሚለውን ግምት ሊያስተባብሉ አልቻሉም በማለት መደምደሙ፤ እንዲሁም ጉልህ ግምት ቢኖር ያንን እንዳፈርስ ወይም እንዳስረዳ እንኳ እድል ሳይሰጥ የተወሰነ ውሳኔ በመሆኑ በዚህ መልኩ የተሰጠው ብይን ተሽሮ ዋስትና ሊፈቀድ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ነገር ግን ተከሣሹ የዋስትና ግዴታውን ሊፈጽም አይችልም ለማለት የሚያስችል በበቂ ምክንያት የተደገፈ ግምት ካለ ይህ በመኖሩ ብቻ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67/ሀ/ መሠረት ዋስትና መከልከል የሚቻል ሲሆን በተያዘው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት አመልካች የዋስትና መብት የተከለከሉት የዋስትና ግዴታን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ በመቀበሉ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው በአመልካች እና በድርጅታቸው ላይ የቀረቡትን ተደራራቢ ክሶች፤ ክሶቹ የያዙትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን እና ወንጀሉም ግብር አሳውቆ ካለመክፈል እና አሳንሶ ከማሳወቅ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች መሆናቸውን፤ እነዚህ ከፍተኛ ቅጣትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች በመሆናቸው፤ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት እና የወንጀሉ ከባድነት ሁሉ ሲታይ አመልካች በዋስታና ቢወጡ ይቀርባሉ ተብሎ ለመገመት የማያስችል መሆኑን፤ እንዲሁም አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የሚለውን ግምት የሚያስተባብል አሳማኝ ምክንያት ያላቀረቡ መሆኑን በማንሳት ነው፡፡

የወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ) በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካች የሚፈጽሙ የማይመስል እንደሆነ በዋስትና የመለቀቅ ማመልከቻውን መቀበል የማይቻል ስለመሆኑ ቢደነግግም ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከልከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በግልጽ አልተመለከቱም፡፡ በመሆኑም አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወሰደው በቂና ህጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚገባ፤ እንዲሁም ምክንያቶቹ በቂና ህጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59304 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67 መሰረት የዋስትና መብት የሚነፈግባቸው ምክንያቶች ፍርድ ቤቶች ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር እየተመለከቱ ሊመዝኗቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበለው የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታውን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ነው፡፡ ለዚህ በምክንያትነት የተጠቀሰው ከፍ ሲል እንደገለፅነው የቀረቡት ክሶች ተደራራቢነት፤ ክሶቹ የያዙትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን፤ የወንጀሉ አይነት እና የድርጊቱ አፈፃፀም፤ ሊያስከትል የሚችለው ከፍተኛ ቅጣት፤ እንዲሁም አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የማያሰኝ ሁኔታ አለመኖሩን ነው፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ለግምቱ መነሻ እንዳይደረጉ በህጉ ክልከላ ካለመኖሩም በላይ በምክንያትነት ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም የሚባልበት ሁኔታ ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤት በተጠቀሰው ምክንያት እና ግምት ላይ ተመስርቶ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻውን ባለመቀበል በመወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡

በሌላም በኩል ቅሬታው ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በሰበር መ/ቁ 31734 ከሰጠው ትርጉም አንፃር ለማየትም እንዲቻል ተብሎ ቢሆንም በተጠቀሰው መዝገብ ተከሳሹ የብዙ ሃገር ፓስፖርትና ቪዛ በእጁ ስለሚገኝ ብቻ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ለማለት የሚያስችል በቂ መንደርደሪያ ምክንያት ስላለመሆኑ፤ እንዲሁም የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ የሚያደርግ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቻል የተወሰነበት ከመሆኑ ውጭ በሁለቱ መዛግብት የቀረበው ክርክር እና ዋስትና ለመከልከል መንደርደሪያ የተደረጉት ምክንያቶች ተመሳሳይ ናቸው የሚባሉ ሆነው አላገኘናቸውም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት በህጉ ተቀባይነት የላቸውም የማይባሉ ምክንያቶች ላይ በመመስረት አመልካች የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታውን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ የለም በማለት በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67/ሀ/ መሰረት ባለመቀበል በመወሰኑ፤ እንዲሁም

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የይግባኝ ማመልከቻውን ባለመቀበል በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/መ/ቁጥር 141352 ጥቅምት 1 ቀን 2009 ዓ.ም. የተሰጠው ብይን፤ እንዲሁም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 133103 ጥቅምት 15 ቀን 2009 ዓ.ም የተላለፈው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 75/2/ መሠረት በአብላጫ ድምፅ ፀንቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የልዩነት ሃሳብ</u>

እኔ በተራ ቁጥር አንድ ስሜ የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በደረሰበት ድምዳሜና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኑ በሀሳብ ተለይምለሁ፡፡ በሀሳብ የተለየሁባቸውን ምክንያቶች ግልፅ ለማድረግ በመጀመሪያ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን የወንጀል ክሶች ይዘት፣ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን ማስረጃ ከተሰማ በኋላ አመልካች መከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ስላስፈለገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እዲሰናበት የሰጠውን ብይንና ብይኑን በማስተካከል አመልካች በዋስ ልለቀቅ ይገባል በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የስር ፍርድ ቤት የሰጣቸውን ምክንያቶች በአጭሩና በዝርዝር መግለፁ አስፈላጊ ነው ብየ ስለማስብ ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ አስፍሬለሁ፡፡

1. ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 ባቀረበው የወንጀል ክስ
   - አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 33፣ አንቀፅ 32 እና አንቀፅ 411 ንዑስ አንቀፅ 1/ሐ/ እና ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ ከላይ ቁጥሩ በተገለፀው የወንጀል መዝገብ አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሽ ሆነው ከተከሰሱት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣኖች ጋር በመሆን የመንግስት ስራ በማያመች ሁኔታ የመምራት ከባድ የሙስና ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሁለተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ አመልካች በስር ፍርድ ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው ጄ ኤች ሴሚክስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ እንደሆነ ገልፆ፤
   - አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 49 በመተላለፍ ከ1998 ዓ.ም እስከ 2004 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 20,111,328.94 አሳውቆ ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ሰባተኛው ወንጀል ክስ ላይ ገለፀ ሲሆን፣ አመልካች የ19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 56 እና አንቀፅ 49 በመተላለፍ በሰላሳ ሰባተኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ስምንተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
   - አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ አሳውቆ መክፈል ሲገባው 1998 ዓ.ም እስከ 2004 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 20,111,328.94 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ በመደበቅና የተጭበረበረና መረጃ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የመስጠት ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ዘጠንኛው የወንጀል ክስ ላይ ገለፀ ሲሆን፣ አመልካች የ19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 56/1/ እና አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በሰላሳ

ዘጠንኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡

- አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋሽ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 96 የተመለከተውን በመተላለፍ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 29 433 214.24 ያገኘውን ትክክለኛ ገቢ አሳውቆ መክፈል የሚገባውን ገቢ ግብር ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በአርባ አንደኛው ወንጀል ክስ ላይ ገለፀ ሲሆን፣ አመልካች 19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 102/1/ እና አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በአርባ አንደኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባ ሁለተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
- አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ብር 29,433,214.24 ያገኘውን ትክክለኛ ገቢ አሳውቆ መክፈል የሚገባው ገቢ ግብር በመደበቅና ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በአርባ ሶስተኛው ወንጀል ክስ ላይ ገለፀ ሲሆን፣ አመልካች 19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 102/1/ እና አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በአርባ ሶስተኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባ አራተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
- አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 98 የተመለከተውን በመተላለፍ ከቀረጥ ነፃ ያስገባቸውን የቀረጥ መጠናቸው 197556.61 የሆኑ መሳሪያዎች ከተፈቀደለት ተግባር ወጭ ተጠቅሟል በማለት በአርባ አምስተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡

2. አመልካች በሁለተኛው የወንጀል ክስ የተከሰሰበትን ወንጀል ማለትም አመልካች ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 411 ንዑስ አንቀፅ 1/ሐ/ እና ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ ፈፅሞታል የተባለው ከባድ የሙስና ወንጀል ከአስር አመት በላይ የሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል በመሆኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 4/1/ መሰረት አመልካች በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ የሕጉ ድንጋጌ ስለማይፈቀድለት አመልካች በማረሚያ ቤት ሆኖ ሲከራከር ቆይቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በሁለተኛው የወንጀል ክስ የተከሰሰበትን ከባድ የሙስና ወንጀል የፈፀመ ስለመሆኑ ተጠሪ በበቂ ሁኔታ ያላስረዳ በመሆኑ፣ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በመተላለፍ በበኩላቸው የወንጀል ክሶች ከሳሽ /ተጠሪ/ በበቂ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ተከሳሽ /አመልካች/ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የስር ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡

3. የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ከሰማ በኋላ አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ፣ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 4/1/ መሰረት በዋስትና ወረቀት እንዳይለቀቅ ከማያስከለክለው ከባድ ሙስና የወንጀል ክስ ፍርድ ቤቱ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ብይን የተሰጠ መሆኑንና ተከላከል የተባለባቸው ሌሎች ወንጀሎች በዋስትና የመለቀቅ መብትን የሚያስከለክሉ መሆኑን ገልፆ፣ በዋስ የመለቀቅ መብቴ ይከበርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ላቀረበው የዋስና ጥያቄ ተጠሪ ነሐሴ 2 ቀን 2008 ዓ.ም እና መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም መልስ የሰጠ

መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ብይን ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ በዋስትናው ጥያቄ ላይ ያደረጉትን ክርክር ከመረመረ በኋላ፤

- ተከሳሽ በተደራራቢ ወንጀል ማለትም በ37ኛ ፣ 38፣ 40፣ 41፣ 42፣43፣44፣ እና በ45ኛ በድምሩ በስምንት ክሶች ብር 50,374,960 ተጨማሪ እሴት ታክስና ገቢ ግብር አሳውቆ ያለመክፈል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰና ክሶቹ ተደደራቢ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ በመሆናቸው፣
- ተከሳሽ የተከሰሰባቸው ተጨማሪ እሴት ታክስና የገቢ አሳውቆ ያለመክፈል ተደራራቢ ወንጀሎች ሳይከፍል ቀርቷል የተባለው ታክስና ግብር ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያለው (ብር 50,374,960) በመሆኑና ወንጀሉ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛነት ሲታይ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኝነትና የወንጀሉ ከባድነት ተከሳሹ በዋስትና ቢወጣ ይቀርባል ብሎ ከመገመት የማያስችል ምክንያት በመሆኑና፣
- ተከሳሹ ያለውን ኢኮኖሚ አቅም ተጠቅሞ ከአገር አይወጣም የሚለውን ግምት ሊያስተባብል የሚችል አሳማኝ ምክንያት በከሳሽ በኩል ስላልቀረበ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 (ሀ) እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሠረት ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚል እምነት ያለን በመሆኑ ተከሳሹ በማረሚያ ቤት ሆኖ ይከራከር በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ቀርበው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችን ዋስትና መብት ለመገደብ የሰጡት ምክንያት የህገ መንግስቱንና የሌሎች ህግ ድንጋጌዎችን የተከተለ አይደለም በማለት ሲሆን ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

4. በእኔ በኩል የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ በብይኑ ላይ ያስፈራቸው ምክንያቶች ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸው ስለመሆናቸው የስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ያለውን ከፍተኛ የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅም ከአገር የማይወጣ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም በማለት የሰጠው ትርጉምና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዋቢነት የጠቀሰበት ሁኔታ በሰበር ሊታረም የሚገባው መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ በመርህ ደረጃ የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀፅ 6 የመጀመሪያው ሐረግ “የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው” በማለት ቃል በቃል የተደነገገ ሲሆን በህግ በተደነገጉ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የተከሳሹን በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተከሳሹ በዋስትና የመለቀቅ መብት ተገድቦ ሊቆይ እንደሚችል በህግ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 ተከታዩ ሐረግ ይደነግጋል፡፡ በአገራችን የተከሰሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት ሕግ አውጭው በሕግ የገደበባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ሕግ አውጭው የዋስና መብትን አስገዳጅ በሆኑ የህግ ድንጋጌዎ በከለከለባቸው ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን ዳኞች በዋስ የመፍታት ፈቃደ ስልጣን የላቸውም፡፡ ሕግ አውጭው የተከሳሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ የገደበው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 63 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በተሸሻለው ልዩ የሙስና የስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ1 በተመለከቱ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡
5. ሕግ አውጭው የተከሳሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት በህግ ከገደበባቸው ከላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ በሆኑ ሌሎች ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች በመርህ ደረጃ የቀረበባቸው የወንጀል ክስ ሊያስከትል የሚችለው ከፍተኛ የወንጀል ቅጣትና በተከሳሹ ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ ብዛት ግምት ውስጥ ሳይገባ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት በዋስ የመለቀቅ

መብት አላቸው፡፡ በህግ በዋስትና የመለቀቅ መብታቸውን በማያስገድቡ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገደበው መንግስትና ሕዝብን ወክሎ የሚከራከረው ዐቃቤ ህግ ተከሳሹን በዋስ መለቀቅ በመቃወም ክርክር ሲያነሳና ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ በዋስትናው ላይ ያቀረቡትን ክርክር ማስረጃ መርምሮ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት የሚገድብ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ዳኞች በህግ የተሰጣቸውን ፈቃደ ስልጣን በመጠቀም ተከሳሹ በዋስ እንዲለቀቅ ወይም የተከሳሽ በዋስ የመለቀቅ መብት ተገድቦ እዲቆይ ትዕዛዝ የሚሰጡት ምን ምን ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ነው? የሚለው ነጥብ ሲሆን ይህም በዝርዝር ሲታይ፡-

- ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠው በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገድብ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡት ምን አይነት ልዩ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ነው?
- ተከሳሹ በዋስ ለመልቀቅ የማያስችሉና የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በልዩ ሁኔታ ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ማን ነው?
- ተከሳሹን በዋስ ለመልቀቅ የማያስችሉና የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ውሳኔ (ትዕዛዝ በልዩ ሁኔታ ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ወገን፣ የማስረዳት ግዴታውን የሚወጣው በምን ደረጃ (standard of proof) እስከምን ድረስ ነው? የሚሉትን ነጥቦች በዝርዝር ማየት የሚጠይቅ ነው፡፡

6. ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠውን በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገድብ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡባቸውን ጥቅል ሁኔታዎች ህግ አውጭው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 ለማመለከትና ለመደንገግ ሞክሯል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 መሠረት አንድ ተከሳሽ በዋስትና የመለቀቅ መብቱን በፍርድ ቤት በትዕዛዝ ወይም በውሳኔ የሚገደበው፡-

ሀ/ ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም የሚመስል የሆነ እንደሆነ

ለ/ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ተብሎ ሲገመት ወይም

ሐ/ ምስክሮችን በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጅ የሚሆኑበትን ያጠፋል ተብሎ የሚገመት ሲሆን እንደሆነ ቃል በቃል ተደንግጓል፡፡

ከላይ ዝርዝር ይዘታቸው የተገለጸው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በተጀመረው የወንጀል ምርመራ ወይም በፍርድ ቤት በተጀመረው የወንጀል ፍርድ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊሳድሩ የሚችሉ ተግባሮችን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ፍርድ ቤቱ የሚገምተውን ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በማረሚያ ቤት ሆኖ ክርክሩ እንዲከታተል በማዘዝ፣ ወንጀል ምርመራው ወይም የፍርድ ሂደቱ ተከሳሹ በዋስ ተለቅቆ ሊፈጽማቸው ይችላል ተብለው ከሚገመቱ አሉታዊ ተግባራት ነፃ በሆነ ሁኔታ እዲጠናቀቅ ለማስቻል መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች ባህሪ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. ከላይ የተገለጸውን መሠረታዊ ዓላማ ለማሳካት የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት እንዲገድብ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ በህገ መንግስት አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 ዕውቅናና ጥበቃ የተሰጠውን መብት የመገደብ ውጤት ያለው በመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት የገደበው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ክርክር የሚያስነሳ ነው፡፤ ከሁሉም በላይ ፍርድ ቤቱ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ

የጠቀሳቸው ምክንያቶችና ያስቀመጣቸው ሁኔታዎች ህገ መንግስታዊና ህጋዊ መሰረት ያላቸው ናቸው ወይስ አይደለም? የሚለውን ክርክር የሚያስነሱ ናቸው።

8. ለዚህም መሠረት የሚሆነው የህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘትና ትርጓሜ፣ ድንጋጌው በመንግስት ላይ የሚጥለው ግዴታና ኃላፊነትና በወንጀል ፍርድ ሂደት ላይ የሚኖረው ተግባራዊ ተፈፃሚነትና የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ነው። በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 "የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት የሚደነግግ ሲሆን፣ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛ ቅጅ "During proceedings accused persons have the right to be presumed innocent until proved guilty according to the law and not to be compelled to testify against themselves" ተብሎ ተደንግጓል።

9. ተከሳሹ ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስት መብት ያለው በመሆኑ፣ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ ለወደፊት ይዘታቸው ከላይ የተገለጹት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 የተደነገጉ አሉታዊ ውጤት ከሚያስከትሉ ተግባራት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ይፈጽማል ብሎ ፍርድ ቤቱ ከጅምሩ ግምት እዳይዝበት ዋስትናና ጥበቃ ይሰጠዋል። ይህም ማለት ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ከቀረበበት የወንጀል ክስ ውጭ የሆኑ በቂ ምክንያትና ማስረጃ ሳይቀርብበት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከሚችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ ባላይ የሆኑትን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ግምት ለመያዝና የተከሳሽን ዋስትና ጥያቄ እንዲሰርዝ ከላይ ይዘቱን የገለጽነው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የሚፈቅድ አይደለም በዚህ ምክንያት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከምችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ ግምትና መደሚደሚያ ላይ ሊደርስ የሚችልባቸውን ፍሬ ነገሮች የማቅረብና የመስረዳት ግዴታ (burdon of proof) ያለበት ዐቃቤ ህግ ነው።

10. በእርግጥ የዐቃቤ ህግ የማስረዳት ሸክም ደረጃና መጠን (standard of proof) ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከሚችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን በእርግጠኝነት የሚፈፅም መሆኑን በበቂ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ መሆን አይጠበቅበትም። የዐቃቤ ህግ የማስረዳት ሸክም ደረጃና መጠን (stanedard of proof) ተከሻሱ በዋስ ቢለቀቅ፣ የዋስትና ግዴታውን ላይፈጽምና ቀጠሮውን አክብሮ ላይመጣ ይችላል፣ ወይም ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ወይም ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ ምስክሮችን በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጅ የሚሆኑበትን ያጠፉል ብለው ዳኞች የህሊና ግምት ለመውሰድ የሚያስችሉ ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸውና ታዓማኒነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች ከማቅረብ ያለፈ አይደለም። ይህም ዳኞች የተከሳሹን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የሚያደርግ ትዕዛዝ የሚሰጡት በመጀመሪያ ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ወደ ፊት የሚኖረው ባህሪ ለሚፈጽም የሚችላቸው ተግባራትና ስነ ምግባሩ ጥሩ አይሆንም ከሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬና ግምት ላይ እዲደርሱ የሚያስችል ማስረጃ ወይም ፍሬ ነገር ሲያቀርብና ሲያስረዳ መሆኑን ያሳያል።

11. ከላይ የተገለጸውን መሠረታዊ ሀሳብ ይዤ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሰጣቸውን ምክንያቶች አንድ በአንድ ተመልክቻለሁ። የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሰጠው የመጀመሪያው ምክንያት ተከሳሽ የተጨማሪ እሴት ታክስና የገቢ ግብር አሳውቆ ባለመክፈሉ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ቀርበውበታል። አመልካች በስምንት የወንጀል ክሶች መጠኑ ብር 50,374-960 ግብርና ታክስ ያለመክፈል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በተደራራቢ

ወንጀሎች ተከሷል፡፡ ተከሳሽ የተከሰሰባቸው ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ተደደራቢና ከባድ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ በመሆናቸው በወንጀሉ ያልተከፈለው የግብር የገንዘቡ መጠን ከፍተኛኛ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው አስተዋጽኦና የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት ያለው በመሆኑ አመልካች በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ አይቀርብም የሚል ነው፡፡

12. ከላይ እንደተገለጸው" የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት የህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 መደንገጉ፣ የአመልካችን በዋስትና የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለማስገደብ ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ይዘት፣ ብዛትና ወንጀሉ ሊያስቀጣ የሚችለው ቅጣት ክብደት መከራከሪያ አድርጎ ሊያቀርብ እንደማይችል እና ዐቃቤ ህግ መከራከሪያ አድርጎ ቢያቀርብ እንደማችል እና ዐቃቤ ህግ መከራከሪያ አድርጎ ቢያቀርበው እንኳ እንኳ ይህ ምክንያት የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሚያስችል ህጋዊ መሠረትና ተቀባይነት ያለው ምክንያት ተደርጎ በፍርድ ቤት መወሰድ ያሌለበት መሆኑን ነው፡፡ በአንድ ሰው ላይ ዐቃቤ ብዙ የወንጀል ክሶች ማቅረቡ ብቻውን ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ከሚለው ምክንያታዊ ጥርጣሬና ግምት ለማድረስ የሚያስችል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ፍሬ ነገር (ማስረጃ) ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም አንድ ተከሳሽ የተከሰሰው በአንድ የወንጀል ክስ ወይም በብዙ የወንጀል ክሶች መሆኑ፣ ተከሳሹ በተከሰሰባቸው ሁሉም የወንጀል ክስ ወይም በብዙ የወንጀል ክሶች መሆኑ ተከሳሹ በተከሰሰባቸው ሁሉም የወንጀል ክሶች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብቱን የሚያሳጣው አይደለም፡፡ የተከሳሽ ከፍርድ በፊት ንፁህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት በአንፃራዊነት መብቱን የማክበርና ማስከበር ግዴታ ባለበት መንግስት ላይ በጠቅላላውና አግባብነት ባላቸው የመንግስት አካላት ላይ በልዩ ሁኔታ የሚስከትለው ኃላፊነት አለ፡፡

13. የተከሳሽ በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት በተከሳሹ ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ በሚያየው የዳኝነት አካል( ፍርድ ቤት) እንደ አንድ የመንግስት አካልና ጉዳዩን በሚያዩ በዳኞች ላይ የሚጥለው ግዴታና ኃላፊነት አለ፡፡ ይኸውም ህግ መንግስታዊ ኃላፊነትና ግዴታ ተከሳሽ በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት መብት የማክርና የማስከበር ግዴታ እንደሆነ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 3 እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ተግባራዊ ተፈፃሚነትና ህጋዊ ውጤት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የዳኝነት አካሉ እንደተቋምና የወንጀል ጉዳዩን የሚያዩት ዳኞች የተከሳሽን በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንፁ ነው ተብሎ የመገመት መብት የመክበር ኃላፊነታቸውን የሚወጡት የተከሳሹ ጉዳይ መታየት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ከህግ አግባብ ውጭ ሳይሸራረፉ ለተከሳሹ መብት ዕውቅናና ከበሬታ መስጠታቸውን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ጉዳዩን አይተው እልባት ሲሰጡ መሆኑን የህግ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የህግ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

14. ይህም ዐቃቤ ህግ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለማስገደብ የሚያቀርበው ምክንያት ፍሬ ጉዳይና ማስረጃ ተከሳሹ ከተከሰሰበት (ከተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ይዘት ብዛትና ክብደት ውጭ የሆኑ ሌሎች ምክንያቶች መሆን ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ የወንጀል ጉዳዩን የሚያዩት ዳኞች የተከሳሽን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡት በተከሳሽ ላይ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ወይም ክሶች ይዘት ብዛትና ክብደት ተከሳሽ በዋስትና ወረቀት እንዳይለቀቅ ለመወሰን የሚስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት አድርገው በመቀበል መሆን አይገባም፡፡

ምክንያቱም የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት በህግ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ድንጋጌ ዳኞች የፍርድ ሂደቱ ሳይጠናቀቅና በተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ብዙ የወንጀል ክስ ስለቀረበበትና ተከሳሹ በቀረቡበት የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችል ተከሳሹ ወደ ፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ የሚጣልበትን ተደራራቢ ቅጣት በመፍራት የዋስትና ግዴታውን አክብሮ በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ እዲይዙ የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ዐቃቤ ህግ በተከሳሹ ላይ ያቀረባቸውን ወንጀል ክሶች ብዛትና ክብደት መነሻ በማድረግ የተከሳሽን ዋስትና መብት ለመገደብ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ከጅምሩ የተከሳሽን ከፍርድ በፊጽ ንፁህ ነው ተብሎ የመገመት የሚጥስ ነው፡፡

15.በአንጻሩ ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ብዙ የወንጀል ክስ ስለቀረበበትና ተከሳሹ በቀረቡበት ወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችል ተከሳሹ ወደፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ የሚጣልበትን ተደራራቢ ቅጣት በመፍራት የዋስትና ግዴታውን አክብሮ በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ በመያዝ ዳኞች ተከሳሽ በእስር እንዲቆይ የሚሰጡት ትዕዛዝ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ የተከሳሹን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት መብት ከህግ አግባብ ውጭ የተሸራረፈና ያልተከበረ መሆኑን የሚየሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በይዘቱም ሆነ በውጤቱ፣ ተከሳሽ በዐቃቤ ህግ ከቀረቡበት የወንጀል ክሶች በተወሰኑት የወንጀል ክሶች ወይም በሁሉም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ስለሚችል፣ ተከሳሽ ወደ ፊት ጥፋተኛ ቢባል በፍርድ የሚወሰንበትን የወንጀል ቅጣት ለማምለጥ በዋስ ቢለቀቅ ከአገር ሊጠፋ ይችላል የሚል ዕምነትና ግምት ላይ ዳኞች ያላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት ዳኞች የተከሳሽን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት የመብት ባከበረና በሚያስከብር ሁኔታ ጉዳዩን አይተው እልባት የመስጠት ግዴታና ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተከሳሽን ዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የተጠቀመበት ከላይ የተገለፀው ምክንያት ዳኞች አስቀድመው ተከሻሱ የተከሰሰባቸውን ወንጀሎች ፈጽሟቸዋል የሚል ግምትና አቋም ሳይዙ ገለልተኛ ሆነው ጉዳዩን አይተዋል ወይም አላዩም የሚል ክርክር የሚስነሳ የህግ አተረጓጎም ነው፡፡

16. በእኔ እምነት ዐቃቤ ህግ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ በመቃወም ካቀረበው ክርክር አንፃር፣ ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 76 (ሀ) በተደነገገው መሠረት ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም ይመስላል ወይም አይመስልም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን ፍርድ ቤቱ መመልከትና መመዘን ያለበት በተከሳሹ ላይ ዓቃቤ ህግ ያቀረበው ወንጀል ክስ ብዛትና ክብደት ሳይሆን የተከሳሽ ግላዊ ሁኔታ ባህሪውን፣ ስብዕናውን እና ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን በማክበር የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተል ሊያደርጉት የሚያስችሉ ግላዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችና ሌሎች ተጨባጭ ኩነቶች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን በመመዘን መሆን እንዳለበት የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67/ሀ/ ድንጋጌዎች ይዘት የጣምራ ንባብ ይዘት፣ ዓላማና ተግባራዊ ተፈጻሚነት ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍ/ቤቱ ጭብጡን መወሰን ያለበት ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ፣ ተካሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚያስችሉና ተከሳሹን በእስር ከማቆየት የተሻሉ ሌሎች አማራጮች፣ ለምሳሌ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ ከአገር እንዳይወጣ

ወይም ከሚኖርበት ከተማ ውጭ እንዳይንቀሳቀስ በመገደብና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ትእዛዞች በመስጠት ተከሳሽ የዋስትና ግዴውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚቻል መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማገናዘብና በማጣራት መሆን ይገባዋል፡፡ በማጣራቱ ሂደት ፍ/ቤቱ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚያስችሉና ተከሳሹን በእስር ከማቆየት የተሻሉ ሌሎች አማራጮች መኖራቸውን ከተረዳ ተከሳሽ በዋስ እንዲለቀቅ የሚሰጠውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች /የመብት ማዕቀቦች/ ጋር ተጣምረው እንዲፈጸሙ ትእዛዝ በመስጠት ፣ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3፣ እና አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1፣ እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 /ሀ/ ድንጋጌዎች ይዘት የጣምራ ንባብ ይዘትና ዓላማ ማሳካት ይገባዋል ብዬ አስባለሁ፡፡

17. በእኔ እምነት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67/ሀ/ በተደነገገው መሰረት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም ይመስላል ወይም አይመስልም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በተከሳሹ ላይ ዓቃቤ ሕግ ካቀረበው የወንጀል ክስ ክብደትና ብዛት በበለጠ፣

- ተከሳሽ በአገር ውስጥ ተለይቶ የሚታወቅ ቋሚ አድራሻ ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ ፣
- ተከሳሹ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ወይም አለመሆኑና ተከሳሽ ከቤተሰቦቹ ጋር በአገር ውስጥ የሚኖር መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣
- ተከሳሹ በአገር ውስጥ የሚተዳደርበት ቋሚ ስራ፣ የገቢ ምንጭ ወይም ንግድ ወይም ኢንቨስትመንት ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣
- ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ባይቀርብ ፍ/ቤቱ በሕግ አግባብ በቀጣይ በሚሰጠው ትእዛዝ ሊያጣው የሚችለው መብትና ጥቅም ያለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣
- ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ በነጻነቱ ላይ ሌሎች ገደቦችን በመጣል ለምሳሌ ከአገር እንዳይወጣ በመገደብ፣ እንደግለሰቡ ሁኔታ ተከሳሽ በሚኖርበት ከተማ ወይም ቀበሌ በየቀኑ ወይም በየሳምንቱ ለክፍሉ ፖሊስ በአካል እየሄደ ሪፖርት የሚያደርግበትንና ፖሊስም ተከሳሹ በፍርድ ቤት የታዘዘው ገደብና ሁኔታ እያከበረ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግና ፍ/ቤቱ ያስቀመጣቸውን ገደቦችና ሁኔታዎች ተከሳሹ ጥሶ ባገኘው ጊዜ፣ ተከሳሹን በቁጥጥር ስር አውሎ በዋስ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ለሰጠው ፍ/ቤት የሚያቀርብበትን አሰራር በመከተል ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣
- በተከሳሹ ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ ሊወሰን የሚችል መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣
- ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን ባለማክበሩ ጉዳዩ በሌለበት ቢታይና ተከሳሽ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ፣ ፍ/ቤቱ ሊወስን የሚችለውን የወንጀል ፍርድና ቅጣት፣ መንግስት ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን የወንጀል ፍርድና ቅጣት ተከትሎ በሕግ መሰረት በተከሳሽ የንብረት ላይ የሚሰጠው የመወረስ ውሳኔ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው ገንዘብና ሃብት፣ ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ የፍርድ ሂደቱን ጥሎ እንዲፈረጥጥ የሚገፋፉ ናቸው ወይስ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ የቀጠሮውን ቀን አክብሮ የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተል የሚያስገድዱ ተጨባጭ ምክንያቶች የሚለውን በማነጻጸር፣ ከእያንዳንዱ ተከሳሽ ሁኔታ ጋር በማየትና በመመዘን ፍ/ቤቱ ምክንያታዊ ግምትና ሎጅካል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ይገባዋል የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

18. ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ተደራራቢ የወንጀል ክስ ማቅረቡንና ተከሳሽ ሊጣልበት የሚችለውን ተደራራቢ ቅጣት ለመሸሽ በዋስ ቢለቀቅ ቀነ -ቀጠሮውን አክብሮ ፍ/ቤት ሊቀርብ አይችልም በማለት የሰጠው ምክንያት ከላይ በተራ ቁጥር 15 እና 16 የገለጽኳቸውን መሰረታዊ ሁኔታዎች ያላገናዘበና ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ ያላገኘሁት በመሆኑ አመልካች በዋስ ሊለቀቅ ይገባል በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

19. ከላይ በዝርዝር የገለጽኩት እንዳለ ሆኖ፣ የስር ፍ/ቤት አመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ አመልካች በስምንት ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ማለትም ተጠሪ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 ባቀረባቸው በ 37ኛ ፣ 38ኛ፣ 40ኛ፣ 41ኛ፣ 42ኛ፣ 43ኛ፣ 44ኛ እና በ 45ኛ በድምሩ በስምንት ክሶች ብር 50,374,960 ግብርና ታክስ እንዳይከፈል በማድረግ ወንጀል እንደተከሰሰና መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን እንደተሰጠበት አድርጎ በብይኑ ውስጥ ያሰፈረው ፍሬ ሃሳብ ሊታረምና ተገቢ የሕግ ትርጉም ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝቸዋሁ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት ለመገደብ ተደራራቢ ናቸው ብሎ የጠቀሳቸው ስምንት ክሶች፣ አመልካች ላይ የቀረቡትን የወንጀል ክሶች ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆኑ አመልካቹ በስራ አስኪያጅነት ሲያስተዳድረው የነበረውና በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው ጄ ኤች ሴሚክስ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ጨምሮ በመቁጠር የአመልካችን ዋስትና መብት መገደቢያ ምክንያት አድርጎ የስር ፍ/ቤት ብይን የሰጠ በመሆኑ ነው፡፡

20. ከላይ ይዘታቸውን በተራ ቁጥር 1 የገለጽኳቸውና ተጠሪ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 በ 37ኛ፣ 41ኛ እና በ 43ኛ ያቀረባቸው ወንጀል ክሶች አመልካች በስራ አስኪያጅነት ሲያስተዳድረው የነበረው በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ ሆነው ጄ ኤች ሴሚክስ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የከሰሰባቸው የወንጀል ክሶች ናቸው፡፡ የንግድ ድርጅቱ የተከሰሰባቸው የወንጀል ክሶች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34ና በአዋጅ ቁጥር 285/94 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 ልዩ ድንጋጌዎች መሰረት የንግድ ድርጅቱ ለተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ፣ አመልካች ሳይሆን ራሱ የንግድ ድርጅቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚወሰንበት የእስራትና የጽኑ እስራት ቅጣት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የሚቀጣባቸውና ቅጣቱን እንዲፈጽም የሚደረግባቸው የወንጀል ክሶች ናቸው፡፡ አስራ ዘጠነኛው ተከሳሽ ሕግ ወለድ ሰው በመሆኑ በፍርድ ሂደቱ በእስር ላይ አይገኝም፡፡ በዚህ ምክንያት አስራ ዘጠነኛው ተከሳሽ ያቀረበውና ሊያቀርበው የሚችለው የዋስትና መብት ጥያቄ የለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ፣ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን የወንጀል ክሶች ብቻ ሳይሆን፣ በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው የንግድ ኩባንያ የከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ጨምሮ በመቁጠር አመልካች ስምንት ተደራራቢ ወንጀል ክሶች እንደቀረቡበት አድርጎ ብይን መስጠቱ በሰበር ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

21. የስር ፍ/ቤት የተከሳሹ የዋስትና መብት ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት ሌላው ምክንያት ተከሳሹ ያለውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅሞ ከአገር ሊወጣ ይችላል የሚለውን ግምት ሊያስተባብል የሚችል አሳማኝ ምክንያት በተከሳሽ በኩል አልቀረበም በማለት ነው፡፡ ሲጀመር ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያለው በወንጀል የተከሰሰ ባለሃብት ያለውን የገንዘብ አቅም ከቀረበበት የወንጀል ክስ ለማምለጥ ሊጠቀምበት ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ ዳኞች ከፍርድ በፊት እንዲይዙ፣ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የተከሳሽ ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት መብት የሚፈቅድ አይደለም፡፡

22. በሁለተኛ ደረጃ ተከሳሽ በዋስ ቢፈታ ያለውን የገንዘብ አቅም ከቀረበበት የወንጀል ክስ ለማምለጥ ሊጠቀምበት ይችላል የሚለውን ፍሬ ጉዳይ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ዓቃቤ ሕግ እንጅ ተከሳሹ አይደለም፡፡ ዓቃቤ ሕግ በህግ የተጣለበትን ማስረዳት ግዴታ የሚወጣው ተከሳሹ ከፍተኛ የገንዘብ

አቅም ያለው መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማሳየት ብቻ አይደለም። በአንጻሩ ተከሳሹ በአገሪቱ ውስጥ ያጠራቀመው ሃብት ወይም ተከሳሹ ኢንቨስት ያደረገበት የንግድ ዘርፍ በባህሪው፣ ተከሳሽ በዚህ አገር ያለውን እሴትና ገንዘብ በቀላል ሰብስቦ ወደ ሌላ አገር ለማሻገር ውጣ ውረድን የማያስከትል መሆኑን፣ ተከሳሹ በዚህ አገር የሚሳሳለትና ወደ ኋላ የሚቀር በቀላሉ ሊያንቀሳቅሰው የማይችል ቋሚ ሃብት የሌለው መሆኑን ተከሳሹ ከአገር ሊጠፋ ይችላል የሚልባቸውን፣ ሌሎች ተጨባጭ ምክንያቶች በማቅረብ መሆን አለበት።

23. በያዝነው ጉዳይ ተከሳሽ በተከሰሰበት ወንጀል ሳይከፍለው የቀረ ነው ተብሎ በወንጀል ክሱ ከተጠቀሰው የግብርና ታክስ ገንዘብ ብር 50,374,960 በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ካፒታል አውጥቶ በረዥም ጊዜ ኢንቨስትመንት ካፒታሉን በሚመልስ ሆቴል ግንባታ ስራ ያዋለ መሆኑን ተጠሪ አይክድም። ይህም ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በዚህ አገር ኢንቨስት ያደረገውን ሃብትና ገንዘብ በቀላሉ ሊያንቀሳቅሰው በማይችለው የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ ያፈሰሰው መሆኑን የሚያሳይ ነው። ተከሳሹ በዚህ አገር የሚሳሳለትና ወደ ኋላ የሚቀር በቀላሉ ሊያንቀሳቅሰው የማይችል ቋሚ ያለው መሆኑና ተከሳሹ ያለው ቋሚ ሃብት በወንጀል ስራው አግኝቶታል ከሚባለው የግብር ገንዘብ በብዙ እጥፍ የሚበልጥ መሆኑ ካላከራከረ፣ ይኸ ምክንያት ተከሳሹ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ የፍርድ ሂደቱን እስከመጨረሻው እንዲከታተል የሚያደርገው የንብረት መብትና ጥቅም ያለው መሆኑን ለመደምደምና ተከሳሽን በዋስ ለመልቀቅ የሚያስችል ምክንያት ከሚሆን በስተቀር ተከሳሽን የዋስትና መብት ለመንፈግ የሚያስችል አይሆንም።

24. ተከሳሽ ከፍተኛ ኢኮኖሚ አቅም ያለው መሆኑን ፍ/ቤቶች የተከሳሽን የዋስትና መብት ለመገደብ በቂ ምክንያት አድርገው መቀበላቸው፣ ኢንቨስተሮችን ወደ አገራችን ለመሳብ በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል የዋስትና ሕግ ድንጋጌ አተረጓጎም ነው። መንግስት የተጀመረውን ፈጣን ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠንና ለማስቀጠል ኢንቨስትመንት ይፈልጋል። መንግስት የአገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮች መዋዕለ ነዋይ፣ ገንዘብና ካፒታል ፍሰት ለማሳደግና ለመሳብ ከሌሎች ኢንቨስትመንት ከሚቀበሉ አገሮች ጋር በሕግ ፣ በአስተዳደርና በፍትህ ዘርፍ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል። መንግስት ኢንቨስተሮችን ለመሳብ የኢንዱስትሪ ፓርክ በመገንባት፣ ከሊዝ ነጻ መሬት በመስጠት፣ የታክስ፣ የግብርና ሌሎች ማበረታቻዎችን በሕግ ከመደንገግና ተፈጻሚ ከማድረግ አልፎ፣ ለውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስተሮች ዓለማቀፍ የመድንና ዋስትና እየሰጠ መሆኑን በዚህ ዙሪያ የወጡ የሕግ ማእቀፎችን፣ የተደረጉ ዓለማቀፍ ስምምነቶችን ይዘትና ተግባራዊ አፈጻጸም በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል።

25. በአገር ደረጃ የተለያየ ማበረታቻ ተሰጥቷቸው፣ መዋዕለ ነዋያችን በዚህ አገር ኢንቨስት ማድረግ ይሻለናል ብለው አገራችን መርጠው የመጡ ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያላቸው ባለሃብቶች በወንጀል ተጠርጥረው ወይም ተከስሰው በቁጥጥር ስር የሚውሉበት አጋጣሚ ይኖራል። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት በግልጽ በብይኑ ባሰፈረው መንገድ፣ ተጠርጣሪዎቹ ወይም ተከሳሾቹ ባለሃብቶችና ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ስላላቸው ከአገር ሊጠፉ ይችላሉ የሚል ግምትና መደምደሚያ ፍ/ቤቶች እየያዙ የዋስ መብታቸውን የማያከብሩላቸው መሆኑን ያመላክታል። ይህንን ግምትና የዋስትና ሕግ ድንጋጌ አተረጓጎም ይህ ሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ ፣ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን ሳያርመው ማለፉ ተገቢ አይደለም ብዬ አስባለው። ይህ የሕግ አተረጓጎምና አገሪቱን መርጠው ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሃብቶች በወንጀል በተጠረጠሩ ወይም በተከሰሱ ጊዜ ይዘውት የመጡት ሃብት ከፍርድ በፊት እነርሱን አስሮ ለማቆየትና የዋስትና መብት ለመንፈግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚያረጋግጥ፣ ለባለሃብቶቹ

ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመትና የነጻነት መብት ዋስትናና ጥበቃ የማይሰጥና አስፈሪና ባለሃብቶቹን በሩቁ እንዲሸሹ የሚያደርግ የሕግ አተረጓጎም ይሆናል፡፡

26. የሕግ አተረጓጎማችን የኢንቨስተሮች /ባለሃብቶች/ በወንጀል ተጠርጥረው በተያዙ ጊዜ ወይም በወንጀል በተከሰሱ ጊዜ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 የተረጋገጠውን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት መብት፣ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠላቸውን በዋስ የመለቀቅ መብትና በአንቀጽ 25 የተረጋገጠውን እኩል የሕግ ጥበቃና የዋስትና ማግኘት መብት የሚጥስና በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ፣ ፈርጀ ብዙ የሆኑ ችግሮችን የሚያስከትል የሕግ አተረጓጎምና ውሳኔ ነው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት አመልካች በዋስ ቢለቀቅ ያለውን ኢኮኖሚ አቅሙን ተጠቅሞ ከአገር የማይወጣ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱን የሚያሳምን ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ የዋስትና ጥያቄውን አልተቀበልነውም በሚል መንገድ የተሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል እምነት ስላለኝ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

27. የስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ከዚህ በፊት፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም የአመልካችን ዋስትና መብት ለመንፈግ በዋቢነት ሲጠቅስ በዚህ መዝገብ የተከሳሽ የዋስትና ጥያቄ ሲታይ የነበሩ ፍሬ ጉዳዮች፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ከተሰጠባቸው ፍሬ ጉዳዮች የሚለያዩበትና የተለየ የሕግ ትርጉም ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን በአግባቡ አላገናዘበም፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 የዋስትና ክርክሩ የተነሳው ተከሳሾች የወንጀል ክስ እንደቀረበባቸው ወዲያውኑ ክሱ በቀረበባቸው በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ነው፤ በዚህ መዝገብ የአመልካች የዋስትና ጥያቄ አከራካሪ የሆነው አመልካች በቀረበበት የወንጀል ክስ ምክንያት ሶስት አመት ከስድስት ወር በላይ በእስር ከቆየ በኃላ ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ ከፍርድ በፊት ታስሮ የቆየበት ጊዜ ተከሳሹ በዋስ እንዲለቀቅ ወይም በእስር እንዲቆይ በመወሰን ሂደት የራሱ የሆነ ትርጉምና ፋይዳ እንደዚሁም ህጋዊ ውጤት አለው፡፡ ረዥም ጊዜ በወሰደ የፍርድ ሂደት ምክንያት፣ አመልካች ከፍርድ በፊት ረዥም ጊዜ በእስር የቆየ መሆኑ በራሱ፣ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ከሚለው ሎጅካል መደምደሚያና ግምት ላይ ለመድረስ የማያስችልና አመልካቹን የዋስትና ጥያቄ ለመቀበልና በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመውጣት የአመልካች የዋስትና ጥያቄ በልዩ ሁኔታ አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ምክንያት ነው፡፡

28. ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠው አመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 የወንጀል ድንጋጌዎች ይዘትና ቅጣት ላይ መሰረታዊ የሕግ ማሻሻያና ለውጥ በሕግ አውጭው ከመደረጉ በፊት ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ ተከሶበት የነበረው የወንጀል ድንጋጌ፣ የተከሳሹ ጉዳይ በመታየት ላይ እያለ፣ ተከሳሽ የተከሰሰበትን የሕግ ማዕቀፍ በሂደት በህግ አውጭው ተከሳሹን የሚጠቅም ይዘት ባለውና ቀላል ቅጣት በሚደነግግ ሌላ ሕግ የተሻሻለና የተለወጠ መሆኑ የተከሳሹን የዋስትና ጥያቄና ከተሻሻለው ህግ አንጻር አይቶ ለመወሰን የሚጠቅም መሆኑ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች ፣ ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 ፣የወንጀል አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 አስገዳጅ ድንጋጌ ጋር በማጣመር ለመተርጎምና ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካችን በተደራራቢ የወንጀል ክስ የተከሰሰባቸው የአዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 ወንጀል ድንጋጌዎች፣ ሕግ አውጭው ባወጣው የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ተሻሽሏል፡፡ የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ድንጋጌዎች አመልካችን የሚጠቅም ይዘትና ቅጣት መጠን ያላቸው መሆኑን ድንጋጌዎቹን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሲሰጥ በወቅቱ ባመለከቱት ተከሳሾች ላይ ተፈጻሚነት ነበራቸው የአዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 ወንጀል ድንጋጌዎች፣ አመልካችን የሚጠቅም ይዘት ባለው አዋጅ ቁጥር 983/2008 ድንጋጌዎች የተለወጡና የተሻሻሉ መሆኑን ሳያገናዝብ የስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአሁኑ ወቅት የተሻረ የሕግ ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አላግባብ በዋቢነት በመጥቀስ አመልካችን ዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው።

29. ከላይ በዝርዝር በገለጽኳቸው የሕግ አተረጓጎም ልዩነቶችና ዝርዝር ምክንያቶች የስር ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በዋስ ቢለቀቅ ይገባል የሚል አቋም ስላለኝ በሃሳብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

## 2.3 የሙስና ወንጀል የዋስትና ሁኔታ[142] ፣ ንብረት እግድ[143] እና ቅድመ ክስ[144]

- በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት በተመሰረተ ክስ ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ይህ ብይን የተሰጠበት ድንጋጌ አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ ሆኖ በተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ ስርአትና የማስረጃ ህግ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት አመት በላይ በሚል የተደነገገውን ቅጣት እንደ መነሻ ቅጣት በመውሰድ የቅጣት መነሻቸው አራት ዓመት የሆነ በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የሚመለከት እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ ዋስትናን መፍቀድ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፤
- ተከሳሹ በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰው የጉዳት መጠንን በተመለከተ አቃቤ ህግ ክስ በመሰረተበት የህግ አንቀጽ በተከሳሹ የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰውን የጉዳት መጠን አለመግለጹ ተከሳሽ በዋስትና ቢለቀቅ ዋስትናውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና መብትን የማያስከለክል ስለመሆኑ፤

የሰ/መ/ቁጥር 182050

ታሕሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም።

አመልካች፡ የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ህግ

ተጠሪ፡ ብርጋዴር ጀነራል ሐድጉ ገ/ጊዮርጊስ

[142]በሰ/መ/ቁ 182050 (ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24
[143]የሰ/መ/ቁ 44594 (ሐምሌ 15 ቀን 2001ዓ.ም) ቅፅ 9
[144]የሰ/መ/ቁ 57938 (ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የዋስትና ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 180500 ላይ ሐምሌ 30/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠባቸው ሁለቱም ድንጋጌዎች የዋስትና መብት የማያስከለክሉ በመሆኑ በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ሲል የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪን ጨምሮ በአራት ግለሰቦች ላይ አዋጅ ቁጥር 881/2007 በመጥቀስ ባቀረበው የሙስና ወንጀል ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን ከሰማ በኋላ ሰኔ 07 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪን በተመለከተ ክስ የቀረበበትን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113/2/ መሠረት ወደ አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ በመቀየር እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ብይን ተከትሎ ተጠሪ ባቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ የተባለ መሆኑን እና የሁለቱ ክሶች ቅጣት ሲደመር ከ10 ዓመት በላይ መሆኑን በመግለፅ የዋስትና ጥያቄውን በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4 መሠረት ውድቅ አድርጓል፡፡

ተጠሪ የዋስትና ጥያቄውን በሚመለከት በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ብይን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ከዋስትና አንፃር የተሰጠውን ብይን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለክላል የሚለው የሕግ አገላለጽ በግልጽ እንደሚያሳየው ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እና በላይ የሆነ ድንጋጌን የሚመለከት እንደሆነ የሚያሻማ አይደለም፤ ተደራራቢ ወንጀሎች እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጊዜ ዋስትና ሊያስከለክል እንደሚገባ የድንጋጌው ሀሳብ ቢሆን ኖሮ ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ ባላስፈለገ ነበር፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ተደራራቢ ወንጀልን የሚመለከት እንጂ ተጠሪ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበት አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ መነሻ ቅጣቱ አንድ ዓመት ቀላል እሥራት ወይም አንድ ዓመት ጽኑ እሥራት የሚለውን የሚጨምር ነው በሚል የሚተረጎም አይደለም፤ በይግባኝ ባይ ላይ የተለየ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ ተደራራቢ ወንጀሎች ተደምረው ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ነው በማለት የዋስትና መብት መከልከሉ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 2 ንኡስ ቁጥር 3/1 ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት ተጠሪ ለብር 100,000 የሚበቃ ዋስ ሲያቀርቡ ከእስር እንዲፈቱ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የተሻሻለው የፀረ- ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4/1 / በአዋጅ ቁር 882/2007 እንደተሻሻለው / የድንጋጌው ይዘት ሊተረጎም የሚገባው ከ4 ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል የቅጣት ጣሪያው ከ4 ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ሲሆን እንደሆነ እና መደመር ያለባቸው ተደራራቢ ወንጀሎች የቅጣት ጣሪያቸውን እና የወንጀሎችን ክብደት መሠረት በማድረግ እንደሚደመሩ ሕጉ ሲረቀቅ መነሻ ከተደረጉት ምክንያቶች እና ከወንጀሎቹ ክብደት አኳያ መረዳት እየተቻለ ይግባኝ ሰሚ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 4 ዓመት የተባለውን እንደመነሻ ቅጣት ወስዶ ተጠሪን በዋስትና መልቀቁ ከህጉ መንፈስ ውጭ ከመሆኑም በላይ የአዋጁን ተፈፃሚነት ከጥያቄ

የሚያስገባ ነው፤ በዚህ አዋጅ እና በሌሎችም የሙስና ወንጀሎች ድንጋጌዎች መነሻቸው አራት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሙስና ወንጀሎች የሉም፤ በሙስና ወንጀል የዋስትና ክርክር ጊዜ ክስ የቀረበበት ድንጋጌ ጣሪያ ቅጣት ሊታይ እንደሚገባ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 ላይ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ 4 ዓመት የተባለው የቅጣቱ ጣሪያ በሚለው ሊወሰድ ሲገባው በሕጉ ባልተደነገገበት ሁኔታ 4 ዓመትን እንደመነሻ ቅጣት መወሰዱ አግባብ አይደለም፤ ከዋስትና አሰጣጥ አንፃር የቀረበው የክስ ብዛት ከግንዛቤ ሊገባ እንደሚገባ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ 59302 ላይ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ እና ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ሁለት ወንጀሎች በመሆኑ ተደራራቢ ክሱ ከሚያስከትለው ቅጣት አንፃር የዋስትና ጥያቄው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ መሠረት ሊታይ ሲገባው መታለፉ አግባብ ስላልሆነ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪ በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቹ የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ የአሁን ተጠሪ በአዋጅ ቁር 881/2007 አንቀፅ 9/1/ ስር በሁለት ወንጀሎች እንዲከከላከሉ ብይን ተሰጥቶ እያለ የስር ፍርድ ቤት በዋስትና እንዲለቀቁ የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1፤ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 2 እና በሰ.መ.ቁ 63344 እና 124750 ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በተጠቀሰው ድንጋጌ ውስጥ 4 ዓመት የተባለው መነሻ ቅጣት ለመሆኑ ህጉ በግልፅ ያስቀመጠ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፤ ዋስትና ሊከለከል የሚችለው ከ4 ዓመት በላይ በሆነ ተደራራቢ ወንጀል ለመሆኑ ሕጉ በግልጽ አስቀምጧል፤ አራት ዓመት እንደቅጣት ጣሪያ ሊወሰድ አይገባም፤ አመልካች ተከላከል የተባልኩበት የሕግ አንቀጽ የቅጣት መነሻ የአንድ ዓመት ቀላል እስራት ነው፤ አመልካች የጠቀሳቸው የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ሲሆን በ2007 ዓ.ም በወጣ አዋጅ ላይም ተፈጻሚ አይሆኑም፤ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አተረጓጎም አዋጅ ቁጥር 881/2007 አፈፃፀምን የሚከለክል አይደለም፤ በአዋጅ ቁር 434/1997 እና በተሻሻለው አዋጅ መካከል ልዩነት ካለ አዲሱ ሕግ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል፤ በሰበር ችሎት ማስቀረቢያ ነጥብ ላይ የተጠቀሱት የሰበር ውሳኔዎች አሁን ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ትርጉም ሳይሆን መነሻ እና መድረሻ ቅጣቱ በግልፅ ተለይቶ ባልተጠቀሰ ድንጋጌ ከመሆኑም በላይ በተሻሻለ ሕግ ላይ የተሰጡ በመሆናቸው አሁን ለቀረበው ጉዳይ ተፈፃሚነት የላቸውም፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ ድንጋጌ መሠረት የቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ በመሆኑም የቀረበው ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 15/2011 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ክስ በቀረበበት አዋጅም ሆነ በወንጀል ህጉ መነሻ ቅጣቱ 4 ዓመት የሆነ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ሕግ አውጪው የማይፈፀም ሕግን ያወጣል ብሎ መውሰድ የሕጉን መንፈስ እና ዓላማ የተከተለ አይደለም፤ ክስ የቀረበበት አዋጅ የሰበር ችሎቱ በሰ.መ.ቁ 63344 ላይ የሰጠውን ትርጉም የሚያጠናክር በመሆኑ ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት የለውም ሊባል አይገባም፤ ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠባቸው ሁለቱም አንቀፆች የቅጣት ጣሪያ ሰበር ችሎቱ በተጠቀሰው መዝገብ ላይ የሰጠው ትርጉም ለአዋጅ ቁጥር 881/2007 ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል፤ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ/ ድንጋጌን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ትርጉም በመሆኑ እና የሰበር ክርክር የሕግ አተረጓጎምን የሚመለከት በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሊመለከተው ሲገባው ያለፈውን ጉዳይ ማቅረቡ ተገቢ ነው በማለት የሰበር አቤቱታው በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/1/ ድንጋጌ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠ እና የሁለቱም ክሶች ቅጣት ሲደመር ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4 መሠረት የዋስትና ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ያደረገው መሆኑን፣ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ተደራራቢ ወንጀልን የሚመለከት እንጂ ተጠሪ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበትን አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ መነሻ ቅጣቱ አንድ ዓመት ቀላል እሥራት ወይም አንድ ዓመት ጽኑ እሥራት የሚለውን የሚጨምር ነው በሚል የሚተረጎም አይደለም በማለት የተጠሪን የዋስ መብት የጠበቀ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ፡-

1. በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትናን ይከለክላል በማለት የተቀመጠው ሀሳብ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት ነው? አይደለም?

2. ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ባስቀመጠ ጊዜ የዋስትናን መብት ጥያቄን ለመወሰን ሲባል ተፈጻሚ የሚሆነው የትኛው የቅጣት አማራጭ ነው?

3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል መከራከሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪ የዋስትና መብት ሊከለከል አይገባም ማለቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም ከላይ ለተያዙት መሠረታዊ የክርክሩ ጭብጦች ምላሽ መስጠት ያስችለን ዘንድ የሙስና ወንጀሎችን አስመልክቶ በሐገራችን የወጡትን ሕጎች እና በየጊዜው የወጡትን የማሻሻያ አዋጆች ሕግ አውጪው ሊያሳካው ከፈለገው ግብ እና ከዋስትና መብት መሠረታዊ መርሆዎች እና ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 እንደተሻሻለ / አዋጅ ቁጥር 239/93 አንቀጽ 51/2 / በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም በማለት ግልጽ ክልከላ ያደረገ አዋጅ የነበረ ሲሆን ሕግ አውጪው አስቀድሞ ባወጣው የሙስና ወንጀሎች ሕግ ዋስትናን በግልጽ ክልከላ /ገደብ/ ያደረገ መሆኑን፣ በሂደት በወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1/ በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ማመልከት ይችላል፣ ሆኖም የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መልቀቅ አይቻልም በማለት የሙስናን ወንጀል ቅጣት መጠንን መሠረት በማድረግ ዋስትናን ለመፍቀድ ወይም ለመንፈግ እንደመስፈርት በማስቀመጥ በዋስ የመለቀቅ መብት በመርህ ደረጃ ሕገ-መንግስታዊ መብት መሆኑን ያመላከተ ነው፡፡

በቀጣይነት የወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ይህንኑ ሕገመንግስታዊ መብት የበለጠ በማስፋት በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው

በዋስ እንዲለቀቅ ለፍ/ቤት ማመልከት እንደሚችል ሆኖም የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በቀደሙት አዋጆች እንደተመለከተው በዋስትና መለቀቅ የማይችል መሆኑን፣ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ግን ዋስትና የሚከለክሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በሙስና ወንጀል የተያዘን ሰው የዋስትና መብትን አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ የወጡት ሕጎች ከላይ በዝርዝር የተገለጹት ሲሆኑ እነዚህ ሕጎች ሊያሳኩት የፈለጉት መሠረታዊ ዓላማ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ ዋስትናን አስመልክቶ ከተደነገጉትን ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሠረቱ የተያዙ ሰዎች በሕገ-መንግስቱ ጥበቃ ከተደረጉላቸው መብቶች አንዱ የዋስትና መብት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6 የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዘመናዊው የሕግ አስተሳሰብም በዋስ ለመለቀቅ ከሚያበቁ ምክንያቶች መካከል ጎልቶ የሚታየው ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሳይሰጥበት ሊቀጣ አይገባውም የሚለው ነው፡፡ በሕገ-መንግስቱ ልዩ ጥበቃ የተሰጠው ይህ መብት መሠረታዊ ዓላማውም ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኝነቱ ሳይረጋገጥበት በእስር እንዳይቆይ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መርሁ መፍቀድ ሲሆን ልዩ ሁኔታው ደግሞ መከልከል ነው፡፡

ይህን መሠረታዊ መብት አስመልክቶ የመወሰን ስልጣን እና ሃለፊነት የተሰጣቸው ፍ/ቤቶችም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው የሚያቀርበውን የዋስትና መብት ጥያቄ እና ከሣሽ የሆነው ዓቃቤሕግም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት በሕገመንግስቱ ዋስትናን አስመልክቶ ከደነገገው መሠረታዊ ዓላማ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ መርምረው ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ሲያደርጉም በመርህ ደረጃ የዋስትናን መብት መፍቀድ ያለባቸው ሲሆን በሕጉ ተለይተው በተቀመጡ ምክንያቶች ግን የዋስትናን መብት በልዩ ሁኔታ ሊነፍጉ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ምክንያቶች መርማሪው ፖሊስ ምርመራውን ገና ያላጠናቀቀ ሲሆን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 59፤ ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስትና ለመለቀቅ የሚከለክል ሲሆን በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 የሕግ ክልከላን መሠረት በማድረግ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች፤ ወይም ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስ መለቀቅን የማይከለክል ቢሆንም ተጠርጣሪው ቢለቀቅ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተገለፁትን ተግባራት ይፈጽማል ተብሎ ሲታመን ነው፡፡ የዋስትና መብትን አስመልክቶ በሕገመንግስቱ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ የተቀመጡት መሠረታዊ መርሆዎች በዝርዝር የተገለጹት ሲሆኑ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረን ወይም የተከሰሰን ሰው አስመልክቶ በየጊዜው ተሻሽለው የወጡት ሕጎች ከዋስትና መብት መሠረታዊ መርሆዎች ጋር ተገናዝበው ሲታዩ ሊያሳኩ የፈለጉት መሠረታዊ ዓላማ ምንድነው የሚለውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 እንደተሻሻለ / አዋጅ ቁጥር 239/93 አንቀጽ 51/2 / በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም በማለት ግልጽ ክልከላ አድርጎ የነበረ አዋጅ ቢሆንም የዋስትና መብት በሕገመንግስቱ እና ኢትዮጲያ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ የተደረገለት መሠረታዊ መብት መሆኑ ታምኖበት በሂደት በወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ እንደማይችል በመግለጽ በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በተከሰሰበት ሕግ ላይ ያለውን የቅጣት መጠን መሠረት በማድረግ የዋስትና መብትን በከፊል የፈቀደ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 ድንጋጌ ከፍተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስ ከመልቀቅ ይልቅ በእስር ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ማድረግ፤ በሌላ በኩል ከ10 ዓመት በታች ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በእስር ከማቆየት ይልቅ በዋስ ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ማድረግ የዋስትና መብት ሕገመንግስታዊ ሽፋን የተሰጠው መሠረታዊ መብት መሆኑ ታምኖበት ሕግ

አውጪው የዋስትና መብትን አስመልክቶ አስቀድሞ በነበረው አዋጅ ላይ አስቀምጦት የነበረውን ፍጹም ክልከላ በተወሰነ ደረጃ በመተው የዋስትና መብትን በተወሰኑ የሙስና ወንጀሎች ላይ የፈቀደ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍ/ቤት ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም፡፡ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል በማለት ይደነግጋል፡፡ በድንጋጌው የመጀመሪያ ሐሳብ ላይ የተቀመጠው እና የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም የሚለው ሐሳብ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም በማለት ከተገለጸው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 የመጀመሪያ ሀሳብ የተለየ ነገር የለውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ላይ የተቀመጠው ሁለተኛው ሀሳብ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የክርክሩ ጭብጥ በመሆኑ በድንጋጌው ላይ የተቀመጠው ሁለተኛ ሀሳብ መሠረታዊ ዓላማ ከድንጋጌው ይዘት፤ አግባብነት ካላቸው የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች እና ከመደበኛው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ሲሆን ይህ ደግሞ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት ቅጣት መጠን በሚገባ ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106/1 ቀላል እስራት ከ10 ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጣ መሆኑን፤ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 108/1 ድንጋጌ ደግሞ ጽኑ እሥራት ከአንድ ዓመት እስከ 25 ዓመት የሚደርስ እና በሕጉ ተገልጾ በተደነገገ ሲሆንም በዕድሜ ልክ የሚያስቀጣ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ የመጀመሪያ ሀሳብ ላይ የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም በማለት የተገለጸ በመሆኑ ይህ ሀሳብ የሚመለከተው በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን ነው፡፡ በዚሁ ድንጋጌ ላይ የተቀመጠው ሁለተኛ ሀሳብ የድንጋጌው የመጀመሪያ ሀሳብ በአራት ነጥብ ከተቋጨ በኋላ ይህንኑ ሀሳብ ተከትሎ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል በማለት የተገለጸ በመሆኑ እና በልዩ ሁኔታ ከወንጀሉ ከባድነት የተነሳ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ ወይም በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ ወይም ወንጀለኛው በተደጋጋሚ ሲቀጣ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል እንደተጠበቀ ሆኖ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣው ከ10 ቀን እስከ ሶስት ዓመት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በማለት የተገለጸው ሀሳብ ከአራት ዓመት በላይ በጽኑ እሥራት ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎችን የሚመለከት እንጂ የቅጣት መነሻቸው አራት ዓመት የሆነ በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የሚመለከት እንዳልሆነ ከድንጋጌው አቀራረጽ እና ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በሚል የተገለጸው ሁለተኛ ሀሳብ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት አይደለም ካልን በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የፈለገውን ያህል ተደራርበው ቢገኙ ሌላ ሕጋዊ ምክንያት

እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው በሚል ምክንያት የተከሰሰውን የዋስትና መብት መከልከል የማይቻል መሆኑ፤ ሆኖም ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እና እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ግን የተከሰሰውን ሰው የዋስትና መብት የሚከለከል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከላይ የተመለከተውን የሕጉን ትንታኔ መነሻ በማድረግ በሙስና ወንጀል ሕግ አዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ወንጀሎች መኖር አለመኖራቸውን በተመለከተ አዋጁን እንደተመለከትነው በአዋጁ አንቀጽ 13/4/ለ የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፤ በአዋጁ አንቀጽ 13/7 የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከሶስት ዓመት እስከ 7 ዓመት እና ከብር 10,000 እስከ 50,000 መቀጮ፤ በአዋጁ አንቀጽ 17/2 የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ7 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ 20,000 በማይበልጥ መቀጮ፤ በአዋጁ አንቀጽ 16/1 ላይ የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከአንድ ዓመት እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ ከእነኚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ድንጋጌዎቹን በመተላለፍ የተከሰሰ ሰው ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል አመላካች ድንጋጌዎች መሆናቸውን ነው፡፡

ይህንኑ መሠረት በማድረግ በእጃችን ያለውን ጉዳይ እንደመረመርነው አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው ክርክር መነሻቸው አራት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሙስና ወንጀሎች የሉም በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ድንጋጌዎች የተከሰሰ ሰው ከአራት አመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል አመላካች ድንጋጌዎች በመሆናቸው እና በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በማለት የተገለጸው ሀሳብ ከአራት ዓመት በላይ በጽኑ እሥራት ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎችን የሚመለከት እንጂ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት ባለመሆኑ አመልካቹ በዚህ ረገድ ያቀረበው መከራከሪያም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በድንጋጌው ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በሚል የተገለጸው የሕጉ አገላለጽ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እና በላይ የሆነን ድንጋጌን የሚመለከት ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበው ክርክር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 በሙስና ወንጀል የዋስትና ክርክር ጊዜ ክስ የቀረበበት ድንጋጌ ጣሪያ ቅጣት ሊታይ እንደሚገባ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ 4 ዓመት የተባለው የቅጣቱ ጣሪያ ሊወሰድ ይገባል በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አኳያ ተጠቃሹ የሰበር ሰሚ ችሎት ወሳኔ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 ሐምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ዋስትናን በሚመለከት የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 676/1 በመተላለፍ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በማለት የተከሰሰን ሰው በሚመለከት የተሰጠ ውሳኔ ሲሆን ድንጋጌው የሚመለከተው ተፈጸመ የተባለውን የወንጀል ድርጊት እና ቅጣቱን የሚመለከት እንጂ አማራጭ ቅጣት አልተቀመጠበትም፤ በድንጋጌው ጥፋተኛ የተባለም ሰው ከአምስት ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ መሆኑን ይገልጻል፤ ይህንኑ ድንጋጌ እና የአዋጅ 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ በመዝገቡ የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ መውሰድ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ተፈጻሚ

የማያደርግ እና ሕግ አውጭው የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግን በማውጣት ለማሳካት የሚፈልገውን ግብ የማያሳካ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ አስገዳጅ ትርጉም አንድ ቅጣት ብቻ ተለይቶ የተቀመጠበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 676/1 በሚመለከት የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንጂ ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ በሆነ ጊዜ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ፍ/ቤቱ የትኛውን የቅጣት አማራጭ መውሰድ እንዳለበት በመግለጽ የሰጠው የሕግ ትርጉም የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት አለው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በሰ.መ.ቁ 124750 የተሰጠው ውሳኔም አስቀድሞ በሰ.መ.ቁ 63344 የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ፤ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 58 አዋጁ በስራ ላይ ከመፈጸሙ በፊት የተፈጸሙ ወንጀሎች በነባሩ የስነምግባር እና የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ የሚል በመሆኑ እና አመልካች ፈጸሙት የተባለው የሙስና ወንጀል አዋጅ ቁጥር 882/2007 ከወጣ በኋላ በመሆኑ ተጠቃሾ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አይደሉም፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠበት የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/1/ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ10 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል በሚል አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ በመሆኑ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰመ.ቁ 63344 ም ሆነ በሰ.መ.ቁ 124750 በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ባስቀመጠ ጊዜ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ሊያዝ የሚገባው ቅጣት የትኛው እንደሆነ ገዢ ትርጉም ያልሰጠበት በመሆኑ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ሊወሰድ የሚገባው የቅጣት አማራጭ የትኛው ነው የሚለው በጥንቃቄ ሊታይ ይገባዋል፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ሲሆን ይህ ደግሞ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ ነው፡፡ ከላይ በዝርዝር ካስቀመጥናቸው የሕጉ ትንታኔዎች አኳያ ፍ/ቤቱ ቀላል የእስራት ቅጣት አማራጩን የሚወስድ ከሆነ የተጠሪ የዋስትና መብት የሚፈቀድ ሲሆን ፍ/ቤቱ የጽኑ እሥራት አማራጭን የሚወስድ ከሆነ ደግሞ የተጠሪ የዋስትና መብት የሚከለከል ይሆናል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል በድንጋጌው ከተቀመጡት ሁለት የቅጣት አማራጮች ውስጥ የትኛውን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ተከሳሹ ፈጽሞታል ከተባለው ድርጊት፤ ከሙስና ወንጀል አዋጆች ልዩ ባሕርይ እና ከዋስትና መብት መሠረታዊ ዓላማ ጋር በማገናዘብ መለየት ይኖርበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አስቀድሞ ክስ የቀረበባቸውን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113 በመለወጥ በአንቀፅ 9/1/ሀ/ለ እንዲከላከሉ ብይን ሲሰጥ እንደምክንያት ያስቀመጠው በተጠሪ አድራጎት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን ተጠሪ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ የተቀመጠ አይደለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ፈጽመውታል በተባለው የወንጀል ድርጊት ምክንያት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን በዓቃቤሕግ ክስ ላይ የተገለጸው አይደለም የሚባል ከሆነ ተጠሪ ይከላከሉ ከተባለበት የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ላይ ከተቀመጡት የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት የቅጣት አማራጮች ውስጥ የዋስትና መብት ሕገመንግስታዊ ሽፋን የተሰጠው መሠረታዊ መብት ከመሆኑ አኳያ ለዋስትናው ጉዳይ ሲባል የቀላል እሥራት አማራጭን መውሰድ ተመራጭ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ይከላከሉ ከተባለበት የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ላይ ከተቀመጡት የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት የቅጣት አማራጮች ውስጥ ለዋስትናው ጉዳይ ሲባል የቀላል እሥራት አማራጭ የተወሰደ በመሆኑ እና በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የፈለገውን ያህል ተደራርበው ቢገኙ ዋስትናን

ለማስከልከል የሚያስችል ሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው በሚል ምክንያት የተከሰሰውን ሰው የዋስትና መብት መከልከል አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው ክርክር ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ሁለት ወንጀሎች በመሆኑ ተደራራቢ ክሱ ከሚያስከትለው ቅጣት አንፃር የዋስትና ጥያቄው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ መሠረት ሊታይ ሲገባው መታለፉ አግባብ አይደለም በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አኳያ የስር ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል መከራከሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪን የዋስትና መብት መከልከል አግባብ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ በብይን ሲቀይር ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት የዋስትና መብት እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ በዋስትና ጥያቄው ላይ በሰጠው አስተያየት ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በሁለት ክሶች በመሆኑ እና የዋስትና መብት ቢጠበቅላቸው ቅጣቱን በመሸሽ የዋስትና ግዴታቸውን አክብረው ስለማይቀርቡ የዋስትና ጥያቄው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት የተቃወመ ስለመሆኑ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ብይን በግልጽ የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች የተጠሪ የዋስትና መብት በሕግ ባይከለከልም ዋስትናን ሊያስከለክሉ በሚችሉ ሁኔታዎች ሊነፈግ ይገባል በማለት የተከራከረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 መሠረት በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 በተገለጸው አግባብ የተጠሪን የዋስትና መብት ለማስከልከል የሚያስችሉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን መመርመር አላስፈለገውም ነበር፡፡ ተጠሪ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት የዋስትና መብታቸውን በመከልከል በሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበው በተደረገው የቃል ክርክር አመልካች ባቀረበው ክርክር ተጠሪ ጥፋተኛ ሆነው ቢገኙ ሊወሰድ የሚችለው ቅጣት ከባድ ሊሆን እንደሚችል ግምት ከተወሰደ የክሶችን ብዛት እና ከባድነት መነሻ በማድረግ የዋስትና መብት ሊከለከሉ ይገባል በማለት የተከራከረ ስለመሆኑ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት መዝገብ አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ዋስትናን ለማስከልከል የሚያስችል መከራከሪያ አልቀረበም ማለቱ አመልካች በስር ከፍተኛው ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ዋስትናን በሚመለከት ያቀረበውን ክርክር ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተጠሪ የዋስትና መብት ሊከለከል ይገባል የሚል ክርክር ያቀረበ በመሆኑ የተጠሪ የዋስትና መብት በሁኔታ ሊከለከል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 ድንጋጌ ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች የማይፈጽም የማይመስል እንደሆነ የዋስትና ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ፍ/ቤቱ ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በግልጽ አላመላከተም፡፡ በመሆኑም አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም እንደማይመስል ግምት የሚወሰደው በቂ እና ሕጋዊ ሊባል በሚችል ምክንያት ሊሆን ይገባል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች ከተለያዩ ከባቢያዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባሕርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ነጥብ ነው ተብሎ የሚታሰብ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አስቀድሞ ክስ የቀረበባቸውን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113 በመለወጥ በአንቀፅ 9/1/ሀ/ለ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ ብይን ሲሰጥ እንደምክንያት ያስቀመጠው በተጠሪ አድራጎት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን ተጠሪ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ የተቀመጠ አይደለም በሚል ነው፡፡ በተጠሪ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን በዓቃቤሕግ ክስ ላይ የተገለጸው አይደለም የሚባል ከሆነ ተጠሪ በዋስትና ቢለቀቁ ዋስትናውን አክብረው ሊቀርቡ አይችሉም የሚል ግምት የሚያስይዝ ሆኖ

አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የዋስትና መብታቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ሊከለከል አይገባም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎ ፍ/ቤት የተጠሪን የዋስትና መብት በመፍቀድ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት በውጤት ደረጃ ተቀብለነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 180500 ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት በውጤት ደረጃ ጸንቷል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ከተሰየምን ዳኞች ውስጥ ሶስት ዳኞች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተጠሪ የዋስትና መብት በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 መሠረት ሊከለከል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረስን በመሆኑ፤ ከችሎቱ ዳኞች ውስጥ አራት ዳኞች አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተጠሪ የዋስትና መብት በሁኔታ ሊከለከል ይገባል በማለት መከራከሪያ ያቀረበ ቢሆንም የተጠሪ የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ሊከለከል አይገባም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረስን በመሆኑ ተጠሪ በሌላ ወንጀል የሚፈለጉ ካልሆነ በቀር በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን ሊከታተሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 180500 ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ተጠሪ እንዲያስይዙ ካዘዘው የዋስትና መጠን በተጨማሪ ተጠሪ ከሐገር እንዳይወጡ ታዟል፡፡ ይጻፍ፤ ትዕዛዙ ለሚመለከታቸው አካላት ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኛ ፊርማ አለበት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 3 ሥር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ ከሌሎቹ የችሎት ዳኞች በሃሣብ የሚለየኝ በፍሬ ጉዳዩ በአመልካች ተከለከል የተባለበት የህግ ድንጋጌዎች ዋስትና መብትን የሚያስነፍግ አይደለም በሚል በአብላጫው ድምጽ የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል የምደግፍ በመሆኑ በዚህ ላይ ልዩነት የለኝም፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በእርግጥ በሕግ ጉዳይ ዋስትና የሚያስነፍግ አይደለም በማለት ውሣኔ መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕግ ዋስትና በሚያስፈቅድ ጉዳይ ዋስትና መፍቀድ የሚችል ቢሆንም ዋስትና ሊፈቀድ አይገባም በማለት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ተጠቅሶ ክርክር ካለ ይህንንም መመልከት ይጠበቅበታል፡፡

ነገር ግን የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 67 በሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተነስቶ የነበረ እና ፍ/ቤቱ በዚህ ላይ ግራ ቀኙን ሳያከራክር እና ዓቃቤ ሕግ አለኝ የሚለውን የሕግ ግምት የሚያስጥሉ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ፤ተከሣሽም በዐቃቤ ሕግ የተነሳበትን የሕግ ግምትን እና የቀረበበትን ማስረጃ የሚያስተባብሉ መከላከያ እንዲያቀርብ ሳይደረግ ሕጉ ዋስትና መብትን አያስከለክልም በሚል ዋስትና መፈቀዱ ተገቢ ሆኖ ስላላገኘሁት፤እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር ዋስትና ሊፈቀድ አይገባም ብሎ ሲወስን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተነሳውን መከራከሪያ በሥር ፍ/ቤት የተነሳ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት አከራክሮ ውሣኔ ያላሳረፈበት መሆኑን ከጉዳዩ ከተረዳ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክርክር ተደርጎበት ውሣኔ እንዲሰጥ መመለስ ሲገባው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 መሠረት የቀረበ ጥያቄ የለም በማለት ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ተገቢ ክርክር ተደርጎበት ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ

አንቀፅ ተጣርቶ ዋስትና የመፍቀድ ወይም የመከልከል ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባው የነበረ ሆኖ ይህ ሳያደረግ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማጽናት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ ሆኖ ስላገኘሁት ከወዲሁ በሥር ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ.67 ላይ የተሰጠ ውሣኔ ሳይኖር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ባለበት ደረጃ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ድንጋጌን በማንሳት ዋስትና ሊፈቀድ ይገባል በሚል በአብላጫው ድምጽ ሊወሰን አይገባም ነበር በማለት ከባልደረቦቼ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

**የልዩነት ሀሳብ**

- ስማችን በሁለተኛ እና በአራተኛ መስመር ላይ የተጠቀሰው ዳኞች ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 67 አንፃር በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የምንስማማ ሲሆን አብላጫው ድምፅ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 3(1) ድንጋጌ አተረጓጎምን አስመልክቶ በጠቀሰው ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ የልዩነት ሀሳባችንን በሚከተለው መልኩ አስፍረናል፡፡

- በመሰረቱ በአብላጫ ድምፅም እንደተገለፀው በዋስ የመለቀቅ መብት ህገ መንግስታዊ መርህ ሲሆን በህግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል የሚችል ለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 19(6) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የዋስትና መብትን በተመለከተ በህግ በልዩ ሁኔታ ገደብ ከተጣለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያዘ የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስረዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4(1) ከአስር ዓመት በላይ ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ሊለቀቅ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

- ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው የተሻሻለው ልዩ የፀረ ሙስና የሥነ ሥረዓትና የማስረጃ ህግ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 882/2007 በአንቀፅ 3(1) ስር ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች የተከሰሰን ሰው ጉዳይ በተመለከተ ከላይ የሰፈረውን ድንጋጌ ቃል በቃል ከደገመ በኋላ ቀጥሎ ባለው ዓረፍተ ነገር ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን አስመልክቶ አዲስ ሀሳብ አስፍሯል፡፡ ይህም ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እየተደመሩ ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል የሚል ነው፡፡

- ግራ ቀኙን ለዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ያበቃውም ይኸው በማሻሻያ አዋጁ ውስጥ የተጨመረው አዲስ ሀሳብ አተረጓጎምን የሚመለከት እንጂ ክስ በቀረበበት ወይም ተከላከል በተባለበት አንቀፅ ስር አማራጭ ቅጣት በተቀመጠ ጊዜ ለዋስትና ሲባል የትኛው ቅጣት መታየት አለበት የሚል ባለመሆኑ ለቀረበው ጉዳይ እንደ ዋና ጭብጥ ተደርጎ በአብላጫው ድምፅ መያዙ አግባብ አይመስለንም፡፡ ያም ሆኖ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ተከሳሹ ለሚያቀርበው የዋስትና ጥያቄ ፍርድ ቤቶች ተከሳሹ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለውን የቅጣት ጣሪያ መነሻ በማድረግ ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚገባ ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁ/63344 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ዝቅተኛው ቅጣት የሚያዝበት አግባብ የለም፡፡ በእርግጥ አብላጫው ድምፅ ይህ የሰበር ችሎቱ ትርጉም አሁን ለቀረበው ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብሏል፡፡ ሆኖም ትርጉሙ የተሰጠው የሙስና ወንጀልን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ከዋስትና ጋር በተያያዘ መነሻ ሊደረግ የሚገባን ነጥብ ያመለከተ እንጂ የቅጣት ዓይነትን ለይቶ የተሰጠ ባለመሆኑ አሁን ለቀረበው ጉዳት ተፈፃሚነት የለውም ሊባል አይገባም፡፡ እናም እነዚህ ነጥቦች ታሳቢ ተደርገው የቀረበውን ጉዳይ በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

- በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አተረጓጎም መሰረት በድንጋጌው ውስጥ የተጠቀሰው አራት ዓመት መነሻ ቅጣታቸው አራት ዓመት እና በላይ የሆኑ ወንጀሎችን የሚመለከት ነው የሚል ሲሆን በተጠሪ ጠበቃ በኩል ተመሳሳይ አረዳድ መኖሩን ከቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከአራት ዓመት በላይ ተብሎ የተጠቀሰው መነሻ ቅጣትን ሳይሆን የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀሎችን ጣሪያ ቅጣት የሚመለከት ነው የሚል ነው፡፡

- የድንጋጌውን አተረጓጎም ልዩነት በአግባቡ ለመፍታት ይረዳ ዘንድ ጉዳዩን ከሶስት አበይት ነጥቦች አኳያ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የዋስትና መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እድገታዊ አመጣጥን የሚመለከት ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት የሙስና ወንጀልን በተመለከተ ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ መጀመሪያ የታወጀው በአዋጅ ቁጥር 236/1993 ነው፡፡ ይህ አዋጅ በታወጀ በ20 ቀኑ በአዋጅ ቁጥር 239/1993 የተሻሻለ ሲሆን ማሻሻያ አዋጁ በአንቀፅ 2 ስር በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት የሌለው መሆኑን ደንግጓል፡፡ ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 434/1997 ደግሞ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የዋስትና መብት የከለከለው ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስር ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰን ሰው መሆኑን በአንቀፅ 4 ስር ደንግጓል፡፡ በመጨረሻም ይህንን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 882/2007 ደግሞ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ሆነው ነገር ግን ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰ ሰው የተደራራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ ዋስትና የሚከለከል መሆኑን ደንግጓል፡፡

- የድንጋጌዎቹ የእድገት አመጣጥ የሚያሳየው መጀመሪያ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው ሙሉ በሙሉ ዋስትና ተከለከለ፤ ቀጥሎ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው ብቻ ተከለከለ፤ በመጨረሻም ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰ እና የተደራራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ የሆነ ተከሳሽ ብቻ እንዲከለከል መደረጉን ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ የእድገቱ አመጣጥ አንፃር አዋጅ ቁጥር 882/2007 በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 434/1997 ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት ሚያስቀጡን ወንጀሎችን በተመለከተ በተቃራኒ ንባብ እውቅና ተሰጥቶት የነበረውን የዋስትና መብትን በልዩ ሁኔታ የሚገድብ እንጂ አብላጫው ድምፅ በገለፀው አኳኋን የዋስትና መብትን በተሻለ የሚያሰፋ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከልዩ ህጎች የሚጠበቀው ዋስትና መፍቀጃ ምክንያቶችን መዘርዘር ሳይሆን በህገ መንግስቱ የተረጋገጠው መብት ሊገደብ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታን ብቻ ለይቶ ማስቀመጥ ነው፡፡ ከተጠቀሱ አዋጆች የእድገት ሂደትም መገንዘብ የሚቻለው ከጊዜ ወደ ጊዜ ዋስትና የሚያስከለክሉ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ እየተለዩ መምጣቸውን ነው፡፡

- አዋጅ ቁጥር 434/1997 ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ሊለቀቅ እንደማይችል ከመደንገጉ ውጭ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ስለ ተከሰሰ ሰው ያለው ነገር የለም፡፡ እናም ከፍርድ በፊት ያለመታሰር መብት ህገ መንግስታዊ መርህ በመሆኑ የድንጋጌውን ተቃራኒ ንባብ በመውሰድ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው በመደበኛው የወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ሊቀርቡ የሚችሉ የዋስትና መቃወሚያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በዋስትና የመለቀቅ መብት ይኖረዋል ማለት ይቻላል፡፡

- ሆኖም ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡም ሆነው በርካታ ተደራራቢ ወንጀሎች ሊፈፀሙ የሚችሉበት እድል መኖሩ በመዘንጋቱ በአዋጁ ሽፋን አልተሰጠውም፡፡ እናም ከድንጋጌው ይዘት መረዳት የሚቻለው ከዋስትና አንፃር የአዋጅ ቁጥር 882/2007 ዋነኛ ትኩረት ይህንኑ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን ጉዳይ መልክ ማስያዝ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

- የድንጋጌዎቹ የእድገት አመጣጥ ይህን የሚመስል ከሆነ ቀጥሎ ሊታይ የሚገባው ሁለተኛው አበይት ነጥብ የድንጋጌው የቃላት አጠቃቀም ዘዬ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የድንጋጌው ዋና ዓላማ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን የዋስትና ሁኔታ መምራት ነው፡፡ ይህ ከሆነ በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራረቢ ወንጀሎች" የሚለው አገላለፅ ለምን አስፈለገ የሚለው በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ነጥብ ይሆናል፡፡ ከድንጋጌው የቃላት አጠቃቀም በጥቅሉ መገንዘብ የሚቻለው የህግ አውጭው ዓላማ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱትን ሁሉንም ተከሳሾች ዋስትና መከልከል አለመሆኑን ነው፡፡ ይልቁንም ዋስትና መከልከል የተፈለገው እያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ የተደራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ወንጀል የተከሰሱትን ሰዎችን ብቻ ነው፡፡

- የድንጋጌው መልዕክት ይህ ከሆነ ከአራት ዓመት በላይ የተባለው የሚያመለክተው የተደራቢ ወንጀሉን መነሻ ቅጣት ነው ወይስ ጣሪያ ቅጣት የሚለው ቀጥሎ የሚታይ ሶስተኛው አበይት ነጥብ ይሆናል፡፡ የዚህን ሀረግ ትክክለኛ ትርጉም ለመረዳት የሙስና ወንጀልን በሚደነግገው መደበኛ የወንጀል ህጉ እና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ስር ለእያንዳንዱ የሙስና ወንጀል የተቀመጠውን ቅጣት መጠን በጥንቃቄ በመፈተሽ ከላይ ከሰፈረው ድንጋጌ ተግባራዊ አፈፃፀም ጋር አዛምዶ ማየትን ይጠይቃል፡፡

- በዚሁ መሰረት በወንጀል ህጉም ሆነ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ውስጥ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እስራት የሆነ የሙስና ወንጀል የለም፡፡ መነሻ ቅጣታቸው ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር አመት በታች የሆኑት ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ አንዱ መነሻው አምስት አመት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መነሻ ቅጣቱ ሰባት ዓመት የሆነ ነው፡፡ የእነዚህ ሁለቱ ቅጣቶች ጣሪያ ቅጣት እንደ ወንጀሉ ዓይነት የሚለያይ ቢሆንም መዳረሻው ግን ከአስራ አምስት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ነው፡፡

- በዚሁ አግባብ በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ" የሚለው ሀረግ የሚያሳየው የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀል መነሻ ቅጣት ነው የሚባል ከሆነ ጣሪያ ቅጣቱ ቢያንስ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እሰራት ይሆናል፡፡ ጉዳዩ ይህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4(1) እና ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/63344 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ የድንጋጌው ጣሪያ ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በመሆኑ እና በራሱ ከመነሻው ዋስትናን የሚያስከለክል በመሆኑ ስለ ተደራራቢ ወንጀል ማንሳት አያስፈልግም፡፡ በመሆኑም "ከአራት ዓመት በላይ" የሚለው ሀረግ መነሻ ቅጣትን የሚያሳይ ነው የሚለው አተረጓጎም የድንጋጌውን ተግባራዊ አፈፃፀም ትርጉም የሚያሳጣ በመሆኑ የሚያስኬድ አይደለም፡፡

- በአንፃሩ መነሻ ቅጣታቸው ምንም ይሁን ምን ጣሪያ ቅጣታቸው ግን ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሆኑ በአዋጁ ብቻ ከሃያ አንድ በላይ ድንጋጌዎች እንዲሁም ከአራት ዓመት በታች ጣሪያ ቅጣት ያላቸው ወደ አራት ድንጋጌዎች መኖራቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተለያየ ምክንያት አንድን የህግ ድንጋጌን መተርጎም ቢያስፈልግ ከመተርጎሚያ ስልቶች ውስጥ አንዱ ህጉን ማወጅ ካስፈለገበት መሰረታዊ ዓላማ አንፃር ድንጋጌው ተግባራዊ ሊሆን በሚችልበት አግባብ መተርጎም (Purposive Interpretation) ስለመሆኑ የህግ አተረጓጎም መሰረተ ሀሳብ ያስገነዝባል፡፡

- ከዚህ አኳያ የህግ አውጭው ዓላማ ነው ተብሎ ከላይ የተመለከተው ተግባራዊ ሊሆን እና በአግባቡ ከግብ ሊደርስ የሚችለው በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ" ተብሎ የተጠቀሰው ሀረግ የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀሎች ጣሪያ ቅጣት የሚመለከት ነው በሚል ሲተረጎም ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

 የድንጋጌው ትርጉም ይህ ከሆነ የአሁን ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን በተሰጠባቸው እያንዳንዱ ድንጋጌ ስር ያለው ጣሪያ ቅጣት ከአስር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ሲሆን የሁለቱ ተደራራቢ ወንጀል ጠቅላላ ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በመሆኑ በፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥረዓትና የማስረጃ ህግ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥት 882/2007 አንቀፅ 3(1) መሰረት ዋስትና የሚያስከለክል ነው፡፡ እናም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አረዳድ የህጉን መንፈስ የተከተለ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተከተለው አተረጓጎም ከዚህ አኳያ ሊቃና ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረቦቻችን የተለየ አቋም ይዘናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኛ ፊርማ አለበት

## 2.4 ዋስትና በድጋሚ የሚታይበት አግባብ እና ይግባኝ[145]

- በወንጀል በተጠረጠረ ሰዉ ላይ ምርመራ ማድረጊያ ጊዜ በፍርድ ቤት እየተሰጠ ቆይቶ በወንጀል መርማሪ እና/ወይም በዐቃቤ ሕግ የተጠየቀዉን ተጨማሪ የምርመራ ማከናወኛ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ባለመፍቀድ እስከ 15 ቀን ድረስ ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰረት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109/1 መሰረት የሰጠዉ ትእዛዝ ጸንቶ እያለ እና የተሰጠዉ ክስ መመስረቻ ጊዜ ካለቀ በኋላ በተጠርጣሪዉ ላይ ክስ ሳይመሰረት ተጠርጣሪዉን በእስር ላይ ማቆየት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2 እና በተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9/1 የተከለከለዉን በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ወይም በዘፈቀደ አስሮ እንደማቆየት የሚቆጠር ነዉ፡፡
- በወንጀል ምርመራ ሂደት የዋስትና መብት እንዲጠበቅለት ተጠርጣሪዉ ጥያቄ አቀርቦ ጥያቄዉ ተቀባይነት ከአጣ በኋላ የዋስትና ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችል አዲስ ሁኔታ ሲፈጠር ይህንኑ አዲስ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ለዚያዉ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪዉ የዋስትና መብት ጥያቄ በድጋሚ ለማቅረብ ሥነ ሥርዓታዊ መብት ያለው ስለመሆኑ፤[146]

የሰ/መ/ቁ 252231

ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀናዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካች - አቶ አየለ ዳመና

ተጠሪ - የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

---

[145]የሰ/መ/ቁ 252231 (ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም)

[146]በሰ/መ/ቁ 73569 (ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ በሰ/መ/ቁ 59855 (ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣በሰ/መ/ቁ 110969 (ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ሰ/መ/ቁ 113436 (ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 61275 (ሚያዚያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ 146727 (ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአመልካች የዋስትና መብት ይከበርልኝ ጥያቄ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ለማሳረም የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠረጠሩበት ወንጀል ምርመራ እየተደረገ ቆይቶ በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ በ15 ቀናት ዉስጥ ክስ እንዲመሰርት ጊዜ ሰጥቶ መዝገቡን መዝጋቱን፤በዚህ መልኩ በተሰጠዉ ጊዜ ዉስጥ በአመልካች ላይ የወንጀል ክስ አለመመስረቱን ምክንያት በማድረግ አመልካች ለፍርድ ቤቱ የዋስትና መብታቸዉ እንዲጠበቅላቸዉ ጠይቀዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥ አዝዞ በሰጠዉ መልስ አመልካች በፈጸሙት የእምነት ማጉደል እና ከባድ ማታለል ወንጀል የተጠረጠሩና ድርጊቱም በተለያዩ 12 ሰዎች ላይ የተፈጸመ በመሆኑ፣በማታለል ብር 924,814 በባንክ ሂሳባቸዉ ማስገባታቸዉ የተደረሰበት በመሆኑ፤የኦዲት ሥራዉ ስላልተጠናቀቀ በተባለዉ ጊዜ ዉስጥ ክስ መመስረት አንችልም፡፡ስለሆነም አመልካች ከዚህ ቀደም ያቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ ስለተደረገ በድጋሚ ያቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ ይደረገልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 121631 ላይ በቀን 10/11/2015ዓ/ም በሰጠዉ ትዕዛዝ አመልካች እምነት የማጉደል እና የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ከመጠርጠራቸዉ ጋር በተያያዘ ከዚህ በፊት የዋስትና መብት ጥያቄ አቅርቦ በቀን 23/09/2015 ዓ/ም ዉድቅ ከተደረገ በኋላ አሁን በድጋሜ የዋስትና መብት ጥያቄ ማንሳታቸዉ ተቀባይነት የለዉም፡፡ጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የመጨረሻ ዉሳኔ ስለተሰጠበት በይግባኝ ካልተስተካከለ በስተቀር በድጋሚ ሊጠይቁ አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል በአመልካች ላይ እየተደረገ ያለዉን ምርመራ በተመለከተ የኦዲት ሂደቱ ያልተጠናቀቀ መሆኑንና በሂደት ላይ መሆኑን በመግለጽ ዐቃቤ ሕግ የቀረበዉ በቂ ምክንያት ስለሆነ ዐቃቤ ሕግ ክሱን በአጭር ጊዜ ዉስጥ እንዲመሰረት በማለት የአመልካችን የዋስትና መብት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ወሰነ፡፡

አመልካች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት በየደረጃዉ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ አመልካች የተጠረጠሩበት ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/2 ስር ተደነገገዉን ተላልፈዋል በሚል በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 መሰረት ለአመልካች የዋስትና መብት መከልከሉ በአግባቡ ነዉ በማለት ሠርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 10/12/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ አጭር ይዘት ፡- ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 መሰረት በ15 ቀን ጊዜ ዉስጥ ክስ እንዲመሰርት ቢታዘዝም ክስ ባልመሰረተበት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 19/6 ጥበቃ የተደረገልኝን የዋስትና መብት ተከልክያለሁ፡፡ የዋስትና መብት ጥያቄ አንድ ጊዜ ተጠይቆ በሌላ ጊዜ የተለየ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ የዋስትና መብት መጠየቅ እንዳይቻል የሚከለክል ሕግ በሌለበት አመልካች አስቀድሞ የዋስትና ጥያቄ አቅርበዉ ዉድቅ ተደርጓል በሚል ምክንያት ዐቃቤ ሕግ በ15 ቀን ዉስጥ የወንጀል ክስ እንዲመሰርት በተሰጠዉ ጊዜ ክስ አለመመስረቱ ተረጋግጦ እያለ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ ማድረጉ ስህተት ነዉ፡፡በምርመራ መዝገቡ በቀረበዉ ማስረጃ መሰረት አመልካች ሊከሰስ የሚችለዉ በወንጀል ሕግ ቁጥር 676 እና 692 መሰረት ሆኖ እያለ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32 መሰረት ሊከሰስ ይችላል በሚል የዋስትና መብት ጥያቄዬ ዉድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ አንድን ሰዉ በወንጀል ተጠርጥሯል በሚል ምክንያት ብቻ በአስር ላይ ማቆየት በራሱ የዜጎችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጥስ ነዉ ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ተሽሮ የዋስትና መብቴ ይጠበቅልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች በተጠረጠሩበት ወንጀል ክስ ሳይቀርብባቸዉ የሚከሰሱት ዋስትና ሊያስከለክል በሚችል ድንጋጌ ነዉ በሚል ምክንያት ብቻ የዋስ መብታቸዉ

የተከለከለበትን አግባብ ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 07/01/2016ዓ/ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ የመልሱም አጭር ይዘት፡- አመልካች የአቢሲኒያ ባንክ ቦሩ ጃዊ ቅርንጫፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆነዉ ሲሰሩ ከተለያዩ 13 የሚሆኑ የባንኩ ደንበኞች ላይ ብር 1,024,817.00 ስብስበዉ ወደ ደንበኞች ሂሳብ ቁጥር ሳያስገቡ ለራሳቸዉ ጥቅም በማዋላቸዉ በከባድ የእምነት ማጉደልና የማታለል የሙስና ወንጀል ተጠርጥረዋል፡፡ይህ ጉዳይ ከባንክ ጋር የተያያዘ ከመሆኑ አንጻር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለዉም፡፡ክስ መመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠን ሳንጠይቅ የስር ፍርድ ቤት በ15 ቀን ዉስጥ ክስ እንዲንመሰርት ያዘዘዉ ሥልጣን ሳይኖረዉ ነዉ፡፡ ይህ ጊዜ የተሰጠዉ የምርመራ መዝገቡ ለተጠሪ ከመላኩ በፊት ነዉ፡፡ ጉዳዩ ተጨማሪ የማጣራት ሥራ የሚያስፈልገዉ ነዉ፡፡ አመልካች አቢሲኒያ ባንክ ከመግባታቸዉ በፊት የዘመን ባንክ ሠራተኛ የነበሩ ቢሆንም ከዚህ ባንክ የተሰናበቱት በዲሲፕሊን ግድፈት ቢሆንም ከዚህ ባንክ ባልተጻፈ ማስረጃ በአቢሲኒያ ባንክ ስለተቀጠሩ በተጨማሪነት በሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የሙስና ወንጀል ለመክሰስ እየተጣራ ይገኛል፡፡ አመልካች በገቢ ደረሰኝ ላይ ሲያትሙ የነበረዉ ማህተም በባንኩ ለማን የተሰጠ እንደሆነ ከባንኩ ተጠይቆ ማስረጃ ተገኝቷል፡፡በደረሰኞቹ ላይ ያለዉ ፊርማ በፎረንሲክ እንዲመረመር ተደርጎ ዉጤቱ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ ስለሆነም አመልካች በከባድ ማታለል፣በከባድ እምነት ማጉደልና ሀሰተኛ ሰነድን በማዘጋጀትና በመገልገል ተደራራቢ ወንጀሎች የተጠረጠሩ በመሆኑ የጉዳዩ ክብደት ከግምት ገብቶ የአመልካች የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ በመደረጉ የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት አመልካች የዋስትና መብት እንዲጠበቅላቸዉ ያቀረቡት ጥያቄ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች የዋስትና መብት ጥያቄ ያቀረቡት ስር ፍርድ ቤት ምርመራ ተጠናቋል በሚል ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰርት በተሰጠዉ 15 ቀን ዉስጥ ክስ እንዳልመሰረተባቸዉ፣ በተጠረጠሩበት ወንጀል ክስ ሊቀርብባቸዉ የሚችለዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 676 እና 692 መሰረት ስለሆነ የተጠረጠሩበት ወንጀል የዋስትና መብት የሚያስከለክል እንዳልሆነ እና ክስ ሳይመሰረትባቸዉ ከሕግ አግባብ ዉጭ በእስር ላይ እንደሚገኙ በመግለጽ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ ያቀረቡትን የዋስትና መብት ይጠበቅልኝ ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ዉድቅ በማድረጋቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ደግሞ አመልካች በእስር ላይ የሚገኙት በፌዴራል መንግሥት በተመዘገበዉ ባንክ (ሕዝባዊ ድርጅት) ላይ ከባድ የማታለል ፣ ከባድ የእምነት ማጉደል እና ሀሰተኛ ሰነድ የማዘጋጀትና የመገልገል ተደራራቢ ወንጀሎችን ፈመዋል በሚል በመጠርጠራቸዉ እንደሆነ፣ምርመራዉ ሳይጠናቀቅና የምርመራ መዝገብ ለዐቃቤ ሕግ ሳይተላለፍ ክስ መመስረቻ ተብሎ 15 ቀን መሰጠቱ ስህተት እንደሆነ፣ ይህንን ትእዛዝ የሰጠዉ ፍርድ ቤት ሥልጣን እንደሌለዉና ክስ መመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠዉም እንዳልተጠየቀ በመግለጽ በአመልካች ላይ ተደራራቢ የወንጀል ክስ ሊቀርብባቸዉ የሚችለዉ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ መሰረት በመሆኑ የዋስትና ጥያቄያቸዉ ዉድቅ መደረጉ በአግባቡ ነዉ ሲል ተከራክሯል፡፡

በዚህ መልኩ ግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር እና ከስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ግልባጭ እንደተረዳነዉ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉን ቀጥለን የምንመለከተዉ ሆኖ ፍርድ ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109/1 መሰረት ዐቃቤ ሕግ በ15 ቀናት ዉስጥ በአመልካች ላይ ክስ እንዲመሰርት የሰጠዉ ጊዜ አመልካች የዋስትና ጥያቄ ከማቅረባቸዉ በፊት እንደተጠናቀቀ የግራ ቀኙ ክርክር ያሳያል፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስቀድሞ ለምርመራ ተጨማሪ

ጊዜ ቀጠሮ መስጠት እንደማይገባ አምኖበት ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ እንዲመሰርት የ15 ቀናት ጊዜ ከተሰጠ በኂላ እና ይህ ጊዜ ካለቀ በኂላ አመልካች በቀን 06/11/2015ዓ/ም ለሁለተኛ ጊዜ የዋስትና ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም በማለት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ ሲያደርግ የወንጀል ምርመራ አለመጠናቀቁን መረዳቱን ገልጾ ተጠሪ በአጭር ጊዜ ዉስጥ በአመልካች ላይ ክስ እንዲመሰርት አዝዞ መዝገቡን መዝጋቱን የትዕዛዙ ይዘት ያሳያል፡፡በዚህ መልኩ በቀን 10/11/2015ዓ/ም ትዕዛዝ ተሰጥቶ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ ከተዘጋ በኂላ በዐቃቤ ሕግ መልስ ላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ላይ እስካሁን ወይም ቢያንስ ዐቃቤ ሕግ ለዚህ ችሎት መልሱን እስካቀረበበት ቀን 07/01/2016ዓ/ም ድረስ የወንጀል ክስ አለመመስረቱን ተገንዝበናል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2 ስር ማንኛዉም ሰዉ በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ሊያዝ፣ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይችል በመደንገግ ለነጻነት መብት ጥበቃ ተደርጓል፡፡ ይህ መብት የሀገራችን የሕግ አካል በሆነዉ በተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9/1 ላይ በግልጽ እዉቅና የተሰጠዉ መብት ነዉ፡፡በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/6 ስር የተያዙ ሰዎች በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የዋስትና መብት ጥያቄዎችን ላይቀበል የሚችልበት ወይም በገደብ መብታቸዉን የሚያስጠብቅበት ሁኔታ ሊኖር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በመርህ ደረጃ በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸዉ ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በአመልካች ከባድ አታላይነትና ከባድ የእምነት የማጉደል ወንጀል ተፈጽሞበታል የተባለዉ አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ በመሆኑ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 2/4 ትርጓሜ መሰረት ወንጀሉ የተፈጸመዉ ሕዝባዊ ድርጅት ላይ ነዉ፡፡አመልካች የዚህ ባንክ ቅርንጫፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ እንደነበሩ ከተገለጸዉ ጋር ተደምሮ ሲታይ ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ የወንጀል ክስ የሚመሰርት ከሆነ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ስር የተደነገገዉን ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ በተሻሻለዉ የፀረ ሙስና የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 7(1 እና 4) ስር እንደተመለከተዉ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የሚነሱ የመያዝ፣ የብርበራ፣የቀነ ቀጠሮ፣በማረፊያ ቤት የማቆየት፣የዋስትና፣የዕግድ እንዲሁም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የሚታዩት የሙስና ወንጀሎችን ክስ ለማየት ሥልጣን በተሰጠዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ እንዲሁም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/2 ስር እንደተመለከተዉ በአዋጅ ቁጥር 322/1995 መሰረት የዉክልና ሥልጣናቸዉ ያልተነሳባቸዉ የክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ይህ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 7/4 ስር የተደነገገዉ ቢኖርም ይህንን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 7/5 ስር እንደተደነገገዉ በአዋጁ የመያዣ፣ የብርበራ፣ የቀነ ቀጠሮ፣...የዋስትና መብት ጥያቄ የሚመለከቱ ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዮች የሙስና ወንጀሉን የማየት ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እንዲታዩ መደረጉ የተከሳሹን መብት የሚያጣብብ ወይም ማስረጃ እንዲጠፋ ምክንያት የሚሆን ወይም ተገቢ ላልሆነ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን አግባብ ያለዉ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር እና/ወይም ለመክሰስ ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ካመነበት እንደ ሁኔታዉ በአቅራቢያዉ በሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሊወስን ይችላል፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ በአመልካች ላይ የወንጀል ምርመራ ሲያደርግ የነበረዉ አካል ለስር ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን አቅርቦ ለምርመራ የሚያስፈልገዉን ጊዜ ቀጠሮ ሲጠይቅ እንደነበርና በዚያዉ መዝገብ ላይ አመልካች የዋስትና መብታቸዉ እንዲጠበቅላቸዉ ጠይቀዋል፡፡ በዚህ አግባብ የቀረበዉን የወንጀል ምርመራ ለማድረግ የሚያስፈልገዉን ጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ እና የአመልካች የዋስትና መብት ጥያቄ አይቶ ለመወሰን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 434/1997 (በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደገና እንደተሻሻለዉ) በአንቀጽ 7/5 ስር በተደነገገዉ መሰረት ሥልጣን አለዉ ብለናል፡፡በመሆኑም ተጠሪ ጉዳዩ የታየዉ ሥልጣን በሌለዉ ፍርድ ቤት ነዉ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡

እንዲሁም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109/1 መሰረት ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ በ15 ቀናት ዉስጥ ክስ እንዲመሰርት ትእዛዝ ሰጥቶ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ተጠሪ በአመልካች ላይ የሚደረገዉ የወንጀል ምርመራ ሳይጠናቀቅ ክስ መመስረቻ ጊዜ ተሰጥቶ መዝገቡ መዘጋቱ ትክክል አይደለም የሚል ከሆነና በትእዛዙ ላይ ቅሬታ ካለዉ አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት ይግባኝ ጠይቆ ማሻርና በአመልካች ላይ ምርመራ ማድረጊያ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠዉ ማስፈቀድ ሲገባዉ ይህንን አላደረገም፡፡ ክስ እንዲመሰርት የተሰጠዉ ጊዜ ካለቀ በኋላ እስካሁን በአመልካች ላይ ክስ ሳይመሰርት አመልካች በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ በማረፊያ ቤት ታስረዉ እንዲቆዩ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ወይም አመልካችን የያዘዉ የወንጀል መርማሪ አካል በዚህ አግባብ አመልካችን እስር ላይ እንዲያቆዩ የሚፈቅድላቸዉ ሕግ የለም፡፡

አመልካች የዋስትና መብታቸዉ ተጠብቆ ከእስር ለመለቀቅ ለሁለተኛ ጊዜ ማመልከቻ ያቀረቡት አዲስ የተፈጠረዉን ሁኔታ ማለትም ዐቃቤ ሕግ በተሰጠዉ 15 ቀናት ዉስጥ ክስ ያልመሰረተባቸዉ መሆኑን መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ተመልክቶ የዋስትና መብታቸዉ እንዳይጠበቅ የሚያደርግ ሕጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን መርመሮ መወሰን ሲገባዉ አመልካች የዋስትና ጥያቄ አቅርበዉ አስቀድሞ በተሰጠ ትእዛዝ ዉድቅ መደረጉን በመግለጽ ይህን ትእዛዝ አመልካች በይግባኝ ሳያሽሩ ለሁለተኛ ጊዜ ጥያቄዉን ማቅረባቸዉ ተገቢ አይደለም በማለት ዉድቅ ማድረጉ የክርክሩን ልዩ ባህርይና የተፈጠረዉን አዲስ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡ በተጨማሪም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በአጭር ጊዜ ዉስጥ በአመልካች ላይ ክስ ይመስርት  በማለት መዝገቡን መዝጋቱ የጊዜዉን አጭርነት ዐቃቤ ሕግ በመሰለዉ እንዲወስን በሚፈቅድ አኳኋን የመወሰን ሥልጣኑን ለዐቃቤ ሕግ አሳልፎ መስጠቱን እና አመልካች ላልተገደበ ጊዜ በእስር ላይ እንዲቆዩ ሊያደርግ የሚችል ትእዛዝ መስጠቱን ያሳያል፡፡ ይህም የዳኝነት ሥራ አመራር የሚጠይቀዉን የገለልተኛነትና የዳኝነት ነጻነት መርሆዎችን የሚቃረንና ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገለትን የአመልካችን የነጻነትና የዋስትና መብቶች የሚጥስ ነዉ፡፡ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝና በሰበር ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እነዚህን ስህተቶች ማረም ሲገባዉ ያልተረጋገጠ መነሻ ይዞ አመልካች ዋስትና በሚያስከለክል የሙስና ወንጀል ሊከሰሱ ይችላሉ በማለት የአመልካችን ይግባኝና የሰበር አቤቱታዎች በትእዛዝ መሰረዙም ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል በወንጀል በተጠረጠረ ሰዉ ላይ ምርመራ ማድረጊያ ጊዜ በፍርድ ቤት እየተሰጠ ቆይቶ በወንጀል መርማሪ እና/ወይም በዐቃቤ ሕግ የተጠየቀዉን ተጨማሪ የምርመራ ማከናወኛ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ባለመፍቀድ እስከ 15 ቀን ድረስ ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰረት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109/1 መሰረት የሰጠዉ ትእዛዝ ጸንቶ እያለ እና የተሰጠዉ ክስ መመስረቻ ጊዜ ከአለቀ በኋላ በተጠርጣሪዉ ላይ ክስ ሳይመሰረት ተጠርጣሪዉን በእስር ላይ ማቆየት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2 እና በተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9/1 የተከለከለዉን በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ወይም በዘፈቀደ አስሮ እንደማቆየት የሚቆጠር ነዉ፡፡ በወንጀል ምርመራ ሂደት የዋስትና መብት እንዲጠበቅለት ተጠርጣሪዉ ጥያቄ አቀርቦ ጥያቄዉ ተቀባይነት ከአጣ በኋላ የዋስትና ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችል አዲስ ሁኔታ ሲፈጠር ይህንኑ አዲስ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ለዚያዉ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪዉ የዋስትና መብት ጥያቄ በድጋሚ ለማቅረብ ሥነ ሥርዓታዊ መብት አለዉ ብለናል፡፡ በዚህ አግባብ አዲስ ሁኔታ በመፈጠሩ ወይም ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰረት የተሰጠዉ ጊዜ ክስ ሳይመሰረት በማለቁ ምክንያት የተያዘዉ (የታሰረዉ) ሰዉ በዋስትና ለመለቀቅ የሚያቀርበዉ ጥያቄ አግባብነት ካለዉ ሕግ አንጻር ሳይመረመር በደፈናዉ ጥያቄዉ ቀድሞ ተቀባይነት ያላገኘ ነዉ በሚል የተያዘዉ ሰዉ ክስ ሳይመሰረትበት ላልተወሰነ ጊዜ ታስሮ እንዲቆይ የሚያደርግ ትእዛዝ/ዉሳኔ መስጠት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና 10(1/ሐ) ስር በተደነገገዉ መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች ላይ

የወንጀል ክስ እንዲመሰረት የተሰጠዉ የ15 ቀን ጊዜ ከአለቀ በኂላ አመልካች ላይ የወንጀል ክስ ሳይመሰረትባቸዉ በእስር ላይ የሚገኙት በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ በመሆኑ የአመልካች የዋስትና መብታቸዉ ተጠብቆ ከእስር ሊፈቱ ይገባል ብለናል። በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል።

**ዉ ሳ ኔ**

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 121631 ላይ በቀን 10/11/2015ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 433052 ላይ በቀን 20/11/2015ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 436417 በቀን 02/12/2015ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል።

2. አመልካች ብር 50,000.00(ሃምሳ ሺህ ብር) በዋስትና አስይዘዉ ወይም ለዚህ በቂ የሆነ መያዣ ሲያቀርቡ ከእስር እንዲፈቱ ታዟል። አመልካች በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 6/መ መሰረት ከአገር እንዳይወጡ ታግደዋል። ይጻፍ። በዚህ ትእዛዝ መሰረት አመልካች በዋስትና ከመለቀቃቸዉ በፊት ከአገር እንዳይወጡ የተሰጠዉ የዕግድ ትእዛዝ በሚመለከተዉ አካል ተመዝግቦ ዉጤቱ ሲገለጽ ከእስር እንዲለቀቁ ይጻፍ።

**ትዕዛዝ**

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ። ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ።
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## 2.5 በምርመራ ወይም በወንጀል ክርክር ሂደት የግለሰቦች መብት እና ነፃነት[147]

- በወንጀል ተጠርጥረው በፍርድ ቤት በነፃ የተለቀቁ ግለሰቦችን ፖሊስ ከእሥር ባለመልቀቁ ግለሰቦች ለፍርድ ቤት መልሰው አቤቱታ በሚቃርቡበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ የጠለያዩ ትዕዛዞችን በሚሰጥበት ጊዜ ስለአቆያየታቸው ግን ትዕዛዝ ሳይሰጥበት ማለፍ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፤[148]

የሰ.መ.ቁ 222914

ግንቦት 16 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. ኪሲ ቂጡማ ረጋሳ - አልቀረቡም

2. ኮሎኔል ገመቹ አያና ሮሮ- ከአጃቢ ኮንስታብል ሳሙኤል አየነው ጋር ከፌደራል ፖሊስ ቀረቡ ጠበቃቸው ቱሊ ባይሳ ቀርበዋል

[147]የሰ.መ.ቁ 222914 (ግንቦት 16 ቀን 2014 ዓ.ም)
[148]በሰ/መ/ቁ 237767 (ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም)

3. አማኑኤል እጅጉ መርጋ - አልቀረቡም

4. ኡስማን ሀሰን ባንጂ - አልቀረቡም

5. ለሜሳ ታከለ ዊርቱ አልቀረቡም

**ብይን**

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው 2ኛ ተጠሪን በሚመለከት መርምሮ ተገቢውን ብይን ለመስጠት ነው፡፡ አመልካች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 208968 የካቲት 02 ቀን 2014 ዓ.ም የፍትሕ ሚኒስቴር ተጠሪዎች ፍርድ ቤት በነጻ ከለቀቃቸው በኋላ የታሰሩት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነው? ወይስ አይደለም? የታሰሩት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከሆነ ማን እንዳሰራቸው? ተጠሪዎች እንዳመለከቱትም የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞባቸዋል? ወይስ አልተፈጸመባቸውም? ተፈጽሞ ከሆነ የፈጸመው አካል ላይ ምርመራ በማጣራት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርግ፤ ተጠሪዎች ወደፊት በሚጣራው ምክንያት በነጻነት መልስ ለመስጠት ከጠበቆቻቸው ጋር ተነጋግረው መቅረብ ያልቻሉ በመሆኑ ሁኔታው ተጣርቶ ተጠሪዎች ያሉበት ሁኔታ ከታወቀ እና መልስ ለመስጠት እና ለመከራከር በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ መገኘታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ክርክሩን የማንቀሳቀስ መብት ጠብቀን መዝገቡን ዘግተናል በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም መጋቢት 05 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ አቅቧል፡፡

የአመልች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ስለታሰሩበት ሁኔታ የፍትሕ ሚኒስቴር በማጣራት ሪፖርት እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ እያለ መዝገቡ ለጊዜው የዘጋበትን አግባብነት ከመሠረታዊ የወንጀል ክርክር አመራር ስነ ስርኣት አንጻር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች ግንቦት 08 ቀን 2014 ዓ.ም መልስ እንዲሰጡበት ታዞ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በተቀጠሩበት ግንቦት 08 ቀን 2014 ዓ.ም 2ኛ ተጠሪ የሆኑት ኮሎኔል ገመቹ አያና ቀርበው መልስ አዘጋጅተው እንዲቀርቡ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው በመጠየቃቸው እና ቀሪ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር መዝገቡ ለችሎት እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መዝገቡ ለችሎት ቀርቦ በዕለቱ 2ኛ ተጠሪ ከፌዴራል ፖሊስ በአጃቢ የቀረቡ ሲሆን ጠበቃቸውም ቀርበው የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት በነጻ ከለቀቀኝ በኋላ ግንቦት 10 ቀን 2013 ዓ.ም በኦሮሚያ ልዩ ሀይል እና በፌዴራል ፖሊስ ተይዤ ለአንድ ዓመት ያህል በተለያየ ቦታ ታስሬአለሁ፤ የተያዝኩበትን ምክንያት አላውቅምም አልተነገረኝም በኦሮሚያ ክልል በአንድ የዶሮ ማርቢያ ከዶሮ ጋር ታስሬ ምግብ ተከልክያለሁ ቤተሰብ እንዳላይ ተደርጌአለሁ ጸሐይ እንዳላይ ተከልክያለሁ በማለት ለችሎቱ በመግለጻቸው ችሎቱ ዓቃቤሕግ እና የፌዴራል ፖሊስ ግንቦት 10 ቀን 2014 ዓ.ም ቀርበው በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት የፌዴራል ዓቃቤሕግ ቀርቦ 2ኛ ተጠሪ በእስር ያሉበትን ምክንያት እንዲገልጽ ለቀረበለት ጥያቄ እኛ በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ከማቅረባችን በቀር ግለሰቡን አላሰርንም፤ በእስር እንዲቆዩ የሰጠነው ትዕዛዝም የለም፤ ፌዴራል ፖሊስ ከኦሮሚያ ፖሊስ በአደራ ተረክቤአቸዋለሁ ስላለ ለኦሮሚያ ፖሊስ እንዲያስረክብ ጠይቀናል፤ ፌዴራል ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ለመረከብ የኦሮሚያ ፖሊስ ፈቃደኛ አይደለም በማለቱም የኦሮሚያ ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ለመረከብ የማይፈልግ እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተጠርጣሪዎችን የሚፈልግበት የምርመራ መዝገብ ከሌለው ከእስር ልትለቋቸው ይገባል በማለት በደብዳቤ አሳውቀናቸዋል በማለት ገልጸዋል ይህንኑ አስመልክቶም የተደራጁ እና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ሚያዝያ 07 ቀን 2014 ዓ.ም ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ቢሮ የጻፈውን ደብዳቤ ግልባጭ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ግለሰቡ ከእሥር ቢፈቱም አንቃወምም በማለት አስመዝግቧል፡፡ በዕለቱ የፌዴራል ፖሊስ በችሎቱ ትዕዛዝ መሠረት ባለመቅረቡ 2ኛ ተጠሪ የሆኑትን ኮሎኔል ገመቹ አያናን ከኦሮሚያ ፖሊስ በአደራ

ተረክቤአለሁ ያለው የፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ የሚመለከተው የስራ ሀላፊ 2ኛ ተጠሪን በአደራ የተረከበበትን ጉዳይ እና ምክንያት ከማን እንደተረከበ በምን ምክንያት እና በማን ትዕዛዝ እንደተረከበ በጹሑፍ እንዲገልጽ እና የግለሰቡን የአደራ መረካካቢያ ሰነድ በመያዝ ችሎት ቀርቦ እንዲያስረዳ ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ከፌዴራል ፖሊስ ቀርበው 2ኛ ተጠሪን በአደራ አልተረከብንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቀርቡ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከኦሮሚያ ፖሊስ ጠይቀን ታሕሳስ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ፍርድ ቤት አቅርበናቸዋል፤ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠም በኋላ የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር 3-11811/14 በተጻፈ ደብዳቤ እስካሁን ድረስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባለመሰጠቱ መልስ ሰጪዎች በማረፊያ ቤት ስለሚገኙ ምን እናድርግ ትዕዛዝ ይሰጠን ብለን ጠይቀን መጀመሪያም አስረህ አቆይ ብለን የሰጠነው ትዕዛዝ በሌለበት ይፈታ ብለን ትዕዛዝ መስጠት አንችልም ተብለናል፡፡ ከዚህ በኋላ ዓቃቤሕግን ምን እናድርግ ብለን ጠይቀን ለኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን እንድናስረክብ ዓቃቤሕግ አዘዘን፤ በትዕዛዙ መሠረትም የኦሮሚያ ፖሊስ ግለሰቡን እንዲረከበን ከደብዳቤ ጋር ስንወስዳቸው ምክንያት ሳይሰጡ አንረከብም ብለው መልሰውናል፤ ከዚህ በኋላ ለ2ኛ ጊዜ ዓቃቤሕግን ጠይቀን መልስ እየጠበቅን ሳለ የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ደርሶናል በማለት ለችሎቱ ገልጸዋል፤ ይህንኑ አስመልክቶም ግንቦት 11 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ ሁለት ገጽ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ 2ኛ ተጠሪም የሰብአዊ መብት ጥሰት ስለተፈጸመብኝ እና በከፍተኛው ፍርድ ቤት በነጻ ከተለቀቅኩ በኋላ አላግባብ ስለታሰርኪ ዛሬውኑ እንድፈታ ይታዘዝልኝ በማለት ለችሎቱ በቃል አሳስበዋል፡፡

ይህ ችሎትም የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ምላሽ ተከትሎ የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን 2ኛ ተጠሪ በሆኑት ኮሎኔል ገመቹ አያና ሮሮ የጀመረው የወንጀል ምርመራ መኖር አለመኖሩን እንዲሁም ግለሰቡን በአደራ ለፌዴራል ፖሊስ መስጠት አለመስጠቱን የሚገልጽ መልስ በጽሑፍ በማዘጋጀት ይዞ ጉዳዩ የሚመለከተው ሃላፊ ቀርቦ በችሎት እንዲያስረዳ እና ትዕዛዙም በፌዴራል ፖሊስ በኩል እንዲደርሰው ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የፌዴራል ፖሊስ በቁጥር 3-1465114 በቀን 12/09/2014 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የችሎቱን ትዕዛዝ ለኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ያደረሰ መሆኑን ገልጿል ማረጋገጫውንም አቅርቧል፡፡ የኦሮሚያ ፖሊስ የዚህ ችሎት ትዕዛዝ ደርሶት ቀርቦ በችሎቱ ትዕዛዝ መሠረት ያላስረዳ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልፈለገ ተቆጥሮ መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የ2ኛ ተጠሪን አቆያየት በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት አጣርቶ ያገኘውን ምላሽ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጪ ነጻነቱን አያጣም፤ በሕግ ከተመለከተው ሥርዓት ውጪ ሊያዝ ክስ ሊቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም በማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 17 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ሐሳብ ኢትዮጲያ በተቀበለቻቸ ዓለማቀፋዊ ሰነዶች እንደሚከተው ተገልጾአል፡፡

ሁሉአቀፍ የሰዎች መብት መግለጫ አንቀጽ 9 “ no one shall be subjected to arbitrary arrest, detention or exile ” በማለት ይደነግጋል፡፡

ኢትዮጲያ የተቀበለችው ዓለምዓቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 9/1 “ everyone has the right to liberty and security of person. No one shall be subjected to arbitrary arrest or detention. No one shall be deprived of his liberty except on such grounds and in accordance with such procedure as are established by law ‘ በማለት ይደነግጋል፡፡

የሕገመንግስቱ አንቀጽ 10 እና 13 ድንጋጌዎችም ሰብአዊ መብቶች እና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱ እና የማይገፈፉ መሆናቸው፤ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስት እና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካሎች መሠረታዊ መብቶችን እና ነጻነቶችን አስመልክቶ በሕገመንግስቱ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበር እና የማስከበር ሀላፊነት እና ግዴታ እንዳለባቸው እና እነኚህ ድንጋጌዎችም ሐገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት፤ ስምምነቶች እና መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ሊተረጎሙ እንደሚገባ በግልጽ ያስገነዝባሉ፡፡

በመሠረቱ ፍርድ ቤቶች የዜጎችን ሰብአዊ መብቶች እና ነጻነቶች የማስከበር ተፈጥሮአዊ ሥልጣን ያላቸው ሲሆን ሕገመንግስታዊ ግዴታቸውም ጭምር ነው፡፡ ይህ ሕገመንግስታዊ ግዴታም መብቱ ተጥሶብኛል የሚለው ወገን ለፍርድ ቤቱ ሲያመለክት ወይም ፍርድ ቤቱ መብቱ የተጣሰ ስለመሆኑ በየትኛውም ደረጃ ላይ ባለ ክርክር ራሱ ሲደርስበት በላቀ ሁኔታ ሊተገበር ይገባል፡፡ ሕግ አስፈጻሚ የሆኑት ፖሊስ እና ዓቃቤሕግም ሰብአዊ መብቶችን እና ነጻነቶችን የማስከበር ሕገመንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ በከፍተኛ የሀላፊነት ስሜት መብቱን ለማስከበር ሊተጉ እና ሊያስፈጽሙ ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች ከተከሰሰቡት የሽብር ወንጀል በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነጻ ከተሰናበቱ በኂላ ውሳኔውን በመቃወም የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የፈዴራሉን ጠቅለይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመዝገብ ቁጥር 208968 የሆነውን መዝገብ አስቀርበን መገንዘብ የቻልነው ዓቃቤሕግ ያቀረበው ይግባኝ ተመርምሮ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዞ ዓቃቤሕግ ተለዋጭ ቀጠሮ በመጠየቁ ለተጠሪዎች በክፍሉ ፖሊስ በኩል መጥሪያ እና የይግባኝ ቅሬታ እንዲደርሳቸው እና መልስ እንዲያቀርቡ ካዘዘ በኂላ የፌዴራል ፖሊስ ከፌዴራል ፖሊስ የተጻፈ ደብዳቤ ለኦሮሚያ ፖሊስ ይዞ በመቅረቡ የኦሮሚያ ፖሊስም ተጠሪዎችን ለማቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ በመጠየቁ በታዘዘው መሠረት የኦሮሚያ ፖሊስ እንዲያቀርባቸው የፌዴራል ፖሊስም እንዲሁ ተጠሪዎችን ከፌዴራል ፖሊስ ወደ ኦሮሚያ ማረሚያ ቤት መሄዳቸውን ከመግለጹ በቀር አሁን ያሉበትን ሁኔታ ስላላወቀ ሁለቱ ተናበው ያሉበት አድራሻ የሚመለከተው ፖሊስ መጥሪያ እና ቅሬታ ያድርስላቸው በማለት ያዘዘ ስለመሆኑ ጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም ከሰጠው ትዕዛዝ መረዳት ተችሏል፡፡

የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የካቲት 02 ቀን 2014 ዓ.ም የፍትሕ ሚኒስቴር ተጠሪዎች ፍርድ ቤት በነጻ ከለቀቃቸው በኂላ የታሰሩበትን ምክንያት እና የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞባቸው ከሆነም ይህን በፈጸመው አካል ላይ ምርመራ በማጣራት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርግ ትዕዛዝ በመስጠት ክርክሩን የማንቀሳቀስ መብት ጠብቆ መዝገቡን ሲዘጋ የተጠሪዎችን አቆያይት በሚመለከት የሰጠው ትዕዘዝ የለም፤ ይህንኑ ተከትሎ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር 3-11811/14 በተጻፈ ደብዳቤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪዎችን በማረፊያ ቤት እንዲያቆይ በቃል ትዕዛዝ መስጠቱ ይታወሳል፤ ሆኖም እስካሁን ድረስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባለመሰጠቱ ተጠሪዎች በማረፊያ ቤት ስለሚገኙ ምን ማድረግ እንዳለብን ትዕዛዝ ይሰጠን በማለት በመጠየቁ ችሎቱም የተጠሪዎች መታሰር በፍርድ ቤቱ የቃል ትዕዛዝ እንደሆነ ለማድረግ የቀረበው ጥያቄ ያላግባብ እና የፍርድ ቤቱን ስራ ባልተገባ መንገድ ለማጠልሸት ሆኖ ስለተገኘ ደብዳቤውን የጻፈው ክፍል ቀርቦ እንዲያስረዳ ትዕዛዝ ሰጥቶ በዚሁ መሠረት የፌዴራል ፖሊስ ተወካይ መጋቢት 28 ቀን 2014 ዓ.ም በችሎቱ ቀርቦ በቃል ትዕዛዝ ሰው ታስሮ እንዲቆይ ታዘንም አናውቅም ቀደም ሲል በቀን 30/06/2014 ዓ.ም የጻፍነው ደብዳቤ ስሕተት ነው በማለት ይቅርታ የጠየቀ መሆኑን መዝግቦ ቀደም ሲል የተዘጋው መዝገብ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ሲል ትዕዛዝ የሰጠ ስለመሆኑ የስር መዝገብ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት 2ኛ ተጠሪን ይዞ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው የፌዴራል ፖሊስ የተጠሪዎችን አቆያየት በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለበት ዓቃቤሕግን

ጠይቄ ለኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን እንዳስረክብ ታዝዤ በትዕዛዙ መሠረት የኦሮሚያ ፖሊስ ግለሰቡን እንዲረከበኝ ብጠይቅም አልረከብም በማለት መልሶኛል ከዚህ በኋላ ለ2ኛ ጊዜ ዓቃቤሕግን ጠይቄ በመጠባበቅ ላይ ሳለሁ የዚህ ችሎት ትዕዛዝ ደርሶኛል ከማለት በቀር ሌላ የፈጸመው ነገር የለም፣ የፌዴራል ዓቃቤሕግም ግለሰቡን አላሰርንም፣ በእስር እንዲቆዩ የሰጠነው ትዕዛዝም የለም፣ ፌዴራል ፖሊስ ከኦሮሚያ ፖሊስ በአደራ ተረክቤአቸዋለሁ ስላለ ለኦሮሚያ ፖሊስ እንዲያስረክብ ጠይቀናል፣ በመቀጠልም የኦሮሚያ ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ለመረከብ ፈቃደኛ አለመሆኑ ስለተገለጸልን የኦሮሚያ ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን ለመረከብ የማይፈልግ እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተጠርጣሪዎችን የሚፈልግበት የምርመራ መዝገብ ከሌለው ከእስር ልትለቋቸው ይገባል በማለት በደብዳቤ እንዳሳወቀ እና ግለሰቡ ከእሥር ቢፈቱም እንደማይቃወም ገልጾአል፡፡ የኦሮሚያ ፖሊስ 2ኛ ተጠሪን አስመልክቶ የጀመረው የወንጀል ምርመራ መኖር አለመኖሩን እንዲሁም ግለሰቡን በአደራ ለፌዴራል ፖሊስ መስጠት አለመስጠቱን ቀርቦ እንዲያስረዳ ታዞ እና የችሎቱ ትዕዛዝም ደርሶት አልቀረበም፡፡ ይህም በጉዳዩ ላይ መልስ መስጠት እንዳልፈለገ የሚያሳይ ነው፡፡

ስለሆነም የ2ኛ ተጠሪን አያያዝ ሕጋዊነት በተመለከተ የማስረዳት ሀላፊነት ያለባቸው የፌዴራልም ሆነ የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን የአያያዛቸውን ሕጋዊነት ያላስረዱ በመሆኑ ይህ ችሎት የ2ኛ ተጠሪ አያያዝ ሕገወጥ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ይህም ዜጎች በሕገመንግስቱ እና አገሪቱ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፋዊ ስምምነቶች የተረጋገጠላቸውን ሰብአዊ መብቶች እና ነጻነቶች የሚጻረር ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች ፖሊስ ካቀረባቸው በኋላ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት በነጻ ከተለቀቁ በኋላ የታሰሩበትን ምክንያት እና የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞባቸው ከሆነም ይህን በፈጸመው አካል ላይ ምርመራ በማጣራት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርግ ትዕዛዝ በመስጠት ክርክሩን የማንቀሳቀስ መብት ጠብቆ መዝገቡን ሲዘጋ የተጠሪዎችን አቆያይት በሚመለከት ምንም ዓይነት ትዕዛዝ ሳይሰጥ ማለፉ፣ ይህንኑ ተከትሎ የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪዎችን በማረፊያ ቤት እንዲያቆይ በቃል ትዕዛዝ መስጠቱ ይታወሳል፣ ሆኖም እስካሁን ድረስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባለመሰጠቱ ተጠሪዎች በማረፊያ ቤት ስለሚገኙ ምን ማድረግ እንዳለብን ትዕዛዝ ይሰጠን በማለት የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ ስሕተት መሆኑን በችሎት ቀርቦ አስረድቷል በማለት ከመመዝገቡ በቀር የግለሰቡን አቆያየት በሚመለከት ምንም ዓይነት ትዕዛዝ ሳይሰጥ ማለፉ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራል ፖሊሰ ኮሚሽንም ሆነ የፌዴራሉ ዓቃቤሕግ አንዱ ለሌላኛው ደብዳቤ ከመጻፍ በቀር እስከመጨረሻው ድረስ በመሄድ የግለሰቡን የነጻነት መብት አለማስከበራቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም ከቀረበባቸው የወንጀል ክስ በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት በነጻ ከተሰናበቱ በኋላ ሕጋዊነቱ ባልተረጋገጠ ሁኔታ የተያዙት እና እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ በእስር ያሉት 2ኛ ተጠሪ ኮሎኔል ገመቹ አያና ሮሮ ከእሥር ሊለቀቁ ይገባል በማለት ብይን ሰጥተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. ከላይ በተሰጠው ብይን ሐተታ ላይ በሰፊው በተገለጸው ምክንያት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን 2ኛ ተጠሪ የሆኑትን ኮሎኔል ገመቹ አያና ሮሮ ን በዛሬው ዕለት እንዲለቅ ታዟል፣ በትዕዛዙ መሠረት መፈጸም ይቻለው ዘንድ የዚህ ብይን እና ትዕዛዝ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት በመዝገቡ የተያዘው ቀነ ቀጠሮ አልተለወጠም፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

## ክፍል ሶስት

## 3.ክስ ስለመሰማት

### 3.1 የወንጀል ክስ አዘገጃጀት[149]

- ዓቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ የሚያቀርበው የወንጀል ክስ የወንጀሉን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ ያለበት በተለይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን መግለጽ አለበት፡፡[150]

የሰ/መ/ቁጥር - 57644

ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች :- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች :- መምህር ዓወት ተካ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ :- የትግራይ ዐቃቤ ሕግ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ብሔራዊ ክልል የምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የዞኑ ዐቃቤ ሕግ አመልካች በአንደኛ ተከሳሽ ስሙን በመመዝገብ በሥር ፍርድ ቤት አብረው ክስ ከቀረበባቸው ሌሎች ሦስት ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ጳጉሜ 2 ቀን 1998 በአዲግራት ከተማ ቀበሌ 01 ዞን 4 ዓለም መስፍን ሆቴል ፊት ለፊት ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አቶ ፅጌ ባህታን በድንጋይ አናቱንና ሌላውን ሰውነቱን መትተው የገደሉት ስለሆነ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ዐቃቤ ሕግ በጠቀሰው ቀንና ሰዓት አብረውት ከተከሰሱት ሦስት ሰዎችና ክስ ካልቀረበበት ኃይለማርያም አብርሀ ከተባለ ልጅ አህዋ ሆቴል ከተባለው ሆቴል ሲጠጡ ቆይተው ወደ ቤት በመሄድ ላይ እያሉ ዓለም መስፍን ሆቴል ሲደርስ ሙዚቃ ሰምቶ ቀድሞ ከዓለም መስፍን ሆቴል ሲደርስ ሟች ከሆቴሉ ውስጥ ሲወጣ በር ላይ አግኝቶት ሟች ሂድ አንተ ምናባህ ብሎ እንደገፋው፣ አመልካችም ሟች ወታደር ስለመሰለው ምን አደረግሁህ ጋሼ እንዳለውና ሟች አከታትሎ መትቶት ከአስፋልት ላይ እንደጣለውና መነሳት እንዳልቻለ አመልካችም ኡኡ ብሎ እንደጮኸና ከዚያ በኋላ ሟችን በድንጋይ ማን እንደመታው እንዳላየና ተፈንክቶ ስለነበር ተነስቶ እየተንገዳገደ እንደሄደ በመግለፅ በሟች ግድያ ተካፋይ አይደለሁም ወንጀሉን አልፈፀምኩም በማለት ተከራክሯል፡፡

---

[149]በሰ/መ/ቁ 57644 (ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12

[150]የሰ/መ/ቁ 91535 (የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅጽ 15፣ የሰ/መ/ቁ 72304 (ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ የሰ/መ/ቁ 94070 (ሚያዚያ 22 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅጽ 16

ተጠሪ አመልካችና ሌሎቹ ተከሳሾች ዋና ወንጀል አድራጊና የወንጀል ተካፋይ በመሆን ሟችን መግደላቸውን ያስረዳልኛል በማለት አምስት ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ካቀረባቸው ምስክሮች ውስጥ ዐቃቤ ሕግ በአራተኛው ተራ ቁጥር የማስረጃ ዝርዝር ላይ ስሙን የገለፀው ምስክር ሥራው ፖሊስ መሆኑን ገልፆ በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ እና አራተኛ ተከሳሽ ለፖሊስ ቃል ሲሰጡ የሰማ መሆኑንና ሟች አመልካችን ወድቀው ሟች ክላይ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው አመልካች ከታች ሆነው እንዳገኟቸውና ሁለተኛ ተከሳሽ ሟችን በድንጋይ አናቱን የመታው መሆኑንና አራተኛ ተከሳሽ በእግሩ ሟችን የመታው መሆኑን ሲናገሩ ሰምቻለሁ አንደኛ ተከሳሽ /አመልካች/ መናገሩን አላስታውስም በማለት መስክሮ ተመልሷል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ ዝርዝሩ ስሙ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የጠቀሰው ምስክር ሥራው ፖሊስ መሆኑን ገልፆ በሥር ሁስተኛና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሰዎች ስለወንጀሉ አፈፃፀም ለፖሊስ ቃላቸውን ሲሰጡ የሰማ መሆኑን በዝርዝር መስክሮ የተመለሰ ነው፡፡ ለፖሊስ የተሰጠን ቃል የመሰከረው የዐቃቤ ሕግ ሶስተኛ ምስክር ሁሉም በጠቡ ተሳታፊ መሆናቸውን የመሰከሩ መሆኑንና ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በድምፅና በምስል በተቀረፀ ካሴት የሰጡት ቃልና ከአዲግራት ሆስፒታል የተሰጠ ማስረጃ በማስረጃነት የቀረበ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በወረዳ ፍርድ ቤት የሰጡት የእምነት ቃል ሶስት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት የሰጡት የምስክርነት ቃልና በማስረጃነት እንደቀረበ የዞኑ ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልጿል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ሌሎች ተከሳሾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ብይን ሰጥቶ የአመልካችና የሌሎቹን ተከሳሾች መከላከያ ማስረጃ ከሰማ በኂላ በሥር ሶስተኛ ተከሳሽ የነበረው በነፃ እንዲሰናበት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በሥር ሁለተኛ ተከሳሽና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሰዎች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 540ን በመተላለፍ የሰው መግደል ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት አመልካች በሰባት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በአብላጫ ድምፅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዐቃቤ ሕግ እኔን ሟችን በመግደል ወንጀል የከሰሰኝ ቢሆንም ዐቃቤ ህግ ያቀረበው የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ በወቅቱ ሟች እኔን መሬት ላይ ጥሎ እየደበደበኝ እያለ ኡኡታ የሰማሁ መሆኑንና በሥር ሁለተኛ ተከሳሽና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሟችን የመቱት መሆኑንና እኔም ከወደቅሁበት ተነስቼ መሄዴን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ ሟች መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበኝ የኡኡታና የጩኸት ድምፅ ማሰማቴ በወንጀሉ ድርጊት ተካፋይ ወይም ግብረ አበር የነበርኩ መሆኑን አያስረዳም፡፡ ስለሆነም በወንጀሉ ድርጊት የተሳተፍኩ መሆኔን የሚያሳይ ምንም ዓይነት ማስረጃ ተጠሪ አቅርቦ ባላስረዳበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብዬ መቀጣቴ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በፅሑፍ መልሱን እንዲያቀርብ መጥሪያ ከደረሰው በኂላ በፅሑፍ መልሱን ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ሟችን በመግደል ወንጀል ጥፋተኛ ነው ተብሎ የተወሰነበት የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ዐቃቤ ህግ /ተጠሪ/ ባቀረበው ማስረጃ አመልካች የወንጀሉ ሥራ ዋና ወንጀል አድራጊ /ተካፋይ/ አባሪ ወይም ረዳት መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. በተጠሪ ማስረጃ ምስክሮች ስለ አመልካች ያረጋገጡትን ፍሬ ጉዳይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሳስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በመጨረሻው ገፅ በአንደኛው ፓራግራፍ "አንደኛ ተከሳሽ ከሟች ጋር ወድቆ ሲመታ እንደነበረ በምስክሮች የተመሰከረ ሆኖ ነገሩ በመጀመሪያ መነሻው ተከሳሽ ነው ወይስ ሟች ያስነሳው የሚለው ባይታወቅም ሟች ተከሳሹን ጥሎ ይመታው እንደነበር ተከሳሽም እየተመታ እንደነበር ምስክሮችን ሰምቶ ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦና ተረድቷል በሚል መንገድ በአጭሩ ገልፆታል፡፡ ተጠሪ ለዞነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረባቸው የምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃዎች ሟች አመልካችን ጥሎ እየደበደበው እያለ አመልካች የኡኡታና የጫጫታ ድምፅ ያሰማ መሆኑንና የአመልካች የጩኸት ድምፅ በሰሙትና ከአመልካች ጋር አብረው ያመሹት በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች ሟች ከላይ አመልካች ከታች ሆነው ሟች አመልካችን እየደበደበ እንዳለ ሟችን መሐል ራሱን በድንጋይ እንደመቱት የሚያረጋግጡ መሆናቸው የሥር ፍርድ ቤት ስለ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ይዘት በውሣኔው በክርክር ከገለፀው ፍሬ ጉዳይ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ሟች መሬት ላይ ጥሎ እየደበደበው እያለ የኡኡታና የጩኸት ድምፅ በማሰማቱና የአመልካችን ጩኸት ሰምተው የመጡት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በቦታው የደረሱና ሟችን በድንጋይ የመቱት መሆኑን እንጂ ተጠሪ ዐቃቤ ሕግ አመልካች ሟችን ለሞት ያበቃው ድርጊት ሌሎቹ ተከሳሾች ሲፈፅሙ በተግባር ወይም በመላ ሃሳቡ ተካፋይ የነበረ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ በመሠረቱ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የሚያቀርበው የወንጀል ክስ የወንጀሉን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ እንዳለበት በተለይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን መግለፅ ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 112 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከት ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ አመልካች በወንጀሉ ድርጊት በምን ሁኔታ እንደተሳተፈ የሚገልፅ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችና ከአመልካች ጋር የተከሰሱት ሌሎች ሰዎች በወንጀሉ ሥራ ያደረጉትን ተሳትፎና በወንጀሉ ተካፋይ ናቸው የሚልበትን ምክንያት በመዘረዘርና ክሱን እንዲያሻሻል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 119 መሠረት ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው የአመልካች የወንጀል ተሳትፎና ተካፋይነት በዝርዝር የማይገልፀውን የወንጀል ክስ ተቀብሎ ማከራከሩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 112 ድንጋጌን መሠረታዊ ግብ ሳይከተል ክርክሩን የመራው መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ተጠሪ በወንጀል ክሱ በገለፀው ስፍራና ጊዜ ሟች አመልካችን መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና የጩኸት ድምፅ ያሰማ ከመሆኑ ውጭ አመልካች ሟችን ለመግደል የሃሳብ ወይም የድርጊት ተካፋይ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ አንድ ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት በኃላፊነት የሚጠየቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 /ከሀ-ሐ/ በተደነገጉት መሠረት በወንጀሉ ሥራ ተካፋይ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 /ከሀ-ሐ/ በተደነገገው መሠረት ሟችን ለሞት ያበቃውን ድብደባ ሌሎቹ ተከሳሾች ሲፈፅሙ ተካፋይ የነበረ መሆኑ ተጠሪ አላስረዳም፡፡ በተለይም አመልካች ሟችን ሀሳብና አድርጎቱ እንደዚሁም በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ኃላፊነቱን /Burden of proof/ የተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔያቸው አላረጋገጡም፡፡ በአንፃሩ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ጓደኞች የነበሩት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሽ ሟችን በድንጋይ ሲደበድቡት አመልካች የሟች ጥቃት ሰለባ ሆኖ መሬት ላይ ወድቆ ሟች እየደበደበው የነበረና አመልካችም የኡኡታና የጩኸት ድምፅ እያሰማ እንደነበር ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ማስረጃ ይዘት በማጠቃለል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሣኔው ካስፈረው ለመረዳት ችለናል፡፡

አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር የወንጀል ተካፋይ ሆኗል የሚባለው በወንጀሉ አፈፃፀም የግዙፍ ተግባር፣ የሃሳብና የሕግ ሁኔታዎች በመተላለፍና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት በወንጀሉ ድርጊት ተሳታፊ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 በጣምራ በማንበብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ ሰው ጥቃት እየተፈፀመበት ከመሬት ላይ ወድቆ እየተደበደበ ያለ ሰው የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ማሰማቱን በወንጀልነት የሚፈርጅ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ አመልካችን ሟች መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ከመስማቱ ውጭ ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች ሟችን እንዲገድሉት ያነሳሳ ወይም የወንጀሉ አባሪ ስለመሆኑ አያሳይም፡፡ በአጠቃላይ አመልካችን ሟች በመሬት ላይ ጥሎ እየደበደበው እያለ የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ማስማቱ የወንጀል ግዙፍ ተግባር አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ሟችን የመግደል ሃሳብ የነበረው ወይም በመላ ሃሣቡ አድራጎቱ የሚሰጠውን ውጤት የራሱ በማድረግ በወንጀሉ ተካፋይ መሆኑን ተጠሪ በቂ ማስረጃ በማቅረብ እንዳላስረዳ ከሥር ፍርድ ቤት የውሣኔ ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ኡኡታና ጩኸት ማሰማቱ ለሟች መሞት ያስከተለ ተግባር ነው ብሎ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በምክንያትና በውጤት መካከል ግንኙነት እንዳለ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ሟች አመልካችን መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው የጩኸትና ኡኡታ ድምፅ ባያስማ ኖሮ፤ ሟችን በድንጋይ ደብድበው የገደሉት ሌሎቹ ተከሳሾች ከቦታው አይደርሱም ነበር፡፡ ሌሎቹ ተከሳሾች ጩኸቱን ሰምተው መጥተው ሟች አመልካችን እየደበደበው ባያገኙት ኖሮ ሟችን በድንጋይ አይደበድቡትም ነበር የሚል ሕጋዊ መሠረት የሌለው መነሻ በመያዝ አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ እና አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሟችን ለመግደል በተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ተካፍሏል በማለት የሰጠው ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23/1/ ንዑስ አንቀጽ 2፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎትም ከላይ በዝርዝር የተገለፀውና የሕግ ስህተት ያለበትን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ማረምና ማስተካከል ሲገባቸው ውሣኔውን በአብላጫ ድምፅ ማፅናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አነስተኛ ድምፅ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ እና አንቀፅ 540 በመተላለፍ ሳይሆን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 በመተላለፍ ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን የገለፀው ሃሳብ ተገቢነት ያለው መሆኑን መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 " ማንም ሰው አስቦ ሌላውን ሰው በቅርብ ለሚደርስ የሞት አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ወይም ከሶሶት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል" በሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠው ሟች አመልካችን ከመሬት ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና ጩኸት ድምፅ ያሰማ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ሟችን ሆን ብሎና አስቦ ለሞት አደጋ ለማጋለጥ የጩኸትና ኡኡታ ድምፅ ያሰማ ስለመሆኑ ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ማስረጃ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ አመልካች ሟችን ለሞት አደጋ ለማጋለጥ በማሰብ የፈፀመው ተግባር መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 የተዘረዘረውን የወንጀል ድርጊት የፈፀመ ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ ባላስረዳበት ሁኔታ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 571ን በመተላለፍ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በሥር ፍርድ ባቀረበው የወንጀል ክስ በገለፀው ስፍራና ጊዜ ሟች ከመሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና ጩኸት ድምፅ ከማሰማቱ ውጭ አመልካች ሟች በሌሎች

ተከሳሾች በድንጋይ ሲደበደብ በወንጀሉ ዋና አድራጊነት /ተካፋይነት/ በአነሳሽነት፣ ወይም በአባሪነት የተሳተፈ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን አልተወጣም፡፡ ተጠሪ አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት ወይም ከተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ውጭ የሆነ በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የፈፀመ መሆኑን በበቂ ማስረጃ እንዳላስረዳ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ስላቀረበው ማስረጃ ይዘት በውሣኔው ካስፈረው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ አመልካች ሟችን ለህልፈት ባበቃው ድርጊት በመሳ ድርጊቱ፣ ወይም ሃሣቡ ተሳታፊ መሆኑን በበቂ ማስረጃ ካላስረዳ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁ. 141 መሠረት በነፃ ማሰናበት ሲገባው አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ በማድረግ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሣኔ ማፅናቱ ከላይ የተገለፁትን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈፅመዋል በማለት ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልል የምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ እንደዚሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ፍርድ በማፅናት የሰጡት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ)(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ ይሰናበታል በማለት በወንጀለኛ ሕግ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2/ለ/ -1 መሠረት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 3.2 የወንጀል ክስ ማሻሻል[151]

- ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርበው የክስ አቤቱታ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ያልቀረበ ሆኖ ሲገኝ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ክሱ በህጉ አግባብ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ እና ዓቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ ሳይደረግ በህጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በህግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ ጥፋተኛ ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ፤[152]

የሰ.መ.ቁ 165440

ጥር 27 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች:- እትመት አሠፋ
ጻውሎስ ኦርሾ
ፀሐይ መንክር
መላኩ ካሣዬ
እስቲበል አንዱዓለም፡፡

---

[151]በሰ/መ/ቁ 165440 (ጥር 27 ቀን 20112 ዓ.ም) ቅጽ 24

[152]በሰ/መ/ቁ 175121 (ታህሳስ 23 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24፣ በሰ/መ/ቁ 155789 (ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅጽ 23፣ በሰ/መ/ቁ 116405 (መጋቢት 02 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅጽ 20፣ በሰ/መ/ቁ 103452 (ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 17፤ በሰ/መ/ቁ 141677 (ሕደር 29 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅጽ 22፣የሰ/መ/ቁ 93234 (መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 93234 (መስከረም 27 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 17

አመልካች:- አየለ ሀፌቦ

ተጠሪዎች፡- የደቡብ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 06 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 09609 ግንቦት 06 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ግንቦት 07 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18276 ጥር 05 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 11028 ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዱና ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፤ ሌሎች አራት ግለሰቦች ደግሞ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በሌሎች ተከሳሾች ላይ በስር ፍ/ቤት ካቀረባቸው ክሶች ውስጥ አመልካችን የሚመለከተው 1ኛ እና 3ኛ ክስ ሲሆን ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤60/ለ እና 462/2/ሀ በመተላለፍ ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም ጌምቤራ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ደሪሎ ኒሪም የተባለ ግለሰብ በፍ/ቤት መያዣ ትዕዛዝ ለመያዝ የሄዱት የፖሊስ አባላት ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ካዋሉት በኋላ አመልካች እነዚህ ፖሊሶች ያለእኔ ዕውቅና የመጡ ስለሆነ ተጠርጣሪውን መያዝ እና መውሰድ አይችሉም በማለት ፖሊሶቹን ተባብረው በመያዝ እና በመምታት እስረኛውን አስመልጠዋል የሚል ሲሆን፡-

3ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤ 60/ለ እና 441 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ለፈጸመው ድርጊት የክፍሉን ፖሊሶች በሀይል እና በማስገደድ ስራቸውን እንዳይሰሩ በማድረጋቸው በፈጸሙት የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት አመልካችን እና የስር ተከሳሾችን ጥፋተኛ ሆነው ስላገኛቸው በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማስላት ለ1ኛ ክስ ድርጊቱ የተፈጸመው በቡድን እና በጸጥታ አስከባሪ አካላት ላይ በመሆኑ የጽኑ እሥራት አማራጭ ተወስዷል በማለት፤ የወንጀል ደረጃውን መካከለኛ በማለት በእርከን 15 ላይ በማሳረፍ፤ ምንም እንኳን አመልካች ያነሳሳ ቢሆንም በቀጥታ የፖሊሱን አካል ያልያዘ በመሆኑ መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከአስር ወር በመያዝ፤ ለ3ኛ ክስ የወንጀሉን ደረጃ መካከለኛ በማለት በእርከን 6 ላይ በማሳረፍ አንድ ዓመት እስራት የተወሰደ ቢሆንም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/ለ መሠረት አንድ ጽኑ እስራት እና አንድ ቀላል እሥራት ተደራርበው በተፈጸሙ ጊዜ ቀላል እስራት ታጥፎ መደመር ያለበት በመሆኑ ቀላል እስራቱን ወደ ስድስት ወር ጽኑ እስራት በመቀየር በድምሩ ሶስት ዓመት ከአራት ወር በመያዝ በእርከን 17 ላይ በማሳረፍ፤ በዓቃቤሕግ በኩል የቀረበውን የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ባለመቀበል እና ለአመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ቅጣቱን አቅሎ በእርከን 15 ላይ በማሳረፍ አመልካች በሁለት ዓመት ከአስራአንድ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር

ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ክሱን አላስተባበለም በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2 እና 441/2 ድንጋጌ ጥፋተኛ ብሎታል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ ደግሞ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ የአመልካች ድርጊት አፈጻጸም በጠለፋ የተጠረጠረን ግለሰብ ለማስመለጥ በሕግ አስከባሪ አካላት ላይ በቡድን የተፈጸመ ወንጀል በመሆኑ በከባድ ሊቀጣ ይገባል በማለት የወንጀሉን ደረጃ መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከስድስት ወር በመያዝ፤ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 የወንጀል ደረጃውን መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት በመያዝ፤ አመልካች ጥፋተኛ ለተባለበት ሕግ የተያዙትን መነሻ ቅጣቶች በመደመር አራት ዓመት ከስድስት ወር መነሻ ቅጣት በመያዝ እና በእርከን 19 ላይ በማሳረፍ፤ አመልካች የተያዘለት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በመያዝ ቅጣቱን አቅሎ በእርከን 17 ላይ በማሳረፍ በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ምስክሮች አመልካች ወንጀል የፈጸምኩ ስለመሆኔ አላስረዳም፤ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች የቀረበብኝን ክስ እንድከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ባቀረብኩት መከላከያ ማስረጃ የአቃቤሕግን ክስ አስተባብየ ሳለ ጥፋተኛ መባሌ አግባብ አይደለም፤ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ አልገለጸም፤ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብኩት አቤቱታ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔው አግባብ አይደለም የሚል ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ካጸና በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ባልተጠየቀ ዳኝነት የቅጣት ውሳኔውን አምስት ዓመት ከሁለት ወር ብሎ በመያዝ ከፍ በማድረግ ቀንሶ እንዳሻሻለ በማድረግ የሶስት ዓመት ከሶስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት አመልካች በሁለት ዓመት ከአስራአንድ ወር እስራት እንዲቀጣ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በስር ፍ/ቤት ከተወሰነበት ቅጣት በላይ በሦስት ዓመት ከሦስት ወር እንዲቀጣ በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ስላልቀረበ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካችን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ፤ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ፡-

1. የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረው 3ኛ ክስ አቀራረብ በወንጀል ስነስርዓት ሕጉ ስለክስ አቀራረብ በተቀመጡት ድንጋጌዎች አግባብ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም?

2. በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ ቀርቦ የነበረውን 3ኛ ክስን አስመልክቶ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በስር ተከሳሾች ላይ አቅርቦት የነበረው 3ኛ ክስ ይዘት ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤ 60/ለ እና 441 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ለፈጸመው ድርጊት የክፍሉን ፖሊሶች በሀይል እና በማስገደድ ስራቸውን እንዳይሰሩ በማድረጋቸው በፈጸሙት የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 441፡- ማንም ሰው፡-

ሀ/ አንድ የመንግስት ሰራተኛ የስራ ግዴታው የሆነውን ተግባ እንዳያከናውን በዛቻ፣ በማስገደድ ወይም በሀይል ድርጊት ያሰናከለ ወይም ይህን ግዴታውን እንዲያከናውን ወይም ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ ያስገደደ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ የመንግስት ሰራተኛን ወይም በስራው የሚረዳውን ሰው የደበደበ ወይም የሀይል ወይም የማስገደድ ድርጊት ወይም ማናቸውንም ሌላ የማስገደድ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፣

ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ንዑስ (ሀ) እና (ለ) ላይ የተቀመጡት የወንጀል ማቋቋሚያ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ መስፈርቶች መሆናቸውን ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው 3ኛ ክስ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 441 በመተላለፍ የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል ከማለት በቀር ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 ላይ በተለያየ ንዑስ ቁጥር ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ የትኛውን የንዑስ ቁጥር ድንጋጌ እንደተላለፉ በክሱ ላይ ለይቶ አላመለከተም፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍ/ቤትም አመልካችን በ3ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 መሠረት ጥፋተኛ ከማለት በቀር አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የድንጋጌውን ንዑስ ቁጥር ለይቶ አላመለከተም፤ በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም 3ኛን ክስ በሚመለከት አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 ጥፋተኛ ሲለው ይህን ያደረገበትን ምክንያት አልገለጸም፡፡

በመሠረቱ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ የሚቀርበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ በምን አኳኃን መቅረብ እንዳለበት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 111 እና 112 ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ በሚያቀርበው ክስ ላይ በዝርዝር እንዲገልጽ ከሚጠበቅበት መሰረታዊ ፍሬነገሮች ዉስጥ ተከሳሹ ተላልፎታል የተባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና ተከሳሹ የፈጸመዉ የወንጀል ተግባር በመሠረታዊነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ክሱ በዚህ አግባብ ተዘጋጅቶ እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተከሳሽ የሆነው ወገን ክሱን በአግባቡ ሊረዳ እና ክሱን ሊከላከል አይችልም፡፡ ይህም በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ የተጠበቀላቸውን የቀረበባቸውን ክስ የመረዳት እና የመከላከል መሠረታዊ መብት የሚጻረር ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ዓቃቤሕጉ ያቀረበው የክስ አቤቱታ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ያልቀረበ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በራሱ አነሳሽነት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 118 እና 119/1 ላይ በተገለጸው አግባብ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ እስካልተደረገ ጊዜ ድረስ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 3ኛውን ክስ በተመለከተ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 441 በመተላለፍ የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል ከማለት በቀር ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 ላይ በተለያየ ንዑስ ቁጥር ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ የትኛውን የንዑስ ቁጥር ድንጋጌ እንደተላለፉ በክሱ ላይ ለይቶ አላመለከተም፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው 3ኛ ክስ የተለያዩ ንዑስ አንቀጾች ያሉት እና በንዑስ አንቀጾቹ ላይ የተቀመጡት የወንጀል ማቋቋሚያ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ መስፈርቶች በመሆናቸው አመልካች ተላልፎታል የተባለው ንዑስ አንቀጽ ተለይቶ በክስ አቤቱታው ላይ እስካልተገለጸ ጊዜ ድረስ አመልካች የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ሊረዳ አይችልም፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ እስካልተደረገ ጊዜ ድረስ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ መነሻነት ጥፋተኛ ሊባል አይገባም፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረበው ክስ በሕጉ መሠረት የቀረበ አለመሆኑን ሲረዳው ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው አመልካች በተከሰሰበት ሕግ ከተቀመጡት ንዑስ አንቀጾች ውስጥ አመልካች የተላለፈውን የሕግ ድንጋጌ ሳይለይ በደፈናው አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 መሠረት ጥፋተኛ ማለቱ፤ ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይሕንኑ ሳያርም እና ምንም ዓይነት ምክንያት ሳይሰጥ አመልካችን በ3ኛው ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ዓቃቤሕግ በአመልካች ላይ ያቀረበው 1ኛ ክስ በሕጉ አግባብ የቀረበ እና አመልካች በክሱ ላይ የተመለከተውን ድርጊት ስለመፈጸሙ ተረጋግጦበት ክሱን ያልተካላከለ በመሆኑ አመልካች 1ኛውን ክስ በሚመለከት ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ 3ኛ ክስን በተመለከተ ያስተላለፉትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር 1ኛ ክስን በሚመለከት ብቻ ቅጣቱን እንደሚከተለው አስልተናል፡፡

በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በ1ኛ ክስ ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከስድስት ወር የተያዘለት በመሆኑ ይህ መነሻ በእርከን 12 ላይ የሚያርፍ ነው፤ በአመልካች ላይ ተቀባይነት ያገኘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፤ አመልካች በስር ፍ/ቤት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የተያዘለት በመሆኑ ቅጣቱ ሲቀል በእርከን 10 ላይ ያርፋል፤ በእርከን 10 ያለው ፍቅደ ስልጣን ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት ነው፡፡ በዚህ እርከን ስር አመልካችን ያርማል ሌሎቹንም ያስጠነቅቃል ብለን ያመንበትን አመልካች በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 09609 ግንቦት 06 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ግንቦት 07 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18276 ጥር 05 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 11028 ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔበወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል ፡፡

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ከ3ኛ ክስ በነጻ ተሰናብቷል፡፡

3. አመልካች ከ3ኛ ክስ በነጻ የተሰናበተ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤቶች ተላልሎ የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ አመልካች በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወነ መሆኑን አውቆ በተሻሻለው ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡

- በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ 18276 የሆነው መዝገብ በመጣበት አኳሃን ወደ መጣበት ይመለስ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

## 3.3 የወንጀል ክስ ወደሌላ ስፍራ ማዛወር[153]

- ክስ ወደ ሌላ ስፍራ ይዛወርልኝ አቤቱታን ጨምሮ ተከራካሪ ወገኖች ዳኞች እና የፍርድ ቤት አመራሮች በነፃነት እና ያለአድሎ የመዳኘት ግዴታቸውን አልተወጡም በማለት የሚያቀርቡት ማናቸውም አቤቱታ ህጋዊ መሰረት ያለው እና በተጨባጭ ማስረጃ ተረጋግጦ ሊቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ፤

የሰ.መ.ቁ 189472

ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አሸብር አውዴ

ተጠሪ፡- በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የወላይታ ምድብ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው። በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 18 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 31815 መስከረም 06 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች ያቀረበውን የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 31696 ታሕሳስ 01 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።

ጉዳዩ የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው። የአሁን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት በፍርድ ቤት አስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ የፍርድ ቤቱን ስም እና ዝናን የሚያጎድፍ እና ዛቻ መሰል አስተያየት እንደተጻፈ እና የእጅ ጽሑፉ ከአመልካች ጋር እንደሚመሳሰል በመግለጽ በቀን 06/11/2010 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ቢሮ ቀርቤ ምላሽ እንድሰጥ ትዕዛዝ ሰጥቶኛል፤ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ላይ በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዲስፕሊን ክስ አቅርቤአለሁ፤ በዚህም ምክንያት የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ዳኞች እና ሠራተኞችም በማሰባሰብ በአስተያየት መስጫ መዝገቡ ላይ እኔ እንደጻፍኩ ገልጸዋል፤ ስማቸው በአቤቱታው ላይ የተጠቀሰው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሁለት ዳኞች ተከሳሽ በሆንኩበት የፍ.መ.ቁ 30379 በሆነው መዝገብ ተከሳሺን ለመጥቀም ከስነ-ስርዓት ውጪ ክርክሩን በመምራታቸው ምክንያት በዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ አቅርቤባቸዋለሁ፤ የመ.ቁ 32160፤ 33749 እና 30379 በሆኑት

[153]በሰ/መ/ቁ 189472 (ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅጽ 25

መዛግብት የተፈጸመብኝን በደል ይግባኝ ጠይቄ ፍትሕ አግኝቻለሁ፤ በመ.ቁ 36642 ለቀረበብኝ የቼክ ወንጀል መቃወሚያ ያቀረብኩ ቢሆንም የዲስፕሊን ክስ ያቀረብኩበት የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ተሰይሞ ሕግን ባልተከተለ ሁኔታ መቃወሚያየን ውድቅ አድርጓል፤ አመልካች በቂም እና በጥላቻ በተደጋጋሚ የፍትሕ መዛባት የደረሰብኝ እና በተጠቀሱት ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ያለአድሎ የቀረበውን ክስ ሊሰማ የማይችል በመሆኑ ክሱ ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ተዛውሮ ይታይልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ፕሬዝደንቱ ጉዳዩን ለማጣራት አስተዳደራዊ ስራ ሰርቷል፤ ፕሬዝደንቱን በሚመለከት ለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የደረሰ ክስ የለም፤ ሁለቱ ዳኞች የዲስፕሊን ክስ ቢቀርብባቸውም የመጨረሻ ውሳኔ አልተሰጠም፤ አንደኛው ዳኛ ከችሎት እንዲነሱ አቤቱታ ቀርቦ እንዲነሱ ተደርጓል፤ ሌላኛዋ ዳኛ ደግሞ የፍትሐብሔር ዳኛ በመሆን ዓመቱን ሙሉ የጨረሱ እና አሁንም እዚያው ያሉ ናቸው፤ ጉዳዮችን በይግባኝ ማሻር ለክስ ይዛወር ምክንያት አይሆንም፤ ፍርድ ቤቱ ከአስራ ሁለት በላይ ዳኞች ያሉበት እና በአሁኑ ጊዜ ጉዳዩን እያዩ ያሉት ዳኞች ከተጠቀሱት ዳኞች ውጪ በመሆናቸው አመልካች ያቀረቡት የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር መርምሮ ፕሬዝደንቱ በሕግ በተሰጠው ስልጣን አስተዳደራዊ ተግባር መፈጸሙ ለክስ ይዛወርልኝ ምክንያትነት አይሆንም፤ ለክልሉ ዳኞች አስተዳድ ጉባኤ ክስ አቅርቤአለሁ በማለት ቀሪ ደብዳቤ መቅረቡ በእርግጥም አቤቱታው መድረሱን የሚያሳይ አይደለም፤ ደርሷል ቢባል እንኳን ክሱ ተቀባይነት አግኝቶ መልስ እንዲሰጡ የተደረገበት ሁኔታ የለም፤ በተቋሙ ባልደረቦችም በኩል በክፉ ዓይን እየታየሁ ነው በማለት የቀረበውም የራስ ጥርጣሬ ከሚሆን በቀር በምክንያትነት ሊወሰድ አይችልም፤ በዳኞቹ ላይ ለዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ የቀረበባቸው ቢሆንም ጉዳዩ የመጨረሻ ዕልባት ስለማግኘቱ የቀረበ ማስረጃ የለም፤ አንደኛው ዳኛ ክስ የቀረበባቸው በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩን እንዳያዩ መደረጉ በችሎቱ ሂደት ተመዝግቦ እያለ ጉዳዩን በማያዩ ዳኛ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ መቅረቡ እንዲሁም በስ ተጠቃሿ ሌላኛዋ ዳኛም ጉዳዩን እያዩ ባለመሆኑ ጥያቄው ሕግን የተከተለ አይደለም፤ በይግባኝ ሥርዓት ጉዳዮች እንዲሻሩ፤ እንዲሻሻሉ ወይም እንዲጸኑ ማድረግ ሕጋዊ ሥርዓት ሲሆን ክርክሩ ደረጃውን ጠብቆ በይግባኝ ወይም በሰበር ስርዓት የሚቀጥል እና ተሻረ የተባለውም ጉዳይ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶት የሚሻርበት ወይም የሚሻሻልበት ሥርዓቶች በመሆናቸው ለክስ ይዛወርልኝ ምክንያት መሆን አይችሉም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ይህም ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ከፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ዛቻ እና ማስፈራራት እንደደረሰብኝ እና ከፍተኛ ጥላቻ እንዲያድርብኝ ማስደረጉን፤ ለክልሉ የሕዝብ ምክር ቤት እና ለዞኑ ምክር ቤት አቤቱታ ማቅረቤን እና በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ ማቅረቤን የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቤአለሁ፤ በተለያዩ መዝገቦች ከሙግት ስነ ስርዓት ውጪ ክርክር በመምራታቸው በአምስት የፍርድ ቤቱ ዳኞች ላይ የዲስፕሊን ክስ አቅርቤአለሁ፤ በተከሰስኩበት የቼክ ወንጀል ፕሬዝደንቱ ሆን ብሎ የመሃል ዳኛ ሆኖ በመሰየም በዲስፕሊን ከከሰስኳቸው ዳኞች ጋር በመሆን መቃወሚያዬን ከሕግ ውጪ ውድቅ ማድረጉን፤ ክሱ የሚታይበት ፕሬዝደንት ዘመድ በሆነች ግለሰብ ላይ ያቀረብኩባትን የጉዳት ካሣና ኪሣራ ክስ አመልካች የጎፋ ብሔር ተወላጅ በመሆኔ ምክንያት ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው፤ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቤ በሰ.መ.ቁ 164842 ጥቅምት 27 ቀ 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ በክርክር አመራር ረገድ የሕግ ስሕተት መፈጸሙን እና የአመልካችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጋፋ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔውን ያረመ መሆኑን፤ የክስ ይዛወርልኝ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የግል ተበዳይ የተባለው የዞኑ ጠቅላይ ዓቃቤሕግ መምሪያ ሃላፊ አጎቱ በመሆኑ እና በአካባቢው በሀብቱ እና በዘመዶቹ ብዛት ስሜን በማጥፋት መጠቋቆሚያ ያደረገኝ መሆኑን

የሚያሳዩ ማስረጃዎች ባቀረብኩበት ሁኔታ አመልካች ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የስር ጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ባደረሰብኝ በደል በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዲስፕሊን ክስ ያቀረብኩ በመሆኑ በገለልተኝነት ጉዳዩን ፍርድ ቤቱ ሊመለከት አይችልም በማለት ያቀረበውን የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ አቤቱታ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ያቀረበው የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ በጠቅላይ ፍርድ ቱውድቅ ተደርጎበታል፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 106/2 መሠረት በግልጽ እንደተደነገገው እንዲዚህ ዓይነት ትዕዛዞች ይግባኝ የማይባልባቸው በመሆኑ አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ የወንጀል ሥነ ሥርዓቱን ያልተከተለ ነው፤ በጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ በተጻፈው የዛቻና የማስፈራሪያ ቃል አንጻር የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ይህን ጽሁፍ ጽፈዋል ተብለው ከተጠቆሙ ሰዎች ውስጥ አመልካችን ቢሮአቸው ጠርተው በማወያየታቸው እና የአስተዳደር ስራ በመስራታቸው ብቻ ለምን ተጠራሁ በሚል በሀሰት አቤቱታ ከማቅረባቸው በቀር አመልካች እንደሚሉት በፕሬዝደንቱ ላይ የቀረበ የዲስፕሊን ክስ የለም፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ  በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ማዛወር / change of venue / ትርጉም እንደሚከተለው አስቀምጦታል፡፡ Change of venue is the removal of a suit began in one country or district to another country or district for trial, though the term is also sometimes applied to the removal of a suit from one court to another court of the same country or district.

በእኛም ሐገር ይህ ጽንስ ሐሳብ በአንድ ሥፍራ የተጀመረን ክስ ወደ ሌላ ስፍራ ሄዶ እንዲታይ ማድረግ ወይም በአንድ ፍርድ ቤት የተጀመረን ክስ በዚያው ሥፍራ ላይ ወደሚገኝ ሌላ ፍርድ ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ማድረግ ማለት እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዶበታል፡፡  በወንጀል ጉዳይ የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ የሚቀርብበት ሥርዓት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 106 ላይ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓትን እና የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/1968 ተሻሽሏል፡፡ በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ መሠረት በወንጀል ጉዳይ ክስ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር መጠየቅ የሚቻለው ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ዓቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መሥማት የጀመረው የበታች ፍርድ ቤት በማመልከቻ የቀረበለትን ጉዳይ ያለአድሎ በትክክል ለመስማት የማይችል መሆኑን ወይም ጉዳዩ ዘወትር የማያጋጥም አስቸጋሪ የሕግ ክርክር የሚያስነሳ መስሎ መታየቱን ወይም በድንጋጌው አግባብ ትዕዛዝ ቢሰጥ ለሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም ለምስክሮች ምቹ መሆኑን ወይም ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ቢሰጥ በአጭር ጊዜ ትክክለኛ ፍርድ ለማስገኘት የሚያስችል ወይም ትዕዛዝ እንዲሰጥ የዚህ ሕግ ድንጋጌ የሚጠይቅ መሆኑን ሲያመለክት ነው፡፡

ከክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጽንስ ሐሳብ እና ከላይ ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ ወይም በዚያው ሥፍራ ላይ ወደሚገኝ ሌላ ፍርድ ቤት ሊዛወር የሚችለው ክሱ እየታየ ባለበት

ሥፍራ ወይም ፍርድ ቤት ውስጥ ጉዳዩን ለማየት የሚችል ሥልጣን ያለው ሌላ ችሎት የሌለ በሆነ ጊዜ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር ሲጠይቁ ያቀረቧቸው ምክንያቶች በሙሉ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ያለአድሎ ሊያይልኝ አይችልም በሚል የቀረቡ በመሆኑ የአመልካች ዋነኛ የክርክር አውድ የሚያጠነጥነው ከፍርድ ቤቱ ገለልተኝነት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም በእርግጥም አመልካች ያቀረቧቸው ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ያለአድሎ እንዳያይ የሚያደርጉ እና ክስ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር የሚያስችሉ ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች ናቸው? ወይስ አይደሉም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ ነጻ የዳኝነት አካል የተቋቋመ ስለመሆኑ፤ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግስት አካል፤ ከማናቸውም ባለስልጣንም ሆነ ከማናቸውም ሌላ ተጽዕኖ ነጻ መሆኑን፤ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ሊያከናውኑ እንደሚገባ እና ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሊመሩ እንደማይገባ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78 እና 79 ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም የዳኝነት ሥርዓቱ መሠረታዊ መርህ በመሆኑ ዳኞች እና የፍርድ ቤት አመራሮች በላቀ ሥነ-ምግባር እና በጥብቅ ሊተገበሩት ይገባል፡፡ ይህን ተላልፈው በተገኙ ጊዜም አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ተጠያቂነት ያለባቸው ስለመሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በሕገ-መንግስቱ በተቋቋመው ነጻ የዳኝነት አካል ፊት በመቅረብ ፍትሕ የማግኘት መብታቸው የተረጋገጠላቸው ዜጎች ጉዳያቸው ውሳኔ ከማግኘቱ በፊትም ሆነ በኋላ ይህ መብታቸው በአግባቡ እንዲከበር ለማድረግ የሚያስችሉ መፍትሔዎች በተለያዩ ሕጎች ላይ ተቀምጠውላቸዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ገለልተኛ ያልሆነው ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ መጠየቅ፤ የክስ ወደ ሌላ ስፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄን ማቅረብ እና ዳኛው የሰጠው ፍርድ በይግባኝ እና በሰበር ስርዓት ማሳረም የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ስለሆነም በነጻነት እና ያለ አድሎ የመዳኘት ሕገ-መንግስታዊ ግዴታቸውን አክብረው ሥራቸውን ይከውናሉ ተብሎ ግምት የሚወሰድባቸው ዳኞች እና የፍርድ ቤት አመራሮች ይህን ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ አልተወጡም በማለት ተከራካሪ ወገኖች መብታቸውን ለማስከበር የሚያቀርቡት ማናቸውም አቤቱታ ሕጋዊ መሠረት ያለው እና በተጨባጭ ማስረጃ የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ላቀረቡት የክሥ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄ ያቀረቧቸው የመጀመሪያዎቹ ምክንያቶች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት በፍርድ ቤት አስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ የፍርድ ቤቱን ስም እና ዝናን የሚያጎድፍ እና ዛቻ መሰል አስተያየት እንደተጻፈ እና የእጅ ጽሑፉ ከአመልካች ጋር እንደሚመሳሰል በመግለጽ ቢሮ ቀርቤ ምላሽ እንድሰጥ ትዕዛዝ በመስጠቱ የዲስፕሊን ክስ አቅርቤአለሁ፤ ይህንኑ ተከትሎ የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ዳኞች እና ሠራተኞችም በማሰባሰብ በአስተያየት መስጫ መዝገቡ ላይ እኔ እንደጻፍኩ በመግለጽ በጥላቻ እንድታይ አድርገዋል፤ ስማቸው በአቤቱታው ላይ የተጠቀሱት ሁለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች ተከሳሽ በሆንኩበት የፍ.መ.ቁ 30379 በሆነው መዝገብ ተከሳሿን ለመጥቀም ከስነ-ስርዓት ውጪ ክርክሩን በመምራታቸው በዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ አቅርቤባቸዋለሁ፤ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያዩ መዝገቦች ባደረግኩት ክርክር አላግባብ የተሰጠብኝን ውሳኔ በይግባኝ አሳርሜያለሁ፤ በመ.ቁ 36642 ለቀረበብኝ የቼክ ወንጀል መቃወሚያ ያቀረብኩ ቢሆንም የዲስፕሊን ክስ ያቀረብኩበት የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ተሰይሞ ሕግን ባልተከተለ ሁኔታ መቃወሚያዬን ውድቅ አድርጓል፤ ተጠቃሾቹ ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ያለአድሎ ሊያይ እንደማይችል ማሳያ ናቸው በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ፍርድ ቤቱን በበላይነት የሚመራ በመሆኑ ራሱም ሆነ የፍርድ ቤቱ ዳኞች ከማናቸውም አካል ተጽእኖ ነጻ ሆነው ጉዳዮችን ያለአድሎ እንዲያዩ የማድረግ ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ ያለበት ሲሆን የፍርድ ቤቱንም ስም እና ክብር የመጠበቅ እና የማስጠበቅ ሀላፊነት አለበት፡፡ ይህንኑ ሲያደርግም ሕግን እስካልተላለፈ ድረስ ተቋሙን በሚመለከት የሚቀርቡለትን

ማናቸውንም መረጃዎች እና ማስረጃዎች እንደ አግባብነታቸው ሊጠቀምባቸው እና ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ያላቸውን አካላት ሊያነጋግር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት በፍርድ ቤቱ አስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ የፍርድ ቤቱን ስም እና ዝና የሚያጎድፍ ጽሑፍ በማየቱ ምክንያት አስተያየቱን ጽፏል ብሎ የገመተውን አመልካች ምላሽ እንዲሰጥበት ደብዳቤ መጻፉ ብቻውን አስተዳደራዊ ስራውን ሰርቷል ከሚያስብል በቀር የአመልካች ጉዳይ በነጻነት እና ያለአድሎ እንዳይታይ የማድረግ ውጤት አይኖረውም፡፡ ሆኖም የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ከዚህ አልፎ አመልካች የፍርድ ቤቱን ስም እና ዝና የሚያጎድፍ ጽሑፍ ጽፏል በሚል ምክንያት በፍርድ ቤቱ ዳኞች ላይ ተጽእኖ በመፍጠር የአመልካች ጉዳይ በገለልተኝነት እንዳይታይ የሚያደርግ ተግባር የፈጸመ ስለመሆኑ በተጨባጭ ማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ ክስ ወደ ሌላ ስፍራ ይዛወርልኝ ብሎ ለመጠየቅ የሚያስችል በቂ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደተመለከትነው አመልካች የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ፈጽሙት ያለውን ድርጊት ከማመላከት በቀር ፕሬዝደንቱ አቤቱታ ቀርቦባቸው መልስ ስለመስጠታቸውም ሆነ በቀረበው የዲስፕሊን ክስ መሠረት የተላለፈባቸው ውሳኔ ስለመኖሩ በመግለጽ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡

አመልካች ስማቸው በአቤቱታው ላይ የተጠቀሱት የፍርድ ቤቱ ዳኞች ተከሳሽ በሆንኩበት የፍ.መ.ቁ 30379 በሆነው መዝገብ ተከሳሿን ለመጥቀም ከስነ-ስርዓት ውጪ ክርክሩን በመምራታቸው በዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ አቅርቤባቸዋለሁ በማለት የተከራከሩ ሲሆን በስም ተጠቃሾቹ ዳኞች ላይ ለዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ የቀረበባቸው ቢሆንም ጉዳዩ የመጨረሻ ዕልባት ማግኘቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፤ አንደኛው ዳኛ ክስ የቀረበባቸው በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩን እንዳያዩ የተደረገ መሆኑ እና ሌላኛዋም ዳኛ ጉዳዩን የማያዩ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም ይህ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ጉዳያቸውን በማየት ላይ የሌሉ ዳኞች ጉዳዩን በገለልተኝነት ሊያዩ አይችሉም በሚል ያቀረቡት የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች በመ.ቁ 36642 ለቀረበብኝ የቼክ ወንጀል ክስ መቃወሚያ ያቀረብኩ ቢሆንም የዲስፕሊን ክስ ያቀረብኩበት የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ተሰይሞ ሕግን ባልተከተለ ሁኔታ መቃወሚያዬን ውድቅ አድርጓል በማለት ያቀረቡት ምክንያትም ፕሬዝደንቱ አመልካችን ለመጉዳት ብለው ከሕግ ውጪ መቃወሚያውን ውድቅ ስለማድረጋቸው በማስረጃ አለማረጋገጣቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በመዝገቡ ላይ ተሰየሙ የተባሉት ፕሬዝደንት ገለልተኛ ሆነው ጉዳዩን አያዩም የሚሉ ከሆነ ፕሬዝደንቱ ከችሎት እንዲነሱ አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ከሚሆን በቀር ክስ ወደ ሌላ ስፍራ እንዲዛወር ለመጠየቅ የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም፡፡

ከላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወርላቸው ለመጠየቅ የሰጡት ሌላው ምክንያት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዘመድ ላይ ያቀረብኩት ክስ አላግባብ ውድቅ ተደርጎ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች አቤቱታ አቅርቤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 164842 ጥቅምት 27 ቀ 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ በክርክር አመራር ረገድ የሕግ ስሕተት መፈጸሙን እና የአመልካችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጋፋ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔውን አርሟል፤ ይህም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በገለልተኝነት እንደማያይልኝ ማሳያ ነው የሚል ነው፡፡

ስለይግባኝ ሥርዓት በተመለከተው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ስድስተኛ መጽሐፍ ቁጥር 320 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በተለይም ከቁጥር 337፤ 341፤ 343 እና 348 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ የተጠየቀበት ፍርድ ሊጸና፤ ሊሻሻል፤ ሊለወጥ፤ ሊሻር ወይም ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን በማለት ፍርዱን ለሰጠው ችሎት ሊመለስለት እንደሚችል ነው፡፡

አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 164842 አቤቱታ አቅርበው ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው ውሳኔ ይዘት አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ፕሬዝደንት ዘመድ ናቸው የሚልዋቸው የመዝገቡ 1ኛ ተጠሪ ሽንት ቤቱን ማፍረሳቸው ተረጋግጦ የፈረሰውን ለመገንባት የሚያስከትለውን ወጪ እንዲከፍሉ እና የተዘጋውን ሽንት ቤት እንዲከፍቱ ተወስኖ እያለና ውሳኔው ስለመሻሩ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ሳይቀርብ አመልካች በዚህ ምክንያት የተቋረጠውን ገቢ ሲጠይቁ ሀላፊነትን የሚያሳይ የጸና ፍርድ ሕጋዊ ውጤት ምንድነው የሚለውን ሳይመለከቱ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ ሀላፊ አይደሉም ሲሉ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢ አይደለም፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች በክርክር አመራር ረገድ የፈጸሙት ስሕተት የአመልካች ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጋፋ ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች እና በመዝገቡ 1ኛ ተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር በመቀጠል ጭብጥ መስርቶ አከራክሮ እንዲወስን በሚል የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ ይህም በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ ስለ ይግባኝ ሥርዓት በተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ክርክር ተደርጎ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ አመልካች እንደሚሉት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጉዳይ ገለልተኛ ሆኖ ባለማየቱ ምክንያት የተሰጠ ውሳኔ ስለመሆኑ ተገልጾ ውሳኔው የተሻረ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንኑ መሠረት በማድረግ ያቀረቡት የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው መልስ ፍርድ ቤቱ ከአስራ ሁለት በላይ ዳኞች ያሉበት እና በአሁኑ ጊዜ ጉዳዩን እያዩ ያሉት ዳኞች ከተጠቀሱት ዳኞች ውጪ ናቸው በማለት ያቀረበው ክርክር በአመልካች በኩል ያልተካደ ከመሆኑ አኳያ አመልካች ጉዳዬ በገለልተኝት ሊታይ አይችልም በማለት ያቀረቡት ምክንያት ተቀባይነት አለው ቢባል እንኳን ጉዳዩን የሚያዩት ዳኞች ከችሎት እንዲነሱ በሚቀርብ አቤቱታ መነሻነት ክሱ በዚያው ፍርድ ቤት ውስጥ በሚገኝ ሌላ ችሎት ላይ በሚያስችሉ ዳኞች እንዲታይ ከሚደረግ በቀር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ ያሉት ዳኞች በሙሉ የአመልካችን ጉዳይ በገለልተኝነት እንደማያዩ ተቆጥሮ ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር ማድረግ ፍርድ ቤቶች በሕገ-መንግስቱ የተጣለባቸውን ግዴታ አክብረው ነጻ እና ገለልተኛ ሆነው ጉዳዮችን ይዳኛሉ በሚል በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን አመኔታ በእጅጉ የሚሸረሽር በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ በማለት ላቀረቡት አቤቱታ የጠቀስዋቸው ምክንያቶች ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው እና በተጨባጭ ማስረጃ ያልተረጋገጡ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 31815 መስከረም 06 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 31696 ታሕሳስ 01 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ጥር 21 ቀን 2012 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የልዩነት ሃሳብ

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 2 ስር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ በሌሎች ባልደረቦቼ በሚከተለው ምክንያት በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

አመልካች ክሱ ወደ ሌላ ስፍራ ተዛውሮ እንዲታይላቸው ያቀረቧቸው ምክንያቶች ክሱን ወደ ሌላ ስፍራ ለማዛወር የሚያስችል በቂ ምክንያቶች ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

ህገ መንግስቱ ለፍ/ቤቶች እና ለዳኞች ካጐናፀፈው መብት አንዱ እና ዋነኛው ነፃ ፍ/ቤት ገለልተኛ ዳኝነትን ስለመሆኑ የድንጋጌው አንቀት 78 እና 79 ይደነግጋሉ፡፡ በዚህ መሠረት አንድ ጉዳይ የቀረበለት ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ በሚያይበት ጊዜ ከማንኛውም ተጽእኖ ነፃ እና ተገልተኛ ሆኖ መዳኘነት ይገባዋል፡፡ የዳኝነት ነፃነትና ገለልተኝነት ደግሞ ለዳኛው ብቻ የተሰጠ መብት ሳይሆን ተገልጋዩም ጭምር በገለልተኛ ዳኛ እና በነፃ ፍ/ቤት የመዳኘት መብት አለው፡፡

ክስን ወደ ሌላ ሥፍራ ስለማዛወር የሚደነግገው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 106 ነገሩ ከመሰማቱ በፊት0ቃቤ ሕጉ ወይም ተከሣሹ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ ይደደነግጋል፡፡ በዚሁ መሠረት አቤቱታ የሚያቀርበው 0ቃቤ ህግ ወይም ተከሣሹ ክሱ ወደ ሌላ ስፍራ የሚዛወርበትን ምክንያት ዘርዝሮ ማቅረብ የሚገባው ሲሆን ከምክንያቶቹ አነዱ በድንጋጌው ፊደል “ሀ” ስር “ የበታች ፍ/ቤት ይህንን ነገር ያለአድሎ በትክክል ለመስማት የማይችል መሆኑን” ነው፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከላይ እንደተገለፀው የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በገለልተኝነት አያይልኝም ሲሉ ምክንያቶቹን በዝርዝር ገልፀዋል፡፡ ማሳያዎች ናቸው ያሏቸውን ማስረጃዎችንም ከአቤቱታቸው ጋር ለፍ/ቤቱ አቅርበዋል፡፡

አመልካች ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ ተዛውሮ እንዲታይላቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡበት ምክንያት ከላይ እንደተገለፀው የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ኘሬዚዳንት በአስተያየት መስጫ ላይ የፍ/ቤቱን ስምና ዝና የሚያጐድጽ ነገር ጽፈሃል በማለት በደብዳቤ መፃፋቸውን፣በቢሮ አስጠርተው ዛቻ እና ማስፈራሪያ ያደረሱባቸው መሆኑን፣ዳኞች በተሰበሰቡበት የተናገሯቸው መሆኑን እንዲሁም በሌላ መዝገብ ከአመልካች ጋር ተከራካሪ የሆኑት ግለሰብ የኘሬዚዳንቱ ዘመንድ መሆናቸውን፣ በተለያዩ መዛግብት ላይ አግባብነት የሌለው የክርክር አመራር ግድፈት በመጸፀም የወሰኑባቸው መሆኑን፣ ይህ ውሣኔም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሻሩን፣ኘሬዚዳንቱ በፍ/ብሄር ክርክር በመሐል ዳኝነት ተሰኝመው ማስረጃ ለአመልካች እንዳይቀርብ ትዕዛዝ የሰጡ መሆኑን፣ እና ሌሎች ዝርዝር ምክንያቶችን በማንሳት የፍ/ቤቱን ኘሬዚዳንት እና ሌሎች ዳኞችን በዲስኘሊን ከሰው ጉዳዩ በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ እየታየ ያለ መሆኑን የክልሉ መክር ቤትም ይህንን ጉዳይ እንደሚያውቅ በመጥቀስ በዚህ ፍ/ቤት የሚታየው የወንጀል ጉዳይ በገለልተኝነት ይታይልኛል ብዬ አልገምትም በማለት የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ማቅረባቸውን ከቀረበው አቤቱታ እና በስር ፍ/ቤት ከተሰጠው ትዕዛዝ ግልባጭ ላይ ለመመልከት ተችሏል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥ/ሥ/ ድንጋጌ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ማለትም 0ቃቤ ሕግ ወይም ተከሣሹ የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ሊያቀርብ የሚገባው በድንጋጌው ሥር የተዘረዘሩ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን፣ በገለልተኝነት ጉዳዩ ይታይልኛል ብሎ የማያምን ከሆነ ይህን አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡

አመልካች በአቤቱታቸው የዘረዘሯቸው ምክንያቶችን በጥቅሉ ስናይ የቀረበው ጉዳይ በገለልተኝነት አይታይልኝም በሚል የአመልካችን ህሊና የሚረብሽ ነገር የተፈጠረ መሆኑን መገዘብ ያስችላል፡፡ አመልካች ከላይ የዘረዘሯቸው ድርጊቶች ተፈጽመውብኛል በመሆኑም ነፃ እና ገለልተኛ ዳኝነት አገኛለሁ ብዬ እምነት የለኝም በማለት የዘረዘሯቸው የኘሬዚዳንቱ በፍትሐብሄር ጉዳይ የመሐል ዳኛ ሆነው ተሰይመው የአመልካችን የማስረጃ ይቅረብልኝ ጥያቄው ውድቅ ስለማድረጋቸው፣ የፍ/ብ/ክርክር

ላይ ከአመልካች ጋር ተከራካሪ የሆኑት ግለሰብ የኘሬዚዳንቱ ዘመድ ስለመሆናቸው፣በአመልካች ላይ በኘሬዚዳንቱ ስለደረሰባቸው ዛቻና ማስፈራራት፣5 ዳኞች እና ኘሬዚዳንቱ በዲስኘሊን ስለመከሰሳቸው፣ እና ሌሎች ምክንያቶች ተጠሪ አልተፈፀሙም ብሎ እየተከራከረ ሳይሆን የዲስኘሊን ክሱ ውሣኔ የተሰጠበት አይደለም፣ በሰበር የስር ፍ/ቤት ውሣኔን ማሻርም ለክስ መዛወር ምክንያት ሊሆን አይገባም በሚል ነው፡፡

የስር ፍ/ቤትም የአመልካች አቤቱታ ሳይቀበል የቀረበት ምክንያት አመልካች ያነሷቸውን ዝርዝር ምክንያቶች ያልተፈፀሙ ስለመሆናቸው አረጋግጦ ሳይሆን በደፈናው በፍ/ቤቱ ብዙ ዳኞች ያሉ መሆኑን፣ እንዲሁም በሰበር ውሣኔ የተሻረ መሆኑ ችሎት መዛወር ጥያቄን የማያስነሳ ስለመሆኑ፣ የዲስኘሊን ክሱ ያልደረሰ መሆኑን በማንሳት ነው፡፡ ሆኖም ግን የአመልካች አቤቱታ በፍ/ቤቱ ያሉት ዳኞች በሙሉ በተሰበሰቡበት በፍ/ቤቱ ኘሬዚዳንት ፍ/ቤቱ ላይ ችግር እየፈጠሩ ያሉት ሰው አመልካች መሆናቸውን በመንገር ዛቻና ማስፈራራት የደረሰባቸው መሆኑን ጭምር በመግለጽ በመሆኑ ቀሪ ዳኞችም ጉዳዩን ቢያዩት ገለልተኛ ሆነው ያዩልኛል የሚል እምነት የሌላቸው መሆኑን የምገነዘብ ሲሆን በሌላ በኩል እዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የተወሰነው መዝገብ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻሩ ብቻ ሳይሆን ክርክርን በአግባቡ ያለመምራት ችግር ያለበትና በተለያዩ መዛግብት የፍ/ቤቱ ኘሬዚዳንት ዘመድ ናቸው ከተባሉ ግለሰብ ጋር ክርክር አድርጌ ተወስኖብኛል በማለት አመልካች የሚገልፁትን ግለሰብን በተጠሪነት የያዘ መሆኑን ስንመለከት  የአመልካችን አቤቱታ የሚያጠናክር መሆኑን እንጂ እንደተባለውም የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶችን ጉዳይ አይተው የሚወስኑበትን ሥልጣን የላቸው ከሚልና በሰበር መሻሩ ብቻውን የችሎት ይዛወርልኝ ጥያቄን ለመጠየቅ መስፈርት ነው የሚል እምነት እኔም የለኝም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት የህገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች አንፃር ተከራካሪ የሆነ ሰው ጉዳዩ የሚታይበት ፍ/ቤት ነፃና ገለልተኝነትን የማረጋገጥ እና በነፃ ፍ/ቤት በገለልተኛ ዳኝነት የመዳኘት መብት ያለው ከመሆኑ አንፃር አመልካች በእሳቸው ላይ በዐቃቤ ሕግ የቀረበባቸውን የወንጀል ክስ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት እና ዳኞች ከተጽዕኖ የፀዳ ፍትህ አገኛለው ብለው ለማመን የህሊና ፈተና የገጠማቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ያቀረቡት አቤቱታ በቂና አሳማኝ ሆኖ እያለ አቤቱታው የቀረበለት ፍ/ቤት አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤትን ስህተት ሳያርም ማለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል እምነት ስላለኝ አብላጫው ድምጽ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በሚል ክሱ ወደ ሌላ ስፍራ ተዛውሮ መታየት ይገባዋል ብዬ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

## 3.4 የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ[154]

- ተከሳሽ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርባቸው ስለሚችላቸው መከራከሪያዎች ተከሳሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት የሚያቀርባቸው መቃወሚያዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130 ላይ የተመለከተቱት ጉዳዬች ጋር ብቻ በተገናኘ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣
- ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት የወንጀል  ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ ካልተደነገገ  በስተቀር ሊቀጣ የማይችልና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተፈፃሚ በነበረው ህግ ከተመለከተው የቅጣት ጣሪያ በላይ ሊቀጣ የማይችል ስለመሆኑ፣

[154]በሰ/መ/ቁ 73514 (ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅጽ 14

* የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑና ዳኞች ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ክስ የቀረበበት ድርጊት ወንጀል ስለመሆኑ የሚደነግገው ህግ ፀንቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን ከተረዱ በማናቸውም ጊዜ አንስተው ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉ ስለመሆኑ፣
* ፍ/ቤቶች በዐ/ህግ የቀረበ የወንጀል ክስ በህገ-መንግስቱና በወንጀል ህጉ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር የተቀመጡ መርሆዎችና ድንጋጌዎችን የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ፣[155]

የሰ/መ/ቁ. 73514

ህዳር 6 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኰንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡-ተስፋዬ ጡምሮ

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን - ዐቃቤ ህግ ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡

ተጠሪ አመልካች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ ቁጥር 419 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ፣ ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ ሰርቷል፡፡ ተከሳሽ የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ በወር ብር 420 (አራት መቶ ሃያ ብር) እና ብር 530 (አምስት መቶ ሰላሳ ብር) እየተከፈለው የቆየ ቢሆንም፣ በመንግስት ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሲያገኝ ከነበረው ገቢ ጋር የማይመጣጠን ብር 1,167,637.60 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከስልሳ ሳንቲም) በዳሽን ባንክ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በወጋገን ባንክና በንብ ባንክ ሲያንቀሳቅስ በመቆየቱና የሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ. 2-78716 የቤት አውቶሞቢል መኪና በስሙ በመገኘቱ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ የመገኘት ወንጀል ፈፅሟል በማለት ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ አመልካች የክሱ ግልባጭ ከደረሰውና ከተነበበለት በኋላ የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ለማስረዳት አመልካች ሲያንቀሳቅስ ስለነበረው ሒሳብ የሚያሳዩ ከተለያዩ ባንኮች የተሰጠውን የሂሳብ ማመዛዘኛ የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ አመልካች በተጠሪ የቀረበበትን የሰነድ ማስረጃ መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብል የስር ፍ/ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሾጌ የሲሚንቶ ውጤቶች የሁለገብ የህብረት ስራ ማህበር የሚባል በህግ የተመዘገበና ዕውቅና ያለው ድርጅት የሚሰጣቸው የሲሚንቶ ውጤቶች ዋጋ በመቀበል በስሙ

---

[155]በሰ/መ/ቁ 237473 (መጋቢት 25 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ ሰ/መ/ቁ 243034 (ጥቅምት 6 ቀን 2016ዓ.ም)

ሒሳብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎች ናቸው በማለት የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በስሙ በተለያዩ ባንኮች ሲያንቀሳቅስ የነበረው በወንጀል ክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብና መኪና ምንጩ ህጋዊ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች አጠራጣሪ ናቸው በማለት አመልካች በ1997 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ይዞ የተገኘ ጥፋተኛ ነው ብሎ፣ አመልካች በሁለት ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 66,660 መቀጮ እንዲቀጣ፡፡ መኪናውና በባንክ የተገኘው ብር 27,330 (ሃያ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ብር) እንዲወረሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አቅርቦ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ጥቅምት 2 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ እኔ የመንግስት ሰራተኛ የነበርኩት ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ/ም መሆኑ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ በግልፅ ተጠቅሷል፡፡ አዲሱ የወንጀል ህግ በስራ ላይ እንዲውል ህግ አውጭው የደነገገው ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ይህም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 419 ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ በማድረግ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 የተደነገገውን መርህ የሚጥስ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ፍርድ የተሰጠብኝ መሆኑን ያሳያል፡፡ የታርጋ ቁጥር ኮድ 2- 78716 የሆነችው መኪና የተገዛቸው በ2002 ዓ.ም መሆኑና ምንጩም የታወቀ መሆኑን አስረድቼ እያለ ለመንግስት ውርስ እንድትሆን መወሰኑ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ስለዚህ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ በነፃ እንድሰናበት በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የወንጀል ህጉ ወደኋላ ተመልሶ ሊሰራ አይገባም በማለት ያቀረበውን መከራከሪያ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 130 መሰረት በመጀመሪያ ክስ መቃወሚያ አድርጎ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ በሰበር ደረጃ ይህንን መከራከሪያ አድርጎ እንዲያቀርብ የሚፈቅድለት ህግ የሌለ በመሆኑ ክርክሩ ውድቅ እንዲደረግልን፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን 1992 እስከ 1996 ዓ/ም ባለው ጊዜ ብቻ እንደተፈፀመ አድርጎ ያቀረበው ክርክር የወንጀሉን ባህሪ ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች የወንጀል ምርመራ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስና እስከተከሰሰበት ድረስ የወንጀል ድርጊቱ ተፈፅሞ ተጠናቅቋል ለማለት ስለማይችል የአመልካቹ የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥር 23 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው እስከ 1996 ዓ.ም መሆኑን ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ በግልጽ አስፍሯል፡፡ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ መሆናቸው ከ1996 ዓ.ም በኋላ ከቆመ፣ በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ምርመራ እስከተጣራበትና ክስ እስከቀረበበት ድረስ ወንጀሉ የሚቀጥልበት ሁኔታ የለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም (1) ተጠሪ አመልካች በ1997 ዓ.ም ሥራ ላይ የዋለው የወንጀል ህግ በእኔ ላይ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑ፣ በዚህ ህግ መሰረት ልከሰስና ልቀጣ አይገባኝም በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 130 መሰረት በመጀመሪያ ክስ መቃወሚያነት ያላቀረበው በመሆኑ አሁን ይህንን ነጥብ የሰበር መከራከሪያ ሊያደርገው አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?

(2) የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በ1997 ዓ.ም የወጣውንና ግንቦት 1 ቀን 1997 የፀናውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ ተገኝቷል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- የወንጀል ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ፎርምና ይዘት በመቃወም፣ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችል መሆኑ

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 130 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ክስ የቀረበበት ተከሳሹ፦

- ጉዳዩ በሌላ ፍርድ ቤት እየታየ ያለመሆኑን፣
- ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን ወይም በይቅርታ ወይም በምህረት የተለቀቀ መሆኑን፣
- ጉዳዩ ከሌሎቹ ተከሳሾች ጋር መጣመሩ መብቱን የሚያጣብብ መሆኑን፣
- ዐ/ህግ የወንጀል ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆነውን ፈቃድ ሳያሟላ የወንጀል ክስ ማቅረቡን፣

- በሌላ ፍ/ቤት የተያዘው ጉዳይ ካላለቀ የወንጀል ክስ ለማቅረብ የማይችል መሆኑንና ለድርጊቱ በኃላፊነት የማይጠየቅ መሆኑን በመጀመሪያ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርብ እንደሚችል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት መቃወሚያዎች ተከሳሽ ወዲያውኑ ማቅረብ እንዳለበት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት የወንጀል ክስ መቃወሚያዎች አመላካች (indicative provision) እንጅ ሁሉንም በመቃወሚያነት ሊቀርቡ የሚችሉ ጉዳዮችን በሙሉ የሚዘረዝር (exhaustive provision) ድንጋጌ አይደለም፡፡ አመልካች የሰበር መከራከሪያ ያደረገው ነጥብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130(2) የተመለከተ አይደለም ሆኖም ተጠሪ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ከመጽናቱ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ/ም በፊት 1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም እንደሆነ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ በግልፅ አስፍሮታል፡፡

የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ዳኞች ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ፀንቶ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን ከተረዱ በማናቸውም ጊዜ አንስተው ውሳኔ ለመስጠት የማይከለክሉና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) የተጣለባቸውን ሰብአዊ መብት የማስከበር ግዴታቸውን የሚወጡበት አንደኛው መንገድ በመሆኑና የወንጀል ክስ የቀረበበት ድርጊት በወንጀለኝነት የሚደነግግ ግልጽ የወንጀል ህግ ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ዳኞች በመመርመር የህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 የተደነገገውን መሰረታዊ መርህ የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ስልጣን በማናቸውም ደረጃ በሚገኝ ፍ/ቤት የተሰየሙ ዳኞች ያላቸው በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፣ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የፀደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ የሚፀናው በልዩ መፅሐፍ በነጋሪት ታትሞ ከወጣ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 3 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የመንግስት ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች በሙስና ወንጀል ተጠያቂ ስለሚሆኑበት ወንጀል ዝርዝርና መሰረታዊ መርሆችን የሚደነግግ ከአንቀጽ 402 እስከ አንቀጽ 419 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም እና ከዚያ በኂላ የመንግስት ሰራተኛ በሆኑ ሰዎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህንንም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2" የወንጀል ህጉ ድርጊቱ በዚህ ህግ መሰረት ወንጀል ሆኖ በተሻረው የወንጀል ህግ ግን እንደወንጀል ካልተቆጠረና የተፈፀመው ይህ ህግ ከመጽናቱ በፊት ከሆነ ሊያስቀጣ አይችልም" በማለት ደንግጎታል፡፡ ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም መሆኑን በግልጽ አስፍሯል፡፡ የወንጀል ህጉ በፀናበትና ስራ ላይ በዋለበት ግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም አመልካች የመንግስት ሰራተኛ እንዳልነበረ የተጠሪ የክስ ማመልከቻ ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረበው አመልካች የወንጀል ህጉ ከመጽናቱ ከግንቦት 1 ቀን

1997 ዓ.ም በፊት የመንግስት ሰራተኛ የነበረ መሆኑንና አመልካች ምርመራ በተጣራበት 2001 ዓ.ም በስሙ የተለያዩ ባንኮች ሒሳብ ከፍቶ ሲያንቀሳቅስ የነበረውን ገንዘብና በስሙ የገዛትን መኪና ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ሲያገኝ ከነበረው ደመወዝ ጋር በማመዛዘን ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ይዟል በማለት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ እንደማይችልና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተፈፃሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ ሊቀጣ እንደማይችል በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም አገራችን ባፀደቀችው ዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 "No one shalll be held guilty of any criminal offence on account of any act or omission which did not constitute a criminal offence under national or international law, at the time which the criminal offence was committed" በሚል መንገድ ተደንግጓል፡፡ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው የኢፌዲሪ ወንጀል ህግ ከመጽናቱ በፊት ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት የነበራቸው የወንጀል የህግ ማዕቀፎች በ1949 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግና በ1974 ዓ.ም የወጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ቁጥር 214/1974 ናቸው፡፡ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ የወንጀል ድርጊት ሆኖ የተደነገገውና ይዘቱ የተዘረዘረው የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት ባላቸው የወንጀል ህግ ማዕቀፎች የወንጀል ድርጊት ሆኖ የተደነገገ ድርጊት አይደለም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ከመፅናቱ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት የመንግስት ሰራተኛ በነበረውና የወንጀል ህጉ ከመፅናቱ በፊት የመንግስት ስራውን ለቅቆ በንግድ ስራ መሰማራቱ በክርክር ሂደት በተገለፀው አመልካች ላይ የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 በመጥቀስ ያቀረበው ክስ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 የዓለም አቀፉን የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን መሰረታዊ የወንጀል ህግ መርህ የሚጥስና የአመልካችን መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የተገለፀውን የህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ በማስፈፀም የተጠሪን የወንጀል ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ በመገኘት የሙስና ወንጀል፣ የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) 1 መሰረት በመሻር አመልካች በነፃ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች በነፃ እንዲሰናበት የተወሰነ በመሆኑ በሌላ ጉዳይ ካልታሰረ በስተቀር በዚህ ጉዳይ ከእስር እንዲለቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት የመፈቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡

3. አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የወሰኑት የገንዘብ መቀጮና በአመልካች ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብና ቁጥር 2-78716 አ.አ የሆነችው መኪና እንዲወረስ የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 3.4.1 የምርመራ ሥራውን የማከናወን እና የመዳኘት ሥልጣንን በተመለከተ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ[156]

- የብሔር ግጭትን በተመለከተ የመመርም ሆነ የመዳኘነት ሥልጣን የፌደራል መንግስት እንጂ የክልሎች ስልጣን ስላለመሆኑ፤
- የፍርድ ቤት የዳኘነት ሥልጣን ፍርድ ቤት የሚፀና ፍርድ እንዳይሰጥ ከሚያደርጉት በክስ መቃወሚያ ዝርዝር ውስጥ ሊካተቱ ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ ስለመሆኑ፤
- ግጭቱ የብሄር መሆኑን በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተው ፍሬ ነገር የሚያሳይ ሆኖ እያለና በማስረጃም ተረጋግጦ ባለበት አመልካቾች እና የግል ተበዳይ በአንድ አካባቢ መኖራቸው ግጭቱ የብሄር አይደለም ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ አይችልም፡፡
- የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የወንጀል የዳኘነት ሥልጣን የሚደነግገው ቁጥር 4(9) እንደሚያመለክተው በተለያዩ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦች፤ ጎሳዎች፤ ሐይማኖት ተከታዮች፤ ወይም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ከተፈጠረ ግጭት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን የማየት ሥልጣን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሕገ-ምንግስታዊ ውክልና ባልተነሳባቸው ክልሎች ይህን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ የዳኘነት ሥልጣን አይቶ የመዳኘት ሥልጣን በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(2) መሠረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡
- የምርመራ ስራውን የመራው እና ክሱንም ያቀረበው በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ወይንም በህግ የተወከለ አለመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ስልጣን የሌለው መሆኑ ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት በታየው ጉዳይ ላይ የቀረበው ይግባኝ መሰረዙ እና የፌደራል ጉዳይን የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት ማየቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ፤

የሰ/መ/ቁ 243034

ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች ፡- 1. ጋሻው አሳዩ የቀረበ የለም

2. አሰግድ አሳዩ

ተጠሪ ፡- የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ - ዐ/ህ ጠጅቱ በቀለ ቀርቧል

ለምርመራ የተቀጠረውን መዝገብ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

---

[156]የሰ/መ/ቁ 243034 (ጥቅምት 6 ቀን 2016ዓ/ም)

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) 35 እና 539 ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ ከባድ የግድያ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ጥፋተኛ ተብሎ በ18 (በአስራ ስምት) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተላለፈው የጥፋተኝት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተገኘበትም በማለት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠበር አጣሪው ችሎት የሰበር አቤቱታውን በሰበር መዝገብ ቁጥር 421338 ጥር 17 ቀን 2015ዓ/ም በዋለው ችሎት መሰረዙ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት በሰበር ሰሚ ችሎቱ ለማሳረም አመልቾች የካቲት 20 ቀን 2015ዓ/ም የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ከባድ የግድያ ወንጀል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ህዳር 3 ቀን 2014ዓ/ም ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች በ1996ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) 35 እና 539(1)(ሀ)ን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስበው ህዳር 5 ቀን 2014ዓ/ም በምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳ አባቦ ሞሌ በሚባል አካባቢ በአማራ እና በኦሮሞ ብሔረሰብ መካከል በተፈጠረ ግጭት ምክንያት በግምት ከጠዋት 3፡00 ሲሆን ዓይነቱ የማይታወቅ የጦር መሳርያ በመያዝ ከሌሎች 200 ሰዎች ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ወደሆነው ሟች ድሪባ ቀነኒ መኖሪያ ቤት በመሄድ ከአመልካቾች ማን እንደመታው መለየት በማይቻልበት ሁኔታ ግራ ጆሮው አካባቢ ላይ በመተኮስ በቀኝ በኩል በመውጣት ዘግናኝ በሆነ መልኩ ጉድለውት ስለሄዱ ከባድ የግድያ ወንጀል በመፈጸም ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የእምነት ክደት ቃላቸውን ተጠይቀው የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ ዐቃቤ ህግ አመልካቾች የወንጀል ድርጊቱን መፈጸማቸውን የሚያስረዱ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ እንዲታዘዝለት ጠይቆ ምስክሮቹ ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተመሳሳይ በሚባል መልኩ አመልካቾች ከፊት እየመሩ ሌሎች 200 በላይ ከሚሆኑ ሰዎች ጋር በመሆን ህዳር 5 ቀን 2014ዓ/ም ከጠዋቱ 3፡00 አካባቢ ኖኖ ወረዳ አባቦ ሞለ በሚባል አካባቢ መሳሪያ እየተኮሱ ወደ ሟች መኖሪያ ቤት ወደ ጊቢ ሲገቡ ሟች ጺሙን እየተላጨ ነበር ምስክሮቹ ወደ ጫካ ሸሽተው 7፡00 ሰዓት ላይ ወደ ቤት ሲመለሱ የግል ተበዳይ ሞቶ እንዳገኙት የተመታውም በግራ ጆሮው አካባቢ ሆኖ በቀኝ መውጣቱን መስክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ አመልካቾች በተከሰሱበት አንቀጽ ሥር እንዲከላከሉ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አመልካቾች ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታ እንዳልነበሩ ያውቁልናል በማለት የቆጠሯቸው 3 የመከላከያ ምስክሮች ቀርበው ተሰምተዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የመከላከያ ምስክሮቹ አመልካቾች የወንጀል ድርጊቱን እንዳልፈፀሙ መከላከል አለመከላከላቸውን በጭብጥነት ይዞ መዝገቡን እንደመረመረው፡፡ የመከላከያ ምስክሮች የምስክርነት ቃል የተምታታ እና የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የሰጡትን ቃል የሚያጠናክር እንጅ ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ ባለመሆኑ የአቃቤ ህግ ምስክሮች ምስክርነት ቃል የሚያስተባብል ሆኖ ስላልተገኘ አመልካቾች በተከሰሱበት ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.149(2) መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም መነሻው ምክንያቱ በአማራ ብሄር እና ኦሮሞ ብሔር መካከል የተፈጠረ ግጭት አመልካቾች ወደ ግል ተበዳይ ቤት በመሄድ ወንጀሉን እንደፈፀሙ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም ምክንያት አመልካቾች መሆኑን ስለምያመለክት እንዲሁም አደገኛ የጦር መሳርያ በመጠቀም ወንጀሉን ስለፈፀሙ የወንጀሉን ደረጃ ሁለተኛ እርከን 38 መነሻ ወስዶ በሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እርከን 36 ሥር እያንዳንዳቸው በ18ዓመት እስራት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም በየደረጃውም ላሉት ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር ቅሬታ ተቀባይነት ስላላገኘ የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች የካቲት 20 ቀን 2015ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ክሱ የቀረበብን በውሸት ነው፤ እኛ የአማራ ብሔር ተወላጅ በመሆናችን እንጂ ድርጊቱን አልፈጸምንም ፤ ድርቱ ተፈጸመ በተባለ ቀን ድርጊቱ ተፈጽሟል በተባለው አካባቢ አልነበርንም ፣ የሟቹ ባለቤት በእኛ ላይ አልመሰክርም ስትል ፖሊስ እናሳስርሻለን በማለት ሲያስፈራራት ነው የመሰከረችብን፣ በወቅቱ ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታ ከ200 በላይ ሰዎች ከነበሩ የወንጀል ድርጊቱን ማን እንዴት እንደፈጸመ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች በግልጽ አላስረዱም፣ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ድርጊቱ ሲፈጸም ድርጊቱ ተፈጽሟል ከተባለበት ስፍራ ወደ ጫካ ሸሽተው ሲመለሱ የግል ተበዳዩ ሞቶ እንዳገኙት ከመመስከር ውጪ ሟችን ማን እንደገደለው ባላስረዱበት ሁኔታ የአቃቤ ህግ ምስክሮች ቃል በአግባቡ ሳይመዘን የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲሁም፣ የግል ተበዳይ የሞተው በአንድ ጥይት ተመቶ መሆኑ ተመስክሮ እያለ በከባድ የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለን የተጣለብን ቅጣት ውሳኔ ተገቢነት የለውም፣ የወንጀል ድርጊቱን ያልፈጸምን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀረበው ክስ እና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ከሰጡት የምስክርነት ቃል መገንዘብ እንደሚቻለው ለወንጀል ድርጊቱ መፈጸም ምክንያት የሖነው በአማራ እና ኦሮሞ ብሄር መካከል የተነሳ ግጭት በመሆኑ ወንጀሉን የመመርመር ሆነ ክስ የማቅረብ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሆኖ እያለ በክልል ፖሊስ እና ዐቃቤ ሕግ ወንጀሉ ተመርምሮ ክሱ ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ መታየቱ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ የስር ቤቶች ውሳኔው በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካቾች የተከሰሱበት ወንጀል በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመታየቱ አግባብነት፤ እንዲሁም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539(1/) ሥር የጥፋተኝነት ውሳኔው የመሰጠቱን ተገቢነት ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 7/3/ አንጻር መመርመር አስፈላጊ በመሆኑ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዞ ምላሹን ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 25 ቀን 2015ዓ.ም የሰው መልስ ይዘት ባጭሩ፡- አመልካቾች ሆን ብለው ድርጊቱን መፈጸማቸው ባቀረብናቸው ምስክሮች በአግባቡ ተረጋግጧል፤ በወቅቱ ብዙ ሰዎች አብረዋቸው የነበሩ ቢሆንም የወንጀል ድርጊቱን የፈጸሙት አመልካቾች ናቸው፣ ወንጀሉ የተፈፀመው በብሔር ግጭት ሳይሆን በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዋሪዎች እና ግለሰቦች መካከል የተነሳ ግጭት እንጂ የብሔር ግጭት ባለመሆኑና አመልካቾችም ሆነ የግል ተበዳይ የሚኖሩት አንድ አካባቢ ሲሆን የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም ወንጀል አድራጊዎቹ የሚያውቋቸው የአከባቢ ነዋሪዎች መሆናቸውን ስላረጋገጡ የክልሉ ዐቃቤ ህግ ክስ የመመስረት ፣ የክልሉ ፍርድ ቤቶችም በጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡ አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ በመከላከያ ምስክሮቻቸው አላስተባበሉም፤ አመልካቾች 200 የሚሆኑ ግብርአበሮቻቸውን አስከትለው ሰውን በመግደል ሀሳብ ሟች ቤት ሄደው የገደሉት በመሆኑ በከባድ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ ነው ፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንዱ ዓላማ አንድ የወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት ከታየ በኋላ ተከሳሹ ጥፋተኛ ከሆነ የሚገባውንና የሚያስተምረው ቅጣት እንዲያገኝ፤ ጥፋተኛም ካልሆነ በቶሎ ወደ መደበኛ የህይወት ምህዋሩ እንዲመለስ ለማስቻልና ህዝቡም ከወንጀል አድራጊዎች እንደሚጠበቅ በፍትህ ሂደቱ እምነት እንዲኖረው ለማድረግ ወንጀል አድራጊዎችን በቶሎ በመዳኘት የፍትህ ሂደቱን ውጤት ማሳወቅ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ የመንግስትን፣ የህዝብንና የምስክሮቹን ሃብትና ጊዜ ከወሰደ በኋላ የሚሰጠው ፍርድ መጽናት አለበት፡፡

የክስ መቃዎሚያ ፍርድ ቤት ወደ ሥረ ነገሩ ከመግባት የሚያግደው ወይንም ወደ ሥረ ነገር ከመግባቱ በፊት ትዕዛዝ ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ የክስ መቃወሚያ በአብዛኛው የሕግ ጉዳዮችን የሚመለከት

ነው፡፡ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ ቁጥር 130 ሥር የተዘረዘሩት የክስ መቃወሚያዎች አመልካች እንጅ ሙሉ እንዳልሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 73514 ላይ ከሰጠው ውሳኔ መረዳት ይቻላል፡፡ የፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ፍርድ ቤት የሚፀና ፍርድ እንዳይሰጥ ከሚያደርጉት በክስ መቃወሚያ ዝርዝር ውስጥ ሊካተቱ ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ የፍርድ ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 11-20 በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥረዓት ሕጉ አንቀጽ 99-107፣ በ1ኛው ሰንጠረዥ፣ በፍርድ ቤቶች አዋጅ እና በመሠረታዊ ሕጎች/substantive laws/ ተደንግጎ እናገኛቸዋለን፡፡ የሥረ ነገር ሥልጣን ባልተሰጠው ፍርድ ቤት የሚሰጥ ውሳኔ አይፀናም፡፡

የፍርድ ቤት የሥረ ነገር ስልጣን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 130 ሥር በክስ መቃወሚያነት ያልተጠቀሰ ቢሆንም ተከሳሹ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ከክሱ እንዲሰናበት ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ከሌለው መዝገቡን ዘግቶ ተከሳሹን ከክሱ ማሰናበት ይጠበቅበታል፡፡

የክስ መቃወሚያ ወዲያው መነሳት ያለበት ሲሆን፣ መቃወሚያዎቹ ፍርድ ቤቱ የሚፀና ውሳኔ ከመስጠት የሚከለክሉ በሆኑ ጊዜ ብቻ በቀጣይ ቀጠሮዎች ጭምር ሊነሳ እንደሚችል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 130/3 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረቡት የክስ መቃወሚያዎችን መዝግቦ ዐቃቤ ሕግ አስተያየት ካለው ጠይቆ ወዲያውኑ፣ አልያም በማስረጃ አጣርቶ ብይን እንደሚሰጥ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 131 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ሕገ መንግስታዊ ይዘት ያላቸው እና ፍርድ ቤቱን የፀና ፍርድ እንዳይሰጥ የሚከለክሉ የክስ መቃወሚያዎች ፍርድ ቤቱ ወደ ሥረ ነገሩ ከመግባቱ በፊት ተገቢውን ትእዛዝ ካልሰጠባቸው የተከሳሹን ሕገ-መንግስታዊ መብት ስለሚገድቡ ተከሳሹ ወይንም ጠበቃው ክሱን ለመቃወም የሚያበቃ የሕግ ጉዳይ ሲኖር በማንኛውም ጊዜ ቢያቀርቡ ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት አወቃቀር ፌደራላዊ ከመሆኑ አንፃር የዳኝነት አካሉም በፌደራል እና ክልል ደረጃ የተቋቋመ ቢሆንም፤ የፍርድ ቤቶቹ አደረጃጀት ትይዩ ባለመሆኑ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በክልላቸው ከሚሰጣቸው የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ደርበው የሚሰሩ ሲሆን፤የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችም በክልላቸው ከሚኖራቸው የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታዩ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን አላቸው፡፡(የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(2) እና 80(4) ይመለከቷል፡፡) የፌደራል መንግስቱም ሆነ የክልል መንግስት ሥልጣን ምንጭ ሕገ-መንግስት መሆኑን፤ለፌደራሉ መንግስት የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መከበር ያለበት መሆኑን፤በተመሳሳይ ለክልሎች የተሰጠውን ሥልጣን የፌደራል መንግስት ማክበር እንዳለበት የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 50(8) ያመለክታል፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን በክልል ጉዳዮች ላይ ብቻ የተገደበ መሆኑን ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 80(3) (ለ) ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሕገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አይተው የሰጡትን ውሳኔ በሰበር የማረም ሥልጣን በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 10(1)(ሠ) ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የተሰጠ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ያፀደቀችው እና በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 9(4) ድንጋጌ መሠረት የሀገሪቱ የህግ አካል የሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን(international covenant on civil and political Rights) አንቀጽ 14(1) ማንኛውም ሰው በወንጀልም ሆነ በፍትሐ ብሔር የቀረበበትን ክስ በሕግ በተቋቋመ፤ ስልጣን ባለው ነፃና ገለልተኛ አካል የመዳኘት መብት ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን የሚደነግገው ቁጥር 4(9) እንደሚያመለክተው በተለያዩ ብሔሮች፤ብሔረሰቦች፤ጎሳዎች፤ሐይማኖት ተከታዮች፤ወይም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ከተፈጠረ ግጭት፤ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን የማየት

ሥልጣን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑ ተመልክቷል። ሕገ-ምንግስታዊ ውክልና ባልተነሳባቸው ክልሎች ይህን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን አይቶ የመዳኘት ሥልጣን በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(2) መሠረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ናቸው። በፌደራል ፍርድ ቤት ሥልጣን ስር የሚወድቅ የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር ማድረግ፤ የተጀመረ የወንጀል ምርመራ ላይ ክትትል ሪፖርት እንዲቀርብ ማድረግ እንዲሁም ምርመራው በአግባቡ ተከናውኖ እንዲጠናቀቅ፤የህዝብ ጥቅም መነሻ አድርጎ ወይንም በወንጀል የማያስጠይቅ ሲሆን ምርመራው እንዲቋረጥ ወይንም የተቋረጠው ወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ማድረግ፤ምርመራው በህጉ አግባብ መከናወኑን ማረጋገጥ፤የፌደራል መንግስትን በመወከል በወንጀል ጉዳዮች ክስ መመስረት፤መከራከር፤ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ክስ ማንሳት፤የተነሳ ክስ እንዲቀጥል ማስደረግ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥልጣን መሆኑን የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 ቁጥር 6(3)(ሀ) እና(ሠ) ይደነግጋል።

በተያዘው ጉዳይ በአመልካቾች ላይ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1),(ሀ) (ለ)፣ 35 እና 539(1)(ሀ)ን በመተላለፍ በክሱ ላይ በተገለጸው ጊዜ በምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳ አባቦ ሞሌ በሚባል አካባቢ በአማራ እና በኦሮሞ ብሄረሰብ መካከል በተፈጠረ ግጭት ምክንያት ዓይነቱ የማይታወቅ የጦር መሳሪያ በመያዝ ከሌሎች 200 ሰዎች ጋር በመሆን ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው። ክሱ የቀረበለት የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ለወንጀል ድርጊቱ መፈጸም መነሻው ምክንያቱ በአማራ ብሄር እና ኦሮሞ ብሄር መካከል በተፈጠረ ግጭት አመልካቾች ከሌሎች 200 በላይ ከሚሆኑ ሰዎች ጋር ወደ ግል ተበዳይ ቤት በመሄድ ወንጀሉን እንደፈፀሙ በማስረጃ ማረጋገጡን ውሳኔው ያመለክታል። አመልካቾች ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም ምክንያት የሆነው በአማራ እና ኦሮሞ ብሄር መካከል የተነሳ ግጭት በመሆኑ ወንጀሉን የመመርመር ሆነ ክስ ማቅረብ የፌደራል ዓቃቤ ህግ ሆኖ እያለ በክልል ፓሊስ እና ዐቃቤ ህግ ወንጀሉ ተመርምሮ ክሱ ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረቡን በመቃወም ላቀረቡት አቤቱታ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካቾችም ሆነ የግል ተበዳይ የሚኖሩት አንድ አካባቢ በመሆኑ ግጭቱ የብሄር አይደለም የሚል ክርክር አሰቷል። ግጭቱ የብሄር መሆኑን በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተው ፍሬ ነገር የሚያሳይ ሆኖ እያለና በማስረጃም ተረጋግጦ ባለበት አመልካቾች እና የግል ተበዳይ በአንድ አካባቢ መኖራቸው ግጭቱ የብሄር አይደለም ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ አይችልም።

ሲጠቃለል የምርመራ ስራውን የመራው እና ክሱንም ያቀረበው በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ወይንም በህግ የተወከለ አለመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ስልጣን የሌለው መሆኑ ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት በታየው ጉዳይ ላይ የቀረበው ይግባኝ መሰረዙ እና የፌደራል ጉዳይን የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት ማየቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል።

**ውሳኔ**

1. የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 421338 ጥር 17 ቀን 2015ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 354596 ታህሳስ 27 ቀን 2015ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ እንዲሁም የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 42542 ታህሳስ 11 ቀን 2015ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ ቁጥር 195(2)(2) መሰረት ተሽሯል።
2. የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔው በህግ ስልጣን ባልተሰጠው ፍርድ ቤት በመሰጠቱ ምክንያት ስለተሻረ አመልካቾች ከማረሚያ ቤት እንዲወጡ ትዕዛዝ ይተላለፍ ብለናል።

3. የውሳኔው ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች እና ለምዕራብ ሸዋ ዞን መረሚያ ቤት ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 3.5 የእምነት ክህደት ቃል[157]

- በወንጀል ሕጉ መሰረት በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ዉሳኔ መስጠት የሚቻለዉ ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረዉን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡ በወንጀል በተከሰሰ ሰዉ ላይ የሚሰጥ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በተከሳሹ ሕይወት እና/ወይም ነጻነት ላይ የሚፈጸም እንደመሆኑ በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ መብት በጥንቃቄ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለዚህ መብት የበለጠ ጥበቃ ለማድረግ ካለዉ ዓላማ ሕግ አዉጪዉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 134/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመስራቱ በሙሉ በማመኑ ጥፋነኛ ነኝ ብሏል ተብሎ በመዝገቡ ቢጻፍም እንኳን ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕጉ ክሱን የሚደግፍለትን ማስረጃ እንዲያቀርብና ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃዉን አቅርቦ እንዲያስረዳ ማዘዝ እንዲችል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
- ተከሳሽ በከፊል አምኖ በከፊል ክዶ የተከራከረ ከሆነ ፍርድ ቤት የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ መርምሮና መዝኖ ክሱን መከላከል ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ መወሰን ሲገባዉ የመከላከል መብትን ሳይጠብቅ በቀጥታ ጥፋተኛ በማለት በተካደው ጉዳይ ላይ መወሰን የክርክር አመራር ስህተት ስለመሆኑ፡፡[158]

የሰ/መ/ቁጥር 237315

መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች ፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች ፡- ቤተልሔም ጌታቸዉ ታደሰ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- በፍትሕ ሚኒስቴር - የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ክርክር አመራር የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረተዉ የወንጀል ክስ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 (2/መ) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በቀን 05/09/2014 ዓ.ም በግምት 12:20 ሰዓት ሲሆን ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ልዩ ቦታዉ ቴዲ ጋራዥ አካባቢ ንብረትነቱ የግል ተበዳይ ማህሌት ሽፈራዉ የሆነና በመኖሪያ ቤቷ ዉስጥ የቤት ሠራተኛ ሆና በምትሰራበት ወቅት አንድ ዲም ላይት ጌጥ፣ አንድ የሴት ቀሚስ፣ የእጅ ቦርሳ በዉስጡ 1,500.00 ብር እንደያዘ፣ ሁለት አሻንጉሊት፣ሁለት

---

[157]የሰ/መ/ቁ 237315 (መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ/ም)

[158]የሰ/መ/ቁ 232549 (ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 77842 (ታህሳስ 3 ቀን 2005ዓ.ም) ቅፅ 14፣የሰ/መ/ቁ 96954 (ሚያዚያ 24 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16

የሕጻን ቀሚስ አጠቃላይ የዋጋ ግምታቸዉ ብር 4,920.00 የሚገመት ወስዳ በልብስ ሻንጣዋ ዉስጥ አስቀምጣ በመገኘቷ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽማለች በማለት ክስ መስርቶባታል፡፡

ለአመልካች ክሱ እንዲደርሳት ተደርጎ ተነቦላት በክሱ ላይ መቃወሚያ የለኝም በማለት አልባሳቱን ፣ ቦርሳ፣ አሻንጉሊትና ጌጣጌጡን ወስጃለሁ፡፡ በክሱ የተጠቀሰዉ ብር 1500.00 ግን የራሴ ገንዘብ ነዉ በማለት ገልጻለች፡፡ ዐቃቤ ሕግ አመልካች የእኔ ነዉ ባለችዉ ገንዘብ ላይ ምስክር አቅርበን እናሰማለን ሌሎች ዕቃዎች በተመለከተ ስላመነች የጥፋተኝነት ዉሳኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም ዐቃቤ ሕግ ምስክር አቅርቦ እንዲያሰማ ትእዛዝ ሰጥቶ የግል ተበዳይ አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ምስክሯም የእጅ ዋሌት ቦርሳዬ ብር 1500.00 እና የባንክ ቡክ በዉስጡ እንዳለ ከመሳቢያ ዉስጥ ባጣሁ ጊዜ በጥርጣሬ የአመልካችን ሻንጣ ስፈትሸዉ በልብሶቿ ዉስጥ አግኝቻለሁ፡፡ ገንዘቡ የራሴ ነዉ በማለት መስክራለች፡፡ በመቀጠል ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 89076 ላይ በቀን 15/09/2014ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች የቀረበባትን ክስ በዝርዝር ያመነች በመሆኑ በተከሰሰችበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 (2/መ) ስር ጥፋተኛ ናት በማለት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 134/1ን በመጥቀስ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

በመቀጠልም ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቶ ዐቃቤ ሕግ የቅጣት ማክበጃ ምንያት አለማቅረቡን አመልካች ደግሞ በወንጀል ሕግ ቁጥር 82 (1/ሀ)፣82(1/ሠ) እና 86 ስር የሚሸፈኑ ሶስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ማቅረቧን በመግለጽ የተሰረቀዉ ንብረት ግምቱ ብር 4920.00 በመሆኑ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት የቅጣቱ ደረጃ 4 በእርከን 19 ስር ያረፈዉ በተያዙት ሶስት ማቅለያዎች ወደ እርከን 16 ዝቅ ስለሚል በዚህ እርከን ላይ በተመለከተዉ ፍቅድ ሥልጣን መሰረት አመልካችን ያስተምራል ሌሎችንም ያስጠነቅቃል ሲል አመልካች በ3 (ሶስት) ዓመት ጽኑ እስራት እንድትቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 010609 ላይ ይግባኝ ያቀረበች ቢሆንም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 07/03/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበችዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- ድርጊቱን የፈጸምኩት የታመመች እናቴን ለማዳን ብዬ ካቀረብኩት የቅጣት አስተያየት አንጻር የኑሮ ደረጃዬ ዝቅተኛ መሆኑንና የሕግ እዉቀት እንደሌለኝ ከግምት በማስገባት የስር ፍርድ ቤት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82(1/ሐ) መሰረት ድርጊቱን የፈጸምሁት ከፍተኛ የሆነ ቁሳዊ እጦት ስለገጠመኝ መሆኑን በመገንዘብ እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ አለመያዙ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም በክሱ የተዘረዘረዉ ንብረት ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስ ለግል ተበዳይ የተመለሰ መሆኑን ከግምት በማስገባት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 27(1 እና 3) እና 179 ስር በተደነገገዉ መሰረት ቅጣቱን ማቅለል ሲገባዉ በዝምታ ማለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ታርሞ ቅጣቱ ይቅለልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ምንም እንኳን አመልካች በጥፋተኝነት ላይ ያቀረበችዉ ቅሬታ ባይኖርም ጉዳዩ የወንጀል ጉዳይ መሆኑን፣አመልካች ካላት ክሱን የመከላከል መብት፣ ከክርክር አመራር እና ከሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን አኳያ አመልካች በክሱ ሰረቀች ከተባለዉ ዉስጥ ብር 1500.00 የራሴ ገንዘብ ነዉ አልሰረቅኩም በማለት ቃሏን በመስጠቷ እንደካደች ተቆጥሮ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ከተሰማ በኋላ የተመሰከረባት መሆኑ ተገልጾ ክሱን እንድትከላከል ሳይደረግ ሙሉ በሙሉ ክሱን እንዳመነች በማድረግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 134/1 መሰረት ጥፋተኛ ናት ሲል የስር ፍርድ ቤት ቅጣት የወሰነበትን አግባብ ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በቀን 08/06/2015ዓ/ም በተጻፈ መልሱ የስር ፍርድ ቤት የዐቃቤ ሕግን ምስክር ከሰማ በኋላ ማስረጃዉን መዝኖ ተገቢዉን ብይን ሳይሰጥ አመልካች አምናለች በማለት ዉሳኔ መስጠቱን መዝገቡ ስለሚያሳይ ችሎቱ ተገቢ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ ቢሰጥበት አንቃወምም በማለት መልሱን ሰጥቷል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም አመልካች የቀረበባትን የወንጀል ክስ በከፊል አምና በከፊል ክዳ በመከራከሯ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 134/1ን በመጥቀስ በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በማስተላለፉ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም አንድ ሕገ-ወጥነቱና አሰቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን የወንጀል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በተሟላ መልኩ መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ አግባብ መቀጣት ይገባዋል፡፡ በዚህ መልኩ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለዉ በተለይም ተከሳሹ በክሱ የተጠቀሰዉን የወንጀል ድርጊት ወይም አል ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ከተከራከረ በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በሚያሳይ አግባብ ተከሳሹ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በማስረጃ ሲያስረዳ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት፣ በወንጀል ሕጉ እና በሌሎች ልዩ ልዩ ሕግጋት ሥነ ሥርዓታዊ ባህሪያት ያላቸዉ መርሆዎች፣ መብትና ግዴታ የሚደነግጉ ድንጋጌዎች መኖራቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ክርክር በዋናነት የሚመራዉ በ1954 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 185 ጸድቆ ሥራ ላይ በዋለዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ በተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት መሰረት ነዉ፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20 ስር በተለይም በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ያላቸዉ መብቶች በዝርዝር ተደንግጎ ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ ተድርጓል፡፡ ከእነዚህ መብቶች ዉስጥ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ ዉስጥ የመሰማት መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ፣በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተገቢዉን ሂደት ተከትሎ ጥፋተኛ መሆናቸዉን አረጋግጦ የጥፋተኝነት ፍርድ ከመስጠቱ በፊት እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር ፣የቀረበባቸዉን ማናቸዉንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸዉን ምስክሮች የመጠየቅ ፣ለመከላከል የሚያስችላቸዉን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸዉ ቀርበዉ እንዲሰሙላቸዉ የመጠየቅ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ እና ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸዉ ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ያላቸዉን ቅሬታ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት አቅርበዉ የማሳረም ወይም ይግባኝ የመጠየቅ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ የተደነገጉት ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ እነዚህ የተከሰሱ ሰዎች መብቶች በዓለም አቀፉ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን (International Convention on Civil and Political Rights) አንቀጽ 10(2 እና 3)፣ 11 እና 14 እንዲሁም በዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights) አንቀጽ 10 እና 11 ስር በተደነገገዉ መስረት እዉቅና የተሰጣቸዉና ጥበቃ የተደረገላቸዉ መብቶች ስለሆኑ በአጋራችን የሕግ ሥርዓት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸዉ ናቸዉ፡፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 128 እና 129 ስር በተደነገገዉ መሰረት የተከሳሹ ማንነት ተረጋግጦ የክሱ ማመልከቻ እንዲደርሰዉ ተደርጎ ከተነበበለት በኋላ ተከሳሹ በክሱ ላይ በቁጥር 130 ስር በተደነገገዉ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ መወሚያነት የሚያቀርበዉ መከራከሪያ ካለ እንደሚሰማ፣የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የለኝም ካለ በሕጉ ከቁጥር 131 እስከ 135 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተከሳሹ በክሱ ፈጸመ ተብሎ በተገለጸዉ የወንጀል ድርጊት ላይ የሚያሰማዉ የእምነት ክህደት ቃል እንደሚሰማ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ለተከሳሹ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳዉ ከተደረገ በኋላ ክሱን የካደ እንደሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል ተብሎ እንደሚመዘገብ፣ወንጀሉን መፈጸሙን አምኖ በአፈጻጸሙ ረገድ ለይቶ መብቱን የጠበቀ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል ተብሎ መዝግቦ ክዶ በተከራከረዉ ልክ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃዉን አቅርቦ እንዲያስረዳ መደረግ እንዳለበት በሕጉ በቁጥር 133 ስር የተደነገገዉ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 134/1 መሰረት በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ዉሳኔ መስጠት የሚቻለዉ ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረዉን ወንጀል

ለመስራቱ በሙሉ ያመነ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡ በወንጀል በተከሰሰ ሰዉ ላይ የሚሰጥ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በተከሳሹ ሕይወት እና/ወይም ነጻነት ላይ የሚፈጸም እንደመሆኑ በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ መብት በጥንቃቄ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለዚህ መብት የበለጠ ጥበቃ ለማድረግ ካለዉ ዓላማ ሕግ አዉጪዉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 134/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመስራቱ በሙሉ በማመኑ ጥፋነኛ ነኝ ብሏል ተብሎ በመዝገቡ ቢጻፍም እንኳን ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕጉ ክሱን የሚደግፍለትን ማስረጃ እንዲያቀርብና ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃዉን አቅርቦ እንዲያስረዳ ማዘዝ እንዲችል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በሕጉ ቁጥር 136 እና ተከታዮቹ መሰረት ዐቃቤ ሕግ ማስረጃዉን አቅርቦ አሰምቶ በወንጀል ክሱ ላይ የተገለጸዉን ድርጊት ወይም አል ድርጊት ተከሳሹ ስለመፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃዉን አቅርቦ ራሱን እንዲከላከል ማድረግ እንደሚገባ በሕጉ ቁጥር 141 እና 142 ስር የተደነገገዉ ያስገነዝባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በክሱ ሰርቃለች ተብሎ የተዘረዘሩትን አልባሳትና ሌሎች እቃዎች መስረቋን አምና በክሱ ሰረቀች ተብሎ የተገለጸዉን ብር 1500.00 እንዳልሰረቀችና የራሷ እንደሆነ በመግለጽ ክዳ ተከራክራለች፡፡ በዚህ ምክንያት ዐቃቤ ሕግ አመልካች የካደችዉን ምስክር አቅርቦ እንዲያስረዳ ታዞ የግል ተበዳይን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ምስክሯም የአመልካች አሰሪ መሆኗን ገልጻ በክሱ የተጠቀሰዉን የራሷን ብር አመልካች እንደሰረቀች መመስከሯን በዉሳኔዉ ላይ የሰፈረዉ የምስክሯ ቃል ያሳያል፡፡ ከዚህ በኋላ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ መርምሮና መዝኖ አመልካች ክሱን መከላከል ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ መወሰን ሲገባዉ የዐቃቤ ሕግን ምስክር ከሰማ በኋላ የክርክሩን ሂደት ወደኋላ በመመለስ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 134/1ን በመጥቀስ በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት ዉሳኔ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡ ይህም ዓለም አቀፍ እዉቅና ያለዉንና ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ የተሰጠዉን የአመልካችን የመሰማትና ክሱን የመከላከል መብት የጣሰ የክርክር አመራር ነዉ ብለናል፡፡ እንዲሁም አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስህተቱን በማረም የአመልካችን ሥነ ሥርዓታዊና ሕገ መንግስታዊ መብት ማስከበር ሲገባዉ ይግባኙን መሰረዙም ፍርድ ቤቱ ኃላፊነቱን በአግባቡ አለመወጣቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የመሰማትና ክሱን የመከላከል መብት በሚጥስ አኳኋን ክርክሩን በመምራት የሰጡት ዉሳኔ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና 10(1/ሀ) ስር በተደነገገዉ መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ዉ ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 89076 ላይ በቀን 15/09/2014ዓ/ም እና 25/09/2014 የሰጠዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔዎች እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 010609 ላይ በቀን 19/12/2014 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195(2/ሀ) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች በቀረበባት የወንጀል ክስ የተዘረዘሩትን ዕቃዎች መስረቋን ያመነች በመሆኑና በከፊል አልሰረቅኩም በማለት የካደችዉን ብር 1500.00 በተመለከተ ዐቃቤ ሕግ ምስክር አቅርቦ በማሰማት ስላስረዳ በዐቃቤ ሕግ ምስክር የተመሰከረባትን የመከላከያ ማስረጃ አቅርባ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669(2/መ) ስር እንድትከላከል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 142/1 መሰረት ወስነናል፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አስቀድሞ ያላየ ዳኛ (ችሎት) መዝገቡን በማንቀሳቀስ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት እና የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሮ ሕግን መሰረት ያደረገ ፍርድ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

## ትዕዛዝ

1. በስር ፍርድ ቤት መዝገቡ ተንቀሳቀሶ ስለዋስትና ተገቢዉ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ አመልካች የብር 500.00(አምስት መቶ ብር) ዋስ በመጥራት ወይም ለዚህ በቂ የሚሆን መያዣ በማቅረብ ወይም ገንዘቡን በማስያዝ ከዛሬ ጀምሮ ከእስር እንድትፈታ ታዟል፡፡ ለአ.አ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
2. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## 3.6 የወንጀል ድንጋጌን ፍርድ ቤት የሚለውጥበት አግባብ[159]

- የተከሰሰ ሰው ክሱን የመከላከል መሠረታዊ የሆነ መብት ያለው ሲሆን የመደመጥ መብቱ ሙሉ የሚሆነው የሚከላከለውን የክስ ድንጋጌ ተለይቶ ድንጋጌው የያዘው ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ሲሆን ነው፡፡
- ተከሳሾች እንዲከላከሉ የታዘዙት በወ/ሕ/ቁ. 420/2 ሥር ሆኖ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተለወጠው የወ/ሕ/ቁ. 407/1 ሥልጣንን ያላግባብ መገልገል ወንጀል መሠረት አድርገው ጥፋተኛ መባል በተያዘው ጭብጥ መሰረት ማስረጃቸውን ያላቀረቡ በመሆኑ በተሟላ ሁኔታ ክሱን የመከላከል መብታቸው ተከብሯል የሚያስብል አይደለም፡፡[160]

የሰ/መ/ቁ 243119

ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ
ደጀኔ አያንሳ
ብርቅነሽ እሱባለው
ሀብታሙ እርቅይሁን
ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች፡-
1. አቶ ጌታቸው ሌንጮ
2. አቶ አዲሱ ቀነዓ
3. አቶ ወንድሙ በቀለ
4. አቶ ደረጀ ኢትቻ
5. ወ/ሮ ሽታዬ አያሌው
6. አቶ አያሌው ታደሰ
7. አቶ ዮናስ በለጠ

ተጠሪ ፡- የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

---

[159]በሰ/መ/ቁ 243119 (ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም)

[160]በሰ/መ/ቁ 155789 (ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 137262 (መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22፣ በሰ/መ/ቁ 43049 (ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 45595 (ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ 140253 (ታህሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 240096 (መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው ተጠሪ በአመልካቾች እና በሌሎች 3 የስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻ ግራቀኙ ማስረጃቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ የወ/ሕ/ቁ 33 እና 407/2 የተመለከተውን በመተላለፍ በጋራ በመሆን በኢሉ አባ ቦር ዞን መቱ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የአሁን አመልካቾችን ጨምሮ ሌሎች 2 የስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች በ2001 ዓ/ም ውስጥ የከተማ አስተዳደሩ የካቢኔ አባላት ሆነው የመንግስት ሥራ ሲሠሩ በነበረበት ወቅት በስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ የሆነው አቶ ከኔሳ ለገሰ ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኝ እና በመንግስት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ ከተማ አስተዳደሩ ያወጣውን መመሪያ በመጣስ በ15/11/2001 ዓ/ም ስብሰባ ተቀምጠው ቃለ ጉባዔ በመያዝ ሉሲ የሚባል ሆቴል በልማት ባንክ ዕዳ ለስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ በብር 1,500,000.00 ሲሸጥ ወደ ስሙ በነጻ እንዲዘዋወር በመወሰን እና 3ኛ አመልካች በቃለ ጉባዔ በተወሰነው ውሳኔ መሰረት በደብዳቤ ቁጥር 1346/Bu-5/2005 በ19/12/2001 ዓ/ም ለውልና እና ማስረጃ ምዝገባ ክፍል ጽፎ መንግስት ከሚደረገው የስም ዝውውር ማግኘት የሚገባውን ገቢ ብር 150,000.00 ስላሳጡ እና የስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኝ ስላደረጉ ሥልጣን አላግባብ መጠቀም የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች የፈጸምነው ወንጀል የለም በማለት ክደው በመከራከራቸው ዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፤ በክስ የተቆጠሩ ሁለት ምስክሮች በህይወት የሌሉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 145/1 መሰረት በፖሊስ ጽሕፈት ቤት የሰጡት በተጠሪ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘ ሲሆን የሰነድ ማስረጃም ተያይዟል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ድርጊቱ የተፈጸመው ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ዓላማ ነው፤ ስለዚህ አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ዓላማ ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ብለው የፈጸሙ መሆኑ ተጠሪ ባቀረባቸው ምስክሮች ቃል እስካስገነዘቡ ድረስ ደግሞ ድርጊቱ በወ/ህ/ቁ. 407/2 ስር የሚወድቅ ሳይሆን የሥራ ድርሻ ግዴታን አለመወጣት ስለሆነ በወ/ህ/ቁ. 420 ስር የሚታይ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስለዚህ አመልካቾች በመንግስት ሥራ ኃላፊነት የነበረውን በአግባቡ ባለመወጣት የመቱ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የስም ዝውውሩ እንዲፈጸም በቃለ ጉባዔ በመወሰን የስም ማዘዋዋሪያ ክፍያ ብር 150,000.00 መንግስት እንዲያጣ ማድረጋቸው በሰው ምስክሮች እና በሰነድ ማስረጃዎች ስለተረጋገጠ፣ መንግስት ያጣው ገቢ መጠን ከፍተኛ ስለሆነ ድርጊቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 113/2 መሰረት ወደ ወ/ህ/ቁ. 420/2 ክስ ከተመሰረተበት ተቀይሮ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተብሏል፡፡

አመልካቾች የመከላከያ ምስክሮች እና ከኢትዮጲያ ልማት ባንክ በ19/04/99 ዓ/ም የተጻፈው ደብዳቤ በማስረጃነት አቅርበው አሰምተዋል፡፡ የከተማው አስተዳደር ምክር ቤት የከተማውን የውስጥ ገቢ የመሰብሰብ፣ የውስጥ ገቢ ታሪፍ የመወሰን ስልጣን እንዳለው የቀረቡት የአመልካቾች ምስክሮችም ሆኑ የተጠሪ ምስክሮች በሚደጋገፍ መልኩ አስገንዝበዋል፡፡ የሆቴሉ ስመ ሀብት በነጻ ወደ ስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ እንዲዘዋወር የወሰኑት የመንግስትን ወይም የግለሰብን ጥቅም የሚጎዳ ከመሆኑ በላይ የከተማውን ማህበረሰብ ይጠቅማል በሚል ሁኔታ ኢንቨስትመንትን ማበረታታት እንደሆነ የተጠሪ ምስክሮችን ጨምሮ የቀረቡት የአመልካቾች ምስክሮች በሚደጋገፍ ሁኔታ አሳይተዋል፡፡ ኢንቨስትመንትን የማበረታታት ዓላማ በሚል የውስጥ ገቢ ታሪፍ እንዲሰበስብ የተወሰነውን የስም ዝውውር በነጻ እንዲፈጸም በማለት ይህንን ድርጊት መፈጸማቸው የቀረቡት የመከላከያ ማስረጃዎች አረጋግጧል፡፡ አመልካቾች የፈጸሙት ድርጊት በግልጽ በኢንቨስትመንት ለማበረታታት በግዢ የተገኘው ሆቴል ስም ዝውውር በነጻ እንዲደረግ የከተማው ውስጥ ገቢ ለማስተዳደርን ለመሰብሰብ በህጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል የሚሰበስበው የከተማው የውስጥ ገቢን በግልጽ በማስቀረት ነጻ ማድረግ አይችሉም በማለት በህጉ ድንጋጌ በግልጽ የተከለከለ መሆኑ ግልጽ ባይሆንም እንኳን ስልጣናቸው የውስጥ ገቢን የማስተዳደር፣ የመሰብሰብ እና ታሪፍ የመወሰን እንደሆነ ካለው ህግና መመሪያ ላይ

መገንዘብ ይቻላል፡፡ በግልጽ በከተማው አስተዳደር ካቢኔ ስልጣን የሆቴል ግዢ የፈጸመው አካል በነጻ ስም ዝውውር እንዲያደርግ በልዩ ሁኔታ ኢንቨስትመንትን ማበረታታት በሚል ምክንያት ስልጣን ያላቸው መሆኑ በህግ ሳይታይ የቀረቡ የመከላከያ ምስክሮች አመልካቾች ከፈጸሙት ድርጊት ጋር የህግ ክፍል እና የድርጊት ክፍል ከመኖሩ ውጪ የሀሳብ ክፍል ከመኖሩም በላይ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለከተማው ማህበረሰብ አስፈላጊ መሆኑን ሀሳብ ኖሯቸው ዝውውሩ በነጻ እንዲደረግ ያደረጉ መሆኑን በቀረቡት የሰው ምስክሮች አስገንዝቧል፡፡ በመሆኑም በወ/ህ/ቁ. 23/2 መሰረት የሀሳብ ክፍል ሥራቸውን በአግባቡ ባለመወጣት በመንግስትም ሆነ በግለሰብ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት እንዲከላከሉ በተባለው መሰረት አመልካቾች ለህዝብ ጥቅም ድርጊቱን የፈጸሙ መሆኑን ስለአስገነዘቡ፣ ባሲያዙት ጭብጥ መሰረት ስላረጋገጡ እና የተጠሪ ምስክሮችን ጥርጣሬ ውስጥ በሚያስገባ መልኩ ስለመሰከሩ ከክሱ በነጻ ሊሰናቱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ አመልካቾችን በነጻ ማሰናበቱ አግባብ ነው? ወይስ አይደለም? ክስ ከቀረበበት የህግ ቁጥር በመቀየር እንዲከላከሉ ማዘዙ አግባብ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦችን መዝገቡን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ ሆቴል ከባንክ ገዝቶ በነጻ ወደ ስሙ እንዲዛወርለት ቃለ ጉባዔ በመያዝ ወስነው፣ የውልና ማስረጃ ምዝገባ ክፍል በውሳኔያቸው መሰረት ወደ ግለሰቡ ስም በነጻ እንዲያዘውር ደብዳቤ ተጽፎ መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የሰው ምስክሮች እና የጽሑፍ ማስረጃ ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች ይህንን መፈጸማቸውን ክደው አልተከራከሩም፡፡ አመልካቾች በዓቃቤ ህግ ክስ ውስጥ የተገለጸውን ድርጊት መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ አንድ ተጠርጣሪ እንዲከላከል ከተባለ ነጻ ሊወጣ የሚችለው የተጠሪን ምስክሮች ቃል ጥርጣሬ ውስጥ አስገብቶ ሲገኝ ነው፡፡ በየደረጃው ያሉ የከተማው ካቢኔ ኮሚቴ ስለስም ዝውውር አስመልክቶ ማን የመንግስትን ገቢ መክፈል እንዳለበት የከተማው ካቢኔ የመወሰን ስልጣን ቢኖረው ኖሮ በሁሉም ክልል መጠኑ ተወስኖ በመመሪያ የሚወጣበት አግባብ በሌለ ነበር፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች የከተማውን የውስጥ ገቢ ማስቀረት ወይንም ክፍያውን ነጻ ለማድረግ ስልጣን ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ በግልጽ የተቀመጠ ህግ የለም እያለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ስልጣን አላቸው በማለት መርምሮ በነጻ እንዲሰናበቱ ማድረጉ የሚቃረን ስለሆነ ስህተት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ በኢንቨስትመንት ለመስራት በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት ያሟላ መሆኑ ወይም የኢንቨስትመንት ፍቃድ ያለው መሆኑ፤ የኢንቨስትመንት ህግ ባለሀብት ቤት በሚገዛበት ጊዜ ከስም ማዘዋወሪያ ክፍያ ነጻ ይሆናል ማለቱ ባልረጋገጠበት በማስረጃ የተደገፈ ሆኖ አልተገኘም፡፡

አመልካቾች በህግ ከተሰጣቸው ስልጣን ውጪ በመውጣት የስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ ለመንግስት መክፈል የሚገባውን ክፍያ እንዳይከፍል ማድረጋቸው ያለአግባብ በስልጣን የመጠቀም ወንጀል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የወ/ህግ ቁጥር 420 ተፈጻሚነት የሚኖረው ግዴታቸውን ባልተወጡ የመንግስት ሠራተኞች ላይ ነው፤ የደረሰው ጉዳት መጠን ዝቅተኛ ስለሆነ አስረጂነት ያለው ቁጥር 407/1/ለ/ መሆን አለበት፡፡ የስም ማዞሪያ ክፍያ ትክክለኛ ፐርሰንት ተለይቶ የተቀመጠ ስለሌለ ለዚህ የወንጀል ቅጣት ብቻ ፍርድ ቤቱ 4% ወስዷል፡፡ የተገዛው ቤት ግምት ደግሞ ብር 1,500,000.00 ስለሆነ 4% ብር 60,000.00 ይሆናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትን አንቀጽ ቀይሮ አመልካቾችን በነጻ ማሰናበቱ ስህተት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤትን ፍርድ በመሻር አመልካቾች በወ/ህግ ቁጥር 32/1/ሀ እና 407/1/ለ ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እና በብር 1000 እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይሕ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች በ15/06/2015 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ላይ የተከሰስንበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ

በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 113/2 በሚያዘው መሰረት ወደ ወ/ህ/ቁ 420/2 ሲቀየር ፍርድ ቤቱ መሰረት ያደረገው የተከሰስንበት ክስ ውስጥ ስልጣናችንን በግልጽ ተግባር ወይም ግድፈት ያለአግባብ የተጠቀምንበት ሳይሆን በካቢኔ ስልጣናችን መሰረት ለክሱ ምክንያት የሆነውን ፍሬ ጉዳይ በአግባቡ ባለማጣራታችን የተፈጸመ ድርጊት መሆኑን ከማስረጃው ይዘት በመረዳት የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ መባላችን ስህተት ነው፡፡ የወንጀል ህጉን ወደ ወ/ህ/ቁ 407/1 በመቀየር የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠበት አግባብ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የመከላከያ ማስረጃችንን አቅርበን ያሰማነው ከወ/ህ/ቁ 420/2 አንጻ ከተከሰስንበት የወ/ህ/ቁ 407/2 አንጻር እንዳልሆነ እየታወቀ ባልተከላከልንበት እና ክርክር ባላደረግንበት የወንጀል ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባላችን በህገ-መንግስቱ ቁጥር 20/4 ስር ከተደነገገው የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብታችንን ጭምር የነፈገ ህግ እና የህገ-መንግስታዊ ስህተት የተፈጸመበት ውሳኔ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል፡፡ የወ/ህ.ቁ 420/2 የቅጣት ጣሪያ 3 ዓመት ስለሆነ እና ክሱ የቀረበብንም ድርጊቱ ከተፈጸመ ከ13 ዓመት በኋላ ስለሆነ ተከላከሉ የተባለበትን ድንጋጌ በወ/ህጉ ቁጥር 224/1/ሐ መሰረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ተብሎ ከቀረበብን ክስ በነጻ መሰናበት ነበረብን፡፡ የስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ ሳይከፍል ቀረ የተባለው የብር 1,500,000.00 3% እንደሆነ በመከላከያ ማስረጃችን ጭምር አረጋግጠን ሳለ በመንግስት ላይ ከፍ ያለ ጉዳት እንዳደረስን ተቆጥሮ ጥፋተኛ መባላችን ስህተት ነው በማለት ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች በወ/ህ/ቁ. 407/2 ክስ ቀርቦባቸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍርድ ቤት በወ/ህ/ቁ. 420/2 መሰረት እንዲከላከሉ አዞ እና ተከላክለዋል በማለት በነጻ እንዲሰናበቱ ከወሰነ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሊከላከሉ ይገባው የነበረው በወ/ህ/ቁ. 407 ስር ነው በማለት እና በዚህ መሰረት እንዲከላከሉ ሳያደርግ በወ/ህ/ቁ. 407 መሰረት ጥፋተኛ በማለት መወሰኑ መጣራት ያለበት መሆኑን ስለታመነበት ተጠሪ የመከላከያ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪም በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በ21/07/2015 ዓ.ም የመከላከያ መልስ የሰጠ ሲሆን ይዘቱም የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካስተላላፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ላይ መገንዘብ እንደሚቻለው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍርድ ቤት የዓቃቤ ህግን ምስክሮች ከሰማ በኋላ የዓቃቤ ህግ ምስክር በወ/ህ/ቁ. 407 መሰረት ተረጋግጦ እያለ በወ/ህ/ቁ. 420/2 መሰረት እንዲከላከሉ ማዘዙ እና ተከላክለዋል በማለት በነጻ እንዲሰናበቱ ሲወስን ማስረጃ አመዛዘኑ ትክክል አይደለም፤ የተጠሪ ምስክር ያስረዳው በወ/ህ/ቁ. 407 መሰረት ሆኖ ሳለ በወ/ህ/ቁ. 420/2 ስር ተከላክለዋል በማለት በነጻ መልቀቁ ትክክል አይደለም የሚል ነው እንጂ ሊከላከሉ ይገባ የነበረው በወ/ህ/ቁ. 407 ነው በማለት እና በዚህ መሰረት እንዲከላከሉ ሳያደርግ አይደለም በወ/ህ/ቁ. 407 መሰረት ጥፋተኛ በማለት የወሰነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያሰሙትን ምስክሮች መዝኖ ስለሆነ ውሳኔ የሰጠው የአሁኑ አመልካቾች መከላከያ አቅርበው እንዲከላከሉ ለማድረግ የሚያስችለው የህግ አግባብ የለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቅጣት እንዲጸናልን ብሏል፡፡ አመልካቾች ሚያዚያ 09 ቀን 2015 ዓ/ም ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖር አለመኖሩ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ የወ/ሕ/ቁ. 33 እና 407/2 የተመለከተውን በመተላለፍ በጋራ በመሆን በኢሉ አባ ቦር ዞን መቱ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የአሁን አመልካቾችን ጨምሮ ሌሎች 2 የስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች በ2001 ዓ/ም ውስጥ የከተማ አስተዳደሩ የካቢኔ አባላት ሆነው የመንግስት ሥራ ሲሠሩ በነበረበት ወቅት በስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ የሆነው አቶ ከኔሳ ለገሰ ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኝ እና በመንግስት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ ከተማ አስተዳደሩ ያወጣውን መመሪያ በመጣስ በ15/11/2001 ዓ/ም ስብሰባ ተቀምጠው ቃለ ጉባዔ በመያዝ ሉሲ የሚባል

ሆቴል በልማት ባንክ ዕዳ ለስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ በብር 1,500,000.00 ሲሸጥ ወደ ስሙ በነጻ እንዲዘዋወር በመወሰን እና 3ኛ አመልካች በቃለ ጉባዔ በተወሰነው ውሳኔ መሰረት በደብዳቤ ቁጥር 1346/Bu-5/2005 በ19/12/2001 ዓ/ም ለውልና እና ማስረጃ ምዝገባ ክፍል ጽፎ መንግስት ከሚደረገው የስም ዝውውር ማግኘት የሚገባውን ገቢ ብር 150,000.00 ስላሳጡ እና የስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኝ ስላደረጉ ሥልጣን አላግባብ መጠቀም የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

በወንጀል ሕግ ቁጥር 23(2) መሠረት ወንጀል አድራጊ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ የወንጀሉ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር፣ የሃሳብ ክፍሉ እና ሕጋዊ ፍሬ ነገሩ ተሟልተው ሲገኙ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ሊባል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ አመልካቾች የተከሰሱበት የሙስና ወንጀል በመሆኑ በወ/ሕ/ቁ. 403 መሠረት ዐቃቤ ሕግ ግዙፋዊ ፍሬ ነገሩ መፈጸሙን ካስረዳ የሙስና ወንጀሉ የተፈጸመው ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ለማስገኘት ወይም የሌላ ሰውን መብት/ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን መዝኖ አመልካቾች የመቱ ከተማ አስተዳደር የካቢኔ አባላት ሆነው ሲሰሩ በከተማው ምክር ቤት በወጣው መመሪያና ታሪፍ መሠረት የሥም መዛወሪያ ማስከፈል ሲገባቸው የሥር 10ኛ ተከሳሽ ሆቴል ከባንክ ገዝቶ በነጻ ወደ ስሙ እንዲዛወርለት ቃለ ጉባዔ በመያዝ ወስነው፣ የውልና ማስረጃ ምዝገባ ክፍል በውሳኔያቸው መሰረት ወደ ግለሰቡ ስም በነጻ እንዲያዘውር ደብዳቤ ተጽፎ በነጻ ሥመ-ሐብቱ የተዛወረ ስለመሆኑ ተጠሪ ባቀረበው የሰው ምስክሮች እና የጽሑፍ ማስረጃ አረጋግጧል፡፡ አመልካቾች የካቢኔ አባላት በመሆናቸው የመወሰን ሥልጣን ያላቸው ሲሆን በህግ ከተሰጣቸው ስልጣን ውጪ በመውጣት የስር ፍርድ ቤት 10ኛ ተከሳሽ ለመንግስት መክፈል የሚገበውን ክፍያ እንዳይከፍል ማድረጋቸው ያለአግባብ በወ/ሕ/ቁ. 407/1 ሥር የተመለከተውን የስልጣን ያላግባብ መጠቀም ወንጀል መፈጸማቸውን ተጠሪ ያስረዳ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ተጠሪ ያስረዳው የወ/ሕ/ቁ. 407/1 ሆኖ እያለ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች በወ/ሕ/ቁ. 420/2 ሥር እንዲከላከሉ መወሰኑ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ማለቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ በመመዝን ክሱን አልተከላከሉም በማለት ጥፋተኛ ናቸው ሲል የቅጣት ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ አመልካቾችም በሰበር አቤቱታቸው የመከላከያ ማስረጃችንን አቅርበን ያሰማነው ከወ/ህ/ቁ 420/2 እንጂ ከተከሰስንበት የወ/ህ/ቁ. 407/2 አንጻር እንዳልሆነ እየታወቀ ባልተከላከልንበት እና ክርክር ባላደረግንበት የወንጀል ድንጋጌ ስር በወ/ሕ/ቁ. 407/1 ጥፋተኛ መባላችን በህገ-መንግስቱ ቁጥር 20/4 ስር ከተደነገገው የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብታችንን ጭምር የነፈገ ህግ እና የህገ-መንግስታዊ ስህተት የተፈጸመበት ውሳኔ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የተከሰሰ ሰው ክሱን የመከላከል መሠረታዊ የሆነ መብት ያለው ሲሆን የመደመጥ መብቱ ሙሉ የሚሆነው የሚከላከለውን የክስ ድንጋጌ ተለይቶ ድንጋጌው የያዘው ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ሲሆን ነው፡፡ አመልካቾች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመከላከያ ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም እንዲከላከሉ የታዘዙት በወ/ሕ/ቁ. 420/2 ሥር በመሆኑ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተለወጠው የወ/ሕ/ቁ. 407/1 ሥልጣንን ያላግባብ መገልገል ወንጀል መሠረት አድርገው ጭብጣቸውንና ማስረጃቸውን ያላቀረቡ በመሆኑ በተሟላ ሁኔታ ክሱን የመከላከል መብታቸው ተከብሯል የሚያስብል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች አመልካቾች በወ/ሕ/ቁ. 407/1 መሠረት እንዲከላከሉ እድል ሳይሰጣቸው እና ወደሥር ፍርድ ቤት ሳይመለስ በድንጋጌው ሥር ጥፋተኛ ናቸው በሚል ውሳኔ መስጠታቸው ውሳኔው የአመልካቾችን ሕገ-መንግስታዊ የመከላል መብት ያላከበረና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሀ) እና 10(1)(ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 420585 ታህሳስ 10 ቀን 2015 ዓ/ም፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 389508 ሕዳር 27 ቀን 2015 ዓ/ም እና የኢሉ አባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32181 ግንቦት 05 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

2. አመልካቾች በወ/ሕ/ቁ. 32(1)(ሀ) እና 407(1)(ለ) ሥር ሥልጣንን ያላግባብ መገልገል ወንጀል ሊከላከሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

3. የኢሉ አባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች እንዲከላሉ በታዘዙበት ድንጋጌ ሥር የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ በጉዳዩ በሌላ ችሎት/ቀድሞ ጉዳዩን ባላዩት ዳኞች የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሠናል፡፡

**ትዕዛዝ**

- አመልካቾች ጉዳዩ በሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ተንቀሳቅሶ እስከሚታይ ድረስ ጸንቶ የሚቆይ እያንዳንዳቸው ብር 5,000.00/አምስት ሺህ ብር/ ገንዘቡን ሲያሲዙ ወይም ለገንዘቡ የሚበቃ በቂ የሰው ዋስ ወይም ንብረት ሲያቀርቡብ ከእስር እንዲፈቱ አዘናል፡፡ ይጻፍ
- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የኢሉ አባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲያስፈጽም አናል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

## ክፍል አራት

### የወንጀል ክስ ማስረጃ አቀራረብ እና ምዘና[161]

- የወንጀል ክስ ያቀረበ ከሳሽ ጉዳዩን የማስረዳት ግዴታና ሃላፊነት ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰንም የመጀመሪያው የማነጻጸሪያና መመዘኛ መስፈርት ራሱ ከሳሽ ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡
- የከሳሽ ማስረጃ እርስ በእርስ የማይደጋገፍና በክሱ የተገለጸውን ፍሬ ጉዳይ የማያረጋግጥ በተቀራኒው የከሳሽ ማስረጃና በክሱ የተገለጸው ፍሬ ጉዳይ በሌላ የከሳሽ ማስረጃ እውነትነት የሌለው መሆኑ በተገለጸ ጊዜ ከሳሽ ክሱን የማስረዳት ግዴታና ሀላፊነቱን በአግባቡ ተወጥቷል ከሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡
- አንድ ማስረጃ ሊመረመር እና ሊመዘን የሚገባው ከእነሙሉ ይዘቱ እንጂ ከሳሽን የሚጠቅመውን ክፍል ነጥሎ በማውጣትና ከሳሽ ካቀረበው ክስ ጋር የሚጣጣመውን የማስረጃ ክፍል ይዘት ለይቶ በመያዝ መሆን የለበትም፡፡ ምስክር የሰጠው ቃል እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ምስክሩ ቃለ መሃላ መፈፀሙ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የምስክሩ ቃል ተዓማኒነት ያለው መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፡፡[162]

---

[161]በሰ/መ/ቁ 51706 (ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅጽ 10

[162]በሰ/መ/ቁ 241561 (ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 100712 (መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ በሰ/መ/ቁ 66767 (ሐምሌ 28 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ 240622 (ሰኔ 2 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 95921 (ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 100860 (ሐምሌ 15 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 111742 (ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 89640 (መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 6፣ በሰ/መ/ቁ 92141 (መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ በሰ/መ/ቁ 75922 (ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 75980

የሰ/መ/ቁ 51706

ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ትኩ - ከማረሚያ ቤት ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45521 ጥቅምት 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ጥር 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ መጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 በመተላለፉ ሁለት ወንጀሎችን እንደፈፀመ በመግለጽ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ከአቶ መሐመድ ኑር በአቶ ዮናስ ገብርአብ በኩል ብር 2,300(ሁለት ሺህ ሦስት መቶ) ጉቦ ተቀብሏል ተብሎ የተከሰሰበትን ወንጀል ተጠሪ እንደ ክሱ አቀራረብ ባለማሥረዳቱ አመልካች በከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲያሰናበት ብይን በመስጠቱና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን ለይግባኝ ሰሚ ችሎት የፀና በመሆኑ በዚህ መዝገብ የግራ ቀኙ የመከራከሪያ ጭብጥ ሆኖ አልተያዘም፡፡

---

(ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 245494 (ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 226651 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 45595 (ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ 64813 (ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 225975 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 228692 (ሕዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ 217634 (ታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 222478 (ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 223573 (ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 224338 (ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 224533 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፤ የሰ/መ/ቁ 225720 (ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 227851 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፤ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 109441 (ጥር 17 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19፣ የሰ/መ/ቁ 89676 (ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 35697 (ጥቅምት 20 ቀን 2000ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ የሰ/መ/ቁ 138244 (ታህሳስ 27 ቀን 2010ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 140253 (ታህሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 78470 (ሚያዚያ 7 ቀን 2005ዓ.ም) ቅፅ 15 ፣ የሰ/መ/ቁ 212950 (ሕዳር 30 ቀን 2014ዓ.ም) ቅፅ 27፣ የሰ/መ/ቁ 208644 /208645 (ጥቅምት 26 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 26፣ የሰ/መ/ቁ 137545 (መስከረም 30 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ/መ/ቁ 113143 (መጋቢት 30 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 20፣ የሰ/መ/ቁ 111498 (የካቲት 25 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 19፣ የሰ/መ/ቁ 113464 (ሕዳር 22 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 19

በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሆኖ ሲሰራ በልደታ ምድብ በመዝገብ ቁጥር 03453 እነ ካልዩ ኡመር በሚል በሚጠራው ፋይል ተከሳሽ የሆኑት አቶ አልዩ ኡመር ጉዳዩ እንዲወሰንለት ከፈለገ ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ይክፈል በማለት አብረሐም ገብረክርስቶስ በተባለ አደራዳሪ አማካኝነት ጉቦ እንዲሰጠው በመጠየቅ የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ተጠሪ የቀረበውን ማስረጃ የአመልካችን መከላከያ ማስረጃና በፍርድ ቤት ተጣርተው እንዲቀርቡ የተደረጉ ማስረጃዎችን በመመርመር የከፍተኛው ፍርድ አመልካች በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ውሣኔ ተጠሪ በይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በሥር የተደረገው ክርክር መሰረታዊ ይዘት ስንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀረበውን አንደኛ ክስ ለማስረዳት ሶስት ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አንደኛውን ለማስረዳት የቀረበው የመጀመሪያው የተጠሪ ምስክር ለተጠሪ የወንጀል ክስ በግል ተበዳይነት ስማቸው የተጠቀሰው አቶ ኡመር አልዩ ናቸው፡፡ ምስክሩ 1989 ዓ.ም በሊዝ ቦታ ገዝቶ የነበረ ቢሆንም በፍርድ ቤት ክርክር የነበረበት በመጀመሪያ ጉዳዩን የያዙት ዳኛ ሌላ ዳኛ የነበሩ መሆኑንና አመልካች ጉዳዩን የያዙት ዳኛ በእድገት ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከተዛወሩ በኋላ ማየት እንደጀመሩ ጉዳዩ ስለተጓተተብኝ ጉዳዩን ብርሃኑ ለተባለ ጠበቃ እንዳማከሩትና ጠበቃውም አብርሃም ገብረክርስቶስ የሚባለውን የተጠሪ ምስክር አመልካችን ስለሚያውቀው ይጨርስልሐል ብሎ ያማከረው መሆኑን አስረድቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ምስክሩ ሌላውን የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ ደውሎ ለሆነ ጉዳይ እፈልግሐለሁ እንዳለውና ጉዳዩን ለመወሰን ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ) አመልካች እንደሚፈልግ አብርሃም ገብረክርስቶስ የነገረው መሆኑን፣ ከአመልካች ቢሮ በመሄድ ገንዘቡ ስለሚበዛ እንዲቀንስለት እንደጠየቀው አመልካችም ስልክህን ስጠኝ እደውልልሃለሁ በማለት እንደጠየቀውና ምስክሩ ስልኩን ሰጥቶት እንደወጣ መስክሯል፡፡ ምስክሩ ከዚህ በኋላ ግንቦት 23 ቀን 1999 የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር እንዳመለከተ ገልፆአል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ስልክ ደውሎ ተዘጋጅተሐል ወይ ብሎ እንደጠየቀውና ደሴ ሆቴል አካባቢ እንዲመጣ እንደነገረው ምስክሩም ለአመልካች መልሶ ስልክ እንደደወለለትና ደሴ ሆቴል ሄዶ እየጠበቀው እንዳለ አመልካች ስልክ ደውሎ ቆዳ ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ ለለበሰ ሰው እንዲልክ የነገረው መሆኑን ምስክሩም በተነገረው ምልክት መሰረት የተላከውን ሰው ደሴ ሆቴል አግኝቶ ሰላሣ ሺህ ብር እንደሰጠው መሥክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምስክሩ በዚያው እለት ገንዘቡን ሰጥቶ ተመልሶ ቂራ አካባቢ እንደደረሰ አመልካች ስልክ ደውሎ ገንዘቡ ለምን ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ)እንደቀነሰ እንደጠየቀውና አስር ሺህ ብር ካልጨመረ እንደማያስወስንለት የስጠው ገንዘብ እንደማይመለስ የገለፁለት መሆኑን ምስክሩም በሐሳቡ በመስማማት ቀደም ብሎ 30,000 (ሰላሳ ሺህ ብሩን) የተቀበለው ሰው ደውሎለት ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) እንደሰጠ መሥክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ምስክሩ ገንዘቡን የተቀበለውን ሰው አግኝቶት ዓለም ባንክ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ወደሚገኘው የተከሳሹ (አመልካች) መኖሪያ ቤት ውሣኔ ከመስጠቱ ከአንድ ቀን በፊት በግምት ከዘጠኝ እስከ አስር ሰዓት ባለው ጊዜ ሄደው አመልካች ከቤቱ ወጥቶ ተቀብሏቸው መኪና ውስጥ እንደገባ ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) ምክስሩን ከዚህ በፊት ገንዘብ ለተቀበለው ሰው እንደሰጠና ሰውየውም ተቀብሎ ለአመልካች እንደሰጠው ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ እንደሰጠው ከዚህ በኋላ ለሥነ- ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት እንዳደረገ መሥክሯል፡፡ አመልካች ለተጠሪ ምስክር ኡመር አልዩ ይደውልላቸው የነበረው ቁጥራቸው 0911-18-54-60 እና 0911-64-14-31 በሆኑ የሞባይል ስልኮች እንደነበርና የምስክሩ የሞባይል ስልክ ቁጥር 0911-20-00-79 መሆኑን አስረድተው የተመለሱ መሆኑን ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀረበውን አንደኛ ክስ ለማስረዳት አቅርቦ በምስክርነት የሰማው አቶ አስማረ ገበየሁን ሲሆን አመልካችን ከተጠሪ ምስክር አብርሃም ጋር ያስተዋወቀው መሆኑን ከዚያ በኋላ ለአራት ወራት ለመስክ ሥራ መሄዱንና ከመስክ ሲመለስ አብርሃም አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ጠይቋል በሚል ምርመራ እየተጣራበት መሆኑን ሲነግረው በመደናገጥ ለአመልካች ደውሎ የሰማውን ሲነግረው አመልካች በመቆጣት መረጃው ሐሰተኛ መሆኑን የማያውቀው ነገር ውስጥ እንዳይገባ እንደነገረው መስክሯል፡፡ ይኸው ምስክር አብርሃምን በመጠራጠር መረጃው የመነጨው ከእሱ አለመሆኑን ተከሳሹን (አመልካችን) ለማሣመን እንድችል አብርሃም መረጃውን በድጋሚ እንድነግረው በማድረግ የአብርሃምን ንግግር በሞባይል ቀድቶ ለአመልካች እንዳሰማው አመልካች አብርሃም ወስላታ ነው አትመነው እዳለውና ከዚህ በኋላ አብርሃምን ያላየኸውን ያልሰማኸውን የምታወራው ለምንድን ነው ሁለተኛ አትደውል ብሎ የነገረው መሆኑንና የአመልካችና የአብርሃም ግንኙነት እንደተቋረጠ መሥክሯል፡፡ አብርሃምን የቀዳው አብርሃም ሣያውቅ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የፀረ ሙስና ኮሚሽን መርማሪዎች ጠይቀው ሞባይል ውስጥ የነበረውን ንግግር ቅጅ ወስደዋል በማለት የመሠከረ፡፡

የተጠሪ የመጨረሻው ምስክር አቶ አብርሃም ገ/ክርስቶስ ሲሆን ይኸው ምስክር አመልካችን ቀደም ብሎ እንደሚያውቀውና አስማረ ገበየሁ የተጠሪ ምስክር አመልካችን እንዳስተዋወቀው ከገለፀ በኋላ መሐመድ የሚባል የተጠሪ የመጀመሪያ ምስክር የሆኑት የአቶ ዑመር አልዬ ልጅ ጋር ቀደም ሲል ጓደኝነት የነበረው መሆኑንና መሐመድ የሚባለው የዑመር አልዬ ልጅ አሁን አሜሪካን አገር የሚኖር መሆኑን ከገለፀ በኋላ መሐመድ የእኔና የአመልካች ጓደኛሞች መሆናችንን ያውቅ ስለነበር በመጀመሪያ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ አመልካች የያዘው ጉዳይ እንዳለው ሲነግረው የእኔና የአመልካች ግንኙነት ንፁህ ጓደኝነት ነው ብሎ እንደመለሰለትና በዳኝነት በያዘው ጉዳይ ማነጋገር እንደማይፈልግ እንደገለፁለት ይህንን ጉዳይ ሁለተኛ እንዳያነሳበት በመግለጽ እንደመለሱለት መሥክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ ልጅ መሐመድ ከአሜሪካን አገር ደውሎ የጓደኛህ በችሎት ላይ እየሰደበው አባቴን አሞታል በማለት የነገረው መሆኑንና እሱም ለማጣራት ለአቶ ዑመር አልዬ ሲደውል ጓደኛህ ከባለጋራዎቼ ፊት በችሎት ስለሰደበኝ በዚህ ምክንያት ታምሜአለሁ ብሎ የነገረው መሆኑን ገልጿል፡፡ ይኸው ምስክር ይህንኑ ጉዳይ ደውሎ ለአመልካች እንደነገረውና ለአመልካች ስም ጥሩ እንዳልሆነ እንደገለፁለት አመልካችም አቶ ዑመር አልዬ ጉዳያቸው በተለየ መልኩ የተያዘ አስመስለው ችሎት ላይ ኦቨር አክት በማድረጋቸው እንደተቆጣቸው የገለፁለትና ቢሮ ላካቸው አነጋግራቸዋለሁ እንዳለ መስክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ አመልካች ቢሮ በመሄድ እንዳነጋግራቸው ጉዳዩን አመልካች በብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሊይዝልኝ ነው በማለት አቶ ዑመር እንደነገሩትና ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው የለኝም ብሎ ምስክሩ አቶ ዑመርን እንደመለሰስላቸውና ስለዚህ ጉዳይ አመልካችን እንዳልጠየቀው አቶ ዑመር አልዬ ቤት ሲመጣ የለም ብለው እንዲመልሱት ለቤተሰቦቹ መናገራቸው ስልኩንም ማንሣቱን በማቆም ግንኙነቱ እንዳቋረጥ ከአቶ ዑመር አልዬ ጋር የሚከራከሩት ሙክታርና ሴኮ የሚባሉ ወንድማማቾች አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተቀብሎ ሊወስንብን ስለሆነ አመልካችን አናግርልን ብለው የጠየቁት መሆኑንና አመልካች ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ የነበረ በመሆኑ ለአመልካች እንዳልነገረው መመሥከሩን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል ተጠሪ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 03453 በዳኝነት ተሰይሞ የነበረውና ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አስማረ ገበየሁ የተባለው የተጠሪ ምስክርና አብርሃም ገብረክርስቶስ የተባለው የተጠሪ ምስክር የተለዋወጡትን ንግግር ቅጅ የያዘ ሲዲ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ አመልካች አምስት የመከላከያ ምስክሮች ቃል ያሰማ ሲሆን ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች የመዝገብ ቁጥር 05016 የሰጠው ውሣኔ እንዲያያዝለት አድርጓል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ እና በአመልካች መካከል የስልክ ልውውጥ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚያዝያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም በተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬና በአመልካች መካከል የተደረገ የስልክ ጥሪ መኖሩን አጣርቶ እንዲልክ ለቴሌኮሚኒኬሽን ተደጋጋሚ ትእዛዝ ሰጥቶ መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሸኝ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ ስድስት ገጽ ማስረጃ ተልኮለታል፡፡ ክቴሌኮሚኒኬሽን በተላከው ደብዳቤ መሰረት የአመልካች ስልክ ነው በማለት የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ቁጥራቸውን የገለፃቸው ሞባይሎች ቁጥር 0911-18-54-60 የሆነው በአቶ ሰይድ አደም ዑመር ስም ቁጥሩ 0911-64-14-31 የሆነው በአመልካች ስም ያሉ መሆኑን ተረጋግጧል ከዚህ በተጨማሪ፡፡

- የተጠሪ ምስክር የሆነው የአቶ ዑመር አልዬ ነው የተባለው ቁጥሩ 0911-20-00-79 እና የአመልካች ስልክ ናቸው በተባሉት ቁጥራቸው 0911-18-54-60 እና 0911 40-90-99 መካከል የተደረገ የስልክ ግንኙነት ፍርድ ቤቱ በጠየቀው ጊዜ ውስጥ አለመኖሩንና ከተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ስልክ ነው በተባለው ቁጥር 0911-20-00-79 የተከሳሹ ስልክ ነው ወደተባለው ቁጥሩ 0911-64-14-31 ወደሆነው ሞባይል በፈረንጆች አቆጣጠር ጁላይ 8 ቀን 2007 ዓ.ም አንድ ጥሪ ጁላይ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ሁለት ጥሪዎች በድምሩ ሶስት ጥሪዎች መደረጋቸው ተረጋግጧል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ የተከሳሽ ነው ከተባለው ቁጥሩ 0911 64-14-31 ከሆነው ሞባይል የተጠሪ ምስክር የአቶ ዑመር አልዬ ስልክ ነው ወደተባለው ቁጥሩ 0911-20-00-79 ወደሆነው ሞባይል የተደረገ የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑን በቀረበው ማስረጃ ተገልጿል፡፡ የአፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪ ምክስርና የግል ተበዳይ ነኝ የሚሉት አቶ ዑመር አልዬ አመልካች በስልክ ደውሎ ገንዘቡን እሱ በምልክት ስላከው ሰው አቀብያለሁ በማለት የሰጡት ምስክርነት ከአመልካች ወደ ተጠሪ ምስክር ስልክ የስልክ ጥሪ ያልተደረገ መሆኑ ከቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የምስክሩ ቃል ታዓማኒነት የለውም በማለት አመልካች በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 149/2/ መሰረት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ የይግባኝ ችሎቱ መዝገቡ ለአስራ ሁለት ቀጠሮዎች የተቀጠረ መሆኑ በቴሌኮሚኬሽን የመጣው መረጃ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ የሚያጠናክር ሆኖ እያለ ለጉዳዩ ግንኙነት የለውም መባሉ ተገቢ አይደለም የግል ተበዳዩ ቤቱ ድረስ መሄዳቸውን 10,000(አስር ሺ ብር) መስጠታቸው የመሰከሩ በመሆኑንና ምስክሩ እውነቱን ይመሰክራሉ ተብለው ስለሚገመቱ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ አመልካች ወንጀሉን መፈፀሙን አረጋግጦል በማለት አመልካች በክሱ የተጠቀሰበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብሎ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ጥር 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ሸክም አልተወጣም፡፡ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ ወንጀሉን አለመፈፀሜን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት ውሣኔ የሰጠው በአቃቤ ሕግ ምስክሮች የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ መሰረት በማድረግ ሣይሆን የራሱን የሕሊና ግምት በውሰድ ነው፡፡ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ እና ወንጀሉን የፈፀምኩ ስለመሆኔ ለማቋቋም ብቃት የሌላቸው ናቸው የተጠሪ ምስክር ከግል የነበራቸውን ጥላቻ መነሻ በማድረግ በሰጡት የሐሰት ምስክርነት መነሻ በማድረግ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የቅጣት ውሣኔም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ያገናዘበ አይደለም የሚል ይዘት ያለው አስራዘጠኝ ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሰበር ችሎቱን የሚጠይቀው የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ስህተት

እንዲታረምለት ነው፡፡ አመልካች የግል ተበዳዩን ከአስራ ሁለት ቀጠሮ በላይ በማጉላላት የግል ተበዳይ ጉቦ እንዲሰጧቸው ያስገደዷቸው መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለህሊና ግምት ሣይሆን በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ መሰረት በማድረግ የስጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው ሰፊ የቃል ክርክር አቅርቧል አመልካች በቃል ክርክሩ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የግራ ቀኙ መካከል በሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ክርክርና በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃ ይዘት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማስረጃ ተዓማኒነት በመመርመር ረገድ በመለያየት የሰጡት የተለያየ ፍርድ ይዘትና በሰበር አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት የፈፀሙ ስለመሆኑ በሕግ የተጣለበትን ሸክም ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚለውን ጭብጥ በወንጀል ጉዳይ ተከራካሪዎች ስላለባቸው የማስረዳት ግዴታ ኃላፊነት (Burden of proof) ፍርድ ቤቶች የተከራካሪዎቹን ማስረጃ ታዓማኒነት በሚመረምሩበት ወቅት ሊከተላቸው የሚገባቸውን መሰረታዊ የማስረጃ ሕግ መርሆችንና ሌሎች አግባባነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የከሳሽ(ተጠሪ) የማስረዳት ሸክምና ኃላፊነት የሚወጣው በምን ሁኔታ ነው? የሚለውንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦች መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ አንድ ተከራካሪ የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል ወይም አልተወጣም የሚለው ጭብጥ ለመወሰን የመጀመሪያው ማነፃፀሪያ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ለመመለሥ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና የመመዘን ሥልጣንና ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ሰጭ አካላት በትኩረት ሊመረምሩት የሚገባውን ጉዳይ ለማየት ያስችላል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ወንጀል ፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ የቀረበ ተከሳሽ የወንጀሉ ድርጊት ስለመፈፀሙ ብቻ ሣይሆን ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜ ወንጀሉ እንዴት እንደተፈፀመና ወንጀሉ በእነማን እንደተፈፀመ ዝርዝር ሁኔታዎችን ግልጽ በሚያደርግ መንገድ የማቅረብ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርአትም አንድ የወንጀል ክስ ውስጥ የጥ ሊገለፁ የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥ ቁጥር 111 ተደንግጓል፡፡
   የወንጀል ክስ የቀረበ ከሳሽ ጉዳዩን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይም አልተወጣም? የሚለው ጭብጥ ለመወሰን የመጀመሪያው የማነፃፀሪያና የመመዘኛ መስፈርት ራሱ ከሳሽ ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አንድ ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን በመግለጽ ክስ ያቀረበ ወገን በክሱ የገለፀውን ፍሬ ጉዳይ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት የሚለወ ነው ሕግ መ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ ጉዳዩን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚለው ነጥብ እልባት የሚሰጠው ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ውስጥ የተገለፁትን ፍሬ ጉዳዮች ትክክለኛነት ተጠሪ የወንጀል ክሱን ለማስረዳት ባቀረባቸው የተለያዩ ማስረጃዎች የሚያረጋግጡና የወንጀል ክሱ ውስጥ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይና ክሱን ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና ተያያዥነት ያላቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ በአጠቃላይ ካሳሽ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ለጉዳዩ ያላቸው አግባብነት (Relevancy of Evidence) እና የከሳሽ ማስረጃ የአስረጅነት ዋጋ ያላቸውና ታዓማኒነት ያላቸው መሆኑ የሚመረመረው ከሳሽ በወንጀል ክስ ማመልከቻው የገለፃቸውን ፍሬ ጉዳዮች መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ተጠሪም ክሱን የማስረዳት ሸክሙን (ክሱን የማስረዳት ግዴታውን) የተወጣ መሆኑ ወይም አለመሆኑ መመርመር ያለበት ተጠሪ በክሱ ማመልከቻው የገለፃቸውን ፍሬ ጉዳዮች እውነት

መሆናቸውን በተጠሪ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑንና ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተደጋጋፊ እና እርስ በርሳቸው የማይቃረኑ መሆናቸውን መሰረት በማድረግ ማስረጃዎቹን በመመርመር ነው፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት ተመሣሣይ ይዘት ያላቸውን ማስረጃዎች ታዓማኒነት አስመልስቶ የተለያዩበት ዋናው ምክንያት የተጠሪ ማስረጃዎች እውነተኛ መሆናቸው መመርመር ያለበት ከምን አንፃር ነው በሚለው መስፈርት ላይ ከተጠሪ ክስ አንፃር ባለመመርመራቸው ነው፡፡ ተጠሪ በክሱ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተውን በመተላለፍ በሐምሌ ወር 1999 በመዝገብ ቁጥር ቁጥር 03453 ተከራካሪ የነበሩትን አቶ ዑመር አልዬ (የተጠሪ ምስክር) ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) ይክፈል በማለት በሶስተኛ የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ በተባለ አደራዳሪ በኩል ጠይቋል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡

የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ በተባለ አደራዳሪ በኩል ጉቦ ጠይቋል የሚል ክስ የተጠሪ ክስ አመልካች በአብርሃም ገብረክርስቶስ በኩ ጉቦ ጠደ ከይቋል በሚል ሲሆን የግል ተበዳዩና አንደኛ ተጠሪ ምስክር አብርሃም እንዲያነጋግርልኝ አድርጌ ብር 50,000(ሃምሣ ሺህ ብር) አምጣ ተብለሐል ብሎ ነገረኝ በማለት የመሰከረ ሲሆን በወንጀል ክሱ አደራዳሪና ጉቦ ለአመልካች የተ የተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳዩ እንዲሰጥ ጠየቀ የተባለው ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር አብርሃም ም ገብረክርስቶስ አመልካች የግል ተበዳይ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) ይሰጠኝ ብሎ ያልጠየቀው በመሆኑ በተቃራኒው አመልካች ስለስለያዘው ጉዳይ የአቃቤ ሕግ ምስክር የሆነው የግል ተበዳይ እንዳያነሳበት እንደነገረው የአቶ ዑመር አልዬ አሜሪካን አገር የሚኖር መሐመድ የተባለ ልጅ አባቴን ጓደኛህ በድሎት ታሞ ተኝቷል ብሎ እንደደወለለት እሱም ወደ ወደ አቶ ዑመር አልዬ ስልክ ሲደውል ከባለጋራዎቼ ፊት ሰደበኝ አዋረደኝ በዚህ ምክንያት ታምሜአለሁ ብለ ለው እንደነገሩት እሱም አመልካችን ለስሙ ጥሩ እንዳልሆነና የተባለውን ስነግረው ምስክሩ በችሎ ችሎት ከሥ ሥርአት ወጥተው ስለነበር እንደተናገራቸውና ቢሮ ላካቸው አነጋግራቸዋለሁ በማለት እንደነገረውና የተጠሪ አንደኛ ምስክር ዑመር አልዬ ከአመልካች ቢሮው ውስጥ እንዳነጋገራቸውና በብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሊሰራሪ ራልኝ ተስማምተናል ብለው እንደነገሩት አብርሃም ገብረክርስቶስ ስለዚህ የሚያውቀው የሌለ መሆኑን ገልፆ ከግል ተበዳይ ጋር የነበረውን ግንኙነት እንዳቋረጠ መሥክሯል፡፡ በሌላ ጊዜ ከተጠሪ አንደኛ ምስክር ጋር የሚከራከሩ ሰዎች አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተቀብሎ ሊፈርድብን ነው ብለው እንደነገሩት መሥክሯል፡፡

ተጠሪ በክሱ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ "አመልካች በአብርሃም ገብረክርስቶስ በኩል ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ጉቦ እንድሰጠው የግል ተበዳይ ዑመር አልዬን መጠየቁን ያስረዳልኛል" በማለት ያቀረበው የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ አመልካች በዚህ አይነት ጥያቄ ያላቀረበለትን የግል ተበዳዩ ሰደበኝ ብሎ ስሞታ ከተናገረ በኋላ ቢሮው ሄዶ እንዲያነጋግረው ከተደረገ በኋላ በብር 50,000(ሃምሳ ሽህ ብር) ሊይዝልኝ ተስማምተናል በማለት የግል ተበዳይ ራሱ ለተጠሪ ምስክር አብርሃም እንደነገረው መስክሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ያቀረባቸው ምስክሮች ዕርስ በርሱ የሚቃረን ማስረጃ (contradictory evidence) የሰጡ መሆናቸውን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጠሪ ማስረጃ ዕርስ በርሱ የሚደጋገፍና በክሱ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ የማያረጋግጥ በሆነ ጊዜና በተቃራኒው የተጠሪ ማስረጃና በክስ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ በሌላ የተጠሪ ማስረጃ እውነትነት የሌለው መሆኑ በተገለፀ ጊዜ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነትቱን በአግባቡ ተወጥቷል ከሚል መደመደሚያ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ክስ የተገለፀውንና በግል ተበዳይ የተሰጠውን የምስክርነት ቃል

ተጠሪ ክሴን ያስረዳልኛል በማለት ባቀረበው አብርሃም ገብረክርስቶስ በሰጠው የምስክርነት ቃል እውነትነት የሌለው መሆኑ የተገለፀ ሆኖ እያለ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ተጠሪ ባቀረበው ክስና በተጠሪ አንደኛ ምስክር ቃልና በተጠሪ ሶስተኛ ምስክር ቃል መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት በማየት ሣይመረምር ማለፉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ይህ ጉዳይ የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጅ የሕግ ስህተት አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

1. ተጠሪ አመልካች በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት በአጥጋቢ ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 141 እና 149 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል የሚባለው ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ታዓማኒነት ያላቸውና ክሱን ለማስረዳት የሚችል ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ የማስረጃ ታዓማኒነት የሚለካው ማስረጃው በይዘቱ ወጥነት ያለውና ዕርስ በርሱ የሚፋለሱ ፍሬ ጉዳዮችን ያልያዘ መሆኑን በመመርመርና በማስረጃው የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ ያንኑ ክስ ለማስረዳት ከቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎች ጋር የሚጣጣም ተደጋጋፊና ተመሣሣይ ፍሬ ጉዳይ ለማስረዳት የሚችል መሆኑን በማገናዘብ ነው፡፡

   ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) በመዝገብ ተከራካሪ የነበሩት አቶ ዑመር አልዬ ከሶስተኛ የተጠሪ ምስክር(አብርሃም) አደራዳሪነት እንደሰጡት ጠይቋል ከማለት ውጭ አመልካች ከግል ተበዳይ ገንዘብ የተቀበለ መሆነ መቼ እንደተቀበለና በማን በኩል እንደተቀበለ የገለፀ አለመሆኑን ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ እነዚህ ነገሮች ግልጽ በማድረግ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 119 መሰረት ትእዛዝ መስጠት ነበረበት፡፡ ተጠሪ በወንጀል ክሱ በዝርዝር ያልገለፃቸው ፍሬ ጉዳዮች የግል ተበዳይና የተጠሪ ምስክር በሆኑት አቶ ዑመር አልዬ ተገልፆዋል፡፡ ይኸው ምስክር በአንድ ቀን አመልካች በራሱ ስልክ ሶስት የስልክ ጥሪ ያደረገለት መሆኑን በመጀመሪያ ተዘጋጅተሐል ወይ ብሎ እንደጠየቀውና ደሴ ሆቴል አካባቢ እንደነገረው ከዚያም ምስክሩ ወደ አመልካች ስልክ በመደወል ደሴ ሆቴል እየጠበቀው መሆኑን ነግሮት እንደዘጋ ከዚያ በኂላ አመልካች ስልክ በመደወል ቆዳ ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ ለለበሰ ሰው እንዲልክ እንደነገረው ምስክሩ በተነገረው መሰረት ደሴ ሆቴል ስውየውን አግኝቶ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) እንደሰጠው ከዚያ በኂላ ተመልሶ ወደ ቀራ አካባቢ ሲደርስ አመልካች ለሶስትኛ ጊዜ ስልክ ደውሎ ገንዘቡ ለምን ከ50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) እንደቀነስ እንደጠየቀውና አስር ሺህ ብር (10,000) ካልጨመረ እንደማይሰራለት እንደነገረው መሥክሯል፡፡ አመልካች ከግል ተበዳይና የተጠሪ ምስክር ጋር ግንኙኝነት ያደርግ የነበረው በስልክ መሆኑን የተጠሪ ምስክር ገልጿል፡፡ የተጠሪ ምስክር ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ ብር ) ማንነቱን ለማላውቀው ሰው ሌዘር ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ የለበሰ የሚል ምልክት አመልካች በስልክ ደውሎ ነግሮኝ ሰጥቻለሁ ያለበትን ቀን ሰዓት አልገለፀም፡፡ ምስክሩ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ስሙ ማንነቱ ለማይታወቅ ሰው ሰጠሁ ባሉበት ቀን ብቻ አመልካች በእሱ የስልክ ሞባይል ሶስት ጥሪያዎችን እንዳደረገላቸው መስክረዋል፡፡ ይሕ የተጠሪ ምስክር በእምነታቸው መሰረት ቃለ መሐላ ፈጽመው ለፍርድ ቤቱ የመሰከሩት እና የገለፁት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ይህንን ምስክርነት እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ምስክሩ ቃለ መሐላ መፈፀማቸው ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የምስክሩ ቃል ታዓማኒነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚያዚያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም የምስክሩ ጉዳይ ውሳኔ እስካገኘበት ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከአመልካች ወደ ምስክሩ የስልክ ጥሪ ስለመደረጉ እንዳያረጋግጥ የቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተጠይቆ እንኳንስ በአንድ ቀን አመልካች ለተጠሪ ምስክር ሶስት

ጊዜ ስልክ ሊደውል ይቅርና በሶስት ወራት ውስጥ አመልካች ለተጠሪ ምስክር ያደረገው የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ምስክሩ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ጁላይ 8 ቀን 2007 አንድ ጥሪ ጁላይ 21 ቀን 2007 ሁለት ጥሪዎች ወደ አመልካች ማድረጉ ምስክሩ ተጠሪ በቀን ሶስት ጊዜ ያሕል ደውሎ የት እንደምጠብቀው ገንዘቡን ለማን እንደምሰጥና ለምን ገንዘብ 30,000(ሰላሣ ሺህ) ሆነ አስር ሺህ ብር ጨምር በማለት አናግሮኛል በማለት የሰጠው ምስክርነት እውነት መሆኑን አያረጋግጥም፡፡ ስለዚህ የተጠሪ አንደኛ ምስክርና የግል ተበዳይ ነኝ ባዩ ዑመር አልዬ እውነት ነው በማለት ለፍርድ ቤት ስለወንጀሉ አፈፃፀም ያስረዱት ፍሬ ነገር ጭራሹኑ አመልካች የተደረገላቸው የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ምስክሩ የሰጡት ቃል ታዓማኒነት ያለው ነው በማለት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መደምደሙ አንድ ማስረጃ ሊመርመርና ሊመዘን ከነ ሙሉ ይዘቱ እን ንጂ ተከሳሹን የሚጠቅመውን ክፍል ነጥሎ በማውጣትና ከሳሽ ካቀረበው ክስ ጋር የሚጣጣመውን የማስረጃ ክፍልና ይዘት ለይቶ በመያዝ መሆን እንደማይገባው በበርካታ አገሮች ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ታዓማኒነት ምርመራና ምዘና መርህ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. በያዝነው ጉዳይ አመልካች ጋር ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተስማማን በማለት ለሶስተኛ የተጠሪ ምስክር የተናገረው የግል ተበዳይ ነኝ ያለው አቶ ዑመር አልዬ እንደሆነ ሶስተኛ ምስክር መስክሯል፡፡ ሁለተኛው የአቃቤ ሕግ ምስክር ሰማሁ የሚለው ከሶስተኛው ምስክር ከአብርሃም ነው፡፡ ለአመልካች እንዲሰጥ በመጀመጀመሪያ 30,000(ሰላሳ ሺህ ብር) ቀጥሎ አስር ሺህ ብር /10,000/ በመጨረሻ አስር ሺህ ብር /10,000/ ከአመልካች መኖሪያ ቤት ሄጀ ሰጠሁ የሚለው ማንነቱን ያልገለፀው የለበሰውን ልብስ ብቻ በምልክት ከገለፀው ሰው ጋር ነው፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ጉቦ ጠየቀኝም ጉቦ ሰጠሁትም የሚለው ወሬ ብቸኛ ምንጭ የግል ተበዳዩ ዑመር አልዬ ሲሆን ሌሎቹ የግል ተበዳይ አወራን ወይም አብርሃም ሲያወራ ሰማሁ በማለት ሁለተኛ ምስክር የመሰከረ መሆኑንና የስሚ ስሚ ማስረጃ መሆናቸው ለመገንዘብ ይችላል፡፡

አንደኛ የተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳይ አመልካች ጉቦ የጠየቀው በአብርሃም አደራዳሪነት እንደሆነ ምስክርነቱ የገለጸ ሲሆን አብርሃም የተጠሪ ምስክር ሆኖ በመቅረብ ይህ የግል ተበዳይ ምስክርነት በሚቃረን መንገድ መሥክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምስክሩ አመልካች በችሎት ሰደበኝ በሚል ምክንያት ታሞም እስከመተኛት ደርሶ የነበረ መሆኑንና ይህንን ሁኔታ የግል ተበዳይ ውጭ የሚኖር ልጅ ጭምር ሰምቶ ከውጭ አገር አብርሃምን ስልክ ደውሎ እንዳናገረው የተጠሪ ምስክር አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግል ተበዳይ ብር 30,000(ሰላሣ ሺህ ብር) ሰጠሁ ባሉበት አንድ ቀን ውስጥ ብቻ አመልካች በእሱ ስልክ ሶስት ጊዜ ደውሎ ነበር በማለት የሰጡት ምስክርነት ከሚያዚያ 1 ቀን 1999 እስከ ሐምሌ 30 1999 ጊዜ ውስጥ አመልካች ለተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳይ ዑመር አልዬ ያደረገው የስልክ ጥሪ አለመኖሩን በማረጋገጫ የቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ከሰጠው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህ ያለፈው ከተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ ቃለ መሐላ ፈጽመው የሰጡት የምስክርነት ቃል እውነት ነው ተብሎ ይገመታል በማለት ነው፡፡ ሆኖም ከላይ የተገለፁት ማስረጃዎች ምስክሩ እውነተኛ አለመሆናቸውን የሚያሣዩ ግምቱን የሚያፈርሱ መሆነን ሣይመረምር ማለፉ በራሱ ተገቢነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል አንድ ዳኛ የዳኝነት ሥራውን ከማናቸውም ሰው ጣልቃገብነት ነፃ ሆኖና ገለልተኛ ሆኖ ያከናውናል ተብሎ የሚገመት መሆኑ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ነው፡፡ ዳኛው በጉቦ ወስዷል የሚል ወገን ይህንኑ ፍሬ ጉዳይ ተዓማኒነት ያለው በቂ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ አመልካች በዳኝነት በያዘው

ጉዳይ በችሎት አዋርዶኛል፤ጉዳዩን አጓትቷል የሚል ቅሬታ ያላቸው መሆኑ ተጠሪ ምስክሬ ነው በማለት ባቀረበው አብርሃም ገብረክርስቶስ በኩል ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሰጥቻለሁ የሚለው አመልካች በዳኝነት ባየው ጉዳይ ተከራካሪ የነበረው አቶ ዑመር አልዬ ከሰጠው የምስክርነት ቃል ውጭ አመልካች ይህንን ገንዘብ መቀበሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተጠሪ አላቀበም፡፡ የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ገንዘቡን ሰጠሁ የሚሉበትና አመልካች ጠየቀኝ የሚሉበት ሁኔታ በተለይ አመልካች ስልክ ደውሎ የት ቦታ እንደሚጠብቁት ከዚያም ሁለተኛ ደውሎ ገንዘቡን ለማን እንደሚሰጡ ሶስተኛ ደውሎ ገንዘቡ ለምን አነሰ ብሎ እንደጠየቃቸው የሰጡት ምስክርነት ከአመልካች ወደ ምስክሩ የተደረገ የሥልክ ጥሪ አለመኖሩ ስለተረጋገጠ እውነትነት የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይኸም የተጠሪ ምስክር የአቶ ዑመር አልዬ የምስክርነት ቃል ታዓማኒነት የሌለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ ከላይ በተገለፀው መንገድ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን አልተወጣም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በመሻር በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ1/ መሰረት ሽረናል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሰረት አጽንተናል፡፡
3. አመልካች በነፃ የተሰናበተ ስለሆነ ከእስር እንዲፈታው ለማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>4.1 የሰበር ችሎቱ ማስረጃ የመዘነበት መዛግብት[163]</u>

## <u>(የተከሳሽ የመከላከያ መስረጃ የሚመዘንበት የማስረጃ መለኪያ)[164]</u>

- ዐቃቤ ሕግ ባሰማው አግባብነት እና ተቀባይነት ባለው ማስረጃ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወይም ተቀራራቢ እና ተለዋጭ ወንጀል መፈፀሙን በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) አስረድቷል ወይስ አላስረዳም የሚለው ጭብጥ ታይቶ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተቃራኒ ማስረጃ ባይቀርብበትም ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያበቃ መሆን አለበት፡፡ እነዚህ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተከሳሽ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) ያላስረዱ እንደሆነ ተከሳሹ መከላከል ሳያስፈልገው ፍርድ ቤቱ በነፃ ያሰናብተዋል፡፡ ሆኖም ማስረጃዎቹ ተከሳሹ ወንጀሉን ለመፈፀሙ በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) ያረጋገጡበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያሰማ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
- ተከሳሹ በከባድ ወንጀል ተከሶ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በክሱ የቀረበውን ወንጀል መፈፀሙን ሳይሆን ያረጋገጠው በተለዋጭ ሊያስከስስ የሚችል አነስተኛ ወንጀል ከሆነ ፍርድ ቤቱ አንቀጹ ለውጦ በዚሁ በተረጋገጠውና በዝቅተኛው ወንጀል ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊለው ይችላል፡፡ ሌለው ተከሳሽ

---

[163]በሰ/መ/ቁ 228271 በቀን መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም እና በሰ/መ/ቁ 240096 መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም

[164]የሰ/መ/ቁ 240096 (መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ሰ/መ/ቁ 228271 (መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም) ሲሆን ጭብጥ ያልተለየለት ተመሳሳይ በመሆኑ ነው፡፡

የተከሰሳው በዋና ወንጀል አዱራጊነት ሆኖ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተከሳሽ ዋና ወንጀል አድራጊ መሆኑን ሳይሆን ተባባሪ መሆኑን ካሳዬ ፍርድ ቤት በዚሁ በተባባሪነት ጥፋተኛ ሊለው ይችላል፡፡ ተከሳሽ የተከሰሰው ወንጀል ፈጽሟል ቢባል እና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተከሳሹ በእርግጥ ወንጀሉን መፈጽሙን ሳይሆን ወንጀሉን መሞከሩን ከሆነ ያረጋገጠው ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ወንጀሉን በመሞከሩ ጥፋተኛ ሊለው ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ እነዚህ ነገሮች መኖራቸውን የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በተሰማበት ጊዜ ከሆነ ያረጋገጠው ተከሳሹ በዚሁ አንቀጽ ሥር መከላከያውን እንዲያሰማ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ትዕዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡[165]

የሰ/መ/ቁ 240096

መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡…

እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡…….. አቶ ፈይሳ ኢንሳ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡………. የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ አላግባብ ክስ የቀረበበት አንቀጽ መቀየሩን በመቃወም የቀረ የሰበር አቤቱታን የሚለከት ሆኖ መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 604(1) ተላልፏል በማለት ያቀረበውን ክስ ቤቱን ለመጠበቅ በደሞዝ ተቀጥሮ የሚሰራ መሆኑንና ቤቱንም ለቆ አለመውጣቱ የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች ስስላስረዱ አመልካች ቤቱን ሰብሮ እንዳልገባ ተስተባብሎ እያለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ የቀረበበትን አንቀጽ አላግባብ ቀይሮ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 436(ለ) ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት በብር አንድ ሺህ መቅጣቱ ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመቃወም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ መሰረዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም አመልካች ጥር 4 ቀን 2015 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩ ቤት መድፈርን የሚመለከት የወንጀል ክርስ ሲሆን ፤ ዐቃቤ ሕግ በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ይዘት፡- በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 604 (1) (ሀ) ድንጋጌን በመተላለፍ ሚያዝያ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 4፡30 ሰዓት ሲሆን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ክልል ልዩ ቦታው ሚሊኒዬም ተብሎ በሚጣራው አከባቢ የግል ተበዳይ ወ/ሮ እየሩሳሌም ከሳ በውክልና በሚያስተዳድሩት መኖሪያ ቤት ሳይፈቃድላቸው ቤቱን ሰብረው በመግባት

[165] በሰ/መ/ቁ 38161 (የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9 ፤ የሰ/መ/ቁ 91535 (የካቲት 12 ቀን 2006ዓ.ም) ቅፅ 15 ፤ የሰ/መ/ቁ 57644 (ሐምሌ 25 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12 ፤የሰ/መ/ቁ 51706 (ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10፣ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014ዓ.ም)

እየኖሩበት በመሆኑ በፈፀሙት የግል ቤት መድፈር ተከሰዋል በሚል ሲሆን፤ በአማራጭነት ደግሞ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 686(2) ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ መብት ሳይኖረው ጥቅም ለማግኘት ሲል በመጀመሪያው ክስ ላይ በተገለፀ ጊዜ እና ቦታ ወ/ሮ እየሩሳሌም ከሳ በውክልና በሚያስተዳድሩትን መኖሪያ ቤት ሰብረው በመግባት እየኖሩበት በመሆኑ በሰው ንብረት ላይ በፈፀሙት የሁከት ድርጊት ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ አመልካችም ድርጊቱን አልፈፀምኩም ፤ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ምስክሮች አመልካች የግል ተበዳይ ወ/ሮ እየሩሳሌም ከሳ በውክልና በሚያስተዳድሩትን መኖሪያ ቤት በነፃ እየጠበቀ እንዲኖርበት በ2008 ዓ.ም ገብቶ ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ዕቃውን ጭኖ ከወጣ በኋላ ሚያዝያ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ቤቱ ውስጥ ገብቶ መገኘቱን ስላስረዱ በወንጀ ሕጉ ቁጥር 604(1) (ሀ) ሥር በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 142(1) መሠረት እንዲከላከል ብይን ሰጥቶ አመልካችም ስምንት ዓመት ጥበቃ ሆኖ የሰራው ደሞዙ እንዲከፈለው ከመጠየቅ ውጪ ከቤቱ ወጥቶ ተመልሶ አለመግባቱን የመከላከያ ምስክሮቹ እንድሚያስረዱለት ጭብጥ አስይዞ አራት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አስምቷል፡፡ የመከላከያ ምስክሮቹም ቤቱን ለመጠበቅ ከ2005/2006 ዓ.ም ጀምሮ በደሞዝ ተቀጥሮ እየጠበቀ ከሚኖርበት ቤት ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም እንዳልወጣ እና ሚያዝያ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ቤቱን ሰብሮ እንዳልገባ መስክረዋል፡፡ የመከላከያ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት በዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ላይ ጥርጣሬን የፈጠረ በመሆኑ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተጠሪን ጥፋተኛ ለማሰኘት ብቃት የሌለው በመሆኑና አመልካች ባሰማዉ የመከላከያ ማስረጃ የቀረበበትን ክስ ተከላክሏል በማለት በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 149(1) መሠረት ከተከሰሰበት ክስ በነፃ አሰናብቷል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የመረመረው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቃቤ ሕግ ምስክሮች በክሱ ላይ በተመለከተው ቦታ እና ጊዜ ሳይፈቀድለት ቤት ሰብሮ የገባ መሆኑን የመሰከሩ ሲሆን ፤የአመልካች መከላከያ ምስክሮች በከሱ የተመለከተው ቤት የአመልካች አለመሆኑን ፤በጥበቃ ተቀጥሮ የሚሰራ መሆኑንና አመልካች ቤቱን ለቆ እንድወጣ ተነግሮት ያልወጣበት ምክንያት ሊከፈረው የሚገባው ክፍያ ስላልተከፈለው መሆኑን መስክረዋል፡፡ አመልካች ቤቱ ሰብሮ ገብቶ መኖሩ በመከላከያ ምስክር የተስተባበለ ቢሆንም እንኳን አመልካች የያዘው ቤት የግሉ አለመሆኑ ፤ እንዲወጣ መታዘዙ እና የእርሱ ገንዘብ ከባለቤቱ ስላሌው ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሆኖእያለ አመልካች ሙሉ በሙሉ ተከላክሏል ተብሎ በነፃ መሰናበቱ ተገቢነት የሌለው በመሆኑና የማስረጃ ሚዘና መርህን ያላገናዘበ በመሆኑ አመልካች በተከሰሰበት ወንጅል ጥፋተኛ ባይባል እንኳን መብትን በሕግ ወጥ መንገድ በማስከበር ወንጀል ሕጉ አንቀጽ 436(ለ) ጥፋተኛ ሊባል ይገባል በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር በ1,000.00(አንድ ሺ.ህ) ብር እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 195(1) መሠረት የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶቹ ፍርድ እና ውሳኔ መሠራተዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ በሰጠው መልስ፡- በሥር ፍርድ ቤት ቀርበው የተሰሙት ምስክሮች እንደ ክሱ አቀራረብ አስረድተዋል፡፡ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ይዘት አመልካች ቀድም ሲል በቤቱ ውስጥ የሚኖር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አመልካችም የጥበቃ ሥራ ከሚሰራበት ቤት አልወጣም ማለቱን ክዶ ያልተከራከረ በመሆኑ አለኝ የሚለውን መብት በሕጉ አግባብ ማስጠበቅ ሲገባው በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት ሳይኖረው አለቅም ማለቱ አግባብ ባለመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 436(ሐ) ሥር ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ በመሆኑ ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ ሊፀና አመልካችም በመልስ መልስ ክርክራቸው

ባልተከሰስኩበት እና ባልተከራከርኩበት አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ነህ ማለቱ ሕግ ስህተት ነው በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ዝርዝር ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፊ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(2) የተከሰሱ ሰዎች ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት እንዳላቸው ስለሚደነግግ በደንብ መተላፍ ችሎቱ በያዘው መዝገብ ቅጣት መወሰን በሚችልባቸው የችሎት መድፈር ወንጀሎች ውጪ ያሉ ጉዳዮች ሁሉ ክሱ በጽሁፍ ከልቀረበ በቀር ጉዳይ ሊታይ እንደማይችል እና የክሱ ግልባጭ በነፃ ለተከሳሹ እንደሚሰጥ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 108(1) (2) እና ቁጥር 109(4) ይደነግጋል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ክስ ተፈፀመ የተባለውን ወንጀል የሚያቋቁሙ ሕጋዊ ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድ ላይ ተጣምሮ መገኘታቸውንና የወንጀሉን አፈፃፀም ሁኔታ መግለጽ አለበት፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ተከሳሽ የተከከሰበት ድርጊት ወንጀል መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል ፣ ተከሻሹም የቀረበበትን ክስ እንዲረዳ እና በአግባቡ መከላከያውን ማቅረብ እንዲችል እና ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ሕግ ተፈፀመ የተባለውን የወንጀል ድርጊት የማስረዳት ግዴታውን ለመመዘን እንዲያስችለው ነው፡፡ (በሰበር መዝገብ ቁጥር 38161 ፣ 91535 ፣ 57644 ፣ 51706 የተሰጡ አስገዳጅ ውሳኔዎችን ይመለከቷል፡፡)

አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ወይንም የተከሰሰ ሰው በፍርድ ቤት የወንጀል ጥፋተኛነቱ እስክረጋገጥ ድረስ እንደወንጀለኛ ያለመቆጠር ሕግ መንግስታዊ መብት አለው፡፡ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 20(3)) የዚህ ሕግ መንግስታዊ መብት አፈፃፀም መግለጫ ባህሪያት በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው የተከሳሹ አያያዝ ሁኔታ ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ እስከሚባል ድረስ ነፃ እንደሆነ የመቆጠር መብት ሲሆን ፣ ሁለተኛው ተከሳሽ የከሰሰበትን ወንጀል የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮችን በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ)(standard of proof) የማስረዳት የዐቃቤ ሕግ ግዴታ መሆኑን ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ ባሰማው አግባብነት እና ተቀባይነት ባለው ማስረጃ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወይም ተቀራራቢ እና ተለዋጭ ወንጀል መፈፀሙን በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) አስረድቷል ወይስ አላስረዳም የሚለው ጭብጥ ታይቶ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተቃራኒ ማስረጃ ባይቀርብበትም ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያበቃ መሆን አለበት፡፡ እነዚህ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተከሳሽ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) ያላስረዱ እንደሆነ ተከሳሹ መከላከል ሳያስፈልገው ፍርድ ቤቱ በነፃ ያሰናብተዋል፡፡ ሆኖም ማስረጃዎቹ ተከሳሹ ወንጀሉን ለመፈፀሙ በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) ያረጋገጡበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያሰማ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

ከዚህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት ጉዳይ ተከሳሽ ተከላከል የሚባልት አንቀጽ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(2) የተከሰሱ ሰዎች ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት እንዳላቸው ስለሚደነግግ በደንብ መተላፍ ችሎቱ በያዘው መዝገብ ቅጣት መወሰን በሚችልባቸው የችሎት መድፈር ወንጀሎች ውጪ ያሉ ጉዳዮች ሁሉ ክሱ በጽሁፍ ከልቀረበ በቀር ጉዳይ ሊታይ እንደማይችል እና የክሱ ግልባጭ በነፃ ለተከሳሹ እንደሚሰጥ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 108(1) (2) እና ቁጥር 109(4) ይደነግጋል፡፡ ይህ መርህ የተወሰኑ ልዩ ድንጋጌዎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ተከሳሹ በከባድ ወንጀል ተከሶ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በክሱ የቀረበውን ወንጀል መፈፀሙን ሳይሆን ያረጋገጠው በተለዋጭ ሊያስከስስ የሚችል አነስተኛ ወንጀል ከሆነ ፍርድ ቤቱ አንቀጹ ለውጦ በዚሁ በተረጋገጠውና በዝቅተኛው ወንጀል ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊለው እንደምችል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113(2) ያመለክታል፡፡ ሌለው ተከሳሽ የተከሰሳው በዋና ወንጀል አዲራጊነት ሆኖ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተከሳሽ ዋና ወንጀል አድራጊ መሆኑን ሳይሆን ተባባሪ መሆኑን

ካሳዬ ፍርድ ቤት በዚሁ በተባባሪነት ጥፋተኛ ሊለው እንደሚችል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 115(2) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በመጨረም ተከሳሽ የተከሰሰው ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ቢሆንና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተከሳሹ በእርግጥ ወንጀሉን መፈጽሙን ሳይሆን ወንጀሉን መሞከሩን ከሆነ ያረጋገጠው ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ወንጀሉን በመሞከሩ ጥፋተኛ ሊለው ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ እነዚህ ነገሮች መኖራቸውን የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በተሰማበት ጊዜ ከሆነ ያረጋገጠው ተከሳሹ በዚሁ አንቀጽ ሥር መከላከያውን እንዲያሰማ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ትዕዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በተረጋገጠበት ወንጀል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113(2) መሠረት ጥፋተኛ የሚያሰኘው ከሆና ተከሳሹ የሚከላከልበት ወንጀል ተጠቅሶ ካልተነገረው የሚያቀርበው መከላከያ ውጤታማ ስለማይሆን የተከሣሹን መከላከያ የማቅረብ መብት የሚጣብብ ከመሆኑም በላይ የፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ በተረጋገጠ ፍሬ ነገር ላይ ያረፈ መሆኑ አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡ (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(4) ይመለከቷል)፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን ተከላከል ሲለው መከላከል ያለበትን ወንጀል አንቀጽ ጠቅሶ ሊነግረው ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የግል ተበዳይ ወ/ሮ እየሩሳሌም ከሳ በውክልና በሚያስተዳድሩትን መኖሪያ ቤት ሳይፈቃድላቸው ቤቱን ሰብረው በመግባት እየኖሩበት በመሆኑ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 604 (1) (ሀ) ድንጋጌን በመተላለፍ የግል ቤት መድፈር ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ሲሆን ፤ አመልካች የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት አልፈፀምኩም ፤ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች አመልካች የግል ተበዳይ ወ/ሮ እየሩሳሌም ከሳ በውክልና በሚያስተዳድሩትን መኖሪያ ቤት በነፃ እየጠበቀ እንዲኖርበት በ2008 ዓ.ም ገብቶ ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ዕቃውን ጭኖ ከወጣ በኋላ ሚያዝያ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ቤቱ ውስጥ ገብቶ መገኘቱን ስላስረዱ በወንጀ ሕጉ ቁጥር 604(1) (ሀ) ሥር በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 142(1) መሠረት እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካችም ስምንት ዓመት ጥበቃ ሆኖ የሰራው ደሞዙ እንዲከፈለው ከመጠየቅ ውጪ ከቤቱ ወጥቶ ተመልሶ አለመግባቱን የመከላከያ ምስክሮቹ ያስረዱልኛል የሚል ጭብጥ አስይዞ ቀርቦ የተሰሙት የመከላከያ ምስክሮች አመልካች በጥበቃነት ከ2005/2006 ዓ.ም ጀምሮ በደሞዝ ተቀጥሮ እየጠበቀ ከሚኖርበት ቤት ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም እንዳልወጣ እና ሚያዝያ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ቤቱን ሰብሮ እንዳልገባ መስክረዋል፡፡ አመልካች ደፍሯል የተባለው ቤት ነዋሪ የነበረ መሆኑ በግራ ቀኙ ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች አመልካች ከነበረበት ቤት ከወጣ በኋላ ተመልሶ ገብቷል በማለት የሰጡትን ምስክርነት የመከላከያ ምስክሮቹ በጥበቃ ሠራተኝነት ከገባበት ቤት እንዳልወጣ እና ከወጣ በኋላ ተመልሶ ያልገባ መሆኑን ስላረጋገጡ አመልካች ወደ ቤቱ የገባው በስምምነት በጥበቃ ሠራተኝነት ሆኖ ከቤቱም ስላልወጣ የቤቱ ሕጋዊ ነዋሪ እየተቃወመው ወደ ቤቱ የገባ ባለመሆኑ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 604 (1) (ሀ) ድንጋጌን ተላልፍፏ የሚባልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡ አመልካች በቤቱ ወስጥ የገባው በስምምነት መሆኑና ከቤቱ ከወጣ በኋላ ወደ ቤቱ ተመልሶ እንዳልገባ ስለተረጋገጠ የቀረበበትን ክስ ሙሉ በሙሉ ተከላክሎ እያለ በስምምነት ወደ ቤት የገባ ሰው ቤቱን ለቆ የሚወጣበት አግባብ እራሱን ችሎ የሚታይ ሆኖእያለ አመልካች በስምምነት ለጥበቃ ከገባበት ቤት አልወጣ ያለው ያልተከፈለው ደሞዝ በመኖሩ ምክንያት መሆኑን የመከላከያ ምስክሮች ስለተናገሩ መብቱን ሕገወጥ በሆነ መንገድ አስከብሯል በሚል አመልካች ሊከፈለው የሚገባውን ከፍያ ለማግኘት ሲል የወሰደው የባለዕዳው የሆነ ተንቀሳቃሽ ዕቃ በሌለበት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 436 (ለ) ሥር ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 237260 ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ፤ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 237260 ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፤ ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 89251 ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ትዕዛዝ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 228271

መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡...

1. እትመት አሰፋ
2. ደጀኔ አያንሳ
3. ብርቅነሽ እሱባለው
4. ሀብታሙ እርቅይሁን
5. ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡........ ፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ -አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡.......... 1ኛ. ራሄል ዘሪሁን- አመሃ በድሉ

2ኛ. አለምፀሐይ ዘሪሁን

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተጠሪዎች በተከሰሱበት የጋራ ንብረቶች ስርቆት፤ የተሰረቀ ንብረትን መሸሸግ እና እምነት ማጉደል ወንጀሎችን መፈፀማቸው ተረጋግጦ እያለ በነፃ ተለቀዋል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታን የሚለከት ሆኖ መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 667(1), 675(1) እና 862(1) ሥር የተደረገገውን መተላለፋቸው ተረጋግጦ እያለ አላግባብ በነፃ መለቀቃቸው የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም አመልካች ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩ የጋራ ንብረት ስርቆት ፤ እምነት ማጉደል ፤ እንዲሁም የተሰረቀ ንብረት መሸሸግን የሚመለከት ሆኖ 1ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተከሳሽነት ፤ 2ኛ ተጠሪ ያቀረበው የክስ ይዘት፡- የመጀመሪያው ክስ በሁለቱም ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሆኖ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 37(1) እና 667(1) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌን በመተላለፍ ህዳር 16 ቀን 2010 ዓ.ም ከምሽቱ 3፤00 ሰዓት እስከ ጠዋት 2:00 ባለው ጊዜ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ልዩ ቦታው ቶፕ ቪው ሆቴል ፊት ለፊት ከግል ተበዳይ አቶ ዳንኤል መብራቱ ጋር ባላቸው የጋብቻ ግንኙነት የጋራ የሆኑ ንብረቶችን 1ኛ.በለመስታወስት የጌጣጌጥ ማስቀመጫ የዋጋ ግምቱ 110,000.00 (አንድ መቶ አሥራ አሥር ሺ.ህ) ብር የሆነ ፤ 2ኛ.የተለያዩ የምግብ ሳህኖች የዋጋ ግምታቸው ብር 95,000.00 (ዘጠና አምስት ሺ.ህ) የሆነ ፤

3ኛ.የውሃ እና አልኮል ብርጨርቆዎች የዋጋ ግምታቸው ብር 60,500.00 (ስልሳ ሺህ አምስት መቶ) የሆነ ፤ 4ኛ.ማክሮአቬን የዋጋ ግምቱ ብር 3,000.00 (ሶስት ሺህ) የሆነ ፤ 5ኛ.የተለያዩ የምግብ ማብሰያ ዕቃዎች የዋጋ ግምታቸው ብር 56,500.00 (ሃምሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ) የሆነ፤ 6ኛ.ቨንድለር የሳሎን መብራት ከነጌጣጌጡ የዋጋ ግምቱ ብር 155,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ) የሆነ ፤ 7ኛ.የምግብ ቤት መብራቶች የዋጋ ግምታቸው ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) የሆነ፤ 8ኛ.ሁለት ወርቃማ የግርግዳ ሥዕሎች የዋጋ ግምታቸው ብር 260,000.00 (ሁለት መቶ ስልሳ ሺህ) የሆነ ፤ 9ኛ. በእጅ የተሳሉ ሥዕሎች የዋጋ ግምታቸው ብር 120,000.00 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ) የሆነ ፤ 10ኛ.ፍላት እስክሪን ቴሌቪዥን ባለ 60 አንች የዋጋ ግምቱ ብር 45,000.00 (አርባ አምስት ሺህ) የሆነ ፤ 11ኛ.ስድስት የሶፋ ትራሶች የዋጋ ግምታቸው ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ) የሆነ ፤ 12ኛ. ሁለት አልጋዎች የዋጋ ግምታቸው ብር 85,000.00 (ሰማንያ አምስት ሺህ) የሆነ ፤ 13ኛ.የስፖርት መሥሪያ ሳይክል የዋጋ ግምቱ ብር 22,000.00 (ሃያ ሁለት ሺህ) የሆነ ፤ 14ኛ.የባኞ ቤት ወንበሮች የዋጋ ግምታቸው 3,000.00 (ሶስት ሺህ) የሆነ፤ 15ኛ.የተለያዩ አንሶላዎች የዋጋ ግምታቸው ብር 35,000.00 (ሰላሳ አምስት ሺህ) የሆነ ፤ 16ኛ.የተለያዩ የአልጋ ልብሶች የዋጋ ግምታቸው ብር 45,000.00 (አርባ አምስት ሺህ) የሆነ ፤ 17ኛ.የመፀዳጃ ቤት ግጣጌጦች የዋጋ ግምታቸው ብር 12,000.00 (አሥራ ሁለት ሺህ) የሆነ ፤18ኛ.የቁምሳጥ ጌጣጌጦች ያልተገጣጠሙ ብዛታቸው 50 የዋጋ ግምታቸው ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ) የሆኑ ፤19ኛ.የልጆች አልጋ የዋጋ ግምቱ ብር 35,000.00 (ሰላሳ አምስት ሺህ) የሆነ ፤20ኛ.ሁለት የእስፕሪግ ፍራሽ እና የራስጌ መብራት የዋጋ ግምታቸው ብር 18,000.00 (አስራ ስምት ሺህ) የሆኑ ፤ 21ኛ.የተለያዩ የመስኮቶች እና የበሮች መጋረጃዎች የዋጋ ግምታቸው ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ አምሳ ሺህ) የሆኑ ፤ 22ኛ.የተለያዩ የትራስ ልብሶች የዋጋ ግምታቸው ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ አምሳ ሺህ) የሆኑ ፤ 23ኛ.የቤት ማሞቂያ የዋጋ ግምቱ ብር 350,000.00 (ሶስት መቶ አምሳ ሺህ) የሆነ ፤ 24ኛ.የግሪል መጥበሻ የዋጋ ግምቱ ብር 28,000.00 (ሃያ ስምት ሺህ) የሆነ ፤ 25ኛ.የአበባ መትከያ ዕቃዎች የዋጋ ግምታቸው ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) የሆኑ ፤ 26ኛ.የገና ዛፍ ከነእስታብላይዘሩ የዋጋ ግምቱ ብር 75,000.00 (ሰባ አምስት ሺህ) የሆነ፤ 27ኛ. የግርግዳ ዋልፔፐር የዋጋ ግምቱ ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) የሆነ 28ኛ.የተለያዩ የሰርግ ፍቶግራፎች የዋጋ ግምታቸው ብር 75,000.00 (ሰባ አምስት ሺህ) የሆኑ፤ በአጠቀላይ ብር 1,967,500.00(አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ አምት መቶ) የሚገምቱ ንብረቶችን ከመኖሪያ ቤታቸው የወሰደች ሲሆን ፤ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ንብረቶቹን በተሽከሪካሪ ላይ በማጫጫን 1ኛ ተጠሪን ስለረዳቻት 1ኛ ተከሳሽ በዋና ወንንጀል አድራጊነት 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ በአባሪነት የጋራ ንብረት ስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

2ኛው የዐቃቤ ሕግ ክስ 1ኛ ተጠሪን ብቻ የሚለከት ሆኖ ይዘቱ፡- በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌን በመተላለፍ መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ውስጥ በሚገኘው የኮሪያ ሆስፒታል ውስጥ የግል ተባዳይ አቶ ዳንኤል መብራቱ ንብረት የሆኑትን 1ኛ.ሮሌክስ የእጅ ሰዓት የዋጋ ግምቱ ብር 600,000.00(ስድስት መቶ ሺህ) የሆነ ፤ 2ኛ. ያጣት ቀለበት የዋጋ ግምቱ ብር 21,700.00 (ሃያ እንድ ሺህ ሰባት መቶ) የሆነ በአጠቃላይ 621,700.00 (ስድስት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ) የሚገመቱ ንብረቶችን ለማስቀመጥ ተቀብላ ሳትመልስ ስለቀረች እምነት በማጉደል ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው፡፡ 3ኛው ክስ 2ኛ አመልካችን የሚመለት ሆኖ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 682(1) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌን በመተላለፍ ህዳር 16 ቀን 2010 ዓ.ም ከምሽቱ 3፤00 ሰዓት እስከ ጠዋት 2፡00 ባለው ጊዜ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ግሎባል ሆቴል በቅሎ ቤት በሚባል አከባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤቷ በአንደኛ ክስ ላይ የተጠቀሱትን ሁሉንም ንብረቶች በክሱ በተመለከተው አግባብ ከግል ተበዳይ አቶ አቶ ዳንኤል መብራቱ ከተወሰዱ በኋላ ንብረቶቹን ያስቀመጠች በመሆኑ በመሸሸግ ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች የዕምነት ክደት ቃላቸውን ተጠይቀው ወንጀሉን አልፈፀምንም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ሰምቶ 1ኛ ተጠሪ የቀረባቸውን ሁለቱንም ክሶች እንዲከላከሉ ፤ 2ኛ ተጠሪ በ1ኛው ክስ አልተመሰከረባቸውም በማለት በነፃ ሲያሰናብት፤ 2ኛ በተከሰሱበት የመሸሸግ መንጀል እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች እንዲከላከሉ ብይን በተሰጠባቸው ክሶችን በተመለከተ የተጠሪዎችን ቃል ተቀብሎ እና የ1ኛ ተጠሪን የመከላከያ ምስክሮች ሰምቶ የዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ በመከላከያ ማስረጃ መስተባበል/አለማስተባበሉን በጭብጭነት በመያዝ መዝገቡን እንደመረመረው፡- በክስ አንድ ሥር የተዘረዘሩ ንብረቶች በሙሉ የግል ተበዳይ እና 1ኛ ተጠሪ የጋራ መሆኑና በ1ኛ ተጠሪ ተሰርቆ መወሰዱን በተመለከተ የግራ ቀኙ ማስረጃ ሲመዘን 1ኛ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ሕግን ክስና ማስረጃ ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ ስለተገኘ የመጀመሪያውን ክስ በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ሕግን ክስና ማስረጃ በመስተባበሉ ፤ በ2ኛው ክስም 2ኛ ተጠሪ ወንጀሉ ተፈጽሟል በተባለበት ጊዜ ወንጀሉ ተፈጽሞበታል በተባለው ቦታ ሳይሆን በሥራ ገበታቸው ላይ የነበሩ መሆኑ በመረጋገጡ፤ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በክስ አንድ ሥር የሥርቆት ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ የቀረበባቸው ክስ ስለተስተባበለ 2ኛ ተጠሪ የመሸሸግ ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ሊጠየቁ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የሌለ በመሆኑ፤ ተጠሪዎች ስርቆት፤ እምነት ማጉደል እና የመሸሸግ ወንጆችን ፈጽመዋል በማለት የቀረበባቸው ክስ በመከላከያ ማስረጃ ስለተስተባበለ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149(2) ድንጋጌ መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 195(1) መሠረት በመሰረዙ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- 1ኛ ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር በጋብቻ ተሳስራ ሲትኖር በተፈሩ የጋራ ንብረቶች ላይ ስርቆት ፈጽማለች በማለት በተጠሪ ያቀረበው ክስ በቤት ሠራተኝነት፤ በጥበቃ እና በጽዳት ሠራተኝነት እያገለገለ በቤቱ ወስጥ አብሮ የሚኖሩ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ፤ ምስክሮቹም የግል ተበዳይ ለሕክምና ወደ ውጪ ሀገር በሄደበት 1ኛ ተጠሪ ዕቃዎቹን ጭና መውሰዷን እና ድርጊቱን የተቃወመውን 7ኛ ምስክር አስደብድባ ማባረሯን እንደ ክሱ አቀራረብ አስረድተው እያለ የሥር ፍርድ ቤት የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠውን የዲጋፍ ደብዳቤ መሠረት አድርጎ 1ኛ ተጠሪ የወሰደችው የግል ንብረቷን ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ ነው፡፡ የትብብር ደብዳቤው የተፃፈው 1ኛ ተጠሪ እና የግል ተበዳይ በትዳር ውስጥ እያሉ በመሆኑ ንብረቶቹ የጋራ እንደሆኑ የሚገመት ሲሆን፤ የግል ናቸው ቢባል እንኳን ይህን ደብዳቤ መሠረት አድርጎ የገቡ ዕቃዎችን በዝርዝር ባልተለዩበት ሁኔታ 1ኛ ተጠሪን በጋራ ንብረት ስርቆት ኃላፊነት የለባቸው መባሉ አግባብነት የለውም፡፡ በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ንብረቶቹ የማን እንደሆኑ በትክክል ስለማያውቁ ተጠሪዋ የግል ነው ብላ ስለነገረቻቸው ብቻ የግሏ ነው ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ ምስክሮቹ የሰጡት ምስክርነትም የሰሚ ሰሚ በመሆኑ ቅቡልነት ያለው ማስረጃ አይደለም፡፡ ንብረቶቹ መቼ እንደተገዙ፤ በማን እንደተገዙ ፤ የማን እንደሆኑ ሳይጣራ የግል ተበዳይ እና 1ኛ ተጠሪ ለረዝም ዓመት በትዳር ቆይታቸው የተፈራ ለመሆኑ አሳማኝ  የሕግ ግምት እያለ እና በግል ተበዳይ ገንዘብ ከሮም ተገዝተው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የጋራ ንብረቶች መሆናቸውን የሚያስረዱ የተለያዩ ደረሰኞች እና ሌሎች ማስረጃዎች ቀርበው ባለበት 1ኛ ተጠሪ የወሰዱት  ከውጭ ሀገር ይዘው የገቡትን ዕቃዎች ነው መባሉ ተገቢነት የለውም፡፡ 1ኛ ተጠሪ የቀረበባቸውን 2ኛ ክስ ለመከላከል ያቀረቡት ማስረጃ የሥራ መግቢያ ሰዓትን የሚያመለክቱ ከመሆኑም በላይ 1ኛ ተጠሪ በሥራ ገበታቸው ላይ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ የ1ኛ ተጠሪ የሥራ ቦታ እና የግል ተበዳይ የተከሙበት የኮሪያ ሆስፒታል ቅርብ ለቅርብ ከመሆኑ አንፃር እና 1ኛተጠሪ እና የግል ተበዳይ ካላቸው ግንኙነት የተነሳ 1ኛ ተጠሪ ከሥራ ወጥተው የግል ተበዳይን ጠይቆ ሊመለሱ የሚችሉበት ሰፊ አጋጣሚ እያለ 1ኛ ተጠሪ የተከሰሱበትን የዕምነት ማጉደል ወንጀል አልፈፀሙም መባሉ ሕግን ያልተከተለ ነው፡፡ የ1ኛ ተጠሪ እና የግል ተበዳይ የጋራ ንብረኞች በ1ኛ ተጠሪ ተሰርቆ በ2ኛ ተጠሪ

ቤት የተቀመጡ መሆኑን አመልካች አስረድቶ እያለ 2ኛ ተጠሪን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል የጥፋተኝነት ፍርድ እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎችን በተከሰሱበት ወንጀል በነፃ የመሰናበታቸው አግባብነት ከማስረጃ ሚዘና መርህ አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ 1ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው መልስ ስላሰጡ መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን፤ 2ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ የወሰዱት የግል ንብረታቸውን መሆኑን ስለተከራከሩ አመልካች ንብረቶቹ የ1ኛ ተጠሪ እና የግል ተበዳይ የጋራ መሆናቸውን ያላስረዳ ሲሆን፤ በአንፃሩ ተጠሪ የወሰዷቸው ንብረቶች ከግል ተበዳይ ጋር ትዳር ከመመስረታቸው በፊት የተፈሩ የግል ንብረቶች መሆናቸውን ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ስላስረዱ ወደ 2ኛ ተጠሪ ቤት የተወሰዱት የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረቶች መሆናቸው ስለተረጋገጠ 2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው የመሸሸግ ወንጀል በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን የመጀመሪያን ክስ የሚከተል በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ በነፃ መሰነበታቸው የሚነቅፍ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፊ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ወይንም የተከሰሰ ሰው በፍርድ ቤት የወንጀል ጥፋተኛነቱ እስክረጋገጥ ድረስ እንደወንጀለኛ ያለመቆጠር ሕግ መንግስታዊ መብት አለው፡፡ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 20(3)) የዚህ ሕግ መንግስታዊ መብት አፈፃፀም መግጫ ባህሪያት በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው የተከሳሹ አያያዝ ሁኔታ ተከሳሹ በተከከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ እስከሚባል ድረስ ነፃ እንደሆነ የመቆጠር መብት ሲሆን፤ ሁለተኛው ተከሳሽ የከሰሰበት ወንጀል የሚያቋቋሙ ፍሬ ነገሮችን በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) የማስረዳት የዐቃቤ ሕግ ግዴታ መሆኑን ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ ባሰማው አግባብነት እና ተቀባይነት ባለው ማስረጃ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወይም ተቀራራቢ እና ተለዋጭ ወንጀል መፈፀሙን በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) አስረድቷል ወይስ አላስረዳም የሚለው ጭብጥ ታይቶ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተቃራኒ ማስረጃ ባይቀርብበትም ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያበቃ መሆን አለበት፡፡ እነዚህ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተከሳሽ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) ያላስረዱ እንደሆነ ተከሳሹ መከላከል ሳያስፈልገው ፍርድ ቤቱ በነፃ ያሰናብተዋል፡፡ ሆኖም ማስረጃዎቹ ተከሳሹ ወንጀሉን ለመፈፀሙን በወንጀል ክስ የሚጠበቀውን የማስረዳት ደረጃ (መለኪያ) (standard of proof) ያረጋገጡበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያሰማ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

ከዚህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት ጉዳይ ተከሳሽ ተከላከል የሚባልት አንቀጽ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(2) የተከሰሱ ሰዎች ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት እንዳላቸው ስለሚደነግግ በደንብ መተላለፍ ችሎቱ በያዘው መዝገብ ቅጣት መወሰን በሚችልባቸው የችሎት መድፈር ወንጀሎች ውጪ ያሉ ጉዳዮች ሁሉ ክሱ በጽሁፍ ከልቀረበ በቀር ጉዳይ ሊታይ እንደማይችል እና የክሱ ግልባጭ በነፃ ለተከሳሹ እንደሚሰጥ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 108(1) (2) እና ቁጥር 109(4) ይደነግጋል፡፡ ይህ መርህ የተወሰኑ ልዩ ድንጋጌዎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ተከሳሹ በከባድ ወንጀል ተከሶ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በክሱ የቀረበውን ወንጀል መፈፀሙን ሳይሆን ያረጋገጠው በተለዋጭ ሊያስከስስ የሚችል አነስተኛ ወንጀል ከሆነ ፍርድ ቤቱ አንቀጹ ለውጦ በዚሁ በተረጋገጠውና በዝቅተኛው ወንጀል ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊለው

እንደምችል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113(2) ያመለክታል፡፡ ሌለው ተከሳሽ የተከሰሳው በዋና ወንጀል አዲራጊነት ሆኖ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተከሳሽ ዋና ወንጀል አድራጊ መሆኑን ሳይሆን ተባባሪ መሆኑን ከሳየ ፍርድ ቤት በዚሁ በተባባሪነት ጥፋተኛ ሊለው እንደሚችል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 115 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በመጨረም ተከሳሽ የተከሰሰው ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ሲሆንና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተከሳሹ በእርግጥ ወንጀሉን መፈጽሙን ሳይሆን ወንጀሉን መሞከሩን ከሆነ ያረጋገጠው ፤ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ወንጀሉን በመሞከሩ ጥፋተኛ ሊለው ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ እነዚህ ነገሮች መኖራቸውን የተገነዘበው የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በተሰማበት ጊዜ ከሆነ ተከሳሹ በዚሁ አንቀጽ ሥር መከላከያውን እንዲያሰማ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ትዕዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበት ወንጀል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113(2) መሠረት ጥፋተኛ የሚያሰኘው ከሆና ተከሳሹ የሚከላከልበት ወንጀል ተጠቅሶ ካልተነገረው የሚያቀርበው መከላከያ ውጤታማ ስለማይሆን የተከሣሹን መከላከያ የማቅረብ መብት የሚያጣብብ ከመሆኑም በላይ የፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ በተረጋገጠ ፍሬ ነገር ላይ ያረፈ መሆኑን አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡ (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(4) ይመለከቷል)፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን ተከላከል ሲለው መከላከል ያለበትን ወንጀል አንቀጽ ጠቅሶ ሊነግረው ይገባል፡፡ የከሳሹ መከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የሰጡትን ምስርነት ተገቢ ጥርጣሬ ወስጥ ያስገባ ከሆነ ተከሳሹ ከቀረበበት የወንጀል ክስ በነፃ ይሰናበል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ተገቢ ያልሆና ብልጽግና ለማግኘት ከግል ተበዳይ አቶ ዳንኤል መብራቱ ጋር በባልና ሚስትነት በጋራ ያፈሩት በመጀመሪያ ክስ ሥር የተመለከቱ አጠቃላይ 1,967,500.00(አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ አምት መቶ) ብር የሚገምቱ ንብረቶችን ከመኖሪያ ቤታቸው ስለወሰደች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 667(1) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌን በመተላለፍ የጋራ ንብረት ስርቆት ፈጽማለች በማለት የቀረበባትን ክስ በመካድ ተከራካራለች፡፡ 1ኛ ተጠሪ የወሰደቻቸው ንብረቶች የባልና ሚስት የጋራ ንብረቶች ሳይሆኑ ከግል ተበዳይ ጋር በትዳር ከመተሳሰራቸው በፊት የተፈሩ የግል ንብረቶቿ መሆኑን ተከራክራለች፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከጋብቻ በፊት የገዛሁትን የግል ንብረቴ ነው የወሰዱኩት በማለት ስለምትከራከር የወሰደችው የግል ንብረቶቿን ሳይሆን ከግል ተበዳይ ጋር የጋራ የሆኑ ንብረቶች መሆኑን ዐቃቤ ሕግ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ የአመልካች ምስክሮች 1ኛ ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር የጋራ የሆኑ ንብረቶችን ወስዳ 2ኛ ተጠሪ መኖሪያ ቤት እንዳስቀመጠች ያስረዱ ቢሆንም፤ 1ኛ ተጠሪ የግል ተበዳይን ከማወቁ በፊት የገዟኂቸውን የግል ንብረቶቼን ነው የወሰድኩት በማለት ቃሏን የሰጠች ሲሆን ፤ 3ኛ የ1ኛ ተጠሪ መከላከያ ምስክርም ተጠሪዋ የራሴ ነው የሚትላቸውን ንብረቶች ከውጪ ሀገር ይዛ ስትመጣ የዕቃዎቹን ዕሽግ መፍታታቸውንና እነዚህኑ ዕቃዎች መልሶ ማሸጉን ፤1ኛ ተጠሪ የግል ተበዳይ በሌሉበት እነዚህኑ ዕቃዎች ይዞ መሄዷን አስረድተዋል፡፡ 4ኛ የመከላከያ ምስክርም በበኩላቸው የግል ተበዳይ ዱባይ ሆነው ሳጅን መሀመድ የተባሉ የፖሊስ አባል በስልክ አናግረው ለፖሊሱ 1ኛ ተጠሪ ዕቃዋን ይዛ ትውጣ ብሎ መናገራቸውን፤ በዚሁ አግባብ 1ኛ ተጠሪ ዕቃዎቹን ይዛ መውጣቷንና ሌሎች ቤት ውስጥ የቀሩ ዕቃዎች መኖራቸውን አስረድተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከ16 ዓመት በላይ በውጪ ሀገር ስትሰራ ቆይታ መመለሷን ፤ በ2008 እና 2009 ዓ.ም የተለያዩ ያገለገሉ እና ሌሎች ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ይዛ መግባቷን የሚያመለክት የሰነድ ማስረጃ መቅረቡ፤ ከዋሽንግተን የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተፃፈው ደብዳቤም 1ኛ ተጠሪ ዋሽንግተን የሚገኘው ኢትዮጵያ አየር መንገድ ቅርጫፍ ለ16 ዓመት ሲሰሩ የነበረ መሆኑን ገልፆ፤ ከማርች 1/2016 ጀምሮ ኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ አካዳሚ ኃላፍ ሆነው ወደ አዲስ አበባ በመዛወራቸው ያላቸውን ንብረት ይዘው መግባት እንዲችሉ ትብብር እንዲደረግላቸው ይገልፃል፡፡ የግል ተበዳይ በሰጡት ምስክርነት በ1ኛ ተጠሪ የተወሰዱት አብዛኞቹ የኪችን ዕቃዎች የቀድሞ ጋብቻው ሲፈርስ የተካፈልኩት የግል ንብረቶች ናቸው ቢሉም ዕቃዎቹን በዝርዝር መግለጽ ያልቻሉ መሆኑን፤ በተመሳሳይ መልኩ 1ኛ ተጠሪ እና የግል ተበዳይ በጋብቻ

ውስጥ እያሉ ከጣሊያን እና አሜርካ ለመጡ ዕቃዎች የግል ተበዳይ ገንዘብ መክፈላቸውን የመሰከሩ ቢሆንም ዕቃዎቹን መዘርዘር እንዳልቻሉ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ መገንዘብ ተችሏል፡፡

1ኛ ተጠሪ እና የግል ተበዳይ ስርቆቱ ተፈፀመ በተባለ ጊዜ ጋብቻ ውስጥ የነበሩ መሆኑ በቀረበው የሰነድ ማስረጃ ስለተረጋገጠ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 58 መሰረት ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት የተጋቢዎቹ የግል ንብረት ሲሆን፤ በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ ንብረቶች ደግሞ የባልና ሚስቱ የጋራ እንደሆኑ እንደሚገመት ከአንቀጽ 62 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች 1ኛ ተጠሪ የወሰዱት ከግል ተበዳይ ጋር በጋራ የነበራቸውን ንብረቶች በመሆኑ ይሕ ድርጊታቸው የጋራ ንብረት ስርቶት ነው በማለት ያቀረቡትን ክስ ቀርቦ በተሰሙት ምስክሮቻቸው ያስረዱ ቢሆንም፤ የመከላከያ ምስክሮቹ እና የሰነድ ማስረጃው 1ኛ ተጠሪ በውጪ ሀገር ሲኖሩ ንብረት የነበራቸው መሆኑን፤ ንብረቶቹን ይዞ ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸውን ፤ ከውጪ ሀገር ይዘው የገቡትን ንብረቶች የግል ተበዳይ በሌሉበት ከቤት ይዞ መውጣታቸውንና የግል ተበዳይም በስልክ 1ኛ ተጠሪ የግል ንብረቶቻቸውን ይዘው እንዲወጡ መናገራቸውን ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ ስለሚያመለክት፤ የመከላከያ ማስረጃው የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ላይ ተገቢውን ጥርጣሬ የፈጠረ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ አለአግባብ ለመበልፀግ ከግል ተበዳይ ጋር በጋራ ያፈሩትን የጋራ ንብረቶች የሰረቁ መሆኑ ስላልተረጋገጠ በተከሰሱበት የስርቆት ወንጀል ነፃ መባላቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ቀርበው በተሰሙት የመከላከያ ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃ የእምነት ማጉደል ወንጀሉን ፈጽመዋል በተባሉበት ቦታ ያልነበሩ መሆኑንና በሥራ ገበታቸው ላይ እንደነበሩ ስላስረዱ፤ በተመሳሳይ ሰዓት ወንጀሉ ተፈጽሞበታል በተባለው ቦታ እና በሥራ ገበታቸው ላይ መገኘት ስለማይችሉ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ተገቢ ጥርጣሬ ውስጥ ስለገባ፤ የቀረበባቸው ክስ ስለተስተባበለ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149(2) ድንጋጌ መሠረት በነፃ እንዲሰናበቱ መወሰኑ ስህተት ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበባቸው የስርቆት ወንጀል በመከላከያ ማስረጃ ስለተስተባበለ 2ኛ ተጠሪ የመሸሸግ ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ሊጠየቁ አይገባም መባሉ በአግባቡ ነው፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪዎች ፈጽመዋል ተብሎ የቀረበባበቸው ክስ ላይ የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት በመከላከያ ማስረጃ ተገቢ ጥርጣሬ ውስጥ ስለገባ በተጠሪዎች ወንጀሎቹን አልፈፀሙም ተብሎ በነፃ መሰነበታቸው ሕግን የተከተለነው ከሚባል ባቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ስላልተቻለ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳ ኔ

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 163159 ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርደ እና ትዕዛዝ ፤ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 283614 የካቲት 18 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ፍርድ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ክፍል አምስት

## 5.ክስ ማንሳት[166]

- የወንጀል ክርክር በሚመራበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 122(2) መሠረት አንድ ክስ በከሳሽ (በዓቃቤ ሕግ) ጥያቄ እንዲነሳ ከተደረገ በኋላ ክሱን ለወደፊት ለመቀጠል የሚከለክል እንደማይሆን በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 5 ላይ ተመልክቷል፡፡ የወንጀል ሕግ መርህም የሚከተለው በወንጀል የተከሰሰ ሰው በተከሰሰበት ጉዳይ ጥፋተኛ ነው ከተባለ ወይንም በነጻ ከተለቀቀ በኋላ በዚያው ጉዳይ ዳግመኛ ክስ የማይቀርብበት መሆኑን በተመለከተ ነው::[167]

የሰ/መ/ቁ.28952

መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ - ሙሉእመቤት ውባየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ባንቲ ታኤራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተጠሪ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 122(2) መሰረት ካነሳ በኋላ በድጋሚ ክስ ሊያቀርብ አይችልም በማለት ድጋሚ የቀረበውን ክስ የሥር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉት በመቅረታቸው ነው፡፡

ይህ ችሎትም የቀበረውን የሰበር ቤቱታ መርምሮ የቀረበው የወንጀል ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 122(2) መሰረት ለጊዜው ተቋርጧል ተብሎ ከታዘዘ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ ክሱን ለመቀጠል አይችልም መባሉ ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሥር ፍ/ቤቶች ክሱ ሊቀጥል አይችልም ያሉበት ምክንያት አግባብነት እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የወንጀል ክርክር በሚመራበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 122(2) መሠረት አንድ ክስ በከሳሽ (በዓቃቤ ሕግ) ጥያቄ እንዲነሳ ከተደረገ በኋላ ክሱን ለወደፊት ለመቀጠል የሚከለክል እንደማይሆን በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 5 ላይ ተመልክቷል፡፡ የወንጀል ሕግ መርህም የሚከተለው በወንጀል የተከሰሰ ሰው በተከሰሰበት ጉዳይ ጥፋተኛ ነው ከተባለ ወይንም በነጻ ከተለቀቀ በኋላ በዚያው ጉዳይ ዳግመኛ ክስ የማይቀርብበት መሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

ስለሆነም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት ከሳሽ (ዓቃቤ ሕግ) ክስ ማንሳት እንደሚችልና ያነሳውንም ክስ መቀጠል እንደሚችል የተመለከተ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ

---

[166]በሰ/መ/ቁ 28952 (መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅጽ 7

[167]በሰ/መ/ቁ 127312 (ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 21

ፍ/ቤት የተነሳው ክስ ሊቀጥል አይችልም በማለት የዐ/ህግን ጥያቄ ሳይቀበለው መቅረቱ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43170 በ27/3/97 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 35780 ሕዳር 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች አስቀድሞ ክስ ማንሳቱ በድጋሚ ክሱን ለመቀጠል የሥነ ሥርዓት ሕጉ የሚፈቅድት ስለሆነ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ተመልሶለታል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ክፍል ስድስት

### 6.በግል አቤቱታ ስለሚቀርብ የወንጀል ክስ[168]

- በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ በግል አቤቱታ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት ሰው በቀር በሌላ በማንም ሠው የክስ ጉዳይ ሊንቀሳቀስ አይችልም፡፡
- የግል ከሳሹ የክሱን ማመልከቻ ካዘጋጀ በኋላ የክሱ ጉዳይ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 150-153 በተገለፀው መሠረት ይመራል፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 141978

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ - ሙሉተስፋ ከበደ

ተጠሪ፡- እዮኤል ተስፋዬ የሺጥላ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን

የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 114261 በቀን 22/02/09 የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 183790 በቀን 13/06/2009 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡ ጉዳዩ በዐቃቤ ህግ አማካኝነት የቀረበን ክስ ስለማንሳትና ከክርክር ውጭ ስለመሆን

---

[168]በሰ/መ/ቁ 141978 (መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅጽ 22

የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ሁለት የወንጀል ክስ ያቀረበ ሲሆን ይኸውም የወንጀል ህግ ቁጥር 559/2/ እና 575 /2/ /ሀ/ የተመለከተውን ተላልፎ በዋናው መንገድ ለሚጓዝ ተሽከርካሪ ቅድሚያ በመከልከልና ያለጥንቃቄ ሲያሽከረክር የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-06155 ኢ.ት የሆነ መኪና የኋላ ግራ ጉን የገጨና አቅጣጫ እንዲስትና ከድንጋይ ጋር ተጋጭቶ በውስጡ የነበሩት የግል ተበዳይ አብነት ጉሹ በመኪናው አካል ተመትቶ የአንገት የቀኝ እግር እና የአካል ጡንቻዎች ላይ የህመም ስሜት እንዲሰማ ያደረገ እና እርዳታ ሳያደርግ በሌላ መኪና ገብቶ ያመለጠ በመሆኑ በቸልተኝነት ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰና በአደጋ ላይ የሚገኝ ሰውን አለመርዳት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ የቀረበው ክስ ደርሶት እምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ከግል ተበዳይ ጋር የታረቀ መሆኑን የገለፀ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህንኑ ገልጾ በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በወንጀል ህግ ሥ/ሥርዓት ቁ 151/2/ መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሳይቀበል መዝገቡን ዘግቶቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በተጠሪ ላይ የቀረበው የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ በወንጀል ህግ 212 መሠረት በግል አቤቱታ የማይቀርብና በወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት በእርቅ ሊነሳ የማይችል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን ያቋረጠው መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ የቀረበ ክስ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት በእርቅ በመጨረስ የሚቋረጥ መሆኑን ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ታዞ በሰጠው መልሱ በወቅቱ እኔም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኝ እራሴን ለማዳን ወደ ህክምና ተቋም ሄጀለሁ ሆነ ብዬ ሰውን ላለመርዳት አልሄድኩም ብሎ ክሱን በመካድ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪም ዕርቁን የማይቃወም መሆኑን እና የሚያቀርቡት ማስረጃ እንደሌለ በመግለጽ ፍ/ቤቱ ክሱን አቋርጧል እንጂ የግል አቤቱታ ነው በማለት አይደለም፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልኝ ብሏል፡፡ አመልካች በሰጠው የመልስ መልስም ሁለቱም ክሱ የተቋረጠው በእርቅ እንጂ አመልካች ማስረጃ ባለማቅረቡ ወይም እንደክሱ ባለማስረዳቱ አይደለም የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/3/ የተመለከተውን ተቃውሞ አላነሳንም እንጂ በሁለተኛው ክስ ላይ ተቃውሞ ገልፀናል፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ክሱን ማቋረጡ ተገቢ አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነው በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶችንና የሚቀርቡበትን አግባብ የሚመለከት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ ከቀረበው ጭብጥ አንጻር የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ሀ/ በወንጀል ህግ ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት ከተበዳዩ ጋር በዕርቅ በመጨረስ ክሱ የሚቋረጥ ስለመሆኑ አለመሆኑ ምላሽ የሚሰጥ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የወንጀል ህግ ግብ ስለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የሀገሪቱን መንግስት የህዝቦችን የነዋሪዎቹን ሰላም ደህንነት ሥርዓት መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ መንግስት በህዝብ ስም ሆኖ ለዜጐች ተወክሎ የወንጀል ጉዳይን እንዲከታተልና ከሶ እንዲያስቀጣ ኃላፊነት ሊወድቅበት የቻለውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም የጠቅላላውን ህዝብ ሰላምና ፀጥታ የሚያደፈርሱ ከተጐጂው ሠው ጥቅም በላይ አልፈው የሌሎችን ጥቅም የማይነኩ አሉ፡፡ በእርግጥ በጠቅላላው ተበዳይ ቢስማማም ባይስማማም የወንጀል ክስን መከታተል የመንግስት ኃላፊነት ቢሆንም በእነደዚህ ባሉ ነገሮች የተጐዳው ሠው ጉዳዩን ክሶ በፍርድ እንዲታይለት ፈቃደኛ መሆኑ በእርግጥ ካላሳየ በቀር መንግስት ይህንን ግዳጁን አያከናውንም፡፡ የወንጀል ህጉ ክስ በቀረበ ጊዜ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች የሚገልጽ የተጠናቀቀ ዝርዝር አይገልጽም፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 212 ቢሆንም በጠቅላላው መልክ ነው በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ውስጥም የሚገኙ ድንጋጌዎች “ማናቸውም … የግል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ …. ይቀጣል” ሲል ያዛሉ፡፡ እነዚህን አንቀጾች በመተላለፍ ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ በግል አቤቱታ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት

ሰው በቀር በሌላ በማንም ሠው የክስ ጉዳይ ሊንቀሳቀስ አይችልም፡፡ የግል ከሳሹ የክሱን ማመልከቻ ካዘጋጀ በኋላ የክሱ ጉዳይ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 150-153 በተገለፀው መሠረት ይመራል፡፡ በያዝነው ጉዳይ በአመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት ክሶች 1ኛ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/2/ እና 2ኛ የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ በግል ተበዳይ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ አማኻኝነት የሚቀርቡ ወይም እንዲቀርቡ የታዘዙ ክሶች አይደሉም፡፡ ክሱም በስር ፍርድ ቤት የቀረበው በአመልካች /በመንግስት/ በዐቃቤ ህግ ነው፡፡ ክሱን የሚመራው በወ/ህ/ሥ/ሥ /ቁ 132-135 ፣ 185፣196፣117፣ 94-98፣ 123-131 እና 136-149 በተመለከቱት መሠረት ይሆናል፡፡ ስለሆነም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን የወንጀል ክስ የግል ተበዳይ ክሱን ትቷል በማለት በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 151/3/ መሠረት በግል አቤት ባይ የቀረበ ክስ በሚመራበት ሥነ ሥርዓት የወንጀል ክሱን ያቋረጠው የወንጀል ህግን ግብ እና በዓቃቤ ህግ ስለሚቀርቡ የወንጀል ክስ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ክስ አመራር ያልተከተለ በመሆኑ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንን ሳያርም ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 114261 በቀን 22/02/09 የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 183750 በቀን 13/06/2009 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች የቀረበውን ክስ ተጠሪን አስቀርቦ የወንጀል ክሱን በመስማት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /መ/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>7.ተከሳሽ በሌለበት ክርክር ስለመቀጠል እና መጥሪያ አደራረስ</u>[169]

### <u>7.1 ከእምነት ክህደት ቃል እና መከላከያ ማስረጃ በኋላ የተከሳሽ አለመቅረብ</u>[170]

- ተከሳሽ በተከሰሰበት የወንጀል ክስ ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶ እና የመከላከያ ማስረጃውን አሰምቶ ውሳኔ በሚሰጥበት እለት አለመቅረቡ በሌለበት የታየ ነው ሊባል አለመቻሉ፤[171]

---

[169]የሰ/መ/ቁ 94227 (ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16

[170]በሰ/መ/ቁ 29325 ( የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅጽ 7

[171]በሰ/መ/ቁ 231732 (ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 179416 (ሰኔ 23 ቀን 2012ዓ.ም) ቅጽ 24፣ በሰ/መ/ቁ 173967 (መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24፣ በሰ/መ/ቁ 127313 (መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅጽ 22፣ በሰ/መ/ቁ 104220 (ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 18፣ በሰ/መ/ቁ 98014 (ሐምሌ 14 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 93577 (ሕዳር 22 ቀን 2007ዓ.ም) ቅጽ 17፣ በሰ/መ/ቁ 95875 (ሰኔ 17 ቀን 2006ዓ.ም) ቅጽ 16፣ በሰ/መ/ቁ 57632 (ታህሳስ 25 ቀን 2003ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 76909 (ግንት 10 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ በሰ/መ/ቁ 211518 (ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 154444 (የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 159451 (መጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 160767 (ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 141081 (መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 140719 (ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 144724 (ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 95261 (ሐምሌ 02 ቀን 2006 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 228597 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)

የ/መ/ቁ. 29325

የካቲት 18 ቀን 2000ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ኤርምያስ ካሣ ተፈራ - ጠበቃ ስንታየሁ ባህሩ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ሕግ - ሺበሺ ይግዛው ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 26583 ታህሣሥ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ተሰምቶአል፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረው አመልካች የተከሰሰው የወ/መ/ሕግ ቁ.27/1/ እና 522/1/ሀ/ ድንጋጌን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም አመልካች ቀርቦ ሲጠየቅ ጥፋተኛ አይደለሁም ስላለ ፍ/ቤቱ በቅድሚያ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በመቀጠልም አመልካች እንዲከላከል ብይን በመስጠት የአመልካችን የመከለከያ ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በመጨረሻም አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኘው በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ነው ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበው፡፡ ፍ/ቤቱ ግን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የወሰነው አመልካቹ በሌለበት ስለሆነ ይግባኝ ከማለቱ በፊት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት ማመልከት አለበት የሚል ምክንያት በመስጠት ወደ ይግባኙ ስረ ነገር ሳይገባ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት አቤቱታውን አስቀርቦ የሰማው አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለወንጀሉ ክስ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶ እና የመከላከያ ማስረጃውንም አሰምቶ ተከራክሮ እያለ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሣኔ ሲሰጥ በመገኘቱ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንደታየ ተቆጥሮ ይግባኙ ሳይታይ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህንን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ትዕዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል በዝርዝር እንደተገለፀው ክርክሩ /ጉዳዩ/ ከመሠረቱ አመልካች በሌለበት የታየ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካች በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ በሰጠው መልስ ክሱን ክዶ በመከራከሩ በዓቃቤ ሕግ በኩል የተቆጠሩት ማስረጃዎች እና በአመልካች በኩል የተቆጠሩት የመከላከያ ማስረጃዎች አመልካቹ ባለበት ተሰምተዋል፡፡ የክርክሩ መሰማት ሂደት በዚህ መልክ ከተካሄደም ቀጥሎ የሚሆነው በተሰማው ክስ እና ማስረጃ መሠረት የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት ነው፡፡ ውሣኔው የሚመሠረተውም በተሰማው ክርክር እና ማስረጃ ላይ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የጥፋተኛነቱንም ሆነ የቅጣት ውሣኔውን የሰጠው አመልካች ባለበት የሰማውን ክርክር እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ ውሣኔው በተሰጠበት ጊዜ አመልካች ፍ/ቤት አልቀረበም፡፡ ከዚህ የተነሣም ውሣኔው የተሰጠው አመልካች በሌለበት እንደሆነ በውሳኔው መግቢያ ላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ለተያዘው አቤቱታ አወሳሰን ሊታይ የሚገባው ነጥብ ክሱና ማስረጃው ለውሣኔ በተቀጠረ ጊዜ የቀረ ተከሣሽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 161/1/ በተደነገገው መሠረት ጉዳዩ በሌለበት እንደተሰማ ይቆጠራል ወይ? የሚለው ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው በወንጀል የተከሰሰ ሰው ፍ/ቤት እንዲቀርብ የሚጠራው የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲያውቅ እና የሚከላከል ቢሆንም ሕጉ በሰጠው መብት እንዲጠቀም ነው፡፡ ተከሣሹ ይህ የመከላከል መብቱን ላለመጠቀም በተደረገለት ጥሪ መሠረት ሳይቀርብ ቢቀር ሕጉ ባስቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ጉዳዩ /ክሱ/ ተከሣሹ በሌለበት ተሰምቶ ይወሰናል፡፡ እዚህ ላይ እንግዲህ ትኩረት የሚያስፈልገው ቁልፍ ነገር የተከሣሹን የመከላከል መብት ሲሆን፣ ይህም የእምነት ክህደት ቃል ከመስጠት ጀምሮ የመከላከያ ማስረጃ እስከ መስማት ድረስ ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ነው፡፡ በመሆኑም ተከሣሹ ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶ እና የመከላከያ ማስረጃውን አሰምቶ ከሆነ ክሱ እሱ በሌለበት ነው የታየው ለማለት የሚቻልበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ዓቃቤ ሕግ ለሰበር አቤቱታው የሰጠው መልስ አመልካች የተሰጠበትን ውሣኔ በመሸሸ የተደበቀ በመሆነ በጠበቃው አማካይነት የቀረበው አቤቱታ ሊታይለት አይገባም በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡ ይሁንና ይህ ክርክር ምን ውጤት ይኖረዋል? የሚለው ይግባኙን በሚሰማው ፍ/ቤት ከሚታይ በስተቀር በዚህ ሰበር የሚስተናገድ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለል ጉዳዩ /ክሱ/ የታየው አመልካች በሌለበት ነው በሚል የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195 መሠረት ተሽሮአል፡፡

2. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት አመልካች የቀረበለትን ይግባኝ እንዲቀበል፤ በመሰለው ሁኔታ ይግባኙን አይቶ የራሱን ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ እንዲስጥ ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 7.2 ተራ የሆነ የሰው ግዲያ ሙከራ ወንጀል ተከሳሽ በሌለበት የማይታይ[172]

- ሕገ መንግስቱ በአብዛኛዉ ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴል (The Due Process Model) በሚል ለሚታወቀው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ትልቅ ስፍራ እንደሚሰጥ የሚያስገነዝብ ነው፡፡
- በመመሪያው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ለተደነገገው የእስራት ቅጣት 6 ደረጃዎች የወጣለት ሲሆን የደረጃ 1 መነሻ እርከን እርከን 21 ሲሆን ደረጃ 6 ደግሞ መነሻ ቅጣቱ እርከን 33 ላይ እንዲሆን የተደረገ ነው፡፡
- በተከሳሽ ላይ በቀረበው የወንጀል ክስ የተጠቀሰው ድንጋጌ የሚያስቀጣው መነሻ ቅጣት ከአስራ ሁለት ዓመት ባነሰ ጽኑ እስራት ሆኖ የድንጋጌው ጣሪያ ደግሞ ከአስራ ሁለት ዓመት በላይ ከሆነና ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት ያነሰ ሊቀጣ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ከሆነ ተከሳሹ በሌለበት ክርክሩ ሊሰማ አይገባም፡፡

---

[172] የሰ/መ/ቁ 231732 (ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ/ም) ይህ የሰበር የህግ ትርጉም ምንም አንኳን ተከሳሽ በሌለችበት ክሱ ሊሰማ ይገባል ወይስ አይገባም የሚል ጭብጥ ለመመለስ ቢሆንም ችሎቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስትን ጨምሮ ሕገ መንግስቱ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ በኂላ በወጡት የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በዋናነት መሰረት በማድረግ በአገራችን ተግባራዊ እየሆነ ያለዉን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ወይም ሞዴሎች (Criminal Justice Administration Process Model/s) በሰፊው መርምሯል፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 231732

ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች - በፍትሕ ሚኒስቴር - የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ዘነበች ቸሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰው ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተከሰሰ ሰው በሌለበት ክርክሩ ሊታይ የሚችል መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 የተደነገገዉን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽማለች በሚል ክስ መስርቶባታል፡፡ ለተጠሪ በአድራሻዋ መጥሪያ እንዲደርሳት ታዞ በአድራሻዋ ባለመገኘቷ መጥሪያ ማድረስ ባለመቻሉ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎላትም አልቀረበችም፡፡ይህንን ተከትሎ የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 266638 ላይ በቀን 07/07/2014ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ላይ በተደነገገው መሰረት ተከሳሹ ከአስራ ሁለት ዓመት በታች በሚቀጣ ድንጋጌ የተከሰሰ እንደሆነ ክርክሩ በሌለበት ሊቀጥል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ በተከሰሰችበት ወንጀል ጥፋተኛ ብትሆን ልትቀጣ የምትችለው መነሻውን 5 ዓመት ጣሪያውን 20 ዓመት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ጥፋተኛ ሆና ከተገኘች በዚህ ፍቅድ ሥልጣን ዉስጥ ቅጣቱን ስለሚወስን ተጠሪ ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ለትቀጣ ትችላለች፡፡ስለሆነም ተጠሪ የተከሰሰችበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ሊያስቀጣ የሚችል ስለሆነ በሌሉበት የሚታይ ባለመሆኑ ተጠሪ ሲገኙ መዝገቡን አመልካች ማንቀሳቀስ እንዲችል መብት ተጠብቆለታል በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡በሀሳብ የተለዩት ዳኛ ተጠሪ የተከሰሰችበት ድንጋጌ ምንም እንኳን መነሻ ቅጣቱ 5 ዓመት የሚል ቢሆንም መድረሻ ቅጣቱ እስከ 20 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ተጠሪ በሌለችበት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል በመሆኑ በሌለችበት ክርክሩ ሊሰማ ይገባል የሚል ምክንያት አስፍረዋል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ቢያቀርብም ችሎቱ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉድለት የለበትም በሚል በመ/ቁጥር 225068 ላይ በቀን 10/09/2014ዓ/ም በሰጠው ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት ይግባኙን ሰርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 25/11/2014ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ - ተጠሪ የተከሰሰችበት ድንጋጌ ላይ የተመለከተው መነሻ ቅጣት ምንም እንኳን 5 ዓመት ቢሆንም እስከ 20 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ተጠሪ በሌለችበት ለመታየት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) የተደነገገው መስፈርት ተሟልቶ እያለ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሌለበት ሊታይ አይችልም በማለት መዝገቡን

መዝጋቱም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ ላይ የቀረበዉን ይግባኝ መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ታርሞ ክርክሩ ተጠሪ በሌለችበት ሊቀጥል ይገባል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 27/1 እና 540ን ተላልፋለች በሚል የተመሰረተባት የወንጀል ክስ ተጠሪ በሌለችበት ሊታይ አይችልም በማለት የተወሰነበትን አግባብነት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161 ጋር ተገናዝቦ ተጠሪ ባለችበት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በአድራሻዋ በአካል ባለመገኘቷ ትኖርበታለች በተባለው ቤት ላይ በአስተዳደሩ በኩል መጥሪያዉ ተለጥፎ ባለመቅረቧ መልስ የመስጠት መብቷ ታልፎ በሌለችበት እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረተው የወንጀል ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 27/1 እና 540 ስር የተደነገገዉን ተራ የሆነ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ቀርበው እንዲከራከሩ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ በወጣ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎላት ባለመቅረቧ አመልካች ተጠሪ በሌለችበት እንዲታይ ጠይቋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት እንዲያይ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ)ን በመጥቀስ ተጠሪ የተከሰሰችበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት ያነሰ ሊያስቀጣ የሚችል በመሆኑ ክሱ ተጠሪ በሌለችበት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ባለመቀበል ተጠሪ ሲገኙ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ መብት ጠብቆ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትንም የአመልካችን ይግባኝ ሰርዟል፡፡እኛም ተጠሪ የተከሰሰችበት ወንጀል ተጠሪ በሌለችበት ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን? በጭብጥነት በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከፍ ሲል በተገለጸዉ መሰረት ለተያዘው ጭብጥ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስትን ጨምሮ ሕገ መንግስቱ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በወጡት የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በዋናነት መሰረት በማድረግ በአገራችን ተግባራዊ እየሆነ ያለዉን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ወይም ሞዴሎች (Criminal Justice Administration Process Model/s) ምንነት መመርመር ይጠይቃል፡፡

አገራት በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓታቸው አሜሪካዊው የሕግ ሊቅ ሔርበርት ፓከር (The American legal scholar, Herbert Packer) እ.ኤ.አ.1964 "*The Two Models of the Criminal Proces* (1964)" በሚል ባሳተሙት የምርምር ጽሁፋቸው ላይ ያስተዋወቁትን ሁለት የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎችን በተለያየ ሁኔታና ደረጃ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎች ወንጀል የመቆጣጠር እና ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴሎች (The Crime Control and Due Process Models) በሚል የሚታወቁ ናቸዉ፡፡ የእነዚህ ሞዴሎች መገለጫዎች እና ዓላማዎች በጥቅሉ የተመለከትን እንደሆነ ወንጀል የመቆጣጠር ሞዴል (The Crime Control Model) የሕብረተሰብን ሰላም፣ደህንነትና ጸጥታ ማረጋገጥን ዓላማዉ በማድረግ በቀዳሚነት ዋጋ የሚሰጠዉ ለቅልጥፍና እና የሕዝቡን ደህንነትና ንብረት ከጥቃት መከላከል ላይ ነው፡፡ ይህ ወንጀልን የመቆጣጠር ሞዴል የወንጀል ተጠርጣሪዎች መብት በመጠበቅ ላይ ትኩረት ማድረጉ አጥፊዎችን የማስቀጣቱን ሂደት አስቸጋሪ ስለሚያደርግ በዚህ ምክንያት ወንጀለኞች ከተጠያቂነት ከሚያመልጡ አጥፊዎቹን ለመቅጣት በተዘረጋው ሂደት ንጹሀን የሚቀጡበት ሁኔታ ቢያጋጥም ይሻላል ብሎ ያምናል፡፡ ከዚህ እምነቱ በመነሳት በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ለማስቀጣት ጥቅም ላይ የሚያውለው ሂደት ተጠርጣሪውን እንደወንጀለኛ የሚገምት (Presumption of guilt) መሆኑ፣የወንጀሎች አፈጻጸም መቀነስ ላይ ቅድሚያ መስጠት( Priority is reducing criminal conduct )፣የምርመራና የፍርድ ሂደቱን ፈጣን ማድረግና የመጨረሻ ውሳኔ በመስጠት ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ ከፍርድ ሂደት በፊት በተጠርጣሪው ጥፋተኝነት ላይ ድርድር ማድረግ እና ብዙ ሰዎችን አስሮ መመርመርን (Mass incarceration) ትኩረት የሚያደርግ፣ እውነታን መፈለግ ላይ

ውስንነት (Limited fact finding) የሚታይበት እና ጥፋተኛ አድርጎ የማስቀጣት ምጣኔ ከፍተኛ (High Rate of Conviction) እንዲሆን የሚያደርግ ውጤት የሚያስከትል ነው፡፡

በሌላ በኩል ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴል (The Due Process Model) ቀዳሚ ትኩረቱ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ፍትሐዊ እንዲሆንና በተሳሳተ ሂደት በመከተል ንጹሃን እንዲቀጡ ማድረግ አይገባም ብሎ የሚያምን ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ንጹህ ሰው ያለጥፋቱ ቀጥቶ ከመጉዳት በሂደቱ ወንጀለኞች ከተጠያቂነት ቢያመልጡ ይሻላል ብሎ ያምናል፡፡ከዚህ እምነቱ በመነሳት የወንጀል ተጠርጣሪዎች በተጠረጠሩበት ወይም ተከሳሾች በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመገመት (Presumption of innocence)፤ ለተጠረጠሩ/ ለተከሰሱ ግለሰቦች መብት አጠባበቅ ቅድሚያ መስጠት (Priority on protecting individual rights)፣ ሂደቱን ፍትሐዊ ማድረጉ ላይ ትኩረት መስጠት (Emphasizes fairness in the process)፣እውነታን መፈለግ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ማድረግ (Emphasizes the importance of fact-finding) ፣ ማቅለያዎችንና አክባጅ ምክንያቶችን ከግምት በማስገባት እያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ፍትሃዊነት እንዲረጋገጥ ማድረግ (Individualized justice that considers mitigating and aggravating factors)፣ እንዲሁም የሚታሰሩ ሰዎች ምጣኔ አነስተኛ እንዲሆን (Lower incarceration rates) የሚያደርጉ እና እነዚህን የመሳሰሉትን ሌሎች ሂደቶችንና አሰራሮችን መከተልን የሚመርጥ ሞዴል ነው፡፡በዚህ አመለካከቱ የተነሳ የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ መብት እንዲጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት በፖሊስ እና በሕግ አስፈጻሚ ላይ ይጥላል፤በፖሊሶች ሥልጣን ላይም ገደብ ያደርጋል፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል ፖሊስ በወንጀል የጠረጠረውን ሰው እንደፈለገ አስሮ ምርመራ እንዳያደርግ የተጠረጠሩ ሰዎች ስለሚታሰሩበት አግባብ ሥርዓት ይዘረጋል ፣የተጠረጠሩ ሰዎች ስለተጠረጠሩበት ጉዳይ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁ ዝም የማለት መብት እንዳላቸው መርማሪ ፖሊስ እንዲነግራቸው ግዴታ ይጥላል፣ ተጠርጣሪዎችን በማስገደድ ማስረጃ እንዳይሰበስብ ማድረግና ፖሊስ ተጠርጣሪን አስገድዶ የሰበሰበው ማስረጃ ተቀባይነት እንዳያገኝ ማድረግ ለአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱም ሞዴሎች የየራሳቸዉ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳላቸው በዘርፉ የተጻፉ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡እንዲሁም ሁለቱም ሞዴሎች ነባራዊ ሁኔታን ችላ በማለት የየራሳቸውን ጽንፍ በመያዛቸው እና የወንጀል ተጎጂዎችን (crime victims) ዘንግተዋል የሚል ትችት ይቀርብባቸዋል፡፡ ከእዚህ የተነሳ አገራት በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓታቸው ሌሎች ሞዴሎችን በተጨማሪነት ተግባራዊ ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡በዚህ ረገድ የሚጠቀሰዉ አንደኛው በእንግሊዝኛ መጠሪያው The Punitive Model of Victims' Rights በሚል የሚታወቅ ሆኖ በግርድፉ የተጎጂዎችን መብቶች ማዕከል ያደረገ የአስቀጭነት ሞዴል ተብሎ ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡ ይህ ሞዴል የወንጀል ጉዳዮች የማጥራት እና የማስቀጣት ምጣኔ ጥሩ እንዲሆን ከተፈለገ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓቱ ቀጣይነት ባለዉ ሁኔታ ራሱን ማሻሻል ይኖርበታል፤የወንጀል ተጎጂዎች የተፈጸመባቸዉን የወንጀል ድርጊት ሪፖርት የሚያደርጉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደቱ በሚፈጸሙ ተግባራት የዳግም ተጠቂነት ሰለባ እንዳይሆኑ ለመከላከል( to prevent revictimization within the criminal process)የሚያስችል እርምጃ መዉሰድን፣ከወንጀል አፈጻጸም ድርድር (Conduct Plea Bargaining ) እና ከጥፋተኝነት ድርድር (Guilty Plea Bargaining) ጋር በተያያዘ ተጎጂዎችንና የወንጀል ድርጊቱን ፈጻሚ ማዕከል ማድረግ ይገባል የሚሉ አመለካከቶችን የሚያራምድ ነው፡፡

ሌላዉ The Non-Punitive Model of Victims' Rights: A Circle Model በሚል የሚታወቅ ሞዴል ሲሆን ከሚያራምደው አመለካከት ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል አንዴ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ አጥፊውን መቅጣት ተፈጽሞ ያለፈውን ጥፋት(ያለፈ ጊዜ/ተግባር) ማዕከል ማድረጉ ላይ ስለሚያተኩርና እምብዛም የወደፊቱን ጊዜ የማመለከት እና ወደፊት ሊፈጸም የሚችልን ወንጀል የማያስቀር በመሆኑ ቅጣትን ማዕከል ከማድረግ ይልቅ የወንጀል ተጎጂዎችን መብት በጠበቀ አኳኋን

እና ጉዳዩ የሚያገባቸውን በሂደቱ ማሳተፍ ላይ (የወንጀሉ ድርጊትና ውጤቱ የሚመለከታቸውን ሰዎች ሁሉ በማሳተፍ) ትኩረት በማድረግ በወንጀሉ ምክንያት የተፈጠረውን ማንኛውንም ጉዳት እና አለመግባባት መፍታት/ማከም፣ ተጎጂዉን መካስ እና ከጉዳቱ በፊት ወደነበሩበት የሚመልስ ፍትህ ማስገኘት (healing, compensation, and restorative justice) ይገባል ብሎ የሚያምን ነው፡፡በዚህ መሰረት ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ተሳትፎ ሳያደርግ አጥፊውን ከመቅጣት ይልቅ በተፈጸመው ወንጀል ተጎጂ የሆኑ ሰዎችን፣ የእነርሱን ቤተሰቦች፣ የወንጀሉን ፈጻሚዎች እና ደጋፊዎቻቸውን ሊያሳትፍ የሚችል አማራጭ የመፍትሄ ዘዴዎችን በመከተል ለአብነት አጥፊው በሂደቱ በሚያደርገው ተሳትፎ ለፈጸመው በደል በራሱ ኃላፊነቱን ወስዶ ይቅርታ በመጠየቅ በደሉን እንዲያክምና ተጎጂዉን እንዲክስ የሚያደርግ ሂደት መከተል ይገባል ይላል፡፡ እንዲሁም አጥፊውን መቅጣት አስፈላጊ ከሆነም ለተጎጂው ጉዳት እውቅና ለመስጠትና ተጎጂውን ከማክበር አኳያ ታይቶ ቅጣት መወሰን ማዕከል ያደረገ ሂደት መከተል ይገባል የሚል አቋም ያለዉ ሞዴል ነው፡፡ይህ ሞዴል በዉጤታማነት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ እና ለወደፊትም የወንጀል አፈጻጸም ምጣኔ እንዲቀንስ የማህበረሰብ እድገት (social development) የሚያመጡ ሥራዎችን በተለይም በሕጻንነት የዕድሜ ጊዜ (Early childhood) ለዚህ የሚያግዙ ሥራዎችን መስራት እንደሚገባ በዚህ ሞዴል ዙሪያ የተጻፉት የሕግ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡

ከላይ ስለወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎች ጽንሰ ሀሳባ በአጭሩ የተመለከትነዉን ከግምት በማስገባት የእኛ አገር የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ምን እንደሚመስል መርምረናል፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት ስለተያዙ እና ስለተከሰሱ ሰዎች መብቶች፣በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት፣የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሠራ ስለመሆኑ፣በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለሚከለክል…ወዘተ መርሆዎች ከአንቀጽ 19-23 ድረስ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡በዚህ መልኩ በሕገ መንግስቱ እውቅና ከተሰጣቸው መብቶችና መርሆዎች ውስጥ በአንቀጽ 20 ስር የተደነገገውን የተከሰሱ ሰዎችን መብት ያየን እንደሆነ የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት እንዳላቸው፣በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት እንዳላቸው፣ የቀረቡባቸውን ማናቸዉንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው፣በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል እና የፍርዱ ሂደት በሚገባቸው ቋንቋ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡እነዚህ የተከሰሱ ሰዎች መብቶች ተከሳሽ በሌለበት በሚታይ የፍርድ ሂደት ጭምር ክሱን በሚያቀርበው ዐቃቤ ሕግ እና መብቱን በሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ላይ እንደ ግዴታ የሚቆጠር ቢሆንም እነዚህ መብቶች *በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውሉት* ተከሳሹ በፍርድ ቤት ቀርቦ የፍርድ ሂደቱን ሲከታተል በመሆኑ ሕገ መንግስቱ ተከሳሽ ባለበት የፍርድ ሂደቱ እንደሚከናወን በማሰብ እንደደነገጋቸዉ የሚቆጠሩ ናቸዉ፡፡ ይህም ተከሳሽ ባለበትም ሆነ ተከሳሽ በሌለበት በሚታይ የፍርድ ሂደት የተከሰሱ ሰዎች መብቶች እንዲከበሩ ሕገ መንግስቱ እንደሚፈልግ ማሳያ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ሕገ መንግስቱ በአብዛኛዉ ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴል (The Due Process Model) በሚል ለሚታወቀው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ትልቅ ስፍራ እንደሚሰጥ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በተመሳሳይ ኢትዮጵያ በተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ 14 ላይም የተከሰሱ ሰዎች ተመሳሳይ መብቶች እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡በተለይ በዚህ ቃል ኪዳን አንቀጽ 14(3/መ) ላይ ተከሳሹ በአካል ችሎት ቀርቦ ራሱን የመከላከል (የመዳኘት) መብት እንዳለው በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ በተጠቃሹ ቃል ኪዳን የተደነገገው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/4 እና 13/2 ስር በተደነገገው መሰረት የአገራችን የሕግ አካል ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑ በሕገ መንግስቱ እና በተዋረድ ባሉ ሕግጋት ስለተከሰሱ ሰዎች መብቶች የተደነገገው በዚህ ቃል ኪዳን ከተደነገገው ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ሊተረጎም እና/ወይም ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በ2003ዓ/ም

ወጥቶ ተግባራዊ እየሆነ የሚገኘዉን የኢፌዲሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የተመለከትን እንደሆነ በፖሊሲው ተራ ቁጥር 3.2 ላይ እንደተመለከተዉ ሕብረተሰቡ የወንጀል ሕጉን ከማስፈጸም አኳያ የወንጀል ድርጊቶችን ሪፖርት በማድረግ እና በተለያየ ደረጃ በወንጀል ምርመራ እና በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎችን በማገዝ እንዲሳተፍ ማድረግ፤ ቁጥር 3.3 ላይ እንደተመለከተው የመርማሪ ፖሊሶችንና የዐቃቤያነ ሕግን የሙያ ዕውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውንና የሥነ ምግባር ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ እና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን የሚያሳድጉ ሥራዎችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መስራት፤በቁጥር 3.4 ላይ እንደተገለጸው የወንጀል ምርመራ ዓላማ በአጠቃላይ ስለ ወንጀል የማወቅ ፣ወንጀል እንዳይፈጸም የማስቆም፣ወንጀል ከተፈጸመ ጉዳቶችን የመቀነስ፣ የወንጀል ዒላማ የሆኑትን ሰዎች፣ንብረቶች ወይም ጥቅሞችን የመከላከል፣ወንጀል ፈጻሚዎችን ለሕግ የማቅረብ እና የወንጀል ተጎጂዎችን መብቶችና ጥቅሞችን የማስከበር ነው፡፡ ውጤታማና ቀልጣፋ የወንጀል ምርመራ ሥራን በማከናወን የሕዝብ ጥቅም፣በወንጀል ድርጊት የተጎዱ ሰዎች እና የተጠርጣሪዎች መብት እንዲጠበቅ ማድረግ እንዲቻል የወንጀል ምርማሪ የምርመራ ሥራውን ከዐቃቤ ሕግ ጋር ሊያከናውን እንደሚገባ በፖሊሲው ቁጥር 3.6 ላይ መገለጹ፤ በቁጥር 3.9 ላይ እንደተገለጸው በቀላል እስራት ወይም በሕጉ መሰረት በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ እና በግለሰብ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች በተበዳዩ እና በተጠርጣሪው መካከል እርቅ ከተፈጸመ ወንጀል ምርመራው ወይም የተመሰረተው ክስ እንዲቋረጥ ሊደረግ እንደሚችል፤ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ የሆነ ማስረጃ የሌለ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ እና ተጠርጣሪው በሌለበት ክሱ ሊታይ የማይችል እንደሆነ…ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ አይመሰረትም በማለት መወሰን እንደሚችል በቁጥር 3.11 ላይ መገለጹ፤ የክስና የፍርድ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅ ተከሳሹ ተገቢ ለሆነ አጭር ጊዜ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ሊደረግ እንደሚችል እንዲሁም በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ከምርመራ ወይም ከፍርድ ሂደት መጠናቀቅ ጋር በተያየዘ በእስር ላይ የሚቆዩ ተጠርጣሪዎችን ወይም ተከሳሾችን ቁጥር ለመቀነስ እንዲቻል የምርመራ ወይም የፍርድ ሂደት የሚቀላጠፍበትን ሁኔታዎች ከማመቻቸት በተጨማሪ ከእስር ውጭ ያሉ ሌሎች አማራጮችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚቻልባቸውን መንገዶች በጥናት በመለየት ተግባራዊ ማድረግ በቁጥር 3.16.2 ስር መገለጹ፤ የምስክሮች አለመገኘትና የማስረጃ መጥፋት ምክንያት የሚፈጠረውን የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማ አለመሆን ለማስቀረት…ተጠርጣሪዎች ቀደም ብለው ጥፋተኝነታቸውን እንዲያምኑ ማበረታታትና የጥፋተኝነት ድርድር የሚካሄድበትን የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፣የወንጀል ጉዳዮች ክርክር በመደበኛ የፍርድ ሂደት ዉስጥ በማለፋቸው ምክንያት በተጎጂዎች፣በምስክሮችና በተከሳሾች ሥነ ልቦና ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለማስቀረት የሚያስችል የጥፋተኝነት ድርድር ማድረግና ተከሳሹ ለፈጸመው ጥፋት በራሱ ነጻ ፍቃድ ኃላፊነት ወስዶ ባደረገው ድርጊት ተጸጽቶ በመታረም ለወደፊቱ ሰላማዊ ሆኖ እንዲኖር ማድረግ እንደሚቻል በቁጥር 4.1.፣4.5.4 ላይ መስፈሩ፤ እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚሰጡ አላስፈላጊ ቀጠሮዎችን ለመቀነስና የፍርድ ሂደቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ …መርማሪዎች እና ዐቃቤያነ ሕግ ከፍርድ ቤት በሚሰጥ መጥሪያ መሰረት ተከሳሽን እና ምስክሮችን በችሎት የማቅረብ ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ በፖሊሲው ቁጥር 4.3.2 ስር መገለጹ፤ ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚችል ማስረጃ ቢኖርም ጉዳዩ በአማራጭ የመፍትሄ እርምጃ መታየቱ የሕዝብን ጥቅምና የተጎጂውን መብቶች በተሻለ የሚያስጠብቅ ከሆነ በተጠርጣሪና በግል ተበዳይ መካከል የተፈጠረውን የወንጀል ምክንያት…ከፍርድ ሂደት ውጭ ባሉ አማራጭ ዘዴዎች ተጠርጣሪው/ተከሳሹ በራሱ ፈቃድ ኃላፊነት እንዲወስድ በማድረግ፣ የግል ተበዳዩንና ወንጀል አድራጊውን በማስታረቅ እንዲሁም ተጠርጣሪው ለግል ተበዳዩ ካሳ እንዲከፍል በማድረግ ዘላቂ መፍትሔ እንዲገኝ ማድረግ፣ በተጨማሪም በወንጀሉ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው በጉዳዩ ላይ በሚደረገው የምርመራ ፣የክስ አቀራረብ እና የፍርድ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርግ፣ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ በቅርብ የመከታተል እና ስለሚሰጡት ውሳኔዎች ተገቢውን መረጃ የማግኘት…መብት እንዳለው በቁጥር 4.6.2. እና 6.2.1

ተገልጿል። በምርመራም ሆነ በክስና በክርክር ሂደት ልዩ ትኩረት የሚሰጥባቸው የወንጀል ጉዳዮች በተመለከተም በፖሊሲው ቁጥር 3.15 ላይ በሕዝብ ሰላምና ደኅንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ በሕገ መንግስትና በሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈጸሙ እንደሽብርተኝነት፣ የሀገር ክህደት፣ከባድ የሰው ግድያ...የመሳሰሉት ከባድ ወንጀሎች ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ከባድ ወንጀሎች እንደሆኑ ተመልክቷል።

ከዚህ በላይ በዝርዝር የተጠቀሰው የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ይዘት ከፍ ሲል የተጠቀሱትን አራቱንም የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎችን ከግምት ያስገባ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ተግባራዊ ማድረጉንና በሚወጡ ሕጎችም እነዚሁ ሞዴሎችን ታሳቢ ያደረገ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ተግባራዊ እንዲደረግ ፍላጎቱ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

እንዲሁም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገውን የወንጀል ሕጉን ዓላማና ግብ የተመለከትን እንደሆነ የወንጀል ሕጉ ዓላማ የአገሪቱን መንግስት፣ የሕዝቦቹን፣ የነዋሪዎቹን ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት መብትና ጥቅም ማረጋገጥ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልኩ ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀልን መከላከል፣አጥፊዎች በመቅጣት በማረም ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ በማድረግ እና ሌሎችን የማስተማር ግብ መያዙ ወንጀል የመቆጣጠር ሞዴል(The Crime Control Model) ለሚባለው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት ሞዴል ትኩረት እንደሚሰጥ ያሳያል።በሌላ በኩል በሕጉ የመጀመሪያ ታላቅ ክፍል ስለሕጋዊነት መርህ የተደነገገው፣በሕግ ፊት እኩል ስለመሆን፣የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ፣ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቀልለትን የተሻለውን ሕግ ተፈጻሚ ስለማድረግ፣ስለይርጋ ጊዜ አፈጻጸም ደንቦች የደነገገው፣በተሻረው ሕግ መሰረት የተሰጡ ፍርዶች አፈጻጸም ...ወዘተ የሚመለከቱ መርሆዎች እና ስለቅጣት ማቅለያዎችና ማክበጃ ምክንያቶችና አፈጻጸማቸው እንዲሁም በሕግ በግልጽ ሲፈቀድ ፍርድ ቤት በመሰለው ቅጣት የሚያቀልበትን አግባብ መደንገጉ የወንጀል ሕጉ ፍትሐዊ ሂደት የመከተል ሞዴል (The Due Process Model) ጭምር የተንጸባረቀበት ሕግ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም በወንጀል ሕጉ በወንጀል ክስ አቅራቢነት ከሚያስከስሱ ወንጀሎች በተጨማሪ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ስለሚያስቀጡ ወንጀሎች (offence is punishable upon complaint) መደንገጉ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት የግል ተበዳይን(የተጎጂን) ተሳትፎ ማረጋገጡንና የተጎጂዎችን መብቶች ማዕከል ያደረገ የአስቀጭነት ሞዴል (The Punitive Model of Victims' Rights) ያካተተ ሕግ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

በተጨማሪም የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6(3/መ) ስር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የጥፋተኝነት ድርድር እንዲወስን፣ድርድር እንዲደረግ፣አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ እንዲወሰድ መወሰን እንዲችል ከተሰጠው ሥልጣን መገንዘብ የሚቻለው በሕጉ የተንጸባረቀው ወንጀል የመቆጣጠር ሞዴል መከተል ብቻ ሳይሆን ቅጣትን ማዕከል ከማድረግ ይልቅ የወንጀል ተጎጂዎችን መብት በጠበቀ አኳኋንና በወንጀሉ ምክንያት የተፈጠረውን ማንኛውም ጉዳት እና አለመግባባት ፣መፍታት/ማከም፣መካስ እና ከጉዳቱ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ የሚያደርስ አማራጭ ፍትህ የማግኛ መንገዶችን የሚመለከተውን ሞዴል (The Non-Punitive Model of Victims' Rights) ጭምር መከተል እንዲቻል እድል የሚሰጥ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሂደት መከተል እንደሚቻል መደንገጉን የሚያሳይ ሕግ ነው። በተጨማሪም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/8 ስር ስለሰብዓዊ መብት በተመለከተ የተደነገገውም በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት የምንከተለው ሞዴል ወንጀል የመቆጣጠር ብቻ ሳይሆን የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ፣አከበበርና ማሟላት ጋር በተያያዘም ሕጉ ትኩረት መስጠቱን ስለሚያመላክት ፍትሐዊ ሒደት የመከተል ሞዴል በሕጉ መንጸባረቁን የሚያሳይ ነው።

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉን የተመለከትን እንደሆነ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ስለሚያዝበት፣ ስለብርበራ፣የተያዘ ሰው ፍርድ ቤት መቅረብ ስላለበት ጊዜ እና ሁኔታ፣በወንጀል ምርመራ ወቅት ቃሉን ለመስጠት ያለመገደድና ዝም የማለት መብት ያለው ስለመሆኑ፣የተያዘው

ሰው ለምርመራ ዓላማ ተጨማሪ ጊዜ በእስር ላይ የሚቆየው በፍርድ ቤት ፈቃድ መሆኑ፣በዋስትና ወረቀት የመለቀቀ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ሲከሰስም ስለወንጀሉ አፈጻጸም በቂ ዝርዝር ከያዘ የክስ ማመልከቻ ጋር መጥሪያ ደርሶት ችሎት ቀርቦ በግልጽ ችሎት የመዳኘት፣ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የመመርመር፣ አለኝ የሚለውን መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ራሱን የመከላከልና የመሰማት መብት እንዳለው በተለያዩ ድንጋጌዎች ላይ መደንገጉ የተከሰሰ ሰው መብት የተጠበቀበትን ወንጀል የመቆጣጠር ሂደትን ማዕከል ያደረገ ወንጀል የመቆጣጠር እና ፍትሐዊ ሂደት የመከተል የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎችን አጣምሮ የያዘ ሕግ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ድንጋጌዎችን የያዘ ሕግ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ሥነ ሥርዓት ሕጉ በዚህ መልኩ ከያዛቸው ድንጋጌዎች መካከል የተከሰሰ ሰው በሌለበት ክሱ ስለሚሰማበት ሥርዓት በተመለከተ በቁጥር 161 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተዘረጋው ሥነ ሥርዓት ይገኝበታል፡፡

ከተያዘው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተፈጻሚነት ያለው የተከሰሰ ሰው በሌለበት ነገሩ ስለሚሰማበት ሥነ ሥርዓት የሚደነግገው የወ/መ/ሥ/ሥሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) እንደሚከተለው ይነበባል፡-

“ (2) …ከዚህ በታች በተመለከቱት ወንጀሎች ካልሆነ በቀር ተከሳሹ በሌለበት የወንጀል ክስ አይሰማም፡፡ (ሀ) ከአሥራ ሁለት ዓመት በታች በማያንስ ጽኑ እስራት የማያስስር ወንጀል የሠራ … ሲሆን ነው፡፡” የሚል ሲሆን የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ቅጅ ደግሞ “(2) No accused person may be tried in his absence … unless he is charged with: (a) an offence punishable with rigorous imprisonment for not less than twelve years.”የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

ከሕግ አተረጓጎም ጽንሰ ሀሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው የተለያዩ የአተረጓጎም ስልቶችንና መርሆዎችን በመጠቀም አንድ ሕግ ወይም የሕግ ድንጋጌ ሊተረጎም የሚገባው ሕጉ ወይም የሕጉ ድንጋጌ አሻሚ፣ ግልጽነት የጎደለው፣አንዱ ድንጋጌ ከሌላው ጋር የሚጣረስ ሲሆንና የሕግ አውጪውን ሀሳብ በግልጽ የማያሳይ ሆኖ የሕግ አውጪውን ሀሳብ ለማግኘትና በሚተረጎመው ሕግ ወይም ድንጋጌ ለማሳካት የታቀደው ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ለማድረግ ሕጉን/ድንጋጌውን መተርጎም የግድ የሚል ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው ሕጉ/የሕጉ ድንጋጌ ግልጽ በሆነ ጊዜ በቀጥታ ተግባራዊ እንዲሆን ከማድረግ ባለፈ ትርጉም እንደማያስፈልገው ነው፡፡

በመሰረቱ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20፣ በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 14(3/መ)፣በኢፌዲሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ላይ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161 ስር ከተደነገገው መረዳት እንደሚቻለው በመርህ ደረጃ የወንጀል ክስ ተከሳሹ በሌለበት አይሰማም፡፡ የዚህ መርህ ልዩ ሁኔታ ከላይ ይዘቱ የተጠቀሰው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) እና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ለ) ስር በመንግስት ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሆነው በጽኑ እስራት ወይም ከብር 5,000.00 በላይ በሚያስቀጡ ከባድ ወንጀሎች የተከሰሰ እንደሆነ በሚል የተገለጸው ነው፡፡ ይህም ሲባል በሌላ ልዩ ሕግ ላይ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደጠበቀ ሆኖ ማለት ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው እና በሌሎች ሕጎቻችን የመንግስትን፣እና የአገሪቱን ሕዝቦች ጥቅም እና የተጎጂዎችን መብት ለመጠበቅ በተለያየ መንገድ ያንጸባረቁት አቋሞች እንደተጠበቁ ሆነው ይህ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) የተከሰሱ ሰዎችን መብት ባስጠበቀ መልኩ ወንጀልን የመቆጣጠር ቅይጥ ሞዴሎች የሚከተል የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት እንዳለን ማሳያ ሊሆን የሚችል ድንጋጌ እንደሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም ምንም እንኳን የሥነ ሥርዓት ሕጉ ሕገ መንግስቱን እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውን ቀድሞ የወጣና ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ እድሜ ያለው ቢሆንም የሥነ ሥርዓት ሕጉ የተከሰሱ ሰዎችን መብት ባስጠበቀ መልኩ ወንጀልን የመቆጣጠር ቅይጥ ሞዴል ነጸብራቅ የሆኑ ድንጋጌዎችን በመያዝ የወጣ ነው በሚያስብል መልኩ አብዛኛዎቹ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች በአካል በተገኙበት ተሰምቶ እንዲወሰን መፈለጉን እና ለተከሳሾች የመሰማትና ራስን የመከላከል መብት

እዉቅና ከመስጠቱም ባሻገር ለተከሰሱ ሰዎች መብት ከፍተኛ ጥበቃ ማድረጉን ከዚህ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ይዘት፣መንፈስና ዓለማ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሕግ አውጪው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ)ን በመደንገግ አቋም ሲወስድ ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ የወንጀል ክሶች ማለትም በወንጀል ሕጉ(በ1949 በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ) መነሻ ቅጣታቸው በአስራ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ውስን መሆናቸውን እና አብዛኞቹ የወንጀል ክሶች ተከሳሽ ባለበት ብቻ የሚታዩ እንደሆኑ እያወቀ ነው፡፡ ሕግ አውጪው እንዲህ አይነት አቋም የያዘው ወንጀል ፈጽመዋል በሚል የሚከሰሱ ሰዎች ከፍርድ ሂደት ተሰዉረዉ የወንጀሉ ተጎጂዎች ፍትህ የማግኘት መብት እንደማይጣስ ብሎም የወንጀል ሕጉ ዓላማ ከግብ ሳይደርስ ቀርቶ ጠቅላላዉ ሕብረተሰብ ተገጂ እንዳይሆን ማድረግ እንደሚቻል በማመን ነው፡፡ ይህም እምነቱ እውን እንዲሆን ፖሊስ እና ሌሎች በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው ሕግ አስፈጻሚዎች የተከሰሰውን ሰው በአድራሻው ፈልገው መጥሪያ እንዲደርሰው ማድረግ እንደሚችሉ እና ተከሳሹ መጥሪያ ደርሶትም ሆነ መጥሪያ ላለመቀበል ብሎ በመሰወሩ ምክንያት መጥሪያ ማድረስ ካልተቻለ ወይም በሌላ በቂ ባልሆነ ምክንያት ተከሳሹ ፍርድ ቤት ካልቀረበ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ተይዞ እንዲቀርብ ተገቢውን ትእዛዝ እንደሚሰጥና ፖሊስ ብርቱ ጥረት አድርጎ ተከሳሹን ካለበት ፈልጎ ችሎት እንዲያቀርበው ከፍተኛ ኃላፊነት በፖሊስና በሌሎች ሕግ አስፈጻሚ አካላት ላይ መጣሉን ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 160 እና 161(1 እና 2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ይዘቱ የተጠቀሰዉ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ)ድንጋጌ ለብቻዉ ሲታይ *በወንጀል የተከሰሰ ሰው በሌለበት ክሱ ሊሰማ የሚችለው የተከሰሰበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ (offence punishable with rigorous imprisonment for not less than twelve years) ሲሆን ብቻ ነው* የሚል ግልጽ ይዘት ያለው ድንጋጌ በመሆኑ ትርጉም ሳያስፈልገው በቀጥታ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ትርጉም የሚሻዉ ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል የሚያስቀጣው የጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ሆኖ የጽኑ እስራት ጣሪያ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት በላይ በሆነ የእስራት ቅጣት የሚያስቀጣ ሆኖ በተደነገገ ጊዜ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ተከሳሹ የተከሰሰበት የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ከሚያስቀጣዉ ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በሕጎቻችንና በወንጀል ፍትህ ፖሊስ ስለምንከተለው የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ሞዴሎች የተንጸባረቀውን እና የተከሰሱ ሰዎችን መብት ባገናዘበ መልኩ ሊተረጎም ይገባል፡፡እንዲሁም ተከሳሽ በሌለበት ክስ መስማት(የፍርድ ሂደት ማከናወን) ከላይ እንደገለጽነው ልዩ የሥነ ሥርዓት ሁኔታ(ድንጋጌ) በመሆኑ በሕግ አተረጓጎም ጽንሰ ሀሳብ/መርህ መሰረት በጠባቡ መተርጎም እንዳለበት ከግንዛቤ ማስገባት ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ የመሰረተው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ሙከራ ፈጽማለች በሚል በመሆኑ ይህ ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ነው፡፡የዚህ ድንጋጌ መነሻ ቅጣት ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያንስ በመሆኑ የተነሳ በተያዘው ጉዳይ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ)ን መተርጎም ያስፈልጋል፡፡ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት መፈጸሟ በዐቃቤ ማስረጃ ቢረጋገጥና ተጠሪ በማስተባበል መከላከል አለመቻሏ ተረጋግጦ ጥፋተኛ ብትባል ልትቀጣ የምትችለው በሕጉ አንቀጽ 540 ስር በተደነገገው እና በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ አስራ ሁለት ስር በተመለከተው ደረጃና እርከን መሰረት ነው፡፡ በመመሪያው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ለተደነገገው የእስራት ቅጣት 6 ደረጃዎች የወጣለት ሲሆን የደረጃ 1 መነሻ እርከን እርከን 21 ሲሆን ደረጃ 6 ደግሞ መነሻ ቅጣቱ እርከን 33 ላይ እንዲሆን የተደረገ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከወጡት 6 ደረጃዎች መካከል ሁለቱ ደረጃዎች ማለትም በደረጃ 5 እና

6 ስር የተመደበው የእስራት መነሻ ቅጣት ብቻ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን ቀሪዎች 4 ደረጃዎች ከአስራ ሁለት ዓመት በአነሰ ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ መነሻ እርከኖች የያዙ ናቸው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በተከሰሰችበት ወንጀል ጥፋተኛ ብትባል በአብዛኛው ልትቀጣ የምትችለው ከአስራ ሁለት ዓመት ባነሰ ጽኑ እስራት ሊሆን የሚችልበት ዕድል ሰፊ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተጠሪ ፈጸመች ተብላ የተከሰሰችው ተራ የሆነ የግድያ ሙከራ ወንጀል በመሆኑ ተራ በሆነ ግድያ ሙከራ ጥፋተኛ ብትሆን ፍርድ ቤቱ ከነገሩ ሁኔታዎች በመነሳት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ስር ከተደነገገው አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ዝቅ ብሎ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179/ሐ ስር በተደነገገው መሰረት ቅጣት ሊወስን የሚችልበት ተጨማሪ እድል በመኖሩ ይህም ተጠሪ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት በአነሰ ልትቀጣ እንደምትችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ሲጠቃለል በተከሳሽ ላይ በቀረበው የወንጀል ክስ የተጠቀሰው ድንጋጌ የሚያስቀጣው መነሻ ቅጣት ከአስራ ሁለት ዓመት ባነሰ ጽኑ እስራት ሆኖ የድንጋጌው ጣሪያ ደግሞ ከአስራ ሁለት ዓመት በላይ ከሆነና ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት ያነሰ ሊቀጣ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ከሆነ ተከሳሹ በሌለበት ክርክሩ ሊሰማ አይገባም፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተው የወንጀል ክስ ተጠሪ ጥፋተኛ ሆና ከተገኘች ከአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት ያነሰ ቅጣት ሊወሰንባት የሚችልበት ዕድል ሰፊ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰችበትን ድንጋጌ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ የፍርድ ሂደቱ ተጠሪ በሌለችበት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በሰጠው ትእዛዝም ሆነ በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትእዛዝ በመሰረዙ የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 266638 ላይ በቀን 07/07/2014ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 225068 ላይ በቀን 10/09/2014ዓ/ም ትዕዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ሲጠይቁ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸው፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሠ/መ/ቁጥር 231732

## የሃሳብ ልዩነት

ስሜ በተራ ቁጥር አራት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1 እና 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽማለች በሚል ክስ መስርቶባታል፡፡ ለተጠሪ በአድራሻዋ መጥሪያ እንዲደርሳት ታዞ በአድራሻዋ ባለመገኘቷ መጥሪያ ማድረስ ባለመቻሉ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎላትም አልቀረበችም፡፡ይህንን ተከትሎ የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 266638 ላይ በቀን 07/07/2014ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 161(2/ሀ) ላይ በተደነገገው መሰረት ተከሳሹ ከአስራ ሁለት ዓመት

በታች በሚቀጣ ድንጋጌ የተከሰሰ እንደሆነ ክርክሩ በሌለበት ሊቀጥል አይችልም። ተጠሪ በተከሰሰችበት ወንጀል ጥፋተኛ ብትሆን ልትቀጣ የምትችለው መነሻውን 5 ዓመት ጣሪያውን 20 ዓመት ነው። ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ጥፋተኛ ሆና ከተገኘች በዚህ ፍቅድ ሥልጣን ውስጥ ቅጣቱን ስለሚወስን ተጠሪ ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ላትቀጣ ትችላለች።ስለሆነም ተጠሪ የተከሰሰችበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት በታች ሊያስቀጣ የሚችል ስለሆነ በሌሉበት የሚታይ ባለመሆኑ ተጠሪ ሲገኙ መዝገቡን አመልካች ማንቀሳቀስ እንዲችል መብት ተጠብቆለታል በማለት መዝገቡን በመዝጋት የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው።

ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ የወንጀል ዓይነቶች በወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 161 (2) የተጠቀሱት ብቻ ናቸው። አንደኛው ሁኔታ በፊደል (ሀ) የተገለፀው ከአስራ ሁለት ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ሁኔታ በፊደል (ለ) የተገለፀው በወ/መ/ሕ/ቁ.354-365 ድረስ ያሉትን ወንጀሎች ፈፅሞ ፅኑ እስራት ወይም ከአምስት ሽህ ብር በላይ መቀጮ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ሲሆን ነው። ይህ ድንጋጌ በቀላል እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ እንደማይሰማ ያስረዳል።

ተከሳሽ በሌለበት ማየት የሚቻለዉ ለፍትህ ጥቅም ሲባል ቢሆንም ተከሳሹ ስለ ክሱ እና ክርክሩ ሂደት እዉቅና እንዲኖረው ለማድርግ ፍ/ቤቱ ሁሉንም የማሳወቂያ ሂደቶች በመጠቀም የማሳወቅ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ተከሳሽ በክርክሩ የመገኘት መብቱን በግልፅ የተወ ሆኖ ሲገኝ ግን በራሱ ክርክሩን በመተው (waive) ምክንያት በሌለበት ሊታይ ይችላል። ይህ የመተው መብት ተገቢ የሚሆነው ፍ/ቤት የራሱን ግዴታ በተለይ ተከሳሹ መከሰሱን እንዲያውቀው ጥሪ አድርጎ እና መጥሪያው የደረሰው መሆኑ የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ ነው። ሃገራት ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩን ሊመለከቱ የሚችሉ ቢሆንም ይህ የሚቻለው በቅድሚያ ለተከሳሽ በቂ ጊዜ በመስጠት በአግባቡ መጥሪያ ተሰጥቶት ለክርክሩ እንዲቀርብ የችሎቱ ጊዜና ቦታ ተገልፆ የተጠራ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ የቀጠለው ተከሳሹ የመገኘት መብቱን በመተው ምክንያት በሆነ ጊዜ ግን በክርክር የመገኘት መብት ሊታይ የሚገባው ከተከሳሽ የመሰማት መብት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከተጎጂዎችና ከምስክሮች እንዲሁም ከጠቅላላው ማህበረሰብ ጥቅምና ፍላጎት አኳያ ጭምር መሆን አለበት። የወንጀል ክስ ጉዳይ ዐ/ህግንና ተከሳሽን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የወንጀል ሰለባዎችንም የሚመለከት ሆኖ እዉነትን በመፈለግ ፍትህን የማረጋገጥ ጉዳይ ጭምር በመሆኑ ከዚህ አኳያም ማየት ይገባል። ይህ ህጋዊ የማህበረሰብ ጥቅም በዋናነት የሚገለፀውና የሚረጋገጠው ደግሞ የተከሰሰ ሰው በወንጀል ክርክር ሂደት በፍ/ቤት እየቀረበ ሲከታተል በመሆኑ የራሱን የተከሳሹን መብት፣ የተጎጂዎችን እና የምስክሮችንም ፍላጎት እንዲሁም ጥቅም የሚያስጠብቅ ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

የሥነ-ሥርዓት ሕግ ዓላማውም የሥነ-ሥርዓታዊ ፍትሕን በማረጋገጥ ክርክር ወጭና ጊዜ ቆጣቢ ሆነ ውጤታማ በሆነ አግባብ እንዲመራ ማስቻል ነው። ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትሕ /procedural justice/ በተመሳሳይ በመሠረታዊ ሕግ እንደተመለከተው መብትና ፍትሕ /substantive justice/ መከበርና መተግበር አለበት። አንዱን ከአንዱ ማበላለጥ ሆነ አንደኛውን የፍትሕ ዘንግ ለማስከበር ሌላኛውን መጣስ ተገቢ አይደለም። የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ሲተረጎም የወንጀል ሕጉ ሊያሳካው የፈለገው ግብ ከተከሳሽ ሰብዓዊ መብት አተገባበር ጋር ተጣጥሞ ሊሆን ይገባል። በዚህ ሂደትም ድንጋጌው ውጤት ሊሰጥ በሚችል መልኩ መተርጎም አለበት። በወንጀል ጉዳዮች አከራካሪዉ ነጥብ ከ12 ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ የሚለዉ አገላለፅ ምን ማለት ነው የሚለው ነው። አንዱ የሚነሳው ሃሳብ እና በአብላጫው የውሳኔ ሃሳብም የተገለጸው ተከሳሽ በሌለበት ክሱ ሊሰማ የሚገባው ተከሳሽ በተከሰሰበት ወንጀል ፍ/ቤቱ በተጨባጭ የሚወስነው ቅጣት 12 ዓመትና በላይ ሆኖ መገኘት ነው የሚል ሲሆን በወንጀል ክርክር ሂደት ማስረጃው ሳይሰማ አስቀድሞ የሚወሰነውን ቅጣት ምን ያህል እንደሚሆን ማወቅ አይቻልም። ለምሳሌ በወ/ሕ/ቁ. 27(1) እና 539 ከባድ ሰው ግድያ ሙከራ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የወንጀሉ አፈፃፀም በማስረጃ ተመዝኖ ዝቅተኛውን ቅጣት በ10 ዓመት

ፅኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል፡፡ በሌሎች ወንጀሎችም ተመሳሳይ ሁኔታ ይገጥማል፡፡ የቅጣት አስተያየትና ክርክር በግራቀኙ ወገኖች ሳይደረግ፣ የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ምክንያቶች ሳይታወቁ፣ የወንጀሉ ዝርዝር አፈጻጸም ሳይታይ፣ የደረሰው ጉዳት በማስረጃ ሳይጣራ ቅጣት መጠኑን መለየት አይቻልም፡፡ ተከሻሽ ጉዳዩ በሌለበት ሊታይ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ማስረጃ ከመስማቱ በፊት በመሆኑና ቅጣቱን ከማስረጃና ከክርክር በፊት በትክክል ለይቶ አስቀድሞ ማወቅ ስለማይቻል ድንጋጌው ይህን ሀሳብ የያዘ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

ሁለተኛው ሃሳብ የወንጀሉ ድንጋጌ የቅጣት መነሻ 12 ዓመት ፅኑ እስራት በላይ ከሆነ ነው የሚል ሲሆን የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎችን ስንመለከት መነሻ ቅጣታቸው 12 ዓመት የሚሆን ባይኖሩም ከዚህ በታች መነሻ ኖሯቸው እስከ እድሜ ልክ ወይም ሞት እስከሚደርስ የሚያስቀጡ ድንጋጌዎች የወ/መ/ሕ/ቁ. 522 (ከባድ ሰው ግድያ)፤ 638 (ዘረፋ)፤ 637/2 (ከባድ ውንብድና)፤ 639 (የባህር ላይ ውንብድና) እና 270 (በመንግስት ግዛት ሀገር የሚፈጸሙ ወንጀሎች) ናቸው፡፡ በ1996 በተሻሻለዉ የወንጀል ህግ መነሻ ቅጣታቸው በ1949 ከነበረው ከፍ ብሎ ከ12 ዓመት በላይ የተደረጉ ድንጋጌዎችም አሉ (ለምሳሌ የወ/ሕ/ቁ. 620/3 እና 627/1 መመልከት ይቻላል)፡፡ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 161/2 የተቀረጸው የተከሳሽ ሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ልዩ ሁኔታ ሆኖ የሕዝብ ጥቅምን ለማስፈን ነው፡፡ ለእነዚህ ውስን ድንጋጌዎች የተቀረጸ ነው በማለት መተርጎም ሕጉ ውጤት እንዳይኖረው ከማድረግ ባለፈ የሕብረተሰቡን ጥቅም የሆነውን የህግ የበላይነት መኖርን የሚያስጠብቅ አይደለም፡፡

ሕጉ የወጣለትን ዓላማ ለማሳካትና ውጤት በሚሰጥ መልኩ መተርጎም ያለበት በወንጀል ህጉ ተከሳሽ የተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ላይ የተመለከተው የቅጣት መጠን በመመልከት ከ12 ዓመት በላይ የመቀጣት እድል ያለው መሆን አለመሆኑን በመመርመር የሚወሰን እንጂ ተከሳሽ ግለሰብ ሊቀጣ የሚችለውን ልዩ ቅጣት በማስላት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የተከሰሱበት የወ/ሕ/ቁ. 27/1 እና 540 ከ5-20 ዓመት ጽኑ እስራት ያስቀጣል፡፡ ከድንጋጌው የቅጣት መጠን አንጻር አማካኙ ከ12 ዓመት በላይ በመሆኑ ተጠሪ ከ12 ዓመት በላይ ሊቀጡበት የሚችልበት እድል ሰፊ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለቡት ሊታይ የሚችል ነው፤ ይህ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በሌለቡት ሊታይ አይችልም በማለት መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ማስረጃ ተሰምቶ ጉዳዩ እንዲወሰን ወደሥር ፍርድ ቤት ሊመለስ ይገባል በማለት ከአብላጫው ሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ  የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

## ክፍል ስምንት

## 8. የይግባኝ ሥነ ሥርዓት እና የሰበር አቤቱታ

### 8.1 የይግባኝ  ሥነ ሥርዓት[173]

- ከስር ተከሳሾች መካከል ፍ/ቤት የሠጠው ውሣኔ ለአንዱ የሚጠቅም በሆነ ጊዜና ይግባኝ ባዩ ጋር ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ሰዎች ይግባኝ ቢያቀርቡ ኖሮ በይግባኝ ሰሚው ፍቤት ውሣኔ ሊጠቀሙ ይችሉ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ላላቀረቡት ተከሳሾች ጭምር ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑ፡፡[174]

---

[173] የሰ/መ/ቁ - 96378 (ህዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 17

[174] በሰ/መ/ቁ 116405 (መጋቢት 02 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 131088 (ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21፣ በሰ/መ/ቁ 134834 (ሰኔ 29 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 21፣ በሰ/መ/ቁ 200520 (የካቲት 10 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣ በሰ/መ/ቁ 98014 (ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 18፣ በሰ/መ/ቁ 73264 (መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ በሰ/መ/ቁ 101056 (ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 18፣ በሰ/መ/ቁ 57632 (ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 63741

የሰ/መ/ቁ - 96378

ህዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ሀቢብ ጀማል

ተጠሪ፡- የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ -

አቤቱታ አቅራቢዎች፡- 1.ረዳት ሳጅን መሐመድ እንድሪስ ጉዳዩን ተከታታዮች ተስፋዬ

2. አብዱ ኡመር - አለሙ እና ወሰላ ከድር

3. ደግፌ አለሙ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን መዝገቡ የተከፈተው በሀቢብ ጀማል አመልካችነት ሁኖ ከተጠሪ ጋር ክርክሩ ተካሂዶ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዚህ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት ከሀቢብ ጀማል ጋር ተከሳሽ የነበሩትን የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎችንም የሚጠቅም በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196 ድንጋጌ መሰረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል በማለት ህዳር 02 ቀን 2007 ዓ/ም ማመልከቻ ስለአቀረቡ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአቤቱታ አቅራቢዎችን ጥያቄ ለማስተናገድ ይቻለው ዘንድ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2007 ዓ/ም ባቀረበው አስተያየት አቤቱታ አቅራቢዎቹ ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸው መሆኑን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 196 ከአስቀመጠው ድንጋጌ የሚገነዘበው መሆኑን ዘርዝሮ አቤቱታ

---

(ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 63014 (ሚያዚያ 09 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 248728 (ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 236400 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 101003 (ሕዳር 2 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 20፣ በሰ/መ/ቁ 120762 (የካቲት 25 ቀን 2009ዓ.ም) ቅጽ 19፣ በሰ/መ/ቁ 59537 (ሚያዚያ 19 ቀን 2003ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 47755 (ግንቦት 5 ቀን 2003ዓ.ም)ቅጽ12፣ በሰ/መ/ቁ 48617 (ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅጽ 10፣ በሰ/መ/ቁ 95875 (ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16፣ በሰ/መ/ቁ 35611 (ሰኔ 19 ቀን 2000ዓ.ም) ቅጽ 7፣ በሰ/መ/ቁ 39722 (ታህሳስ 23 ቀን 2001ዓ.ም) ቅጽ 9፣ በሰ/መ/ቁ 198600 (ግንቦት 23 ቀን 2013 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 188086 (ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 156999 (ጥቅምት 27 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23፣ በሰ/መ/ቁ 158480 (ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 143820 (ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 138870 (ሚያዚያ 30 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ፣ በሰ/መ/ቁ 138874 (ግንቦት 17 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 208890 (ሕዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅፅ 26፣ የሰ/መ/ቁ 203051 (የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣የሰ/መ/ቁ 74041 (ሰኔ 4 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13፣ የሰ/መ/ቁ 93234 (መስከረም 27 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 118252 (ጥር 24 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 19 ፣የሰ/መ/ቁ 117877 (ሐምሌ 22 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 20፣ የሰ/መ/ቁ 127484 (መስከረም 23 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22

አቅራቢዎች አቶ ሀቢብ ጀማል ጥፋተኛ በተባሉበት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 422(1) ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብለው በስር ፍርድ ቤት የቀረቡባቸው የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሰረት ተደርገው ቅጣት ሊወሰንባቸው እንደሚገባ ገልፆ አስተያየቱን ሰጥቷል።

እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል።

የጉዳዩ መነሻ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት የስልጤ ዞን ዐ/ሕግ ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የጥፋተኝነት እና ተገቢውን የቅጣት ውሳኔ በሰጣቸው አቶ ሃቢብ ጀማልና በአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይ አራቱም ተከሳሾች በወ/ህ/ቁ 32/1//ሀ/፣ 37፣ 27/1/ እና 671/1/ሀ/ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የማይገባቸውን ብልፅግና ለማግኘትና ለሌላውም ለማስገኘት በማሰብ በስልጤ ወረዳ ውስጥ አሻኖ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ከወራቤ ወደ ቡታጅራ በሚወስደው አስፋልት መንገድ ላይ ሚያዚያ 08 ቀን 2005 ዓ/ም ከምሽቱ 5:00 ሰኣት እስከ 7:30 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ የውንብድና ወንጀል ተግባር ለመፈፀም አስቀድመው በማሰብ በቡድን /ህብረት/ ሁነውና ተደራጅተው የጦር መሳሪያና ለዚሁ ተግባር የሚያግዛቸውን ተሽከርካሪ ጭምር በማዘጋጀት በመንገዱ ላይ ከአዲስ አበባ ወደ ወራቤ ምርጥ ዘር እና ሰዎችን ጭኖ ይጓዝ የነበረውንና በአቶ አብዱረዛቅ ዑመር አማካኝነት የሚሽከረከረውን ኤፍ.ኤስ.አር መኪና በማስቆም ከባድ የሆነ የውንብድና ወንጀል ለመፈፀም ሞክረዋል የሚል ሁኖ እያንዳንዱ ግብረ አበር በወቅቱ ፈፀመ የተባለውን ድርጊትም ክሱ ይዘረዝራል።

የአሁን አቤቱታ አቅራቢዎች በተከሳሽነታቸው ቀርበው ድርጊቱን አልፈፀምነም፤ ጥፋተኛም አይደለንም በማለት ክደው ተከራክረዋል። በአቃቤ ሕግ በኩል በማስረጃነት የሰው ማስረጃና የሰነድ ማስረጃዎች ቀርበዋል። ከዚህም በኋላ ሁሉም ተከሳሾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል። ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተካሳሾቹ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው በአቃቤ ሕግ ተነግሮባቸው በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አላስተባበሉም በሚል ምክንያት በአቃቤ ሕግ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎአል። ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመርመሩን በማጣቀስ አቶ ሀቢብ ጀማልንና የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢ ከሆኑት 1ኛውን (የሥር 1ኛ ተከሳሽ) እና 2ኛውን (የሥር 2ኛ ተከሳሽን) እያንዳንዳቸውን በሰባት ዓመት፣ የስር 3ኛ ተከሳሽን (የአሁኑን ሶስተኛ አቤቱታ አቅራቢን) ደግሞ በስድስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል። በዚህ ውሳኔ አቶ ሀቢብ ጀማል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም። የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ግን በዚህ አግባብ የይግባኝና የሠበር አቤቱታቸውን ስለማቅረባቸው የክርክሩ ሂደት አያሳይም።

ሆኖም ከአቤቱታ አቅራቢዎች ጋር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ4ኛ ተከሳሽነት ተሰይሞ የነበረውና በበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት አቶ ሃቢብ ጀማል በሕጉ አግባብ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ለዚህ ችሎት የሠበር አቤቱታ አቅርቦ ጉዳዩ ተጠሪ ባለበት ከተጣራ በኋላ ተጠሪ አድራጎቱ የሚሸፈንበትን የሕግ ድንጋጌ በመለየትና የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጡበት ድንጋጌ ለስር ተከሳሾች አድራጎት አግባብነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ በሰጠው መልስ መነሻ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ተከሳሾች አድራጎት የሚያቋቁመው በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 32(1(ለ)፣ 33 እና 422(1) ድንጋጌ መሆኑን ገልፆ አቶ ሀቢብ ጀማልን በዚሁ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ የቅጣት ውሳኔውንም በዚሁ ድንጋጌ አግባብ ወስኗል። ይህ ውሳኔ በሕግ አተገባበርና አተረጓጎም ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የፈጸሙበትን ስህተት ከማረሙም በላይ በውጤቱ ደግሞ አቶ ሀቢብ ጀማልን የጠቀመ መሆኑ ግልጽ ነው። ከስር ተከሳሾች መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ለይግባኝ ባዩ የሚጠቅም በሆነ ጊዜና ከይግባኝ ባዩ ጋር ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ሰዎች ይግባኝ ቢያቀርቡ ኑሮ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊጠቀሙ ይችሉ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት

የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ላላቀረቡት ተከሳሾች ጭምር ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደሚገባ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196(1(ሀ) እና(ለ) ድንጋጌዎች ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ ለዚህ ችሎት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትም ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም ችሎቱ የሚመራበት የተለየ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ የለምና፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ከአቶ ሀቢብ ጀማል ጋር ለዚህ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡ ኑሮ የፍርዱ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አቶ ሀቢብ ጀማልን በተመለከተ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 196(1))(ሀ) (ለ) መሰረት ለአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይም ተፈጻሚነት አለው ብለናል፡፡

ቅጣቱን በተመለከተ ግን አቶ ሀቢብ ጀማል ላይ የተሠጠው እንዳለ ተግባራዊ ይሁን የሚል ግልፅ ድንጋጌ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196 ድንጋጌ ስር አለ ለማለት ስለማይቻልና በመርህ ደረጃም እያንዳንዱ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው በተሳትፎውና ግላዊ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕጉ አንቀጽ 40 ድንጋጌ እና ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን መርሆዎች የምንገነዘበው በመሆኑ የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠንን መመልከቱ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ከአሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ውስጥ 1ኛው ረዳት ሳጅን መሀመድ እንድሪስ፣ እና 2ኛው አብዲ አሙር ከሀቢብ ጀማል ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ የተቀጡ በመሆኑ በአቶ ሀቢብ ጀማል ላይ በዚህ ችሎት የተጣለው ቅጣት ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በጥያቄ አቅራቢዎች ላይ በቅጣት ማክበጃነት በስር ፍርድ ቤት የተያዙት ምክንያቶች እንዲያዙ የጠየቀ ቢሆንም ይህ ችሎት በአቶ ሀቢብ ጀማል ላይ የቅጣት ውሳኔ ሲሰጥ በከፊል ውድቅ ያደረጋቸው በመሆኑ በአሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ላይም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የሚያገኙበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘም፡፡

3ኛውን ጥያቄ አቅራቢ አቶ ደግፌ አለሙን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተያዙለት የቅጣት ማቅላያ ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ ይሄውም ሪኮርድ የሌለበት መሆኑና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ናቸው፡፡ ይህንኑ ይዘን የቅጣት እርከኑን ስንመለከተው በአንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ከእርከን 11 ወደ እርከን 12 ከፍ የሚል ሲሆን ጥያቄ አቅራቢው አቶ ደግፌ አለሙ ሁለት የቅጣት ማቅላያ ምክንያት ስላላቸው በመመሪያው አንቀፅ 13(5) መሰረት በጥያቄ አቅራቢው ላይ ሊጣል ይችል የነበረው ቅጣት በአራት እርከን እንዲወርድ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረትም ከእርከን 12 ወደ እርከን 8 የሚወርድ ሁኖ በዚሁ መጨረሻ እርከን ስር የተመለከተው የቅጣት አይነትና የመጠን ሬንጅ ከአንድ አመት ከሁለት ወር እስከ አንድ አመት ከስድስት ወርበመሆኑ ለፍ/ቤቱ በተሰጠው ፍቅድ ስልጣን መሰረት አቶ ደግፌ አለሙ ለፈፀሙት ጥፋት ተመጣጣኝ፣ ለመሰል አጥፊዎችን ደግሞ አስተማሪ ነው ብለን ያገኘነው አንድ አመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ነው፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች በጥያቄ ባሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09466 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ/ም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196/1/ /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት ተሻሽሎ ጥያቄ አቅራቢ በሆኑት፡-

ሀ/ ረዳት ሳጅን መሐመድ እንድሪስ

ለ/ አብዱ ኡመር

ሐ/ ደግፌ አለሙ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በአቶ ሀቢብ ጀማል በሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተፈፃሚነት አለው ብለናል፡፡ ስለሆነም ጥያቄ አቅራቢዎቹ ሊጠየቁ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33፣ 32(1(ለ) እና 422(1) ድንጋጌ ስር ነው ብለናል፡፡

2. ቅጣቱን በተመለከተም ረዳት ሳጅን መሐመድ እና እንድሪስ አብዱ ኡመር እያንዳንዳቸው በጉዳዩ የታሰሩት ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ ሊቀጡ የሚገባው በአንድ አመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት ነው በማለት ወስነናል፡፡ ደግፌ አለሙን በተመለከተ ደግሞ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሁኖ በአንድ አመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ነው ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለወራቤ ማረሚያ ተቋም ይገለጽለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## 8.2 የሰበር አቤቱታ[175]

- የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196(1) ለሰበር ሥርዓትም ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑ፤[176]

የሰ/መ/ቁ - 101056

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጠታ

አመልካች፡- አቶ አይሸሽም ገብሬ - ጉዳዩ ተከታታይ ቤተሰብ ቀረበች

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ - ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

1. ጉዳዩ የቀረበው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 በዋና ወንጀል ሠሪነትና በግብረአበርነት አንድ የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው በፍርድ ተረጋግጦ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየው ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት /ይግባኝ ሰሚ ችሎት/ተመሣሣይ ፍርድና የቅጣት ውሣኔ የተሰጠባቸው ሰዎች በተለያየ መዝገብ የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበው•የአንደኛው የሰበር አቤቱታ አቅራቢ የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቅጽ 22 መሠረት ቢዘጋና የሌላኛው የሰበር አቤቱታ አቅራቢ የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ወይም ፍርድ ቤት የስጡት የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሣኔ ቢሻሻልና የሰበር ችሎት በማሻሻል የሰጠው ፍርድ ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚያስቀርብ ነጥብ የለውም ተብሎ የተዘጋበትን አቤቱታ አቅራቢ የሚጠቅመው ሆኖ ቢገኝ• የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም?የሚለውን አከራካሪ የህግ ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

---

[175]በሰ/መ/ቁ 101056 (ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 18

[176]የሰ/መ/ቁ 149962 (መጋቢት 25 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22

2. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች አንደኛ ተከሳሽ በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የነበረው አክሊለብርሃን አባቡ ሁለተኛ ተከሳሽ ሆነው በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)ሀ እና አንቀጽ 408 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንዛፍ ጽ/ቤት ኦዲተሮች ሆነው ሲሰሩ ኦዲት እንዲያደርጉ ከተመደቡበት አትራክን/ጄኔራል ኢትዮጵያ ሰርቪስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቆዳና ሌጦ ፋብሪካ ግብይት አቅራቢ ድርጅት ሂሳቡ አምስት ሚሊዮን ብር ብር /5000,000/ጉድለት ያሳያል በማለት ከድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ጋር በአካልና በስልክ በመደራደር ብር 600,000 /ስድስት መቶ ሺህ እንዲከፍላቸው በመስማማት ሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ አስራ ሁለት ሠዓት ከድርጅቱሥራ አስኪያጅ ጋር ቀጠሮ በያዙበት ቦታ ተገኝተውና ከድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ መኪና ውስጥ ገብተው በተደራደሩበት ገንዘብ ውስጥ ብር 100,000/አንድ መቶ ሺህ/ አንደኛ ተከሳሽ የአሁኑት አመልካች በጥቁር ፌስታል እንደተጠቀለለ ተቀብሎ ሲወርድ ሁለተኛ ተከሳሽ /በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013/አመልካች የነበረው አክሊለብርሃን አባቡ መኪናው ውስጥ ተቀምጦ ቀሪውን ገንዘብ ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ እያለ የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በመደባቸው የክትትል አባሎች እጅ ከፍንጅ መያዛቸውን በማረጋገጥ• የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የተከሰሱበትን የህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ከባድ የጉቦ መቀበል የሙስና ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት በመዝገብ ቁጥር 123410 የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

3. የቅጣት ውሣኔውን በተመለከተ• ወንጀሉ በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ነው በማለትና የቅጣት ደረጃው ከሰባት ዓመት እስከ ዘጠኝ ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት መሆኑን ገልፆ በሁለቱም ላይ የመነሻ ቅጣቱ ስምንት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 4000/አራት ሺህ ብር/ መቀጮ እንደሆነ ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች አራት ታናናሽ እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑን በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝለት ያቀረበውን ጥያቄ አስተዳድራቸዋለው ያልከው ልጆችህን ወይም ሚስትህን አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ ካደረገ በኃላ አመልካች የወንጀል ሪከርድ የሌለበት መሆኑንና እና ፀባያቸው መልካም የነበረ መሆኑን አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትን በመቀበል በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን በመቀነስ ከእርከን ሃያ ስድስት ወደ እርከን ሃያ አምስት ዝቅ በማድረግ ተከሳሾች በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 3000/ሶስት ሺህ ብር/መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት የቅጣት ውሣኔ በመቃወም የአሁኑ አመልካች የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 96631 ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ•ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉዳዩ የሚያስገባ ምክንያት የለም በማለት የካቲት 20 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ/ትዕዛዝ/ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 አቤቱታ ያቀረበው የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ በበኩሉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመቃወም በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 96526 ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉዳዩ የሚያስገባ ምክንያት የለም በማለት የካቲት 25 2006 ዓ.ም በሠጠው ውሳኔ/ ትእዛዝ ይግባኙን ስርዞታል፡፡

5. የአሁን አመልካች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም ግንቦት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ አቅርቦ፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታውንና መዝገቡን ከመረመረመ በኃላ በቀረበው ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተሰርቷል ማለት አልተቻለም በመሆኑም መዝገቡ ለሰበር አያስቀርብም ብለናል በሚል ትዕዛዝ ቅጥምት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶበት ተዘግቷል፡፡

6. ከአመልካች ጋር በወንጀል ተካፋይነት የተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው እንደዚሁም ይግባኙ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 95526 ይግባኝ ሰሚው ችሎት የካቲት 25 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ

/ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት አክሊለብርሃን አባቡ በሰበር መዝገብ 101013 ግንቦት 11 ቀን 2006 ዓ.ም ፅፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በመመርመር የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የጥፋተኝነት ቅጣቱን የወሰንኩት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ለሰበር ችሎት በመቅረቡ፣ ይኸ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሣኔ አፅንቶ የቅጣት ውሣኔውን በማሻሻል መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

7. በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም የቅጣት ውሣኔውን ሲያሻሽል የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሁለት መሠረታዊ የህግ ስህተቶች ሠርተዋል፡፡ የመጀመሪያ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት በተለይም እናት አባት ወንድም እህት ማስተዳደርና መርዳት /ልጅና ሚስት/ካልሆነ በስተቀር በወንጀል ህግ አንቀጽ 86 የሚሸፍን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሊሆን አይችልም በማለት የሰጡት የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት መሆኑን በመተንተን• ተከሳሹ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ወንድሞቹን እህቶቹን እናትና አባቱን እየረዳና እያስተዳደረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከቀረበ በወንጀል ህግ አንቀጽ 86 ሥር የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ምክንያት እንደሚሆን ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ቅጣቱ መሠላት ያለበት መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት በመተንተን• በመዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የነበረው ሰው• እናቱን አባቱን ወንድምና እህቶቹን የሚረዳ መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት እንዲያዝለትና•በሁለቱ የቅጣት ምክንያቶች በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንሁስ አንቀፅ 7 መሠረት ሶስት እርከን በአጠቃላይ ስድስት እርከን ሲቀንስ ከእርከን ሃያ ስድስት ወደ እርከን አስራ ዘጠኝ ዝቅ የሚል በመሆኑ አመልካች አክለስብርሃን አባቡ በእርከን አስራ ዘጠኝ ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ውስጥ በአራት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 3000/ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101013 መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል ፡፡

8. ከዚህ በኋላ አመልካች በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 የቅጣት ውሳኔ ከተሻሻለበት አክሊብርሃን አባቡ ጋር ተመሣሣይ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያቀረቡ መሆኑን ገልያ እህቶችህን የማስተዳድር መሆኑ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አይሆንም በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚችሎት የሰጡት የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት መሆኑ በሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑና በጉዳዩም ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሆኑ በሰበር ችሎት የተወሰነ ሆኖ እያለ• የእኔ የሰበር አቤቱታ የሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚቀርብ ነጥብ የለውም በሎ ስለዘጋው ብቻ የእኩልነትና ፍትህ የማግኘት መብቴ ተገድቦ ሊቀር ስለማይገባው• የሰበር ችሎት መዝገብ ቁጥር 101013 የሰጠው ፍርድ የሚጠቅመኝ በመሆኑ በፍርድ ተጠቃሚ ሊሆንና የቅጣት ውሣኔው ሊሻሻልልኝ ይገባል በማለት አቤቱታውንና ክርክሩን አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በራሱ መንገድ ይግባኝና የሰበር አቤቱታ አቅርቦ እድሉን አሚጥጦ የጨረሰና የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በሰበር ማጣሪያ ችሎት ያፀናበት በመሆኑ• ይኸ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101013 በሰጠው ውሣኔ የሚጠቀምበት የህግ ሥርዓት የለም፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 የሰበር አቤቱታ ላላቀረቡ ተከሳሾች እንጅ በአመልካች ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

9. መዝገቡ በዚህ ሰበር ችሎት የቀረበበት መሠረታዊና አከራካሪ የህግ ጭብጥ አመልካች በዚህ መዝገብ• ከአመልካች ጋር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከሳሽ የነበረው ሰው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ያለፈበት ሂደትና የተሰጠ ትዕዛዝና ውሣኔ ይዘት ከላይ የተገለፀው፣ ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 196 ንዑስ አንቀፅ 1 በአመልካች ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ወይም የለውም? የሚለውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 የተሰጠው ፍርድ አመልካችን የሚጠቅመው ነው ወይስ

አይደለም? የአመልካች ጉዳይ ለሰበር ችሎት ቢቀርብ ኖሮ በአመልካች ላይ የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ ሊሻሻልለት ይችል ነበር ወይስ አልነበረም? የሚሉትን ነጥቦች መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. አመልካችና በመዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የሆነው ሰው በወንጀል ህግ አንቀፅ 32/1/ሀ እና አንቀፅ 408 ንዑስ አንቀፅ 1 በመተላለፍ፣ በዋና ወንጀል ሠሪነት አንድ ላይ ከአንድ ሰው ከባድ ጉቦ የመቀበል ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ መሆናቸው እስከሰበር ችሎት ድረስ በተሰጠው ፍርድ ተረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለቱም ተከሳሾች ከዚህ በፊት ወንጀል ፈፅመው የማያውቁና የዘወትር ባህሪያቸው መልካም የነበረ መሆኑን አንድ የቅጣት ማቅለያ አድርጎ የያዘላቸው ሲሆን ይህንኑ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተቀብሎታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለቱም ተከሳሾች በወንጀል በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በሁለቱም ተከሳሾች ለአንድ የቅጣት ማቅለያ አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ በእርከን ሃያ አምስት የተመለከተው ሁለቱም ስድስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 3000/ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ተከሳሾቹ በተናጠል ያስከፈቱትን የይግባኝ መዝገብ መርምሮ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

11. ይህም የሚያሳየው ከአመልካች ጋር በዋና ወንጀል ተካፋይነት ጥፋተኛ የተባለው በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው ሰው ለሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በአራት ዓመት ፅኑ እስራትና በሶስት ሺ ብር/3000 ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ የተወሰነው፣ ከአመልካች ያነሰ የወንጀል ተሣትፎ ስለነበረው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር አጣሪ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የወሰነውን የቅጣት ውሣኔ ያፀኑት በወንጀል ህግ አንቀፅ 41 በሚደነግገው መሠረት ቅጣቱን በአመልካች ላይ ለይቶ ለመወሰንና ለማፅናት የሚያስችሉ የግል ምክንያቶች ያሉ መሆናቸውን በማረጋገጥና ይህንንም በሰጡት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ በግልፅ በማስፈር እንዳልሆነ ተረድተናል፡፡

12. በአንፃሩ የአሁን አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ጉዳዩ ታይቶ የቅጣት ውሳኔው ከተሻሻለለትና በወንጀል ተካፋይነት አብሮት ጥፋተኛ ከተባለው ሰው፣ የተለየ ቅጣት እንዲፀናበት የተደረገው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 41 ወይም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 88 በተደነገጉና በግልፅ ተለይተው በሚታወቁ ምክንያቶች ሣይሆን፣ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ልጅና ሚስት ካልሆነ በስተቀር ወንድምና እህት እናትና አባት መርዳትና ማስተዳደር በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አይሆንም በማለት በሰጡት የተሣሣተ ትርጉምና ይኸ ሰበር ችሎት 101013 እህትና ወንድም አባትና እናት መርዳትና ማስተዳደር በወንጀል ህግ አንቀፅ 86 የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ይሆናል በማለት በሰጠውና አመልካችን ተጠቃሚ በሚያደርገው ትርጉም ውሳኔ፣' ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ባለመቅረቡ ተጠቃሚ ሣይሆን በመቅረቱና አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት ሣይያዝለት በመቅረቱ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 ግንቦት 7 ቀን 2006 በቅጣት አወሳሰን ሂደት የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር፣ ቅጣት ለመወሰን፣ ተፈፃሚነት ያለው የወንጀል ድርጊት ሲፈፀም ስራ ላይ የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው በማለት የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 22 እና የወንጀል ህግን አንቀፅ 5 መሰረት በማድረግና ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 ግንቦት 7 ቀን 2006 የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም የስር ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባለመከተላቸውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመፈፀማቸው ምክንያት ነው፡፡

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ተይዞለት፣ ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች ያሉት መሆኑንና በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 7 መሰረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሶስት እርከን በድምሩ ስድስት እርከን ሲቀነስ በእርከን አስራ ዘጠኝ ከተገለፁት የቅጣት ሬንጅ ውስጥ የሚወድቅ መሆንና በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በተሰጠው ፍርድ የሚጠቀም መሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አላገኘነውም፡፡

14. አመልካች በወንጀል ተካፋይነት አብሮት በተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው ሰው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ፍርድ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ከተረጋገጠ አመልካች በተናጠል በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ታይቶ ጥቅምት 7 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ውድቅ መደረጉ አመልካች የሰበር አቤቱታ ባያቀርብ ኖሮ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሊያገኝ የነበረውን ጥቅምና መብት የሚያስቀርበት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ፣ ጉዳዩ የወንጀል ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር በፌዴራል ደረጃ ከተዘረጋው የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማና ግብ መሠረት በማድረግ መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

16. ሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) የተዘረጋው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በሰበር አይቶ በማረም በአገር ውስጥ ሕጎች ወጥ በሆነ መንገድ እንዲተረጎምና ተፈፃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የህግ የበላይነትንና ፍትህን ማስፈን ነው፡፡ የሰበር ሥርዓት ከይግባኝ እና ሌሎች የፍርድ ላይ የሚፈፀሙ ስህተቶች ማረሚያ መንገዶች የተለያየና የራሱ የሆነ ባህሪ ያለው በመሆኑ ይህንኑ ባህሪውን ያገናዘበና ዓላማውን ለማሣካት የሚያስችል የሥነ ሥርዓት ሌሎች አሠራሮች ያስፈልጉታል፡፡

17. በአገራችን የሰበር ሥርዓቱ የሚመራበት ሰበር የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ የሥነ ሥርዓቱ ህግ የለም፡፡ የሰበር ችሎት እየሠራ የሚገኘው ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ በሚታዩበት ወቅት እንዲያገለግሉ ታስበው ከግማሽ ምዕተዓመት በፊት የወጡና ሌሎች የሥነ ሥርዓት ሕግ ማዕቀፎችን ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በሥራ ላይ ያሉትንና የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ባህሪና አላማ ግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ ህግ አውጭው የወደዳቸውን የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከሰበር ሥርዓቱ መሠረታዊ ባህሪ ጋር በማጣጣምና የሰበርን መሠረታዊ ዓላማ ለመስማት በሚያስችል መንገድ በመተርጎም በማጣጣም ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

18. ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ክርክር ያስነሳው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ 196 ንዑስ አንቀፅ 1 ህግ አውጭው የደነገገውና በሥራ ላይ እንዲውል ያደረገው በአገራችን የሰበር ሥርዓት ባልዘረጋበት ጊዜና የይግባኝ ሥርዓቱ በፍርድ የሚፈጸም የፍሬ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን መሠረታዊ የህግ ስህተት ማረሚያ ዋና ሥርዓት ተደርጎ በተዘረጋበት ወቅት መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት የታወጀበትን ጥቅምት 23 ቀን 1954 ዓ.ም መመልከቱ ብቻ በቂ ነው፡፡በዚያን የታወጀው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት አንቀጽ 196 “የተፈረደባቸው ስዎች ሆነው አንድ ብቻ ይግባኝ ሲያቀርብ” የሚል እርዕስ ያለው ሲሆን የደነገገው ንዑስ አንቀጽ 1 ቃል በቃል ሲነበብ “ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበው ይግባኝ ስለተፈረደባቸው ብዙ ሰዎች የሚመለከት ሆኖ ይግባኝ ያለው ግን የተፈረደበት አንድ ሰው ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በታች የተመለከተው ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚሰጠው ፍርድ ይግባኝ ላሉትም ሰዎች ይግባኝ እንዳለ ተቆጥሮ ይፈጸምላቸዋል ለማለት የሚችለው /ሀ/ በይግባኝ የተሰጠው ፍርድ ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም በሆነ ጊዜና /ለ/ ተከሳሾች ይግባኝ ቢሉ ኖሮ በፍርድ እነርሱም ሊጠቀሙ ይችሉ ነበር የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ ነው” የሚል ይሁንታ ያለው ነው፡፡

19. ይህንን ድንጋጌ አሁን ላለው የሰበር ስርዓት ለመጠቀም ካለው የሰበር ችሎት አደራጃጀትና አሰራር ጋር በሚጣጣምና የሰበርን መሰረታዊ ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መንገድ መተርጎምና ስራ ላይ ማዋል ይጠይቃል፡፡ የመጀመሪያው ብዙ ተከሳሾች አንድ ወንጀል የወንጀል ስራው ተካፋይና ግብረ አበር ሆነዋል ተብለው ክስ ቀርቦባቸውና፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ባየው ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ባዩው ፍርድ ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አንደኛው ተከሳሽ የሰበር አቤቱታ አቅርቦ፣ አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ በሰበር ችሎት ታይቶ፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ አይቶ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሳኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔው መሰረታዊ

ህግ ስህተት አለበት ተብሎ ከተሻረ፣ ከተሻሻለ ወይም ከተለወጠና የሰበር ችሎት በመሻር፣ በማሻሻል ወይም በመለወጥ የሰጠው ውሳኔ የሰበር አቤቱታ ያላቀረቡትን ሌሎቹ በአንድ ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎችን የሚጠቅም ሆኖ በተገኘ ጊዜ፣ ሰዎቹ ፍርድን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ባያቀርቡም ሰበር ችሎት በሰጠው ውሳኔ ወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተጠቃሚ እንደሆነ በሚያደርግ አግባብ ድንጋጌው መተርጎምና ስራ ላይ መዋል አለበት የሚለው፡፡

20. ሁለተኛው በአንድ ወንጀል አድራጎት በወንጀል ህግ ስለወንጀል ተካፋይነት አድራጊነት ወይም ስለግብረአበርነት በተደነገጉት መሰረት በአንድ ላይ ፈጽመዋል ተብለው ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየውና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተወሰነባቸው ሰዎች ብዙ ሰዎች ሁሉም በግላቸው የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር መዝገብ አስከፍተው ከፊሎቹ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታና የስከፈቱት የሰበር መዝገብ በሰበር ችሎት የሚቀርብ መሠረታዊ የህግ ስህተት ጭብጥ የለውም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 22 መሠረት በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ ቢደረግና ቢዘጋ የከፊሎቹ ወይም አንደኛው ተከሳሽ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር የሚጣራ መሠረታዊ የህግ ጭብጥ አለው ተብሎ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሰበር ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የጥፋተኝነት ውሣኔውን ወይም የቅጣት ውሳኔውን ወይም የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔውን መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር ችሎት ከሻረው ካሻሸለው ወይም ከለወጠውና ውሳኔው የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር ማጣሪያ ችሎት የሚጣራ መሠረታዊ የህግ ስህተት ጭብጥ የለውም ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ያደረገባቸውን ሰዎች የሚጠቅም ሆኖ በተገኘ ጊዜ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል የሚለው ነው፡፡

21. ለዚህም ምክንያቱ ለይግባኝ ሥርዓት ታስቦ የተደነገገው የወንጀለኛ መቅጫ ሥርዓት ህግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 አሁን ያለውንና በአዋጅ ቁጥር 25/88 የተደነገገውንና የተዘጋውን የሰበር ችሎት አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መንገድ ሥራ ላይ ካልዋለና• አሁን በመዝገቡ ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚ የማይሆን ከሆነ አንድ የወንጀል ድርጊት በአንድ ላይ ፈፅማችኃል ተብለው ተከሰው ቢኖር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከተመሣሣይ የወንጀል ህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ ተብለውና በወንጀሉ የነበራቸው ተሣትፎ እና ሌሎች ግላዊ ሁኔታዎች ተመሣሣይ ሆኖ በመገኘቱ ተመሣሣይ የሆነ የቅጣት ውሣኔ የተላላፈባቸው ሰዎች፣ የአንደኛው የሰበር አቤቱታ የሚጣራ የህግ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት ሰለቀረበና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑ ተገልጾ በሚሰጠው ፍርድ ተጠቃሚ የሚሆንበት የሌላኛው የሰበር አቤቱታ የሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚቀርብ የለውም ተብሎ ውድቅ ስለተደረገበት ብቻ የፍርዱ ተጠቃሚ የማይሆንበትን አግባብ መከተል በህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 4 የተደነገገውን የእኩልነት መርህ የሚጥስና የሰበርን መሠረታዊ ዓላማ የማያሳካ ይሆናል፡፡

22. ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ወንጀል በጋራ ፈፅማችኂል ተብለው የተከሰሱና ጥፋተኛ ተብለው ከተቀጡ ሰዎች መካከል፣ ሌሎቹ ሰዎች መብታቸውን ለሰበር #ነት ለማቅረብ ዳኛ ሆነው አንደኛው ተከሳሽ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሰበር ችሎት በሰጠው ፍርድ ሌሎቹ ተከሳሾች በሚጠቅሙበት አግባብ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 ጥቅም ላይ የሚውሉና የሚፈፀም ከሆነ፤ በአንድ የወንጀል ድርጊት የተከሰሱ ሁሉም ሰዎች መብታቸውን ለሰበር ለማቅረብ ተገቢውን ትጋት አሳይተው ለሰበር ችሎት በማቅረባቸውና የከፊሎቹ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመደረጉና የከፊሎቹ ለሰበር የሚቀርብ ነጥብ የለም ተብሎ በመዘጋቱ የሰበር ችሎት የሰጠው ፍርድ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ የተደረገባቸውን ሰዎች የሚጠቅም ሆኖ እያለ በፍርዱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረግ፣ በአጠቃላይ የሰበር ሥርዓቱን መሠረታዊ አላማና ሕግ አውጭው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 196 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ሊያወጣ የፈለገውን ግብ፣ አሁን ካለው የሰበር አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መንገድ ሥራ ላይ እንዳይውል የሚደረግና ሰዎች ተግተው

የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ምክንያት ብቻ የድንጋጌው ቱርፋት እንዳይደርሳቸው የሚያደርግ በመሆኑ፣ ይህንኑ ድንጋጌ ይህንኑ ሁኔታ በሚሰጥበት አግባብ መተርጐም ሥራ ላይ መዋል ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

23. አመልካች የሰበር አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ ባይደረግ ኖሮ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በሰጠው ፍርድ እና ከአመልካቹ ጋር ዋና ወንጀል አድራጊ ሆኖ በተከሰሰው ሰው፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪነቱ በልዩ ቅጣት ማቅለያነት እንዳይዝለት ይኸ ሰበር ችሎት በሰጠው የህግ ትርጉም ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2001 አንቀጽ 17 ፀዑስአንቀጽ 1መሠረት ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ሶስት እርከን መቀነስ እንዳለበት ይጭ ሰበር ችሎት መሠረታዊ ዓላማ፣ ለማሳካት ፣ በህገ መንግስቱአንቀጽ 80 ፀጉስ አንቀጽ 3ን/ሀ/የተደነገገውን የሰበር ችሎት መሠረታዊ ዓላማ፣ ለማሳካት፣ በህገመንግስቱ አንቀጽ 25 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 4 የተደነገገውን የእኩልነት መርህ ተግባራዊ ለድረግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 196ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ከስር አደረጃጀትና አሠራር ጋር በማጣጣም መተርጐምናአመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በተሰጠው ፍርድ ተጠቃሚ ማድረግ አስፈላጊ ነው በማለት ወስነናል፡፡

24. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 86 ልዩ የቅጣት ማቅለያ ሆኖ ሲያዝለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከያዙለት አንድ የቅጣት ማቅለያ ጋር ተደምሮ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ይኖረዋል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወሰኑት የቅጣት መነሻ ከሚገኝበት እርከን ሃያ ስድስት እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 7 መሠረት ሶስት እርከን ሲቀነስ በአመልካች ላይ የሚወሰነው ቅጣት እርከን አስራዘጠኝ ላይ የሚወድቅ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በእርከን አስራዘጠኝ ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ፈቃደ ስልጣናችንን ተጠቅመን አመልካች በቀሩት ዓመት ፅኑ እስራት እና ብር 3000 /ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ ይቀጣል በማለት ወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአመልካች ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሣኔ አሻሽለን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 123410 የሰጠው የቅጣት ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 93631 የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/196 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ተሻሽሎአል፡፡

2.የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ማጣሪያ ችሎት ጥቅምት 10 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በዚህ ፍርድ ተለውጧል፡፡

3.አመልካች በዚህ ጉዳይ ተጠርጥሮ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ አራት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 3000 /ሶስት ሺ ብር/ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ወስነናል፡፡

4.የቅጣት ውሣኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ሊክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

5.መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

## I.የሰበር ውሳኔዎች ማጣቀሻዎች

## ምዕራፍ አራት

### ክፍል -1

በሰ/መ/ቁ 152038 (ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅጽ 23፣ በሰ/መ/ቁ 240930 (ሐምሌ 25 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 242866 (ሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 126017 (ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 21፣ በሰ/መ/ቁ 58822 (መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 11፣ የሰ/መ/ቁ 62504 (ታህሳስ 06 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ በሰ/መ/ቁ 176890 (ግንቦት 25 ቀን 2012 ዓ.ም)፣በሰ/መ/ቁ 211525 (መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅጽ 25

### ክፍል-2

በሰ/መ/ቁ 199786 (ሰኔ 19 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ ሰ/መ/ቁ 275196 (የካታት 27 ቀን 2017 ዓ.ም) በሰ/መ/ቁ 35695 (ህዳር 11 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 09 ፣ በሰ/መ/ቁ 63344 (ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12 ፣ በሰ/መ/ቁ 263872 (ሐምሌ 30 ቀን 2016 ዓ.ም) ፣፣ በሰ/መ/ቁ 34077 (መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 247563 (ሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣የሰ/መ/ቁ.134228 ( የካቲት 08 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20፣ በሰ/መ/ቁ 35611 (ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅጽ 07 ፣ በሰ/መ/ቁ 67874 (ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 13 ፣ በሰ/መ/ቁ 59304 (ህዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ ሰ/መ/ቁ 68407 (ሐምሌ 14 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣

በሰ/መ/ቁ 244554 (ጥቅምት 6 ቀን 2016 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 262650 (ሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 262313 (ሐምሌ 30 ቀን 2016 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 112725 (ጥቅምት 22 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19 ፣ በሰ/መ/ቁ 182266 (ጥቅምት 19 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24 ፣በሰ/መ/ቁ 119391 (ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 134228 (የካቲት 08 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 132055 (ጥቅምት 08 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 23 ፣ በሰ/መ/ቁ 182050 (ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅፅ 24 ፣ በሰ/መ/ቁ 271048 (ህዳር 23 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 273594 (ታህሳስ 21 ቀን 2017 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 131863 (ህዳር 08 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 31734 (ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 218737 (የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 225533 (ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 233903 (ጥቅምት 08 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 218080 (የካቲት 22 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 269430 (ጥቅምት 29 ቀን 2017ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 172185 (ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 198881 (የካቲት 2 ቀን 2013 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 273144 (ታህሳስ 21 ቀን 2017 ዓ.ም) ፣ ሰ/መ/ቁ 253740 (ሕዳር 27 ቀን 2016ዓ.ም)፣ ሰ/መ/ቁ 275196 (የካታት 27-2017 ዓ.ም) ፣በሰ/መ/ቁ 182050 (ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24፣የሰ/መ/ቁ 57938 (ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ 252231 (ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 73569 (ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ በሰ/መ/ቁ 59855 (ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12 ፣በሰ/መ/ቁ 110969 (ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣የሰ/መ/ቁ 44594 (ሐምሌ 15 ቀን 2001ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ ሰ/መ/ቁ 113436 (ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 61275 (ሚያዚያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ 146727 (ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22፣የሰ.መ.ቁ 222914 (ግንቦት 16 ቀን 2014 ዓ.ም) ፣በሰ/መ/ቁ 237767 (ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም)

### ክፍል-3

በሰ/መ/ቁ 57644 (ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ የሰ/መ/ቁ 91535 (የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅጽ 15፣ የሰ/መ/ቁ 72304 (ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ የሰ/መ/ቁ 94070 (ሚያዚያ 22 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅጽ 16፣[1] በሰ/መ/ቁ 165440 (ጥር 27 ቀን 20112 ዓ.ም) ቅጽ 24፣ በሰ/መ/ቁ 175121 (ታህሳስ 23 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24፣ በሰ/መ/ቁ 155789 (ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም)

ቅጽ 23፣ በሰ/መ/ቁ 116405 (መጋቢት 02 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅጽ 20፣ በሰ/መ/ቁ 103452 (ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 17፤ በሰ/መ/ቁ 141677 (ሕደር 29 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅጽ 22፣በሰ/መ/ቁ 189472 (ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅጽ 25፣በሰ/መ/ቁ 73514 (ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ.ም) ቅጽ 14፣በሰ/መ/ቁ 237473 (መጋቢት 25 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ ሰ/መ/ቁ 243034 (ጥቅምት 6 ቀን 2016ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 243034 (ጥቅምት 6 ቀን 2016ዓ/ም)፣የሰ/መ/ቁ 237315 (መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ/ም)፣ የሰ/መ/ቁ 232549 (ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም)፣በሰ/መ/ቁ 243119 (ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም)፣በሰ/መ/ቁ 155789 (ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 137262 (መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ/መ/ቁ 93234 (መስከረም 27 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 17 ፣ በሰ/መ/ቁ 43049 (ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ የሰ/መ/ቁ 93234 (መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ በሰ/መ/ቁ 45595 (ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ የሰ/መ/ቁ 77842 (ታህሳስ 3 ቀን 2005ዓ.ም) ቅፅ 14፣የሰ/መ/ቁ 96954 (ሚያዚያ 24 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16፣ የሰ/መ/ቁ 140253 (ታህሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 240096 (መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)

## ክፍል-4

የሰ/መ/ቁ 212950 (ሕዳር 30 ቀን 2014ዓ.ም) ቅፅ 27፣ የሰ/መ/ቁ 208644 /208645 (ጥቅምት 26 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 26፣ የሰ/መ/ቁ 137545 (መስከረም 30 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ/መ/ቁ 113143 (መጋቢት 30 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 20፣ የሰ/መ/ቁ 111498 (የካቲት 25 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 19፣ የሰ/መ/ቁ 113464 (ሕዳር 22 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 19፣ በሰ/መ/ቁ 51706 (ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅጽ 10 ፣ በሰ/መ/ቁ 241561 (ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 100712 (መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ በሰ/መ/ቁ 66767 (ሐምሌ 28 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ 240622 (ሰኔ 2 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 95921 (ሚያዝያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 100860 (ሐምሌ 15 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 111742 (ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 89640 (መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 6፣ በሰ/መ/ቁ 92141 (መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ በሰ/መ/ቁ 75922 (ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 75980 (ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 245494 (ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 226651 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 45595 (ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅፅ 12፣ በሰ/መ/ቁ 64813 (ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 225975 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 228692 (ሕዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ 217634 (ታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 222478 (ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 223573 (ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 224338 (ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 224533 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፤ የሰ/መ/ቁ 225720 (ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም)፣ የሰ/መ/ቁ 227851 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም) ፤ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 109441 (ጥር 17 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 19፣ የሰ/መ/ቁ 89676 (ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 35697 (ጥቅምት 20 ቀን 2000ዓ.ም) ቅፅ 9 ፣ የሰ/መ/ቁ 138244 (ታህሳስ 27 ቀን 2010ዓ.ም) ፣ የሰ/መ/ቁ 140253 (ታህሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም)፣በሰ/መ/ቁ 228271 በቀን መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም እና በሰ/መ/ቁ 240096 መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም፣ የሰ/መ/ቁ 240096 (መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣ ሰ/መ/ቁ 228271 (መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም) ፣በሰ/መ/ቁ 38161 (የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም) ቅፅ 9 ፤ የሰ/መ/ቁ 91535 (የካቲት 12 ቀን 2006ዓ.ም) ቅፅ 15 ፤ የሰ/መ/ቁ 57644 (ሐምሌ 25 ቀን 2003ዓ.ም) ቅፅ 12 ፤የሰ/መ/ቁ 51706 (ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅፅ 10፣ የሰ/መ/ቁ 203253 (28/01/2014ዓ.ም)፣ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 78470 (ሚያዚያ 7 ቀን 2005ዓ.ም) ቅፅ 15

***ክፍል-5***

በሰ/መ/ቁ 28952 (መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅጽ 7፣ በሰ/መ/ቁ 127312 (ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 21

***ክፍል-6***

በሰ/መ/ቁ 141978 (መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅጽ 22

***ክፍል-7***

የሰ/መ/ቁ 94227 (ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16፣ በሰ/መ/ቁ 29325 ( የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም) ቅጽ 7፣ በሰ/መ/ቁ 231732 (ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 179416 (ሰኔ 23 ቀን 2012ዓ.ም) ቅጽ 24፣ በሰ/መ/ቁ 173967 (መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም) ቅጽ 24፣ በሰ/መ/ቁ 127313 (መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅጽ 22፣ በሰ/መ/ቁ 104220 (ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 18፣ በሰ/መ/ቁ 98014 (ሐምሌ 14 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 18፣ በሰ/መ/ቁ 93577 (ሕዳር 22 ቀን 2007ዓ.ም) ቅጽ 17፣ በሰ/መ/ቁ 95875 (ሰኔ 17 ቀን 2006ዓ.ም) ቅጽ 16፣ በሰ/መ/ቁ 57632 (ታህሳስ 25 ቀን 2003ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 76909 (ግንት 10 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ በሰ/መ/ቁ 211518 (ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 154444 (የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 159451 (መጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 160767 (ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 141081 (መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 140719 (ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 144724 (ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 95261 (ሐምሌ 02 ቀን 2006 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 228597 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም)፣የሰ/መ/ቁ 231732 (ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ/ም)

***ክፍል-8***

የሰ/መ/ቁ - 96378 (ህዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 17፣ በሰ/መ/ቁ 116405 (መጋቢት 02 ቀን 2008 ዓ.ም) ቅፅ 20 ፣ በሰ/መ/ቁ 131088 (ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅፅ 21፣ በሰ/መ/ቁ 134834 (ሰኔ 29 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 21፣ በሰ/መ/ቁ 200520 (የካቲት 10 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣ በሰ/መ/ቁ 98014 (ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 18፣ በሰ/መ/ቁ 73264 (መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 13፣ በሰ/መ/ቁ 101056 (ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 18፣ በሰ/መ/ቁ 57632 (ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 63741 (ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 63014 (ሚያዚያ 09 ቀን 2004 ዓ.ም) ቅፅ 13፣ በሰ/መ/ቁ 248728 (ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 236400 (የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 101003 (ሕዳር 2 ቀን 2009 ዓ.ም) ቅጽ 20፣ በሰ/መ/ቁ 120762 (የካቲት 25 ቀን 2009ዓ.ም) ቅጽ 19፣ በሰ/መ/ቁ 59537 (ሚያዚያ 19 ቀን 2003ዓ.ም) ቅጽ 12፣ በሰ/መ/ቁ 47755 (ግንቦት 5 ቀን 2003ዓ.ም)ቅጽ12፣ በሰ/መ/ቁ 48617 (ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም) ቅጽ 10፣ በሰ/መ/ቁ 95875 (ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም) ቅፅ 16፣ በሰ/መ/ቁ 35611 (ሰኔ 19 ቀን 2000ዓ.ም) ቅጽ 7፣ በሰ/መ/ቁ 39722 (ታህሳስ 23 ቀን 2001ዓ.ም) ቅጽ 9፣ በሰ/መ/ቁ 198600 (ግንቦት 23 ቀን 2013 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 188086 (ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 156999 (ጥቅምት 27 ቀን 2011 ዓ.ም) ቅፅ 23፣ በሰ/መ/ቁ 158480 (ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 143820 (ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም) ፣ በሰ/መ/ቁ 138870 (ሚያዚያ 30 ቀን 2010 ዓ.ም) ቅፅ፣ በሰ/መ/ቁ 138874 (ግንቦት 17 ቀን 2010 ዓ.ም)፣ በሰ/መ/ቁ 208890 (ሕዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም) ቅፅ 26፣ የሰ/መ/ቁ 203051 (የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም) ቅፅ 25፣በሰ/መ/ቁ 101056 (ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም) ቅጽ 18፣የሰ/መ/ቁ 93234 (መስከረም 27 ቀን 2007ዓ.ም) ቅፅ 17፣ የሰ/መ/ቁ 118252 (ጥር 24 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 19 ፣የሰ/መ/ቁ 117877 (ሐምሌ 22 ቀን 2008ዓ.ም) ቅፅ 20፣ የሰ/መ/ቁ 127484 (መስከረም 23 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22፣ የሰ/መ/ቁ 74041 (ሰኔ 4 ቀን 2004ዓ.ም) ቅፅ 13፣የሰ/መ/ቁ 149962 (መጋቢት 25 ቀን 2010ዓ.ም) ቅፅ 22

## II.የሕግ ማጣቀሻዎች

- በተባበሩት መንግስታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9፣ 10፣ 11፣ 14
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፣ 1987 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 11ኛ አመት፣ ቁጥር 1 አንቀጽ 13፣ 17፣ 19፣ 20፣ 22፣ 26፣ 40፣ 78፣ 79፣ 80
- የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት እና የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 84/1968
- የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ህግ 1954 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 182/1954 የተጠቀሱ አንቀፆች አንቀጽ 22፣ 23፣ 27፣ 30፣ 32፣ 33፣ 35፣ 59፣ 63፣67፣ 74፣ 75፣ 94-98፣ 106፣ 108፣ 109፣ 111፣ 112፣ 113፣ 115፣ 119፣122፣124፣ 128፣129፣ 130፣ 131፣ 132፣ 133፣ 134፣ 135፣ 136፣ 141፣142፣ 146፣ 149፣ 150፣ 151፣ 152፣ 153፣ 161፣ 185፣ 195፣
- የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍትህ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ድንጋጌ፣ 1958 አንቀጽ 145፣ 320፣ 337፣ 341፣ 343፣ 348
- የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓት እና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 236/93 እና 239/93 አንቀጽ 2 አንቀጽ 51
- የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 58 እና አንቀጽ 62የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ፣ 1996 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 414/1996 ዓ.ም የተጠቀሱ አንቀፆች አንቀጽ 3፣ 5፣ 23፣ 24፣ 27፣ 32፣ 33፣ 35፣ 37፣ 60፣ 82፣ 179፣ 184፣ 190፣ 192፣ 194፣ 197፣ 212፣ 224፣ 239፣ 403፣ 407፣ 408፣ 419፣ 420፣ 422፣ 436፣ 441፣ 462፣ 559፣ 540፣ 571፣ 575፣604፣ 665፣ 667፣ 669፣ 671፣ 675፣ 676፣ 686፣ 692፣ 862
- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 322/1995
- የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓት የማስረጃ ህግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 7
- የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 2፣ 9፣ 13፣ 16፣ 32
- የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርአትና የማስረጃ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ አዋጅ 882/2007 አንቀጽ 2፣ 3፣ 7፣ 58
- የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 46
- የወንጀል ህግ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1160/2011) አንቀጽ 168
- የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 22፣ 49
- የቡና ግብይት እና ቁጥጥር ጥራት አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 7፣ 17፣ 19
- የቡና ግብይት እና ቁጥጥር ጥራት አዋጅን ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 002/2012 አንቀጽ 14
- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ 2013 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ዓ.ም ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 2ኛ አመት፣ ቁጥር 13 አንቀጽ 2፣ 10

**III. የመፈለጊያ ቃላቶች**


1. **የፖሊስ ምርመራ** …. 8፣ 9፣ 153፣ 300፣ 346፣ 421፣ 447፣ 466
2. **የእምነት ቃል** …. 9፣ 53፣ 55፣ 121፣ 125፣ 346፣ 347፣ 369፣ 370፣ 372፣ 455
3. **ኢግዚቢት** …. 9፣ 349፣ 350፣ 351፣ 352
4. **ብርበራ** …. 9፣ 353፣ 354፣ 355፣ 356
5. **መገደብ** …. 102፣ 108፣ 111፣ 113፣ 114፣ 116፣ 121
6. **ክስ አዘገጃጀት** …. 9፣ 403
7. **ክስ ማሻሻል** …. 9፣ 407
8. **ዋስትና** …. 9፣ 362፣ 365፣ 380፣ 381፣ 382፣ 393
9. **ምርመራ** …. 7፣ 8፣ 346፣ 398፣ 421፣ 469
10. **ክስ መመስረቻ** …. 11፣ 403፣ 404
11. **መቃወሚያ** …. 9፣ 413፣ 419፣ 430
12. **ሕገ-ወጥ** …. 3፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8፣ 145፣ 158፣ 188፣ 235፣ 282፣ 295፣ 307፣ 344፣ 353
13. **ሰብዓዊ** …. 12፣ 401፣ 423
14. **ቅጣት** …. 4፣ 5፣ 12፣ 52፣ 70፣ 74፣ 82፣ 86፣ 92፣ 94፣ 112፣ 129፣ 173፣ 409፣ 430
15. **ጥፋተኛ** …. 4፣ 55፣ 59፣ 62፣ 130፣ 240፣ 409፣ 432
16. **መከላከል** …. 83፣ 178፣ 228፣ 229፣ 240፣ 344
17. **መከላከያ** …. 197፣ 198፣ 199፣ 301፣ 304፣ 432፣ 461
18. **ዛቻ** …. 8፣ 84፣ 217፣ 218፣ 219፣ 221፣ 222፣ 223፣ 224፣ 225
19. **አስተዳደር** …. 1፣ 5፣ 7፣ 8፣ 12፣ 15፣ 152፣ 246፣ 247፣ 263፣ 266፣ 327
20. **ዲሲፕሊን** …. 419፣ 420
21. **ስርቆት** …. 5፣ 6፣ 195፣ 209፣ 210፣ 211፣ 212፣ 213፣ 214፣ 215፣ 216፣ 222፣ 224፣ 431
22. **ሕጋዊነት** …. 9፣ 12፣ 15፣ 353፣ 354፣ 441፣ 452፣ 460
23. **ይግባኝ** …. 9፣ 10፣ 381፣ 393፣ 474፣ 475፣ 477፣ 478፣ 480
24. **ማስረጃ ምዘና** …. 9፣ 12፣ 443፣ 445፣ 446፣ 447፣ 448፣ 452
25. **ጉቦ** …. 7፣ 332፣ 333፣ 334፣ 335፣ 336
26. **እምነት ክህደት** …. 9፣ 435፣ 437፣ 439፣ 440፣ 441
27. **እምነት ማጉደል** …. 6፣ 226፣ 227፣ 228፣ 229
28. **ፍርድ ቤት መድፈር** …. 8፣ 342፣ 343፣ 344፣ 345
29. **ደንብ መተላለፍ** …. 8፣ 350፣ 351
30. **ክስ ማንሳት** …. 9፣ 424፣ 425፣ 426፣ 427
31. **ሽብር** …. 4፣ 8፣ 85፣ 86፣ 87፣ 88፣ 89፣ 90፣ 91፣ 356
32. **ያለመገደድ** …. 9፣ 415፣ 421
33. **መሰየም** …. 404፣ 405፣ 406፣ 407
34. **ያለመከሰስ** …. 21፣ 301፣ 302፣ 303፣ 304
35. **ካሳ** …. 4፣ 132፣ 133፣ 134፣ 135
36. **መፀፀት** …. 133፣ 134፣ 135
37. **ይርጋ** …. 9፣ 142፣ 143፣ 144፣ 145

38. **ውንብድና** …. 6፣ 217፣ 218፣ 219፣ 220፣ 221፣ 431
39. **ማቅለያ** …. 9፣ 51፣ 53፣ 179
40. **ማክበጃ** …. 9፣ 120፣ 127
41. **መሸሸግ** …. 7፣ 117፣ 118፣ 119፣ 120፣ 233፣ 234፣ 235፣ 236፣ 237፣ 238፣ 317
42. **አራጣ** …. 7፣ 220፣ 246፣ 247፣ 248፣ 249፣ 250
43. **መያዣ** …. 9፣ 401፣ 402፣ 403፣ 415፣ 416፣ 417፣ 418፣ 419፣ 431
44. **ስረ ነገር ሥልጣን** …. 9፣ 12፣ 325፣ 326፣ 327፣ 328፣ 329፣ 330፣ 391፣ 392፣ 393
45. **ሙከራ** …. 5፣ 27፣ 28፣ 29፣ 30፣ 31፣ 32፣ 33፣ 34፣ 35፣ 36፣ 39፣ 194፣ 195፣ 356
46. **መውረስ** …. 4፣ 7፣ 97፣ 121፣ 122፣ 123፣ 124፣ 125፣ 134፣ 250፣ 317፣ 431
47. **ማታለል** …. 7፣ 202፣ 239፣ 240፣ 241፣ 242፣ 243፣ 244፣ 245፣ 315
48. **ማነሳሳት** …. 5፣ 40፣ 41፣ 42፣ 43፣ 44፣ 45፣ 46፣ 52፣ 316
49. **ሐሰተኛ** …. 7፣ 127-131፣ 152፣ 239፣ 251-257፣ 279፣ 356
50. **አባሪ** …. 5፣ 41፣ 47-53፣ 316
51. **ቀላል** …. 24፣ 25፣ 86፣ 87፣ 185፣ 188-190፣ 205፣ 217፣ 414
52. **ሙስና** …. 8፣ 148፣ 149፣ 245፣ 307-317፣ 380፣ 400
53. **መርዳት** …. 5፣ 47-53፣ 117-120
54. **አመክሮ** …. 4፣ 135-143
55. **ኢ-ኃላፊነት** …. 5፣ 47፣ 54-60
56. **ክልከላ** …. 4፣ 104-108፣ 133፣ 301፣ 317
57. **አሳብ** …. 19-27፣ 55፣ 182-184፣ 194፣ 216፣ 245
58. **መቀጮ** …. 4፣ 86፣ 88-95፣ 114
59. **ቸልተኛ** …. 19፣ 24-26፣ 35፣ 59፣ 165፣ 186-192
60. **ተደራራቢ** …. 5፣ 61-70
61. **ቅጣት (ዝርዝር)** …. 4፣ 71-86፣ 487
62. **ሪከርድ** …. 83፣ 106፣ 314
63. **መግደል** …. 4፣ 19-33፣ 47-52፣ 58፣ 62-73፣ 83፣ 99-103፣ 118-120፣ 165-194፣ 212፣ 412-413
64. **ግዙፋዊ** …. 27፣ 28፣ 34፣ 35፣ 47፣ 48፣ 50፣ 61፣ 64፣ 65፣ 68፣ 117፣ 118፣ 182፣ 192
65. **ሞራላዊ** …. 47-53፣ 58፣ 60፣ 72፣ 117
66. **ምህረት** …. 5፣ 100-101፣ 126፣ 144-150
67. **ይቅርታ** …. 5፣ 71፣ 73፣ 100-101፣ 126፣ 144-150